ትንሳኤ ዘ-ኢትዮጵያ

ከመንታ መንገድ፣



ከተመጽዋችነት ወደ አፍሪካዊ ኩራት የተደረገ ሽግግር
መጻዒ ፈተናዎችና መልካም ዕድሎች

በረከት ስምኦን



Brought to you by

Ethiopian Bookstore

https://t.me/etbookstore

ትንሳኤ ዘ-ኢትዮጵያ

ከ መ ን ታ መ ን ገ ድ

ከተመፅዋችነት ወደ አፍሪካዊ ኩራት የተደረገ ሽግግር
መፃኢ ፈተናዎችና መልካም ዕድሎች

በረከት ስምኦን

©2010 ዓ.ም በረከት ስምዖን
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ትንሳዔ ዘ-ኢትዮጵያ
ከመንታ መንገድ

የመጀመሪያ ዕትም
ሚያዝያ 2010 ዓ.ም
ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛትም ሆነ ለሌላ ጥቅም ማዋል የተከለከለ ነው።

ISBN 978-99944-72-42-0

Printed by:- Angkor Publishers Pvt.Ltd.
India

መታሰቢያነቱ

ለምንጊዜም መምህሬ መለስ ዜናዊ፣

ካላንተ ይህቺ ኢትየጵያ በዚህ ወቅት ካሸለበችበት ቀና አትልም ነበር፡፡ ይህን የምለው የጓዶችህንና የሰፊውን ህዝበ-ኢትዮጵያ ሁሉ ሚና አሳንሼ በማየት አይደለም፡፡ ካለእነርሱ አንተም እንዲህ አትሆንም ነበርና፡፡ ነገር ግን አንተ ልዩ ሰው ነበርክ፡፡ በዚህ መጽሐፍ በበቂ ሁኔታ ብገልፀውም ባልገልጸውም፣ በተሟላውም በተነካካውም አሻራህ የሌለበት፣ አርቆ አስተዋይነትህ ያላረፈበት ከቶ ምን ነገር ነበር? በርግጥ ያላንተ የማሽቆልቆሉ ጉዞ ይገታ ነበርን? ቀና ማለትስ እንችል ነበርን? ታሪክ ሠሪው ሰፊው ህዝብ መሆኑ ባያከራክርም፣ በታሪክ የማይተካ ሚና የሚጫወቱ አንተን የመሰሉ ታላቅ መሪዎች በሌሉበት አገራችን ይህን ያክል ርቀት መጓዝ አትችልም ነበር፡፡ ሌት ተቀን ባደረግከው ጥረት ራስህን በማብቃት፣ ያለምንም ስስት በጠራ ሀሳብ ለሞላኸው አዕምሮ ምሥጋናዬ ወደር የለውም፡፡ የተገለጠ መጽሐፍ ከመሆን በላይ ምን አለና፡፡

እንዲሁም በኢህአፓ አባልነት ህዝባዊ ተልዕኮ ሊፈጽም ሲንቀሳቀስ ጐጃም ላይ ተይዞ በደርግ ለተገደለውና በሂስ ውስጥ መኖር ላስተማረኝ በሪሁን ዳኘው(ጋንች)ና ለአሥራ ዘጠኝ ሥድሳዎቹና ሰባዎቹ የትግልና የመሥዕዋት ትውልድ

መግቢያ

“የሁለት ምርጫዎች ወግ” በሚለው መጽሐፌ ማጠቃለያ ላይ ለእኛው ዘመን የታጋይ ትውልድ የተሻለ የሥራና የእፎይታ ዘመን በመመኘት ስሰናበት “እውን የዚህች አገርና የህዝቦቿ ሁኔታ ለማንም እረፍት የሚሰጥበት ደረጃ ላይ ደርሶ ከሆነ” በሚል አንቀጽ ነበር ያሳረግኩት። “የሁለት ምርጫዎች ወግ” ከታተመ ስድስት ዓመታት አልፈዋል። በእነዚህ ዓመታት ሁሉ የሆነውን መለስ ብዬ ሳሰላስለው፣ በተለይ ደግሞ አሁን የምንገኝበትን ጊዜያዊና አላፊ ነገር ግን ደግሞ ከባድና ፈታኝ ችግር ስመለከተው በርግጥም የአገራችን ሁኔታ ለማንም እረፍት የሚሰጥበት ደረጃ ላይ አልደረሰም። በእነዚህ ዓመታት ኢኮኖሚያችን ከፍተኛ እርምጃ ተራምዶ፣ የድኅነት ቅነሳችን ትርጉም ባለው ደረጃ መሻሻል የታየበት ቢሆንም፣ ወደላይ በተነሳን ቁጥር እንደገና ወደአዲስና ሌላ የተወሳሰበ ሁኔታ ውስጥ መግባታችን ግን አልቀረም። ስለሆነም አንድ አስተማማኝና የማይቀለበስ የዕድገት ምዕራፍ ውስጥ እስከንገባ ድረስ አሁንም ቢሆን እፎይታን በሚነሳ አገር ውስጥ እንኖራለን።

ከዚህ በመነሳት ይህ መጽሐፍ በአጠቃላይ ባለፉት አርባና አምሳ ዓመታት፣ በዋነኛነት ደግሞ ከ1980 ዓ.ም ወዲህ ባሉት ሠላሣ ዓመታት የነበረውን የትግልና የለውጥ ሂደት ይዳስሳል። ከዚህ የትግል ጉዞና አገራችን አሁን ከደረሰችበት ደረጃ በመነሳት ደግሞ የወደፊቱን ዕድላችንን የሚወስኑ መሠረታዊ ጉዳዮችን ያመላክታል። ይህም በመሆኑ መጽሐፉ በስድሣዎቹና ሰባዎቹ የትግል ትውልድና እርሱ በቀየሰው የለውጥ ጉዞ ላይ የተመሠረተ ነው። ከተማሪዎች ንቅናቄ ጀምሮ ከግማሽ ምእተ ዓመት ጥቂት ዘለግ ያለ እድሜ ባስቆጠረው በዚህ ሂደት፣ ይህ የትግልና ለውጥ ትውልድ አዳዲስ የለውጥ ሀሳቦችን በማመንጨትና በኋላም በትጥቅ ትግሉ ወቅት ይበልጥ የጠራ አመራር በመስጠት ለውጡን ከአንድ ምዕራፍ ወደሌላ ምዕራፍ እያሸጋገረ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ችሏል።

ከታላላቆቹ የኢትዮጵያ ሥልጣኔዎች ጀምሮ እስከ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የዘለቀው አገራዊ የለውጥ ጉዞ፣ በውስጡ በጣም ብዙ ምዕራፎች የነበሩት የዘመናት ሂደት ነው። የአገራችን ህዝቦች በእነዚህ ዘመናት ሁሉ የሚደርስባቸውን ግፍና በደል ለማስቀረት ከቡር መስዋዕት እየከፈሉ ለመብትና ጥቅሞቻቸው ታግለዋል። አገራችን ዛሬ የምትገኝበት ደረጃ፣ በተለይ ደግሞ በመመዝገብ ላይ ያሉት ለውጦች የነዚህ ትውልዶች ሁሉ የትግልና ከቡር መስዋዕትነት ድምር ውጤት ነው።

ኢትዮጵያ እንደማንኛውም ሕብረተሰብ የለውጥ ፈላጊ ትውልድ መካን ያልነበረች አገር ነች። ታላላቆቹ የኢትዮጵያ ሥልጣኔዎች የተወለዱት በለውጥ ፈላጊ ዜጐቿ ጥረት ነበር። እንስሣትን ያላመዱ፣ ጤፍና ገብስን ከዱር በቀልነት ወደምግብ ሰብልነት የቀየሩ፣

ቡናን ለመንፈስ ማደሻነት ያዋሉ ኢትዮጵያውያን የፈጠራ ሰዎች ለውጥ ፈላጊዎች ነበሩ። በሁሉም የአገራችን ክፍሎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች የትግል ተሳትፎ እዚህ ድረስ የዘለቀው ይህ ህዝባዊ ትግል፣ እንደተወርዋሪ ኮከብ ብልጭ ብለው ሳይጠገቡ የከሰሙ ምርጥ የለውጥ ሐዋርያት የተመረቱበት ሲሆን ያለእነርሱ ጥረት የዛሬው ለውጥ ፍፁም ሊታሰብ የማይችል ነበር። ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ጀምሮ እንኳ፣ እንደ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም፣ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ ሐዲስ ዓለማየሁ፣ አቤ ጉበኛ፣ መንግሥቱና ገርማሜ ነዋይ፣ ታደሰ ብሩ፤ አበራ ገሙ፣ ማርቆስ ሐጐስ፣ ዋለልኝ መኮንን፣ ማርታ መብራቱ፣ ጌታቸው ማሩ፣ አቦማ መኮነን፣ ሰሎሞን ዋዳ፣ መለስ ዜናዊ የመሳሰሉ የለውጥ አራማጆች ባመነጩዋቸው ሀሳቦች እየተመራ በቅብብሎሽ እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ ነው።

ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ በኋላ ያለው የለውጥ ሂደት እውነተኛ መሐንዲስ የሆነው የስድሣዎቹና የሰባዎቹ የትግል ትውልድ ደግሞ በዚህ ረዥም የታሪክ ሠንሰለት ውስጥ አንድ ዘለበት ብቻ ነው:: በመሆኑም ብቻውን ጀምሮ ብቻውን የጨረሰው የተሟላ ለውጥ አልነበረም። ሌሎች በጀመሩት ላይ የእርሱን ድርሻ እየጨመረበት እንደተጓዘው ሁሉ፣ እርሱ በጀመረው ለውጥ ላይ ደግሞ ሌሎች ትውልዶች እያከሉበት ትግሉና ለውጡ እዚህ ላይ ደርሷል። ስለሆነም ኢትዮጵያን የመለወጡ ሂደት መልካም ውጤት ካመጣ ዘንድ፣ ለሁሉም ዘመን የለውጥ ትውልዶች ምስጋና ይገባቸዋል:: የዚህ መጽሐፍ ትኩረት በስድሣና ሰባዎቹ ትውልድ ላይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምስጋናው ደግሞ ትግሉን ጀምረው ቢጨርሱትም ባይጨርሱትም የለውጥን አይቀሬነትና አስፈላጊነት አምነው ለለውጥ የአቅማቸውንና ሁኔታው የፈቀደላቸውን ያህል ላበረከቱ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የለውጡ ትውልዶች ይሆናል:: በየትኛውም ትውልድ ዘመን የሚካሔድ ለውጥ ሁሌም ጅምር ሥራ ነው:: በመሆኑም ይህ መጽሐፍ በአንድና ሁለት ትውልድ የለውጥ ሥራዎች ላይ ቢያተኩር፣ ለውጡን ያመጣውና የጨረሰው ይኸው ትውልድ ብቻ ስለሆነ አይደለም:: በዚህ ትውልድ አባልነቴ የኖርኩበትን፣ በቅርብ የማውቀውንና የተሳተፍኩበትን ሂደት በገባኝ መልክ ለማበርከት ያክል ብቻ ነው::

ስለሁሉም የለውጥ ትውልዶች ይህን ያህል ከተባለ፣ በኢህአዴግ የተመራውና ከአራት አሥርት ዓመታት በላይ የዘለቀው የለውጥ ጉዞ ደግሞ የተለየ ገጽታ ነበረው:: በጥልቅ ፍልስፍናዊ እሣቤዎች ላይ የተመሠረተው ይህ የለውጥ ጉዞና ተግባርን መፈጸም እንጅ ታሪክ ማውራት የማይቀናው ይህ ትውልድ ብዙም ያልተጻፈለት ነው:: ይህ የለውጥ ንቅናቄ ለበርካታ ከፍለ ዘመናት በማሽቆልቆል ጉዞ ውስጥ የኳተነችውን አገራችን፣ ደረጃ በደረጃ ዓለምን በእጅጉ ማነጋገር የቻለ ፈጣን ዕድገት እንድታስመዘግብ አድርጓታል። ንቅናቄው

መጀመሪያ ላይ የለውጥ እንቅፋት የነበረውን የደርግ አገዛዝ በከባድ ትግል አስወግዷል። ቀጥሎም አገሪቱ ከሩብ ምእተ ዓመት በላይ የዘለቀና ያልተቋረጠ ዕድገት እንድታስመዘግብ አድርጓል። በዚህ መጽሐፍ ይህ የለውጥ ሂደት ምን እንደሚመስል፣ በምን ዓይነት ዓለማዊና አገራዊ ሁኔታ ውስጥ በማለፍ የተፈጸመ እንደሆነ፣ በየመንገዱ ያጋጠሙት ፈተናዎች ምን እንደነበሩና እንዴት እንደታለፉ ለማውሳት ተሞክሯል። መጽሐፉ ያለፉትን ጥቂት አሥርት ዓመታት ፍጻሜዎች ከመተረከም በላይ አገራችን አሁን የደረሰችበትን ደረጃ በዋና ዋና መስፈርቶች ለማሳየት ይሞክራል።

ኢትዮጵያ ከጥቂት ዓመታት ስኬታማ የለውጥ ሂደት በኋላ እጅግ የሚያስጐመጅና የሚያሳሳ፣ እንዲሁም በጣም የሚያሳስብና የሚያስፈራ ሁኔታዎች ተዳብለው የሚገኙባት አገር ሁናለች። በአንድ በኩል ለዓመታት በተካሔደው ልማታዊ ጥረት ወደዋናው የትራንስፎርሜሽን አዙሪት ለመግባት የሚያስችላት አዎንታዊ የተከማቸ አቅም /Critical Mass/ ፈጥራለች። ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ የመልካም ዕድል መስኮቶችን የከፈተችና በሚያስጐመዥር የታሪክ ምዕራፍ ላይ የምትገኝ መሆኗ ከማይጠበቁ ወገኖች ሳይቀር የተመሰከረለት ሆኗል። ይህ የሳንቲሙ አንድ ገጽታ ነው።

የሳንቲሙ ሌላው ገጽታ ደግሞ ኢትዮጵያ ለጊዜውም ቢሆን ከመልካም ዕድሎቹ ጐን የሚያስፈራ ሁኔታ የሞላባት አገር መሆኗ ነው። የተከማቸውን አዎንታዊ አቅም ሊያመክኑ የሚችሉ ነባርና አዳዲስ ችግሮች የተጋረጡባት አገርም ነች። በመሆኑም የመልካም ዕድል መስኮቶች የተከፈቱባት ብቻ ሳትሆን፣ ፈጥነው ሊዘጉ የሚችሉባትም ነች። ፈረንጆች የመልካም ዕድል መስኮቶች የሚሏቸው አብዛኛውን ጊዜ ጠበብ ብለው የሚከፈቱ ዕድሎች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በጥንቃቄ፣ በብስለትና በብቃት ካልተጠቀሙባቸው በስተቀር ከተከፈቱበት በላቀ ፍጥነት ሊዘጉ የሚችሉና አንዴ ከተዘጉ ደግሞ እንደገና እስኪከፈቱ ድረስ ሌላ ዘመን ሊጠይቁ የሚችሉ ናቸው። ይህ በብዙ አገሮች በግልጽ የታየ ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ ብዙ አልራቀችም። መለስ "ከጫካው ገና አልወጣንም" (We are not yet out of the woods) በማለት ደጋግሞ ይገልጸው እንደነበረው፣ በኢትዮጵያ የመልካም ዕድል መስኮቶቹ የተከፈቱት በጅምር ደረጃ ብቻ ነው። ስለሆነም በተከፈቱት ዕድሎች በብቃት እየተጠቀሙ፣ ሌሎች አዳዲስ መስኮቶች በብዛትና በስፋት መከፈት ይገባል። የመልካም ዕድል መስኮቶችን የሚያጠቡ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የሙስና፣ በትንሽ ድል የመኩራራትና ለችግሮች ደንታቢስ የመሆን፣ እንዲሁም በብሔረተኝነት ጭምብል እየተሸፈኑ ያለአንዳች ተጠያቂነት ያሻህን የመሥራት አዝማሚያዎችን በጥብቅ ማስወገድ ይጠይቃል። በተፈጠሩት ቅድመ ሁኔታዎችና መልካም ዕድሎች በብቃትና

በአስተዋይነት መጠቀም መቻል ወይም አለመቻል ቀጣዩ መልካም ዘመን እውን እንዲሆን ወይም እንዳይሆን የሚያደርግ ይሆናልና::

ልክ እንደኢትዮጵያ ሁሉ በሁለቱም አቅጣጫ ይህን የመሰለ አቅም የፈጠሩና ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች በብስለት እየፈቱ መልካም ዕድሎችን ለማስፋት የቻሉ አገሮች ወዳሰቡትና ወደተመኙት ከፍታ ወጥተዋል:: በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ይህን አቅምና መልካም ዕድል ያባከኑ ሁሉ ደግሞ ባለህበት እርገጥ ከማለት ጀምሮ እንደ ቱኒዘዝያና ዩጐዝላቪያ ለከባድ ውድመትና መመሰቃቀል ተዳርገዋል። ሁለቱ አገሮች ልክ እንደኢትዮጵያ ሁሉ ረዘም ላሉ ዓመታት ከፍተኛ የዕድገት ምጣኔ እያስመዘገቡ የተጓዙ ቢሆኑም በከፈቱት የመልካም ዕድል መስኮት በዘላቂነት መጠቀም ባለመቻላቸው ለቀውስና መመሰቃቀል መዳረጋቸው ያለፍንበት ሩብ ምእተ ዓመት ታሪክ የመዘገበው ነው።

በዚህ መጽሐፍ ከሃያ አምስት ዓመታት የለውጥ ጉዞ በኋላ የተፈጠረው የተከማቸ አቅምና የመጭው ዘመን መልካም ዕድሎችና ፈተናዎች ይሆናሉ የተባሉትን ጉዳዮች ለማመላከት ተሞክሯል:: መልካም ዕድሎቹ ይበልጥ እንዲሰፉ የሚያስችሉ ጉዳዮችና ይህን ሊያመክኑ የሚችሉ የስጋትና የፈተና ምንጮችም አብረው ተመላክተዋል:: ኢህአዴግ የአገሪቱ ዕድል ከማንም በላይ በህዝቦቿ መወሰን እንዳለበት አምኖ በተግባር እያዋለ እንደመጠጣው ሁሉ፣ ፈተናዎቹም ሆኑ መልካም ዕድሎቹ ከህዝብ ሊደበቁ አይገባም:: ኢህአዴግ ህዝብን ይዞና በህዝብ ተማምኖ መልካም ዕድሎችን እየፈጠረና እየተጠቀመ፣ ፈተናዎችንም እያለፈ የተጓዘ ድርጅት ነው:: የዛሬ መልካም ዕድሎችና ፈተናዎችም እንደትላንቱ ሁሉ፣ ህዝብ በግልጽነት ሊመክርባቸውና እጅ ለእጅ ተያይዞ በመረባረብ ሊፈታቸው ከቻለ፣ አገራችን እንደገና ወደሌላ ዕድገት ከፍ እንደምትል ይታመናል። ስለዚህም ከፓርቲው በተጨማሪ፣ የሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ በማረጋገጥና ህዝባዊ አቅምን በመጠቀም የሚፈቱት ችግሮችም ሆኑ ጥቅም ላይ የሚውሉት የተከማቹ አዎንታዊ አቅሞች ግልጽ ውይይት ሊካሔድባቸው ይገባል::

ይህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ "ትንሳኤ ዘ-ኢትዮጵያ በመንታ መንገድ" በሚል ርዕስ እንዲታተም የተዘጋጀ ነበር። በሂደት ግን "በመንታ" መንገድ ላይ ከመሆናችን ይልቅ ከመንታ መንገድ መውጣት እንደጀመርንና እንደምንችል የሚያመላክቱ ነገሮች የሚበዙ እንደሆኑ አስተዋልኩ። እነዚህን በግልፅ ቋንቋና የተስተካከለ ይዘት በማቅረብ የበኩሌን አስተዋጽዖ ባበረከት የዘመኑ ትውልድ በሚያካሂደው ትግል ጥንታዊ የሥልጣኔ ታሪኳን በአዲስና ዘመናዊ ደረጃ ሊያድሰው እንደሚችል በመተማመን "ትንሳኤ ዘ-ኢትዮጵያ ከመንታ መንገድ" በሚል ርዕስ እንዲታተም ማድረግን መረጥኩ። በመነሳት ላይ ያለችውና የአዲሲቱ ኢትዮጵያ

መሠረት የተጣለው አገራችን አሁን የገጠሟትን ጊዜያዊ ችግሮች ሁሉ አልፋ እንድትሄድ በሚያስችል ቅኝት ነውና ርዕሱ ከእውነታው ብዙም ይርቃል ብዬ አልገመትኩም።

የመጽሐፉ የመጀመሪያ ክፍል የሚያተኩረው ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. ጥቂት ቀደም ብሎ ከነበረው አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ በመነሳት ላለፈው ሩብ ምእተ ዓመት በተካሄደው የለውጥ ትግልና በተመዘገቡት ውጤቶች ላይ ነው። ይህ ወቅት በአብዛኛው በኢህአዴግ የተመራው አገራዊ የለውጥ ሂደት የፖሊሲ ነጻነትን ለማስጠበቅና አገራችንን በራሳችን አገር በቀል ፕሮግራም አማካይነት ለመለወጥ ከኒዮ-ሊበራሊዝም ጋር ከባድ ፍልሚያ የተካሄደበት ነው። የዚችን ትልቅ አገርና የህዝቦቿን ጥቅም ማዕከል በማድረግ የተካሄደው ይህ ትግል ምን ያህል ውስብስብ፣ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች የበዙበት እንደነበርና ይህን በማለፍ የተመዘገቡት ውጤቶች ምን እንደሚመስሉ ያመላክታል። በክፍል ሁለት በ1993ዓ.ም. ኢህአዴግን ያጋጠመው የአመራር ቀውስና ከዚህ በመውጣት የተለኮሰው የአስራ ስድስት ዓመታት አገራዊ የህዳሴ ጉዞ አነሳስ፣ ይዘት፣ ተግባራዊ እንቅስቃሴና ውጤት ተዳስሷል። በክፍል ሦስት ደግሞ አሁን በአገራችን ፊት የተደቀኑ ውስጣዊና በተወሰነ ደረጃም ውጫዊ ፈተናዎች፣ እንዲሁም በእጇ ውስጥ የገቡ ወይም የሚገኙ መልካም ዕድሎች ተመላክተዋል። በመጨረሻም ፈተናዎቹን ለማለፍና በመልካም ዕድሎቹም በአግባቡ በመጠቀም አገራዊ ትንሳኤያችንን ከመንታ መንገድ ለማውጣት ያግዛሉ ብዬ ያመንኩባቸው ጥቂት የመፍትሄ ሀሳቦች ለውይይት መነሻ በሚሆን ደረጃ ቀርበዋል።

በክፍል ሦስት በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ስለተካሄደው ትግልና በግሌ ለስህተቶቹም ሆነ ለመልካም ሥራዎቹ ስላበረከትኩት አስተዋፅዖ ጥቂት ነገሮችን ጠቅለል በማድረግ ለማለት እወዳለሁ። በዚህ ክፍል የቀረቡት ሀሳቦች በመስከረም ወር 2010 ዓ.ም. ከኃላፊነት ለመገለል ጥያቄ ካቀረብኩ በኋላ የተለወጠና አዲስ ነገር በመኖሩ የቀረቡ ሀሳቦች አይደሉም:: ይልቁንም ከኢትዮጵያ ሚሌኒየም አከባበር ማግስት ጀምሮ በመንግሥትና ድርጅት ኃላፊዎች በድል የመኩራራት ዝንባሌ መከሰት እንደጀመረ በመታዘብ ያቀረብኳቸው ናቸው። አንዳንዶቹ ሀሳቦች በየውይይት መድረኩ ቢቃል የተነሱ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከመለስ ጋር በመወያየትና ከ2002 ዓ.ም. ክረምት ጀምሮ ቢያንስ በየዓመቱ በጉዳዩ ላይ የሚያተኩር አንድ ጽሁፍ በማቅረብ የተነሱ ነበሩ። ሌሎቹ ደግሞ ከ2004 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ በየዓመቱ በርከት ያሉ ፅሁፎች በማቅረብ የሚመለከታቸው አካላት እንዲወያዩበት ተነሳሽነቱን በመውሰድ የተራመዱ ናቸው:: ውስጣዊ መድረኮች የሀሳብ ግብይት የሚካሄድባቸው ቀዳሚ መድረኮች ናቸው ብሎ እንደሚያምን ማንኛውም ሰው፣ ሌላ የውጭ መድረክ ሳልፈልግና ሳልጠብቅ በዲስፕሊን ለሚመለከተው አካል በቀረቡት ሰነዶች ያራመድኳቸው፣ የተከራከርኩባቸውና

በሀሳብ ትግልና የይዘት ብልጫ ሳይሆን በአስተዳደራዊ መንገድ የተረታሁባቸው ናቸው። ስፔናዊው ሚጉዌል ደ ኡናሙኖ "ታሸንፍ ይሆናል፣ ነገር ግን ማንንም አታሳምንም" እንደሚለው መሆኑ ነው።

በእያንዳንዳችን ውስጥ ይብዛም ይነስም እውነትና እውቀት አለ። ስለዚህም የእውቀትም ሆነ የእውነት ሞኖፖሊ ያለው ሰው የለም ብዬ አምናለሁ። ስለዚህም ሀሳቦች በነጻ መድረክ የሚንሸራሸሩባቸው ዕድሎች ያለማቋረጥ መስፋት ይገባቸዋል። ኢህአዴግን እዚህ ደረጃ ላይ ያደረሰው ተወያይቶና ተመካክሮ መሥራት መሆኑ ተዘንግቶ የምንሳተፈበት መድረክ እየጠበበ፣ በትግሉ ሂደት ያካበትነውን ልምድና የማስተዋል ጥበብ በአግባቡ ሊጠቀምበት የሚሻ አመራር በቁጥሩ እየተመናመነ ሲሄድ፣ በየመድረኩ እንደ ተቀናቃኝ ሳይሆን እንደ ሀሳብ ቋት (Resource Person) እንድንታይ ያቀረብኩት ተማጽኖ በተደፈኑ ጆሮዎች ላይ መውደቁን እያረጋገጥኩ መጣሁ። ውስጣችንን በውል ለማያውቁ የውጭ ታዛቢዎች ሥርዓቱን ከኋላ ሆነን የምናሽከረክረው እኛ ተደርገን የምንታይ ቢሆንም ተመካክሮ መሥራት በሌለበትና መገለል በበዛበት ሁኔታ ስያሜው ተሠጠን። በዚህ ሂደት ሐሳቦቹን በውስጥ መድረክ ለማራመድ የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ እጅግ በአብዛኛው ሲከሽፉ "እብደት አንድን ነገር ደጋግመው እየሰሩ የተለየ ውጤት መጠበቅ ነው" የሚለው የአልበርት አይነስታይን ምክር ወደልቦናዬ ዘልቆ ገብቶ ሌላ መንገድ ማማተሬ አይቀሬ ሆነ። ተደማጭነት በሌለባቸው ጠባብ መድረኮች በሀሳብ የመግጠም ዕድል እያነሰ ሲሄድ ትክክልም ይሁን ስህተት በውስጤ ያሉትን ሀሳቦች በመፅሐፍ መልክ አሳትሞ ሁሉም እንዲያውቃቸው ማድረግን የተሻለ ሆኖ አገኘሁት።

በዚህ መጽሐፍ የቀረቡት ፈተናዎችም ሆኑ መልካም ዕድሎች የሁላችንም የሥራ ውጤቶች ናቸውና የእኔና የመሰሎቼ ተሳትፎ በተረጋገጠበት አኳኋን የመጡ እውነታዎች መሆናቸውን ሳልገልፅ አላልፍም። ስለሆነም እኔን ጨምሮ በስኬቶቹ በጋራ የምንኮራውን ያህል፣ በድክመቶቹም ታላፊነትንና ተጠያቂነቱን በጋራ እንወስዳለን። በግሌ ትልልቅ ስህተቶች ከመፈፀም ተቆጥቤ እንደኖርኩ ህሊናዬ ቢነግረኝም፣ ድክመቶች ብዬ በማቀርባቸው ጉዳዮች ሁሉ፣ አንድም አሚልቶ ባለመታገል አለያም በተለይ ደግሞ ወደኋላ በመሰላቸት አስተዋፅኦ ያላደረግኩበት ነገር ትንሽ ነው ብዬ አላምንም። ማርቲን ሉተር ኪንግ "ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ዝምታን የመረጥን ቀን ሕይወታችን ያበቃል" ይላል። በጠቃሚ ጉዳዮች ላይ ከፊል ወይ ሙሉ ዝምታን በመረጥንበት ጊዜ ሁሉ የፈራነው ደርሷልና በዚህ መጽሐፍ የማነሳቸው ድክመቶችም ሆኑ ጥንካሬዎች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት እኔንም ይመለከታሉ።

በመጽሐፉ ውስጥ የአዝማሚያ ትንታኔ በማድረግ ላይ ለመወሰን ከፍተኛ ጥረት ያደረግኩ ቢሆንም፣ በእኛ አገር በኃላፊነት ላይ በሚገኝ ግለሰብ ደረጃ ባልተለመደ አኳኋን በሂደቱ ውስጥ በበጐም ይሁን በድክመት የየራሳቸውን ሚና የተጫወቱ አንዳንድ ግለሰቦችና ተቋማት ከፈጸሙት ወይም ካራመዱት ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተወሰኑ መረጃዎች ለማቅረብ ሞክሬያለሁ። በዚህ መሠረት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አገራዊውን ሂደት በአሉታዊ መንገድ የቃኙ ወይም ያልተገባ ተፅዕኖ ያሳረፉበት ሰዎች አግባብ ሆኖ በተገኘበት አጋጣሚ ሁሉ በስም እየተጠቀሱ ከነአቋማቸውና ድርጊታቸው ቀርበዋል። ይህም ከግለሰቦቹ ወይም ተቋሞቹ ጋር ባለኝ ግላዊ ፍቅር ወይም ጥላቻ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ በዚህ የለውጥ ሂደት የነበራቸውን አሉታዊ ወይም አወንታዊ ተፅዕኖ በማሳየት ለወደፊቱ ትምሕርት እንዲወሰድባቸው በማመን ብቻ ነው።

ይህ በኢህአዴግ ውስጥ እስካለን ድረስ በውስጥ ማለቅ ያለበትን ጉዳይ እዚያው መጨረስ ስለማይገባና ስለማይቻል የተመረጠ አቀራረብ አይደለም። ይልቁንም በአንድ በኩል ሕገ-መንግሥታዊው የግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር እየሸሸን ባለበት በዚህ ወቅት ተገቢውን ድፍረት በማሳየት ወደግልጽነትና ተጠያቂነት ሥርዓት ለመመለስ እንድንችል የተመረጠ አቀራረብ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፌዴራልና በሁሉም ክልሎች የምታዘበውን የማን አለብኝነት አዝማሚያ በግልጽ አደባባይ መግጠም በትዕቢት ለተሞሉ መሪዎች የዴሞክራሲያችንን ወርድና ስፋት ለማሳየትና እያንዳንዳችን ለምንወስነው ውሳኔ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንደማይቀርልን ለማስገንዘብ ጭምር ነው። ታላቁ የግሪክ ፈላስፋ ፕሌቶ "የምጨነቀው ለአሁኑ ሳይሆን ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ ለሚኖረው ስሜ ነው" እንዳለው፤ ዛሬን ብቻ እያሰቡ፣ ሕይወታቸውን ያለ ትህትና ለሚኖሩና ለሚመሩ ሰዎች ሁሉ የፍርድ ቀን እዚሁ ምድር ላይ እንደሚጀምር ለማስገነዘብም ጭምር ነው። ታዋቂው አልጄሪያዊና ፈረንሳዊ ፈላስፋ አልበርት ካሙ "የመጨረሻውን የፍርድ ቀን አትጠብቅ፣ እዚሁ በምድራችን ላይ በየቀኑ እየተፈፀመ ነውና" ይላል። እናም የፍርድ ቀንን ከሰማይ ሲጠብቁ ጊዜ ያላቸው ለሚመስላቸው ሁሉ ማኅበራዊ ብይንን እዚሁ በምድር ላይ ከቅርባቸው እንደሚያገኙት ለማሳየትም ጭምር ነው። አለዚያማ ግለሰቦች የአገር መነጋገሪያ ርዕሰ ጉዳይ መሆናቸውን ከእኔ በላይ ማን ሊጠላ ይችል ኖሯል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያቀረብኳቸው አንዳንድ ድምዳሜዎች ላይ ለመድረስ በለውጥ ጉዞው ውስጥ በጋራ የተፈፀሙና የሚታወቁ እንዲሁም የግለሰብ አንጡራ ሀብት ያልሆኑ መረጃዎችን የተጠቀምኩ ቢሆንም፣ በአዝማሚያ ትንተና ላይ በአስተያየትና አቋም መልክ የቀረቡት ሀሳቦች ሁሉ የራሴ የግል አስተያየቶች ብቻ ናቸው። በዚሁ ልክ ደግሞ

ላቀረብካቸው ሀሳቦችና አስተያየቶች በሙሉ የግል ኃላፊነትን እወስዳለሁ::

በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ ብዙ ሰዎች የተለመደ ድጋፋቸውን አድርገውልኛል። ከማንም በፊት በትየባ የተባበሩኝን ስንዱ ምሕረቴና ዓለም፣ ተደጋጋሚ የአርትኦት ሥራዎች የጠየቁትን ድካም ሳይሰለቹ በመወጣት ለአንባቢያን እንዳደርሰው አግዘውኛልና ከፍ ያለ ምስጋና ይድረሳቸው። ረቂቁን በማንበብ በጽሁፍና በቃል ጠቃሚ አስተያየት የለገሳችሁኝ ታደሰ፣ ህላዌ፣ መዝሙር፣ አሸናፊ፣ ሳሙኤል፣ ታምራት፣ ቢንያም፣ ፀደቀ፣ በቋንቋ አርትዖት የተባበራችሁኝ ጋሽ አማረ ማሞና ብሥራት፣ ከመጽሐፉ ላይ ተነቅሰው ለሚወጡ ስህተቶች ኃላፊነቱ የእኔ ቢሆንም ለትክክለኛ ሀሳቦችና ለቋንቋው ጥራት እናንተም ድርሻ ነበራችሁና በድጋሚ ላመሰግን እወዳለሁ። ስለመጽሐፉ ህትመት ሙያዊ፣ እንዲሁም ወንድማዊና የእህትነት ምክርና ድጋፍ ለሰጣችሁኝ ፍኖተ፣ ናኒ፣ ጀሰን፣ አስፍሓ፣ ሰሎሞን፣ ዓለምና አስመሮም እንዲሁም ከጐኔ ላልተለያችሁት ልጆቼ፣ መላ ቤተሰቦቼና ሌሎችም በስም ያልጠቀስኳችሁ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ውዷ የትዳር አጋሬ አሲ ይህ መጽሐፍ ያላንች ድጋፍና ተሳትፎ እዚህ አይደርስም ነበር። ሰዎች ለአንድ መጽሐፍ ምን ያህል እጅ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ በደራሲነት እንደሚመዘገቡ ባለማወቄ ብቻ የጋራ ደራሲነትን ባላካፍልሽም በላይኛው ሽፋን ላይ በረከትና አሲ ተብሎ ቢፃፍ እንደማይበዛብሽ አምናለሁ። ከባዶቹን የሕይወቴን ቀናት ባሰብኩ ቁጥር ያላንች ብርታት በአገራችን ከባድና የተወሳሰበ ፖለቲካ ይህን ያህል ዓመታት መዝለቄን እጠራጠራለሁ። እናቴ ለምን ከእኔ ከልጇ በላይ አንችን ትወድሽ እንደነበረ በጣም የገባኝ አሁን ነው። ኑሪልኝ።

በረከት ስምኦን

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

የመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት፤

ምዕራፍ አንድ፣ የግንቦት ዋዜማና የግንቦት ሰሞን እውነታዎች፣ 3

ምዕራፍ ሁለት፣ በአዲሲቱ ኢትዮጵያ የድኅረ ሰማንያ ሦስት የለውጥ እውነታዎች፣ 26

ምዕራፍ ሦስት፣ ለመሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ የተካሄደው ትግል፣ 73

ምዕራፍ አራት፡- ለመልካም ጉርብትና የተካሔደው ትግልና ውጤቱ፣ 138

ምዕራፍ አምስት፡- በስኬትና ፈተናዎች የተሞሉት የመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት፤ 162

ክፍል ሁለት 179

አሥራ አምስት ዓመታት በተሃድሶ አቅጣጫ፤

ምዕራፍ ስድስት፣ ጀማሪ ካፒታሊዝምና የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት እንደ ሥርዓት አደጋ፣ 181

ምዕራፍ ሰባት፣ የስድሣዎቹና የሰባዎቹ ትውልድ የሩብ ምእተ ዓመት ትግል ትሩፋቶች፣ 210

ክፍል ሦስት 237

የኢትዮጵያን መጻኢ ዘመን የሚወስኑ ፈተናዎችና መልካም ዕድሎች፣

ምዕራፍ ስምንት፣ የሩብ ምእተ ዓመት የዴሞክራሲ ሙከራና የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ፈተናዎች፣ 239

ምዕራፍ ዘጠኝ፣ ልማታዊ መንግሥታትን የፈተኑ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ሁሉ ኢትዮጵያንም፣ 295

ምዕራፍ አሥር፣ ዓለም አቀፍ ሁኔታውና ተፅዕኖዎቹ፣ 358

ምዕራፍ አሥራ አንድ፣ ኢትዮጵያና በእጇ የገቡ መልካም ዕድሎች፣ 380

ምዕራፍ አሥራ ሁለት፣ ጥቂት ሀሳቦች ከመንታ መንገድ በፍጥነት ለመውጣት፣ 408

ምዕራፍ አሥራ ሦስት፣ ማጠቃለያና መሰናበቻ ወግ፣ 416

ክፍል አንድ፤

የመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት፤

"ገና ድሮ በወጣትነቴ 'የታሪክን ትርጉም' የማወጅ ብቃት እንዳለኝ አድርጌ የመመልከት ድፍረቱ ነበረኝ። አሁን ግን የታሪክ ትርጉም ተፈልጐ ሊገኝ እንጂ ሊታወጅ እንደማይችል ተገንዝቤያለሁ። አቅማችን የፈቀደውን ያህል ታሪክ ምን ማለት እንደሆነ ለመተርጐም ስንሞክር፣ ሁሌም ቢሆን ለሙግትና ለተለያዩ ትርጉሞች ክፍት መሆኑን በመቀበል ሊሆን ይገባል። የእያንዳንዱ ትውልድ አስተዋጽዖ የሚመዘነው፣ በአንድ በኩል የሰው ልጅችን ሕይወት የሚፈትኑ መሠረታዊና ከባድ ጥያቄዎችን ለመጋፈጥ በነበረው ዝግጁነት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ የነበረው አመራር የሚወስደው እርምጃ የረኸርም ጊዜ ውጤት ምን እንደሆነ ለማወቅ ችሎታው ባልነበረበት የማለዳ ወቅት፣ ለእነዘህ ፈተናዎች በሰጠው ምላሽ ነው።"

ሔንሪ ኪሲንጀር

ምዕራፍ አንድ፣

የግንቦት ዋዜማና የግንቦት ሰሞን እውነታዎች፣

ሃያኛው ከፍለ ዘመን ከመገባደዱ ከአሥራ ሰባት ዓመታት በፊት ታሪካዊቷና የብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አገር የሆነችው ኢትዮጵያ ከደርግ አስከፊ ወታደራዊ አገዛዝ ተላቀቀች፡፡ የደርግ መንግሥት በመረጠው የኃይልና የግጭት መንገድ የተረታበት ይህ ወቅት በአገራችን ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም አቀፍ ሁኔታውም ላይ ከፍተኛ ለውጥ የተከሰተበት ነበር፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ሩብ ምእተ ዓመት በተለይም ደግሞ በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት (1983-2010) በኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ በትከክል ለመገንዘብ ከደርግ ውድቀት ጥቂት ቀደም ብሎ የነበሩትን ሁኔታዎች በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርጐ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

የትጥቅ ትግሉ ለዓመታት ከአዲስ አበባ በስተሰሜን ታጥሮ ከቆየ በኋላ ወደመሐልና ምዕራብ ኢትዮጵያ መዛመት የጀመረው ከግንቦት 1983 ዓ.ም. ጥቂት ቀደም ብሎ ነበር፡፡ በሰማኒያዎቹ መጀመሪያ አጠቃላዩን አገራዊ የለውጥ ሂደትና የወቅቱ ዋነኛ መገለጫ የነበረውን ጦርነቱን የሚመራበትን ፖለቲካዊና ወታደራዊ መሥመር በጥራት ነድፎ ደረጃ በደረጃ ተግባር ላይ ያዋለው ኢህአዴግ መጀመሪያ ትግራይን፣ ቀጥሎ በዘመቻ "ሰላም በትግል" አማካይነት ወሎን እንዲሁም ደቡብ ጐንደርን ከደርግ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ አላቀቀ። በመርሳ፣ ደብረታቦርና ሰሜን ሸዋ ግንባሮች ደርግ የሰነዘራቸውን መልሶ ማጥቃቶች ካከሸፈ በኋላ ደግሞ ከ1983 ዓ.ም. መጀመሪያ ጀምሮ ለወሳኙ ስትራቴጅያዊ ማጥቃት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ጀመረ። በዚህም ደቡብ ወሎና ከፊል ሰሜን ሸዋን በዘመቻ "ዋለልኝ"፣ ከፊል ሰሜን ጐንደርንና ጐጃምን ደግሞ በዘመቻ "ቴዎድሮስ" ከደርግ አገዛዝ ነጻ አወጣ። ኢህአዴግ ከአዲስ አበባ በስተሰሜን የነበረውን መላውን የአገሪቱን ከፍል ነጻ ያወጣባቸው እነዚህ ዘመቻዎችና የደርግን እድሜ ለማሳጠር የሰነዘረው ስትራቴጅያዊ ማጥቃት በበቂ ዝግጅትና የአቅም ግንባታ የተፈጸሙ ነበሩ፡፡

ሠራዊቱ ከአዲስ አበባ በስተሰሜን ያሉትን አካባቢዎች በአጭር ጊዜ ከተቆጣጠረ በኋላ ዋና ከተማዋን ጨምሮ መላ አገሪቱን ከደርግ የጭቆና አገዛዝ ነጻ በማውጣት ሥርዓቱን ለማስወገድ መንቀሳቀስ ጀመረ። ይህን ለማድረግ የሚያስችለውን ስትራቴጂያዊ ማጥቃት በደብረ ብርሃን፣ በጐሐ ጽዮንና በምዕራብ ኢትዮጵያ በወለጋና አምቦ መሥመር በመሰንዘር በእነዚህ ሦስት ግንባሮች በኩል ወደአዲስ አበባ ገሰገሰ፡፡ በምዕራብ ኢትዮጵያ የተካሔደው

ዘመቻ "ቢሊሱማ ወልቂጡማ" የሚል አዲስ ምዕራፍ አብሳሪ ስያሜ የተሰጠው ነበር። በዚህ ዘመቻ ባልተመጣጠነው የየአካባቢው የተቃውሞ ንቅናቄ ሳቢያ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ታጥሮ የነበረው ህዝባዊ የትጥቅ ትግል ቅጽበታዊ በሚባል ፍጥነት ወደኦሮሚያ ዘልቆ ገባ። "እያንዳንዱ ህዝብ ከድኅነትና ኋላቀርነት በአስተማማኝ ደረጃ የሚላቀቀው በራሱ ትግል ነው" ለሚለው ኢህአዴግ፣ ትጥቅ ትግሉ ከሰሜን ኢትዮጵያ ወጥቶ ወደኦሮሚያ መግባቱ ልዩ የታሪክ ምዕራፍ መከፈቱን የሚያበስር ነበር።

በምዕራብ ኢትዮጵያ የተከፈተውን ዘመቻ ተከትሎ ጥቃቱን ከወሊጋ በኩል የሰነዘረው የኢህአዴግ ሠራዊት፣ በኢትዮጵያዊው ገኮብ[1] በጄኔራል ኃየሎም አርአያ (ከሕወሓት)፣ አቶ አዲሱ ለገሠና ጄኔራል ሥዩም ሐጐስ (ከኢህዴን) እና ጄኔራል አባዱላ ገመዳ(ከአህዴድ) በመሳሰሉ ታጋዮች የተመራ ነበር። ሠራዊቱ በመንገዱ ላይ ያገኘውን የደርግ ወታደራዊ ኃይል እየጠራረገ፣ በአጭር ጊዜ አምቦ ከተማ ለመድረስ አፍታም አልወሰደበትም። ከአዲስ አበባ በስተሰሜን ምሥራቅ የነበረውና በጄኔራል ሳሞራ የኑስና በጄነራል ጻድቃን ገብረ ትንሳኤና በእነ ጄኔራል አበባው ታደሰ፣ የተመራው ሠራዊት ደግሞ በሰሜን ሸዋ ከተሞች ላይ መሸጉ የነበረውን ሠራዊት በማጥቃት፣ በአዲስ አበባና በኢህአዴግ ሠራዊት መካከል የነበረውን ርቀት ከቀናት ወደሰዓታት ጉዞ ዝቅ አደረገው። ሠራዊቱ በደርግ ወታደራዊ የጊዜ አገላለጽ በማንኛውም ሰ-ሰዓት (D-Day) የአገሪቱን ዋና ከተማ እንዲይዝ ቢታዘዝ አፍታ በማይወስድበት በሰሜንና ደቡብ ሸዋ ወረዳዎች ተቀመጠ። በመጨረሻም ኢህአዴግ በጥር ወር 1983 ዓ.ም. ባካሔደው የመጀመሪያ ጉባዔ የወሰነውን ስትራቴጅያዊ ማጥቃት በሦስቱ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ።

ከግንቦት መጀመሪያ አንስቶ በእነዚህ ግንባሮች የደረሰበትን የተቀናጀ ጥቃት መቋቋም የተሳነው የደርግ ሠራዊት ቀስ በቀስ እየተበተነ ወደአዲስ አበባ አመራ። ጉልበት ያለው የሞት ሞቱን ጠብመንጃውን እንደተሸከመ፣ አቅም ያነሰው መሣሪያውን መሬት ለመሬት እየጐተተና በየስርቻው እያዝረከረከ ወደከተማዋ ተመመ። የራበውና የተጠማው መሣሪያውን በምግብና ውሃ እየለወጠ፣ የሞት ሞቱን ወደየትውልድ መንደሩ አመራ። አዲስ አበባ በተራቡና በተጠሙ፣ መንፈሳቸውና አካላቸው በደከመ የመንግሥት ወታደሮች ተሞላች። አንዳንዶቹ ከነትጥቃቸው፣ ብዙዎቹ ደግሞ ባዶ እጃቸውን የነበሩ ቢሆንም በከተማዋ ላይ የሰብዓዊ ቀውስ ጥላ አንጣበበ። ደራሲ ባሴ ሀብቴ "ጭጋግና ጠል" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ጽሁፍ በግንቦት 1983 ዓ.ም. ዋዜማ የነበረውን ይህን ሁኔታ፦

> "ሐሙስ ወደማታና አርብ-አዲስ አበባ በተጐሳቆሉ የመንግሥት ወታደሮች ተሞላች። ሁለት አውቶማቲክ ጠብመንጃ በቀኝና በግራ ትከሻቸው ያነገቱ፣

ላውንቸር የተሸከሙ፣ ባዙቃ ተሸክመው አውቶማቲክ ጠብመንጃ የደረቡ፣ ...ሁለት አውቶማቲክ ጠብመንጃ አንግተው ሦስተኛውን መሬት ለመሬት የሚጐትቱ፣ ቸር-ር...ር...ር...ር እያደረጉ የሚጓዙ፤ ወታደር... ወታደር... ወታደር፣ አዲስ አበባ ወታደር በወታደር ሆነች፡፡ ወታደር-ያደፈ ፊልድ ጃኬት፣ የተበጣጠሰ ፊልድ ጃኬት፣ የወየበ ፊልድ ጃኬት፣ ያደፈ ቅጠልያ፣ የወየበ ቅጠልያ፣ አፈር የመሰለ ቅጠልያ፣ አፈር የመሰለ፣ የተጐሳቆለ ወታደር መጥቶ ፈሰሰ፡፡ ዓይኔ እሰው ላይ ባረፈ ቁጥር ያ ሰው ወታደር ሆነ፡፡

...አዲስ አበባ ሥጋት ላይ ወደቀች፡፡ አንዱ- 'ይኸ የገባው የእኛ ወታደር ነው ብላችሁ ነው?... እነሱ ናቸው፡፡ በቃ ከተማውን ያዙት' ይላል፡፡ ሌላው 'ይኸ ሞራሉ የወደቀ ወታደር ፈጀን፡፡ ወታደር ሞራሉ ወድቆ ከሥርዓት ውጭ ከሆነ፣ ...በዚያ ላይ ተርቧል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ መሣሪያውን እንደያዘ ነው፡፡ አስቡት፣- አለቅን፣...' ይላል፡፡"[2] በማለት ገልጾት ነበር።

ይህ የባሴ ሀብቴ ሥዕላዊ አገላለጽ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይወሰን፣ በመላ አገሪቱ የነበረውን አስፈሪ ሁኔታና የወቅቱን የሥጋት ሥነ-ልቦና በትክክል ያመላክታል፡፡ በህዝቡ ውስጥ ይታይ እንደነበረው ስጋት ይህ የታጠቀ፣ ተስፋ የቆረጠና ጦርነት ላይ ለማገደው የደርግ ሥርዓት የመረረ ጥላቻ ያዳበረ ወታደር፣ በበቀል ስሜት ተነሳስቶና በጠብመንጃው ተማምኖ መተኮስ ቢጀምር ጉዳቱ ከፍ ያለ ይሆን ነበር፡፡ ደግነቱ በማያምንበት ጦርነት ተገዶ የገባው ወታደር ከሽንፈት ወደሽንፈት እየተሸጋገረ ዙሪያ ገባው ሁሉ ጨለማ የሆነበትና ሞራሉ ከፉኛ የወደቀ ነበር፡፡ እንደወታደር ቆፍጣና መሆኑ ቀርቶ በመሩት አቅጣጫ የሚጓዝና ወደሳቡትም የሚሔድ ሆኗል፡፡ በዚህ ላይ አንዳንድ የከተማው ወጣቶችና ኗሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የወታደሩን ትጥቅ እየሰበሰቡና ህዝቡን አስተባብረው ምግብና ውሃ እያቀረቡ፣ ከተማዋን ከሰብዓዊ ቀውስ ሲታደጓት ቆዩ። በመጨረሻም በከተማዋ ዙሪያ የነበረው የኢህአዴግ ሠራዊት ግንቦት ሃያ ላይ ከተማዋን ተቆጣጥሮ የተሰጋው የሰብዓዊ ቀውስ ሳያጋጥም ወደሰላምና መረጋጋት ማምራት ተቻለ፡፡

ሠራዊቱ ወደአዲስ አበባ በመገስገስ ላይ በነበረበት በዚህ ወቅት፣ ቀደም ሲል በደርግና በኢህአዴግ መካከል ተጀምሮ የተቋረጠውን የሰላም ድርድር እንደገና ለማስቀጠል ኢህአዴግ በወሰደው ተነሳሽነት አዲስ የድርድር ሥምምነት ተደርሶ ነበር። ይህም ኢህአዴግ በዚህ ወቅት በጦርነቱ ማሸነፍ እንደሚችል እርግጠኛ የነበረ ቢሆንም፣ የተቻለውን ያህል ሰብዓዊና ቁሣዊ ውድመትን ለመቀነስ በማሰብ እንደገና ባቀረበው የሰላማዊ መፍትሔ ድርድር ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። የድርድሩ ሀሳብ በደርግ በኩል ተቀባይነት በማግኘቱ የኢህአዴግና የህዝባዊ

ግንባር ሓርነት ኤርትራ ልዑካን በግንቦት መጀመሪያ አካባቢ ለአዲስ ድርድር ወደእንግሊዝ አመሩ። በመለስ ዜናዊ የሚመራው ቡድን ኢህአዴግን በመወከል በትግል ነጻ ከወጣው መሬት፣ አነግ በሌንጮ ለታ፣ በወቅቱ የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩት በአሻግሬ ይግለጡ መሪነት የሚደራደረው የልዑካን ቡድን ደግሞ ደርግን በመወከል ከአዲስ አበባ ለንደን ገቡ። የሚወከሉት መንግሥት ገና ድርድሩ ሳይጀመር መፍረሱንና ሁኔታው እንዳበቃለት የተገነዘቡት የደርግ ልዑካን፣ ተልዕኳቸውን ትተው በዚያው ጥገኝነት መጠየቅ ጀመሩ። የደርግ ልዑካን የቁራ መልዕክተኛ መሆናቸውን የታዘበውና የአገሪቱን የዕለት ተዕለት ሁኔታ ለንደን ላይ ሆኖ ይከታተል የነበረው ታጋይ መለስ ዜናዊም የደርግ ነገር ሙሉ በሙሉ እንዳበቃለት አረጋገጠ። በዚህ ወቅት ማንኛውንም ሰብዓዊ ቀውስ ለማስወገድ በፍጥነት አዲስ አበባን መቆጣጠር እንደሚገባም አመነበት። ስለዚህም እዚያው ለንደን ላይ እያለ ሠራዊቱ ሳይውል ሳያድር ወደአዲስ አበባ ከተማ እንዲገባ መመሪያ ሰጠ። እርሱ ራሱ ደግሞ በወቅቱ በተፈጠረው ያለመረጋጋት ሁኔታ ኬንያ ላይ ተጠልለው የነበሩት የኢትዮጵያ አየር መንገድ አይሮፕላኖች ሥራ እስኪጀምሩ ሳይጠብቅ ከሱዳን መንግሥት በተዋሳት አይሮፕላን ተሳፍሮ ወደአዲስ አበባ አመራ።

ከከፍተኛው ዕዝ ግልጽ መመሪያ የተላለፈለት የኢህአዴግ ሠራዊት ከሁሉም አቅጣጫ ሌሊቱን ተጉዞ ንጋት ላይ ዋና ከተማዋን ተቆጣጠረ። ኢህአዴግ አስቀድሞ ባካሔደው ማጥቃት ወሳኙ ጦርነት ከከተማው ውጭ ተጠናቆ ስለነበር፣ በቤተ-መንግሥትና በጣም ጥቂት በሚባሉ ቦታዎች ካጋጠመው እዚህ ግባ የማይባል ተቃውሞ በስተቀር፣ አዲስ አበባ ያለብዙ ግጭትና ደም መፋሰስ ነጻ ወጣች። ውጊያው ፈረንሳዮች "ኩ ደ ግረስ" የሚሉት ዓይነት፣ ለጥቂት ሰዓታት የተካሔደ የማሳረጊያ ግጭት ብቻ ነበር፡

እነሆ ወታደራዊው ሥርዓት አገሪቱን አንቀጥቅጦ ከገዛ ከአሥራ ሰባት ዓመታት በኋላ በኢህአዴግ በተመራው ህዝባዊ ትግል ተገረሰሰ። የሰላማዊ ፖለቲካዊ ውድድር ዕድልን ከልከሎ ተቃውሞን ሁሉ በኃይል ለማስወገድ ይሻ የነበረው ወታደራዊ አገዛዝ ከበርካታ የግፍ አገዛዝ ዓመታት በኋላ በመረጠው የግጭት መንገድ ተረታ። በእርግጥም ይህች ታሪካዊ አገር በከባድ ተጋድሎ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዋዜማ ላይ ከደርግ መንጋጋ ተመንጥቃ ነጻ ወጣች። የህዝቦቿ ሉዓላዊነት ተከብሮ፣ አገራቸውን በራሳቸው ፍላጐት ሊመሩና ሊለውጧት የሚችሉበት አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ። ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ኢትዮጵያ ከረዥም የማሽቆልቆል ጉዞ በኋላ አዲስ የፊት ማርሽ ያስገባችበት የለውጥ መነሻ ነጥብም ሆነ።

ዓለም በገበያ አክራሪው የኒዮ - ሊበራል ርዕዮት የተናጠችበት ሰሞን፣

በአገር ውስጥ ከተካሔደው ከዚህ መሠረታዊ ለውጥ ጥቂት ቀደም ብሎና በዚያው ሰሞን የነበረው ዓለማዊ ሁኔታም ከፍተኛ መለዋወጥ የታየበት ነበር። በዓለም አቀፍ ደረጃ ነገር ዓለሙ መገለባበጥ ከጀመረ ቢሰነባብትም፣ ቀዝቃዛው ጦርነት በምዕራባውያኑ ድል አድራጊነት የተደመደመው ለሰባ ዓመታት ያህል የምዕራቡ ዓለም ተፎካካሪ የነበረው የሶሻሊስቱ ጐራ በ1982 ዓ.ም. እንዳልነበረ ሆኖ ሲፈረካከስ ነው። አሜሪካኖች ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ ለበላይነት የተፎካከሩዋቸውን ጀርመኖች በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ካሸነፉና ካዳከሙ በኋላ ዋነኛ ተፎካካሪያቸው በሶቭዬት ሕብረት የተመራው የምሥራቁ ጐራ ነበር። በዚህ የተነሳም በሁለቱ ታላላቅ የዓለም ጦርነቶች ብዙም ጉዳት ሳይደርስባቸው የበላይነትን የተጐናጸፉት አሜሪካኖች ከሃያኛው ከፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ውድድራቸው ከምሥራቁ ጐራ ጋር ሆነ። ዓለም በሁለት ርዕዮተ ዓለሞች ተከፍላ የተናቆረችበት ይህ ወቅት ከመለስተኛ ግጭቶች አልፎ ሦስተኛውን የዓለም ጦርነት ባያስከትልም በምዕራባውያኑና በምሥራቃውያኑ መካከል ለአርባ አምስት ዓመታት ያህል የዘለቀ ቀዝቃዛ ጦርነት የተካሔደበት ነበር።

በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በተካሔደው በዚህ ከባድ ፉክክር ምዕራባውያኑ ቀልጣፋና ተነቃናቂ ኢኮኖሚ ገንብተው ሲወጡ፣ የምሥራቁ ጐራ ደግሞ ግዙፍና ብዙም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያልነበራቸውን የጦር መሣሪያ አምራች ኢንዱስትሪዎች ታቅፎ ቀረ። ይኸው የሶሻሊስት ነን ባይ አገሮች ጐራ በኢኮኖሚ ልማት እየተዳከመ መሔዱን ተከትሎ ፈጽሞ መላወስ ተሳነው። በከባድ ችግር መዋጥ የጀመሩት የራሱ ህዝቦችም ሳይንህን ለአፈር ይሉት ጀመር። የማታ ማታ ደግሞ እ.ኤ.አ በ1989 ሥርዓቱ መልሶ ሊያንሰራራ በማይችልበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ከውስጥ ፈነዳ። ለአርባ አምስት ዓመታት የምዕራቡን ዓለም ከምሥራቁ ለይቶ የነበረው የበርሊን ግንብ በራሳቸው በምሥራቃውያኑ ህዝቦች ተናደ። ምዕራባውያኑም ቀዝቃዛውን ጦርነት በበላይነት አጠናቀቁ። የዚህ ጐራ ፈታውራሪ የነበሩት አሜሪካኖች በቅርብ ርቀት የሚከተላቸው ተፎካካሪ በሌለበት ዋነኛው የዓለማችን ልእለ ኃያል አገር ሆነው ወጡ።

የምዕራቡ ዓለም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሊበራል መሠረቱን ሳይለቅ፣ በሶሻል ዴሞክራሲና የበጐ አድራጐት መንግሥት (Welfare State) አስተሳሰብ ይመራ የነበረ ቢሆንም፣ ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ግን ለዘብተኛነቱን ትቶ በዘመናችን ኒዮ-ሊበራላዊ ወይም የገበያ አክራሪነት በመባል በሚታወቀው ርዕዮተ-ዓለም ይመራ ነበር። በመሆኑም፣ ከበርሊን ግንብ መፍረስና ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ያለው ዓለማዊ ሂደት፣ አንዳንዶች እንደሚሉት፣ በዓለማችን ኒዮ-ሊበራል የጥፋት ኃይል (Counter Revolution) ያሸነፈበትና የበላይነቱን የተቀዳጀበት የኋልዮሽ ጉዞ ነው። በእርግጥም በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ ሠራተኛ

ህዝቦች፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በትግላቸው የተቀዳጁዋቸውን ድሎች በመቀልበስ ላይ ያነጣጠረው ኒዮ-ሊበራሊዝም፣ በባሕርይው በዴሞክራሲና በህዝቦች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ነው። ከራሱ አገር ህዝቦች አልፎ የታዳጊ ዓለም ህዝቦችን ጭምር ለባሰ ጉዳት የዳረገና የሚዳርግም ነበር። ይህን በማስመልከት ታዋቂዋ የልማታዊ መንግሥታት ተንታኝ አሊስ አምስደን የኒዮ ሊበራሊዝም ዋነኛ አራማጅና የበላይ ጠባቂ ስለሆነችው አሜሪካ፡-

> "ከ1950-80 ድረስ በነበረው የአሜሪካን የመጀመሪያው ኢምፓየር የተመራው ምዕራፍ የዓለማችን ወርቃማ ዘመን ሊባል ይችላል። [በዚህ ምዕራፍ] አፍሪካና መካከለኛውን ምሥራቅ ጨምሮ የታዳጊ አገሮች ዕድገት አንሰራራ። ከዚህ ጊዜ በፊትም ሆነ በኋላ ተመሳሳይ መሻሻል ያልታየ ሲሆን፣ ዕድገቱ በብሔራዊም ሆነ በነፍስ ወከፍ ገቢ ደረጃ ከየትኛውም የቅኝ አገዛዝ ዘመን የተሻለ ነበር። ስለዚህም የመጀመሪያው የአሜሪካን ኢምፓየር የተከታዮቹን ሕይወት በማሻሻሉ በኩራት ቀና ሊል ይገባዋል። በቀጣዮቹ 30 ዓመታት ግን ሂደቱ በመብረቅ የተመታ ያህል ቆመ። የማታ ማታ ደግሞ በቬትናም ጦርነት፣ በ[1973] ነዳጅ ቀውስ እንዲሁም ከዎል ስትሪት በሚመጣው ርካሽ ብድር እጅ ሞተ። እናም 1970ዎቹ ሲገባደድ ሕይወት ከመጥፎ ወደመቀመቅ ተሸጋገረች። ከፍራንክሊን ሩዝቬልት እስከ ሪቻርድ ኒክሰን ዘመን የነበረው የብልጽግና ዘመን ተንገራግጮ ቆመ። ከሮናልድ ሬጋንና ከማርጋሬት ታቸር ወደሥልጣን መምጣት ጀምሮም ሁለተኛው የአሜሪካ ኢምፓየር ተወለደ። ወዲያውም የብድር ጫናና ቀውስ ድሃ አገሮችን ሰንጎ ያዛቸው። ሁለተኛው የአሜሪካን ኢምፓየር ለቀጣዮቹ 25 ዓመታት የለገሰው ፈውስ አነሰ ቢባል ሳይታደጋቸው ቀረ። ምድራዊው ገነትም ቀስ በቀስ ቦታውን ለምድራዊ ገሃነም ለቀቀ።[3] ማለቷ ይህንኑ ያረጋግጣል።

በዚህ አኳኋን ብቅ ያለው ኒዮ-ሊበራሉ ኃይል የአውሮፓ ሠራተኛ ህዝቦች ከ1945–75 ባካሔዱት ትግል የተጐናጸፏቸውን ድሎች መቀልበሱን ተያያዘው። ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከመቆጣጠሩ ከጥቂት ጊዜ በፊት በዓለማችን የታየው ይህ አዲስ ክስተት፣ በኢትዮጵያም ሆነ በመላው የዓለም ህዝቦች መጻዒ ዕድል ላይ ያልተገመቱ ከባድ ተፅዕኖዎችን ይዞ መጣ።

በአሜሪካን የሚመራው የምዕራቡ ዓለም፣ ይህን የመሰለ ድል ከመጐናጸፉ ኢሥራ አምስት ዓመታት ቀደም ብሎ በቬትናም ጦርነት ከባድ ሽንፈት ደርሶበት ነበር። ኢንዶ-ቻይናውያን "የአሜሪካ ጦርነት" የሚሉት፣ መላው ዓለም ደግሞ "የቬትናም ጦርነት" እያለ የሚጠራው ይህ ጦርነት የተጀመረው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ነው። የጦርነቱ አውድማ የሆነችው ቬትናም መጀመሪያ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ነበረች። በወቅቱ በወታደራዊ ጀብደኝነት የሰከሩት

ጃፓኖች ከልማታዊ ጐዳና አፈንግጠው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መላውን ምሥራቅ እስያ በወረሩ ጊዜ ፈረንሳይ ቬትናምን ጥላ ሸሸች። በፈረንሳይ እግር ተተክታ ቬትናምን ለአራት ዓመታት ያህል ያስተዳደረችው ጃፓን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአሜሪካን ስትሸንፍ ደግሞ እርሷም በተራዋ ቬትናምን ጥላ ለመውጣት ተገደደች። ይህን ተከትሎ ፈረንሳዮች በሸሸት የለቀቁዋትን ቬትናም "ለእኛ ትገባናለች" በማለት እንደገና በቁጥጥራቸው ሥር ለማስገባት ተሯሯጡ። ነገር ግን ከጃፓን ሽንፈት በኋላ ነጻነታቸውን የመጐናጸፍ ሕልም ብቻ የነበራቸው ቬትናማውያን ይህን የፈረንሳይ አስነዋሪ ሙከራ ፈጽሞ ሊቀበሉት አልፈቀዱም። በዚህ ምክንያት ቬትናማውያኑ አገራቸውን ከፈረንሳይ ዳግም ቅኝ አገዛዝ ለማላቀቅ ትጥቅ ለማንሳት ተገደዱ። በፈረንሳይ ቅኝ ገዥዎች ላይ መራር የትጥቅ ትግል ያካሔዱት ቬትናማውያን እ.ኤ.አ. በ1954 በታዋቂው የዲያን ቢያንፉ ውጊያ አሥራ ስድስት የፈረንሳይ ሬጅመንቶችን በመደምሰስ የማታ ማታ አገራቸውን በከፊልም ቢሆን ከፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት ቻሉ።

የቬትናም ጦርነት የመጀመሪያ በሆነው በዚህ ድሉ፣ ፈረንሳይን ያህል ትልቅ አገር፣ በአንድ ትንሽና ያልበለጸገ አገር በአሳፋሪ ሁኔታ ሊሸነፍ እንደሚችል ቢያሳይም፣ ኢትዮጵያ በአድዋ ጦርነት ወራሪውን ጣልያን ድል በነሳች ጊዜ እንደሆነው ሁሉ የቬትናማውያን ድል የበለጸገውን ዓለም መሪዎች አስቆጣ። ድሉ በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከልእለ ኃያላንም በላይ ልቀው የዓለም አለቃ መሆን የጀመሩትን አሜሪካኖች እንደእግር ውስጥ እሣት አንገበገባቸው። በወቅቱ ከሶቭዬት ሕብረት ጀምሮ ወደምሥራቅ እስያ እንደሰደድ እሣት በመቀጣጠል ላይ የነበረው ሶሻሊስታዊ እንቅስቃሴ በዚህ ሽንፈት ይበልጥ እንደሚጠናከር የተገነዘቡት አሜሪካኖች፣ የፈረንሳይን ውርደት እንደራሳቸው ቆጥረው ቬትናማውያንን አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት ለማቆም ወሰኑ። አሊስ አምስደን ቢወርቃማው ዘመን የነበረው የአሜሪካ መንግሥትና የመጠቀ አስተሳሰብ የነበራቸው መሪዎቹ በዚህ ጉዳይ ላይ ስለፈፀሙት የግምገማ ስህተት ያቀረበችው ይህን በግልፅ ያመላክታል። አምስደን፡-

> "ምንም እንኳ ወቅቱ የአሜሪካ ወርቃማ ዘመን የነበረ፣፣ የያኔው ትውልድ መሪዎችም ምንም ያህል ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ፣ ሥነ-ልቦናና የላቀ ብቃት የነበራቸው ቢሆኑም ከጅልነት የማይለይ ስህተት ይፈፅሙ ነበር። የወረቀት ነብር የነበረችውን ሶቭየት ሕብረት እንደእውነተኛ ነብር፣ እውነተኛ ነብር የነበረችውን ቬትናም ደግሞ እንደ ወረቀት ላይ ነብር መቁጠራቸው ይህን ያሳያል"[4] ትላለች።

አሜሪካኖች ከዚህ የግምገማ ስህተት በመነሳት በፈረንሳይ እግር ተተክው ጦርነቱን ቀጠሉበት። ይህም ሆኖ የእነርሱም ዕጣ ፈንታ ተመሳሳይ ውርደት ከመሆን ሊያመልጥ

አልቻለም።

በዚህ ጦርነት አሜሪካኖች በታጋዩ የቬትናም ህዝብ ላይ ያላወረዱት የቦምብ ናዳ አልነበረም፡፡ የተቀጣጣይነት ባሕርይ የነበረውን ናፓልም ቦምብ ጨምሮ፣ በጣም ሰፊ መሬት የመሸፈን አቅም የነበራቸውን ክላስተር (ከአየር ላይ የሚለቀቁና ደጋግመው የሚፈነዱ ብዙ ቦምቦችን የያዘ በርሜል) ቦምቦች፣ እንዲሁም በጨረር የሚመሩ ልዩ ልዩ ተተኳሾች በሰፊው ተጠቅመዋል፡፡ ከአውሮፕላን የሚጣሉ አሥራ ስድስት ዓይነት ቦምቦችና ሃያ አንድ ዓይነት ተመሪ ሚሳይሎችን በመጠቀም የጦርነቱን ውጤት ለመወሰን ተረባርበዋል፡፡ ነገር ግን ለነጻነቱ ቀናዒ በነበረው በቬትናም ህዝብ ከመሸነፍ አላመለጡም፡፡ የቬትናም ህዝቦች አርነታዊ ትግል እንደገና አንድ ትንሽና ያልበለጸገ አገር፣ ሌላው ቀርቶ አሜሪካንን የሚያህል ዋናውን የዓለም አለቃ ሊያሸንፍ እንደሚችል ለሁለተኛ ጊዜ አረጋገጠ፡፡ የድሉ ይዘትና ባሕርይ በግዙፍነት ሳይሆን፣ ባነገብከው ጥያቄ ፍትሃዊነት የሚወሰን መሆኑም ጭምር በግልጽ ተመሰከረ፡፡

ይህን ውድቀት ተከትሎ በአጠቃላይ የምዕራቡ ዓለም፣ በተለይ ደግሞ አሜሪካዊያኑ ለተወሰኑ ዓመታት ለከባድ የሞራል ስብራት ተዳረጉ፡፡ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ ሕብረተሰቡ "የቬትናም ልከፍት" (The Vietnam Syndrome) ተብሎ በሚታወቀው ከባድ ሥነ-ልቦናዊ ቀውስ በመመታቱ ጦርነትንና ማንኛውንም የውጭ ጣልቃ ገብነት እስከመጥላት ደረሰ፡፡ ከቬትናም ጦርነት የተመለሱ የአሜሪካ ወታደሮች ደግሞ ዋናዎቹ የጉዳቱ ሰለባዎች መሆናቸው በአገሪቱ ደረጃ ከባድ ማኅበራዊ ምስቅልቅል አስከተለ፡፡ የማታ ማታ ግን በቬትናም ሽንፈቱ በዓለም ላይ የነበረው ግርማ ሞገስ ተገፎ የቆየው አሜሪካ መራሹ የምዕራቡ ዓለም፣ የምሥራቁን ጐራ መፈራረስ ተከትሎ፣ በምድራችን ላይ የበላይነቱን በውድም በግድም ለማስመስከር የሚችልበት አቅም እንዳለው ለማሳየት ቆርጦ ተነሳ፡፡

አሜሪካኖች በቬትናም ህዝቦች ትግል የፈነጠቀውን አዲስ የትግልና የድል አድራጊነት ተስፋ ለማፍረስ ኢይበገሬነታቸውን በሚያጐሉ የሆሊውድ ፊልሞች እየታገዙ ከባድ ፕሮፓጋንዳ ሲያካሂዱ ከከረሙ በኋላ፣ ሳዳም ሁሴን እ.ኤ.አ. በ1990 ኩዌትን መውረሩ ያልተጠበቀ መልካም ዕድል ፈጠረላቸው፡፡ በእርግጥ የሳዳም መንግሥት አንድን ሉዓላዊ አገር በእብሪት መውረሩ ከባድ ነውርና መሠረታዊ ስህተት ነበር፡፡ ስለዚህም ወረራው እንዲቀለበስ መጠየቅም ሆነ ተባብሮ መቀልበስ ተገቢነት ነበረው፡፡ ነገር ግን የሳዳም ሁሴን ወረራ ለአሜሪካኖች ከዚህም በላይ ዘልቆ የሚሔድ መልካም አጋጣሚ ነበር። በሳዳም ቅሌት የተነሳ በቬትናም ህዝቦች ትግል የደረሰባቸውን ሽንፈትና ከዚያም በኋላ በማሽቆልቆል ላይ የነበረውን ግርማ ሞገሳቸውን መልሰው የሚጐናጸፉበት መልካም አጋጣሚ በእጃቸው ገባ፡፡

ሳዳም ሁሴን የኩዌትን ሉዓላዊነት እንዲያከብሩ የቀረበላቸውን የሰላም ሀሳብ አሻፈረኝ ብለው "አገሪቱን አንድ የኢራቅ ግዛት አድርጌ እቀጥላለሁ" ማለታቸው፣ ፍፁም የበላይነታቸውን

ለማሳየት በሚሹት አሜሪካኖች ዘንድ "ከፈጣሪ የተላከ" ስጦታ እንደሆነ ተደርጐ ተወሰደ። ከዚህም በመነሳት አሜሪካኖች ሳይውሉ ሳያድሩ የሳዳምን ጦር አከርካሪ በመስበር ከኩዌት ፈንቅለው እንደሚያስወጡት አሳወቁ። ይህም ሆኖ "በኢራቅ ላይ የሚወሰደው እርምጃ ምን ያህል ልኬታ ሊኖረው ይገባል? የሳዳም ሁሴን ጦር ከኩዌት እንዲወጣ ከተደረገ በኋላስ ጦርነቱ የት ድረስ ይቀጥላል?" የሚል ጥያቄ መነሳቱ አልቀረም።

የአሜሪካኖች ፍላጐት በዚህ ዕድል በመጠቀም ያላቸውን ተፎካካሪ የሌለው አቅም ማሳየት ነበር። ስለሆነም ኩዌትን "ነጻ በማውጣት" ዘመቻቸው ሳዳም ሁሴንን ከመንበረ ሥልጣናቸው ከመንቀል ባሻገር፣ "ሳዳምን አድናለሁ" ብሎ የሚወራጭ የትላንት ተፎካካሪ ቢኖር፣ እርሱንም ደርበው ከመቅጣት እንደማይመለሱ አመላከቱ። ለዚህም ይረዳቸው ዘንድ የምዕራቡን የፕሮፖጋንዳ አውታር በሙሉ መላውን ዓለም በሳዳም ሁሴን የጭካኔ አገዛዝ ላይ ለማነሳሳት ተጠቀሙበት። በዓለማችን ታዋቂ የሆኑት የግል ሚዲያዎችም ሳይቀሩ ይህን የአሜሪካንን ፕሮጀክት ደግፈው፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የፈጠራ ድርሰቶች በማቅረብና በማራገብ ጭምር በርዕዮተ ዓለም አመራር ሰጭነት ተሰለፉ። ሳዳም ሁሴን የፈጸሙት ብቻ ሳይሆን ያልፈጸሙት ኃጢያት ሁሉ በፈጠራ ድርሰት ተቀናባብሮ እየቀረበ ለጦርነቱ ድጋፍ ማሰባሰብ ተጀመረ።

ከእነዚህ አስገራሚ የፈጠራ ድርሰቶች አንዱ፣ በወቅቱ በአሜሪካን የህገረ ኩዌት አምባሳደር የነበሩት የሳውድ ናስር አልሣባህ የአሥራ አምስት ዓመት ልጅ፣ ናይራህ አልሣባህ እንድታቀርብ የተደረገው ሆን ተብሎ የተቀነባበረ "ወንጀል" ነበር። ናይራህ በዚህ ድርሰት የሳዳም ሁሴን ወታደሮች ከኩዌት ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎችን ነቃቅለው ወደባግዳድ ሲልኩ፣ "ዘጠኝ ወር ሳይሞላቸው የተወለዱና በሆስፒታል ውስጥ በኢንኩቤተር እንክበካቤ ይደረገላቸው ከነበሩ የኩዌት ሕጻናት መካከል 312ቱ ወደሜዳ ተጥለው ሞተዋል" በማለት በጥንቃቄ የተቀነባበረና የተጠና ተውኔት እንድታቀርብ ተደረገ። የአምባሳደሩ ልጅ የሳዳም ወታደሮች "መሣሪያዎቹን ሲነቃቅሉ" በዓይኗ በብረቱ እንዳየችና እርሷም ከዚህ አደገኛ ጥቃት አምልጣ የተረፈች እንደሆነች በማስመሰል በለቅሶ እየተንፈቀፈቀች ገለጸች። ይሁን እንጅ በጥንቃቄ ተጠንቶና ተደጋጋሚ ልምምድ ተደርጐበት የቀረበው ይህ "ታሪክ" ፈጽሞ መሠረተ ቢስ ድርሰት ነበር። የድርሰቱ አቀናባሪ ደግሞ ለዚህ የፕሮፓጋንዳ ሥራው ከኩዌት መንግሥት በትንሹ 12 ሚሊዮን ዶላር የተከፈለው፣ "ሂል ኤንድ ኖውልተን" የሚባል አሜሪካዊ የህዝብ ግንኙነት ተቋም ነበር።

ኩባንያው የዓለምን ህዝብ አንጀት ለማላወስና ለዘመቻው ሰፊ የበጐ ፈቃደኞች ግንባር ለመፍጠር በማለም ያቀነባበረው ይህ የፈጠራ ድርሰት፣ ሳይውል ሳያድር በሁሉም የምዕራቡ ዓለም ታላላቅ ሚዲያዎች እውነት መስሎ እንዲቀርብ ተደረገ። የአምባሳደሩ ልጅ በለቅሶ

እየተንሰቀሰቀች ያቀረበችው መረጃ የፈጠራ ድርሰት ቢሆንም፣ የአሜሪካና የአውሮፓ መገናኛ ብዙኅን ጉዳዩን በእውነት የተፈጸመ አስመስለው እየተቀባበሉ አራገቡት። ከዚህም አልፎ ይኸው የፈጠራ ድርሰት የአገሪቱ ባለሥልጣናት ተከታታይ መግለጫ የሚሰጡበት አውራ ርዕሰ ጉዳይ እስከመሆን ደረሰ። በወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት ትልቁ ጆርጅ ቡሽ፣ ድርጊቱ በእርግጥም የተፈጸመ እንደሆነ በማስመሰል በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብቻ በስድስት ይፋ አጋጣሚዎች የሳዳም ሁሴንን ግፈኛነት አጉልተው ለማሳየት ተጠቀሙበት። "እውነትን ብቻ እንናገራለን" የሚሉት፣ የምዕራቡ ዓለም መገናኛ ብዙኅንም፣ ነገርየው የሐሰት መሆኑን እያወቁ ጭምር፣ ወሬውን በዓለም ዙሪያ ናኙት። በሳዳም ሁሴን የሚመራው ሥርዓት በተጨባጭ የፈጸማቸው በርካታ ግፎች በራሳቸው በቂ የፕሮፖጋንዳ ግብአት ሆነው እያለ፣ በጣም ብዙ የፈጠራ ወንጀሎች በታከሉበት ሁኔታ ለዘመቻው ዝግጅት ተደረገ።

ዝግጅቱ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ጦርነቱ "የበረሐው ማዕበል" በሚል ስያሜ ተካሔደ። የሳዳም ሁሴን ምርጥ የተባሉ የሠራዊት እዞች በዘመቻው በተሰነዘረባቸው ከባድ ጥቃት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከጥቅም ውጭ ሆኑ። ከባድ መሣሪያዎች፣ ታንኮች፣ የጦር አውሮፕላኖችና ሚሳይሎቻቸው ከመሬት ሳይነቃነቁ ተደመሰሱ። ድብደባውን መቋቋም ያቃታቸው ሳዳም ሁሴን በመቶዎች የሚቆጠሩ የጦር አውሮፕላኖቻቸውን በወቅቱ በደመኛ ጠላትነት ይመለከቷት ወደነበረችው ወደኢራን አሸሹ። ለአንድ መንፈቅ ያህል በዘለቀው በዚህ ጦርነትና ድብደባ የሳዳም ሁሴን መንግሥትና ሠራዊታቸው ውልቅልቁ ወጣ። አሜሪካ መራሹ ሕብረት ኩዌት ላይ የሰፈረውን የኢራቅ ወራሪ ኃይል በድብደባ ካደባየው በኋላ ወደኢራቅ ዘልቆ በመግባት የጐን ጥቃት (ቆረጣ) ሰነዘረ። ይህም የሳዳምን መንግሥት ሕልውና በራሷ በኢራቅም ጭምር አደጋ ላይ የሚጥል ሆነ።

ሳዳም ሁሴን ከኩዌት በሰላም እንዲለቁ የቀረበላቸውን አማራጭ አሻፈረኝ ካሉ በኋላ፣ ጥቃቱን መቋቋም ሲያቅታቸው ነጭ ባንዴራ አውለብልበው ኩዌትን እንደሚለቁ ሲገልፁ ጦርነቱ ተደመደመ። አሜሪካ 146፣ ሴኔጋል 92፣ እንግሊዝ 47፣ ሳውዲ አረቢያ 24፣ ፈረንሳይ 9፣ ከግብጽ እስከ ኩዌት ደግሞ ከ11 እስከ 1 ሰው ድረስ በከፈሉት መዋጮ አሜሪካን መራሹ ዘመቻ በፈቃደኞች ሕብረት አሸናፊነት ተጠናቀቀ። የሳዳም ሁሴን የቅርብ ወዳጅ የነበሩ የቀድሞ ልእለ ኃያላን አገሮች የእርዳታ እጃቸውን ለመዘርጋት እንዳችም ሙከራ ሳያደርጉ ጦርነቱ ተደመደመ። ይህም አሜሪካኖች በቬትናም ጦርነት የደረሰባቸውን ውርደት የሚያስረሳ አዲስ ምዕራፍ ተደርጐ የሚወሰድ ነበር።

የአሜሪካ ጦር ሳዳም ሁሴንን አሸንፎ ለመላው ዓለም የበላይነቱን የሚያሳይ መልዕክት ካስተላለፈ በኋላ ወደየመጣበት አልተመለሰም። በሜዲትራንያንና በቀይ ባህር፣ በፋርስ ባህረ ሰላጤና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ መንቀሳቀስና መመሸግ ጀመረ። በበርካታ የመካከለኛው

ምሥራቅ ነዳጅ አምራች አገሮች ላይ ከመስፈሩ በተጨማሪ፣ እዚሁ በእኛው ደጃፍ ደግሞ የባብዔል መንደብን አሻግሮ ለመቆጣጠር ያመቸው ዘንድ አንድ እግሩን ወደጅቡቲ አስገባ። አሰፋፈሩ ቀውስ በተቀሰቀሰበትና የአሜሪካንን ስትራቴጂያዊና ታክቲካዊ ጥቅሞች ለአደጋ የሚያጋልጡ ምልክቶች በታዩበት ሁሉ በፍጥነት ገብቶ ለ"ማረጋጋት"ና ነገሮች በቁጥጥር ሥር እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል ነበር። ይህም ከጥቂት ዓመታት በኋላ የአሜሪካ መንግሥት በሶማሊያ ጣልቃ ሲገባ እንደታየው፣ ሰብዓዊ ቀውስና የመንግሥት መክሰም አደጋ ሲያጋጥም እጁን ለማስገባት በሚያስችለው አኳኋን ለመሰማራት ሰፊ ዕድል ከፈተለት።

ይህ የሆነው በኢትዮጵያ የደርግ መንግሥት መክሰም በተቃረበበት በመጨረሻዎቹ ጊዜያትና ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሊገባ ጥቂት ወራት ሲቀሩት ነበር። ሽግግሩ በጠራ አኳኋንና በፍጥነት ተጠናቅቆ ተተኪው መንግሥት በአሳታፊ መርሕና ሂደት ካልተቋቋመ በስተቀር፣ የተንዘላዘለ የሽግግር ሂደት ምን ዓይነት ዓለም አቀፍ ግብረ-መልስ እንደሚያስከትል ለመገመት አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ነበር። በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ ሰብዓዊ ቀውስን በማስወገድ ስም ማንኛውንም ዓይነት የውጭ ጣልቃ ገብነት የሚጋብዝ ሁኔታ እንዳይፈጠር ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነበር። የደርግን መውደቅ ተከትሎ አንዳች ዓይነት ሥርዓተ አልበኛ ሁኔታ ሳይፈጠር፣ በፍጥነት ተተኪ መንግሥት መመሥረትና የተረጋጋ አገርና ሕብረተሰብ መሆናችንን ማረጋገጥ አማራጭ አልነበረውም። ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የተፋላሚዎች አቻነትና የሰብዓዊ ሁኔታ መመሰቃቀል /Humanitarian Crisis/ ችግር እንዳያጋጥም ለማድረግ የመንግሥት መተካካቱን ቅጽበታዊ በሚባል ፍጥነት ለማስፈጸም የተንቀሳቀሰበት አንዱ ምክንያት ይህ ነበር። በፍጥነት የተረጋጋችና ሰብዓዊ መመሰቃቀል የማይከሰትባት አገር መፍጠር፣ በማንኛውም ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን ሌላ የውጭ ጣልቃ ገብነት ለማስወገድ አማራጭ ያልነበረው የአገር ጉዳይ ነውና።

ኢትዮጵያም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የለውጥ ማዕበል . . .፣

ዓለም አቀፋዊና የአካባቢያችን ሁኔታዎች ይህን የሚመስል መልክ በያዙበት ወቅት በአገሪቱ ውስጥ የነበረው ሁኔታም ለውጡን ልክ እንደቀዶ ጥገና ሕክምና በቅጽበትና በተሟላ ደረጃ መፈጸምን የግድ የሚል ነበር። የአገሪቱ ኢኮኖሚ ተንገራግጮ ቆሟል። የዚህ ውድቀት ዋነኛ መንስዔ ደርግ ለአነስተኛው አርሶ አደር እርሻ ተገቢውን ትኩረት ነፍጐ መላ ጉልበቱን በመንግሥታዊ እርሻዎች ላይ ማድረጉ ነበር። የመንግሥት እርሻዎች ለአጠቃላዩ አገራዊ የግብርና ምርት የነበራቸው አስተዋጽዖ ስድስት በመቶ ብቻ ቢሆንም፣ ከአገሪቱ የሚገበርና በጀት 50 በመቶ የሚሆነው ይመደብላቸው ነበር። ነገር ግን እነዚህ እርሻዎች ከቀዳዳ

በርሜልነት ወጥተው ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ትርጉም ያለው አስተዋጽዖ የሚያደርጉ አልገዘፉሃ፡፡ በዚህ ላይ አርሶ አደሩ በራሱ ጥረት ካመረተው ከግማሽ የማያንሰውን፣ ደርግ "ማልባ፣ ወልባ፣ ወዘተ..." እያለ ይጠራቸው በነበሩ የሕብረት ሥራ ማኅበራትና በእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት/እሰገድ/አማካይነት፣ ለመንግሥት እንዲያስረክብ መገደዱ የግብርናውን ምርታማነት ከፉኛ አዳቅቆታል፡፡ እስከዚያ ድረስ ከዓለማችን ረዣዥም ግጭቶች አንዱ የነበረው የእርስ በርስ ጦርነት እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ በአርሶ አደሩ የምርት፣ የጉልበትና የሕይወት መዋጮ ይካሔድ የነበረ መሆኑም የገበሬውን የማምረት ፍላጐት የሚገድል ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የገጠሩ ወጣት ኃይል ለወታደርነት በግድ እየታፈሰ በጦርነቱ እንዲማገድ መደረጉም የኢኮኖሚ ቀውሱን አባብሶታል፡፡ በአገራችን ወሳኙ ከፍለ ኢኮኖሚ የሆነው ግብርና በዚህ የተሳሳተ የመንግሥት ፖሊሲና በጦርነቱ ምክንያት በመዳከሙ አገራዊ የእርሻ ምርታማነት በሔክታር ከዘጠኝ ኩንታል የማይበልጥ ነበር፡፡

አብዛኛው ህዝብ በገጠርና ግብርና ላይ የተመሠረተ ሕይወት በሚኖርባቸው አገሮች ግብርና ከተዳከመ የኢንዱስትሪው የመልማት ዕድል በጣም ዝቅተኛ መሆኑ አይቀርም፡፡ በኢትዮጵያም በዚህ ምክንያት የአገሪቱ ዘመናዊ የኢኮኖሚ ከፍል ከጥንት ከጠዋቱ የቀጨጨ ነበር፡፡ ይህ አልበቃ ብሎ ደርግ በአገሪቱ የግል ሴክተር እንዳይለማ መከልከሉ ዕድገቱን ፈጽሞ ገድቦታል፡፡ ወታደራዊው መንግሥት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከአምስት መቶ ሺህ ብር በላይ ሀብት እንዳያከማች ከከለከለ በኋላ የአገሪቱ የልማት ጣራ ዝቅ ብሎ ተከርችሟል፡፡ የግል ዘርፍ ማደግና መስፋፋቱ ቀርቶ በጠላትነት ተፈርጆ ይህ ነው የሚባል መላወሻ ምህዳር እንዳይኖረው ተደርጓል፡፡ ይባስ ብሎ የኢንዱስትሪ ዘርፉ በመንግሥት ዋነኛ ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነት የሚንቀሳቀስ መሆኑም ዕድገቱን ገድቦታል፡፡

ኢኮኖሚው ለኢንዱስትሪ ግብዓትና መለዋወጫ፣ ከዚያም አልፎ ራሱን ኢንዱስትሪውን ለመግዛት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ለማመንጨት ባለመቻሉ፣ ኢህአዴግ አገሪቱን ማስተዳደር ሲጀምር በመንግሥት ካዝና ውስጥ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ከጥቂት ሚሊዮን ዶላሮች የማይበልጥ ነበር፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በደርግ የመጨረሻ ወራት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከማምረት አቅሙ የሚጠቀመው በአማካይ ሃያ በመቶውን ብቻ ሆኗል። ይህም "ሁሉም ነገር ወደጦር ግንባር" በሚል መፈክር የተገነባው የደርግ ኢኮኖሚ፣ ወንዝ የማያሻግርና አገራችን የተጓዘችበትን የማሽቆልቆል ሂደት ይበልጥ በማፋጠን ተያይዞ መጥፋትን ተጨባጭና የቅርብ አደጋ አድርጐታል፡፡

የአገሪቱ ፖለቲካም በኢኮኖሚያዊ ቀውሱና በራሱ ምክንያት ምስቅልቅሉ ከወጣ ከርሟል፡፡ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩት ልዩ ልዩ ቅራኔዎች በሰላም የሚገለፁበት ዕድል ተዘግቶ የኃይል መፍትሔ ብቸኛው አማራጭ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ የጠየቀ ብቻ ሳይሆን

ያሰበ በሚቀጣባት አገር፣ ፍላጐትን በዴሞክራሲያዊ መንገድ መግለጽና በብዙሐን ድምጽ በመመራት ማስፈጸም አይቻልም። በነጻነት ተደራጅቶ፣ ተከራክሮና ተሟግቶ የመርታትም ሆነ የመረታት ዕድልም የለም። ስለዚህም በዚያ ወቅት የተቃውሞ ሀሳብ ላላቸው ወገኖች ሁሉ ዓላማቸውን ለማስፈጸም የነበረው አማራጭ የትጥቅ ትግል ብቻ ከሆነ ውሎ አድሯል።

በዚህ ምክንያት በመላ የደርግ አገዛዝ ዓመታት የተከፋና ሌላ አማራጭ ያጣ ሁሉ በአንድ ዓይነት ንቅናቄ መልክ ተሰባስቦ የትጥቅ ትግል ያካሂዳል። ነባር ብቻ ሳይሆን አዳዲስ ድርጅቶች እየተፈጠሩና የየራሳቸውን ነጻ መሬት እያበጁ ቀስ በቀስ መንግሥት የሚቆጣጠረውን ግዛት እያጠበቡ ይፋለማሉ። ይህም በደርግ መንግሥት የመጨረሻ ዓመታት ላይ ታጥቀው የሚፋለሙ ድርጅቶችን ቁጥር አሥራ ሰባት አደረሰው። በአፋር፣ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ በቤኒሻንጉል፣ በጋምቤላና የሱማሌ ክልል የሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ድርጅቶች ተበራከቱ። በአንድ ብሔረሰብ ውስጥ ከአንድ በላይ የታጠቁ ድርጅቶች ማየትም የተለመደ ነበር። ያኔ የኢትዮጵያ አካል በነበረችው ኤርትራ ሕግኃኤ፣ ሣግምና ዴምሓኤ፣ በኦሮሚያ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)፣ የኦሮሚያ እስላማዊ ነጻነት ግንባር (ኦእነግ)ና በባሌ አካባቢ በጀነራል ዋቆ ጉቱ ሥም ይንቀሳቀስ የነበረው ድርጅት ነበሩ። በአፋር ክልል ደግሞ አርዱፍ፣ ኡጉጉመና የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ (አብዴፓ)፤ በሶማሌ ክልል የኦጋዴን ነጻ አውጭ ግንባር(ኦብነግ)ና የምዕራብ ሶማሊያ ነጻ አውጭ ግንባር (ምሶነአግ)፣ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን)በሲዳማ፣ በትግራይ ሕወሓት፣ የጋምቤላ ህዝቦች ነጻነት ንቅናቄ (ጋህነን) በጋምቤላ፣ የቤኒሻንጉል ህዝቦች ነጻነት ንቅናቄ (ቤህነን) በቤኒሻንጉል፣ በአማራ ክልል ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)ና የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) የተባሉ ድርጅቶች በወቅቱ በተለያዩ ዓላማዎች ሥር የተደራጁ የታጠቁ ብሔራዊና ሕብረ-ብሔር ንቅናቄዎችን ሕልውና ያሳያል። ይህ ሁሉ ተዳምሮ ወቅቱ በኢትዮጵያ የትጥቅ ትግሉ የተፋፋመበት ብቻ ሳይሆን፣ በብዙዎች ዘንድ ስለውጤቱም እርግጠኛ ለመሆን የማይቻልበት ሆኗል። ይህም ደርግን በአፋጣኝ ከማስወገድ በተጨማሪ የመንግሥት መተካካቱ በፍጥነትና እርግጠኝነትን በሚፈጥር አኳኋን እንዲካሔድ የግድ ይል ነበር።

ኢህአዴግ የደርግን መንግሥት ግብዓተ መሬት ከመፈጸሙ ጥቂት ቀደም ብሎ የነበረው ዓለም አቀፋዊ፣ ከባቢያዊና አገራዊ ሁኔታ ከፍ ሲል እንደተገለጸው የተመሰቃቀለና ዝብርቅርቁ የወጣ ነበር። በዓለም አቀፍ ደረጃ አርእድ አንቀጥቅጥ ወይም ፈረንጆች "Tectonic Shift" የሚሉት ዓይነት ለውጥ ተመዝግቧል። ይህ ዓይነቱ ለውጥ ጸንተው የቆዩ ተቋማትን፣ ግንኙነቶችን፣ አስተሳሰብና ልማዶችን በአጠቃላይም ሥርዓቶችን የማናጋት ችሎታ ያለው ለውጥ ነው። የነበረውን የሚንድ በመሆኑ ላይ የማያጠያይቅ፣ ነገር ግን ደግሞ በተተኪው

ምንነትና ባሕርይ ላይ የተሟላ መተማመንን የማይፈጥር፣ ስለዚህም ደግሞ በቀላሉ ሊመሰቃቀል ወይም ከመስመር ሊወጣ የሚችል ለውጥ ነው። በአገራችን ውስጥ የተካሔደው ለውጥም በተመሳሳይ "ቴክቶኒክ" ለውጥነት ሊታይ ይችላል። እርሱም በፋንታው ለዘመናት ጸንተው የቆዩ ግንኙነቶችንና ሥርዓቱን የመገለባበጥ ችሎታ ነበረው። በዚህ ምክንያት በ80ዎቹ መጀመሪያ የነበረው የኢትዮጵያ ሁኔታ፣ ያረጀው ሥርዓት ሞቶ ስለመቀበሩ እንጅ ስለወደፊቱ በአጥጋቢ ደረጃ እርግጠኛ መሆን የማይቻልበት፣ ይልቁንም እንደገበታ ውሃ የሚዋልል፣ በጣም አሳሳቢና አገሪቱን በቀላሉ ለከፉ አደጋ ሊያጋልጥ የሚችል የታሪክ ምዕራፍ ነበር።

በዚህ የተነሳ ከአሮጌው ወደአዲሱ በመሸጋገር የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በቅድሚያ መረጋጋትንና በከፍተኛ ደረጃ የሚዋልለውን አገራዊ ሁኔታ ማጽናትን የግድ ይል ነበር። ይህ እንደተሳካ ደግሞ ያለማቋረጥ በዴሞክራሲና ዕድገት ጐዳና መገስገስን ይጠይቅ ነበር። የደርግን መንግሥት ከማስወገድ በኋላ የተሻለውን አማራጭ ይዞ ለመጓዝ የማሽቆልቆል ሂደቱን በአፋጣኝ ማስቆምና ስላም፣ ልማትና ዴሞክራሲን ማስፈን አንገብጋቢ የሆነው በዚህ ምክንያት ነበር። ኢህአዴግ የደርግን መንግሥት አስወግዶ የተረከባት አገር ግን ከእነዚህ ወቅታዊና አጣዳፊ ተግባራት ባሻገር የተሟላ ለውጥ ይመጣባት ዘንድ በመሠረታዊ ባሕሪዋና መለያዎቿ ጭምር በውል መታወቅ ነበረባት። በደንብ የማታውቃቸውን አገርና ሕብረተሰብ መለወጥ አይቻልምና።

በትጥቅ ትግሉ ወቅት ኢህአዴግ በገጠር በገነባው ዴሞክራሲና ባዳበረው ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል በመታገዝ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ መሠረታዊ አወቃቀር አጥንቷል። ትጥቅ ትግሉን በትክክል መርቶ ለማሳካት ያስቻለው አንዱ ምሥጢርም ሂደቱን በእውቀት ላይ ተመስርቶ የመራ ድርጅት በመሆኑ ነው። ኢህአዴግ ስለኢትዮጵያ የነበረውና ያለው አተያይ ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ አቶ መለስ በኢትዮጵያ ሚሌንዬም በዓል ላይ ካሰማው ንግግር መነሳት ተገቢ ይሆናል። በመለስ አገላለጽ ኢህአዴግ ከደርግ የተረከባት ኢትዮጵያ ሦስት ዋና ዋና መለያ ባሕርያት ያሏት አገር ነች።

የኢትዮጵያ ቀዳሚው መለያ ባሕርይ የልዩ ልዩ ገናና ሥልጣኔዎች ቀደምት ባለቤት የነበረችና በሂደት አሽቆልቁላ ወደተመጽዋችነት የወረደች አገር መሆኗ ነው። ሁለተኛው የአገሪቱ መለያ ለዘመናት ነጻነቷን ያስከበረች አገር መሆኗ ነው። ሦስተኛው ደግሞ በዋነኝነት በብሔርና በሃይማኖት ብዙኅነት የተዋቀረች አገር ሆና እያለ፣ ይህንኑ ብዙኅነት በዴሞክራሲያዊ መንገድ ማስተዳደር ተስኗት ለብዙ ችግሮች የተዳረገች አገር መሆኗ ነው። የአገሪቱ መለያ ባህርያት ተብለው ከተቀመጡት ጉዳዮች በማይተናነስ ደረጃ፣ አገራችን ህዝቦቿ ለሙበትና ተጠቃሚነታቸው የተፋለሙና ከባድ መሥዋዕት የከፈሉባት መሆኗም በተለያዩ አጋጣሚዎች የተገለጸና በጥብቅ የሚታመንበት ጉዳይ ነው። እነዚህን የአገሪቱ ዋና ዋና መለያዎች ዘርዘር

አድርጐ መመልከት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ለመግባባት መልካም መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

ለውጥና ቀጣይነትን የምትሻው ኢትዮጵያ . . .፣

ምንም እንኳ የአገራችን ፖለቲካ በተካረሩና ወደጽንፍ በሚጠጉ የፖለቲካ አቋሞች መልከ የሚገለጽ ቢሆንም፣ ሰከን ብሎ መነጋገር ከተቻለ ከፍ ሲል የተመላከቱት የአገራችን መለያዎች በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ መግባባት ሊፈጠርባቸው የሚችሉ ናቸው። ከመለያዎቹ አንዳንዶቹ የአገሪቱን ታሪካዊ ጥንካሬ ያሳያሉ። ሌሎቹ ደግሞ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የመጣውን ግዙፍ የችግር እውነታ የሚያመላክቱ ናቸው። በመሆኑም አኩሪ መለያዎችን መጠበቅና በተጨማሪ አዳዲስ ጥንካሬዎች ማጐልበት፣ ወደጥፋት የሚያመሩ አስቸጋሪ የታሪክ ገጽታዎችን ደግሞ ማስተካከል የግድ ነበር። በአጭሩ በአንዴ ለውጥና ቀጣይነትን ማረጋገጥ የሚሹ፣ ስለዚህም ደግሞ መለወጥ ሆነ መቀጠል በሚገባቸው የኢትዮጵያ እውነታዎች ላይ በሁሉም ዘንድ መግባባት መፍጠር የሚጠይቁ ጉዳዮች ነበሩ።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መለያ ራሷን ከባእድ ገዥዎች ጠብቃ የቆየችና አኩሪ የነጻነት ታሪክ ያላት አገር መሆኗ ነው። ኢትዮጵያ በዓለማችን በባእድ ካልተገዙ ጥቂት አገሮች አንዷ ነች። በእርግጥ አገሪቱን ለመግዛት በመሻት ብዙ የባዕድ ኃይሎች የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገዋል። የሱዳን ድርቡሾችና ማሕዲስቶች፣ ግብጻውያን፣ ቱርኮችና ጣሊያኖች ቀጥተኛ ወረራዎችን ሞክረዋል። አልፎ አልፎ ደከም ያሉ መንግሥታት በከፈቱት ዕድል በመጠቀም የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ሊያደርጓት የሞከሩ ባይታጡም በቀጥታ ቅኝ አገዛዝ መዳፉ ሥር ያስገባት አገር አልነበረም። ይህ የኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ነጻነት በከባድ መስዋዕትነት የተገኘና የተጠበቀ፣ በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በዓለም ማኅበረሰብም ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ያደረ ነው። ኢህአዴግ ከደርግ መንግሥት የተረከባት ኢትዮጵያ አንዱ መለያ ይኸው ነጻነቷን አስጠብቃ የቆየች ትልቅና ባለታሪክ አገር የመሆኗ እውነታ ነው።

ስለኢትዮጵያ ጥንታዊ ነጻነት ሲነሳ ግን ከዘመነ ግሎባላይዜሽን ጋር ተያይዞ የተለየ ሁኔታ እንደተፈጠረ በመገንዘብ ጭምር ሊሆን ይገባዋል። ዘመነ ግሎባላይዜሽን ዓለም በጥብቅ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ገመድ የተሳሰረችበት በመሆኑ ሁሉም አገሮች በትስስሩ ልክ ለውጭ ተፅዕኖ የሚጋለጡበት ዘመን ሆኗል። አልፎ ተርፎም የሉዐላዊ መንግሥታትን ህልውና የሚፈታተን ሂደት ተጠናክሮ መጥቷል። በትስስሩ ውስጥ የገቡ አገሮች በሚኖራቸው ኢኮኖሚያዊ አቅምና ተፅዕኖ የማሳረፍ ደረጃ አንድም ሰፊ ነጻነት ያላቸው ለጋሽና አድራጊ ፈጣሪ አገሮች ይሆናሉ። ወይም ደግሞ በድህነታቸው ምክንያት ተመጽዋችና ማንም እንዳሻው እጁን እያስገባ የሚያመሰቃቅላቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

እንደገናም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታው አንድም ባለብዙ ዋልታ፣ አለያም ባለአንድ ዋልታ ሊሆን ይችላል:: ዘመኑ በዛ ያሉ ልእለ ኃያላን የሚተውኑበትና በመካከላቸው በሚኖር የኃይል ሚዛን አቻነት ወይም ተነጻጻሪ ብልጫ ላይ የተመሠረተ ጐራ የሚፈጠርበት ሲሆን፣ ትንንሽና ደካማ አገሮች በዚሁ የብዙ ዋልታዎች ማዕቀፍ በአባሪና ተባባሪነት ለመንቀሳቀስ ዕድል ያገኛሉ:: ከሞላ ጐደል በበላይ ጠባቂነት ጥላ ከለላ በሰጣቸው ልእለ ኃያል አገር ሥር፣ ተለጣፊና ተላላኪ የሚሆኑበት አጋጣሚም ይፈጠራል:: ይህ እውነታ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በግልጽ የተንፀባረቀ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ በዚሁ ማዕቀፍ በነጻነቷ ላይ ገደብ የጣለ ሁኔታ ፈጥራ ነበር:: በንጉሡ ዘመን ከገለልተኝነት ባፈነገጠ መርሕ ከአሜሪካን ጋር በመወገን በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ግጭቶች ውስጥ የተሳተፈችው በዚህ የተነሳ ነው:: በኮሪያ የእርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ጐራ ለይታ መሳተፏ፣ በቬትናም ጦርነት ወቅት ደግሞ ለአሜሪካን መንግሥት በጦር ሰፈርነት ያገለግል ዘንድ በአሥመራ ከተማ ውስጥ "ቃኘው ስቴሽን" የሚባለውን ወታደራዊ ሰፈር መፍቀዷ ይህንኑ ያመላክታሉ:: አንድ አገር ሌሎች አገሮች በግዛቷ ውስጥ የጦር ሰፈር (Military Base) እንዲገነቡ እስከመፍቀድ ከደረሰች ሉዓላዊነቷን በውዴታዋ አሳልፋ እንደሰጠች ይቆጠራል:: አፄ ኃይለ ሥላሴ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ እ.ኤ.አ. በ1961 ሲቋቋም ኢትዮጵያ በመሥራች አባልነት እንድትሳተፍ ማድረጋቸው መልካም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥርዓተ ግዛታቸው ዓይነተኛ መለያ የንቅናቄው መሥራች እንደነበሩት ብዙዎቹ አገራት ከገለልተኝነት ባፈነገጠ ወገናዊ መርሕ መመራት ነበር።

የደርግ መንግሥት በበኩሉ በተመሳሳይ ጐራ የለየ ዓለም አቀፋዊ ትስስር ውስጥ ገብቶ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ ከባድ ተፅዕኖ እንዲከተል አድርጓል። ደርግ ጠንካራ ማኅበራዊ መሠረት ሳይኖረው ሥልጣን ላይ የወጣ መንግሥት ነበር። ደርግ ሌሎች ዜጐችን ጨምሮ ስድሣ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናትን ያለፍርድ በመረሸኑና የምዕራባውያን ይዞታ የነበሩ ተቋማትን ደርቦ በመውረሱ ከምዕራቡ ዓለም ጋር የተቆራረጠው ገና በጠዋቱ ነበር:: በዚህ የተነሳ ምዕራባውያኑ ፊታቸውን አዞሩበት። ይህም ደርግ የህዝቡን ተቃውሞ ለማፈን የሚያስፈልገው ቁሳዊና የገንዘብ ድጋፍ እንዳይሟላለት በማድረጉ ፊቱን ወደምሥራቁ ጐራ ለማዞር ተገደደ። ፈጽሞ በማያውቀውና በማያምንበት የምሥራቁ ዓለም ርዕዮት እመራለሁ በማለት መጀመሪያ ከቻይና፣ ቀጥሎ ደግሞ በመኢሶን አጋፋሪነት ከሶቭዬት ሕብረት ጋር ተወዳጀ:: የሩሲያና ተከታዮቿ የጦር መሣሪያ ጐረፈለት። የአገራቱ ወታደራዊ ጠበብትና ፖለቲካዊ አማካሪዎች በአገራችን እንደልባቸው ይርመሰመሱም ጀመር::

በእነዚህ ድጋፍ፣ ምክርና መመሪያ የሶማሊያን ወረራ ለመመከት ከተካሔደው የምሥራቅ ግንባር እስከሰሜናዊ ሣህል ዘመቻዎች፣ ከ"ሁሉም ነገር ወደጦር ግንባር መፈክር" እስከ ቀይ ኮከብ ዘመቻ ድረስ ተነደፉ:: የኩባና የምሥራቅ አውሮፓ ወታደሮች የሶማልያን ወረራ ለመመከት

በቀጥታ ተዋጊነት እስከመሳተፍ ደረሱ፡፡ በሰሜኑ ጦርነት ከተካፈሉት የሩስያና የምሥራቅ ጀርመን አዛዦች መካከል ደግሞ ጥቂቶች በኤርትራ የነጻነት ታጋዮች ተማርከው ነበር፡፡ አሰላለፉ ከጦርነት አልፎ የአገሪቱን ስፖርት ጭምር በመበከሉ ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ አደባባይ በነጻነት መሳተፏ ቀርቶ የሶቭዬት ሕብረትን አቋም ተከትላ እንድትጓዝ ተደረገ፡፡ በዚህ ዓለም አቀፍ ግንኙነት አገራችን የሶቭዬት ሕብረትና አጋሮቿ ጉዳይ ፈጻሚ ወደመሆን ዝቅ አለች፡፡ እነዚህ እውነታዎች በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በአገሪቱ መሪዎች ስህተት ኢትዮጵያ አንዴ ከምዕራቡ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከምሥራቁ ዓለም ጋር ጐራ ለይታ ስትወዳጅ እንደቆየች ያሳያሉ፡፡ ኢትዮጵያ ከገለልተኝነት መርሕ ባፈነገጠ አኳኋን ዓለም አቀፍ ግንኙነቷን መምራቷ የአገሪቱ ነጻነት ለአደጋ እንዲጋለጥ ያደረገ ነበር፡፡

ዓለማችን ባለብዙ ዋልታ ከነበረችበት እውነታ በተለየ አኳኋን ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የአሜሪካ ፍፁም የበላይነት የሰፈነባት ሆና ቆይታለች፡፡ ይህ በደርግ ውድቀት ዋዜማ የተከሰተ ሲሆን አገሮች ሁሉ ለታላቋ አሜሪካና በእርሷ ለሚመራው የምዕራቡ ዓለም ሊሰግዱ የሚገደዱበትን ሁኔታ አስከተለ፡፡ በእነዚህ ዓመታት ዓለም መፈናፈኛው በጠበበ ሁኔታ በአንድ ዓለማዊ የበላይ ኃይል ሥር ገብታለች፡፡ ይህ ኃይል ከመስከረም አንዱ የአሸባሪዎች ጥቃት ማግስት ይፋ እንዳደረገው፣ "ከእኛ ጋር ያልሆነ ሁሉ በእኛ ላይ የተነሳ ነው" (Either you are with us, or against us) በማለት ሁሉንም አገሮች በተፅዕኖው ሥር ማስገባት የሚችል አቅም ነበረው። በዚህም የተነሳ ብዙ አገሮች ሳይወዱ በግድ በማያምኑበት ጦርነት ውስጥ ለመግባት ተገደዱ፡፡ በትንሹ ጆርጅ ቡሽ መሪነት በተካሔደው ሁለተኛው የፋርስ ባሕረ ሰላጤ ጦርነት "የወዶ ገቦች ጥምረት" (Coalition of the Willings)፣ የሚል ስያሜ የተሰጠው የዘማች አገሮች ስብስብ የዚህ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ አኳኋን ዓለም ባለአንድ ዋልታ ከሆነች በኋላ አገሮች ተነጻጻሪ ነጻነታቸውን ተነፍገው በልእለ ኃያላን መካከል የነበረውን ልዩነት በመጠቀምና በአንጻራዊ ነጻነት ለመንቀሳቀስ የነበራቸው ዕድል እጅጉን ቀነሰ፡፡ በወዶ ዘማቾች ማኅበር ውስጥ ላለመግባት የወሰነም ቢሆን፣ ዋናውን የዓለም አለቃ የሚያስቆጣ ነገር እንዳይፈጽም በእጅጉ ሊጠነቀቅ ተገደደ፡፡

ስለኢትዮጵያ ነጻነት ሲነሳ፣ በተከፈለው ከቡር መስዋእትነት ተጠብቆ የቆየውን ያህል፣ የአገሪቱ ድኅነት ነጻነቷን አስጠብቆ ለመቀጠል ምን ያህል ፈተና ሆኖ እንደቆየ መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ አንድ አገር የራሱን ህዝብ ለመቀለብ ተቸግሮ በተመጽዋችነት ከተሰለፈ በከባድ መሥዋዕትነት ያስከበረውን ነጻነት አስጠብቆ የመቀጠል ብቃቱ ከፋኛ ይሸረሸራል፡፡ በተመጽዋችነት የተሰለፈ አገር ነጻነት፣ ክብርና ኩራት አይኖረውም ብሎ ያመነና የምጽዋት እጁን የዘረጋ ሁሉ በአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ገብቶ እንዲፈትፍት ምቹ ሁኔታ ይፈጠርለታል፡፡ ይህም በዘመነ ግሎባላይዜሽን ማንኛውም አገር ከድኅነት መላቀቅ

ካቃተው በከባድ ተጋድሎ አስጠብቆተ የቆየውን ነጻነተ በቀላሉ ሳሳባተ የሚተልበተ ዕድል ሰፊ እንደሆነ ያሳያል።

ኢህአዴግ ከደርግ የተረከባት አገር ነጻነቷን አስከብራ የኖረች ብትሆንም በዘመነ ግሎባላይዜሽን ድኅነትና ኋላቀርነት ተጭነዋት፣ ነጻነቷም በዚያው ልክ ለአደጋ በመጋለጥ ላይ የነበረች አገር ነች። ከዚህ አኳያ የአዲሱ መንግሥት አንዱ ትልቁ ፈተና በድኅነትና ኋላቀርነት ምክንያት ለአደጋ የተጋለጠውን ነጻነት፣ በጠንካራ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አጐልብቶ የማይናወጥ መሠረት የማስያዝ ፈተና ነበር። ኢህአዴግ ይህን ፈተና እንዴት እንደተወጣው ቆየት ብሎ የሚዳሰስ ይሆናል።

ሁለተኛውና ኢህአዴግ ከቀደምት መንግሥታት የተረከበው እውነታ አገሪቱ ከተከታታይ ገናና ሥልጣኔዎች ብትነሳም የማታ ማታ ለተከታታይ ከፍለ ዘመናት በማሽቆልቆል ሂደት ውስጥ ልታልፍ የተገደደች አገር መሆኗ ነው። ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ ከመሆኗ በተጨማሪ የታላላቅ ሥልጣኔዎች መነሻ አገርም ነች። ዘመን አመጣሽ የብሔር መንግሥት (Nation State) ሳትሆን ጥንታዊ ሥልጣኔያዊ መንግሥት (Civilizational State) የነበራትም አገር ነች።

በዚህ ዘመን ያሉትን የዓለማችን አገሮች ከሥልጣኔ አኳያ በጥቅሉ በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። አንዳንድ አገሮች ከረጅም ዘመናት ጀምሮ በሥልጣኔ ጐዳና ሲራመዱ የቆዩና የመጡ ናቸው። በዚህ ምክንያት አገሮቹ ጥንታዊ ሥልጣኔያዊ መንግሥታት የነበራቸውና የዘመናት ታሪክ ያላቸው ሆነው ይገኛሉ። እነዚህ አገሮች የመውደቅ ወይም የመነሳት፣ የመስፋት ወይም የመጥበብ ከስተት ሊያጋጥማቸው ቢችልም፣ ሥረ-መሠረታቸው በሥልጣኔ የጀመረና የተገነባ አገሮች ናቸው። ቻይና፣ ግብጽ፣ ጣሊያን፣ ግሪክ፣ ኢራቅ፣ ፋርስ፣ ሕንድና ኢትዮጵያ ከብዙ በጥቂቱ ለዚህ ዓይነቱ ሥልጣኔያዊ መንግሥት እንደ አብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ አገሮች ናቸው።

ከእነዚህ በተለየ ሁኔታ የብሔር መንግሥታት የሆኑት ደግሞ ከሞላ ጐደል ከገበያ ሥርዓት መጀመር ጋር ተያይዘው በተለይ ከ17ኛውና ከ18ኛው ከፍላተ ዘመናት በኋላ የተፈጠሩ አገሮች ናቸው። በመሆኑም የብሔር መንግሥታትና አገሮች የዘመነ ካፒታሊዝም ውጤቶች ናቸው። የትኛውንም ያህል ዘመናዊነት ቢኖረውም፣ የእነዚህ አገሮች መንግሥታት ሕልውናና ታሪክ በመሠረቱ ከሁለት እስከ አምሥት ምእተ-ዓመታት የበለጠ እድሜ አያስቆጥርም። ታላቋን አሜሪካ ጨምሮ በርካታ የአውሮፖና የላቲን አሜሪካ አገሮች በዚህ ማዕቀፍ የሚታዩ ናቸው። ከዚህ በንጽጽር ሲታይ ኢትዮጵያ ከአራት ሺህ ዓመታት ልቆ የሚሔድ ሥልጣኔያዊ መንግሥት የነበራት አገር ነች። በአገሪቱ ዘመናዊና የተማከለ የመንግሥት አስተዳዳር የተጀመረው በ19ኛው ከፍለ ዘመን መጨረሻ በአፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት በመሆኑ ዘመናዊ ታሪኳ ከመቶ አምሳ ዓመታት ያልበለጠ ቢሆንም፣ ይህ ግን ኢትዮጵያ የረዥም ዘመናት ሥልጣኔያዊ መንግሥት

ነዘጠፕ፣ የጠረጥ የመሆኗን አውገታ የሚቀይረው አይደለም፡፡ “የጥንታዊት ኢትዮጵያ ሥልጣኔያዊ መንግሥት መነሻ መሠረቱ የት ነው?” የሚለው ጉዳይ ግን፣ አገራችን የሰው ልጅ መገኛ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ይበልጥ መጠናት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ አገር መሆኗ በታሪከና ቅድመ ታሪከ ጥናትና ግኝት የተረጋገጠና በየጊዜው በሚገኙ ተጨማሪ የጥንታዊ ሰው ቅሪቶች ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ ግዙፍ እውነታ የሚመነጩና በቅጡ ያልተጠኑ በርካታ ጉዳዮች መኖራቸው ደግሞ ብዙም አያከራከርም፡፡ ለምሣሌ ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ ከሆነች ሥራም የተጀመረባት አገር ነበረች ማለት ነውን? የሚለው ጥያቄ ሊነሳና ሊመረመር ይችላል፡፡ “ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ ነው” ከሚለው ሳይንሳዊ መላምት በመነሳት፣ የሰው ልጅ መገኛ የሆነችውን አገር የመጀመሪያውን ሰብዓዊ የልማት ተግባር መነሻ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ የሰውን ልጅ ቀዳሚ የሥራ ማሳለጫ መሣሪያዎች ለማግኘት ከፍተኛ ፍለጋ ማድረግ ይቻላል፣ ይገባልም፡፡ እንደገናም፣ ኢትዮጵያን ከሰው ልጅ ህልውናና ማኅበራዊ ሕይወት ጋር የማይነጠለውን ቋንቋ መነሻ ነጥብ ማድረግም ይቻላል፡፡ ቋንቋ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ሕይወት ሲጀምር የሥራና መግባቢያ መሣሪያ ሆኖ የተፈጠረ ነው፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ቋንቋ የተፈጠረና የተነገረባት አገር የመሆን ዕድል ያላትም አገር ነች፡፡ በዚህ ሳይገደቡ በምድር ላይ የሰው ልጆችን የሚያስተዳድረው መንግሥት አስቀድሞ በዚች አገር ሊመሠረት የሚችልበት ዕድል እንደነበር ወይም እንዳልነበር መፈተሽም አብሮ ሊታይ የሚገባው ይሆናል፡፡ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ አዳዲስ ጥያቄዎች ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ የመሆኗን እውነታ በመንተራስና ሉሲና ሰላምን የመሳሰሉ የታሪክ እውነታዎች ይበልጥ አሚልቶ በመመርመር ሊመለሱ የሚገባቸው ይሆናል፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ የኢትዮጵያን ታሪክ አሚልቶ ማቅረብ ይገባል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በኋለኛው ዘመን የታየው የዕድገት መገታትና፣ ማሽቆልቆል ደግሞ አገሪቱን እጅግ በሚያሳፍር ደረጃ ላይ ማስቀመጡ መታወስ ይገባዋል፡፡ ያለዚህ እውነታ አኩሪው የዘመናት የሥልጣኔ ታሪክ ከፊል ሐቅ ብቻ መሆኑ አይቀርም፡፡

ኢትዮጵያ ከይሓ ዘመን ጀምሮ ሲቆጠር ከአራት ሺህ ዓመታት በላይ ዘልቆ የሚሔድ ሥልጣኔ የነበራት አገር ነች፡፡ ይህ ሥልጣኔ ይበልጥ እያደገ ሔዶ ታላቁን የአክሱም ሥልጣኔ አስከትሏል፡፡ በምሕንድስናና ሥነፈለክ መስኮች ከፍተኛ ዕድገት አሳይቶ የነበረው አክሱማዊው ሥልጣኔ በታላቅነቱ ከኢትዮጵያ ዳር ድንበር አልፎ መካከለኛው ምሥራቅና ሕንድ ድረስ ተፅዕኖ የማሳደር ብቃት የነበረው ነው፡፡ ኢትዮጵያ ቢያንስ ከእነዚህ ዘመናት ጀምሮ መንግሥታዊና ሃይማኖታዊ ተቋማት የገነባችና በእነዚህም አማካይነት ጥንታዊ ሥልጡን አገር ልትሆን የበቃች ነች፡፡

የአክሱም ሥልጣኔ መዳከምን ተከትሎ በመንፈሳዊና ምሕንድስና መስክ ተጨማሪ

ምጥቀት የታየበት የአገው ሥልጣኔም ዓለምን ባስደነቁት የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ግንባታ ጥበብ ተከታዩን የኢትዮጵያ ታላቅነት ዘመን አመላካች ነው፡፡ ከሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዳግም መምጣት ጋር ተያይዞ የታየው የአማራ ሥልጣኔም በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍ ላይ ከፍተኛ ዕድገት የታየበት ነበር፡፡ ከዚህ በመቀጠል የመጣው የጐንደር ሥልጣኔም በሥነ-ህንጻ፣ በሥነ-ጥበብ፣ በፍልስፍናና መንግሥት አስተዳደር መስኮች ምጥቀት የታየበት መሆኑ ዘመን ተሻግረው በተላለፉት ቅርሶች የሚታይ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብም በዚህ ዘመን የተፈጠረና አስተዋጽኦ ያበረከተ ነው፡፡ የኦሮሚያ የገዳ ሥርዓትና የራሱ የተለየ ባሕርይ ያለው የጉዲፈቻ ባሕል በአርሶ አደርና አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች ለየት ያለ ባሕርይ ይዞ የዳበረውን የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሂደትና ዘመናት ያስቆጠረ የመቻቻልና የአብሮ መኖር ጥበብ ያሳያል። በደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች የጢያ ትክል ድንጋይና የኮንሶ የድንጋይ እርከን ሥራ ጥበብ፣ እንዲሁም የሐረሪ የጀጐል ግንብ ሁሉ ተዳምረው ኢትዮጵያ በተከታታይ ትውልዶች የተጀመረና የዳበረ ሥልጣኔ ያላቸው ህዝቦች መናኸሪያ አገር እንደሆነች ይመሰከራሉ፡፡

ይሁንና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረው ሥልጣኔ ቆስ በቀስ እየተንሸራተተ አገሪቱ በማያቋርጥ የማሽቆልቆል ሂደት ውስጥ ለማለፍ ተገደደች፡፡ በተለይ ከዘመነ መሣፍንት የተፋፋመ የእርስ በእርስ ግጭት ጀምሮ እስከሃያኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ድረስ በተካሔዱ በርካታ ጦርነቶች አገሪቱ ከድጡ ወደማጡ ተሸጋገረች፡፡ በተወሰነ ደረጃ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ወታደራዊ ተፈላጊነት ኖሯቸው የተጀመሩት ብረት የማቅለጥ፣ መድፍና ሰረገላ የመሥራት እንዲሁም የመንገድ ሥራ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለዘመናዊነት በር ከፋች ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር ሊገመት ቢችልም ይህ ጅምር ሁኔታው ባለመመቸቱ ተጨናግፎ አገሪቱ በማሽቆልቆል ሂደት መጓዝ ቀጠለች፡፡

ይህ ወቅት በአውሮፓ የካፒታሊስት ሥርዓት ወደተሟላ እድገት የተሸጋገረበት ዘመን ሲሆን፣ ጃፓኖች የአውሮፓን ቴክኖሎጅ በስፋት ኮርጀው ከሞላ ጐደል ለተፋጠነ የኢንዱስትሪ ዕድገት የበቁበት ዘመን ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜ የጃፓን የሜጂ አስተዳደር አውሮፓዊውን ቴክኖሎጅ ትንሽ ለየት ባለ ስልት ኮርጆ በመማር አገሩን ወደበለጸገ ሕብረተሰብ ሲያሸጋግር፣ የካሣ ኃይሉ (ቴዎድሮስ) ሕልምና ራዕይ ግን ካለዘመኑ የበቀለ ሆነና ለክሽፈት ተዳረገ፡፡ ይባስ ብሎም የማሽቆልቆል ሂደቱ በንጉሥ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመነ መንግሥት የከፋ ጫፍ ላይ ደርሶ ሚሊዮኖች በረሐብ ቸነፈር እየተገረፉ እንደቅጠል የሚረግፉበት ደረጃ ላይ ተደረሰ፡፡ ኢትዮጵያ ሥልጣኔያዊ መንግሥት ከፈጠሩት ቀዳሚ አገሮች አንዷና ይህን የሚመስከሩ ዘመን ተሻጋሪ አሻራዎች የሞሏት አገር ብትሆንም፣ ይህ ገናና ሥልጣኔ በሂደት ተዳክሞ አገሪቱና ህዝቦቿ የዓለም መዘባበቻ የሆኑበት ደረጃ ላይ ደረሱ፡፡ ኢህአዴግ ይህችን የመሰለች አገር ከደርግ መንግሥት ሲረከብ የማሽቆልቆሉን ሂደት ገትቶ ኢትዮጵያን በዕድገትና አዲስ አይነት የሥልጣኔ ጐዳና

በማራመድ በማንኛውም መስፈርት የተከበረች አገር ለመፍጠር መቻል ወይም አለመቻሉ ሁለተኛው ከባዱ ፈተና ነበር።

ከትውልድ ትውልድ የተሸጋገረውና አሁን ላለው ትውልድ በውርስ የተላለፈው ሦስተኛው የኢትዮጵያ መለያ በብዙኀነት የተዋቀረችና ይህን ግን በብቃት ማስተናገድ ተስኗት የኖረች አገር መሆኗ ነው። ኢትዮጵያ የብሔርና የሃይማኖት ብዙኀነት የነበራትና ያላት አገር ነች። ይህ ከጥንት ከጠዋቱ ጀምሮ የነበረ የአገሪቷ ገጽታ ነው። በፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን አገላለጽ ኢትዮጵያ በአምስት ያህል ትልልቅ የዘር ግንዶች የተዋቀረችና[5] ከእነዚህ የሚፈልቁ በርካታ የየራሳቸው ማንነት (Identity) ያላቸው ማኅበረሰቦችን አቅፋ የምትገኝ የብዙኀነት አገር ነች። እነዚህ በሕገ-መንግሥቱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ የሚል የማንነት መለያ የተሰጣቸው ማኅበረሰቦች በአንድ በኩልና በአብዛኛው በራሳቸው መልከዓ ምድር ተወስነው የሚኖሩ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ከዘመናዊ ኢኮኖሚ ግንባታና ትሥሥር መጠናከር ጋር በተለይ በከተሞችና በተጐራባች መልከዓ ምድሮች እየሰፋ በመጣ ደረጃ ተሰባጥረው የሚገኙ ህዝቦች ናቸው።

በዚህ መሠረታዊ ነባራዊ እውነታ ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ዜጐች በአንዴ አገራዊም ብሔረሰባዊም መለያ ወይም ማንነት ይዘው ይገኛሉ። ኢትዮጵያዊነት የማንነታቸው አንድ መገለጫ እንደሆነ ሁሉ፣ ብሔረሰባዊ ማንነታቸው ደግሞ ሌላው መገለጫቸው ነው። ሁለቱ በመተካካት ሳይሆን በተመጋጋቢነት ሊከበሩ የሚችሉና የሚገባቸው ነበሩ፣ ዛሬም ናቸው። ነገር ግን አገሪቱን ለዘመናት ያስተዳደሩት ገዥዎች ሁለቱን የአንድ ሳንቲም ገጽታዎች እንደሚተካኩ አድርገው በመቁጠር ሰዎች አንድ ማንነት ብቻ እንዲኖራቸው ሚስገደዳቸው የተለመደ ነበር። በዚህ የተነሳ ቀደምት ሥርዓቶች ብዙኀነትን እንደድከመት በመመልከት ብሔረሰባዊ ማንነትን በአስተዳደራዊ መንገድ ለማጥፋትና በአንድ ወጥነት ለመተካት ተንቀሳቅሰዋል። ኢትዮጵያዊነት ብቸኛው የማንነት መገለጫ ሆኖ እንዲመረጥ፣ ከዚህ ውጭ በቋንቋ፣ በባሕልና በታሪክ ከምትመሳሰለው ጋር የመቀራረብ ዕድል እንዳይኖር ተከላከለዋል። ነገር ግን በጣም ብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦችን ማንነታቸውን በግድ በማጥፋት አንድ ወጥ ማኅበረሰብ መፍጠር አይቻልምና፣ ከገዥዎቹ ፍላጐት ባሻገር የኢትዮጵያ ብዙኀነት እንደተጠበቀ ሊቀጥል ችሏል።

የኢትዮጵያ ብዙኀነት ሌላው መገለጫ በርከት ያሉ ነባርና አዳዲስ ሃይማኖቶች እንዲሁም አገር በቀል እምነቶች የሚመለኩና የሚሰበኩባት አገር መሆኗ ነው። ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በዓለማችን የተሰበኩ ልዩ ልዩ እምነቶችን አስተናግዳለች። ከአይሁድ እምነት ጀምሮ ከመካከለኛው ምሥራቅ የፈለቁትን የክርሥትናና እስልምና ሃይማኖቶችን እጇን ዘርግታ ተቀብላለች። የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንትና የፔንቴኮስታል እምነቶችም ከምዕራቡ ዓለም ደግሞ ወደአገሪቱ ገብተዋል። ከእነዚህ በፊትና ጐን ለጐን ደግሞ የተለያዩ አገር በቀል እምነቶች

የሚመለከባት አገር ነበረች፣ ዛሬም ነች።

ይህ የእምነት ብዙኀነት የነበረና ያለ ቢሆንም፣ በአገሪቱ እምነቶች መካከል ሁለት ዓይነት ግንኙነት ተንሰራፍቶ ኖሯል። በአንድ በኩል በህዝቦች መካከል በመቻቻልና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ አድልዎ፣ መናናቅና አለመከባበር ተዳብሎ የታየበት ሂደት ታልፏል። በዚህ ምክንያት በአገሪቱ ቀላል የማይባሉ የሃይማኖት ግጭቶች እየተቀሰቀሱ ህዝቡን ለጉዳት ሲዳርጉት ቆይተዋል። ከ14ኛው እስከ16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በክርስትናና እስልምና መሪዎችና ተከታዮቻቸው መካከል የተካሔዱት የእርስ በእርስ ጦርነቶች፣ ከፖርቱጋል እርዳታ ጋር ተያይዞ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ባለው የካቶሊክ እምነትና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል በ17ኛው ክፍለ ዘመን የተካሔዱት ደም አፋሳሽ ግጭቶች፣ በኋላም በአፄ ዮሐንስና አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥታት የተካሔዱትና ዛሬም ድረስ አልፎ አልፎ የሚከሰቱት ግጭቶች የአገራችንን ሰላም የሚያውክ የሃይማኖት ብዙኀነት አያያዝ እንደነበር ያሳያሉ። እነዚህ ግጭቶች አብዛኛውን ጊዜ ሥልጣን ላይ በወጡት ነገሥታት ፍላጐት መሠረት መንግሥትና ሃይማኖት አንድ አካል አንድ አምሳል እንዲሆኑ ከመደረጉ የመነጩ ናቸው። በዚህ የተነሳ መንግሥታዊ ሥልጣን የተጋሩት ሃይማኖቶች በሌሎች እምነቶች ላይ የበላይ የሚሆኑበትና እኩልነት ጠፍቶ እርስ በእርስ መጠራጠርና አለመግባባት፣ አልፎ አልፎም ደም አፋሳሽ ግጭት ጉልህ የአገራችን የታሪክ ገጽታ ነበር። በመንግሥታዊ ሥልጣን ያልተደገፉ ሃይማኖቶች ተከታዮች ደግሞ አመች ሁኔታ ሲፈጠርላቸውና በተነጻጻሪ ሻል ያለ ወታደራዊ አቅም ሲያደራጁ የራሳቸውን ግጭትና ጦርነት እየቀሰቀሱ ብዙ ደም መፋሰስና እልቂት አስከትለዋል።

ኢትዮጵያ በብሔርና ሃይማኖት ብዙኀነት የተዋቀረች አገር ብትሆንም፣ ይህንኑ በአግባቡ ማስተናገድ ባለመቻሏ ከፍተኛና ውድ ዋጋ የከፈለች አገር ነች። ልዩነትን በተፈጥሯዊ ከስተትነቱ በጸጋ ተቀብሎ የጥንካሬ ምንጭ ከማድረግ ይልቅ እንደድከመት ተመልክቶ ለማጥፋትና በግድ አንድ ወጥ ለማድረግ የተደረገው ጥረት ተሳክቶ ላይሳካ ብዙ የሕይወት፣ የንብረትና የጊዜ ዋጋ አስከፍሏል። በተለይ ደግሞ፣ ብዙኃኑን ህዝብ የማይወክሉ ሆነው እያለ ሥልጣን ላይ ወጥተው አድልዎ የሚፈጽሙ ገዥዎችን ገመና ለመሸፈን ሲባል በብሔረሰባዊ ማንነት ላይ የተመሠረተው እውነታ እንዲደፈቅ የተደረገው ጥረት ከባድ ቁስልና ጠባሳ ትቶ አልፏል። ማኅበረሰቦች አፍ የፈቱበትን ቋንቋ እንዲተው፣ ባሕልና ታሪካቸውን በሌላ ባሕልና ታሪክ እንዲተኩ መደረጉ፣ በተለይ ደግሞ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ጀምሮ ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸውን ተቋማዊ መልክ በያዘ ብሔራዊ ጭቆና መነጠቃቸው አገሪቱ በእርግጥም ብዙኀነትን በአግባቡ ማስተናገድ እንዲሳናት አደረገ። ይህም እንደገና በማንነት ላይ የተመሠረተው ቅራኔ አጣዳፊ ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ ካላገኘ በስተቀር፣ አገሪቱን ወደመበታተን የሚያመራ ተጨባጭ አደጋ እንዲሆን አስከማድረግ ደረሰ።

ከዚህ በመነሳት ሲታይ፣ ብዙኅነትን በአግባቡ የሚያስተናግድ ሥርዓት የመገንባት ጉዳይ ኢትዮጵያን እንደአገር ለማስቀጠልም ሆነ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ተጠናክራ እንድትቆም ለማድረግ ልዩ ሚና የሚጫወት ጉዳይ ነበር። በዚህ የተነሳ አዲሱ ሥርዓት በማንነት ልዩነት ላይ የተመሠረተ ብዙኅነትን ከኢትዮጵያዊነት ጋር አጣጥሞ ለመገንባት የሚችል መሆን ነበረበት። አገሪቱን ወደመበታተን ቋፍ ያስጠጋትን የብሔር ጭቆና በማስወገድ ከማንኛውም መሠረታዊ ውስጣዊ መቃቃር የጸዳና በእኩልነት የዳበረ አዲስ ዓይነት ኢትዮጵያዊነት እንዲፈጠር ማድረግ አማራጭ አልነበረውም። በመሆኑም፣ በደርግ ውድቀት ማግስት ኢትዮጵያን እንደአገር የማስቀጠልና ያለማስቀጠል ዕድል ከሚወሰንባቸው አጀንዳዎች መካከል፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት የመገንባትና ብዙኅነትን አዲስ አይነት የጥንካሬ ምንጭ አድርጐ በአግባቡ የመግራትና የመምራት ጉዳይ ነበር።

ኢህአዴግ ከወታደራዊው መንግሥት አላቅቆ የተረከባት አገር መሠረታዊ ገጽታዎቿ ከላይ የተገለፁት ነበሩ። ነጻነቷ የተከበረ፣ ነገር ግን ይኸው ነጻነት የዘመነ ግሎባላይዜሽንን ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ለመቋቋም በሚያስችል የኢኮኖሚ ግስጋሴና አቅም ላይ ያልተመሠረተባት አገር ነበረች። ከገናና ሥልጣኔ በማሽቆልቆል ወደተመጽዋችነት ጫፍ የደረሰችና ሃይማኖታዊና ብሔረሰባዊ ብዙኅነትን በአግባቡ ማስተናገድ ተስኗት አንድነቷ በቋፍ ላይ የተንጠለጠለ አገር ነበረች። በእነዚህ ምክንያቶች ቀላል ለማይባል የመበታተን አደጋ የተጋለጠችም ነበረች።

ይህ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ቀላል አደጋ አልነበረም። የአገሪቱን መኖር ወይም አለመኖር የሚወስን፣ በተለይ ደግሞ ከድኅነትና ኋላቀርነት መባባስ ጋር ተያይዞ ወደብዙ ብጥስጣሽ አገሮች የመፈረካከስ ዕድልን የሚያሰፋና የአደጋውን መከሰት የሚያፋጥን ነበር። ኢህአዴግ የደርግን መንግሥት ባስወገደ ማግስት አንዳንዶች "ኢትዮጵያ አብቅቶላታል፣ እጣ ፈንታዋም የዩጐዝላቪያ፣ የላይቤሪያና የሶማሊያ ዓይነት ይሆናል" በማለት እንዲተነብዩ ያደረጋቸው ነባራዊ እውነታ ይህ ነበር። ክሽግግሩ መድረክና የለውጥ ሂደት ጀምሮ ያለው ሂደት በአገሪቱ ሕልውና ላይ ያንዣበቡትን እነዚህን አደጋዎች ለማስወገድ በነበረው ችሎታና ብቃት እንዲለካ ያደረገው ምክንያት የተፈጠረውም ከእነዚህ ጉልህ እውነታዎች ጋር ተያይዞ ነው። ከዚህ በመነሳት ያለፈውን ሩብ ምዕተ ዓመት ጉዞና የተገኘውን ውጤት ኢህአዴግ ከተነሳበት መሠረት ጋር እያነጻጸሩ መመልከት ትግሉን የመራውና ያስቀጠለው የስድሣዎቹና የሰባዎቹ የትግል ትውልድ ተጨባጭ አስተዋጽኦ ምን እንደሚመስል ለመለካት ያስችላል።

ምዕራፍ ሁለት፣

በአዲሲቱ ኢትዮጵያ የድኅረ ሰማንያ ሦስት የለውጥ እውነታዎች፣

ኢህአዴግ የትጥቅ ትግሉን በድል አድራጊነት ካጠናቀቀ በኋላ ቀጣዩ ሥራ ኢትዮጵያን በላይዋ ላይ ካንዣበቡት አደጋዎች አላቆ ወደተሻለ አቅጣጫ መምራት ነበር፡፡ ይህ ተግባር በአንድ ጀንበር ምሽት የማይጠናቀቅ ምናልባትም የበርካታ ትውልዶችን የለውጥ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም፣ ኢህአዴግ ከቀደምት ትውልዶች የተረከበውን የለውጥ እንቅስቃሴ ከራሱ ዘመን ልዩ ሁኔታዎች በሚፈልቁ ተልዕኮዎች አዳብሮ በመፈጸም ለቀጣዩ የአመራር ትውልድ የተሻለ መነሻ መፍጠር ነበረበት፡፡

ይህን ሂደት በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም ኢህአዴግ ጥርት ብሎ በተቀረጸ የለውጥ አስተሳሰብ መመራትና ወቅቱ የሚጠይቃቸውን ልዩ ልዩ እርምጃዎች መውሰድ ይገባው ነበር፡፡ ይህም በጠራ አስተሳሰብ የሚመራ መሆን ነበረበት። ከዚህ አኳያ ኢህአዴግ ከሌሎች የፖለቲካ ንቅናቄዎች ተለይቶ በመመራያነት ከተቀበለውና አገሪቱን ከመራበት አስተሳሰብ በመጀመር የለውጡን ሂደት መተንተን ተገቢ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ወገኖች ኢህአዴግ ሶሻሊሰታዊ ቅኝት አለው ሲሉ የሚደመጡ ቢሆኑም ግንባሩ የሚመራበት አስተሳሰብ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነው። በመሆኑም የዚህን አስተሳሰብ ታሪካዊ አነሳስ፣ ይዘትና ዕድገት ካስገኛቸው ውጤቶች ጋር እያነጻጸሩ በመመልከት በሃያ አንደኛው ከፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ያለችው ኢትዮጵያ በትክክለኛ አቅጣጫ ላይ መሆን አለመሆኗን መፈተሽ ይገባል፡፡ ከዚሁም ጋር አብዮታዊ ዴሞክራሲን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከሶሻሊዝም ጋር ተመሳሳይ አድርገው ለሚያቀርቡ ወገኖች በሁለቱ መካከል ስላለው ልዩነት የመነሻ ሀሳብ ማቅረብ ይቻላል። በዚያውም አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምን ማለት እንደሆነ ከአስተሳሰቡ አራማጆች አንደበት ትክክለኛ ይዘቱን ለማሰማት ያግዛል፡፡ ስለዚህም የአብዮታዊ ዴሞክራሲን አስተሳሰብ አነሳስና ዕድገት በጥቂቱም ቢሆን በጨረፍታ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዋዜማ የዴሞክራሲ ጥያቄና የኢትዮጵያ የለውጥ ጉዞ፣

ኢትዮጵያ በፊውዳላዊና ቀጥሎ ደግሞ በወታደራዊ አገዛዝ ሥር በወደቀችበት ጊዜ ዋናውና አንገብጋቢው የሕብረተሰቡ ጥያቄ የዴሞክራሲ ጥያቄ ነበር፡፡ ይህም በአገሪቱ የነበረው ሥርዓት የዜጐችና የልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች መሠረታዊ የግልና የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተጣሱበት ከመሆኑ ይመነጫል፡፡ በእነዚህ ዘመናት ዜጐች ሰብዓዊ መብትና ነጻነታቸውን ተነፍገው ኖረዋል፡፡ የተለያዩ ማኅበረሰቦች ደግሞ ዴሞክራሲያዊ የቡድን መብታቸውን ተነጥቀዋል፡፡ በደርግ ዘመን የነጻ እርምጃና ጅምላ ግድያ እንደታየው ዜጐች በሕይወት የመኖር

ዋስትናም ሆነ ከማንኛውም ኢ-ሰብዓዊ ጥቃት የመጠበቅ ሕጋዊ መብት አልነበራቸውም፡፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመደራጀት፣ የመቃወም፣ ከቦታ ቦታ በነጻነት የመንቀሳቀስ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና ሥራ የማቆም መብቶቻቸውም ሕጋዊ እውቅና አላገኙም ነበር፡፡

ብሔር፣ ብሔረሰቦች የቋንቋ፣ የባሕል፣ የታሪክ እኩልነት እንዲሁም ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት አልነበራቸውም፡፡ ላልተማከለ ሥልጣንን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለሚያከፋፍል የአስተዳደር ሥርዓትም አልበቁም ነበር፡፡ የሃይማኖትና የፆታ እኩልነትም አይታወቅም፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ በተናጠል ዜጐችም ሆኑ መላው የአገሪቱ ህዝቦች ከምንም ነገር በላይ የሚሰቃዩት በዴሞክራሲ እጦት ነበር፡፡ ዴሞክራሲ ባለመኖሩ የተሳሳቱ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ታግሎ ለማስተካከልም ሆነ ተፈጻሚ እንዳይሆኑ በመከላከል የህዝብን በደል ማስወገድ የሚቻልበት ዕድል አልነበረም፡፡ በተጨባጭ እንደታየው ህዝቡ ይህን የጭቆና ሥርዓት ቢቃወምም፣ የበላይ የነበሩት የቀድሞ ገዥዎች በገነቡዋቸው ግዙፍ የአፈና ተቋማት እየታገዙ ለበርካታ ምእተ ዓመታት ለመግዛት ችለዋል፡፡

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ በኢትዮጵያ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በአንድ በኩል አሮጌውን ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ማፍረስ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዜጐችና የህዝቦችን መሠረታዊ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች በምሉእነት መመለስ የግድ ነበር፡፡ ለዚህም ሲባል የገዥዎቹ መደቦች መተማመኛ የነበሩትን የአፈና ተቋማት በሥር-ነቀል ወይም አብዮታዊ ደረጃ ማፈራረስና ማስወገድ አማራጭ አልነበረውም፡፡ በብዙ አገሮች የትግል ታሪክ እንደታየው፣ የህዝብን መብትና ጥቅም በተሟላ ደረጃ ለማስከበር የሚካሔድ የለውጥ እንቅስቃሴ ተፈላጊውን ውጤት የሚያስገኘው አሮጌውን ሥርዓት ከነአፋኝ ተቋማቱ በመጠራረግ ወይም ሥርዓቱ ፈጽሞ እንዳያንሰራራ አድርጐ በማስወገድ ሲጀምር ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሚካሔደው ለውጥ የህዝቡን መብትና ተጠቃሚነት አሟልቶ የሚያስከበር ይሆን ዘንድ በዚህ ሥር ነቀል መንገድ መፈጸሙን ማረጋገጥ አማራጭ አልነበረውም፡፡

ሕብረተሰብን በዚህ ሥር-ነቀል (Radical) መልክ ወደዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማሸጋገር ጉዳይ ከዴሞክራሲያዊ አብዮት ጋር እንጅ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ከሶሻሊዝም ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ በማኅበራዊ አብዮቶች ሳይንስና በተጨባጭ ሂደቱ እንደሚታየው በዓለማችን የተካሔዱ አብዮቶች ሁሉ ሶሻሊስታዊ ባሕርይ ብቻ የነበራቸው አይደሉም፡፡ በየአገሩ የሚካሔደው አብዮት እንደተጨባጭ ሁኔታው በዋነኛነት አርሶ አደሩን ከጭሰኝነት ነጻ ለማውጣትና ሕብረተሰቡንም ከኋላቀርነት በማላቀቅ ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚካሔድ ፀረ-ፊውዳል ዴሞክራሲያዊ አብዮት ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ አገሮቹ የዳበረ የገበያ ሥርዓት ላይ የደረሱ ከሆነ ለሠራተኛው መብትና ልእልና መስፈን ሲባል የሚካሔድ ሶሻሊስታዊ አብዮት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ሁሉም አብዮት የሚል ቅጽል የተለጠፈላቸው ንቅናቄዎች

ሁሉ ሶሻሊስታዊ ባሕርይ አላቸው ሊባል አይችልም። ይህም ሆኖ አብዮት ሲባል ሁሌም ሶሻሊስታዊ የለውጥ ንቅናቄ መስሎ የሚታያቸው ወገኖች ይኖራሉ። በዚህ ብዥታ የተነሳ በኢትዮጵያ የሚካሔደውን ለውጥ ሶሻሊስታዊ አድርገው የሚመለከቱ ጥቂቶች አይደሉም። "አብዮታዊ" የሚለው ቅጽል መወገድ ካለበት አሮጌ ሥርዓት ጋር በተሟላ ደረጃ ተለያይቶ መጀመርን እንጅ ቀጥሎ የሚገነባውን አዲስ ሥርዓት ባሕርይ የሚያመለክት አይደለም። ይህን ከአውሮፓ አብዮቶች ጋር አስተሳስሮ በመመልከት መገንዘብ ይቻላል።

በአውሮፓ የመጀመሪያው ታላቅ አብዮት የተካሔደው እ.ኤ.አ. በ1789 በፈረንሳይ ሲሆን፣ ይህም በዓለማችን የመጀመሪያው የከበርቴ አብዮት በመባል ይታወቃል። ይህ አብዮት ከሶሻሊዝም ጋር ፈጽሞ ግንኙነት ያልነበረው ዴሞክራሲያዊ አብዮት ነው። እንደገና እ.ኤ.አ በ1848 ለሁለተኛ ጊዜ በከፍለ-ዓለሙ የተካሔደው ሥር ነቀል አብዮትም ቢሆን በዋነኛነት ሌላ የከበርቴ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ነበር። ይህም አብዮቶችን በተደጋጋሚ በማስተናገድ አቻ በማይገኝላት ፈረንሳይና ሌሎች የአውሮፓ አገሮች በመጀመሪያው አብዮት ከሥልጣን የተጠራረጉት ፊውዳሎች እንደገና በማንሰራራታቸው የከበርቴ ዴሞክራሲ አብዮቱን በድጋሚ ማካሔድ በማስፈለጉ ነበር። በአንጻሩ ለሶሻሊዝም ሲባል በምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ አብዮት የተካሔደው አሁንም በፈረንሳይ አገር እ.ኤ.አ በ1871 ሲሆን፣ ይህም የመጀመሪያውን ሶሻሊስታዊ መንግሥት በፓሪስ ከተማ ላይ ለመመሥረት ያስቻለ ነበር። በወቅቱ "የፓሪስ ኮምዩን" በመባል የሚታወቀው ይህ ሶሻሊስታዊ አብዮት የመጀመሪያው ፀረ-ፊውዳል ዴሞክራሲያዊ አብዮት ከተካሔደ ከአንድ መቶ ዓመታት በኋላ የተካሔደ ነበር። ይህም በዴሞክራሲያዊና ሶሻሊስት አብዮቶች መካከል የይዘት ብቻ ሳይሆን የጊዜ ልዩነት እንዳለም የሚያመላክት ነው።

ይህን የአውሮፓ ሁኔታ እንደመነሻ በመውሰድ በኢትዮጵያ የነበረውን ህዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴ በንጽጽር መመልከት ተገቢ ይሆናል። በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገር አቀፍ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ አብዮት የተካሔደው በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም. ነው። የየካቲቱ ህዝባዊ አብዮት በደርግ በመጨናገፉ አገሪቱ እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ የዴሞክራሲ ረሐብተኛ ሆና ልትቀጥል ተገዳለች። በዚህም የተነሳ የደርግን መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ የሚያልም ማንኛውም አብዮት ዴሞክራሲያዊ እንጅ ሶሻሊስታዊ ግቦችን ሊያልም የሚችል አልነበረም። በዚህ የተነሳ ትግሉና የሚካሔደው ለውጥ ሶሻሊስታዊ ባሕርይ ያለው ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ግቦችን የማሳካት ባሕርይ የተላበሰ ሊሆን ተገደደ። የመድረኩ ቀዳሚና ዋነኛ ጥያቄ ሶሻሊዝም ባይሆንም ለውጡ አሮጌውን ሥርዓት በማስወገድ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብቶች አሟልቶ ማስከበር ይጠይቅ ስለነበር ሥርዓቱን ከነአፈና ተቋማቱ ማፍረስ የግድ ነበር። ይህም ሆኖ በደርግ ውድቀት ዋዜማ ላይ በዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ዙሪያ ሁለት የማይቀራረቡ አማራጭ መንገዶች መራመድ ጀመሩ። በዚህ ጉዳይ ላይ የተሻለ ግልጽነት ለመያዝ በዋነኛነት

ምሥራቅ ነዳጅ አምራች አገሮች ላይ ከመስፈሩ በተጨማሪ፣ እዚሁ በእኛው ደጃፍ ደግሞ የባብዔል መንደብን አሻግሮ ለመቆጣጠር ያመቸው ዘንድ አንድ እግሩን ወደጅቡቲ አስገባ። አሰፋፈሩ ቀውስ በተቀሰቀሰበትና የአሜሪካንን ስትራቴጂያዊና ታክቲካዊ ጥቅሞች ለአደጋ የሚያጋልጡ ምልክቶች በታዩበት ሁሉ በፍጥነት ገብቶ ለ"ማረጋጋት"ና ነገሮች በቁጥጥር ሥር እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል ነበር። ይህም ከጥቂት ዓመታት በኋላ የአሜሪካ መንግሥት በሶማሊያ ጣልቃ ሲገባ እንደታየው፣ ሰብዓዊ ቀውስና የመንግሥት መክሰም አደጋ ሲያጋጥም እጁን ለማስገባት በሚያስችለው አኳኋን ለመሰማራት ሰፊ ዕድል ከፈተለት።

ይህ የሆነው በኢትዮጵያ የደርግ መንግሥት መክሰም በተቃረበበት በመጨረሻዎቹ ጊዜያትና ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሊገባ ጥቂት ወራት ሲቀሩት ነበር። ሽግግሩ በጠራ አኳኋንና በፍጥነት ተጠናቅቆ ተተኪው መንግሥት በአሳታፊ መርሕና ሂደት ካልተቋቋመ በስተቀር፣ የተንዘላዘለ የሽግግር ሂደት ምን ዓይነት ዓለም አቀፍ ግብረ-መልስ እንደሚያስከትል ለመገመት አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ነበር። በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ ሰብዓዊ ቀውስን በማስወገድ ስም ማንኛውንም ዓይነት የውጭ ጣልቃ ገብነት የሚጋብዝ ሁኔታ እንዳይፈጠር ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነበር። የደርግን መውደቅ ተከትሎ አንዳች ዓይነት ሥርዓተ አልበኛ ሁኔታ ሳይፈጠር፣ በፍጥነት ተተኪ መንግሥት መመሥረትና የተረጋጋ አገርና ሕብረተሰብ መሆናችንን ማረጋገጥ አማራጭ አልነበረውም። ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የተፋላሚዎች አቻነትና የሰብዓዊ ሁኔታ መመሰቃቀል /Humanitarian Crisis/ ችግር እንዳያጋጥም ለማድረግ የመንግሥት መተካካቱን ቅጽበታዊ በሚባል ፍጥነት ለማስፈጸም የተንቀሳቀሰበት አንዱ ምክንያት ይህ ነበር። በፍጥነት የተረጋጋችና ሰብዓዊ መመሰቃቀል የማይከሰትባት አገር መፍጠር፣ በማንኛውም ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን ሌላ የውጭ ጣልቃ ገብነት ለማስወገድ አማራጭ ያልነበረው የአገር ጉዳይ ነውና።

ኢትዮጵያም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የለውጥ ማዕበል . . .፣

ዓለም አቀፋዊና የአካባቢያችን ሁኔታዎች ይህን የሚመስል መልክ በያዙበት ወቅት በአገሪቱ ውስጥ የነበረው ሁኔታም ለውጡን ልክ እንደቀዶ ጥገና ሕክምና በቅጽበትና በተሟላ ደረጃ መፈጸምን የግድ የሚል ነበር። የአገሪቱ ኢኮኖሚ ተንገራግጮ ቆሟል። የዚህ ውድቀት ዋነኛ መንስዔ ደርግ ለአነስተኛው አርሶ አደር እርሻ ተገቢውን ትኩረት ነፍጐ መላ ጉልበቱን በመንግሥታዊ እርሻዎች ላይ ማድረጉ ነበር። የመንግሥት እርሻዎች ለአጠቃላዩ አገራዊ የግብርና ምርት የነበራቸው አስተዋጽዖ ስድስት በመቶ ብቻ ቢሆንም፣ ከአገሪቱ የሚገበርና በጀት 50 በመቶ የሚሆነው ይመደብላቸው ነበር። ነገር ግን እነዚህ እርሻዎች ከቀዳዳ

መሪዎች ፖሊሲ ይማረር ለነበረውና ለውጥ ለሚሻው የአሜሪካ ህዝብ በ"ለውጥ" (Change) ላይ የተመሠረተው መልዕክትና መፈክር እጅግ አማላይ ነበር። በተለይ ከ2005 የኢኮኖሚ ቀውስ በኋላ ደግሞ እጅጉን ለተማረረው አሜሪካዊ ለውጥ የሚያማልል የፖለቲካ ፕሮግራም ሆነ። በመሆኑም በውስጥም በውጭም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳያቸውና በዓለም አቀፍ ግንኙነታቸው ለውጥ ለሚሹት አሜሪካዊያን "ለውጥን" የምረጡኝ ዘመቻቸው አጀንዳ ያደረጉት ባራክ አባማ የመራጩን ልብ በቀላሉ መማረክ ቻሉ። የህዝቡ የለውጥ ፍላጐትና የአባማ የምርጫ መልዕክት እንደሰኔና ሰኞ ተገጣጥመው የፕሬዚዳንትነትን ሥልጣን ለጥቁሮችና ለሴቶች ለመስጠት በምትፈራው አሜሪካ ጥቁሩ እጩ አሸንፈው ወደነጩ ቤተ መንግሥት ተረማመዱ።

ይሁንና አባማ ከሥልጣን በኋላ የለውጥ ሀሳባቸውን ተግባራዊ ሊያደርጉ የሞከሩት ፈጽሞ ባልተቀየረው የአሜሪካ የአገዛዝ አውታር በመጠቀም ነበር። በመሆኑም፣ በነባሩ የአገዛዝ አውታር የተማመኑት አባማ የተመኙትንና ቃል የገቡትን ያህል የለውጥ ሀሳባቸውን ተግባራዊ ማድረግ ተሳናቸው። ብዙኃኑ የአባማ መራጭ አሜሪካውያን ከዛሬ ነገ እውን ይሆናል ብለው የጠበቁት የለውጥ ሀሳብ ጸንቶ በቆየውና ሥር በሰደደው የአገዛዝ መዋቅር ፊት ፈጽሞ መላወስ ተሳነው። አባማ ቃላቸውን ለመጠበቅ የተወሰኑ ትልልቅ ሥራዎችን ቢያከናውኑም ያመጡት መሠረታዊ ለውጥ ግን የለም። በጤና መስክ አባማኬር በሚባለው የጤና መድህን ሽፋንን ባስፋፋው ፕሮግራም ብዙ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን አሜሪካውያን ተጠቃሚ አድርገዋል። በኢራቅ ሰፍሮ የነበረውን ሠራዊታቸውን በቃላቸው መሠረት አንስተዋል። ከኩባ ጋር የነበረውን ግንኙነትም በተለየ አዲስ አቅጣጫ ማስጓዝ ችለዋል። ይህም ሆኖ ግን የገቡትን መሠረታዊ የለውጥ ቃል ኪዳን ተግባራዊ ሊያደርጉ አልቻሉም። ይህንንም ራሳቸው አባም የሚያምኑት ጉዳይ ነው። ስለሆነም ለመሠረታዊ ለውጥ ቆርጦ የተነሳ ማንኛውም ኃይል ያለፈውን ሥርዓት የአገዛዝ መዋቅር ከመሠረቱ በመቀየር ካልሆነ በስተቀር በመውረስ የተሟላ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም።

በኢትዮጵያ አብዮታዊ ዴሞክራሲን አስፈላጊ ያደረገው ነባራዊ ሁኔታ አገሪቱ በአምባገነናዊ አገዛዝ ሥር ዴሞክራሲን ተነፍጋ መቆየቷ ነው። ገዥዎቹ ዴሞክራሲ እንዳይሰፍን ያደረጉት ደግሞ ለረዥም ዓመታት በገነቡዋቸውና ከአንዱ መንግሥት ወደሌላው በውርስ በተላለፉት የአፈና ተቋማት አማካይነት ነበር። እነዚህ የአፈና ተቋማት ሳይፈራርሱ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ከቀን ሕልምነት የሚያልፍ አልነበረም። ስለዚህም ለዴሞክራሲ የሚካሔደው የለውጥ እንቅስቃሴ፣ የቆዩትን የአፈና ተቋማት ሙሉ በሙሉ የመጠራረግ ሥር-ነቀል ባሕርይ ሊላበስና በዚያው ልክ ደግሞ አብዮታዊ ሊሆን ይገደድ ነበር።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለውጡ ዴሞክራሲያዊ ይዘት እንዲኖረው የሚያስገድዱ ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችም ነበሩ። ከእነዚህም ዋናው አገሪቱ በአርሶ አደር ዋነኛ ማኅበራዊ ኃይልነት

የተዋቀረች መሆኗ ነው። ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያ በጣም ፈጣን ዕድገት ከተመዘገበባት ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላም የሕብረተሰቡ አወቃቀር ከመሠረቱ አልተቀየረም። አብዛኛው ህዝብ አሁንም አርሶ አደር ነው። ኢንዱስትሪና ከተሜነት ገና በቅጡ አልተስፋፋም። አርሶ አደሩ ደግሞ በባሕርይው የግል ንብረት ያለውና ከሶሻሊዝም በጣም ርቆ የሚገኝ ማኅበረሰብ ነው። በግራ ዘመም የፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ ለሶሻሊዝም የቀረበ ነው ተብሎ የሚወሰደው የሕብረተሰብ ከፍል የፋብሪካ ሠራተኛው ወይም ላብ አደሩ ነው። አርሶ አደሩ በባሕርይው የራሱ ትንሽ ማሳ እንዲሁም ጥቂት የቤት እንስሳትና እህል ያለው፣ ስለዚህም የጋርዮሽ ሕይወትን በቀላሉ ሊመርጥ የማይችል ነው። ይህም ሆኖ አርሶ አደሩ የጋርዮሽ ሕይወትን ባይመርጥም በላዩ ላይ የሚፈጸሙትን በደሎች ሁሉ ይጠላል። እንዲወገዱለትም ይሻል። በምዝበራ እንዲደኸይ በሚያደርገው አገዛዝ ሥር እንዲማቅቅ የሚያደርጉት የአፈና ተቋማት ከላዩ ላይ እንዲወገዱለትና በምትኩም ለተሟላ ዴሞክራሲ እንዲበቃ ይፈልጋል። ሥር ነቀል ለውጥና የተሟላ ዴሞክራሲን የሚሻ በመሆኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የራሴ ብሎ ሊቀበለውና በዚህም ዙሪያ ተሰባስቦ ሊታገል ይችላል።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ አርሶ አደሩን ብቻ ሳይሆን የከተማውን ንዑስ ባለሀብትም ካለፈው ብልሹ አስተዳደር ሥር-ነቀል በሆነ መንገድ ሊያላቅቀውና ለተሟላ ዴሞክራሲ ሊያበቃው የሚችል አስተሳሰብ ነው። ብዙኃኑ የከተማ ህዝብ ኑሮው በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ገቢ ላይ የተመሠረተና ዴሞክራሲን የተነፈገ በመሆኑ፣ እርሱም እንደአርሶ አደሩ ካለፈው ሙሉ በሙሉ በመላቀቅና በምትኩ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባት ሊጠቀም የሚፈልግና የሚችል ማኅበረሰብ ነው። በመሆኑም አንዳችም ሶሻሊስታዊ ይዘትና ቅኝት የሌለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የትላንትን በደል ለማስወገድና በዴሞክራሲ መሣሪያነት ዛሬና ነገን ከትላንት የተሻለ ለማድረግ የምልዓተ ህዝቡን ድጋፍ በቀላሉ አግኝቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል።

የኢህአዴግ መሥራች ድርጅቶች ትግሉን የጀመሩት በዚህ አስተሳሰብ በመመራት ሲሆን በሂደት ደግሞ በውስጣቸው የነበሩና ግራ ቀመስ የነበሩ ምሁራን የየራሳቸውን የተናጠልና የጋራ ማርክሣዊና ሌኒናዊ ድርጅቶች እስከመፍጠር ደርሰው ነበር። በየግንባሩ ውስጥ የነበሩት ማርክሣዊ ሌኒናዊ ርዕዮት መከተልን የመረጡ ምሁራን በትጥቅ ትግሉ ማብቂያ አካባቢ "የትግራይ ማርክሣዊ ሌኒናዊ ሊግ /ማሌሊት/"፣ "የኢትዮጵያ ማርክሣዊ ሌኒናዊ ኃይሎች /ኢማሌኃ/"ና "የኦሮሞ ማርክሣዊ ሌኒናዊ ንቅናቄን /አማሌን/" የሚባሉ የግራ ድርጅቶችን መሥርተው ነበር። ድርጅቶቹ የበርሊን ግንብ እስኪናድና ደርግ ሊወድቅ አንድ ዓመት እስኪቀረው ድረስ ሶሻሊዝምን የረጅም ጊዜ ፕሮግራም፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ደግሞ የአጭርና መካከለኛ ጊዜ (መለስተኛ) ፕሮግራም አድርገው እንደሚታገሉ ገልጸውም ነበር። እ.ኤ.አ በ1989 የበርሊን ግንብ ከፈረሰ በኋላ ግን ይህን አማራጭ ትተው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራምን የረጅም

ጊዜ ግባቸው በማድረግ ብቻ ተወሰኑ::

ከሶሻሊዝም ጋር ይህ ነው የሚባል ተፈጥሯዊ መመሳሰል የሌለው የግንባሩ አብዮታዊ ዴሞከራሲ አስተሳሰብ ሶሻሊስታዊ ቅኝት እንዳለው ተደርጐ እንዲተረጐም መንገድ የከፈተው አንዱ ዋነኛ ጉዳይ ይህ ነበር:: ማርከሣዊ ሌኒናዊ የነበሩት ድርጅቶች በተመሠረቱ በአጭር ጊዜ የከሰሙ ቢሆንም ከእነርሱ ጋር ተያይዞ ስለኢህአዴግ የተያዘው አተያይ ዛሬም ድረስ እንደቀጠለ ነው:: ይህም በአንድ በኩል ተቃዋሚው ኃይል "ኢህአዴግ የሶሻሊዝም አቀንቃኝ የነበረና ይህን ቅኝትም ያላስተካከለ" እንደሆነ በማስመሰል ሰፊና ያልተቋረጠ ዘመቻ በማካሔዱ የመጣ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ ራሱ ይህን ዘመቻ በበቂ ደረጃ ባለመመከቱ፣ ከአህጉረ አፍሪካ ትልቁን የግል ዘርፍ ግንባታ የሚመራውና ከሶሻሊዝም በብርሐን ዓመታት የራቀው "ኢህአዴግ ዛሬም ሶሻሊስት ነው"፣ ወይም "ሶሻሊስታዊ ግቦችን ያራምዳል" ብለው የሚጠራጠሩ ጥቂቶች አይደሉም::

አብዮታዊ ዴሞከራሲ ከሶሻሊዝም ጋር የማይገናኝና ራሱን ችሎ የሚቆም አስተሳሰብና አማራጭ መንገድ እንደሆነ በዓለም አቀፍና በአገራዊ ሁኔታው ላይ ከመጣው ለውጥ ጋር አገናዝቦ መመልከትም ይቻላል:: ከፍ ብሎ የተገለጸውና በዓለምአቀፍ ሁኔታው ላይ የታየው ለውጥ እነማሌሊት በተመሠረቱ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ያጋጠመ ነበር:: በዚህ የተነሳ ሩስያና የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች በኢኮኖሚ ልማትም ሆነ በዴሞከራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ረገድ ከምዕራቡ ዓለም የተሻሉ ሆነው መገኘት አቅቷቸው ተፈረካከሰዋል:: በእነዚህ አገሮች የነበሩት ሶሻሊስት ሥርዓቶች የህዝብ ጥያቄዎችን መመለስ ሲያቅታቸው በአንድ ወቅት ሶሻሊዝምን አምነው ለዚሁ አስተሳሰብ ተግባራዊነት የተፋለሙ የራሳቸው ህዝቦች በተቃውሞ ተነሳስተው ሊጥሏቸው በቁ። የእነዚህ ኃይሎች ውድቀት እዚያው ሳለም ሶሻሊዝም ህዝቦችን በጉልበት እያስገደዱ በመጋት ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችልና እንደማይገባው አረጋገጠ::

በኢትዮጵያም ህዝቡ በደርግ "ሶሻሊዝም" ተማሮ የሕብረት ሥራዎችንና በሶሻሊዝም ሥም የተጀመሩ የመንደር ምሥረታዎችን በአመጽ አስከማፈራረስ ደርሶ ነበር። በራሱ በደርግ የሶሻሊዝም ሞዴል ተደርጋ ትቀርብ የነበረችው የየትኖራ ገበሬዎችም ሳይቀር ከሶሻሊዝም መውጣት ያሳዩት ፍላጐት ቀላል አልነበረም። የደርግ መንግሥት በ1982 ዓ.ም የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ፈለግን በመተው የቅይጥ ኢኮኖሚ አቅጣጫ እንደሚከተል የገለጸው ህዝቡ ባካሔደው በዚህ ፀረ "ሶሻሊዝም" ትግል አስገዳጅነት ነው:: ወደአዲስ አበባ ለመግባት ስትራቴጂያዊ ዝግጅት እናደርግ በነበረበት በ1983 ዓ.ም. የመጀመሪያ አጋማሽ ለጥቂት ጐጃም ውስጥ በደጀን ወረዳ የትኖራ ቀበሌ ተቀምጠን ነበር። የየትኖራ ገበሬዎችን ባነጋገርን ቁጥር ከ"ሶሻሊስታዊ" ሙከራው አንዳንድ ጥቅም እንዳገኙ ቢቆጥሩም በዚሁ ቅኝት የመቀጠል ፍላጐት እንዳልነበራቸው ደግሞ አልደበቁንም። በኋላ በሰማኒያዎቹ መጨረሻ መሬት ሲከፋፈል ደግሞ የየትኖራ ገበሬዎች

ቃል ዘቃል "ግለ'ነነተ ነፈዋ'ነ" ዘሠገለተ የአምራቶተ ሕብረተ ሥራ ማኅበራቱ'ን አፈራርሰው መሬታቸውን ተከፋፍለዋል። በመሆኑም ኢህአዴግ በሶሻሊዝም የሚያምን ሆኖ ቢገኝ እንኳ ህዝብ አልቀበለውም ያለውን ሶሻሊስታዊ ፈለግ በህዝብ ላይ በመጫን ከኪሳራ በስተቀር አንዳችም የፖለቲካ ትርፍ አያገኝም ነበር።

በኢህአዴግ ውስጥ የነበረው ማርክሣዊ ሌኒናዊ ኃይል ዓለም አቀፍ ሁኔታውን በቅርብ በመከታተል እ.ኤ.አ. ከ1989 ጀምሮ በመጣው ለውጥ ኒዮ-ሊበራሊዝም በድል አድራጊነት መውጣቱን ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። ከዚህ በመነሳት "ሶሻሊዝም መጥፎ ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ ባይደርስም በአዲሱ ዓለማዊና አገራዊ ሁኔታ ተግባራዊ ሊደረግ እንደማይችል ግን ሙሉ በሙሉ ተስማማ። በዚህም አብዮታዊ ዴሞክራሲን ተግባራዊ ካደረገ ከተነጻጻሪ መለስተኛ ጊዜ በኋላ ወደሶሻሊዝም ለመረማመድ የነበረውን ፕሮግራም ሙሉ በሙሉ ሰረዘው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሶሻሊዝምን ሀሳቦች እርግፍ አድርጐ በመተው፣ የገበያ ሥርዓት በመገንባት ማዕቀፍ የአገራችን ብዙኃን ህዝቦች መብትና ጥቅም በተነጻጻሪ ተሟልቶ እንዲከበር ለማድረግ ቆርጦ ተነሳ። በተለምዶ በዝርፊያ ከሚከበርበት የገበያ ሥርዓት ይልቅ የጋራ ተጠቃሚነት በሚረጋገጥበት አቅጣጫ ሰርቶ የሚከበርበት የገበያ ሥርዓት ለመገንባት መንቀሳቀስ ጀመረ።

ይህ የአቋም ለውጥ በኢህአዴግ ውስጥ የነበረው ግራ ዘመም ኃይል የተለወጠውን ዓለማዊ ሁኔታ በውል ለመገንዘብና ከጊዜው ጋር አብሮ ለመራመድ ከነበረው ፍላጐት የመነጨ ነው። ዓለም በተለወጠበት ዘመን በሁኔታዎች ግምገማ አዲስ እውነታ እንደተፈጠረና ይህም አዳዲስ አቅጣጫዎችን መከተል እንደሚጠይቅ በመገንዘብ ራስን ለለውጥ ማዘጋጀት በቀላሉ የማይገኝ ብቃት ነው። በአንድ በኩል ከልብ በህዝብ መተማመንን፣ በሌላ በኩል በመርህ ተገዝቶ ለእያንዳንዱ ተጨባጭ ሁኔታ ብቁ መልስ የመስጠት ችሎታ ላይ መድረስን ይጠይቃል። ብዙ ፓርቲዎች ይህን መሰሉን የተለወጠ ሁኔታ በመገምገም ራሳቸውን ከአዲሱ ሁኔታ ጋር ማጣጣም አቅቷቸው ለአደጋ ተጋልጠዋል። ኢህአዴግ ውስጥ የነበረው ግራ ዘመም ኃይል ግን "ካፈርኩ አይመልሰኝ" በሚል ግትርነት ይህን መንገድ መከተል አልመረጠም። ምንም እንኳ የተሟላ የአቋም ለውጥ የተካሔደው በ1990ዎቹ መጀመሪያ በኢህአዴግ አመራር መካከል በተቀሰቀሰው ልዩነት ራሱን ከድርጅቱ ያገለለው ቡድን "ኢህአዴግ የሶሻሊዝምን መንገድ ትቶ ነጭ ካፒታሊዝምን መገንባቱን እቃወማለሁ፣" ካለ በኋላ ቢሆንም ኢህአዴግ የገበያ ሥርዓት በመገንባት ብቻ የመወሰን የአቋም ለውጥ ያሳየው ከበርሊን ግንብ መፍረስ ማግሥት ነው። ይህም ሆኖ የገበያ ሥርዓትን እንዳለ በጥሬው የመኮረጅ ፍላጐት አልነበረውም።

በኢትዮጵያ መገንባት ያለበት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሥርዓት ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የገበያ ቢሆንም፣ በዚህ ውስጥ የማን ጥቅም ይከበር? የሚለው ጥያቄ ብዙ አከራካሪ ጉዳዮችና

ልዩነቶች አሉበት፡፡ ይህን ልዩነት በቅጡ ለመገንዘብ የገበያ ሥርዓትን የሚመለከቱ አንኳኑድ መሠረታዊ ሀቆችን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ ኢህአዴግ የሚያልመውን የገበያ ሥርዓት ይዘትና ባሕርይ በትክክል ተገንዝቦ ለመፍረድ ይቻል ዘንድ ስለገበያ ሥርዓት ምንነት የተወሰኑ መነሻ ሀሳቦችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

የገበያ ሥርዓትና ልዩ ልዩ ገጽታዎቹ፣

በኢትዮጵያ እንዲገነባ የሚፈለገው በገበያ የሚመራ ካፒታሊስታዊ ሥርዓት ለዓለማችን አዲስ አይደለም፡፡ ላለፉት አምስት መቶ ዓመታት ያህል በምድራችን ሰፍኖ የቆየ ነው፡፡ በሰዎች መካከል የመገበያየት ግንኙነት የተጀመረው ትርፍ ምርት መታየት ከጀመረበት ጥንታዊ ጊዜ አንስቶ ቢሆንም፣ ሕብረተሰብ በካፒታሊስታዊ ሥርዓት መልክ ተዋቅሮ በካፒታል የበላይነት ሥር መንቀሳቀስ ከጀመረ ግን ከግማሽ ሚሌንየም ብዙም አልራቀም፡፡ ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት አሐዱ ብሎ ቬኒስና ፍሎረንስን በመሳሰሉ የጣሊያን ከተሞች ከታየበት ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ባሉት ሁለትና ሦስት መቶ ዓመታት ሂደት ታላላቆቹን የምዕራብ አውሮፖ አገሮች ለመሸፈን በቅቷል።

በቅድሚያ እንግሊዝን፣ በማስከተል ስፔን፣ ዳችና ፈረንሳይን፣ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ደግሞ እነጀርመንን የሸፈነው የገበያ ሥርዓት "ካፒታሊስታዊ የሆነ የገበያ ሥርዓት" (Capitalist Market Economy) በመባል ይታወቃል፡፡ በምሥራቅ እስያ አገሮች ደግሞ ከምዕራቡ ዓለም ለየት ባለ ሂደትና ካፒታሊስታዊ ባልሆነ መንገድ ረዘም ላሉ ከፍለ ዘመናት የተገነባ የገበያ ሥርዓት ይገኛል። በግብርናና በጐጆ ኢንዱስትሪ ምርቶች ልውውጥ ላይ የተመሠረተና የራሱ ለየት ያለ ባህርይ የነበረው ይህ የገበያ ሥርዓት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ በጃፓን በተቀሰቀሰው ፈጣን ኢንዱስትሪያዊ ልማት እየተመራ ምሥራቅ እስያን ሊሸፍን ችሏል፡፡ በተለይ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ደግሞ በህዝብ ብዛት ቀዳሚዋን ቻይና ጨምሮ ብዙ የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮችን ወደተሟላ የገበያ ሥርዓት ለማሸጋገር በቅቷል፡፡ ጆቫኒ አሪጊ (1994) ይህን ዓይነቱን የገበያ ሥርዓት "ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የገበያ ሥርዓት" (Non-Capitalist Market Economy) ብሎ ይጠራዋል፡፡ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ደግሞ የመጀመሪያው "ጥቂቶች ብዙኃኑን እያደኸዩ የሚከብሩበት"[6] (Accumulation by Dispossession) ሲሆን የኋለኛው ተያይዞ ማደግ የሚቻልበት ነው ይላል፡፡ ከዚህ በመነሳት በእርግጥም ካፒታሊዝም በመሠረታዊ አቅጣጫው አንድ ቢሆንም ከአገር ወደአገር ልዩነት የሚታይበትና በሁሉም አገር አንድ ዓይነት ቅርጽና ፍፁም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሥርዓት አለመሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በየአገሩ የሚታዩ ተመሳሳይ ባሕርያትንና ልዩነቶችን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

ሁሉም የገበያ ሥርዓት የምርት ተግባር የሚከናነው በዋነኛነት ለራስ ፍጆታ ሳይሆን ለገበያ ተብሎ ነው። ባለሀብቱ ገንዘብ አሰማርቶ ምርትና አገልገሎት ካመረተ በኋላ ይህንኑ ወደገበያ አውጥቶ ለሸማቾች በመሸጥ መጀመሪያ ካሰማራው የላቀ ገንዘብ ማግኘቱም የገበያ ሥርዓት ሁሉ ባህርይ ነው። ይህ የአመራረት ሥርዓት በቅድሚያ በአንዳንድ የጣሊያን ከተሞች ከታየ በኋላ በኢንዱስትሪ አብዮት አማካይነት በእንግሊዝ አገራዊ የበላይነቱን ካረጋገጠ ጀምሮ በአጠቃላይ በዓለም በተለይ ደግሞ በምድረ አውሮፓና አሜሪካ የራሱን አገራዊ ገጽታ ይዞ በመገንባት በድምሩ የበላይ ሊሆን ችሏል።

እንግሊዝ በጨርቃ ጨርቅ በተለይም በሱፍ ጨርቅ ምርት ዙሪያ ኢንዱስትሪያዊ አቅሟን መገንባት የጀመረችበት ይህ የካፒታሊስታዊ ገበያ ሥርዓት ግንባታ ሂደት እዚያው ሳለም አርሶ አደሩን ከመሬት በማፈናቀል የተከናወነ ነበር። አርሶ አደሩ ይዞት የነበረውን የእርሻ መሬት እየነጠቁ የሱፍ ልብስ ለማምረት ዋነኛ ግብዓት የነበረውን የበግ ጸጉር በገፍ ለማቅረብ የቋመጡት የእንግሊዝ ባለሀብቶች ገበሬውን በጉልበት ከመሬት እያፈናቀሉ የበግ እርባታን አስፋፉ። ታዋቂው የማኅበረሰብ ተመራማሪ ዶክተር ባሪንግተን ሙር "በጐቹ ሰዎቹን በሏቸው"[7] እስኪል ድረስ በተካሔደው ዘግናኝ ሂደት የተፈናቀለው የእንግሊዝ አርሶ አደር ምንም ሀብት ንብረት እንዳይኖረው ተደረገ። በዚህ የተነሳ ገጠሩን እየለቀቀ ወደከተሞች ለማቅናት ተገደደ።

ከመሬቱ ተባርሮ የእንግሊዝ ከተሞችን ያጥለቀለቀው ተፈናቃይ የመጀመሪያ እጣ ፈንታው ሥራ አጥነትና ያጣ የነጣ ድኅነት ነበር። በዚህ የተነሳ ለመኖር ሲል ጉልበቱን ሸጦ ለማደር ተገደደ። ይህም በወቅቱ ጀማሪ ለነበሩት የአገሪቱ ኢንዱስትሪዎች በርካሽ ተቀጥሮ የሚሠራ ብዙ የሰው ኃይል ወይም ጉልበት ለማቅረብ ሰፊ ዕድል ከፈተ። የሰው ኃይል አቅርቦቱ በተነጻጻሪ ሰፊ ስለነበር የፋብሪካ ሥራ የሚገኘው በሠራተኞች መካከል በሚካሔድ ከባድ ፉክክር ነበር። ይህም ባለሀብቶቹ ለጉልበት የሚከፍሉትን ዋጋ ዝቅ ለማድረግ ሰፊ ዕድል ፈጠረላቸው። በዚህ የተነሳ እንግሊዛዊያን ከበርቴዎች መሬቱን ከመንጠቅ አልፈው ይህን አዲስ የሀብት ምንጭ በቀን አሥራ ስድስት ሰዓት ለዚያውም እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ክፍያ እያሠሩ ከፍተኛ ሀብት እንዲፈጥርላቸው አደረጉት። ስለዚህም፣ አውሮፓዊው የገበያ ሥርዓት ብዙኅኑን ከመሬት በማፈናቀል ንብረት አልባ አድርጐ በዝቅተኛ ምንዳ በመመዝበር የጀመረ ካፒታሊዝም ሆነ።

የኢንዱስትሪ አብዮት ጀማሪዎች የሆኑት እንግሊዛውያን በዚህ ዕድል በመጠቀም በፈጠሩት የካፒታልና የቴክኖሎጅ አቅም ራሳቸውን የወቅቱ ብቸኛ ዓለማዊ ልእለ ኃያል አድርገዋል። ልእለ ኃያልነታቸው በሰጣቸው ብልጫ ታግዘውም የአገራቸውን ኢንዱስትሪና ገበያ ማንም ሌላ ተፎካካሪ እንዳይደርስበት ተከላከለዋል። በዚህም "የራስን ገበያ" የመከላከል (Protectionism) ጀማሪዎችም ነበሩ። እንግሊዛውያን ኢንዱስትሪያቸውን አሳድገው ይህንኑ በሕግ ድጋፍ መከላከል የማያስፈልጋቸው ደረጃ ላይ ሲደርሱ ደግሞ ሌሎች አገሮች የውስጥ

ገበያቸውን ስለመዝጋት እንዳያስቡ ማስገደድ ጀመሩ። ሐ ጁን ቻንግ፣ ታዋቂው ጀርመናዊ ኢኮኖሚስት ፍሬድሪክ ሊስት "መሰላሉን ስለመግፋት"[8] ያቀረበውን ምሣሌ በመጥቀስ ይህን ያረጋግጣል። ይህ ተምሣሌያዊ አገላለጽ እንግሊዝ በጀማሪው የካፒታሊዝም ግንባታ ወቅት በመሰላል ሊመሰል በሚችለው መንግሥታዊ ድጋፍ ተንጠላጥላ ወደላይ ወጥታ ከፍተኛውን ማማ ከተቆናጠጠች በኋላ ሌሎች እንዳይከተሏት መሰላሉን ገፍታ በመጣል ብቸኛ ተጠቃሚ ለመሆን ያደረገችውን ጥረት የሚያመላክት ነው።

እንግሊዞች የኢንዱስትሪ አብዮት በማካሔድ ቀዳሚ ቢሆኑም ሂደቱ ሳይውል ሳያድር ምድረ አውሮፓን እስከመሸፈን ደርሷል። ዘገየ ቢባል እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የቀጠለው የአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮት የማኑፋክቸሪንግ አቅምን በማስፋፋት የተፈጸመ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዋነኛነት ዝቅተኛ ገቢ ያለውን ሕብረተሰብ ጉልበት በርካሽ ዋጋ በመምጠጥ ላይ የተመሠረተ ሂደት ነበር። ይህም በመሆኑ የአውሮፓ ኢንዱስትሪያላይዜሽን ፈረንጆች "ጐረቤትህን ማደህየት" /Beggar thy neighbour/ ብለው በሚገልፁት አኳኋን ብዙኃኑ እየተራቆቱ ጥቂቶች በሚበለጽጉበት አቅጣጫ የተገነባ ሊሆን ቻለ። ብዙኃኑ አውሮፓውያን በተራዘመ ሂደት ከሌሎች የዓለም ህዝቦች ለተሻለ የኑሮ ደረጃ መብቃታቸው ይህን እውነታ የሚቀይረው አይደለም። ጆቫኒ አሪጊ ይህን "ሌሎችን በማራቆት ሀብት የማግበስበስ ሂደት" በማለት የገለጸው ያለምክንያት አይደለም። የሊበራል የገበያ ኢኮኖሚ ንድፈ-ሀሳብ አመንጭ የሆነው አዳም ስሚዝም ቢሆን ያረጋገጠው ይህንኑ ነው። አዳም ስሚዝ አውሮፓውያኑ የካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት መሥራቾች ግዙፍ ኃይል ገንብተው በስተምዕራብ አሜሪካንን፣ በምሥራቅ ደግሞ በኬፕ አፍ ጉድ ሆፕስ በኩል አልፈው የኢስት ኢንዲስ አገሮችን ማስገበራቸውን መነሻ በማድረግ፡-

> "የወረራና ማስገበር ኩነቶቹ ለሰው ልጆች ይዘውት የመጡትን ትሩፋትና ሰቆቃ የትኛውም ምጡቅ አስተሳሰብ ያለው ሰው አስቀድሞ ሊተነበየው አይችልም ነበር። በአንድ በኩል በጣም የተራራቁ ህዝቦችን አንድነት በማፋጠን፣ አንዱ የሌላውን ፍላጐት በሚያረካ፣ አንዱ ለሌላው ደስታ በሚጨምር አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ፣ በሌላ በኩል የእያንዳንዱን የኢንዱስትሪ ልማት በማበረታታት አዝማሚያቸው ጠቃሚ ይመስላሉ። ይህም ሆኖ በምዕራብና በምሥራቅ ኢንዲስ ለተወረሩት ህዝቦች ከዚህ ዓይነቱ ኩነት ሊገኝ ይችል የነበረው ጥቅም ሁሉ በተፈጸመባቸው ግፍና በደል የተነሳ ጨርሶ ሊጠፋ ችሏል። ወረራው በተፈጸመበት ወቅት አውሮፓውያኑ የተሟላ የኃይል ብልጫ ስለነበራቸው በእነዚህ ህዝቦች ላይ በፍፁም ህሊና ቢስነት ያልፈጸሙት ዘግናኝ

ግፍ አልነበረም።/ሰረዝ የተጨመረ/ ወደፊት ምናልባትም የእነዚህ አገሮች ጥንካሬ ጨምሮ፣ ወይም ደግሞ አውሮፓውያኑ ተዳክመው በሁሉም የዓለም ማዕዘናት የሚገኙ ህዝቦች ወደተመጣጣኝ የኃይልና ድፍረት ደረጃ ደርሰው በሚፈጠር የወል ፍርሐት የተነሳ፣ የአውሮፓ ነጻ አገሮች የሚፈጽሙትን ወንጀል አስቁሞ አንዱ የሌላውን መብት ወደሚያከብርበት ምዕራፍ እንሸጋገር ይሆናል። ይህን የመሰለው የኃይል አቻነት ግን በአገሮች መካከል ከሚካሔድ መሠረተ-ሰፊ የንግድ ልውውጥና ይህን ተከትሎ ከሚስፋፋ እውቀትና የጋራ መሻሻል ውጭ እውን ይሆናል ተብሎ አይታሰብም።"[9] በማለት ነበር።

ከዚህ የአዳም ስሚዝ ሀሳብ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ምዕራባውያኑ ገና ከጠዋቱ ካፒታልን በስፋትና በብዛት በመጠቀም ላይ በተመሠረተውና ነገረ ሥራው ሁሉ ካፒታል ተኮር በሆነው የኢኮኖሚ ልማት ቅኝታቸው መልካም ነገሮችን ብቻ ሳይሆን በሰብዓዊ ፍጡራን ላይ የሚዘገንን ግፍ ፈጽመዋል። በተጨባጭ የሚታወቀው የቅኝ አገዛዝ የታሪክ ማህደራቸውም ይህን የሚያረጋግጥ ነው። የምዕራብ አውሮፓና የአሜሪካ የገበያ ሥርዓት ገና ከመጀመሪያው ብዙኃኑን በማራቆት ጥቂቶችን የማበልጸግ አቅጣጫ ተከትሎ የተገነባው ከዚህ በተነሳ ነው። ስለዚህም የገበያ ቅኝት ያለው ብቻ ሳይሆን የካፒታልን የበላይነትና የብዙኃኑን መመዝበር ያረጋገጠ ሥርዓትም ነው። ይህን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓ የኢኮኖሚ ቀውስን ለመፍታት ያስቻለውን የኢኮኖሚ ምክረ-ሀሳብ ያፈለቀውን ኬይንስ በመጥቀስም ማረጋገጥ ይቻላል። ኬይንስ ካፒታል ለማከማቸት ሲባልና በአምልኮተ-ገንዘብ ላይ ተመሥርቶ የሚካሄደውን የካፒታሊዝም እንቅስቃሴ መነሻ በማድረግ፦

"ሀብት ማከማቸት ከምንም ነገር የላቀ የሕይወት ሙሉ መሆኑ ሲያቋርጥ በሰው ልጆች ሥነ-ምግባራዊ እሴቶች ላይ ከፍተኛ መሻሻል መታየት ይጀምራል። ... ንብረት ለማከማቸት ሰንል ያዳበርነውን አፍቅሮተ ገንዘብ፣ እውነተኛ ደስታን ለመሸመት ከሚያስፈልገን ገንዘብ ለያይተን መመልከት ስንጀምር ለከፊል ወንጀለኛና ከፊል የሉአምሮ በሽተኛነት ዳርጐ ሞት እንዲጠናወተን ካደረገን አስተሳሰብ መላቀቅ እንጀምራለን። ውጤታቸው መጥፎ ሆኖ እያለ በማንኛውም ስልት ታግዘን የምንጠብቃቸውንና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልንና የኢኮኖሚ ማትጊያና ቅጣት እደላን የሚወስኑትን ማኅበራዊ ልምዶች አሽቀንጥረን ለመጣል በምንችልበት ደረጃ ነጻ እንሆናለን።"[10] ይላል።

አዳም ስሚዝም ሆነ ኬይንስ በከፍተኛ ደረጃ የተሟገቱለትና በሂደቱም ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያሳረፉበት ካፒታሊዝም በሰው ልጆች የዕድገት ደረጃ ላይ የተከሰተ አንድ ራሱን የቻለና ብዙ

መልካምና ፈታኝ ነገሮች የሞሉበት ሕብረተሰብ ነው። ካፒታሊዝም ላለፉት አምስተ መቶ ዓመታት ዋናው የዓለማችን አመራረትና ማኅበራዊ ግንኙነት ሆኖ የቆየ ሲሆን ሕብረተሰቡም በዋነኛነት በካፒታል የበላይነት ላይ የተመሠረተ ነው። ካፒታል በሰው ልጅ ጉልበት የተመረተ ሀብትና ራሱን የቻለ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ነው። የሰው ጉልበት የፈጠረውን ይህን ሀብት የተቆጣጠሩ ሰዎች (ባለሀብቶች) በእጃቸው የገባውን ካፒታል በመጠቀም አዳዲስ ሠራተኛ እየቀጠሩ በማሠራት ካፒታላቸውን ያለማቋረጥ ያሳድጋሉ። ያፈሩትን ምርትና አገልግሎት ለገበያ አቅርበው በመሸጥ ትርፋቸውን እውን ያደርጋሉ። በትንሽ ገንዘብ ስምሪት ጀምረው በማምረትና በመሸጥ ሂደት የማታ ማታ በትርፍ መልከ የላቀ ገንዘብ ያገኛሉ። በዚህ አኳኋን የሥርዓቱ አልፋ ኦሜጋ የሆነውን የካፒታልን የበላይነት ለማረጋገጥ ይችላሉ።

አውሮፓዊው ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት ገና ከጠዋቱ ከሰው ኃይል ይልቅ፣ ብዙ ካፒታልን በማንቀሳቀስ ላይ የተመሠረተ ከመሆኑ በተጨማሪ ከጉልበት ይልቅ ማሽነሪን ዋነኛ የሥራ ማሳለጫ በማድረግ ላይ የተመሠረተ ነበር። እንደሚታወቀው አውሮፓ ከአውስትራሊያና ከአሜሪካ ቀጥሎ አነስተኛው የዓለማችን ማኅበረሰብ የሚኖርበትና እጅግ ጠባብ በሆነ መሬት ላይ የተመሠረተ ክፍለ-ዓለም ነው። እያንዳንዱ አገርም ሆነ ከፍለ ዓለሙ በድምር ትንሽ ህዝብ የሰፈረባቸው ናቸው። መሬታቸውም ከአሜሪካን በስተቀር በጣም ጠባብ ነው። ስለዚህም፣ አውሮፓውያን ብዙ ጉልበትና ሰፊ መሬትን በመጠቀም ተማምነው ሊለሙ አይችሉም ነበር። ይህ ውሱንነት ሊቃለል ይችል የነበረው በኃይል ምንጭ (Energy) የሚንቀሳቀስ ማሽነሪን በስፋት በመጠቀም ስለነበር፣ የኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫቸው የኃይል ምንጭን በስፋትና በብዛት በመጠቀም ላይ የተመሠረተ ሆነ። በዚህ የተነሳ መጀመሪያ የድንጋይ ከሰልን፣ በሂደት ደግሞ ነዳጅን በሰፊው በመጠቀም ለአካባቢ ብክለት መጨመር ዋነኞቹ ምክንያቶች ሆኑ። ምዕራባውያኑ ለዓለም ብከለት ብዙም ደንታ ሳይኖራቸው ዋነኞቹ የኃይድሮ ካርቦን ተጠቃሚዎችና የበካይ ጋዞች አመንጭዎች ሆነው የኖሩበት አይነተኛ ምክንያትም ይኸው ነው።

በምዕራቡ ዓለም የተገነባው ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት በዋነኛነት በካፒታልና የኃይል ምንጭ ሰፊ ተጠቃሚነት አቅጣጫን ተከትሎ የካፒታልን የበላይነት ያረጋገጠና ብዙኃኑን እያደኸየ ጥቂቶችን የማበልጸግ አቅጣጫ የሚከተል የሆነው በዚህ ምክንያት ነው። የምዕራቡን ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት ፈለግ (Model) እከተላለሁ የሚል ሁሉ ተወደደም ተጠላም እነዚህን መሠረታዊ አቅጣጫዎች ከነሙሉ ትርጉማቸውና እንድምታቸው በመቀበል ሊሆን ይገባል። ነገር ግን የገበያ ሥርዓት ካፒታሊስታዊ ብቻ ሳይሆን ካፒታሊስታዊ ባልሆነ ቅኝትና አቅጣጫ ሊገነባ እንደሚችል በዓለማችን ምሥራቃዊ ክፍል ላይ ታይቷልና ምዕራባዊው የዕድገት አቅጣጫ ብቸኛው አማራጭ ነው ሊባል አይችልም።

በአውሮፓ ካፒታሊስታዊው የገበያ ሥርዓት ከተገነባበት ተመሳሳይ ወቅት ጀምሮ በምሥራቁ የዓለማችን ከፍል ካፒታሊስታዊ ያልሆነው የገበያ ሥርዓት በመገንባት ላይ ነበር። ቻይናን ማዕከል በማድረግ የተካሔደው የገበያ ሥርዓት ግንባታ አውሮፓ ላይ ከነበረው የገበያ ሥርዓት የተለየና የራሱ ባህሪያት የነበሩት ነው። በ20ኛው ክፍለ ዘመን "የሰሜን ምሥራቅ እስያ ነብሮች" (Asian Tigers) ተብለው በተሰየሙት አገሮችና በራስዋ በቻይና እየተገነባ ያለው የገበያ ሥርዓት ይህንኑ ልዩነት አስጠብቆ ቀጥሏል።

አውሮፓ መሠልጠን በጀመረበት ጊዜ ምሥራቅ እስያ ወደፊት የተራመደ እንደነበር በጥናት ያረጋገጠው ካኦሩ ሱጊሐራ (2003) እ.ኤ.አ ከ1800 በፊት በሁለቱ ክፍለ ዓለሞች የታየው መሠረታዊ የአቅጣጫ ልዩነት በህዝብና መሬት ምጣኔ ልዩነት ላይ የተመሠረተ እንደነበር ያወሳል። በምሥራቁ ዓለም የሚገኙት ትልልቅ አገሮች በአንድ በኩል የህዝብ ብዛት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመሬት ጥበት ነበራቸው። ይህ እውነታ እነዚህ አገሮች ከአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮት (Industrial Revolution) በተለየ ቅኝት የተካሔደውን የራሳቸውን የኢንዱስትሪያዊነት አብዮት (Industrious Revolution) እንዲያካሂዱ አድርጓቸዋል። ከ16ኛው እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን በነበሩት ወሳኝ ዓመታት የምሥራቅ እስያን የተፈጥሮ ሀብት ውሱንነት፣ በተለይ ደግሞ የነበረባቸውን የመሬት እጥረት ለመቅረፍ እንደሚያስችል የታመነበት ዋናው የልማት አቅጣጫ ጉልበትን በስፋት የሚጠቀሙ ቴክኖሎጂዎችና ተቋማት መገንባት ነበር። ጉልበት በጣም ተፈላጊ በሆነበት በምሥራቅ እስያ አገሮች የሰው ልጆችን መራባት የሚያበረታታ ሁኔታ በመፈጠሩ በአጭር ጊዜ የህዝቡ ቁጥር በእጅጉ ሊጨምር ቻለ። ይህም በሱጊሐራ አተያይ የህዝብ አኗኗር በሚያሽቆለቁልበት ሳይሆን ተነጻጻሪ መሻሻል በሚያመጣበት አኳኋን የተፈጸመ ነበር። ከዚህ በመነሳት ካኦሩ ሱጊሐራ፦

> "ይህ ከፍተኛ የህዝብ ብዛትና በዓለም አጠቃላይ ኢኮኖሚ (GDP) ላይ የነበረው ተፅዕኖ በእንግሊዝ ከተካሔደው የኢንዱስትሪ አብዮት የላቀ ውጤት ያስገኘ ነበር። እንግሊዝ ከኢንዱስትሪ አብዮቱ በኋላ በዓለም ኢኮኖሚ ከነበራት ከ6% ያነሰ ድርሻ በእጅጉ የላቀ ነበር። ይህ የቻይና ተአምራዊ ውጤት አነስ ያለ መልከዓ ምድርና የህዝብ ዕድገት ምጣኔ በነበራት ጃፓን ላይ ደግሞ የላቀ የህዝብ የኑሮ ደረጃ መሻሻል አምጥቷል። ...ይህ የዕድገት አማራጭ በገበያ ላይ የተመሠረተ ዕድገት ቢሆንም፣ በእንግሊዝ እንደታየውና ወደአሜሪካ እንደተስፋፋው ካፒታልን በስፋት የመፍጠርና የመጠቀምም ሆነ የኃይል ምንጭን በስፋት በመጠቀም ላይ ያተኮረ የዕድገት አቅጣጫ አልነበረም"[11] ይላል።

ከዓለም ህዝቦት ውስጥ እስከ ሃያ አምስተ ዘመኑ ያህሉ በንሥራዋ አበያ ይኖራል። በዚህ ክፍለ ዓለም የሚገኙ አገሮች ከምንም ነገር በላይ ዋናው ሀብታቸው ብዛት ያለው ሰብዓዊ ኃይላቸው ነው። ይህም በመሆኑ፣ የልማት ዕድላቸው ሰብዓዊ ኃይላቸውን ለማልማትና ለመንከባከብ ባላቸው ችሎታ ይወሰናል። በእነዚህ አካባቢዎች በህዝብ ጉልበት በመተማመን የሚካሔድ ማንኛውም ልማት የመሳካት ዕድሉ ሰፊ ነው። በአንጻሩ የህዝብን ጉልበት የሚያመክን ማንኛውም አቅጣጫ ደግሞ አገሮቹን በማያቋርጥ የድኅነት አዙሪት ውስጥ ያሽከረክራቸዋል። የህዝቡን ጉልበት ዋነኛ መተማመኛ ማድረግ የሚቻለው ደግሞ በሰብዓዊ ልማት ላይ በማተኮር፣ በትምሕርትና ሥልጠና አማካይነት እውቀትና ክህሎት እንዲሰፋፋና በዚህም ህዝቡ ገቢውን እንዲያሻሽል በማድረግ ነው። ስለዚህም፣ የምሥራቅ እስያና የምዕራቡ ዓለም የገበያ ሥርዓቶች የየራሳቸው የተለየ ገጽታ አላቸው። በተለይም በታላቋ ቻይና ታሪክ በግልጽ እንደታየው የምሥራቁ ዓለም የገበያ ሥርዓት የሰው ልጆችን እየዘረፉ በማራቆትና በብዙኀን ጉስቁልና ጥቂቶችን በማበልጸግ ላይ የተመሠረተ አይደለም። ይልቁንም፣ በጋራ ተያይዞ የማደግ መንገድን የተከተለ የልማት አቅጣጫ ነው። በዛሬዋ ቻይና የሚታየው እውነታም ይህን የሚያረጋግጥ ነው።

ካፒታሊስት ባልሆነ የገበያ ሥርዓት ስትመራ የኖረችው ቻይና እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ድረስ ከዓለማችን እጅግ ሀብታሚ አገር ነበረች። እስከ 19ኛው ክፍል ዘመን መጀመሪያ ድረስ የአገሪቱ ዜጐች የነፍስ ወከፍ ገቢ ከዓለም ትልቁ ነበር። "የኦፕየም ጦርነት" በመባል እስከሚታወቀው ግጭት ድረስ ደግሞ ቻይና የዓለማችን ዋናዋ ልእለ-ኃያል አገር ነበረች። አዳም ስሚዝ እ.ኤ.አ. በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ "የቻይና የአገር ውስጥ ገበያ ሁሉም የአውሮፓ አገሮች በድምር ከነበራቸው ገበያ የማይተናነስ ነበር"[12] በማለት ቻይና ሰብዓዊ ሀብትን ማዕከል ባደረገ ልማት ቀዳሚዋና ከየትኛውም የአውሮፓ ክፍል የላቀ ብልጽግና እንደነበራት አመላክቷል። በቻይና ማዕከልነት የተካሔደው ይህ የምሥራቅ እስያ ህዝቦች የረጅም ጊዜ ሥልጣኔ በዋነኛነት ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የገበያ ኢኮኖሚ አቅጣጫን በመከተል የተገነባ ነበር።

ይህም ሆኖ የቻይና ገናናነት እንደ አጀማመሩ አልቀጠለም። ሱጊሐራ (2003) በአንድ በኩል ከፍተኛ የህዝብ ብዛት ይዞ ነገር ግን የኑሮ ደረጃን በተወሰነ ደረጃ እንጂ በቀጣይነት ለማሻሻል የሚቸገር አገር "ከፍ ባለ የአቻነት ወጥመድ (High level Equilibrium trap) ውስጥ መግባቱ የማይቀር ነው" ይላል። በዚህ የተነሳ ቻይናም የዕድገት መገታት ወጥመድ ላይ ወደቀች። በዚህ ላይ የነቀዘው አስተዳደሯ እንግሊዝና ፈረንሳይ በትብብር በሰነዘሩበት ተደጋጋሚ ጥቃት በመሸነፉ እ.ኤ.አ. ከ1840 ጀምሮ እስከ 1949 በነበሩት ዓመታት ደካማና ለመበታተን የተቃረበች አገር ልትሆን ተገደደች። ቻይና ከዚህ ዓይነቱ ድከመት መውጣት የጀመረችው፣ በአጠቃላይ እ.ኤ.አ. ከ1949 ጀምሮ ራሷን ከውጭ ተፅዕኖ ያላቀቃት የሥርዓት ለውጥ በማካሔድ፣ በተለይ ደግሞ ከ1978 በኋላ በለኮሰችው "የማሻሻልና ግልጽነት"

(Reform and Openness) እንቅስቃሴ ብቻ ነው። ቻይና ከዚህ ጊዜ ወዲህ ባሉት 37 ዓመታት ወደሰባት መቶ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ከድኅነት ወለል አውጥታ ወደመካከለኛ ገቢ እንዲሸጋገር አድርጋለች። ይህ ቁጥር ከሞላ ጐደል አውሮፓና አሜሪካ በድምር ካላቸው የህዝብ ብዛት ጋር እኩል ነው።

በምዕራቡ ዓለም ይህን የመሰለው ለውጥ ይመጣ ዘንድ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ የወሰደና አፈጻጸሙ እጅግ አዝጋሚ ነበር። በአንድ በኩል በብዙኀኑ ድኅነት ጥቂቶችን የማበልጸግ አቅጣጫቸው፣ በሌላ በኩል የድንጋይ ከሰልንና በኋላም የነዳጅ ኃይልን የመጠቀም አቅጣጫቸው ባሳደረበት ተፅዕኖ ምክንያት የብዙኃኑን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ጉዳይ ረዥም ጊዜ ወስዷል። በዚያው ልክ ደግሞ ፍትሃዊነት የጐደለው ሂደትም ነበር። በአንጻሩ በምሥራቁ ዓለም የተገነባው የገበያ ሥርዓት በኃይል ምንጭ ልማትና አጠቃቀም ረገድ የተከተለው አቅጣጫ ከሞላ ጐደል ለአረንጓዴ ልማት ትኩረት የሚሰጥ መሆኑ በተግባር የተሻለ ውጤት የተገኘበት ሊሆን ችሏል።

የምሥራቁ ዓለም ዋናው መተማመኛ ሰብዓዊ ኃይሉ መሆኑን ተከትሎ ዋነኛ የልማት አቅጣጫው በሰብዓዊ ልማት እንጅ በኃይል ምንጭ ሰፊ ተጠቃሚነት ላይ ያተኮረ ሆኖ አልተቀየሰም። ስለሆነም እጅግ አብዛኛው ሥራ የሚከናወነው ኃይልን ወይም ጉልበትን በሰፊው በማንቀሳቀስ ነው። ዛሬ ቻይና የዓለማችን ቀዳሚ ኢኮኖሚ መሆን ብትጀምርም በኃይል አጠቃቀም ረገድ በህዝብ ብዛት የእርሷን አርባ በመቶ ያህል ብቻ ከሚሆነው አውሮፓ በእጅጉ ያነሰ ደረጃ ላይ ትገኛለች። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ከመኪና ይልቅ ሞተር ሳይክልና ሳይክልን፣ አሁን ደግሞ እንደ ጥይት የሚፈጥኑ ባቡሮችን ዋነኛ የመጓጓዣ አውታር ማድረግ በመረጠችው ቻይና የኃይል አጠቃቀም ከምዕራቡ ዓለም ጋር ሲነጻጸር በእርግጥም በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ጆቫኒ አሪጊ እንደሚገልጸው የምሥራቁ ዓለም ይህን አቅጣጫውን ትቶ ልክ እንደምዕራባውያን አገሮች በአንድ ቤት ሦስትና አራት መኪኖችን መጠቀም የጀመረ ቀን ዓለማችን ወደእቶን እሣትነት[13] እንደምትቀየር ብዙም አያከራክርም።

የገበያ ሥርዓት በእነዚህ ሁለት መሠረታዊ ልዩነቶች ላይ የተገነባ ከመሆኑ በተጨማሪ በእያንዳንዱ ዋነኛ ፈለግ ደረጃም ልዩነቶች የሚታዩበት ነው። በአውሮፓና በአሜሪካ የገበያ ሥርዓቶች መካከል ራሱን የቻለ ልዩነት ይታያል። በሰሜንና በደቡብ አውሮፓ ካፒታሊዝም መካከል ጉልህ ልዩነት አለ። የጀርመንና የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና የጀርመን ካፒታሊዝምም በሁለመናቸው አንድ አይደሉም። ስለሆነም ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም። ካፒታሊስታዊ ያልሆነው የገበያ ሥርዓትም ቢሆን አንድ ወጥ ሳይሆን መልከ ብዙ ሥርዓት ነው። በጃፓን፣ በኮሪያ፣ በታይዋን፣ በሲንጋፖርና ሆንግ ኮንግ አሁን ደግሞ በቻይና የገበያ ኢኮኖሚዎች መካከል ጉልህ መመሳሰል ብቻ ሳይሆን ትንሽ የማይባሉ ልዩነቶችም ይታያሉ። ስለሆነም የገበያ ሥርዓት ከአገሮችና ክፍላተ ዓለማት ልዩና ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት

የተገነባ ብዙኅነት ያለው ሥርዓት ነው። ብዙ መጥፎና ጥሩ ነገሮችን አደባልቆ የያዘና ለአገሮችና ልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች እንደየምርጫቸው የተለያየ ዕድል የሚሰጥ ሥርዓት ነው። በዚህ ምክንያት የገበያ ሥርዓትን በአንድ ወጥነት እያሰቡ፣ ልክ በገፍ እንደሚመረት ተመሳሳይ የፋብሪካ ዕቃ ያለአንዳች ልዩነት ለመገንባት መሞከር፣ ከውድቀት ውጭ ሌላ አዝመራ የማይታፈስበት ይሆናል። በኢትዮጵያ ሊገነባ የሚችለው ካፒታሊዝም፣ የአገሪቱን ታሪካዊና የተለየ ነባራዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ፣ በመሠረታዊ ባሕርዩ ከሌሎች ተመሳሳይ ሆኖ የራሱ የተለየ ገጽታ ያለው ካፒታሊዝም ሊሆን የሚችለውና የሚገባው በዚህ የተነሳ ነው።

የድኅነትን ፈተና በመቋቋም የፖሊሲ ነጻነትን ማስከበርና ልማትን የማፋጠን ጥያቄ፣

የገበያሥርዓት መሠረታዊ ባሕርይውን ሳይለቅ ብዙ መልኮች ይዞ የተገነባ ሥርዓት ቢሆንም፣ በገበያ አከራሪነት አስተሳሰብ የሚመሩ ሁሉ የገበያ ሥርዓትን ያለአንዳች ልዩነት በተመሳሳይ ይዘትና ገጽታ ለመገንባት ይሻሉ። ድህና ሀብታም፣ የለማና ያልለማ ገበያ ያላቸው፣ በትምሕርትና መሠረተ-ልማት ዕድገት ደረጃ የሰማይና ምድር ልዩነት ያላቸው አገሮች ሁሉ ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓትን በፍፁም መመሳሰል እንዲገነቡ ጥብቅ መመሪያ ይሰጣሉ። ሁሉንም የሚሳብ ጥያቄዎች በአንድ ቀመር መመለስ ይቻል ይመስል፣ ላደገውም ላላደገውም አገር ተመሳሳይ ቀመር መመሪያ ያስተላልፋሉ።

ኢህአዴግ በገበያ ሥርዓት አስተሳሰብ በመመራት አዲሲቱን ኢትዮጵያ ለመገንባት ሲነሳ ከሁሉ በፊት እነዚህን ጉዳዮች ታሳቢ አድርጓል። በተለይ ደግሞ ግንባሩ ወደሥልጣን የመጣው ኒዮ-ሊበራሊዝም በዓለማችን የበላይነት በተቀዳጀበት ጊዜ ስለነበር፣ የአዲሱ ሥርዓት ግንባታ አገራችንን ዘመኑ ካገነነው የገበያ አከራሪ አሉታዊ ተፅዕኖዎች የሚታደግ መሆን ነበረበት። በዚህ ወቅት ዓለም አቀፉ የገበያ አከራሪነት ኃይል ለካፒታልና ለባለሀብቱ ብቻ የተመቸ ሁኔታ ለመፍጠር የማይገለብጠው ድንጋይ አልነበረም።

ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ የሚገነባው የገበያ ሥርዓት ብዙኅኑን ለድኅነትና ጉስቁልና እየዳረገ፣ ጥቂቶችን ብቻ የሚያበለጽግ አለመሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነበር። ከምንም ነገር በላይ ደግሞ የህዝቡን ልማታዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አኳኋን የሚገነባ መሆን ነበረበት። አገራችን ሰፊ መሬትና ጉልበት ያላት በመሆኑ በምዕራቡ ዓለም ከሚታየው መጠነ ሰፊ የኃይል ምንጭ ተጠቃሚነትና ካፒታል ተኮር አቅጣጫ ይልቅ፣ በምሥራቅ እስያ ከታየው ጉልበትና መሬት ተኮር ልማት ጋር ይበልጥ ተመሳሳይነት ባለው አቅጣጫ መገንባት ነበረበት። በዚህ የተነሳ ለሰብዓዊ ኃይል ልማትና ተጠቃሚነት የላቀ አጽንኦት የሚሰጥ፣ በታዳሽ አረንጓዴ ልማት ላይ የተመሠረተ አቅጣጫ መከተል ተገቢ ነበር። ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት ይህን

ገና ከጠዋቱ በተሟላ ግንዛቤ ባይጀምረውም እንኳ መሠረታዊ አቅጣጫውን ተከትሎ በሂደት እያዳበረው ሊሔድና ሊገነባው ይገባ ነበር:: በኢህአዴግ መሪነት የተካሔደው የገበያ ሥርዓት ግንባታ ምን እንደሚመስል ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት አገራዊ የፖሊሲ ነጻነትን ለማስጠበቅ ከተካሔደው ትግልና ከተመዘገበው ውጤት በመጀመር መመልከት ይቻላል::

መላው ዓለም በጥብቅ የኢኮኖሚ ገመድ ተሳስሮ የእርስ በእርስ ተፅዕኖው ኃያል በሆነበት በዘመነ ግሎባላይዜሽን የአገሮች ሉዓላዊነት ተከብሯል ከሚባልባቸው መስፈርቶች የመጀመሪያውና ወሳኙ የፖሊሲ ነጻነትን ለማስከበር ከመቻልና ካለመቻል ጋር የተያየዘ ነው:: የኮሪያን ልማታዊ ዕድገት ከመሩት ሰዎች አንዱ የነበረው ኪም ቹንግ ዩም፣ አንድ አገር ከሌሎች አገሮች ጋር መገናኘቷና ከሌሎችም መማሯ እንደተጠበቀ ሆኖ የፖሊሲ ነጻነቷን በጥብቅ ማስከበር እንዳለባት ሲመክር :-

> "አንድ አገር ከሌሎች በንቃት መገናኘትና መማሯ ባይቀርም ቁልፉ ጉዳይ <u>የራሷን ዕድገት በባለቤትነት ለመምራት መቻሏና እያደገ በሚሔድ ደረጃ አቅሟን መገንባትና የሥጋት ምንጮችን ለመቆጣጠር መቻሏ</u> ነው:: ሁሌም ቢሆን የፈጠራና ቅንጅት በጐ ተፅዕኖዎችን እያጐለበተች በመንግሥት በኩል የሚታይ ሙስና የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ደግሞ በእጅጉ ለመቀነስ መቻል አለባት:: በተጨማሪም፣ የበጀት ዲሲፕሊንና ጥብቅ የመቆጣጠር አቅም ልታዳብር፣ ማንኛውንም የገበያ ነውጥ ለመቋቋም በሚያስችላት ደረጃ ዋጋን ከሁኔታ ጋር የማጣጣም ብቃት መገንባት አለባት:: ከሁሉ በላይ ደግሞ ለሰብዓዊ ልማት ትኩረት ልትሰጥ፣ የሕብረተሰቡን ውሕደት የሚያናጉና ዕድገትን የሚገድቡ ግጭቶችም ልታስወግድ ይገባታል::"[14] ይላል።

ልክ እንደኪም ቹንግ ሁሉ አሊስ አምስደንም (2007) በአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስጀመር በፖሊሲ ጉዳይ ላይ ለመወሰን የመቻል እውነተኛ ነጻነት መስፈኑ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ትገልጻለች:: ከእነዚህ ጥቅሶች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ አንድ አገር የራሷን ዕድገት በባለቤትነት መምራት የምትችለው ከምንም ነገር በላይ የፖሊሲ ነጻነት ሲኖራት ነው:: የፖሊሲ ነጻነት ሲባል መንግሥት የራሱን አገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ገምግሞ፣ መዳረሻ ግቡን ለይቶ ወደዚህ የሚያመሩትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንዲሁም የውጭ ግንኙነት አቅጣጫዎች በነጻነት ለመተለምና ለማስፈጸም የመቻል ብቃት ማለት ነው:: ይህን የመሰለው ነጻነት በሁሉም አገሮች በተሟላና በእኩል ደረጃ አይገኝም:: በተለይ ድሃና ኋላቀር አገሮች ለተመጽዋችነት የቀረቡ በመሆናቸው ምክንያት በተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በቀላሉ የማይጐናጸፉት ጸጋ ነው:: በቀጥተኛና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር የወደቁ አገሮች ከፖሊሲ

በቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ሥር የገቡ አገሮች ሁለመናቸው በባእድ መንግሥታት ቁጥጥር ውስጥ የገባ ነው። ህዝባቸውም ሆነ መሬታቸው በባዕዳን ተፅዕኖ ሥር የወደቀ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ የፖሊሲ ነጻነት ብሎ ነገር ፈጽሞ ሊታሰብ አይችልም። በመሆኑም እነዚህ ህዝቦችና አገሮች ቅኝ ገዥዎቹ የነገሯቸውን ከመፈጸም ውጭ ሌላ ዕድልም ሆነ መብት የላቸውም። በተመሳሳይ ሁኔታ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር የገቡ አገሮች ዕድልም ከሞላ ጎደል በባዕድ ኃይሎች እጅ ያለ ነው። እነዚህ አገሮች ለስሙ የሚያውለበልቡት ባንዴራ ያላቸው ቢሆንም በኢኮኖሚና በፖለቲካ ጉዳዮች ግን ጥገኛ ናቸው። ስለሆነም የራስን አገራዊ ፖሊሲ በነጻነት የመንደፍና የማስፈጸም ተጨባጭ ዕድልም ሆነ ችሎታ የላቸውም። ከቀጥተኛ ወይም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ባልተናነሰ ግሎባላይዜሽን ማደግ በተሳናቸው አገሮች ላይ የሚያሳድረው ጫናም ተመሳሳይ ውጤት ያለው ሆኗል።

ኒዮ-ሊበራሊዝም በገነነበት ዘመነ ግሎባላይዜሽን በጣም የተዳከመ ኢኮኖሚ ያላቸው አገሮች የተሟላ አገራዊ ነጻነት ሊጐናጸፉ የሚችሉበት ዕድል በጣም ጠቧል። በመጽዋችነት የሚሰለፉ አገሮች ሁሉ የተዳከመ ኢኮኖሚ ላለው ማንኛውም አገር እርዳታ ሲሰጡ ሲለመኑ "ነጻ ምሳ ብሎ ነገር የለም" በሚል መርህ ወይም እሳቤ ይመራሉ። ጥቂት የማይባሉ ለጋሽ አገሮች ከሰጡት እርዳታና ብድር በላይ ተረጅው መንግሥትና አገር በምላሹ አንድ አይነት ድርጉ እንዲሰጣቸው ያስገድዳሉ። እንዲያም ሲል በተመጽዋቹ አገር የውስጥ ጉዳይ ገብተው ይፈተፍታሉ። ለዚህም ያመቻቸው ዘንድ ሁሉም የፖሊሲ አጥሮች ተበረጋግደው እንዲከፈቱ ከፍተኛ ግፊት ያደርጋሉ። ይህን ሁኔታ በይበልጥ ለመገንዘብ መለስ (2003ዓ.ም.) ኒዮ-ሊበራሊዝም በአፍሪካ ላይ ስላደረሰው የፖሊሲ ጫናና ይህም ስላስከተለው መዘዝ ያቀረበውን ትንታኔ መመልከት ተገቢ ይሆናል። መለስ በ1970ዎቹ የተከሰቱት ሁለት የነዳጅ ቀውሶችና የእዳ ጫና አላላውስ ያላቸው የአፍሪካ አገሮች ተጨማሪ ብድር ጥየቃ በሔዱ ጊዜ ኒዮ-ሊበራሊዝም ያደረሰባቸውን የፖሊሲ ጫና :-

> "የአፍሪካ መንግሥታት ያደራጇዋቸው የልማት ድርጅቶች ሁሉ እንደ ስልክ፣ መብራት የመጠጥ ውሃ ያለ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ጭምር ቁልፍ የኪራይ ሰብሣቢነት ምንጭ ስለሆኑ በአፋጣኝ ወደግሉ ባለሀብት እንዲሸጋገሩ ይደረግ ብሎ ኒዮ-ሊበራሊዝም አወጀ። ...ቁልፍ የሆኑ ተቋሞች እጅግ ርካሽ በሆነ ዋጋ በውጭ ኩባንያዎች ተገዙ። ...ከውጭ ኩባንያዎች የተረፈውንም በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች በወዳጆቻቸው፣ በቤተሰቦቻቸው ወዘተ አማካኝነት በርካሽ ዋጋ ወሰዱት። በዚህ መልክ ሊሸጡ ያልቻሉት ደግሞ ተዘጉ። የፕራይቬታይዜሽን

እንቅስቃሴ በተግባር በብዙ አካባቢዎች የመንግሥት ንብረት ዝርፊያ ዘመቻ፣ በማቆጥቆጥ ላይ የነበሩት ኢንዱስትሪዎች መዝጊያና (De-Industrialization) የሥራ አጥነት መፈልፈያ ሆነ፡፡ አፈጻጸሙ ከባድ ጉዳት አስከትሎ ከፍተኛ ጫጫታ በማስነሳቱ ኒዮ-ሊበራሊዝም ፕራይቬታይዜሽኑ ባጭር ጊዜ ባፋጣኝ መጠናቀቅ አለበት የሚለውን አቋም በሂደት በማለዘብ ከ90ዎቹ ጀምሮ በተቻለ ፍጥነት መፈጸም አለበት ወደሚል አቋም ተሸጋገረ፡፡...ኒዮ-ሊበራሊዝም በዚህ ብቻ ሳይወሰን መሠረታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾችም (Indexes) በገበያ ዋጋ መወሰን አለባቸው የሚል አቋም ወሰደ፡፡ ከዚህ በመነሳት 'የወለድ ምጣኔ በባንኮች በነጻ ውድድር መወሰን አለበት፣ የመንግሥት ባንኮች መሸጥ አለባቸው፣ የአገር ውስጥና የውጭ ባንኮች በነጻ መወዳደር አለባቸው' የሚል አቋም ተወሰደ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ 'የአፍሪካ መገበያያ ገንዘቦች የውጭ ምንዛሪ ተመን በነጻ ገበያ መወሰን አለበት፣ የውጭ ምንዛሬ እንደማንኛውም ዕቃ በባንኮች ብቻ ሳይሆን በሱቆችም በነጻ መሸጥ መለወጥ' አለበት ተባለ፡፡ በተጨማሪም 'የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር ሲባል የመንግሥት ወጪና ገቢ እኩል መሆን አለበት፣ የበጀት ጉድለት መወገድ አለበት፣ ብሔራዊ ባንክም ሥራው የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠር ብቻ ሆኖ የወለድ ምጣኔውም ግሽበቱን ለመቆጣጠር በሚያስችል አኳኋን ከፍ ማለት አለበት ተባለ፡፡'[15] በማለት ለሁሉም ያለልዩነት የተሰጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ ያስረዳል፡፡

ኒዮ-ሊበራሊዝም ያስከተለው ይህን የመሰለው ምስቅልቅል በአፍሪካ ብቻ የታጠረ አልነበረም። በአውሮፓ አገሮችም ሳይቀር ከፍተኛ ጉዳትና ምስቅልቅል አስከትሏል፡፡ ከ2008ቱ የዓለም ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በኋላ ከፉኛ የተደቆሰችውን ግሪክ "ከእዳ ጫና ለማውጣት" በሚል ሽፋን የተካሔደው የሊበራላይዜሽን ዘመቻም የአበዳሪ አገሮችና ተቋማትን ሥር የሰደደ ሥግብግብ ፍላጐትና ተግባር በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ በእርግጥ የግሪክ ችግር ከማምረት አቅሙ በላይ በድጐማ የሚኖር ሕብረተሰብ ከመሆኗና በዋነኛነት ከመንግሥት ውደቀት (State Failure) የመነጨ ነው፡፡ መንግሥት በትክክለኛ አቅጣጫ በመራመድ ኃላፊነቱን መወጣት አለመቻሉ ግሪክን ወደቀውስ ያመራት ዋነኛው ምክንያት ነው፡፡ በብዙ ተመሳሳይ የአገራዊ ቀውስ አጋጣሚዎች እንደታየው የችግሩ ምንጭ የመንግሥት ውድቀት ቢሆንም "መፍትሔው" ከበሽታው የባሰ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ አገራቱ ለባሰ ቀውስ ይዳረጋሉ፡፡

ግሪክ በዓለም ገንዘብ ድርጅት አጋፋሪነት የተጋተችውን ኒዮ-ሊበራል የመፍትሔ ሀሳቦች ሁሉ አንሰቶ ለመመርመር ጊዜና ቦታው ባይፈቅድም፣ ኒዮ-ሊበራሊዝም ያቀረበላት የመፍትሔ

ሃሣብረ-ሀሳብሦተ "ፈሡቡ" ከዘበታው ዮነበ መርዝ አንደሆነሦተ ያሳያሉ፡፡ በዓለም የገንዘብ ድርድሮችና በአውሮፓ ባንክ አጋፋሪነት ግሪክ ላይ የተጫነውና አገሮች በተቃወሱ ጊዜ ሁሉ ቀበቶን በማጥበቅ ሽፋን በመፍትሔነት የሚቀርበው "አጠራቃቂ የኢኮኖሚ እርምጃ" (Austerity) የመጀመሪያው የተሳሳተ መፍትሔ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎም አበዳሪዎቹና የኒዮ-ሊበራል መገናኛ ብዙኀኖች ግሪክ እዳዋን ለመክፈል ባለመቻሏ ጥብቅ እርምጃ ሊወሰድባት ይገባል አሉ። አዲስ ብድር ለማግኘትም ከባድ ዋጋ መክፈል ይገባታል አሉ። የቀኝ ዘመም ባሕርይ ያለው "የከሪስቲያን ሳይንስ ሞኒተር" ጋዜጣ፣ ሁለት የጀርመን የፓርላማ አባላት የተናገሩትን በመጥቀስ ለአበዳሪዎች የሰጠው ምክረ-ሀሳብ ኒዮ-ሊበራሊዝም የፖሊሲ በቻ ሳይሆን አገራዊ ነጻነትን በመጋፋትም የት ድረስ ሊሔድ እንደሚችል የሚያመላክት ነው፡፡

ይህ ጋዜጣ በኤፕሪል 2010 እትሙ "ግሪክ እዳዋን ለመክፈል መሸጥ ያለባት አሥር ትልልቅ ነገሮች" (The top 10 things Greece can sell to pay off its debt)[16] በሚል ርዕስ ባተመው ጽሁፍ ይህን በግልጽ አመላክቶ ነበር፡፡ ጋዜጣውና የጀርመን ፓርላማ አባላት ለሽያጭ ይቅረቡ ያሏቸው አሥር ነገሮች ዋነኞቹ የግሪክ ጥንታዊና ታሪካዊ መመኪያ ቅርሶች ናቸው፡፡ በጋዜጣው ምክረ-ሀሳብ መሠረት በዓመት 2.5 ሚሊዮን የጀርመን ቱሪስቶች የሚጐበኙትን የማይኮኖስ ደሴት ጨምሮ ታላቁ የፓርቴኖን ጥንታዊ ህንጻ፣ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የተገነባው ጥንታዊው የኢፒዳረስ አምፊ ቲያትር፣ ጥንታዊው የአቴና ዴልፊ የእምነ በረድ ሐውልት፣ በዓለም የመጀመሪያው የረዥም ርቀት ሩጫ የተከናወነበት የኦሎምፒያ አደባባይ፣ ጥንታዊቷ የኮርፉ ከተማ፣ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበውና ብዙ ታሪካዊ ቅርሶች የሰፈሩበት የአቶስ ተራራ ለሽያጭ ይቅረቡ ተብሏል፡፡ የግሪክ ኩራት የሆነው ጥንታዊውና ዝነኛው አክሮፖሊስም አልቀረለትም፡፡ በገበያ አክራሪነት አስተሳሰብ ለገበያ የማትቀርብ የተቀደሰች ላም የለችምና እርሱም ለጨረታ ይቅረብ ተብሏል፡፡ ይህ የኒዮ-ሊበራሉ ዓለም ሥግብግብነት በሼክስፔር ድርሳነ ተውኔት በገጸ ባሕርይነት ከተሳለው "ከቬኒሱ ነጋዴ" የማይተናነስ ነው፡፡ አራጣ አበዳሪውና ባለሉካንዳ ቤቱ ሻይሎክ ቢላውን እያፋጨ አስቀድመው በገቡት ውለታ መሠረት ብድራቸውን በጊዜ ከማይመልሱ ሰዎች ገላ ላይ ሙዳ ሥጋ ቆርጦ ለመውሰድ እንደሚዝተው ሁሉ፣ ዓለም አቀፍ አበዳሪ ተቋማትም በዚህ ምክረ-ሀሳባቸው ከግሪክ ላይ ደሴቶቿን ቆርጠው ለመውሰድ መዘጋጀታቸውን በግላጭ አሳይተዋል፡፡

እነዚህ ታሪካዊ ቅርሶች ለግሪክ ምን ማለት እንደሆኑ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በጥብቅ የምንገነዘበው ነው፡፡ ታላቁ የአክሱም ሐውልት በጣሊያን ወራሪዎች ተዘርፎ በሮም አደባባይ በተተከለባቸው 65 ዓመታት ኢትዮጵያውያን በምን ያህል ከባድ ሐዘን ውስጥ እንዳለፍን ሐውልቱን ለማስመለስ መላው ህዝብ ካካሔደው ከባድ ትግልና ከተከፈለው መስዋዕትነት በመነሳት ለመገመት አያስቸግርም፡፡ በመካከለኛው ምሥራቅና በትንሿ እስያ የሚገኙ አክራሪና

ጽንፈኛ ኃይሎች ከሰው ልጆች ቀዳሚ ሥልጣኔዎች መካከል የሜሶፖታሚያ ዘመን ቅርሶችንና ታላላቅ የቡድሐ ሐውልቶችን በማፈራረስ የሚያካሂዱት ዘግናኝ ውድመትም ኢራቅና ሶርያን የመሳሰሉ ጥንታዊ የሥልጣኔ አገሮች ምን ያህል እንዳሚያንገበግባቸው የሚታወቅ ነው። ናአሚ ክሌን (2007) እንደገለጽችው፣ አሜሪካ መራሹ ጦር የባግዳድን ሙዝየም ዘርፎና አዘርፎ የአውሮፕላኖችን ወንበር እየነቃቀለ እስከመጫን መድረሱ የፈጠረው እልህና ቁጭትም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። የግሪክን ታሪካዊ ቅርሶች በወለድ አገድ ይዞ ለመዝረፍ የተዘጋጀው ኒዮ-ሊበራል ኃይል ለጨረታ ይቅረቡ ባላቸው የግሪክ መመኪያዎች ላይ ማነጣጠሩ በርግጥም ስግብግብነቱ ዲካ እንደሌለው የሚያሳይ ነው። ከዚህ በመነሳት፣ የዓለማችን ታዋቂ ኢኮኖሚስቶች ሳይቀሩ ኒዮ-ሊበራሊዝም መፍትሔ እንዳልሆነ በአጽንኦት እየገለፁ ይገኛሉ። ከዘመናችን ታላላቅና የኖቤል ተሸላሚ ከሆኑት ኢኮኖሚስቶች መካከል ጆሴፍ ስቲግሊዝ፡-

> "ከአምስት ዓመታት በፊት ትሮይካዎች (የአውሮፓ ኮሚሽን፣ የአውሮፓ ሴንትራል ባንክና ዓለምአቀፉ የገንዘብ ድርጅት) ግሪክን ከጋቱት ፕሮግራም ጀርባ ያለው የኢኮኖሚ እሳቤ የግሪክን አጠቃላይ አገራዊ ምርት(GDP) በ25% እንዲያሽቆለቁል ያደረገ ነበር። በበኩሌ ይህን ያህል ዘግናኝ ውጤት ያስከተለና ታስቦበት የተፈጠረ የኢኮኖሚ ውድቀት አለ ብዬ ለማሰብ እቸገራለሁ። ግሪክ ያላት የወጣት ሥራ አጥነት ከ60% በላይ ሆኗል። ስለጉዳዩ በጣም ግልጽ ልንሆን ይገባናል። ለግሪክ የተሰጠው ከፍተኛ ብድር ከሞላ ጎደል ሁሉም ወደአገሪቱ አልገባም። ገንዘቡ የተላለፈው የፈረንሳይና ጀርመን ባንኮችን ጨምሮ ለግል አበዳሪዎች ነው። ለግሪክ የደረሳት ትንሽ ቅንጥብጣቢ ገንዘብ ቢሆንም፣ የእነዚህን አገሮች የባንኮች ሥርዓት ለማስቀጠል ሲባል ከባድ ዋጋ እንድትከፍል ተደርጓል። አይ ኤም ኤፍና ሌሎች "ይፋ" አበዳሪዎች ከግሪክ የሚጠየቀውን ይህን ገንዘብ ስለማይፈልጉት መልሰው ለዚችው አገር ማበደራቸው አይቀርም። እናም ግሪክ በሪፍረንደሙ አሻፈረኝ የሚል ድምጽ ብትሰጥ በነበራት ዴሞክራሲያዊ ባሕል በመታገዝ ዕድሏን በእጇ አስገብታ አሁን ከሚደርስባት በደልና ስቃይም በተገላገለች።"[17] ብሎ ነበር።

በግሪክም ጭምር እንደታየው በጠንካራ አገራዊ ኢኮኖሚ ላይ ያልተገነባ ነጻነት አገራዊ ታሪካዊ ቅርሶችና ደሴቶችን ሳይቀር ለሽያጭ የማቅረብ አደጋ ጭምር እንደሚጋብዝ ያሳያል። ይህ በራሱ በአይ ኤም ኤፍ ጭምር የተረጋገጠ ነው። የግሪክን አንጡራ ቅርሶች ለማሻሻጥ አመቺ ሁኔታ የፈጠረውን "አጠራቃቂ የኢኮኖሚ እርምጃ" በግንባር ቀደምትነት ያራመደው የዓለም

ገንዘብ ድርጅት የራሱን ኒዮ-ሊበራል ምክረ-ሀሳብ በማስመልከት ያቀረበው አዲስ ግምገማ ይህን ያሳያል። የዓለም ገንዘብ ድርጅት "የፋይናንስ ዴቨሎፕመንት" በሚል ርዕስ በሚያዘጋጀው የጁን 2016 እትም መጽሔቱ፣ "ከልክ በላይ የተሸጠው ኒዮ-ሊበራሊዝም?" (Neoliberalism: Oversold?) በሚል ርዕስ ባቀረበው ጽሁፍ፣ ስለኒዮ-ሊበራሊዝም ጥቅሞች ከዘረዘረ በኋላ፡-

> "ይሁን እንጂ ኒዮ-ሊበራሊዝም የታሰበውን ያህል ውጤት ያላስገኙ ገጽታዎችም አሉት። በዚህ ጉዳይ ላይ ያካሔድነው ግምገማ ፖሊሲው ባስከተላቸው ሁለት ውጤቶች ላይ ብቻ የታጠረ ነው። የመጀመሪያው ነጻ የካፒታል ዝውውር (Capital Account Liberalization) ወይም ካፒታል በአገሮች መካከል ድንበር ሳይገድበው ለመንቀሳቀስ እንዳይችል የሚያደርጉ ገደቦች እንዲነሱ የሚያደርገው ፖሊሲ ውጤት ግምገማ ነው። ሁለተኛው "አጠራቃቂ የኢኮኖሚ እርምጃ" ተብሎ በሚጠራው የበጀት አጣብቂኝ ላይ ያተኮረ ግምገማ ሲሆን፣ ይህም የመንግሥት የበጀት ጉድለትንና የእዳ መጠንን ለመቀነስ ባለመው ፖሊሲ አፈጻጸምና ውጤት ላይ ያተኮረ ነው። የእነዚህ ልዩ [ኒዮ-ሊበራል] ፖሊሲዎች አፈጻጸምና ውጤት ግምገማ የሚያሳፍር ድምዳሜዎች ላይ የሚያደርስ ሆኗል። በዚህ መሠረት ፖሊሲው የዕድገት ጭማሪ ያስገኛል የተባለውን መነሻ በማድረግ በተካሔደ ግምገማ በርካታ አገሮች በተጨባጭ የዕድገት ተቋዳሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አልተቻለም። በተጨማሪም ከፖሊሲው ትግበራ በኋላ በእነዚህ አገሮች የሀብት ልዩነት መጥበቡ ቀርቶ ሰፍቷል። በዚህም ምክንያት ከባድ ዋጋ ሊከፍሉ ተገደዋል። የሀብትና ተጠቃሚነት ልዩነት መስፋት ደግሞ እንደገና ተመልሶ ዕድገትን የማዳከም ውጤት አስከትሏል።"[18] በማለት ገልጸታል።

የፖሊሲ ጫና ዋና ምንጭ ስለሆኑት ተቋማትና ከእነርሱም ጋር ስለሚካሔደው ድርድር መያዝ ያለበት ግንዛቤ ግን ከዚህም ልቆ የሚሔድና "የዋሽንግተን መግባባት" (The Washington Concensus) በመባል ስለሚጠራው ተፅዕኖ አድራጊ ኃይል መያዝ ያለበትን ግንዛቤ የሚጨምር ሊሆን ይገባዋል። ዳንኤል የርጊንና ጆሴፍ ስታኒስላቭ (2008) ስለ "ዋሽንግተን መግባባት"

> "ስያሜው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የፖሊሲ ውሳኔ የሚያሳልፈው ማን እንደሆነ የሚያመላክት ነው። ይህም [ሉዓላዊ] መንግሥታት ሳይሆኑ ዋሽንግተን የፖሊሲ ምንጭ ከመሆኗ ጋር የተያያዘ ነው። ዋሽንግተን የዓለም ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ብቻ ሳይሆኑ እነዚህን ባልተሸፋፈነ መንገድ የሚመራቸውን የአሜሪካን መንግሥት ያቀፈች ከተማ ነች። ከዚህ መንግሥት

ጀርባ ደግሞ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ሊቃውንትና የምዕራቡ ዓለም የቢዝነስ ተቋማትና ጥቅሞቻቸው ይገኛሉ።"[19] ይላሉ።

"የዋሽንግተን መግባባት" አንድ አካል የሆነው የዓለም ገንዘብ ድርጅት በከባድ ግፊትና ጫና ተግባራዊ ስላደረጋቸው ኒዮ-ሊበራል ፖሊሲዎች አሉታዊ ውጤት በተቋሙ ባልተለመደ ግልጽነት ይህን ማለቱ ከመሸና እጅግ የሚዘገንን ጥፋት ካደረሰ በኋላ ቢሆንም እንደኢትዮጵያ ላሉ አገሮች ታላቅ ድል ነው። ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በሁለታችን መካከል አገራዊ የፖሊሲ ነጻነታችንን ለማስከበርና ለመንጠቅ በሁለቱ ወገኖች መካከል ከባድ ፍልሚያ ተካሂዷል። በዚህ ሂደትም በሌሎች አገሮችና መንግሥታት ላይ የፖሊሲ ተፅዕኖ ማድረግ የለመዱና የሚሹ መንግሥታትና ተቋማት እነርሱን ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን ፖሊሲ በአገራቱ ላይ ለመጫን ያልተቋረጠ ጥረት አድርገዋል። ሥር የሰደደውን የአገራችን ድኅነት መጠኗን አድርገው ተፅዕኖ በማብዛት የፖሊሲ ነጻነታችንን ለማጥበብ ከባድ ጫና አድርሰዋል።

ከዚህ በግልባጩ የአገራችን መንግሥት ደግሞ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን ፖሊሲ የመንደፍና የማስፈጸም ጉዳይ፣ በህዝብ የተመረጠው መንግሥትና የአገሬው ህዝብ ኃላፊነት ብቻ ነው ብሎ በማመን፣ ይሕንኑ ለማስጠበቅና በተግባር ላይ ለማዋል ጥረት አድርጓል። አገራችን በምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ጥንካሬና ደረጃ ላይ ትሁን፣ የፖሊሲ ነጻነቷን ላለማሰደፈር ከባድ የመከላከል ትግል ተካሂዷል። በአንድ በኩል በዓለም ገንዘብ ድርጅትና በዓለም ባንክ ፊታውራሪነት በሚመራው ኒዮ-ሊበራሊዝም፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአገራችን መንግሥት መካከል የተካሔደው ትግል፣ ሁለቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ከሁለት አሥርት ዓመታት ላለነሰ ጊዜ በከባድ ሁኔታ የተፋለሙበት ነበር።

ከ1980ዎቹ በኋላ የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮት ማዕከላት በሆኑት በእነዚህ ግዙፍና ኃያል ተቋማት ፊታውራሪነት የተካሔደው ዘመቻ ከባድና አስቸጋሪ ነበር። ይህም ሆኖ፣ መንግሥት በመርሕ ላይ ቆሞ የቻለውን ያህል በመፋለም የእስካሁኑን ግፊት ተቋቁሞ አልፏል። የተሳሳተ የሊበራላይዜሽንና የፕራይቬታይዜሽን መመሪያ ሰጥሞው አንዳንድ ጊዜ "ለኢትዮጵያ የማይበጅ ፖሊሲ በመቃበራችን ላይ ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም" እያለ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በልዩ ልዩ ስልቶች በመታገዝ ጊዜ እየገዛ ተከላክሏል። በዚህ ረገድ የተካሔዱትን ትግሎች በአብነት አስደግፎ ማቅረብ ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል።

መንግሥት የኢትዮጵያን አገራዊ የፖሊሲ ነጻነት ከማስጠበቅ አኳያ ያደረገው ጥረትና ትግል አሐዱ ብሎ የተጀመረው በ1984 ዓ.ም. ነበር። ይህም "የመዋቅራዊ ማስተካከያ ለውጥ" (Structural Adjustment Programme, SAP) በመባል በሚታወቀውና በዓለም ባንክና በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት በሚራመደው ፕሮግራም ዙሪያ የተካሔደ ትግል ነው።

ኒዮ-ሊበራላዊው የመዋቅራዊ ማስተካከያ ለውጥ ከ1980ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት አንስቶ የብዙ ያልበለጸጉ አገሮችን በር ብርግድግድ አድርጎ ያስከፈተው የሊበራላይዜሽን የመነሻ ነጥብ ነበር። ይህ ማዕቀፍ በአንድ በኩል "መንግሥት የችግሮች ሁሉ ምንጭ ነው"፣ በሌላ በኩል ደግሞ "ሁሉም የኢኮኖሚ ችግሮች በገበያውና በባለሀብቱ ሊፈቱ ይችላሉ"፣ በሚል የተሳሳተ አመከንዮ በዋነኛነትና በቅድሚያ መንግሥት ከኢኮኖሚው ላይ እጁን እንዲያነሳ ያስገድዳል። በመንግሥት እጅ የሚገኙ የማምረቻ መሣሪያዎችን በሙሉ በጥድፊያና በአስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎች ወደግል እንዲዛወሩ ያደርጋል። መንግሥት የሰበሰበውን የሰው ኃይል በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ ወይም እንዲያራግፍ፣ ምርቶችና አገልግሎቶች ቁጥጥር በማይደረግበት የገበያ መሣሪያነት እንዲለዋወጡ ያስገድዳል። ኢኮኖሚው ሙሉ ለሙሉ ሊበራላይዝ እንዲደረግ፣ የማክሮ ኢኮኖሚ መለኪያዎች የሆኑት የውጭ ምንዛሬ ተመንና የወለድ ምጣኔ በገበያ እንዲወሰኑ በማድረግ፣ ዶላር በየሱቁ እንዲቸረቸርና መንግሥታት ተበድረውና ተለቅተው ያመጡትን ይህን ውድ ጸጋ በከንቱ እንዲያባክኑም መንገድ ያመላክታል። እነዚህ ያነሱ ይመስል፣ የ"መዋቅራዊ ማስተካከያ" ፕሮግራም የሊበራላይዜሽን፣ የዲሬጉሌሽንና የፕራይቬታይዜሽን ምክረ-ሐሳቦቹ ቅጽበታዊ በሚባል ፍጥነት ተግባራዊ እንዲደረጉ አስገዳጅነት ነበረው።

አንዳንዴ በተቋቋሙበት ቦታ ሥም የ"ብሪተንውድስ ተቋማት" በሚል ስያሜ የሚታወቁት የዓለም ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ያመጧቸው ሀሳቦች፣ በመሠረታዊ ይዘታቸው ኢህአዴግ ከነደፈው የሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር የተሰዩና የሚጋጩ ነበሩ። እነርሱ "የመንግሥት መጠናከር የኢኮኖሚ ልማትን ያዳክማል" ሲሉ፣ ኢህአዴግ "ጠንካራ መንግሥት ለልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም በማንም የማይተካ ተፈላጊነት አለው" የሚል አስተሳሰብ ነበረው። አሁንም አለው። ስለዚህም መንግሥትን የሚያዳክሙ ምክረ- ሀሳቦችን ገና ከጥዋቱ እንደማይቀበል አስታወቀ። በመንግሥት እጅ ያሉ ተቋማት ሁሉ በትከከል ስለማይመሩ በአፋጣኝ ወደግል ይዞታ መዛወር አለባቸው የሚለውን መመሪያም አልተቀበለውም። አትራፊ ያልሆኑ የመንግሥት ተቋማት ውድድርን እስካልከለከሉ ድረስ ወደግል መዛወራቸው ተገቢ ቢሆንም፣ ለኢኮኖሚያዊ ልማቱ ቁልፍ ተፈላጊነት ያላቸውና የሞኖፖል ባሕርይ ያላቸው ተቋማት ግን ወደግል ይዞታ መዛወራቸው ጉጂ ስለሆነ በሂደት ካልሆነ በስተቀር በፍጥነት መዛወር የለባቸውም የሚል አቋሙን ገፋበት። ተቋማቱ የውጭ ምንዛሪ ተመንና የወለድ ምጣኔ በገበያ መወሰን አለባቸው ቢሉም፣ የአገራችን መንግሥት ግን "እነዚህ የኢኮኖሚ ልማት ማሳለጫ መሣሪያዎች በገበያ ይወሰኑ ከተባለ ኢኮኖሚው ለአየር በአየር ነጋዴዎች እንጂ ለአምራቾች የተመቸ አይሆንም" የሚል አቋም በመያዝ ኢኮኖሚው በውድድር ላይ የተመሠረተ ሆኖ እስኪገነባ ድረስ በዋነኛነት በመንግሥት አደረገ። ኢህአዴግ ከዚህ በተጨማሪ በአጠቃላይ ሂደቱ የራሱን ጊዜ ወስዶ እንጂ በጥድፊያ ሊፈጸም አይገባም ይል ነበር።

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የደርግ መንግሥት ሲወገድ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እጅግ ከፍተኛ ውድቀት ላይ ደርሶ ነበር። በተዳከመው የአርሶ አደሩ የማምረት አቅምና ፍላጐት ላይ ዋናው አምራች የሆነው ወጣት አንድም በጦርነቱ በመጠመዱ ወይም ከጦርነቱ ለማምለጥ በሥጋት እየተበራገገ ባለመረጋጋቱ የግብርና ምርታማነት ከፍተኛ ውድቀት አጋጥሞታል። የአገሪቱ ኢንዱስትሪም በጥሬ ዕቃና ከዶላር እጥረት ጋር ተያይዞ በተከሰተ የመለዋወጫ አቅርቦት ችግር ከነበረው አቅም ከሃያ በመቶ ያነሰውን ብቻ ይጠቀም ነበር። በወቅቱ በመንግሥት ካዝና ውስጥ የነበረችውን ጥቂት ዶላር ብቻ ይዞ ኢኮኖሚውን በራስ አገራዊ አቅም በመተማመን ብቻ ማስጀመርም ሆነ ማስቀጠል ለአዲሱ መንግሥት ከባድ ፈተና ነበር። በዚህ የተነሳ አዲሱ መንግሥት፣ ገና ከሽግግሩ ወቅት ጀምሮ እርዳታና ብድር በማፈላለግ ይህንኑ ለአገራዊ ልማት ለማዋልና ኢኮኖሚው እንደገና እንዲያንሰራራ ለማድረግ ተገደደ። ተፈላጊው በአጠቃላይ ለልማት የሚፈለገው ፋይናንስም ሆነ የውጭ ምንዛሬ የሚገኘው በዋነኛነት ከዓለም ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክን ከመሳሰሉ አበዳሪ ተቋማት በመሆኑ ኢኮኖሚውን ለማነቃነቅ ሲል ከተቋማቱና የፓሪስ ክለብ በመባል ከሚታወቁት አበዳሪ አገሮች ጋር ወደመደራደር አመራ።

ድርድሩ የሚካሔደው ከደቀ መዛሙርት ጋር ሳይሆን የብዙ አገሮችን የፖሊሲ አጥር በረጋገደው የማስከፈት የዳበረ ልምድ ካላቸው የርዕዮቱ ባለቤት ተቋማት ጋር በመሆኑ የአገራችን መንግሥት ወደዚህ ከባድ ፍልሚያ ሲገባ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሆን ነበረበት። መንግሥት ገና ወደ ድርድር ከመግባቱ አስቀድሞ በአንድ በኩል ከእነዚህ ተቋማት በኩል የለየለት የገበያ አክራሪ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብ እንደሚመጣ ተገንዝቧል። በሌላ በኩል ደግሞ ለድርድር ከመቅረብና በዚህም ሂደት አገራዊ ጥቅማችንን ከማስከበር ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለውም አውቋል። የፖሊሲ ተፅዕኖን በመፍራት ብቻ ከእነዚህ ተቋማት ጋር ድርድርን መሸሽ ተንገራግጮ የቆመውን ኢኮኖሚ ለማስነሳት የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ምንጭ የማያስከፍት ነበር። በድኅነትና በባዶ እጅ ለድርድር መቅረብ ደግሞ ራስን ለከባድ የፖሊሲ ተፅዕኖ ማጋለጥ ነበር።

አዲሱ መንግሥት ገና በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የገባበት ይህን የመሰለው አጣብቂኝ፣ ፈረንጆች ራስን "በዲያቢሎስና በጥልቁ ሰማያዊ ባሕር መካከል ማግኘት" የሚሉት ዓይነት ነበር። ይህም ሆኖ ኢህአዴግ የሀሳብ መሪነት ሚና የተጫወተበት የሽግግር መንግሥት በድርድሩ ውስጥ በመሳተፍ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች ማስከበርን መረጠ። የኢትዮጵያን መሠረታዊ ብሔራዊ ጥቅሞች ማዕከል በማድረግና መርሕን ተከትሎ በመደራደር በ"ዲያቢሎስና" በጥልቁ ሰማያዊ ባሕር መካከል መቀመጥ ብቸኛው አማራጭ እንዳልሆነ፣ ይልቁንም ሌሎች ጠቃሚ መንገዶች እንዳሉ በተግባር ለማሳየት ቆርጦ ተነሳ። በብቁ ዝግጅት ለድርድር እየቀረበ የተደቀነበትን አጣብቂኝ ለማለፍም ጥረት አደረገ።

የኒዮ-ሊበራል ፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦችን በጽናት መቋቋም የሚቻለው ከሁሉ በፊት ድርድሩ በራሳችን አገርበቀል ፕሮግራም ላይ እንጅ በአበዳሪዎች ቅድመ ሁኔታ ላይ የማይመሠረት ሲሆን ነው። በመሆኑም፣ መንግሥት ወደድርድሩ ከመግባቱ በፊት አገራዊ ፖሊሲዎቹን በዝርዝር አዘጋጅቶ መጨረስ ነበረበት። በዚህ መሠረት በወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበረው በአቶ ታምራት ላይኔ ስም ታትሞ የወጣው የሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ በሽግግሩ የተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ ተደረገ። ሰነዱ ከፀደቀ በኋላ ከተቋማቱና ከፓሪስ ክለብ አገሮች ጋር የሚካሔደው ድርድር በዚህ የፖሊሲ ማዕቀፍ የሚገዛ እንዲሆን አደረገ። ከዚህ ፕሮግራም ጋር የሚጣጣሙ ምክረ-ሀሳቦች ሁሉ ከየትም ይምጡ ከየት የሥምምነት አቋሞች እንዲሆኑ፣ በአንጻሩ ከሽግግሩ ወቅት ፖሊሲ ጋር የማይጣጣሙት ደግሞ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ተደረገ። መንግሥት አስቀድሞ የፖሊሲ ነጻነቱን አስከብሮ ወደድርድሩ ሜዳ መግባት ጀመረ። አብዛኞቹ ያልበለጸጉ አገሮች መንግሥታት ወደድርድሩ ገበታ የሚገቡት የራሳቸውን አገርበቀል ፕሮግራም ሳያዘጋጁ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ራሱ ባዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ተመሥርቶ ተደራደረ። ከግዙፎቹ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በእነርሱ ሕግ ሳይሆን በራሱ ሕግ፣ በእነርሱ ፕሮግራም ሳይሆን በራሱ ፕሮግራም እየተመራ ተደራደረ። ተደራድሮም ተሳካለት። እነሆ የአዲሱ መንግሥት የፖሊሲ ነጻነት የኢትዮጵያ ትንሳኤ መሠረት ሊሆንም በቃ።

በመዋቅራዊ ማስተካከያ ፕሮግራም ዙሪያ በአገራቸን መንግሥትና በገንዘብ ተቋማቱ መካከል የተካሔደው ድርድር እነዚህን የመሳሰሉ ጉላ ያሉ የልዩነት ሀሳቦች በመያዝ የተጀመረና በሂደት ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ አጀንዳዎች እየታከሉበት የተካሔደ ነው። በእነርሱ በኩል በመንግሥት እጅ ያሉ ትልልቅ ተቋማትን በተለይ ባንኮችን፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና ቴሌኮምን በፍጥነት ወደግል የማዛወር ሀሳብ እንደማለዳ ጸሎት ተዘውትረው ይቀርቡ ነበር። መሬት በገበያ የሚሸጥ የሚለወጥ ሸቀጥ እንዲሆንና የውጭ ኩባንያዎችና መንግሥታት ገደብ በሌለው ሁኔታ በአገራችን እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችሉ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦችም እንደዚሁ የማይቀሩ አጀንዳዎች ሆኑ። መንግሥት በበኩሉ ከመሠረታዊ አገራዊ ጥቅማችን በመነሳት ጐጂ ናቸው ያላቸውን የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንደማይቀበል እየገለጸና በአቋሙ ጸንቶ እየተከራከረ ተጓዘ። ከዚህም አልፎ በምድረ-ኢትዮጵያ ተግባራዊ የሚሆኑት በኢትዮጵያውያን መብቶችና ጥቅሞች ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንጅ ክፍላተ-ኃገራችን ውጭ የሚጫኑብን የሌላ ወገን አስተሳሰቦች እንደማይሆኑ በተግባር ለማሳየት ተንቀሳቀሰ። ቡሀላይ ደግሞ ኢኮኖሚውን በልማታዊ አቅጣጫ ለመምራት የሚያስችሉና በተለምዶ የኢኮኖሚ ማዘዣ ከፍታዎች (Commanding Heights) የሚባሉት ዘርፎች ወደግል ይዞታ እንደማይዛወሩ አረጋገጠ።

ይህን የመንግሥት ቁርጠኝነት የተመለከቱት ተቋማት ሁሉም ነገር እንዳሰቡት ሊሔድላቸው አለመቻሉን ሲገንዘቡ አንዳንዱን ጥያቄ ለየት ባለና በተዘዋዋሪ መንገድ ማቅረብ ጀመሩ። አንዱ ሥልት ሲከሽፍ ሌላውን እየቀየሩ እስከመጨረሻው ዕድላቸውን መሞከርን ተያያዙት። ለምሣሌ የንግድ ባንክ ወደግል እንዲዛወር በተቋማቱ የቀረበው ምክረ-ሀሳብ ተቀባይነት ሲያጣ፣ በባንኮች መካከል ውድድር እንዲኖር ለማድረግ በሚል ሽፋን፣ "ንግድ ባንክ ወደአራት ትንንሽ ባንኮች ቢከፋፈል ይሻላል" የሚል ሀሳብ አቅርበው እንደነበር በአንድ ወቅት ለኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተገልጾ ነበር። ይህ ሀሳብ ላይ ላዩን ሲታይ መልካም ቢመስልም፣ መንግሥት የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ይሆነኛል ብሎ የሚተማመንበትን ባንክ የሚያዳክምና ከእጁ እንዲወጣ የሚያደርግ ነበር። መንግሥት ባንኩን እንደያዘ ቢቆይ የወጪ ንግድን ለማሳደግና የገቢ ምርቶችን የሚተኩ (Import Substitution) ፋብሪካዎችን ለማስፋፋት እንደሚችል ያምን ነበር። በተጨማሪም በአነስተኛ ንግድና ዘመናዊ ግብርና ለሚሰማሩ ወገኖች የሚያስፈልገውን ብድር በአነስተኛ ወለድ ማቅረብ ይችል ነበር። ይሕ ካልሆነ በስተቀር የአገሪቱ ኢንዱስትሪያዊ ልማት ፈቅ እንደማይል ያመነው መንግሥት፣ ንግድ ባንክን ወደአራት የመበታተንን ሀሳብ እንደማይቀበል አረጋገጠ። "መሬት የሚሸጥ የሚለወጠው በኢህአዴግ መቃብር ላይ ነው" ብሎ እንደጸናው ሁሉ፣ በውድድር ሽፋን ይሁን በሌላ ምክንያት ንግድ ባንክን በማስመልከት የመጣውን ሀሳብም ፈጽሞ የማይሞከር ነው ብሎ ጸና።

የውጭ ካፒታል አገሪቱን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠር ዘንድ "ሁሉም ነገር ተበረጋግዶ ይከፈት፣ የውጭ ባለሀብቶች ያለአንዳች ቁጥጥር በሁሉም መስኮች ይሳተፉ" የሚለው ከሞላ ጎደል አስገዳጅ ሊባል የሚችል ምክረ-ሀሳብም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። ባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት፣ ግዙፍ የኤሌክትሪክ ማመንጫዎች፣ በተለይ ደግሞ የኃይል ማከፋፈያ መሥመሮች፣ የቴሌኮም አገልግሎት፣ የጅምላና ችርቻሮ ንግድ፣ እንዲሁም ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተከፈቱ እንደሚሆኑ በጥብቅ ተሰመረበት። የመንግሥት የተመረጠ ጣልቃ ገብነት ተግባራዊ የሚደረግባቸው ሌሎች መስኮች ደግሞ ለልማት መፋጠንና የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ባላቸው ፋይዳ እየታዩ ተወሰኑ። ተቋማትን ወደግል የማዛወሩ ሂደትም በጥድፊያ ሳይሆን የራሱን ጊዜ ወስዶና የህዝብን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አኳኋን እንዲፈጸም ተደረገ።

ድርድሩ በእነርሱ በኩል የሚሰጡን ብድርና እርዳታ፣ እንዲሁም አገራችን የሚሰረዝላት እዳ መጠን ስለ ውስጥ እየገባ፣ በመንግሥት በኩል ደግሞ አገራዊ ጥቅማችንን በማስጠበቅ መርሕ የተቀረፁትን አገር-በቀል ፖሊሲዎች የምናስፈጽምበት ነጻነት ቅድሚያ እየተሰጣቸው ቀጠለ። ይህም ሆኖ ግን መንግሥት ከእነዚህ ተቋማት ጋር ያሉትም ጉዳዮች ልዩነት ነበረው ማለት አይደለም። መሠረታዊ አቅጣጫቸው የተለያየ መሆኑ እንደተጠበቀ የሚስማሙባቸው

መለስተኛ ጉዳዮችም ነበሩ። ለምሣሌ፣ ከተቋማቱ በኩል የተረጋጋ የግከሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ስለመፍጠር፣ የዋጋ ግሽበትን ስለመቆጣጠር፣ መንግሥት ከባንክ የሚበደረውን ገንዘብ በዝቅተኛ ደረጃ ስለመገደብ የቀረቡትን ሀሳቦች ሁሉ ከልብ ተቀብሎ ተግባራዊ አድርጓል። ስለሆነም ባለፉት በርካታ ዓመታት ፈጣን ዕድገት በማስመዘገብ ለመዝለቅ የተቻለው በአንድ በኩል ከተቋማቱ ጋር በሚያለያዩ ጉዳዮች መንግሥት የራሱን አገራዊ ፖሊሲዎች እየተከተለ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱ ካቀረቧቸው መካከል ጠቃሚ የሆኑትን ምክረ-ሀሳቦች ተቀብሎ ተግባራዊ እያደረገ ለመጓዝ በመቻሉ ነው።

በዚህ መሠረት መግባባት የተደረሰባቸውን አቋሞች ወዲያውኑ ተግባራዊ ማድረግ ተጀመረ። ይህ ሥራ በብዙ አገሮች የተወሳሰበና ብዙ ጉዳት ባስከተለ መንገድ የተፈጸመ ነበር። በዚህ የተነሳ ብዙ መንግሥታት በሙስና ቅሌት ውስጥ እስከመዘፈቅ ደርሰዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በሚሸጡት ተቋማት ውስጥ የነበሩት ሠራተኞች መብትና ጥቅማቸውን አጥተዋል። በመሆኑም በእኛ አገር ይህ ተግባር ከመነሻው ጀምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ጥንቃቄ ባልተለየው ሁኔታ መፈጸም ስለነበረበት፣ በቅድሚያ ተቋማቱን ወደግል የማዛወሩ ሂደት በግልጽ የጨረታ ሥርዓት እንዲፈጸም ተደረገ። በተጨማሪም በዚህ ሂደት በወቅቱ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሥራ አስኪያጅ የነበሩና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኃላፊዎች ከነበሩት መካከል የሙስና ቅሌት ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦች ወደሕግ አደባባይ ቀርበው ማስረጃ የተገኘባቸው እንዲቀጡ ተደረገ። የንብረት ባለቤትነት ዝውውሩ የተቻለውን ያሕል በተቋማቱ ውስጥ የነበሩትን ሠራተኞች መብትና ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ተፈጸመ። በቀላሉ አትራፊ እንደሚሆኑ የታመነባቸው አንዳንድ ተቋማት ደግሞ በቀጥታ ለሠራተኞች ተላለፉ። ከእነዚህ ተቋማት አንዱ ዋልያ አገር አቋራጭ የትራንስፖርት ድርጅት ሲሆን፣ ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማትም በውስጣቸው የነበሩ ሠራተኞች በባለቤትነት እንዲረከቡዋቸው ተደርጓል። ባለሀብቶች በጨረታ በሚገዟቸው ተቋማት ውስጥ የሚቀጥሉ ሠራተኞችን በቀላሉ ከሥራ እንዳያባርሩና የሠራተኞችን ጥቅም የሚጎዳ አርምጃ እንዳይወስዱ ሲባልም ጠበቅ ያሉ መመሪያዎች ተቀርጸው ተግባራዊ ተደርገዋል።

በኢትዮጵያ የተካሔደውን የመንግሥትን ንብረት ወደግል የማዛወር ሂደት ባሕርይ በትክክል ለመገንዘብ በክፍለ ዘመኑ ማብቂያ ላይ በሩስያ ከተፈጸመው ፕራይቬታይዜሽን ጋር በማነጻጸር መመልከት የቀለለ ይሆናል። በናያሚ ክሌን አገላለጽ ሶቭዬት ሕብረት በቀዝቃዛው ጦርነት ተሸንፋ ከተበታተነችና ወደታላቋ ሩስያ መንግሥትነት ከተለወጠች በኋላ፣ "በጀፍሪ ሣክስ አጋፋሪነት በተካሔደው ፕራይቬታይዜሽን በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ በመንግሥት እጅ የነበሩ ወደሩብ ሚሊዮን የሚጠጉ ተቋማት(225,000) ወደግል ይዞታ"[20] ተሸጋግረዋል።

ይህን ያህል የህዝብ ሀብት በጥድፊያ ወደግሉ ሴክተር የተላለፈው ለግምት በሚያስቸግር ዝቅተኛ ዋጋ ነበር። በዚህ የጥድፊያ ሽያጭ የነዳጅ ጉድጓዶችና ኩባንያዎች በመጣያ ዋጋ ተሸጠው በአንድ ጀንበር ምሽት ቢሊየነሮች ተፈጥረዋል። ይህን የመሰለው ነውጠኛ የኒዮ-ሊበራል ፍልስፍና ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ሩስያ ብዙ ሚሊዬነሮች አልነበሯትም። ከዚህ እርምጃ በኋላ ግን በከባድ ዝርፊያ የከበሩ አስራ ሰባት ቢሊዬነሮች ተፈጥረዋል። በዓለም ዙሪያ የተካሔደው ፈጣን ፕራይቬታይዜሽን በሁሉም አገሮች ይህን ያህል ቁጥር ያላቸው ቢሊዬነሮች ባይፈጥርም፤ በሜክሲኮ እንደካርሎስ ሣሊናስ የመሳሰሉ ባለብዙ ቢሊዮኖችን ፈጥሯል። ይህን ያህል ባይሆንም፣ በአፍሪካና መሰል ያልበለጸጉ አገሮች ተግባራዊ በተደረገው ኒዮ- ሊበራላዊ አቅጣጫ የተከሰተው ውጤትም በህዝብና በአገር ሀብት ላይ ተመሳሳይ ዝርፊያ የተካሔደበት ነበር። በአፍሪካ ላይ የተካሔደውን ኒዮ-ሊበራል ጥቃት በአጭሩ መመልከት ይህን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል።

እ.ኤ.አ በ1973 በታየውና በኋላም በ1979 በተደገመው የነዳጅ ቀውስ ከፉኛ የተመቱት አፍሪካውያን ባጋጠማቸው የከፍያ ሚዛን መዛባትና የማክሮ-ኢኮኖሚ አለመረጋጋት ተገደው ከነዓለም ባንክ ብድር ሲጠይቁ የቀረበላቸው አማራጭ ኒዮ-ሊበራላዊ ምክረ-ሀሳብ ነበር። በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ የአፍሪካ መንግሥታት ራሳቸውን በዓለትና በቋጥኝ መካከል አገኙት። መበደሩ የገንዘብ ችግራቸውን ለጊዜው ቢያቃልለውም፣ በዓለም አቀፍ ተቋማቱ የቀረበላቸውን አስከፊ ምክረ-ሀሳብ መጋት ደግሞ ለሌላ የከፋ ቀውስ የሚዳርግ ሆነባቸው። በርካታ የአፍሪካ መንግሥታት አማራጩን ጠልተው አንበደርም ካሉ ለሠራተኞቻቸው ደሞዝ መክፈል ወደማይችሉበት ደረጃ ይወርዳሉ። ምክረ-ሀሳቡን ተቀብለው ተግባራዊ ማድረግ ደግሞ መንግሥትን በማዳከም፣ የልማት ተቋማትን በርካሽ በመሸጥ፣ ሠራተኞችን በገፍ በመቀነስ ወዘተ..... ለሌላ የባሰ ቀውስ የሚያጋልጣቸው ነበር።

በመጨረሻም ሁለት ክፉ አማራጮች የቀረቡላቸው የአፍሪካ መንግሥታት፣ "ከፋቱ በተነጻጻሪ ዝቅ ያለ ነው" (The lesser Evil) ብለው የገመቱትን ኒዮ-ሊበራል ምክር በመቀበል መዋቅራዊ ለውጥንና ጽንፈኛ እርምጃዎችን ወሰዱ። የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾችን በገበያ ከማስወሰን ጀምሮ በመንግሥት እጅ የነበሩ ንብረቶችን በጥድፊያ ሸጡ። ቁበሪካዎቹን ብቻ ሳይሆን የኤሌክትሪከና የቴሌኮሙኒኬሽን ከዛም አልፎ የከተማ መጠጥ ውሐን ጭምር ወደግል ይዞታ አስተላለፉ። ነገር ግን ይሕን ባደረጉ ማግስት የአገራቱ ኢኮኖሚ ይበልጥ ተቃወሰ። ሥራ አጥነትና ድኅነት ተባብሶ መመሰቃቀሉና በማሽቆልቆል ጉዳና መቀጠሉም አልቀረለትም። በራሱ በአይ ኤም ኤፍ የእምነት ቃል መሠረት፣ "ፖሊሲው የዕድገት ጭማሪ ያስገኛል የተባለለትን ያህል፣ በርካታ አገሮች በተጨባጭ የዕድገት ተቋዳሽ ሳይሆኑ ቀሩ"። ከፖሊሲው ትግበራ በኋላ በእነዚህ አገሮች "የሀብት ልዩነት መጥበቡ ቀርቶ በመስፋቱ ከባድ ዋጋ ሊከፍሉ ተገደዱ"። ይህም

"እንደገና ተመልሶ ዕድገትን የማዳከም ውጤት አስከተለ"። የዓለም ገንዘብ ድርጅት ኒዮ-ሊበራሊዝም ባስከተለው ጥፋትና ውድቀት ዙሪያ ያቀረበው ይህ ግምገማ ለዘብ ያለ ግለሂስ ከመሆኑ በስተቀር መለስ ዜናዊ በጉዳዩ ላይ ካቀረበው ትንተና ጋር በይዘቱ ተመሳሳይ ነው። መለስ ለሥልጠና እንዲያገለግል ባዘጋጀው "የተሃድሶው መሥመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ" መጽሐፍ ላይ፣

> "የዚህ [ኒዮ-ሊበራል] ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ውጤት በአብዛኛው ጥፋት፣ የሥራ አጥነት ጫፍ መርገጥና የኢንዱስትሪ ልማት ሳይሆን የነበሩት ጥቂት ኢንዱስትሪዎች መክሰም ሆነ። የባንክ ሥርዓቱ በውጭ ባንኮች በሞኖፖሊ ተይዞ የወለድ ምጣኔ በቀላሉ ለመበደር በማይቻልበት አኳኋን ወደሰማይ አሻቀበ። ይህን ንግድ እንጅ አምራቹ ዘርፍ ሊሸከመው ስላልቻለ ለኢምፓርተርስ በማበደር ላይ የታጠረና ከውጭ ምንዛሬ ተመን መውጣት መውረድ ጋር ተያይዞ ቁማር የሚጫወት፣ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነዶችን በማገላበጥ ብቻ ትርፍ የሚያጋብስ ዘርፍ ወደመሆን ተሸጋገረ። ለልማት በተለይም ለኢንዱስትሪ ልማት የሚያገለግል ቁልፍ መሣሪያ ሊሆን ይችል የነበረው ዘርፍ፣ እድሜ ለኒዮ-ሊበራሊዝም፣ የቁማርና በሞኖፖሊ የተያዘ ኪራይ ሰብሣቢነት መናኸሪያ ሆኖ ቀረ። የውጭ ምንዛሬ ተመን በገበያ መወሰን አለበት ተብሎ በየሱቁ መሸጥ ሲጀምር፣ ተመኑ እጅግ በከፍተኛ መጠን ወድቆ ያለማቋረጥ አሽቆለቆለ። የተፈጥሮ ሀብት ኪራይ በማግኘት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት ወይም ከዳያስፖራ በተገኘ ገቢ ዶላር ያገኘ በእጅጉ የሚያልፍለት፣ ሌላው ግን የሚዘረርበት ሁኔታ ተፈጠረ። ...የውጭ ምንዛሪ ገበያው ኢንቨስትመንትና ኤክስፖርትን ከማደፋፈር ይልቅ የሚያቀጭጭ ሆነ። የኢኮኖሚ ተዋንያኑ ዋና ተግባር የእርዳታና የዳያስፖራ ገንዘብና ገቢን ማሳደድ ሆነ።"[21] በማለት ገልጸታል።

በሩስያም ሆነ በአፍሪካ የተካሔደው ሊበራላይዜሽንና ፕራይቬታይዜሽን ለጥቂቶች ከሰማይ የተላከ መና ሆኖላቸዋል። በዓለም ገንዘብ ድርጅት ምክረ-ሀሳብ በመመራት የሚካሔድ የአገራዊ ሀብት ዝውውር በመሠረቱ በዝርፍያና በንጥቂያ ለመክበር ከሚያስችለው ከምዕራቡ ዓለም ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት ባሕርይ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ እንደሆነ በግልጽ ታይቷል። በአፍሪካ የምዕራባውያኑን ምክር ቃል በቃል ተግባራዊ ለማድረግ የተካሔደው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እዚያው በዚያው ድኅነትን የሚያባብስ ውጤት ያስገኘ ነበር። ይሁንና ከዚህ ሂደት በሩቁም ቢሆን ተገቢውን ትምሕርት የቀሰመችው ኢትዮጵያ ይህን የጥፋት ምክር አልተቀበለችም። ሩስያን ያክል አገር በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከሁለት መቶ ሺህ በላይ

ተቋማትን እንዲሸጥ ሲገደድ፣ በኢትዮጵያ ከሦስት መቶ የማይበልጡ የመንግሥት ተቋማትን ወደግል ይዞታ ለማዛወር ከሃያ ሦስት ዓመታት በላይ ወስዷል። ይህም እንደገና መንግሥት በጥድፊያ እንዲፈጽመው ግፊት የተደረገበትን ፕራይቬታይዜሽን ተቋቁሞ ሂደቱን በራሱ ውሳኔና አገሪቱን በሚጠቅም ጊዜና መንገድ ብቻ ለማስፈጸም እንደቻለ ሌላ ማረጋገጫ ነው።

ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች ያመጡት የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብ በመንግሥት እጅ ያሉ ተቋማት በጥድፊያ እንዲሸጡ በማስገደድ ደረጃ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። "መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም" በሚለው የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮተ-ዓለማዊ መመሪያ መሠረት፣ በአዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ላይ መሰማራትም የተፈቀደ አልነበረም። ነገር ግን የአገራችን መንግሥት ይህን የመሰለውን ምክረ-ሀሳብ መቀበል አልፈቀደም። ይልቁንም የሽግግሩን ወቅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ በተግባር ለማዋል በመሠረተ- ልማት ኢንቨስትመንት ውስጥ ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ ጀመረ። በአባይ ወንዝ ላይ የመጀመሪያውን የጫራ ጫራ ግድብ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በራሱ በመንግሥት አቅምና ባለቤትነት ገነባ። እንደገናም በየአቅጣጫው አዳዲስ አገር አቋራጭ መንገዶችን መገንባትና ነባሮችንም ደረጃቸውን ከፍ አደረገ። የዓለም ከተማ-ሰቆጣ-አቢይ ዓዲንና የአዲስ አበባ ሐዋሳ እንዲሁም የአዲስ አበባ አስቦ መንገዶችን ደረጃ የማሳደግ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሆኑት በዚህ ጊዜ ነበር።

እነዚህ ጥቂት አብነቶች አገሪቱ ከሽግግሩ ወቅት ጀምሮ የፖሊሲ ነጻነቷን አስከብራ ለመቀጠል እንደቻለች ያሳያሉ። በማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾችም ረገድ መንግሥት የተመራበት አቅጣጫ ከብሪተን ውድስ ተቋማት ምክር ያፈነገጠ ነበር። በኢትዮጵያ አዲስ መንግሥት ከመመሥረቱ በፊት ባሉት አሥር ዓመታት በአፍሪካ ተግባራዊ የተደረገው የመዋቅር ማስተካከያ የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትን ያስከተለ ሲሆን፣ በሩስያም "ፈውስ" ይሆናል የተባለው ሊበራላይዜሽን የዋጋ ግሽበትን በከፍተኛ ደረጃ አባብሷል። ስለሆነም፣ የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾችን በገበያ አከራሪነት መርሕ እየተመሩ ለመወሰን መሞከር በራሱ በግለሰም ገንዘብ ድርጅት እንደታመነበት በእርግጥም ከኢኮኖሚ ቀውስ ውጭ ሌላ መልካም ውጤት የሚያመጣ አልነበረም።

ገና ከጠዋቱ ይህን የተገነዘበው የአገራችን መንግሥት በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ግንባታ መጀመሪያ ላይ የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾች በገበያ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ጣልቃ ገብነት የሚወሰኑበትን ሥርዓት ተከተለ። ደረጃ በደረጃም በገበያ እንዲወሰኑ በማድረግ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙን በራሳችን እቅድና አዝጋሚ በሆነ ሂደት ተግባራዊ አደረገ። ይህ መሠረት በአገሪቱ ለረጅም ጊዜ ይሠራበት የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ተመን ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲቀየር አደረገ። ቀደም ሲል ኢኮኖሚው በፈቅድም ባይፈቅድም የኢትዮጵያ ብር ከአሜሪካን ዶላር ጋር በቋሚ ተመን (Fixed Exchange Rate) ሲለዋወጥ

ነበር። አገሪቱ ትከተል በነበረው ቋሚ የልውውጥ ተመን መሬት ከፍ ሰማይ ዝቅ ቢል አንድ የአሜሪካ ዶላር በብር 2.07 ሳንቲም ብቻ ይለዋወጥ ነበር።

ደርግ የኢትዮጵያ ብር በሌለው ክብደት ከአሜሪካን ዶላር ጋር በቋሚ የብር 2.07ሳንቲም እንዲለዋወጥ ማድረጉ የኢኮኖሚውን ክብደት እንደሚያሳይ አድርጐ ቢቆጥረውም፣ በዚህ ተመን በመለዋወጥ ለአዲሱ መንግሥት በካዝናው ውስጥ ያቆየው ዶላር ለአንድ ወር የሚሆን ነዳጅና ሌላም ሸቀጥ ከውጭ ለማስገባት የማይበቃ ነበር። ይህም የውጭ ምንዛሬ ትመና ፖሊሲው አንዳችም የልማታዊ ኢኮኖሚ ግንባታ አመክንዮ ሳይኖረው የመንግሥታዊ ካፒታሊስቱን ኀዠመደብ ጥቅም ማዕከል በማድረግና ለዝና ሲባል ብቻ የተቀረጸ ስለነበር ነው። ደርግ የግሉን ሴክተር ሰዕድገት በአዋጅ ከገደበ በኋላ ዋና ዓላማው ሥልጣን ይዞ የአገሪቱን ሀብት በመመዝበር ራሱን ወደመንግሥታዊ ባለሀብትነት (State Capitalism) ያሸጋገረውን የወታደራዊ መኮንኖች ቡድን ጥቅም ማስከበር ነበር። ስለሆነም ወታደራዊው መንግሥት ከነአይ ኤም ኤፍ የገበያ አክራሪ አስተሳሰብ በተቃራኒ በመንግሥት ጽንፈኛ ጣልቃ ገብነት አስተሳሰብ እየተመራ በባዶ ኪስ በመኮፈስ የግብዝነት መንፈስ የቀረጸው የውጭ ምንዛሬ ተመን በአገሪቱ ሰፍኖ የነበረው የእዝ ኢኮኖሚ አንድ መገለጫ ነበር።

አዲሱ መንግሥት በአንድ በኩል ከብሪተን ውድስ ተቋማት የገበያ አክራሪነት ምክረ-ሀሳብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከደርግ የእዝ ኢኮኖሚ መንግሥታዊ ጽንፈኝነት በተቃራኒ ባደረገው የውጭ ምንዛሪ ተመን ማስተካከያ የኢትዮጵያ ብር ከአሜሪካን ዶላር ጋር በተመጣጣኝና ቋሚ ተመን ሳይሆን፣ ከእውነተኛ ክብደቱ ጥቂት ዝቅ ብሎ በመለዋወጥ እንዲጀምር አደረገ። ደረጃ በደረጃ ደግሞ ገበያው በጣም ልቅ ባልሆነ መንገድ ተመኑን እያስተካከለው እንዲሔድ በማድረግ ተንሳፋፊ የውጭ ምንዛሪ ተመን (Floating Exchange Rate) ፖሊሲ መከተል ጀመረ። ተንሳፋፊ የውጭ ምንዛሪ ተመን ከአሜሪካን ዶላር በትይዩ ለአንዴና ለብዙ ጊዜ ያልረጋ ወይም ቋሚ ያልሆነና ገበያውን ተከትሎ ከፍና ዝቅ ሊል የሚችል የምንዛሬ ተመን ነው።

ከዚህ በመነሳት መጀመሪያ ላይ በመንግሥት አስተዳደራዊ ውሳኔ አንድ የአሜሪካን ዶላር በአምስት የኢትዮጵያ ብር እንዲለዋወጥ ተደረገ። ቀስ በቀስ ደግሞ የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን የገበያ ሕግጋቱን ተከትሎ በአቅርቦትና ፍላጐት አማካይነት እንዲወሰን ተደረገ። ፍላጐቱ አይሎ ለአያንዳንዱ ዶላር ዜጐች በገበያ ሊሰጡት የተዘጋጁት የብር መጠን ከፍ ሲል የዶላር አቅርቦትን በማሳደግ፣ በአንጻሩ ፍላጐቱ ቀንሶ ለአያንዳንዱ ዶላር የሚሰጠው የብር ተመን ዝቅ ሲል አቅርቦቱን በማሳነስ መንግሥት ይህን ውድ ሀብት በአግባቡ ማስተዳደር ጀመረ።

የተጋነነው ትመና ሲስተካከል አገሪቱ ወደውጭ የምትልካቸውን ምርቶች በመጠንና በዓይነት ለማሳደግ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ። የብር የምንዛሪ ተመን ከመደበኛ ደረጃውም ትንሽ

ዝዋ ብሎ አንዲረጋጋ መደረጉ ለውጭ ገበያ አልመው የሚያመርቱ ወገኖችና ኤክስፖርተሮች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉበት ዕድል እንዲሰፋ አደረገ። በእነ ዓለም ባንክ መመሪያ ዶላር በየሱቁና ሱቅ በደረቱው እንዲሸጥ ያደረጉ አገሮች ከዶላሩም ከዕድገቱም መሆን ሲሳናቸው፣ ኢትዮጵያ ግን የዶላር አቅሟ ከጊዜ ወደጊዜ እየጐለበተ፣ ዕድገቷም በዚያው ልክ እየተፋጠነ ልትሔድ ቻለች። ከደርግ በጣም ጥቂት ዶላር ብቻ የተረከበው መንግሥት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዋዜማ ላይ ወደዘጠኝ መቶ ሚሊዮን ዶላር ለማከማቸት በቃ። በስንት ጥረት የተከማቸውን ይህን ውድ ሀብት ለሁለት ዓመታት የቆየው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እንደገና መጥጥ አድርጐ የበላው መሆኑ ከፋ እንጂ፣ ልማታዊ ጥረቱ ከነውሱንነቱም ሆኖ መልካም ፍሬ ማስገኘት ጀምሮ ነበር። በዚህም ማክሮ ኢኮኖሚው ተረጋግቶ ከመቀጠሉ በተጨማሪ አገሪቱ በጣም ፈጣን የዕድገት ምጣኔ እያስመዘገበች ልትቀጥልና ከደርግ ውድቀት በኋላ በነበሩት አሥር ዓመታት የኢኮኖሚ አለመረጋጋትና የዕድገት ማሽቆልቆል የሥርዓቱ ፈተና መሆኑ አቋረጠ።

ይህ አጭር ምሣሌ እንደሚያመላክተው በአገሪቱ መመዝገብ የጀመረው ፈጣን ዕድገት የአገራችን መንግሥት ፖሊሲዎቹን ከብሪተን ውድስ ተቋማት ነጻ በሆነ መንገድ ለመንደፍና ተግባራዊ ለማድረግ በመቻሉ የተገኘ ውጤት ነው። ነገር ግን የፖሊሲ ነጻነት መገኖናጸፍ እንደ ሕብስተ መና ከሰማይ የሚወርድ ጸጋ አይደለም። ከሁሉ በፊት ጠንካራ አገራዊ ስሜትና ህዝባዊ ወገናዊነት ያለው ድርጅትና መንግሥት መኖሩን ይጠይቃል። በተጨማሪም በንድፈ- ሀሳብ መበልጸግን የግድ ይላል። ጆሴፍ ስቲግሊዝ "Globalization and Its Discontents" በሚለው መጽሐፉ ጠንካራ አገራዊ ስሜትና ህዝባዊ ኃላፊነት ለዚህ ዓይነቱ ውጤት የሚያበቃ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ይገልጻል። ስቲግሊዝ በዚህ መጽሐፍ "Ethiopia and the Struggle Between Power Politics and Poverty" በሚል ንዑስ-ርዕስ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የአገራችን መንግሥት ከአይ ኤም ኤፍ ጋር ስላደረገው ትግልና ስለወገዘቡ፡-

> "እኔ እ.ኤ.አ በ1997 [ወደዓለም ባንክ] ስገባ መለስ ከአይ ኤም ኤፍ ጋር ከፍተኛ ሙግት ውስጥ ገብቶ አገኘሁት። አይ ኤም ኤፍ በወቅቱ ለኢትዮጵያ ይሰጥ የነበረውን የብድር ፕሮግራም ሰርዘት ነበር። በዚያ ወቅት አይ ኤም ኤፍ ሊያተኩርበት የሚገባው የኢትዮጵያ ማክሮ ኢኮኖሚና ይህም ያመጣው ውጤት ከዚያ የተሻለ ሊሆን አይችልም ነበር። የአገሪቱ ምርት እየጨመረ ከመሔዱም በላይ የዋጋ ግሽበትም አልነበረም። ይልቁንም የሸቀጦች ዋጋ በመቀነስ ላይ ነበር። መለስ በትክክለኛ ፖሊሲ ለመመራት እስከተቻለ ድረስ አንዲት ድሃ አፍሪካዊት አገር ዘላቂ ዕድገት ለማስመዝገብ እንደምትችል በተግባር ቢያሳይም፣ በመለስና በአይ ኤም ኤፍ መካከል ችግር ተፈጥሮ ነበር።"[22] በማለት ጽፏል።

ስቲግሊዝ በመጽሐፉ "ኢትዮጵያ በምታገኘው እርዳታና ብድር ትምህርት ቤቶችና የጤና ተቋማትን ከመገንባት ተቆጥባ መጠባበቂያ የገንዘብ ክምችቷን ማበራከት ይገባታል" የሚለው የአይ ኤም ኤፍ አቋም፣ ለማኅበራዊ ልማት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ከሚፈልገው የመንግሥት አቋም ጋር ሊጣጣም አለመቻሉ ዋናው የውዝግቡ መንስዔ እንደሆነ ይገልጻል። በአይ ኤም ኤፍ አቋሞችና ዋሽንግተን ላይ ተቀምጦ ቁጭን ትእዛዝ በሚያስተላልፈው የፈረንጅ ቢሮክራት ድርጊት የተከፋው መለስ፡-

> "ለአሥራ ሰባት ዓመታት በረሀ ለበረሀ በትግል የተንከራተትነው ሊጋሽ አገሮችን አሳምነን ባገኘነው ገንዘብ አንድ ዓለም አቀፍ ቢሮክራት ለህዝባችሁ ትምህርት ቤትና ክሊኒክ ልትሠሩ አትችሉም ብሎ መመሪያ እንዲሰጠን አይደለም"[23] የሚል ኃይለ ቃል ሲናገር እንደሰማውም ይመሰክራል።

ስቲግሊዝ አይ ኤም ኤፍ ለኢትዮጵያ በነበረው አቀራረብ ምን ያህል የተሳሳተ እንደነበርም በግልጽ ያነሳል። በመለስ የተመራው መንግሥት ይህን ለመቋቋም ያደረገውን ትግልና ውዝግቡ በዚህ ብቻ የማይወሰን እንደነበር፣ ይልቁንም "የብድር አመላለስና የኢትዮጵያን የፋይናንስ ሴክተር ለውጭ ክፍት ማድረግን ወዘተ" የሚመለከቱ ጉዳዮችም አወዛጋቢ እንደነበሩ በመጽሐፉ ላይ የሚያወሳው ስቲግሊዝ፡-

> "ጠቅላይ መምሪያውን በ19ኛው ስትሪት ላይ ባደረገው አይ ኤም ኤፍ ዘንድ አገሮችን በጥብቅ መቆጣጠርና ውጤት ተኮር ምዘና ማድረግ ለዓመታት የተያዘው ፈለጥ ነበር። ከዚህ አኳያ አገር በቀል ፖሊሲ በመከተል አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ የጀመረችው ኢትዮጵያ ራሷን የመምራት ብቃት እንዳላት ሌላ ማረጋገጫ አያስፈልግም ነበር። ነገር ግን አይ ኤም ኤፍ ከተቋሙ የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ አገሮች ሁሉ ስለማንኛውም ነገር ዝርዝር ሪፖርት ሊያቀርቡለት እንደሚገባ፣ ይህን አለማድረግ ደግሞ እርምጃው ተገቢ ቢሆንም ባይሆንም የድጋፍ ፕሮግራሞች ስረዛን እንደሚያስከትል ያምን ነበር። ለኢትዮጵያ ደግሞ ይህን የመሰለው ግልጽ ጣልቃ ገብነት አዲስ ዓይነት የቅኝ አገዛዝ ምልክት ነበር"[24] ይላል።

ስቲግሊዝ በዘመነ ግሎባላይዜሽን የኢትዮጵያን አገራዊ የፖሊሲ ነጻነት ለማስከበር የተካሔደውን ትግል ከአዲሱ ትውልድ የፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ጋር በማመሳሰል ከገለጸው በተጨማሪ ኬኒች አኖ አምስት የምሥራቅ እስያ አገሮችና ከአፍሪካ ደግሞ ኢትዮጵያን በማጥናት የልማታዊ መንግሥታትን ተመክሮ በቀመረበት "Learning to

Industrialize" በተሰኘ መጽሐፉ፡-

> "ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች በብዙ መንገዶች ትለያለች፡፡ ለሃያ ዓመታት ያህል በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተመራው ፌዴራላዊ መንግሥት ጠንካራና ተግባር ተኮር ነው፡፡ አገሪቱ በዴሞክራሲያዊ ልማታዊነት ላይ የተመሠረተ ልማታዊ ራዕይና ተመጋጋቢ ስትራቴጂዎችን ነድፋለች፡፡ ከሁሉ በፊት በአገሪቱ ጠንካራ የፖሊሲ ባለቤትነት አለ፡፡ ኢትዮጵያ ትልቅ የውጭ እርዳታ የምታገኝና በተለምዶ ከሚታወቁት የኤክስፖርት ምርቶች የምታገኘው ገቢ ዝቅተኛ ቢሆንም፣ የአገሪቱ መንግሥት በጥራት የተቀረጸ አገር በቀል የልማት ስትራቴጂ አለው፡፡ ኢትዮጵያ ለጋሾች ከሚያፈቅሯቸው በርካታ የአፍሪካ አገሮች በተለየ ሁኔታ የሁለትዮሽ ተባባሪዎቿም ሆኑ ዓለም አቀፍ ለጋሾች፣ 'እርዳታን በማጣጣም ወይም የበጅት ድጎማ በማድረግ ሥም'፣ ወይም "የብድር ቅድመ ሁኔታዎችንና ዓለም አቀፍ መልካም ልምዶችን የሚጋራት አሠራርን" ተገን አድርገው የፖለሲ ተዕዕኖ እንዲያደርጉባት አትፈቅድም፡፡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትም (FDI) ሆነ ከባሕር ማዶ የሚመጣ እርዳታ (ODA) እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው ከአገራዊ የልማት አቅጣጫዋ ጋር የተጣጣሙ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡"[25] ይላል፡፡

አሁን ስላለው የውጭም ሆነ የአገር ውስጥ ባለሀብት አያያዝ ቆየት ብዬ የምመለስበት ሆኖ ኬኒቺ ኦኖ የሰጠው ይህ የምስክርነት ቃልም ኢትዮጵያ በዘመነ ግሎባላይዜሽን የፖሊሲ ነጻነቷን አስከብራ ለመቀጠል ያደረገችውን ተጋድሎ ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ድህና በፍጥነት ወደብልጽግና ለመረማመድ የምትጣጣር አገር ብትሆንም፣ የፖለሲ ነጻነቷን ያስከበረች አገር ልትሆን የቻለችው የህዝቦቿን የዴሞክራሲና የልማት ፍላጐት መሠረት አድርጐ የሚንቀሳቀስ መንግሥት ስላገኘች ነው፡፡

በየትኛውም አገር ከፍተኛ ዕድገት ለማስመዝገብ የሚቻለው አዲስ ሀብት ለመፍጠር የሚያስችል የተሟላ አስተሳሰብ ለመያዝ ከተቻለ ብቻ ነው፡፡ ህዝቡን ከድኅነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ ቆርጦ የተነሳና ለዚህም የሚበጁ ትከክለኛ የለውጥ ሀሳቦችን አመንጭቶ ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ያለው አመራር ሲኖር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ብዙዎቹ ያልበለጸጉ አገሮች መሪዎች ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብት በጥሬው እየሸጡ ከዚህም የሚገኘውን ገቢ በመቀራመት ተጠቃሚ እንሆናለን ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡ እነዚህ መሪዎች የህዝብን ጉልበት አንቀሳቅሶ አዲስ ሀብት በመፍጠር የማያምኑ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን እየሸጡ በሚያገኙት ሀብት የራሳቸውን ክብርና ዝና፣ አምባገነንነትና መናኛ ጥቅም የሚያማትሩ ናቸው፡፡ ስለዚህም ደግሞ አዲስ ሀብት

ለመፍጠር የሚያስችል አስተሳሰብ ያልታጠቁ ናቸው። ይህ ብዙ ተንታኖች በስግብግብነት ስለተበከሉ መሪዎች ባቀረቡት ሀሳብ የተብራራ ሲሆን፣ በአፍሪካ ታሪክ ላይ ሰፊ ጥናት በማድረግ በርካታ መጻሕፍትን የጻፈው የአርተር ሉዊስ አገላለጽ ስለችግሩ ባሕርይ ለመገንዘብ የተሻለ ዕድል ይሰጣል። ሉዊስ፦

> "በእነዚህ አገሮች ውስጥ የሚሆነው ሁሉ የሰው ልጆች ለሥልጣንና ሀብት ያላቸው ስግብግብነት መገለጫ ነው። ከእነዚህ የሚገኘው ጥቅም እጅግ ከፍተኛ ነው። ሥልጣን ኃይል፣ ክብርና ገንዘብን ያጐናጽፋል። በእጅ የሚገባው ሥልጣን ወደር የለውም። አብዛኞቹ የምዕራብ አፍሪካ ሚኒስትሮች ራሳቸውን ከሕግ በላይ አድርገው ይመለከታሉ። ፖሊሶችም ከሕግ በላይ አድርገው ያዩዋቸዋል። ውሳኔ የሚሰጡት እንዳሻቸው ነው። በበለጸጉ አገሮች አብዛኛውን ጊዜ ለሲቪል ሰርቪስ ሙያተኞችና ለቴክኒሻኖች የሚተወው ውሳኔ በእነዚህ አገሮች ግን በሚኒስትሮች ይሰጣል። ይህም ሲሆን በሙያው የተካኑ ሰዎችን ምክር መሻቴ የለም። ክብሩም እንደዚሁ መረን የለቀቀ ነው። ዴሞክራቶች ነን ብለው የሚመጻደቁት ሰዎች ልክ እንደነገሥታት መመለክ ይሻሉ። ራሳቸውን ብቻ መንግሥት ለማስመሰል የሚያግዟቸው ዩኒፎርሞች ይለብሳሉ። ቤተ መንግሥቶች ይገነባሉ። እነርሱ ሲንቀሳቀሱ የአገሩ ትራፊክ በአንድ እግሩ ይቆማል። ውድ ሰልፎች እንዲካሔዱ ያደርጋሉ። በአጠቃላይም እንደግብጽ ፈርዖኖች እንዲሰገድላቸው ይሻሉ። ገንዘቡም ቢሆን ትንሽ አይደለም። በለስ ቀንቷቸው የተመረጡት ለፓርላማ አባልነት ብቻ ቢሆን እንኳ ቀደም ሲል ያገኙት ከነበረው ሦስትና አራት እጥፍ ያገኛሉ። የውሎ አበል፣ የውጭ ጉዞና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችም ያገኛሉ። በዚህ ላይ ጉበው፣ የመንግሥት ሥራዎችን ኮንትራት በመስጠትና የህዝብን ሀብት ወደግል በማዞር የሚገኘው ጥቅምና ኮሚሽኖች ሲታከሉበት ገቢው የት የለሌ ይደርሳል። ሚኒስትር መሆን የሕይወት ዘመን ብልጽግናን መታደል ይሆናል።"[26] ይላል።

እንደ አርተር ሉዊስ ሁሉ ማርቲን ሜሪድዝ በበኩሉ ልክ ከዘመነ ቅኝ አገዛዝ ማክተም በኋላ ስለተፈጠረው ሁኔታና በኢሕጉሪቱ የፖለቲካ ሥልጣን የያዙ ሰዎች ራሳቸውን እንደሥርዓት እስከመመልከት እንደደረሱ፦

> "ቀስ በቀስ የአፍሪካ መሪዎች ከመቸውም ጊዜ የሚልቅ ግላዊ ሥልጣንና ኃይል በማካበት በሕብረተሰብ ላይ የቁጥጥር መረባቸውን ለማስፋፋት ቻሉ። ከሕገ-መንግሥታዊውና ፓርላማዊው የአሠራር ሥርዓት ይልቅ የራሳቸውን

የጥቅም መረብ በመዘርጋት መግዛት ጀመሩ። ፓርላማዎች አሉ ከተባለም በታማኝነት በሚታወቁ ሰዎች ተሞሉ። የመንግሥት ቢሮክራሲም በፓርቲ ታማኞች ታጨቀ። የሠራተኛና የአርሶ አደር ማኅበራት የመንግሥት ተቀጥላዎች ሆኑ። ፕሬስም የመንግሥት ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ከመሆን ያለፈ አልነበረም። የፖለቲካ ክርክር በድጋፍና ሙገሳ ንግግሮች ተተክቶ ከቁምነገር የማይጣፍበት ሁኔታ ተፈጠረ። የቱኒስያ ፕሬዚዳንት የነበሩት ሓቢብ ቡርጊባ በአንድ ወቅት ስለአገራቸው የፖለቲካ ሥርዓት ሲጠየቁ፣ በስላቅ ድምጽ "ሥርዓት? የምን ሥርዓት?" ካሉ በኋላ "የፖለቲካ ሥርዓት ማለት እኔው ራሴ ነኝ" እንዳሉት መሆኑ ነው።"[27] በማለት ይገልጻል።

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ ብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች ሀብትን በሞኖፖል በመቆጣጠር የሚከብሩና በተቻላቸው ሁሉ ህዝባቸውን በድኅነት አረንቋ ውስጥ በማቆየት የሚያኖሩ ናቸው። እነዚህ ከራሳቸው ጥቅም ውጭ ሌላ ራዕይ የሌላቸው መሪዎች አገራቸውንና ማኅበረሰባቸውን ከድኅነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ የሚያግዙ አዳዲስ ሀሳቦችን ለማምጣት ፍላጐትም ሆነ ተነሳሽነቱ የላቸውም። በዚህ ምክንያት አገራቸውን ለቁሳዊና መንፈሳዊ ብልጽግና ሊያበቃ ይችል የነበረውን የሀሳብ ጥራት መጐናጸፍ ያልቻሉ ናቸው። በዚያው ልክ ደግሞ የአገራቸውን ልማት ማፋጠን የተሳናቸውና አልፎ ተርፎም አንዳንዶች የተፈጥሮ ሀብትን በመቀራመት ዙሪያ አገራቸውን ወደምስቅልቅል ያስገቡና፣ የቀሩትም በዚህ አቅጣጫ ሕብረተሰባቸውን ወደቀውስ ማስገባት የማይቀርላቸው ናቸው። ይህን በቅርቡ ወደእርስ በእርስ ጦርነት ከተሸጋገረችው ደቡብ ሱዳን ጋር በተያያዘ የታዘብኩትን አንድ ገጠመኝ በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል።

በደቡብ ሱዳን የእርስ በእርስ ጦርነቱ ከመቀስቀሱ ከሁለት ወራት በፊት ለአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የኢትዮጵያን ልማታዊ ተሞክሮ በሥልጠና መልክ የማካፈል ዕድል አግኝቼ ነበር። ለሥልጠና ይዤው የቀረብኩት ርዕስ "ሀብት ፈጠራና የኢትዮጵያ ልማታዊ መንግሥት በጐ ተሞክሮዎች" የሚል ነበር። ሥልጠናው በደቡብ አፍሪካ የተካሔደ ሲሆን፣ ለእኔ ገለጻ የተመደበው ጊዜ እስኪደርስ የኬንያ መንግሥት ልውካን በሚሰጡት ገለጻና በዚህ ዙሪያ በሚካሔደው ውይይት ለመሳተፍ ወደአዳራሹ ጐራ አልኩ። ስብሰባው ከተጀመረ በኋላ በመግባቴ ለውይይት መነሻ የሆነው መንደርደሪያ ቢያመልጠኝም መነጋገሪያ አጀንዳቸው ከተፈጥሮ ጸጋዎች አስተዳዳር፣ አጠቃቀምና ከፍፍል ጋር ተያይዞ የቀረበ የኬንያ በጐ ልምድ እንደሆነ ከሀሳብ ልውውጡ ለመገንዘብ ቻልኩ። ኬንያውያኑ ባቀረቡት ገለጻ ላይ በመመስረት ደቡብ ሱዳናውያኑ የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ሁሉ የሚያጠነጥኑት "ምን ዓይነት ሀብት? ለማን?

እንዴትና ለምን ደረሰው?"፣ "ያች አምስት በመቶ ድርሻ ለማን ተሰጠች?"፣ "ፕሬዚዳንቱስ በዚህ ጉዳይ ላይ ለምን ይህን ያህል ድርሻ ተፈቀደለት? ለፕሬዚዳንቱ የተሰጠው ሥልጣንና ድርሻ ለጽሕፈት ቤቱ መሆን ሲገባው ለምን በስሙ ሆነ?" የሚሉ ጉዳዮች ነበሩ።

ደቡብ ሱዳን ነበሯት ከሚባሉት ከሰባት መቶ አምሳ በላይ ጀኔራሎችና በርካታ ሚኒስትሮች በዚህ መድረክ የተገኙት ሃያ ዘጠኝ ያህል ሲሆኑ አንዳቸውም ያለችውን የተፈጥሮ ሀብት ስለመቀራመት እንጅ ሳት ብሏቸው አዲስ ሀብት መፍጠር ስለሚቻልበት መንገድ አልጠየቁም። የኬንያና የጋና አሠልጣኞቻቸውም አብዝተው የተጣጣሩት ሀብትን መቀራመት መወጫ የሌለው ገደል እንዳልሆነ ለማሳመን ነበር። ቀደም ብለው ጠብመንጃቸውን ወልውለው የጨረሱት የደቡብ ሱዳን መሪዎች ግን "ደህና ወደአገሬ ልመለስ እንጅ ድርሻየን ካላገኘሁ አሠራለታለሁ" የሚል መንፈስ ይዘው በግማሽ ልብ ብቻ የሚሰሙ ይመስሉ ነበር።

የእኔ ተራ ሲደርስ ከኢትዮጵያ ልምድ በመነሳት ባቀረብኩት የልማታዊ መንግሥት ተሞክሮ ከድኅነትና ኋላ ቀርነት መላቀቂያ መንገዱ አስቀድሞ የተፈጠረን ሀብት መቀራመት ሳይሆን፣ በልማት በርትቶ አዳዲስ ሀብት መፍጠር እንደሆነ ለማሳየት ጥረት አደረግኩ። ከቀረበው ገለጻ በመነሳት በኢትዮጵያ የህዝብን ጉልበት በማንቀሳቀስ ብቻ ካለአንዳች ጠብታ ነዳጅ ያልነበረ ሀብት መፍጠር እንደተቻለና ይህም እንዲቀጥል የሚያደርግ የተለየ አቅጣጫ እንደምንከተል ለመገንዘብ ዕድል አገኙ። ለሥራ ጉዳይ በሚመላለሱባት ኢትዮጵያ ለውጡ በጉልህ የሚታይ ነበርና የቀረበው መንደርደሪያ ንድፈ-ሀሳባዊ መላምት ብቻ ሳይሆን፣ በተግባር የተተረጎመ አስተሳሰብ እንደሆነ ለማስረዳት ብዙም አስቸጋሪ አልነበረም። በጥያቄና መልስ ሂደቱ ሌላው ቀርቶ አሠልጣኝ የነበሩት ጭምር ከሊበራላይዜሽንና ፕራይቬታይዜሽን ውጭ ሌላ መንገድ እንዳለ ቢጥቁቱ ቢገነዘቡም፣ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ኪራይ መሰብሰብ ለለመደው አዲሱ የደቡብ ሱዳን መንግሥት ግን ጊዜው መሸቶ ነበር። ቢሠልጠናው ለተካፈለው የኢትዮጵያ መንግሥት የልዑካን ቡድን ደግሞ የደቡብ ሱዳን ግጭት አይቀሬ ብቻ ሳይሆን ግድግዳው ላይ በትልቁ ተጽፎ የሚነበብ ማስታወቂያ ይመስል ነበር።

ሥልጠናው በተጠናቀቀ በሁለተኛ ወሩ የዓለማችን አዲሷ ነጻ አገር ከጫፍ ጫፍ በባሩድ ጭስ መታጠን ጀመረች። በአገሪቱ መሥሪያ ቤቶች የተሰገሰጉት በሺዎች የሚቆጠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ የውጭ ድርጅቶችም፣ ደቡብ ሱዳን መቃጠል ስትጀምር በሩዋንዳ እንዳደረጉት ሁሉ አገሪቱን ጥለው ውልቅ አሉ። የደቡብ ሱዳን የእርስ በእርስ ግጭት የተፈጥሮ ሀብትን በመቀራመት ላይ የተመሠረተው ያልበለጸጉ አገሮች አቅጣጫ ምን ያህል አፍራሽ እንደሆነ ያሳያል። መለስ ዜናዊ ይህን ጉዳይ በማስመልከት "በአፍሪካ የዘራፊው መንግሥት አነሳሥና ቀውስ" ከዘመነ ቅኝ አገዛዝ እንደሚጀምር፣

"ከቅኝ ተገዥዋ አፍሪካ በፊት የነበረው ኢኮኖሚ በቅድመ ኢንዱስተሪና ዘዋድሙ ካፒታሊስት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነበር፡፡...ቅኝ አገዛዝ ግን ይህን ሁኔታ በዓይነቱ ቀየረው፡፡ ቅኝ ገዥው መንግሥት ዋናው የኪራይ ሰብሣቢነትና የጥገኝነት መረብ ማዕከልና አንቀሳቃሽ ሆነ፡፡ ቅኝ ገዥው መንግሥት ሀብት በቀላሉ የሚሸመጠጥባቸውን የማዕድን፣ የኤክስፖርት ግብርና ዘርፍና የመሳሰሉትን ተቆጣጥሮ ከፍተኛ ኪራይ ማግበስበስ ጀመረ፡፡ አፍሪካዊው አውሮፓውያኑ ከተቆጣጠሩት ዋነኛ የኪራይ ምንጭና ይህን ከሚያሳካው መንግሥታዊ ሥልጣን የተገለለ ሲሆን፣ በመንግሥት እጅ ያልነበሩት ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሀብት ምንጮች ደግሞ በዋነኛነት በምዕራባውያን ኩባንያዎች የተያዙ ነበሩ፡፡ ከእነዚህ የተረፈው ደግሞ በእስያውያንና በሊባኖሳውያን እጅ ነበር፡፡ አፍሪካዊው ገበሬ ለገበያ ተብሎ በሚመረት ግብርና ላይ እስካተኮረ ድረስ በሥርዓቱ ሠንሠለት ውስጥ ገብቶ የውጭ ኩባንያዎች የሰጡትን የሚቀበል ሆኗል፡፡ አፍሪካዊው የጉልበት ሠራተኛ የሚሰማራበት ኢንዱስትሪ ባይኖርም፣ በማዕድንና በመንግሥት እርሻዎች ተቀጣሪ በመሆን የሥርዓቱ አካል ተደርጓል፡፡ አፍሪካዊው ምሁር በበኩሉ ከንግድ ሥራዎች የተገለለ ቢሆንም፣ የቅኝ ገዥው መንግሥት የጥገኝነት መረብ ውስጥ ገብቶ የሥርዓቱ አንድ አካል ሆኗል፡፡...ቅኝ አገዛዝ ካከተመ በኋላ መሪነቱን የጨበጠው አፍሪካዊ መንግሥት ቢተከተለው የዕድገት አቅጣጫ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ የነበራቸውን እነዚህን ተጨባጭ ውጫዊና ውስጣዊ ቅድመ ሁኔታዎች ለመውረስ ተገደደ፡፡ ስለዚህም፣ አፍሪካዊው መንግሥት በቅኝ ገዥዎቹ የተፈጠረውን የፖለቲካ ኢኮኖሚ አጥብቆ ይዞና በተወሰነ ደረጃ አሻሽሎ ቀጠለበት፡፡ በዚህ የተነሳ አፍሪካዊው መንግሥት በባሕርይው ግለሰባዊ የሀብት ማከማቻ ማዕከልና ሀብት ከማከማቸት ሂደት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የፈጠረ መንግሥት ሆነ፡፡"[28] በማለት ያብራራል።

በተለምዶ ባልበለጸጉ አገሮች፣ በተለይ ደግሞ በአፍሪካ ከሚታዩ እነዚህን ከመሰሉ መንግሥታት የተለዩ ልማታዊ ሀሳቦችን ያዳበረውና ትክክለኛ ፖሊሲዎች ነድፎ ተግባራዊ ሲያደርግ የቆየው ኢህአዴግ የህዝብ ወገንተኝነትና የንድፈ-ሀሳባዊ ብስለትን አሟልቶ የተነሳ ድርጅት ነው፡፡ መነሻና መድረሻው የኢትዮጵያ ህዝቦች መብትና ተጠቃሚነት ነው፡፡ በመሆኑም፣ የአገሪቱ ህዝቦች መብትና ጥቅም እንዳይከበር ያደረጉ ችግሮች ከምን እንደሚመነጩ ለመለየት ጥረት አድርጓል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ችግሮቹን ለመፍታት ያስችላሉ ያላቸውን መንገዶች ሁሉ ፈትሾ ለኢትዮጵያ ተሰማሚነት ያላቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ነድፏል፡፡ አገሪቱና ህዝቦቿ ከተጋዘጡበት የማሽቆልቆል አቅጣጫ ተላቀው በዕድገት ጐዳና መረማመድ እንዲጀምሩ ያደረገበት

ቀዳሚ ምስጢርም፣ የአገራቱን ችግሮች የሚያቃልሉ ሳይንሳዊ መፍትሔዎችን በመቀመር ተግባራዊ ለማድረግ መቻሉ ነው።

ከእነዓለም ባንክ ጋር በተካሔዱት ድርድሮች የተሳተፉና የእኛን መንግሥት ባሕርይ በትክክል የተገነዘቡ የተቋማቱ መልዕክተኞች የአገራችንን ተወካዮች ከሌሎች መሰል አገሮች አቻዎቻቸው ጋር በማነጻጸር ሲገመግሙ፡ በተደጋጋሚ የሚጠቀሙበት አገላለጽ ነበራቸው። የተቋማቱ ተወካዮች የኢትዮጵያ መንግሥት ከብዙዎቹ መሰል አገሮች በተለየ ሁኔታ የሚሰጠውን ምክር እንዳለ በጭፍን አምኖ አይቀበልም ይሉ ነበር። ስለሆነም፣ ተወካዮቹ "የኢትዮጵያ መንግሥት 'ዝለል' ሲባል የመጀመሪያ ጥያቄው 'ለምን?' የሚል እንደሆነ፤ በአንጻሩ የሌሎች አገሮች ተወካዮች ደግሞ "ዝለሉ ሲባሉ በምን ያህል ከፍታ? የሚል ጥያቄ እንደሚያስቀድሙ በመገረም ያነሳሉ። ከዚህም አልፎ "ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ተደራድሮ መግባባት ከባድ እንደሆነ፣ አንዴ ከተግባቡ በኋላ ደግሞ መንግሥት ሥምምነቱን በጥብቅ ዲስፕሊን እንደሚፈጽም፣ በአንጻሩ ከብዙ ያልበለጸጉ አገሮች መንግሥታት ጋር በሚያካሂዱት ድርድር መግባባት ቀላል ቢሆንም፣ የተስማሙበትን በጥብቅ ዲስፕሊን ማስፈጸም ደግሞ ዋናው ፈተና እንደሚሆንባቸው" ይገልጻሉ። ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የኢትዮጵያ መንግሥት ከብዙ መሰል አገሮች በተለየ አኳኋን በብሪተን ውድስ ተቋማት ላይ ጭፍን እምነት አልነበረውም። በጭፍን ጥላቻ የመራቅ ወይም በራስ ባለመተማመን የመሸቆጥቆጥ መንፈስም አልነበረውም። ከእነዚህ ግዙፍና ኃይለኛ ተቋማት ጋር ለመደራደር ሲቀርብ፣ ስቴቨን ኮቪይ (2011) የሚገልጸው ዓይነት አስተዋይነት የተሞላበት እምነት (Smart Trust) ብቻ ነበረው።

ከፍ ሲል ከተገለፁት ጉዳዮች በመነሳት በኢህአዴግ የተመራው መንግሥት ከምንም ነገር በፊት የፖሊሲ ነጻነቱን በማስጠበቅ እንደጀመረ ለመገንዘብ ይቻላል። ይህ የፖሊሲ ነጻነት በሂደት ከልምድና ከኢኮኖሚው መጠናከር ጋር አብሮ እየጐለበተ የሔደ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዛሬም ከፊተናዎች ሙሉ ለሙሉ ነጻ የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት ግን አይቻልም። አገሪቱ፣ መንግሥትና ህዝቦቿ ገና ብዙ ትግል የሚጠይቅ ሂደት ከፊታቸው ይጠብቃቸዋል። የፖሊሲ ነጻነታችን በቀጣይነት ሊጠበቅ የሚችለው በየመድረኩ የሚገኘው አመራር ከወገናዊነት በተጨማሪ ራሱን በተራማጅ አስተሳሰብ ወይም ንድፈ-ሀሳብ ሲገነባ ነው። ከፍ ሲል እንደተመላከተው ኢህአዴግ የፖሊሲ ነጻነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል አቋም ላይ ሊገኝ የቻለው ድርጅቱ ሥር የሰደደ ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል ስለነበረው ነው።

ኢህአዴግና ንድፈ - ሀሳባዊ ባህሉ፤

በድኅነትና ኋላቀርነት የሚማቅቁ ብዙ ያልበለጸጉ አገሮች ከሚሰቃዩባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱ ቁሣዊ ድኅነት(Object Gap) ቢሆንም፣ ለዚህ የሚዳርጋቸው ቀዳሚው

ችግር ግን የሀሳብ ድኅነት(Ideas Gap) ነው:: ዳንኤል ዬርጊንና ጆሴፍ ስታኒስላው የ20ኛው ክፍለ ዘመን ታዋቂ ኢኮኖሚስት ኬይንስ "ሀሳቦች በተለምዶ ከምንገነዘበውም በላይ ኃያል ናቸው። እንዲያውም ዓለማችን የምትገዛው በሌላ ሳይሆን በሀሳብ ነው። ይዋል ይደር እንጅ ሰዎች ካዳበሩት ቀጥተኛ ጥቅም ይልቅ ሀሳቦች በበጐም ይሁን ከፉ ጉዳዮች ላይ ከባድ ተፅዕኖ አላቸው" በማለት ያነሳውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ "የኢኮኖሚ ሊቃውንትና ሌሎች አሳቢዎች አማራጭ ሀሳብ ሊኖራቸው ቢችልም፣ በሥራ ላይ የሚያውሉዋቸው ግን ፖለቲከኞች ናቸው። ከዚህ ሊወሰድ የሚችለው ዋናው ትምሕርት ደግሞ የመሪዎችና አመራር ጉዳይ እጅግ ተፈላጊ መሆኑ ነው።"[29] ይላሉ።

የሀሳብ ድኅነት ለውጥ የሚያመጡ ፍልስፍናዎች፣ ፖሊሲና ስትራቴጅዎች እጦትን የሚያጠቃልል ጉዳይ ነው:: ይህ እጦት በሚቀረፍበት ጊዜ አገሮች ያላቸውን ትንሽም ይሁን ብዙ በአግባቡ ያልለማ ጸጋና አቅም በፍጥነትና በተነጻጻሪ ውጤታማነት ለማልማት ይችላሉ:: የሀሳብ ድኅነትን ከማስወገድ አኳያ ኢህአዴግ በማንኛውም መስፈርት ቢለካ አንጻራዊ ብልጫ ነበረው።

ኢህአዴግ ገና ከጥዋቱ ጠንካራ ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል ካጐለበተው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ጋር በብርቱ ቁርኝት የተፈጠረ ድርጅት ነው:: ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በባሕርይው የብዙኅን ንቅናቄ የነበረ ቢሆንም፣ ለንድፈ-ሀሳብ ጥናትና ከርከሮች ይሰጠው በነበረው ቦታና ትኩረት ሲመዘን ግን ከብዙ ተራማጅ ፓርቲዎች የማይተናነስ ጠንካራ ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል ያዳበረ ነበር:: በኢትዮጵያ የሚያኮራ የንባብ ባሕል መዳበር የጀመረው ቀደም ሲል ቢሆንም ግራ ቀመስ መጻሕፍት ከ1950ዎቹ መጨረሻና ከስድሣዎቹ መጀመሪያ አንሥቶ በነበሩት ተማሪዎችና የንቅናቄው መሪዎች ዘንድ የንጉሣዊውን ሥርዓት የቁጥጥርና የሳንሱር ኬላዎች አልፈው በተማሪዎች እጅ ይደርሱ ጀመር:: ህዝባዊ ትግሉን ከልብ የተቀላቀሉ ወጣቶች ሁሉ መጻሕፍቱን በመናጠቅ የሚያነቡበት ባሕል ሥር እየሰደደ የሔደበት ይህ ወቅት፣ በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ እንደነዋለልኝ መኮንን የመሳሰሉ የመጠቁ ወጣቶች የተፈጠሩበት የንድፈ-ሀሳባዊ ብስለት ዘመን ነበር:: ሕይወት ተፈራ፣ ጌታቸው ማሩ በስድሣዎቹ መጀመሪያና አጋማሽ ላይ የነማርክስን ብቻ ሳይሆን የእነአንቶንዮ ግራምሺን[30] መጻሕፍት ልቅም አድርጐ እንዳነበበ ያቀረበችው መረጃ፣ የዚያ ዘመን ትውልድ ምን ዓይነት ምርጥ መጻሕፍት በማንበብ ለአገራችን ችግሮች መፍትሔ ያፈላልግ እንደነበር ያስገነዝባል። ታላቅ ወንድሜ ካሳሁን ገና የአሥራ ሰባት ዓመት ወጣት እያለ ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ የኃይለ ሥላሴን የሳንሱር ኬላ አልፈው የሚገቡ ግራ ቀመስ መጻሕፍትን ከጓዶቹ ጋር እየተናጠቀ ያነብ የነበረ መሆኑ የያኔው ወጣት ትውልድ ለአስተሳሰብ ዕድገት የተለየ ትኩረት እንደነበረው በአግራሞት ይታወሰኛል። በስድሣዎቹ አጋማሽ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመቅረጽ ሥራ ላይ ተጠምደው የነበሩት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ደግሞ ከዚህም በጣም ርቀው የሄዱ ነበሩ። እነዚህ ተራማጅ ወጣቶች ለአጠቃላዩ የዴሞክራሲ፣ በተለይ ደግሞ ለብሔሮች እኩልነትና ለአርሶ አደሩ የመሬት ጥያቄ

የቀመሩዋቸው የመፍትሔ ሀሳቦች የወቅቱ ወጣት ተማሪዎች ንድፈ-ሀሳቡን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማጣጣም ብቃት ያዳበሩ ጭምር እንደነበሩ ያሳያል።

ይህ ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል የየካቲት አብዮት ከተቀሰቀሰ በኋላ እስከ 1970ዎቹ መጀመሪያ ድረስ የቀጠለ ቢሆንም፣ ብዙም ሳይቆይ ደርግ በትውልዱ ላይ በሠነዘረው ዘግናኝ ቅጣት፣ በተለይ በከተሞች ደብዛው መጥፋት ጀመረ። በኢትዮጵያ የአዳዲስ ሀሳቦች ፈር ቀዳጅ የነበረውን ትውልድ በቀይ ሽብርና ነጻ ርምጃ ያጠፋው ደርግ በተማሪዎች ንቅናቄ ያበበውን ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል በጭካኔ ዘመተበት። በአንድ ወቅት መጻሕፍትን ሰብስቦ ለዚያውም በወመዘክር ግቢ እስከማቃጠል የደረሰው መንግሥት፣ የማሰብ ነጻነትን በወንጀልነት ከፈረጀ በኋላ የንድፈ-ሀሳባዊ ከርከር ማዕከላት የነበሩት ከተሞች በፍርሀት ተዋጡ። የማሰብ ነጻነታቸውን ተጠቅመው ለኢትዮጵያ መልካም ያሰቡ ወጣቶች እሥር ቤቶችን አጣበቡ። ይህን ተከትሎ ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕልን የመጠበቅና የማሳደግ ዕድል ከከተሞች ይልቅ በትጥቅ ትግል ነጻ ወደሚወጡ ገጠሮች ተዛወረ። ትጥቅ ትግል የማካሔድ አቅጣጫን የመረጡ ድርጅቶች በማይደፈሩ ተራራማ ነጻ መሬቶች ውስጥ የንባብ፣ የንድፈ-ሀሳባዊ ጥናትና የአስተሳሰብ ግንባታ ዕድሎች መስፋት ጀመሩ።

በዚህ ለመጠቀም ይችሉ ከነበሩት ድርጅቶች ሁሉ የተሻለ ዕድል ወይም ችሎታ የነበራቸው ኢህአፓና ሕወሓት ነበሩ። ሁለቱም የትጥቅ ትግላቸውን ትግራይ ላይ የጀመሩ ሲሆን ኢህአፓ ወደጐንደርና ወሎ በመስፋፋት ተጨማሪ ነጻ መሬቶችን ፈጥሮ ነበር። ነገር ግን የኢህአፓ አመራር ትግሉን በብቃት ለመምራት ያስችለው የነበረውን የህዝብ ወገናዊነትና የጥናትና ከርከር ባሕል አዳከመው። በተጨማሪም በፈጸማቸው ስትራቴጂያዊ ስህተቶች ምክንያት በየወቅቱ በአባላቱ ይነሱ የነበሩ ልዩነቶችን በአስተዳደራዊ መንገድ ለመፍታት ቅድሚያ መስጠት ጀመረ። የድርጅቱ መሥራቾች የነበሩት ብርሃነ መስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ ያራመዱትን የልዩነት ሀሳብ ሳይቀር ከአባላት በተደበቀ መንገድ ለመፍታት ተንቀሳቀሰ። በመጨረሻም ሁለቱን በማሰርና ጌታቸው ማሩን ደግሞ በመግደል ያነሱዋቸውን ሀሳቦች ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ እርምጃ ለማፈን ሞከረ። እነጌታቸው ማሩ ያራመዱዋቸው ንድፈ-ሀሳባዊና ተግባራዊ የልዩነት ሀሳቦች ትክክልም ይሁኑ ስህተት በአስተዳደራዊ መንገድ መፈታት አልነበረባቸውም። ዛሬም ድረስ ሁለቱ ሰዎች ባነሱት ሀሳብ ላይ የተሟላ አስተያየት ለመስጠት የምንቸገረው ልዩነቱ ሀሳቦች በነጻነት መንፈስ በሚንሸራሸሩበትና እያንዳንዱ የተለየ ሓሳብ የሚያራምድ ሰው በሥስተኛ ወገን ወሬ ሳይሆን በራሱ ጽሑፍና አንደበት የሚሟገትበት ዕድል በመዘጋቱ ነው። የኢህአፓ መሪዎች ሰዎችን በመግደል ሀሳቦችን መግደል እንደሚችሉ አድርገው በመቁጠር ዴሞክራሲውን ማጥበባቸው ግን ሌላው ቀርቶ ለራሱ ለኢህአፓም የሚበጅ አልሆነም። ስለዚህ በኢህአፓ ውስጥ የተከሰቱ ልዩነቶች የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ማዳበር ጀምረውት በነበረው የንድፈ-ሀሳባዊ ከርከር ባሕል በመመራት የድርጅቱን ፖለቲካዊ ብቃት በሚያጠናክር አኳኋን እንዲፈቱ መደረግ ነበረባቸው።

እንደገናም በ1969 ዓ.ም አሲምባ በነበረው ሠራዊት ዘንድ የተቀሰቀሰውን የእርማት እንቅስቃሴ ተከትሎ የኢህአፓ አመራር ለሁለተኛ ጊዜ ጥያቄ ያነሡ ታጋዮቹን በአንጀኘነት ፈርጆ መምታትን መረጠ፡፡ በሠራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት የነበራቸውንና በአገር ውስጥና በውጭ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ንቁ ተዋናይ የነበሩትን እነ ይርጋ ተሰማና (የትግል ስሙ መዝሙር)፣ ውብሸት መኮነንን (የትግል ስሙ አቡበከር) ጨምሮ አሥራ አንድ ታጋዮችን በግፍ እስከ መግደል ደረሰ፡፡ የኢህአፓ አመራር እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ አንግቦ የተነሳውን የበለሳው ንቅናቄ አባላትና መሪዎች በአንጀኘነት ፈርጆ ለመምታት ሞከረ፡፡ ይህ ንቅናቄ በኋላ ኢህዴንን የመሠረቱ ታጋዮች የተሰባሰቡበት ሲሆን፣ በኢህአፓ ውስጥ እያለ የፓርቲው አመራር የፈጸማቸውን ስህተቶች ለማረም የሚያስችል የእርማት ንቅናቄ እንዲካሔድ ከመጠየቅ ውጭ ሌላ የፖለቲካ ወንጀል አልፈጸመም። የኢህአፓ አመራር ይህን ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ በማሰርና በመግደል ሊፈታው ከሞከረ በኋላ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተጀመረውን ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል ለመጠበቅና ለማጐልበት የሚችልበት ዕድል አከተመ፡፡ ይህ ዕድል እንደአዲስ ሊሞከር ይችል የነበረው ከኢህአፓ አፈንግጦ በወጣውና በኋላም የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኢህዴን የአሁኑ ብአዴን/ በሚል ሥያሜ ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ በተደራጀው አዲስ ንቅናቄ ሆነ፡፡

በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተጀመረውን ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል በትጥቅ ትግል ነጻ በወጣው መሬት ላይ ኮትኩቶ የማሳደግ ሌላው ዕድል የተገኘው በህዝባዊ ወያነ ሐርነት ትግራይ / ሕወሓት/ ነበር፡፡ ሕወሓት ገና ከመጀመሪያው በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ንቁ ተዋንያን በነበሩ ሰዎች የተመሠረተ ድርጅት ነው፡፡ በመሆኑም በንቅናቄው ውስጥ የተጀመረውን ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል የሚያውቅና ይህንኑ ለማስቀጠል ዕድሉ የነበረው ድርጅት ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በድርጅቱ የመጀመሪያ ዓመታት ቁልፍ የአመራር ኃላፊነትን ከጨበጡት ሰዎች እንደአረጋዊ በርሔ ዓይነቶቹ ከንድፈ-ሀሳብ ለተነጠለ ተግባር የላቀ ትኩረት የሚሰጡ ነበሩ፡፡ በዚህ ላይ ድርጅቱ ከብዙ ኃይሎች ጋር እየተፋለመ ሕልውናውን ለማስጠበቅ የተገደደ ድርጅት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ሕወሓት እስከ 1970ዎቹ መጀመሪያ ድረስ በከባድ ተግባራዊ እንቅስቃሴና ተነቃናቂነት የተጠመደ ድርጅት ነበር፡፡

ይህም ሆኖ ሕወሓት ገና ከማለዳው በንድፈ-ሀሳባዊ መስክ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ሰዎችን ፈጥሯል፡፡ ሁኔታው በፈቀደው ልክ በድርጅቱ ነጻ መሬት ውስጥ የተገኙ መጻሕፍት እየተጠኑ፣ የህዝባዊ ትግሉ አቅጣጫና አካሔድ እየተተነተነ ከዚህ ቀጥሎ የሚደረስባቸውን ንድፈ-ሀሳባዊ ድምዳሜዎች የተግባር መመሪያው ሲያደርግም ነበር፡፡ ይህ ሂደት ቀስ በቀስ የተቀመሩ የትግል ሀሳቦች እንዲበራከቱና የተግባር መመሪያ እንዲሆኑ ከማድረግ ባሻገር የንድፈ-ሀሳባዊ ጥናትና ግንባታ ፋይዳ ትልቅ እንደሆነ ለማስገንዘብ በር ከፈተ፡፡ ድርጅቱ ንድፈ-ሀሳብ የማይመራው ማንኛውም ንቅናቄ መክሸፉ እንደማይቀር ተገንዝቦ ለንድፈ-ሀሳብ ግንባታ የላቀ

ትኩረት እየሰጠ ራሱን በራሱ እንዲገነባም አስቻለው::

ሕወሓት ለንድፈ-ሀሳባዊ ግንባታ በሰጠው ትኩረት ከፍተኛ አመራሩን ብቻ ሳይሆን በየደረጃው የሚገኘውን አመራርም ማብቃት እንዳለበት በማመን ከ1970ዎቹ ጀምሮ ሰፋፊና ተከታታይ ሥልጠናዎችን አዘጋጀ:: በእነዚህ የሥልጠና መድረኮች የልዩ ልዩ አገሮች አብዮታዊ ንቅናቄዎች ተሞክሮ ተጠንቶና ተቀምሮ እየቀረበ ክርክሮች ይካሔድበት ጀመር:: በኢትዮጵያ ከተሞች የጠፋው የንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል በትግል ነጻ በወጡት የትግራይ ገጠሮች እንደ አዲስ ተጠናክሮ መገንባት ቀጠለ:: ይህም በኢህአዴግ ተጠብቆ ለቆየው ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል ጠንካራ መሠረት ሆኖ አገለገለ::

በ1970ዎቹ መጀመሪያ ከኢህአፓ ተገንጥሎ የራሱን አዲስ ድርጅት ለመመስረት ወደ ትግራይ ያቀናው የኢህዴን መስራች ኃይል ትግራይ እንደገባ ያገኘው አዲስ እውነታ በትግራይ ነጻ መሬት ልዩ ልዩ የህዝባዊ ትግል ጥያቄዎች እየተነሱ የሞቀ ክርክር የሚካሔድባቸው መሆኑን ነበር:: ይህ ኃይል በኢህአፓ ውስጥ ሆኖ ሲታገል በነበረበት ወቅት በተገኘው መጽሐፍ በመታገዝ የራሱን ፖለቲካዊ ሕይወት ለመገንባት ከፍተኛ ፍላጐት የነበረው ነው:: ከኢህአፓ ጋር የፈጠረው ልዩነት እየሰፋ መሔዱን ተከትሎ ደግሞ የፓርቲውን ስህተቶች እያነሳ በውስጡ ሰፊ ክርክር በማካሔድ ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕሉ እንዳይዳከም ይልቁንም ተጠብቆ እንዲቀጥል ጥረት አድርጓል:: ኢህአፓ በስትራቴጂና ታክቲክ ደረጃ የሠራቸውን ስሕተቶች በጥልቀት መርምሮ አቋም በመውሰድ በበሰለ አስተሳሰብ ከድርጅቱ እስከመለየት የደረሰም ነበር:: በ1972 ዓ.ም. ከምሥራቅ ጐንደር አፈግፍጐ ወደትግራይ ሲያቀና በሕወሓት ውስጥ መልካም የሚባል ንድፈ-ሀሳባዊ እንቅስቃሴ እንደሚካሔድ ተገነዘበ:: ይሕም በኢህአፓ አመራር ድክመት ምክንያት ተፈጥሮ የነበረውን ከፍተት ለመሙላት በጣም የተሻለ ዕድል ስለፈጠረለት የንቅናቄው አባላት ሕወሓትን በአጭር ጊዜ ውስጥ በዝርዝር ለማጥናትና ለማወቅ ቻሉ:: ከዚህም አልፎ በተፈጠሩ አጋጣሚዎች ሁሉ በንድፈ-ሀሳባዊ ክርክሮች ውስጥ መሳተፍ ጀመሩ:: ሕወሓት ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ያጠራቸውን ሀሳቦች በአጭር ጊዜ በመገንዘብና በየክርክሮቹ በመሳተፍ ከዚህም አልፎ የራሱን ጥናቶች በቀጣይነት በማካሔድ የኢህዴን መሥራች ኃይል ለንድፈ-ሀሳባዊ ባሕሉ መጐልበት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ጀመረ:: ሕወሓትና ኢህዴን እጅ ለእጅ ተያይዘው በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ መሠረቱ የተጣለውን ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል ወደአዲስ ከፍታ ለማውጣት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ፈጠሩ::

በዚህ የንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል ግንባታ ሂደት ታጋይ መለስ ዜናዊ የተጫወተው ሚና በማንኛውም መስፈርት ልዩ ነበር:: ከዩኒቨርሲቲ የትምሕርት ጊዜው ጀምሮ ለንድፈ-ሀሳባዊ ጥናትና ምርምር ልዩ ትኩረት ይሰጥ የነበረው መለስ፣ በትጥቅ ትግሉ ወቅትም ይህንኑ ይበልጥ አጠናክሮ ገፍቶበታል:: የመለስና ጓዶቹ ምርምር በዋነኛነት ከላሲካል በሚባሉ ንድፈ-ሀሳባዊ

ሥራዎች ላይ የተመሠረተ ነበር። በተለይ ደግሞ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የካፒታሊስት ሥርዓትን ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ በማጥናትና በመተንተን ለትክክለኛ የትግል አቅጣጫዎች ፈር የቀደደውን የማርክስና ደቀ መዛሙርቱን ሥራዎች በጥልቀት በማጥናትና በመገንዘብ መሠረታዊ የሆነውን ንድፈ-ሀሳባዊ ትጥቅ ለመጨበጥ ያስቻለ ነበር። መለስ ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ በመነሳት የአውሮፓ፣ የሩስያና የምሥራቅ እስያ ህዝቦችን ትግሎች በጥልቀት አጥንቷል። ከማርክስ እስከኤንግልስ፣ ከሌኒን እስከአንቶንዮ ግራምሺና ማኦዜዶንግ ድረስ የነበሩ ንድፈ-ሀሳባዊ ሥራዎችና የህዝባዊ ንቅናቄ ተግባራዊ ተሞክሮዎችን ልቅም አድርጐ በማንበብ ጥልቅ ምርምሮችን አካሂዷል። ይህን ጥናት መሠረት ያደረጉና በየምዕራፉ የተካሔደውን ትግል በውጤታማነት ለመምራት ያስቻሉ የራሱን ንድፈ-ሀሳባዊ ሥራዎች አምርቷል። በእነዚህ ላይ የተመሠረቱ ተከታታይ ሥልጠናዎችን በመስጠት በኢህአዴግ ውስጥ ጠንካራ የሀሳብና የትግል አንድነት ለመፍጠርም ልዩ ሚና ተጫውቷል።

ይህ ንድፈ-ሀሳባዊ ሥራ ደረጃ በደረጃ እየተጠናከረ ሔዶ ከ1977 ዓ.ም እስከ 1980 ድረስ በነበሩት ዓመታት የመጀመሪያውን ወሳኝ የአስተሳሰብ እመርታ ለማስመዝገብ አስቻለ። ይህ ሂደት በዋነኛነት "የመሥመር ማጥራት መድረክ" በሚል ይታወቅ የነበረ ሲሆን፣ ዋነኛ ባሕርይውም በፖለቲካ ጥናትና ምርምር፣ በክርክርና በማያቋርጥ የሀሳብ ትግል የጠራ የትግል አቅጣጫ የተኘደፈበት መሆኑ ነው። በዚህ የመሥመር ማጥራት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ለሚካሔደው ህዝባዊ ትግል ሳይንሳዊ አመራር ለመስጠት ያስቻሉ የዳበሩ አስተሳሰቦችን ለመጐናጸፍ ተቻለ። ብቁ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ስትራቴጂና ታክቲኮችም ተነደፉ። በእነዚህ ቀመሮች ዙሪያ በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ታጋዮች ሥልጠና ተሰጠ። የህወሓትንና የኢህዴን አባላት በአዳዲሶቹ አስተሳሰቦች እየተገነቡ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ የብስለት ደረጃ ላይ ደረሱ። ከአርሶ አደር የሠራዊት አባላት እስከ መለስተኛና ከፍተኛ ምሁር ድረስ፣ ከሚሊሻዎች እስከ ህዝባዊ ሽንጐዎችና የብዙኀን ማኅበራት አባላት ድረስ የነበሩት የትግሉ ደጀኖች ሁሉ በዚሁ ማዕቀፍ ለዳበረ ንቃት በቁ። ይህም ረኸሙንና መራራውን የትጥቅ ትግል ጊዜ የደርግን እድሜ ለማሳጠር በር ከፈተ።

በኢህአዴግ አመራርና በድርጅቱ ውስጥ የተገነባው ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል በትጥቅ ትግሉ ዘመን ብቻ የታጠረ አልነበረም። ያዝ ለቀቅ ያልተለየው ቢሆንም ከትጥቅ ትግሉ በኋላም ቀጥሏል። ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ በትጥቅ ትግልና በፖለቲካዊ ሥራ ብቻ በተጠመደባቸው የቅድመ 83 ዓመታት ሌላ ሥራ ባለመኖሩ ምክንያት ታጋዩ መላ ጊዜውን የሚያሳልፈው አንድም በመዋጋት አሊያም በፖለቲካዊ ጥናቶችና ከርከሮች ላይ ነበር። ከትጥቅ ትግሉ ማብቃት በኋላ ደግሞ የዕለት ተዕለት ዘርፈ-ብዙ አገር የማስተዳደር ሥራ በትግልና በፖለቲካ ሕይወት ላይ የራሱን ተፅዕኖ ያሳረፈ ቢሆንም፣ ይህንኑ ጠብቆ ለማቆየት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ በቆየባቸው በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት በራሱ በመለስ ዜናዊ ልዩ ትኩረት

የተሰጠውና በተለይ በምሥራቅ እስያ አገሮች ላይ ያተኮረ ሰፊ ጥናት ተከናውኗል። ይህም ሆኖ በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት በአንድ በኩል የእለት ተእለት ተግባራዊ ሥራው ጫና እየበዛ በመሔዱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሥልጣን ላይ ከነበረው ኃይል መካከል ትንሽ የማይባል የአመራር አባል አላግባብ በመጠቀም ዝንባሌ እየተዋጠ መሔድ በመጀመሩ የንድፈ-ሀሳባዊ ባህሉ ደረጃ በደረጃ መዳከም ጀምሮ ነበር። የንድፈ-ሀሳባዊ ባህሉ በ1993 ከተካሔደው የተሃድሶ ንቅናቄ ማግስት እንደገና እስኪያንሰራራ ድረስ ከ80ዎቹ መጨረሻ ዓመታት ጀምሮ ጉልህ የመዳከም አዝማሚያ ታይቶበታል።

ንድፈ-ሀሳባዊ ባሕል በተለይ ጥራት ያለው አስተሳሰብ ለማዳበር የሚያስችል ከሆነ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ አንድን ትግል ከማንኛውም ዓይነት የዘፈቀደና የደመ ነፍስ ጉዞ ነጻ የማድረግ ዕድል አለው። ነገሮችን ከመሠረታዊ የተፈጥሮና የሕብረተሰብ ሕግጋት በመነሳት ለመተንተንና ለመገንዘብ ያስችላል። የተጨባጩን እውነታ ይዘትና መልክ ብቻ ሳይሆን የወደፊት አዝማሚያዎችን በትክክል ለመገንዘብ ያበቃል። በትግሉ ሂደት አገርና ህዝብን የሚጠቅሙ ዕድሎች እንዲሰፉ፣ በአንጻሩ ደግሞ ጐጂ አዝማሚያዎች እንዲቀንሱና እንዲወገዱ ለማድረግ ያስችላል። በአንጻሩ ደግሞ ከንድፈ-ሀሳባዊ ብቃት ውጭ በዘፈቀደ መራመድ የሚያዝ የሚጨበጥ አሳጥቶ በሁኔታዎች እየተገፋ ወይም እየተጐተተ መሔድን ብቻ ያስከትላል። በተለይ የራሳቸውን ጥቅሞች ለይተው ይህንኑ በዓለም ዙሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚንቀሳቀሱት የገበያ አከራሪ ኃይሎች በኩል ለሚመጣው ከባድ ርዕዮተ-ዓለማዊ ጥቃት በቀላሉ ተጋላጭ ያደርጋል። የፖሊሲ ነጻነትን አሳልፎ መስጠትም አይቀሬ ይሆናል። በኢህአዴግ የተመራው ትግል የአገሪቱን የፖሊሲ ነጻነት አስከብሮ ለውጤት የበቃው በዚህ መልክ ከምንም ነገር በላይ በጠራ ንድፈ-ሀሳብና በህዝባዊ ወገንተኝነት መንፈስ በመመራቱ ነው።

በየትኛውም አገር የፖሊሲ ነጻነትን ማስከበር አስፈላጊ የሚሆነው በቅድሚያ የአገሬው ህዝብ በአገሩ መሬት ላይ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤት ሆኖ በሚመቸውና በሚጠቅመው ፖሊሲ እየተመራ ሕይወቱን እንዲመራና እንዲለውጥ ለማድረግ ነው። በኢትዮጵያም እንደዚሁ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፖሊሲ ነጻነትን በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተው ለውጥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በመጀመርና በዚሁ ላይ በመተማመን ሊፈጸም የሚገባው ነበር። በተመሳሳይ መልኩ በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስክ የህዝቡን መብትና ጥቅም ማዕከል አድርጐ መካሔድ ነበረበት። በአገር ውስጥና በውጭ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያንን መብትና ጥቅሞች ማዕከል በማድረግ ለፖሊሲ ነጻነት መካሔድ የነበረበት ትግል በተግባር እንዴት እንደተካሔደና የት እንደደረሰ፣ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በልዩ ልዩ መስኮች የተካሔደውን ትግልና የመጣውን ለውጥ በመመልከት ለመመዘን ይቻላል።

ምዕራፍ ሦስት

ለመሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ የተካሄደው ትግል፣

በአገራችን ህዝቡ በገዥዎች የተነጠቀ መብቱን ለማስመለስና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ያካሔደው ትግል ዘመናትን ያስቆጠረ ነው፡፡ ይህ ትግል አብዛኛውን ጊዜ "ከፈጣሪ የተቀባን ነን" የሚሉ ነገስታትና በጠመንጃ ተማምነው ሥልጣን የያዙት ወታደሮች ከላይ፣ ህዝቡ ደግሞ ከታች ሆነው የተካሔደ ትግል ነበር፡፡ ወታደራዊው አምባገነን መንግሥት በ1983 ዓ.ም ሲወገድ፣ በአንድ በኩል ከላይ መንግሥታዊ ሥልጣን በመያዝ፣ በሌላ በኩል ብዙኃኑ ደግሞ ህዝቡ ከታች ሆነው በንቃት በሚያካሂዱት ትግል ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ የሚያስችል እጅግ የተመቸ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

ኢህአዴግ በ1983 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ባካሔደው 1ኛ ድርጅታዊ ጉባዔው ወደዚህ የዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለመሸጋገር ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ለሁለትና ሦስት ዓመታት የሚቆይ የሽግግር መንግሥትና ሂደት እንዲኖር ለማድረግም ወስኖ ነበር። ሂደቱ ራሱን በቻለ የሽግግር ወቅት ዴሞክራሲያዊ ቻርተር የሚመራ እንዲሆንና ይሕም ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማኅበራት በሚሳተፉበት ኮንፈረንስ ተመክሮበት ከፀደቀ በኋላ የሽግግሩ መንግሥት መመሪያ እንዲሆን ጥረት መደረግ እንዳለበት ታመነበት፡፡

ኮንፈረንሱም ሆነ የሽግግር መንግሥቱ በአሳታፊነት እንጂ በአግላይነት መርሕ የማይመሩ መሆን እንዳለባቸው፣ ስለዚህም ደግሞ ዓላማቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ ውድድር ለማሳካት የሚጥሩ ድርጅቶችን ሁሉ የሚያሳትፍ መሆን እንዳለበትም ታመነበት፡፡ በአንጻሩ የትጥቅ ትግልን ዋነኛ አማራጭ አድርገው እየቀጠሉ በሽግግሩ ሂደት መሳተፍ እንፈልጋለን ለሚሉት ደግሞ ሁለት አማራጭ ይዞ የመግባት ዕድል እንዳይኖራቸው ተደረገ፡፡ ከዚህ በመነሳት የሂደቱ አካል መሆን ከፈለጉ ትጥቅ ትግሉን እንዲተው፣ ትጥቅ ትግሉን አንተውም ካሉ የሽግግሩ ሂደት አካል ሊሆኑ እንደማይችሉ የሚያረጋግጥ አቅጣጫ ተቀመጠ፡፡ የሽግግሩ መንግሥት በኮንፈረንሱ እስኪመሠረት ድረስ ደግሞ ኢህአዴግ ደርግን ካስወገደ በኋላ በብቸኝነት ሥልጣን ላይ የሚቆየው ለአንድ ወር ብቻ እንዲሆን ተወሰነ፡፡ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ከመግባቱ በፊት ያስቀመጣቸው እነዚህ መሠረታዊ አቅጣጫዎች ድርጅቱ በከፍተኛ ዲሲፕሊን ተገዝቶ ተግባራዊ ያደረጋቸው ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሂደቱ እንዲህ ቀላል አልነበረም፡፡

የሽግግሩ መንግሥት ከመመሥረቱ በፊት ኢህአዴግ በእቅዱና በገባው ቃል መሠረት ለአንድ ወር ብቻ የሚቆይ ጊዜያዊ መንግሥት አደራጀ፡፡ የዚህ መንግሥት ዋነኛ ተልዕኮ ደግሞ የሽግግሩን መንግሥት ለመመሥረት ለሚጠራው ኮንፈረንስ የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ነበር። በእርግጥ ወቅቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የደርግ ሠራዊትና ትጥቅ በመላ አገሪቱ ተበትኖ የሠላምና መረጋጋት ጦስ ሊሆን የሚችልበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ አንድ ወር በለውጡ ያልተደሰቱ አንዳንድ ወገኖች የአመጽ መልክ የነበራቸው ተደጋጋሚ ሰልፎች በማካሔድ አገር እንዳይረጋጋ ለማድረግ የሚሞክሩበትና ከአዲሱ መንግሥት ጋር ወደቀጥተኛ ግጭት ያመሩበትም ነበር። አዲስ አበባ ውስጥ ተደብቀው የነበሩ አንዳንድ የደርግ ሠራዊት አዛዦች ባካሔዱት የሸንሔው ፍንዳታ በተቀሰቀሰው ከባድ ሥጋት ትንሽ በማይባል የሕብረተሰብ ክፍል ዘንድ ሂደቱ በጥሩ መንገድ ሊቋጭ ስለመቻሉም እርግጠኛነት አልነበረም፡፡

ይህን የተገነዘበው ኢህአዴግ በዚህች የአንድ ወር የሥልጣን ቆይታው ከጊዜ ጋር እየተሻማ በደርግ የግፍ አገዛዝ ተሳታፊ የነበሩና በሕግ ሊጠየቁ የሚገባቸው ባለሥልጣናት እየተለዩ በቁጥጥር ስር እንዲወሉ ማድረግ ጀመረ፡፡ የተበተነውን የቀድሞ ወታደር በመመዝገብ ወደ ሕብረተሰቡ ገብቶ እንዲቋቋም ተፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አካሔደ፡፡ ከዚህ ጐን ለጐን የሽግግሩ መንግሥት ከመመስረቱ በፊት በነበረችው አንድ ወር ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ልዩ ወቅታዊ ተፈላጊነት የነበራቸውን ተጨማሪ ፖለቲካዊ እርምጃዎች በመውሰድ የፖለቲካ አስረኞች እንዲፈቱ አደረገ፡፡ ሀሳብን በነጻ በመግለጽ መብት ላይ ተጥሎ የነበረውን የቅድመ ምርመራ (ሳንሱር) ግዴታና ገደብ አነሳ፡፡ ብዙም ሳይቆይ "ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት በኋላ መግባት መውጣት አይቻልም" ይል የነበረውን የሰዓት እላፊ ገደብ ሕግ ሙሉ በሙሉ ሽሮ የመንቀሳቀስ መብትን አስከበረ፡፡ ዜጐች በየትኛውም ቦታና ጊዜ ያለጠያቂ ለመንቀሳቀስ ያላቸው ሰብዓዊ መብት እንዲከበርና ተግባራዊ እንዲሆን አደረገ፡፡ ከኮንፈረንሱ በፊት የአሮምኛና የትግርኛ የቴሌቪዥን ሥርጭቶች እንዲጀምሩ በማድረግ አዲስ ዘመን መጀመሩን አበሰረ።

ኢህአዴግ እነዚህን እርምጃዎች የወሰደው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ በዘላቂነት በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ እንደሚገነባ ካለመገንዘብ፣ ወይም ደግሞ የዴሞክራሲው ዋነኛና ከፍተኛ መገለጫዎች ስለሆኑ አልነበረም፡፡ በእነዚህ እርምጃዎች በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ህዝቦች መለስተኛም ቢሆኑ አንዳንድ የዴሞክራሲ ጸጋዎችን እንዲቋደሱ ማድረግ በሽግግሩ ሂደት ለበለጠ ዴሞክራሲያዊ ውጤት ተግተው እንዲታገሉ ያስችላል ብሎ ስላመነ ነበር፡፡ በሌላ በኩል የሽግግሩ ሂደት እንዴትና በምን አግባብ እንደሚፈጸም የራሱ እቅድ የነበረው ቢሆንም፣ መድረኩ ልዩ ልዩ ኃይሎች የሚተውኑበት ስለነበር ለዴሞክራሲ የሚካሔደውን ትግል የማጐልበት ፋይዳ

ያላቸውን ምልከቶች ገና ከማለዳው ማስተላለፍ ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘው ነበር።

ለአንድ ወር በቆየችው የጊዜያዊ መንግሥት ሥልጣኑ ኢህአዴግ ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን ተልዕኮዎች በጥንቃቄ ፈጽሟል። የተልዕኮው ወሳኝ ክፍል የነበረውን የሽግግር ሂደት በተስተካከለ አቅጣጫ ለማስፈጸም ደግሞ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ኃይሎችን በመጋበዝ የሽግግሩ መንግሥት መሥራች ኮንፈረንስ ሰኔ 24 ቀን 1983 ዓ.ም. ተጠራ። ኮንፈረንሱ ከ28 የማያንሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማኅበራት የተሳተፉበት ነበር። በዚህ መድረክ ያልተሳተፉት አንጋፋ ድርጅቶች ትጥቅ ትግልን የመረጡትና የራሳቸው የተለየ አማራጭ የሽግግር ፕሮግራም ይዘው የቀረቡት ኢህአፓና መኢሶን ብቻ ነበሩ። በተጨማሪም ከ30 ዓመታት የትጥቅ ትግል በኋላ ኤርትራን ከደርግ ቁጥጥር ነጻ ያደረገው የኤርትራው ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ በመሪዎቹ አማካይነት ተወክሎ ያለድምጽ እንዲሳተፍ ተደርጓል። ኮንፈረንሱ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ የሚኖረው የሽግግር መድረክ የሚመራበት ቻርተር ይዘት ምን መምሰል እንዳለበትና የሽግግር መንግሥቱ በሚቋቋምበት ሥርዓት ላይ የሚመክርበት ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በራሱ ትግል ነጻ የወጣው የኤርትራ ህዝብ በሕጋዊ ሪፈረንደም ፍላጐቱ የሚታወቅበትን ሥርዓት የሚወስን ነበር። የኤርትራ መሪዎች በዚህ ኮንፈረንስ ቢሳተፉም፣ ኤርትራን በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ብቻ የተወሰነ ሀሳብ ከማቅረብ የዘለለ ተሳትፎ አልነበራቸውም። ይህም በሁሉቱም ወገን የኢትዮጵያ ጉዳይ እንደማይመለከታቸው ስለታመነበት ነበር።

በዚህ መሠረት ለሽግግሩ ወቅት ይበጃል ተብሎ በኢህአዴግ ተዘጋጅቶ የቀረበው ረቂቅ ቻርተር ለውይይት ተዘረጋ። ቻርተሩ እጥር ምጥን ያለ ቢሆንም መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ ባሕርይና ይዘት ነበረው። በተጨማሪም ፈጽሞ የማይቀራረብ የፖሊሲ አቅጣጫ ከተያዘበት ከመሬት ጥያቄ በመለስ በሽግግሩ መድረክ በሁሉም ፓርቲዎች ታምኖባቸው ሊተገበሩ የሚችሉ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ አንቀጾችን የያዘ ነበር። በመሬት ጥያቄ ላይ ግን በአንድ በኩል እንደ ኢህአዴግ ያሉ "መሬት ሊሸጥ ሊለወጥ የማይገባ የአገር ሀብት መሆን አለበት" የሚሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ኢዴህ ያሉ "መሬት የግል ይዞታ ሆኖ ሊሸጥ ሊለወጥ መቻል አለበት" የሚል አቋም ባላቸው ድርጅቶች መካከል መሠረታዊ ልዩነት የተያዘበት ነበር። የኮንፈረንሱ ሊቀ-መንበር በመሆን ያገለግል የነበረውና ይህን ልዩነት በግልጽ የሚገነዘበው መለስ "ልዩነቱ በሕገ-መንግሥት ተወስኖ እስኪፈታ ድረስ የደርግ የመሬት ይዞታ እንደተጠበቀ ቢቆይ ይሻላል" በማለት ያቀረበው የማሰማሚያ ሀሳብ ተቀባይነት በማግኘቱ ይህ በቻርተሩ እንዲሰፍር ተደረገ። መለስ ያቀረበው ይህ ሀሳብ በኢህአዴግና በሌሎች ፓርቲዎች መካከል በቀላሉ መተማመንን የፈጠረ ነበር።

የሽግግሩ ኮንፈረንስ የኤርትራ ጥያቄ ስለሚፈታበት አቅጣጫም ኢህአዴግ ያቀረበውን መነሻ ሀሳብ መሠረት በማድረግ መክሮበታል። የቀረበው የመፍትሔ ሀሳብም "የኤርትራ

መሪዎች ነጻነታችንን በኃይል ነጥቀናል በማለት ሂደቱ እንዳበቃለት ከመቁጠር ተቆጥበው፣ የኤርትራ ህዝብ ፍላጐቱን በሕጋዊ ህዝበ-ውሳኔ እንዲያሳውቅ በማድረግ ጥያቄው የመጨረሻ እልባት ሊሰጠው ይገባል" የሚል ነበር:: ይህም ሪፍረንደሙ ህዝቡ በተጋጋለ ስሜት ውስጥ በገባበት ወቅት በጥድፊያ ከሚካሔድ በሰከነ ሁኔታ አመዛዝኖ አቋም ከወሰደ በኋላ ቢፈጸም የተሻለ መተማመን ይፈጥራል ተብሎ ስለታመነበት ነው። መፍትሔው የኢትዮጵያን ህዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን የኤርትራን ህዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች በህዝበ ውሳኔው አፈጻጸም ላይ ለማግባባት ዕድል የሚሰጥ ነበር:: በመሆኑም፣ የኤርትራውን ህዝባዊ ግንባር ዋና ጸሐፊ ጨምሮ፣ ሀሳቡ በሁሉም ወገን ተቀባይነት በማግኘቱ የሽግግሩ ወቅት አንድ የስምምነት ሀሳብ ሊሆን ቻለ:: ቻርተሩ በሁሉም ተሳታፊዎች የሞቀ ከርከር ከተካሔደበትና ከፀደቀ በኋላ የሽግግሩ ወቅት የተግባር መመሪያ እንዲሆን ተደረገ:: ለአንድ ወር በቆየው የኢህአዴግ ጊዜያዊ መንግሥት ምትክ ደግሞ የሽግግሩ ወቅት መንግሥት ተመሠረተ::

የሽግግሩ መንግሥት በተቋቋመ ማግሥት የተወካዮች ምክር ቤቱ ከፖርቲዎች በተውጣጡ ተወካዮች ተሰየመ:: በምክር ቤቱ ከነበሩት ሰባ ሁለት ወንበሮች ሠላሳ ሁለቱ ለኢህአዴግ ሲደለደሉ ሕወሓት፣ ኢህዴንና ኦህዴድ እያንዳንዳቸው አሥር አሥር ወንበሮች ደረሳቸው:: የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አንድነት ንቅናቄ /ኢዴመአን/ ደግሞ ሁለት ወንበሮች አገኘ። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አሥራ ሁለት ወንበሮች ሲደርሰው፣ የቀሩትን ደግሞ ልዩ ልዩ ፓርቲዎችና የሠራተኛና የምሁራን ተወካዮች እንዲከፋፈሉዋቸው ተደረገ:: የሽግግሩን መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤትም፣ አቶ መለስ ከኢህአዴግ በሊቀ-መንበርነት፣ ዶከተር ፈቃደ ገዳሙ ከኢዴቅ በምክትል ሊቀ-መንበርነት፣ እንዲሁም አቶ ተስፋዬ ሓቢሶ ከከምባታ ህዝቦች ድርጅት በጸሐፊነት የሚያስተባብሩት ተቋም ነበር።

ከዚህ ጐን ለጐን የመንግሥት ሚኒስትሮች ምክር ቤትም የሁሉንም ፓርቲዎች ተሳትፎ ባረጋገጠ አኳኋን ተዋቀረ:: ኢህአዴግ አቶ ታምራት ላይኔ ከያዙት የጠቅላይ ሚኒስትርነት ኃላፊነት ጋር የውጭ ጉዳይ፣ የመከላከያና የአገር ውስጥ ጉዳይ መሥሪያ ቤቶችን ሲመራ፣ አነግ ደግሞ የማስታወቂያ፣ የግብርናና ትምሕርት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን እንዲመራ ተደረገ:: ልዩ ልዩ የደቡብ ኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችም በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ እየተመደቡ እንዲያገለግሉ ተደረገ:: ዶከተር በየነ ጴጥሮስ ምክትል የትምሕርት ሚኒስትር ሆነው ተመደቡ:: የንግድና ኢንዱስትሪ፣ እንዲሁም ሌሎች መሥሪያ ቤቶችም እንደ አቶ አራጋው ጥሩነህና አቶ አሰፋ የመሳሰሉ ገለልተኛ ፕሮፌሽናሎች በሚኒስትርነት ተመደቡላቸው:: የሽግግሩ መንግሥት እስከ 1987 ዓ.ም አገራዊና ከልላዊ ምርጫ ድረስ በሁሉም መሥራች ድርጅቶች ተሳትፎ ሲቀጥል ከቆየ በኋላ፣ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር(አነግ) ከሽግግሩ መድረክ አቋርጦ በመውጣቱ የድርጅቱ ተወካዮች የነበራቸው ተሳትፎ እስከ1985 ዓ.ም ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ ብቻ የቀጠለ ነበር::

አገሪ በበሆነሩ ጊዴጥ ለጃኒጦ የሠሣበጥ ሁኔዖጥ ገበ በኒበኒ ዝበሆ ቢሪዖይ በሊጎነ አያ ነሠኤኣበ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ ገና ከማለዳው የገጠመውን ችግር በትንሹ ሊያመላክት ይችላል::

አነግ ከኤርትራ ግንባሮች ቀጥሎ የተቋቋመ አንጋፋ ድርጅት ቢሆንም፣ ደርግ እስኪወድቅ ድረስ ከሁለት ሺህ የማይበልጥ ተዋጊ ብቻ ነበረው። የራሴ የሚለው ትልቅ ነጻ መሬትም አልነበረውም:: ይሕም ሆኖ ከሌሎች የሽግግሩ ወቅት ተሳታፊ ድርጅቶች ከኢህአዴግ ቀጥሎ በተነጻጻሪ የተሻለ አቅም ነበረው:: አነግ ይህን አቅም ይዞ በኦሮሚያም ሆነ በኢትዮጵያ ብስለት ያለውና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ ይዞ የሚፋለም ድርጅት ቢሆን ኑሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ገንቢ ሚና ሊጫወት በበቃ ነበር:: ነገር ግን አነግ ይህን የማድረግ ፍላጐትም ችሎታም አልነበረውም:: ከዚህ ይልቅ ደርግ በወደቀ ማግሥት የተበተነውን ወታደርና ትጥቅ እያሳባሰበ በአጭር ጊዜ ወታደራዊ አቅሙን ወደሃያ ሺህ ገደማ አድርሶ በዚህ በመተማመን የመገንጠል ዓላማውን በኃይል ለማስፈጸም መዘጋጀት ጀመረ:: ይህም ሆኖ ከትጥቅ ትግሉ መጠናቀቅ በፊት የየራሳቸው ሠራዊት ገንብተው ለታገሉ ድርጅቶች እንደተደረገው ሁሉ፣ በአጭር ጊዜ አነግ ያሰባሰበው ሃያ ሺህ ያህል ወታደርም በሽግግር መንግሥቱ ሥምምነት መሠረት በካምፕ ውስጥ ተቀምጦ ቀለብ እየተሰፈረለት እንዲኖር ተደረገ::

የሽግግሩ ሂደት ጥቂት እንደቀጠለ ግን አነግ በባሌ ዞን በወተር አካባቢ በሰላማዊ ዜጐች ላይ ዘግናኝ እርምጃዎችን በመውሰድ የመጀመሪያውን ጥቃት በመሰንዘር የመገንጠል ዓላማውን ለማሳካት መንቀሳቀስ ጀመረ። ይህ ጉዳይ በወቅቱ በተወካዮች ምክር ቤት በተቋቋመ አጣሪ ኮሚቴ በተደረገ ምርምራ ተጣርቶ በርግጥም አነግ በህዝብ ላይ በተጨባጭ ግፍ እንደፈጸመ ተረጋግጦ ድርጅቱ ህዝቡን ይቅርታ እንዲጠይቅ ተወሰነበት:: በዚህ ሂደት በፓርላማ ውስጥ የነበሩት የአነግ መሪዎች ከብዙ ከርከር በኋላ ይህን በድምጽ ጭምር ተቀብለው በይፋ ይቅርታ ጠየቁ። ነገር ግን አነግ ብዙም ሳይቆይ ለነጻነት አበቃዋለሁ ከሚለው የኦሮሞ ብሔር የፈለቁ ወንድምና እህቶች ጨምሮ ከአገሪቱ ሌሎች ከፍሎች የመጡ ወጐኖችን በግፍ አሰቃይቶ ከገደለ በኋላ በደኖ በተባለ ቦታ ላይ ጉድጓድ ውስጥ ጨምሯቸው ተገኘ:: የቀይ ሽብር ሰቆቃና መንፈሳዊ ጥቃት ጨርሶ ባልጠፋበት በዚህ ወቅት፣ የአነግ መሪዎች ብዙ ህዝቦችን አደባልቀው በመግደል ጉድጓድ ውስጥ መከተታቸው፣ በመላ የአገሪቱ ህዝቦች ላይ ከፉ ትውስታ ቀስቅሶ በአነግ ላይ ከፍተኛ ውግዘት አስከተለ:: የአነግ መሪዎች በአንድ በኩል ውግዘቱን መቋቋም ሲሳናቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያሰባሰቡት ሃያ ሺህ የቀድሞ ወታደር ዓላማቸውን በትጥቅ ትግል ለማስፈጸም እንደሚያስችል አጉል መተማመን ላይ ሲደርሱ ሠራዊቱ ከካምፕ እንዲወጣ አደረጉ::

የአነግ ሠራዊት በመሪዎቹ የተሳሳተ እሳቤ ከካምፕ ወጥቶ ወደጫካ እንደሚገባ ከኢህአዴግ የተሰወረ አልነበረም:: የአነግ መሪዎች አዝማሚያና ፍላጐት አስቀድሞም ቢሆን ይታወቅ ነበርና ሠራዊቱ አንድ ቀን ከካምፕ እንደሚወጣ ለመገመት ከባድ አልነበረም::

በመሆኑም በኢህአዴግ በኩል በሽግግሩ መንግሥት ላይ መነሳቱ የማይቀረውን የአነግ ሠራዊት እንዴት መያዝ እንደሚቻልና እንደሚገባ ምክክር ይደረግበት ነበር፡፡ በዚህ ምክክር በአንድ በኩል "አነግ መሸፈቱ ስለማይቀር ይህን ኃይል በካምፕ ውስጥ እያለ ማጥቃት ይሻላል" የሚል፣ በሌላ በኩል ደግሞ "አነግ ካምፕ ውስጥ እያለ ፈጽሞ ጥቃት ሊደርስበት አይገባውም" የሚሉ አስተያየቶች ይንሸራሸሩ ነበር፡፡ አነግ ከካምፕ ሳይለቅ ጥቃት ሊሰነዘርበት ይገባዋል የሚሉት ጥቂቶች ቢሆኑም፣ "ድርጅቱ ወደሽምቅ ውጊያ ካመራ በኋላ ይህን ኃይል መቆጣጠር ያስቸግራል" የሚል መከራከሪያ ነበራቸው፡፡ በአንጻሩ "ካምፕ ውስጥ እያለ ልናጠቃው አይገባንም" የሚለው ወገን ደግሞ፣ "በአንድ በኩል ድርጅቱ የሠራው ስህተት በህዝብ ሳይታይና ሳይጋለጥ ጥቃት ቢሰነዘርበት አመኔታ የምናጣው እኛ እንሆናለን። በዚህ የተነሳም ከደርግ ጦርነት የተረፈው ወታደር እንደገና በሌላ ጦርነት ወደእልቂት እንዲያመራ ማድረግ የለብንም" የሚል አመክንዮ ነበረው፡፡ በእነዚህ ሀሳቦች ዙሪያ በተካሔደው የሀሳብ ትግል "አነግ ካምፕ ውስጥ እያለ ጥቃት ሊደርስበት አይገባም" የሚለው ሀሳብ የጋራ አቋም ሆኖ ተያዘ። የድርጅቱ ወታደሮችም ማንም ሳይነካቸው ካምፓቸውን ጥለው ወጡ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ራሱ አነግ ከሽግግሩ መንግሥት አቋርጦ መውጣቱን በይፋ አሳወቀ፡፡

የአነግ ሠራዊት ካምፑን ለቆ ወደየገጠሩ ከወጣ በኋላ ኢህአዴግ በየአካባቢው ለተቀመጡ የሠራዊት አባላት "አነግ ካልተኮሰባችሁ በስተቀር እንዳትተኩሱበት" የሚል ጥብቅ መመሪያ አስተላለፈ፡፡ ይህ መመሪያ አሁንም አነግ ሌላ ስህተት ካልሠራ በስተቀር ከሽግግሩ ሂደት ስለወጣ ብቻ ጥቃት ሊሰነዘርበት አይገባም ከሚል ሀሳብ የተነሳ ነው፡፡ ነገር ግን "ካልተኮሰባችሁ እንዳትተኩሱበት" የሚለው መመሪያ ለብዙ የሠራዊት አባላት በቀላሉ የሚዋጥ አልሆነም፡፡ ጥቂት የማይባሉ የሠራዊት አባላት "ኢህአዴግ እንዴት እንዲህ ዓይነት የእብድ መመሪያ ያወጣል፣ እኛ እስከንሞት ድረስ ነወይ የሚጠብቀው" ማለትም ጀመሩ፡፡ ነገር ግን የአገራችንን ሰላም ላለማደፍረስ፣ የዜጐችን እልቂት ለማስቀረትና እዚያው ሳለም የአነግን ምንነት ለማሳዬት መመሪያው በጥብቅ ዲስፕሊን ተግባራዊ መደረጉ አማራጭ እንደሌለው ኢህአዴግ አመነበት፡፡ ታጋዮቹንም በከባድ ጥረት እዚህ አቋም ላይ እንዲደርሱ አግባባቸው፡፡

ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ እስከዚህ ጊዜ ድረስና በተወሰነ ደረጃ ከአነግ ላይ እምነቱን አላነሳም ነበር፡፡ አነግ ከሽግግሩ ሂደት ማፈንገጡን ህዝቡ ባይቀበለውም፣ ከዚህ በላይ እስካልሔደ ድረስ ሊሸከመውም አይቸገርም ነበር፡፡ ነገር ግን አነግ ከካምፕ ከወጣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሽግግሩ መንግሥት ወታደሮችና በራሱ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ግልጽ ጥቃት መሰንዘር ጀመረ፡፡ ይህም በአነግና በኦሮሞ ህዝብ መካከል የነበረውን ግንኙነት እስከመበጠስ ደረሰ፡፡ ሰላም ወዳዱ የኦሮሞ ህዝብም የተሳሳተ መንገድ የያዘውን አነግ በመመከት በወቅቱ የተደቀነውን ይህን አደጋ ለማስወገድ ወሳኝ ሚና ተጫወተ። ይህም የሽግግሩ መንግሥት ዋነኛ ትኩረት የነበረው

ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት የማዘጋጀት ተልዕኮ ያለብዙ እንቅፋት እንዲፈጸም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ፈጠረ፡፡

የወቅቱ ዋነኛ ፖለቲካዊ ተልዕኮ የነበረው በህዝብ ወሳኝ ተሳትፎ ሕገ-መንግሥት የማጽደቅ ሂደት ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ተጠሪነቱ ለተወካዮች ምክር ቤት ሆኖ በተመሠረተው የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን አማካይነት የተፈጸመ ነበር። ኮሚሽኑ ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ከፍተኛ አስተዋጽኦ በነበራቸው አቶ ክፍሌ ወዳጆና አቶ ዳዊት ዮሐንስ በሊቀ-መንበርነትና ጸሐፊነት የተመራ ነበር። በእነዚህ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን የተመራው የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን በርከት ያሉ ነጻና ገለልተኛ አገር ወዳድ ምሁራን የተሳተፉበትና ታሪክ የማይረሳው ልዩ ሚና የተጫወተ ተቋም ነበር።

ኮሚሽኑ ተልዕኮውን ለመፈጸም ይችል ዘንድ፣ ከሁሉ በፊት በሁሉም አከራካሪ ጉዳዩች ላይ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያምኑባቸውንና የሚያራምዷቸውን ሁለት ሦስት አማራጭ አንቀጾችን የያዘ ረቂቅ ሕገ-መንግሥት አዘጋጀ፡፡ በረቂቅ ሕገ-መንግሥቱ ላይ በተካሔደ ህዝባዊ ውይይት እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ከአሥራ ስድስት ሚሊዮን የማያንሱ ወገኖች ተሳተፉ፡፡ በመጨረሻ ደግሞ ህዝቡ በሕገ-መንግሥት አጽዳቂ ጉባዔ የሚሳተፉ ተወካዮቹን በነጻነት ከመረጠ በኋላ በአሁኑ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለዚሁ ተብሎ በተገነባው አዳራሽ ሕገ-መንግሥት አጽዳቂ ጉባኤው ተሠየመ፡፡ ጉባኤው በህዝብ የተመረጡ የኢህአዴግና የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት የተሳተፉበትና ከፍተኛ ሙግት የተካሔደበት ነበር። እንደነሻለቃ አድማሴ የመሳሰሉ በግል የተመረጡ ሰዎችም በህዝብ ተወክለው በመሳተፍ በርካታ የልዩነት ሀሳቦችን አራምደዋል። በእነዚህ መካከል በነበሩ ጠንካራ የሀሳብ ልዩነቶች ላይ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ በረቂቅ ሰነዶቹ ላይ አንቀጽ በአንቀጽ ዴሞክራሲያዊ ሙግትና ክርክር ከተካሔደ በኋላ ሕገ-መንግሥቱ ሕዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም. ፀደቀ፡፡

ይህ ዴሞክራሲያዊ ሂደት በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት የማውጣት ታሪክ ቀደም ሲል ከታዩት ሁለት ሦስት አካሔዶችና ባሕል ፈጽሞ የተለየ ነበር፡፡ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ከአንድም ሁለት ጊዜ ሕገ-መንግሥት ከላይ ከንጉሡ የተሰጠ ችሮታ ሆኖ በ ህዝቡ ላይ ተጭኗል፡፡ የ1923ቱም ሆነ የ1948ቱ ሕገ-መንግሥታት ንጉሡ የሉዓላዊነቴ ማረጋገጫ ናቸው ያሉዋቸውን ሕገ-መንግሥታት "ለህዝቤ" ሰጥቻለሁ ያሉባቸው ነበሩ፡፡ የደርግም ሕገ-መንግሥት ለህዝብ ውይይት የተዘረጋና በብሔራዊ ሽንጐው የተመከረበት ቢሆንም፣ ከኢሠፓ በስተቀር የሌላ ፓርቲ ሕልውና ባልተፈቀደበትና ልዩ ልዩ አማራጮች በሌሉበት የፀደቀ ነበር፡፡ ስለዚህም በይዘቱ ከላይ የተሰጠ ሕገ-መንግሥት ነበር፡፡ በአንጻሩ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ከእነዚህ ፈጽሞ ሊነጻጸር በማይችል ዴሞክራሲያዊ ሂደትና የሚሊዮኖች ተሳትፎ የፀደቀ ብቸኛው የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ነው፡፡

ከልማታዊነት ቀድሞ የመጣው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ፣

በብዙ የምሥራቅ እስያ አገሮች መጀመሪያ በሙሉ ወይ ከፊል አምባገናነዊ ሥርዓት ልማት ከመጣ በኋላ ዴሞክራሲ ዘግይቶ መከተሉ የሚታወቅ ነው። ከዚህ በመነሳት አንዳንዶች በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ሂደት እንዳለ አስመስለው ያቀርባሉ። ኢትዮጵያ በልማት መራመድ መጀመሯ አከራካሪ ባልሆነበት በዚህ ዘመን እነዚህ ወገኖች ልማቱ የመጣው ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ ነው የሚል መከራከሪያ ሲያቀርቡ መስማት የተለመደ ነው። ነገር ግን በአገራችን የነበረውና ያለው ሂደት የዚህ ቀጥተኛ ግልባጭ ነው። ዴሞክራሲ ቀድሞ ልማቱ ተከትሏል። የሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲው ይዘትና ተግባራዊ የተደረገበት ሂደት ይህን ያረጋግጣል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ የፀደቀ ከመሆኑ በተጨማሪ ይዘቱ በጥልቅ ዴሞክራሲያዊ መርሆዎች የተዋቀረና በተግባር ላይ የዋለበት ሂደትም ይህንኑ የተከተለ ነው። ይህን በዴሞክራሲ ጥያቄ ዙሪያ በወቅቱ የነበሩትን ልዩነቶች መነሻ በማድረግና ይዘቱን ከዓለም አቀፍ ልምዶች ጋር አነጻጽሮ በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል።

ዴሞክራሲ በጽንሰ-ሀሳብ ደረጃ ሁለንተናዊ ባሕርይ ያለውና ተግባራዊ በተደረገባቸው የዳበሩ አገሮች ሁሉ መላውን ዜጐች ያላንዳች ልዩነት የሚያገለግል የአስተዳደር ሥርዓት ተመስሎ ቢቀርብም፣ በቅርበት ሲፈተሽ ግን የትም ቢሆን ወገናዊ ባሕርይ ያለው የአስተዳደር ሥርዓት ነው። አንድም የኢኮኖሚ ሀብት ምንጮችን የሚቆጣጠሩትን ባለንብረቶች ወይም ደግሞ ከዚህ በተጻራሪ ብዙኃኑን ህዝብ ሊያገለግል የሚችል የአስተዳደር ሥርዓት ነው። ይህም ወገናዊነቱም ሆነ አገልግሎቱ ለዴሞክራሲ በሚካሔደው ትግል ከሚሳተፉት የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥንካሬና የኃይል ሚዛን ጋር ተያይዞ የሚወሰን በመሆኑ ነው። ዴሞክራሲ ከላይ በሚንቆረቆር ችሮታ ለህዝብ የሚሰጥ በሆነበት ሁሉ፣ በዋነኛነት ለገዥዎች ያደላና ህዝቡን ያገለለ ይሆናል። የብዙኃኑ የትግል ተሳትፎ ዝቅተኛ ወይም የተቀዛቀዘ ከሆነ ህዝቡ ከሚመሠረተው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር የሚያገኘው መብትና አገልግሎት በዚያው ልክ ያነሰ መሆኑ አይቀርም። ይህ በበለጸጉት አገሮች የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዞ ላይ በግልጽ የታየ ነው። በአንጻሩ ለዴሞክራሲ የሚካሔደው ትግል ምልዓተ ህዝቡን በንቃት የሚያሳትፍ በሆነበት ደግሞ የዴሞክራሲው ይዘትና አገልግሎት ብዙኃኑን ማዕከል ያደረገ ይሆናል። የዴሞክራሲን ወገናዊነት በትክክል ለመገንዘብ በአውሮፓ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር የተያያዘውን ሂደት አጠር አድርጐ መመልከት ተገቢ ይሆናል።

ዴሞክራሲያዊ አብዮት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሔደው በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ በአውሮፓ ነው። በ16ኛውና በ17ኛው ክፍለ ዘመናት በአውሮፓ የበላይነት የነበራቸው ፍፁማዊ የዘውድ አስተዳደሮች ነበሩ። እነዚህ ከፈጣሪ የተሰጠ መለኮታዊ ሥልጣን አለን የሚሉ

አገዛዞች ስለነበሩ በሰው ልጆች መካከል እኩልነት አለ የሚለውን መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ መርሆ የማይቀበሉ ኋላቀር አስተዳደሮች ነበሩ። መሬትን በግል ሀብትነት ይዘው በግዛታቸው ውስጥ የሚገኙ አርሶ አደሮች ሁሉ የፊውዳሎቹ አገልጋዮች እንዲሆኑ የሚያስገድዱ ነበሩ። ይልቁንም ነገስታቱ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች እንደሆኑና ሌላው ሰው በሙሉ ከእነርሱ በታች እንደሆነ አድርገው በመቁጠር በሰዎች መካከል የጌታና የሎሌ ግንኙነትን ፈጥረው ነበር። ዛሬም ድረስ በእንግሊዝና በአንዳንድ የአውሮፓ አገሮች የሚታዩ ነገስታት "የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች እኛ ብቻ ነን" ሲሉ የሚደመጡ መሆኑ፣ ቅሪት አስተሳሰቡ ከዘመናዊነት ጋር አብሮ የማይራመድ ፀረ-እኩልነት ይዘት እንዳለው ያሳያል።

እኩልነት ያልሰፈነባቸው እነዚህ ማኅበረሰቦች ከአርሶ አደሮች ጋር በማያቋርጥ ቅራኔ ውስጥ የገቡ ስለነበሩ አርሶ አደሮች ከተጫናቸው የግፍ አገዛዝ ለመላቀቅ ያላሰለሰ ትግል አካሂደዋል። በአርሶ አደሩ በኩል የተካሔደው ይህ ትግል መሠረቱ የሰው ልጆች ክብርና ሰብዓዊነት ነበር። በፊውዳሉ መደብ ከሰው ተራ የማይቆጠሩት አርሶ አደሮች ከመሬታቸው የተነቀሉ፣ ካመረቱት ምርት አብዛኛውን የሚነጠቁ፣ በፊውዳሎቹ ዘግናኝ ቅጣት የሚፈጸምባቸው በአጭሩ ሰብዓዊ ክብራቸውን የተነፈጉና የተዋረዱ ማኅበረሰቦች ነበሩ። በዚህ ምክንያት ከጀርመን እስከ ፈረንሳይ፣ ከእንግሊዝ እስከሩስያ አርሶ አደሮች ያለማቋረጥ ያካሔዱዋቸው አመጾችና ጦርነቶች በአብዛኛው የሰው ልጆችን ክብር የሚመልስ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመገንባት ዓላማና ባሕርይ ነበራቸው።

ከዚህ አኳያ ሲታይ ለዴሞክራሲ የሚካሔደው ትግል የሰው ልጆችንና ሰብዓዊነትን ማዕከል አድርጐ ሊቀሰቀስ የሚችል ትግል እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል። በየትኛውም ዓለም አርሶ አደሮች ያካሔዱት ትግል ለአርሶ አደሮች የበላይ ገዥነት ሆኖ አያውቅም። በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ለመገንባት ከመፋለም አልፎ የአርሶ አደሩን አምባገነንት ለመገንባት ታግሎ የሚያውቅ አርሶ አደርም ሆነ ጠንካራ የአርሶ አደር ፓርቲ በምድራችን ላይ ብዙም ታይቶ አያውቅም። በታላቋ ሩስያ በ1880ዎቹ ወደሥልጣን ለመምጣት የሞከረ የአርሶ አደር ፓርቲ የታየ ቢሆንም፣ ይህም ሰሳይሳካለት የቀረ ፓርቲ ነበር። በየአገሩ አርሶ አደሩ ለብዙ ዘመናት በቁጥሩ የበዛው የህዝብ ክፍል የነበረ ቢሆንም ራሱን በዘላቂነት ወደገዥ መንግሥትነት አሸጋግሮ አያውቅም። ራሱን በገዥነት የማስቀመጥ ራዕይም ሆነ ሕልምም የለውም። ስለሆነም፣ ለዴሞክራሲ የሚካሔደው ትግል ከአርሶ አደሩና ከሌሎች ብዙኃን ህዝቦች ጥቅምና ፍላጐት ሲነሳና በአርሶ አደሩ ተሳትፎ ሲካሔድ ዓላማውም ሆነ ውጤቱ እኩልነትና ፍትህን ማረጋገጥ ብቻ ይሆናል። በገበሬ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲ ለሰው ልጆች ተገቢውን ክብር በመስጠትና በሰብዓዊነት ላይ የተገነባ ዴሞክራሲን ከማስፈን አልፎ ለበላይነት የሚያልም አይሆንም።

በአውሮፓ የነበሩት ፍፁማዊ የዘውድ አገዛዝ ሥርዓቶች ቅራኔ ውስጥ የገቡት ግን ከአርሶ አደሩ ጋር ብቻ አልነበረም። የገበያ ሥርዓት የመገንባት ህልም ይዞ ከተነሳው ባለሀብትም ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብተው ነበር። የፊውዳላዊ ሥርዓቱ ቁንጮዎች በግዛታቸው ውስጥ የሚገኘውን መሬት ጠቅልለው የያዙ ስለነበሩ ማንም ቢሆን ያለእነርሱ ፈቃድ በግዛታቸው ውስጥ መንቀሳቀስ አይችልም ነበር። ሉዓላዊነታቸውን በገነቡበት ትንሽ ይሁን ሰፊ ግዛት መውጫና መግቢያ ላይ ኬላ ገትረው ወጭ ወራጁን ግብር በማስከፈል እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር የሚሞክሩ ነበሩ። በተበጣጠሱ ትንንሽ ግዛቶቻቸው ያሰፈኑት ተጠያቂነት የሌለበት ሥርዓት የሕብረተሰቡ ታዳጊ ፍላጐት ሆኖ በመጣው የጉልበትና የሸቀጥ ነጻ ዝውውር ላይ ከባድ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል። በዚህም ምክንያት የገበያ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚፈልገው ባለሀብት ሸቀጡን ለማምረት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃና የሰው ጉልበት ከቦታ ቦታ በቀላሉ ለማንቀሳቀስ ተቸገረ። በአስቸጋሪ ሁኔታ ያመረተውን ሸቀጥ ኬላ ሳይገድበው አዘዋውሮ ለመሸጥና ትርፉን በእጁ ለማስገባት የነበረውን ጉጉት የፊውዳሉ ሥርዓት ከባድ ገደብ አሳረፈበት።

ይህን የመሰለው ፊውዳላዊ ሥርዓት መቼም ቢሆን ትርፍ ለማግኘትና ካፒታሉን ለማሳደግ ለሚጓጓው ባለሀብት ሊታገሠው ከሚችለው በላይ እንቅፋት ሆነበት። ይህም የማታ ማታ በዘውዳዊ አገዛዙቹና በጣም ተነቃናቂ በሆነው የገበያ ሥርዓት ወኪል መካከል ቀጥተኛ ቅራኔና የጥቅም ግጭት አስከተለ። እንቅፋቶች የበዙበት ባለሀብት ፊውዳላዊውን ሥርዓት ለማስወገድና በምትኩ ዴሞክራሲን ለማስፈን ቆርጦ ተነሳ። የካፒታልን ልእልናና የአትራፊነቱን ዘላለማዊነት የሚያረጋግጥ ሥርአት ለመገንባትም ቆርጦ ተነሳ። በቁጥሩ እጅግ አናሳ የሆነው ባለሀብት ለካፒታልና ትርፍ ልእልና ሲል ብዙኀኑን አርሶ አደርና ሌሎች ተራማጅ የሕብረተሰብ ክፍሎች አስተባብሮ ዴሞክራሲያዊ አብዮቱን አካሔደ።

በአውሮፓ ለዴሞክራሲ የተካሔደው ትግል በአንድ በኩል በአርሶ አደሩ ግብታዊ መነሳሳት መልክ ለበርካታ ዓመታት የተካሔደ ሲሆን፣ የኋላ ኋላ ደግሞ ባለሀብቱ ከራሱ ጥቅም በመነሳት ቡርጆ አካኋን መሪነቱን ጨብጦ የተሳተፈበት ነበር። ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ የተፈጠረው የፋብሪካ ሠራተኛና የከተማው ንዑስ ባለሀብትም ለዴሞክራሲ የሚካሔደውን ትግል በሂደት ተቀላቅለውታል። በመሆኑም ለዴሞክራሲ የተካሔደው ትግል እነዚህ ትልልቅ ማኅበረሰቦች ከየራሳቸው ፍላጐት በመነሳት የተሳተፉበትና ውጤቱንም ለመወሰን የተንቀሳቀሱበት ነበር። ለፊውዳሉ አስተዳደር በነበራቸው ጥላቻ ሁሉም ተመሳሳይ አቋም የነበራቸው ቢሆኑም በመካከላቸው ከባድ የጥቅም ፍላጐት ልዩነት ነበራቸው።

በዚህ የተነሳ አርሶ አደሩ፣ የፋብሪካ ሠራተኛውና የከተማው ንዑስ ባለሀብቱ በሲቪዊነት ላይ ለተዋቀረ መሠረተ ለፊ ዴሞክራሲ፣ ባለሀብቱ ደግሞ የካፒታልና ትርፍን የበላይነት የሚያበቃ በራሱ ዙሪያ የሚሽከረከርና የተመጠነ የዴሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት ተፋልመዋል።

የመጀመሪያዎቹ ገደብ የሌለበት ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ሲፋለሙ፣ ባለሀብቱ ደግሞ የካፒታልን ልእልና የማይጻረርና የማይጐዳ በዋነኛነት ደግሞ በራሱ በባለሀብቱ ምሕዋር ብቻ የሚሽከረከር፣ መሠረተ ጠባብና የተገደበ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ተረባርቧል። ለዴሞክራሲ በተካሔደው በዚህ ትግል የአርሶ አደሩና የሠራተኛው ዴሞክራሲ ወይስ የባለሀብቱ ዴሞክራሲ ይሰፈን የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው በመካከላቸው በነበረው የኃይል ሚዛን ነበር። ስለሆነም የባለሀብቱ ጡንቻ ሲፈረጥም ዴሞክራሲው ጠባብና ብዙኃኑን ያገለለ፣ በአንጻሩ የአርሶ አደሩ፣ የሠራተኛውና የንዑስ ባለሀብቱ ጡንቻ ሲፈረጥም ደግሞ መሠረተ-ሰፊ እየሆነ የታየውም በዚሁ የተነሳ ነው።

በአውሮፓ የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት በጀመረበት ወቅት የዴሞክራሲው አንዱ መገለጫ የሆነው የመምረጥና የመመረጥ መብት ይዘትና ተግባራዊነት ይህን ያሳያል። መንግሥታት በምርጫ መመስረት በጀመሩባቸው በእነዚህ ዓመታት የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት የተፈቀደው ቋሚ ንብረት ለነበራቸው ባለሀብቶችና የመሬት ከበርቴዎች ብቻ ነው። መሬትና ቤት፣ ፋብሪካና ሌላ ተቋም የነበራቸው ሁሉ ለመመረጥ መወዳደር ሲችሉ፣ ቋሚ ሀብት ያልነበራቸው ብዙኃኑ አውሮፓውያን ደግሞ ከምርጫ ዴሞክራሲ የተገለሉ ነበሩ። የመመረጥም ሆነ የመምረጥ መብት አልነበራቸውም። ነገር ግን ብዙኃኑ የአውሮፓ ህዝቦች እንደሰው ተቆጥረው ለመምረጥና መመረጥ መብታቸው መከበር ባካሔዱት ትግል ከብዙ ዓመታት በኋላ መጀመሪያ የፋብሪካ ሠራተኞች የመመረጥ መብትን የማይጨምር የመምረጥ መብት ብቻ አግኝተዋል። ይህም ሲሆን ሴቶች የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት እንዳይኖራቸው የተጣለው ገደብ እስከ ሃያኛው ከፍለ ዘመን መጀመሪያ አልተነሳም ነበር። በአሜሪካን አገር ሴቶች በምርጫ መሳተፍ የጀመሩት ከ1922 በኋላ ነው። ጥቁሮች እንደሰው ተቆጥረው መምረጥ የጀመሩት በ1950ዎቹ የተፋፋመውን የጥቁሮች የመብት እንቅስቃሴ ተከትሎ ብቻ ነበር። አሜሪካንን ለመምራት የቢቃ አንድ ጥቁር አሜሪካዊ ለመመልከት የበቃነውም በአገሪቱ ዴሞክራሲ ከተተከለ ከሁለት መቶ አምሳ ዓመታት በኋላ ነው።

በበለጸጉት አገሮች ዴሞክራሲው መሠረተ-ጠባብ ሆኖ ከጀመረ በኋላ በሂደት በህዝቡ ትግል ብቻ እየሰፋ እንደሔደ ከዚህ አጭር መረጃ ለመገንዘብ ይቻላል። የመደራጀት መብትን ወስዶ በመመልከትም ይህንኑ ማረጋገጥ ይቻላል። በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ በተለይ ኒዮ-ሊበራሊዝም የበላይነት መያዝ ከጀመረ በኋላ የተደራጀ የሕብረተሰብ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ጥቃት ተሰንዝሮበታል። በዴሞክራሲ መብቶች ላይም ጥቃቱ ተባብሷል። ስለሆነም በእነዚህ አገሮች የዴሞክራሲያዊ መብት ለስሙ እንዳለ ቢነገርም በተደራጁ የሠራተኛ ማኅበራት ላይ ግልጽና የማያቋርጥ ጥቃት ተካሂዷል። የዚህ ጥቃት ምንጭ ባለሀብቱና ካፒታል ናቸው። ባለሀብቱ ጠንካራ የመደራደር አቅም ያለው የሠራተኛ ኃይል የካፒታልን ልእልናና አትራፊነት ይቀንሳል ብሎ በመስጋት በሠራተኛው ላይ የማያቋርጥ ጥቃት ያደርሳል። ጥቃቱ በማኅበራዊና

ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካዊ መልክ ጭምር የሚፈጸም ነው። ይህም ፖለቲካዊ ጥቃት የሠራተኛውን ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለማቋረጥ በማዳከም መልክ ይገለጻል። ቢቨርሊ ጀ. ሲልቨርና ጆን ማርኮፍ ይህ ጥቃት በዓለማችን ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ በሚኖሩ ህዝቦች ላይ በተለይ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ እየተባባሰ እንደሔደ በማስመልከት፡-

> "በደቡቡ የዓለማችን ህዝቦች ላይ የሚደርሰው ጫና በተለይ ከእዳ ቅነሳ ጋር ተያይዞ ይበልጥ እየከበደና አስቸጋሪ እየሆነ ሔዷል። በሃያኛው ክፍለ-ዘመን መጨረሻ የተቀሰቀሰው ግሎባል የዴሞክራሲያዊነት ማዕበል በብዙ አገሮች ስማዊ ዴሞክራሲን ቢያመጣም የሠራተኛው መደብ ዋነኛ ጉዳይ በሆነው የተሟላ መብት /Universal Suffrage/ ላይ ግን መዳከምን አስከትሏል። ለስሙ ነጻ የሆኑ መንግሥታት ሁሉ መሠረታዊ የኢኮኖሚና ፖሊሲ ውሳኔዎችን የመረጣቸውን ህዝብ ሳይሆን የዓለም ገንዘብ ድርጅትና ድንበር ዘለል ካፒታልን ለማስደሰት ሲሉ ይወስዳሉ።[31] በማለት ገልጸውታል።

ከፍ ሲል ከተገለፁት ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ኃይሎች ትግል ለዴሞክራሲ የተካሔደው ትግል የተለያየ መነሻና ግብ እንደሚኖረው ለመገንዘብ ይቻላል። ኢህአዴግ ኢትዮጵያን የማስተዳደር ኃላፊነት በተረከበበት ጊዜም ለዴሞክራሲ የሚካሔደው ትግል ከእነዚህ የተለያዩ ፍላጐቶችና ተፅዕኖዎች ነጻ አልነበረም። በአገር ውስጥ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚነሳው ልዩነትም ሆነ ዓለም አቀፍ ኃይሎች የዴሞክራሲውን ባሕርይና ወሰን በማስመልከት ሊያሳርፉት ይሹ የነበረው ተፅዕኖ አንድም መሠረተ-ጠባብ አሊያም መሠረተ-ሰፊ ዴሞክራሲ ከማስፈን ፍላጐት ጋር የተያያዘ ነበር። በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለመገንባት የተካሔደው ትግል "ዴሞክራሲው በዋነኛነት በየትኛው አቅጣጫ ይገንባ?" የሚለውን ጥያቄ ቸል በማለት ሊወሰን የሚችል አልነበረም። አገሪቱ ከባድ የዴሞክራሲ ድኅነት የነበረባት በመሆኑና ሁሉም "ዴሞክራሲን እፈልጋለሁ" ይል ስለነበር ብቻ በደፈናው ተስማምቶ ሊገነባ የሚችል ሥርዓት አልነበረም። እያንዳንዱ አንቀጽ ልሂቃንን ወይም ብዙኀንን ታሳቢ ከማድረግ ውጭ ሊቀረጽ የሚችል ስላልነበር ኢህአዴግ የጠራ ግንዛቤ ይዞ እንዲቀረጽ ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረውም።

ኢህአዴግ ቁልፍ ሚና በተጫወተበት ሕገ-መንግሥት የማጽደቅ ሂደት እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች በመገንዘብ ሕገ-መንግሥቱ የልሂቃንን መብትና ጥቅም በማስከብር ብቻ የሚታጠር እንዳይሆን፣ ይልቁንም ብዙኃኑን ማዕከል ያደረገ ዴሞክራሲን የሚያሰፍን እንዲሆን ከባድ ትግል ተካሂዷል። ኢህአዴግ ሕገ-መንግሥቱ በፀደቀ ማግሥት በ1987 ዓ.ም. ባዘጋጀው የመጀመሪያው መርሕ ግብር ላይ ይህን በማሰመልከት፣

"ዴሞክራሲያችን ሥር ሊሰድ የሚችለው፣ መላው ህዝብ የተሳተፈበትና በኑሮዬ ላይ ለውጥ የሚያመጣ ምርጥ ነገር ነው ብሎ የሚያምንበት ሲሆን ነው። ዴሞክራሲ የጥቂቶች መሣሪያ እስከሆነ ድረስ በጥልቀት ሥር ሊሰድና ዋስትና ያለው ሊሆን አይችልም። ዴሞክራሲያችን ሥር እንዲሰድና ዘላቂ እንዲሆን በህዝብ ዙሪያ መለስና ቀጥተኛ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት" [32] ማለቱ ገና ከጠዋቱ ጀምሮ ህዝብ የሚጠቀምበትን መሠረተ-ሰፊ ዴሞክራሲ ያልም እንዳልነበረ ያሳያል።

ኢትዮጵያ በአንድ በኩል ልዩ ልዩ ማኅበረሰቦችን በሌላ በኩል ደግሞ ግለሰብ ዜጐችን የያዘች አገር ነች። የሕልውናዋ መሠረት እነዚሁ ህዝቦቿና ዜጐቿ ናቸው። በመሆኑም፣ አገሪቱ ዴሞክራሲና ሰላም የሰፈነባት ትሆን ዘንድ ለህዝቦቿና ለዜጐቿ ክብርና ምኞት ዋስትና የምትሰጥ አገር ሆና መገንባት አለባት። ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ገና ከጠዋቱ ሲቀረጽ መነሻ መሠረቱና መዳረሻ ግቡ ካፒታልና አትራፊነት ሳይሆን ህዝብና ተናጠል ዜጐች በአጭሩ ደግሞ ሰብዓዊ ፍጡራን እንዲሆኑ ተደረገ።

ቀደምት ሥርዓቶች እነዚህን የኢትዮጵያ መሠረቶች የሚያከብሩ አልነበሩም። ኢትዮጵያ ቀደም ባለው ታሪኳ የግለሰብን ሆነ የማኅበረሰቦቿን መብቶች የሚያከብሩ መንግሥታትና ሥርዓቶች አግኝታ አታውቅም። ምንም እንኳ የአገሪቱ ህዝቦችና ዜጐች አቅማቸው የፈቀደውን ያህል በመካከላቸው መልካም የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት የሰፈነባት አገር ለመገንባት ጥረት ያደረጉ ቢሆኑም፣ ዕጣ ፋንታቸው የተወሰነው በገዥዎቻቸው ስለነበር ይህን በጐ ፍላጐታቸውን እውን ማድረግ አልቻሉም ነበር። ይህን እውነታ ከግንዛቤ በማስገባት የሕገ-መንግሥቱ ይዘት ከታሪክ የተወረሱ የተዛቡ ግንኙነቶችን በማረምና ቢኖሩ የተገነቡ መልካም እሴቶችን ደግሞ በማዳበር ላይ የተዋቀረ እንዲሆን ተደርጓል። አዲሲቱ ኢትዮጵያ ከህዝብና ከዜጐች መብትና ተጠቃሚነት በመነሳት መሠረተ-ሰፊ ዴሞክራሲን ትገነባ ዘንድ ዕድል የሚሰጥ ሕገ-መንግሥት ሆኖ እንዲቀረጽ ተደርጓል።

ከዚህ አኳያ ሲታይ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ በካፒታልና በባለሀብቱ ልእልናና እጅግ ጠባብ በሆነ መሠረት ከተገነባው የአውሮፓና የአሜሪካን ዴሞክራሲ በሰፋ መሠረት ላይ የተዋቀረ ሆኖ የጀመረ ነው። በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥታዊው ዴሞክራሲ ሉዐላዊነትን የህዝብ ሥልጣን አድርጓል። በአንጻሩ የዴሞክራሲ ጀማሪ የሆነችው እንግሊዝ ዛሬም ሉዐላዊነትን የንጉሣውያኑ የማይነካ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳደረገችው ቀጥላለች። በኢትዮጵያ የግልና የቡድን መብቶች አንዱ ከሌላው በማይበልጥ አኳኋን እንዲከበሩ ያደረገ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲ ፀድቋል። በበለጸጉት አገሮች ህዝብ በተደራጀ አኳኋን ለመብቱ የሚያካሂደውን

ትግል እንዳያጠናክርና የካፒታልን ልእልና እንዳይጋፋ ሲባል የቡድን መብት አይበረታታም። ዴቪድ ሐርቬይ በአንድ ወቅት የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ማርጋሬት ታቸር "ተናጠል ግለሰብ ወንዶችና ሴቶች እንጅ ማኅበረሰብ የሚባል ነገር ፈጽሞ የለም"[33] ማለታቸውን መነሻ በማድረግ፣ የበለጸገው ዓለም ለቡድን መብት ከብር እንደሌለው ይገልጻል። እ.ኤ.አ በ1980ዎቹ ኒዮ-ሊበራሊዝም በሰው ልጆች ላይ አዲስ ጥቃት በከፈተበት ጊዜ ይህንኑ በተደራጀ ትግል ለመቋቋም የሞከሩትን የእንግሊዝ የከሰል ማዕድን ሠራተኞች ማኅበር እያሳደዱ በመቀጥቀጥ ሲያፈራርሱ የነበሩት ታቸር፣ ይህን ማለታቸው የአውሮፓውያኑ ዴሞክራሲ ለማኅበረሰብ የሚሰጠው ክብርና ቦታ እጅግ ያነሰ እንደሆነ አመልካች ነው።

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲ "የዜጐች መብት ካልተከበረ የማኅበረሰቦች መብት ሊከበር፣ የማኅበረሰብ መብት ባልተከበረበትም የግለሰብ መብት ሊከበር አይችልም" በሚል አስተሳሰብ፣ ሁለቱንም ሳይነጣጥልና በምሉእነት በማከበር መርሕ ላይ የተዋቀረ ነው። በዚህ ባሕርዩም በተባበሩት መንግሥታት የጸደቁ ሁለት መሠረታዊ የመብት ድንጋጌዎችን ካለማበላለጥና መነጣጠል እኩል ያከብራል። በአንድ በኩል "ዓለም አቀፍ የሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች ጥበቃ ስምምነትን" (International Covenant on Civil and Political Rights /ICCPR/) በሌላ በኩል ደግሞ ዓለም አቀፉን የኢኮኖሚ ማኅበራዊና ባሕላዊ መብቶች ጥበቃ ሥምምነትን (International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights /ICESCR/) በጥብቅ አዋህዶ ያስከበረ መሆኑም ከሌሎች ሕገ-መንግሥታት የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል። በኢትዮጵያ የዴሞክራሲን አጀማመር መሠረተ-ጠባብ ከነበረው የአውሮፓና የአሜሪካን ዴሞክራሲ የተለየ የሚያደርገው አንዱ መሠረታዊ ባሕርይ የግልና የቡድን መብቶችን በእኩል ክብደትና ትኩረት የሚያከብር መሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲ በዜጐች የመምረጥና የመመረጥ መብት ጉዳይ ላይ ከአዝጋሚው የአውሮፓውያን ዴሞክራሲ በተለየ አቅጣጫ አሥራ ስምንት ዓመት የሞላቸውን ዜጐች የፆታና የሃይማኖት፣ የብሔርና የገቢ ደረጃ ልዩነት በማያደርግ አኳኋን ለመምረጥና ለመመረጥ መብት ያበቃው ከመጀመሪያዋ እለት ጀምሮ መሆኑም ይህን በግልጽ የሚያሳይ ነው።

በሕገ-መንግሥቱ ላይ የሰፈሩት የዜጐችን መብት የሚመለከቱ አንቀጾች በየትኛውም ዓለም አቀፍ ዴሞክራሲያዊ የሕግ ማዕቀፍ የሚገኙ መሠረታዊ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አሟልተው የያዙ ናቸው። በዚህ ሕገ-መንግሥት የሕይወትና የአካል ደኅንነትና የነጻነት መብት ተከብሮ ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸው ተደንግጓል። የአመለካከትና ሀሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶታል። የመደራጀት፣ ከቦታ ቦታ በነጻነት የመንቀሳቀስና በመረጥከው ቦታ የመኖር የዜግነት መብቶች ተከብረዋል። የሴቶችና የሕጻናት መብት፣ ፍትህ

የሥልጣንና የመምረጥ መመረጥ መብትና የመሳሰሉ መብቶች ሁሉ የተሟላ ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትናና ጥበቃ አግኝተዋል። የንብረት ዋስትናም እንደዚሁ። በዚህ ረገድ በሕገ-መንግሥቱ የተዘረዘሩት የዜጐችና የማኅበረሰቦች መብቶች የትኛውም ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ከሚተዳደርባቸው ሕገ-መንግሥታት ቢበልጡ እንጅ አያንሱም። ይህን ሕገ-መንግሥቱ ለቡድን መብት በተለይ ለብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ያጐናጸፋቸውን መብቶች ከሌሎች አገሮች ጋር በማነጻጸር ብቻ ልዩነቱ ትንሽ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ይቻላል።

በኢትዮጵያ በመገንባት ላይ ያለው ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲ በሌሎች ሕገ-መንግሥታት ባልተለመደ አኳኋን ለቡድን መብቶች በተለይ ደግሞ ለብሔር፣ ብሔረሰብ መብቶች የተሟላ እውቅና በመስጠት የተዋቀረ ነው። የቡድን መብቶች ብዙ ማኅበረሰቦችን የሚመለከቱ መብቶች ናቸው። ሕብረተሰብ በቋንቋቸው፣ በባሕላቸውና በታሪካቸው፣ በሚኖሩበት መልከአ-ምድር፣ በሚያመልኩት እምነት፣ በእድሜያቸው፣ በጾታቸው፣ በተሰማሩበት የሥራ መስክና በአካላዊ ሁኔታቸው ተመሳሳይነት ወይም ተለያይነት ያላቸው ልዩ ልዩ ማኅበረሰቦችን በውስጡ ያቀፈ ነው። ብሔረሰቦች፣ ሃይማኖቶች፣ ሴቶች፣ የፋብሪካ ሠራተኞች፣ አርሶ አደሮች፣ ልዩ ፍላጐት ያላቸው የሕብረተሰብ ከፍሎች ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መልክ የሚገለጽ የየራሳቸው የጋራ ፍላጐት ያላቸው ቡድን ተኮር ማኅበረሰቦች ናቸው። ይህን የመሳሰሉ ቡድኖች አንዱ ተፈጥረው ያበቁ ሳይሆኑ ከሕብረተሰብ ዕድገት ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩና ምናልባትም ሊከስሙ የሚችሉ ናቸው። ዋናው ነገር ተጨባጭ ሕልውና ያላቸው ሆነው በሚገኙበት ጊዜ ሁሉ የጋራ ፍላጐት ያላቸውና ይህም እንዲከበርላቸው የሚሹ መሆናቸው የማይቀርና ይህን መብት ማወቅ ግዴታ መሆኑ ነው።

በኢትዮጵያ እነዚህን የመሳሰሉ ማኅበረሰቦች እንዳሉ ብዙም ባያከራክርም፣ የእነዚህን ማኅበረሰቦች ሕልውና ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከት ጉልህ ልዩነት የሚታይበት የመፍትሔ ሀሳብ ማቀንቀን የተለመደ ነው። አንዳንዶች ብዙኅነትን በነባራዊ እውነታነቱ ተመልከተው በአግባቡ የማስተናገድ ፍላጐት ያሳያሉ። ሌሎች ደግሞ ነባራዊ እውነታ ቢሆንም "ብዙኅነት አገርን ያዳክማል" ብለው በማመን በአርቲፊሻል መንገድ ሊያጠፉት ይፈልጋሉ። በዚህ ረገድ በተለይ አከራካሪ ሆኖ የሚገኘው የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና የተለያዩ ሃይማኖታዊ እምነቶች ሕልውናና መብትን የሚመለከተው ጉዳይ ነው።

በእርግጥ በመገንባት ላይ ያለው ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ኢትዮጵያ በብዙኅነት የተዋቀረች አገር መሆኗን ነባራዊ እውነታ አድርጐ ከመመልከት ባሻገር ይህንኑ በደፈናው የሥጋት ወይም የመልካም ዕድል ምንጭ አድርጐ አይመለከተውም። ብዙኅነት ተፈጥሮ የሰጠን አንድ ነባራዊ እውነታ ብቻ በመሆኑ በራሱ ጥሩም መጥፎም አይደለም። ብዙኅነት ያላቸውም የሌላቸውም ማኅበረሰቦች በደፈናው አስቸጋሪ ተብለው አይወሰዱም።

ሁለቱም በማንኛውም አገር የመልካም ዕድል ወይም የሥጋት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉት በሚያዙበት መንገድ ብቻ ነው። የማንነት ልዩነት ባለበት ቦታ ይህን እንደአንድ ጐጅ ነገር ተመልክቶ ሊያጠፋው የሚፈልግ ኃይል ሁሉ ከነባራዊ እውነታ ጋር በመጋጨት አዲስ የሕልውና ፈተና ይደቅናል። በአንጻሩ ብዙኀነትን በነባራዊ እውነታነቱ ተቀብሎ በአግባቡ የሚያስተናግድ ደግሞ ከታሪክ ሆነ ከገሐዱ ዓለም ተስማምቶ ይኖራል። በዚህም አቅጣጫው ዓለም ለሰው ልጆች የተመቸች እንድትሆን ያደርጋል።

ከዚህ መሠረታዊ አተያይ በመነሳት በኢትዮጵያ የተገነባው አዲስ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ብዙኀነት አንድ የአገሪቱ ነባራዊ እውነታ መሆኑን ተቀብሎ፣ በአግባቡ በማስተናገድ ለሰው ልጅ ማኅበረሰቦች ያለውን ታላቅ ክብር አረጋግጧል። በተጻፈም ባልተጻፈም ሕገ-መንግሥት እየተመራን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብተናል እያሉ፣ "የግለሰብን እንጂ የቡድንን መብት አናስተናግድም" ከሚሉ ሥርዓቶች፣ በእጅጉ የላቀ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሆን የሚያደርገው አንዱ መሠረታዊ ባሕርይ ከዚሁ የመነጨ ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ መሠረቱ ካፒታልና የባለሀብቱ መብትና ጥቅም ሳይሆን የመላ የአገሪቱ ህዝቦች ፍላጐትና ተጠቃሚነት፣ በአጭሩ መነሻ መሠረቱ ሰብዓዊ ፍጡራን፣ በተለይ የብዙኀኑ ህዝብ ጥልቅ ሰብአዊነት ነውና። ይህም ሆኖ በኢትዮጵያ የማኅበረሰቦች /ቡድን/ መብት ከእነርሱ በመሠረቱ በተለየ ሁኔታ እንደተከበረ እየተመለከቱ፣ ይህንኑ ሲያጣጥሉት ማየትና መስማት የተለመደ ነው። የብሔር፣ ብሔረሰቦችን መብት በማስከበር ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ በጐሳ ፖለቲካ መልክ በመሠየም ዘርና ደም በመምረጥ ላይ የተመሠረተ ለማስመሰል የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።

የጐሳ ፌደራሊዝም (Ethenic Federalism) የሚባለው መነሻና መድረሻው ደምና ዘር ነው። በኢትዮጵያ እየተገነባ ያለው ዴሞክራሲም ሆነ አገራዊ አንድነት ግን መነሻና መድረሻው ዘርና ደም አይደለም። በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል ከብሔር ልዩነት ባሻገር የዓላማና የተግባር አንድነት እንዲፈጠር አድርጐ የቆየውም ይኸው ነው። የኢህአዴግ አባል በሆኑ ብሔራዊ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ታጋዮችን ከየብሔራቸው ውጭ ካሉ ዴሞክራቶች ጋር አንድ ላይ ያሰለፈው ፌዴራላዊ ሥርዓቱ ከደም ባሻገር ባለ ፖለቲካዊ ትስስር ስለሚመራ ነው። እንደገናም አሮሞዎቹን ዶ/ር መረራ ከኩማ ደመቅሳ፣ ሐድያዎቹን ዶ/ር ሽፈራው ተከለማሪያም ከፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ አማሮቹን አዲሱ ለገሰ ከአሥራት ጣሴ፣ ትግራዮቹን መለስ ዜናዊ ከገብሩ አሥራት ወይም ከዶ/ር ኃይሉ አርዓያ ጋር መሳ ለመሳ አስቁሞ ያፋጠጣቸውም ሥርዓቱ ደምና ዘርን በመቁጠር የተገነባ አለመሆኑ ነው። ይልቁንም አሱሳለፉ በኢኮኖሚ ጥቅሞችና ፖለቲካዊ አቋሞች ላይ የተመሠረተ ነው። አንዳቸው ለተገፉ ብዙኀን፣ ሌላኛው ለውሑዳን የቆሙ መሆናቸው ነው። ይህን በትክክል ለመገንዘብ በ2002 አገራዊ ምርጫ ዋዜማ በርካታ

የፖለቲካ ፓርቲዎች ከጆሴፍ ስቲግሊዝ ጋር በተወያዩበት ጊዜ የተፈጠረው አጋጣሚ ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፡፡

ስቲግሊዝ በ4ኛው አገራዊና ከልላዊ ምርጫ ዋዜማ ወደአገራችን መጥቶ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተገናኝቶ ነበር፡፡ ስብሰባው ስቲግሊዝ ስለኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ከሚሰማው ባሻገር በራሱ ቀጥተኛ ጥናት ለማወቅ በመፈለጉ የተጠራ ነበር። ከማስታውሳቸው መካከል መድረክ፣ ኢዴፓ፣ አብኮ፣ ሌሎች ተቃዋሚዎችና ኢህአዴግ የተገኙበት ነበር፡፡ ከጥቂት የትውውቅ ጊዜ በኋላ ስቲግሊዝ ወደእጅጉዳው በመግባት፣ “እስኪ ዓላማችሁን አስረዱኝ” ብሎ ለሁላችንም አንድ ጥያቄ አቀረበ፡፡ ጥያቄው ግልጽና አጭር ቢሆንም ማንኛችንም ተሸቀዳድመን መመለስ ስላልፈለግን ለተወሰነ ጊዜ ከፍሉን ዝምታ ዋጠው። “ዓላማችሁን ነገሩኝ” ለምትል አጭር ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ሲጠፋ፣ በበኩላችን ዝምታውን ለመስበር ዓላማችንን በደንብ ለሚያውቀውና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለሚሟገትልን ስቲግሊዝ ለማስረዳት ኢህአዴጐች ቅድሚያ ወሰድን፡፡ ከጥቂት መንደፎደሪያ በኋላ ዓላማችንን እርሱ በሚቀበለው ቋንቋ “ድርጅታችን በኢኮኖሚና ማኅበራዊ መስክ ለፈጣን፣ መሠረተ ሰፊና ድሐ ተኮር ለውጥ፤ በፖለቲካው ደግሞ ለመሠረተ-ሰፊ ዴሞክራሲ እንደሚታገል” አስረዳን፡፡ ዝምታው ሲሰበር ከተቃዋሚዎች ዶክተር ኃይሉ አርአያ በቀዳሚነት ዕድሉን በመውሰድ “የለም፣ የለም! እኛ ድሐ ተኮር አይደለንም፣ ድሐ ተኮር በሚባል ከፋፋይ ዓላማ ፈጽሞ አናምንም!” በማለት በድሐ ተኮር ምክረ-ሀሳቦቹ ለሚታወቀው ጆሴፍ ስቲግሊዝ ዓላማቸውን ገለፁለት፡፡ በአንዲት ድህና ኋላቀር አገር ውስጥ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚታገሉት መድረኮች በሰጡት ምላሽ እጅጉን የተገረመው ስቲግሊዝ “ድሐ ተኮር መሆንኮ ነውር የለውም” ቢላቸውም ዶክተር ኃይሉ ወደኋላ የሚሉ ሰው አልሆኑም፡፡ ይህ የመድረክ መሪ ማብራሪያ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ ካቀረበው ሀሳብ ጋር ያላቸውን ተቃርኖ ለማሳየት ስለፈለጉ የቀረበ ሀሳብ ብቻ ነው ተብሎ ቢወሰድ እንኳ፣ ከዶክተር ኃይሉ ምላሽ፣ አንዱ ወገን ለብዙሐኑ የተገፉ ህዝቦች፣ ሌላኛው ለውሑዳን የቆሙ መሆናቸውን ቢያንስ በአዝማሚያ ደረጃ ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት ይህን በመሰለ የማኅበራዊ ጥቅም ልዩነትና ከዚህ በሚፈልቅ አስተሳሰብ ላይ እንጅ በደምና በወንዝ ልጅነት ላይ የተመሠረተ አሰላለፍ የሚከተል አይደለም፡፡ በእርግጥ ከራሱ ከገዥው ፓርቲ አባላት መካከል በንቃት ማነስም ሆነ በልዩ ልዩ የተሳሳቱ ተግባራት ውስጥ በመግባት የብሔርና የወንዝ ልጅነትን እንደማምለጫ በሽፋንነት ሊጠቀሙበት የሚሹ ሰዎች አይታጡም፡፡ ይህ ግን በመገንባት ላይ ያለው ሥርዓት በደምና ዘር ላይ የተመሠረተ ያለመሆኑን እውነታ የሚቀይረው አይደለም፡፡ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ መሠረታዊ የግልና የቡድን ሰብዓዊ መብቶችን ያለልዩነት ለሁሉም ያጐናጸፈና በነጻ ገበያ ማዕቀፍ የብዙኃኑ መብትና ጥቅሞች እንዲከበሩ ለማድረግ አልሞ የተነሳ ነው፡፡ ሐቁ ይህ ቢሆንም የአዲሲቱ

ኢትዮጵያ እውነታ እነዚህ ኃይሎች በሥርዓቱ ላይ ለሚወስዱት አቋም መነሻ መሆን አልቻለም። የውጭም ሆነ የውስጥ ተቃዋሚ ኃይሎች ዋነኛ አጀንዳቸው እውነታውን መቀበል ሳይሆን ሌላ ስለሆነ አቋማቸውን በዚህ አዲስ እውነታ ላይ ለመመሥረት አልፈለጉም።

በኢትዮጵያ የግልና የቡድን መብትን ያስከበረው ዴሞክራሲ በተግባር መገንባት ከጀመረ በኋላ ብዙ የውጭ ኃይሎች በሰብአዊ መብት ሽፋን በአገሪቱ ዴሞክራሲ ላይ የማያቋርጥ የማጥላላት ዘመቻ አካሂደዋል። ዘመቻው "አገሪቱ ትፈራርሳለች" ከማለት ጀምሮ "ኢትዮጵያ በዚህ ሥርዓት በመመራት ከውድቀት በስተቀር ሌላ ዕድል እንደማይኖራት" በመተንበይ ጭምር የተካሔደ ነበር። ነገር ግን ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት እንደታየው፣ እነርሱ ያሰቡትና የተነበዩት ቀርቶ ያልገመቱት ውጤት መጣ። አገሪቱ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከማስከበር አልፋ ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ ቻለች። በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት በአማካይ 5% ዓመታዊ ዕድገት አስመዘገበች። ዘላቂ ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈንም በቃች። በብዙ አገሮች ከአምባገነንነት ወደዴሞክራሲ፣ ከእዝ ወደገበያ ኢኮኖሚ የሚደረገው ሽግግር ምስቅልቅሉ የወጣ ነበር። በኢትዮጵያ ግን ሽግግሩ በተረጋጋ ብቻ ሳይሆን፣ በወቅቱ በአፍሪካ ደረጃ ፈጣን የሚባለውን ዕድገት በማስመዝገብ የተከናወነ ሊሆን ቻለ።

ይህም ኢኮኖሚያዊ ልማቱ በሰፊ ዴሞክራሲ ላይ መገንባት ከመጀመሩ ጋር የተያያዘ ጭምር ነው። የፖሊሲው ትክክለኛነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንኑ የህዝብን ተነሳሽነት መልቀቅ በጀመረ ዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ ለማስፈጸም በመቻሉ የተገኘ ውጤት ነው። ነገር ግን ዕድገቱና ዴሞክራሲው ቀጥተኛ ተዛምዶና መስተጋብር ያላቸው ሆኖ እያለ አሁን አሁን ዕድገቱን ተቀብሎ በአምባገነንነት ሥር የመጣ ዕድገት እንደሆነ ለማስመሰል ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል። በኢትዮጵያ ከልማት በፊት ዴሞክራሲ መምጣቱን እየሸፈኑ ለዴሞክራሲ አልባ ልማት ቅድሚያ የሚሰጠው በማስመሰል የአገሪቱን ገጽታ ለማበላሸት የሚደረገው ጥረትም ቀጥሏል።

በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው በዚህ አኳኋን መሠረቱ የተጣለው ከ1983 ዓ.ም እስከ 1990ዎቹ ድረስ በነበሩት የመጀመሪያ ዓመታት ነበር። እነዚህ ዓመታት ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ልማት ከተጓዘችበት ርቀት ይልቅ ዴሞክራሲን ተቋማዊ የአስተዳደር ሥርዓት በማድረግ ረገድ ረጅም ርቀት የተጓዘችባቸው ዓመታት ነበሩ። ይህም ለውጡ ከኢኮኖሚው በፊት በዴሞክራሲው ወይም በፖለቲካ አስተዳደሩ መስክ እንደተጀመረ ያሳያል። በእርግጥም ከምንም ነገር በላይ በዴሞክራሲ እጦት ለሚሠቃዩ ህዝቦችና አገሮች፣ ለውጡን ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ሕጋዊና ተቋማዊ በማድረግ ከመጀመር የበለጠ ነገር አልነበረም፣ የለምም። ምንም እንኳ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ለውጥ በተመጋጋቢነት የሚከናወኑ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ቢሆኑም፣ በብዙ ልማታዊ መንግሥታት የታየው መጀመሪያ ልማቱን አምጥቶ ዴሞክራሲውን ከዓመታት በኋላ ማስከተል ነው። ኮሪያ በአምባገነናዊ አመራር ሥር ልማቷን

አፋጥና ዴሞክራሲውን ከሠላሳ ዓመታት በኋላ ነበር ያስከተለችው፡፡ ታይዋንም እንደዚሁ፡፡ ከእነዚህ ለየት ያለው ሂደት በጃፓን የነበረው ነው፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የለውጡ ሂደት ዴሞክራሲውን በማስቀደም ተጀመረ፡፡ ሥርዓቱ ልማታዊ በመሆኑ ከምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታት የመጀመሪያ ደረጃ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል ቢሆንም ዴሞክራሲን ከልማቱ በፊት ያስቀደመ በመሆኑ ደግሞ በዓይነቱ የተለየ ነው፡፡ ሥርዓቱ የልማታዊነትን አቅጣጫ በተሟላ ደረጃ መላበስ የጀመረው የምሥራቅ እስያ ነብሮችን ታሪክ በማጥናት፣ ይህንኑ ለኢትዮጵያ በሚመች አኳኋን ከቀመረና በገዥው ፓርቲ ውስጥ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሰሞን የተቀሰቀሰውን የጥገኛ ዝቅጠት አደጋ የሚያስወግድ የተሃድሶ እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህም በኢትዮጵያ ልማታዊነት ዘግይቶ የመጣ ከስተት ነው፡፡ ኢህአዴግ ገና ከጠዋቱ ለልማት ትኩረት የሰጠ ቢሆንም በተሟላ የልማታዊነት ንድፈ-ሀሳብ ላይ የተመሠረተው ጉዞ የተጀመረው ከዘጠናዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በብዙ የምሥራቅ እስያ አገሮች መጀመሪያ ላይ የተገነቡት መንግሥታት ልማታዊ ብቻ ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ ግን የሥርዓቱ ገንቢ ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት ሲሆን በቃ፡፡ ይህ አዲስ የፖለቲካ ክስተትና ዕድገት የመጣበትን ሂደት በከፍል ሁለት መመልከት የሚቻል ሲሆን ወደዚህ ከመሸጋገሬ በፊት ግን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ለውጥ ለማምጣት በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት የተካሔደውን ትግልና የተገኘውን ውጤት በአጭሩ ማቅረብ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና መሠረተ - ልማት የተካሔደ ትግልና ውጤቱ፣

ከደርግ መወገድ በኋላ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለመገንባት የተካሔደው ትግል በጣም የተወሳሰበና ኢህአዴግ የአገር ኢኮኖሚ የመምራት ልምድ ሳይኖረው የተጀመረ ሥራ ነበር፡፡ በእርግጥ ድርጅቱ አገር የማስተዳደር ኃላፊነትን ገና ሳይረከብ በአሥር ሺዎች የሚቆጠር ሠራዊትና ሰፋ ያለ ነጻ መሬት የማስተዳደር ኃላፊነትን ተሸክሞ ይህንኑ በብቃት ተወጥቷል፡፡ ነገር ግን በጣም ውስብስብ ችግሮች የሞሉባትን አገርና እንደ አዲስ አበባ ዓይነት ትልቅ ከተማን የማስተዳደር አዲስ ኃላፊነት ከትጥቅ ትግሉ በዓይነቱ የተለየ ነበር፡፡ ስለዚህም የተወሳሰበውን አገር የማስተዳደርም ሆነ ኢኮኖሚውን የመገንባት ተልዕኮ እየወደቀ እየተነሳ፣ ወይም ፈረንጆች "እየሰሩ መማር" /Learning by Doing/ በሚሉት አቅጣጫ መፈጸም ነበረበት፡፡ ኢህአዴግ በፖለቲካው መስክ ጥልቅና በረዥም ጊዜ ትግልና ዴሞክራሲያዊ ባሕል ላይ የተመሠረተ ልምድ የነበረው ድርጅት በመሆኑ ዴሞክራሲን በአጭር ጊዜ ሥር እንዲሰድ ለማድረግ አልተቸገረም፡፡ በኢኮኖሚው መስክ ግን በእርግጥም እየሠራ ከመማር ውጭ ሌላ ዕድልም አማራጭም አልነበረውም፡፡ ይህም ሆኖ ኢህአዴግ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በብቃት

ለማንቀሳቀስ ረጅም ጊዜ እንዳይወስድበት የሚያደርጉት መሠረታዊ ጥንካሬዎች ነበሩት።

የመጀመሪያ ጥንካሬው ድርጅቱ የኢኮኖሚ ሕግጋትን ጠንቅቆ የሚያውቅ ድርጅት መሆኑ ነበር። መለስና የትግል ጓዶቹ እንዲሁም የገነቡት የካድሬ ኃይል ይከተሉት ከነበረው ግራ-ዘመም አስተሳሰብ በመነሳትና በዚህም በመመራት መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግጋትን የተገንዘቡ ነበሩ። በዚህ ላይ የድርጅቱ አመራር በንድፈ-ሀሳባዊ ባሕሉ በመታገዝ ባካሔደው ጥናት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ፣ በተለይ ስለአገሪቱ የወቅቱ የመሬት ይዞታና ይህም ለዕድገት ስለነበረው አስተዋጽኦ ገና ከትጥቅ ትግሉ በፊት ጀምሮ ተግባብቶበት ነበር። በዚህ ላይ በሌሎች አገሮች የተካሔዱ ህዝባዊ አብዮቶች በተለይ በኢኮኖሚ መስክ ያካሔዱትን ግንባታ በማጥናት ከዚህ ሊቀሰም የሚችለውን ያህል ትምሕርት ቀስሟል። የምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታትን ልምድም አጥንቶ ከግራ ዘመም አስተሳሰቡ በመነሳት ተንትኖታል። በትጥቅ ትግሉ የመጨረሻ ዓመታት ታጋይ መለስ ዜናዊ "በኢትዮጵያ የነጻ አገራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ጥያቄ" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ሰነድ፣ ከደርግ ውድቀት በኋላ የምንከተለው የልማትና የአገር ግንባታ አጠቃላይ አቅጣጫና የሚገነባው ኢኮኖሚ መሠረታዊ ባሕርይ ምን ዓይነት እንደሚሆን አመላክቷል። እነዚህ ሥራዎች ከትጥቅ ትግሉ መጠናቀቅ በፊት መከናወናቸው ድርጅቱ አገር የመምራት ኃላፊነትን ሲረከብ ብዙ እንዳይቸገር የሚያደርጉ ነበሩ። ይህም ሆኖ በተጨባጭ አገሪቱን የማስተዳደር ኃላፊነት ሲያዝ የሚያጋጥሙት መልካም ዕድሎችና ችግሮች በንድፈ-ሀሳብ ብቻ የተሟላ ግንዛቤ ሊያዝባቸው የሚችሉ አልነበሩም። ወደተግባር ገብቶ እየሰሩ በመማር ብቻ ሊታወቁ የሚችሉና የሚገባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ የተወሰኑ የመለማመጃ ዓመታትን የሚጠይቁ ነበሩ።

ሁለተኛው የኢህአዴግ ጥንካሬ ድርጅቱ በኢኮኖሚ ግንባታ ጥያቄ ላይ የብዙኃኑን ህዝብ ተጠቃሚነት ማዕከል ያደረገ ድርጅት መሆኑ ነበር። ለኢህአዴግ የማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲና እቅድ ትክክለኛነት መመዘኛ ብዙኃኑ ህዝብ የሚያገኘው ጥቅም ነው። ህዝብን የሚጠቅምና ይህን እያዳበረ ለማስቀጠል የሚያስችል ማንኛውም ፖሊሲና እቅድ ትክክለኛ ነው ተብሎ ይወሰዳል። በጥብቅ ተይዞም በዲሲፕሊን ተግባራዊ ይደረጋል። ማንኛውም የህዝብን ጥቅም የሚጐዳ፣ ወይም ደግሞ ከልክ በላይ የሚያጓትት ፖሊሲና እቅድ ደግሞ የተሳሳተ ለመሆኑ በጥብቅ ይመከታል። ለኢህአዴግ ከህዝብ በላይ ማንም የለም፣ አልነበረምም። በመሆኑም ህዝብን የሚጠቅሙ የልማት አማራጮችን እያፈላለገ በማግኘት በጥብቅ ዲሲፕሊን ተግባራዊ አድርጓል። የራሱን የአፈጻጸም ልምዶች እየገመገመ በአጭር ጊዜ የኢኮኖሚውን የማምረት አቅም አሳድጓል። ይህ የኢኮኖሚ ልማት አመራርን በፍጥነት እንዲማር ያደረገው ተጨማሪ ምክንያት ነበር።

ኢህአዴግ በአስተሳሰብ ደረጃ ገና ከጅምሩ የብዙኀን ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም ለማስከበር በወገናዊነት ከመንቀሳቀሱ ጐን ለጐን "ጥቂቶች ካለፈላቸው ብዙኀኑም ጊዜውን ጠብቆ ያልፍላቸዋል" የሚለውን የኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ ከሽግግሩ ወቅት ጀምሮ በጥብቅ ተቃውሞታል። ይህ በብዙ ኢኮኖሚስቶች ዘንድ "ተንጠባጥቦ የሚቃመስ ኢኮኖሚ" (Trickle Down Economics) በመባል የሚታወቅ የኒዮ-ሊበራል መርህ፣ መጀመሪያ ጥቂቶች በጣም እንዲበለጽጉ ማድረግን የሚያስቀድም ነው። አስተሳሰቡ "በጣም ጥቂት ባለሀብቶች በሚገባ ከበለጸጉ ብቻቸውን ስለማይበሉ በተራዘመ ሂደትም ቢሆን ሌሎችን ይዘው ይወጣሉ" የሚል ቅኝት ያለውና በፍጥነት ከድኅነት መላቀቅ ባለባቸው እንደኢትዮጵያ ባሉ አገሮች የድኅነትን እድሜ በማራዘም የህዝብን ስቃይ የሚያባብስ ነው። በመሆኑም ይህን አማራጭ ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር የኢኮኖሚ ማሽቆልቆሉን የሚገታው ካለመሆኑም በላይ የህዝቡ ጐስቋላ ሕይወት ተባብሶ እንዲቀጥል ያደርጋል። የምሥራቅ እስያ አገሮች ከአምሳ ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ መላ ህዝባቸውን ወደብልጽግና ባሸጋገሩበት፣ አሁን ደግሞ ቻይና በሠላሳ ሰባት ዓመታት ውስጥ ወደሰባት መቶ ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ወደመካከለኛ ገቢ ባሸጋገረችበት ዘመን ይህን የኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ መመሪያ ማድረግ ለህዝብ ደንታ ቢስ ከመሆን ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ከዚህ በመነሳት ኢህአዴግ ይህን አደገኛ ኒዮ-ሊበራል አቅጣጫ ገና ከማለዳው በጽናት ተቃውሞታል። ከዚህ በኋላ ባለው ሂደትም ድርጅቱ የሚመርጥና የሚከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ትክክለኛ መሆን አለመሆን ከሚለካባቸው መስፈርቶች አንዱና ዋነኛው የአገሪቱ ብዙኀን ህዝብ በፍጥነት ተጠቃሚ ማድረግ አለማድረጉ ሆነ። እየሠራ በመማር ሂደት በሚያልፍበት ሁሉ የፖሊሲ ጠቃሚና ጐጂነት መለኪያው የህዝብን ኪስ የመሙላት ወይም የማጉደል ጉዳይ መሆኑ በፍጥነት እንዲማርም ሆነ ለውጥ እንዲያመጣ ያስቻለው ዋናው ጉዳይ ነበር።

አገር የማስተዳደር የተከማቸ ልምድ ያልነበረው ድርጅት፣ በአጭር ጊዜ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ ያስቻለው ሦስተኛው ምክንያት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ማዕከል ያደረገ ፖሊሲ መከተሉ ነው። በዘመነ ግሎባላይዜሽን አገሮችን የሚገጥማቸው አንዱና ከባዱ ፈተና የሚነድፏቸው ፖሊሲዎች መሠረት አገራዊ ጥቅም ወይስ የድንበር የለሽ ኩባንያዎች ጥቅም መሆን አለመሆኑ ነው። በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስር ውስጥ መግባት አማራጭ የሌለው በሆነበት በዚህ ዘመን፣ እንደ ኢትዮጵያ ለመሰሉ ድሃና ኋላቀር አገሮች ብዙ የተጠቃሚነት አማራጮች የሉም። እጅግ ሰፊው ዕድል ነገሮች ለዓለም አቀፍ ካፒታል ጥቅም ተገዥ በሆነ አቅጣጫ የሚጓዙበት ነው። ዓለም አቀፍ ካፒታል ባለው የዳበረ ተሞክሮ፣ የፋይናንስ አቅምና የዓለም አቀፍ ሕግ ድጋፍ ተማምኖ፣ ከድሃና ኋላቀር አገሮች ጋር ያለውን ግንኙነት የእርሱን ጥቅም በሚያሰፋ አኳኋን የተዋቀረ እንዲሆን አድርጐታል። በአንጻሩ ድሃና ኋላቀር አገሮች

የራሳቸውን ጥቀም ሣዕከል አድርገው ይህንኑ ሲያበጉ የሚተውበተ የጉይነ ንበሃሥ ሆነ የሐገ ድጋጉ የላቸውም:: ያላቸው ልምድም ዝቅተኛ ነው:: በመሆኑም በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስር ውስጥ ሲገቡ በሚጠቀሙበት ሳይሆን በሚጐዱበት ሥርዓት ውስጥ ለመግባት ይገደዳሉ::

ድሃና ያልበለጸጉ አገሮች ከዚህ ኒዮ-ሊበራል አቅጣጫ ባፈነገጠ አኳኋን በትስስሩ ውስጥ ይገቡ ዘንድ፣ አገራዊ ጥቅሙን በትክክል የተገነዘበና ይህንንም የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍሎ ለማስጠበቅ የቆመ መንግሥት የግድ ሊኖራቸው ይገባል:: ግሎባላይዜሽን የሚከፍታቸውን መልካም ዕድሎች አሟልቶ ለመጠቀም፣ የሚደቅናቸውን ፈተናዎች ሁሉ ደግሞ በብስለት ለማለፍ የተዘጋጀና ጠንካራ አገራዊ ስሜት ያለው መንግሥት መኖሩን የግድ ይላል:: ለዚህ ሲባል ኢትዮጵያን የሚጠቅሙ የፖሊሲ አማራጮችን ሁሉ አጥብቆ የሚይዝና የሚያስፈጽም፣ በአንጻሩ ደግሞ ኢትዮጵያን የሚጐዱ አማራጮችን በሙሉ አሻፈረኝ የሚል ጠንካራ የአርበኝነት ስሜት ያለው መንግሥት መኖሩን ይጠይቃል:: ኢትዮጵያን የሚጠቅም ሁሉ የግድ ሌላውን መጉዳት ስለሌለበት፣ በጋራ ጥቅሞች የሚያምንና ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ ፖሊሲ መከተል የሚችል አስተዋይ መንግሥት መሆንንም ይሻል:: ሌሎችን በማደኽየት የመበልጸግን የዜሮ ድምር ዓለም አቀፍ ግንኙነት አምርሮ የሚጠላና ራሱንም ከተመሳሳይ አስተሳሰብና ግንኙነት ያጸዳ አገራዊ መንግሥት መሆን አገራዊ ጥቅምን ለማስቀደም ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው::

ኢህአዴግ እነዚህ ሦስት ጥንካሬዎች የነበሩት ድርጅት ነው:: የኢኮኖሚ ሕግጋትን ጠንቅቆ የተገነዘበ፣ ህዝባዊ ወገናዊነትና አገራዊ ተቆርቋሪነት የነበረውና ይህንም ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በተግባር ያሳየ ድርጅት ነው:: በዚህ ላይ መለስን የመሰለ ምጡቅ መሪ ነበረው:: ስለሆነም ኢትዮጵያን የመሰለች ብዙ ህዝብና ሥር የሰደዱ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሏትን አገር የማስተዳደር ኃላፊነት ሲረከብ የተከማቸ ልምድ ባይኖረውም ኢኮኖሚው በአጭር ጊዜ እንዲያንሰራራ ለማድረግ ጊዜ አልወሰደበትም:: በዚህ ምክንያት በሽግግሩ ወቅትና ከዛም በኋላ ባሉት ጥቂት ዓመታት የአገሪቱ ኢኮኖሚ በአማካይ አምስት በመቶ ማስመዘገቡ ዕድገት የዚህ ውጤት ነው። እንደኢትዮጵያ በሽግግር ውስጥ የሚያልፉ ብዙ አገሮች ከአንዱ ቀውስ ወደሌላው ሲረማመዱ፣ በኢህአዴግ የተመራችው ኢትዮጵያ ለአሥር ዓመታት በአማካይ የአምስት በመቶ ዕድገት አስመዘገበች:: ይህ በአፍሪካ እንደቦትስዋና ከመሳሰሉ ጥቂት አገሮች በስተቀር በሌሎች ያልታየ ዕድገት ነው:: ይህም በኢህአዴግ የተመራው የሽግግር ሂደትና ቀጥሎ የተመሠረተው ቋሚ መንግሥት በተከተሉት ፖሊሲ የተመዘገበ ውጤት ነበር:: ይህንንም በወቅቱ ተነድፈው ተግባራዊ ከተደረጉት ፖሊሲዎች በመጀመር መመልከት ይቻላል::

ኢህአዴግ የሽግግር መንግሥት በተመሠረተ ማግስት አገሪቱን በልማት አቅጣጫ ለመምራት ይቻል ዘንድ የወሰደው የመጀመሪያው እርምጃ የሽግግር ወቅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማውጣት ነበር:: ፖሊሲው የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በመተንተን የኢኮኖሚ ልማት ግቦቹን

በጠራ አኳኋን በማስቀመጥ የተዘጋጀ ነው። እንደሚታወቀው ኢህአዴግ አገሪቱን ከደርግ እጅ አላቅቆ ሲረከብ ኢኮኖሚው የእዝ ባሕርይ እንደተላበሰ ነበር። የደርግ መንግሥት በአገር ውስጥ በደረሰበት ተቃውሞና በዓለም አቀፍ ሁኔታዎች አስገዳጅነት በ1982 ዓ.ም. የእዝ ኢኮኖሚ ፖሊሲውን በቅይጥ ኢኮኖሚ ቀይሬዋለሁ ቢልም በአንድ ዓመት የመጣ መሠረታዊ ለውጥ አልነበረም። ያኔም ቢሆን አርሶ አደሩ በእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት (እሰገድ) አማካይነት መመዝበሩ አልቀረለትም። የግሉ ሴክተር በተወሰነ ደረጃ እንዲንቀሳቀስ ቢፈቀድለትም የካፒታል አቅሙ ደካማና በሥርዓቱ ላይ የነበረው አመኔታም እጅግ የተዳከመ ነበር። ሌላው ቀርቶ ራሱ ከጉልት ንግድ ጀምሮ ወሳኝ ተቋማትን የተቆጣጠረው የደርግ መንግሥት በጦርነቱ ምክንያት በኢኮኖሚው ውስጥ የነበረው ተሳትፎ እጅጉን ተዳክሟል። ስለዚህም የአገሪቱ ኢኮኖሚ የእዝ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ከተዘመረለት ቅይጥ ኢኮኖሚ በኋላም በመሠረቱ ያልተቀየረ፣ ለዛውም ደግሞ የማሽቆልቆል ጉዞውን ያላቋረጠ የእዝ ኢኮኖሚ ነበር።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሽግግሩ ወቅት በተቀረጸው የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት አገራዊውን ኢኮኖሚ ሁለት የማይነጣጠሉ ግቦች በመያዝ መገንባት ተጀመረ። የመጀመሪያው የኢኮኖሚ ግብ የእዝ ኢኮኖሚውን ደረጃ በደረጃና ከባድ ምስቅልቅል በማያስከትል አኳኋን ወደገቢያ ኢኮኖሚ መቀየር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከማሽቆልቆል ወጥቶ በዕድገት ጐዳና እንዲረማመድ ማድረግ ነበር። ይህም ሆኖ ሁለቱም ቀላል ግቦች አልነበሩም።

ከእዝ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ የተደረገው ሽግግር በብዙ አገሮች ከባድ ፈተና የደቀነ ነው። ይህም ሽግግሩ የግድ መካሔድ የነበረበት በመሆኑና ሂደቱ ህዝባዊ ወገናዊነት ባልነበራቸው ይልቁንም የራሳቸውን ጥቅም በሚያስቀድሙ ኃይሎችና በዓለም አቀፉ የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮት ተፅዕኖ ሥር የወደቀ ከመሆኑ የመነጨ ነው። የገበያ አክራሪነት መርሆዎችን በእጅጉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚሻው ኒዮ-ሊበራሊዝም በምዕራቡ ዓለም ላይ የበላይነት ከተጐናጸፈ በኋላ ባልበለጸጉ አገሮች ላይ ርዕዮቱን ለመጫን መላ አቅሙን ሲያረባረብ ቆይቷል። በዚህ ምክንያት ከእዝ ወደገበያ መሸጋገር በመረጡት አገሮች ወደገበያ ኢኮኖሚ የሚካሔደውን ሽግግር በቀውስ የተሞላ አድርጐታል። ይህ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችን በተለይ ደግሞ ሶቭየት ሕብረትን ባልተወለደ አንጀቱ ለማፈራረስና አገሪቱ ያላትን እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው የተፈጥሮ ሀብት በቁጥጥሩ ሥር ለማስገባት ካደረገው እንቅስቃሴ ለመገንዘብ ይቻላል።

ኒዮ-ሊበራሊዝም ሶቭየት ሕብረትን በተካቻት ታላቋ ሩስያ በፕሬዚዳንት የልሲን ዘመን የተፈጠረውን የአመራር ምስቅልቅልና አገራዊ ግራ መጋባት መጠቢያ በማድረግ፣ ወደገበያ ሥርዓት የሚደረገው ሽግግር ካፒታሊስታዊ ቅኝት ያለው እንዲሆን አድርጓል። አልፎ ተርፎም ሂደቱ የአገሪቱን አንጡራ ሀብት በሽያጭ ለምዕራቡ ዓለም ቱጃሮች እንዲተላለፍም አስገድዷል። በእነ ጀፍሪ ሣክስ መሲሕነት በሩስያ የተካሔደውን ይህን ኒዮ-ሊበራል ጥቃት

በግንባር ቀደምትነት የመሩት የዓለም ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ሲሆኑ፣ ሃያኛው ከፍለ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት የተካሔደው ይኸው የፕራይቬታይዜሽን ዘመቻ፣ ከሪስቲያ ፍሪላንድ(2000) በተባለችው ፀሐፊ አገላለጽ "የከፍለ ዘመናችን ታላቁ ሽያጭ" በሚል ርዕስ ባሳተመችው መጽሐፍ "በድህረ ኮሙኒዝም ሩስያ በዋነኛነት የተመሩበት የለውጥ ሀሳብ በብድር ላይ የተመሠረተ ሼር (Loans-for-shares) ብለው የሰየሙት የተወሳሰበ የአገራዊ ሀብት ሽያጭ (Privatization) ያስከተለው የተወላገደ ካፒታሊዝምንና በድኅነት የተዳቀቀችና የተማረረች አገር ብቻ ነው"[34] በመባል እስከመሰየም የደረሰ ነው:: ጉዳዩ የህዝብ ሀብትን አልባሌ በሆነ ዋጋ ወደግለሰቦች በማዘዋወር ብቻ የሚያበቃ ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር:: ታላቋ ሩስያ ዳግም አገር ሆና እንዳታንሰራራ ቆርጠው የተነሱት ምዕራባውያን ሌሎች የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦችን እንድትጋት ያስገደዱበትም ነበር:: በዚህ መሠረት የፕሬዚዳንት የልሲን መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ቁጥጥር ችሎታውን እንዲያጣ ተደረገ:: መንግሥት የገንዘብ ፖሊሲውን መቆጣጠር ተስኖት በእነ ጀፍሪ ሣክስ መሪነትና አስፈጻሚነት "ነውጠኛ ፈውስ" የተባለውን የፖሊሲ ምክረ-ሀሳብ በላይ በላዩ ተግባራዊ ለማድረግ ተገደደ:: ይህም በሩስያ ከባድ የዋጋ ግሽበትን አስከተለ:: የዋጋ ግሽበቱ የሩስያውያንን ሀብት ወደግለሰቦችና የምዕራቡ ዓለም ኩባንያዎች የማሸጋገር ውጤት ስለነበረው የሩስያን ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ ያደኸየ ሲሆን፣ ምዕራባውያኑ ደግሞ ከፍተኛ ጥቅም አግኝተውበታል::

በዚህ መንገድ ነውጠኛው ፈውስ ተግባራዊ በተደረገባት ሩስያ ድኅነት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ተስፋፍቷል:: የታላቋ ሩስያ ህዝብ በተስፋ መቁረጥ ተመትቶ ነገረ ሥራው ሁሉ ቮድካ ወደመጨለጥ ተቀይሮ ነበር። አልፎ ተርፎም በዬቪድ ሐርቬይ "ሕጋዊ የመገበያያ ገንዘብ የነበረው ሩብል በ1990ዎቹ በኒዮ-ሊበራሊዝም ምክረ-ሀሳቦች በተመራው ሪፎርም ሳቢያ ለከፍተኛ ግሽበት በመጋለጡና የንግድ ሥርዓቱ በመፈራረሱ ቮድካ ተወዳጁ የሩስያውያን የአልኮል መጠጥ ከመሆን አልፎ በጠርሙሶች የተሞላ ቮድካ የአገሪቱ መገበያያ ሆኖ ነበር።"[35] ሴቶች በስፋት ወደዝሙት ኢዳሪነት ተሸጋገረዋል:: ብዙ ሰዎች የኤች. አይ. ቪ ኤድስ ሰለባ ሆነዋል:: በዚህ የተነሳ በሩስያ ከሚወለደው ይልቅ የሚሞተው ተበራከቶ አገሪቱ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የህዝብ ዕድገት ምጣኔዋ ከዜሮ በታች እስከመውረድ ደርሷል:: የዚህ አደገኛ ፖሊሲ ዳፋ በሩስያ የፕሬዚዳንት የልሲን መንግሥት በነበረበት ጊዜ ብቻ የተወሰነ አልነበረም:: ቭላድሚር ፑቲን በሥልጣን ላይ ከወጡና የሩሲያን ታላቅነት እንደገና ለመገንባት ቆርጠው ከተነሱ በኋላም ለተወሰነ ጊዜ ቀጥሏል:: በመሆኑም አገሪቱ እንደገና ከዜሮ በላይ የሚታይ የህዝብ ቁጥር ዕድገት ማሳየት የጀመረችው እ.ኤ.አ. ከ2014 በኋላ ብቻ ነበር:: ይህም የኒዮ-ሊበራሊዝም ምስቅልቅል አገሮችን እስከ ወዲያኛው የሚገ፦ዳ ተፅዕኖ ያለው እንደሆነ አመላካች ነው:: ኢትዮጵያን በመሰሉ አገሮች ሊደገም የሚይገባው ስህተት የተፈጸመበት ይህ ሽግግር፣

ከእዝ ኢኮኖሚ ለመላቀቅ የሚደረገው ጥረት፣ በትክክለኛ አስተሳሰብና ፖሊሲ ካልተመራ በስተቀር፣ ምንጊዜም የተመሰቃቀለ አገር መፍጠሩ እንደማይቀር ትልቅ ትምሕርት የሚቀሰምበት ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያ ከእዝ ኢኮኖሚ ወደገበያ መር ኢኮኖሚ የምታደርገው ሽግግር ከፍተኛ ጥንቃቄ ያልተለየው መሆን ነበረበት፡፡ በጥድፊያ ሊበራላይዝ ከማድረግ ተቆጥቦ ነገር ግን በእርግጠኛነት ሊበራላይዝ የማድረግ አቅጣጫን ደረጃ በደረጃና ከከፍተኛ ጥንቃቄ ጋር የሚከተል መሆን ነበረበት፡፡

በኢትዮጵያ ከእዝ ወደገበያ ኢኮኖሚ በተደረገው ሽግግር ቅድሚያ የተሰጠው የገጠሩን ኢኮኖሚ ከመንግሥት ቁጥጥርና መረን የለቀቀ ጣልቃ ገብነት ለማላቀቅ ነው፡፡ ይህ ሳይደረግ ዋናው አምራች ኃይል በነጻነት ሊንቀሳቀስ አይችልም ነበር፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የተመሠረተው በግብርና ላይ በተለይም በአነስተኛ አርሶ አደር ማሳ ላይ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ደርግ ሥልጣን ላይ በነበረባቸው ዓመታት ሁሉ አርሶ አደሩ ምን ማምረት እንዳለበት፣ ያመረተውን ሰብል ለማን መሸጥ እንዳለበትና በዚህ የግብይት ሂደት ደግሞ ምን አይነት የገቢ ከፍፍል መኖር እንዳለበት የሚወሰነው በመንግሥት ነበር። በመሆኑም ደርግ ለራሱ የፈለገውን ካስቀረ በኋላ ለአርሶ አደሩ የተወሰነ ምርት የሚተውበት ሥርዓት ነበር፡፡ ሌ/ኮለኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዘጠነኛ ስብሰባ ላይ፡-

> “የገበሬው በአምራቾች ሕብረት ሥራ ማኅበር መደራጀት በወቅቱ ባለው ቴክኖሎጅ በመጠቀም የሚታረሰው መሬት ስፋትም ሳይጨምር የግብርናን ምርት ለማሳደግ የሚያስችልባቸው በርካታ የአሰራር ለውጦች ያስገኛል፡፡ ከእነዚህም አንደኛው የገበሬውን አመራረት በማዕከላዊነት ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ማስቻሉ ነው፡፡...በዚህም የቁጥጥር ዕድል በመጠቀም በመላ አገሪቱ በጥቅም ላይ ከዋለው መሬትና ገበሬ እጅግ ቢያንስ ሊገኝ የሚችለውን የምርታማነት ደረጃ ለመወሰንና ይህንንም በሥራ ላይ ሊያውሉ ባልቻሉት ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት መሬት ጦም እንዳያድር ብቻ ሳይሆን፣ ከጊዜ ወደጊዜ ምርታማነት የሚያድግባቸውን ሥልቶች ሥራ ላይ በማዋል የግብርና ምርትን ለማሻሻል ይቻላል፡፡ ዛሬ ባለው አሠራር የገበሬውን ምርት ዕድገት ለመቆጣጠር እንዳልተቻለው ሁሉ የገቢውንም አጠቃቀም ለመቆጣጠር [አጽንዖት የተጨመረ] አልተቻለም፡፡”[36] ብለው ነበር፡፡

ከዚህ አገላለጽ ደርግ የምርት ሂደቱን ብቻ ሳይሆን፣ አርሶ አደሩ ምርቱን እንዴት ሊጠቀምበት እንደሚገባ ጭምር ለመቆጣጠር ሀሳብ እንደነበረው ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የደርግ መንግሥት ከአርሶ አደሩ ላይ በልዩ ልዩ ሥልቶች እየታገዘ ምርቱን ሲነጥቀው የቆየ ቢሆንም፣

በዚህ ብቻ የምዝበራ ፍላጐቱን ማርካት አልቻለም:: ዋጋው እያሻቀበ የሔደውን ጦርነት ግዙፍ ወጭ፣ ከዚያ በፊት በተጠቀመባቸው የንጥቂያ ሥልቶች ብቻ በመተማመን መሸፈን አልችልም ብሎ በማሰብ የአርሶ አደሩን የገቢ አጠቃቀም እስከመቆጣጠር ድረስ የሚዘልቅ ጨካኝ እርምጃ ለመውሰድ ተዘጋጅቶ ነበር::

ኢህአዴግ የደርግን መንግሥት ለማስወገድ በተቃረበበት በመጨረሻዎቹ ዓመታት "የአርሶ አደሩ የምርት ነጻ ተጠቃሚነት መብት ይከበር!" የሚል መፈከር ቀርፆ በመንቀሳቀሱ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የአርሶ አደሩን ከፍተኛ ድጋፍ ሊያገኝ ችሏል:: ከደርግ ውድቀት በኋላ ደግሞ የአርሶ አደሩን የምርት ነጻ ተጠቃሚነት በተግባር ላይ አዋለ:: በዚህ መሠረት በእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት /አሰገድ/ አማካይነት ይካሔድ የነበረው ምዝበራ ሳይውል ሳያድር እንዲቋረጥ አደረገ:: አሰገድ ባይፈርስም በመንግሥት ጡንቻ ተማምኖ ገበሬውን በማስገደድ ምርት እንዳይገዛ ተከለከለ:: አርሶ አደሩ ምርቱን በፈለገው ጊዜ፣ ቦታና ዋጋ እንዲሁም ለፈለገው ግለሰብ የመሸጥ ነጻነት ተጐናጸፈ:: መንግሥት ከአርሶ አደሩ ላይ እህል በሚገዛበት ጊዜ በገበያ ዋጋና በግልጽ ውድድር ላይ በመመሥረት ብቻ እንዲሆን ተደረገ:: በዚህ እርምጃ አርሶ አደሩ ምርቱን ሸጦ ለውጦ የሚያገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ ወደኪሱ መግባት በመጀመሩ የገጠሩ ኢኮኖሚ ቅጽበታዊ በሚባል ፍጥነት ከእዝ ወደገበያ መር ለመሸጋገር ቻለ:: ሚሊዮኖች በአንዴ ከእዝ አኮኖሚ ቁጥጥር ነጻ ወጡ::

ይህ እርምጃ በኢትዮጵያ ገጠሮች የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የገበያ ኢኮኖሚን እንዲቀላቀሉ አስቻለ:: ይህም ሲሆን በምዕራቡ ዓለም እንደተመለከትነው አርሶ አደሮች ከማሳቸው በኃይል እየተነቀሉ የፋብሪካ ሠራተኛ በሚሆኑበት መንገድ ሳይሆን፣ በማሳቸውና በምርታቸው ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያደርግ ሁኔታ ነው:: ከዚህ በመነሳት ሲታይ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ትንሳኤ በገጠር የብዙኃኑን ህዝቦቿን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አኳኋን የተጀመረ ነው:: የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከእዝ ወደገበያ በማሸጋገሩ ሂደት ብዙኃኑ ኢትዮጵያውያን፣ በተለይ ደግሞ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሮች የሽግግሩ ሰለባ እንዳይሆኑ የተወሰዱት እነዚህ እርምጃዎች በኢትዮጵያ መጻኢ ዕድልና ጉዞ ላይ ከምንም ነገር በላይ ተፅዕኖ አድራጊዎች ነበሩ:: በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ላይ በመተማመን የሚገነባው የገበያ ሥርዓት፣ በርግጥም ከምዕራቡ ካፒታሊስት አቅጣጫ በዓይነቱ የተለየ መሆኑ የማይቀር ነበር:: ኢህአዴግ ሊበራላይዝ ለማድረግ በተገደደበትም ወቅት ለውጡ ብዙኃኑን ህዝብ በሚጠቅም እንጂ በማይጐዳ መንገድ እንዲጀመር ማድረጉ እዚያው ሳለም ለብዙኃኑ ተቆርቋሪ በመሆን መጀመሩን የሚያረጋግጥ ነው::

መሬት የህዝብ ሆኖ አርሶ መጠቀም ለሚፈልግ ሁሉ መታደሉና የምርት ነጻ ተጠቃሚነት መብት መከበሩ ገጠሩን ከእዝ ኢኮኖሚ ለማላቀቅ የመጀመሪያው እርምጃ ቢሆንም፣ ብቻውን ግን

ተፈጣጊሠ ነ ዐድገተ ለሚነበመዝገብ የሚያስተል አልነበረም፡፡ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ለዘመናት ከሚጠቀሙበት ተለምዷዊ የግብርና ሥርዓት እንዲላቀቁና ወደዘመናዊነት እንዲሸጋገሩ ማድረግም አስፈላጊ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው በደርግ አገዛዝ አርሶ አደሩ ለዘመናት ሲጠቀምበት የነበረው አስተራረስ አልተለወጠም፡፡ መንግሥት ከአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ይልቅ ለመንግሥት እርሻዎች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥ ስለነበር፣ በአገሪቱ የአርሶ አደሩን ማሳ ምርታማነት ለማሳደግ የተደረገው ጥረት በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በሔክታር የሚገኘው አማካይ የምርት መጠን ከ9 ኩንታል የሚበልጥ አልነበረም፡፡ ይህ በአማካይ ስድስት አባላት ላሉት የአንድ አርሶ አደር ቤተሰብ በነፍስ ወከፍ 150 ኪሎ ዓመታዊ ምግብ ለማቅረብ የሚያስችል ሲሆን፣ ዓመታዊ ምርቱ ወደእለታዊ ቀለብ ሲመነዘር ለአንድ ሰው በቀን የ410 ግራም እህል አቅርቦት ማለት ነው፡፡ ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ በድርቅና በተፈጥሮ አደጋ ለተጐዱ ሰዎች ከሚሰጠው የአስቸኳይ ጊዜ የ500 ግራም የእህል እርዳታ ያነሰ የምግብ አቅርቦት ለማሟላትና ሰዎችን በሞትና በሕይወት መካከል የሚያቆይ ቀለብ ብቻ ነበር፡፡ በረሃብ ምክንያት በሞትና በሕይወት መካከል የሚኖር ህዝብ በበዛባት ኢትዮጵያ፣ አርሶ አደሩ የመሬትና የምርት ነጻ ተጠቃሚነት መብቱን እንዲጐናጸፍ ከተደረገ በኋላ ምርታማነትን በቀጣይነት ለማሳደግ ከሚያስችል ድጋፍ ውጭ ረሀብን ማስወገድ አይቻልም ነበር፡፡

ይህ እንዲሆን ግን ኢትዮጵያ ግብርናን ለማልማት የምትከተለው አቅጣጫ ካሉት ብዙ አማራጮች መካከል በጥንቃቄና በብስለት መመረጥ ነበረበት፡፡ ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ግብርና "በአነስተኛ እርሻዎች ወይስ በሰፋፊ እርሻዎች ላይ ተመሥርቶ ማደግ ይገባዋል?" የሚለው ጥያቄ፣ ቀጥሎም "ጉልበትና መሬት ተኮር ወይስ ካፒታልና የኃይል ምንጭ ተኮር/ Energy Intensive/ በሆነ መንገድ መልማት አለበት" የሚለው ጉዳይ በጥንቃቄ መመለስ ነበረባቸው፡፡ እነዚህ የልማት አማራጮች የሚያተኩሩበት ጉዳይ የተለያየ እንደሆነው ሁሉ የሚያስገኙት ውጤትም በእጅጉ የተለያየ ነው፡፡

ግብርናው በአነስተኛው አርሶ አደር ትንንሽ ማሳዎች በመተማመን የሚለማ ከሆነ ከሁሉ በፊት የአርሶ አደሩን ጉልበት በሰፊው መጠቀመ አይቀርም፡፡ ይህም በአንድ በኩል የጉልበት ብክነትን ለማስወገድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ የካፒታል አቅርቦት ባይኖርም በዚሁ ጉልበት በአግባቡ በመጠቀም ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ነው፡፡ በአንጻሩ ግብርናው በሰፋፊ እርሻዎች ላይ የሚመሠረት ከሆነ፣ በተለይ ብዙ ህዝብ በሚኖርባቸው ደጋማና ወይና ደጋማ የአገሪቱ ክፍሎች፣ በቅድሚያ አርሶ አደሩን ከመሬቱ በማፈናቀል ጥቂት ባለሀብቶች ሰፋፊ መሬት እንዲይዙ ማድረግን የግድ ይላል፡፡ ህዝብ በማይኖርባቸው ቆላማ አካባቢዎች የሚፈናቀሉ አርሶ አደሮች ባይኖሩም በደጋና ወይና ደጋ አካባቢዎች ግን አርሶ አደሩን ከማፈናቀል ውጭ ስለሰፋፊ እርሻዎች ማሰብ አይቻልም፡፡ ይህ የማፈናቀል ተግባር ከተፈጸመ መለስ በ1994ዓ.ም. ባዘጋጀው

የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ፣ በተራቴዲና ታክቲኮተ በነድ ላይ አንደገለጸው አብዛኛው ህዝብ በሚኖርባቸው በእነዚህ የአገሪቱ ክፍሎች የአርሶ አደሩ ጉልበት የሚሰማራበት መሬት እንዲያጣ በማድረግ የጉልበት ብክነትን ሊያስከትል ይችላል። ሰፋፊ እርሻዎች ለመፍጠር ሲባል የሚደረገውን አርሶ አደር የማፈናቀል እርምጃ ተከትሎም ሥራ የፈታው ጉልበት በጥቅም ላይ የሚውልበት አማራጭ ካልተገኘ የተፈናቀለው ህዝብ አቅም መባከኑ አይቀርም።

ከዚህ አኳያ ያለው አማራጭ ሁለት ሲሆን፣ አንደኛው አርሶ አደሩን ከመሬቱ ካፈናቀሉ በኋላ ለአዳዲሶቹ የመሬት ከበርቴዎች ተቀጣሪ ሆኖ ጉልበቱን እንዲያንቀሳቅስ ማድረግ ነው። ይህ አማራጭ የንብረት በተለይ ደግሞ የመሬት ባለቤትነትን ከማዛወር ውጭ በጉልበት አጠቃቀም ረገድ የሚያመጣው አንዳችም ጭማሪ የለም። ይልቁንም አርሶ አደሩ መሬቱን ለነጠቀው ባለሀብት አገልጋይ መሆኑን በመጥላት የምርት እንቅስቃሴውን ማዳከሙ እንደማይቀር በልዩ ልዩ ጥናቶች የተረጋገጠ ነው። ጆ ስቱድዌል አንድ የጃፓን ከፍተኛ የግብርና ባለሥልጣን እ.ኤ.አ በ1928 በሁለቱ መካከል ስላለው ልዩነት የሰጠውን የምስክርነት ቃል፡-

> "ባለቤት በሆነ አምራች አርሶ አደርና ጭሰኛ አምራች በሆነ ገበሬ መካከል ከፍተኛ የምርታማነት ልዩነት አለ። በሕይወታቸው አንድም ቀን ማረሻ ነክተው የማያውቁ የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎች አዝመራውን በጨረፍታ በመመልከት ብቻ መሬቱ በጭሰኛ ወይም የመሬቱ ባለቤት በሆነ አምራች የሚለማ እንደሆነ ለመናገር ይችላሉ"[37] በማለት አቅርቦታል።

ከዚህ በመነሳት አርሶ አደሩን ለሰፋፊ እርሻዎች ሲባል ከመሬቱ ማፈናቀልና የባለሐብቱ ተቀጣሪ ማድረግ የግብርና ምርታማነትን በሚፈለገው ደረጃ እንደማይጨምር ለመገንዘብ ይቻላል። ጃፓን በ1930ዎቹ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ መሬት የማከፋፈል ተግባር እንድታከናውን የገፋፋት በአነስተኛ አርሶ አደር ባለቤትነት የሚለማ መሬት የተሻለ ምርታማ እንደሆነ ማረጋገጧ ነበር።

ይህ አማራጭ ምርታማነትን አያሳድግም በሚል እሳቤ፣ አርሶ አደሩን በእርሻ ማሽነሪዎች የመተካት አማራጭ ከተወሰደ ደግሞ ጉልበት ሥራ በመፍታቱ ምክንያት ገጠሩን ለቆ ወደከተማ መሰደዱ የማይቀር ይሆናል። በከተሞች ይህን ጉልበት ሊጠቀምበት የሚችል የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ የተስፋፋ ከሆነ፣ ከመሬቱ የተፈናቀለው አርሶ አደር ሳይባክን ወደልማት ሊያመራ ይችላል። ይሁንና እንደኢትዮጵያ በመሰሉና ኢንዱስትሪ ባልተስፋፋባቸው አገሮች፣ ከገጠር የፈለሰውን ጉልበት ሙሉ በሙሉ ለመቀበልና ለማስተናገድ የሚችል አስቀድሞ የለማ ዘርፍ በከተሞች አይገኝም። ስለዚህም ለሰፋፊ እርሻዎች ሲባል ከመሬት የሚፈናቀለው አርሶ አደር ከምርት ተግባር ተነጥሎ በከተሞች በሥራ አጥነት የሚባክን ሊሆን ይገደዳል። በብዙ

አገሮች ለሰፋፊ እርሻዎች ሲባል ከእርሻ ማሳው የሚፈናቀል የገጠር ህዝብ በከተሞች የሥራ አጥነት ሰለባ ሲሆን ይታያል። ይህም እንደገና ሥራ አጥነት የሚፈጥራቸው የወንጀልና ዝሙት ችግሮች እንዲበራከቱ ያደርጋል። ስለሆነም በኢትዮጵያ በሰፋፊ የህብታም እርሻዎች ወይስ በአነስተኛ የአርሶ አደር ማሳዎች ላይ የተመሠረተ የልማት አማራጭ የመከተል ጉዳይ በጥንቃቄ ሊወሰን የሚገባው እነዚህን የመሳሰሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችና ሥጋቶችን የሚያስነሳ በመሆኑ ነው።

የቴክኖሎጂ ምርጫም ከውጤት አኳያ ተመሳሳይ ተፅዕኖ ያለው ነው። ከሰፋፊ እርሻዎች ጋር ተያይዞ ጉልበትን የሚተካ ወይም ካፒታል ተኮር ማሽነሪ በስፋት መጠቀም አንድ አማራጭ ነው። ይህ አማራጭ ከተወሰደ ጉልበት በማሽነሪ ይተካና ከልማት አውድማ እንዲወጣ ያደርጋል። እዚህም ላይ፣ በከተሞች ይህን ሥራ የፈታ ጉልበት ሙሉ በሙሉ ወደሥራ ለማሰማራት የሚችል ምርታማ ዘርፍ ካልተስፋፋ፣ ከገጠር የተፈናቀለው ሰብዓዊ ኃይል ሥራ አጥ ለመሆን ይገደዳል። በአንጻሩ በአነስተኛ አርሶ አደር ማሳ በመተማመን ብቻ ሳይወሰኑ፣ የአርሶ አደሩን ጉልበት በሚያመክኑ ሳይሆን በሚደግፉ ጉልበት ተኮር ማሽነሪዎች በመታገዝ መሬቱን ማልማት ከተቻለ ምርታማነትን በአጭር ጊዜ ለማሳደግ ይቻላል። ሥራ አጥነትና ተዛማጅ ማኅበራዊ ችግሮች ሳያስፋፉ ኢኮኖሚውን መገንባትም ይቻላል።

አርሶ አደሩ ጉልበት አለው። በተወሰነ ደረጃ ራሱን በዝቅተኛ ወጪ የሚያስተዳደርና አልፎ ተርፎም በዚሁ አነስተኛ ካፒታል በመተማመን የሚያመርት ኃይል ነው። በመሆኑም በራሱ ጉልበትና ወጪ በመጠቀም ሌላ ከፍተኛ የካፒታል ኢንቨስትመንት ሳይጠይቅ ብዙ ተጨማሪ ሀብት ሊያፈራ ይችላል። ትንሽ በማይባል አጋጣሚ በአስተሳሰብ ደረጃ የሚታይበትን የታካችነት አመለካከትና ባሕል በማስተካከል ዓመቱን ሙሉ በምርት ተግባር እንዲጠመድ ማድረግ ከተቻለ በጣም ሰፊ ሀብት ሊፈጥር ይችላል። በአውቀት እጥረትና በቴክኖሎጂ አቅርቦት ችግር ተተብትቦ ለዘመናት ሲጠቀምበት ከኖረው ልማዳዊ አሠራር በማላቀቅ ለዘመናዊ የግብርና ዘዴዎች ማብቃት ከተቻለ፣ የሀብት ፈጠራ ዕድሉ በቀጣይነት እንዲሰፋ ማድረግ ይቻላል። ከዚህ አኳያ ሲታይ በአርሶ አደር ጉልበትና አነስተኛ ማሳ በመተማመን የሚካሔደው የግብርና ልማት ሰፊ የካፒታል መነሻ ሳያስፈልገው ብዙ አዲስ ሀብት ለመፍጠር ያስችላል። በዚህ አማራጭ በእጅ ያለውን ጉልበትና መሬት ሳያባክኑ በጣም በአነስተኛ ወጪ እሴት ለመጨመርና ለዚያውም በገጠር ትንሽ የማይባል አዲስ ሀብት ለመፍጠር ይቻላል።

ኢህአዴግ በገጠር ልማት ዙሪያ የተከተለው አቅጣጫ በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ በመተማመን፣ ጉልበትን የሚተኩ ሳይሆን የሚደግፉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ላይ የተመሠረተ ነው። በተግባርም በአነስተኛ አርሶ አደሩ ማሳ ልማት ላይ የተመሠረተውን የዕድገት ስትራቴጂ የተከተለ ሲሆን፣ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ የአርሶ አደሩን ምርታማነት ለማሳደግ ሦስት

ተመጋጋቢ አቅጣጫዎችን ተልሞ ተንቀሳቅሷል። ከእነዚህ አቅጣጫዎች የመጀመሪያው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ተግባርን ማከናወን ሲሆን፣ ሁለተኛው በተለይ ከ1987ዓ.ም. ጀምሮ በነበሩት አሥር ዓመታት ውስጥ በዋናነት በአርሶ አደሩ ጉልበት አሥር ሺህ ያህል አነስተኛ ግድቦችን በመገንባት መስኖን ማስፋፋት ነበር። ሦስተኛው ደግሞ በሳሳካዋ ግሎባል ፈንድ በመታገዝ የግብርና ዘዴዎችን የማሻሻል አቅጣጫዎች ሲሆን፣ ሦስቱም ሰፊውን የኢትዮጵያ ገጠር ለማልማትና በዘላቂነት ደግሞ ወደኢንዱስትሪያዊ ልማት ለመሸጋገር ቁልፍ አስተዋጽዖ እንደሚኖራቸው የታመነባቸው ነበሩ።

ኢህአዴግ በገጠር ድኅነትን በራሱ በአርሶ አደሩ ጥረትና ትግል ለማሸነፍ ሲነሳ፣ በቅድሚያ የተገነዘበው ጉዳይ በአገሪቱ አርሶ አደሩን ለመደገፍና በሙያ ለመምራት የሚያስችል ብቃት ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት እንዳልነበረ ነው። ደርግ መላ ትኩረቱን በዋነኛነት በመንግሥት እርሻዎች ላይ አድርጐ የአነስተኛውን አርሶ አደር ማሳ ለማልማት አጋዥ የነበረውን የኤክስቴንሽን ሥርዓት ከሞላ ጐደል ዘንግቶት ነበር። በዚህ ምክንያት የግብርና ሙያተኞችን በብዛት ማሠልጠንና አርሶና አርብቶ አደሩን እንዲደግፉ አድርጐ እንደአዲስ ማሰማራት አስፈላጊ ሆነ። ይህ ሳይከናወን የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራውም ሆነ የእርሻ ማሳዎችንና የእንሰሳት ሀብት ልማቱን ማፋጠን የሚቻል አልነበረም። ከዚህ አኳያ ሲታይ በኢህአዴግ የተመራው መንግሥት በገጠር አዲስ የልማት አቅጣጫ በመቀየስ ብቻ ሳይወሰን ተግባራዊ የሚደረግበት ብቃት ያለው የግብርና ወይም የኤከስቴሽን ድጋፍና የአመራር ሥርዓት መገንባትም ነበረበት።

ኢህአዴግ በዚህ ረገድ ከደርግ የተለየ አቅጣጫ ቢከተልም፣ በተለይ የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓቱን በተሟላ የሰው ኃይል ለማዋቀር ከተግባር ብዙ መማር ነበረበት። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ስድሣ ሺህ የግብርና ሙያተኞች አሠልጥኖ እነዚህን በየቀበሌው እስኪመድብ ድረስ በጥቂት መቶዎች ግፋ ቢል በጥቂት ሺዎች የሚቆጠሩ ሙያተኞችን እያሠለጠነ በመመደብ የለውጡን ግስጋሴ በተነጻጻሪ አነስ ያለ አድርጐት ቆይቷል። በዚህ ወቅት በመጣው የአቅጣጫና የትኩረት ለውጥ፣ ግብርናው የድርቅ አደጋ ካላጋጠመው በስተቀር፣ መልካም የሚባል ዕድገት እያስመዘገበ መጓዝ ጀመረ። ይህም ሆኖ በተደጋጋሚ የሚከሰተው ድርቅ ከባድ ፈተና መሆኑ አልቀረም። የአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ሥር የሰደደ ስለነበር በተለይ ሰሜናዊና ምሥራቃዊ የአገሪቱ ከፍሎች ለተከታታይ ድርቅ ይጋለጡ ነበር። ተደጋግሞ የሚከሰተው ድርቅ ወደረሀብ አደጋ እንዳይቀየር ለማድረግ ቢቻልም፣ አገሪቱን ቢያንስ በየሁለት ግፋ ሲል ደግሞ በየሦስት ዓመቱ ሰፋ ያለ ድርቅ ይጐበኛት ስለነበር በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት የግብርናው ተጋላጭነት በጉልህ የሚታይ ችግር ነበር።

የግብርና ኤክስቴንሽን ሙያተኞችን ሰፋ ባለ ቁጥር ማሠልጠን ከተጀመረ በኋላ በእነዚህ ሙያተኞች በመታገዝ፣ በአንድ በኩል በተራራማና ተዳፋት መሬቶች ላይ በተነጻጻሪ ሰፋ

ያለ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ማከናወን ተጀመረ። እንደምሥራቅ ሐረርጌ በመሰሉ የአገሪቱ አካባቢዎች አርሶ አደሩ ያዳበራቸውን የእርከን ሥራዎች ልምድ መነሻ በማድረግ፣ ሥራው በማይታወቅባቸው ሌሎች አካባቢዎችም ለማላመድ ጥረት ተደረገ። አርሶ አደሮችን በማሳመን በሳምንት አንድ ወይም ሁለት ቀን እየከተቱ የአካባቢያቸውን ተራሮች በእርከን እንዲገድቡ ተደረገ። ሥራው አድካሚ ቢሆንም፣ አርሶ አደሩን በማግባባት እንዲከናወን በመደረጉ በብዙ የገጠር አካባቢዎች የተራራ ላይ እርከኖች ተሰሩ። በጐርፍ በተበሉ መሬቶች ላይም ትንንሽ የውሃ መገደቢያ የድንጋይ እርከኖች ተነጠፉ። የአፈር መከላትን የሚያስቀሩ የሳርና የሸንበቆ ዝርያዎች ተተከሉ። ደርቀው የነበሩ ወንዞች ውሃ ማፍለቅ፣ ደኖችም እንደገና መለምለም ጀመሩ። በአንዳንድ አካባቢዎች የተመናመነው የተፈጥሮ ሀብት እንደገና ማገገም ጀመረ። በተከለሉ አካባቢዎችም የዱር አራዊት መበራከት ተከተለ።

የተፈጥሮ ሀብት ሥራው በተጀመረባቸው ዓመታት በአርሶ አደሩ ዘንድ በጣም ብዙ ኋላቀር አመለካከቶች የነበሩ ሲሆን፣ ከሥራው መጀመር ጋር ተያይዞ በተካሔደ የአስተሳሰብ ትግል ግን እየተቀረፉ ሊሔዱ ችለዋል። በአንዱ አካባቢ በተራራዎች ላይ እርከን የመሥራት ሀሳብ ሲቀርብ "ይህን ተራራ ከነካካነው አድባር ይቆጣና መዓት ያወርድብናል" የሚሉ፣ ሌላውን ወንዝ ለመገደብ ወይም ለመጥለፍ ሙከራ ሲደረግ ደግሞ "አንዳች መቅሰፍት ይወርድብናል" ብለው የሚሞግቱ ብዙ ነበሩ።

እነዚህን የመሳሰሉ ኋላቀርና በአጉል እምነት ላይ የተመሠረቱ አስተሳሰቦች ያጋጥሙ በነበረበት ወቅት በጉራጌ ዞን በአንድ ስሙን በዘነጋሁት ቀበሌ ያጋጠመው ሁኔታ ከአርሶ አደሩ መካከል በአስተሳሰብ የመጠቁት ይህን የመሰለውን የአስተሳሰብ ችግር ለመቅረፍ ያደርጉ የነበረውን ጥረት ያመላክታል። የቀበሌው ሊቀ-መንበርና የሥራ ባልደረቦቹ በአካባቢው ተራራ ላይ እርከን የመሥራት ሀሳብ አንስተው ለአርሶ አደሩ ባካፈሉት ጊዜ የገበሬዎቹ ምላሽ ይህን ተራራ ከነካካነው ከባድ ቁጣ እንቀሰቅሳለን የሚል ነበር። ያም ሆኖ የቀበሌው አስተዳደሮች እንደምንም በማግባባት ጥቂት ሰዎች ይዘው ሥራውን ይጀምሩታል። በሂደት ከተራራው ላይ የተንከባለለ የድንጋይ ናዳ የሊቀ መንበሩን እግር ይሰብረዋል። ይህ አጋጣሚ በአርሶ አደሩ ዘንድ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት ያጠናከረዋል ብለው የሰጉት የቀበሌው አመራሮች፣ በጉዳዩ ላይ ከመከሩ በኋላ ሊቀ-መንበራቸውን በምስጢር ወደ አጐራባች ቀበሌ ልከው ድኖ እስኪመጣ ድረስ እዚያው እንዲቆይ ይወስናሉ። ይህን አድርገውም ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ በማስመሰል ሥራውን ይቀጥሉበታል። የተፈጠረ ቁጣ እንደሌለ ያረጋገጠው የቀበሌው አርሶ አደር ደግሞ የማታ ማታ የሥራውን ጠቀሜታ እየተገነዘበ በተራሮች ላይ የሚሠራውን እርከን ለማስፋፋት መተባበር ጀመረ። የቀበሌው ሊቀ-መንበር ከስብራቱ አገግሞ ወደሥራ ሲመለስ ደግሞ በአርሶ አደሩ ዘንድ ከዚህ ሥራ ጋር ተያይዞ የተነሳው ኋላቀር አስተሳሰብ በተግባር ተሸንፎ ነበር። ይህን

የመሳሰሉ በርካታ አደናቃፊ አስተሳሰቦች በዚህ ወሳኝ ተግባር ላይ ያጋጥሙ የነበረ ቢሆንም፣ ኢህአዴግና መንግሥት በትዕግስትና ያለመሰልቸት አርሶ አደሩን ከልምድ እያስተማሩ እንዲፈቱ በማድረጋቸው ሥራው ተጠናክሮ ሊቀጥል ችሏል።

ይህም ሁሉ ሆኖ በመጀመሪያው አሥር ዓመት የተከናወነው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ በመጠኑ በጣም አነስተኛና የችግሩ ስፋትና ጥልቀት የሚጠይቀውን ያህል አልነበረም። አርሶ አደሩ ያለውን ጉልበት በሙሉ ለማንቀሳቀስም አልተቻለም ነበር። የሴቶች ልማታዊ ተሳትፎ መሆን የሚችለውንና የሚገባውን ያህል አልደረሰም። በልማዳዊ ወጐች የተተበተበ አርሶ አደር የሴቶችን ጉልበት ጠቀሜታ እስኪገነዘብ ድረስ፣ የገጠር ሴቶች በዚህ ቁልፍ ተግባር ላይ የነበራቸው ተሳትፎ የተገደበ ነበር። በዚያው ልክ ደግሞ ሥራው የሚሸፍናቸው ቀበሌዎች መጠንም ሆነ አጠቃላይ የተገኘው ውጤት መሆን ከሚችለውና ከሚገባው በጣም ያነሰ ነበር። በሁለተኛው አሥር ዓመት፣ በተለይ ደግሞ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የላቀ የሴቶች ተሳትፎ በማረጋገጥ ከተሠራው ጋር በማነጻጸር ሲታይ፣ የመጀመሪያው አሥር ዓመት ዋናው ጥቅም የገጠር ልማት ሥራዎችን የማደራጀትና የማስፈጸም ልምድ የተገኘበት መሆኑ ነው።

በእነዚህ ዓመታት በገጠር ልማትን ለማስፋፋት ለየት ያለ ትኩረት የተሰጠው በአርሶ አደሩ ተሳትፎ አነስተኛ ግድቦችን ለማልማት ነበር። ይህ ሥራ ኢህአዴግ በ1987 ዓ.ም. በተካሔደው የመጀመሪያው አገራዊ ምርጫ በመወዳደሪያነት ባቀረበው የአምስት ዓመት መርሃ ግብር ልዩ ትኩረት የተሰጠው ነበር። ኢህአዴግ የአገራችን ግብርና ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ አገሪቱ ባላት የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃ በመጠቀም የምታመርትበት ሊሆን እንደሚገባው ይገነዘባል። በእርግጥ በአገሪቱ ከ60 በመቶ የማያንሰው የገጠር አካባቢ በየዓመቱ የተሻለ ምርት ለማግኘት የሚያስችለው የእርጥበት መጠን ያለው በመሆኑ በክረምት ዝናብ በመታገዝ ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል። ነገር ግን ደግሞ አገሪቱ ትንሽ የማይባል በድርቅ የሚጠቃ አካባቢ ያላት በመሆኑ በእነዚህ ቦታዎች በልዩ ትኩረት አነስተኛ ግድቦች ወይም ሌላ አይነት የውሃ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ ማድረግ አስፈላጊ ነበር።

በኢትዮጵያ የድርቅ አካባቢዎች ከሆኑት አብዛኞቹ ከእስራኤል የተሻለ የዝናብና የእርጥበት መጠን ያላቸው ናቸው። ነገር ግን እስራኤል ከ400 ሚ.ሜ በማይበልጥ ዓመታዊ ዝናብ የበረሃ ገነት ስትፈጥር፣ በኢትዮጵያ በአብዛኞቹ የድርቅ አካባቢዎች ከ600 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ዓመታዊ የዝናብ መጠን እየተገኘም ድርቁ ይደጋገማል። ይህም እርጥበት ከማጣት ሳይሆን ውሃን ከመቆጣጠር ችግር ጋር የተያያዘ ነው። ኢህአዴግ ከዚህ በመነሳት በአሥር ዓመታት ውስጥ አሥር ሺህ የሚደርሱ አነስተኛ ግድቦችን የማስፋፋት እቅድ ነደፈ። ይህን እውን ለማድረግ ደግሞ በትግራይ"ሳርት" (Sustainable Agricultural

& Environmental Rehabilitatio of Tigray)፣ በአማራ ክልል ደግሞ ሴራር" (Sustainable Environmental & Agricultural Rehabilitation in Amhara Region) የሚባሉ ተቋማትን አደራጀ። የሁለቱን ተቋማት የአፈጻጸም ልምድ በመቀመር ደግሞ ሥራው በሌሎች የአገሪቱ ክልሎች እንዲስፋፋ ጥረት ተደረገ።

ድርጅቶቹ ከተመሠረቱ በኋላ ለሁለቱ ክልሎች የውሃ ሀብት ልማት ተፈላጊው ስትራቴጂ ተነደፈ። መለስተኛና አነስተኛ የአፈር ግድቦች ለመሥራት የሚያስችሉ መሬቶች እየተለዩ በእነርሱ ላይ የሚገነቡት ግድቦች ተቀየሱ። ብዙም ሳይቆይ በዋነኛነት የአርሶ አደሩን ጉልበት በመጠቀምና ይህንኑ በጥቂት ማሽነሪዎች በመደገፍ ግድቦቹን መገንባት ተጀመረ። ወንዶች ቋጥኝ እየፈነቀሉና ድንጋይ እየፈለጡ፣ ሴቶች በማዳበሪያ ከረጢት አፈርና ድንጋይ እየተሸከሙ በማጓጓዝ ግድቦችን መሙላት ጀመሩ። ግድቦቹ የውሃ ሥርገትን የመከላከል ብቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ አርሶ አደሮች በማሽነሪ ምትክ ብርታት የሚሰጣቸውን ባህላዊ የደቦ ዘፈኖች እያዜሙ ድንጋዩንና አፈሩን በእግራቸው እየጠቀጠቁ ተረባረቡ።

ይህን በመሰለው ሥራ አቅመ ደካሞችና የታመሙ ካልሆኑ በስተቀር አለመሳተፍ እንደነውር ተቆጠረ። በድርቅ አካባቢዎች ደግሞ ከሞላ ጐደል አብዛኛውን የዓመቱን ጊዜ ከጠዋት እስከ ማታ በዚህ ተግባር ላይ ማሳለፍ እየተለመደ መጣ። አነስ ያሉ የአፈር ግድቦች ሥራው በተጀመረ በዓመቱ፣ ተለቅ ያሉት ደግሞ ሁለትና ሦስት ዓመታት እየወሰዱ ተጠናቀቁ። ከፍ ያለ ውሃ በያዙት ግድቦች አርባና አምሳ፣ አነስ ያሉት ደግሞ ከዚህ ያነሱ ሔክታሮችን እንዲያለሙ ተደረገ። በሳርትና ሴራር አማካይነት በጥቂት ዓመታት በድምሩ ከ150 የማይበልጡ ግድቦች ተሰሩ። በእነዚህ አነስተኛ መስኖዎች አርሶ አደሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በተከማቸው ውሃ ከረምት ከበጋ ማምረት ጀመረ።

በአርሶ አደሮች ጉልበትና በጥቂት ማሽነሪ ድጋፍ አነስተኛ የመስኖ አገልግሎት የሚሰጡ ግድቦችን መሥራት በራሱ ትልቅ ነገር የነበረውን ያህል፣ በአንድ በኩል አሥር ሺህ ግድቦችን በአሥር ዓመት ለመሥራት የሚቻልና የማይቻል መሆኑን ከተግባሩ በመነሳት ለማየት ዕድል የከፈተ ነበር። በሌላ በኩል በአነስተኛ ግድቦች የሚለማ አነስተኛ መስኖ ጠንካራና ደካማ ጐኖችን እንዲሁም አዋጭነቱን ለመለካት የሚያስችል ዕድል አስገኘ። ይህን መነሻ በማድረግ በአነስተኛ ግድቦች አማካይነት የሚካሔደው የመስኖ ልማት ዝርዝር ባህሪ እንዲሁም አፈጻጸሙ እንዲገመገም ተደረገ።

የአነስተኛ ግድቦች ሥራ የመጀመሪያው ጠቀሜታ ለዘመናት በአገሪቱ ሰፍኖ የኖረውን ውሃን ያለመቆጣጠር ችግር በህዝብ ጥረት ማቃለል እንደሚቻል ማረጋገጡ ነበር። አርሶ አደሩን አንቀሳቅሶ ግድብ በመሥራት ውሃ መያዝ እንደሚቻል ብቻ ሳይሆን፣ በዓመት ሁለትና ሶስት

ጊዜ ማምረት እንደሚቻል በተግባር ተረጋገጠ፡፡ ጉልበቱ ተገኝቶ ግድቡ በትክክለኛ ቦታዎች ላይ ከተሠራ በተከማቸው ውሃ አስተማማኝ ምርት ማግኘት እንደሚቻል በተግባር ታየ፡፡ በግድብ ሥራው ሂደት ከራሳችን ተግባር በሰው ልጅ ጥረት ውሃን ለመቆጣጠርና የተፈጥሮ ጥገኛ ከመሆን እጣ ፋንታ ትርጉም ባለው ደረጃ መላቀቅ እንደሚቻልም ትምሕርት ተገኘበት፡፡

እነዚህ እንደተጠበቁ ሆነው የአነስተኛ ግድብ ሥራው መፍትሔ የሚሹ ችግሮችም ነበሩበት፡፡ የመጀመሪያው ችግር በሥራው ላይ የሚሠማራው ህዝብ ብዙ ሆኖ ተጠቃሚው ግን በቁጥሩ አነስተኛ መሆኑ ነበር፡፡ በአነስተኛ የአፈር ግድብ ሥራው ላይ ከሞላ ጐደል በግድቡ ዙሪያ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ሁሉ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ነገር ግን በተከማቸው ውሃ የሚለማው መሬት በተነጻጻሪ ትንሽና ተጠቃሚውም በታችኛው ተፋሰስ የሚገኘው የተወሰነ ህዝብ ብቻ ነበር፡፡ ይህ የአነስተኛ የአፈር ግድቦች ልማት ሥራ አንድ መሠረታዊ ውሱንነት ነበር፡፡

በዚህ ምክንያት ብዙኀኑ አርሶ አደር ቀስ በቀስ "ጉልበታችንን የምናፈሰው በማንጠቀምበት ግድብ ላይ ነው" የሚል አመለካከት መያዝ ጀመረ፡፡ መለስተኛ ውሃ የማሰባሰብ አቅም ኖሯቸው ብዙኀኑ አርሶ አደር በማይጠቀምባቸው ግድቦች ላይ ሁሉም የአካባቢው ህዝብ ጉልበቱን እንዲያፈስ ማድረግ በሂደት የፍትሃዊነት ጥያቄ ማስነሳት ጀመረ፡፡ ግድቦቹ ተሠርተው እስኪጠናቀቁ ድረስ በከፍተኛ ወጌ የተረባረበው አርሶ አደር፣ በግድቦቹ ከተጠራቀመው ውሃ የሚለማው ማሳ መጠን እርሱን የማይጨምር እንደሆነ መመልከት ሲጀምር፣ በቀጣይ ተመሳሳይ ሥራ ላይ ለመግባት ያለው ፍላጐት መቀዛቀዝ ጀመረ፡፡ ይህም በአርሶ አደር ጉልበት ኢሥር ሺህ አነስተኛ ግድቦችን በኢሥር ዓመት የመገንባትን ሀሳብ ተፈጻሚነት አጠራጣሪ አደረገው፡፡ በዚህ ምክንያት በመጀመሪያው የአምስት ዓመት የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም መርሐ ግብር የተነደፈው የትንንሽ የአፈር ግድቦች ልማት ቀስ በቀስ መቀዛቀዝ ጀመረ፡፡ ሳርትና ሴራር ደረጃ በደረጃ በአርሶ አደር ጉልበት ከሚሠራው የአነስተኛ ግድብና የመስኖ ልማት አቅጣጫ እየወጡ፣ በማሽነሪ ድጋፍ የሚከናወኑ በተነጻጻሪ ሰፋ ያለ መሬትን የሚያለሙ የመስኖ ፕሮጀክቶችን በተጓዳኝ ወደመገንባት ተሸጋገሩ፡፡ የማታ ማታ ደግሞ በአርሶ አደር ጉልበት የሚሰሩት አነስተኛ ግድቦች ከሞላ ጐደል ወደመቆም አመሩ፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት የአነስተኛ መስኖ ልማትን ጨርሶ አላቆመውም፡፡ የአፈር ግድቦች ግንባታ ቢቆምም በአነስተኛ የወንዝ ጠለፋዎችና በተራሮች ላይ በሚካሔደው የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና የውሃ ማስረግ ሥራ በመታገዝ በየማሳው ዙሪያ በሚቆፈሩ አነስተኛ የውሃ ጉድጓዶች ውሃ እያወጡ መሬትን በመስኖ የመሸፈን አቅጣጫ መከተል ተጀመረ፡፡ በድርቅ አካባቢዎች አርሶ አደሮች አንድም በሲሚንቶ የተገነቡ፣ አሊያም ጂአሜምብሬን በመባል የሚታወቀውን ወፍራም ላስቲክ በማንጠፍ ውሃ እያከማቹ የደጋፊ መስኖ (Supplimentary Irrigation) ልማቱ እንዲቀጥል ተደረገ፡፡ በዚህም ሥራ አንድ ዓይነት የውሃ ማቆር ቴክኖሎጂ

ብቻ ሳይሆን ብዙ ዓይነት አማራጮች እንዳሉና ከእነዚህም መካከል አዋጭ የሆነው ተመርጦ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ እንደሚቻል ትምሕርት ተወሰደ፡፡ በአነስተኛ ግድቦች መቋረጥ ምክንያት የመስኖ ልማቱ ሳይስተጓጐል እንዲቀጥል ለማድረግና አዋጭነት ባላቸው ሌሎች ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የላቀ ልማት ለማረጋገጥ እንደሚቻልም ታመነበት፡፡ በመሆኑም የአነስተኛ መስኖ ልማት በተለይ ከተሃድሶ መድረኩ በኋላ በአዳዲስና አዋጭ የውሃ ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ ተደረገ፡፡

በመርሐ ግብሩ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ሦስተኛው ጉዳይ የግብርና ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችሉ የአስተራረስ ዘዴዎችንና ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎችን ለማስተዋወቅና ተግባራዊ ለማድረግ ነበር፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው ይህ እንቅስቃሴ በሰፊው የተጀመረው ሳሳካዋ ግሎባል ፈንድና ካርተር ሴንተር አዳዲስ የግብርና ዘዴዎችን ማስተዋወቅ ከጀመሩ በኋላ ነው፡፡ በዚህ የግብርና ልማት ማሻሻያ እንቅስቃሴ መሬትን ደጋግሞ በማረስና በማለስለስ ካዘጋጁ በኋላ፣ የተሻሻሉና በፀረ-ተባይ መድኃኒት የታሹ የበቆሎ ዝርያዎችን በመስመር በመዝራትና ሁለትና ሶ ስት ጊዜ በማረም ምርታማነቱ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር ተረጋገጠ፡፡

እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በብዙ የአፍሪካ አገሮች ከረዥም ጊዜ በፊት ጀምሮ ጥቅም ላይ ሲውሉ የቆዩ ቢሆኑም፣ በአገራችን ግን ለአርሶ አደሩ ትኩረት በነፈገው የደርግ መንግሥት ችላ የተባሉና በዚያው ልክ ደግሞ የአገሪቱ የግብርና ምርታማነት እጅግ አናሳ ሆኖ እንዲቆይ ያደረጉ ነበሩ፡፡ ደርግ ሌላው ቀርቶ በአርሲ ጭላሎና ወላይታ አካባቢዎች በንጉሱ ዘመን በስዊድኖች ርዳታ በትንሹ የተሞካከሩትን መልካም ሥራዎች እንኳ ለማስፋፋት አልሞከረም። በቆሎ በብዙ አገሮች በአማካይ በሔክታር ከአርባ ኩንታል የማያንስ ምርት የሚታፈስበት ቢሆንም፣ በአገራችን አማካይ ምርቱ በሔክታር ከ20 ኩንታል ያነሰ ነበር፡፡ የሳሳካዋ ግሎባል ፈንድ ፕሮግራም ጥሩ እንከብካቤ በተደረገላቸው የበቆሎ ማሳዎች ምርታማነትን በሔክታር እስከ ሰማንያ ኩንታል በማድረስ በኢትዮጵያ የአነስተኛውን አርሶ አደር ግብርና በአጭር ጊዜ ለማሳደግ የሚያስችለው ድጋፍና አቅጣጫ የትኛው መሆን እንዳለበት አመላከተ፡፡

በሽግግሩ ወቅትና በመጀመሪያው አሥር ዓመት የተከናወኑት የልማት ተግባራት፣ በአንድ በኩል የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ለማስቀረት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመጠኑም ቢሆን የአገሪቱን የውሃ ሀብት ለማበልጸግ ያስቻሉ ነበሩ፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ደግሞ በሰብል ምርት የተሻለ ውጤት ማግኘት እንደሚቻል ያመላከቱ ነበሩ፡፡ በመሆኑም ለዘመናት በማሽቆልቆል ሂደት ውስጥ ያለፈውን ግብርናና ገጠር መንግሥትና ህዝብ በትከከለኛ አቅጣጫ እየተመሩ ተባብረው እስከሰሩ ድረስ ወደፅድጎት ማምራት እንደሚቻል በጥቂት ዓመታት ተግባራዊ ልምድ ተረጋገጠ፡፡ ምንም እንኳ መንግሥት የገጠሩን ኢኮኖሚ በብቃት የመምራት ደረጃ ላይ እስኪደርስ ተጨማሪ

መውደቅ መነሳት ያልቀረለት ቢሆንም፣ በጥቂት ዓመታት ጥረት ግብርናውም ሆነ የገጠሩ ኢኮኖሚ በማንሰራራቱ ለአነስተኛው አርሶ አደርና ማሳው ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ታይቷል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ግብርና በተለይ ደግሞ የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ልማት እመርታ ማምጣት የጀመረው የተሃድሶ እንቅስቃሴው ከተጀመረ ከሁለት ዓመታት በኋላ በተለይ ደግሞ ከ1995 ዓ.ም የከረምት ወራት ጀምሮ በተደረገው ጥረት ነው። ይህ በከፍል ሁለት የሚዳሰስ ይሆናል።

ለማኅበራዊ ልማት የተካሔደው ትግልና ውጤቱ፣

ባለፉት ሃያ ዓመታት በማኅበራዊ መስክ ለውጥ ለማምጣት የተካሔደው እንቅስቃሴ በርካታ ዘርፎችን የሚዳስስ ነበር። ቀደም ሲል በነበሩት ሥርዓቶች አገሪቱ በሁሉም መሠረታዊ መለኪያዎች ወደኋላ የቀረች ስለነበረች ለውጡ ዘርፈ ብዙና ሥር ነቀል መሆን ነበረበት። ትምሕርት ከጥቂት ከተሞች በስተቀር አልተስፋፋም። የነበሩት መንግሥታት ትምሕርት መብትና የለውጥ መሣሪያ መሆኑን ከልብ ያልተቀበሉ ስለነበሩ፣ ለትምሕርት መስፋፋት ተገቢውን ትኩረት የሚሰጡ አልነበሩም። እጅግ አብዛኛው ህዝብ የሚኖረው በገጠር ቢሆንም የትምሕርት አገልግሎት ወደገጠር ቀበሌዎች ይቅርና ወደወረዳ ከተሞች አልዘለቀም። የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምሕርት ይቅርና ራሱ የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት መስፋፋት እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። 50 ሚሊዮን ለሚሆን ህዝብ የነበሩት 4152 አንደኛ ደረጃና 275 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብቻ ነበሩ። በደርግ ዘመን የመጨረሻ ዓመት የተማሪዎች ቁጥር 2.1 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም ከጠቅላላው ህዝብ 3.5 በመቶ የማይበልጥ ነው። ይህ በ2007 ዓ.ም ከጠቅላላው ህዝቧ ውስጥ ከ27 በመቶ በላይ የሆነውን በማስተማር ላይ ከነበረችው ኢትዮጵያ ጋር ፊጽሞ በማይነጻጸር ደረጃ ዝቅተኛ ነበር። በዓመት ሦስት ሺህ ተማሪዎች ብቻ የመቀበል አቅም የነበረው አንድ ዩኒቨርሲቲና ከአምስት የማይበልጡ መለስተኛ ኮሌጆች እንዲሁም ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ ተማሪዎች በላይ የማያስመርቅ የሙያና ቴከኒክ ኮሌጅ ብቻ የነበሩ መሆናቸው ይህንኑ የሚያሳይ ነው።

ትምሕርት በአገሪቱ ካለመስፋፋቱ በተጨማሪ በፍትሃዊነት የመዳረስ ችግርም ነበረበት። አገልግሎቱ ገጠሮች የተዘነጉበትና በአብዛኛው በከተሞች የታጠረ ነበር። አብሶ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የትምሕርት ዕድል እንዲቋደሱ አልተደረገም። የሴቶች ተሳትፎም እጅግ አናሳ ነበር። ሴቶች አንድም በሚደርስባቸው ከባድ ልማዳዊ ተፅዕኖ፣ አሊያም ለሴቶች ትኩረት የሚነፍግ ሥርዓት በመኖሩ ምክንያት ከተማሪው ማኅበረሰብ ከአስር በመቶ የማይበልጥ ድርሻ ብቻ ነበራቸው። ከዚህ በመነሳት መላ የአገሪቱ ህዝቦች በተለይ ደግሞ የተማረው ከፍል ለፍትሃዊና ዘመናዊ ትምሕርት መስፋፋት ከባድ ትግል አካሂዷል። በንጉሱ ዘመን በየካቲት አብዮት ዋዜማ

ላይ መምህራን "ሴክተር ሪቪው" በመባል የሚታወቀውንና የድሃ ልጆችን የመማር ዕድል የሚያጠበውን የተሳሳተ አማራጭ በመቃወም ከባድ ትግል አካሂደዋል። በዚያው ልክ ደግሞ ለንጉሣዊው ሥርዓት መገርሰስ የበኩላቸውን ኃላፊነት ተወጥተዋል።

ከደርግ መምጣት በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያ ትምሕርት በማያቋርጥ የማሽቆልቆል ሂደት ውስጥ ለማለፍ ተገደደ። ከሁሉ በፊት ደርግ በ1960ዎቹ መጨረሻና በ1970ዎቹ መጀመሪያ ባካሔደው ከባድ ጭፍጨፋ በኢትዮጵያ ታሪክ ሰፋ ባለ ደረጃ መፈጠር ጀምሮ የነበረውን የተማረ የሰው ኃይል በብዛት አጥፍቶታል። ቀይ ሽብር የተፋፋመው በዋነኛነት በከተሞችና በተማረው ወጣት ላይ ስለነበር፣ ይህ በራሱ የትምሕርትን መስፋፋት በብዙ መልኮች የሚገድብ ውጤት ነበረው። ይህ ካለፈ በኋላ ደግሞ ትምሕርት የርዕዮተ-ዓለማዊ ትግሉ ሰለባ የሆነበት ሂደት መስፋፋቱ የትምሕርትን ጥራት ይበልጥ መግደል ጀመረ። በዚህ ላይ ሥርዓቱ በነጻነት የማሰብ ዕድልን ፈጽሞ የከለከለ ስለነበር፣ በነጻ የመመራመርና አማራጭ ሀሳብና ቴክኖሎጂ የማፍለቅ ዕድል ጨርሶ ተዘጋ። መንግሥት ሌሎች ተዋናዮችን ሁሉ ከልክሎ ብቸኛው የኢኮኖሚ ተዋናይ መሆኑም መማር ለመንግሥት ተቀጣሪነት እንጂ ለሌላ ተግባር የማይፈይድ እስከመሆን ደረሰ። በወቅቱ 12ኛ ክፍልን አጠናቀው ወደከፍተኛ ትምሕርትም ሆነ የቴክኒክና ሙያ መስክ የመግባት ዕድል የማያገኙት ብዙኃን ተማሪዎች የመጨረሻ ዕጣ ፋንታቸው ሥራ አጥነት ሆነ። የሥርዓቱ ጦረኛ ባህሪ ገኖ በወጣባቸው የመጨረሻዎቹ ዓመታት ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም ቀጥተኛ ትዕዛዝ ወደብላቴ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ጣቢያ እንዲገቡ ተደረገ። የአገሪቱ ትምሕርት ከጊዜ ወደጊዜ እየተዳከመ በመሔድ ሳይወሰን፣ በደርጉ የመጨረሻ ዓመታት የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን የሆኑ ተራ ወታደሮች ወደማምረት ደረጃ ዝቅ አለ። ዛሬ በኤርትራ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በሙሉ ለወታደራዊ ዓላማ እንዲሰለፉ ማስገደድ እንዳለ የሚገነዘብ ሁሉ በዚህ ዓይነቱ የተሳሳተ የመንግሥት አቅጣጫ መገረሙ የተለመደ ነው። በደርግ የመጨረሻ ዓመታት የኢትዮጵያ የትምሕርት አገልግሎት ወደዚህ ደረጃ ዝቅ ብሎ እንደነበር ሲታወስ አምባገነን አገዛዞች በሰፈኑበት ሁሉ ተመሳሳይ ችግሮች አይቀሬ እንደሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል። በኢትዮጵያ የትምሕርት ልማትን የማረጋገጥ ጉዳይ እነዚህን ችግሮች ሁሉ ማቃለል ይጠይቅ ነበር።

ልክ እንደ ትምሕርት ሁሉ በአገሪቱ የጤና ልማትን የማረጋገጥ ጉዳይም ልዩ ጥረት የሚጠይቅ ነበር። በኢትዮጵያ ዘመናዊ የጤና ሥርዓት መገንባት የጀመረው ከሞላ ጐደል ከጣሊያን ወረራ በኋላ ነው። የዚህ አገልግሎት ዋነኛ ባህርይ በሽታን የማከምና የመፈወስ፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ የመከላከል ሲሆን፣ ለዚህ ሲባል በንጉሱ ዘመን ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (የአሁኑ አአዩ) በተጨማሪ በጐንደርና ጅማ ኮሌጆች የጤና መኮንኖችንና ሐኪሞችን በተወሰነ ደረጃ ማሠልጠን ተጀምሮ ነበር። በወቅቱ የሚሠለጥነው ሙያተኛ ቁጥር በጣም

አነስተኛ ሲሆን፣ በጠቅላይ ግዛት ከተሞች በሚገኙ ሆስፒታሎችና በጥቂቱ በተስፋፉት የገጠር ጤና ጣቢያዎች የሚመደብበት የጤና ሥርዓት ተደራጅቶም ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በዓለም ጤና ድርጅት እርዳታ በሚካሔዱት የጤና ፕሮግራሞች የወባ ትንኝን የመከላከል መከራዎች ተደርገዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ሥርዓቱ በዋነኛነት መከላከልን ሳይሆን ህክምናን ማዕከል በማድረግ የተቀረጸ ስለነበር፣ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ጉዳት ሲያስከትሉ የነበሩትን ተላላፊ በሽታዎች የመቆጣጠር ብቃት አልነበረውም። ይህ ያነሰ ይመስል ደርግ ሥልጣኑን በኃይል ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ የጤና ሥርዓት ላይ የታየው ቀውስ ይበልጥ እየተባባሰ ሊሔድ ችሏል። በቀይ ሽብር የተመታው ሰፊ የተማረ የሰው ኃይልና ይህን ተከትሎ የነገሰው የፍርሀት ድባብ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ጤና ከነበረው የፖሊሲ ቀውስ ጋር ተዳምሮ ይበልጥ እየተዳከመ እንዲሔድ አደረገ። ከለውጡ በፊት የነበሩት እነዚህ እውነታዎች አዲሱ ሥርዓት በማኅበራዊ መስክ ብዙ የተወሳሰቡና ያልተፈቱ ችግሮችን እንዲወርስ አድርገዋል። በዚያው ልክ ደግሞ መሠረታዊ የፖሊሲ ለውጥ ከማምጣት ጀምሮ፣ ይህንኑ በተግባር ላይ እያዋሉ የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወን የግድ የሚሉ ነበሩ።

በትምሕርትና በጤና ልማት መስክ ትከከለኛ ውጤት ሊገኝ ይችል የነበረው የተስተካከለ ፖሊሲ በመከተል ብቻ ስለነበር በቅድሚያ የትምሕርትና ጤና ፖሊሲዎቹን የማስተካከል እርምጃ ተወሰደ። በትምሕርት ፖሊሲው ላይ ሰፊ ጥናት እንዲካሔድበት ሲደረግ ከቆየ በኋላ፣ በ1987 ዓ.ም በተካሔደው ምርጫ ኢህአዴግ ማሸነፉን ተከትሎ አዲሱ የትምሕርት ፖሊሲ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ ተደረገ። በዚህ መሠረት የአገሪቱ የትምሕርት ፖሊሲ በቅድሚያ ትምሕርት ፍትሃዊነትን በሚያረጋግጥ አኳኋን እንዲስፋፋ ለማድረግ የሚያስችል ሆኖ ተቀረጸ። የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት እስከ ስምንተኛ ክፍል ሆኖ ለመላው ዜጐች መዳረስ ያለበት መብት እንደሆነ በፖሊሲው ተሰመረበት። አፈጻጸሙም በሁለት እርከን /Cycle/ ተከፈለ። የመጀመሪያው እርከን ከ1-4፣ ሁለተኛው ደግሞ ከ5-8 ድረስ ሆኖ ከእንግሊዘኛ በስተቀር ሁሉም ትምሕርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሆን ተደረገ። አማርኛን በሥራ ቋንቋነት የመረጡ አካባቢዎች ደግሞ በዚሁ የመጠቀም ምርጫቸው ተከበረላቸው።

በመጀመሪያው እርከን በዋነኛነት ትኩረት የተሰጠው ህጻናት የመማር ክህሎት እንዲያዳብሩ፣ እውቀት ለማስያዝ የሚደረገው ጥረት ደግሞ በወሳኝነት የሁለተኛው እርከን ተልዕኮ እንዲሆን ተደረገ። ከዚህ በተጨማሪ በሁለተኛ ደረጃ ይሰጥ የነበረው የአራት ዓመታት ትምሕርት በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የሚሰጥ ሆኖ ቀድሞ በ12ኛ ክፍል ይሰጥ የነበረው የመልቀቂያ ፈተና 10ኛ ክፍል ላይ እንዲሰጥ ተወሰነ። በዚህ ፈተና ወደኮሌጅ ለመግባት የሚያስችል ውጤት የሚያመጡ ለሁለት ዓመታት የመሰናዶ ትምሕርት እንዲወስዱ፣ የኮሌጅ መግቢያ ውጤት ያላገኙ ደግሞ ወደቴክኒክና ሙያ ትምሕርት ገብተው በአንድ ዓይነት ሙያ ክህሎት የሚያዳብሩበት

ለሦስተኛ ጥቁመጠ። ለኢኮኖሚው የሚያበፈልገውን ከፍተና ሙያተና የማሠልጠን ተግባር ደግሞ የከፍተኛ ትምሕርት ተልዕኮ እንዲሆን ተደረገ። ፍትሃዊነትን ከማረጋገጥ ጐን ለጐን ለትምሕርት ጥራት ትኩረት መስጠት የፖሊሲው አንድ ዋነኛ አቅጣጫ ተደረገ። በዚህ ላይ የትምሕርት አስተዳደር ሥርዓቱ በባህሪው ያልተማከለ ሆኖ ፌዴራላዊ የአስተዳደር ሥርዓቱን እንዲከተል ተወስኖ፣ ክልሎች ከአንደኛ ደረጃ እስከመለስተኛ ኮሌጆች ድረስ ያሉትን እንዲመሩና እንዲያስፋፉ፣ የፌዴራል መንግሥቱ ደግሞ የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማትን እንዲያስተዳድር አቅጣጫ ተቀመጠ።

ይህ ፖሊሲ በይዘቱ ተራማጅና የህዝብን መሠረታዊ ጥቅምና የአገር ልማትን የሚያፋጥን ቢሆንም ከውስጥም ከውጭም ከባድ ተቃውሞዎች ሳያጋጥመው አላለፈም። ከውጭ በዓለም ባንክ ደረጃ "ኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ ትምሕርትን እስከ 8ኛ ክፍል ማድረግ ይበዛባታል፣ ስለዚህም አንደኛ ደረጃ 6ኛ ክፍል ላይ መጠናቀቅ ይገባዋል" የሚል ተቃውሞ አጋጥሞ ነበር። ይህም ሆኖ ምክረ-ሀሳቡ ከኢትዮጵያ ህዝቦች መብትና ተጠቃሚነት የሚመነጭ አልነበረም። የአገራችን ህዝቦች የሚጠቀሙት 8ኛ ክፍል ድረስ የሚዘልቅ የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ለሁሉም ዜጐች በነጻ ሲዳረስ ነበርና። ነገር ግን የትምሕርት ፖሊሲው ከመቀረፁ ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ በዓለማችን የበላይነት መያዝ የጀመረው ኒዮ-ሊበራል ርዕዮት የመንግሥትን አቅም በማጠናከርና መንግሥት ለህዝቦች የሚሰጠውን አገልግሎት በማስፋት ጠቀሜታ የሚያምን አልነበረም። ስለሆነም ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ የአገራችን መንግሥት ግዙፍ የገንዘብ ወጪ በመመደብ የትምሕርት አገልግሎት የሚያስፋፋበትን ልማታዊ አቅጣጫ በቀላሉ ሊቀበል የሚችል አልነበረም። በአንድ በኩል መንግሥትን የማዳከም፣ በሌላ በኩል በመንግሥት ለህዝብ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማመናመን አቅጣጫ የሚከተለው ኒዮ-ሊበራል ዓለም፣ ትምሕርትም በገበያና በገንዘብ የሚሸጥ ሸቀጥ እንዲሆን ማድረግን ይመርጥ ነበር።

ይህ ትምሕርትን በገበያና ለባለሀብቱ በሚያስገኘው ትርፍ የሚወሰን ልማት እንዲሆን የማድረግ አቅጣጫ ሌላው ቀርቶ በትምሕርት ብዙ ተራምዳለች የምትባለውን ሕንድ እንኳ ተወዳዳሪ አገር ሊያደርጋት የቻለ አይደለም። በሕንድ ትንሳኤ ዙሪያ የነበራቸውን ከፍተኛ ጥርጣሬ በጥልቅ ጥናት ያረጋገጡት የኖቪል ተሸላሚው አማርቲያ ሴንና ጀን ድሬዜ በ2013 ባሳተሙት መጽሐፍ ይህን በማስመልከት፡-

> "ምንም እንኳ በሕንድ አገራዊ ንቅናቄ ውስጥ ለትምሕርት መስፋፋት ቀናዒነት እንዳለ የሚያስመስል ከባድ ስብከት የሚካሔድ ቢሆንም፣ በአገሪቱ የትምሕርት አገልግሎት በሚያስደነግጥ ዝቅተኛ የመስፋፋት ደረጃ ላይ ይገኛል። በትምሕርት አገልግሎት ሕንድ ከምሥራቅ እስያ አቻዎቿ እጅግ ወደኋላ የቀረች

አገር ሆናለች:: በሕንድ የትምሕርት ሥርዓት ላይ የሚታየው መዋቅራዊ ችግር ሲፈተሽ ቅልጥፍናና ፍትሃዊነት በተጓደሉበት፣ መላ የአገሪቱ ትኩረት ለጥቂቶች በጣም ጥራት ያለው ትምሕርት ማቅረብ በሆነበት፣ በኢኮኖሚያዊ ድኅነት፣ በመደብና በጐሳ እንዲሁም በፆታና ማኅበራዊ ልዩነቶች በተለይ ደግሞ በብሔርና ማኅበረሰብ ላይ የተመሠረተና ብዙኃኑ የተዘነጋበት መሆኑ ብዙ ኪሳራ አስከትሎባታል::"[38] ይላሉ::

ሐቁ ይህ ቢሆንም፣ የኒዮ-ሊበራል ርዕዮት ፊታውራሪ የሆነው የዓለም ባንክ የሚያራምደው አቋም ከዚህ በጣም የተለየ ነበር:: በዚህ መሠረት ተቋሙ በዋነኛ አበዳሪነት የሚሰጠው ገንዘብ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከመንግሥት የተስፋፋ የትምሕርት አገልግሎት እንዲጐናጸፉ የሚያደርግ አለመሆኑን ማረጋገጡ የማይጠበቅ አልነበረም:: በስቲግሊዝ እንደተመሰከረው በመሊስ የተመራው ኢህአዴግ፣ "አንድ ዓለም አቀፍ ቢሮክራት ዋሽንግተን ላይ ሆኖ ለሚያስተላልፈው መመሪያ ሆነ ለሚለግሰው የተሳሳተ ምክረ-ሀሳብ" ጆሮውን ለማዋስ ፈቃደኛ ስላልነበረ ብቻ፣ በኢትዮጵያ ትምሕርት እስከ 8ኛ ክፍል ለመላው ዜጐች በነጻ የሚዳረስ አገልግሎት መሆኑ መሠረታዊ የፖሊሲው ምሰሶ ሆኖ ሊቀጥል ቻለ::

ከዚህ ውጫዊ ተቃውሞ ባልተናነሰ የአገሪቱ ተቃዋሚዎችም በትምሕርት ፖሊሲው ላይ የማያቋርጥ የማጥላላት ዘመቻ አካሂደዋል:: ተቃዋሚዎች በደፈናው "የንጉሡና የደርግ ዘመን የትምሕርት ሥርዓት አደረጃጀት ይሻላል" ከሚል አቋም በመነሳት ነባሩን የትምሕርት ሥርዓት አደረጃጀት ለመመለስ ይፈልጉ ነበር:: ነገር ግን ተቃውሟቸው በዚህ ብቻ የታጠረ አልነበረም:: ሕጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸውን አጥብቀው ይቃወሙ ነበር:: በብዙ ዘግይተው በለሙ አገሮች፣ ከጀማሪ ደረጃ አልፎ ከፍተኛ ትምሕርት ጭምር በራስ አገር ቋንቋ እየተሰጠ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣቱ የማያወዛግብ ቢሆንም፣ ትምሕርት ቢአማርኛም ሆነ በሌሎች አገርኛ ቋንቋዎች መሰጠቱን አጥብቀው ይቃወሙት ነበር:: አንዳንዶች "በእንግሊዝኛ የማይሰጥ ትምሕርት እርባና ቢስ ነው" እስከማለት የደረሱበት ጊዜም ነበር::

ይህ ተቃውሞ ግን በተቃዋሚ ፓርቲዎች ብቻ የተወሰነ አልነበረም:: ለምሣሌ ሥርዓተ ትምሕርቱ ተግባራዊ መደረግ በጀመረባቸው ዓመታት በአማራ ክልል ከ1-8ኛ ያለው ትምሕርት በአማርኛ መሰጠቱን አንዳንድ የክልሉ ባለሥልጣናትን ጨምሮ ሰፋ ያለ ቁጥር የክበራቸው ምሁራን በግላጭ ይቃወሙት ነበር:: በሌሎች የአገራችን ብሔረሰቦች የሚገኙ ሕጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሳይሆን፣ በአማርኛ መማር አለባቸው ብለው የሚሞግቱት እነዚህ ወገኖች፣ የአማራ ልጆችን በአማርኛ ማስተማርን የሚቃወሙበት አመክንዮ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም፣ "ልጆቻችን በእንግሊዝኛ ካልተማሩ በስተቀር በአማርኛ ተምረው እውቀት ሊይገበዩም" ኤላስማሬት ይደርሱ

ነበር። ቀስ በቀስ ይህ የተሳሳተ እሳቤ በክልሉ የበላይነት በማግኘቱ በ1998 ዓ.ም. ከሰባተኛ ክፍል ጀምሮ ሁሉም ትምህርት በእንግሊዘኛ እንዲካሔድ እስከመወሰን መድረሱ ይህ መሠረታዊ የመብትና የሥነ-ትምህርት /Pedagogy/ መርሕ በአግባቡ እንዳልተያዘ የሚያመላክት ነበር።

ከዚህ የሥነ-ትምህርት ብቸኛ በላይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር የአገር መበታተንን ያስከትላል ከሚል መሠረተ ቢስ ስጋት በመነሳት ሥርዓተ ትምህርቱን የሚቃወሙ ኃይሎችም ነበሩ። የቋንቋ እኩልነት እንዲከበር ማድረግ፣ በህዝቦች መካከል መግባባትና ፍቅርን የሚያጐለብት ነበር፤ ዛሬም ነው። በዚህ ላይ ሕጻናት በሌላ ብሔር ቋንቋ እንዲማሩ ማስገደድ የእውቀት መያዣ መንገድን እጅግ ጠመዝማዛና አስቸጋሪ ያደርገዋል። እያንዳንዱን ፅንሰ-ሀሳብና ቀመር ከመገንዘብ በፊት፣ የቋንቋ ትርጉም እንዲሰሩ በማስገደድ የመማርና የመገንዘብ ፍጥነትም ይቀንሳል። ከዚያም አልፎ በግዴታ የተጫነባቸውን ቋንቋና ተናጋሪውን ወንድም ህዝብ ወደመጥላት እንዲያመሩ ያደርጋል። ስለሆነም እውቀትን ለማስፋፋትም ሆነ፣ በእኩልነት መርህ ላይ ተመሥርቶ ጠንካራ ህዝባዊ አንድነትን ለማጐልበት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር ተመራጭ ነበር። ነገር ግን የቋንቋ እኩልነትን የማይቀበሉት ወገኖች ከዚህ አቋማቸው በመነሳት ገና ከጥዋቱ "አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ትውልድ ገዳይ ነው" የሚል ቅጽል እንዲለጠፍበት አድርገው በዚሁ ቅኝት የተቃውሞ ዘመቻውን ሲያካሂዱ ከረሙ። ኢትዮጵያ በሁሉም መስኮች ፈጣንና ህዝብ የሚጠቀምበት ዕድገት በማምጣት ላይ የመሆኗ እውነታ ጐልቶ እየታየና አዲሱ ትውልድ በከባድ የአገር ግንባታ ተግባር ላይ መጠመዱ በይፋ እየተመሰከረ ባለበትም ዘመቻው ሳያባራ ቀጠለ። አዲሱ ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ በኋላ ያሉ ለውጦችን በመመልከት ሥርዓተ ትምህርቱ ትውልድን የሚያድን እንጂ የሚገድል እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ቢቻልም ይህን ግን መነሻ ማድረግ አልተፈለገም።

አዲሱ የኢትዮጵያ ሥርዓተ-ትምህርት ፖሊሲ በይዘቱ ጥራት ያለው ፍትሃዊ የትምህርት ሥርጭትን በሚያረጋግጥ አካኋን ከተቀረጸ በኋላ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ከሁሉም ዘርፎች የላቀ የመንግሥት በጀት እየተመደበለት በተግባር ላይ ሲውል ቆይቷል። መንግሥት ለመሠረተ-ልማት የሚመድበው ገንዘብ በተለይ ከግዙፍ ወይም ሜጋ ፕሮጀክቶች መስፋፋት ጋር ተያይዞ በእጅጉ በጨመረባቸው ዓመታትም፣ ትምህርት ሁለተኛው ትልቅ የበጀት ምደባ የሚደረግለት ሴክተር ሆኖ ቀጥሏል። በተለይ ከተሃድሶ በኋላ ደግሞ፣ ትምህርት ከኢኮኖሚያዊ ልማት ጋር ተያይዞ እንዲስፋፋ ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል። ፖሊሲው በዚህ አቅጣጫ ተተልሞ ይህንኑ ተግባራዊ የማድረግ እንቅስቃሴ በመካሔድ ላይ ነው። ስኬታማ አገራዊ የፖሊሲ ትግበራውን ተከትሎ በሂደት ብዙ መሻሻሎች የተደረጉ ቢሆንም፣ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በአገሪቱ ተግባራዊ የተደረገው የትምህርት ፖሊሲ ፍትሃዊና ተደራሽ፣ እንዲሁም ጥራቱ የተጠበቀና ፋይዳ ያለው ትምህርት ለሁሉም ዜጐች የማዳረስ ቅኝት የተላበሰ ነበር።

የትምሕርት ፖሊሲው ከተቀየሰ በኋላ የመጀመሪያው ርብርብ ትምሕርትን ለማስፋፋት እንዲሆን ተደረገ፡፡ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲስፋፋ ከመደረጉም በላይ ይህን ሥራ ክልላዊ መንግሥታት በባለቤትነት እንዲመሩት ተደረገ፡፡ ክልሎች ይህን ኃላፊነት ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ በፌዴራል ደረጃ የተቀመጠውን መሠረታዊ አቅጣጫ ተከትለው የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት እንዲስፋፋ አድርገዋል፡፡ በዚህ መሠረት የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች ከሰምንት እጥፍ በላይ ተበራከተው በ2007 ዓ.ም 34,255 ደርሰዋል፡፡ በ1983 ዓ.ም 2.06 ሚሊዮን ብቻ የነበሩት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በ2007 ዓ.ም 19.2 ሚሊዮን ደርሰዋል፡፡ በ1983 ዓ.ም ከሞላ ጐደል ከባዶ የተነሳው የቅድመ መደበኛ ትምሕርትም በተመሳሳይ ዓመት 3.3 ሚሊዮን ህጻናትን ተቀብሎ ያስተማረ ሲሆን፣ በአንደኛ ደረጃ ትምሕርት በድምር 22.6 ሚሊዮን ተማሪዎች እንዲስተናገዱ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ይህ አኃዝ አዲሱ ሥርዓት ከሞላ ጐደል በየዓመቱ በአማካይ ለ900 ሺህ አዳዲስ ተማሪዎች የሚሆኑ ተጨማሪ ትምሕርት ቤቶች፣ የተሟሉ መማሪያ ክፍሎች፣ መምህራንና መጻህፍት ማቅረብ እንደተቻለ ያሳያል፡፡ በየዓመቱ አንድ ሚሊዮን ተማሪዎችን ለተጨማሪ የትምሕርት ዕድል ማብቃት ከባድ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅና ጥቂት አገሮች ብቻ በዚህ የስፋት ደረጃ ያረጋገጡት ስኬት ነው፡፡

በ2007 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በኢትዮጵያ አጠቃላይ የተማሪዎች ቁጥር በድምሩ 26 ሚሊዮን ያህል የደረሰ ሲሆን ይህም ከሞላ ጐደል መካከለኛ የህዝብ ብዛት ካለው አንድ አፍሪካዊ አገር የህዝብ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን ነው፡፡ ለምሣሌ ጋና ያላት የህዝብ ብዛት 26.4 ሚሊዮን ያህል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ያላት የተማሪ ቁጥር ከሞላ ጐደል የጋናን ህዝብ ያክላል፡፡ ወይም ደግሞ በ2017 ቆጠራ መሠረት በአፍሪካ አራት ተኩል ሚሊዮን ህዝብ ካላት መካከለኛዋ አፍሪካ ጀምሮ ያሉት አስራ ዘጠኝ ትንንሽ አገሮች ካሏቸው ህዝቦች ድምር ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡ በመሆኑም ልማቱ የሃያ አፍሪካዊ አገሮች ህዝቦችን በአንዴ ወደትምሕርት ቤት ለመላክ በሚያስችል ደረጃ ተስፋፍቷል፡፡ ትምሕርት መብት ብቻ ሳይሆን የለውጥ መሣሪያ መሆኑን መነሻ በማድረግ፣ ኢትዮጵያ ለፈጣን ልማት እንድትበቃ ማድረግ የተቻለውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "የአፍሪካ አናብስት" ከሚባሉት ቀዳሚዋ እንድትሆን ያደረገው እውነታ ከዚህ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ መንግሥት በፖሊሲው ላይ ትምሕርትን ለማስፋፋት ቅድሚያ መስጠቱ እጅግ የተሳካ ውጤት የተገኘበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዜጐች ለዘመናት ተነፍጓቸው የኖረውን የመማር ዕድል የተጐናጸፉበት፣ በትምሕርት እውቀትና ክህሎት እየተጐናጸፉ፣ የማምረት አቅማቸውና በራስ መተማመናቸው እየተገነባ እንዲሔድ ማድረግ የተጀመረበት ሥርዓት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ ጐን ለጐን ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የትምሕርትን ጥራት ለማረጋገጥ ብዙ እንቅስቃሴ ተካሂዷል፡፡ ከሁሉ በፊት ሥርዓተ-ትምህርቱ ጥራት ባለው አኳኋን ተቀርጿል፡፡

ኢትዮጵያ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ጠንካራ ተፎካካሪ ልትሆን የምትችለው የማምረት አቅምን በመገንባት ነው። በመሆኑም ከምንም ነገር በላይ ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢንጅነሪንግ መስኮች የላቀ ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል። ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ለእነዚህ የትምሕርት መስኮች ልዩ ትኩረት መስጠት ተጀምሯል። ከፍተኛ ትምሕርት 70 በመቶ ለእነዚህ መስኮች ትኩረት በሚሰጥ ቅኝት እንዲስፋፋ ተደርጓል። ትምሕርት በምርምርና ተግባራዊ ሙከራ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በመደረግም ላይ ነው። ይህም በመሆኑ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ብዙ ሳይንቲስቶች፣ ኢንጂነሮችና ቴክኖሎጂ አመንጪዎች በማፍለቅ በከፍለ ዓለመ ብቁ ተወዳዳሪ የመሆን ዕድል ተከፍቶላታል። ለምሣሌ በእነዚህ መስኮች ደቡብ አፍሪካ በየዓመቱ የምታስመርቀው የሰው ኃይል ከ23 ሺህ የማይበልጥ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ በሶስቱ መስኮች የምትቀበለው የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ በአሁኑ ጊዜ ከ70 ሺህ የማያንስ ሆኗል። ደቡብ አፍሪካ ከአህጉራችን በጣም የተሻለ የብቃት ደረጃ ያላቸው ዩኒቨርሲቲዎች የተስፋፉባት አገር መሆኗ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ያሳየችው ግሥጋሴ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። እነዚህ ተማሪዎች በየዓመቱ መመረቅ ሲጀምሩ በእርግጥም አገራችን በነደፈችው ሥርዓተ ትምሕርት ትግበራ የተነሳ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ሳይንቲስቶችና ኢንጂነሮች አገር መሆን ትጀምራለች።

ይህ ስኬት በተወሰነ ደረጃ የትምሕርትን ጥራት በማረጋገጥም ጭምር የተመዘገበ ነበር። በአገሪቱ የትምሕርት ፖሊሲ አገልግሎቱን ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን ጥራቱንም ማስጠበቅ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው መሆን እንዳለበት በግልጽ የተመላከተ ነው። የትምሕርት ጥራት ሲባል የተሟላ እውቀትና ከህሎት ያለው፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ በመልካም ሥነ-ምግባርና የሥነ-ዜጋ እሴቶች የተገነባና በሁሉም የሕይወት መስኮች ተፈላጊውን ውጤት ማምጣት የሚችል ትውልድ መገንባት መቻል ማለት ነው። ይህ ውጤት የብዙ ሥራዎች ድምር ፍሬ ነው። ጥራት ያለው ሥርዓተ-ትምሕርት ከመቅረጽ ጀምሮ ብቁ መምህራን በተፈላጊው ቁጥር በማቅረብ፣ የመጻሕፍት፣ የተማሪዎችና የመማሪያ ክፍሎችን ጥምርታ በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻል የሚሟላ ነው። እነዚህ ሁሉ ከምንም ነገር በላይ የመንግሥትና የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የመምህራንና የተማሪዎችን እንዲሁም የመላውን ሕብረተሰብ ልባዊ ትኩረትና ቁርጠኝነት የሚጠይቁ ናቸው። ከግንባታ ጀምሮ እስከ መጻሕፍት አቅርቦት ድረስ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅርቦትን የግድ የሚሉም ናቸው። አቅሞቹ ደረጃ በደረጃ እየተገነቡ የሚሔዱ በመሆናቸው ጥራትን የማረጋገጥ ጉዳይ ሂደት እንጂ በአንዴ ተሠርቶ የሚጠናቀቅ ጉዳይ አይደለም። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ በራሱ ትምሕርትን ማስፋፋት ቅድሚያ ማግኘት ይገባው የነበረ ከባድ ሥራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በሥራው ላይ ተጨማሪ ከብደት የሚጭንበት ነበር።

በዚህ የተነሳ የትምሕርት ጥራትን የማረጋገጥ ጉዳይ ከባድ ጥረትና ርብርብ የሚጠይቅ እንጅ አልጋ በአልጋ የሚረማመዱበት ሊሆን አይችልም። በሥነ ምግባርና በሥነ ዜጋ የታነጸ

ትውልድ ለመፍጠር እንዲቻል ከኪራይ ሰብሣቢነተ የጸዳ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መገንባት የግድ ይላል። የፖለቲካ ሥርዓቱን የሚመሩት ልሂቃን፣ በተለይ ደግሞ ፖለቲካዊ መሪዎች ከስግብግብነት የጸዱና የላቀ አርዓያነት ያላቸው መሆናቸውን ይጠይቃል። ኮንፊውሽስ "አገርን የሚያስተዳድሩ ሰዎች ንፁህ፣ ቀጥተኛና በስስት ያልተበከሉ ሲሆኑ፣ ዜጐች ሁሉ ስርቆትን የሚጠየፉ ይሆናሉ።" እንደሚለው፣ ሳይሰሩ የመከበር አዝማሚያ በመሪዎችም ሆነ በተመሪው ሕብረተሰብ ዘንድ ቦታ ሊያጣ ይገባዋል። መምህራንም ሆነ መላው የትምሕርት ማኅበረሰብ ወጣቶቻችንን በመልካም ሥነ-ምግባርና በሥነ-ዜጋ እሴቶች መገንባት ለማንም የተሰየ የፖለቲካ ትርፍ የማያስገኝ፣ ይልቁንም መላውን ኢትዮጵያውያን ያለ ልዩነት ተጠቃሚና አሸናፊ የሚያደርግ ተግባር እንደሆነ ተገንዝበው የሚረባረቡበት ሊሆን ይገባዋል።

አንዳንድ ወገኖች "የሥነ-ዜጋና የመልካም ሥነ-ምግባር ትምሕርት የፓርቲ ፖለቲካ ማራመጃ ነው" እንደሚሉት ሳይሆን፤ መልካም ሰብዕና ጊዜና ቦታ፣ ባሕልና ልምድ ሳይወሰነው ማንንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ፀጋ እንደሆነ በመተማመን ብቁ ዜጋ ለመገንባት መረባረብ ይገባል። ትምሕርት ቤቶች ሚሊዮኖችን መልካም ዜጐች አድርገው መቅረጽ ከቻሉ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፓርቲዎች እጅ ወጥቶ የዜጐች የለውጥ መሣሪያ መሆን ይጀምራል። መምህራን ይህን ተገንዝበው ለመልካም ሥነ-ምግባርና የዜግነት እሴቶች ሲረባረቡ፣ በእርግጥም አዲሱ ትውልድ የትም ይሁን መቼ አገሩንና ህዝቡን የሚወድና የሚያከብር፣ ሠርቶ የሚለወጥና አገሩንም የሚለውጥ ሆኖ ይገነባል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ልክ እንደሌሎች ሥራዎች ሁሉ በትምሕርት መስክ፣ በተለይ ደግሞ ጥራትን በማረጋገጥ ጉዳይ ላይ ቀላል የማይባሉ ችግሮች እያሉም ቢሆን አገሪቱ በትክክለኛው ፈርና ጅምር ደረጃ ላይ ትገኛለች። ምንጊዜም ቢሆን የአገር ግንባታ ተግባር ለየዘመኑ ትውልድ ከጅምር የማያልፍ ሥራ ነውና።

በማኅበራዊ ልማት መስክ ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት ሌላው ተግባር የጤና ልማት ነበር። በኢትዮጵያ ህዝቡ ለከፍተኛ ስቃይ የተዳረገበት አንዱ መሠረታዊ ምክንያት በበሽታ፣ በተለይ ደግሞ በመከላከል ሊወገዱ በሚችሉና በሚገባቸው በሽታዎች ሲጠቃ በመኖሩ ነው። ከዚህ በመነሳት ባለፉት በርካታ ዓመታት የህዝቡን የጤንነት ሁኔታ ለማሻሻል በመከላከል ላይ የተመሠረተውን የጤና ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ለዚህም እንዲበጅ መንግሥት ከአርባ ሺህ በላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች አሠልጥኖ አሰማርቷል። በገጠርም ሆነ በከተማ የህዝቡን ጤንነት ለመጠበቅ ያስችላሉ ተብሎ የታመነባቸው በርካታ የጤና ልማት ፓኬጆች ተቀርጸው ተግባራዊ ሆነዋል። ከዚህም ውስጥ የእናቶችና የሕጻናትን ደህንነት ለመንከባከብ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ዋነኞቹ ነበሩ። በተጨማሪም በገጠር ህዝቡን የሚያስቸግሩ ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ህዝብን ያሳተፉ እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል።

የወባ መራባትና መስፋፋትን ለመከላከል ውሃ የሚከማችባቸውን ቦታዎች ከማጽዳት ጀምሮ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር አጎበር በማሠራጨት በዚህ አደገኛ በሽታ የሚሰቃዩና የሚያልቁ ወገኖችን ለመታደግ ተችሏል። አጎበር በማሰራጨት ጉዳይ ኢትዮጵያ ከሩዋንዳ ቀጥሎ በአፍሪካ ሁለተኛዋ አገር ሆናለች። ይህም ሆኖ የህዝብ ብዛት በኢትዮጵያ ላይ የሚጭነው ሸክም ግምት ውስጥ ሲገባ ኢትዮጵያ ብልጫ ትወስዳለች። የጤና ልማት ፕሮግራሙ ከምንም ነገር በላይ በሴቶች ተሳትፎ ሲከናወን ውጤቱ አስተማማኝ እንደሚሆን በማመን ሴቶች የልማቱ ማዕከል እንዲሆኑ ተደርጓል። በእርግጥም የግል፣ የቤተሰብና የአካባቢ ጤንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የሴቶችን ያህል ተፅዕኖ አድራጊ የለምና በኢትዮጵያ ገጠሮች ለተመዘገበው የጤና ስኬት ሴቶች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። ከእነዚህ የመከላከል እንቅስቃሴዎች በተጓዳኝ በሕክምና የሚድኑ በሽታዎችን ለመፈወስ የሚያግዙ ደረጃቸውን የጠበቁ የጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች ተገንብተዋል። ደርግ ከሥልጣን ሲወገድ በአገር ደረጃ 153 ብቻ የነበሩት ጤና ጣቢያዎች ለእያንዳንዱ ሃያ አምስት ሺህ ህዝብ አንዳንድ ጤና ጣቢያ ለማዳረስ በተካሔደ ጥረት ከ3,500 በላይ ደርሰዋል። 72 ብቻ የነበሩት ሆስፒታሎች ተበራክተው ለእያንዳንዱ 100ሺህ ህዝብ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፣ ለእያንዳንዱ 1.5 ሚሊዮን ህዝብ ደግሞ አንድ ሪፈራል ሆስፒታል የመገንባት እንቅስቃሴ በመካሔድ ላይ ነው።

ምንም እንኳ አሁንም ብዙ መሥራት እንደሚገባ ባያጠያይቅም በዚህ ጥረት የተገኘው ውጤት ትልቅና ተስፋ የሚሰጥ ነው። የእናቶችና የሕጻናት ሞት በእጅጉ ቀንሷል። በሆስፒታል የሚወልዱ እናቶች ቁጥር በእጅጉ ጨምሯል። የተላላፊ በሽታዎች የመሰራጨት ምጣኔ በከፍተኛ ደረጃ አሽቆልቁሏል። ትላንት ከትላንት ወዲያ ዝናብ ጠብ ባለ ቁጥር በወባ ትንኝ እየተለከፉ፣ የአልጋ ቁራኛ ,ይሆኑ የነበሩ ዜጐች፣ ዛሬ ከዚህ ተላላፊ በሽታ ነፃ ወጥተዋል። በኢትዮጵያ የወባ ወረርሽኝ መከሰት ካቆመ ከአሥር ዓመታት በላይ ሆኖታል። ኢትዮጵያ ብዙዎችን የምእተ ዓመቱ የጤና ልማት ግቦች ካሳኩ ጥቂት አገሮች አንዷ ልትሆን በቅታለች። ይህ በጥቂት ዓመታት ሥራ የተገኘ ውጤት መንግሥት፣ በመስኩ የተሰማሩ ሙያተኞችና ህዝቡ ያደረጉት ያልተቆጠበ ጥረት ውጤት ነው። ምንም እንኳ በዚህም መስክ ከተሠራው ይልቅ ያልተሰራው የሚበዛ ቢሆንም፣ እስካሁን በተካሔደው ጥረት የተገኘው ውጤት እጅግ ተስፋ የሚሰጥ ነው። በጤና መስክ የተመዘገበው ድል በቸልተኝነት ሳይቀለበስ ይልቁንም ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንግሥትና ህዝቡ ጥረታቸውን አጠናክረው ከቀጠሉ፣ ኢትዮጵያ በርግጥም ከኋላቀርነት የሚመነጩ በሽታዎች ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር የዋሉባትና የህዝቦቿ ጤንነት በከፍተኛ ደረጃ ዮኮጠበቀባት አገር ትሆናለች።

ለመሠረተ - ልማት የተካሔደው ትግልና ውጤቱ፣

በአገሮች መካከል የልማት ልዩነት ጐልቶ ከሚታይባቸው ምክንያቶች አንዱ የመሠረተ-ልማት መስፋፋት ደረጃ ነው፡፡ መሠረተ-ልማት መንገድን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ለሁሉም ማዳረስን፣ የቴሌኮም አገልግሎትን በጥራትና በስፋት ማቅረብን፣ ለሰውና እንሰሳት የመጠጥና ሌላም አገልግሎት፣ ለኢንዱስትሪና ለግብርና ምርት ተግባር የሚሆን በቂ የውሃ መጠን በተመጣጣኝ ከፍያ ማቅረብንና የመሳሰሉትን አገልግልቶች የሚያጠቃልል ነው፡፡ በለሙ አገሮች እነዚህ አገልግሎቶች ከተቻለ በርካሽ ዋጋና በከፍተኛ መጠን ተሟልተው ይገኛሉ፡፡ አገልግሎቶቹ የመልማት ውጤቶች ናቸው፡፡ እዚያው ሳሉ ደግሞ ለመልማት ተፈላጊ ግብዓቶች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት አገልግሎቱ በተስፋፋባቸው አገሮች ሁሉ ዜጐች ሁለቱንም ጥቅሞች ያገኛሉ፡፡ በአንድ በኩል በአገልግሎቱ መስፋፋት የተመቻቸ ሕይወት ይኖራሉ፡፡ በሌላ በኩል የተስፋፋውን መሠረተ-ልማት አዲስ ሀብት ለመፍጠር በማሳለጫነት ይጠቀመበታል፡፡ ለምሣሌ አንድ ጀርመናዊ ከመኖሪያ ቤቱ በአማካይ በ200 ሜትር ርቀት ወይም አምስት ደቂቃ እንኳ በእግሩ ሳይጓዝ የመኪና መንገድ ያገኛል፡፡ ይህም በመሆኑ እንደእኛ አገር ሰው ለሰዓታት በእግሩ እየኳተነ ጉልበቱን ያልሆነ ቦታ ላይ በማፍሰስ ጊዜውን አያባክንም፡፡ በቅርብ በሚያገኘው መንገድ ተጉዞ በፍጥነት ወደማምረቻ ቦታው በመድረስ ያመርታል፣ ምርቱንም ወደተጠቃሚው ያጓጉዛል፡፡ ይህም በመሆኑ መሠረተ-ልማት በጥራትና በስፋት በተገነባባቸው አገሮች ለተፋጠነ ልማትና ለተመቻቸ የህዝብ ህይወት አስተማማኝ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በበለጸገው ዓለም ያለው ሁኔታ ይህን የመሰለ ሲሆን፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ በሁሉም ያልበለጸጉ አገሮች መሠረተ-ልማት በዝቅተኛ የመስፋፋት ደረጃ ላይ የሚገኝ አገልግሎት ነው፡፡ መንገዶች ጥቂትና አስቸጋሪ ናቸው፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትም ሆነ ማዳረስ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የቴሌኮም አገልግሎት ከሞባይልና የሳተላይት መረቦች ጋር ተያይዞ በመስፋፋት ላይ ቢሆንም፣ በሰፊ አውራ ጐዳናነት የሚታወቀው የፋይበር ኦፕቲክስ መረብ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ለሰው፣ ለእንስሳት፣ ለግብርናና ለኢንዱስትሪ ልማት የሚሆን የውሃ አቅርቦት አልተስፋፋም፡፡ በአጭሩ መሠረተ-ልማት በውጤትነትም ሆነ በግብዓትነት ተሟልቶ አይገኝም፡፡ ይህም በመሆኑ በእነዚህ አገሮች የሚገኙ ዜጐች ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውንና ያላቸውን የገንዘብና ሌላም ፀጋ አቀናጅተው ወደልማት ተግባር ለመሰማራት ይቸገራሉ፡፡ ለማምረት አስፈላጊው የመሠረተ-ልማት አቅርቦት ባለመሟላቱ ሥራውን ከመጀመር ይቆጠባሉ፡፡ እንደምንም ሥራውን ከጀመሩና ካመረቱ በኋላም ምርታቸውን የማከፋፈል ጉዳይ በአቅርቦቱ አለመሟላት ምክንያት ይታነቃል፡፡ ስለዚህም መሠረተ-ልማት ያልበለጸጉ አገሮችን ሁሉ ከዕድገት ገትቶ የሚይዝ አንድ መሠረታዊ ችግር ነው፡፡ ይህን ችግር መፍታት የተሳነው

ማንኛውም አገር ልማቱን መጀመርም ሆነ ማፋጠን ይሳነዋል። በአንጻሩ ይህን አገልግሎት ማቅረብ የጀመረ አገር በዚያው ልክ ለፈጣን ልማት ይታደላል።

መሠረተ-ልማት መስፋፋት ወይም አለመስፋፋቱ ይህን ያህል የልማት ዕድልን የሚወስን ቢሆንም፣ ሁሉም መንግሥታት፣ ተቋማትና ግለሰቦች በጉዳዩ ላይ ተመሳሳይ አቋም የላቸውም። በዚህ ምዕራፍ ሁሉንም ልዩነቶች በዝርዝር መመልከት ባይቻልም በዘርፉ ልማት ዙሪያ ቁልፍ ሚና በሚጫወቱ ኃይሎች መካከል የሚታየውን የአቋም ልዩነት አጠር አድርጎ መመልከት በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለመያዝ ያግዛል። በኢትዮጵያ ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ ሲካሔድ የቆየውን የመሠረተ-ልማት ግንባታ ሲመራና ሲያስፈጽም የቆየውን የትግል ትውልድ ፍልስፍና፣ ተጨባጭ ትግልና ያስመዘገባቸውን ውጤቶች በምሉእነት ለመገንዘብም ዕድል ይሰጣል።

በመሠረተ-ልማት አውታሮች ግንባታና የማስፋፋት ተግባር ዙሪያ የሚታየው መሠረታዊ ልዩነት፣ በአንድ በኩል በኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ፣ በሌላ በኩል በልማታዊ መንግሥት ቅኝት በሚመሩ ኃይሎች መካከል ያለ ልዩነት ነው። ኒዮ-ሊበራሎች በዓለማችን የበላይነትን ከያዙባቸው ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ "ሁሉም የኢኮኖሚና የልማት ተግባር በገበያውና በባለሀብቱ ብቻ ሊሰራ ይገባዋል" ከሚል አቋም በመነሳት፣ "መንግሥት ይህን አገልግሎት በማቅረብ ላይ ከተሰማራ መ·ስና የማይቀር በመሆኑ ሕብረተሰብ ኪሳራ እንጂ ትርፍ አያገኝም፣ ስለዚህም የመንግሥት ሚና ባለሀብቱና ገበያው የማምረትና የማከፋፈል ተግባራቸውን ያለ እንከን እንዲፈጽሙ ሕግና ሥርዓትን በማስከበር ብቻ መወሰን አለበት" ይላሉ።

ኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ እንከተላለን የሚሉት ኃይሎች ከዚህ ርዕዮት በመነሳት መንግሥት በመሠረተ-ልማት ላይ የሚያደርገውን ኢንቨስትመንት ይቃወማሉ። በመንግሥት የሚሰጡ አገልግሎቶች ሁሉ ተቋርጠው የተቻለውን ያህል በባለሀብቱና በገበያው እንዲቀርቡ መደረግ አለባቸው ይላሉ። "መንግሥት ከባንክ እየተበደረም ሆነ፣ ከሌላ ምንጭ እያገኘ ለልማት በሚመድበው ገንዘብ የባለሐብቱን የመሳተፍ ዕድል የሚያጣብበው ስለሚሆን፣ ከዚህ ዓይነቱ ልማት እጁን ሙሉ በሙሉ ማንሳት አለበት" ይላሉ። አልፎ ተርፎም የመንግሥት ወጪ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ፣ በዚህም ምክንያት ለልማት የሚመድበው በጀት ከይስሙላነት ያልዘለለ እንዲሆን ይመክራሉ። በአጠቃላይ መንግሥት በመሠረተ-ልማት ግንባታና ህዝባዊ አገልግሎቶችን በማስፋፋት ተግባር ላይ ከተጠመደ ለጥቂቶች የበላይነት የማይመች ሁኔታ ይፈጠራል ብለው በመስጋት ተሳትፎው የተገደበ እንዲሆን ይፈልጋሉ። ለብድር ሲሉ የፖሊሲ ነጻነታቸውን ያጡና በዚህ አስተሳሰብ ለመመራት የተገደዱ አገሮች ሁሉ ግን እንደተመከሩት በግሉ ሴክተርና በገበያው ለተስፋፋ መሠረተ-ልማት ሲበቁ አልታዩም። በዚህ የተነሳ በኒዮ-ሊበራሎቹ ምክር ተመርተው መሠረተ-ልማታቸውን ተወዳዳሪ በሆነ ደረጃ በተጨባጭ የገነቡ

ታዳጊ አገሮች ማግኘት አስቸጋሪ ሆኗል። ራሱ የዓለም ገንዘብ ድርጅቶ "ፖሊሲው የዕድገት ጭማሪ ያስገኛል የተባለውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ በተካሔደ ግምገማ በርካታ አገሮች በተጨባጭ የዕድገት ተቋዳሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አልተቻለም።" በማለት ለማመን እንደተገደደው ባለሀብቱም ገበያውም በሌሉበት ተጨባጭ ሁኔታ በእነዚህ በመተማመን ሊገነባ የሚችል መሠረተ-ልማት አልነበረምና።

ኒዮ-ሊበራሎቹ የሚያራምዱት ይህ አስተሳሰብ ኪራይ ሰብሣቢነትና የእርሱም አንድ መገለጫ የሆነው ሙስና መንግሥታዊ ከስተት ብቻ እንጂ ባለሀብቱን የሚመለከት ችግር እንዳልሆነ የሚያስመስል ነው። ሐቁ ግን እንደኢትዮጵያ ባሉ ኋላቀር አገሮች ውስጥ ኪራይ ሰብሣቢነት ሠርቶ ለመከበር የሚያስችል ልማትን የሚደግፍ ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ የሚፈጠር ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ነው። በመሆኑም ዝንባሌው መንግሥትን የሚበከለውን ያህል የግል ሴክተሩንም የመበከል ችሎታ ያለው ሲሆን፣ ባለሀብቱ በሙስና የመከበር እንቅስቃሴ ላይ በብዛት ቀዳሚነትን ሲወስድ መታየቱ ይህን የሚያረጋግጥ ነው። ስለሆነም ሙስናን መንግሥታዊ ዝንባሌ ብቻ አድርጎ ማስቀመጥም ሆነ መንግሥትን ብቻ የዚህ ዝንባሌ ቀዳሚ ጠበቃ ማድረግ ስህተት ነው።

ከዚህ በመነሳት መንግሥት ለሕብረተሰብ ዕድገትና ለብዙኀኑ ልማታዊ ተጠቃሚነት ቁልፍ ጠቀሜታ ያለውን መሠረተ-ልማት እንዳይገነባ መከልከል፣ ማስተጓጎልም ሆነ ማደናቀፍ ያልበለጸጉ አገሮችን ከባድ ዋጋ የሚያስከፍል ስህተት ነው። ይልቁንም በሙስና የመከበርን ዕድል እያጠበበ፣ በልማት ለመከበር የሚያግዝ መሠረተ-ልማት ግንባታ ላይ ለመረባረብ የቆረጠን መንግሥት ማበረታታትና መደገፍ ይገባል። አገልግሎቱ በገበያውና በባለሀብቱ አለመስፋፋት፣ ባልበለጸጉ አገሮች የሚገኙ መንግሥታት መሠረተ-ልማትን በማስፋፋት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ በቂ ምክንያት ቢሆንም፣ መንግሥት በዚህ ቁልፍ ተግባር ላይ እንዲሰማራ ማድረግን የግድ የሚሉ ሌሎች በርካታ ምክንያቶችም አሉ።

በመሠረተ-ልማት ግንባታ ላይ መንግሥት ተነሳሽነቱን ሊወስድ ከሚገደድባቸው ምክንያቶች ዋናው ድሃና ኋላቀር አገሮች ለዕድገት የሚያስፈልጋቸውን መሠረተ-ሰፊ የልማት አውታር አሟልቶ የሚያቀርብ ባለሀብትም ሆነ ገበያ የሌላቸው መሆኑ ነው። እንደሚታወቀው ባልበለጸጉ አገሮች በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሠማርቶ ሰፊ ሀብት በመፍጠር የካፒታል አቅሙ የተገነባ ብዙ ባለሀብት የለም። በዚህ ምክንያት እንኳን መሠረተ-ሰፊና ሁሉን አቀፍ የመሠረተ-ልማት አውታሮችን ለማስፋፋት፣ ጥቂት መንገዶችን ብቻ ለመሥራት የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ያለው ባለሀብትም አይገኝም። ይህን የመሰለ ብቃት ያለው ባለሀብት ባልተፈጠረበት ወይም በሌለበት በባለሀብቱ በመተማማን መሠረተ-ልማትን ማሟላትና ከድኅነትና ኋላቀርነት መላቀቅ አይቻልም። ባለሀብቱ እስኪፈጠር ድረስ እጅን አጣጥፎ በመቀመጥም ለብልጽግና

መብረቃተ አይቻልም::

አገር በቀል ኩባንያ ባይኖርም ከፍተኛ አቅም ባላቸው የውጭ ባለሐብቶች አማካይነት መሠረተ-ልማትን እናስፋፋ ቢባልም ይህም የራሱ የተለያዩ ችግሮች ያሉበት ነው:: በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ የውጭው ባለሀብት ገንዘቡን ይዞ በመምጣት መሠረተ-ልማት እንዲያስፋፋና አገልግሎቱን እየሸጠ ወጭውን ለማስመለስ እንዲችል የማድረግ አማራጭ ሊሞከር ይችላል:: ይሁንና የውጭው ባለሀብት ይህን ያድርግ ቢባል ባልበለጸጉ አገሮች ወጭውንም ሆነ ትርፉን ከመሠረተ-ልማት አገልግሎት ሽያጭ በቅርብ ርቀት መልሶ ለማግኘት አይችልም:: ድሃ አገሮች ያላቸው የመከፈል አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ወጭውን በጣም በተራዘመ ጊዜ፣ ለዛውም አስተማማኝ ባልሆነ ደረጃ ከማስመለስ ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖረውም:: ይህም በመሆኑ በአጭር ጊዜ ወጭውን አስመልሶ ትርፍ ማግኘት ለሚሻው የውጭ ባለሀብት ይህ አማራጭ የሚዋጥለት ሆኖ አይታይም::

አንዳንዶቹ የመሠረተ-ልማት አገልግሎቶች ደግሞ በተጠቃሚዎች መካከል የከፍያ ልዩነት ማድረግን የማይፈቅዱ ናቸው:: ሁሉም ሰው በነጻ ካልሆነ በስተቀር በከፍያ ሊጠቀምባቸው የማይችሉ በርካታ የመሠረተ-ልማት አገልግሎቶች አሉ:: ለምሣሌ በቀን አምሳ መኪና ብቻ በሚመላለስበት አንድ የገጠር መንገድ ገንዘብ የከፈሉት ብቻ በመንገዱ መኪናቸውን እንዲያመላልሱ ማድረግና ያልከፈሉትን መከልከል አይቻልም:: ባለሀብቱ መንገዱን ከገነባ በኋላ አገልግሎቱን በከፍያ ይስጥ ቢባል እንኳ የተመላላሽ መኪኖች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ትርጉም ያለው ወጪ የማስመለስ ሥራ ሊያከናውን አይችልም:: በዚህ ላይ መንገዱ ለተገልጋዮች ያለ ልዩነት ከፍት የሚደረግ በመሆኑ ሁሉም ሰው ሳይከፍል መጠቀምን መምረጡና ባሕል ማድረጉ አይቀርም:: ይህም በመሆኑ የውጭው ባለሀብት መሠረተ-ልማትን ባልበለጸጉ አገሮች ላይ ለማስፋፋት ኢንቨስት ያድርግ ቢባል በአብዛኛው ከኪሳራ በስተቀር ትርፍ ሊያገኝ አይችልም:: ስለዚህም በአገር በቀል ሆነ በውጭ ባለሀብቶች በመተግመን የድህና ኋላቀር አገሮችን የመሠረተ-ልማት ጥያቄ መመለስ አይቻልም:: የውጭውም ሆነ የአገር ውስጡ የግል ሴክተር ዕድገቱ የሚጠይቀውን ያህል መሠረተ-ሰፊ የልማት አውታር መገንባት ይቅርና የመንግሥትን መሠረተ-ልማት የማስፋፋት ጥረት በትንሹም ሊደግፍ የሚችል ኢንቨስትመንት ያደርጋሉ ተብሎ ሊጠበቅ አይችልም::

ከዚህ በመነሳት በታዳጊ አገሮች ዘርፈ ብዙ የመሠረተ-ልማት አውታሮችን የመገንባት ጉዳይ በወሳኝነት በመንግሥትና በህዝብ ትከሻ ላይ የወደቀ ኃላፊነት ይሆናል:: በዋነኛነት መንግሥት ይህን ሚና ካልተጫወተ በስተቀር የግሉን ባለሀብት ጨምሮ የሁሉም ዜጐች ልማታዊ ጥረት መሰናከሉ አይቀርም:: ስለሆነም በታዳጊ አገሮች የሚገኙ መንግሥታት በመሠረተ-ልማት አውታሮች ግንባታ ላይ ግንባር ቀደም መሆን ይገባቸዋል:: ተግባሩ የሞት ሽረት ጉዳይ እንደሆነ

ተገንዝበው በላቀ የፍይናንስ ሲቪሊዚን ልሂቅ ሃገራት ሃገራዊ ሥራዎች ሲሆኑ ይታዩ። በእርግጥ ኒዮ-ሊበራሊዝም መንግሥትን ከጨዋታ ውጪ ከሚያደርገው አስተሳሰቡ ባሻገር የሚያነሳውን የሙስና ስጋት ቸል ማለት አይቻልም። ይሁንና ይህን በመስጋት የመንግሥትን ልማታዊ ተሳትፎ ከመገደብ ይልቅ፣ ሙስናን እንደአንድ ተጨባጭ አደጋ ተመልከቶ ይህንኑ ከልማቱ ጐን ለጐን በመታገል ማስወገድ የተሻለ ይሆናል። በዚህ መንገድ ባልበለጸጉ አገሮች በግሉ ሴክተር ተዋናይነት ሊሟላ የማይችለውን የመሠረተ-ልማት በመንግሥት አማካይነት በፍጥነትና በጥራት ማሟላት ይገባል። ይህን ማድረግ ሲቻል ብቻ የበለጸጉ አገሮች በተራዘመ ሂደት የገነቡትን የመሠረተ-ልማት አውታር የሚመጥን ግንባታ ማካሔድና አገርን ለመሠረታዊ ለውጥ ማብቃት ይቻላል። በመሠረተ-ልማት ግንባታ ጥያቄ በኢህአዴግና በዓለም አቀፉ የኒዮ-ሊበራል ኃይል መካከል ያለው ዋናው ልዩነት ይህ ነው። ኢህአዴግ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በዚህ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ የያዘውን ትክክለኛ አቅጣጫ ጠብቆ ተጉዟል። የኢትዮጵያን ልማት ለማፋጠንና የህዝቦቿን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሲባል የመሠረተ-ልማት አውታሮችን ማስፋፋት ከመንግሥት ቀዳሚ ተልዕኮዎች አንዱና ዋነኛው እንዲሆን አድርጓል።

ኢህአዴግ ከመሠረተ-ልማት አውታሮች መካከል ቅድሚያ ትኩረት የሰጠው መንገድን ለማስፋፋት ነበር። በኢትዮጵያ ከአፄ ሚኒልክ ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም የተሠሩት መንገዶች በድምሩ ከሠላሳ ሶስት ሺህ ኪሎ ሜትር የማይበልጡ ነበሩ። ከዚህ ውስጥ አስራ ስድስት ሺህ ኪሎ ሜትር ያህሉ እስከንጉሱ ዘመን የተሠራ ሲሆን ቀሪው ደግሞ የተሠራው በደርግ መንግሥት ነው። ከዚህ መንገድ ውስጥ 60 በመቶ ያህሉ በኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ትርፍ አምራች አካባቢዎች ላይ የተገነባ ነበር። መሠረተ-ልማቱ በእነዚህ አካባቢዎች የተስፋፋበት አንዱ ምክንያት የቀድሞዎቹ ገዥዎች ከእነዚህ አካባቢዎች ላይ በግዳጅ ይሰበስቡት የነበረውን ትርፍ ምርት ለማጓጓዝ ነበር። ትርፍ ምርት አይገኝባቸውም ተብሎ የሚታመኑትና በአብዛኛው ሰንሰለታማ ተራሮች የሚበዙባቸው የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ደግሞ ከዚሁ የመንገድ ግንባታ በተገቢው ደረጃ ተቋዳሽ አልነበሩም። ይህን እውነታ በዘውዳዊው አገዛዝ ዘመን የብሔራዊ ባንክ ገዥ የነበሩት አቶ ተፈራ ደግፌ ስለተወለዱባት አንኮበርና አካባቢዋ በ1964ዓ.ም. ካካሔዱት ጉብኝት በመነሳት ፣

> "አንኮበር በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሀብታምና የዘርፈ ብዙ የግብርና ኢኮኖሚ ባለቤት የሆነች መንበረ ነገሥታት ነበረች። ወረዳዋ ከዋና ዋና መንገዶች ራቅ ብላ በዳርቻ ላይ የምትገኝ በመሆኗ የእህል ንግድ ገበያ ሠርፆ አልገባባትም። በዚህ የተነሳ የድሮ ብልጽግናዋ ደብዛው ጠፍቷል።... የትውልድ መንደሬን ስጐበኝ ወደኋላ ተመልሼ እንዳስተውልና እንዳሰላስል ዕድል በማግኘቴ ድሮ በነበረኝ

> ያልጠራ አይታኒ አሁን ላየሁተ አውነታ መካከል ቀራኔ ውስጥ ወድቄያለሁ። በገጠር ፍፁም በተዘነጋው የአገሬ ገበሬዎች ደህንነት (Welfare) ሐፍረት ተሰምቶኛል። ጠቀም ያለ ደመወዝና ስኬታማ የሥራ ሕይወት ቢኖረኝም፣ ለመንደሬ ሰዎችና የትምሕርት ወጭዬን ለሸፈኑት አርሶ አደር ወገኖቼ ምንም ባለመሥራቴ የጸጸት ስሜት አድሮብኛል።"[39] በማለት በሰጡት ምስክርነት ማረጋገጥ ይቻላል።

ኢህአዴግ አገሪቱን ማስተዳደር ሲጀምር ትርፍ የማምረት አቅምን ለማሳደግ እንጂ ትርፍ ምርት ለመቃረምና ለመንጠቅ ሲባል ብቻ የሚከናወነውን ይህን የመንገድ ሥራ ቅኝት መቀየር ነበረበት፡፡ በዚህ መሠረት አዳዲስ አገር አቋራጭ መንገዶች የመገንባት ሆነ ነባሮችን የመጠገንና የማስፋፋት ሥራ በልማታዊና ህዝባዊ ቅኝት የሚመራ እንዲሆን ተደረገ፡፡ በ1980ዎቹ አጋማሽ ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ በጀት የተጀመረው የዓለም ከተማ-ሰቆጣ-ዓቢይ ዓዲ መንገድ ይህን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ መንገድ በዋነኛነት ከአዲስ አበባ-ደሴ-መቐለ ከሚወስደው መንገድ በስተምዕራብ የሚገኘውን ሰፊ የአማራ ህዝብ የሚያገለግል መንገድ ሲሆን፣ በዚህ የአገሪቱ ክፍል የሚኖረው ህዝብ ለዘመናት ከአገር አቋራጭ መንገዶች በጣም ርቆ ኖሯል፡፡ በዚህ ምክንያት የምርት ተግባሩንና ማኅበራዊ እንቅስቃሴውን የሚደግፍ የመሠረተ-ልማት አገልግሎት ማግኘት ሳይችል ቆይቷል፡፡ ይህ መንገድ ተሠርቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰዱ የአፈጻጸም ችግር ያልተለየው ቢሆንም፣ ኢህአዴግ የመንገድ ልማትን ህዝብን በሚጠቅም ቅኝት ማስኬድ እንደጀመረ ግን አመላካች ነው፡፡ በተመሳሳይ ወቅት የተጀመሩት የአዲስ አበባ አሰብ መንገድ ጥገናና የአዲስ አበባ ሐዋሳ መስመር ወደ ኮንክሪት አስፓልት እንዲሸጋገር መደረጉም በተመሳሳይ መስፈርት የተከናወኑ ነበሩ፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ በወጣ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት እነዚህን መንገዶች በመገንባት የተጀመረው እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋና እየዳበረ ሔዷል፡፡ በሂደት ደግሞ በፊዴራል መንግሥትና በአካባቢ አስተዳደሮች መካከል የጠራ የሥራ ከፍፍል በማድረግ የአውራ ጐዳናዎችና የገጠር መንገዶች ግንባታና ደረጃን የማሻሻል ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ከአዲስ አበባ ወደሁሉም የአገሪቱ ጫፎች የሚወስዱ መንገዶች ሁሉ ደረጃቸው ከፍ ብሎ የአስፓልት ኮንክሪት ሆነዋል፡፡ በስተደቡብ ምሥራቅና ደቡብ ከአዲስ አበባ-ሐረር/ጅግጅጋ፣ ከአዲስ-አሰላ/ሮቤ፣ ከአዲስ አበባ-ሐዋሳ/ሞያሌ መንገዶች አስፋልት ለብሰዋል። በደቡብ ምዕራብና ምዕራብ አቅጣጫ ከአዲስ አበባ ጅማ/ጋምቤላ፣ ነቀምት/አሶሳ፣ በስተሰሜን ምዕራብ ከአዲስ አበባ ባሕር ዳር/ጐንደር/መተማና ሁመራ፣ በስተሰሜን ደሴ/መቐለ/አዲ-ግራት፣ በስተምሥራቅ ደግሞ ወደሰመራና ጅቡቲ የሚወስዱ መንገዶች ሁሉ ወደዘመናዊ የአስፓልት መንገድ አድገዋል፡፡

ከእነዚህ ሌላ እንደወሮታ/ወልዲያ፣ ሶዶ/ጪዳ፣ ግንደ ወይን/ኮምቦልቻ፣ ሐራ/ሚሌ፣ ሽሬ/ሁመራ፣ ነቀምት/ጅማ የመሳሰሉ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው ኮሪደሮች እየተለዩ በአስፓልት መንገዶች እንዲገናኙ ተደርጓል። አሁን ደግሞ በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ብዙ ተሽከርካሪዎችን በፍጥነት የሚያስተላለፉ ሰፋፊ ጎዳናዎች /Expressways/ መገንባት ተጀምሯል። የአዲስ አበባ አዋሽ ኤክስፕረስ መንገድና በአቅድ የተያዙት ተመሳሳይ መንገዶች ይህን ያመላክታሉ።

ክልሎች በበኩላቸው በየራሳቸው አቅም በቀን አሥር መኪና ከሚያስተላልፉ የገጠር መንገዶች ጀምሮ አምሳ መኪኖች እስከሚያስተላልፉ እጅግ በርካታ መንገዶችን ገንብተዋል። ከመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ጀምሮ ደግሞ ቀበሌዎችና የወረዳ ማዕከላትን በ"ሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም" (Universal Rural Road Access Program URRAP) አማካይነት ለማገናኘት የከረምት ከበጋ መንገድ ግንባታዎች እየተስፋፉ ነው። ይህ የገጠር መንገድን የማስፋፋት እንቅስቃሴ እዛው ሳሉ የአገር ውስጥ የመንገድ ሥራ ኩባንያዎች ለመፍጠርና በርካታ አገር በቀል ኮንትራክተሮችን ኮትኩቶ ለማሳደግ ዕድል ከፍቷል።

በኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ ዓመታት የተካሔደው የመንገድ ልማት በአውራ ጎዳናዎችና በገጠር መንገዶች ብቻ የተወሰነ አልነበረም። የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የባቡር ሐዲዶችን በማስፋፋት ጭምር የተከናወነ ነው። በኢህአዴግ የተመራው መንግሥት በኢትዮጵያ መሠረቱ ተጥሎ የቆየውንና ከፍተኛ ዝና ያለውን አየር መንገድ ተደራሽነት እጅግ አስፋፍቶታል። በአገር ውስጥ ነባርና አዳዲስ የአየር ማረፊያዎችና ተርሚናሎችን ከመገንባትና ከማስፋፋት በተጨማሪ የአገሪቱ የአየር ትራንስፖርት አቅም በከፍተኛ ደረጃ ተገንብቷል። የአዲስ አበባ፣ ባህር-ዳርና ድሬ-ዳዋ ነባር የአስፓልት አየር ማረፊያዎችን አስፋፍቷል። የጠጠር ማኮብኮቢያ ከነበራቸው አውሮፕላን ማረፊያዎች ከሞላ ጉደል ሁሉም ወደአስፓልት ተቀይረዋል። የቱሪስት መዳረሻ በሆኑት እንደላሊበላ በመሳሰሉና ለኢንቨስትመንት እየተከፈቱ ባሉ እንደአሶሳ ዓይነት ቦታዎች ላይ አዳዲስ ዘመናዊ የአየር ማረፊያዎች ተገንብተዋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የነበረው መለስተኛ የሰውና የጭነት ማጓጓዣ አቅም በብዙ እጥፍ እንዲያድግ ተደርጓል። አየር መንገዱ ከመንግሥት በተሰጠው ልዩ ትኩረትና ድጋፍ እንዲሁም በሰብዓዊ ኃይሉ ትጋትና ከፍተኛ ርብርብ በእርግጥም የአፍሪካ ቀዳሚ አየር መንገድ ሊሆን ችሏል። ለመኩራራት በር በማይከፍት፣ ይልቁንም ከውድድሩ ከባድነት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ በሚገባበት ወቅት ላይ መገኘታችን ሳይዘነጋ፣ በዓለማችን የልዩ ልዩ አገሮች ባንዲራ አውለብላቢ አየር መንገዶች በከሰሩበት ዓለም በስፋት መብረሩን ቀጥሏል።

በኢትዮጵያ የመንገድ መሠረተ-ልማት መበፋፋት ያለበተ መሆኑ አንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ተግባር ከአገሪቱ የዕድገት ደረጃ ጋር የተገናዘበ፣ የአሁኑን ዕድገት የሚሸከምና ቀጣዩንም ዕድገት የሚደግፍ መሆን እንዳለበት ይታመናል። ይህ ካልሆነ በስተቀር አገሪቱ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ተወዳዳሪ የሆነ የመንገድ መሠረተ-ልማት ሊኖራት አይችልም። ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ በመነሳትና በተለይ ደግሞ በአገሪቱ በመመዝገብ ላይ ያለው ፈጣንና መሠረተ-ሰፊ ዕድገት የሚያስገኛቸውን ምርቶች በፍጥነትና በላቀ መጠን ለማጓጓዝ የባቡር መሠረተ-ልማት መስፋፋት እንዳለበት አያከራክርም። በኢትዮጵያ እየተካሔደ ያለውን ለውጥ ተከትሎ ከትንንሽ ማጓጓዣዎች በአንዴ ብዙ ሰዎችና ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ቁሣቁሶ ች ወደማጓጓዝ (Mass Transport) መሸጋገር አንድ የወቅቱ ዐቢይ ጥያቄ እየሆነ መጥቷል። አገሪቱ በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ በመተማመን በትንሹ እስከ አንድ ቢሊዮን ኩንታል እህል የማምረት ችሎታ አላት። በመኸር ዝናብና በመስኖ በመጠቀም ከሚለማው 20 ሚሊዮን ያህል ሔክታር ምርታማነትን በአማካይ በሔክታር አምሳ ኩንታል በማድረስ ብቻ ይህን ውጤት ማምጣት ይቻላል። ከዚህ ውጭ ደግሞ አገሪቱ ወደፊት ልታመርታቸው የምትችላቸውን እንደፖታሽ፣ ነዳጅና ብረት የመሳሰሉ የማዕድን ምርቶች ጨምሮ በጭነት መኪና ብቻ ሊጓጓዝ የማይችል መጠነ ሰፊ ሎጅስቲክስ የሚጠይቅ ምርት እንደሚኖራት ይጠበቃል።

እነዚህና በአንድ ጊዜ ሚሊዮኖችን ከቦታ ቦታ የማጓጓዝና አገልግሎቱ የአካባቢ ብክለትን በማያስከትል ደረጃ እንዲስፋፋ የማድረግ አስፈላጊነት ተዳምረው ይህን ከፍተኛ የማጓጓዣ አቅም መገንባት አጣዳፊ ሆኗል። ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት በኢህአዴግ የተመራው መንግሥት በጥቂት ዓመታት ውስጥ በሺዎች ኪሎ ሜትሮች የተዘረጋ የባቡር መሠረተ-ልማት የማስፋፋት አቅድ ነድፎ ይህንኑ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። የመቶ ዓመታት እድሜ ያለውን የኢትዮ-ጂቡቲ የባቡር መስመር ከጠባብ ወደሰፊ (Standard Gauge) በማሳደግ የተጀመረው ይህ ግንባታ በአሁኑ ጊዜ ወደመጨረሻው ምዕራፍ ደርሷል። ከምሥራቅ ወደምዕራብ፣ ከሰሜን ወደደቡብ የሚወስዱና ከብዙዎቹ ጐረቤቶቻችን ጋር የሚያገናኙ የባቡር ሐዲዶች ግንባታ ተጀምሯል። በዚህም ሂደት አገራዊ የባቡር መሠረተ-ልማት የማስፋፋት ቴክኖሎጂያዊ ብቃት ለመገንባት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል። ይህ አቅም በአንድ በኩል ክሊሎች ጋር በመተባበርና እየሠሩ በመማር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመስኩ በአገር ውስጥና በውጭ በሺዎች የሚቆጠሩ መሐንዲሶን ማሠልጠንና ማፍራት በሚያስችል ቅኝት መፈጸም እንዳለበት በመታመኑ ይህን ለማሳካት እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ ነባሩንም ሆነ አዳዲሶቹን የባቡር መሠረተ-ልማቶች ከዓለም አቀፍ ደረጃ ጋር በተጣጣመ አኳኋን ለመገንባት የጀመረችው እንቅስቃሴ ከኒዮ-ሊበራል ተቋማት በኩል ቀላል የማይባል እንቅፋት ሳያጋጥመው አላለፈም። ለባቡር ሥራው መስፋፋት

ከፍተና የገንዘብ ብድር ሊያቀርቡ ይተላሉ ተብለው የተገመቱተ አበዳሪ ተጫማተ፣ "ኢተዮጵያ ወደስታንዳርድ ጌጅ መሸጋገር አያስፈልጋትም" የሚል ከረር ያለ ምከረ-ሀሳብ አቅርበው ነበር። ይህ ማለት "ኢትዮጵያ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ማስፋፋት ያለባት አገሮችን አቆራርጦ የሚያገናኝ የባቡር መሠረተ-ልማትን ሳይሆን፣ ነባሩንና ወይም ከእርሱ በትንሹ ሰፋ ብሎ ከመደበኛው ዓለም አቀፍ የባቡር ሐዲድ ስፋት ጋር የማይገጥመውን ጠባብ ሀዲድ በማስቀጠል መወሰን ይገባታል" ማለት ነው።

ይህም ሆኖ መንግሥት ይህን አቅጣጫ ላለመቀበል ጸንቶ በመቆመ· ብቻ ይህ ምከረ-ሀሳብ ተግባራዊ ሳይደረግ ቀርቷል። በቅርቡ ከዩጋንዳ የፓርላማ አባላት ጋር ለልምድ ልውውጥ በሐድኩ ጊዜ የባቡር ልማትን ጨምሮ ስለኢትዮጵያ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የዕድገት አቅጣጫ የተወሰነ ማብራሪያ ለማቅረብ ዕድል አግኝቼ ነበር። የሰጠሁትን ማብራሪያ መነሻ በማድረግ በተካሔደው ውይይት ከአገሪቱ መሪ ፕሬዚዳንት ዩዌሪ መሴቬኒ አንደበት፣ መንግሥታቸው ጠባቡን የቅኝ ግዛት ዘመን ሐዲድ ለመቀየር ቢፈልግም፣ አበዳሪ ተቋማት እንደከለከሉት፣ በአንጻሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ከእነዚህ ተቋማት ምከር አፈንግጦ ለአገሩ የሚጠቅም ሰፊ የባቡር ሐዲድ መስመር መገንባት መጀመሩ ወኔያቸውን ቀስቅሶ ይበልጥ እንዳበረታታቸው ሲነገር መስማቴ፣ የኢትዮጵያ አቋም ለአፍሪካውያን ጥሩ ተምሳሌት መሆን እንደጀመረ መገንዘብ ይቻላል።

በኢትዮጵያ ፈጣኑን ዕድገት የሚደግፍ መሠረተ-ልማት ለማስፋፋት የተደረገው ሌላው ጥረት የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨትና ከማስተላለፍ ጋር የተያያዘ ነው። የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለልማት ቁልፍ ተፈላጊነት ያለው ሲሆን፣ መስኩ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ሰፊ ጥረት የተደረገበትና ትልቅ ውጤት የተገኘበት ጭምር ነበር። ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ ታዳሽ የኃይል ምንጮች ያሉዋት አገር ነች። ከታላቁ የአባይ ወንዝ ጀምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ መለስተኛና ከፍተኛ ወንዞች አሉዋት። ተራሮቿን አቆራርጠው የሚፈሱት ብዙዎቹ ወንዞች ለግድብ ሥራ የተመቹ ናቸው። በተጨማሪም ትንሽ የማይባል የጂኦተርማልና ሰፊ የፀሐይና የንፋስ የኃይል ምንጭ አላት። ይሁንና ከዚህ ሠፊ አቅም ውስጥ እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ የምታመነጨው ከ320 ሜጋ ዋት የማይበልጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ብቻ ነበር። በመሆኑም በመስኩ ያላት ድልብ አቅም ሁሉ መከኖ ቆይቷል። በተለይ ደግሞ ከውሃ ሀብቷ ያለብዙ ውስብስብ ቴክኖሎጂ ሊለማ የሚችለው የኤሌክትሪክ ኃይል ትርጉም ባለው ደረጃ አልተነካም ነበር።

ይህ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ጠንካራ ኢኮኖሚ ገንብቶ በራስ አቅም ግድቦችን ለመሥራት የሚችል ራዕይና ብቃት ያለው መንግሥት ስላልነበረ የተከሰተ ችግር ነው። በሌላ በኩልና በተወሰነ ደረጃ ደግሞ የግብጽ መሪዎች በተሳካ ዲፕሎማሲያዊ ሥራ አገሪቱ ከዓለም

አቀፍ ማኅበረሰብ ብድርና እርዳታ እንዳታገኝ በማደናቀፋቸው የተከሰተ ነበር። የግብጽ መሪዎች አገራቸው በአባይ ተፋሰስ ላይ የነበራትን ጥቅም በብቸኝነት ለማስቀጠል፣ በዓለም ዙሪያ ባሉ ውሃ ነክ ተቋማት ሁሉ የራሳቸውን ዜጎች አስርገው በማስገባት ኢትዮጵያ አንዳችም ብድርና እርዳታ እንዳታገኝ ሲያስከለክሉ ኖረዋል። የ1903፣ የ1929 እና የ1959 አ.ፍትሃዊ ስምምነቶችን ተገን አድርገው ግዙፍ አበዳሪ ተቋማት በአባይ ተፋሰስ ላይ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨትም ሆነ ለመስኖ ልማት እንዳያበድሩን ለማድረግ በሸረቡት ተንኮል እስካሁንም ድረስ አንድም የብድር መስኮት ትርጉም ባለው ደረጃ አልተከፈተላትም። በዚህ ምክንያት አገሪቱ ከምዕራቡ ዓለም አበዳሪ ተቋማት ለግድብ ሥራ አስፈላጊውን የገንዘብ ብድር ሳታገኝ ኖራለች።

አገራችን በአባይ ተፋሰስ ላይ ለሚሠራ ግድብ ለመጀመሪያ ጊዜ ብድር ያገኘችው በአማራ ክልል ከባሕር ዳር በስተደቡብ በሚገኘው የቆጋ ወንዝ ላይ ሰባት ሺህ ያህል ሔክታር የሚያለማውን ግድብ ለመሥራት ነው። ከዓለም ባንክ ያገኘችው ይህ የ600 ሚሊዮን ያህል ብር ብድር ወለዱና የመክፈያ ጊዜው ክሌሎች ብድሮች በተነጻጻሪ ከባድ ነበር። ነገር ግን መንግሥት ብድሩን መወሰድ በአበዳሪ ተቋማትና አገሮች ዘንድ ጸንቶ የቆየውን ያለማበደር ልማድ ለመስበርና ምናልባትም አዲስ ቅኝት ለማስጀመር ያስችል ይሆናል በሚል እሳቤ የተስማማበት ነበር። ይህም ሆኖ የግብጽ መሪዎች በተበተቡት ሠንሰለት የተዘጋው የእርዳታና የብድር ዕድል መንግሥት እንደገመተው ዛሬም ድረስ ብዙም አልተከፈተም።

በዚህ ምክንያት በአባይ ተፋሰስ ዙሪያ የሚካሔድ ልማት ከጅምሩ እስከታላቁ የህዳሴ ግድብ በራሳችን አቅም በመተማመን የሚገነባ ሆነ። በተወሰነ ደረጃ ከምሥራቁ ዓለም የሚገኝ ብድር ባይታጣም፣ ወሳኙ አቅም የራሳችን እንደሆነ በመገንዘብና በራስ በመተማመን ግንባታውን ማስቀጠል አማራጭ አልነበረውም። መለስ በታላቁ ህዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የማኖር ሥነ-ሥርዓት ላይ "መሐንዲሶቹም የፋይናንስ ምንጮቹም እኛው ነን" ብሎ በልበ ሙሉነት የተናገረው፣ ከሃያ ዓመታት ከባድ ጥረት በኋላ በአባይ ተፋሰስ ላይ ለሚካሔድ የኃይል ምንጭ ልማት ትርጉም ያለው የወጭ ብድርና እርዳታ እንደማይገኝ በማረጋገጡ ነው። በተጨማሪም ኢትዮጵያ የራሷን አገራዊ አቅም መገንባት እንደጀመረች በመተማመኑ ነው። የመለስ ሀሳብ መነሻና መድረሻ "እኛ ኢትዮጵያውያን የማንንም እርዳታና ምጽዋት ሳንጠብቅ፣ ወንዞቻችንን የማልማት ኃላፊነትን ትጥቃችንን ጠበቅ አድርገን በራሳችን በመተማመን ልንወጣው ይገባናል" የሚል ነበር።

በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ ከተደረገ በኋላ የመጀመሪያው የውሃ ኃይል ምንጭ ልማት የታቀደው አባይ ከጣና ሐይቅ ተለይቶ በሚወጣበትና ጫራ ጫራ ተብሎ በሚታወቀው ቦታ ላይ ነበር። የጫራ ጫራ ፕሮጀክት ወንዙ ከጣና ተለይቶ በሚወጣባት መነሻ ነጥብ

ላይ ትንሽ ግድብ በመሥራት የጣና ሐይቅ ከፍታን ለመጨመር የሚያስችል ነበር፡፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ባመነጨው ሀሳብ የተሠራው ይህ ግድብ አነሥተኛም ቢሆን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ነበሩት፡፡ አሥራ ሁለት ሜጋዋት ብቻ ስታመርት ከኖረችው የጭስ አባይ አንድ የኃይል ማመንጫ ጐን ለጐን ጭስ አባይ ሁለት በመባል የሚታወቅ ሌላ አዲስ የኃይል ማመንጫ ለመገንባትና ተጨማሪ ሰባ ሁለት ሜጋ ዋት ለማምረት የሚያስችል ነበር፡፡ በጣና ሐይቅ ምዕራባዊ አቅጣጫ በኩል አዲስ ቦይ ቆፍሮ ውሃውን ወደበለስ አቅጣጫ እንዲፈስ በማድረግም ሌላ 400 መቶ ሜጋ ዋት ያህል ኃይል ማመንጨትና እስከመቶ ሺህ ሔክታር መሬት በመስኖ ለማልማት የሚያስችል ሌላም ጠቀሜታ ነበረው፡፡

የጫራ ጫራ ግድብ ግንባታ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ማብቂያ ላይ በሁለት ኢትዮጵያውያን መሐንዲሶች ተቋቁሞ በጣም ተስፋ ያለው ሥራ ማከናወን ጀምሮ በነበረው "በርታ ኩባንያ" እንዲፈጸም ተደረገ፡፡ በርታ ኮንስትራክሽን በብዙ የአገራችን ታሪካዊ ቦታዎች ዘመናዊና ታሪካዊ ሆቴሎችንና አገር አቋራጭ መንገዶችን መሥራት ጀምሮ የነበረ ተስፋ ያለው አንጋፋ ኩባንያ የነበረ ቢሆንም፣ በደርግ መንግሥት ከተወረሰ በኋላ ግን ተዳክሞ ነበር፡፡ ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ የበርታ ኮንስትራክሽን ድርጅትን ወደቀድሞ ባለቤቶቹ በመመለስ የግድብ ሥራውን እንዲያከናውን አደረገ፡፡ መንግሥት ገና ከጥዋቱ አገር በቀል የኮንስትራክሽን አቅምን ለመገንባት ይቻል ዘንድ፣ በወሰደው በዚህ እርምጃ በመታገዝ የበርታ ኮንስትራክሽን ኩባንያ የጫራ ጫራ ግድብን በጥራት ሠርቶ በማስረከቡ እነሆ ዛሬ ግድቡ የጣና በለስን የመስኖና የኤሌክትሪክ ኃይል ትሩፋትና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ሊያስገኝ ችሏል፡፡

የጫራ ጫራ ግድብ መገንባት ከእነዚህ ኃይል የማመንጨትና የመስኖ ጥቅሞች ባሻገር፣ ግብፆችን ጨምሮ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ፣ ኢትዮጵያ አቅም እስካላት ድረስ በአባይ ወንዝ ላይ ፍትሃዊ ተጠቃሚነቷን የሚያረጋግጥ ግንባታ ለማካሔድ ማንም ከልካይ ሊኖርባት እንደማይችልና ማንንም ማስፈቀድ እንደሌለባት ያመላከተ ነበር፡፡ በግብፁ የቀድሞ ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳት ዘመን፣ "ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ አንዳችም ዓይነት ፕሮጀክት ብታስብ ግብጽ ወረራ ትሰነዝራለች" እየተባለ ይነገር የነበረውንና በተወሰነ ደረጃ እንደቋሚ መመሪያ ያገለግል የነበረውን ማስጠንቀቂያ ለመስበርም አስችሏል፡፡ በአባይ ወንዝ ላይ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንጂ፣ ግብጽን ጨምሮ የማንም ብቸኛ ተጠቃሚነት የሚባል መርህ ኢትዮጵያን እንደማይገዛት አረጋግጧል፡፡

በጫራ ጫራና በቆጋ ግድቦች ግንባታ አጋጣሚ በአመራሩ ዘንድ ይካሔድ በነበረው ውይይት በኢትዮጵያ የትልልቅ ወንዞች ልማት፣ በተለይ ደግሞ በአባይ ወንዝና በገባሮቹ ላይ የሚካሔደው ልማት አቅጣጫ ጥርት ብሎ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ ያላትን የክርሰ ምድርና የገፀ-ምድር ውሃ በቀጣይነት በማልማት የኤሌክትሪክ ኃይል

ከማመንጨት ባሻገር ለመስኖ፣ ለኢንዱስትሪና ለንፁህ መጠጥ የውሃ አቅርቦት ማሟላት እንደሚገባት ተሰምሮበታል፡፡ "የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው" በሚል ስላቅ መልክ የሚገለጸው የውሃ ረሐብተኛነት ቆሞ፣ አገሪቱ በውሃ ሐብቷ ያሻትን ልማት ማከናወን እንዳለባትና እንደምትችልም ተወስኗል፡፡ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀማችን በዓለም አቀፍ ሕግና የወንዞች አስተዳደር መርሆ በመመራት፣ በታችኛው ተፋሰስ አገሮችና ህዝቦች ላይ ጉልህ ጉዳት በማያስከትልና የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያጐለብት ቅኝት የሚፈጸም መሆን እንዳለበትም ተመላክቷል። ይህ የታላላቅ ግድቦች ግንባታ ከአጭር ጊዜ አኳያ ኃይል ለማመንጨት ቅድሚያ በመስጠት፣ በሂደት ከመካከለኛና ረዥም ጊዜ አኳያ ደግሞ መስኖና ሌሎች ጥቅሞችን ለማስፋፋት እንዲቻል፣ ግድቦቹ የሚገነቡበት ቦታ ሁሉ የመስኖ ልማትን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ መመረጥ እንዳለበትም መግባባት ተደርሶበታል፡፡

ሁሉም ግድቦች በዚህ ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲገነቡ በተደረገበት በዚህ ሂደት ከግልገል ጊቤ ሁለት ጋር የተያያዘ አንድ ገጠመኝ ማውሳት በወቅቱ ስለነበረው አፈጻጸም የተሻለ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የግልገል ጊቤ አንድ የኃይል ማመንጫ በወንዙ አናት አካባቢ አንድ መለስተኛ ግድብ በመሥራትና ውሃውን በተራራ ውስጥ በተሠራ ትልቅ ዋሻ መሰል ቦይ አማካይነት በማስተላለፍ 184 ሜጋ ዋት የተመረተበት ነበር፡፡ ውሃው በዚህ አኳኋን ኤሌክትሪክ ካመነጨ በኋላ ተመልሶ ወደመደበኛ መፋሰሻው ወንዝ ይገባል፡፡ ከዚያ በኋላ ሌላ ግድብ የሚሠራበት ቦታ በቅርብ እንደነበረ ባለመታወቁ መንግሥት በዚሁ ውሃ ሌላ ኃይል የማመንጨት ሀሳብ ሳይኖረው ፕሮጀክቱ ወደመቋጨት ያመራል፡፡

በመካከሉ የሳሊኒ ኮንስትራክሽን ኃላፊዎች፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስን አግኝተው ያለ ብዙ ወጪ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የሚያስችል አንድ አዲስ ሀሳብ እንዳላቸውና ይህንንም በፕሮጀክት መልክ ቀርጸው ጥናት እንዳደረጉበት ይገልፁለታል፡፡ መንግሥት ይህን ሀሳብ ከተቀበላቸውና ፋይናንስ የሚያደርገው ከሆነም ኢትዮጵያ ሌላ ግድብ መሥራት ሳያስፈልጋት ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እንደምትችል አረጋገጡለት። በሳሊኒዎች የቀረበው ይህ ፕሮጀክት ከመጀመሪያው ኃይል ማመንጫ ጫፍ አንድ ኪሎ ሜትር ዝቅ ብሎ በተራራው ውስጥ 26 ኪሎ ሜትር ቦይ ሠርቶ ውሃውን በማጓጓዝ በነባሩ ግድብ በተጠራቀመው ውሃ ብቻ ተጨማሪ 320 ሜጋ ዋት ኃይል ሊገኝ እንደሚችል የሚያሳይ ነበር። የሳሊኒ መሪዎች ኩባንያው መሣሪያውን ነቃቅሎ ከወሰደ በኋላ ግንባታውን ለመጀመር ቢፈለግ፣ ሌላ ተጨማሪ የሎጀስቲክስ ሥራና ወጭ እንደሚጠይቅና ይህም ለአገሪቱ ኪሳራ እንደሚሆን በመግለጽ ያቀረቡት የፕሮጀክት ሀሳብ አሳማኝና ለአገሪቱም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነበር፡፡

ይህ በጥናት የተደገፈ ተጨማሪ ኃይል የማምረት ሀሳብ የቀረበለት መለስ፣ መንግሥት ለዚህ ፕሮጀክት የመደበው አምስት ሳንቲም ያልነበረ ቢሆንም፣ ግንባታውን ለማስፈጸም ግን

ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደረሰ፡፡ "የአገሩን ሠርዶ በአገሩ በሬ" እንዲሉ፣ ለሳሊኒ ኃላፊዎት ከአውሮፖ እርዳታ አፈላልገው ካመጡ ፕሮጀክቱን እነርሱ እንዲፈጽሙት ዕድል እንደሚሰጣቸው ገለጸላቸው፡፡ ሳሊኒዎች የአውሮፓን ገንዘብ ፈልገው ማምጣት የማይሳናቸው፣ ለዚያውም ስመ-ጥር አውሮፖዊ ኩባንያዎች መሆናቸው ብቻ ለመለስ በቂ ነበር፡፡ ሳሊኒዎች አይናቸውን ሳያሹ፣ ጊዜያቸውን ሳያባክኑ የአውሮፖን የሥልጣን ኮሪደሮች አስከፍተው ለግልገል ጊቤ ሁለት ፋይናንሱን አቀረቡ፡፡ እነርሱ ባመጡት ገንዘብ ግድቡን እንዲሠሩ ተደረገ፡፡ ኢትዮጵያም የግድቡ ባለቤት ሆነች፡፡ በጫራ ጫራ ግድብ የጀመረው የመለስ የብርሃን ዘመን በግልገል ጊቤ ሁለት ተጠናከረ፡፡

ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ወንዞችን በመገደብ ኃይል ለማመንጨትና መስኖ ለማስፋፋት ከግልገል ጊቤ አንድ እስከ ሦስት፣ በተከዜ፣ በጣና-በለስ፣ በፊንጫ-ውሃ፣ የተሠሩት ግድቦችና አሁን ደግሞ በታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ አገሪቱ የተከተለችው አቅጣጫ በዚህ ቅኝት የተከናወኑ ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ደግሞ በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች ከነፋስ ኃይል የማመንጨት ፕሮጀክቶች በሥራ ላይ ውለዋል፡፡ በእነዚህ ፕሮጀክቶች አማካይነት አገሪቱ ያላት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት ችሎታ በቅርቡ ከ4,000 ሜጋ ዋት ያለፈ ሲሆን፣ 6,420 ሜጋዋት የሚያመነጨው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በጥቂት ዓመታት ሲጠናቀቅ ደግሞ ከ10,400 ሜጋ ዋት በላይ እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡

በኢትዮጵያ ከታዳሽ ምንጮች ሰፊ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማምረት ከሚደረገው ጥረት በተጨማሪ፣ የመነጨውን ኃይል ወደተጠቃሚው ሕብረተሰብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ መጠነ-ሰፊ የማስተላለፊያና የማከፋፈያ መስመር በመዘርጋት ላይ ነው፡፡ ይህ የማስፋፊያና የማሻሻያ ሥራ ደረጃ በደረጃ እስኪጠናቀቅ ድረስ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ችግር ያልተለየንና የማይለየን ቢሆንም የማስተላለፊያ መስመር ዝርጋታው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአራት መቶና አምስት መቶ ኪሎ ቮልት ኃይል ተሸካሚ መስመሮችን በማስፋፋት ጭምር እየተከናወነ ነው። በዚህም ከ5,500 የማያንሱ የገጠር ቀበሌዎችና ከተሞች ከብሔራዊ መስመሩ (National Grid) ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርጓል፡፡ የገጠሩን ሕብረተሰብ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ማድረግ እጅግ በጣም ብዙ ጥቅሞች እንዳለው በመገንዘብ በመለስ መሐንዲስነት የገጠር "ኤሌክትሪፊኬሽን" ፕሮግራም ተቀርፆ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል ለገጠር ሕብረተሰብ በቀረበ ቁጥር የተፈጥሮ ሀብት ውድመት ይወገዳል፡፡ ሴቶች ጊዜያቸውን እንጨት በመስበርና ኩበት በመልቀም ማሳለፋቸው ቀርቶ፣ በሌላ የሀብት ፈጠራ ተግባር ላይ እንዲያውሉት ዕድል ያገኛሉ፡፡ የገጠር ተማሪዎች ከከተማ ተማሪዎች የማይተናነስ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ተጠቃሚዎች ይሆናሉ። የገጠር ኢንዱስትሪ ልማትና ከተሜነት በተመጋጋቢነት ይስፋፋሉ፡፡ ከዚህም አልፎ በኢትዮጵያ ለኑሮና ለሥራ የተመቹ የተመጣጠኑ ዕድገት ያላቸው ከተሞች

ባልተማከለ አኳኋን ይበራከታሉ።

መንግሥት የኢነርጂ ልማት በአጠቃላይ ለፈጣን ዕድገት፣ በተለይ ደግሞ ለተሟላ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ መሠረተ-ልማቱን በገጠርም ጭምር በልዩ ትኩረት ሲያስፋፋ ቆይቷል። ይህም ሆኖ በመስኩ የተደረገው ጥረት ያላንዳች እንቅፋት የተከናወነ አልነበረም። የኤሌክትሪክ መስመሮችን ሲቆርጡ ከሚያድሩ የውስጥ እንቅፋቶች ጀምሮ እስከ ዓለም አቀፍ ኒዮ-ሊበራል ኃይሉና በአባይ ወንዝ ላይ ብቸኛ ተጠቃሚነት አዳብረው እስከቆዩት አገሮች ድረስ የደቀኑዋቸው ብዙ እንቅፋቶች ገጥመውታል። "ግዙፍ የኃይል ምንጭ ልማት ፕሮጀክቶች አያስፈልጓችሁም" ከሚለው ምክርና ተግሳጽ ጀምሮ፣ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ተራ የፖለቲካ ድጋፍ ማሰባሰቢያ አስመስሎ እስከማቅረብ ድረስ ያልተካሔደ ዘመቻ አልነበረም። በግብጽ "የሙስሊም ወንድማማቾች" ፓርቲን በመወከል በ2012 ሥልጣን ይዘው የነበሩት ሞሐመድ ሞርሲ፣ "በኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች እየታገዙ የኢትዮጵያን ልማት ከማደናቀፍ ጀምሮ፣ እንደኤርትራ መንግሥት በመሳሰሉ ተላላኪዎች አማካይነት ጦርነት ለመለኮስ" የነበራቸውን ውጥን በይፋ ገልጸው ነበር። በኢትዮጵያ የኃይል ምንጭ ልማት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የተደረገው እነዘህና እነዚህን የመሳሰሉ እንቅፋቶችን ሁሉ በማለፍ ነው።

በኢትዮጵያ ልማትን ለማፋጠንና የህዝብ ተጠቃሚነትን እውን ለማድረግ በልዩ ትኩረት ሊለሙ ከሚገባቸው መሠረተ-ልማቶች ሌላው የቴሌኮም አገልግሎት ነው። ቴሌኮም ወደአገሪቱ የገባው ከሞላ ጎደል ከበለጸገው ዓለም ጥቂት ዓመታት ብቻ ዘግይቶ ነው። በአውሮፓ የመጀመሪያው የኤሌክትሪክ ቴሌፎን የተፈለሰፈው በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በተለይ ከ1870ዎቹ ጀምሮ ሲሆን ወደኢትዮጵያ የገባው ደግሞ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነበር። በመሆኑም ከአውሮፓ ብዙም ሳይዘገይ የጀመረ እድሜ-ጠገብ አገልግሎት ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያ ከአናሎግ የቴሌኮም አገልግሎት ውጭ ሌላ ብቃት አልነበራትም። በአገሪቱ አንዳንድ ቦታዎች የተወሰኑ የሚይክሮዌቭ ማማዎችን በየቦታው በማቆም ለስልክና የቴሌቪዥን ሥርጭት ማስተላለፊያ እንዲሆኑ ተደርጐ የነበረ ቢሆንም፣ ጥቅም ላይ የዋለው በድምሩ ከ150 ሺህ የማይበልጥ የሽቦ ስልክና ባለአንድ መስመር የቴሌቪዥን እንዲሁም ከሦስት የማይበልጡ የሬዲዮ ሚጋ ኸርዞች ብቻ ነበር። ይህም በመሆኑ እስከ1983ዓ.ም. ድረስ በነበረው ጊዜ የቴሌኮም አገልግሎት በቅጡ የተስፋፋ አልነበረም። ቴሌኮም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት አገልግሎት ሊታሰብ ቀርቶ ድምጽ ብቻ ለማስተላለፍ የነበረው ውሱንነት ከፍተኛ ነበር። አንድ የቴሌቪዥን ጣቢያ መስመር ለመጨመር ቢታሰብ ያሉትን የስልክ መስመሮች ሁሉ መዝጋት የግድ የሚልበት ወቅት ነበር። በመሆኑም እድሜ-ጠገብ የሆነው የኢትዮጵያ የቴሌኮም አገልግሎት ምንም እንኳ በዘመነ-ግሎባላይዜሽን ላይ የሚገኝ መሆኑ ባይቀርም፣ ሊላው ቀርቶ ከብዙ ያልበለጸጉ አገሮች ጋር እንኳ ተወዳዳሪ ለመሆን

የማያስችል አገልግሎት ነበር፡፡

ከ1983ዓ.ም. በኋላ የተመሠረተው አዲስ መንግሥት የቴሌኮምን መሠረታዊ ፋይዳ በመገንዘብ በመስኩ ሰፊ ኢንቨስትመንት አካሂዷል፡፡ የአገሪቱ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ደረጃ እንዲሻሻልና ቴሌኮም ለቴክኖሎጂ መስፋፋትና አቅም ግንባታ እንዲውል ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ እንቅስቃሴው መለስ "ዘግይተው የሚለሙ አገሮች አላቸው የሚባለውን ብልጫ ወይም መልካም ዕድል (Late Comers Advantage) በብስለት በመጠቀም፣ በእነርሱና በበለጸገው ዓለም መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ ይችላሉ" የሚለውን ሀሳብ ካስተዋወቀ በኋላ የተጀመረ ነበር፡፡ ከዚህም በመነሳት የኢትዮጵያ ቴሌኮም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በብዙ የዓለማችን ከፍሎች ያልተሞከረ የለውጥ መሣሪያ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህን በኢትዮጵያ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን የቪ-ሳት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ከተወሰደው እርምጃ በመነሳት መመልከት ይቻላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ ወጣቶች፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድም ወደከፍተኛ ትምሕርት፣ አለያም ወደቴክኒከና ሙያ ሥልጠና እንደሚገቡ በመገንዘብ ጥራት ያለው ትምሕርት እንዲጐናጸፉ ማድረግ ከፍተኛ ተፈላጊነት አለው፡፡ በተጨማሪም ጥራት ያለው ትምሕርት የማቅረቡ ጉዳይ በፍትሃዊነት መርሕ የሚመራ እንዲሆን መደረግ ነበረበት፡፡ አዲስ አበባ ላይ ለዚያውም በጥቂት የልሂቃን ማፍሪያ ትምሕርት ቤቶች ብቻ የማይታጠር፣ ጥራት ያለው ትምሕርት ለሁሉም እንዲዳረስ ማድረግ ይገባ ነበር፡፡ የአርሶ አደር ልጆች በሚማሩባቸው ገጠሮችም ጭምር ትምሕርት በተመሳሳይ ጥራት መሰጠቱን ማረጋገጥም አማራጭ አልነበረውም፡፡ ከዚህ አኳቤ በመነሳት መንግሥት በሁሉም የአገሪቱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሳተላይት ግንኙነት የሚታገዝ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር አድርጓል፡፡ በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ትምሕርት በሳተላይት ሥርጭት ታግዞ እንዲሰጥ አድርጓል፡፡

በዚህ መሠረት ሥርዓተ-ትምሕርቱ በጥራት ከተቀረጸ በኋላ፣ ገለጻው ብቃት ባላቸውና ከውጭ በተመለመሉ መምህራን አማካይነት ከአንድ ማዕከል ለሁሉም እንዲተላለፍ ተደረገ፡፡ በየከፍሉ የሚመደቡት መምህራን ገለጻውን የሚደግፉ ማብራሪያዎችና የማስተማር ድጋፍ አገልግሎት /Tutorial/ በመስጠት እንዲያግዙ፣ በተጨማሪም ት/ቤቶች በዚሁ የቪ-ሳትና የቴሌኮም አገልግሎት በመታገዝ ለተማሪዎች ነጻ የኢንተርኔት አገልግሎት ማቅረብ ጀመሩ፡፡ ኢትዮጵያ ከበለጸገው ዓለም ቴክኖሎጂ በመዋስ ዲጂታል ልዩነትን ለማጥበብ የሚቻል እንደሆነ የሚያረጋግጠውን ይህን የመሰለ ተነሳሽነት መውሰዷ በእርግጥም አገሪቱን ቀዳሚ የሚያደርጋት ነበር፡፡ በዓለማችን የቪዲዮ ኮንፈረንስና ቴሌኮምን ለከፍተኛ ትምሕርትና ለርቀት ህክምና ያዋሉ ብዙ አገሮች ያሉ ቢሆንም፣ የርቀት ትምሕርትን በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመጠቀም ደረጃ ኢትዮጵያ በእርግጥም ጀማሪ አገር ነበረች፡፡

ቴሌኮምን ለሰብአዊ ኃይል ልማት ለማዋል ከተደረገው እንቅስቃሴ ልምድ በመማር በኢትዮጵያ የብሮድባንድ የፋይበር ኦፕቲክስ መስመሮችን ማስፋፋት የተጀመረው ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ነበር፡፡ ቴሌኮምን ከቀጭኗ የስልክ ሽቦና አናሎግ የአገልግሎት ደረጃ በማላቀቅ ወደሰፊው አውራ ጐዳና ማስገባት የሚቻለው በፋይበር ኦፕቲክስ መሥመሮች አማካይነት ነው፡፡ በመሆኑም በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ16,000 ኪሎ ሜትር በላይ የፋይበር ኦፕቲክስ መስመር በሁሉም አቅጣጫዎች ተዘርግቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ከደቡብ አፍሪካና ናይጄሪያ በስተቀር በሳብ-ሰሐራ አፍሪካ ይህን ያህል የፋይበር ኦፕቲክስ መስመር የዘረጉ ብዙ አገሮች አልነበሩም፡፡ ኢትዮጵያ በእርግጥም ዲጂታል ልዩነትን ከማጥበብ አኳያ ብዙ እንደሠራች ከዚህ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ለብዙ ደህና ኋላቀር አገሮች በጣም ቀላል ሆኖ የሚገኘውን የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎት በማስፋፋት ረገድም ኢትዮጵያ ረጅም ርቀት ተጉዛለች፡፡ ከአምሳ ሚሊዮን በላይ ተገልጋዮች የማስተናገድ አቅም ገንብታለች፡፡ የሞባይልም ሆነ የባለገመድ ስልክና ኢንተርኔት የ4G አገልግሎትን የሚያካትት ሆኖ በፍጥነት እንዲስፋፋ በመደረግ ላይ ነው፡፡

ቴሌኮም ገና በዓለማችን መስፋፋት ሲጀምር ዋነኛ አገልግሎቱ በስልክ ሽቦዎች አማካይነት ድምጽን ማስተላለፍ ብቻ ነበር፡፡ ከቴሌቪዥን መጀመር በኋላ ደግሞ በሂደት ምስልን ጨምሮ መልዕክቶችን የማድረሻ መሣሪያ ወደመሆን ተሸጋገረ፡፡ በሃያኛው ከፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ላይ በአውሮፓና በአሜሪካ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች እየተነቀሉ ርካሽ ጉልበት በብዛት ወደሚገኝበት ምሥራቅ እስያ መሸጋገራቸውን ተከትሎ፣ በተለይ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ደግሞ የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎትና የዚህ አንድ ወሳኝ አካል የሆነው ኢንተርኔት ተስፋፋ፡፡ ከቴሌኮም አውራ ጐዳና መስፋፋት ጋር ተያይዞ መጠነ ሰፊ መረጃዎችን በድምጽ፣ በምስልና በጽሁፍ ቅጽበታዊ በሚባል ደረጃ ማስተላለፊያ ወደመሆንም አደገ፡፡

የኤሌክትሮኒፊኬሽን መስፋፋት፣ በተለይ ደግሞ ኢንተርኔት ወይም ዓለም አቀፍ ድረ-ገጽ በመባል የሚታወቀው የፈጣን ግንኙነት መረብ መጀመር መጀመሪያ ላይ በዋነኛነት ይፈለግ የነበረው ትእዛዝና መረጃን ለማለዋወጥ ነበር፡፡ ከአምራችነት እየወጣ ወደሸማችነት ከተሸጋገረው የምዕራቡ ዓለም ትዕዛዝ፣ አምራች ከሆነው የምሥራቁ ዓለም ደግሞ የምርት መረጃ በጣም በፍጥነት የማለዋወጥ ፍላጐት የዚህን ሥልጣኔ መወለድ አስከተለ፡፡ በዚህ የተነሳ ኤሌክትሮኒፊኬሽን የወቅቱን ኢኮኖሚያዊ ፍላጐት ተከትሎ በዓለማችን ቅጽበታዊ በሚባል ደረጃ ተስፋፍቶ ምርቶችን በኮንቴይነር ከማጓጓዝ በተጨማሪ አንድ የዘመነ-ግሎባላይዜሽን መለያ እስከመሆን ደረሰ፡፡ በአገሮች ውስጥና መካከል ፈጣን የመረጃ ልውውጥ የሚካሔድባቸው የባሕር ውስጥና የመሬት ለመሬት ኬብሎች በሰፊው ተዘረጉ፡፡ እነዚህ በተለይ ከግሎባላይዜሽን መጠናከር ጋር ተያይዞ ዓለም አቀፋዊው የኢኮኖሚ ዕድገት ያመጣቸውን

ለውጦች በአግባቡ ለማስተናገድና ለካፒታል መስፋፋት ሲባል ቁልፍ ተፈላጊነት ነበራቸው::

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓለም አቀፍ ድረ-ገጽ ወይም ኢንተርኔት በጣም ያልተገመተና አብዮታዊ የሚባል ተፅዕኖ የሚያሳርፍ መሠረተ-ልማት ወደመሆን ሲሸጋገር ጊዜ አልወሰደበትም:: የመረጃ ተደራሽነትና ዝውውር እጅግ ለግምት በሚያስቸግር ፍጥነትና ደረጃ ተስፋፋ:: ይህም በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በአንዴ ቀላልና ውስብስብ አደረገው:: በአምራቾችና በሸማቾች፣ በመንግሥትና በህዝብ፣ በመሪዎችና በተመሪዎች፣ እንዲሁም በአገሮች በተለይ በበለጸገው ዓለምና ባልበለጸጉ አገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት አዲስ መልከና ባሕርይ አላበሰው:: የሰው ልጆች ጊዜና ርቀት ሳይገድባቸው እርስ በእርሳቸው በሰፊው መገናኘት ጀመሩ:: አገሮችና ሉዓላዊ መንግሥታት በቀላሉ ለውጭ ከባድ ተፅዕኖ መጋለጥ ጀመሩ:: የውጭ ኃይሎች በተለይ ደግሞ ዓለም አቀፍ የገበያ አከራሪነት ኃይሎች የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት መስፋፋትን በቁልፍ መሣሪያነት በመጠቀም መንግሥታትን በተፅዕኖዋቸው ሥር ለማስገባት ከባድ እንቅስቃሴ ማካሔድ ጀመሩ::

የኢንተርኔት አገልግሎት በሳተላይትም ይሁን በመሬትና በባሕር ላይ በሚዘረጉ ኬብሎች አማካይነት ተስፋፍቶ ድምጽ፣ ምስልና መጠነ-ሰፊ ዳታ በአንዴ የሚገፍበት አውራ ጐዳና መሆኑ ሌላም አብዮታዊ ውጤት ነበረው:: ይህም ጦርነትን በተለምዶ ከሚታወቅበት ባህርይው በማላቀቅ በዋነኛነት ከኢንፎርሜሽን ፍሰት ጋር የተያያዘና የቴሌኮም አውታርን ደህንነት ከማስጠበቅ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንዲሆን ማድረጉ ነበር:: በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የአየር ሞገዱን ከማንኛውም እንቅፋት ጠብቆ፣ ትዕዛዝና መረጃ ባልተቆራረጠ አኳኋን የሚያስተላልፍ አገር አሸናፊ የሚሆንበት፣ የአየር ሞገዱን ለጥቃት ያጋለጠው ተፋላሚ ደግሞ ምንም ያህል ቢታጠቅ ተሸናፊ መሆኑ አይቀሬ ሆነ:: ከዚህም አልፎ መደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፣ የባንኮችና የፋይናንስ ሥራዎች፣ የትምሕርትና ጤና አገልግሎቶች አሁን አሁን ደግሞ መልካም አስተዳደር የማስፈን ወይም ያለማስፈን ችሎታ በዚሁ መሠረተ-ልማት ከባድ ተፅዕኖ ያርፍባቸው ጀመር:: በአጭሩ ዘመናዊና ደኅንነቱ የተጠበቀ የቴሌኮም መሠረተ-ልማት ከብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሆነ:: ቴሌኮምን ለሌላ አገርና ከባንያዎች አሳልፎ የሰጠ ብሔራዊ ደኅንነቱንም አብሮ አሳልፎ የሚሰጥበት ሁኔታ ተፈጠረ:: በዚህ የተነሳ ዋናው የቴሌኮም አውታር ለብሔራዊ ደኅንነትና ለአገር ሉዓላዊነት፣ ለተፋጠነ የቴክኖሎጅ ሽግግርና ብሔራዊ ሀብት ፈጠራ ሲባል በመንግሥት እጅ እንደተያዘ መቀጠል ያለበት መሠረተ-ልማት ሆነ::

ይህ ግንዛቤ በኢትዮጵያ መንግሥት በጥብቅ የሚታመንበት ብቻ ሳይሆን ባለፈው ሩብ ምዕተ ዓመት በጥብቅ ተግባራዊ የተደረገ ነበር:: በዚህ የተነሳ ዘርፉን የማስፋፋት ጉዳይ ከዚህ መሠረታዊ አቅጣጫ በመነሳት ብቻ እንዲፈጸም ተደርጓል:: ነገር ግን የቴሌኮም መሠረተ-

ልማትን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ በውል የሚያውቁት የበለጸገው ዓለም አገሮችና ተቋሞቻቸው ኢትዮጵያ የያዘችውን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስቀየር ከፍተኛ ጫና አድርገዋል፡፡ ብዙዎቹ "ኢትዮጵያ ቴሌኮምን ወደግል ባለሀብቱ እጅ ማዛወር አለባት" የሚል ምክርና አልፎ አልፎ ደግሞ መመሪያ ቢጤ መስጠታቸው የተለመደ ነበር፡፡ ይህም ሆኖ የዚህ ዓይነቱን ምክርና መመሪያ ለመንግሥት የሚያቀርቡት ዓለም አቀፍ ተቋማት አንድም ጊዜ ቴሌኮም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ደህንነት ለአደጋ ሊያጋልጥ ስለመቻሉ ወይም ስላለመቻሉ በጨረፍታም ቢሆን አንስተው አያውቁም፡፡ መነሻና መድረሻቸው የአገልግሎት ጥራትን ማረጋገጥ፣ ትርፍ ማግኘትና የግል ሴክተርን አቅም መገንባት እንዲሁም ተፎካካሪነትን ማረጋገጥ የሚሉ ነበሩ፡፡

የአገልግሎት ጥራት በመንግሥትም ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ቴሌኮም አትራፊ መሆኑ ባያከራክርም ትርፉ ወደውጭ ከሚጐርፍ እዚሁ በአገር ውስጥ ቀርቶ ለሌሎች ልማቶች እንዲውል ሊደረግ ይችላል፡፡ ለምሣሌ በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮ-ቴሌኮም ከሚገኘው ትርፍ ከፊሉ በኢትዮጵያ የባቡር መሠረተ-ልማትን ፋይናንስ ለማድረግ እንዲውል እየተደረገ ይገኛል፡፡ የፉክክር አስፈላጊነት ብዙም የሚያከራክር አይደለም። በምርትና አገልግሎት አቅራቢ ባለሀብቶች መካከል የሚካሔድ ፉክክር ሸማቾችን ይጠቅማል። ፉክክርን ማበረታታት ለጥራት መሻሻልና የዋጋ ቅነሳ ቁልፍ ተፈላጊነት አለው፡፡ ስለዚህም በቴሌኮም አገልግሎት ረገድ ፉክክር እንዲጠናከር ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ከቴሌኮም አገልግሎት አኳያ በዓለማችን በተጨባጭ የሚታየው ተግባርና አዝማሚያ ሞኖፖሊ እንጅ ፉክክር አይደለም፡፡ በዓለማችን እጅግ ከፍተኛ የሞኖፖሊ ይዞታ ካለባቸው መሠረተ-ልማቶች መካከል ዋናው የቴሌኮም አገልግሎት ነው፡፡ ቴሌኮም ከፍተኛ የትርፍ ምንጭ በመሆኑ መስኩን የተቆጣጠሩት ግዙፍ ኩባንያዎች ይዞታቸውን ለፉክክር በማጋለጥ ትርፋቸውን ለአደጋ አያጋልጡም፡፡ አሜሪካኖች ሁዋዌ የተባለው የቻይና የቴሌኮም ተቋም በጨረታ ያሸነፈባቸውን ውድድሮች "የብሔራዊ ደህንነት" ምክንያት እያቀረቡ የሠረዙት ከብሔራዊ ደኅንነት በተጨማሪ ከዘርፉ ሞኖፖሊያዊ ባሕርይ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ይህም የቴሌኮም መሠረተ-ልማትን በአንድ በኩል ከብሔራዊ ደኅንነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሞኖፖሊያዊ ትርፍ በመነሳት ብቻ እንደሚመለከቱት ያሳያል፡፡ ስለዚህም አገልግሎቱ ፉክክርን የሚፈቅድ እንዲሆን ለማድረግ የሚባለው ከንድፈ-ሀሳባዊ ቃልኪዳንነት የማይዘልና ተጨባጭ መሠረት የሌለው ነው፡፡

ኢትዮጵያ በሌሎች መስኮች እንዳጋጠማት ሁሉ በቴሌኮም አገልግሎት ዘርፍም የማያቋርጥ የፖለቲካ ዘመቻና ግፊት አልተለያትም፡፡ ዘርፉ በኢትዮጵያ እየለማ ያለው ብዙ እንቅፋቶችን በማለፍና በመቋቋም ብቻ ነው፡፡ ከቴሌኮሙኒኬሽን ሊበራላይዜሽንና ፕራይቬታይዜሽን አቋም በመነሳት "በኢትዮጵያ ለግል ሴክተር ልማት የሚበጅ ምሕዳር የለም" ያልተባለበት ጊዜ አልነበረም፡፡ አገልግሎቱ ከተወሰነ የጥራት ችግር ጋር እየተስፋፋ ባለበትም

ሆነ፣ የአገልግሎቱ ጥራት በሚሻሻልበት ጊዜ ሁሉ ዘርፉ ወደግሉ ባለሀብት ቢሸጋገር ኖሮ ችግሩ ሁሉ በአንዴ ይወገድ ነበር ተብሏል። የአሜሪካ ሰብአዊ መብት ቢሮ እ.ኤ.አ. በ2011 ባወጣው ሪፖርት አገሪቱ ቴሌኮምን ለሽያጭ ባለማቅረቧ "ሰብአዊ መብትን እየተጋፋች ነው" እስከማለት ደርሶ ነበር። በዚህ ዘመቻ ከቴሌኮም ፕራይቬታዜሽን ዋነኞቹ ተጠቃሚዎች የሆኑት የምዕራብ አገሮችና ኩባንያዎቻቸው ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ ኢትዮጵያውያንና አፍሪካውያንም ጭምር ተሳታፊዎች ናቸው።

በቴሌኮም ጉዳይ ላይ በ1997 ዓ.ም. አካባቢ ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት የዩጋንዳ አምባሳደር ጋር ያደረገኩት ውይይት አንድ ለየት ያለ ገጠመኝ ነበር። አምባሰደሩ "ለጥብቅ ጉዳይ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ" በማለት ወደቢሮዬ መጥተው ነበር። ከጥቂት የሰላምታ ልውውጥ በኋላ "የኢትዮጵያ መንግሥት ቴሌኮምን ወደግል ይዞታ የሚያዛውረው መቼ ነው?" የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝ። ኒዮ-ሊበራሎቹ ይህን ጥያቄ ደጋግመው እያነሡ የሚነተርኩን አልበቃ ብሎ፣ የዩጋንዳው አምባሳደር በዚህ ላይ መጨመራቸው የሚያስገርምም ግራ የሚያጋባም ነበር።

የመጡበትን መነሻ ሀሳብ እንዳጠቃለሉ፣ "ኢትዮጵያ የቴሌኮም አገልግሎቷን ለሽያጭ እንድታቀርብ ለምን እንደፈለጉ" ጠየቅኳቸው። እሳቸውም የመግዛት ፍላጐት እንዳላቸው በመግለጽ ጀምረው፣ "በዩጋንዳ እርሳቸውም ድርሻ ባላቸው የግል የቴሌኮም ኩባንያዎች አማካይነት ሊስትሮዎች ሁሉ የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች እንደሆኑና ለመግዛት ዕድል ቢያገኙ ሞባይል ስልክ በአጭር ጊዜ ወደገጠርም ጭምር እንደሚስፋፋ" ገለፁልኝ። በውይይታችን ሂደት ቴሌኮምን ወደግል ለማዛወር የማይሞክሩ መንግሥታት "ጅሎች" ናቸው እስከማለትም ደረሱ። በመጨረሻ የኢትዮጵያ ቴሌኮምን ቢገዙት "በጥቂት ዓመታት ውስጥ አሥር ሺ ኪሎሜትር የፋይበር ኦፕቲክስ መሥመር ይዘረጉ?"፣ ወይም "ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶችን በነጻ የቪ-ሳት ተጠቃሚ በማድረግ አገልግሎቱን አገራዊ የቴክኖሎጅ ሽግግር መሣሪያ ለማድረግ በሚያስችል ደረጃ ያቀርቡ እንደሆነ? ጠየቅኳቸው። በተጨማሪም ቴሌኮምን ወደግል በማዛወር የብሔራዊ ደኅንነትና መሰል ጉዳዮችን ከአደጋ መጠበቅ ይችሉ እንደሆነም?" ጠየቅኩዋቸው። ከመልሳቸው ስለእነዚህ ልማቶችና አገልግሎቱን ወደግል በማዛወር ስለሚደርሰው ጉዳት ብዙም የጠራ ግንዛቤ እንዳልነበራቸው ካረጋገጥኩ በኋላ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ ረገድ እያደረገ ያለውን ጥረት ዘርዘር ካለመረጃ ጋር አቀረብኩላቸው። በዚያውም አገልግሎቱን ለሽያጭ የማቅረብ ፍላጐት እንደሌለን ገለጽኩላቸው። አምባሳደሩ ያቀረብኩትን ሀሳብ በጽሞና ካዳመጡ በኋላ "በእውነቱ የእናንተ አቅጣጫ በጣም የተለየ ነው" በማለት ተሰነባብተውኝ ተለያየን።

አምባሳደሩ በዩጋንዳ ወደግል በተዛወረው ቴሌኮም እጅግ በጣም ትንሽ ድርሻ ያላቸው ቢሆኑም፣ የኢትዮጵያን ቴሌኮም ለመግዛት ግን ፈጽሞ አቅም አልነበራቸውም። የኢትዮጵያ ቴሌኮም አሁን ባለው የካፒታል መጠን ለገበያ ቢቀርብ ከአምሳ ሚሊዮን የማያንስ የሞባይል

ተጠቃሚ ብቻ በየቀኑ በብዙ ሚሊዮን ዶላር ለሚቆጠር ትርፍ ምንጭ በመሆኑ በአሥር ቢሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር እንደማይበቃው ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህም የዩጋንዳው አምባሳደር በዚህ መሰሉ ስምሪት ውስጥ ለግዙፍ ድንበር ተሻጋሪ የምዕራብ ኩባንያዎች በጉዳይ አስፈጻሚነት ከማገልገል አልፈው በእርግጥም ዋናው ገዥ ሊሆኑ አይችሉም ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ አንዳንድ የራሳችንም ሆነ የሌሎች ያልበለጸጉ አገሮች ዜጐች፣ ከዚህ ዓይነቱ የፕራይቬታይዜሽን ሂደት ዋናዎቹ ተጠቃሚዎች ባይሆኑም፣ በመንግሥት ላይ ተጨማሪ ጫና የሚያሳድሩ ሆነው ቆይተዋል፡፡ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ደኅንነት የሚያረጋግጥ ቅኝት ያለውና አገልግሎቱን በጥራትና በስፋት ለማዳረስ ሲዘረጋ የቆየው የቴሌኮም አገልግሎት፣ በዚህ አዲስ ልማታዊ ቅኝትና መንፈስ ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህን መሰል ተፅዕኖዎች በመቋቋም ጭምር የተገነባ ነው፡፡

ምዕራፍ አራት

ለመልካም ጉርብትና የተካሔደው ትግልና ውጤቱ፣

ከ1983ዓ.ም. በኋላ በኢትዮጵያ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የተካሔደው ትግል በአገር ውስጥ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ መስኮች ብቻ የታጠረ አልነበረም፡፡ በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ቅኝትና ተጨባጭ ዲፕሎማሲ ላይ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት ጭምር የተካሔደ ነበር፡፡ ይህን በትክክል ለመገንዘብ በንጉሣዊውና በደርግ አስተዳደር ወቅት የነበረውን የአገሪቱን የውጭ ግንኙነት መሠረታዊ ይዘትና ባሕርይ ከመመልከት መጀመር ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ በቀድሞ መንግሥታት ዘመን የውጭ ግንኙነት ሥራዎቿን የምታካሂደው በትክክለኛ ፖሊሲ በመመራት አልነበረም፡፡ በንጉሡ ዘመን አገሪቱ የምትመራበት የተጻፈ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አልነበራትም፡፡ በመሆኑም ንጉሡና ባለሥልጣናቱ ከሞላ ጎደል ከራሳቸው ጥቅምና አተያይ በመነሳት ብቻ በሚሰጡት መመሪያ የሚፈጸም ግንኙነት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የነበረው የውጭ ግንኙነት ምንም እንኳ ባልተጻፈ ፖሊሲ ይመራ የነበረ ቢሆንም ሦስት መሠረታዊ ባሕርይ ወይም ቅኝት ነበረው፡፡ የመጀመሪያው ንጉሣዊውን የፊውዳል አስተዳደር ዘላለማዊነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ሁለተኛው መለያ ባሕርዩ በዓለም አቀፍ አሰላለፍ ከምዕራቡ ዓለም ጋር በጥብቅ የተቆራኘ መሆኑ ነበር። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ከውጭ ወደውስጥ የሚመለከት መሆኑ ነበር፡፡ እነዚህ በንጉሡ ዘመን የነበረውን የውጭ ግንኙነት የሚገዙ ማዕቀፎች ነበሩ፡፡ ንጉሱ በአንድ ወቅት ለአረብ አገሮች የሰጡት ድጋፍና ከቻይና ኮምዩኒስት መንግሥት ጋር የመሠረቱት ወዳጅነት፣ እንዲሁም በገለልተኛ አገሮች ማኅበር በመሳተፍ አልፎ አልፎ ከእነዚህ ማዕቀፎች ወጣ ያለ ግንኙነት ይፈጥሩ የነበረ ቢሆንም፣ መሠረታዊ ይዘቱ ግን ከዚህ ውጭ አልነበረም፡፡

በንጉሣዊው አስተዳደር ዘመን የነበረው ሥርዓት በከባድ ውስጣዊ ቅራኔ የተሞላ፣ በተለይ ደግሞ የህዝብ መደባዊና የብሔራዊ እኩልነት ጥያቄዎች የተበራከቱበት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት የሚቀሰቀሰው ቅሬታና ትግልም ኃያል ነበር፡፡ ይህን ሰፊ ትግል አቅጣጫ ለማሳት የሚቻለው የአገሪቱ ህዝቦች ትኩረታቸውን በመሉ በውጭ "ጠላቶች" ላይ ሲያደርጉ እንደሆነ በማመን፣ መሪዎቹ ከሞላ ጎደል አብዛኞቹን የቅርብ ጎረቤቶችና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በጠላትነት እንዲታዩ የማድረግ ፍላጐት ነበራቸው፡፡ አገሪቱ "የክርስቲያን ደሴት እንደሆነችና በዚህ ምክንያት ዋናው የህልውና ፈተና በአካባቢው ካሉት መስሊም አገሮች የገጠማት ከበባ

እንደሆነ" በሚሰመሰል በህዝብ ልቦና ውስጥ ፍርሃት ሚገነሥ የሥርዓቱ ዓይነተና ዘዴ ነበር።

በተመሳሳይ ቅኝት የሚጓዙ የአካባቢ አገሮች መሪዎችም ተመሳሳይ ስልቶች ይከተሉ ነበር። እነርሱም ህዝባቸውን ከውስጥ ችግር ለማዘናጋት በዓለም አቀፍ ግንኙነታቸው የውጭ ጠላት የሚፈጥሩና የሚያበራክቱበት ሂደት የተለመደና ዛሬም ድረስ የሚታይ ነው። በዚህ የተነሳ እነዚህ የተሳሳቱ የውስጥና የውጭ አቅጣጫዎች እርስ በርስ እየተመጋገቡ ራሱን የቻለ የግጭት እውነታ ሲፈጥሩ ቆይተዋል። በተጨማሪም ዓለም በሁለት ጐራ ተከፋፍላ በቀዝቃዛው ጦርነት በምትናጥበት በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ የምዕራቡን ዓለም ደግፋ ነበር። በዚህ ማዕቀፍ በወገናዊነት ከመሰለፍ አልፋ አሜሪካኖች የቃኘው ወታደራዊ መደብርን በአስመራ ከተማ እንዲከፍቱ ፈቅዳለች። ባሕር ተሻግራም በማይመለከታት ጦርነት ውስጥ ጐራ ለይታ እስከመዋጋት ደርሳለች። እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ በንጉሣዊ አስተዳደር ዘመን አገሪቱ ባልተጻፈ፣ ነገር ግን በተግባር ላይ በዋለ የተሳሳተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ስትመራ እንደነበር ያመላክታሉ።

ወታደራዊው መንግሥት ሥልጣኑን ከወሰደ በኋላ ደግሞ፣ በንጉሡና ሥራውን በሚመሩት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ስሜቶች፣ ግምቶችና እሳቤዎች ላይ ተመሥርቶ ባልተጻፈ ፖሊሲ በመመራት ሲካሔድ የነበረው የውጭ ግንኙነት በይፋ ባይሰራጭም በተጻፈ ሰነድ በሚመራ ግንኙነት ተተካ። ደርግ ሥልጣን ከያዘ ከሞላ ጐደል ከአሥር ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጥናት እንዲካሔድና በዚህ ላይ የተመሠረተ አዲስ ሰነድ እንዲዘጋጅ አድርጓል። ይህም ሰነድ በብርቱ ሚስጥርነት የተያዘ እንጂ በይፋ ታትሞ የተሠራጨ አልነበረም። በመሆኑም በደርግ ጊዜ አገሪቱ በይፋ በህዝብ የሚታወቅ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲም ሆነ ሰነድ አልነበራትም ማለት ይቻላል። በዚያው ልክ ደግሞ የውጭ ግንኙነት ሥራው ከህዝብ ተደብቆ የሚካሔድ የጥቂት የደርግ ባለሥልጣናት ተግባር ብቻ ነበር። ወታደራዊው አገዛዝ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሳየው የአሰላለፍና የጐራ መቀያየር በስተቀር የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በሁሉም ይዘቶቹ መሠረታዊ ለውጥ እንዳላመጣ ደርግ ይመራበት ከነበረው ሰነድ ለመገንዘብ ይቻላል።

ደርግ በ1976 ዓ.ም ባዘጋጀው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጥናት ሰነድ ላይ "የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ ዓላማዎች፣ መርሆዎችና ግቦች" በሚለው ርዕስ ሥር የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ ዓላማዎችን ሲዘረዝር፣ "በኢትዮጵያ የሶሻሊስት ሥርዓት፣ ብሎም ኮሙኒስት ሥርዓት ለመመሥረትና ዓለም አቀፍ የሶሻሊስት ሥርዓትን በወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ለመገንባት ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ያለውን ወዳጅነት፣ ትብብርና ጽኑ የትግል አንድነት በሁሉም መስክ ማጠናከር፤"[40] የሚለውን በቀዳሚነት ያስቀምጣል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ ግቦች በሚል ርዕስ ሥር፣ "በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውን ችግር መፍታት"፣ እንዲሁም

"በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል ላለው ችግር ዘላቂ መፍትሔ መስጠት" በሚሉ ርዕሶች ሥር፣ መሠረታዊ ችግር አድርጉ የሚያቀርበው "ኢምፔሪያሊዝምና አድሐሪ የአረብ መንግሥታት ኢትዮጵያን ለሚጥፋት የወጠኑት ሴራ" የሚለውን ነበር። በደርግ አተያይ ሁሉም ችግሮች የመነጩትም ሆነ ተጋላጭነታችን የተፈጠረው በአገር ውስጥ ባለው ድኅነትና ኋላቀርነት ምክንያት አልነበረም። አገሪቱን ለመበታተን የተቃረቡትን የድኅነትና የኋላቀርነት ጉዳዮች አንድም ቦታ ላይ የችግሩ መሠረታዊ መንስዔ አድርጉ አያስቀምጥም። ለደርግ መንግሥት የችግሮቹ ሁሉ መንስዔ ውጫዊ ቢሆንም እውነታው ግን ከዚህ በብርሃን ዓመታት የራቀ ነበር።

በኢትዮጵያ መጀመሪያ ላይ ፊውዳላዊ የአመራረት ዘይቤና በህዝብ ላይ የሚፈጸም የኢኮኖሚ ምዝበራ፣ ከዚህ በተጓዳኝ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ አስተዳደር እጦት የአገሪቱ ችግሮች ሁሉ ዋነኛና መሠረታዊ ምንጮች ነበሩ። አገሪቱ ራሷን ለቀጥተኛ ቅኝ ተገዥነት ሳታጋልጥ የኖረች በመሆኗ በርግጥም የውጭ ኃይሎችን የችግሮቿ ሁሉ ቀዳሚ ምንጮች ለማድረግ የሚያስችል ተጨባጭም ሆነ ሞራላዊ መሠረት አልነበራትም። አልፎ አልፎ የውጭ ኃይሎች ጥቃት ያጋጠማት ቢሆንም ከገናና ሥልጣኔ ወደተመጽዋችነት የወረደችው በመሠረቱ በራሷ መሪዎች ጥፋትና የብቃት መጓደል ነበር። ስለሆነም ገዥዎቹ ህዝብን ሊያሳምኑ እንደሞከሩት የአገሪቱ ኋላቀርነት ዋናው ምንጭ መፈናፈኛ ያሳጡዋት መሠሪ የውጭ ኃይሎች አልነበሩም። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ሌሎች በቅኝ ግዛት የወደቁ አፍሪካውያን ወንድምና እህቶች አውሮፓውያኑን ለማማረር ያላቸውን ያህል፣ የውጭ ኃይሎችን በእጅጉ ልታማርር የምትችልበት ሞራላዊ አመክንዮ የላትም። በባሪያ ንግድ የወጣቶቻቸውን ጉልበት ከመነጠቅ ጀምሮ ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸውን ተነፍገው፣ ሕይወታቸውን ባሻቸው መንገድ መምራት ያልቻሉት አፍሪካውያን የውጭ ኃይሎችን ቢያማርሩ ይገባቸዋል። በፀረ-ቅኝ አገዛዝ ታሪኳ ለምትኮራው ኢትዮጵያ ግን "መሰሪ" ኢምፔሪያሊዝምና "አድሐሪ የአረብ መንግሥታት" ለአገሪቱ ዕድገት መገታት የሩቅ እንጅ የቅርብ ምክንያቶች ሊሆኑ አይችሉም።

በንጉሣዊው አስተዳደር ዘመን ፊውዳላዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ዋናው የችግር ምንጭ እንደነበረው ሁሉ፣ በደርግ አስራ ሰባት ዓመታት ዘመነ-መንግሥት ደግሞ የእዝ ኢኮኖሚና በዚህ ላይ የተመሠረተው ምዝበራና ፀረ-ዴሞክራሲ ዋናዎቹ የዕድገት መገታት ጠንቆች ነበሩ። በጥናት ደረጃም ቢሆን እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች ቸል በማለት የተዘረዘረው የደርግ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ትክክለኛ ይዘት ኖሮት ሊቀረጽ አይችልም ነበር። በዚህ ምክንያት የደርግ መንግሥት እስከእለተ-ሞቱ ድረስ ውስጣዊ ቅራኔዎችን ሁሉ በውጭ ኃይሎች ግፊት የተፈጠሩ አድርጉ በመመልከት መላ አቅሙን እነዚህን ለማጥፋት በመረባረብ አሳልፏል። ደርግ በጥናታዊ ሰነዱ ላይ ስለ ኤርትራ ህዝቦች ትግል፡-

"በአሁኑም ወቅት ቢሆን በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አቀናባባሪነት፣ የሱዳን መንግሥት፣ ሳውዲ አረብያና ሌሎችም የፋርስ ባሕረ-ሰላጤ መንግሥታት ተገንጣይ ቡድኖችን ከምንጊዜውም ይልቅ በማስተባበር፣ በማደራጀት፣ በማስታጠቅና አመራር በመስጠትም ጭምር ድጋፋቸውን ከፍ ስላደረጉላቸው ተጠናክረው ይገኛሉ:: በቀይ ኮኮብ ሁለገብ ዘመቻ ወቅት ተዳክመውና በጥቂት አካባቢዎች ብቻ ታጥረው የነበሩት በአሁኑ ወቅት ባልተጠበቀ ሁኔታ አንሰራርተው ለአብዮቱ ከፍተኛ እንቅፋት ሆነው ይገኛሉ::"[41] ብሎ ነበር።

ደርግ በዚህ መንገድ ችግሩ በመሠረቱ ከውስጥ ያልመነጨ እንደሆነ በማስመሰል ቅራኔውን በኃይል መፍታትን ብቸኛ አማራጭ አድርጐ ቀጥሎበታል:: የኢትዮጵያ ችግሮች የተስተካከለ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመቅረጽና አሳታፊ ዴሞክራሲን በማስፈን ሊፈቱ የሚችሉና የሚገባቸው ቢሆኑም፣ የኃይል እርምጃን በማስቀደም ለመፍታት ያደረገው ሙከራ ሁሉ ከሽፎ የማታ ማታ የራሱን የደርግ መንግሥት ውድቀት የሚያፋጥን ሆነ::

ከፍ ሲል ከተመላከቱት ጉዳዮች ለመገንዘብ እንደሚቻለው የኢትዮጵያ ያለፉ የውጭ ግንኙነቶች በአገር ውስጥ ካሉት መሠረታዊ የድኅነትና ኋላቀርነት ችግሮች የሚነሱና እነርሱንም ለመፍታት አጋዥ ሚና የሚጫወቱ አልነበሩም:: ይልቁንም በአገር ውስጥ ይታይ የነበረውን መሠረታዊ ችግር የመድፈቅና የማድበስበስ ባሕርይ ነበራቸው። የአገሪቱን ህዝቦች የሚያሰቃዩት መሠረታዊ ችግሮች ዋነኛ መንስዔዎች ምዝበራና ፀረ-ዴሞክራሲ ስለነበሩ፣ እነዚህን ጠንቆች ለመቅረፍ ከተፈለገ አሮጌዎቹን ሥርዓቶች ከሥረ መሠረታቸው ማፍረስ የግድ ነበር:: ይህን ደግሞ የሥርዓቱ ባለቤቶችና ተጠቃሚዎች በራሳቸው ተነሳሽነትና ፍላጐት ሊያደርጉት አይችሉም ነበር:: ከ1983 ዓ.ም በኋላ በአገሪቱ በተጨባጭ እንደተደረገው ሥርዓቶቹ በኃይል እንዲወገዱ ከተደረገ በኋላ አዲስ ሥርዓት በመገንባት ብቻ ሊፈጸም ይችልና ይገባው የነበረ ነው::

ከወታደራዊው አገዛዝ መወገድ በኋላ የተመሠረተው የሽግግር መንግሥት ከምንም ነገር በፊት ምርጫው መላ አቅሙን ለአገር ግንባታ ማዋል ነበር:: ይህን የመሰለው ከባድ ተልዕኮ ደግሞ ውስጣዊና ውጫዊ ሰላምን ከማረጋገጥና ዴሞክራሲን ከማስፈን ውጭ እውን ሊሆን አይችልም:: ለሠላሳ ዓመታት በጦርነት የደቀቀችና የተመሰቃቀለችውን አገር አስተማማኝ ሰላም በማስፈን ካልሆነ በስተቀር፣ ወደልማትና ዴሞክራሲ መምራት አይቻልም ነበር:: ዴሞክራሲ ለሰላምና ልማት፣ ሠላም ለልማትና ዴሞክራሲ፣ ልማትም ለሰላምና ዴሞክራሲ የማይነጣጠልና ተመጋጋቢ ተፈላጊነት ነበራቸው። የልማትና ዴሞክራሲ ሥራዎቹ ቀደም ሲል የተዘረዘሩ በመሆናቸው በዚህ ክፍል ከሰላም አኳያ በተካሔደው እንቅስቃሴ በመወሰን ሂደቱን አጠር አድርጐ መመልከት በመስኩ አገሪቱ የተጓዘችበትን ርቀት ሊያሳይ ይችላል::

የሽግግሩ መንግሥት ዴሞክራሲን ለማስፈንና ለአገሪቱ ኢኮኖሚ መልሶ ግንባታ ቁዳሚ ትኩረት በሰጠበት በዚህ ወቅት፣ በውጭ ግንኙነት ፖሊሲው ላይ ከሁሉም አገሮች በተለይ ደግሞ ከጎረቤት አገሮች አዲስና ያልተለመደ ግንኙነት ለመመሥረት ዝግጁ እንደሆነ አስታወቀ። ይህም የአገሮችን ሉዓላዊነት በማከበርና በውስጥ ጉዳያቸው ጣልቃ ባለመግባት መርሕ የሚገዛ ግንኙነት የመመሥረት አቅጣጫ ሲሆን፣ በአፍሪካ ቀንድ የትርምስ ቀጠና እየኖረ ፖሊሲውን በይፋ ከማስታወቅ አልፎ ተምኔታዊ ሊባል በሚቻል ደረጃም አመነበት፡፡ በርግጥም የቀጠናው ታላቅ አገር ኢትዮጵያ፣ በዚህ አኳኋን ከራሷ ጋር ከታረቀችና በውስጧ ሰላም ካወረደች በኋላ ከሌሎች ጋር በሰላም ለመኖር የሚኖራት በጎ አስተዋጽኦ በተግባርም እንደታየው አቻ አልነበረውም፡፡

የሽግግሩ መንግሥት በዚህ አኳኋን ዋነኛ ትኩረቱን በአገር ውስጥ የለወጥ ተግባራት ላይ ለማድረግ በመወሰኑ የአፍሪካ ቀንድ አስተማማኝ ሰላም የሰፈነበት ሊሆን ይችላል ብሎ አመነ፡፡ ከዚህም በመነሳት የአገሪቱ ወታደራዊ አቅም ከኢኮኖሚው ዕድገት ጋር በተገናዘበ መጠን ሊገነባ እንደሚገባው አሰመረበት፡፡ ከእነዚህና በኋላም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ተዋጽኦው የተመጣጠነ ሠራዊት ለመገንባት ከነበረው ፋይዳ በመነሳት፣ ከነባሩ የኢህአዴግ ተዋጊ ኃይል በሽዎች የሚቆጠሩ ልምድ ያላቸው ታጋዮችን ቀንሶ ፣ ወደግብርና ልማት እንዲሰማሩና በዚያው እንዲቋቋሙ አደረገ፡፡ ኢትዮጵያ ከራሷ ጋር ሰላም እስካወረደች ድረስ ለውጭ ጥቃት የሚኖራት ተጋላጭነት በእጅጉ እንደሚቀንስ በመተማመን የተወሰደው ይህ ርምጃ በእርግጥም አዲሱ መንግሥት ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም በአጭር ታጥቆ እንደተነሳ የሚያመላክት ነበር፡፡

የሽግግሩ መንግሥት ከወጭ ግንኙነት አኳያ ሌላም አብዮታዊ የሚባል እርምጃ ወስዷል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ የየትኛውንም የጎረቤት አገር መንግሥት በኃይል የሚፋለመው የትግል ድርጅቶች በአገሯ ውስጥ የታጠቀ ህልውና እንዲኖራቸው የማትፈቅድ መሆኗን ማሳወቁ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት በደርግ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰፍሩ የተፈቀደላቸው የደቡብ ሱዳን አማጽያን ወደአገራቸው ሔደው የራሳቸውን ነጻ መሬት እየፈጠሩ እንዲታገሉ በጋምቤላ የነበረው ወታደራዊ ሰፈራቸው እንዲዘጋ ተደረገ፡፡ የኤርትራን መንግሥት የሚቃወመው የትግል ድርጅቶችም በኤርትራ ነጻ መሬት ፈጥረው ትግላቸውን እንዲያካሔዱ ማድረግ የተሻለውና ትክክለኛው አማራጭ ሆኖ ተወሰነ፡፡ ከኢትዮጵያ እየተንደረደሩ ሉዐላዊ መንግሥታትን መፋለምና ተመልሶ ወደኢትዮጵያ በመግባት የሚካሔድ ትጥቅ ትግል፣ መልካም ጉርብትናን ከማጥፋት ውጭ እታገላለሁ የሚለውንም ኃይል ለስትራቴጂያዊ ድል የሚያበቃ አልነበረም፡፡ ይልቁንም በራሱ አገር የራሱን ነጻ መሬት በትግል እየፈጠረና ህዝብን እያሳተፈ የመሔድ ዕድሉን የሚያቀጭጭበት ነበር፡፡ ኢትዮጵያን ከጎረቤቶቿ ጋር በማጋጨት አጸፋ እንዲመልሱና በሌሎች

መስኮችም እንዲጐዷት በር ይከፍት ነበር። በመሆኑም ኢትዮጵያ ለሌሎች አገሮች ታጋዮች ወታደራዊ ሰፈር ከመስጠት በመለስ ተፈላጊ ሆነው በሚገኙ ትብብሮች ብቻ እንድትወሰን ተደረገ። ፖሊሲው ኢትዮጵያ በራሷ ላይ የጫነችው አዲስና ትከከለኛ ውሳኔ ነበር። በራሱ ሌላ ምክንያት በተቀሰቀሰው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ካጋጠማት የሁለት ዓመት ግጭት በመለስ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የዘለቀ አስተማማኝ ሰላም እንዲኖራት ያስቻለው ዋናው ምክንያትም ይኸው ነበር።

ኢትዮጵያ በሰላም መኖር የጀመረችባቸው እነዚህ ዓመታት በልማትና ዴሞክራሲ ረገድም ጉልህ ለውጥ ያመጣችባቸው ነበሩ። ምንም እንኳ ዋናው የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እመርታ ከተሃድሶ እንቅስቃሴው በኋላ የተመዘገበ ቢሆንም መሠረቱ የተጣለው በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ነበር። በዚህ ወቅት አገሪቱ ደረጃ በደረጃ እየተሻሻለች ከመሔዷም በላይ በብዙ የምዕራብ አገሮች ልሂቃን ዘንድ "አዲሱ የአመራር ትውልድ" በመባል መታወቅ በጀመሩት መሪዎች ወደፊት መራመድ ጀመረች። በቀዝቃዛው ጦርነት መጀመሪያ ላይ በኮንጐና ኮሪያ ጦርነት ውስጥ ገራ ለይታ በመሰለፍ በ1950ና 60ዎቹ ካደረገችው ተሳትፎ በኋላ ለቀውስና የእርስ በእርስ ግጭት የተዳረጉ የአፍሪካ አገሮችን ለማረጋጋት ሠራዊቷን ማሰማራት የጀመረችውም በዚሁ ጊዜ ነበር።

በዚህ መሠረት በ1980ዎቹ አጋማሽ በቡሩንዲ የተቀሰቀሰውን ግጭት ለማቃለል የሰላም አስከባሪ ላከች። በዚህም በንፁህ የገለልተኝነት መንፈስ የእርስ በእርስ ግጭቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲቆም ተገቢና ትከከለኛ አስተዋጽዖ አበረከተች። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ በሩዋንዳ የተቀሰቀሰውን የእርስ በእርስ ጦርነትና የዘር ማጥፋት እንቅስቃሴ ለማስቆም ጉልህ ሚና የነበረው የሰላም ማስከበር ተግባር አከናወነች። በሁለቱም አገሮች የቀድሞ ቅኝ ገዥዎች ራሳቸው በረጨት የአስተሳሰብ መርዝ የተቀሰቀሰውን ግጭትና ደም መፋሰስ ከማቆም ይልቅ ጥለው እየወጡ ሌላ የታሪክ ስህተት ሲፈጽሙ፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በሰላም አስከባሪነት ተሰማርቶ አገራቱ ወደዘላቂ ሰላም እንዲሸጋገሩ መንገድ ከፈተ። ተመሳሳይ ግጭት በማይለያት አፍሪካ የላይቤሪያን አደገኛ የእርስ በእርስ ጦርነት በአጭር ጊዜ አስቁሞ ሰላም ለማስፈን የተቻለውም በኢትዮጵያና በመከላከያ ሠራዊቷ የሚደነቅ ተሳትፎ ነበር። የሱዳን የእርስ በእርስ ጦርነት በፍትሃዊ መንገድ እልባት እንዲያገኝ ከማድረግ በተጨማሪ አገሪቱ ከሁለት ከተከፈለች በኋላም ቦዳርፉርና አቢዬ አካባቢ ስኬታማ የሰላም ማስከበር ተግባርም ተከናውኗል። በመሆኑም አገራችን ውስጧን ሰላማዊ በማድረግ ሳትወሰን፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተተራመሱ የአፍሪካ አገሮችን ወደዘላቂ ሰላም ለማምራት ያስቻለ ሚና ተጫውታለች። ይህም ኢትዮጵያ ከማንም በላይ በአፍሪካው ያን ወንድምና እህት ህዝቦች ዘንድ አመኔታ የሚጣልባትና ከፍተኛ ተሰሚነት ያላት አገር እንድትሆን አስችሏታል።

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የጀመረችው ይህ አዲስ ዓይነት የውጭ ግንኙነትና በተለይ በአፍሪካ ጉዳይ ላይ መጫወት የጀመረችው የላቀ ገንቢ ሚና ከ1993ቱ የተሃድሶ እንቅስቃሴ በኋላም ሰፍቶና ዳብሮ ቀጥሏል። ይህም እንደገና አገሪቱ መከተል በጀመረችው ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ አቅጣጫ ላይ በተመሠረቱ ዘርፈ-ብዙ ለውጦች ምክንያት የመጣ ነው። አገሪቱ ከ1995 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ባሉት አሥራ ሦስት ዓመታት በአማካይ የ10.5 በመቶ ተከታታይ ዕድገት ለማስመዝገብ ከመቻሏ ጋር ተያይዞ ተቀባይነቷ ይበልጥ የጨመረበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በተጨማሪም መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን በመወከል በአህጉራዊ መድረኮች ገንቢና በጣም በሳል ሚና መጫወታቸው አገራችን የነበራትን ተቀባይነት ወደላቀ ከፍታ አውጥቶታል። ታቦ እምቤኪን ከመሳሰሉ ተራማጆች ጋር በመሆን የአፍሪካ ህዳሴ (African Renaissance) መሠረተ-ሀሳብን ለመንደፍ፣ ለማስፋፋትና በተግባር ለማዋል ግንባር ቀደም ሚና በመጫወቱ ይህ ተቀባይነት ይበልጥ ሊጠናከር ችሏል። ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህዳሴ ሀሳቦችን በራሷ ምድር ተግባራዊ በማድረግና የአቻ ግምገማና (Peer Review) የመሳሰሉትን መሠረተ-ሀሳቦች ለማመንጨትና ተግባራዊ ለማድረግ መቻሏ በእርግጥም በውጭ ግንኙነት መስክ የአፍሪካውያንን የላቀ ድጋፍ አስገኝቶላታል።

በዚህ ላይ መሪዎቿ ከኢትዮጵያ የተናጠል ፍላጎትና ጥቅም በተጨማሪ የአፍሪካን መብትና ጥቅም በመወከል በዓለም አቀፍ መድረኮች ሰፊና አሳማኝ እንቅስቃሴ በማካሔዳቸው የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ተቆርቋሪ በመሆን የተቀባይነት ደረጃዋ እንዲጨምር ለማድረግ ተችሏል። ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ አፍሪካን በመወከል በቡድን 8 እንዲሁም በቡድን 20 አገሮች ስብሰባዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንድትሆን ባበቃት በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሚና በእርግጥም አንድ ባለከባድ ሚዛን አፍሪካዊ አገር ለመሆን በቅታለች። ይህ ኢትዮጵያ በታሪኳ አግኝታው የማታውቀው ግዙፍ የፖለቲካ ካፒታል ነው። ይህ ካፒታል ሊፈጠርና ሊከማች የቻለው ደግሞ ከምንም ነገር በላይ በውስጧ ዴሞክራሲ፣ ልማትና ሰላም የሰፈነባት አገር እየሆነች ከመሔዷ ጋር ተያይዞ ነው።

ይህም ሆኖ ባለፉት ዓመታት በውጭ ግንኙነት ረገድ ተጨባጭ ችግሮች አላጋጠሟትም ማለት አይደለም። ይህን አዲስ የዲፕሎማሲ ካፒታል ለአደጋ የሚያጋልጡ ችግሮች የሉባትም ማለትም አይቻልም። ከአንዴም ሁለቴ ከባድ ፈተና የደቀኑባት ሁለት ጦርነቶችና ሌሎች ችግሮች አጋጥመዋታል። የመጀመሪያው ትልቅ ጦርነት ከ1990-1992 ዓ.ም ድረስ ለሁለት ዓመታት የተካሔደው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ነበር። ሁለተኛው ደግሞ በ1999 ዓ.ም በሶማሊያ የአልሸባብ ኃይል የደቀነውን አደጋ ለማስወገድ የተካሔደው ጦርነት ነበር። ሁለቱን ጦርነቶች አጠር አድርገው መመልከት አገሪቱ የገጠማትን ፈተና ባሕርይና ይህንም እንዴት እንዳለፈችው ለመመልከት ያስችላል።

የኤርትራ ወረራ፣ መነሻ ምክንያቱ፣ አመካከቱና እንደምታው፣

የመጨረሻው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የተቀሰቀሰው ለሠላሳ ዓመታት የተካሔደው ረጅሙ ጦርነት ካከተመ ከሰባት ዓመታት በኋላ ነበር፡፡ ሰላም በሰፈነና አዲሶቹ የአፍሪካ የአመራር ትውልዶች "አገራቱን ለአዲስ ዓይነት ግንኙነት ያበቁዋቸዋል" ተብሎ በታመነ ማግስት የተቀሰቀሰው የዚህ ጦርነት ዝርዝር ሂደት፣ ራሳቸውን የቻሉ በርካታ መጻሕፍት ሊወጣው የሚችልና የሚገባው ነው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ትኩረት የሰጠሁት ለጦርነቱ ምክንያት የሆኑትን ዋና ዋና ጉዳዮችና ኢትዮጵያ ችግሩ እንዳይፈጠር ለማድረግ ገና ከጠዋቱና በኋላም በጦርነቱ ሂደት ያደረገችውን ጥረት ከነትርጉሙ በአጭሩ በመዳሰስ መረጃዎችን ለማካፈል ነው፡፡

ኢትዮጵያና ኤርትራ ከደርግ አገዛዝ የተላቀቁት በአራት ቀናት ልዩነት ነበር፡፡ የኤርትራው ህዝባዊ ግንባር አስመራን ግንቦት 16 ቀን 1983 ዓ.ም በመያዝ መላዋን ኤርትራ ሲቆጣጠር፣ በኢህአዴግ የተመራው ትግል ደግሞ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ መላዋን ኢትዮጵያ ከደርግ መዳፍ አላቀቀ፡፡ ሁለቱን ከተሞች የቱቆጣጠሩት የነጻነት ግንባሮች በመሠረታዊ ባህሪያቸው በጣም የተለያዩ ናቸው፡፡ አልፎ አልፎም ትጥቅ ትግሉ ሳይጠናቀቅ በከባድ የፖለቲካ ልዩነት ምክንያት በመኮራረፍ ግንኙነታቸውን እስከማቋረጥ የሚደርሱ ነበሩ፡፡ ለግንኙነቱ መሻከር ዋነኛ ምክንያቱ የኤርትራው ህዝባዊ ግንባር ይከተለው የነበረው አቅጣጫና ይህን ለማስተካከል ይቀርብለት የነበረውን ገንቢ አስተያየት ለመቀበል አለመፍቀዱ ነበር፡፡

በሁለቱ ግንባሮች መካከል የነበረው ግንኙነት በይፋ መሻከር የጀመረው ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ነው፡፡ በትግራይ ከማሌሊት ምስረታ ጋር ተያይዞ "በታጋይ ድርጅቶች መካከል የአስተሳሰብ ትግል በነጻነት ሊካሔድ ይገባዋል" ተብሎ ስለታመነበት፣ በ1977 ዓ.ም አካባቢ ሕወሓት የኤርትራው ህዝባዊ ግንባር በሚመራበት አስተሳሰብ ላይ ጠንካራ ሂስ ሰነዘረ፡፡ ሂሱ በዋነኛነት ግንባሩ ከኤርትራ ህዝብ ተነጥሎ በሳህል ተራሮች ላይ ተንጠልጥሎ የተሳሳተ ወታደራዊ ስትራቴጂ ከመከተሉ የተነሳ ነበር። በተጨማሪም ንቅናቄውን የሚመራበት አስተሳሰብ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑና በሶቭየት ሕብረት ጣልቃ ገብነት ላይ የነበረው የተለሳለሰ አቋም ለሂሱ መሠረቶች ነበሩ። እነዚህ በወቅቱ ለኤርትራ ህዝቦች ትግል ብቻ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ የደርግን ሥርዓት እድሜ ለማሳጠር በነበራቸው ፋይዳ የቀረቡ ገንቢ ሂሶች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ራሱን ከአፍሪካ የትጥቅ ትግል አባቶች እንደአንዱ ለሚቆጥረው ህዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራና ለመሪዎቹ ይህ የሚዋጥላቸው አልነበረም፡፡ በተለይ ደግሞ ሂሱ ከእነርሱ በኋላ ተመሥርቶ በራሱ መንገድ እያደገ ከተጓዘ ድርጅት ሲመጣ በቀላሉ የሚዋጥ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ምክንያት የኤርትራው ህዝባዊ ግንባር የቀረበለትን ሂስ በጸጋ ከመቀበል ይልቅ ወደኩርፊያ አመራ፡፡ ከዚህም አልፎ በ1977 ዓ.ም. የተከሰተውን አስከፊ ድርቅ ለመቋቋም

የእርዳታ እህል ጭነው ወደትግራይ ይገቡ የነበሩ የጭነት መኪኖችን ኤርትራ መሬት ላይ ገትቶ እስከመያዝ ደረሰ፡፡ በረሀብ ጠኔ የተያዘውን ህዝብ ለማዳን የተላከን እህል በመከልከል የሀሳብ ትግሉን ለማስቆም የተደረገው ይህ መከራ ግንኙነቱን ይበልጥ አሻከረው፡፡ ሕወሓት በምዕራብ ትግራይ በኩል በፈጣን ርብርብ አዲስ መንገድ ሰርቶ ከሱዳን ጋር በመገናኘት የእርዳታ እህሉ እንዲጓጓዝ በማድረግ ጊዜያዊውን ችግር ቢያቃልለውም፣ በሁለቱ ግንባሮች መካከል ያለው ግንኙነት ግን ከመሻከር አልፎ እስከ 1980 ዓ.ም. ድረስ ለሶስት ዓመታት ያህል ተቋረጠ፡፡

ግንኙነቱ በዚህ አኳኋን በተበላሸበት ወቅት በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው ትግል ከፍተኛ የአስተሳሰብና የወታደራዊ ጥንካሬ ተገኖናጸፈ፡፡ ሕወሓት በዚህ የዳበረ አስተሳሰብ በመመራት በ1980 ዓ.ም. የበጋ ወራት፣ በሰሜናዊ ምሥራቅ ትግራይ ከምጉላት ጀምሮ እስከመቀሌ ጥግ ድረስ መሸገው የነበረውን የደርግ ሠራዊት በማጥቃት ከሞላ ጐደል መላውን **ትግራይ በ1980 ዓ.ም**. የበጋ ወራት ነጻ አወጣ፡፡ በዚህ ሳይወሰን በአግዓዚ ኦፕሬሽን በመቀሌ **ከተማ ውስጥ እንዳኢየሱስ** በተባለ ቦታ የነበረውን እስር ቤት በማጥቃት በርካታ የፖለቲካ እስረኞችን አስፈታ፡፡ **ይህ**ም ሕወሓት ቀደም ባሉት ዓመታት በፖለቲካዊና ወታደራዊ መስክ ከፍተኛ ለውጥ ለማ**ምጣ**ት ይቻል ዘንድ በቀመራቸው ጥራት ያላቸው ጽንሰ-ሀሳቦች መመራት በመጀመሩና ገና በትንሹ ተግባራዊ መሆን በጀመረው አዲስ የትግል መስመር ውጤታማነት የተገኘ ድል ነበር፡፡ እርምጃዎቹ በሕወሓትና ኢህዴን አመራሮች መካከል ዴሞክራሲያዊ ግንባር ለመፍጠር የነበረውን የቆየ ራዕይ እውን ለማድረግ ጊዜው መድረሱንም አመላክቱ፡፡

በዚህ መሠረት በማያዝያ/ግንቦት ወር 1980 ዓ.ም. በምዕራብ ትግራይ ደጀና በሚባለው የሕወሓት ወታደራዊ ሰፈር ከሕወሓት መለስ፣ አባይ፣ ስዩም፣ ስየ፣ ስብሓት፣ ተወልደ፣ ጻድቃንና ገብሩ፣ ከኢህዴን ደግሞ ታምራት ላይኔ፣ በረከት ስምዖንና መለስ ጥላሁን በተገኘንበት ስብሰባ አገራዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ለመመሥረት የመጀመሪያ ደረጃ ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ ኢህአዴግ የሚለው ስያሜና አርማው ቀጥሎ በተካሔደው የሐምሌ ስብሰባ እስኪጸድቅ ድርስ ሳይጠበቅ፣ የስምምነቱ ማብሰሪያ ይሆን ዘንድ ከማይጨው እስከኮረም (ግራካሹ) መሸገው የነበረውን የደርግ ሠራዊት በጋራ የማጥቃት እቅድ "ጣምራ ከንዳችን" በሚል የዘመቻ ስያሜ ተዘጋጀ፡፡ የሁለቱ ድርጅቶች ሠራዊቶች በግንባት አጋማሽ ላይ እቅዱን በተሳካ ሁኔታ በጋራ ፈጽመው በርግጥም በአንድ እዝ የሚንቀሳቀስ አገራዊ ግንባርና ሠራዊት መፈጠሩን ለመላ የኢትዮጵያ ህዝቦች አበሰሩ፡፡

በዚህ ተቀራራቢ ወቅት የኤርትራው ህዝባዊ ግንባር በናደው እዝ ላይ ከባድ ጥቃት ሠንዝሮ በደርግ ላይ ከፍተኛ ውድቀት አድርሶ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎም በሁለቱ አካባቢዎች የተካሔዱት እነዚህ ጥቃቶች የአርነት ንቅናቄዎቹ ልዩነታቸውንና መኮራረፋቸውን አለዝበው እንደገና ወደትብብር እንዲመጡ የየራሳቸው አስገዳጅ ሁኔታ ፈጠሩ፡፡ በተለይ ደግሞ የኤርትራው ህዝባዊ ግንባር በፈጸመው ስህተት ምክንያት ግንኙነቱ ለዘላለም መበላሸት

አይኖርበትም የሚል ግንዛቤ ላይ የደረሰው ሕወሓት፣ ያለፈውን ረስቶ የወደፊቱን ቅድሚያ ሰጥቶ በመመልከት ለግንኙነቱ መሻሻል የሚበጁ የመቀራረብ ሀሳቦችን በማምጣቱ ተበጥሶ የነበረው ግንኙነት እንደገና ተቀጠለ፡፡ ከሞላ ጎደል ተመጋጋቢ ጥቃቶችን በመሰንዘር የደርግን እድሜ ለማሳጠር የሚያስችሉ ትብብሮች እየተጠናከሩ መምጣት ጀመሩ፡፡ በትግራይና በአማራ ክልል ሰፍሮ በነበረው የደርግ ሠራዊት ላይ ጥቃቱን ማፋፋም የጀመረው ኢህአዴግ ቀስ በቀስ ወደአዲስ አበባ ማቅናት ጀመረ፡፡

እንደአዲስ መሻሻል የጀመረው ይህ ግንኙነት ከደርግ ውድቀት ማግስትም የቀጠለ ነበር፡፡ ይህም ሆኖ በኤርትራና በኢትዮጵያ የተመሠረቱት መንግሥታት መሠረታዊ ልዩነት የነበራቸው የመሆኑ እውነታ ግን አልተቀየረም፡፡ የሚመሩባቸው ፖሊሲዎችና ከመሪዎቹ አስተሳሰብ የሚፈልቁት ስሌቶችም የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት ነበራቸው፡፡ አዲሱ የኤርትራ መንግሥት ራሱን እንደአንድ ነጻ አገር ያደራጀ ቢሆንም፣ መሪዎቹ መላውን የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ለመምራትና ለእነርሱ ጥቅም በሚበጅ አኳኋን የማንቀሳቀስ ፍላጎትና ዝንባሌ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ካፒታልን ከነግሳንግሱ የመሳብ ፍላጎትና ቅኝት ይዘው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ገና ሥልጣን ከያዙበት እለት ጀምሮ ዓለም አቀፉን ኒዮ-ሊበራል ኃይል ለማግለል ያስቻለናል የሚሉትን የገበያ አከራሪነት አስተሳሰብ ቢያምኑበትም ባያምኑበትም ይምሉ ይገዘቱበት ጀመር፡፡ ኤርትራ አንዲት ትንሽና ነጻ አገር ብትሆንም የምሥራቅና መላው አፍሪካ መግቢያ በር (Gateway to Africa) ልትሆን ትችላለች የሚል ቅኝት በመያዝ ይህን አስተሳሰብ ሳይውሉ ሳያድሩ በፖለሲ መልክ ቀርጸው መንቀሳቀስና ራሳቸውን ማስተዋወቅ ጀመሩ፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ የቀይ ባሕር ሰርጥ ጂኦ-ፖለቲካዊ ፋይዳ እጅጉን በቀነሰበት ወቅት፣ የኤርትራ መንግሥት ከብዙ የምዕራቡ ዓለም መሪዎች ጋር የተለየ ቅርበት ሊፈጥር የቻለው ይህን በመሰለ ተጨባጭ ያልሆነ ምስል ነበር፡፡

በዚህ መሠረት ኤርትራ ማንኛውም ዘርፍ በልቅ የገበያ ፖለሲ የሚመራባት አገር እንደሆነች አወጁ፡፡ በኤርትራ የፋይናንስ ዘርፉ ለዓለም አቀፍ ካፒታል ከፍት እንደሆነ አበሰሩ፡፡ የውጭ ካፒታል ያላንዳች ገደብና ቁጥጥር ኤርትራ ውስጥ መንቀሳቀስና መሰማራት እንደሚችልም አሳወቁ፡፡ ይህ መቼም ትንሿን የኤርትራ አገራዊ ገበያ ብቻ ታሳቢ በማድረግ የተመረጠ ፖሊሲ አልነበረም፡፡ ዓለም አቀፍ ካፒታል ኤርትራን በተናጠል ተመልከቶ በገበያዋ ስፋት በመማለል ይመጣል ከሚል ስሌት የመነጨ ሊሆን አይችልምና፡፡ ኤርትራ ከራሷ ይልቅ በምሥራቅ አፍሪካ ለሚኖረው ሰፊ ገበያ መተላለፊያ ልትሆነው እንደምትችል በማመን ኤርትራን የመነሻ ነጥብ ሊያደርግ ይችላል በሚል ስሌት የተመረጠ ብቻ ነበር፡፡ ልከ በአንድ ወቅት በመካከለኛው ምሥራቅ ቤይሩት፣ ዛሬ ዛሬ ደግሞ የተባበሩት አረብ አምሬትስ አካል በሆነችው ዱባይ፣ በሩቅ ምሥራቅ ደግሞ ሲንጋፖርና ሆንግ ኮንግ የተጫወቱትን የፋይናንስ ማዕከልነት ሚና

ታሳቢ በማድረግ የተቀረጸ ፖሊሲ ነበር። የኤርትራው ፕሬዚዳንትና ባለሥልጣኖቻቸው እንዲህ እንደዛሬው ሳይመሸባቸው በየንግግራቸው ጣልቃ እያስገቡ "ኤርትራን የአፍሪካ ሲንጋፖር እናደርጋታለን" በማለት ያሰሙት የነበረው ዲስኩር ከዚህ የመነጨ ነበር።

የኤርትራ መንግሥት ከዚህ ቅኝት በመነሳት በብዙ የምሥራቅና የመካከለኛው አፍሪካ አገሮች የተለያየ ስምሪት ማድረግ ጀምሮ ነበር። በአንድ ወቅት ለኬንያው ፕሬዚዳንት የግል ጠባቂዎችን ለመመደብ መወሰን አድርጌ ነበር። በቀድሞው የፕሬዚዳንት ካቢላ የአገዛዝ ዘመን በኮንጐ የማዕድን አሰሳ እስከመሳተፍ መድረሱና የኤርትራ ታርጋ የነበራቸው የጭነት መኪኖች በብዙ የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች እስከ 1980ዎቹ መጨረሻ ይርመሰመሱ የነበረ መሆኑ ይህን ያረጋግጣል። ይህ በኤርትራ ጸጋዎችና ከሁሉም በላይ ደግሞ በህዝቦቿ የማይተማመን መንግሥት፣ ገና ከጠዋቱ የሌሎች አገሮችን ሀብት እንደራስ ይዞታ በመቁጠር እጁን ሊያሳርፍበት ከመሻት አልፎ ተጨባጭ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርግ እንደነበር ያሳያል።

ኢትዮጵያን ከደርግ አገዛዝ ነጻ ያወጣው ኢህአዴግ ወደሥልጣን የመጣው በተመሳሳይ ግንቦት ወር ቢሆንም፣ ከዚህ የጥገኝነት መንገድ በእጅጉ የራቀ የፖሊሲ ቅኝትና አስተሳሰብ ነበረው። በኢህአዴግ የተመራው የሽግግር መንግሥት በወቅቱ የበላይነት ከነበረው ኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ ራሱን ቢመጠበቅ በኢትዮጵያ ህዝቦችና በራሷ አገራዊ ጸጋዎች የሚተማመን ነጻ አገራዊ የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲ መከተልን የመረጠ ነው። በኢትዮጵያ የገበያ ሥርዓት መገንባት እንዳለበት ተቀብሎ በወሳኝነት የራስን አገራዊ አቅም ለመገንባትና የውጭ ካፒታልን ለዚህ በደጋፊነት ብቻ ለማሰማራት የቆረጠም ነበር። ከዚህ በመነሳት ሳይውል ሳያድር ለውጭ ካፒታል የማይፈቀዱ በርካታ የስምሪት መስኮች እንዳሉት አሳወቀ። ከምንም ነገር በላይ ደግሞ የፋይናንስ ሴክተሩ ለውጭ ካፒታል ፈጽሞ ሊፈቀድ እንደማይችልና እንደማይገበው በይፋ አወጀ። ኢትዮጵያ በራሷ አገራዊ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ይህን መሰል ጤናማ ፖሊሲ መከተሏ ከባድ የውጭ ተፅዕኖ ያስከተለባት ቢሆንም፣ ከብሔራዊ ጥቅም የሚቀድም ነገር እንደሌለ በመገንዘብ ፖሊሲውን ከነሁሉ ውጤቱ አጥብቃ ትገፋበት ጀመር።

ኢትዮጵያ በውጭ ካፒታል ስምሪት ላይ ገደብ በመጣል የቀየሰችው ይህ ፖሊሲ በኤርትራ የተመሠረተው አዲስ መንግሥት ራሱን እንደምሥራቅ አፍሪካ መግቢያ በር በመቁጠር የጀመረውን ሊበራላይዜሽን ሳይወለድ እንዲጨናገፍ አደረገው። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ፖሊሲ ለራሱ ሲል እንጂ ኤርትራን ለመጉዳት በማሰብ የነደፈው ባይሆንም፣ በተግባር የኤርትራን መንግሥት የተሳሳተ ስሌት ተግባራዊነት ያጨናገፈ ነበር። በዚህ ምክንያት የውጭ ፋይናንስ ካፒታል በኤርትራ በኩል ወደደቡብ አቅጣጫ ዘልቆ ሊገባ ይችላል በሚል ስሌት የተቀየሰው የሻዕቢያ ሊበራላይዜሽን ለራሷ ለኤርትራም የማሆን የውጭ ካፒታል ለመጋበዝ የማያስችል ሆነ። ይህም ሁለቱ አዳዲስ መንግሥታት በፖሊሲ አንድነት ሳይሆን በጐላ የፖሊሲ

ልዩነት እንደጀመሩ ያሳያል። ልዩነቱ እዚያው በዚያው የኤርትራ መንግሥት በሌሎት አገሮት ጸጋዎች ለመበልጸግ የነበረው ህልም እንደከሸፈበትና ከሰባት ዓመታት በኋላ ለቀሰቀሰው ጦርነት ዋናው መነሻ መሠረቱ ይኸው የፖለቲካ ኢኮኖሚ አቅጣጫ ልዩነት እንደነበር ያሳያል።

በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል የነበረው የፖሊሲ ልዩነት አንዱ በሌላው ጸጋ ካለአግባብ እንዳይጠቀም በሩን የዘጋ ቢሆንም፣ ሁለቱ አገሮች በሁሉም መስክ ነጻ አገሮች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አዲስ እውነታ እስኪፈጠር ድረስ የራሱን ጊዜ የሚጠይቅ ነበር። ይህም ጊዜ እስኪደርስ በሁለቱ አገሮች መካከል ሰፋ ያለና በአግባቡ መልክ ያልያዘ የኢኮኖሚ ግንኙነት እንዲኖር የግድ የሚሉ ሁኔታዎች ነበሩ። ሁለቱ አገሮች ሪፈረንደሙ እስኪካሔድ ድረስ ሕጋዊ ፍቺ ያለፈጸሙ አንድ አገር ነበሩ። ሁለቱም በኢትዮጵያ ብር ይገበያዩና በዋነኛነት ደግሞ በአሰብና ምጽዋ ወደቦች ይጠቀሙ ነበር። ይህም በኢኮኖሚ መስክ የነበራቸው ግንኙነት በኤርትራ ሪፈረንደሙ እስኪካሔድ ብቻ ሳይሆን፣ ከዚያም አልፎ እስከጦርነቱ ዋዜማ ድረስ እንዲቀጥል አድርጓል። የኢትዮጵያ መንግሥት ስለቀጠናው ሠላም ከነበረው አስተያየትና ከረጅም ደም አፋሳሽ ጦርነት በኋላ ሁለቱ አገሮች ለሠላም የመሥራት ጠንካራ ፍላጐት ይኖራቸዋል በሚል በጐ እሳቤ ከኤርትራ ጋር የወታደራዊ መከላከል ስምምነት ተፈራርሞም ነበር። የኤርትራ መንግሥት ገሪቤቶቹን በተደጋጋሚ በመተንኮስና ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያን በመውረር ይህ ስምምነት የተመሠረተባቸውን ታሳቢዎች በመሉ ፉርሽ እስኪያደርጋቸው ድረስም ወታደራዊ የትብብር ስምምነቱ ፀንቶ ቆይቷል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈጠረው ግንኙነት እንደሚቀጥል በመገመት የግንኙነቱ ባሕርይ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ መሆን እንዳለበት በጥብቅ ያምን ነበር። ሁለቱ አገሮች ቀደም ሲል በታሪክ አጋጣሚና በተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት ለግጭት የተዳረጉ ቢሆኑም፣ ዕጣ ፋንታቸው ፈጽሞ የተነጣጠለና የማይገናኝ ነው ብሎ ግን የሚያምን መንግሥት አልነበረም። በሁለቱ አገሮች ህዝቦች መካከል መሠረታዊ የመብትና የጥቅም ግጭቶች እንደሌሉም ይገነዘብ ነበር። በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ ህዝቦች መገዳት የሌሎች አገሮች ህዝቦች እንዲጠቀሙ የማይፈልገውን ያህል፣ በሌሎች መገዳት የኢትዮጵያን ህዝቦች መጥቀም አለብኝ ብሎ የተነሳ መንግሥትም አልነበረም። ይህ በኢትዮጵያና በኤርትራ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ቀንድ ህዝቦችን ጨምሮ ከመላው የዓለም ህዝቦች ጋር ባለው ግንኙነት የሚመራበት አስተሳሰብ ለአንዳንዶች በተምኔታዊነት ሊተረጐም ቢችልም፣ በኢህአዴግ የተመራው መንግሥት ገና ከጠዋቱ በጥብቅ ይዞ የተመራበት በጐ እሳቤ ነበር።

መንግሥት በነበረው በዚህ በጐ አስተሳሰብ የተነሳ ከወረራው በፊት ከሌሎች ተጓራባች አገሮች በላቀም ደረጃ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ሰፊ የኢኮኖሚ ግንኙነት ተፈጥሮ ነበር። ሁለቱ አገሮች የራሳቸውን ነጻ የንግድ ሥምምነት ተፈራርመው ምርቶቻቸውን አንዱ በሌላው

ግዛት ከቀረጥ ነጻ ያስተላልፉ ነበር። ከኢትዮጵያ ወደኤርትራ ወይም ከኤርተራ ወደኢተዮጵያ በሚተላለፉ ምርቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር አልነበረም። ይሁንና የኤርትራ መንግሥት ከሚመራበት አስተሳሰብ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ጸጋዎች ካላአግባብ የመጠቀም ዝንባሌው እየሰፋ ሔደ። በሂደት ደግሞ ለአያያዝ አስቸጋሪ መሆን ጀመረ። ያልተበጠሰው የኢኮኖሚ ግንኙነት በፈጠረለት ዕድል በመታገዝ የሰሊጥ፣ የቡና እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ጥቁር ገበያ እንቅስቃሴ ወሰጥ ገባ። ከሦስተኛ አገሮች በኢትዮጵያ በኩል ወደኤርትራ ሊያስተላልፋቸው ያመጣቸውን ከቀረጥ ነጻ ምርቶች በኢትዮጵያ ገበያዎች ማራገፍና መሸጥም ጀመረ። ይህ ዝንባሌ የተሳሳተና የኢትዮጵያ ቀረጥ ከፋይ ነጋዴዎችን የሚገዳ በመሆኑ እንዲያስተካከል ጥረት ቢደረግም ለማስተካከል ግን ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ።

ይህን ተከትሎ በሁለቱ አገሮች ግንኙነት ላይ ልዩነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ፣ አለመግባባቱም እየጠነከረ መሔድ ጀመረ። ከዚህም አልፎ የኤርትራ መንግሥት ሁሉንም የሚዛናዊ አስተሳሰብ መስፈርቶች ጥሶ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ከመፈጸሙ ጥቂት ቀደም ብሎ ጅቡቲ፣ ሱዳንና የመንን ተነኮሰ። ይህም በኢትዮጵያ በኩል የግንኙነቱን ባሕርይ በማሰመልከት ሲነሱ የቆዩትን በርካታ ጥያቄዎች ይበልጥ አጠናከራቸው። ይህም ሆኖ የኤርትራ መንግሥት በአንድ በኩል ከገባበት አጣብቂኝ እንዲወጣ የአስታራቂነት ሚና በመጫወት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከዜሮ ድምር የፖለቲካ አስተሳሰብ ወጥቶ ወደሠለጠነ የአገሮች ግንኙነት እንዲያመራ ለማድረግ የተለያዩ መነሻዎች ማድረግ ተመረጠ። በሐኒሽ ደሴቶች የይገባኛል ጥያቄ በማሳበብ ኤርትራ የመንን በወረረችበት ጊዜ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የወታደራዊ መከላከል ሥምምነቱን ተከትሎ ከኢሳያስ መንግሥት ጋር ከማበድ ይልቅ፣ ለአንደኛው አገር ሳያዳላ በገለልተኝነት መርህ ተመስርቶ የማሸማገል ሚና ተጫወተ።

የኤርትራ መንግሥት ይፈጽማቸው የነበሩት ስህተቶች ተራና ቀላል የስሌት ስህተቶች አልነበሩም። ይልቁንም ከመንግሥቱ መሠረታዊ ባሕርይ የሚመነጩ መሠረታዊ ስህተቶች ነበሩ። በኢሳያስ አፈወርቂ መሪነት ኤርትራ ላይ የተመሠረተው መንግሥት በባሕርይው ነጣቂ (Predator State) ከሚባለው የመንግሥት ዓይነት የሚፈረጅ ነው። በሥልጣኑ ተጠቅሞ የአገሪቱን ሀብት በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ከተንቀሳቀሰው የደርግ መንግሥት የተለየ ባሕርይ አልነበረውም። ይህም ሆኖ በህዝባዊ ሪፈረንደም የተመሠረተች አንዲት ነጻ አገር መንግሥት ነበር። ኤርትራውያን ከመንግሥቱ ወደኢሳያስ አገዛዝ በሪፈረንደም መሸጋገር እስከመረጡ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ይህን ተቀብሎ በሰላም፣ በመልካም ጉርብትና መርሕና በዓለም-አቀፍ ሕግ ተግባሮ ከመኖር የተሻለ አማራጭ አልነበረውም።

ከዚህ በመነሳት በአንድ በኩል የኤርትራ መንግሥት በሌሎች አገሮች ጸጋ ለመበልጸግ የነበረው ሕልም እውን ሊሆን እንደማይችል ለማሳየት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ የዜሮ ድምር አቅጣጫ ይልቅ የጋራ ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበት ገንቢና የተሻለ የግንኙነት ዕድል እንዳለ ለማስገንዘብ መንቀሳቀስ እንዳለበት ታመነበት። የኤርትራ መንግሥት ያሰበው ሳይሳካ በመቅረቱ ከጊዜ ወደጊዜ አፍራሽነቱ እየጎላ በሒድም፣ የአገራችን መንግሥት በበኩሉ የዜሮ ድምር መንገድ መዘጋት ግለት የጋራ ተጠቃሚነት መንገድ አለመከፈት ግለት እንዳልሆነ ለማሳየት ተዘጋጀ። የኤርትራ መንግሥት በመስከረም ወር 1990 ዓ.ም የራሱን መገበያያ ገንዘብ አሳትሞ መጠቀም ከመጀመሩ ጋር ደግሞ ይህን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ መልካም አጋጣሚ ተፈጠረለት።

የኤርትራ መንግሥት የራሱን ገንዘብ ናቅፋ በሚል ስያሜ ሲያትም፣ ኢትዮጵያም ሁለቱ አገሮች በጋራ ይጠቀሙበት የነበረውን የብር ኖት በመቀየር አዲስ የብር ኖት አሳተመች። ይህ ነባሩን የብር ኖት በያዙ ኢትዮጵያውያን እጅ የነበረውን አሮጌ ብር ጨምሮ በማንም እጅ የነበረውን የብር ኖት የሚቀይር ነበር። ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት ብር የያዙ ወገኖች ሁሉ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ወደባንኮች በመሔድ እንዲቀይሩ ሰፋ ያለ ዕድል ከፈተ። በዚህ ወቅት በኤርትራ መንግሥት እጅ እስከ አንድ ቢሊዮን የሚደርስ የብር ኖት ይገኝ እንደነበር የሚገመት ሲሆን፣ በዚሁ ብር ከኢትዮጵያ አምራቾች የፊለገውን ዕቃ ሊገዛበት እንዲችል ዕድል ተሰጠው። ይህም ለፕሬዚዳንቱ በግልጽ ተነገረ። ነገር ግን የኤርትራ መንግሥት ብራችሁን ወስዳችሁ ዶላር ካልሰጣችሁኝ በስተቀር በተሰጠው ዕድል አልጠቀምም አለ። በኢትዮጵያ ብር ላይ "ለአምጭው እንዲከፈል ሕግ ያስገድዳል" የሚለውን ጽሁፍ እያነበበ ባደገ ትውልድ የሚመራው የአገራችን መንግሥት በበኩሉ፣ ዶላር ለመስጠት ባይሻም (ይህ ምናልባትም ከዶላር እጥረት በላይ የኢሳያስ መንግሥት በጥቁር ገበያ የሰበሰበው ዶላር ስላንገበገበው ሊሆን ይችላል) የከፈተውን መልካም ዕድል ተሸቀዳደሞ መዝጋት ደግሞ አልፈለገም።

የኢሳያስ መንግሥት ግን ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ አምራቾች ብቻ ሳይሆን ኤርትራም በጋራ ተጠቃሚ እንድትሆን በተከፈተው በዚህ መልካም ዕድል ሳይጠቀምበት ቀረ። ብሩን አምጥቶ ማንኛውንም ሸቀጥ ከኢትዮጵያ ሊገዛ ቢችል ኖሮ ላመጣው ብር በሸቀጥ መልክ ዋጋውን ባገኘ ነበር። የኢትዮጵያ አምራቾች ደግሞ ምርታቸውን ሸጠው የሚያገኙትን አሮጌ ገንዘብ በአዲሱ ብር በመቀየር ሀብታቸው ሳይጓደል ተጠቃሚዎች በሆኑ ነበር። በትዕቢትና በግብዝነት አስተሳሰብ የተሞላው የኤርትራ መንግሥት ግን አንዱም ወገን ለኪሳራ ሳይዳረግ ሁሉንም አሸናፊ በሚያደርገው በዚህ ዕድል ሊጠቀም አልፈለገም። በዚህ የተነሳ አሮጌው ብር ይሰበሰብበታል ተብሎ የተሰጠው ቀነ-ቀጠሮ እስኪያልፍ በቸልታ በመመልከት በእጁ የነበረውን ገንዘብ ዶግ አመድ አደረገው።

የኤርትራ መንግሥት በአግባቡ ሳይጠቀምበት የቀረው የጋራ ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ዕድል ግን ይህ ብቻ አልነበረም። የቀረበለትን በጎ ምክር ሁሉ በእብሪት እየገፋ መጓዝን ልምድ ያደረገው የኢሳያስ "አባደፋር" መንግሥት ብዙ መልካም ዕድሎችንም አምክኗል። ወደኋላ እንደሚታየው የሠላማዊ መፍትሔ ሀሳብን በተደጋጋሚ አልቀበል ያለው የኢሳያስ መንግሥት ልቦናው ለጋራ ተጠቃሚነት መርሕ ዝግ ሆነና፣ ኤርትራ የነበሯትን ሁለት ወደቦች ያመክነ የእብደት አማራጭም ወስዷል። ይህ እብደት ለኢትዮጵያ እጅግ አመቺ የነበሩትን ሁለቱን ወደቦች 'ወደግመል ውሃ መጠጫነት' ሲቀይር፣ ጅቡቲ ደግሞ ያልታሰበ ሲሳይ ዕድል (Windfall Gain) እንድታገኝ ያስቻለ ነበር። ይህም በ97 ምርጫ ቅንጅቶች አዲስ አበባ ላይ ለኢህአዴግ በተሰጠ የተቃውሞ ድምጽ ያገኙትን ከተማዋን የማስተዳደር ዕድል እንዳባከኑት ማለት ነው። በዚያ የምርጫ ውዝግብ ሰሞን ቅንጅቶች በአዲስ አበባ ማሸነፋቸውን ተከትሎ ከአንድ የውጭ ሚዲያ ጋር ባካሔድኩት ቃለ ምልልስ "ያልተገመተና ያልታሰበ ውጤት እንዳገኙ" በእንግሊዝኛ "Windfall Gain" አገኙ በማለት የሰጠሁትን አስተያየት፣ ሪፖርተር ጋዜጣ "ነፋስ" ሰጣቸው ብሎ በመተርጎም፣ በአንዳንድ የከተማው ነዋሪዎች ዘንድ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲፈጠር ካደረገ በኋላ ይህን ቃል መጠቀም ባልወድም፣ ጅቡቲ በርግጥም ያላሰበችውና ያልገመተችው ዕድል አገኘች። "ነፋስ" ስለሰጣት ሳይሆን፣ ኢሳያስ አፈወርቂ በኩርፊያ ምሳቸውን እራት ለማድረግ ስለመረጡ የተገኘ ያልታሰበና ያልተገመተ ዕድል ነበር።

መንግሥት ቀደም ሲል የታዘበውን የኮንትሮባንድ ዝንባሌ ለመከላከልና በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት መልከ ለማስያዝ በማሰብ ግብይቱ በእዳ ሰነድ /Letter of Credit/ አማካይነት እንዲፈጸምና የምርትና አገልግሎት ልውውጡ ደግሞ በዓለም አቀፍ ገንዘብ እንዲሆን የማድረግ ተጨማሪ ሀሳብ አቅርቦ ነበር። ይህ በማንኛውም ሁለት ነጻ አገሮች መካከል በሚኖር የኢኮኖሚ ግንኙነትና ልውውጥ መደበኛ የሆነው አሠራር ነው። ስለዚህም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ባለው ግንኙነትም መሥራት የሚችልና የሚገባው የግንኙነት ሥርዓት ነበር። ነገር ግን የኤርትራ መንግሥት በእዳ ሰነድና በውጭ ምንዛሪ የመጠቀም አሠራርን ለመቀበል ፈቃደኝነት ገ.ደለው። ከዚህ ይልቅ በአገሮቹ መካከል በብርና ናቅፋ አማካይነት በቀጥታ የመገበያያት ሀሳብ አቀረበ። ነገር ግን ይህ በኢትዮጵያ መንግሥት ተቀባይነት አላገኘም ያገኘ አልነበረም።

መንግሥት ይህን ሀሳብ ያልተቀበለው በአገሮች መካከል ሥምምነትና መተማመን እስካለ ድረስ በየራሳቸው ገንዘብ የምርትና አገልግሎት ልውውጥ ማድረጋቸው ስህተት ስለሆነ አልነበረም። ዛሬ ሩስያና ቻይና ከጠቅላላ ምርቶቻቸው ሰባት በመቶ ያህሉን በሩብልና ዩዋን ይገበያያሉ። ይህም በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሔድ ላይ ነው። ነገር ግን ቻይናና ሩስያ ይህን ማድረግ የቻሉት የሚታወቅ፣ የሚተመንና የፉይናንስ ዲስፕሊን ባላቸው መንግሥታት የሚመራ

ኢኮኖሚ በላላተው ነው፡፡ ኤርተራ እንጓን በ1990ሥቱ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይም ይህን የመሰለ ኢኮኖሚ አልገነባችም፡፡ ከግጭቱ በፊት የነበረው የኤርትራ ኢኮኖሚ የቁማር ወይም የካዚኖ ባህርይ ነበረው፡፡ በኤርትራ ኢኮኖሚ ላይ የሚታየው ቁማር መሰል ባህርይ ከሃያ አምስት የነጻነት ዓመታት ጉዞ በኋላም አልተቀየረም፡፡ አገሪቱ ይህ ነው የሚባል ኢኮኖሚ አላት ለማለት የሚያስደፍር ነገር ባይኖርም፣ ያለችውም ትንሽ ኢኮኖሚ ብትሆን አገሪቱን በሚመሩት ሰዎች በተለይ በመሪያቸው በአቶ ኢሳያስ እጅ ያለች ነች፡፡ ዛሬም ኤርትራ ዓመታዊ የመንግሥትና የአገር በጀት የሚባል ነገር የላትም። የመንግሥት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለፓርላማ ሳይሆን (ለከፋቱ ደግሞ ኤርትራ ፓርላማ የላትም) በፕሬዚዳንቱ የግንቦት16 "የነጻነት ቀን" ንግግር በአደባባይ ለተሰበሰበ ህዝብ ቀርቦ በጭብጨባና በጭፍራ በሚጠቃለልባት አገር፣ መደበኛ ሳይሆን የካዚኖ ኢኮኖሚን ከመገንባት ውጭ ሌላ ዕድል አልነበረም፤ ዛሬም የለም፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ከግምት በማስገባት በወቅቱ በአገር ደረጃ በብርና በናቅፋ ለመገበያየት የቀረበለትን ሀሳብ አልቀበልም ማለቱ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የተገናዘበ እርምጃ ነበር፡፡

የሁለቱ አገሮች የኢኮኖሚ ግንኙነት መልከ እንዲይዝና በዓለም አቀፍ ሕግ የሚመራ እንዲሆን ለማድረግ ከተወሰዱት ከእነዚህ እርምጃዎች በተጨማሪ በኢትዮጵያ በኩል ሌሎች በጐ ሀሳቦችም ተራምደው ነበር፡፡ ከእነዚህ አንዱ በአዋሳኝ ቦታዎች በሚኖሩ የሁለቱ አገሮች ዜጐች መካከል እስከ 2000 ብር/ናቅፋ የሚያወጡ ምርቶችን በቀጥታ እንዲለዋወጡ ዕድል መከፈቱ ነበር፡፡ ይህም በተጐራባች ወረዳዎችና አካባቢዎች የሚገኙ ህዝቦች የእዳ ሰነድ መከፈት ሳያስፈልጋቸው ሊገበያዩና ፍላጐታቸውን ሊያሟሉ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ታስቦ የተከፈተ በር ነው፡፡

በእርግጥም ለዘመናት አብረው የኖሩት ህዝቦች በአገራቱ መካከል የተፈጠረው ዳር ድንበር፡፡ ወይም የመንግሥታት ፍቅርና ኩርፊያ ሳይገድባቸው ዘመን ተሻጋሪ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቁርኝት የፈጠሩ ነበሩና እነዚህን ህዝቦች በእዳ ሰነድ (L/C) ካልተገበያያችሁ በስተቀር አንዳችም ዓይነት የንግድ ግንኙነት አይኖራችሁም ማለት ስህተት ይሆን ነበር፡፡ መንግሥታቱ ቢከለክሏቸው እንኳ የሁለቱ አገሮች ህዝቦች በተጨባጭ መገበያየታቸው አይቀሬ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ሁለቱ ህዝቦች ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በኋላ የተፈጠረው ውጥረት የተሞላበት ድንበር ሳይከልላቸው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነታቸውን ቀጥለውበታል፡፡ የሁለቱ አገሮች ተጐራባች ህዝቦች ሴቶች ወንዝ ሲወርዱ በእንስራ ሞልተው በወሰዱት ጥሬ ዕቃ ቀጥተኛ ልውውጥ እንደሚያደርጉ የሚነገረው እውነት ከሆነ ይህ ሐቅ ብቻ በተጐራባች ህዝቦች መካከል የንግድ ልውውጥን በዓለም አቀፍ ሕግ ብቻ መምራት እንደማይቻልና እንደማይገባ ያሳያል፡፡ የአገራችን መንግሥት "ተጐራባች ህዝቦች የ2000 ብር/ናቅፋ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች በቀጥታ ሊለዋወጡ ይችላሉ" የሚል ምክረ-ሀሳብ ይዞ ሲቀርብ፣ በመንግሥታቱ መካከል ያለው ግንኙነት

ይርገብም ይወጠር በህዝቦች መካከል ያለውን ዘመን ተሻጋሪ ግንኙነት በመልካም አቅጣጫ ለማስቀጠል በማለም ነበር። ይህም ሆኖ እንደሌሎች በጉ ዕድሎች ሁሉ ይህም መልካም ሀሳብ በኤርትራ መንግሥት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።

ከመስከረም 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ግንኙነቱን በአዲስና ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስቀጠል የተደረጉት መከራዎች ሁሉ በኤርትራ መንግሥት ተቀባይነት ካለማግኘታቸው በተጨማሪ በኤርትራ መሪዎች ዘንድ በእልሕና ደም ፍላት የመመራት አስተሳሰብ እየተጠናከረ ሔደ። በአንድ በኩል ወትሮም በሚታወቁበት የወታደራዊ ጀብደኝነት አስተሳሰብ በመመካት፣ በሌላ በኩል በውስጧ ብዙኃነትን በአግባቡ ለማስተናገድ በጀመረችው አዲስ አቅጣጫ የተነሳ ኢትዮጵያ አቅም የላትም ተዳክማለች ብለው በማሰብ የከፋት ሀሳብ ማውጠንጠን ጀመሩ። የኢትዮጵያ መንግሥት ነባር ታጋዮችን ትርጉም ባለው ደረጃ አሰናብቶ ወታደራዊ ኃይሉን በቀነሰበት ወቅት ስምንት ተከታታይ የብሔራዊ ውትድርና ሰልጣኞችን አስመርቀው የሠራዊታቸውን ቁጥር ከፍ ማድረጋቸውም የልብ ልብ እንዲሰማቸው አደረገ። በእነዚህ ከፍተኛ የሥሌት ስህተቶች ላይ በመመሥረት ጦርነትን ብቸኛ የችግር መፍቻ አማራጭ በማድረግ ለወረራም ተዘጋጁ። የአፍሪካ የነጻነት ንቅናቄዎች አባቶች ነን የሚሉት የህዝባዊ ግንባር መሪዎች፣ ተዳከማለች ብለው የገመቷትን ኢትዮጵያ ሲሆን በማስፈራራት እንዲያም ሲል በጦርነት አስገድደን የጥቅማችን አስፈጻሚ ልናደርጋት እንችላለን ብለው አመኑ። አምነውም ከመስከረም ጀምሮ ተከታታይ ትንኮሳዎችን ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ በግንቦት 1990 ዓ.ም. ሙሉ ወረራ አካሔዱ። ከዚያ በኋላ የሆነው ሁሉ ብዙ መጽሐፍት የሚወጣው ሌላ አዲስ ታሪክ ብቻ ነበር።

በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዋዜማና በሂደቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም፣ ለመልካም ጉርብትናና የጋራ ተጠቃሚነት መርሆዎች ከብርና ቅድሚያ በመስጠት መንቀሳቀሱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ነበር ማለት አይቻልም። በኢህአዴግ የተመራው መንግሥት ገና ከጅምሩ ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም በጉ እሳቤ ይዞ የተነሳ ቢሆንም ሰላምና መልካም ጉርብትና በአንድ እጅ በማጨብጨብ ብቻ እውን የማይሆኑ እሴቶች ናቸው። ሰላምና መልካም ጉርብትና የሁለትዮሽ ወይም የበርካታ ተጐራባች አገሮችን መልካም እሳቤና ግንኙነት የግድ የሚሉ እንደሆኑ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ነው። ሌላው ቀርቶ አንደኛው ወገን በጠብ አጫሪነት አስተሳሰብ ሲመራ፣ ለተበላሸ ግንኙነት ጦስ የሆነው ይኸው ወገን ሌላውንም ጐትቶ ወደስህተት ሊያስገባው የሚችልበት ዕድል ትንሽ አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ ራሱ ጤናማው ወገን አንድም ለጊዜው በሚይዛቸው የተሳሳቱ ሀሳቦች፣ ወይም ደግሞ በሂደት ራሱን ለልዩ ልዩ የተሳሳቱ ዝንባሌዎች ግፊት ሲያጋልጥ ስህተቶች ሊፈፅም ይችላል። ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያ መንግሥት በኢትዮ-ኤርትራ ግንኙነት ሂደት ምሉእ በኩልሔ ነበር ማለት አይቻልም። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዝርዝር ጥናት ሊካሔድና ተገቢው ትምሕርት ሊቀሰምበት የሚችልና የሚገባ

መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የራሱ ስህተቶች እንደነበሩት ለመካድ አይቻልም::

የጦርነቱ ጀማሪ የኤርትራ መንግሥት ነበር:: በእብሪት ተነሳስቶ በሠላም ላይ አሻፈረኝ ያለውም እርሱ ነው:: በመሆኑም የግጭቱ መሠረታዊ ጠንቅ የኢሳያስ መንግሥትብቻ መሆኑ ፈጽሞ አያጠያይቅም:: የኢትዮጵያ መንግሥት ተጠቂና ተከላካይ ነበር:: ከጥቂት አጋጣሚዎች በመለስ ችግሩ ሠላማዊ መፍትሔ ያገኝ ዘንድ በመርህ ላይ የተመሠረተ ጽኑ አቋም የወሰደ መንግሥት ስለነበር ከወረራው ራሱን መከላከሉ ተገቢና ፍትሃዊ ነበር:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ በገፍ የተባረሩበት ሂደት፣ በተለይ ኢህአዴግን ለመሰለ ህዝባዊ ድርጅትና በእርሱ ለሚመራው መንግሥት ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው ስህተት ነበር:: በእርግጥ ለኢትዮጵያ የጸጥታ ሥጋት የሆኑ ኤርትራውያን ከአገር እንዲወጡ መደረጉ ተገቢና አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም:: ይህም ሲሆን "በደረቅ አበሳ እርጥብ ይነዳል" በሚባለው መልክ መሆን አልነበረበትም:: በመሆኑም ይህ የጅምላ እርምጃ ብዙ ንፁኃን ሰዎች ካለ አበሳቸው የተሰቃዩበት ነበር::

የኤርትራ መንግሥት ገና ከ1983 ዓ.ም. ክረምት ጀምሮ ኢትዮጵያውያንን ከኤርትራ ማባረሩ፣ እንደገናም ከጦርነቱ በፊት ይህንኑ ግፍ እያሰለሰ ሲፈጽመው መቆየቱ፣ በመጨረሻ ደግሞ በጦርነቱ ወቅት ልማዳዊ ግፉን አጠናክሮ መቀጠሉ፣ በኢህአዴግ በኩል የተፈጸመውን የመርሕ ስህተት አሳንሶ ለመመልከት ምክንያት ሊሆን አይችልም:: የኤርትራ መንግሥት በተፈጥሮው ህዝብን የሚያከብር ባለመሆኑ የሰራው ይህ ስህተት ከእርሱ የማይጠበቅ አልነበረም:: ዘርና ብሔር ሳይለይ ለህዝብ ልዩ አክብሮት ላለው ኢህአዴግ ደግሞ ይህ ስህተት ፈጽሞ የሚጠበቅ አልነበረም:: ያም ሆነ ይህ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ኢትዮጵያ በወሳኝነት የራሷ ባልሆነ ስህተት በላይዋ ላይ የተጫነባት ግጭት ስለነበር የአዲሱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ችግር የቆሰቆሰው አልነበረም:: ጦርነቱ እንደማንኛውም ግጭት አስከፊና አሳዛኝ ደም መፋሰስ ያስከተለ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ በኩል ከሥርዓቱ መሠረታዊ ባህርይ ጋር አንዳችም ተያያዥነት ያልነበረው ፍትሃዊ የመከላከል ጦርነት ነበር:: ይህም ሆኖ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት የራሱን ከባድ ዋጋ ያስከፈለ ቢሆንም፣ በሩብ ምእተ-ዓመት ውስጥ ለሁለት ዓመታት ብቻ የተካሔደና አገሪቱ ከዘመናት የጦርነት ሂደት የመላቀቋን እውነታ የማይቀይር አንዱ የግጭትና የከባድ ጦርነት አጋጣሚ ነበር::

አልሸባብ የደቀነው ተጨባጭ አደጋና አመካከቱ፣

ኢትዮጵያ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ለሁለተኛ ጊዜ ግጭት ውስጥ የገባችው የአልሸባብን አደጋ ለመመከት ወደሶማሊያ በገባችበት ጊዜ ነበር:: ይህ ጦርነት ከሞላ ጐደል ከተሃድሶ እንቅስቃሴ በኋላ በነበረው ክልል የሚጠቃለል ሲሆን ሥረ-መሠረቱ ግን በሶማሊያ

የከሸፈ መንግሥት ከታየበት ጊዜ ጀምሮ የሚመዘዝ ነበር። በሶማሊያ ከዚያድ ባሬ ውድቀት በኋላ የተማከለ መንግሥት የሚባል ነገር ጠፍቶ፣ አገሪቱ ውሉ በማይታወቅ የእርስ በእርስ ጦርነት ስትታመስ ቆይታለች። ይህም መጀመሪያ ላይ ለልዩ ልዩ የጦር አበጋዞች መነሳት ዕድል የከፈተ ነበር። ህዝቡ የጦር አበጋዞችን የግፍ አገዛዝ እየጠላው ሲሔድ ደግሞ በሃይማኖት ሽፋን ለተቀሰቀሱ ጽንፈኛ ንቅናቄዎች የተመቸ ሁኔታ ተፈጠረ።

ይህ ሁኔታ ከመስከረም አንዱ የአሜሪካ የሽብር ጥቃት በኋላ ይበልጥ የተባባሰ ነበር። መነሻቸውን መካከለኛው ምሥራቅ ያደረጉ የጥፋት ንቅናቄዎች በታሊባን መንግሥት ማዕከልነት ከመሸጉባት አፍጋኒስታን በአሜሪካ መራሹ የኔቶ ጥቃት ተበታትነው ካፈገፈጉ በኋላ የተከተሉት አማራጭ መንግሥት አልባዋን ሶማሊያ አዲስ መናኸሪያ ማድረግ ነበር። በዚህ የተነሳ አገሪቱ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከሰሜን አፍሪካና ከጐረቤታችን ሱዳን በተመሙ አክራሪዎች ተወረረች። በሶማሊያ ረዘም ላሉ ዓመታት የሃይማኖት አክራሪነትን በእምነት ቦታዎችና ትምሕርት ቤቶች ሲሰብኩ ከቆዩት አገር-በቀል አክራሪዎች ጋር እጅና ጓንት ሆነው መሥራት ጀመሩ። የማታ ማታ ደግሞ እነዚህ የጥፋት ኃይሎች፣ "እስላማዊ ሕብረት" በሚል ስያሜ ተደራጅተው የጦር አበጋዞችን በማጥቃት ሞቃዲሾ ከተማና አካባቢዋን ለመቆጣጠር በቁ። ይህ ጽንፈኛ ቡድን ራሱን "እስላማዊ" በሚል ቅጽል ቢሸፍንም በእስልምና እምነት ተከታይነቱ የሚታወቀውንና የሚኮራውን የሶማሊያ ህዝብ እንዲሁም እንደማንኛውም ሌላ ሃይማኖት ለሰላም የሚቆመውን እስልምና በሽፋንነት ከመጠቀም አልፎ ከእምነቱ ጋር የሚያያዝ መጻረታዊ ቀኖናዊ ይዘት አልነበረውም። የለየለት የፖለቲካ ንቅናቄ ነበርና። ያም ሆነ ይህ ይህ ጽንፈኛ ኃይል በመንግሥት አልባዋ ሶማሊያ መስፋፋቱ ለዓለም አቀፍ ሙጃሂዲኖች ይበልጥ የተመቸ ሁኔታ ፈጠረ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሕብረቱ ኃይሎች ከአልቃይዳና አልሸባብ ጋር እጅና ጓንት በሆነ ጥምረት በሶማሊያ የሃይማኖት አክራሪነትን ማስፋፋት ተያያዙት። ሕይወትን ቀለል አድርጐ መመልከት የሚቀናውና በባሕርይው ለአክራሪ አስተሳሰብ ብዙም ተጋላጭ ያልነበረው የሶማሊያ ህዝብ ቀስ በቀስ ለእነዚህ የጥፋት ኃይሎች አክራሪ አስተሳሰብ መጋለጥ ጀመረ። በከሸፉ መንግሥታት ማዕቀፍ እንደሚፈጠረውና ለከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ እንደሚጋለጠው ማንኛውም ህዝብ ሶማሊያውያንም የጦር አበጋዞችን የግፍ አገዛዝ የሚያስቀር መስሎ በቀረበው ጽንፈኛ ንቅናቄ መማለል ጀመሩ። ሕብረቱ ለተወሰነ ጊዜ ሌቦችን እያሳደደ በመቅጣት በሶማሊያ ሕግና ሥርዓትን የሚያሰፍን መስሎ ታየ። በጦር አበጋዞች ሥርዓተ-አልበኝነት የተማረረው ህዝብም ቀስ በቀስ ድጋፉን ለገሰለት። ነገር ግን "ጅብ እስኪይዝ ያነክሳል" እንዲሉ የሕብረቱ ጽንፈኛ አስተሳሰብና ድርጊቶቹ ክተደበቁበት ቀና እስኪሉ ብዙ ጊዜ አልወሰደም።

በዚህ የተነሳ ሕብረቱ ብዙም ሳይቆይ በሶማሊያ በሸሪዓ ሥም ግፈኛ አገዛዝን ማስፈን ጀመረ፡፡ ለዘብተኛ ባሕል ባለው የሶማሊያ ሕብረተሰብ ላይ ጨካኝ (Draconian) ሕግጋትን እስከመጫን ደረሰ፡፡ በሕብረቱ ቀጭን ትዕዛዝ ሲኒማ ቤቶች ተዘጉ፡፡ የስፖርት ፊልሞች ማየት ሓራም ተባለ፡፡ እነዚህ ያነሱ ይመስል ሰዎችን በአደባባይ መግረፍ፣ እንዲያም ሲል እጅ መቁረጥ ተስፋፋ፡፡ በሶማሊያውያን ላይ በሃይማኖት ሽፋን ዘግናኝ ቅጣቶች ተበራከቱ፡፡ እነዚህ የግፍ እርምጃዎች ድሮም በከባድ ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ በከረመው የሶማሊያ ህዝብ ዘንድ ይበልጥ ውጥረትና ፍርሀትን አነገሡ፡፡ ሕብረቱና የእርሱም ወታደራዊ ክንፍ የሆነው አልሸባብ፣ ህዝቡ በፍርሀት ስለተዋጠ ብቻ ያመነና የደገፉቸው እንደሆነ አድርገው መቁጠር ጀመሩ፡፡ ከመቁጠርም አልፈው በመላው አፍሪካ "ጅሐዳዊ" ብለው የሠየሙትን መንግሥት እንደሚመሠርቱ፣ ኢትዮጵያም የመጀመሪያዋ ሠለባቸው እንደምትሆን አወጁ፡፡

በሶማሊያ የተፈጠረው አክራሪነት በኢትዮጵያ ላይ ይህን የመሰለ ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ ከመደቀኑ በርካታ ዓመታት በፊት ጀምሮ ኢትዮጵያ ሶማሊያን ወደተረጋጋ አገርና የመንግሥት ባለቤትነት ለመመለስ ያላደረገችው ጥረት አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያና ሶማሊያ በንጉሡና በደርግ መንግሥታት ዘመን በተደጋጋሚ ጦርነቶች የተዋጉ አገሮች ነበሩ፡፡ የሶማሊያ መንግሥት ከአንድም ሁለት ጊዜ ኢትዮጵያን ወርሮ ነበር፡፡ የደርግ መንግሥት በበኩሉም በአንድ ወቅት ወደ ሶማሊያ ግዛት ዘልቆ ገብቶ የራሱን ወረራ ፈጽሞ ነበር፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ የተመሠረተው አዲሱ መንግሥት በቀረጸው አዲስ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና መርሕ መሠረት ሶማሊያን ጨምሮ ከሁሉም ጎረቤት አገሮች ጋር መልካም ጉርብትና ለመፍጠርና ለትብብር ግንኙነት ከፍተኛ ፍላጐት ነበረው፡፡ ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያ ሶማልያን ወደተረጋጋ ሁኔታ ለመመለስ በጣም ብዙ ተደጋጋሚ ሙከራዎችን አድርጋለች፡፡ እነዚህ ጥረቶች የተደረጉት የሶማሊያን ብሔራዊ ጥቅም ብቻ ታሳቢ በማድረግ ነበር፡፡ በከሰመ መንግሥት ሥር ለአስከፊ የእርስ በእርስ ግጭት በተዳረገችው ሶማሊያ ባለፉት በርካታ ዓመታት የአገሪቱና የህዝቦቿ ብሔራዊ ጥቅም ሆኖ የቆየው አገሪቱ ተረጋግታ ጤናማና የሚሠራ መንግሥታዊ አስተዳደር ባለቤት ለመሆን መቻሏ ነው፡፡ በእርግጥ የአንድን አገር ብሔራዊ ጥቅም ከራሱ ህዝብ በላይ የሚያውቅለት ማንም ሌላ ውጫዊ ኃይል እንደሌለ የማያከራክር ቢሆንም፣ ከሶማሊያ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የአገሪቱ የወቅቱ ብሔራዊ ጥቅም ሰላም፣ መረጋጋትና ከከሰመ መንግሥት ወደመደበኛ አገርና መንግሥት መሸጋገር መሆኑ የሚያከራክር አልነበረም፡፡

ኢትዮጵያ ከዚህ በመነሳት ሶማሊያውያን ለተረጋጋ አገርና የጸና መንግሥታዊ አስተዳደር እንዲበቁ ያልተቆጠበ ጥረት አድርጋለች። በዚህም ከልል በራሳቸው ጥቅምና ፍላጐት እየተመሩ አገራቸውን ባሻቸው መንገድ ለመገንባት ያላቸውን ጽኑ ፍላጐት በማከበር ለዚህ እውን

መሆን ተንቀሳቅሳለች:: ነገር ግን ሶማልያን ከህዝቦቿ መብትና ጥቅም በመነሳት ለማገዝ የሚሹ እንደኢትዮጵያ ዓይነት አገሮች ጥቂት ብቻ ነበሩ:: በአንጻሩ ያልተበከለውን የአገሪቱ የባሕር ዳርቻ የኑክሌር ዝቃጭ ማራገፊያ ከማድረግ ፍላጐት ጀምሮ፣ የባሕር ላይ ውንብድናን የመከላከል አጀንዳ አለን በማለት የራሳቸውን ጥቅም መነሻ አድርገው በሶማሊያ ጣልቃ የሚገቡ የቅርብና የሩቅ አገሮችና ተቋማት ደግሞ ብዙ ነበሩ፣ ዛሬም ናቸው:: የመብዛታቸውን ያህል ደግሞ ችግሩን ለመፍታት የሚወሰዱ ጅምር ተነሳሽነቶችና ውድቀቱም ያንኑ ያህል ብዙ ነበር:: ብዙ የውጭ ኃይሎች በመረጡት የተሳሳተ ጣልቃ ገብነት ምክንያት በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ቀን አሳቢዎች የተጀማመሩ መልካም ጥረቶች ሁሉ ዳር ሳይደርሱ የመክሸፍ ጽዋ ደርሶባቸዋል። በዚያው ልክ ደግሞ የአገሪቱ ትርምስና የሶማሊያውያን ሥቃይ ተራዝሟል::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በሶማሊያ የተፈጠረው የመንግሥት መክሰምና ሥርዓተ-አልበኝነት የሶማሊያውያንና የኢትዮጵያ ሰላማዊ ፍላጐት እውን እንዳይሆን እንቅፋት ሆነ:: የማታ ማታ ደግሞ በሶማሊያ የመንግሥት መክሰም ለጽንፈኛና አክራሪ ኃይሎች ልዕልና የተመቸ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር ኢትዮጵያን ለባሰ አደጋ ማጋለጥ ጀመረ:: በሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት ለመፍጠር የተደረጉ ሙከራዎች ሁሉ በከሸፉ ቁጥር ተስፋ መቁረጡ እየባሰ፣ ይህም እንደገና ጽንፈኝነቱን እያስፋፋው አልሸባብና ኢትዮጵያን ያፋጠጠው ተጨባጭና ወቅታዊ አደጋ ሊፈጠር ቢቻ:: ይህ አደጋ አልሸባብና የበላይ ጠባቂው የነበረው "እስላማዊ" ሕብረት በኢትዮጵያ ላይ ግልጽ ጥቃት ለመሰንዘር እንደተዘጋጁ ባወጁ ጊዜ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው እስከመሆን ደረሰ::

ጽንፈኞቹ ኃይሎች ከዚህ ይፋ የጦርነት አዋጅ ጐን በሁለቱ አገሮች አዋሳኝ ቦታዎች የጦር መሣሪያና የሰው ኃይል እያሰረጉ ማሰማራትን ሥራዬ ብለው ሲያያዙት፣ በኢትዮጵያ ፊት የተደቀነው ተጨባጭና ወቅታዊ አደጋ እየተበባሰ ሔደ:: በመሆኑም ኢትዮጵያ በአንድ በኩል አገራዊ ደኅንነቷን ለማስጠበቅ በመሻት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወንድም ለሆነው የሶማሊያ ህዝብ ክልብ በማሰብና በማዘን አገሪቱን ወደመረጋጋት ለመመለስ የሚያግዝ እርምጃ ለመውሰድ ተገደደች:: ቀደም ሲል በጠላትነት ይፈላለጉ በነበሩ በብዙ አገሮች አንዱ ችግር ላይ ሲወድቅ እንዳያንሰራራ አድርጐ መድፈቅ የተለመደ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ከዚህ ኋላቀር ልማዳዊ የመበቃቀል አዙሪት የወጣ እንቅስቃሴ ለማካሔድ ቁርጠኛ አቋም ላይ ደረሰ::

አልሸባብ በኢትዮጵያ ላይ የደቀነው ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ አሳሳቢ እየሆነ በመጣ ጊዜ ጉዳዩ በይፋ ተነስቶ በቅድሚያ ለአገሪቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለውይይት እንዲቀርብ ተደረገ:: ይህም በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት መሠረት ጦርነትን የማወጅ ሥልጣን የአስፈጻሚው ሳይሆን የህዝብ ተወካዮች የመሆኑን ጥልቅ ዴሞክራሲያዊ መርሕ የተከተለና በእርሱም መገዛትን የሚያሳይ ነበር። በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት

የተዋቀረው የወቀቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የሞቀ ክርክር አካሔደበት። በዚህ መድረክ አንዳንድ ተቃዋሚዎች "ጦርነቱ ህዝቡን ከውስጣዊ አጀንዳ ለማራቅ ሲባል የተቀየሰ በመሆኑ የአልሸባብን አደጋ ሶማሊያ ድረስ ገብተን ማምከን የለብንም" ሲሉ፣ ገዥው ፓርቲ ደግሞ "ጉዳዩ በአገራቱ ላይ ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ የደቀነ ሆኗልና ወደሶማሊያ ዘልቀንም ቢሆን ልናመክነው ይገባናል" ብሎ ተሟገተ።

በክርክሩ ሂደት አንዳንዶች ወደሶማሊያ የመግባቱን ጉዳይ የአሜሪካኖችን አጀንዳ ለማስፈጸም ከሚደረግ ጥረት ጋር አያይዘው አቅርበውትም ነበር። አሜሪካኖች በመጀመሪያው የባሕረ ሰላጤ ጦርነት የሳዳምን ጦር አደባይተው እዚህ በአቅራቢያቸን በመሸጉ ሰሞን በሶማሊያ የተፈጠረውን ሰብዓዊ ቀውስ ለማስወገድ በሚል ምክንያት ሠራዊታቸውን ወደሞቃዲሾ አሰማርተው ነበር። ይሁንና ወደሶማሊያ ዘልቀው በመግባት ተልዕኮዋቸውን ለመፈጸም በሞከሩ ጊዜ በታጣቂዎች የተሰነዘረባቸውን ጥቃት መቋቋም ተስኖዋቸው ከብረ-ነክ በሆነ መንገድ ሊያፈገፍጉና እጃቸውን ሊሰበስቡ ተገደውም ነበር። ከዚህ በመነሳት በሌላ ቦታ ያደርጉታል እንደሚባለው በአፍሪካ ቀንድም እነርሱ ሊሠሩት የማይፈልጉትን "አስቀያሚ ሥራ" ሌላ አገር እንዲሠራላቸው ይፈልጋሉ ተብሎ ይወራ ነበር። ይህን ወሬ የሰሙ አንዳንድ የፓርላማ አባላት አንዳቸውም ማስረጃ ባይኖራቸውም፣ ወደሶማሊያ በመግባት አልሸባብን የማስታገስ ተልዕኮ ኢትዮጵያ በቅጥረኝነት ልትሰማራ ስለተዘጋጀች የመጣ አድርገውም ተከራከሩ። በተጨማሪም በሶማሊያ የሚካሔድ ጣልቃ ገብነት ኢትዮጵያ በማትወጣው ረግረግ ውስጥ እንድትሰጥም የሚያደርጋት መሆኑ አይቀርም አሉ። ሶማሊያን የውክልና ጦርነት (Proxy War) የሚካሔድባት አገር የማድረግ ፍላጎት የነበራቸውና ጉዳዩን ከርቀት ሆነው እንደራሳቸው አጀንዳ ይከታተሉት የነበሩት የኤርትራው መሪም ልክ እንደአገራችን አንዳንድ ተቃዋሚዎች በሙሉ ልብ "ኢትዮጵያ የማትወጣው አረንቋ ውስጥ ትገባለች" ብለው እስከመተንበይ ደረሱ።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመከላከል ጦርነቱን አስፈላጊነት በድምጽ ብልጫ ካሳለፈና ሠራዊቱ ተልዕኮውን መፈፀም ሲጀምር አስቀድመው የተነገሩት ትንቢቶችና ሟርቶች ሁሉ ግን አልያዙም። ኢትዮጵያ ሠራዊቷን ባሰማራች በጥቂት ቀናት ውስጥ የአከራሪዎች ሕብረትና አልሸባብ ከሞቃዲሾ ብቻ ሳይሆን ከመካከለኛውና አብዛኛው መሬት ተጠራርገው በደቡብ ሶማሊያ ጫፍ በሚገኙ ጫካዎች ሊደበቁ ተገደዱ። ሰላም ወዳድ ሶማሊያውያን በዲሲፕሊኑ የሚታወቀውን የኢትዮጵያ ህዝባዊ ሠራዊት እንደአብራካቸው ክፋይ ተቀበሉት። በሶማሊያ አዲስ የተስፋ ዘመን ተበሰረ። ኢትዮጵያ በሠራዊቷና ዲፕሎማቶቿ የተቀናጀ ጥረት፣ ሰላም ወዳድ ሶማሊያውያንን ያሳተፈ የሽግግር መንግሥት ሊመሠርቱ ቻሉ። የአልሸባብ ኃይል ከተመከተና ከሶማሊያ በኩል ተደቅኖ የነበረው ወቅታዊና ተጨባጭ አደጋ ከመከነ በኋላ፣

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በአረንቋነት ከተገመተቸው ሳይሆን፣ በተነጻጻሪ መረጋጋት ከጀመረችው ሶማሊያ ከነሙሉ ኩብሩ በሥርዓት ተመለሰ፡፡ በሶማሊያ የኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ በከባድ ሽንፈት ከተደመደመው የአሜሪካኖች ዕጣ ፋንታ የተለየ እንደሆነ በዚህ አኩሪ ሥራ ለማረጋገጥ ተቻለ፡

አሜሪካኖች ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ለመንግሥት "ወደሶማሊያ መግባት ይቅርባችሁ" የሚል ምክር ሰጥተው ነበር፡፡ መነሻቸው ምናልባት ዕጣ ፋንታችሁ ከእኛ የተለየ ላይሆን ይችላል የሚል ሥጋት ሊሆን ይችላል፡፡ በጦርነቱ ባይሳተፉም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ድሉን እያጣጣመ በነበረባቸው የመጨረሻዎቹ ቀናት ግን እነርሱም የራሳቸውን አንድ ውጊያ አካሔዱ፡፡ በራሳቸው እቅድ የተመራች አንዲት ጦርነትም ልትባል ትችላለች፡፡ ከፊትም ከኋላም ሌሎች ብዙ ውጊያዎች ያልነበሯት ጦርነት፡፡ ደግሞስ ጦርነት በአንድ ቀን ተጀምሮ በዚያው ቀን መጠናቀቅ አይችልም ያለው ማነው? ታላቁ የአድዋ ጦርነትስ በአንድ ቀን አይደል የተጠናቀቀው፡፡ ኢትዮጵያ የራሷን ጦርነት በብዙ ትንንሽ ውጊያዎች በፈጸመችባቸው በመጨረሻዎቹ ቀናት አሜሪካኖቹ ከየትኛው ወታደራዊ ሰፈራቸው እንደተነሳ ሳያሳውቁ በተመናመነው የአልሸባብ ጦር ላይ የአውሮፕላን ድብደባ አካሔዱ፡፡ ነገርየው ደመና ባልከበደበት የጠራ ሰማይ ላይ፣ ከየት መጣ የማይባል ነገ•ድ•ድና የብራ ሙበረቅ ዓይነት ነበር፡፡

ይህ በአንዳንዶች ዘንድ "እንደጠበቅነው ኢትዮጵያ የአሜሪካ ጉዳይ አስፈጻሚ መሆኗ ተረጋገጠ" ለማለት ቢያገለግልም፣ ብዙ ኢትዮጵያውያን ግን የሞተን ደግሞ እንደመግደል አድርገው የቆጠሩት ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ ያኔ የአገራችን ፓርላማ ከተቃዋሚዎች ጋር በሚካሔድ ክርክር ይደምቅ በነበረበት ወቅት፣ ስለአሜሪካኖች ተሳትፎና መጠነ-ሰፊ እርዳታ ከአንድ የተቃዋሚ ተወካይ ለመለስ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር፡፡ ለዚህ የስላቅ ጥያቄ የለበጣ መልስ የሰጠው መለስ፣ ከአሜሪካኖች ለጦርነቱ የተሰጠን ድጋፍ እንደሌለ፣ አሜሪካኖች የሚሰጡት እርዳታ በአብዛኛው የእህል፣ የመድኃኒት፣ የኮንዶምና የመሳሰሉ ብቻ እንደሆነ፣ አልሸባብን ደግሞ በጠብመንጃ እንጅ... ብሎ ገና ንግግሩን ሳይጨርሰው የፓርላማው አባላት ብቻ ሳይሆኑ መለስን በቴሌቪዥን መስኮቶች የሚመለከተውም ህዝብ በሳቅ ፈረሱ። ይህም አጋጣሚ ኢትዮጵያ በሶማሊያ ጣልቃ የገባችው በራሷ ሉዓላዊ ጥቅሞች ምክንያት ብቻ እንደነበር በግያዳግም ሁኔታ በግስረገጥ የአጀንዳው መቋጫ ሆነ፡፡

"ትንቢተኛው" ኢሳያስና የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች "ኢትዮጵያ በገባችበት የሶማሊያ አረንቋ ተዘፍቃ ትቀራለች" በማለት ያቀረቡት የጥንቆላ ሀሳብ ይሰምር ዘንድ በመጸለይ ሳይወሰኑ፣ በተለይ ኢሳያስ በአሰብ በኩል ጦራቸውን ወደኢትዮጵያ ማስጠጋታቸው በይፋ የሚታወቅ ጉዳይ ነበር፡፡ መለስ እንደገና ብዙ ተቃዋሚዎች 'መከፈል አይቀርም' ብለው

በጠበቁት ሁለተኛ ግንባር፣ እንኳን ጦርነት ሊከፈት አንዲትም ጣት ያንቀሳቀሰ እንዳልተመለከተ ለፓርላማው አብራራ፡፡ ነገርየው ነጋ ጠባ "መሬታችን በሌላ ተይዞ ገዘም ብለን አንመለከትም" እያሉ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት የሰላማዊ ድርድር የመፍትሐ ሀሳብን አሻፈረኝ ላሉት የኤርትራ መሪ፣ "ምነዋ በሌላ ግንባር በተወጠርንበት በዚህ ወቅት ጣትዎን እንኳ አላንቀሳቀሱም" የሚል የስላቅ ቅላጼና መልእክት እንደነበረው ለተገነዘቡት የፓርላማ አባላት አገላለፁ እንደተለመደው ሌላ የሳቅ ምንጭ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ፣ የሠለጠነ ተቃዋሚና የመቻቻል ፖለቲካ ለአገሪቱ ጌጥ ብቻ ሳይሆን አማራጭ እንዳልነበር በተጨባጭ ባረጋገጥንበት በዚያው ወቅት፣ የነበሩት ተቃዋሚዎች ከነውሰንነታቸውም ሆነው ቢያንስ ኢህአዴግ ሀሳቡን ይበልጥ እንዲያብራራ ዕድል ከፋች ነበሩ፡፡ ከፍ ሲል ደግሞ ፓርላማውን የመድበለ ፓርቲ መልክ ያላበሱት ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ አገርን ከጥቃት የመከላከል ተልዕኮ ተሸከሞ በተሰማራበት ሁሉ ባሰበውና ባቀደው ልክ ውጤታማ መሆን እንደሚችል ያስመሰከረው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ብዙም ሳይቆይ ከነሙሉ ክብሩ ወደእናት አገሩ ተመለሰ፡፡ ለዚያውም አረንቋ የሚባል ነገር ተብትቦ ሳያስቀረው **ብቻ** ሳይሆን በተወሰነ ደረጃ አረንቋውን በማድረቅ ጭምር፡፡

ልክ እንደኤርትራ ጦርነት ሁሉ፣ የሶማሊያው ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ የተጫነና ኢትዮጵያ እንደገና በአሸናፊነት የወጣችበት ነበር፡፡ በተጨማሪም ሶማሊያን ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ወደተረጋጋ መንግሥት ለመመለስ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የተፈጠረበት ወይም ለዚህ ሥራ መሠረቱ የተጣለበት ነበር፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ሁለቱም ጦርነቶች ከቦር መስዋዕትነት የተከፈለባቸው ቢሆኑም፣ ኢትዮጵያ በአሸናፊነት የወጣችባቸውና የአፍሪካ ቀንድን ለተሻለ መረጋጋት ማብቃት እንደሚቻል ያመላከተችባቸው ነበሩ፡፡ ይህም ሆኖ በሁለቱ ጦርነቶች መካከል የጊዜ ልዩነት ነበር፡፡

የሶማሊያው ጦርነት ከተሃድሶ በኋላ የተከናወነ ሲሆን የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ግን ከተሐድሶ ንቅናቄ በፊት የተካሔደ ነበር፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ ግጭት በኢትዮጵያ የአዲስ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ላይ የተደቀኑት ፈተናዎች ለመለየትና ለማሳየት፣ ምናልባትም የውስጥ ተጋላጭነትና ዝቅጠቱ ምን ያህል ሥርዓቱን በከባድ ሁናቴ መፈታተን እንደጀመሩ ለማመላከት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረከተ ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተወሰነ መረጃ ማቅረብ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዋዜማ፣ ሂደትና ማግስት በድርጅትና በሥርዓቱ ደረጃ ማቆጥቆጥ ጀምሮ የነበረውንና በወቅቱ "የቦና ፓርስቲስታዊ ወይም ጥገኛ ዝቅጠት" በመባል የተሰየመውን አደጋ አነሳስና ዕድገት እንዲሁም የተሃድሶ እንቅስቃሴውን አጀማመርና ሂደት በተሻለ ደረጃ ለመገንዘብ ዕድል ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የኢትዮ-ኤርትራን ጦርነት እንደገና ለየት ካለ የመረጃ አቅጣጫ በመነሳት በተወሰነ ደረጃ መዳሰስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ምዕራፍ አምስት

በስኬትና ፈተናዎች የተሞሉት የመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት . . .፤

"አብዮታውያን ብዙ ህገዞባዊ ትግሎችን ከሰለበው ንፁህ - ተአማኒ - ሙሰኛ - የነሸፈ ንቅናቄ የመሆን ዑደት (Clean-legitimate-Corrupt-Demise Cycle) ለማምለጥ ይችላሉ። በበኩላችን ይህን በታሪክ ተደጋግሞ የታዬ ዑደት ለመስበር የሚያስችለንን መንገድ አግኝተናል። ይህም የዴሞክራሲ መንገድ ነው። ህዝቦች መንግሥትን በመቆጣጠር ሲሳተፉ፣ መንግሥት ታታሪና ከሙሰና የጸዳ ይሆናል። ሁሉም ሰው ሲሳተፍ ብቻም ሥርዓቱ ቀጣይነት ይኖረዋል።"

ማኦ ዜዶንግ

አዲሱ መንግሥት ሥልጣን ላይ በቆየባቸው በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት በኢትዮጵያ የመጪውን ዘመን ዕድል የሚወስኑ እጅግ በርካታ መሠረታዊ እርምጃዎች ተወስደዋል። በፖለቲካው መስክ ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል መሠረተ-ሰፊ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲ ለማስፈን መቻሉ፣ በብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሉዓላዊነት ላይ የተመሠረተ ፌዴራላዊ ሥርዓትና አዳዲስ የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ መጀመሩ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ብዙኅነትን የሚያከብር፣ በህዝብ ንቁና የተደራጀ ተሳትፎ ላይ የተገነባ አገራዊ የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካ መጀመሩ ዋና ዋናዎቹ ስኬቶች ነበሩ። እነዚህ በውስጣቸው ብዙ መለስተኛ ባሕርይ ያላቸውን ለውጦች የያዙ ናቸው። በኢኮኖሚና ማኅበራዊ መስክም መሠረታዊ ለውጦች የሚመዘገቡበት መሠረት ተጥሏል። በሌሎች አገሮች የተፈጠረው ምስቅልቅል በኢትዮጵያ ሳይደገም ከእዝ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ ለመሸጋገር ተችሏል። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የህዝብ ሀብት ሆኖ አርሶ መጠቀም ለሚፈልግ ዜጋ በነጻ የሚዳረስበት ሥርዓት ተበጅቷል። ኢኮኖሚው ከገበያ አከራሪዎች ምክርና መመሪያ ባሻገር በልማታዊ ቅኝት ሊገነባ የሚችልበት መሠረት ተጥሏል። ለአገር ዕድገትና ለህዝብ ተጠቃሚነት የሚያበቃ ይዘት ያላቸው የትምሕርትና የጤና ፖሊሲዎች ተቀርጸው ተግባራዊ መሆን ጀምረዋል። የሴቶች እኩልነት ሕጋዊ ዋስትና አግኝቶ በተግባርም ሰፊና ጠቃሚ እርምጃዎች ተወስደዋል። የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በአዲስ ቅኝትና ይዘት የአገሪቱን ወዳጆች ማበራከት ጀምሯል።

እነዚህ እንደተጠበቁ ሆኖ ግን በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ከተመዘገቡት መልካም ውጤቶች ጐን ለጐን የሚታዩ ችግሮችና በሥርዓቱ ላይ ያንዣበቡ ልዩ ልዩ ፈተናዎችም ነበሩ። እነዚህ ፈተናዎች በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ ብቻ የማይወሰኑ፣ ይልቁንም በተግባር ጭምር የሚከሰቱ

ፈተናሦት ነበሩ፡፡ አልፎ ተርፎም ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሁለትና ሦስት ዓመታት ቀደም ብሎ የዕድገት መገታት ምልክቶች እንዲታዩ እስከማድረግ የደረሱ ነበሩ፡፡ የዕድገት መገታት ችግሩ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ተባብሶ ከመቀጠሉም በላይ ድርጅቱ በታሪኩ ከፍተኛ በሚባለው ቀውስ የተናጠውም በዚህ ወቅት ነበር፡፡

ኢህአዴግ በህዝብ ተመርጦ ሥልጣን ከያዘ በኋላም ሆነ በሽግግሩ ወቅት በአዲሱ ሥርዓት ላይ ይንጸባረቁ ከነበሩት ችግሮች መካከል አንዱ የትግሉን ህዝባዊ ዓላማ እየዘነጉ ሥልጣንን የራስ መጠቀሚያ የማድረግ የተሳሳተ አስተሳሰብና ተግባር ነበር፡፡ ይህ ፈተና በቁጥር ትንሽ ቢሆኑም በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች በተቀመጡ አንዳንድ የድርጅቱ አባላትና ካድሬዎች ላይ ቀላል የማይባል ተፅዕኖ ያሳርፍ ነበር፡፡ በእርግጥ ኢህአዴግ ይህን የመሰለ ፈተና እንደማይቀርለት መገንዘብ የጀመረው አዲስ አበባ ከገባ በኋላ አልነበረም፡፡ ገና ትጥቅ ትግሉ ሳይጠናቀቅ ጀምሮ በተለይ አዲስ አበባን መቆጣጠር የጥቂት ጊዜ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ ይበልጥ በተገነዘበባቸው በመጨረሻዎቹ ወራት፣ በከተሞች የሚያጋጥመውን ይህን ፈተና ከሞላ ጐደል አስቀድሞ ለይቶት ነበር፡፡

ደርግ ከመውደቁ አንድ ዓመት በፊት ኢህአዴግ ደርግን አስገድዶ ሰላማዊ የሽግግር ሂደት እንዲቀበል ማድረግ የሚቻልበት ዕድል ከተገኘ ከፊል ኃይሉን ወደከተሞች በማስገባት መታገል እንደሚቻል አጠቃላይ መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘ ወደከተሞች እንዲገቡ የሚላኩ ካድሬዎቹን በማባበል የማበላሸት አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል ገምቶ ይህን አደጋ ከወዲሁ ለማምከን መዘጋጀት ጀምሮም ነበር፡፡ በ1982 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ "ትግላችን ከዬት ወደዬት፣ የአብዮታችን የወደፊቱ አጠቃላይ አቅጣጫ" በሚል ርዕስ በታጋይ መለስ ዜናዊ ተዘጋጅቶ የቀረበውና ለመላው የድርጅቱ አባላት ውይይት የተዘረጋው ሰነድ ይህን በግልጽ ያመላክታል፡፡ መለስ ገና ከደርግ ውድቀት በፊት ባዘጋጀው በዚህ ሰነድ፣

> "በዚያን ጊዜ በሚመጣው ሰላማዊ ሁኔታ ሙስናን ለማስፋፋት የሚረዱ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ ታጋያችን በከተሞች ውስጥ መታገል ያልለመደ ነው፡፡ ከተሞችን የማያውቃቸው ከመሆኑም በላይ አብዛኛው ታጋይ ከተማ አይደለም፡፡ ከተማው ታጋይ ለከተማ ሕይወት አዲስ ባይሆንም ከገንዘብና ቁሳዊ ጥቅም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሊማርኩትና ሊያታልሉት ይችላሉ፡፡ በንዑስ ባለሀብትነቱ ልዩ ልዩ የከተማ ፍላጐቶች የሚስቡት ነው፡፡ ከገጠር የመጣው ታጋይም እንደዚሁ በተለያዩ ጉዳዮች ሊደለል ይችላል፡፡ የተሸነፉት ኃይሎችም ይህን አዝማሚያ ሊጠቀሙበት ይሞከራሉ፡፡ በገንዘብ፣ በወሲብና በማቴርያላዊ ጥቅሞች እያማለሉ ለማበላሸት ይሠራሉ፡፡ እነዚህን አደጋዎች በውስጣችን

በሚካሔድ ትግልና ሥራ ከወዲሁ ካልተቆጣጠርናቸው ግባችን መሰናከሉ አይቀርም።"[42] በማለት ይህንኑ አደጋ በግልጽ አመላክቶ ነበር።

ከዚህ ጥቅስ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ኢህአዴግ ገና አዲስ አበባ ሳይገባ የከተሞች አብረቅራቂ ሕይወት ካድሬዎቹን በከባዱ የሚፈትንበት እንደሚሆን ተገንዝቦ ነበር። ከመገንዘቡም አልፎ ይህን አደጋ ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎች ማከናወን እንዳለበት አምኖ ይህንኑ ሥራ ገና ጦርነቱ ከማብቃቱ በፊት ጀምሮት ነበር። በእርግጥ ገና ከማለዳው አባላቱ በህዝባዊ ዓላማዎች፣ ወገንተኝነትና ዲስፕሊን እንዲታነፁ ላደረገው ኢህአዴግ ችግሩን ለመቋቋም የከተሞችን ውስብስብ ባሕርይ ከነፈተናው የማስገንዘብና የተወሰነ የቅኝት ማስተካከያ ከማድረግ በመለስ አዲስ ሥራ የሚጠይቅ አልነበረም። ድርጅቱ አዲስ አበባ ከመግባቱ በፊት በነበሩት ረጅም ዓመታት ባካሔደው ሥልጠናና ግንባታ በከተሞች ያጋጥማሉ ያላቸውን ፈተናዎች የመቋቋም ብቃት የነበረው ኃይል ገንብቶ ነበር። ከዚህ በመነሳት ኢህአዴግ የከተሞችን ፈተና ተቋቁሞ ቢያንስ ረዘም ላሉ ዓመታት ሊዘልቅ የሚችል ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ኃይል ገንብቶ ነበር ማለት ይቻላል። ይህም ሆኖ በዚህ ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በትጥቅ ትግሉ ወቅት በተካሔደ ሥራ ብቻ እንዳይከሰቱ ማድረግ አይቻልም ነበር። ችግሮቹ መከሰታቸው አይቀሬ እንደነበረው ሁሉ እነዚህን በየመድረኩ በሚካሔድ አዲስ ትግልና ሥራ ማስተካከል ደግሞ አማራጭ የማይገኝለት ነበር። በተግባር የሆነውም ይኸው ነው።

ከትጥቅ ትግሉ መጠናቀቅ በኋላ ኢህአዴግን የገጠመው የመጀመሪያው ፈተና በወሳኝነት በተራ ተዋጊዎቹ አካባቢ የተቀሰቀሰው የ"ይገባናል" ጥያቄ ነበር። ድርጅቱ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከሞላ ጐደል በእኩል ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ሕይወት ነበረው። ንቅናቄው ለሁሉም ሰው መሠረታዊ ከሚባሉ ፍላጐቶች በላይ የማሟላት አቅምና ችሎታ አልነበረውም። ምግብና ልብስ እንዲሁም መጠለያና ለውጊያ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን (አብዛኛው መጠለያ የአርሶ አደር ቤት መሆኑ እንደተጠበቀ) የማቅረብ ችሎታ ብቻ ነው የነበረው። በመሆኑም በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎቶች ሥርጭትና እደላ ላይ ልዩነት ለማድረግ አይቻልም ነበር። ይህ ቀድሞውንም በእኩልነት ለሚያምነው ኢህአዴግ ይህንኑ አስተሳሰብ ለማጽናት የሚያስችል ጠንካራ ቁሣዊ መሠረት ነበር። ከዚህ ነባራዊ ሕይወት ጋር ተያይዞ በድርጅቱ አባላት ዘንድ የፍጹም እኩልነት አመለካከት ሰፍኖ ነበር። በድርጅት ውስጥ እኩልነት መስፈኑ ደግሞ በከባድ መስዋዕትነት ሳይረቱ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለመዝለቅ ያስቻለ እሴት ነበር።

ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ከሞላ ጐደል ይህንኑ ሕይወት ለማስቀጠል መከራ አድርጓል። የሽግግሩ ፓርላማ አባላት ከሆኑት በስተቀር ሠራዊቱም ሆነ በህዝብ ሥራ ላይ የተሰማሩ አባላቱ በወር ከሞላ ጐደል የ130 ብር ድጐማ እያገኙና ስንቅ እየተሰፈረላቸው

እንዲኖሩ አድርጓል። የሽግግሩ የፓርላማ አባላት ብቻ በወር 1200 (አንድ ሺህ ሁለት መቶ) ብር ደሞዝተኛ ሆነው እንዲሠሩ ሲደረግ፣ ሌላው ከበረሐ ይዞት የመጣውን ሕይወት ለረጅም ጊዜ ቀጥሎበታል። ይሁንና በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊነት ላይ የተመደቡ ሰዎች ጽህፈት ቤትና መኖሪያ ቤት ሳይኖራቸው እንደወትሮው ተጓዥ ፖለቲከኛ በመሆን አገራዊ አመራር ሊሰጡ አይችሉም ነበር። ስለዚህም እያንዳንዱ ሰው የሚኖርበት ቤት እንዲያገኝ ተደረገ። እንደቀድሞ በእግር እየተጓዙ መንግሥታዊ ሥራ ማከናወን የማይቻል ስለነበርም እስከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ ለሚገኙ አመራሮች ተሽከርካሪ ተመደበላቸው።

ይህ በ1984 እና በ1985 ዓ.ም. አካባቢ ለነበሩና ከሞላ ጐደል ልዩነት የማይደረግበትን ሕይወት ለለመዱት ታጋዮች በቀላሉ የሚዋጥላቸው ሆኖ አልተገኘም። አመራሩ ከተማ ከገባ በኋላ የከዳቸው መስሎ እንዲሰማቸው ያደረገም ነበር። በእኩልነት አስተሳሰብ ተኮትኩተው ላደጉት የኢህአዴግ ታጋዮች የሚዋጥ ሆኖ ያልተገኘን ነገር በግልጽ ከመፋለም ውጭ ደግሞ ሌላ ባሕል አልነበረም። ስለዚህም ታጋዮቹ ቅሬታቸውን ማቅረብ ጀመሩ። በተከፈቱ መድረኮች ሁሉ "አመራሩ እኛን ረስቶ አላግባብ መጠቀም ጀምሯል" የሚል ወቀሳም አቀረቡ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ገና አዲስ አበባና ሌሎች ትልልቅ ከተሞችን ሳይቆጣጠር ካድሬዎቹን ብልሽት እንዳይፈታተናቸው ተጠንቅቆና ተዘጋጅቶ የመጣው የኢህአዴግ አመራር እንደቡድን ተወስዶ ሲታይ በመሠረቱ ከዚህ ዓይነቱ ችግር የራቀ ነበር። በኋላ እንደታየው በግለሰብ ደረጃ ራሳቸውን ማስቀደም የጀመሩ ሰዎች ባይታጡም፣ የአመራሩ ቡድናዊ ባሕርይ ግን የዚህ ዓይነት ጥርጣሬ የሚያስነሳ አልነበረም። በዲሲፕሊኑ የሚታወቅ አመራር ነበርና።

ከዚህ በመነሳት የኢህአዴግ አመራር በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በአባላቱ ዘንድ ይታዩ የነበሩትን እነዚህን ዝንባሌዎች ለማስተካከል ድርጅታዊ ኮንፈረንሶች አካሔደ። በዋነኛነት በሕወሓትና ኢህዴን ነባር ታጋዮች ዘንድ ይከሰቱ የነበሩት እነዚህ አመለካከቶች በኮንፈረንሶቹ ምከክርና ሰፊ ክርክር ተካሔደባቸው። ብዙዎቹ አባላት "አመራሩ ከድቶናል። ብቻውን እየተጠቀመ ስለሆነ፣ ለእኛም ተመሳሳይ ነገር ይደረግልን።" የሚል አስተያየታቸውን ካላንዳች ይሉኝታና ፍርሐት ገለፁ። ነገር ግን ባቀረቡት ሀሳብ ላይ በመመሥረት በተካሔደው ውይይት አመራሩ በዚህ ዓይነት በሽተኛ ዝንባሌ ያልተበከለ እንደሆነ ተረጋገጠ። አመራሩ ታጋዮቹ የድርጅቱን ደኅንነት ለመጠበቅ ያደረጉትን ትግል አድንቆ፣ ነገር ግን በአመራሩ ላይ እንዲታይ የማይፈልጉትን አዝማሚያ ለራሳቸው በመፍቀድ መልክ ሊፈቱት እንደማይገባ ያቀረበው የማስተካከያ ሀሳብም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አገኘ። በመጨረሻም ጥርጣሬያቸው መሠረት እንዳልነበረውና "ስለታገልን ይገባናል" የሚል ውለታ የማስመለስ አስተሳሰብ ስለተጠናወታቸው የያዙት አመለካከት እንደሆነ፣ ከዚህ አኳያ ደግሞ ዋናው የአመለካከት ስህተት በእነርሱ ዘንድ እንደታየ ለመግባባት ተቻለ።

ደሴ ላይ በተካሔደው የኢህዴን ኮንፈረንስ ላይ ድርጅቱን በቅርብ የተቀላቀሉ ምሁራን ሁሉ ተሳትፈው ነበር። ከእነዘህም መካከል አንዱ አንዳርጋቸው ጽጌ ነበር። አንዳርጋቸው በደሴው የአባላት መድረክ ነባር ታጋዮች ቅሬታቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ የሰማውን ምሬት ማመን አቃተው። የታጋዮቹ የግልጽነት ባሕልም ፈጽሞ ያልጠበቀው እንደሆነ አረጋገጠ። ምሬቱ ባልተሸፋፈነ መንገድ ሲቀርብ ያስተዋለው አንዳርጋቸው ይህማ እጅግ በጣም መልካም አጋጣሚ ነው ብሎ አመነ። አምኖም አመራሩን የሚጋለጥ ዘመቻው ግንባር-ቀደም ወደመሆን ተሸጋገረ። "አመራሩ ታጋዩን ከዶታል፣ በአበባ በተከበበ ቤት ውስጥ እየኖረ የታጋዩ አስከፊ ኑሮ እንዴት ሊሰማው ይችላል? ሰልቫጅ ልብሱን አውልቆ ሱፍ መልበስ የጀመረው የኢህዴን አመራር እንዴትስ አድርጎ ነው የታጋዩ መታረዝ ሊገባው የሚችለው?" እስከማለትም ደረሰ። ድርጅቱን በደንብ የማያውቀው አንዳርጋቸው በአመራሩ ላይ ያዘነበው ውርጅብኝ ለጊዜው የታጋዮችን ቀልብ መሳብ ጀምሮ ነበር። ነገር ግን አመራሩ ሰከን ብሎ በሰጠው ማብራሪያ ታጋዩቹ ያነሱትን ስህተት ለመመልከትና ለመቀበል በመቻላቸው የደፈረሰ ይመስል የነበረው መድረክ በመግባባት ተቋጨ። አንዳርጋቸው ብቻ ልዩነቱን እንደያዘ በዝምታ ተመለሰ።

በሳምንቱ መድረኩ ላይ የነበረ አንድ ግለሰብና አንዳርጋቸው ድንገት ተገናኙ። አንዳርጋቸው ውሃ ያልቀመሰ ምርጥ የጣሊያን ኮት ለብሷል። ግለሰቡም በአለባበሱ ተደንቆ "አንዲ ይህን ሰልቫጅ ከየት አመጣኸው" ብሎ በስላቅ ጠየቀው። አንዳርጋቸው በቁጣ "አሁን ይህ ሰልቫጅ ነው፣ በቅርቡ እህቴ ነች ከለንደን የላከችልኝ፣ እያየህ አትናገርም ወይ" በማለት መለሰ። ጓዱም የደሴውን መድረክ በሚያስታውስ መንፈስ "በትምሕርቱ መሠረት ሰልቫጅ መልበስ'ኮ ችግር አይደለም ብዬ ነው" በማለት መልሶለት ተለያዩ። ከዚያ በኋላ አንዳርጋቸው ብዙም አልቆየም። በራሱ አዲስ አጀንዳ በኤርትራ ዞሮ በየመን በኩል ወደኢትዮጵያ የተመለሰበትን ረጅም የጥፋት ጉዞ፣ ኢህዴን/ኢህአዴግ ደግሞ የውስጥ ችግርን በዴሞክራሲያዊ መንገድ እየፈቱ የሚጓዙበትን ረዥም የሥርዓትና የአገር ግንባታ ተያያዙት።

የ1985 ዓ.ም. ኮንፈረንስ አባላት በአመራሩ ላይ አንስተዋቸው የነበሩትን ጥርጣሬዎች በ.ፍቅም አንዳንድ የአመራሩ አባላት ደግሞ ቀስ በቀስ በዲሲፕሊን የመንቀሳቀስ ግዴታቸውን እርግፍ አድርገው መተው ጀመሩ። አመራሩ እንደቡድን ችግር የለበትም በሚለው አስተሳሰብ ተጠልለው ልዩ ልዩ የተሳሳቱ ተግባራትን ወደመፈጸም አመሩ። ይህ ጥቂት ነባር የአመራር አባላትን የሚመለከት ችግር የነበረ ሲሆን፣ ዘግይተው በተመሠረቱ የትግል ድርጅቶች ደግሞ በአንዳንድ አዳዲስ የአመራር አባላት ዘንድ የሚታይ ተናጠል ከስተት ነበር። ወቅቱ የትግሉን ዓላማዎች ከማናቸውም ዓይነት ራስ ወዳድ ዝንባሌ ተቆጥቦ ህዝብን በማገልገል ማሳካት ይጠይቅ የነበረ ቢሆንም፣ እነዚሁ የተበላሹ የአመራር አባላት ነገረ ሥራቸው ሁሉ ራሳቸውን በመጥቀም ላይ አተኮረ። በተለይ ደግሞ በህዝብ ነጻ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ

ይህ ዝንባሌያቸው መረን መልቀቅ ጀመረ፡፡ በሽግግሩ ወቅት የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በኋላ ደግሞ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ በግላጭ የተፈጸመውና በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ለ18 ዓመታት የእስራት ብይን የዳረጋቸው ከፍተኛ የሙስና ቅሌት ለዚህ አንድ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፡፡

የዚህ ዓይነት ዝንባሌዎች በትንሽ በትንሹም ሆነ እየተበራከቱ መከሰታቸውን ተከትሎ ድርጅቱ የችግሮቹን መንስዔ ከመፈተሸና መፍትሔ ማፈላለግ ቀጠለ፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ለዚህ ዓይነት ችግሮች መከሰት ወሳኙ መንስዔ የተሳሳቱት ግለሰቦች ግላዊ የዲስፕሊን ችግር ተደርጉ ተወሰደ፡፡ በርግጥ ከኢህአዴግ የሥነ-ምግባር መርሆች አፈንግጦ በቀላልም ሆነ ከፍተኛ የሙስና ቅሌት ውስጥ መዘፈቅ ተቀባይነት የሌለው የዲስፕሊን ግድፈት ነው፡፡ ይህን መነሻ በመያዝ ችግሩ ከግለሰባዊ የሥነ-ምግባር ጉድለት ጋር እንጂ ከሥርዓቱ ወይም ከፖለቲካ ኢኮኖሚው ባህርይ ጋር ተያያዥነት ያለው ተደርጉ ሳይወሰድ ቆየ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰቦቹ በሕግ ተጠያቂ እስከሆኑና ሌሎች ደግሞ በሩቁም ቢሆን ትምህርቱን እስካገኙ ድረስ ችግሩ ሊቀረፍ ይችላል የሚል እምነትም ተያዘ፡፡ ነገር ግን የሙስና ቅሌትም ሆነ የዚህ መነሻ መሠረት የሆነው ያለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ እንደኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ከዚህም ርቆ የሚሔድ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረት የነበረውና ያለው ማኅበራዊ ችግር ነው፡፡ ይህን ምንጭ ሳያደርቁ ችግሩን ከሥረ መሠረቱ መፍታት ደግሞ የሚቻል አልነበረም፡፡

በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ መስፋፋት የጀመረው ይህ ዝንባሌና በአመራሩ ውስጥ የፖለቲካ ግንባታ ባሕል መዳከም ቀስ በቀስ በተጀመረው ለውጥ ላይ ተፅዕኖ ያሳርፍበት ጀመር፡፡ አልፎ አልፎ ብቻ ይታዩ የነበሩ የሥነ-ምግባር ጉድለቶችም መደጋገም ጀመሩ፡፡ ከዓመት ዓመት በሚካሔደው ግምገማ ጉድለቶቹ ቢለዩም ምንጫቸውና መፍትሔያቸውን በትክክል ለማስቀመጥ ባለመቻሉ የሚደጋገሙበት ፍጥነትና ስፋት እየጨመረ ነገሩ ሁሉ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እየሆነ ሔደ፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ የተጀመረው ፈጣን የዕድገት ጉዞ ቀስ በቀስ መገታት ጀመረ፡፡ ይህን የተገነዘቡ አንዳንድ የአመራር አባላት በጉዳዩ ላይ መጨነቅና መጠበባቸው ባይቀርም፣ እስከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጅማሬ ድረስ መሠረታዊ ለውጥ ሳይመጣ የኤርትራ መንግሥት በግንቦት 1990 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ላይ ወረራ ፈጸመ፡፡

በኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ወቅት የዝቅጠት አደጋና የአመራር መከፋፈል፣

የኤርትራ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመውን ወረራ የመመከት ጉዳይ ከምንም ነገር በላይ ጉልቶና አጣዳፊ ሆኖ በወጣበት በዚህ ጊዜ፣ አመራሩ ወረራው ከተቻለ በሰላማዊ መንገድ እንዲቀለበስ፣ ካልሆነ ደግሞ ይኸይል የአገሪቱን ሉዓላዊነት ማስከበር እንደሚገባ ተማምኖ

እንቅስቃሴ ውስጥ ገባ፡፡ በወረራው ወቀተም ሆነ ከዚያም ሥግበተ አበበተወበጉ ሠራተ ድረበ በአመራሩ መካከል በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚታይ የሀሳብ ልዩነት አልነበረም፡፡ የኤርትራ መንግሥት በተደጋጋሚ የቀረበለትን ሰላማዊ የመፍትሔ ሀሳብ አልቀበልም በማለቱ ወረራው በኃይል እንዲቀለበስ ማድረግን ዋናው አማራጭ ቢያደርገውም የጦርነቱ ባህርይ የመከላከል ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ኤርትራ በጉልበት ከያዘቻቸው ቦታዎች ከለቀቀች በኋላ ችግሩ ካስፈለገ በሁለትዮሽ ድርድር፣ ይህ ካልተቻለም በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ጭምር እንዲታይ በማድረግ እልባት ሊሰጠው እንደሚገባም የጋራ አቋም ተያዘበት። እስከዚህ ወቅት ድረስ ሁሉም ነገር በግልጽ፣ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ የችግር አፈታት መርሆዎች በመገዛት ሲከናወን ቆዩ። ባድመ በ1991 ዓ.ም. የበጋ ወራት ሠራዊታችን በሰነዘረው መልሶ ማጥቃት ነጻ ከወጣች በኋላ ደግሞ ቀደም ሲል በአመራሩ መካከል በትንሽ በትንሹ የተከሰቱት የሀሳብ ልዩነቶች ይበልጥ ጎልተው መታየት ጀመሩ፡፡

ይህ ልዩነት በቅድሚያ የተከሰተው ጦርነቱን በበላይነት እንዲመራ በተዋቀረው ወታደራዊ ኮሚቴ ነበር፡፡ ወታደራዊ ኮሚቴው በወቅቱ በመንግሥትና በግንባሩ በፖለቲካዊ ሥራ ከፍተኛ ኃላፊነት በነበራቸው አመራሮች የተዋቀረ ነበር። በትጥቅ ትግሉ ወቅት ወታደራዊ ኃላፊነት የነበራቸውና ወደፋውንዴሽን ሥራ የተዛወሩ አመራሮችም የኮሚቴው አባል ነበሩ። በዚህ ውስጥ ያልተካተቱት ደግሞ የፖለቲካ ኮሚቴ አባላት ሆነው ያገለግሉ የነበረ ሲሆን ሁለቱም ኮሚቴዎች በተለምዶ በኢህአዴግ ውስጥ የሚሠራበትን በመተማመን ላይ የተመሠረተ አቅጣጫ በመከተል ይንቀሳቀሱ ነበር። በወታደራዊ ኮሚቴው መካከል የተከሰተው የሀሳብ ልዩነት እየሰፋ ሲሔድ ደግሞ ቀስ በቀስ ነገሮች በድምጽ ብልጫ የሚወሰኑበት ኮሚቴ ወደመሆን አመራ፡፡ ለሰላም እንጅ ለጦርነት ባልተዘጋጀችው አገር ከዚህ ጊዜ በፊት የተመሠረተ የብሔራዊ ፀጥታ ምክር ቤት ስላልነበርም ወታደራዊ ኮሚቴው በተጨባጭ እንደ ጸጥታ ምክር ቤት ያገለግል ነበር። ጦርነቱ በተቀጣጠለበት በመጀመሪያዎቹ ወራት በአመራሩ መካከል የተከሰተው ቀዳሚው የሀሳብ ልዩነት ጀማሪ አደራዳሪ የነበሩት የአሜሪካና ሩዋንዳ መንግሥታት ችግሩን በሰላም ለመፍታት ባቀረቡት ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡

አሜሪካና ሩዋንዳ ያቀረቡት የድርድር ሀሳብ የኢትዮጵያ ፓርላማ ያስተላለፈውን የመፍትሔ ሀሳብ በሥራ ላይ በማዋል ለኢትዮጵያ ድል፣ የኢሳያስን መንግሥት ደግሞ ሽንፈት የሚያከናንብ የነበረ ቢሆንም፣ አብዛኞቻችን የኢህአዴግ አመራር አባላት ይህን መልካም ሀሳብ ለመቀበል አቅማማን፡፡ በእርግጥ ይህን አቋም ለመቀበል ፈቃደኛ ያልነበርነው ወገኖች በሁሉም ጉዳዮች አንድ አይነት አቋም አልነበረንም፡፡ አንዳንዱ ሰው በኤርትራው ህዝባዊ ግንባር ለፍትህና ዴሞክራሲ /ህግደፍ/ ከህደት የተነሳ በእልህና ደም ፍላት ላይ የተመሠረተ አቋም መውሰዱ፣ ሌላው ደግሞ የኢህአዴግን ጡንቻ በማሳየት ትምክህተኛ ሊባል በሚችል ቅኝት መጓዝ በመፈለጉ

የሚያራምደው አቋም ነበር። ያም ሆነ ይህ በዚህ ወቅት የነበረው ብዙኅኑ የኢህአዴግ አመራር ቀስ በቀስ ጦርነትን ብቸኛው የመፍትሔ አማራጭ አድርጎ መውሰድ ጀመረ። በዚህ ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ያነሰ ይመስል፣ ከሥርዓቱ ችግሮች ጋር በተያያዘ በኢህአዴግ አመራር መካከል አዳዲስ ልዩነቶች እየተፈጠሩና እየተበራከቱ በቀላሉ የማይጠገን አቅጣጫ መያዝ ጀመሩ።

ጦርነቱ የመከላከልና በዚህ ባሕሪውም ፍትሃዊነቱ የማያጠያይቅ ሆኖ ቢጀምርም፣ በኮሚቴው ውስጥ ወረራው ከተቀለበሰም በኋላ የኤርትራ መንግሥት እስኪደመሰስ ድረስ መቀጠል አለበት የሚሉ ኃይሎች በሂደት እየተበራከቱ መሔድ ጀመሩ። የኤርትራ መንግሥት "ተናዳፊና ወራሪ ባህርይ እስካለ ድረስ ሰላም አይሰጠንም" በሚል አመክንዮ መገፋት የጀመረው ይህ አስተሳሰብ፣ ቀስ በቀስ በአንዳንዶቹ የአመራር አባላት ኃይልን የማሳየትና አቅሙ እስካለህ ድረስ ያሻህን የመሥራት ቡድናዊ ፍላጐት ወደመሆን ተሸጋገረ። ይህ ትክክል እንዳልሆነና ጦርነት በአጠቃላይ ሁሉንም ህዝቦች፣ በተለይ ደግሞ የተሻለ የመልማት ዕድል ያላትን ኢትዮጵያ ወደኋላ እንደሚመልስ በማመን "ወረራው ከተቻለ በሰላም እንዲቀለበስ አዳዲስና ተጨማሪ ሙከራዎች ማድረግ አለብን" የሚለው ወገን ደግሞ በኮሚቴውም ሆነ በሥራ አስፈጻሚው ውስጥ አነስተኛ ድምጽ ብቻ ነበረው። ይህም ሆኖ አንድ ሰው ብቻም ቢሆን ለመለየትና ፍትሃዊ ጥያቄ አንግቦ ትግል ለመጀመር በቂ በመሆኑ በአመራሩ መካከል ልዩነቱ እየሰፋ እንዲሔድ ለማድረግ ከበቂ በላይ ነበር።

በበኩሌ በወታደራዊ ኮሚቴው ውስጥ ልዩነት መቀስቀሱን ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቅኩት በወቅቱ የኮሚቴው አባል በነበረው በተፈራ ዋልዋ አማካይነት ነው። ለምሳ ወደቤቱ በሔድኩበት ከእለታት በአንዱ ቀን ተፈራ በወታደራዊ ኮሚቴው ውስጥ ካለው ልዩነት በመነሳት "ጥቃቱን አጠናክረን ሻዕቢያን በመደምሰስ አሰብን መልሰን ማምጣት አለብን" የሚል ሀሳብ እንዳለው እንደቀልድ ገለጸልኝ። በውይይታችን ሂደት በበኩሉ፣ አሰብን ከኤርትራ በኃይል የማምጣት ሀሳብ እንዳለው፣ ይህም በዓለም አቀፍ ሕግ ሊደገፍ የሚችልና እኛም ልንመራበት የምንችል እንደሆነ ከገለጸልኝ በኋላ፣ ሀሳቡን እንድቀበል ይሰብከኝ ጀመር። የኤርትራን ነጻነት ከመርሕ በመነሳት ሲደግፍ ለኖረውና ለዚህም ሲባል ብዙዎች ሕይወታቸውን ባጡበት ትግል ውስጥ በአመራርነት የተሳተፈው ተፈራ፣ አዲስ አበባ ከመግባታችን ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ከአሜሪካን ድምጽ ሬድዮ ጣቢያ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ "ኢህአዴግ አዲስ አበባ ላይ አዲስ መንግሥት ሲመሠርት፣ ኤርትራውያንም ነጻ አገር ይዘው አሥመራ ላይ አዲስ መንግሥት ይመሠርታሉ" በማለት በፍፁም ወገንተኝነትና በድፍረት መንፈስ ገልጾ ነበር። ከሥልጣን በፊት ትክክለኛውን አቋም ያለማወላወል የገለጸው ተፈራ፣ ይህን የመሰለ የአቋም ለውጥ ማድረጉ ቢያስገርመኝ በምን አመክንዮ እዚህ የአቋም ለውጥ ላይ እንደደረሰ ለማወቅ አጥብቄ ጠየቅኩት። ነገር ግን "የምንገነባው የካፒታሊስት ሥርዓት ነው፣ ካፒታሊዝም ደግሞ ሁሉም ነገር በጉልበተኞች

ውሳኔ የሚከናወንበት ነው፣ ስለዚህም ካፒታሊዝምን እንገነባለን ማለታችን ሳይለወረ ለጠቀ በጉልበት ለመንጠቅ ይህ በቂ ምክንያት ነው" ብሎ መለሰልኝ። ከዚህ አልፎ ሌላ የሚረባ ሀሳብ ሊያቀርብልኝ ደግሞ ተቸገረ።

"ካፒታሊዝምን በተሻለ ህዝባዊ መንገድ እንገንባ" መባሉ ቀረና "የወረራና ቅኝ ግዛት ሞዴሎቹን መኮረጅ የሕይወት መመሪያችን ሊሆን ይገባዋል" በሚለው በዚህ የተፈራ ሀሳብ ውስጥ፣ "ህዝብና አገር ይጠቀማሉ? ወይስ ይጐዳሉ?" የሚል የተለመደው ህዝባዊ የአቋም መውሰጃ መስፈርት ደብዛው አልነበረም። የቀረኝ ዕድል ይህ የብቻው ወይስ ወታደራዊ ኮሚቴውን ጭምር የበከለ አቋም እንደሆነ ማረጋገጥ ነበር። ለመሆኑ ይህ "የደርግ" አቋም በእነማን ነው የሚገፋው? ብዬ አጥብቄ ጠየቅኩት። አብዛኛው የኮሚቴው አባላት እንደሚያምኑበትና መለስና ጥቂት ጓዶች ብቻ ይህን አቋም አምርረው እንደሚቃወሙት፣ ይህም ሆኖ የእነመለስ አቋም ስህተት ነው ብሎ እንደሚያምን ገለጸልኝ።

የኤርትራን የነጻነት ትግል ደግፎ በሺዎች የሚቆጠሩ የህዝብ ልጆችን ለመስዋዕት የዳረገው አመራር፣ ሥልጣን ላይ ከወጣን በኋላ፣ ሰበብ ፈልጐ እንደገና ሌላ ኢ-ፍትሃዊ ወረራ ማሰቡና የሰማዕታትን ደም ማራከስ መጀመሩ ፈጽሞ ያልጠበቅኩት ነበር። በጥቂቱም ቢሆን ሥልጣን ላይ ከወጣን በኋላ ምን ያህል እየተለወጥን እንደሆነም አመላከተኝ። ከተፈራ ጋር በክርክር መግባባት ቢያቅተኝ፣ ይህ አቋም የኢህአዴግ የሆነ ቀን መንገዳችን እንደሚለያይ ገልጨለት ተለያየን። ነገር ግን በአመራራችን መካከል የተፈጠረው ልዩነት ፈጽሞ እንቅልፍ የሚነሳ ሆነብኝ። ሌላ ቀን ደግሞ በኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ለመካፈል ወደአዳራሽ ስንገባ፣ መለስና ጓድቃን ከወታደራዊ ኮሚቴው ስብሰባ ሲወጡ በር ላይ በመሣሪያ ግዥ ጉዳይ ላይ ሞቅ ያለና ልዩነት እንዳላቸው የሚያመላክት ሙግት ገጥመው አገኘሁዋቸው። ብዙም ሳይቆይ በሰላማዊ መፍትሔ ጥያቄ ዙሪያ ልዩነቱ ወደሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በይፋ ተሸጋገረ።

ይህን ተከትሎ "ሁሉን ነገር በጦርነት ልንፈታው ስለምንችል ሰላማዊ መፍትሔ አያስፈልግም፣ ወይም የሰላማዊ ዕድል መፍትሔ ብለን የኤርትራ መንግሥት ሕልውና እንዲቀጥል መፍቀድ የለብንም" የሚለው ወገን፣ በወቅቱ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የማስከበር ውጤት የነበራቸውን ሰላማዊ የመፍትሔ ሀሳቦች ሳይቀር እንዲከሽፉ ማድረግ ጀመረ። በወታደራዊ ኮሚቴ ውስጥ ከነበሩት አንዳንዶቹና የባሰባቸው ሰዎች ሰላማዊ መፍትሔ የሚገኝ ቢሆን እንኳ ማንኛውንም ሰበብ ፈጥረን ልናከሽፈው ይገባናል እስከማለት ደረሱ። የኤርትራን የነጻነት ትግል እደግፋለሁ ሲሉ እንዳልኖሩ "የቀይ ባሕር አፋር ድርጅት" የሚባል ንቅናቄ በመመሥረት በኤርትራና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ አፋሮችን አዋህዶ አዲስ ግዛት የሚፈጥርና ምናልባትም በቅርብ ርቀት ከኢትዮጵያ የሚዋሐድ መንግሥት የመመሥረት ሕልም ማውጠንጠንም ጀመሩ።

በዚህ ወቅተ፡ በጦርነቱ ሂደተ የኢተዮጵያ ኢኮኖሚ ፈጽሞ መላወስ አየተባነው መምጣቱን በተገነዘበው፡ በመለስ በኩል "ኢኮኖሚው፡ እየተዳቀቀ በመሆኑ ለሰላማዊ መፍትሔ ቅድሚያ እንስጥ" የሚል ሀሳብ ሲቀርብ፣ የሠላማዊ መፍትሔ ሀሳብን ጨርሶ የመቀበል ፍቃደኝነት ካጣው የአመራር ወገን በመሪነት ይታይ የነበረው፡ ተወልደ ወልደ ማርያም "ኢኮኖሚው የፈለገውን ያህል ቢንኮታኮት ጦርነቱ መቆም የለበትም" እስከማለት ደረሰ፡፡ የአሰብ ወደብን በካፒታሊዝም ሕግ ተገዝተን ማምጣት አለብን ይል የነበረው ተፈራም ለሰላማዊ መፍትሔ የነበረውን ጥላቻ ለማሳየት "ምክንያት ቢጠፋ እንኳ ከኤርትራ በኩል ነፋስ ወደኢትዮጵያ ነፈሰ በሚል ሰበብ ጦርነቱ እስከመጨረሻው እንዲቀጥል ማድረግ አለብን" የሚል አቋም አራመደ።

በአንድ ጦርነት ድል ማድረግ የሚወሰንበት የመጀመሪያው መሠረታዊ ጉዳይ ከጦርነቱ ፍትሃዊ መሆን ወይም አለመሆን ጋር የተያያዘ መሆኑ አያጠያይቅም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የጤናማ ኢኮኖሚ ውጤቶች የሆኑት ለሠራዊቱ በቂና አስተማማኝ ቀለብ፣ ተተኳሽና አልባሳት ለማቅረብ መቻልም በውጤቱ ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያሳርፋል፡፡ ነገር ግን ሰላማዊ መፍትሔን አጥብቆ ይቃወም በነበረው፡ ወገን የተያዙትና "ሁሉም ነገር ወደጦር ግንባር" ከሚለው የደርግ አስተሳሰብ ጋር በይዘታቸው ተመሳሳይ የሆኑት አቋሞች በማንኛውም መስፈርት ቢመዘኑ የአገራችንን ብሔራዊ ጥቅም የማስከበር ብቃት አልነበራቸው፡ም። የዚህ አቋም ጽንፈኛ ጫፍ በሆነው የተፈራ አቋም መሠረት ነፋስ የጦርነት መንስዔ መሆን ከጀመረ፣ መምጫው የማይታወቀውን ነፋስ ተከትሎ ኢትዮጵያ ከሁሉም ጐረቤቶቿ ጋር መናከሷ አይቀርም ነበር፡፡ ደግነቱ ይህ የእብሪት አስተሳሰብ ቀስ በቀስ መሸነፍ መጀመሩ በጀ እንጂ፡፡

በጦርነት ውስጥ ላደገው ኢህአዴግ ኃይልን የተመረኮዘ ግጭት ምን ያህል ዘግናኝ ውጤት እንደሚያስከተል ለመገንዘብ አስተማሪ ወይም መካሪ የማያስፈልገው ነው፡፡ ኢህአዴግ የጦርነትን አስከፊነት የሚያወቅ ድርጅት ነው፡፡ ኢ-ፍትሃዊ ዓላማ ይዞ የሚቀሰቀስ ወይም የሚካሔድን የትኛውንም ዓይነት ጦርነት ፈጽሞ የማይደግፍ ድርጅት ነው፡፡ በኢ-ፍትሃዊ ጦርነት በቀላሉ ማሸነፍ እንደማይቻልና ጦርነት ለጦርነት ሲባል ብቻ መካሔድ እንደሌለበትም በጥብቅ ይገነዘባል፡፡ ማንኛውም ወላጅ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚሳሳላቸውን ልጆቹን እንኳን አመክንዮ በሌለው፣ ጠንካራ ፍትሃዊ ምክንያት ባለው ግጭት ውስጥም ለማስገባት ማዘን መጠበቡ አይቀርም፡፡ ልጅ ያለውና ለልጁ የሚሳሳ ሁሉ ከጦርነት ይልቅ ሰላማዊ መፍትሔን ማስቀደሙ ፈጽሞ አያጠያይቅም፡፡ በኢህአዴግ አመራር ውስጥ "ነፋስ ነፈሰ" በሚል ምክንያት ጦርነት ሲሰበክ መስማት በአንድ በኩል ከድርጅቱ አመራር ከፊሉ በጊዜ ሂደት ምን ያህል እየተለወጠ እንደሆነ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአመራሩ ውስጥ አንድ ዓይነት አቋም ያለው ቡድን እየተፈጠረ እንደሆነ የሚያመላክት ነበር።

በዚህ የተነሳ ሉዓላዊነትን ከተቻለ በሰላማዊ መንገድ የማግኘት መፍትሔ የሚያቀነቅነው ወገን ዝቅ በማለቱ በአመራር ውስጥ የጦረኝነት አዝማሚያ ጉልህና የበላይ ሥፍራ አገኘ። የጦርነቱም ዓላማ ለጊዜውም ቢሆን ሉዓላዊነትን ከማስከበር ማዕቀፍ ወጥቶ ኤርትራን ወደማንበርከክ ተቀየረ። ይህ በተግባር ሊሆን የማይችል እንደነበር ባያጠራጥርም፣ ሠላማዊ መፍትሔ አልቀበልም ያለው ወገን አጥብቆ የያዘውና የሚያምንበት መንገድ ነበር። የግታ ማታ በኢህአዴግ አመራር ውስጥ በተካሔደው ትግል ለጊዜው የበላይነት አግኝቶ የነበረው ይህ ጦረኛ አዝማሚያ እየተረታ ሔደ። ቡድኑም ከሞላ ጐደል ከ1992 የመጀመሪያ አጋማሽ ጀምሮ በውስጡ መሰነጣጠቅ ታየበት። ቀስ በቀስ በተካሔደው ከባድ ውስጣዊ ትግል የጦርነቱ ግብ ሉዓላዊነትን በማስከበር ማዕቀፍ፣ የተቻለውን ያህል የኤርትራን ወታደራዊ ኃይል ማዳከም እንዲሆን ተደረገ።

በዚህ ዓላማ በመመራት ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን ለማስከበር የሚያስችላት ወታደራዊና ፖለቲካዊ ዝግጅት እንደተጠናቀቀ የአገር መከላከያ ሠራዊት ስትራተጂያዊ ማጥቃቱን በዓመቱ ሁለተኛ አጋማሽ ሰነዘረ። በዚህ ትክክለኛ ማዕቀፍ በተካሔደው ስትራተጅያዊ ማጥቃት በሶስቱም ግንባሮች የኤርትራን ሠራዊት በመምታትና በመበታተን አገራችን በኃይል የተያዙባትን መሬቶች አስመለሰች። ሠራዊታችን ከባድመና ቡሬ፣ ከፆሮናና ዛላምበሳ አልፎ እስከ ባረንቱና ሰንዓፈ ድረስ ከፊል ኤርትራን ተቆጣጠረ። በመጨረሻም የኤርትራ መንግሥት አሻፈረኝ ያለውን የሰላማዊ መፍትሔ ሀሳብ እቀባላለሁ በማለቱ ጦርነቱ አልባት አገኘ።

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያ ይዛ የተነሳችውን ሉዓላዊነትን የማስከበር ግብ በሚያሳካ ሁኔታ የተጠናቀቀ ቢሆንም፣ በኢህአዴግ አመራር መካከል የተፈጠረውን ልዩነትና መሰነጣጠቅ ግን ማስወገድ አልተቻለም። በድርጅቱ አመራር ውስጥ ጊዜያዊ የበላይነት ተጐናጽፎ የነበረው የጀብደኝነት ኃይል እናት አገርን በመከላከል ሽፋን የተቃወሙትን ብቻ ሳይሆን የጠየቁትን ሁሉ በማስፈራራትና በማሸማቀቅ የፈጸማቸው ተደጋጋሚ ስህተቶች ተዳምረው የራሱ የተበላሸ አካሔድ እስረኛ እንዲሆን አድርገውት ነበር። ይህም ሆኖ ጦርነቱ በመለስ/ኢህአዴግ መስመር ድል አድራጊነት ሲጠናቀቅ፣ ሉዓላዊነትን በማስከበር ሽፋን ሌሎችን ለማሸማቀቅ የሚያገለግል ዕድል ተዘጋ። የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ከተከበረ በኋላ ግለሰቦችን በፀረ-ሉዓላዊነት አቋም ለመወንጀል የሚቻልበት ዕድል እያነሰ፣ ነገሮችን ከሥረ-መሠረታቸው ለመተንተን የሚያስችለው ዕድል እየሰፋ መሔድ ጀመረ። በጦርነት ወቅት ለፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሔድ የሚከፈተው ዕድል ሰላም ከሰፈነ በኋላ ሊገኝ ባለመቻሉ፣ በኢህአዴግ አመራር ውስጥ የተቀሰቀሰው ልዩነት በዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ እንዲፈታ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጠረ። አሉ የተባሉ ችግሮችን ሁሉ በግምገማ መፈተሽም ተጀመረ። የተለያዩ የአመራር አባላት ድርጅቱን ከገባበት አጣብቂኝ ለማውጣት ያግዛሉ የሚሉዋቸውን

ሀሳቦች በጽሁፍ እያቀረቡ ለመከራከር ዝግጅት ማድረግ ጀመሩ።

በዚህ ምክንያት ረዘም ላሉ ዓመታት እየተቀዛቀዘ ሲሔድ የቆየው ውስጣዊ የፖለቲካ ሁኔታ በፍጥነት መቀየር ጀመረ። በድርጅቱ የድህረ-ሥልጣን ዓመታት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በርካታ ጽሁፎች ተዘጋጁ። ለሁሉም ጽሁፎች መነሻው "የቦና ፓርቲስታዊ ዝቅጠት" አደጋን የሚተነትነው የመለስ ጽሁፍ ቢሆንም፣ በተለያዩ የአመራር አባላት ተዘጋጅተው የተሰራጩት ጽሁፎች ደግሞ "የቦና ፓርቲስታዊ ዝቅጠት" ትንታኔን የሚሞግቱ ነበሩ። በዚህ ላይ ሳያተኩሩ በራሳቸው መንገድ የድርጅቱ ችግር ነው ብለው በለዩት ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ጽሁፍ ያቀረቡ ሰዎችም ነበሩ። መለስ ደግሞ ለእነዚህ ሁሉ የመልስ መልስ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን በአጭር ጊዜ እያዘጋጀ ማሰራጨት ቀጠለ። በተፈጠረው የፖለቲካ መነቃቃትና ውስጣዊ የሀሳብ ትግል እየተደሰተ፣ ከትምሕርት ቤት ሕይወቱ ጀምሮ በሚታወቅበት ክርክር ላይ እጅግ በተለየ ትኩረትና የብቃት ደረጃ መሳተፉን ቀጠለ። በመጀመሪያዎቹ አስር የሥልጣን ዓመታት ያካሔደውን ሰፊና ጥልቅ ጥናት መሠረት ያደረጉ መሠረተ-ሀሳቦችን የያዙ ጽሁፎች ቅጽበታዊ በሚባል ፍጥነት እያዘጋጀ ያቀርብ ጀመር። ሥራው ሌት ተቀን መጻፍ ሆነ። በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ጥናትና ምርምርን ዋነኛ ሥራው አድርጎ የከረመው መለስ ወደጽሁፍ ማሽንነት ተሸጋገረ። ለሥራ አስፈጻሚ ስብሰባዎች የሚሆኑ ሰባ ሰማኒያ ገጽ ጽሁፎችን ያለአንዳች ስርዝ ድልዝ፣ ድግግሞሽና የሚያስገርም የሀሳብ ፍሰት ከሁለት በማይበልጡ ቀናት አዘጋጅቶ በማቅረብ የሚታወቀው የኢህአዴግ የጽሁፍ ማሽን፣ በየቀኑ ከአምሳ ገጽ የማያንስ ጥራቱ የተጠበቀ ጽሁፍ ወደማዘጋጀት ደረጃ ተሸጋገረ።

መለስ ለአስተሳሰብ ጥራት መጐልበት አጋዥ ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውና የኢትዮጵያ ህዳሴ መሠረታዊ ጽንሰ-ሀሳቦችን የሚያብራሩት ጽሁፎችም እየታተሙ ለውስጣዊ ፍጆታ ይሰራጩ ጀመር። በዚህ ወቅት የነበረው መለስ ሀሳቡም ሆነ የመጻፍ ክሕሎቱ እጅግ የተሟላ ነበር። በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ያካሔደው ጥናትና ምርምር የህልቀት ደረጃውን በእጅጉ ከፍ አድርጐለት ለነበረው መለስ ዋናው ችግሩ በኮምፒውተር ሳይሆን በእጁ ብቻ የሚጽፍ መሆኑ ነበር። በሚጽፍበት ጊዜ ብዕሩን አጥብቆ የመያዝ ልምድ ለነበረው መለስ በቀኝ እጁ የመሐል ጣት ጫፍ ላይ የሚፈጠረው የሕመም ስሜት ቀላል ያልነበረ ቢሆንም ለዚህም ቢሆን ግን መላ ነበረው። የመሐል ጣቱን ጫፍ በትንሿ የሕክምና ጥላስተር ሸፍኖ ይፅፍ ነበር።

ስለመለስ የጽሁፍ ባሕልና በወቅቱ ስላመረታቸው ጥራት ያላቸው ጽሁፎች ታጋይ ክንፈ ገብረ መድህን፣ በተሃድሶው ሰሞን ጀኔራል ጻድቃን የተጠቀመበት አገላለጽ ብሎ ያጫወተኝ ሁሉንም አጠቃሎ ሊገልጸው ይችላል። ክንፈ በቃል የገለጸልኝን ሌላ የቃል አገላለጽ በጊዜ ብዛት ካልዘነጋሁት፣ ሜጀር ጀኔራል ጻድቃን የወቅቱን የመለስ የጽሁፍ ሥራ በማስመልከት "እኛ በአራት ሰዎች አራት ጽሁፎች አዘጋጅተን እንደአራት መድፍ ለመተኮስ ስንዘጋጅ፣ መለስ

በነበረው አንድ መድፍ ብቻ ደጋግሞ በመተኮስ አራቱን መድፎች ከጥቅም ውጭ አድርጐ የበላይነት ሊጐናጸፍ ቻለ" በማለት ነበር የገለጸው፡፡ ለመለስ የመልስ ምት የተጋለጡት ጽሁፎች ከህወሓት ገብሩ፣ ስዬ፣ ዓለም ሰገድና አባይ፣ ከብአዴን ደግሞ እኔ ያቀረብናቸው አምስት ያህል ጽሁፎች ነበሩ፡፡

ይህ የጻድቃን ወታደራዊ ንጽጽራዊ አገላለጽ በጣም ትክክል ቢሆንም፣ መለስ በጽሁፍ ሥራው አሸናፊ እንዲሆን ያደረገው የመጻፍ ፍጥነት ብቻ ሳይሆን፣ በዋነኝነት የህሳብ ጥራትና ትክክለኛነት የነበረው መሆኑ ነበር፡፡ መለስ በጠራ የህሳብ አቅርቦቱ ሌሎቹን ጽሁፎች በትንተና እያወራረደ "በአራት መድፍ" መልክ የተመሰሉትን ጽሁፎች በርግጥም ከጥቅም ውጭ አደረጋቸው፡፡ ከአራቱ የቡድኑ መድፈኞች መካከል በህሳብ ጥራት ሳይሆን በእልህ፣ ደም ፍላትና ጥላቻ ባሩዶች ተሞልታ ዛሬም ድረስ በተኩስ ላይ ነኝ የምትለው ገብሩ አሥራት የሚተኩሳት መድፍ ብቻ ነች፡፡ እርሷም ብትሆን ጣቱን በፐላሰተር ሸፍኖ እየጻፈ በትንተና የሚያወራርዳት ጀግና እጁን ተንተርሶ "ስለተኛ" በተኩስ ቀጠናው ውስጥ ሌላ ተፋላሚ የሌለ ስለመሰላት ሳይሆን አይቀርም፡፡ እንጂማ ከከሸፉት መድፎች መካከል አንድ ለእናቷ ሆና የቀረችው የገብሩ አሥራት መድፍ ጊዜያዊ ማደናገር ከመፍጠር አልፋ በእውነት የምትመታው ሚላማ ኖሮ አይደለም፡፡ በመድፈኞች መካከል በሚካሔድ ተኩስ ተመስሎ ስለቀረበው ንጽጽራዊ አስተያየት ይህን ያህል ከተነሳ፣ በኢህአዴግ አመራር መካከል የተቀሰቀሰው የህሳብ ትግል ስለቀጠለበትና ስለተቋጨበት ሂደት ጥቂት ነገር ልጨምር፡፡

መድረክ ረግጦ በመውጣት የተቋጨው ቡድን፣

ይህን በመሰለው ለህሳብ ትግልና ለአስተሳሰብ ጥራት በተመቸ ወቅት በተለያዩ የአመራሩ አባላት ተሳትፎ የተዘጋጁት ጽሁፎች በሙሉ በወቅቱ የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ለነበሩ ሁሉ እንዲሰራጩ ተደረገ፡፡ ጽሁፎቹ እየተነበቡ መደበኛ ባልሆኑ ስብሰባዎች መነጋገሪያ መሆን ቢጀምሩም ወደመደበኛ ስብሰባዎች ለመሸጋገር የተደረገው ሙከራ ግን በርካታ እንቅፋቶች ይገጥመው ጀመር፡፡ አንጃ የፈጠረው ኃይል፣ የሚያቀነቅናቸው ህሳቦች ወንዝ የማያሻግሩ መሆናቸውን እየተገነዘበ ሲሔድ፣ የተለያዩ ሰበቦችን እየደረደረ የመደበኛ ስብሰባ ጊዜዎች በተደጋጋሚ እንዲራዘሙ መጠየቅ ጀመረ፡፡ የህሳብ ትግሉን እንደጦር በመፍራት ስብሰባ የሚካሔድና የሚሞገትባቸው መድረኮች የሚጠሩበትን ቀን ማራዘምን ሥራዬ ብሎ ተያያዘው፡፡ ለወትሮው በየሁለት ሳምንቱ ሲሰበሰብ የነበረው የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቀረቡት ጽሁፎች ላይ ለመከራከር የሚያስችለውን ስብሰባ በተቆረጠ ቀን ማካሔድ አቃተው፡፡

ድርጅቱ በህሳብ ልዩነት እየተናጠ በነበረበት በዚህ ጊዜ ዋናው ትኩረት ለዚህ መሠረታዊ ችግር እልባት መስጠት መሆን እንደነበረበት አከራካሪ አልነበረም፡፡ ነገር ግን አንጃ የፈጠረው

ቡድን በመሠረታዊ የልዩነት ሀሳቦች ላይ ለመከራከር የሚያስችለውን መድረክ ላለማስከፈት ተንኮሎች በማብዛቱ ከመስከረም 1993 ዓ.ም ጀምሮ ቡድኑ ከድርጅት አመራር ማዕቀፍ አፈንግጦ እስከወጣበት መጋቢት መጀመሪያ ድረስ አንድም የሚረባ የንድፈ-ሀሳብ ክርክር ሊደረግ ሳይችል ቀረ፡፡ ይህም ቀስ በቀስ የቡድኑ አካሔድ የማይዋጥላቸው የአመራር አባላት እንዲበራከቱ አደረገ፡፡ በመጨረሻም ብዙ የአመራር አባላት የቡድኑ ባሕርይና አቋሞች ከባድ ስህተት የሞላባቸው እንደሆኑ መገንዘብ ሲጀምሩ ቡድኑ ከድርጅቱ አመራርነት በተደራጀ መንገድ አፈንግጦ ወጣ፡፡ የሕወሓት አመራር በከፍተኛ ካድሬዎች ፊት ቀርቦ በሀሳብ ይሟገት ዘንድ በተከፈተው የመቀሊው መድረክ እንደቡድን ረግጦ ከወጣ በኋላ ደግሞ ኢህአዴግ እስከዚያ ወቅት ድረስ ከባድ ችግር ከፈጠረው የአንጃ ኃይል ተፅዕኖ ነጻ ሊሆን ቻለ፡፡

በኢህአዴግ አመራር ውስጥ የተፈጠረው ይህ ቡድን በራሱ ውሳኔ ከድርጅቱ አፈንግጦ ቢወጣም፣ የቡድኑ አባላት ያዘጋጇቸው ጽሁፎች በቀረው የአመራር መካከል የሞቀ ክርክር እንዲካሔድባቸው ተደረገ፡፡ ምንም እንኳ ንድፈ-ሀሳባዊ ክርክሩ ሀሳባቸውን በጽሁፍ ያቀረቡትና ሌሎቹም የቡድኑ አባላት በመሉ በተገኙበት ሊካሔድ ቢችል ኖሮ የሚገኘው ጠቀሜታ ከፍተኛ የነበረ ቢሆንም፣ በቀሩት የአመራር አባላት ዘንድ ክርክር እንዲካሔድበት ተደረገ፡፡ የቡድኑ አባላት በራሳቸው ፈቃድ ባለመገኘታቸው ሳይገታ በተካሔደው ክርክርና ሰፊ የሀሳብ ትግል፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የሥርዓቱ ችግሮች ጥራት ባለው ትንተና ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ ግንዛቤ ተያዝባቸው፡፡ በመፍትሔያቸውም ላይ በሰፊ ምክክር ላይ የተመሠረተ ጠንካራ መግባባት ላይ ተደረሰ፡፡

ከዚህ በኋላ መለስ በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ያጠናቸው የፃሥራቅ እስያ አገሮች ልማታዊ መንግሥታት ልምድ እየቀረበ ይህንኑ ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም የሚያስችል እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ በትጥቅ ትግሉ ዘመን የነበሩ ሶሻሊስታዊ ቅኝት የነበራቸውና በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት በደንብ ያልተስተካከሉ አመለካከቶችን ጨምሮ ከአዲሱ ዘመን ጋር የማይሔዱ ግንዛቤዎች ሁሉ ተሟልተው ተወገዱ፡፡ በኢትዮጵያ የሚገነባው አዲሱ ሥርዓት የገበያ መሆን እንዳለበት ያለአንዳች ማቅማማት ተሰመረበት፡፡ ከገበያ ሥርዓትም በምሥራቅ እስያ ተያይዞ የመበልጸግ እሴቶች እንጅ፣ በምዕራቡ ዓለም የገበያ አከራሪነትና ሌላውን እያደ'ከዩ የመበልጸግ የዘረፋ ካፒታሊዝም ቅኝት የማይመራ የገበያ ሥርዓት መሆን እንዳለበት መግባባት ተያዘበት፡፡ ይህ የአስተሳሰብ አንድነት መፈጠሩ በልዩ ልዩ መድረኮች ከተረጋገጠ በኋላ በመስከረም 1994 ዓ.ም. በተካሔደው የኢህአዴግ አራተኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ላይ የተሣድሶው መስመር መሉ በሙሉ የበላይነት ተጐናጸፈ፡፡ ይህ ታሪካዊ ጉባዔ "የእመርታ ጉባዔ" የሚል ልዩ ስያሜ የተሰጠው ነበር፡፡ ከእመርታ ጉባኤ በኋላ የሆነው ሁሉ የተላለፉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ በማድረግ ማዕቀፍ የኢትዮጵያ ህዳሴን ማረጋገጥ ነበር፡፡

የኢትዮጵያን ህዳሴ የማረጋገጥ ጉዞ የተጀመረበት ይህ ወቅት፣ በራሱ በኢህአዴግ ውስጥ አንድ አዲስ እውነታ መፈጠር የጀመረበት በመሆኑ ሰፋ ባለና ራሱን በቻለ ምዕራፍ ካልታየ በስተቀር የተሟላ ግንዛቤ ሊያዝበት የማይችል ነው፡፡ እንደ ቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት፣ ጥገኝነት፣ ኪራይ ሰብሣቢነት፣ ወዘተ የመሳሰሉ አዳዲስ ጽንሰ-ሀሳቦች ወደመድረክ ብቅ ያሉት በዚህ ጊዜ ነው፡፡ ይህም ሆኖ በወቅቱ የነገሮችን ሂደት በሲራ ፖለቲካ መልክ መተርጐም የሚቀናቸው አንዳንድ ሰዎች፣ እነዚህ ጉዳዮች ሁሉ አንዳችም ተጨባጭ መሠረትና አመክንዮ ሳይኖራቸው፣ አፈንግጦ የወጣውን ቡድን ለመምታት ሲባል ሆን ተብሎ የተቀነባበረ የፖለቲካ ሴራ (Conspiracy) እንደሆኑ በማስመሰል ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነበር፡፡ አንዳችም ማስረጃ ሳይኖራቸው፣ መለስ "ከእጁ ያፈተለከውን የድርጅት ቁጥጥር እንደገና መዳፉ ውስጥ ለማስገባት የተጠቀመበት የብልጠት ስልት፣ ወይም የሲራ ፖለቲካ" አድርገው የሚገነዘቡና የሚያቀርቡ ወገኖች ጥቂት አልነበሩም፡፡ ነገር ግን የስኪፕ ጌትስ "የሲራ ንድፈ-ሀሳቦች የተወሳሰበን ሁኔታ በቅጡ ላለመረዳት የሚያግዙ አማላይ ጉልበት ቆጣቢ ሥልቶች ናቸው"[43] እንደሚለው፣ ይህ ግንዛቤ እንደማንኛውም የሲራ ፖለቲካ ትንታኔ ሁሉ በታካችነት የተያዘ ድምዳሜ ብቻ ነው። ድምዳሜውን የሚያራምዱ ወገኖች ውሃ የሚቋጥር ይዘትም ሆነ ማስረጃ አልነበራቸውምና፡፡

ይህን በመሳሰሉ የተሳሳቱ አመክንዮዎች ላይ በተገነቡ አስተያየቶች ምክንያት የኢትዮጵያን መጻኢ ዕድል በሚወስኑት በእነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የተፈጠረው ብዥታ ትንሽ አልነበረም፡፡ ይሁንና የጥገኛ ዝቅጠት አደጋ ንድፈ-ሀሳብ የትላንቱን ብቻ ሳይሆን፣ እስከተወሰነ ርቀት አገራችን ከእንግዲህም የምትገባባቸውን ምዕራፎች ጉዞ የሚወስን በመሆኑ የድህረ-ተሃድሶ ኢትዮጵያን ሂደት ከእነዚህ ጽንሰ-ሀሳቦች በመነሳት መመልከት ከፍተኛ ተፈላጊነት ይኖረዋል፡፡

ክፍል ሁለት

አሥራ አምስት ዓመታት በተሃድሶ አቅጣጫ፣

"ሕጻናት ጨለማ መፍራታቸው ያልተለመደ አይደለም። በሕይወት ውስጥ ጎልማሶች ብርሃን ሲፈሩ ማዬትን የመሰለ አሳዛኝ ጉዳይ ግን የለም።

ፕሌቶ

ምዕራፍ ስድስት፣

ጀማሪ ካፒታሊዝምና የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት እንደ ሥርዓት አደጋ፣

በኢትዮጵያ ከደርግ ውድቀት በኋላ በነበሩት የመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት አገሪቱን ለመለወጥ ያስቻሉ በርካታ ሥር-ነቀል እርምጃዎች የተወሰዱ ቢሆንም በዚህ ወቅት የተካሔደው ትግል አንድ መሠረታዊ ውሱንነት ነበረው፡፡ ይኸውም ሥርዓቱን የሚፈታተነው አደጋ ምን እንደሆነና ከየትስ እንደሚመነጭ በትክክል ለመለየት ያለመቻል ውሱንነት ነበር፡፡ የትኛውም ሕብረተሰብ በሚያልፍበት የዕድገት ደረጃ ሁሉ ሕልውናውን የሚወስኑ መሠረታዊ ጉዳዮች ወይም ፈተናዎች ያጋጥሙታል፡፡ እነዚህ አብዛኛውን ጊዜ በሕብረተሰብ ውስጥ በአንድ ተጨባጭ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ከሚታዩ መሠረታዊና አበይት ቅራኔዎች ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ ቅራኔዎቹ በትክክል ተለይተው ሕብረተሰቡን ወደፊት ለማራመድ በሚያስችል አኳኋን ከተፈቱ አገሪቱ የዕድገት ጉዞዋን ትቀጥላለች፡፡ ቅራኔዎቹን በትክክል ለመለየት ካልተቻለ፣ ወይም ደግሞ ቅራኔዎቹ ተለይተው ሲያበቁ በትክክል ለመፍታት ካልተቻለ ሕብረተሰብ ባለበት ከመርገጥ ጀምሮ ወደኋላ መመለስም ሊያጋጥመው ይችላል፡፡ እንደሁኔታውም አሁን በኒሊቢያ፣ አፍጋኒስታንና የመን እንደሚታየው የጋራ ውድቀት አይቀሬ ሊሆን ይችላል፡፡

በአገራችንም በእነዚህ ዓመታት የሥርዓቱን ችግሮች በትክክል ለመለየት ካለመቻል ጋር ተያይዞ የተፈጠረው ችግር ደረጃ በደረጃ ወደዚህ እንዳያመራ የሚከለከለው ነገር አልነበረም፡፡ በአመራሩ መካከል የሥርዓቱን ችግሮች በመለየትና በመፍታት ጥያቄ ዙሪያ የተቀሰቀሰው ልዩነትና መሰነጣጠቅ እንዳመላከተው በሂደት ችግሮቹን በትክክል በመለየት ባይፈታ ኖሮ ውጤቱ በማያጠራጥር ሁኔታ አስከፊ ሊሆን ይችል ነበር፡፡ በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት በግብታዊ መንገድ ይለዩ የነበሩትንና በዋናው የሥርዓት አደጋ ላይ የማያነጣጥሩ ችግሮችን አጠር አድርጐ በመመልከት የወቅቱን ዋነኛ ችግር ለመለየት ያለመቻል (Problem Identification) ችግር አንድ መሠረታዊ የአመራር ውሱንነት እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና አዲሱ መንግሥት በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ከአሮጌው ሥርዓት የተረፉ ኃይሎችን እንደትልቅ የሥጋት ምንጭ አድርጐ ይመለከት ነበር፡፡ ይህ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ለፀረ-ነፍጠኝነት ትግሉ በተሰጠው ከልክ በላይ የሔደ ትኩረት የሚታይ ነበር፡፡ በእርግጥ የነፍጠኛ ሥርዓት በመባል የሚታወቀውና በኢትዮጵያ ለአንድ መቶ ዓመታት ያህል የራሱ ልዩ ባህርይ ይዞ የተገነባው ሥርዓት ከወደቀም በኋላ የተወሰነ ትግል የሚጠይቁ ገጽታዎች ነበሩት፡፡ ሥርዓቱ ሰፊውን የአማራ ህዝብ ጨምሮ በሁሉም ህዝቦች ላይ የፈጸመውን በደል እያነሡ ከዚህ

ተገቢውን ትምሕርት መቅሰምም አማራጭ አልነበረውም። በተለይ ደግሞ በዚሁ ሥርዓት ተደቁሰው ስብዕናቸውን እንዲያጡና የበታችነት አስተሳሰብ እንዲጠናወታቸው የተደረጉ ወገኖችን በራስ መተማመን ለመገንባት ሰባል ባለፈው ሥርዓት ላይ ያነጣጠረ የሚጋለጥና የማስተማር ሥራ አስፈላጊ ነበር። በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን በሰፊው ለማስፈን በተጀመረው ጥረት የቀድሞው የኢሠፓ አባላትና ወታደራዊ አዛገቦች በተከፈተው ሰፊ ዕድል በመጠቀም የህትመት ሚዲያውን ተቆጣጥረው የዓላማቸው ማስፈጸሚያ ለማድረግ መሞከራቸው በራሱም ቢሆን አሮጌውን ሥርዓትና የተመራበትን አስተሳሰብ ከታሪክ እያጣቀሱ በማስተማር ማጋለጥን አስፈላጊ ያደርገው ነበር።

ይህም ሆኖ የዚያ ሥርዓት ተዋናዮች በህዝብና አገር ላይ የፈጸሙትን የሚዘገንን በደል የማጋለጥ ሥራ እነርሱ የአዲሱን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕልውናና ዕድገት የሚወስኑ አለመሆናቸው በተሠመረበት አኳኋን መፈጸም የነበረበት ነው። በተጨማሪም የአዲሱ ሥርዓት ሕልውናም ሆነ ዕድገት ከምንም ነገር በላይ የሚወሰነው ራሱ በፈጠራቸው አዳዲስ ቅራኔዎች እንደሆነ በማይሸፍን መንገድ መሆን ነበረበት። ይሁን እንጅ በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት በትግል የተወገደውን አሮጌ ሥርዓት ዋና የሕልውና ፈተና ምንጭ የሚያስመስል አቀራረብ ይዘወተር ነበር። ይህ ነጋ ጠባ በአሮጌው ሥርዓት ኃይሎች ላይ በማትኮር በአንጻሩ ደግሞ ስለአዳዲሶቹ ችግሮች ባለማንሳት የሚገለጽ የግንዛቤ ጉድለት ነበር።

ከዚህ ለየት ባለና በሚመሳሰሰል መልኩ የአዲሱን ሥርዓት ፈተናዎች በትክክል የመለየት ችግር እንዳጋጠመ የሚያሳየው ሌላው ተጨባጭ አብነት በኢህአዴግና በአዲሱ መንግሥት አንዳንድ የአመራር አባላት ዘንድ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ብልሽቶችን በማስመልከት ድርጅቱ ይሰጥ በነበረው ትንታኔ ነው። ያኔ የኢህአዴግ ምክትል ሊቀ-መንበርና የአገሪቱ ምክትል ጠ/ሚኒስትር የነበረው አቶ ታምራት ላይኔ ከሸኽ ሞሐመድ አላመዲን ላይ የአሥራ ስምንት ሚሊዮን ዶላር የማጭበርበር ወንጀል ፈጽሞ በተጋለጠበት ጊዜም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ ስህተቶች ሲያጋጥሙ ድርጅቱ የነበረው አተያይ፣ ብልሽቱ በግለሰብ ደረጃ ፈተናውን ለማለፍ በመቸገር ምክንያት የተከሰተ እንደሆነ የሚያስመስል ነበር።

በእርግጥ አንድ በትግል ያለፈ ሰው ራሱን ጠብቆ በንጽህና በማጓዝበት ሁኔታ፣ ሌላው ለዚህ ዓይነቱ ምግባረ ብልሹነት ተጋላጭ ከሆነ በሁለቱ ልዩነት ላይ የግል ዲሲፕሊን ጉልህ ቦታ የለውም ማለት አይቻልም። በማንኛውም ሁኔታ የሚያጋጥመን ፈተና በዲስፕሊን ማለፍ ሊጋራ ዓላማ በጽናት ከመሰለፍ ጀምሮ በግልም ጠንካራ ዲስፕሊን ማዳበርን የሚጠይቅ ነው። ነገር ግን ይህን የመሰለው ከባድ ቅሌት ከሥርዓት ችግር ተነጥሎ በግለሰብ ጸባይ ወይም የዲሲፕሊን ግድፈት ላይ ብቻ ሊለከከ የሚችል አልነበረም። በተለይ ደግሞ የግለሰቦች ሥነ-ምግባራዊ ጉድለት እየተበራከተና አንዳንድ ኃላፊዎች ሥልጣናቸውን ካለአግባብ ለመጠቀም የሚያደርጉት መከራ

ይህልጥ እየተደጋገመ ሲሔድ ጉዳዩ ከግል ሥነ-ምግባራዊ ማዕቀፍ ወጥቶ የሥርዓት ችግር እንዳለ ያመለክታል። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ገና ከትጥቅ ትግሉ መጠናቀቅ በፊት ወደትልልቅ ኮሪሞች ስንገባ ወይም አዲስ ሥርዓት ስንገነባ የሚያጋጥመን ፈተና ምን ይሆናል? ብሎ ለመተንተንና አደጋዎቹን ገና ከሩቁ ለመለየት ለሞከረው አህአዴግ የሚከብድ መሆን አልነበረበትም። ነገር ግን እስከዚህ ወቅት ድረስ በዋነኛነት ጠቃሚ ተግባራትን በመሥራት ላይ ተሰማርቶ የቆየው ኢህአዴግ፣ አልፎ አልፎ የሚታዩትንና ሥርዓቱን ለአደጋ በማጋለጥ ረገድ ከባድ ትርጉም የነበራቸውን የዲሲፕሊን ግድፈቶችና ሥነ-ምግባራዊ ችግሮች ላይ ላዩን ከመነካካት ባለፈ ሥር-ነቀል በሆነ መንገድ ለመገምገምና ለመፍታት ሳይችል ቀረ።

በዚህ ምክንያት ችግሮቹ ተከማምረው የድርጅቱን ሕልውና ወደመፈታተን እስካመሩበት የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ድረስ ጥልቀት ባለው መንገድ ሳይመከርባቸውና ሳይለያቸው ቆየ። ይህ ሰባል ድከመቶችና ችግሮቹ ማንንም የሚያሳስቡ አልነበሩም ማለት አይደለም። ይልቁንም የችግሮቹ መደጋገምና ስፋት በአንዳንድ የአመራር አባላት ዘንድ ከፍተኛ ምሬትን ማስከተል ጀምሮ ነበር። ከጦርነቱ ሁለትና ሦስት ዓመታት በፊት ጀምሮ "ለምንድን ነው የሥነ-ምግባር ጉድለቶች በድርጅቱ ውስጥ እየተደጋገሙና እየተበራከቱ የሚሔዱት?" የሚሉ ጥያቄዎች እስከማንሳትም ደርሰው ነበር። በድርጅቱ ለቃ-መንበር በታጋይ መለስ በኩልም በጉዳዩ ላይ ሰፊና ዝርዝር ጥናቶች ሲካሔዱ ቆይተዋል። መለስ ጦርነቱ ገና ሳይጠናቀቅ በጻፈው የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋ ጽሑፍም የችግሩ ምንጭና መፍትሔ ነው ብሎ ያመነበትን ጉዳይ ለማመላከት ሞክሯል።

የሥርዓቱን መሠረታዊ ፈተናዎችና ምንጫቸውን ከመለየት አኳያ የታዩት ውሰንነቶች ግን እነዚህ ብቻ አልነበሩም። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ደግሞ በተለይ አፈንግጦ ለወጣው በድን የኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ ምንጭ የኤርትራ መንግሥት ወደመሆን ተሸጋግሮ ነበር። "ሻዕቢያ እስካለ ድረስ ሰላም አናገኝም" በሚል አመክንዮ በተገነባው በዚህ አቋም፣ የአገሪቱ ችግሮች ከራሷ ውስጣዊ ሁኔታ ለዚያውም ከራሱ ከአዲሱ ሥርዓት ባሕርያት የሚፈልቁ መሆናቸው ቀረ። አልፎ ተርፎም የችግሩ ሁሉ መንስዔ የሥርዓቱን ዕድል ከቶውንም የመወሰን ችሎታ ባልነበራቸው ኤርትራና የኤርትራ መንግሥት ትከሻ ላይ ለማስቀመጥ ተሞከረ። "ዋናው ችግር የኤርትራ መንግሥት ሳይሆን በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት ያጋጠመው የመዝቀጥ አደጋ ነው" የሚሉ ወገኖች ሁሉ ለኤርትራ ጥብቅና ስላላቸው ነው ተባለ። "ጦርነቱን በአጭሩ ቋጭተን ፈታችንን የሥርዓቱ ፈተና ዋነኛ ምንጭ ወደሆነው ውስጣዊ ሁኔታ እናዙር" ያሉ ሁሉ፣ ኢትዮጵያ በጦርነቱ በድል አድራጊነት እንድትወጣ ከማንም ያልተናነሰ አስተዋጽዖ አበርክተው እያለም ቢሆን፣ "በሉዓላዊነት ላይ የሚደራደሩ" እስከመባል ደረሱ። መለስ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት አገሪቱን ለድል ያበቁ ምርጥ ወታደራዊ ሀሳቦች እንዲሁም ስትራቴጂና ታክቲኮች ያመነጨ ሆኖ እያለ፣ በውስጡ አሉቹ የምትባለው "ኤርትራዊ ሐረግ" እየተቆጠረች "በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት

ላይ የማይታመን" እስከመባል ደረሰ።

በእርግጥ ይህ የሆነው ያለ ምክንያት አልነበረም። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጊዜ የከፋ የዝቅጠት አስተሳሰብን በመወከል ደረጃ ከሚታወቀው ቡድን መካከል አንዳንዶቹ በተጨባጭ የሙስና ቅሌት ውስጥ ገብተው ይህን ለመሸፈን ከቀድሞ መንግሥታት ባልተናነሰ ደረጃ ወደውጭ ጠላት ማነጣጠርና አቅጣጫ ማሳት በመምረጣቸው ነው። በሌላ በኩል በዚህ ወቅት የዚህ ቡድን አባላት ከነበሩትና በሙስና እንዳልተዘፈቁ ከሚገመቱት አንዳንዶቹ ደግሞ አንድም ራሳቸውን በተስፈኛ ገዥ መደብ መነጽር ማየት በመጀመራቸው፣ አለዚያም በህዝቦች መብት ሳይሆን በግዛት አንድነት ከሚያምነው ኃይል ጋር ለመሸማገል በመፈለጋቸው ምክንያት የመጣ ነበር።

ኢህአዴግና አዲሱ መንግሥት በመጀመሪያዎቹ አሥር የሥልጣን ዓመታት የሥርዓቱን ፈተና በትከከል ባለመለየታቸው ሥርዓቱ ከጊዜ ወደጊዜ ለብዙ ዓይነት ችግሮች መዳረግ ጀመረ። ይባስ ብሎም በመርሕ ላይ የተገነባ የአመራር አንድነት የግድ ይል በነበረው በጦርነቱ ሂደት የአመራር ቀውስ አጋጠመ። ይህ ቀውስ የሥርዓቱ ችግር በትክከል ተለይቶ የአመራር ግንባታው በዚሁ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ካለመደረጉ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ቢሆንም፣ ድርጅቱ በቻይናውያን የቀውስ አተረጓገም ሁሉንም ጉዳዮች ከሥረ መሠረታቸው በመፈተሽ እንደአዲስ ሊግባባ የሚችልበት መልካም ዕድል የፈጠረ ነበር።

ቻይናውያን ቀውስ "አንድን ችግር ለመግንዘብና ለመፍታት ሲባል የተፈጠረ መልካም ዕድል ወይ አጋጣሚ ነው" ይላሉ። በኢህአዴግ አመራር ውስጥ የተከሰተውም ቀውስ ወደአዲስና የተሻለ መግባባት ለመድረስ የሚያስችል መልካም አጋጣሚ ነበር። በእርግጥ ቀውሱ በትክክል ከተያዘና ከተፈታ ኢህኢዴግን ወደአዲስ ጥንካሬ ሊያሸጋግረው የሚችል ነበር። ይህ የሚጠይቀው ቀውስን ቻይናውያን በሚገነዘቡበት መልከ መረዳትና መንቀሳቀስ ብቻ ቢሆንም፣ ከፊሉ የአመራር አባል ግን ኢህአዴግም ሆነ ሥርዓቱ ቀውስ ላይ እንደወደቁ ለመቀበል ፍላጐት አልነበረውም። ይልቁንም ምንም ዓይነት ችግር እንዳልተፈጠረ አስመስሎ፣ አሊያም የገጠመን ቀውስ ከውጭ ኃይሎች ጋር የተያያዘና በአመራር ደረጃ ደግሞ ለዚህ ውጫዊ ኃይል የመንበርከክ ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች በመኖራቸው የተፈጠረ እንደሆነ አድርጐ ይመለከት ነበር። ይህ ግንዛቤ ቀውሱን ውጫዊ ለማስመሰል ይፈልግ የነበረው ቡድን ድርጅቱን ለቆ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ የታየ ሲሆን፣ ቡድኑ መድረክ ረግጦ ከወጣ በኋላ ግን በችግሮቹ ላይ ሰፊ ምክክር ተካሂዶ በቀውሱ መሠረታዊ ባሕርይና በዚሁ ልክ ደግሞ በችግሮቹ መፍትሔ ዙሪያ መግባባት ላይ ተደረሰ። ይህም በኢትዮጵያ የተሃድሶውን ዘመን መጀመር የሚያበስር ሆነ። ባለፉት ኢሥራ አምስት ዓመታት በኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ በትከከል ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ ኢህአዴግ ከረዥም ሂደት በኋላ የሥርዓቱ ፈተና ብሎ የለያቸውን ችግሮች አጠር አድርጐ መመልከት ተገቢ ይሆናል። በተለይ ደግሞ የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋን።

እውን ቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት የሥርዓት ፈተና ነበርን?

የአዲሱን ሥርዓት ፈተናዎች ለመለየት ከተካሔደው ትግል ጋር ተያይዞ ከሞላ ጐደል በአገሪቱ የፖለቲካ ሕይወት የእለት ተዕለት መጠቀሚያ መሆን ከጀመሩት አዳዲስ ጽንሰ-ሀሳቦች መካከል አንዱ ቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት (Bonapartist decadence) የተባለው ነበር። በዓለማችን ደግሞ ይህ ጽንሰ-ሀሳብ የሁለተኛው የፈረንሳይ ሪፐብሊክ መሪ የነበረው ሉዊ ቦናፓርት እ.ኤ.አ. በ1851 ወደሥልጣን ከመጣበት ሂደት ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ የዋለ ነው።በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልክዓ-ምድር ላይ ደግሞ ይህ ጽንሰ-ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነሳው ከደርግ ወደሥልጣን መምጣት ጋር ተያይዞ ነበር። ደርግ በህዝቡ ትግል ተንጠላጥሎ በ1967 ዓ.ም ሥልጣን ሲይዝ የመንግሥቱን ባሕርይ በተመለከተ በወቅቱ ተራማጆች ዘንድ ከፍተኛ ክርክር ተቀስቅሶ ነበር። አንዳንድ ተራማጆች ደርግ "ፋሽስታዊ ዝንባሌ" እንዳለው ሲያወሱ፣ ሌሎች ደግሞ "የለም ቦናፓርቲስታዊ ዝንባሌ ያለው ነው" ይሉ ነበር። የተወሰኑት ደግሞ ደርግ ተራ ወታደራዊ አምባገነናዊ መንግሥት ነው የሚል አቋም ነበራቸው።

እነዚህ ልዩነቶች በተቃውሞ ትግሉ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የነበራቸው ቢሆኑም፣ በአንድ በኩል ደርግ ተራማጆቹን ሁሉ በኃይል ወደማጥፋት በመሸጋገሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ራሳቸው ተራማጆቹ በመቻቻል መርሕ ለተገዛ ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል የነበራቸው ልምድና ዲሲፕሊን የዳበረ ስላልነበር ልዩነቱ በጠራ አኳኋን የተቋጨ አልነበረም። ከዚህ በኋላ ሃያ አምስት ዓመታት ያህል ቆይቶ በኢህአዴግ አመራር መካከል አዲስ ልዩነት እስኪቀሰቀስ ድረስ ጽንሰ-ሀሳቡ ከሞላ ጐደል ተረስቶ ቆየ። በአዲሱ ሥርዓት የመንግሥቱን ባሕርይና ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ሥጋቶችን ለመፍታት ሲባል እንደገና በመለስ ዜናዊ ከተነሳሳ በኋላ ግን ጉዳዩ አገራዊ መነጋገሪያ ሆነ።

መለስ የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋን እንደ ሥርዓት አደጋ መመልከት ከጀመረ የቆየ ቢሆንም፣ በጉዳዩ ላይ የጻፈው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከመጠናቀቁ ከጥቂት ወራት በፊት ነው። ወቅቱ በአመራሩ መካከል የተቀሰቀሰው ልዩነት መቋጫ ያላገኘበት ነበር። ይልቁንም ከቀን ወደቀን እየተወሳሰበና እየተካረረ መሔድ የጀመረበትና በአመራር አባላት ዘንድ የቸግሩን ባሕርይና መንስኤውን ለመለየት ሁሉም ይጨነቅ ይጠበብ የነበረበት ወቅት ነው። በወታደራዊ ኮሚቴው ውስጥ የነበረውን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፣ በሥርዓቱ ውስጥ እያደገ የመጣውን ዝንባሌ በቅርብ ለመከታተል በሚያስችል ቦታ ላይ ሆኖ ሁኔታውን በከፍተኛ የኃላፊነት መንፈስ ይከታተል የነበረው መለስ፣ በታሪክ ከሚያውቃቸው ተመሳሳይ ሂደቶች በመነሳት በዚህ ጉዳይ ላይ የራሱን ምርምር ያካሂድ ነበር። የማታ ማታ ደግሞ ከምንገኝበት የዕድገት ደረጃ ጋር ተገናዝቦ የሚታይና አዲሱ ሥርዓት አይቀሬ የዝቅጠት ፈተና እንደገጠመው በማረጋገጥ ይህንኑ ከፈረንሳይ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር የሚያሳይ አዲስ ትንታኔ ይዞ ቀረበ።

ጽሁፉ በጣም መሠረታዊና የአገሪቱን መጻኢ ዕድል የሚወስን ቢሆንም፣ በአመራር አባላት ከታወቀና ከተነበበ በኋላ በአንድ በኩል ከፍተኛ ተስፋ ሲፈነጥቅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከባድ ጭንቀትና ብስጭትን አስከተለ። ችግሩን በህዝባዊ ወገንተኝነት መንፈስ መፍታት ለሚፈልገው ወገን ተስፋ፣ ችግር ውስጥ ለተዘፈቀው ደግሞ ከባድ የራስ ምታት ሆነ። በግሌ ይህን የመሰለውን እጅግ አነጋጋሪ ጽሁፍ ያገኘሁበት አጋጣሚ ደግሞ ሁሌም ከአእምሮዬ የማይጠፋ ነው።

ለኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሰላማዊ ወይም የግጭት እልባት እናስገኛለት የሚለው ጥያቄ ሰርክ የመወያያ አጀንዳ በነበረበት አንድ የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እነተወልደና ስዬ "መለስ ለኤርትራ መሬት ሰጥተን ሰላም እናውርድ" ብሏል የሚል ፈጽሞ መሠረተ ቢስ የሆነ ወቀሳ አቀረቡ። መለስ በበኩሉ እንደዚህ አላልኩም አለ። በእርግጥም አላለም ነበር። በውይይቱ የነበረ ሰው ሁሉ የሰማው የመለስ መከራከሪያ፣ *"በአገሮች መካከል በሚካሔድ ግጭት መሬት ለጊዜው ሰጥተው አቅማቸው ሲጠነክር መሬታቸውን በትግላቸው ማሰመለስ የተለመደ ነው። ይህን ሩሲያ ከጀርመን ጋር በተዋጋችበት በብረስት ሊቶቭስክ አጋጣሚ አድርጋዋለች። ፈረንሳይና ጀርመን በተደጋጋሚ በተዋጉባቸው በአሊሰና ሎሬን አካባቢዎችም አንዴ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ ተደርጓል። በእኛ ሁኔታ ግን ይህ አስፈላጊ አይደለም"* የሚል ይዘት ነበረው። ስለሆነም መሬት ሰጥተን እንደራደር ያላለው መለስ በተለመደው የኢህአዴግ ባሕል፣ ቃሉ እምነት ተሰጥቶት ጉዳዩ እልባት ማግኘትና በዚሁ መቋጨት ነበረበት።

ሐቁ ይህ እንደሆነ በልባቸው እያወቁ መለስን የማሸማቀቅ ግብ የነበራቸው የቡድኑ አባላት ግን "ብሏል" ብለው ድርቅ አሉ። ቃለ-ጉባዔ ይታይልን እስከ ማለትም ደረሱ። የኢህአዴግ አመራሮች በእምነት ከመሥራት ወጥተው በቃለ ጉባዔ ወደመሟገት ማምራታቸው እጅግ አስፈሪ የሆነባቸው አንዳንድ አባላት፣ ባለመተማመን ላይ የተመሠረተ ይህ አዲስ ባሕል ይቅርብን ቢሉም ሰሚ ሳያገኙ ቀሩ። በመጨረሻ ቃለ-ጉባኤው ተባዝቶ ለሁሉም ሰው ታደለ። እያንዳንዱ ሰው መለስ "መሬት ሰጥተን እንገላገል" ብሎ እንደሆነ ለማረጋገጥ እያንዳንዷን መስመር በጥንቃቄ አነበበ። ካነበበም በኋላ ጉዳዩ እንደገና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ታዬ። "መለስ መሬት እንሰጥ ብሏል" ብለው የተከራከሩት ሳይቀር፣ ከቃለ-ጉባዔው ላይ ማረጋገጫ ሊያገኙ እንዳልቻሉ በግልጽ አመኑ። ቃለ-ጉባዔው ቃል በቃል (Verbatim) በሚባል ደረጃ የተጻፈ ስለነበር ተዘሏል ብሎ ለመከራከር እንኳ በር የሚከፍት አልነበረም። ስዬ አብርሐ በስብሰባው ላይ "የቃለ-ጉባኤ አጻጻፉ ወደር የሌለው ነው" እስከማለት ደርሶ ነበርና በእርግጥም ስላልተጻፈ ነው የሚል መከራከሪያ ማንንም አያዋጣም ነበር። ስለዚህ ብሏል/አላለም በሚለው ጉዳይ ላይ ውይይቱ ሲቀጥል አንድም ሰው ብሏል በሚል ድርቅና ማስረጃ ለማቅረብ ተቸገረ። ይባስ ብሎ መለስን "መሬት ሰጥተን እንገላገል" ብለሀል ብሎ የከሰሰው ስዬ፣ "መለስ መሬት ሰጥተን እንገላገል ሊል አይችልም፣ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ስለሆነ" ብሎ ተናገረ።

ይህም እንደገና አነጋጋሪ ሆነ::

መለስ በዚህ የስዬ አስተሳሰብ በእጅጉ በመገረም "መሬት ሰጥተን እንገላገል ያላልኩት ስላላመንኩበት እንጅ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ስለሆንኩ አይደለም" የሚል መልስ በአጽንኦት አቀረበ:: በክርክሩ ጉዳዩን ቀለል አድርጐ ለማስረዳት በመሻት ደግሞ የአፄ-ምኒሊክን ታሪክ እስከማንሳት ደረሰ:: ከሞላ ጐደል እንዲህም አለ:: "ከአድዋ ድል በኋላ በንጉስ ምኒሊክ ፊት ሁለት ምርጫዎች ነበሩ:: በአንድ በኩል ተሸናፊውን ጣሊያን ኤርትራ ድረስ በማሳደድ ዕድላቸውን የመሞከር ምርጫ ነበር:: በሌላ በኩል መላውን የኤርትራ መሬት በእጃቸው ለማስገባት ሲሉ ለሽንፈት የመጋለጥ አደጋ ተደቅኖባቸው ነበር:: እናም ምኒሊክ መሬት ለመያዝ ሲሉ መላውን ሥርዓት ለሽንፈት የሚዳርግ ነገር ከመሥራት ተቆጥበው የኋለኛውን ሚዛናዊ ምርጫቸው ባደረጉበት አገር መሬት የሥርዓትን ህልውና የሚወስነው ብቸኛ ጉዳይ አይደለም:: ስለዚህም ባምንበት ኖሮ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኘም እለው ነበር:: ያላልኩት ስላላመንኩበት ብቻ ነው አለ::" መለስ እዚህም ላይ እውነቱን ነበር::

ከዚህ በኋላ በጉዳዩ ላይ ድምጽ ሲሰጥ አብዛኛው አመራር "መለስ መሬት እንስጥ አላለም" ብሎ በድምፁ አረጋገጠ:: አንጃ የፈጠረው ቡድን አባላት ግን ድምፀ-ተዓቅቦ ሆኑ:: መለስ በድምጽ ቢያሸንፍም በሂደቱና በጥንት ጓዶቹ አካሔድ ከባድ ሀዘን ተሰማው:: ያም ሆነ ይህ ስብሰባው በመለስ አሸናፊነት ሲጠናቀቅ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት አልፎ ስለነበር ሁሉም ሰው በጥድፊያ ወደየቤቱ አመራ:: እኔና ሕላዌ ዮሴፍ ደግሞ የቃለ-ጉባኤ ወረቀቶቹን ሰብስበን ወደመኪና ለማስገባት ስንሔድ መለስን በአዳራሹ አንድ ጥግ ቆሞ ምርር ብሎ ሲያለቅስ አገኘነው:: ስብሰባው ላይ አብረነው ስለነበርን በማሸነፉ መደሰት ሲገባው በጥልቅ ያዘነበት ምክንያት ብዙም አልተሰወረብንም:: ሁሉም የሥራ አስፈጻሚ አባላት ወደየቤታቸው ሲቻኮሉ እርሱ ግን በተሰበረ መንፈስ ወደቤቱ ለመሔድ እንዳልተቻኮለ ለመገንዘብ አላዳገተንም:: ጥቂት ካጽናናነው በኋላ ሰኞ እለት ወደቢሮው እንደምመጣና እንደምንወያይ ተግባብተን ወደቤቱ ሸኘነው::

በቀጠሯችን መሠረት ሰኞ ከሰዓት በኋላ ወደቢሮው አመራሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ በድርጅቱ ውስጥ ስላለው አዲስ ሁኔታ በግልጽ ተነጋገርን:: ከዚያ በፊት ስለልዩ ልዩ የድርጅቱ ችግሮች በተደጋጋሚ እናወራ የነበረ ቢሆንም፣ በጦርነቱ ወቅት ስለተነሳው ልዩነትና ስለሌሎች ጓዶች አቋም ከመድረክ ውጭ ሳት ብሎት አንስቶልኝ፣ እኔም ጠይቄው አላውቅም ነበር:: ይህም ሁላችንም የውስጠ ድርጅት ልዩነት የሚፈታበትን ዲሲፕሊን ጠንቅቀን ስለምናውቅና በዚህም በጥብቅ ስለምንመራ ነበር:: ልዩነቱ የአደባባይ ምስጢር ከሆነ በኋላማን ለመነጋገር የሚከለከል ዲሲፕሊን ሊኖር አይችልም ነበርና በጉዳዩ ላይ በዝርዝር ተወያየንበት:: በአመራሩ መካከል የተከሰተውን ልዩነት መታዘብ ከጀመርኩ በኋላ ድርጅታችን ከባድ ችግር ላይ እንደወደቀ

ለመገንዘብ ብዙም አላዳገተኝም ነበር።

በበኩሌ ከሰማኒያዎቹ መጨረሻ ለዚያውም ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ዓመታት አስቀድሞ ድርጅቱ የሚያጋጥሙት ፈተናዎች እየበዙ በመሔድ ላይ እንደሆኑ ስታዘብ ቆይቻለሁ። በተለይ በቅርብ የማውቀው ታምራት ላይኔ ከድርጅቱ ዲሲፕሊን ሲያፈነግጥ፣ በዚያ ወቅት ከነበሩ የኦህዴድ መሪዎች አንዳንዶቹ ለብልሽት ሲዳረጉ ጉዳዩ መነጋገሪያ ከሆነ ከርሟል። ከሕወሓትም እንደስዬ አብርሃ የመሳሳሉ ሰዎች ቤተሰባቸውን ለመጥቀም ባልተገባ አቅጣጫ መጓዝ ጀምረዋል እየተባለ ቢያንስ በወሬ ደረጃ በሰፊው ይናፈስ ስለነበር ሁኔታችን አሳሳቢ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረስኩ ሰነባብቻለሁ። ነገር ግን ከጦርነቱ ጋር በተያያዘው ልዩነት በመድረክ ከሚኖረኝ ተሳትፎ በስተቀር እያንዳንዷን ሂደት በጥልቀት በማስተዋል እየታዘብኩ መጓዝን እመርጥ ነበር።

ከመለስ ጋር ስለሁኔታው በዝርዝር አንስተን ስንወያይ በድርጅቱ ውስጥ የሚታየው ዝቅጠት እንደሚያስፈራውና ይህን በተመለከተ ያዘጋጀው ጽሁፍ እንዳለ አጫወተኝ። ጽሁፉ ያኔ በነበረው የአመራሩ ሁኔታ የማሸነፍ ዕድል አለው ብሎ ለማመን እንደተቸገረ፣ ነገር ግን በበኩሉ የሚጠበቅበትን በማድረግ "ከሕሊና ተጠያቂነት ነጻ ለመሆን" እንደተዘጋጀ ገለጸልኝ። ጽሁፉን ማንበብ ከፈለግሁ ደግሞ ሊሰጠኝ እንደሚችልና ካነበብኩት በኋላ ብንገናኝ ጥሩ እንደሆነ አነሳልኝ። የመለስ ጽሁፍ ለዚያውም በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ተገኝቶ እምቢ የሚባል አልነበረም። ተቀብዬ ወስጀ ከእጀ ሳላወርድ አንብቤ ጨረስኩት። ደጋግሜም አነበብኩት። በጣም መሠረታዊና ብዙ ሊያነጋግር የሚችል ምርጥ ጽሁፍ ነበር።

በዚህ ጽሁፍ ከዓመታት የፖለቲካ መፋዘዝ በኋላ የቦናፓርቲዝም ጽንሰ-ሀሳብ እጅግ በሚመስጥ ንጽጽራዊ ትንታኔ ቀርቧል። ከመለስ ጋር በቀጠሯችን እንደተገናኘን የነበረኝን የስምምነትና የልዩነት አስተያየት አቀረብኩለት። በመሠረታዊው ጉዳይ ተስማምቼ በግንባሩ ውስጥ ከነበሩ ማርከሣዊ ሌኒናዊ ፓርቲዎች አኳያ ያልዳሰሳቸው ጉዳዮች እንደነበሩ ያነሳሁለትን ሀሳብ በይደር አቆይተን ከትግርኛ በአማርኛ እንድተረጉመው ተስማምተን ሥራው ተጀመረ። መለስ ለከርከር መነሻ እንዲሆን ያቀረበው የመጀመሪያው ጽሁፍ ይኸው የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋ የሚለው ቢሆንም ሌሎች ተሟጋቾች በበኩላቸው ይህንኑ ፈለግ ተከትለው የየራሳቸውን የመልስ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ በር ከፈተ። በዚህ የመለስ ጽሁፍ ስለተራመደው የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋ ይዘት በትክክል ለመረዳት ይቻል ዘንድ ጉዳዩን በዝርዝር ወደመመልከት ማምራት ተገቢ ቢሆንም በቅድሚያ የቦናፓርቲዝምን ጉዳይ ከሥር ከመሠረቱ መመልከት ሳይጠቅም አይቀርም። ለዚህም ሲባል በምድራችን የመጀመሪያው ቦናፓርቲስታዊ መንግሥት የተመሠረተባትን ፈረንሳይ ሁኔታ አጠር አድርጐ መመልከት ተገቢ ይሆናል።

ፈረንሳይ በአውሮፓ ውስጥ በህዝብና በገዥዎች መካከል ከባድ ፍልሚያ

ከሚካሔድባቸውና ምናልባትም ብዙ ጊዜ ወደውጤት ከሚጠጋባቸው የአውሮፓ አገሮች ቀዳሚዋ ነች፡፡ ይህ ትግል ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሚካሔዱ ከባድ የአርሶ አደር አመፆች መልክ ይገለጽ የነበረ ነው፡፡ በተጨማሪም በሠራተኛውና በባለሀብቱ፣ በባለሀብቱና በፊውዳሎቹ ወዘተ... መካከል በሚካሔድ ከባድ የእርስ በእርስ ጦርነት መልክ የሚገለጽም ነበር፡፡ ይህም ሆኖ በፈረንሳይ ለቦናፓርቲስታዊ መንግሥት መፈጠር ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ የነበረው የአርሶ አደሩ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም የመለስን የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት መሠረተ-ሀሳብ ለመገንዘብ በፈረንሳይ ለቦናፓርቲስታዊ መንግሥት መመሥረት ዋነኛ ቅድመ ሁኔታ የነበረው ነጻ የወጣና እርካታ የተሰማው አርሶ አደር የተፈጠረበትን ሂደት በአጭሩ ከመመልከት የተሻለ ነገር የለም፡፡

በስሙኒዋ ጌታ በቀዳማዊ ናፖሊዮን ቦናፓርት ስም . . .፣

ቀደም ሲል እንደተመላከተው ፈረንሳይ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ እስከከፍለ ዘመኑ አጋማሽ ድረስ በወሳኝነት የአርሶ አደሮች አገር ነበረች፡፡ ታዲያ ይደርስባቸው የነበረውን ግፍ መሸከም ያቃታቸው የፈረንሳይ አርሶ አደሮች እ.ኤ.አ. በ1789 ባካሔዱትና በምድራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ በሆነው ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፊውዳላዊውን ሥርዓት እስከማንኮታኮት ደረሱ፡፡

በ18ኛው ከፍል ዘመን ማብቂያ ላይ የተቀሰቀሰው ይህ የፈረንሳይ አርሶ አደሮች አመጽ በወቅቱ በአገሪቱ ሰፋ ባለ ደረጃ ተፈጥረው የነበሩ ተራማጆች ኃይሎች "እኩልነት፣ ነጻነትና ወንድማማችነት" በሚሉ መፈክሮች ይመሩት የነበረ ንቅናቄ ነው፡፡ የንቅናቄው መሪዎች ኑሮ ያስመረረውን አርሶ አደር ከግፍ አገዛዝ ለማላቀቅ ፊውዳላዊውን የአፈና መዋቅር በመበጣጠስ ሳይወሰኑ መሬት አካፈሉ። በተጨማሪም በወቅቱ የፈረንሳይን አርሶ አደሮች እጅግ ያስመረረውን ግብር እስከማንሳት ደረሱ፡፡ በ1794 እ.ኤ.አ ሥልጣን የያዘው ቀዳማዊ ናፖሊዮን ለፈረንሳይ አርሶ አደሮች ያደረጋት የግብር ቅናሽ 0.25 የፈረንሳይ ፍራንክ ወይም በእኛ አገር የገንዘብ አቆጣጠር ስሙኒ የነበረች ብትሆንም የመሬቱ ባለቤት ለመሆን መቻሉና ስሙኒ የግብር ቅናሽ ማግኘቱ አርሶ አደሩን ከፍተኛ እርካታ እንዲጐናጸፍ አደረገው፡፡

ይህ በታላቁ ናፖሊዮን ዘመን ገበሬውን ለነጻነት ያበቃ እርምጃ የፈረንሳይ አርሶ አደር ለናፖሊዮን መንግሥት የማይናወጥ ድጋፍ ምንጭ እንዲሆን አደረገው፡፡ ታላቁ ናፖሊዮንም በፈረንሳይ አርሶ አደሮች ዘንድ ከትውልድ ወደትውልድ የሚሸጋገር ዝና አተረፈ፡፡ የፈረንሳይ አርሶ አደሮች የናፖሊዮን ስም በተነሳ ቁጥር ስለተካፈሉት መሬትና ስለተቀነሰችላቸው የፈረንሳይ ስሙኒ እያስታወሱ ድጋፍ መስጠታቸውን ልምድ አደረጉት፡፡ ናፖሊዮን አውሮፓን ያስገበረበት ግዙፉ የፈረንሳይ ሠራዊት መሬት ከተካፈለውና የግብር ይቀነስልኝ ጥያቄው ተመልሶለት ከፍተኛ እርካታ ካገኘው አርሶ አደር አብራክ የተፈጠረ ሊሆን የቻለውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ከዚህ

ጊዜ ጀምሮ ጥያቄው የተመለሰለትና እርካታ የተሰማው አርሶ አደር ሚና ከለውጥ ኃይልነት ወደሥርዓት ጠባቂነትና አስቀጣይነት ተሸጋገረ። ይህ ከምንም ነገር በላይ በፈረንሳይ ሁለተኛው ሪፐብሊክ ከተቋቋመበትና የዚህ መንግሥት መሪ የነበረውና በአስመሳይነት እንጅ በሌላ የማይታወቀው ሉዊ ቦናፓርት ወደሥልጣን ከመጣበት ሂደት ጋር ተያይዞ በግልጽ የታየ ነበር።

ታላቁ ናፖሊዮን ቦናፓርት ከሞተ ከሠላሳ አምስት ዓመታት በኋላ ብቅ ያለው ሉዊ ቦናፓርት እ.ኤ.አ. በ1851 በተካሔደው አገራዊ ምርጫ መወዳደሪያው ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ፣ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት የነበረው አጐቱ ታላቁ ናፖሊዮን ለፈረንሳይ አርሶ አደሮች የስሙኒ ግብር ቅናሽ ማድረጉን ነበር። የስሙኒያቸው ጌታ ማን እንደነበር ለሚያውቁት የፈረንሳይ አርሶ አደሮች አስመሳዩ ሉዊ ቦናፓርት በእውነተኛው ናፖሊዮን ቦናፓርት ጭምብል መምጣቱ ጉዳያቸው አልነበረም። ለእነርሱ ትልቁ ነገር ኢያት ቅድመ አያቶቻቸው በነገሯቸው አፈታሪክ ተመርተው ውለታ መመለሳቸው ብቻ ነበር። እናም በአጐቱ ዝና ለማትረፍ ለቆረጠው ሉዊ ቦናፓርት በምርጫው የአርሶ አደሩን ድምጽ አግኝቶ ለማሸነፍ "እኔኮ የስሙኒዋ ጌታ የታላቁ ናፖሊዮን የአጐት ልጅ ነኝ" ማለቱ ብቻ በቂ ነበር። በዚህ ሥልት የተመራው ሉዊ ቦናፓርት ቀደም ሲል የወቅቱ ጥያቄዎቹ ሁሉ ተመልሰውለት እርካታ በተሰማው የፈረንሳይ አርሶ አደር ድጋፍና ትከሻ ወደሥልጣን ለመምጣትና አምባገነናዊ ልማታዊ መንግሥት ለመገንባት ዕድል አገኘ።

ዳግማዊ ናፖሊዮን በምርጫው ካሸነፈ በኋላ በፈረንሳይ የገነባው አዲስ መንግሥት ሦስት በጥብቅ የተቆራኙ መለያ ባሕርያት ነበሩት። የመጀመሪያ መለያው ፈረንሳይን በልማታዊ አቅጣጫ ማንቀሳቀሱ ነበር። በአውሮፓ ቀድመው ከተፈጠሩት ልማታዊ መንግሥታት እንደአንዱ የሚቆጠረው የዳግማዊ ናፖሊዮን መንግሥት በፈረንሳይ ታይቶ የማይታወቅ የመሠረተ-ልማት ግንባታ ያከናወነ ነበር። ከዓለማችን ውብ ከተሞች አንዷ የሆነችው የፓሪስ ከተማ በሚያስገርም ጥራትና ውበት የተገነባችውም በዚሁ ዘመን ነበር። ሁለተኛው የመንግሥቱ መገለጫ ባሕርይ ሙስና እጅግ በሚዘገንን ደረጃ የተስፋፋበት መሆኑ ነበር።

ወቅቱ ፈረንሳዊያን ሀብት ለማከማቸት በተፈጠረላቸው መልካም ዕድል ለመጠቀምና ለመክበር የሚሽቀዳደሙበት ወቅት ነበር። በባለሀብቱና በድሃው ህዝብ መካከል የሥራ ክፍፍሉ ገና ጠንከሮ ባልተለየበት በዚህ ወቅት፣ ሁሉም ሰው በቀላሉ የሀብት ማማን መቆናጠጥ እችላለሁ ብሎ እስከማመን ደርሶ ነበር። ይህን ተከትሎ ደግሞ በእጅም በእግርም ተጉዞ መበልጸግ የወቅቱ መለያ ሆነ። ሙስናና ዝቅጠት በምድረ ፈረንሳይ እንደሰደድ እሣት ተቀጣጠለ። ከዚህ የፈረንሳይ ቦናፓርቲስታዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት በመነሳት በልማት መገስገስ የሚጀምሩ አገሮች አሐዱ ብለው ሲጀምሩ ሙስና ዋናው ፈተና ሆኖ አብሮ እንደሚወለድ ታዬ። የልማታዊ ጉዞው ስኬታማነት ወይም ክሽፈት የሚወሰነውም ይህ ሙስና እንዲያድግ ወይም እንዲከስም

በሚደረገው ትግል ልከ ሆነ።።

የቦናፓርቲስታዊ ሥርዓት ሦስተኛው ዓይነተኛ መለያ ደግሞ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ወይም አምባገነናዊ መሆኑ ነበር። በእርግጥ ዳግማዊ ናፖሊዮን በፈረንሳይ አገር በኮካሔደ ቀጥተኛ ምርጫ የአርሶ አደሮቹን ድጋፍ አግኝቶ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሥልጣን ላይ የወጣ ቢሆንም ከጅምሩ በከተሞች ከባድ የሠራተኛ ተቃውሞ ያልተለየው መንግሥት ነበር። ህዝቡ በተስፋፋው ሙስናና ምግባረ-ብልሹነት በመማረር በሥርዓቱ ላይ የሚያካሂደው አመጽ እየበዛ መሔዱን ተከትሎ፣ ይህን ህዝባዊ አመጽ የሥጋት ምንጭ አድርገዉ ይመለከት የነበረው ሉዊ ቦናፓርት አፈናና የመብት ረገጣን ዋነኛ የአገዛዝ ስልቱ ማድረግ መረጠ። በዚህ የተነሳ ልማታዊ ብቻ ሳይሆን፣ አምባገነናዊ ባሕሪ ያለው መንግሥት ሆነ።አዲሱ የፈረንሳይ ሥርዓት መገንባት በጀመረበት በዚህ ዘመን የነበረው መንግሥት የተቆረናው ይህ ልማታዊ፣ በሙስና የተዘፈቀና አምባገነናዊ ባሕሪ ግን ከምንም ነገር ያልተነሳ አልነበረም። ይልቁንም የወቅቱ የፈረንሳይ አርሶ አደር ያሳየው ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ነበር።።

የመሬትም ሆነ ሌሎች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች፣ የተመለሰሉትና እርካታ የተሰማው አርሶ አደር የሚያሳየው ባሕርይ ጥያቄዎቹ ያልተመለሰሉት አርሶ አደር ከሚያሳየው በዓይነቱ የተለየ እንደሆነ ከፍ ሲል ከተገለጸው የፈረንሳይ ልምድ በመነሳት ሊታይ የሚችል ነው።። በፈረንሳይ አርሶ አደሩ ከመጀመሪያው አብዮት በፊት ከነበሩት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱም በሚያረካ አኳኋን የተመለሰለት አልነበረም። የአገሪቱ መሬት በፊውዳሎች እጅ ተከማችቶ አርሶ አደሩ ተራ ጭሰኛ ብቻ ነበር። ላቡን አንጠፍጥፎ ካመረተው ሀብትም እጅግ አነስተኛ ድርሻ ብቻ ያገኝ ነበር።። በዚህ ላይ ሰብዓዊ ክብሩን የተነጠቀ፣ የተናቀና የተዋረደ ስለነበር አርሶ አደሩ በእነዚህ ምክንያቶች በመከፋት ነገረ ሥራው ሁሉ በሥርዓቱ ላይ ማመጽ ሆነ። ፂኦቼናን ተቀብለውና አሜን ብለው መኖርን ባለመምረጥ ጥያቄዎቹ እስኪመለሱለት ድረስ አንዳንዴ በተከታታይ ዓመታት ሌላ ጊዜ ደግሞ እያሰለሰ ለሥርዓት ለውጥ የሚታገል አርሶ አደር ነበር።። በአውሮፓ በተለይ ደግሞ በፈረንሳይ በ17ኛውና 18ኛው ክፍለ ዘመናት የአርሶ አደር አመፆችና ጦርነቶች የበዙበት ምክንያትም ይኸው ነበር።።

ከዚህ በመነሳት ጥያቄው ያልተመለሰለት አርሶ አደር የትም ይሁን መቼ የአመጽና የለውጥ ኃይል እንደሚሆን ለመገንዘብ ይችላል።። አርሶ አደሩ በሕይወት ዘመኑ ለአርሶ የሚያስብና የሚቆረቆር መንግሥት የሚያገኘው ከተራዘመ ሂደት በኋላ፣ ለዚያውም ዘመናት ካለፉ በኋላ በመሆኑ እጅግ አብዛኛው የአርሶ አደር ትውልድ በአርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ማለፉ የተለመደ ነው።። ጦርነትና ግጭት እያንገሸገሸውም ቢሆን በራሱና በሌሎች ማኅበራዊ ኃይሎች ምክንያቶች በሚቀሰቀሱ ግጭቶች ውስጥ በአንዳች ምክንያት ተገፋፍቶ ወይም ተገዶ ይገባል።። በኢትዮጵያ የዘመነ መሣፍንት ዋነኛ ተዋጊ ኃይል አርሶ አደሩ ነበር።። ማዕከላዊ መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ

የተካሔዱት ጦርነቶችም በአርሶ አደሩ ተዋጊነት የተካሔዱ ናቸው፡፡ በደርግና በነጻነት ታጋዮች መካከል በተካሔደው ረጅም ጦርነትም አርሶ አደሩ ዋነኛው ተዋጊ ኃይል ነበር፡፡

ዕድሜ ልኩን በሰከነ ሕይወት አርሶና አንደፋርሶ በሰላም የመኖር ዕድል ተነፍጐት የቆየው አርሶ አደር ለጥያቄዎቹ ሁሉ በጐ ምላሽ ካገኘ በኋላ ግን ሰላምን አጥብቆ የሚሻ፣ ለውጥን የሚፈራና የሚጠላ የሰላም ኃይል መሆን ይጀምራል፡፡ አርሶ አደሩ በጥቂቱም ቢሆን የሚያስብለት መንግሥት አግኝቶ በተለይ መሬት ተካፍሎ አነሰም በዛም የራሴ የሚለው የእርሻ ማሳ ኖሮት ማደር ሲጀምር ደግሞ፣ በሁለመናው ከማንም ሳይነካካ አርሶ ለራሱና ለቤተሰቡ ቀለቡን በማምረት ላይ መወሰን ይፈልጋል፡፡ ከማናቸውም ግጭት ርቆ ለብዙ ዓመታት ሲናፍቀው የኖረውን ሰላም ለማጣጣምና በሰላም አርሶ ለመብላት ቅድሚያ መስጠት ይጀምራል፡፡ በተለይ ከእጅ ወደአፍ ከሆነ አመራረት ያልተላቀቀ ወይም በገበያ ያልተሳሰረ አርሶ አደር ከየትኛውም ጐረቤቱ ጋር ሳይነካካ ከሌላውም ዓለም ተነጥሎ መኖር ይችላል፡፡

መለስ ይህን የመሰለውን አርሶ አደር ወደአቶምነት የተቀየረና ራሱን ችሎ፣ ከሌላው ተነጥሎ የሚኖር አርሶ አደር (Atomized Peasant) ይለዋል። በዚህም የተነሳ ጥያቄዎቹ ባልተመለሱበት ወቅት አገር ምድሩን በአመጽ የሚያንቀጠቅጠው አርሶ አደር፣ አሉኝ የሚላቸው ጥያቄዎች ተመልሰውለት በተናጠል የሚኖር ከሆነ በኋላ በተነጻጻሪ ለውጥ ፈላጊ መሆኑ ያቋርጣል፡፡ መሬቱን አርሶ እንደነገሩ በተገኘች ምርት ሆዱን መሙላት የሥልጣኔ መጨረሻ እንዳልሆነች እያስተማረና ዓይኑን እየገለጠ በሌላ አዲስ ፍላጐት የሚያነሳሳው መሪ እስካላገኘ ድረስ ደግሞ ዓለምን ዘንግቶ በዓለምም ተዘንግቶ በራሱ ጐጥ ተወስኖ ሊኖር ይችላል፡፡ በዚህም ከለውጥ ኃይልነት ይልቅ የሥርዓት ጠባቂ ኃይል ወደመሆን መሸጋገር ይጀምራል፡፡

ይህም ማለት በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አርሶ አደሩ ያገኛትን ትንሽ ድል እስካልነካት ድረስ ከመንግሥት ሳይጣላ ይልቁንም መንግሥትን እያወደሰና የመንግሥትን የተሳሳቱ ባሕርያት ተሸክሞ ወደመኖር ሊሸጋገር ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአውሮፓ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ አገሮች ሁሉ የታየ ክስተት ነው፡፡ የፈረንሳይ አርሶ አደሮች የስሙኒያቸውን ጌታ ሳይረሱ ዘመን ካለፈ በኋላም እያወደሱት መኖራቸው፤ አልፎ ተርፎም አምባገነኑን ሉዊ ቦናፓርት በመደገፍ ድምጽ መስጠታቸው፣ በእርግጥም ጥያቄው የተመለሰለት አርሶ አደር ለመንግሥት በጐ አመለካካት ከያዘ የዘመናት ውለታን እያስታወሰ በመመለስ ይሉኝታ ጭምር እንደሚሸበብ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ አምባገነንነትን ፈቅዶ የሚሸክም ኃይል እስከመሆንም ይደርሳል፡፡

ይህ አርሶ አደሩ ከሕብረተሰቡ ውስጥ በቁጥሩ ከፍተኛ በሚሆንበትና የአገሪቱም ዕድል

በብዙኃኑ ድምጽ በሚወሰንበት ሁኔታ አደገኛ ሊባል የሚችል ውጤት ጭምር ሊያስገኝ የሚችል ነው። በአርሶ አደር ድጋፍ ለውጥና ዴሞክራሲ ሊመጣ እንደሚችለው ሁሉ አሁንም በአርሶ አደር ድጋፍ አምባገነንነት የተጠናወተው መንግሥት ሊፈጠርና በሥልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል። አርሶ አደሩ የሚገኝበት ሁኔታ የሥርዓትን ዕድል በበጎም በጐ ባልሆነ መልኩም ሊወስን፣ ስለዚህም ደግሞ እንደሁኔታው የሥርዓት ጥንካሬ ወይም የሥርዓት አደጋ ምንጭ ሊሆን ይችላል። ይህ መሬት የተካፈለ አርሶ አደር በነበረባቸው አገሮች ሁሉ የታየ ክስተት ነው።

የፈረንሳይና በሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች ልምድ ላይ የተመሠረተው ይህ ትንታኔ ጥያቄው የተመለሰለትና አርካታ የተሰማው አርሶ አደር ዝቅጠትን ከመሸከም አኳያ ዋና መደላድል ሊሆን ይችላል ለሚለው ንድፈ-ሀሳባዊ መላምት ዋናው መነሻ ነው። ነገር ግን ለቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠትና ለአምባገነንነት መደላድል ሆኖ የሚያገለግለው ጥያቄው የተመለሰለት አርሶ አደር ብቻ አይደለም። ካለ አግባብ በሥልጣን ለመጠቀም የሚሻው ንዑስ ባለሀብት (በተለይ ምሁር) የተቀዛቀዘ ፖለቲካዊ ሁኔታ ባለበት ሥልጣን ላይ ከተቀመጠም ለዚህ ዓይነቱ አደጋ አንድ ሌላ ቁልፍ ምንጭ ይሆናል። ጥያቄው የተመለሰለት በመሆኑ ተቀዛቅዞ የሥርዓት ጠባቂነት ሚና መጫወት በጀመረ አርሶ አደር ትከሻ ላይ ወደሥልጣን የወጣ ንዑስ ባለሀብት ሌላው የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አራማጅ ይሆናል። ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ ሌላ ጉዳይ በመሆኑ ንዑስ ባለሀብት ማነው? ባሕሪያቱስ ምንድናቸው? እነዚህ ባሕርያትስ ከሥርዓት ጤንነትና ብልሽት ጋር ያላቸው ዝምድና ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ ጉዳዩን ትንሽ ፈታ አድርጐ ማየት ተገቢ ይሆናል።

ንዑስ ባለሀብት በመባል የሚታወቀው የሕብረተሰብ ክፍል አንድም መነሻ የምትሆነው ትንሽ ካፒታል ወይም ደግሞ ሥልጠናና እውቀት ይዞ የሚገኝ ነው። በዚህች መነሻ በመታገዝ ራሱን ወደከፍተኛ ባለሀብትነት የማሸጋገር ሕልም ቢኖረውም ይህ ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሳይሳከለት የቆየ ማኅበራዊ ኃይል ነው። ከዚህም አልፎ በከባድ ውድድር ላይ በተመሠረተው ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት ያለማቋረጥ ወደድኅነት ረድፍ ሊገፋ የሚችል በመሆኑ አብዛኛውን የሕይወትን ዘመኑ በሥጋትና በሰቀቀን የሚኖር የሕብረተሰብ ክፍል ነው።

ይህ ማኅበራዊ ኃይል ከሥልጣን የራቀና በምዝበራና በውድድሩ እየተገፋ ወደድኅነት የሚያሽቆለቁል በሚሆንበት ጊዜ ለለውጥ ድምፁን ከፍ አድርጐ የሚያሰማና ተራሮችን የሚያንቀጠቅጥ የትግል ኃይል እስከ መሆን ይደርሳል። በተለይ ደግሞ ልክ እንደ እርሱ ሁሉ ጥያቄው ካልተመለሰለት አርሶ አደር ትግል ጋር የወገነና በዚህም ከባድ ተፅዕኖ የሚያርፍበት ሆኖ ሲገኝ በመለስ አገላለጽ አብዮታዊነቱ ለግምት እስከሚያስቸግር ድረስ ይጠነክራል። የአርሶ አደሩ ትግል በሚቀዛቀዝበት፣ በተለይ ደግሞ ራሱ ንዑስ ባለሀብቱ ይህን በመሰለው ወቅት ሥልጣን ላይ የተቀመጠ በሚሆንበት ጊዜ የለውጥ ሀሳብ የማመንጨትና ግንባር

ቀደም ፊጻሚ የመሆን ችሎታው ቀስ በቀስ መመናመን ይጀምራል። ሥልጣን እየተመቸው በሒደ ቁጥር ያለውን ለመጠበቅ እንጂ ለውጥ ለማምጣት የማይተጋ እጅግ ወግ አጥባቂ ኃይል ወደመሆን ያመራል። ለውጥና ቀጣይነት በትክክለኛ ሚዛናቸው ተጠብቀው መካሔድ ባለባቸው ሕበረተሰቦች ውስጥ ከለውጥ ይልቅ የነበረውና ያለው ተጠብቆ እንዲሔድ የመፈለግ አዝማሚያው ገሎብቶ ይወጣል።

እንደኢትዮጵያ ባለ የቆየውን ኋላቀርነት ጠበቆ ከማቆየት ይልቅ በየእለቱ እያፈረሱ መገንባትን በሚጠይቅ አገር ለውጥን የሚጸረር እስከመሆንም ይደርሳል። የአንድ አገር ዕድል ጥያቄው ተመልሶለት እርካታ ባሳደረ አርሶ አደርና ሥልጣን ላይ ወጥቶ በተመቸው ንዑስ ባለሀብት እጅ በወደቀበት ጊዜ ሁሉ ቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠትና በዚህ ላይ የተመሠረተ አምባገነናዊነት የማይቀር ውጤት ይሆናል። መለስ በቦናፓርቲስት ዝቅጠት ዙሪያ ዓለም አቀፍ ልምድን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ጽሁፍ ከብዙ በጥቂቱ እነዚህን ነጥቦች በመልከ በመልካቸው ደርድሮ የያዘ ነበር።

ኢትዮጵያና የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋ

ዓለም አቀፉ የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልምድ ከተወሰደ በኋላ ይህንኑ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ለመመልከት በተደረገው ጥረት በእርግጥም አገሪቱ ለተመሳሳይ አደጋ መጋለጥ እንደጀመረች ተረጋገጠ። የኢትዮጵያ አርሶ አደር ቀደም ባሉት ዘውዳዊ ሥርዓቶች የመሬቱ ጌታና የላቡ ውጤት ተጠቃሚ አልነበረም። በአገራችን ይፈጸም የነበረው አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና ዋነኛ ሰለባም ነበር።

በዚህ የተነሳ አርሶ አደሩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍትህ እንዲረጋገጥለት ለዘመናት ተፋልሟል። የብሔር እኩልነት እንዲከበር ያላሰለሰ ትግል አካሂዷል። ሃይማኖታዊ ጭቆና ተወግዶ ፍትህ እንዲሰፍን በአጠቃላይ ለዴሞክራሲ መስፈን ከባድ መስዋዕትነት ከፍሏል። የደርግ ሥርዓት በላዩ ላይ ይፈጽመው የነበረው የኢኮኖሚ ምዝበራ ተወግዶ የምርት ነጻ ተጠቃሚነት መብቱ እንዲከበርም ተከታታይ ትግል አካሂዷል። ደርግ በ1982 ዓ.ም. የሕብረት ሥራ ማኅበራትን እንዲያፈርስና የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ እከተላላሁ እንዲል ያስገደደውም በዋነኛነት ይኸው የአርሶ አደር ትግል ነበር።

የአርሶ አደሩ ትግል ኃያልነት የሚታየው ግን መሠረታዊ ጥያቄዎቹ ባልተመለሱበት ጊዜ ሁሉ የተካሔደ ከመሆኑ ጋር ብቻ ተያይዞ አልነበረም። የኢትዮጵያ ተራማጅ ክፍሎች ሁሉ ግንባር ቀደም የታጋይነት ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ ያስቻለ ከባድ አብዮታዊ ተፅዕኖ የነበረው በመሆኑም ጭምር ነው። ገናናው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በመሬት ፍትሃዊ ባለቤትነትና

በዛብሔር፡ በሃይማኖተና በጾታ እኩልነተ ጥያቄዎት ዙሪያ ላቀነቀናቸው ትራማጅ አስተሳሰቦች ዋነኛ ምንጩ ይኸው የአርሶ አደሩ አብዮታዊ ትግል ነበር፡፡ ደርግ በ1967 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በዕድገት በሕበረት ዘማቾች እየተመሩና በራሳቸው ተነሳሽነት ከፊውዳሎች እጅ መሬት መንጠቅ የጀመሩ አርሶ አደሮችን "አርፋችሁ ተቀመጡ፣ ካልሆነ ከባድ ቅጣት ይደርስባችኋል" እንዳላለ፣ በዓመቱ አጋማሽ የመሬት አዋጅ በማውጣት መሬት ሊያከፋፍል የተገደደው አርሶ አደሮች ለመብታቸው ባካሔዱት ትግል ነበር፡፡

በተበተነ አኳኋን ሲካሔድ የነበረው ይህ የአርሶ አደሩ ትግል በኢህአዴግ መሪነት ደርግን ለማስወገድ ከበቃ በኋላ ደግሞ የህዝቡን የዘመናት ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ህዝቡ የሥልጣን ባለቤት ከመሆኑም በላይ በከተማም በገጠርም ቀና ምላሽ ተነፍጓቸው ለቆዩ ህዝባዊ ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ መስጠት ተጀመረ፡፡ አርሶ አደሩ በደርግ አገዛዝ የመጀመሪያ ዓመታት ለመሬት ባካሔደው ትግል በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ክፍሎች ለጥያቄው በከፊል ምላሽ አስገኝቶ ነበር፡፡

በትጥቅ ትግሉ ወቅት ደግሞ በትግራይና በከፊል የአማራ አካባቢዎች አዲስ የመሬት ክፍፍል ተካሂዶ ነበር፡፡ በተጨማሪም ከደርግ ውድቀት በኋላ በቀሩት የአማራ አካባቢዎች በደርግ ዘመን የተፈፀሙ ስህተቶችን በማስተካከል ጭምር መሬት እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡ በዚህም በአማራ ከልል በጎጃም፣ በጐንደር፣በሰሜን ወሎና ሰሜን ሸዋ እስከ አሥር ሚሊዮን ለሚደርሱ አርሶ አደሮች መሬት አካፍሏል። ከ570ሺህ በላይ እማወራ ሴቶችም የመሬት ባለቤት ለመሆን ችለዋል፡፡ በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በራሳቸው ትግል የመሬት ባለቤትነትን ሲያረጋግጡ ይህ የዘመናት ጥያቄያቸው መልስ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ከደርግ መንግሥት መወገድ በኋላ አርሶ አደሩ የተጐናጸፈው ሌላው ድል የምርቱ ነጻ ተጠቃሚ ሊሆን መቻሉ ነበር፡፡ ገበሬዎች ምርታቸውን በፈለጉት ጊዜ፣ በታና ዋጋ የመሸጥ ነጻነት መጐናጸፋቸው፣ የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት በነጻ ገበያ መርሕ ካልሆነ በስተቀር፣ በኮታና በግዳጅ የሚገዛበት ሥርዓት መዘጋቱ ተቋሙ ባይፈርስም የምዝበራ ማስፈጸሚያ መሣሪያ መሆኑ እንዲቋረጥ መደረጉ፣ ከዚህም አልፎ አርሶ አደሮች የዋጋ ውድቀት በሚያጋጥማቸው ጊዜ በማይጐዱበት ተመን እህል እየገዛ ገበያ የሚያረጋጋ ተቋም እንዲሆን መደረጉ የዚህ ማረጋገጫ ነው፡፡ በመሆኑም የአገራችን አርሶና አርብቶ አደሮች ከደርግ ውድቀት ማግስት ቀደም ሲል ላነሷቸው መሠረታዊ የኢኮኖሚ ጥያቄዎቻቸው በሙሉ የተስተካከለ ምላሽ አግኝተዋል፡፡

አርሶ አደሩ በፖለቲካዊ መስክ የተጐናጸፋቸው መብቶችም ተመሳሳይ ባሕርይ ነበራቸው፡፡ ከዘመናት ትግል በኋላ የብሔር እኩልነት መከበሩ፣ በእምነቶች መካከል የነበረው አድሎ ተወግዶ ሁሉም ሃይማኖቶች በእኩልነት መታየት መጀመራቸው አዲሱ ሥርዓት ያስገኘለት

መሠረታዊ ጥቅሞች ነበሩ። የዜግነት መብቶች እውቅና ተሰጥቷቸው የሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑና፣ መንግሥት በአርሶ አደር ወሳኝ ድምጽ የሚቋቋምበት የምርጫ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም መጐናጸፉ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ እርካታ እንዲሰማቸውና ያገኙትን ድል በሰላም እንዲያጣጥሙ የሚገፋፋቸው ሆነ። በዚህ አኳኋን ለረጅም ጊዜ የተንከባለሉ ነባር ጥያቄዎቻቸው የተመለሱላቸው የኢትዮጵያ ገበሬዎች እንደሰው ከመከበር አልፈው የኢትዮጵያ ወሳኝ ፖለቲካዊ ኃይል ለመሆን በቁ። ከ1997 ዓ.ም. የምርጫ ትርምስ ማግሥት የገጠሩን ህዝብ ስሜት ለመለካት በተካሔደ ጥናት፣ ገበሬው ጥያቄዎቹ በአብዛኛው እንደተመለሱለት አድርጐ ይመለከት እንደነበር ከራሱ ቀጥተኛ ምላሽ ለማወቅ ተችሎ ነበር።

አርሶ አደሮች ለምን ኢህአዴግን እንደመረጡ ሲጠየቁ፣ በወቅቱ የነበሩትን ድክመቶችና ቅሬታዎች ከመግለጽ ሳይቆጠቡ፣ "በሕይወታችን ለአርሶ አደር የሚያስብ መንግሥት ያገኘነው ዛሬ ስለሆነ ነው" የሚል መልስ መስጠታቸው ይህንኑ ያመላክታል። ይህም አርሶ አደሩ ለቆዩ ፍትሃዊ ጥያቄዎቹ በተሰጠው ምላሽ ከፍተኛ እርካታ ማግኘት መጀመሩን አሳየ። በዚህ የተነሳም አዲሱን ሕይወት ተረጋግቶ ለማጣጣም የሚፈልግ፣ ከትግል ገሸሽ ያለና ትርምስ የማይፈልግ አርሶ አደር መሆን ጀመረ።

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በለውጡ የመጀመሪያ ዓመታት የተጐናጸፉት ድል በፈረንሳይ ወይም በነታይዋንና ኮርያ የነበሩ አቻዎቻቸው ከተጐናጸፉት ድል የሚልቅ እንጂ የሚያንስ አልነበረም። በፈረንሳይ የተገኘው ውጤት መሠረታዊ የነበረ ቢሆንም፣ ለውጡ በአርሶ አደሮች ግብታዊ ዐመጽ ላይ የተመሠረተ ስለነበር የራሱ ውሱንነት የነበረው ነው። በኢትዮጵያ ለውጡ የተደራጀ፣ በአቅድ የተመራና አርሶ አደሩ በንቃት የተሳተፈበት ሲሆን፣ የለውጡ መሪ ደግሞ ከፈረንሳይ አብዮተኞች ይበልጥ የተደራጀ ብቃት የነበረው ኢህአዴግ ነው።

በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ በተካሔደው ዴሞክራሲያዊ አብዮት የተመዘገበው ለውጥ ከፈረንሳዩ እጅግ የላቀ ነበር። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከመገንባት በመለስ መሬት ለአርሶ አደሮች ካከፋፈሉት የታይዋንና የኮሪያ መንግሥታት እርምጃዎችም በይዘቱ የላቀ ነበር። ስለሆነም በኢትዮጵያ የአርሶ አደሩን ጥያቄ በአጥጋቢ ደረጃ የመለሰው አዲስ ሥርዓት፣ በተለምዶ ለቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት ጥሩ መደላድል እንደፈጠሩ ከሚነገርላቸው አገሮች በባሰ ደረጃ ጥልቅ የአርሶ አደር እርካታ የፈጠረ ነበር። መለስ በኢትዮጵያ ለቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት ምቹ መደላድል ተፈጥሯል የሚል ትንታኔ ሲያቀርብ መነሻው ይህ የአገሪቱ ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ ብቻ ነበር። በአመራሩ መካከል የተነሳው ልዩነትም ሆነ ግለሰቦች ያራመዱት አቋም ወይም ደግሞ የፈጸሙት ስህተት ከቶም የትንታኔው መነሻ አልነበረም።

በኢትዮጵያ ጥያቄው የተመለሰለትና የረካ አርሶ አደር መፈጠሩ ከተበታተነውና የገበያ ትስስር ካልፈጠረው የገጠር ኢኮኖሚ ጋር ተያይዞ በአርሶና አርብቶ አደሮች መልካም ፈቃድና ይሁንታ የሚተማመንና የሚነግድ ኢ-ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንዲፈጠር የሚያስችል አንድ ምቹ ሁኔታ ነበር። የኢትዮጵያ አርሶ አደር ዛሬም መሉ በሙሉ ለገበያ ብሎ ወደሚያመርት ገበሬነት /Commercial Farmer/ የተቀየረ ባለመሆኑ ይህ ያገኘሁት ድል ይበቃኛል የሚል አስተሳሰብ በከፊል ያልተለየው ነው።

የፈረንሳዩ ሉዊ ቦናፓርት የቀዳማዊ ናፖሊዮንን ዝና ተውሶ፣ አምባገነን መንግሥት ለመገንባት እንዳልከበደው ሁሉ፣ ተፈላጊው ጥንቃቄ ካልተደረገ በስተቀር፣ በኢትዮጵያ የአርሶ አደሩን ጥያቄ ለመመለስ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተው ኢህአዴግ፣ "እኔ'ኮ የመሬት፣ የብሔር እኩልነትና የዴሞክራሲ ጥያቄህን የመለስኩልህ ድርጅትህ ነኝ" እያለ ተመሳሳይ አምባገነናዊ ሥርዓት ወደመፍጠር እንዳያመራ የሚያግደው ነገር አልነበረም። የሥርዓቱን አደጋዎች በትክክል ለይቶ እነዚህን ለመቅረፍ የሚያስችል እንቅስቃሴ ካልተደረገ በስተቀር በዴሞክራሲና አምባገነንነት መካከል ያለው ርቀት በቀላሉ እየጠበበ ሊሔድ እንደሚችል በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ነው። ይህ ሥጋት የኢህአዴግ አመራር በማኅበራዊ መሠረቱ ንዑስ ባለሀብት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ምናልባታዊ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ ስጋት ጭምር ነበር።

የኢህአዴግ አመራር በመሠረቱ የተማሪዎች ንቅናቄ ውጤት ነው። ከመካከሉ በቁጥር ጥቂት የአመራር አባላት ወደሥራ ዓለም ገብተው የነበሩ ከመሆናቸው በስተቀር አብዛኛው ትምህርቱን አቋርጦ ወደትግል የተቀላቀለ ነው። ይህም ኃይል ቢሆን ትምህርት ሲጀምር እንደማንኛውም የዘመኑ ወጣት ራሱን ለከፍተኛ ደረጃ ለማብቃት በማለም ነበር። በሂደት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና ጭቁን ህዝቦች በሚደርስባቸው በደል ተማርረው እየታገሉ እንደሆነ ሲገነዘብ ይሕንኑ ትግል ደግፎ ድምፁን ማሰማት ጀመረ። የአርሶ አደሩ ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ ሲሔድ ደግሞ በተማሪው ንቅናቄ መሪዎች ላይ ተፅዕኖው ይበልጥ እያየለ መሔድ ጀመረ። በተለይ ደግሞ በትጥቅ ትግሉ ወቅት አመራሩ ውሎና አዳሩ ከታጋዩ አርሶ አደር ጋር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እጅግ አብዮታዊ የሚባሉ አቋሞች እያዳበረ ለመጓዝ ቻለ። ከዚህ በመነሳት የአርሶ አደሩን የስቃይ ዘመን የሚያሳጥሩ የለውጥ ሀሳቦች እያመነጨ ህዝቡን በዚህ ዙሪያ ከማታገሉም በላይ የመሪዎቹና የህዝቡ ትግል እርስ በእርስ እየተመጋገቡ ትግሉ በሚያስደንቅ ፍጥነት ከድል ወደድል ሊረማመድ ቻለ። በመጨረሻም የደርግ መንግሥት ተገርስሶ የዘመናት የአርሶ አደር እንባ የታበሰበት አዲስ ሥርዓት ተፈጠረ። የአርሶ አደሩን እርካታ ያረጋገጠ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የዘለቀ ትግሉ ቀስ በቀስ እንዲቀዛቀዝ ምክንያት የሆነው አዲስ ሥርዓት መገንባትም ጀመረ።

አዲሱ ሥርዓት ሳይውል ሳያድር የአርሶ አደሩን ጥያቄዎት መመለስ መጀመሩ አርካታ የፈጠረውን ያህል በመሪዎቹ ታጋይነት ላይም የራሱን ማኅተም ማሳረፍ የጀመረ ነበር። ለወትሮው የአርሶ አደሩን ብሶት ተከትሎና ይህንኑ ለመቅረፍ ትግልን የተቀላቀለው ንዑስ ባለሀብት ለብሶቱ መፍትሔ ያገኘውን አርሶ አደር መቀዛቀዝ ተከትሎ እርሱም መብረድ ጀመረ። ምንም እንኳ የአመራር ኃላፊነት ላይ የተቀመጠው ንዑስ ባለሀብት በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት የአገሪቱን ችግሮች ለማቃለል በከባድ የለውጥ ተግባር መጠመዱ ባይቀርም፣ በአዲሱ የትግል ምዕራፍ የነበረው የፖለቲካ ወኔ በትጥቅ ትግሉ ዘመን ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ጉልህ ለውጥ ይታይበት ጀመር። ደረጃ በደረጃ የመቀዛቀዝ መንፈስ እየወረረው ከመሔዱም በላይ በሥልጣን ላይ ሆኖ በአገር ሀብትና ልዩ ልዩ ጸጋዎች ላይ የሚያዝ መሆኑ ደግሞ ቀስ በቀስ ለበዙ ተገቢ ያልሆኑ ስሜቶች የሚያጋልጠው መሆን ጀመረ። በሽግግሩ ወቅት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር እስከማጭበርበር የደረሰውና በተመሳሳይ ድርጊት ውስጥ የገቡት ሌሎችም ሁሉ ችግሩ በትግል ወኔ መቀዛቀዝ ብቻ የማይታጠር፣ የመንግሥት ሥልጣንን ራስን አላግባብ ለመጥቀም በሚያስችል የመዝባሪ ገዥ መደብ ቅኝት እስከመመልከት የደረሰ ተጨባጭ ችግር እንደሆነ የሚያሳይ ነበር። መለስ ስለቦናፓርተስት ዝቅጠት ባቀረበው ጽሁፍ ላይ "መሪው አካል በመሠረቱ ንዑስ ከበርቴ ነው። ይህ ኃይል በተጋጋለ አብዮታዊ ንቅናቄ ውስጥ ሲገባ ተራሮችን የሚንድ ታጋይ ነው። ሁኔታው ተቀይሮ የተጋጋለ አብዮታዊ ንቅናቄ በማይኖርበትና የመድረኩ ተልዕኮ የካፒታል ከምችት በሆነበት ወቅት ግን ትልቁ ምኞቱ ራሱን ወደካፒታሊስታዊ ገዥ መደብነት መቀየር ነው። ሥልጣን ይዞ፣ የሚወረረውን ወርሮ፣ ሊከብር፣ ሊደላደልና ሥልጣኑን እንደርስት ይዞ ተመቻችቶ ሊኖር የሚመኝ መደብ ነው።"[44] ያለው ከዚህ በመነሳት ነው።

እነዚህ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት የተመቸ ነባራዊና ህሊናዊ እየተፈጠረ መሔድ እንደጀመረ የሚያረጋግጡ መሠረታዊ ሐቆች ነበሩ። በኢህአዴግ የተመራው ትግል መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት በማለም የተካሔደ በመሆኑ የአርሶ አደሩ የተወሰኑ ጥያቄዎች ስለተመለሱ የተፈጠረውን እርካታ እንደትግሉ መዳረሻ የሚወስድ አልነበረም። በተመሳሳይ ሁኔታ ከንዑስ ባለሀብቱ መካከል የተወሰነውን ክፍል ለከፍተኛ የአመራር ኃላፊነት ማብቃትና ይህም ኃይል የአገሪቱን ጸጋዎች ሁሉ ተቆጣጥሮ በብቸኝነት እንዲበለጽግ ማድረግ ግቡ አልነበረም። የትግሉ ግብ ኢትዮጵያና ህዝቦቿን በተቻለ ፍጥነት ለዳበረ ብልጽግናና ዴሞክራሲ ማብቃትና የብልጽግናውም ሆነ የዴሞክራሲው ዋነኛ ተጠቃሚዎች የአገሪቱ ህዝቦች እንዲሆኑ ማድረግ ነበር። በሥርዓቱና በድርጅቱ ጤንነት ላይ የተደቀነው ዋነኛውና ከባዱ ፈተና የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋ ነው ተብሎ የተወሰደውም ከዚህ የህዝብ መብትና ተጠቃሚነትን የማስከበር ጉዳይና ከዝቅጠቱ አደጋ ትክክለኛ ትንታኔ በመነሳት ነው።

ኢህአዴግ በዚህ ትንታኔ ላይ በመመሥረት ይህን ችግር የሚቀርፍባቸው መላዎች ወደማፈላለግና መቀመር አመራ። በዚህ ቀመር ምናልባትም ወደሥልጣን በመጡ ብዙ ግራ-ዘመም ኃይሎች ላይ ከባድ ፈተና የደቀነውንና ለመንገዳገድና ለውድቀት የዳረጋቸውን የሥልጣን ወጥመድ ለማለፍ የሚያስችለው ትከከለኛ አቅጣጫ ምን እንደሆነ ከመለየቱ በተጨማሪ ይህንኑ የመፍትሔ ሀሳብ በተግባር በመሞከር የራሱን ንድፈ-ሀሳባዊ አስተዋጽዖ የሚያበረክትበት ዕድልም ተከፈተለት። መለስ በሥልጣን የመባለግን አዙሪት ወይም ወጥመድ ለመበጠስ ያስችላል ብሎ የቀመረው የለወጥ ሀሳብ፣ በእርግጥም ብዙዎቹን የፈተነውን አደጋ የመቅረፍ ብቃት የነበረው ሊሆን በቃ። መለስ ለህዝቦች ትግል ካበረከተው አዲስ ንድፈ-ሀሳባዊ አስተዋጽኦ አንዱ ይኸው የጥገኛ ዝቅጠትን የማስወገጃ ንድፈ-ሀሳብ ነበር። ይህን የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት ካጋጠመ ችግሩ እንዴት ሊቀረፍ እንደሚገባው የሚያመላክተውን የመለስ ሀሳብ አጠር አድርጌ በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል።

"እኛ ሀብታም ሳንሆን ሌሎች ዜጐችን ያለልዩነት ሀብታም በማድረግ" ዝቅጠትን መፋለም

ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ በኢትዮጵያ የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት ተጨባጭና ወቅታዊ አደጋ ቢሆንም መፍትሔ የማይገኝለት ችግር ግን አልነበረም። መፍትሔውም ከችግሩ መንስዔዎች ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነበር። የችግሩ ምንጭ የአርሶ አደሩ እርካታና ይህን ተከትሎ የአመራር እርካብን የተቆናጠጠው ንውስ ባለሀብት ከታጋይነት ባህሪው ይልቅ አላግባብ የመጠቀም ዝንባሌው ጐልቶ መምጣቱ ከሆነ፣ ለዚህ ችግር ዋናው መፍትሔው ደግሞ አርሶ አደሩ በለውጡ እርካታ እንዳይሰማው፣ ይልቁንም አዳዲስ ፍላጐቶች ያዳበረና ለእነዚህ ፍላጐቶቹ መልስ ለማግኘት ሲል መንግሥትን ወጥሮ የሚይዝ እንዲሆን ማድረግ መሆኑ ታመነበት።

ይህ ሲሆን መንግሥት ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የሚገደድ የትግል ተቋም እንደሚሆንም ተሰመረበት። አርሶና አርብቶ አደሩን ከእጅ ወደአፍ ከሆነውና የራሱንና የቤተሰቡን ቀለብ ለማሟላት ብቻ ከሚያስችል ግብርና በማላቀቅ ለገበያ ብሎ ወደሚያመርት ሀብታም ገበሬነት በማሸጋገር ሊፈጸም የሚችልና የሚገባው ነበር። መፍትሔው መሪዎች ራሳቸውን በማበልጸግ ስግብግብነት ከተበከሉ በሥራ ላይ ሊውል ስለማይችል፣ በመለስ አገላለጽ "እኛ ሀብታም ሳንሆን ሌሎች ዜጐችን ያለልዩነት ሀብታም ማድረግ" የአይቀሬው ዝቅጠት ቁልፍ የመፍትሔ ሀሳብ ሆኖ ተቀመጠ።

አርሶ አደሩ ለራሱና ለቤተሰቡ የምትሆነውን አነስተኛ ቀለብ በማምረት ብቻ ከተወሰነ ይህን ለማድረግ ከጉልበቱ፣ ከመሬቱና ከክረምት ዝናብ በላይ የሚፈልገው ነገር አይኖርም። በዚህ አኳኋን ለሺህ ዓመታት በሞትና በሕይወት መካከል የኖረው አርሶ አደር እስክቅርብ ጊዜ

ድረስ ዋነኛው የምርት ግቡ የራሱንና የቤተሰቡን ቀለብ ማሟላተ ነበር። ነገዘያ ለሚሄይመራ ይህን ለመሰለው አርሶ አደር የመንግሥት ድጋፍ የኑሮ መደጐሚያ እንጂ የሕይወት መሠረት ስለማይሆን መንግሥትን ለመወጠር በቂ ምክንያት ሊኖረው አይችልም። ካለ መንግሥት ድጋፍ ከእጅ ወደአፍ የሆነውን ኑሮውን መቀጠል ይችላልና። በአንጻሩ ገበያን በተለይ የውጭ ገበያን ታሳቢ በማድረግ የሚያመርት አርሶ አደር፣ ዋነኛ ግቡ የማይጠረቃውን የዓለም ገበያ ለማርካት ያለመ ይሆናል። በዚያው ልክ የግብርና ምርት አድማሱ ሰፊና ማለቂያ የሌለው መሆን ይጀምራል። በዚህ ዓይነት አርሶ አደሩ ለማይረካው የዓለም ገበያ የግብርና ውጤቱን የማቅረብ ብቃት የሚኖረው ምርታማነቱን በቀጣይነት ለማሳደግ ሲችል ነው። ይህ ደግሞ በፋንታው የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሲሆን ብቻ የሚመጣ ነው። ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ጉልበትን የሚደግፉ ማሽነሪዎች፣ መስኖና የተሻሻሉ የምርት ማጓጓዣዎች በመጠቀም ምርታማነትን ማሳደግ ሲቻል ብቻ እውን የሚሆን ብቃት ነው።

አርሶ አደሩ እነዚህን በተነጻጻሪ ረከስ ያለ ዋጋ ለማግኘት የሚችለው ሁሉም ገበሬዎች በአንዱ ተመሳሳይ ምርቶችን የሚያመርቱ ወይም ስፔሻላይዝ ያደረጉ ሲሆኑ ብቻ ነው። በመሆኑም የግብርና ምርታማነትን በማሳደግ ለገበያ የማምረት ግብን የማሳካት ጉዳይ በመንግሥት በኩል በጣም ብዙ አቅርቦቶች እንዲሟሉ ማድረግን የግድ ይላል። ከተናጠል የአርሶ አደሮች እንቅስቃሴ ይልቅ በተደራጀ አኳኋን በአንዱ ከመንግሥት ጋር መተባበርና በእርሱም ላይ የማያቋርጥ ጫና እየፈጠሩ መጓዝና መሥራትን ይጠይቃል። እነዚህ ሲለመዱና በአንድ በኩል ያለእነዚህ ምርትን ማሳደግ የማይቻል ሲሆን፣ በሌላ በኩል መንግሥት አቅርቦቶቹን የማሟላትም ሆነ ቴክኖሎጂን የማሻሻል ጉዳይ ላይ ዳተኛ መሆን ሲጀምር አርሶ አደሩ በመንግሥት ላይ የማያቋርጥ ግፊት የሚያደርግ ማኅበራዊ ኃይል ወደመሆን ይሸጋገራል። ግፊቱ የተደራጀ ስለሚሆን በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ የማሳረፍ ችሎታው በእጅጉ ይጨምራል።

ከእጅ ወደአፍ በሆነው አመራረት መፋዘዝ ጀምሮ የነበረው አርሶ አደር፣ መላበስ በጀመረው አዲስ የገበያ ተኮር ገበሬነት አስተሳሰብና ባሕል ከፍተኛ ተፅዕኖ አድራጊ መሆን ይጀምራል። የአገር ውስጥ ገበያ ብቻ ሳይሆን የዓለም ገበያም በአርሶ አደሩ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳረፍ ይጀምራል። መላ ዕድሜዋን በገጦ፡ ደረጃ ብቻ ስትሽከረከር የኖረችው የአርሶ አደሩ ሕይወት በዓለም ገበያ ማዕቀፍ በትስስር የምትተውን መሆን ትጀምራለች። ተፅዕኖ አድራጊና ለከባድ የዓለም ገበያ ተፅዕኖ የተጋለጠች፣ ስለዚህም በጣም ከባድ ጥንቃቄ የምትሻ፣ ለመሻሻል ሌት ተቀን የምትተጋ፣ ተኝታ የማታስተኛ ነፍስ መሆን ትጀምራለች።

በዚህ ዓይነት አርሶ አደሩ በማያቋርጥ ሁኔታ ለአዳዲስ ፍላጐቶች መታገል ሲጀምር ተኝቶ የማያስተኛ ይልቁንም ያለማቋረጥ የሚሞግት ወይም ጠያቂ /Demanding/ ሕብረተሰብ መሆን ይጀምራል። በቀላሉ የማይረካ፣ ሁሌ መንግሥትን በአዳዲስ ጥያቄዎች የሚሞግት የአርሶና

የአርብቶ አደር ሥነ-ልቦናና ዝቀጠተን የማይሽከም የገጠር ሕብረተሰብ ይፈጠራል። ይህም እንደገና የተቀዛቀዘውን አመራር የሚያነቃቃው ይሆናል። ይህን መሰል ለጥገኝነት የማይመች የፖለቲካ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚደረግ እንቅስቃሴ ወሳኝ ቢሆንም ብቻውን ግን በቂ እንዳልሆነ በኢህአዴግ የተሃድሶ እንቅስቃሴ መጀመሪያ ላይ በጥብቅ የታመነበት ጉዳይ ነበር። ከዚሁ ጐንና በማይነጠል ሁኔታ መሪ ድርጅቱ በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ እንዲገባ ማድረግና አብዮታዊና ዴሞክራሲያዊ ወይም ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪውን እያጐለበተ እንዲሔድ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ በመነሳት በፖለቲካ ኢኮኖሚውና በድርጅቱ መካከል የቻይና ግንብ ሳይኖር በትስስርና ተመጋጋቢነት እየተለወጡ እንዲጓዙ መደረግ ይኖርበታል።

መለስ ለሌሎች ህዝባዊ ትግሎችም ከፍተኛ ትምሕርት በሚሰጥ አኳኋን በቀመረው በዚህ ንድፈ- ሀሳብ መሠረት፣ የአስተሳሰብ ትግሉ በፓርቲው ውስጥ በተለይም በከፍተኛ አመራር ደረጃ ጀምሮ በዚህ ብቻ ሳይታጠር መቀጠል ነበረበት። የአስተሳሰብ ትግሉ ከአመራሩ ቢጀምርም በፍጥነት ወደአባላት ከዚያም አልፎ ወደህዝቡ ዘልቆ እንዲገባ መደረግ አለበት። ህዝቡ በአዳዲሶቹ ልማታዊ አስተሳሰቦች ትከከለኛነት አምኖ እነዚህን ተግባራዊ ሲያደርጋቸው ለውጡ ከፓርቲው አጥር አልፎ ህዝቡን የሚያካትት መሆን ይጀምራል። በህዝቡ ውስጥ በለውጡ ሀሳብ ተማምነው ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርጉና የላቀ ልማታዊ ውጤት የሚያመጡ አዳዲስ ኃይሎችም ይፈጠራሉ። በገጠርና በከተማ የሚፈጠሩት እነዚህ ኃይሎች የፓርቲውን ሰልፍ እየተቀላቀሉ ድርጅቱን ከሥር በጤናማ ታጋዮች ማጠናከር ይጀምራሉ። ነባርም ሆነ አዲስ አባላት በዋነኛነት በልማትና ዴሞክራሲያዊነት መስፈርቶች የሚለኩና የሚመዘኑ መሆን ይጀምራሉ። በዚህ መስፈርት ተለክተው የሚያልፉት ብቻ የፓርቲው አስተማማኝ አባላት ይሆናሉ። አመራሩም በትግልና በትክክለኛ ተግባር ከተፈተኑ ከእነዚህ ሰዎች መካከል የላቀ ብቃት ባላቸው ሰዎች እየተሞላ የፓርቲው ጤንነት ይበልጥ እንዲጐለብት ያስችላል።

ከሥር የፓርቲው አባላት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ፣ ሠርቀው ሳይሆን ሠርተው የሚከብሩ በሆኑ ቁጥር የፓርቲው ጤንነት የመጠበቅ ዕድሉ ሰፊ ቢሆንም፣ ይህ ብቻውን በቂ ተደርጐ አልተወሰደም። የድርጅቱ መካከለኛና ከፍተኛ አመራሮች ሕብረተሰቡን በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ አንቀሳቅሰው ለመለወጥ በሚያካሂዱት ጥረትና በፓርቲው ውስጥ በቀጣይነት መካሔድ ባለበት የውስጠ ድርጅት ትግል እየታገዙ ራሳቸውን መለወጥም ይገባቸዋል።

ይህም ለውጥ ቦታና ጊዜ ሳይገድበው ተግባራዊ በሚደረግ የህዝብና የአገር አገልጋይነት መንፈስና በማያቋርጥ የአስተሳሰብ ግንባታ የሚገለጽ ሊሆን ይገባዋል። በየደረጃው ያሉት አመራሮች ከእነዚህ አንዳቸውን ሳያጓድሉ የሚፈጽመው ሲሆኑ ጥራት ያለው ብቻ ሳይሆን የህዝብን መብትና ጥቅም ወደአዲስ ከፍታ የሚያወጣ ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍና ተግባራዊ

ማድረግ ይቀጥላሉ፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ ሞጋች መሆን ለደመረው ሕዝበተወላጅ ፓኅዲ ነኝ ብሎ ታዳጊ ምላሽ ለመስጠት ይበቃሉ፡፡ ህዝቡ ከዚህ ምላሽ በመነሳት ለልማት ሥራና ለዲሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል ያጧጡፋል፡፡ ይህን ትግል ተከትሎ ደግሞ እንደገና እስከላይኛው የድርጅቱ አመራር ባሉት እርከኖች መነቃቃት ይፈጠራል፡፡ዝቅጠትን ለማስወገድ በተቀየሰው መፍትሔ መሠረት ይህ ከድርጅት ወደህዝብ፣ እንደገና ከህዝብ ወደድርጅት የሚተላለፍ የበጎ ተፅዕኖ ዑደት በአንዱ ጫፍ ላይ ሳይበጠስ ከቀጠለ የማያቋርጥ የለውጥ መስተጋብር ይፈጠራል፡፡ በተለይ ደግሞ ከአመራር እርከኖቹ በአንዱ በተለይ ደግሞ ከህዝብ በጣም ራቅ ብሎ በሚገኘው ከፍተኛ አመራር ይህ የአዎንታዊ አዙሪትና ተመጋጋቢ ሂደት ካልተበጠሰ በስተቀር ለውጡ እንዲህ እያለ በማያቋርጥ ደረጃና ተመጋጋቢነት ይቀጥላል፡፡

በዚህ ወቅት መለስ ካመጣቸው ሀሳቦች መካከል "እኛ ህብታም ሳንሆን ሌሎች ዜጐችን ህብታም እናድርግ" በማለት ያቀረበው ሀሳብ የተለየ አብዮታዊ መነሳሳትና ስሜት የሚፈጥር ነበር፡፡ በብዙ ያልበለጸጉ አገሮች ዘንድ ከሚታየው በተለየ ሁኔታ፣ "እኛ መሪዎቹ በያዝነው የፖለቲካ ሥልጣን ራሳችንን ለማበልጸግ ቅድሚያ ሳንሰጥ ሌሎች እንዲበለጽጉ እናድርግ" የሚለው የመለስ ሀሳብ፣ አመራሩ ካለው የንዑስ ባለሀብትነት ባሕርይና ይህም በተቀዛቀዘ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ከሚያስከትለው የዝቅጠት ዝንባሌ ጋር ተያይዞ ለሚታየው ችግር መፍትሔ እንዲሆን ተብሎ የቀረበ አቅጣጫ ነበር፡፡ ይህ ሀሳብ በጐ ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን የሚፈትነውን በመንግሥት ሥልጣን ያለአግባብ የመጠቀም አዝማሚያ ለመግታት አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ የታመነበት ነበር፡፡ ሁሉም የአመራር አባላት ከልብ ተቀብለው ተግባራዊ ካደረጉት በእርግጥም ችግሩን ከመቅረፍ አኳያ የራሱን ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል ነበር፡፡

ጽንሰ-ሀሳቡ በጥሬው ሲታይ በሀብት ፈጠራ ላይ በተጠመደና ማንኛውንም ግለሰብ በሚያማልለው የመበልጸግ ዕድል ላይ ክልከላ የሚያስቀምጥ ተደርጐ ሊተረጐም የሚችል መሆኑ አይሳትም፡፡ በተለምዶ ባልበለጸጉ አገሮች የመንግሥት ሥልጣንን ይዞ መዝረፍና መከበር የተለመደ በሆነበት ዓለም ተምኔታዊ የሚመስል ገጽታም አለው፡፡ "ሰው የመበልጸግ ዕድል ሲያጋጥመው የመበልጸግን ቀዳሚነት አትውሰድ የሚባልበት አመክንዮ እንዴት አሳማኝ ሊሆን ይችላል?" ሊያሰኝ የሚችልም ነው፡፡ ከምንም ነገር በላይ ደግሞ "የመንግሥት ሥልጣን ይዞ ራሱን ሳያስቀድም ሌሎችን በመጥቀም ቅኝት የሚንቀሳቀስ ሰው ራሱን እስካልጠቀመ ድረስ ይህ አስተሳሰብ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በር የማይከፍትና የማይሠራ ነው?" የሚል ጥርጣሬ ሊቀሰቅስ የሚችልም ነበር፡፡ ነገር ግን በመለስ ዜናዊ የተቀነቀነው ይህ ሀሳብ በጥገኛ ዝቅጠት መልክ ለሚከሰተው ችግር አንድ ተጨማሪ መፍትሔ ሊሆን የሚችልና በብዙ ልማታዊ አገሮች ዘንድ ተሞክሮ ጥሩ ውጤት የተገኘበት ነበር፡፡ የፖለቲካ ሥልጣኑን የያዙት አካላትና ሲቪል

ሰርቪሱ መላውን ዜጋ በቅንነትና በታማኝነት በማገልገል አገራዊ ሀብት ፈጠራን እንዲያሳድጉና በዚያው ልክ ደግሞ የመንግሥት ሥልጣንን ለራስና ለሚቀርቡህ ብቻ መጠቀሚያ የማድረግ አዝማሚያን ለመቆጣጠርና ለማስወገድ ያስቻለ ነበር።

"እኛ ሀብታም ሳንሆን ሌሎች ዜጐችን ያለልዩነት ሀብታም እናድርግ" የሚለው አስተሳሰብ መንግሥታዊ ሥልጣን የተቆናጠጡ ሁሉ በያዙት ኃላፊነት ራሳቸውን ተጠቃሚ ከማድረጋቸው ይልቅ፣ ሌሎችን የመጥቀም ቅኝት ይዘው እንዲንቀሳቀሱና ዜጐች ሀብት በመፍጠር እንቅስቃሴ ውስጥ በሰፊው እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል ነው። በዚህ አስተሳሰብ ተቃኝቶ ሌሎች ወገኖቹን ያለ አድሎ ሀብታም ለማድረግ የሚሠራ መንግሥት ከምንም ነገር በላይ አገራዊ የሀብት ፈጠራን ያጐለብታል። የዜጐችን ልማታዊ ጥረት ከማደናቀፍ ይልቅ፣ ለልማት አመቸና አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር ሠርተው እንዲበለጽጉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ለልማት ተግተው የሚንቀሳቀሱ ዜጐች ሁሉ በመንገዳቸው ላይ የሚያጋጥማቸውን ችግር በቀጣይነት ለመፍታትና ለማቃለል ጥረት ያደርጋል።

ይህም ሲሆን ከመቼውም ጊዜ በላይ በአገሪቱ ሀብት የመፍጠር እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ዜጐች በአራቱም ማዕዘናት ተንቀሳቅሰው ያልነበረ ሀብት ይፈጥራሉ። ይህ እንደገና መንግሥት ከኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴውና ያለማቋረጥ ከሚፈጠረው ሀብት በግብር መልክ የሚሰበሰበው ገንዘብ በእጅጉ እንዲጨምር በማድረግ የመንግሥት ሠራተኛውንና የኃላፊዎችን ደመወዝ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሳድግ በር ይከፍትለታል። "እኛ ሀብታም ሳንሆን ሌሎች ዜጐችን ያለልዩነት ሀብታም እናድርግ" በሚለው አስተሳሰብ መሠረት ሌሎች ሀብታም ሲሆኑ አገር እኛንም ይዛ ትበለፅጋለች። ስለሆነም አስተሳሰቡ በጋራ ጥረት በመልማት ተያይዞ የመጠቀም እንጅ በዜሮ ድምር ቅኝት ተያይዞ የመጥፋት ይዘት የለውም። በመሆኑም ሁሉንም ተጠቃሚ በማድረግ ባለሀብቱ ሥልጣን ላይ ሲወጣ የሚያጋጥመውን ካለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ ለመግታት የሚችል አስተሳሰብ ነበር።

ኢህአዴግ ጥያቄዎቹ ስለተመለሱለት እርካታ በተጐናጸፈው አርሶ አደር ታጋሽነት ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርለት ይችላል ብሎ የገመተውን የጥገኛ ዝቅጠት አደጋ፣ በአንድ በኩል ለአዳዲስ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች የሚፋለም ሞጋች ሕብረተሰብ በመፍጠር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ራሰን አመራሩን ጨምሮ መላውን ድርጅት ወደአዲስ የለውጥ ንቅናቄ በማስገባት ማስወገድ ይቻላል የሚለውን ይህን አስተሳሰብ በጥብቅ አመነበት። በመሆኑም የተሃድሶ እንቅስቃሴው የሥርዓቱን አደጋዎች በመለየት ብቻ ሳይወሰን የተሃድሶውን የትግል መሥመር በጥራት በመንደፍ የመጀመሪያውን ምዕራፍ አጠናቀቀ። በመስከረም 1994 ዓ.ም በተካሔደው አራተኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ደግሞ ይኸው የተሃድሶ አስተሳሰብ የድርጅቱ ይፋ መታገያ መሥመር ሆኖ ፀደቀ። ከዚህ በኋላ የነበረው የድርጅቱ እንቅስቃሴ ሁሉ ይህንኑ

መሥመር በተግባር ለማዋልና በተጨባጭ የተደቀነውን የጥገና ዝቀጠተ አደጋ ለመቀልበስና የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታውን በማያቋርጥ የለውጥ ንቅናቄ ማዕቀፍ በመፈጸም ላይ ያተኮረ ነበር። በዚህ መነሻነት ባለፉት በርካታ ዓመታት የተከናወኑት ዋና ዋና ሥራዎች ምን እንደሚመስሉ መመልከት ኢህአዴግ የሥርዓት ብልሽት አደጋዎችን ለመከላከል የነደፈው መሥመር ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነና ምን ዓይነት ወጤት እንዳመጣ ለመመዘን ዕድል ይሰጣል።

መሥመሩን ተግባራዊ ለማድረግ የተካሔደው ትግልና ውጤቱ፣

የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የህዳሴ ዘመን ከኢህአዴግ አራተኛ ድርጅታዊ ጉባዔ በኋላ የጀመረ ሲሆን፣ ላለፉት 15 ዓመታት በሁሉም የሕይወት መስኮች ተግባራዊ እንዲሆን የተሞከረና የዚያኑ ያህል ውጤት የተገኘበት ነው። በእነዚህ ዓመታት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ፣ በውጭ ግንኙነትና በአገር ደኅንነት መስኮች ሁሉ ሰፋፊና ሥር-ነቀል እንቅስቃሴዎች ተካሂደዋል። ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር፣ ግብርናና ኢንዱስትሪ፣ ትምሕርትና ጤና፣ መሠረተ-ልማትና አቅም ግንባታ እንዲሁም የውጭ ግንኙነት መስኮች ሁሉ የተሃድሶ መሥመሩን ተግባራዊ ለማድረግ ርብርብ የተደረገባቸው ነበሩ። በሁሉም መስኮች የህዝብ መብትና ጥቅሞች ወይም የአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅሞች እንዲጠበቁና እንዲሰፉ ለማድረግ ተሞክሯል። በመሆኑም ስለሁሉም ዘርፎች የለውጥ እንቅስቃሴ መጻፍ ቢያስፈልግ በጣም ብዙ መረጃዎችን ማቅረብ የሚያስቸግር አይሆንም።

ይሁንና በዚህ መጽሐፍ ለሁሉም ጉዳዮች እኩል ትኩረት መስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ የኢትዮጵያን ህዳሴ ለመጀመርና ለማስቀጠል የላቀ ፋይዳ በነበራቸውና ባላቸው ጉዳዮች ላይ መወሰን መርጫለሁ። በመሆኑም የመጪው ዘመን መልካም ዕድሎችና ፈተናዎች ሰፋ ባለ ደረጃ ለሚዳሰስበት ለከፍል ሦስት ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ መወሰን ተመራጭ በመሆኑ ከተሃድሶ በኋላ የለውጥ እንቅስቃሴው አሐዱ ብሎ በጀመረበት የፖሊሲና ስትራቴጂ ለውጥ በመጀመር ጉዳዩን መመልከት ይገባል። በመቀጠልም በግብርናና መሠረተ-ልማት ዙሪያ የተካሔደውን እንቅስቃሴና በተጓዳኝ ደግሞ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማትን መመልከት ይቻላል።

ቅድሚያ ለፖሊሲና ስትራቴጂ ሠነዶች ዝግጅት፣

አራተኛው ድርጅታዊ ጉባዔ ተካሂዶ የተሃድሶ መስመሩ የድርጅቱ ይፋ መመሪያ ከሆነ በኋላ ቀዳሚው ጉዳይ መሥመሩን በመንግሥታዊ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና እቅድ መልክ አዘጋጅቶ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ነበር። ኢህአዴግ ከተሃድሶ ጥቂት ቀደም ብሎ በ1992 ዓ.ም

በተባሔደው ሁለተኛ አገራዊና ክልላዊ ሃሣቦች አበንፎ ሥልጣንን ላይ የዋጠለ ገዘ ፓርቲ በመሆኑ ፖሊሲና ስትራቴጂዎቹ በእቅድ መልክ ተዘርዝረው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቁ በማድረግ ለማስፈጸም ሕጋዊ ውክልና ነበረው።

ይህን ከግንዛቤ በማስገባት ከ1994 እስከ 1995 ዓ.ም አጋማሽ አምስት መሠረታዊ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሠነዶች አዘጋጀ። እነዚህም የግብርናና ገጠር ልማት፣ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም የማስፈጸም አቅም ግንባታን የሚመለከቱ ነበሩ። የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶቹ ቀደም ሲል ከተዘረዘረው የሥርዓት አደጋ ትንታኔ በተጨማሪ ከሌሎች ሶስት መሠረታዊ ታሳቢዎች የሚነሱ ነበሩ።

አንደኛው ተጨማሪ መነሻ የምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታት ስኬታማ የለውጥ ሂደትና ከዚህ የተቀሰመው አዎንታዊ ልምድ ነው። ሁለተኛው መነሻ በአፍሪካና በብዙ ያልበለጸጉ አገሮች በግዳጅ ተሞክሮ ከፍተኛ ምስቅልቅል ውጤት ያስከተለውና ከአሉታዊ ልምዶች ለመማር ዕድል የከፈተው የገበያ አከራሪነት ርዕዮት ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ በምዕራቡ ዓለም ከተገነባው ዴሞክራሲ ውስጥ መሠረተ-ሰፊ የህዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ልምዶች ነበሩ።

በምዕራቡ ዓለም በስመ-ዴሞክራሲ የጥቂት ልሂቃን ብቻ ወሳኝነት የተረጋገጠበትን አካሔድ ወደጐን የተባሉበት ይህ መሠረታዊ የፖሊሲ ቀረጻ ሂደት ኢትዮጵያ ከሁሉም የዓለም ከፍሎች ምርጥ ምርጡን ለይታ እንድትወስድ ዕድል ያጐናጸፉት ነበር። መለስ በጥብቅ ዲሲፕሊን የተከተለውና ዘግይተው የለሙ አገሮች የሚያገኙትን ይህን መልካም ዕድል ለአገራችን ማጐናጸፍ አለብን በሚል እሳቤ የተጀመረው ይህ ሂደት፣ በእርግጥም ጐጂዎቹን ልምዶች በመተው ጠቃሚዎቹን ብቻ የፖሊሲና ስትራቴጂው የማዕዘን ድንጋይ የሚያደርግ ነበር።

በዚህ ወቅት የተሃድሶ መሥመሩ በመንግሥት ፖሊሲና ስትራቴጂ መልክ ዳብሮና ሕጋዊነት ተላብሶ የሥራ መመሪያ እንዲሆን ከተደረገው ጥረት ጋር ተያይዞ ተጨማሪ አዳዲስ ጽንሰ-ሀሳቦችም ወደኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ለመግባት ችለዋል። ከእነዚህ አንዱ የገበያ ጉድለት ወይም ውድቀት (Market Failure) ንድፈ-ሀሳብ ሲሆን፣ ይህም የፖሊሲ ሠነዶቹ ይበልጥ በበለጸገ የአስተሳሰብ መሠረት ላይ እንዲገነቡ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያበረከተ ነበር። እስከዚህ ጊዜ ድረስ በፓርቲው የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የገበያ ውድቀት ጽንሰ-ሀሳብ እምብዛም የተስፋፋ አልነበረም።

ጽንሰ-ሀሳቡ መታወቅ የጀመረው ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጥቂት ቀደም ብሎ በርከት ያሉ የአመራር አባላት በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚክስ ትምሕርት ሁለተኛ ዲግሪያቸውን

በሚሠሩበት ጊዜ ነበር። ገበያውና ባለሀብቱ ፈተለይ ፈዝዋተና የዐድገተ ደረዳ ላይ ፈሚገ ኮ አገሮች በበቂው ባለመልማታቸው የተነሳ አሟልተው የማያቀርቧቸው ነገር ግን ለዕድገት እጅግ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች እንዳሉ የሚያስገነዝብ ይዘት አለው። በተጨማሪም ባለሀብቱ በሕብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ተፈላጊነት ባለው ማንኛውም ምርት ላይ የሞኖፖል ይዞታ እንዲኖረው ከተፈቀደለት በሚያቀርበው ምርትና አገልግሎት ላይ የፈለገውን ያህል ዋጋ በማስከፈል ገደብ የሌለው ትርፍ የማግበስበስ ዕድል እንዲያገኝ ማስቻልም የገበያ ጉድለት ትሩፋት ነው የሚል ነበር። እነዚህን የመሳሰሉ የገበያ ጉድለቶች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ኢኮኖሚው ልማታዊ አቅጣጫ ይዞ መገንባቱና ከፍተኛ የምርታማነት ጭማሪ መገኘቱ ይቀርና ጥቂቶች ያልሰሩበትን ከፍተኛ ትርፍ የሚያግበሰብሱት፣ ብዙኃኑ ደግሞ ተገዢ የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጠራል። የልማት ጸጋዎችና ሀብትም የላቀ ሳይሆን ያነሰ ውጤት በሚገኝበት አካባቢ እየተሰማራ ይባክናል።

ይህ ሲሆን ካለአግባብ የሚጠቀመው ከፍል ለሕብረተሰብ ካበረከተው አስተዋጽኦ እጅግ የላቀና ፍትሃዊነት የጐደለው ኪራይ መሰብሰብ ይጀምራል። ኪራይ በዘመናዊው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሳይንስ አተረጓጐም በእጥረት ኢኮኖሚ (የገበያ ጉድለት) የተነሳ ዘራፊዎች ሳይወጡ ሳይወርዱ ቁጭ ብለው የሚያገኙት የኢኮኖሚ ጥቅም ማለት ነው። በኪራይ መልክ የሚሰበሰበው ይህ ትርፍ የመንግሥት ሥልጣን በመያዝ ወይም ከባለሥልጣን ጋር በመሻረክ ሊገኝ የሚችል ነው። በዚህ አኳኋን መሬትን፣ ማዕድናትን፣ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶችን ሌላው ቀርቶ የድለላ ሥራዎችን በሞኖፖል በመያዝ የሚገኘው ትርፍ ሁሉ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ንድፈ-ሀሳብ ኪራይ ተብሎ ይጠራል። በአዲስ አበባ ከተማ በሁሉም ነገር ላይ ኪራይ የመሰብሰብ አዝማሚያ እየጐላ መምጣቱን ተከትሎ የተፈጠረውና "ባየ በሰማ" በሚል አገላለጽ የሚታወቀው ኪራይ ሰብሣቢነትም፣ ያልተመጣጠነ የመረጃ እደላና ይዞታ (Information Asymmetry) ኪራይ የሚሰበሰብበት መስክ እንደሆነ የሚያመላክት ነው።

"ባየ በሰማ" ቀልድም ይሁን ቁም ነገር ሁለት ባለጉዳዮች የቢዝነስ ወሬ ሲያወሩ የሰማ፣ ነገር ግን ጉዳዩ የማይመለከተው ሰው "ወሬያችሁን ሰምቻለሁና ከጥቅሙ መጋራት ይገባኛል፣ አለበለዚያ ሚስጢራችሁን ለአገሩ አዳርሰውና ተወዳዳሪ ይመጣባችኋል" በማለት እያስፈራራ ጥቅም የሚያገኝበት አካሔድ ነው። ይህም ያልተመጣጠነ የመረጃ ይዞታ ጭምር የኪራይ ዕድል እንደሚፈጥር ያሳያል። በዚህ መልክ የጨረታ መረጃዎች ለተወሰኑ ብቻ የሚገለፁበት ሁኔታ ሲፈጠር፣ የመረጃ ብልጫ ያላቸው ወገኖች ሌላውን መስፈርት ሁሉ ሳያሟሉም ጨረታዎችን እስከማሸነፍ መድረሳቸው የገበያ ውድቀት የማይጐበኘው መስክ እንደሌለ አመላካች ነው። ከኢንፎርሜሽን እስከቴክኖሎጂ አቅርቦት ድረስ ያሉትን ጨምሮ የፋይናንስ፣ የመሠረተ-ልማት ወዘተ አቅርቦቶች ሁሉ በገበያ ጉድለት ምክንያት አንድም ሳይቀርቡ ሊቀሩ፣ አለያም የሞኖፖል

ሀድል ዘ-ጊፈሳኒ አጓጓን ሊዋርዙ የሚተሉ ሆነዋል፡፡ በመሆኑም እንደኢትዮጵያ በመሰለ ስፊ የገበያ ክፍተት ባለበት ያልበለጸገ አገር ገበያውና ባለሀብቱ ብቻ በጋራ ተጠቃሚነት መርሕ እየተመሩ ሁሉንም ነገር አሟልተው ያቀርባሉ ብሎ መጠበቅ የዋሕነት ብቻ ነው፡፡

ባለሀብቶች አዋጭነት የለውም ብለው የማያስፋፉት፣ ነገር ግን ለአገሪቱ ዕድገት ቁልፍ ተፈላጊነት ያለው ብዙ መስክ አለ፡፡ በአንጻሩ አዋጭነቱ ከፍተኛ የሆነውን ዘርፍ ደግሞ ከውድድር ውጭ በብቸኝነት ሊቆጣጠሩና ሊያልቡት ይፈልጋሉ፡፡ በመሆኑም ለአገር ልማት ጠቃሚ ሆኖ እያለ ባለሀብቶች አዋጭ ሆኖ ስላላገኙት ብቻ ሊያቀርቡት የማይፈልጉትን ምርትና አገልግሎት የእነርሱ የማልማት ፍላጐት እስኪቀሰቀስ ድረስ መጠበቅ መና ከሰማይ ይወርዳል ብሎ አንጋጦ ከመጠበቅ የተለየ አይሆንም፡፡ እነርሱ በሞኖፖል ሊቆጣጠሩት የሚሹትን የከፍተኛ ትርፍ ምንጭ በብቸኝነት እንዲቆጣጠሩት መፍቀድም ልማትን አያመጣም፡፡

በዚህ የተነሳ መንግሥት ለልማት አስፈላጊ ሆኖ እያለ ባለሀብቶች ሊሠሩት ያልፈለጉትን ወይም ያልተዘጋጁበትን ማልማት ይጠበቅበታል፡፡ ጠንካራ የውድድር ሕግ ከማውጣት ጀምሮ ለሁሉም እኩል ዕድል የሚሰጥ የመወዳደሪያ ሜዳ በማዘጋጀት የሞኖፖል ይዞታ እንዳይፈጠር መከላከል ይጠበቅበታል። በተለይ ደግሞ የገበያ ጉድለቱ ሰፊ በሆነባቸው ያልበለጸጉ አገሮች በተለምዶ ከሚታወቀውም በላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ሚና ሊጫወት ይገባዋል፡፡ ይህም በዘፈቀደ የሚወሰንና ዳር ድንበር የሌለው ሳይሆን ባለሀብቱ ሊያለማቸው ያልፈቀዳቸውን፣ የማይቻላቸውን ለልማት ወሳኝ ተፈላጊነት ያላቸውን መስኮች ብቻ የሚመለከት ሊሆን ይገባዋል፡፡

በኢትዮጵያ አዲሶቹ የልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በተነደፉበት በዚህ ወቅት የገበያ ጉድለት በመባል የሚታወቀው ንድፈ-ሀሳብና ይህን ተከትሎ የተቀመረው የመንግሥት የተመረጠ ጣልቃ ገብነት የፖሊሲው ሌላ የማዕዘን ድንጋይ ነበር፡፡ በእርግጥ ወቅቱ በዓለም ደረጃ የኒዮ-ሊበራሊዝም የበላይነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት በመሆኑ ከገበያ ጉድለት በማይተናነስ ደረጃ የመንግሥት ጉድለት ንድፈ-ሀሳብ እየቀረበ መንግሥት ከኢኮኖሚው ላይ እጁን እንዲያነሳ የማያቋርጥ ግፊት ይደርግ የነበረበት ወቅት ነው፡፡ የገበያ አምላኪ ኃይሎች ሀሊም እንደማያደርጉት የመንግሥት ጉድለት መገለጫ የሆኑ ምሣሌዎችን በስፋት እያቀረቡ መንግሥት ከኢኮኖሚው ላይ እጁን እንዲያነሳ ያልጠየቁበት ጊዜ አልነበረም፡፡

መንግሥት በበኩሉ በብዙ አገሮች መንግሥታዊ ሥልጣንን ካለአግባብ በመጠቀም በህዝባቸውና በአገራቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ መንግሥታት ጥቂት እንዳልሆኑ ይገነዘብ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ በዓለማችን ሰሜን ምሥራቃዊ ክፍል በተመረጠና ለውጥ

ዘሞኒያመሠላ የመንግሥተ ጣልቃ ገብነት ከአምሳ ባልበለጡ ዓመታት አገራቸውንና ህዝባቸውን ለብልጽግና ያበቁ መንግሥታት በርካታ እንደሆኑ ደግሞ በጥናት አረጋግጧል። ስለዚህም የመንግሥት ጉድለት የሚያጋጥም ችግር እንደሆነ ተቀብሎ መፍትሔ የሌለው ችግር አድርጐ ግን አልወሰደውም። በተጨማሪም ይህን ጉድለት ለማረም መንግሥትን ማዳከም ወይም በእጅጉ ማሳነስ የሚባለውን መፍትሔ መቀበልም አልመረጠም። ትንሽም ሆኖ የለየለት የኪራይ ሰብሳቢ መንግሥት አለና።

ጐረቤታችን ሶማሊያ ትንሽ ሳይሆን የፈረሰ መንግሥት ይዛ ዕጣ ፋንታዋ በተቀራመቷት የጦር አበጋዞች እጅ ወድቆ እያለም ኪራይ ሰብሣቢነት የተንሰራፋባት አገር ነበረች። አንዱ የጦር አበጋዝ ወደቦቿን፣ ሌላው አውሮፕላን ማረፊያውን፣ ሌላው የጫት ወይም የሲጋራ ወይም የሙዝ ንግዱን ተቆጣጥረው ኪራይ ለመሰብሰብ ችለው ነበር። ሶማሊያን እንደቅርጫ የተከፋፈሉት የጦር አበጋዞች የተበታተኑና ደካማ የመሆናቸው እውነታ ኪራይ ከመሰብሰብ አላገዳቸውም። በደቡብ ሱዳንም "ያች አምስት በመቶ ለማን ደረሰች? ይህችኛዋን የነዳጅ ገቢስ ማን ተቆጣጠራት?" እያሉ በሚናቆሩ ዘራፊዎች የተቋቋመው ደካማ መንግሥት በትንሽነቱ ኪራይ ከመሰብሰብ አልተገታም።

ስለዚህም ጉዳዩ ከመንግሥት ባሕርይ እንጂ ከግዝፈት ወይም ማነስ ጋር የተያያዘ አልነበረም። በዚህ ምክንያት ራሱን ልማታዊ ባሕርይ ለማላበስ ቆርጦ የተነሳው ኢህአዴግ ደካማና የማይፈይድ ሳይሆን፣ ልማትን የሚያፋጥን ጠንካራ መንግሥት ሆኖ መገንባት እንዳለበት አሰመረበት። ሂደቱ ግዙፍ መንግሥት የሚፈጥር ከሆነም የመንግሥቱን ልማታዊ ባሕርይ አስጠብቆ ለማስቀጠል እስከተቻለ ድረስ ስህተት ነው ብሎ እንደማያምን የያዘውን አቋም በይፋ አውጆ ተግባራዊ ማድረግ ቀጠለ።

በኢትዮጵያ ከ1994 ጀምሮ የተቀሰቀሰው የተሃድሶ እንቅስቃሴ የተጀመረው በዚህ አኳኋን ጥርት ባለ ግንዛቤ የተቀረፁ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በማዘጋጀት ነበር። ከተሃድሶ በኋላ በነበሩት ሁለት ዓመታት ፖሊሲዎቹን የመቅረጽና የማስተዋወቅ እንቅስቃሴ ከተካሔደ በኋላ ወደሙሉ ትግበራ ሽግግር ተደረገ። ፖሊሲና ስትራቴጂዎቹ ተግባራዊ የሚሆኑት መንግሥታዊ አስፈጻሚ አካላትና ህዝቡ ሲያውቋቸውና ሲያምኑባቸው በመሆኑ የአፈጻጸም ሂደቱ አካላት የሆኑ አጫጭር ሥልጠናዎች በስፋት ተዘጋጁ። በፖሊሲና ስትራቴጂዎቹ ላይ ተደጋጋሚ ውይይትና ክርክር ተካሔደ። ይህም ሆኖ በተለይ በከተሞች ብዙ ጠቃሚ ሀሳቦች የመገኘታቸውን ያህል አሳሳቢ ብዥታዎች ማጋጠማቸውም አልቀረም። በተለይ በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ በመተማመን የአገሪቱን ልማት ለማፋጠን የተነደፈው የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ገና ከጅምሩ ከባድ ተቃውሞ አጋጥሞት ነበር።

ገበጥ ንሥራን ዘለገዘጥነ ለርቦ ለደር ሥነባ ፈጣን ልማተ ሊመጣ ይተላል ከሚለው ሀሳብ ይልቅ በግዙፍ የመስኖ አውታሮች በሚታገዙ ሰፋፊና ዘመናዊ እርሻዎች ይበልጥ የመተማመን መንፈስ ነበራቸው:: ያም ሆነ ይህ ፖሊሲው መንግሥታዊ በመሆኑ ተግባራዊ መደረግ እንደሚገባው በመስማማት ወደትግበራ ሽግግር ተደርጓል:: በዚያው ልክ ደግሞ አገሪቱ በታሪኳ አይታው በማታውቀው ከፍተኛ የዕድገት ምጣኔ ወደፊት መገስገስ ጀምራለች:: ይህ በዋነኛነት በግብርናውና በመሠረተ-ልማት መስኮች ላይ ተመሥርቶ በሚካሔድ ፍተሻ ሊረጋገጥ የሚችልና የሚገባው ነው:: በሌላ በኩል ይህ ጉዳይ በኢትዮጵያ በጀማሪ ደረጃ ላይ የሚገኘውና ተስፋ የተጣለበት የኢንዱስትሪ በተለይ ደግሞ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከእንግዲህ ማቆሚያ በሌለው ሁኔታ ሊስፋፋ የሚችልበት ዕድል መከፈቱን መነሻ በማድረግም ሊገመገም ይችላል::

ምዕራፍ ሰባት፣

የሰድሣዎቹና የሰባዎቹ ትውልድ የሩብ ምእተ ዓመት ትግል ትሩፋቶች፣

የስድሣዎቹና የሰባዎቹ የትግል ትውልድ ደርግን አስወግዶ አገሪቱን ማስተዳደር ከጀመረበት ከ1983ዓ.ም ወዲህ በነበረው ሩብ ምእተ ዓመት በሁሉም የሕይወት መስኮች መሠረታዊና ጅምር ለውጥ ማምጣቱ ብዙም የሚያከራክር አይደለም። ይህን ለውጥ የአገራችንን የዘንተዓለም ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ሂደቱንና ውጤቱን በመመዘን በዋና ዋና መስፈርቶች በመለካት ማረጋገጥም አይከብድም። ለመጀመር ያህል በአገራችን የአነስተኛውን አርሶ አደር ማሳ ለማልማት በተካሄደው ጥረትና በመመዝገብ ላይ ባለው ውጤት መጀመር ይቻላል።

በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ለልማት ተአምር መሥራት የጀመረ ትውልድ

የኢትዮጵያ ግብርና ከአገሪቱ ህዝብ ውስጥ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ሕይወት የተመሠረተበት ዘርፍ ነው። ግብርና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ዋናው የሥራ ዕድል ብቻ ሳይሆን ዋናው የእሴት ጭማሪ የሚገኝበት ዘርፍ ነበር። ከአገልግሎትም ሆነ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች በበለጠ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግብርናው ነው። በአገሪቱ ሕይወት ላይ ይህን ያህል ጉልህ ሚና ያለው ግብርና የሚለማው ደግሞ በመሠረቱ በአርሶ አደሩ ትንንሽ ማሳዎችና የሥልጠና ዕድል ባላገኘው ጉልበቱ በመሆኑ ነው።

ከዚህ በመነሳት መንግሥት በኢትዮጵያ ዕድገት ለማምጣት ቁልፉ ያለው በአነስተኛ አርሶ አደሮችና በትንሿ ማሳቸው እጅ እንደሆነ በጥብቅ ይገነዘብ ነበር። ቀደም ብሎም የነበረው ይህ ግንዛቤ፣ በተሃድሶ ወቅት ደግሞ የሥርዓቱ ዋነኛ አደጋ ሆኖ የተለየውን የኪራይ ሰብሣቢነት አደጋ ለመመከት የሚቻለው በገጠር ባለ አነስተኛ ማሳውን አርሶ አደር ከተመጽዋችነት አላቅቆ ወደልማታዊ አቅጣጫ በማስገባት ብቻ እንደሆነ በጥብቅ ታምኖበት ወደፖሊሲ ትግበራ ማምራት ተጀመረ። አዲሱ የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲ በተነደፈ ማግስት ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ሲጀመር ግን ያልታሰበ ፈተና ተደቀነበት። በአገሪቱ ታሪክ ከባድ ከሚባሉት አንዱ የሆነው ድርቅ ተከሰተ። በ1994/95 ዓ.ም ያጋጠመው ድርቅ የግብርናው ምርት በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሽቆለቁል አደረገ። በዚህ ወቅት በመላ አገሪቱ የተመረተው የሰብል

ሃሦርተ መጠ፞ን ይህ፞ነኑ በግልጽ የሚያመላክት እንደሆነ ቀጥሎ ከቀረበው የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ አኃዛዊ መረጃ[45] ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 1

ዓ.ም.(እ.ኤ.አ)	የታረሰ የመሬት ስፋት በሔ/ር	የተገኘ አጠቃላይ ምርት (ኩ/ል)	ምርታማነት በሔ/ር (ኩ/ል)
1993(2000/01)	9,445,480.00	106,159,850.00	11.24
1994 (2001/02)	7,805,770.00	99,264,403.00	12.72
1995 (2002/03)	7,859,494.27	73,694,451.91	9.38

ከፍ ሲል የተገለጸው አኃዛዊ መረጃ ሌላም የሚያመለክተው ነገር ነበር፡፡ አገሪቱ ከጦርነቱ በተገላገለች ማግስትና የድርቅ አደጋ በጀመረበት በ1994 ዓ.ም በሰብል የተሸፈነው መሬት ትርጉም ያለው ቅናሽ ባሳየበት ሁኔታ በሔክታር የተገኘው ምርታማነት ከዚያ በፊት ከነበሩት ዓመታት ሁሉ በጣም ከፍ ያለ ነበር፡፡ ከፍ ሲል የተገለጸው አኃዛዊ መረጃ ሌላም የሚያመለክተው ነገር ነበር፡፡ አገሪቱ ከጦርነቱ በተገላገለች ማግስትና የድርቅ አደጋ በጀመረበት በ1994 ዓ.ም በሰብል የተሸፈነው መሬት ትርጉም ያለው ቅናሽ ባሳየበት ሁኔታ በሔክታር የተገኘው ምርታማነት ከዚያ በፊት ከነበሩት ዓመታት ሁሉ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ መረጃው ያሳያል። በጦርነቱ ወቅት በሔክታር ከአሥራ አንድ ኩንታል አልፎ የማያውቀው ምርታማነት በ1994 ዓ.ም በሔክታር ወደ 12.7 ኩንታል አድጓ ነበር፡፡

ይህ ዕድገት በአዲሱ የገጠርና የግብርና ፖሊሲ ተግባራዊነት የመጣ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ወቅት ፖሊሲው ገና እየተዘጋጀ ስለነበር የፖሊሲ ትግበራ ጊዜ ተብሎ ሊቆጠር የሚችለው ከሞላ ጎደል የ1995 ዓ.ም ከረምትና የ1996 ዓ.ም የመኸር ምርት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በ1994 ዓ.ም ለተከሰተው የምርታማነት ከፍተኛ ዕድገት ሌላ ምክንያት ሊገኝለት ይገባል፡፡ በአጠቃላይ መንግሥት ለአርሶ አደሩ ድጋፍ ለመስጠት የነበረው ቁርጠኝነት የተለየ ትልቅ ለውጥ ባላሳየበት በዚህ ወቅት፣ የግብርናውን ትልቅ ዕድገት ሊገልጸው የሚችለው አንድ ጉልህ ምክንያት አገሪቱ ከጦርነት የተላቀቀች መሆኗ ብቻ ነው፡፡

በእርግጥም ከጦርነት የሚላቀቁ አገሮች ሰላምን ባሰፈኑ ማግስት የምርታማነት ጭማሪ ማምጣታቸው በብዙ አገሮች የሚታይ ክስተት ነው፡፡ በኢትዮጵያም ከ1983 ዓ.ም በፊት ለሰላሳ ዓመታት የተካሔደው ጦርነት አብቅቶ ሰላም በወረደ ማግሥት ይ፟ኸው ታይቶ ነበር፡፡

ይህም ሰላም ምን ያህል ልማታዊ ፋይዳ እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ጦርነትም ሆነ ማንኛውም ግጭት የአገሮችን የልማት አቅም በእጅጉ ይገድባል፡፡ የኢኮኖሚው ቅልጥፍና እንዲያንስ በማድረግ ዜጐች በእጃቸው ባለው ቴክኖሎጂ በመታገዝ ሊያመርቱ ከሚችሉት እጅግ ያነሰ የማምረት አቅም እንዲኖራቸው ያስገድዳል፡፡ በመሆኑም ከጦርነት የተገላገለ አገር ያላንዳች የቴክኖሎጂ ለውጥ የምርታማነት ጭማሪ እንደሚያመጣ ሁሉ፣ በ1994 ዓ.ም ከግብርና ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ የተከሰተው ይህ ዕድገት የአገሪቱ ሰላም በተናጋ ቁጥር የምታጣውን ሀብት የመፍጠር ዕድል በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ድርቁ የአጭር ጊዜ ክስተት በመሆኑ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት የግብርናና የገጠር ልማቱ እንዴት እንደቀጠለና ምን ዓይነት ውጤት እንዳስገኘ አጠር አድርጐ በመመልከት የፖሊሲና ስትራቴጅውን ፋይዳ ከተጨባጭ ውጤቱ በመነሳት መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ጥያቄው የተመለሰለትን አርሶ አደር በአዳዲስ የልማት አጀንዳዎች ለማንቀሳቀስ ሰፋ ያለ ጥረት መደረግ የተጀመረው በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት በ1995 ዓ.ም የነበረውን አስፊሪ ሁኔታ ከተራራ ላይ በሚወርድ ናዳ በመመሰል ከዚህ ለማምለጥ መንቀሳቀስ ይገባናል ብሎ ከወሰነ በኋላ ነው፡፡ወቅቱ በአገሪቱ ላይ የተከማመሩ ችግሮች መታየት የጀመሩበትና በተለይ በከተሞች ሥራ አጥነት ወጣቱን ወደተስፋ መቁረጥ ማምራት የጀመረበት ወቅት ነው፡፡ የፋብሪካ ሠራተኞችም በከተሞች የኑሮ ውድነትና የገቢ አለመሻሻል እየተማረሩ የመጡበት ስለዚህም የሠራተኛ ግጭቶችና ሥራ ማቆም ዝንባሌዎች መስፋፋት የጀመሩበት ነበር፡፡ ይህን ሁኔታ የተገነዘበው የኢህአዴግ አመራር ከናዳ ለማምለጥ ሩጫውን በገጠር ለመጀመርተገደደ፡፡ በገጠር በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ አማካይነት የግብርና ምርት ሜካናይዜሽን ማምጣት ከተቻለ አርሶ አደሩን ብቻ ሳይሆን የከተማውን ህዝብ ችግር በማቃለል ብሶትና ተስፋ መቁረጥን መግታትና ህዝቡ በልማት አቅጣጫ መንቀሳቀስ እንዲጀምር የሚያስችል ነበር፡፡

በዚህ መሠረት በ1995 ዓ.ም መልካም ዝናብ እንደሚገኝ የነበረውን የሜትሮሎጂ ትንበያ መነሻ በማድረግ ከሰኔ ጀምሮ ልዩ ልዩ የግብርና ሥራ ማሻሻያ እንቅስቃሴ ተካሔደ። እንቅስቃሴው ማሳን ደጋግሞ ማረስ፣ የተቻለውን ያህል ምርጥ ዘር ተጠቅሞ በጊዜ መዝራት፣ እንዲሁም አረምን መከላከልና አዝመራን ከተባይና በሽታ ጠብቆ በጊዜ የመሰብሰብ ተግባራትን በጥራት በመፈጸም ላይ ያተኮረ ሆኖ በሰኔ ወር ተጀመረ፡፡ ሥራው የተጀመረው በሰኔ ወር በመሆኑ በተለይ መሬትን በበጋው ወራት ደጋግሞ በማረስ ለማለስለስ የነበረው ዕድል ከሞላ ጐደል አምልጦ ነበር፡፡ ከእርሻ ድግግሞሽ አኳያ ጊዜው ያለፈበት ቢመስልም መንግሥት "ዛፍ ለሙትከል

በጣም አመቺው ወቅት ከሃያ ዓመታት በፊት ነበረ፡፡ ሁለተኛው በጣም አመቺ ጊዜ ደግሞ ዛሬ ነው" በሚለው የቻይናዎች ምሣሌ መመራትን መረጠ፡፡ ለእርሻ ድግግሞሽ አመቺው የበጋ ወቅት ቢያልፍም ከሰኔ ጀምሮ ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ በሰፊው ተንቀሳቀሰ፡፡ በተጨማሪም በወቅቱ በእጅ የነበረው ምርጥ ዘር በሙሉ በጊዜ እንዲቀርብና ጥቅም ላይ እንዲውል ከመደረጉም በላይ የምርጥ ዘር እጥረት በማጋጠሙ አርሶ አደሩ የተሻለ ምርታማነት ያለውን የአካባቢ ዘር እያበጠረ እንዲጠቀም ምክር ተሰጠው፡፡ አረም ግን ጊዜ ያለፈበት ስላልነበር ወቅቱን ጠብቆ ሁለት ሦስት ጊዜ ደጋግሞ በማረም የምርት ጭማሪ ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት ተደረገ፡፡

እነዚህ በ1995 ዓ.ም ከረምት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው፣ ነገር ግን በከባድ የጊዜ ውሱንነት ውስጥ መፈጸም የነበረባቸው ተግባራት ነበሩ፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ ከአርሶ አደሩ፣ ከመ.ያተኛውና በየደረጃው ካለው የፖለቲካ አመራር ልባዊ ፍላጎት ውጪ ሊሳኩ የሚችሉ አልነበሩም፡፡ በዚህ መሠረት በነበረችው አጭር ጊዜ መጀመሪያ በየደረጃው ከሚገኙ መ.ያተኞችና የፖለቲካ አመራሮች ጋር መግባባት እንዲፈጠር ጥረት ተደረገ፡፡የፖለቲካ አመራሮችና መ.ያተኞች ከልባቸው አምነው ከተቀበሉት በኋላ ደግሞ ከአርሶ አደሩ ጋር በሰፊው መከሩበት፡፡ ተፈላጊውን መግባባት፣ እንደፈጠሩም የኢትዮጵያን የአነስተኛ አርሶ አደር ግብርና አብዮታዊ በሆነ ቅኝት ለመለወጥ መረባረብ ጀመሩ፡፡ በዚህ ጥረት ድርቁ በተከሰተ ማግሥት የሚታረሰው መሬት ስፋት በአንድ ዓመት የ800 ሺህ ሔክታር ጭማሪ አሳየ፡፡ ምርታማነት ደግሞ በሔክታር ከ9.3 ኩንታል ተነስቶ ወደ 11.95 ኩንታል አደገ፡፡ በ1995 ዓ.ም ወደ 73 ሚሊዮን ዝቅ ብሎ የነበረው የሰብል ምርት በአጭር ጊዜ በተካሔደ ርብርብ በ1996 ዓ.ም ወደ 103 ሚሊዮን ኩንታል አደገ፡፡

በአገሪቱ ታሪክ ግብርናው በአንድ ዓመት የ30 ሚሊዮን ኩንታል ጭማሪ ያመጣበት ብቸኛው ዓመት ይህ ነበር፡፡ በእርግጥ ይህም ሆኖ በዚህ ዓመት የተገኘው ውጤት ከድርቁ በፊት ተደርሶበት ወደነበረው ደረጃ ከመጠጋጋት ያለፈ ስላልነበር መስመሩ በተግባር በዋለባቸው ቀጣይ ዓመታት ከተመዘገቡት ዕድገቶች ጋር ሲነጻጸር ጭማሪው ብዙ ነበር የሚያሰኝ አይደለም፡፡ ጦርነት የማምረት አቅምን አዳከሞ ከቆየ በኋላ ሰላም ለከፍተኛ የምርት ጭማሪ አስተዋጽኦ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ በድርቅ በተጠቃው ግብርና ተገድቦ የነበረው የማምረት አቅም የተሻለ ዝናብ ሲገኝ በፍጥነት ወደቀደሞ ቦታው እንደሚመለስ የሚያሳይም ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ በ1995/96 ዓ.ም የምርት ዓመት የተገኘው ከፍተኛ የዕድገት ምጣኔ የአገሪቱን ግብርና በማያቋርጥ የዕድገት አዙሪት ውስጥ ለማስገባት የመጀመሪያው መነሻ ነጥብ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ያለው አዲስ ታሪክ ነው፡፡

በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ በአነስተኛው የአርሶ አደር ግብና ተግቢው ትኩረት ከተሰጠው በአጭር ጊዜ እመርታዊ ለውጥ ለማስመዝገብ እንደሚችል ታውቆ ያደረ ነው። በዚሁ ዓመት የተካሔደው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ግን ከየትኛውም ንድፈ-ሀሳብ በላይ የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ የአገራችንን ትራንስፎርሜሽን ወይም እመርታዊ ለውጥ እውን ለማድረግ መነሻ ሊሆን እንደሚችል አረጋገጠ። መንግሥትና ኢህአዴግ ከዚህ እንቅስቃሴ በርካታ መሠረታዊ ትምሕርቶችን ወስደው በጐ ልምዶችን ቀመሩ። የአገሪቱ የግብርና ልማት እውን የሚሆነው በመንግሥታዊና ድርጅታዊ ኃላፊነት የተቀመጡ መሪዎችና መ/ያተኞችን ጨምሮ፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የጉልበቱ ባለቤት የሆነው አርሶ አደሩ ከልብ አምኖበት ሲንቀሳቀስ መሆኑ የመጀመሪያው ትምሕርት ነበር። በእርግጥም የሰው ልጅ ካመነበት የማይሠራው ነገር የለምና ከሁሉም ፈጻሚ ኃይሎች ጋር በአስተሳሰብ ተግባብቶ ወደሥራ መግባት ለስኬት የመጀመሪያው ቁልፍ ነው። ሁለተኛው ትምሕርት በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ላይ በመተማመን የሚካሔደው ልማት በፍጥነትና በጥራት ከተፈጸመ የላቀ ውጤት የሚገኝበት እንደሆነ መረጋገጡ ነው። ከሰኔ ጀምሮ በተደረገ አጭር ዝግጅት ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ከተቻለ፣ ከመስከረም ጀምሮ ለበጋና ከረምት ሥራዎች በበቂ ሁኔታ መዘጋጀት ከተቻለ የምርታማነትን ዕድገት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ማድረስ እንደሚቻል ትልቅ ትምሕርት ተቀሰመ።

በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ለምትገኘው ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሀዲሴ መሠረቱ የአነስተኛ አርሶ አደር ማሳ እንደሆነ በጥብቅ ያመነው መንግሥት፣ ከዚህ በመነሳት በእርግጥም የግብርናውን ለውጥና ዕድገት የሚያፋጥኑ እቅዶች አዘጋጅቶ ፖሊሲና ስትራቴጂውን ተግባራዊ ማድረግ ቀጠለ። በዚህ መሠረት ከምንም ነገር በፊት አርሶ አደሩን ሊደግፍ የሚችል የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት ለመገንባት ተንቀሳቀሰ። ከዚህ በፊት ከዘጠኝ ሺህ የማይበልጡ የግብርና ሙያተኞች ብቻ በነበሩባት አገር፣ አንድ የኤክስቴንሽን ሙያተኛ ከስምንት ሺህ በላይ ገበሬዎችን እንዲያማክር ሲደረግ የነበረ በመሆኑ ኢትዮጵያ አርሶ አደሩን የሚደግፍ የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት ነበራት ለማለት አይቻልም። ይህን መሠረታዊ ውሱንነት የተገነዘበው መንግሥት 60 ሺህ የኤክስቴንሽን ሙያተኞችን አሠልጥኖ በ15 ሺህ የገጠር ቀበሌዎች እንዲመደቡ አደረገ። ሙያተኞቹ በተፈጥሮ ሀብት፣ በእርሻ፣ በእንስሳት ሀብት ልማትና በግብይት ሙያዎች የሠለጠኑ ስለነበሩ በገጠር ሁሉን አቀፍ ለውጥ ለማምጣት እጅግ የተመቹ ሁኔታ ተፈጠረ።

ይህ የለውጡ መነሻ ነጥብ ቢሆንም ብቸኛውና የመጨረሻው እርምጃ ግን አልነበረም።

የአነስተኛውን አርሶ አደር ግብርና ውጤታማ የሚያደርጉ የምርጥ ዘር፣ የማዳበሪያ፣ የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦትና ተጠቃሚነት እንዲስፋፋ መደረግ ነበረበት። በድርቅ አካባቢዎች ደግሞ ድርቅን የሚቋቋሙ ዝርያዎችና ለአነስተኛ የርጥበት መጠን ተስማሚ የሆኑ የግብርና መስኮች በተለይም ደግሞ የእንስሳት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የንብ እርባታ መስኮች ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባ ነበር። ትኩረቱ አቅርቦትን ከማሟላት ጀምሮ የአርሶ አደሩን የቴክኖሎጂ ተቀባይነት በማስፋት የሚፈጸም እንዲሆን መደረግም ነበረበት። ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሩ የፋይናንስ አቅሙ ተጠናክሮ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች በራሱ የሚገዛበት ደረጃ ላይ እስኪደርስ በአነስተኛ ወለድ የብድር አገልግሎት እንዲሰጠው ማድረግ አስፈላጊ ነበር። እነዚህ ሁሉ ከፍተኛ የአቅም ውሰንነት ባለባት ኢትዮጵያ በአንዴ ተሟልተው ሊገኙ ወይም ሊቀርቡ የሚችሉ አልነበሩም። ነገር ግን ባለው አቅም ብቻ ሳይሆን በማያቋርጥ ሁኔታ እያደገ በሚሔድ መጠን እንዲቀርቡ ሊደረጉ የሚገባቸው ነበሩ። መንግሥት ይህን ከግንዛቤ በማስገባት ባለፉት አሥራ ሦስት ዓመታት የኢትዮጵያ አነስተኛ ግብርና በዓይነቱ እንዲቀየር በሚያደርግ አኳኋን ተንቀሳቅሷል። ይህ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት እንደሆነ ከዚህ ሠንጠረዥ ለመገንዘብ ይቻላል።

የ23 ዓመታት የግብርና ምርታማነት ዕድገት[46]

ሠንጠረዥ 2

ዓ.ም. (እ.ኤ.አ)	የታረሰ የመሬት ስፋት	የተገኘ አጠቃላይ ምርት	ምርታማነት ኩ/ል በሔ/ር
1987 (94/95)	6,624,825.69	69,266,612.53	10.46
1988 (95/96)	7,948,520.00	92,791,190.00	11.67
1989 (96/97)	8,072,360.00	96,452,380.00	11.95
1990 (97/98)	6,849,300.00	73,626,710.00	10.75
1991 (98/99)	8,016,330.00	85,838,420.00	10.71
1992 (99/2000)	8,216,700.00	88,909,960.00	10.82
1993 (2000/01)	9,445,480.00	106,159,850.00	11.24
1994 (01/02)	7,805,770.00	99,264,403.00	12.72
1995 (02/03)	7,859,494.27	73,694,451.91	9.38
1996 (03/04)	8,669,295.00	103,564,132.00	11.95
1997 (04/05)	9,811,070.00	119,068,102.00	12.14
1998 (05/06)	10,170,911.43	133,821,275.15	13.16
1999 (06/07)	10,592,755.47	149,554,980.91	14.12

2000 (07/08)	10,954,722.54	161,166,574.57	14.71
2001 (08/09)	11,210,501.00	171,167,405.00	15.27
2002 (09/10)	11,503,249.48	180,758,896.00	15.71
2003 (10/11)	11,822,786.20	203,485,288.33	17.21
2004 (11/12)	12,086,603.89	218,570,429.67	18.08
2005 (12/13)	12,282,929.98	231,288,471.77	18.83
2006 (13/14)	12,407,473.46	251,536,623.90	20.27
2007 (14/15)	12,558,444.55	270,328,878.00	21.52
2008 (15/16)	12,486,270.87	266,828,807.04	21.37
2009 (16/17)	12,574,107.33	290,385,593.21	23.09

ከዚህ አኃዝ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የኢትዮጵያ ግብርና ሕገ-መንግሥቱ በፀደቀበት በ1987 ዓ.ም ካስመዘገበው የ69.2 ሚሊዮን ኩንታል ምርት በመነሳት በ2009 ዓ.ም ከ290 ሚሊዮን ኩንታል እህል በላይ ወደማምረት ተሸጋግሯል። ከአሃዛዊ መረጃው ለመገንዘብ እንደሚቻለው አገራችን በ2008 ዓ.ም ባጋጠማት ከፍተኛ የድርቅ አደጋ የመጣው ቅናሽ በሄክታር በአማካይ 15 ኪሎ ብቻ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል። ይህም ድርቅ የማይገመበኛቸው የአገሪቱ ክፍሎች የሚያስመዘግቡት ጭማሪ እዚያው ሳለም የድርቅ አደጋን የመቋቋምና በድርቅ ምክንያት የሚመጣውን ቅናሽ የማካካስ ብቃት እንደተገመናጸፍን ያሳያል። ግብርናው ከሞላ ጎደል በ20 ዓመታት ውስጥ አራት እጥፍ የሚሆን የምርት ጭማሪ ተገኝቶበታል። በአንድ ሔክታር ይገኝ ከነበረው 10.4 ኩንታል ምርት በመነሳት በሔክታር 23 ኩንታል ወደማገኝበት ደረጃ ተደርሷል። ይህ ውጤት ከቅድመ ተሃድሶ ዓመታት ጋር ብቻ ሳይሆን ተሃድሶው መካሔድ ከጀመረበት ከ1995 ዓ.ም ውጤት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ መሻሻል የታየበት ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ በሃያ ዓመታት ውስጥ በእጥፍ ያደገውን ህዝብ ለመቀለብ አልፎ አልፎ ሳይሆን በየአለቱ ምጽዋት ለመጠየቅ እንገደድ ነበር።

በዚህ መሠረት የሰብል ምርት በተሃድሶው አሥር ዓመታት ውስጥ ብቻ ከሞላ ጎደል ከሦስት እጥፍ በላይ አድጓል። ከላይኛው አኃዛዊ ሠንጠረዥ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በኢትዮጵያ የሚታረሰው መሬት ስፋት ከ1987 ዓ.ም ሲነጻጸር ከሞላ ጎደል በእጥፍ ቢያድግም፣ ዋናው የአገሪቱ የግብርና ምርት ዕድገት ከመሬት ስፋት መጨመር የመነጨ አልነበረም። የሚታረሰው መሬት ስፋት ከ6 ሚሊዮን ወደ 12 ሚሊዮን አድጓ በሔክታር የሚገኘው ምርት መጠን 10 ኩንታል ብቻ እንደሆነ ቢቀጥል ኖሮ፣ አገሪቱ በ2007 ዓ.ም የምትደርስበት ዓመታዊ

የግብርና ምርት መጠን 120 ሚሊዮን ኩንታል ብቻ ይሆን ነበር። ነገር ግን የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳና የጉልበት ምርታማነት በተነጻጻሪ ከፍ ያለ ጭማሪ በማምጣቱ 290 ሚሊዮን ኩንታል ማምረት ተችሏል። ይህም የሰብል ምርት ጭማሪው በትንሹ ከመሬት ስፋት፣ በዋነኛነት ደግሞ ከአርሶ አደሩ ምርታማነት ማደግ የመነጨ እንደሆነ ያሳያል።

በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳና ጉልበት በመተማመን በተካሔደው ጥረት በግብርናው ዘርፍ የተገኘው ይህ ውጤት ከፍተኛ የአጭርና የረጅም ጊዜ ፋይዳ የነበረውና ያለው ነው። የመጀመሪያ ጥቅሙ የአርሶ አደሩን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ማስቻሉ ነው። ክረምት ሲደርስ በምርት እጥረት የሚሰቃየውና ያለፈው አዝመራ ከጐተራው በመሟጠጡ፣ አዲሱ አዝመራ ደግሞ ገና ባለመታፈሱ፣ ሐምሌና ነሐሴ ላይ እጅግ መቸገሩን "የፊተኛው አልቆ የኋለኛው ርቆ" በሚል አገርኛ አባባል መግለጽ የሚቀናው አርሶ አደር ከነቤተሰቡ ጠግቦ ማደር መጀመሩ የመጀመሪያው ትልቁ ጠቀሜታው ነበር። የአርሶ አደሩ ምርታማነት በሔክታር ከአሥር ወደሃያ አራት ኩንታል መሸጋገሩ ገቢው በአሥር ዓመት ከእጥፍ በላይ እንዳደገ ከማሳየቱም በላይ ለአሥር ተከታታይ ዓመታት የግብርና ምርቶች ዋጋ ሳይወድቅ ይልቁንም እየጨመረ መሔዱ የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ይበልጥ ያሳደገው ሆኗል።

የተሃድሶው መሥመር የግብርና ፖሊሲ መነሻና መድረሻ የአርሶ አደሩንና የቤተሰቡን ሆድ መሙላት ባይሆንም፣ አርሶ አደሩ ከምርቱ ራሱንና ልጆቹን ሳያቋድስና ሳያጠግብ ምርቱን በሰፊው ወደዓለም ገበያ ማቅረብ እንደማይጀምር ደግሞ አያከራክርም። በመሆኑም አርሶ አደሩ በትንሿ ማሳው ላይ ያመጣው የምርት ጭማሪ ከምንም ነገር በፊት በገጠር የረሀብን ድግግሞሽ በፍጥነት ለመቀነስና ለማስቀረት የቻለ ነበር። ይህ ከ2003-2006 ዓ.ም. ከዓለም አቀፍ ለጋሾች ለአርሶ አደሩ የተሰጠውን የአርዳታ እህል መጠን በመመልከት ብቻ ሊረጋገጥ የሚችል ነው።

ከ2003-2006 የዓለም አቀፍ ዕርዳታ ፍሰትና የተረጂዎች ቁጥር[47]

ሠንጠረዥ 3

ዓ.ም.	የተረጅ ብዛት	የውጭ እዳታ እህል በቶን
2003	4,641,000	504,892
2004	3,843,000	412,488
2005	2,619,000	304,703
2006	2,014,000	131,162

ይህ አኃዝ ባለፉት አምስ ዓመታት ውስጥ ካጋጠሙት ሁሉ የከፋ የሆነው ድርቅ በ2007/08 ከማጋጠሙና የተረጅው ህዝብ ቁጥር ጉልህ ጭማሪ ከማሳየቱ በፊት ባሉት አራት

ዓመታት እርዳታ ፈላጊው ህዝብ ከአራት ተኩል ሚሊዮን ወደሁለት ሚሊዮን እንደ፹ረደ ያመላክታል። ከውጭ በዕርዳታ የገባው እህል መጠንም ከአምስት ሚሊዮን ኩንታል ወደአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዝቅ ብሎ ነበር። ይህ ጥሬ ሐቅ አገሪቱና አርሶ አደሩ በከፍተኛ ፍጥነት ከተመጽዋችነት መላቀቅ እንደጀመሩና ከዚህም አልፎ ገበሬው የራሱንና የቤተሰቡን ቀለብ በማሟላት ሳይወሰን፣ መጠኑ በቀጣይነት ዕያደገ የሚሔድ ትርፍ ምርት ለገበያ ማቅረብ እንደጀመረም ያሳያል። ይህ ገበሬው የተሻለ የመግዛት አቅም እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ በከተሞች የእህል አቅርቦትን በከፍተኛ ደረጃ ለመጨመር አስችሏል።

በእርግጥ በከተሞች የእህል አቅርቦት እየጨመረ በመጣበት ጊዜ በተለይ ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም በነበሩት ዓመታት የዋጋ ግሽበት ከቁጥጥር ውጪ የሚሔድ እስከሚመስል ድረስ ተከስቶ ነበር። ይህም በአብዛኛው ከነዳጅ ዋጋ ንረትና በዚህ የተነሳ ከተፈጠረው የሸማቾች የስጋት ሥነ-ልቦና ጋር የተያያዘ ነበር። ነገር ግን የግብርና ምርት ያለማቋረጥ ማደጉን ተከትሎ የዋጋ ግሽበት ቀስ በቀስ በአንድ አኃዝ እንዲወሰን ለማድረግ ተችሏል። መንግሥት ለጊዜው ከውጭ ገዝቶ ያስገባው የተወሰነ ስንዴ ለዋጋ ግሽበት መረጋጋት ተደራቢ ውጤት የነበረው መሆኑ ባይዘነጋም፣ የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ልማት የእህል አቅርቦትን በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩ ለግሽበቱ መቀነስ ዋነኛው ምክንያት ነበር። እነዚህ በግብርና ልማቱ መስፋፋት የተገኙ ፈጣን ተፅዕኖዎች ነበሩ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በግብርና ልማቱ በተለይ ደግሞ በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ላይ በመተግመን የተቀሰቀሰው መሠረተ-ሰፊ ለውጥ ከዚህም በላይ ልቆ የሚሔድ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ የተገኘበት መሆን ጀምሯል። ይህም ለኢትዮጵያ ፈጣንና መሠረተ-ሰፊ ኢንዱስትሪያዊ ልማት የግድ መሟላት የሚገባው ቅድመ ሁኔታ በአስተማማኝ ደረጃ መሟላት ከመጀመሩ ጋር የተያያዘ ነው። አቶ መለስ በጥብቅ ያምንበትና ይገፋበት የነበረው ግብርና ለኢንዱስትሪ መነሻ የሆነውን የካፒታል፣ የገበያ፣ የሰው ኃይል እንዲሁም የጥሬ ዕቃ አቅርቦት በአስተማማኝ ደረጃ የሚያሟላበት ቅድመ ሁኔታ እውን መሆን ጀምሯል።

ይህ በመሟላት ላይ ያለ ቅድመ ሁኔታ በእንግሊዝ ከተካሔደው ኢንዱስትሪያላይዜሽን ጋር ተያይዞ የዳበረ የገበያ ሥርዓት መነሻ ነጥብ እንደሆነ ተደርጐ የሚቆጠረው "የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት፣" (Primitive Accumulation of capital) በመባል የሚታወቀው ልዩ ምዕራፍ ነው። ይህ ምዕራፍ በአግባቡ ሳይታለፍ፣ ወይም በዚህ ምዕራፍ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ሳይሟላ ኢንዱስትሪያዊ ልማትም ሆነ አስተማማኝ ብልጽግና የሚፈጠርበት ዕድል ጨርሶ ዝግ ነው ባይባልም በአብዛኛው እጅግ አናሳ ነው።

የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት በመባል የሚታወቀው ምዕራፍ የራሱ የተለየ ባሕርይ ያለው ከመሆኑም በላይ በተሳካ ሁኔታ ባልተፈጸመበት አገር ሁሉ ኢንዱስትሪያላይዜሽን በአብዛኛው የቀን ሕልም ሆኖ ቀርቷል። አብዛኞቹ ያልበለጸጉ አገሮች ከፊተናዎች ሁሉ የከበደው ፈተና ሆኖ የሚያገኙት የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት በመባል የሚታወቀውን ይህን ምዕራፍ ነው። ብዙዎቹ ይህን ምዕራፍ በቅጡ ሊጀምሩም ሆነ ሊያሳኩ ካለመቻላቸው ጋር ተያይዞ ኢንዱስትሪያዊ ልማትን የማፋጠን ዕድላቸው እንደመከነ ይገኛል።

ለምሣሌ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አፍሪካ እንደኮሪያ ወይም ታይዋን ይህን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም ባለመቻሏ የብልጽግና መሰላልን መወጣጣት አቅቷት ባለሀበት እርገጥ ስትል ኖራለች። እንደገናም ቻይና ከ1980ዎቹ ጀምሮ ይህን ምዕራፍ በአግባቡ በመፈጸም ወደዕድገት ማማ ስትረማመድ፣ አፍሪካና ላቲን አሜሪካ ግን የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን ማካሔድ ባለመቻላቸው፣ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ብቻ ሁለት ትልልቅ ዕድሎች አምልጠዋቸዋል። (ጆቫኒ አሪጊ 2002) ስለዚህም የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን የማሳካት ወይም ያለማሳካት ጉዳይ ማንኛውም አገር ወደበልጽግና ለመረማመድ ያለውን ዕድል የሚወስን ሆኖ ይገኛል።

ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ በኢትዮጵያ በአስተማማኝ ሁኔታ መሳካት የጀመረው የግብርና ፈጣን ልማት ወደኢንዱስትሪያላይዜሽን ለመሸጋገር ወሳኝ ተፈላጊነት ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት አሐዱ ብሎ ለማሟላት በጣም ምቹ ሁኔታ መፍጠር ጀምሯል። ይህ የመጀመሪያ ካፒታል ክምችት ጽንሰ ሀሳብን ከነተግባራዊ እንድምታው በመጠኑም ቢሆን ዘርዘር አድርጐ በመመልከት በይበልጥ ግልጽ ሊደረግ የሚችል ሲሆን፣ ይህም አገሪቱ በአስካሁን ጉዞዋ ስለፈጠረችው መልካም ዕድል በስፋት በሚዳሰስበት በከፍል ሦስት የሚሸፈን ይሆናል። ከፍል ሁለትን ደግሞ የአምሳዎቹና የስድሣዎቹ የትግል ትውልድ መሐንዲስ ሆኖ በቀየሰው ትግል ባለፉት ሃያ ዓመታት ከተከናወኑ ሥራዎች የጋር ተያይዘው የተፈጠሩ አዳዲስ አገራዊ እውነታዎችን በማጠቃለያ መልክ በማቅረብ መቋጨት ይቻላል።

የተረከባትን አገር በጽኑ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መሠረት ላይ ያዋቀረ ትውልድ፣

ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በተለይ ደግሞ ከተሃድሶ ወዲህ ባሉት ዓመታት የሆነውን ሂደት በዝርዝር መመልከት ጠቀሜታው የጐላ ቢሆንም እንደማንኛውም ተግባር የመጨረሻው ማረጋገጫ ሂደት ሳይሆን ውጤት በመሆኑ የሩብ ምዕተ ዓመታቱን ጉዞ ከወጠት አኳያ መመዘንና ማጠቃለል ተገቢ ይሆናል። በእርግጥ ዛሬም ቢሆን ሂደቱ ጅምር፣

ሰፊና የተወሳሰበ በመሆኑ በዚህ ጽሁፍ ሁሉንም የውጤት ገጽታዎቹን በዝርዝር ለማስቀመጥ አይቻልም። ይሁን እንጅ በዋና ዋና መስኮች የተገኘውን ተጨባጭ ውጤት ማስቀመጥና መመዘን ግን ይቻላል። በዚህ መሠረት የለውጡ መሐንዲስ የነበረው የስድሣዎቹና የሰባዎቹ ትውልድ የተጫወተው ሚና በታሪክ ሲታወስ ምን ሊሆን ይችላል? የዚህ ትውልድ አንድ የተደራጀ አካል የሆነው ኢህአዴግ ደግሞ በመለስ ዜናዊ እየተመራ ባካሔደው ትግል የት ተደረሰ? ከሥልጣኔ አኳያ ኢትዮጵያ በምን ደረጃ ላይ ትገኛለች? ማሸቆልቆሉ ቀጠለ ወይስ ተገታ? ነጻነቷስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ተዳከመ ወይስ ተጠናከረ? ብዙኀነትን በአግባቡ የማስተናገድ ሁኔታዋስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? በሚሉ ጥያቄዎች መነሻነት የተገኙትን ውጤቶች መመልከት ተገቢ ይሆናል። እናም የስድሣዎቹና የሰባዎቹ የትግልና የመስዋዕት ትውልድ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ምን ውጤት አመጣ ቢባል መልሱ የሚከተለው ይሆናል። ይህን ከሌላ ሳይሆን የአገሪቱ ዜጐች ስለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ከተናገሩት ወይም ከሰጡት አስተያየት በመጀመር ማረጋገጥ ይገባል። በ35 የአፍሪካ አገሮች ላይ አምስት ዙር ጥናት ያካሄደው አፍሮባሮሜትር[48] የተባለው የጥናት ተቋም እ.ኤ.አ. በ2013 (2005/06 ዓ.ም.) ጥናቱ ለ2,400 ሰዎች ባቀረበው "የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ምን ያህል ዴሞክራሲያዊ ነች? የሚል ጥያቄ የአገሪቱ ዜጐች የሰጡትን መልስ በሚከተለው ሠንጠረዥ [49] አስፍሮታል።

ሠንጠረዥ 4

	%
የተሟላ ዴሞክራሲ (A full Democracy)	42
መጠነኛ ችግር ያለው ዴሞክራሲ (Democracy with minor problems)	39
ሰፊ ችግር ያለው ዴሞክራሲ (Democracy with major problems)	6
ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ (Not a Democracy)	2
አላውቅም (Don't know)	9
አልገባኝም (Don't understand question/democracy)	1

አፍሮ ባሮሜትር በዚህ ጥናቱ ያገኘውን ውጤትና ለዚህም ምክንያት ያላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ የተቋሙን አስተያየት በማከል፣

"የየትኛውም የኤክስፐርት ጥናታዊ ግምገማ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲ ብሎ ሊሰይማት ባይደፍርም 81 በመቶ ኢትዮጵያውያን ግን አገራቸውን አንድም የተሟላ ዴሞክራሲ ወይም ጥቂት ጉድለቶች ያሉባት ዴሞክራሲ አድርገው ይቆጥሯታል። ይህን "ግራ የሚያጋባ ውጤት" በተሻለ ደረጃ ሊገልጸው የሚችለው ምክንያት ኢትዮጵያውያን ስለአገራቸው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሂደት እጅግ ከፍተኛ አዎንታዊ አመለካከት ያዳበሩ መሆናቸው ነው። ይሁንና እነዚህ አስተያየቶች "ሂሳዊ ግምገማ ያለማድረግ ዝንባሌ የተጠናወተው ዜግነት"ና (A Syndrome of "uncritical citizenship") ስለዴሞክራሲ ለየት ያለ የተጠቃሚነትና የአባታዊነት አመለካከት የሚታይባቸው ናቸው። ለዚህ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሌሎች ምክንያቶች ደግሞ የአገሪቱ ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ፣ በተለይ ደግሞ የትምሕርትና ኮሙኒኬሽን አለመስፋፋትና፣ ለረዥም ጊዜ የቆየው የአንድ ፓርቲ የበላይነትና የፖለቲካ ነፃነት ዝቅተኛነት እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ የሚታይ የፖለቲካ ፍርሃትና በቃለ መጠይቅ ላይ የሚታይ ተጠራጣሪነት ሁሉ ለዚህ አስተዋጽኦ አድርገዋል።"[50] ይላል።

ይህ ጥናት ከተካሄደ አምስት ዓመታት አልፎታል። በእነዚህ ዓመታት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ላይ መሠረታዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚያደርግ ሁኔታ እንዳልተፈጠረ ለማረጋገጥ ባይከብድም ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ላይ ከባድ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳረፋቸው ግን አያጠራጥርም። በዚያው ልክ ደግሞ በዜጐች አስተያያት ላይ ከፍና ዝቅ የሚል ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይህም ሆኖ የአፍሮ ባሮሜትር ጥናት በተጨባጭ ዜጐች ስለአገራቸው ዴሞክራሲ የሰጡትን ምስክርነት ያሳያል። አፍሮባሮሜትር ውጤቱን "ሂሳዊ ግምገማ ያለማድረግ ዝንባሌ የተጠናወተው ዜግነት" አስመስሎ ሊያቀርበው ቢሞክርም የዚህን ዘመንም ሆነ ቀደምት ኢትዮጵያውያንን ሐያሲነት አሳንሶ መመልከት አይቻልም። ኢትዮጵያውያን ስለራሳቸን ብዙ አንናገር ይሆናል እንጅ ስለሌሎች በተለይ ደግሞ ስለመንግሥት ለመናገር አቅመ-ም ድፍረቱም ሞልቶናል። ያም ሆነ ይህ በዜጐች ሳይቀር የተመሰከረለት ዴሞክራሲ በአገሪቱ መስፈኑ የህዝባዊ ትግሉ አንዱና ዋናው ትሩፋት ነው።

ማሽቆልቆልን ገትቶ አገራዊ ትንሳኤን ያፋጠነ ትውልድ፣

በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሽንጡን ገትሮ የታገለው ትውልድ ያለፈበት መንገድ ጠመዝማዛና መሥዋዕት የበዛበት ነበር። ነገር ግን ይህ ትውልድ ገና ከመጀመሪያው አልሞ እንደተነሳው የኢትዮጵያን የማሽቆልቆል ጉዞ ገትቶታል። ከመግታትም

አልፎ በአጠቃላይ ለሃያ አምስተ በተለይ ደግሞ ላለፉተ አሥራ አምስተ ተከታታይ ዓመታተ በዓለማችን ፈጣን ከሚባሉት ዕድገቶች አንዱ የሆነውን የኢትዮጵያ አዲስ የታዳጊነት እውነታ ፈጥሯል።

ኢትዮጵያ ከሞላ ጎደል ከዚህ ሩብ ምእተ ዓመት በፊት በነበሩት አራትና አምስት መቶ ዓመታት በማያቋርጥ የማሽቆልቆል ሂደት ውስጥ ማለፏ ፈጽሞ አያከራከርም። አገሪቱ በእነዚህ በርካታ ዘመናት ከአንዱ ውድቀት ወደሌላው እየተረማመደች በ20ኛው ከፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ራሷን ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ለማግኘት ተገዳ ነበር። የማሽቆልቆሉ ፍጥነት የሚዘገንን ሰብዓዊ እልቂት የሚያስከትል እንደነበር የ1965 ዓ.ም እና የ1977 ዓ.ም ድርቆችና በእነዘህም እንደቅጠል የረገፉትን ኢትዮጵያውያን በማስታወስ ሊገነዘቡት የሚችል ነው። በኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚተረኩ የሰው ልጅ መከራዎችን የሕጻናት ጨዋታ የሚያስመስላቸው ድርቅና ጠኔ በተደጋጋሚ መከሰቱ ሳያንስ አገሪቱን የዘመነ ግሎባላይዜሽን መዘባበቻ እስከመሆን ያደረሳትም ይኸው የማሽቆልቆል ጉዞ ነበር።

ይህ ግን አሁን ታሪክ ሆኗል። በምትኩ ኢትዮጵያ የፈጣን ዕድገት ዓለም አቀፍ ተምሳሌት መሆን ጀምራለች። እኛ ብቻ ሳንሆን ዓለም የመሰከረላት ባለፈጣን ለውጥ አገር የሆነችው ኢትዮጵያ በእርግጥም ማርሹን ወደፊት ካስገባችበት ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም በኋላ ያለው ሂደት በሁሉም መስኮችና አካባቢዎች የፈጣን ለውጥ አገር መሆኗን በገሐድ ያሳየ ነው።

በኢትዮጵያ የማያድግ ዘርፍ የለም። የማይለወጥና ወደፊት የማይራመድ መልከዓ ምድራዊ አካባቢ የለም። ከገጠር እስከ ከተማ ለውጥና ዕድገት ያልጐበኘው የኢትዮጵያ አካባቢ ፈልጐ ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ነው። በቅርቡ ለሥራ ጉዳይ ወደሱዳን ሔጄ ነበር። የሔድኩት ከካርቱም በስተሰሜን 380 ኪ.ሜ ርቀት በገጠር ውስጥ የሚገኝ አንድ ዘመናዊ እርሻ ለመጐብኘት ነው። እርሻው በእርግጥም ዘመናዊ ነበር። ነገር ግን በካርቱምና በእርሻው መካከል ባለው 380 ኪ.ሜ ከሞላ ጎደል አንዳችም ልማት የሚካሔድበት ከተማ አላየሁም። ከተሞቹ ትንንሽ፣ ዘመናዊነት ያልጐበኛቸውና ጥንታዊውን የኑቢያ ሥልጣኔ የሚያመላክቱ ቅሪቶች የሚባሉ ናቸው። ይህ ነው የሚባል አዲስ ግንባታም የለባቸውም። የምጓዘው በመንገዴ ላይ ያየሁዋቸውን የሱዳን ከተሞች ከአዲስ አበባ በሁሉም አቅጣጫዎች በተመሳሳይ ርቀት ካሉ ከተሞች ልማት ጋር ለማስተያየት እየሞከርኩ ነበር። ከአዲስ አበባ ድረዳዋ-ሐረር-ጅግጅጋ፣ ከአዲስ አበባ አሰላ-ሮቤ፣ ከአዲስ አበባ ደሴ-መቀሌ-አዲግራት፣ ከአዲስ አበባ ባሕር ዳር-ጐንደር-መተመ/ሁመራ፣ ከአዲስ አበባ አዋሽ-ሠመራ፣ ከአዲስ አበባ-ሐዋሳ/ሞያሌ፣ ከአዲስ አበባ-ጅማ፣ ከአዲስ አበባ-ነቀምት-አሶሳ ያሉትን ከተሞች ሁሉ በዚህ ንጽጽር ውስጥ አስገባኋቸው። በአገራችን ፈርሶ የማይገነባ ከተማ የለም። በየትኛውም ክልል ትንሳኤ ያልተበሰረለት የኢትዮጵያ ከተማ የለም። የሚቀረን እጅግ ቢበዛም የተጀመረው ለውጥ ደግሞ ትንሽ የሚባል አይደለም።

በብዙ የገጠር አካባቢዎች ተራሮቻችን ከመራቆት ወጥተው በደን መሸፈን ጀምረዋል። በተራሮች ላይ የውሃ ጋኖች እየተቀበሩ መስኮች ውሃ ማመንጨት ጀምረዋል። በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ላይ የምርታማነት አብዮት በመካሔድ ላይ ነው። ገጠሮችን የለውጥ አውድማ በማደረግ የጀመረው የኢትዮጵያ ህዳሴ ከተሞችንም ባልተገመተ ፍጥነት መቀየር ጀምሯል። በዚህ የለውጥ ጉዞ ለእያንዳንዱ ዜጋ ቢያንስ ቢያንስ ሦስት ኩንታል አስተማማኝ የእህል አቅርቦት ማሟላት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። በሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ አምሳ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በዚህች አገር ተጨምረው የህዝባችን ቁጥር ወደ መቶ ሚሊዮን ቢጠጋም፣ በምርት ከፍፍል ረገድ ፍትሃዊነትና ቅልጥፍና ከተረጋገጠ በአርግጥም መለስ እንዳለው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በቀን ሦስቴ በልቶ የሚያድርበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ሱዳን በቀን አራት መቶ ሺህ በርሜል ነዳጅ እያመረተች፣ ከካርቱም ውጭ አንዳችም የሚረባ ግንባታ የሚካሔድባት አገር አለመሆኗ በእጅጉ የሚያስገረምና የሚያሳዝነውን ያህል፣ አንድ በርሜል ነዳጅ የማታመርተው ኢትዮጵያ የባሕር ከፍታ ሲጨምር ወደላይ እንደምትነሳ መርከብ ከጫፍ ጫፍ በትንሳኤ ላይ መሆኗ አግራሞትና ደስታን የሚለግስ ነበር።

ዓለም ሊዘምርለት በጀመረው የኢትዮጵያ ፈጣን ዕድገት ትምሕርትና ጤና እጅጉን ተስፋፍቷል። የመሠረተ-ልማት አቅርቦት በእጅጉ ጨምሯል። መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮም መረብና የውሃና የመስኖ አውታሮች ተስፋፍተዋል። ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለዘመናት የተቆጨንበት የታላቁ ወንዛችን የአባይ ጉዳይም ከኖረው ልማድ ተላቆ በቁጥጥር ሥር መግባት ጀምሯል። በእርግጥም በአፍሪካ ትልቁና የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የአህጉሪቱን የብርሃን ዘመን የሚያበስረው ታላቁ የህዳሴ ግድብ በዚህ ዘመን የለውጥ መሐንዲሶች ኢትዮጵያ ከማሽቆልቆል ወጥታ አዲስ ሥልጣኔ፣ አዲስ ታሪክ መሥራት መጀመራን አብስሯል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ኢህአዴግ ከደርግ የተረከባትን አገር ያለአንዳች ለውጥ ለቀጣዩ ትውልድ የማስረከብን አሳፋሪ ታሪክ ዘግቶ የተለወጠችና ለዚያውም ደግሞ ዓለምን ጉድ ባሰኘ ፍጥነት በመለወጥ ላይ ያለች አገር ለማስረከብ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም ያለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የኢትዮጵያ ጉዞ አዲስ የሥልጣኔ ታሪክ የተሠራበት ነበር ቢባል ከእውነታው የራቀ አይደለም።

አሥራ ዘጠኝ ተጨማሪ የመኖር ዓመታትን የለገሰ ትውልድ፣

እ.ኤ.አ. በ2015 ለህትመት የበቃው ዘ-አፍሪካን ኢኮኖሚ መጽሔት በአክቶበር-ዲሴምበር እትሙ "ደቡብ አፍሪካውያን ዕድሜያቸውን እያሳጠሩ፣ ኢትዮጵያውያን ዕድሜያቸውን እያራዘሙ መሔድ ጀምረዋል።" በሚል ርዕስ፡-

"የሕጻናት ሞት መጠን እየቀነሰ በመጣበት ኢትዮጵያ የወንዶች በሕይወት የመቆየት ዕድሜ (Life Expectancy) በ1983 ከነበረበት 45.5 ዓመት በ2003 ዓ.ም ወደ61.4 ዓመት አድጓል። የሴቶች ዕድሜ በዚህ ጊዜ የጨመረው በአሥር ዓመታት ሲሆን፣ በጤናማ አኳኋን የመኖር ዕድሜ ከዓለም አቀፉ ምጣኔ ሁለት እጥፍ በማደግ በ13.5 ዓመት ጨምሮ 54.3 ዓመት ደርሷል። በአንጻሩ በደቡባዊ አፍሪካ በሕይወት የመኖርም ሆነ በጤንነት የመኖር ዕድሜ ቀንሷል። ከአህጉሩ የዳበረ ኢኮኖሚ አንዷ በሆነችው ደቡብ አፍሪካ ግን ከ1983 ጀምሮ በሕይወት የመኖር ዕድል ቀንሷል። በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ፣ ስትሮክና ኒሞኒያ ምክንያት የወንዶች የመኖር ዕድሜ በ1983 ከነበረው 61 ዓመት ወደ58 የሴቶች ደግሞ ከ69 ወደ61 ዝቅ ብሏል"[51] በማለት ጽፏል።

በመጽሔቱ እንደተዘገበው በምድር ላይ ጤናማ ሕይወት በመኖር መስፈርት ኢትዮጵያውያን እስከ 2003 ዓ.ም የጨመሩት13 ዓመታት ሲሆን በእነዚህ ዓመታት በዓለም ደረጃ የታየው ጭማሪ ግን የኢትዮጵያን ግማሽ ያህል ብቻ ነው። በ2007 ዓ.ም ይኸው በሕይወት የመቆየት ዕድሜ ወደ 64 ዓመት ከፍ ብሏል። በእነዚህ መረጃዎች መሠረት ኢትዮጵያውያን ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ብቻ ከዕድሜያቸን አሥራ ዘጠኝ ዓመታት ቀጥለናል። ይህም ኢህአዴግ ለአምስት ዓመታት በሥልጣን ላይ ሲቆይ፣ የዜጐች በምድር ላይ የመኖር ዕድል በሦስት ዓመት ከስምንት ወር እየጨመረ እንደመጣና በሕይወት የመኖር ዕድል መጨመሩ ለአገራችን የህዝብ ቁጥር በፍጥነት ማደግ የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዳደረገ ያሳያል። ይህ እውነታ በዚህ ጠንካራ መረጃ ተደግፎ ሲቀርብ "ከወዲሁ 'ኢህአዴግን ምረጡ' የሚለው ዘመቻ ተጀመረ እንዴ?" የሚል ተረብ ይጋብዝ ይሆን ወይ? የሚል ሥጋት መቀስቀሱ ባይቀርም፤ ያለ ህድሜ መቀጠፍ እየቀረ፣ በምድር ላይ የመኖር ዕድል እየጨመረ መምጣቱን ያረጋገጠ ውጤት መሆኑ ብዙም አያከራክርም። ሊያከራክር ይችላል ከተባለ ይህ ውጤት የተገኘበት ምክንያት ምንድነው? የሚለው ነው። በዚህም ላይ ሰከን ብሎ መነጋገር ከተቻለ ብዙ ልዩነት ላይኖር ይችላል።

የደርግ ሥርዓት አገሪቱን ያስተዳድር በነበረባቸው የመጨረሻ ዓመታት የዜጐች አማካይ ዕድሜ ወደ 45 ዓመት ዝቅ ብሎ ነበር። ለዚህ ተጠቃሽ የነበሩት ዋና ዋና ምክንያቶች ጦርነቱ፣ በስድሣዎቹ መጨረሻ የተካሔደው ጅምላ ጭፍጨፋ፣ በአንድ ወቅት እንደ ሰደድ እሣት የተቀጣጠለው የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ወረረሽኝ፣ እንደወባ የመሳሰሉ ተላላፊ በሽታዎች መስፋፋትና በረሀብ ምክንያት የሚከሰተው እልቂት ነበሩ። እነዚህ በድምር በለጋ እድሜው የሚሞተውን ዜጋ ቁጥር እንዲያሻቅብ አድርገውት ነበር። ጦርነቱ በየዓመቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ይቀጥፍ ነበር። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኤድስ ጥቃት እንደሆነ

የተረጋገጠውና በደርግ መንግሥት የመጨረሻ ዓመታት ወደወረርሽኝ ደረጃ ተሸጋግሮ የነበረው ችግርም እንደገና በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖችን እልቂት አስከትሏል። እያሰለሰ የሚከሰተው ድርቅ የሚያስከትለውን የረሀብ አደጋ ለመቅረፍ የሚያስችል የመልካም አስተዳደር እጦት በበኩሉ በየዓመቱ ለብዙ ዜጐች ሞት ምክንያት ነበር። በዚህ የተነሳ ድሮም ከአምሳ አምስት ዓመት በላይ ዘልቆ የማያውቀው የመኖር ዕድል በደርግ ዘመን ያለሚቋረጥ ሲያሽቆለቁል ኖሯል።

ይህ ሂደት መገታት የጀመረው በኢትዮጵያ የደርግ መንግሥት ተገርስሶ ሰላም ከወረደና ልማትና ዴሞክራሲ መስፈን ከጀመረ በኋላ ብቻ ነው። ከደርግ ውድቀት በኋላ በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላም ሰፍኗል። በዚህ ምክንያት በ1990-1992 ዓ.ም. በተቀሰቀሰው የኢትዮ-ኤርትራ ግጭት ወቅት ካጋጠመው ሞት በመለስ በወሰጣዊም ሆነ ውጫዊ ግጭቶች ምክንያት የሚከሰት ሰፊ አልቂት የለም። ወጣቶቻችን የጦርነት ሰለባ መሆናቸው ቀርቶ ረሽቦም ዕድሜ ለመኖር ታድለዋል። የኤች.አይቪ.ኤድስ ወረርሽኝ ረዘመ ለሰ ዓመታት ተጉትቶ ቆይቷል። በወባና በረሀብ ምክንያት የሚከሰት መጠነ-ሰፊ የሞት አደጋ ተወግዷል። እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ኢትዮጵያ በሥልጣኔም ሆነ በፋይናንስ አቅም ከእርሷ በብዙ እጥፍ ከምትልቀው ደቡብ አፍሪካ የተሻለ ወጤት እንድታመጣ አስችለዋል። በእርግጥም ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በተከናወኑ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ተግባራት እያንዳንዱ ዜጋ በአማካይ አሥራ ዘጠኝ ተጨማሪ ዓመታት የመኖር ዕድል ተቀዋሎታል። ይህ በማንኛውም መሥፈርት ቢመዘን አገሪቱን ከደርግ የግፍ አገዛዝ በማላቀቅ ለመሠረታዊ ለውጥ ያበቃት የትግል ትውልድ ያስገኘው መልካም ወጤትና የሥራ ፍሬ ነው።

አገራዊ ነፃነትን በጠንካራ መሠረት ላይ የገነባ ትውልድ፣

አ.ህአዴግ የመራው አገራዊ የለውጥ ጉዞ ከወጤት አኳያ የሚመዘንበት ሁለተኛው መስፈርት የኢትዮጵያን አገራዊ ነጻነት ከማጠናከሩ ወይም ከማዳከሙ ጋር በተያያዘ ነው። በኢትዮጵያ የአገራዊ ነጻነት ጉዳይ ከትውልድ ወደትውልድ የተሸጋገረ ለድርድር የማይቀርብ ታላቅ ጸጋ ነው። ይህን ጸጋ በዘመነ ግሎባላይዜሽን በቀላሉ አስጠብቆ ማቆየት በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ አያከራክርም። በአገሮች መካከል ያለው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ትስስርና አንዱ በሌላው ላይ ያለው ጥገኝነት እጅግ በጠነከረበትና በተወሳሰበበት ዘመን፣ ነጻነትን ለዚያውም በጠንካራ መሠረት ላይ ገንቡቦና አስጠብቆ መቀጠል እጅግ ፈታኝ ነው። በተለይ ደግሞ በድኅነት ምክንያት ለተመጽዋችነት የመጋለጥ ዕድል ሰፍቶ በቆየበት ሁኔታ፣ አገራዊ ነጻነትን በብቃት አስጠብቆ የማስቀጠል ጉዳይ በእርግጥም መሪዎችን የሚፈትን መሆኑ አይቀርም። ይህም ሆኖ በኢህአዴግ የተመራው ህዝባዊ ንቅናቄ በዘመነ ግሎባላይዜሽን የኢትዮጵያን ጥንታዊ ነጻነት በአዲስና ጽኑ መሠረት ላይ እየገነባ ተጉዟል።

ኢትዮጵያ በአንጻንድ የኅለሞነተን ክፍሎተ አንደሚያጋተመው ግሎባላይዜሽን በመጥላት ወይም በመፍራት ራሷን ከዓለም ነጥላ እንድትቆም አልተደረገም፡፡ “ግሎባላይዜሽን የሰጠህን ከመቀበል ውጭ ሌላ ዕድል የለም” ብላም እጇን አጣጥፋ አልተቀመጠችም፡፡ ከዚህኛው ወይም ከዚያኛው ጐራ ጋር በመለጠፍ፣ የሌላ ሦስተኛ ወገን መልዕክተኛ እንደትሆንም አልተደረገም፡፡ በራሷ አጀንዳዎች ዙሪያ የምትሽከረከር፣ በራሷ ህዝቦች መብቶችና ጥቅሞች ብቻ የምትመራ፣ ይህን መሠረት በማድረግ ከሌሎች አገሮች ጋር በእኩልነትና በጋራ ተጠቃሚነት መርሆዎች የምትገናኝ፣ ስለዚህም ደግሞ እጅግ የተከበረች ነጻ አገር በምትሆንበት አቅጣጫ እንድትራመድ ተደርጓል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት አገራዊ ፖሊሲዎቿን በነጻነት ስትቀርጽ ቆይታለች፡፡ በቀጥተኛ ወረራ አገሮችን በቁጥጥር ሥር ማስገባት አስቸጋሪ በሆነበት በዚህ ዘመን የፖሊሲ ተፅዕኖ ማድረግ ዋነኛው የመቆጣጠሪያ መንገድ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ በተለይ ድሃና ተመጽዋች ሆነው የጀመሩ አገሮች ከሚሰጣቸው ዕርዳታ በማይተናነስ ደረጃ ከውጭ የፖሊሲ መመሪያ እንዲጫንባቸው ለማድረግ የማይካሔድ ጫና የለም፡፡ አብሶ ደግሞ በድሃና ባልበለጸጉ አገሮች ልማታዊ መንግሥታት በሚቋቋሙበት ጊዜ የበላይነት ካለው የኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ የሚመነጩ የፖሊሲ ጥቃቶች ቀጣይና የማያባሩ ይሆናሉ፡፡ ይህን በመሰለው ሁኔታ አገራዊ የፖሊሲ ነጻነትን አስጠብቆ ለመቀጠል እጅግ ፈታኝ መሆኑ አይቀርም፡፡ ብድርና የእዳ ስረዛ ዕድሎች በዓለም አቀፍ ለጋሾች ምህረት ሥር በወደቁበት ዘመን፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት አላላውስ በሚልበት አገርና እነዚህን ለማግኘት ከዓለም አቀፍ የገበያ አከራሪ ኃይሎች የፖሊሲ መመሪያዎችን መቀበል ግዴታ በሆነበት ዓለም፣ አገራዊ የፖሊሲ ነጻነትን አስከብሮ መቀጠል በእርግጥም ፈታኝ ብቻ ሳይሆን የመቋቋም ብቃት ያለው ልማታዊ መንግሥት ሆኖ መገኘትን የግድ ይላል፡፡

ያለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ጉዞ ከዚህ አኳያ ሲመዘን ኢትዮጵያ የፖሊሲ ነጻነቷን በጥብቅ ያስጠበቀችበት ነበር፡፡ የራሱን አገራዊ ፖሊሲዎች ቀርጾ ከሌሎች ጋር በዚህ መስፈርትና መርሕ ብቻ በመገዛት እየተደራደረ የተጓዘው ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት፣ በእርግጥም የኢትዮጵያን ነጻነት በጠንካራ የአገር በቀል ፖሊሲ መሠረት ላይ የገነባ ነበር፡፡ ገና ከጠዋቱ መዋቅራዊ የማሻሻያ ፕሮግራም (Structural Adjustment Programme) በሚል ስያሜ የመጣውን የኒዮ-ሊበራሊዝም ምክረ-ሀሳብ በራሱ ቅኝት ያስኬደው ኢህአዴግ፣ በየመስኩ የመጡበትን የፖሊሲ ተፅዕኖዎች ተቋቁሟል፡፡ ፕራይቬታይዜሽንን በኢትዮጵያ መሠረታዊ ጥቅሞች ላይ ብቻ ተመሥርቶ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ሊበራላይዜሽንን በተለይ ደግሞ ለውጭ ካፒታል በሚያመች መንገድ የሚካሔድን ሊበራላይዜሽን ለረጅም ጊዜ በጽናት ተቋቁሟል፡፡ በእነዚህ መስኮች የተቃጡ ተፅዕኖዎችን በመቋቋም የጀመረው ንቅናቄ የመሬት መሸጥ መለወጥን

አስቀርቷል፡፡ የፋይናንስ ሴክተሩ ለውጭ ባንኮች እንዳይከፈትና ቴሌኮም አገራዊ ሀብት ሆኖ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡

እየዋለ እያደረ ደግሞ የመንግሥት የተመረጠ ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር፣ መንግሥት ደካማና የኢትዮጵያና የህዝቦቿን ብሔራዊ ጥቅሞች በሚያስጠብቅ ቅኝትና አቅጣጫ ሂደቱን እንዳይመራ የተደረገበትን ጫና ሁሉ ተቋቁሞ በምድረ ኢትዮጵያ በሚኖር የፖሊሲ ቀረጻ የአገሬው ህዝብ ፍላጐትና ጥቅም ገዢ ሆኖ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡ መለስ የፖሊሲ ተፅዕኖዎች ሁሉ “በኢህአዴግ መቃብር ላይ ካልሆነ በስተቀር ኢህአዴግ በቁመ· እያለ ተቀባይነት እንደማይኖራቸው” ደጋግሞ በገለጸው· መሠረት፣ ኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የፖሊሲ ነጻነቷን አስከብራ ቀጥላለች፡፡ አገሪቱ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በገባችበት የፈጣን የዕድገት ምህዋር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አቅሟ መጠናከሩ ነጻነቷ ከፖለቲካዊ ባሻገር በተሻለ ቁሣዊ መሠረት ላይ እንዲገነባ አስችሏታል፡፡ በ2008ዓ.ም የተከሰተውንና ባለፉት አምሳ ዓመታት ካጋጠሙት ሁሉ የከፋውን ድርቅ በራሷ ውስጣዊ አቅም በመተማመን ልትቋቋመው· መቻሏ ብቻ አገራችን በድኅነት ሰበብ ሊደርሱባት ከሚችሉ የፖሊሲ ተፅዕኖዎች ራሷን የመከላከል ብቃቷ እጅጉን ከፍ እንዳለ አረጋግጧል። በዚህ አጋጣሚ የውጭ አገሮችና መንግሥታት ከዚህ ቀደም ላደረጉላት እጅግ ከፍተኛ ድጋፍ ምስጋናዋን በማቅረብ ከእንግዲህ የልማት እንጅ የምግብ ዕርዳታ የሚባል ነገር እንደማያስፈልጋት ለመላው ዓለም ለማሳወቅ የምትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። የስድሣዎቹና የሰባዎቹ የትግል ትውልድ ባደረገው አኩሪ ተጋድሎ አገራችን ከምግብ እህል ተመጽዋችነት ነጻ መውጣቷን በአንድ ታላቅ የምግብ እህል ፌስቲቫል የምትገልጽበት ዘመንም በእጇ ገብቷል።

ኢትዮጵያ ከዓመታት ጥረት በኋላ በራሷ አነስተኛ አርሶ አደሮች ማሳ ልማት ተማምና ህዝቦቿን ለመቀለብ የምትችልበት ደረጃ ላይ መድረሷና ከፍተኛ ሀብት የመፍጠር አቅም ወደሚያጐናጽፋት ኢንዱስትሪያላይዜሽን ለመሸጋገር አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት መጀመሯ በርግጥም አገራዊ ነጻነቷን በጠንካራ የኢኮኖሚ መሠረት ላይ መገንባት እንደጀመረች ያሳያል፡፡ የአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ አቅም ሲገ·ለብት መከበር እንጂ መደፈር እንደማይኖር የዘመናችን ግዙፍ ኢኮኖሚ በመሆን ላይ ካለችው· ቻይና ታሪክ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ እየተገ·ናጸፈችው የመጣችው· ከብርና ዝናም አገሪቱ ለዘመናት የተጓዘችበት የማሽቆልቆል ሂደት ተገትቶ በፈጣን ዕድገትና ለወ·ጥ የመተካቱ ልማታዊ ሂደት ው·ጤት ነው፡፡ ይህ ለመኩራራትና በግብዝ አስተሳሰብ ለመሞላት በር መክፈት የሌለበት፣ ነገር ግን ደግሞ በነባራዊነት የተመዘገበ ታላቅ ውጤት ነው፡፡ ይህን ው·ጤት ማስጠበቅና በአዳዲስ ድሎች ማገ·ልበት ከተቻለ በእርግጥም የኢትዮጵያ ህዳሴ ወደታሰበለት ከፍታ መውጣቱ አያጠራጥርም፡፡ ከዚህ አኳያ ሲመዘን ለው·ጡን በመታንዲስነት የመራው· የስድሣዎችና የሰባዎቹ

ትውልድ በእርግጥም የኢትዮጵያን ጥንታዊ ነጻነት በተነጻጻሪ የተሻለና አዲስ ኢኮኖሚያዊ መሠረት ላይ ገንብቶታል ቢባል አሁንም ከእውነታው የራቀ አይደለም።

ብዙኀነትን ገንቢ አቅጣጫ አስይዞ የመራ ትውልድ፣

በአንድ አገር ውስጥ ብዙኀነት መኖር ወይም አለመኖሩ በራሱ ምንም ማለት ባይሆንም፣ ብዙኀነት ባለበት አገር ይህንኑ በአግባቡ አለመያዝ ደግሞ አገሮችን ለችግር ይዳርጋል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ብዙኀነትን በአግባቡ አለመያዝ አገሪቱ በማያቋርጥ የእርስ በርስ ግጭት እንድትናጥና ድህነቱን በማባባስ አገሪቱ ይበልጥ በማሽቆልቆል ጉዞ አስገብቶ በመበታተን አቅጣጫ እንድትጓዝ በር የከፈተ ነበር። በስድሣዎቹና በሰባዎቹ የለውጥ ትውልድ የተመራው የለውጥ ንቅናቄ ይህን የኢትዮጵያ ፈተና ሆኖ የቆየ ችግር ሥር-ነቀል ሊባል በሚችል መንገድ እንዲፈታ አድርጓል። አገሪቱ ብዙኀነትን በአግባቡ ከመያዝ አኳያ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በተከተለችው መሠረታዊ አቅጣጫ በእርግጥም ሰላምና ፍቅር፣ በእኩልነት መከባበርና አንድነት፣ መተሳሰብና አንድ አገራዊ ስሜት መፈጠር የጀመረባት ጠንካራ የብዙ ህዝቦች አገር መሆን ጀምራለች። አልፎ አልፎ የሚታዩ መለስተኛ ችግሮች የሉም ባይባልም ብዙኀነትን በአግባቡ ያለመያዝ ችግር በመሠረቱ ተፈትቷል።

ይህ አዲስና ብዙኀነትን በአግባቡ ካለመያዝ ጋር ተያይዘው ሲከሰቱ የኖሩ አውዳሚ ግጭቶችን የማስወገድ ብቃት ያገኘና፣ አቅጣጫ ከሁሉ በፊት ኢትዮጵያ የብዙ ህዝቦች አገር መሆኗን በማወቅ የጀመረ ነው። በመሆኑም ከሞላ ጐደል መላ የአገሪቱ ህዝቦች ብዙኀነትን እንደ አንድ ነባራዊ ሁኔታ እንዲቀበሉትና እንዲያምኑበት ለማድረግ ተችሏል። በኢትዮጵያ የቋንቋ፣ የባሕል፣ የታሪክ፣ የመልከዓ-ምድር፣ የእምነት እንዲሁም የሥነ-ልቦና ልዩነትና በተወሰነ ደረጃ ተወራራሽነት ያላቸው በርካታ ህዝቦች እንዳሉ የመንግሥት ይፋ አቋም ብቻ ሳይሆን መላው ህዝቦቿ የሚያምኑበትና የሚቀበሉት ሆኗል። ይህ መሠረታዊ ድል ነው። የአንድ አገር ህዝቦች አንድም ሌላውን በመጫን፣ አሊያም የራስ ያልሆነን በመቀበል እንዲኖሩ ሲገደዱ ለአስከፊ የማንነት ቀውስ ይዳረጋሉ። ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦች አገር ሆና እያለ፣ ኢትዮጵያዊ ለመሆን ብሔራዊ ማንነት ለመስዋዕት መቅረብ አለበት ከተባለ፣ ወይም ደግሞ ብሔራዊ ማንነትን ለማስከበር ሲባል ኢትዮጵያዊነት መስዋዕት ይሁን ከተባለ ሕብረተሰቡ በማያቋርጥ የማንነት ቀውስ መመታቱ አይቀሬ ነው። ሁለቱንም መሆን፣ ሁለቱንም ማወቅና ማከበር እየተቻለ፣ አንዱን ብቻ ምረጥ በሚል አስገዳጅ መርሆ ተዋቅሯ የነበረችው የትላንቷ ኢትዮጵያ፣ ሁለቱንም ማንነቶች በሚያከብር አዲስ ኢትዮጵያዊነት ተዋቅራለች። በአንዳች ምክንያት ወደኋላ የመመለስ ስህተት ካልተፈጸመ በስተቀር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ በማንነት ላይ በተመሠረተ ቀውስ ሕልውናዋ ለከፋ አደጋ የሚጋለጥ አገር መሆኗ አቋርጧል። ከሃይማኖትም አኳያ እንዲሁ ነው።

በኢትዮጵያ ከብዙኀነት ጋር ተያይዞ የተፈጠረው እውነታ ግን በንድፈ-ሀሳብ ወይም በሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ብቻ ተገድቦ የቀረ አይደለም። ይልቁንም ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በተግባር ላይ የዋለ ነው። የቋንቋ፣ የባሕል፣ የታሪክ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር እኩልነት በተግባር ተተርጉሟል። ብሔር፣ ብሔረሰቦች በራሳቸው አስተዳዳር የየአካባቢያቸውን ጸጋ ለማልማትና ለመጠቀም የቻሉበትና የሚችሉበት ሂደት ጐልብቷል። ፈጣኑ የአገሪቱ ዕድገት ብሔር፣ ብሔረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደርን ጨምሮ ከተጐናጸፏቸው መሠረታዊ መብቶች ተግባራዊነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ሩብ ምዕተ ዓመት ብዙኀነትን በተግባር የያዘችበትና ያስተዳደረችበት መንገድ፣ ራሷን ከራሷ ጋር ከማስታረቅ አልፎ፣ በተመሳሳይ ችግሮች የሚናጡ የአፍሪካ ወይም የሌላ ክፍለ ዓለም ህዝቦችን ችግር ለማቃለል ፍቱን መድኃኒት መሆኑ ተመስክሮለታል። ይህ ከጊዜ ወደጊዜ በብዙ ዓለም አቀፍ ተንታኞች ተቀባይነት እያገኘ የመጣ እውነታ ነው።

በኢህአዴግ የተመራው የለውጥ ጉዞ ብዙኀነትን መጠቂያ አድርገው የተሞካከሩ አፍራሽ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ መልከ ለማስያዝና ወደቀና አቅጣጫ ለመመለስ አስችሏል። ይህ እውነታ አዲሲቱ ኢትዮጵያ በአገሪቱ ለዘመናት በአግባቡ ሳይስተናገድ የኖረውን ብዙኀነት በትክክለኛ አቅጣጫ መያዝና ማስተናገድ እንደጀመረች ያመላክታል። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የተጓዘችበት ሂደት ለዘመናት ትልቅ ፈተና ሆኖባት የቆየውን ችግር ከሥረ መሠረቱ መፍታት የጀመረችበት ነው ቢባል አሁንም ከእውነታው የራቀ አይደለም። በዚህ ረገድ ችግር የሚኖር ከሆነ አሁንም አንደኛውን ማንነት ከሌላው በላይ አድርጐ በማጐን ካለአግባብ ለመጠቀም ከመፈለግ ዝንባሌ የሚመነጭ ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ማንነትን ሽፋን አድርገው በመንቀሳቀስ ኢህአዴግ ትምክሕት፣ ጠባብነት፣ ጐሰኝነትና አከራሪነት ብሎ የሚፈርጃቸው የጥፋት አስተሳሰቦች፣ ጨርሶ ያልሞቱ አንዳንዴም አጥፊ በሆነ መልክ የሚያገረሹና የሚገለፁ መሆናቸው አንዱ ፈተና ነው። በየክልሉ በስርቆትና ጸያፍ ዝንባሌ የሚታወቁ አመራሮች ገመናቸውን ለመሸፈን ሲሉ፣ በአጠቃላይ ህዝብን በተለይ ደግሞ የሥራና የብልጽግና ዕድል ሊከፍቱላቸው ያልቻሉ ወጣቶችን በታላቅነትና በበላይነት ስሜት እያነሳሱ በማደናገር ላይ መሆናቸውም ሌላው የችግር ምንጭ ነው። ይህም ሆኖ የበላይነት ይዞ የቆየው አስተሳሰብ ዴሞክራሲያዊ ብሔረተኝነት በመሆኑ እነዚህ አፍራሽ አዝማሚያዎች በአግባቡ እንዲመከቱ ለማድረግ ያስችግራል ሊባል አይችልም። ችግሩ የፊዴራላዊ ሥርዓቱ ወይም ብዙኀነት የተያዘበት መንገድ የተሳሳተ ከመሆኑ የመነጨ አይደለምና።

በተጠቃለለ መልኩ ሲታይ በ60ዎቹና በ70ዎቹ የትግል ትውልድ ተጀምሮ በኢህአዴግ የተመራው የለውጥ ጉዞ ትከከለኛ አቅጣጫዎችን የተከተለ ነበር። ድርጅቱ ከባድ መሥዋዕትነት እየከፈለ ባዳበረው ህዝባዊ ዲስፕሊን እየታገዘ አገራዊ ለውጥን በጽናት ተግባራዊ ያደረገበት

ነበር፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ በኢትዮጵያ ለቀጣዩ ለውጥ መነሻ የሚሆን ጠንካራ መሠረት የተጣለበት ነው፡፡ አገሪቱ በሁሉም የሕይወት መስኮች ወደፊት መራመድ የጀመረችበትና ለቀጣይ ለውጦች የሚሆን የተከማቸ መነሻ አቅም /Critical Mass/ የፈጠረችበት ነው፡፡

ይህም ሆኖ ለውጡ ጅምር እንጂ የተሟላ ለውጥ አይደለም፡፡ አገሪቱ በነብስ ወከፍ ገቢ ደረጃ ስምንት መቶ ዶላር ብትደርስም ዛሬም በዓለም ዝቅተኛ ከሚባሉት አገሮች ተርታ ነች፡፡ ዛሬም ድርቅን የመሰለ አደጋ ያልተለያት፣ ነባርና አዳዲስ ችግሮችና ፈተናዎች የሞሉባት ድሃ አገር ነች፡፡ ለዘመናት ከኖረችበት ጭለማ መላቀቅ የጀመረችና የለኮሰችው ሻማ ደምቆ መብራት የጀመረባት አገር ከመሆን አልፋ የብልጽግና ማማን የተቆናጠጠች አይደለችም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ትላንት ያልነበሩ፣ ነገር ግን በዚህ ዘመን ታጋይ ትውልድ አከራ እንቅስቃሴ የተፈጠሩ በርካታ መልካም መነሻዎች ያሏትም አገር ነች፡፡ እንደማንኛውም የሽግግር ሕብረተሰብ የትላንቱንና የዛሬውን አዳብላ የያዘች፣ ዕጣ ፋንታዋ በእነዚህ መካከል በሚካሔደው ትግል የሚወሰን አገር ነች፡፡ ኢትዮጵያ በመለወጥ ላይ ያለች አገር መሆኗ በራሳችን ብቻ ሳይሆን አንዴ የረሀብ ተምሳሌት አድርገው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሰቆቃዎች ሁሉ ምድር አስመስለው ሲገልፁዋት በኖሩ አገሮችና የዓለም መገናኛ ብዙኀን ሳይቀር የተመሰከረላት ሆኗል፡፡

ይህን ልዩ ልዩ ተቋማት በየመገናኛ ብዙኀኑ ኢትዮጵያን በማስመልከት ከሰጡት መግለጫ በመነሳት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ከሰሐራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመጻፍ የሚታወቀውና ኢ.ኤ.አ በ1982 “Ethiopia: An Heretical Revolution” የሚል መጽሐፍ ያሳተመው ሬኔ ለፎርት አሁን ስላለው የአገራችን ሁኔታ ባቀረበው አዲስ ትንታኔ መመልከት ይቻላል። ሬኔ ላፎርት ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር በመሆን በቅርቡ ባሳተመው መጽሐፍ ፡-

> “ዛሬ ዛሬ አንድ የውጭ ጐብኝ ወደአዲስ አበባ ሲመጣ የሚፈጠርበት የመጀመሪያው ስሜት መደመም ነው”፡፡ ዘመናዊ ባለአራት መሥመር ሰፊ መንገዶችን ጨምሮ አዳዲስ መንገዶች በብዛት ይገነባሉ፡፡ የመጭውን ጊዜ ከሚያመላክቱ ትልልቅና ዘመናዊ ሕንጻዎች ጀምሮ እስከ መለስተኛ ህዝባዊ መኖሪያ ቤቶች ይስፉፋሉ፡፡ ከየትኛውም አፍሪካዊ ዋና ከተማ በላይ ሰፋ ያለ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጥና በድልድዮች ላይ የተዋቀረ የባቡር/ትራም አግልግሎት ሁሉ ተጀምሯል፡፡ ፍጥነቱና ለጥጦ የመመኘቱ ጉዳይ እጅግ የሚያስደንቅ ነው፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአህጉሪቱ ውስጥ የአዲስ አበባን ያህል ፈጣንና መጠነ ሰፊ የዘመናዊነት ጉዞ ያደረገ ዋና ከተማ የለም፡፡ በብዙ የከልል ከተሞችም ተመሳሳይ የለውጥ ሂደት እየተከናወነ ነው፡፡ ...ኢትዮጵያን

ፈሠሠረተ-ልሣተና ከቁባዊ ዕድገት በመነሳት ለሚተነትን ማንኛውም ታዛቢ፣ በተጨባጭ የሚታየው ነገር ሁሉ የሚያረጋግጠው መንግሥት በነዳጅ ላይ ሳይመሰረት ባለፉት ስምንት ዓመታት የሁለት አኃዝ ዕድገት ማረጋገጡ ትክክል እንደሆነ ነው፡፡ አንድ የተቃዋሚነት ዝንባሌ ያለው ጋዜጠኛ 'መንግሥት የምሥራቅ እስያ ዕድገት የመጣባቸውን ምስጢራዊ ኮዶች ፈልፍሎ በማውጣት በኢትዮጵያ መሠረት ላይ ተክሏቸዋል' ብሎ ለማመን መገደዱ ይህንኑ ያሳያል"[52] ይላል፡፡

ጸሐፊው ይህን መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ዕድገት ብዙ ጉድለቶች እንዳለበት ለመጠቆም የሞከረ ቢሆንም፣ ቢያንስ ቢያንስ በጽሁፉ መጀመሪያ ላይ ስለተቀየረው የኢትዮጵያ ሁኔታ ትክክለኛ ማብራሪያ በመስጠት መጀመሩ የአገራችን ዕድገት ጠንካራ ሂስ በሚሰነዝሩ ሰዎች እይታም ሳይቀር የተመሰከረለት እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ቻርሎት አሸተን የተባለው የቢቢሲ ጋዜጠኛ ደግሞ እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 15 ቀን 2011 "ኢትዮጵያ ከዓለማችን ፈጣን ታዳጊ ኢኮኖሚዎች አንዷ" /Ethiopia: One of the Fastest Growing Economies/ በሚል ርዕስ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡

"ድርቅና ርሀብ የተንሰራፋባት እንደሆነች፣ በማያቋርጥ የድንበር ግጭትና የፖለቲካ ጭቆና እንደምትሰቃይ ተደጋግሞ ሲነገርላት የምንሰማት ኢትዮጵያ፣ ፈጣኑ የዓለማችን ኢኮኖሚ ዕድገት የሚታይባት አገር እንደሆነች ቢነገራችሁ ትደነቁ ይሆናል፡፡ አሁን አሁን አፍሪካ ላይ ገንዘባቸውን ኢንቨስት ለማድረግ የሚያመነቱትን የውጭ ኢንቨስተሮች በፍጥነት እያማለለች መገኘቷም የማያስደንቅ ሆኗል"[53] ይላል፡፡

የአፍሪካ የኢኮኖሚክ ሁኔታ ላይ የሚያተኩረውና በአፍሪካ ልማት ባንክ፣ በኦኢሲዲ (The Organization for Economic Co-operation and Development /OECD) የልማት ማዕከልና በተ.መ.ድ የልማት ፕሮግራም ትብብር የተመሠረተው "The African Economic Outlook (AEO)" በአምሳ አራት የአፍሪካ አገሮች ላይ በማተኮር የሚያጠኑ የተለያዩ ተመራማሪዎች፣ ኢኮኖሚስቶች፣ የስታቲስቲክስና ሌሎች ባለሙያዎች ያቀፈ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ2013 ሪፖርቱ ላይ ኢትዮጵያን በማስመልከት፡-

"እ.ኤ.አ. በ2012/13 የበጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ9.7% አደገ፡፡ ይህም ለአሥር ተከታታይ ዓመታት የታየፈጣን ዕድገት ነው፡፡ በ2012 ኢትዮጵያ ከዓለማችን 12ኛዋ ፈጣን ዕድገት ያስመዘገበች አገር ነበረች፡፡ አማካይ የዕድገት ምጣኔዋም 10.9% ነበር፡፡ ይህ የዕድገት አዝማሚያ እ.ኤ.አ. ከ2013–15 ባሉት ዓመታትም አነስ ባለ ፍጥነት እንደሚቀጥል

ይጠበቃል::" ብሎ ነበር::

የእንግሊዙ ዘ-ጋርዳያን ጋዜጣ ዘጋቢ ዴቪድ ስሚዝ በበኩሉ፣ ኢትዮጵያን በማስመልከት "በ'አፍሪካዊ አንበሳነት' የምትሞገሰውና ሚሊየነሮችን በፍጥነት የምታመርተው አገር" ("Ethiopia Hailed as 'African Lion' With Fastest Creation of Millionaires") በሚል ርዕስ፣ "በ1984 ድርቅ በማይከል ቡሬከ ዘገባ የተብጠለጠለችው ኢትዮጵያ በስድስት ዓመታት ውስጥ አገራዊ አጠቃላይ ምርቷ (GDP) በ93% እንዳደገ በጥናት ተረጋገጠ::" በማለት ከጀመረ በኋላ ጉዳዩን ከሰባ ሰባቱ ድርቅ በመነሳት ሲተነትን፣

> "ሲነጋጋ ነው:: ፀሐይ ተፈልቅቃ የሌሊቱን ቁር ማባረር ስትጀምር ከኮረም ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው የተንጣለለ ሜዳ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ከምናውቀው የባሰ የድርቅ እውነታ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ላይ መኖሩን ታጋልጣለች:: በእርዳታ ላይ የተሰማሩት ሠራተኞች 'ይህ ቦታ ለገሐነም የቀረበው ምድራዊ ቦታ ነው' ይላሉ:: እ.ኤ.አ. በ1984 በቢቢሲው ማይከል ቡሬከ የቀረበው ይህ የቴሌቪዥን የዜና ሪፖርት፣ ኢትዮጵያ የድርቅ ምድርና ሊታደጓት የሚገባ አገር እንደሆነች በወቅቱ ለነበረው ትውልድ ያሳስባል:: ከ30 ዓመታት በኋላና አገሪቱ ባለፉት አሥርት ዓመታት ባስመዘገበችው አንጸባራቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ግን በፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ "አፍሪካዊ አንበሳ" በመባል መሞገስ ጀምራለች:: ኒው ወርልድ ዌልዝ በተባለው እንግሊዝና ደቡብ አፍሪካ ላይ በሚገኝ አማካሪ ድርጅት ጥናት መሠረት በአፍሪካዊቷ አገር እ.ኤ.አ. በ2007 አንድ ሺህ ሦስት መቶ ብቻ የነበሩት የዶላር ሚሊኒየሮች በያዝነው ዓመት መስከረም ላይ ወደ 2,700 ከፍ ብለዋል:: ጥናቱ የሚሊዬነሮቹ መነሳት ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ እንደሆነ ያረጋገጠ ሲሆን፣ በዚህም ረገድ ከፍተኛ ውጤት አምጥታለች:: ተከታዩዋ ግብፅ በ81%፣ አንጐላ በ61% ሲያድጉ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ግን [በስድስት ዓመታት] በ93% አድጓል።"[54] ይላል::

በታዋቂው የኒውዮርክ ታይምስ የማርች 3 ቀን 2015(እ.ኤ.አ) ዕትም ላይ የጋዜጣው ዓምደኛ ኢስማኤል ኩሽኩሽ በበኩሉ፣ "ለረጅም ጊዜ በድኅነት የማቀቀችው ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ማንሰራራትን ስትጋልብ" (Ethiopia, Long Mired in Poverty, Rides an Economic Boom) በሚል ርዕስ :-

> "በአንድ ወቅት የድኅነትና ረሐብ ከፍተኛ መገለጫ የነበረችው ኢትዮጵያ በመለወጥ ላይ ነች፣ የአሜሪካን ምርጥ ዘፋኞች 'ዊ አር ዘዎርልድ' ብለው

እንዲዘምሩ ያስገደደችው አገር፣ ድርቅና ረሀቧ ካለፈ ከሦላሳ ዓመታት በኋላ በዓለም ባንክ ሪፖርት መሠረት ከአሥር ዓመታት በላይ የዘለቀ አማካይ የ10% የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ እያስመዘገበች ቀጥላለች::በዚህ አያያዟም ብዙዎቹን የምዕተ-ዓመቱ ግቦች ታሳካለች ተብሎ ይገመታል"[55] ይላል::

አንዳንድ የውጭ ታዛቢዎች ኢትዮጵያን ከማብጠልጠል ወይም ዳር ቆመው በሩቁ ከመታዘብ ወጥተው ስለአገራችን ልማት እንዲህ ከማውራታቸው በፊት ብዙ የውጭ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መገናኛ ብዙኀን በኢትዮጵያ ላይ ያላካሔዱት ዘመቻ አልነበረም:: አፍሪካን ማብጠልጠል የሚቀናቸው እነዚህ የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያ ላይ ሲደርሱ ደግሞ እንዲብስባቸው የሚያደርግ ተጨማሪ ምክንያት ነበር:: አገሪቱ የፖሊሲ ነጻነቷን አስከብራ የምትጓዝ መሆኑ በእነዚህ ወገኖች ለሚሰነዘርባትና ርዕዮተ-ዓለማዊ ለሚባል ጥቃት እንድትጋለጥ ያደረገ ነበር:: በመካከለኛው ምሥራቅ በየአደባባዩ የሰዎችን አንገት የሚቀሉ፣ እጅ የሚቆርጡና ገላን በግርፋት የሚተለትሉ አገዛዞችን ችላ ብለው ኢትዮጵያን ለዓመታት በሲቪልና ፖለቲካዊ መብት ጥሰት ሲከሱ የነበሩት እነዚህ ሰዎችና ተቋማት ግን ስለአገራችን እንደገና መስጠት በጀመሩት አዲስ ምስክርነት ቃላቸው መቀየር ጀምሯል:: ጊዜና ቦታ ባይገድብ ኖሮ በመቀየር ላይ ስላለው የኢትዮጵያ ገጽታ ከዚህም በላይ ማለት ይቻል ነበር::

ላለፉት ሃያ አምስት፣ በተለይ ደግሞ ከተሃድሶው በኋላ ባሉት ዓመታት በኢትዮጵያ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት በተካሔደው ትግል በእርግጥም ልማታዊ አቅም መፈጠር የጀመረውን ያህል ኪራይ ሰብሣቢነትም ላይ ከባድ ትግል በማድረግ መልካም ውጤቶች ተመዝግበዋል:: ነገር ግን ኪራይ ሰብሣቢነትን ተፋልሞ የማዳከሙ ሂደት በተራ የአንድ ለአንድ ሂሳባዊ ስሌት የሚታይ ውጤት የሚገኝበት ነው ማለት ፈጽሞ አይቻልም:: ትግሉ በሕብረተሰብ ውስጥ የሚካሔድ መሆኑን ተከትሎ ብዙ ውጣ ውረድ የሚታይበትና አንዳንዴም ያልተገመቱ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤቶች ሊገኙበት የሚችል ሂደት ነው:: ለምሣሌ በኢትዮጵያ ሀብት የመፍጠር ሂደት መስፋፋቱን ተከትሎ አላግባብ የመጠቀም አዝማሚያ፣ ተግባርና በዚህም ተጠቃሚ መሆን በእጅጉ ተስፋፍቶ ይገኛል:: ፈጣኑ ለውጥ ከእርሱ ጋር የሚመጥን ጥራት ያለው ተቋማዊ የአቅም ግንባታ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሊካሔድ ባለመቻሉ በየቦታው ለአድርባዮችና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ዝንባሌ ላላቸው ሰዎች ወደኃላፊነት መምጣት በር ከፍቷል:: በዚያው ልክ ደግሞ በተለይ በመንግሥታዊ ሥልጣን አላግባብ የመጠቀም አዝማሚያ እንዲሰፋ አድርጓል:: በዚህም ደረጃ ለውጥ የሚጠላና የሚፈራ የተከማቸ አቅም መፈጠር ጀምሯል:: ይህ በማንኛውም የሽግግር ሕብረተሰብ ውስጥ መታየቱ የማይቀር እንደሆነው ሁሉ በኢትዮጵያም ሳይከሰት ይቀራል ተብሎ ሊገመት የማይችልና የማይገባው ነው:: ይህም ሆኖ

ወደኋላ እንደሚታየው በዚህ ረገድ የተፈጸሙና በመፈጸም ላይ ያሉ ስህተቶች የሚያስጐመዥሯ ሁኔታ የፈጠረውን የአገራችን ትንሳኤ ተወደደም ተጠላም ለጊዜው ለአደጋ ማጋለጥ ጀምሯል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በመለስ ዘመን በተነደፈው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ፖሊሲ ተግባራዊነት አገሪቱ ከእንግዲህ በላቀ ፍጥነት ወደፊት ለመወንጨፍ እንድትችል የሚያበቃት የተከማቸ አቅም /Critical Mass/ መፈጠር መጀመሩ፣ ኢትዮጵያን ወደአዲስ የህዳሴ ከፍታ ለማሸጋገር ከበቂ በላይ መልካም መነሻ ነው። ይህ የተከማቸ አቅም አሁንም በመሪ ድርጅቱ እጅ ባሉት ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ዲሲፕሊን የተሞላበት ትግበራ ከተሸኘ፤ ወደፊት ከሚገባባቸው መድረኮች ጋር ተያይዞም እንደገና በጠራና ባደገ ፖሊሲ እንዲመራ ለማድረግ ከተቻለ በእርግጥም የኢትዮጵያን ዘላቂ ህዳሴ ማረጋገጡ አይቀርም። የተከማቸው አዎንታዊ አቅም ገደብ ሊያሳርፉብት ከሚችሉ ተጨባጭ ችግሮችና ድክመቶች ተላቆ በሙሉ አቅሙ እንዲለቀቅ ማድረግ ከቀጠለ፤ ይህ በልማታዊ መንግሥት ፖሊሲዎች ተግባራዊነት የተፈጠረ አስጐምጂ ሁኔታ በሚታዩ አሳሳቢና አስፈሪ ድክመቶች እንዳይመከን ከተደረገ፤ በእርግጥም የኢትዮጵያ የብልጽግና ዕድልና ተስፋ በእጇ ገብቷል። ለዘመናት ተከርችመው የነበሩ የመልካም ዕድል መስኮቶች /Windows of Opportunity/ ለአገሪቱ መከፈት ጀምረዋል።

በዓለማችን መልካም ዕድልና አጋጣሚ፣ በተወሰነ ደረጃም ደግሞ እንደዛሬዋ ኢትዮጵያ ለልማት ጥሩ መነሻ የሚሆን የተከማቸ አቅም ፈጥረው ይህንኑ ወደዕድገትና ትራንስፎርሜሽን መቀየር የተሳናቸው ብዙ አገሮች ታይተዋል። በብዙ አገሮች ጥቂት የማይባሉ የከሸፉ ልማታዊ መንግሥታት እንዲፈጠሩ ካደረጉት መሠረታዊ ምክንያቶች፣ አንዱ በፈጠሩት የተከማቸ አቅምና ጸጋ በአግባቡ ለመጠቀም ካለመቻል ጋር ተይይዞ የተፈጠረ ችግር ነው። ብራዚል ለበርካታ ዓመታት በኪፈል ልማታዊ ባህርይ በነበረው መንግሥት ከፍተኛ የዕድገት ምጣኔ እያስመዘገበች የተጓዘች አገር ነበረች። ነገር ግን የተሟላ ትራንስፎርሜሽን ማምጣት የቻለች አልነበረችም። በርካታ የደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮችም ከ1960ዎቹ ጀምሮ ከፍተኛ የዕድገት ምጣኔ ያስመዘግቡ ቢነበሩ ተመሳሳይ መንግሥታት የሚመሩ ነበሩ። ነገር ግን በልማታዊ ጐዳና ተጉዘው ወደወንዙ ጫፍ መድረስ ሳይቻላቸው ቀርተዋል። ከእነዚህ ቢተጻራሪ ደግሞ፤ የፈጠሩትን የተከማቸ አቅም፣ ሌላ አዲስ ልማታዊ አዙሪት ለመፍጠር የተጠቀሙበትና በዚህም ታግዘው ከግማሽ ምዕተ-ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ለተሟላ ትራንስፎርሜሽን የቦቁ አገሮች፣ ቢተለይ በሲሜን ምሥራቅ እስያ ብዙ ናቸው። ኢትዮጵያ በእነዚህ መሐል ትገኛለች። ወደየትኛው ጐራ እንደምትገባ የሚወሰነው በሦዘቦቿና በመሪዎቿ ምርጫና እያያዥ ነው።

ሁለቱም በአገሪቱ ፊት የተደቀኑትን አዳዲስ ፈተናዎችና የተፈጠሩ መልካም ዕድሎች በመመልከት ለእነዚህ በሚሰጡት ግብረ መልስ የአገሪቱ ጐራ ለይቶለት አንዱን ያቁላቁላል። ከዚህ ውጭ ሌላ ዕድል የለም። ለለያነም ይህ ሂደት ቦከፍተኛ ጥንቃቄና አሰታፊ መርህ ሊመራ

ይገባዋል፡፡ በአመራር ኃላፊነት የነበሩትን ነባር ታጋዮች ጨምሮ፣ አዲሶቹ መሪዎች ብቻ ሂደቱን ሊወስኑት እንደማይችሉና እንደማይገባው ሁሉ፣ ህዝቡም ብቻውን ወደትክክለኛው አቅጣጫ ይገባል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ መሪዎቹ “እኛ ብቻችንን ችግሮቹን ለይተን፣ መፍትሔውን ቀምመን ህዝቡን እንግተዋለን” በማለት እንኳን ወንዙን እስከመዳረሻው ልንዳዝበት በጠባቡ የወንዙ ክፍልም ልንሻገር አንችልም፡፡ ህዝቡም እዚህ ድረስ እየመሩ ያመጡን መሪዎች እስካሉ ድረስ፣ ማርና ወተት ወደሚፈስበት ምድር ሰተት ብለን እንገባለን ብሎ በመጠበቅ ረጅም ርቀት አይሔድም፡፡ የሚያጋጥሙን ፈተናዎችም ሆኑ የሚከፈቱልን መልካም ዕድሎች በጋራ መለየትና መፈታት ያለባቸው ናቸው፡፡ ፈተናውም መልካም ዕድሉም የጋራ ናቸውና ፈተናውን አሸንፎና በመልካም ዕድሉ በተሟላ ደረጃ ተጠቅሞ ካሰቡበት የበለጸገ ሕብረተሰብ ለመድረስ፣ ለጋራ ትግል በጽናት መቆም ይገባል፡፡

እናም እነሆ ፈተና፣ እነሆ መልካም ዕድል
ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ህዝቦችና መሪዎች!!!

ክፍል ሦስት

"በሰው ልጅ የታሪክ ጉዞ ቦታም ሆነ ጊዜ ሳይወሰነው የሚከሰት አንድ ጉዳይ ቢኖር፣ መንግሥታት ከትክክለኛው የአገር ጥቅም የተለየ ፖሊሲ ሲከተሉ የሚታዩ መሆኑ ነው። የሰው ልጅ ከየትኛውም ተግባሩ ሁሉ የመንግሥት አስተዳደርን በትክክል በመምራት ረገድ ከባድ ድክመት ያሳያል። በመሆኑም በመልካም ልምድ ላይ የተመሠረተ ፍትሃዊነትና ሚዛናዊነት እንዲሁም በእጁ ባለው ሰፊ የመረጃ ሀብት ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ ውሳኔ የማሳለፍ ጥበብ ተሰፋ በሚያስቈርጥ ደረጃ ጐድሎት ይገኛል። ስለሆነም ከቶ ለምን ይሆን ከፍተኛውን የሥልጣን ቦታ የሚይዙ ሰዎች በምክንያታዊነትና በሠለጠነ አግባብ የሚራመድን የራስ ጥቅም (Enlightened self interest) በሚጻረር መንገድ የሚራመዱት? ከቶስ ለምን ይሆን በብስለት ላይ የተመሠረተ የማሰብ ሂደት የሚጐድለው?[56]

ባርባራቱችማን

ምዕራፍ ስምንት፣

የኢትዮጵያን መጻኢ ዘመን የሚወስኑ ፈተናዎችና መልካም ዕድሎች፣

በኢትዮጵያ ፊት የተደቀኑ ፈተናዎችና መልካም ዕድሎችን፣ በተለይ ደግሞ ከዚህ ወቅትና ከመጭው ዘመን ጋር በተያያዘ አኳኋን ለመተንተን ሲሞከር፣ በጊዜ ገደብ መወሰን ካልተቻለ በስተቀር ከጥንቆላ የማይለይ ሙከራ መሆኑ አይቀርም፡፡ በእርግጥ አገሪቱ ዛሬ ከደረሰችበት ደረጃ በመነሳት ቅርብ ርቀት ሊሆን የሚችለውን መገመት በጣም አስቸጋሪ ሊሆን አይችልም፣ አይገባምም፡፡ ስለዚህም በዚህ ክፍል ለማመላከት የምሞክረው አገራችን ከደረሰችበት ደረጃ በመነሳት ከፊት ለፊቷ የተደቀኑትን የዛሬና የቅርብ ርቀት ፈተናዎችና መልካም ዕድሎች ነው፡፡ በዚህ መሠረት መጀመሪያ ከአገር ውስጥ የፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች ይቀርባሉ። በመቀጠል ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች የሚፈልቁ ተግዳሮቶችን በማስከተል በመጨረሻ በአገራችን እጅ የገቡ መልካም ዕድሎች የምላቸውን በማቅረብ ወደማጠቃለያው እሸጋገራለሁ።

የሩብ ምእተ ዓመት የዴሞክራሲ ሙከራና የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ፈተናዎች፣

በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ከተጀመረ ሃያ አምስት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት በጣም ብዙ መሠረታዊ ለውጦች እንደመጡ በክፍል አንድና ሁለት ተዘርዝሯል፡፡ አገሪቱ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ ልትበቃ የቻለችው፣ በከባድ ትግል በተመዘገቡት ዴሞክራሲያዊ ለውጦች ምክንያት ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሂደት አዳዲስ የመድረክ ፈተናዎች መቀስቀሳቸው ደግሞ አይቀሬ ነበር፡፡ በመሆኑም በአገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያጋጠሙትን ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች በጥንቃቄና በብስለት እየለየን በመፍታት ለመጓዝ እንደሞከርነው ሁሉ፣ በዚህ መድረክ የሚታዩትን ፈተናዎችም በተመሳሳይ ብስለት መያዝና መፍታት ይገባል፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የአንድ ፓርቲ ብቸኛ ተግባር አይደለም፡፡ ሌሎች ፓርቲዎችም የሚሳተፉበትና ከሁሉ በላይ ደግሞ የዜጐችና የህዝቦች ተሳትፎ በተረጋገጠበት ልኳኋን መከናወን ያለበት የለውጥ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም ተግዳሮቶቹን በመለየትም ሆነ በመፍታት ጉዳይ ላይ ሰፊ አገራዊ ምክክር ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ቀጥለው የቀረቡት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ተግዳሮቶች በዚህ መንፈስ የቀረቡ ናቸው፡፡

በበኩሌ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አኳያ የኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ተግዳሮቶች ናቸው የምላቸው አምስት ጉዳዮችን ነው። ራሳቸውን ችለው ቢታዩ ምናልባት ጐልተው ሊወጡ የሚችሉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ንዑሳን ተግዳሮቶች ሆነው በእነዚህ ውስጥ ተካተው ቀርበዋል። የመጀመሪያው ትልቅ ፈተና መልካም አስተዳደር ከማስፈን ጋር የተያያዘው ነው። ሁለተኛው እውነተኛ የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና፣ የዚህ መገለጫና አራማጅ የሆኑ የዴሞክራሲ ተቋማትን ከመገንባትና ነጻነታቸውን ከማክበር ጋር የተያያዘው ፈተና ነው። ይህም ከሌሎች ተቋማት በተጨማሪ ራሱን አውራ ፓርቲውንና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ይመለከታል። ሦስተኛው ፌዴራላዊ ሥርዓቱን ከጥገኛ አስተሳሰቦች በማላቀቅ አጠናክሮ የመገንባትና የማስቀጠል ጉዳይ ነው። አራተኛው ደግሞ የመሪ ፓርቲውን ጤንነት የመጠበቅ ጉዳይ ሲሆን፣ አምስተኛው ፈተና ደግሞ ከፈጣኑ ዕድገት ጋር የተፈጠረውን የሽግግር ማኅበረሰብ ከመምራት ጋር የተያያዘ ነው። እነዚህን ተግዳሮቶች ዘርዘር **አድርጐ** በመመልከት በመገንባት ላይ ያለውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕጣ ፈንታና የአገሪቱን **መጻኢ** ዕድል እንዴት እንደሚወስኑ ለመገንዘብ ይቻላል።

መልካም አስተዳደርን በዘላቂነት የማስፈን ፈተና፣

በአገራችን በመገንባት ላይ ያለው ሥርዓት በዚህ ረገድ ያጋጠመውን ፈተና ለመገንዘብ የራስ ወዳድነት ዓይነተኛ ምሣሌ ከሆነው "የአይጦች የሩጫ እሽቅድድም" (Rat Race) መነሳት ጥሩ ይሆናል። የአይጦች የሩጫ እሽቅድድም የሚባለው ተምሳሌታዊ አገላለጽ አንድ ነገር ለማግኘት ወይም ከአንድ አደጋ ለመሸሽ ከሚሽቀዳደም የአይጥ መንጋ ባሕርይ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ዓይነቱ እሽቅድድም ውስጥ የገቡ አይጦች በድንገት በመረጡት አንድ አቅጣጫ ግር ብለው ይጓዛሉ። "አንተ ትበስ አንቺ ትብሸ" የሚል መተሣሰብ በሌለበት፣ አንዱ በሌላው አናት ላይ ተረማምዶ ለመቅደም ይሞክራል። ለአቅመ ደካማ፣ ለትንንሾቹ አይጦችም ሆነ ለነፍሰ ጡሮች ማሰብ ብሎ ነገር የለም። ጉልበት ወይ ብልጠት ያለው በውድ ጓደኛው ወይ የአገሩ ልጅ አይጥ አናት ላይ እየተረማመደም ቢሆን ሌላውን ጥሎ ይሮጣል። በዚህ ዓይነቱ የጋራ እብደት (Collective Madness) ውስጥ ሲገቡም ራሳቸውንና ማኅበረ-አይጣቸውን ለከፋ አደጋ ያጋልጣሉ። በመረጋገጥ ብዛት የሚሞተውና ለአካልና የመንፈስ ጉዳት የሚዳረገው ይበዛል። የማታ ማታ ደግሞ ወደተዘጋጀላቸው ወጥመድ ሰተት ብለው መግባታቸው የማይቀር ይሆናል። ይህን በመሰለው የአይጦች የሩጫ እሽቅድድም መርሕ የሚመራ ማንኛውም ፍጥረት ከዚህ ከፉ ዕድል (Predicament) ሊያመልጥ አይችልም። ቤተሰብም ሆነ ማኅበረሰብ፣ ካፒታሊዝም ይሁን ሶሻሊዝም፣ መንግሥትም ይሁን ፓርቲ በዚህ ራስን የማስቀደም መርሕ እስከተመራ ድረስ የስኬትን ሳይሆን የውድቀትን አዝመራ ማጨዱ አይቀሬ ይሆናል። በአገራችንም ከዚህ የተለየ

አይሆንም። ይህ ቋሚ የተፈጥሮና የሕብረተሰብ ሕግ ነውና።

በኢትዮጵያ ዘላቂ መልካም አስተዳደር የማስፈን ጉዳይ አንድ መሠረታዊ የህዝብ ፍላጎት ምላሽ እንዲያገኝ የማድረግ ብቻ ሳይሆን የህልውና ጥያቄ እንደሆነ ታምኖበት ያደረ ነበር። በ1994 ዓ.ም. የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን በተመለከተ የተዘጋጀው የኢህአዴግ ሰነድ ደርግ ሊወድቅ ሲል፣ ብዙ ሰዎች "የአገራችን እጣ ፈንታ ከላይቤርያና ዩጐዝላቪያ የማይለይ ይሆናል" በማለት የተነበዩትን መነሻ በማድረግ መልካም አስተዳደር የማስፈንና ያለማስፈን ጉዳይ በእርግጥም የሕልውና ጉዳይ እንደሆነ፡-

> "ለዘመናት ሥር እየሰደደና እየተወሳሰበ የመጣው ድኅነት፣ ከጦርነቱ ጋር እየተመጋገበ አገራችንን ወደመጨረሻው የጥፋት ጠርዝ ላይ ባደረሰበት ወቅት የተደረገ ትንበያ ስለነበር፣ ይህን ያህል ጽንፈኛ ትንበያ ነበር ማለት አይቻልም። ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን በመገንባት የጦርነቱን ፖለቲካዊ ምንጭ ማድረቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ካልተቻለ እውን መሆኑ በፍፁም የማይቀር ትንበያ ነው የነበረው። ***የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጉዳይ በአገራችን የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ ህዝቡን ከአስከፊ እልቂት፣ አገሪቱን ከጠቅላላ ብተና የመታደግ ጉዳይም ጭምር ነው።***"[57] በማለት በግልጽ ተመላክቶ ነበር።[አጽንዖት የተጨመረ]

ከዚህ በመነሳት በአገራችን መልካም አስተዳደር ማስፈን መሠረታዊ የሕልውና ጉዳይ እንደሆነ ታምኖበት በመስኩ ለውጥ ለማምጣት ያልተቆጠበ ጥረት ተደርጓል። በዚያው ልክ ደግሞ ለመነሻ ሊሆን የሚችል ውጤትም ተመዝግቧል። ነገር ግን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚታዩት ችግሮች እየተባባሱ ሲሔዱና በዚያው ልክ ደግሞ ድርጅትና መንግሥት መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ተስኗቸዋል።

መልካም አስተዳደር ምን ማለት እንደሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር አከራካሪ ቢሆንም በብዙዎች ዘንድ የጋራ ስምምነት የተያዘባቸው አራት ጉዳዮችን ያጠቃልላል። የመልካም አስተዳደር የመጀመሪያው ቁም ነገር የህዝብን መብት፣ ተጠቃሚነትና ተሳትፎ ማረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው የሕግ የበላይነትን ማስፈን ጉዳይ ነው። ሦስተኛው ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ሲሆን፣ በአራተኛ ደረጃ ደግሞ ቀልጣፋና ውጤታማ አስተዳደር መገንባት ነው። ኢህአዴግና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥቱ የተቀበሏቸው የመልካም አስተዳደር መስፈርቶች እነዚህ በመሆናቸው በመስኩ የተገኙ መልካም ውጤቶችንም ሆነ ድክመቶችን ለመተንተን የሚደረገው ሙከራ በእነዚህ ዋነኛ መሥፈርቶች ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

በኢትዮጵያ የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ ቁም ነገሮች ተብለው የተለዩትን እነዚህን አቅጣጫዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ የሪፎርም ፕሮግራሞች ተነድፈው በሥራ ላይ እንዲውሉ ጥረት ተደርጓል፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ፣ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ፣ የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ፣ የንግድ ሥርዓት ማሻሻያ ሁሉ በዚህ ማዕቀፍ የተነደፉ ፕሮግራሞች ነበሩ። በትክክል ተግባር ላይ በዋሉባቸው ተቋማትም ጥሩ ውጤት መምጣት ጀምሮ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት የወልና ማስረጃ፣ የኢሚግሬሽንና የመሳሰሉ መሥሪያ ቤቶች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት የተዋጣላቸው እንደሆኑ በተገልጋዩ ማኅበረሰብ የተመሰከረላቸው በእነዚህ የማሻሻያ ፕሮግራሞች ትግበራ ምክንያት ነበር፡፡ ሌሎችም ፕሮግራሙን ተግባራዊ ባደረጉበት ልክ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆን ሲጀምሩ ህዝበ በሚያገኘው የተቀላጠፈና ፍትሃዊ አገልግሎት የተሰማውን እርካታ በአደባባይ መግለጽ ጀምሮ ነበር፡፡ ይህም መልካም አስተዳደር ለማስፈን ልባዊ ጥረት በተደረገበት ሁሉ ውጤት መምጣቱ እንደማይቀር የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በገጠርና በከተማ የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተካሔደው የኢኮኖሚ ልማት ህዝቡ በተጨባጭ ተጠቃሚ መሆን ጀምሯል፡፡ ይህ በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር ከማስፈን አኳያ አንዱ መሠረታዊ መስፈርት እየተሟላ ሲሔድ እንደቆየ ያመላክታል፡፡ የሕግ የበላይነትን ለማስከበርም ሆነ በሕገ-መንግሥቱ የተደነገጉ የዜጐች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተግባር ላይ እንዲውሉ ሰፊ እንቅስቃሴ ተካሂዷል። የግልጽነትና ተጠያቂነትን መርሕ በሥራ ላይ ለማዋል ፊዴራልና ክልላዊ መንግሥታት እቅድና ባጀታቸውን በይፋ ለህዝብ ያሳውቃሉ፡፡ ስለአፈጻጸሙም በመደበኛ የጊዜ ሰሌዳ ለህዝብ ምክር ቤቶች ሪፖርት እያቀረቡ በይፋ በማስገምገም በአገሪቱ የግልጽነትና የተጠያቂነት ባሕል እንዲሰፍን ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሥልጣናቸውን ካለአግባብ በመጠቀም በህዝብና በአገር ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሰዎች በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ እነዚህ በድምሩ ቀልጣፋና ውጤታማ የአስተዳደር ሥርዓት ለመገንባት የተደረገውን ጥረትና መገኘት ጀምሮ የነበረውን መልካም ውጤት ያሳያሉ፡፡ የሲቪል ሰርቪስና መሰል ማሻሻያ ፕሮግራሞቹ በህዝቡና በአስፈጻሚ አካላት በባለቤትነት መንፈስ ተይዘው ከልብ ተግባራዊ ሲደረጉ፣ ለውጥ ማምጣት ብቻ ሳይሆን፣ የህዝብን እርካታ ጭምር ማረጋገጥ እንደተቻለ ተይቷል፡፡

መንግሥት፣ በተለይ ከመጀመሪያው የተሃድሶ መድረክ በኋላ ባደረገው እንቅስቃሴ፣ የማሻሻያ ፕሮግራሞቹ ከልብ ተግባራዊ በተደረጉበት አካባቢ ከፍተኛ መሻሻል ሊመዘገብ እንደሚችል ያሣየ ቢሆንም በሂደት ግን መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚደረገው ጥረት እየተቀዛቀዘ መሔድ ጀመረ። በብዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለህዝብ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ የሚታየው ጉድለትና ብልሹት ተበራከተ፡፡ መልካም አስተዳደር የማስፈን ጉዳይ የህዝብን

መብት ብቻ ሳይሆን የአገር ሀልውና ጥያቄን ጭምር መመለስ እንደሆነ ተዘንግቶ፣ ህዝብ በተገቢው ደረጃ አገልግሎት የማያገኝበት ሁኔታ እየሰፋ ሔደ።

መልካም አስተዳደር እየጠፋ በሚሔድበት ጊዜ የመጀመሪያ ሰለባ የሚሆነው የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ነው። ሙስና አንድም ለልማት ሊውል የሚችለውን ገንዘብና ሌላም ጸጋ በልዩ ልዩ ስልት በመዝረፍ፣ ወይም ከህዝብ ተገቢ ያልሆነ ከፍያ በመሰብሰብ የሚፈጸም ነው። በሁለቱም መንገዶች የሚከናወን ዝርፍያ ለልማትና የህዝብ ተጠቃሚነት ሊውል ይችል የነበረውን ጸጋ ወደግለሰቦች ኪስ ያስገባዋል። ይህን በማስመልከት ማርቲን ሜሪድዝ በተለምዶ ነጣቂ መንግሥታት (Predator State) በሚባሉ መንግሥታት በሚመሩ የምዕራብ አፍሪካ አገሮች የታዘበውን ሲገልጽ፡-

> "የዝርፊያ ተግባርና ጉቦኝነት ከፖለቲከኞች እስከታክስ ሰብሳቢዎች፣ ከጉምሩክ ኃላፊዎች እስከፖሊሶች፣ ከፖስታ ቤት እስከ ሂሣብ ሠራተኞች በጥቅሉ ከላይ እስከ ታች የተንሰራፋ ነው። ከከፍት የሥራ ዕድሎች ጀምሮ እስከንግድና ሥራ ፈቃድ፣ ከወጭ ትምሕርት እስከወጭ ምንዛሬ እደላ፣ አልፎ ተርፎም ለፋብሪካ መትከያ ቦታ የማግኘት ጉዳይ ሁሉ የሚወሰነው በጉቦና መሰና ነው። ...ከጊዜ በኋላ ደግሞ ጉቦና ሙሰኝነት ገቢህን ጨምሮ የፈለግከውን የምታገኝበት፣ ውጣ ውረድ የምታስወግድና አገልግሎት የምትገዛበት የሕይወት መንገድ ይሆናል።" ይላል። በተጨማሪም ሜሪድዝ ታዋቂው የካሪብያን ተወላጅና የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ታጋይ ፍራንዝ ፋኑን[58] ስለምዕራብ አፍሪካ ፖለቲከኞች "ቅሌቶች በርካታ ናቸው። ሚኒስትሮች ያለማቋረጥ ይበለጽጋሉ። ሚስቶቻቸውም ራሳቸውን ያሳብጣሉ። የፓርላማ አባላትም መረባቸውን ያስፋፋሉ። እስከታች ድረስ በሚገኙት የፖሊስና የገቢዎች መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ድረስ በትልቁ የሙስና መረብ ውስጥ ገብታ ያልተበከለች ነፍስ ማግኘት ያስቸግራል።"[59] በማለት የፃፈውን በመጥቀስ ሃሳቡን ያጠናክራል።

ልክ እንደ ሜሪድዝና ፍራንዝ ፋኑን ሁሉ መለስም ከአፍሪካ ቦትስዋናን፣ ጋናና ዩጋንዳን መነሻ በማድረግ ባካሔደው ጥናት በአፍሪካዊው ዘራፊ መንግሥት ምክንያት በአህጉሪቱ ህዝቦች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በሰፊው ዳስሶታል። መለስ በዚህ መጽሐፉ ከቅኝ አገዛዝ ማከተም በኋላ በትረ ሙሴውን ከባእድ አስተዳዳሪዎች የተረከቡት አፍሪካዊ መንግሥታት አህጉሪቷን ብቻ ሳይሆን የቅኝ ገዥዎችን ኪራይ ሰብሳቢ ባሕርይ፣ ግብና መንገድ አብረው እንደወረሱና ይህንም እንዳስፋፉት ሲያመላክት፡-

"እናም አፍሪካዊው ዘራፊ መንግሥት በባሕርይው የግል ሀብት ለማግበስበስ ቀዳሚውና ዋናው መሣሪያ ነበር፡፡ መንግሥት ሀብት ከማከማቸት ጋር የነበረው ግንኙነት ቀጥተኛ ነበር፡፡ ራሱ ሀብት በማግበስበስ ሥራ ላይ የተሠማራ በመሆኑ ከግሉ ባለሀብት ነጻ የሆነና የተለየ አልነበረም፡፡ በዚህ የተነሳ የሥርዓቱን ዘላቂ ጤንነትና ጥቅም መለየትና ማራመድ ተሳነው፡፡ የሥርዓቱ ጤንነት እንዲሻሻልና እንዲጠበቅ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነው ራስን በራስ የማረምና የማሻሻል ብቃትም አልነበረውም፡፡ የሚመራው ለባለሥልጣናቱ ኪራይ በማግበስበስ አመከንዮ ስለነበረ፣ የኢኮኖሚው ጤንነት እየዳሸቀም ቢሆን በዚሁ ስግብግብነት መመራት ቀጠለ፡፡ ሀብት ማፍራት የፈለጉ ሁሉ በመንግሥት ሥልጣን አማካይነት ከታቡት ምንጮች ቀጥተኛ ግንኙነት ለመፍጠርና ይህንንም በከፍተኛ ደረጃ ሊጠቀሙበት ተንቀሳቀሱ፡፡ መንግሥትን በምርኮኝነት መያዝ የዚሁ የሀብት ማግበስበስ ሂደት ግብና ማስፈጸሚያ መሣሪያ ሆነ፡፡ ስለዚህም መንግሥት የአገሬው ህዝብ በገበያ ሕግጋት ተመርቶ መንቀሳቀሱን ማረጋገጥ ሲገባው፣ ሥራው ሁሉ የመንግሥት ሥልጣንን የተቆጣጠሩ ሰዎች ሀብት ማግበስበሳቸውን ማረጋገጥ ሆነ፡፡ ይህም የአፍሪካዊው ዘራፊ መንግሥት ፋይዳ ቢስነት (Dysfunctionality) አንድ ዋነኛ መንሥዔ ሲሆን፣ ራሳቸውን ካፒታሊስታዊ ወይም ሶሻሊስታዊ ብለው የጠሩትን ዘራፊ የአፍሪካ መንግሥታት ሁሉ የሚያጠቃልል ነበር፡፡"[60] ይላል፡፡

ከእነዚህ ጥቅሶች ለመገንዘብ እንደሚቻለው መንግሥት የግል ይዞታ ወደመሆን ሲቀየር የህዝብ መብትና ጥቅም ይረገጣል። ቀልጣፋ አገልግሎት ማግኘት ሲገባው፣ ለሙስና ሲባል በሚፈጠር መጉላላት ውድ የሆነው የህዝብ ጉልበትና ጊዜ ከቢሮ ቢሮ በመመላለስ ይባክናል፡፡ ከዝርፊያው ባልተናነሰ ሁኔታ ለሙስና ሲባል ሥራዎችን ማጓተት፣ ህዝብና አልሚዎችን ደጅ ማስጠናት እየተበራከተ በሔደ ቁጥር ህዝብ በፍጥነት የመልማትና የመጠቀም እድሉ ይዳከማል፡፡ ይህ በተደጋጋሚ የሚፈጸም ከሆነም በልማት ተጠቃሚ ሊሆን ይችል የነበረው ህዝብ መጀመሪያ ጥቅሙ እየቀነሰ፣ በሂደት ደግሞ በቀጥታ የጉዳቱ ሰለባ እየሆነ ይሔዳል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ በአገራችን እየተስፋፋ የመጣው ሙስናና የመልካም አስተዳደር እጦት የህዝቡን ልማታዊ ተጠቃሚነት እያዳከመ እንደሆነ ለመገንዘብ አያስቸግርም፡፡

በፌዴራልም ሆነ በየከልሉ ደረጃ መልካም አስተዳደር የሚገኝበትን ሁኔታ ለማወቅና ችግሮችን ለመፍታት ይቻል ዘንድ በ2007 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ተቋም ጥናት ተካሂዶ ነበር። ምንም እንኳ በአንድ ቀን ሦስትና አራት የማይተዋወቁ መሥሪያ ቤቶችን በመገ·ብ'ነት ብቻ የመልካም አስተዳደር ችግር ሰፊ እንደሆነ ለማረጋገጥ ባይከብድም፣

በዚህ ጥናት ስፍር ቁጥር በሌላቸው ማስረጃዎች ችግሩ ተጨባጭ እንደሆነ ተረጋግጧል። ይህ ጥናት በዓመቱ መጨረሻ ለከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በቀረበ ጊዜ ግን ጥቂት የማይባሉ ሚኒስትሮች እንደመሠረተ-ቢስ ሊያጣጥሉት ሞክረው ነበር። ይሁንና በዚህ ጥናት እንደተረጋገጠውም ሆነ ህዝቡ በየእለቱ ከሚያነሳቸው ጉዳዮች በመነሳት የመልካም አስተዳደር ጉድለት አንድ ዋነኛ የሥርዓት ተግዳሮት እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም። ይህንም የመልካም አስተዳደር ማረጋገጫ መስፈርቶች ከሆኑት አራት መሠረታዊ ጉዳዮች በመነሳት ማረጋገጥ ይቻላል።

በመልካም አስተዳዳር እጦት የተነሳ የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት መዳከም ጀምሯል። እያደገና እየዳበረ ሊሔድ ይገባ የነበረው ጅምር ተሳትፎ፣ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየሰፋ በመጣው የአመራር ድክመት ምክንያት በመቀዛቀዝና በማሽቆልቆል ላይ ነው። ይህ በዋነኛነት ከላይኛው አመራር ጀምሮ ባለ ድክመት የመጣ ሲሆን ከታች ለህዝቡ በቀረቡ መዋቅሮች ውስጥ በሚፈጸሙ ስህተቶች ደግሞ እየተባባሰ የመጣ ችግር ሆኗል። በብልሽት ውስጥ የገባና በዚሁ አቅጣጫ የሚነጉድ አመራር በየትኛውም እርከን ላይ ይሁን የህዝብን ተሳትፎ ሊያበረታታ የሚችልበት ዕድል እጅግ አናሳ ነው። በአመራር አካላት በሚፈጸሙ የአስተዳደርና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች የተነሳ የህዝብን ፊት ማየት አስፈሪ ሆኗል። ህዝቡ በተከፈቱለት መድረኮች ሁሉ ስለደረሰበት በደልና ስለአመራር አካላት ድክመቶች በግልጽ የሚናገር በመሆኑ በስህተት ውስጥ የገቡ የአመራር አካላት ሁሉ የህዝቡን ዓይኖች ፊት ለፊት የማየት ብቃታቸው ተዳከሚል። በመሆኑም አንድም የህዝብ መድረኮች በተገቢው ፍጥነትና ስፋት አይከፈቱም፤ ቢከፈቱም ነገሮችን ከሥረ መሠረታቸው ለመፈተሽና ለማስተካከል በሚያስችል ደረጃ አይካሄዱም።

ህዝቡ በተከፈቱለት አጋጣሚዎች በአስተዳደር አካላት ላይ ወቀሣ የሚያቀርብ ከሆነም አንዳንድ ኃላፊዎች በሌላ ጊዜና አስተዳደራዊ አጋጣሚ እንደሚበቀሉት በጥናቱ ተረጋግጧል። በነጻነት የተናገሩና የተሟገቱ ሰዎች በራሱ በከፍተኛ አመራሩ መድረኮች እንደሚደረገው ለተለያዩ ይፋ ያልሆኑ ቅጣቶች በመጋለጥ በደል ይደርስባቸዋል። ህዝቡ የማይበገር ሆነ እንጅ በትግራይ ከልል በተከፈቱ አንዳንድ መድረኮች ስብሰባውን የሚመሩ ሰዎች ወቀሳ ያቀረበባቸውን ሰው "እስኪ ስልክ ቁጥርህን አምጣ" በሚል ማስፈራሪያ ዝም ለማሰኘት ይሞክሩ እንደነበር ተረጋግጧል። ይህ ሁሉ ተዳምሮ በህዝብ ተሳትፎ ላይ ከባድ ገደብ ማሳረፍ ጀምሯል። ከመድረኮች መራቅ፣ መሸማቀቅና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ዕድል ማጣት እየበዛ፣ ሌላ አማራጭ ማማተር ወይም ግጭትን የችግር መፍቻ የማድረግ ዝንባሌ እንዲበራከት የራሱን ሚና ተጫውቷል።

ዴሞክራሲን የማጥበብ ዝንባሌ ከሚሄንም በላይ ጐልቶ የሚታየው በበፍተና አመራሩ ነው። የላቀ ተሳትፎ ሊታይበትና ክርክር ሊካሔድበት ይገባው የነበረው የአመራር መድረክ ተገቢው ክርክር የማይካሄድበት ከሆነ ክርሚል። በቅርቡ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በግምገማ እንዳረጋገጠው መሠረታዊ ችግሮችን ወደመመልከት የሚያቀኑ ሀሳቦች መታፈን ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በመለስ ህልፈት ማግስት በ2005 ዓ.ም. የመጀመሪያ ወራት ስለመልካም አስተዳደር ጉድለት የቀረበ አንድ ጽሁፍ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት ልንወያይበት አይገባም በማለታቸው ብቻ ከመድረክ እንዲወጣ ተደርጓል። እንደገናም በ2005 ዓ.ም. ከገቢዎች መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች በቁጥጥር ሥር መዋል ጋር ተያይዞ "በመንግሥት ላይ ስለተደቀነው በባለሀብቶች የመማረክ አደጋ (State Capture)" ወይም መንግሥት የባለሀብቶች ጉዳይ አስፈፃሚ መሆን መጀመሩ ለመልካም አስተዳደር መጥፋት አንድ ጠንቅ ስለመሆኑ የቀረበው ጉዳይም ተብጠልጥሎ ከመድረክ እንዲወጣ ተደርጓል። ይህም አመራሩ የህዝብና የአገርን ጥቅም የሚጐዱ ስህተቶች ሲፈጽም የሚቀርቡበትን ትችቶች የመቋቋም ችሎታው እያነሰ፣ ሂሶችን እንደጦር እየፈራ መሄድ እንደጀመረ ያመላክታል። እናም ከሚቀርቡለት ገንቢ ወቀሣዎች በቅንነት መማር ሲገባው ሂሶች ክብሩን፣ የመሪነት ቦታውን ወይም ያሰበውን ጥቅም የሚያስቀሩበት ሆኖ ይታየዋል። በውስጥም ሆነ በውጭ የሚፈጽማቸውን የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች ነቅሰው እያወጡ የሚሞግቱትን ሁሉ በአንድ ወይ በሌላ መንገድ ያሸማቅቃል። በዚህ የተነሳ ሀሳቦች በነጻነት የሚንሸራሸሩበት አብነታዊ መድረክ ሊሆን የሚገባው የአመራር ስብሰባ፣ አብዛኛው ተሳታፊ ደግሞ አንድም በግድ የለሽነት አለያም በአድርባይነት ላለመጠላት አድፍጦ የሚያልፍባቸው ሆነዋል። በዚህ ቅኝት ለራሱ ሰፊ ዴሞክራሲያዊ መድረክ ማረጋገጥ የተሳነው አመራር ለህዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ መስፋት በር የሚከፍትበት ዕድል አናሳ መሆኑ ደግሞ ሳይታለም የተፈታ ነው። "የገሐነም መንገድ በቅንነት ይጠረጋል" እንዲሉ፣ በመልካም አቅጣጫ ጀምሮ የነበረው የለውጥ ጉዞ በአመራር ዘንድ ራስን በራስ የማረም ባሕልና ፍላጐት ሲዳከም ዛሬ በአገራችን እየሆነ ያለውን ውጤት ማስከተሉ የግድ ሆኗል።

በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ አሁን አሁን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ኃላፊዎችም ሆኑ ሠራተኞች በሥራ ሰዓት የሥራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘት ህዝብን ማጉላላትና ሥራን መበደል እየተበራከተ መጥቷል:: ይህም በመንግሥት የስራ ሰዓት የግል ሥራቸውን ከመሥራት ጀምሮ በተለያዩ ደባል ሱሶች በመጠመድ በሥራ ቦታ ላይ አለመገኘት፣ ቢገኙም በሙሉ ቀልብ አለማስተናገድና አለመሥራት የመሳሰሉት ችግሮች እየተባባሱ መጥተዋል:: በተለያዩ አጋጣሚዎች የበላይ ኃላፊ የሆነ ሰው ሳይቀር የበታች አካላትን ሊያርምና ሊቆጣጠር ቀርቶ በዚህ አይነት ሱስ በመለከፍ መጥፎ አርአያ ሲሆን ይታያል። ጫትና ሌሎች ደባል ሱሶች በሕብረተሰባችን ውስጥ የተስፋፉበት ደረጃ ሲታይ ደግሞ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ

ለየሆነ ለንደመጣ ለመገንዘብ ይቻላል። ለማንም ግልጽ እንደሚሆነው ጫት፣ ሺሻና አልኮል አዘውታሪነት የመሳሰሉ ደባል ሱሶች በሁሉም የአገራችን ክፍል እንደሰደድ እሳት እየተስፋፉ ይገኛሉ። በደርግ ስርአት ሳይቀር አንድ ለኃላፊነት የሚታጭ ግለሰብ ከሚመዘንባቸው መስፈርቶች አንዱ ከተለያዩ ደባል ሱሶች ምን ያህል የጸዳ መሆኑ ነው። ይህ አሰራር በኢህአዴግም ዘንድ እስከተወሰነ ወቅት በተገቢነቱ የሚታመንበትና ጥቅም ላይ የሚውል ነበር። ከጊዜ በኋላ ግን ቸልታው እየጠነከረ በመሄዱ ጉዳዩ ከግል ሥነ-ምግባር ችግርነት አልፎ የመልካም አስተዳደር ችግር ወደማስከተልና ወደማባባሰ ተሸጋግሯል።

ከተሳትፎ ጋር በተመጋጋቢነት እውን የሚሆነው የምልዓተ-ህዝቡ ተጠቃሚነት ጉዳይም በመልካም አስተዳደር እጦት ለአደጋ በመጋለጥ ላይ ነው። ይህን በአገልግሎት ጉድለት የሚደርስበትን ጉዳት በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል። ህዝብ ከመንግሥት ብዙ አገልግሎቶችን ማግኘት ይፈልጋል፤ ይገባዋልም። ነገር ግን ረዘም ላሉ ዓመታት ህዝቡን በቅንነትና ንፁህ መንፈስ እያገለገለ ሲጓዝ የቆየው መንግሥት ባጋጠመው ውስጣዊ ብልሽት የተነሳ የሚሰጠው አገልግሎት ሳንካ በዝቶበታል። በዚህ የተነሳ መንግሥታዊ አገልግሎቶች አንድም በገንዘብ(ጉቦ) ብቻ የሚገኙ፣ አለያም ደግሞ በግድ የለሽነት፣ ስንፍናና በተለያዩ ቢሮክራሲያዊ አሠራሮች ተተብትበው ህዝቡን የሚያንገላቱ ሆነዋል። መንግሥት ለህዝብ ተነሳሽነትና ጥረት ድጋፍ ሰጭና አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ሲገባው ሠርቶ መበልጸግ የሚሻውን ሁሉ በቁጥጥር ብዛት የማያላውስ ተቋም ሆኗል። ዜጐች የግብርም ሆነ የሌላ ግዴታቸውን እንዲወጡ ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ የሚያጨናንቀው መንግሥት የራሱን ግዴታዎች የማይወጣ ከሆነ ሰነባብቷል። ሰዎች የለፉበትን ገንዘብ ለማግኘት ብዙ ደጅ ይጠናሉ። ጉቦም ይጠየቃሉ። በቢሮክራሲው ውስጥ የተሰገሰጉ ጥገኞች በህዝብና በአገር ሀብት ያሻቸውን ጥፋት ለመፈጸም ወደኋላ የማይሉ ሆነው እያለ ህዝብ በሕጋዊና ፍትሃዊ መንገድ ሊያገኘው የሚገባውን አገልግሎት ያጓትታሉ።

የመልካም አስተዳደር እጦት የህዝብን ተጠቃሚነት ለአደጋ እያጋለጠ ያለበት ሌላው ትልቁ ጉዳይ ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ነው። ይህም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር በተካሔደ፣ ነገር ግን አመራሩ ጊዜ እያጓተተ ሊሰማው ባልፈለገው ሰፊና ዝርዝር ጥናት የተረጋገጠ ነው። በዚህ ጥናት መሠረት መንግሥት በልማት ፕሮጀክቶች አማካይነት ህዝብን ተጠቃሚ አደርጋለሁ ብሎ ከፍተኛ በጀት ከመመደብ ባይቆጠብም፣ የፕሮጀክቶች አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀሙ ከውስጥም ከውጭም በሚራኮቱ ጥገኞች ተፅዕኖ ሥር መውደቅ መጀመሩ በግልጽ የሚታይ ሆኗል። ኮንትራክተሮችና ከአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በጥገኝነት የተበከሉ ተቆጣጣሪዎች የፕሮጀክት ገንዘብን በግላጭ መቀራመት እንደጀመሩ በርከት ካሉ ፕሮጀክቶች ጋር ተያይዘ መነሳት ከጀመረ ውሎ አድሯል።

ከስኳር ፋብሪካ እስከ ማዳበሪያ ፋብሪካ፣ ከግድቦች ግንባታ አበበ መንገዶች ሥራ ባሉ ግንባታዎች በጊዜ መጓተትና በዋጋ ንረት የማይሠቃይ ፕሮጀክት ፈልጉ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኗል። በዩኒቨርሲቲዎች፣ ሆስፒታሎችና ሌሎች የመሠረተ-ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶችም በዚሁ የተሳሳተ አቅጣጫና አደገኛ ልከፍት ያልተበከለ ፕሮጀክት ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። ይህ በመንግሥታዊ አገልግሎቶች ግዥም ሆነ አቅርቦት ላይ ጭምር ይከሰታል። የመንግሥት ግዥዎች በአብዛኛው ኮሚሽን የሚበላባቸው ከሆኑ ውሎ አድሯል። የስንዴና ዘይት ግዥ ሂደቶች ለከባድ ሙስና የተጋለጡ ሆነዋል። በ2008 ዓ.ም መጨረሻ በግዥ ኤጀንሲ በኩል የነቀዘና ደረጃውን ያልጠበቀ ስንዴ በብዙ ሚሊዮን ዶላር ተገዝቶ የቀረበለት የመጠባበቂያ እህል ከምችት ኤጀንሲ ይህንኑ ውዳቂ ምርት ለመቀበል በመቸገሩ የተፈጠረው ውዝግብ ይህን ያሣያል። የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በጋምቤላ ከልል ያለአንዳች ወይም መሠረተ-ቢስ የንብረት ዋስትና ያበደረውና መና የቀረው የአገር ሀብትም በህዝብ ሀብት ላይ ያለውን ብከነትና የህዝብና የአገርን ጉዳት ያሳያል። ይህን ብድር የወሰዱ አጭበርባሪዎችና ይህ እንዲሆን የፈቀዱ የባንኩ አመራሮች ግን እዚሁ አገራችን ውስጥ በነጻነት ሲንጐማለሉ ይታያሉ።

የሕግ የበላይነት መዳከምም በአገራችን የመልካም አስተዳደር እጦት ውጤት ሆኖ መጥቷል። ኪራይ ሰብሣቢነት ሲንሰራፋ ሰለባ ከሚያደርጋቸው ጉዳዮች አንዱና የመጀመሪያው ረድፍ ተሰላፊ የሕግ የበላይነት ነው። የሕግ የበላይነት ካለ ወንጀለኛ ይያዛል፣ ይቀጣል፡ ስለዚህም እንዳሻው መሆን አይችልም። ከኪራይ ሰብሳቢነት መስፋፋትና ከመልካም አስተዳደር እጦት ጋር ተያይዞ ይህ በተገቢው ደረጃ የማይፈጸም በመሆኑ ግን የሕግ የበላይነት ለከፍተኛ ጥቃት ተጋልጧል። የሰብዓዊ መብት ጥሰት መበራከት ጀምሯል። የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ባካሄደው ጥናት በብዙ እስር ቤቶች የሕግ እስረኞች የሚደርስባቸው በደልና ኢ-ሕገ መንግሥታዊ አያያዝ እየተበራከተ እንደሆነ ተረጋግጧል። እስር ቤቶች ንፁህን ካለአግባብ የሚታጐሩባቸውና ወንጀለኛ የሚዝናናባቸው ማዕከላት በመሆናቸው ከባድ ወንጀለኞች በጉቦ ኃይል ከእስር ቤት ውጭ በቤታቸው የሚያድሩበት ጊዜ ትንሽ አይደለም። አንዳንድ ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው ሰዎች በተለይ ገንዘብ ያላቸውና ጉቦ የሚሰጡ ለስሙ እስር ቤት ውስጥ ናቸው ቢባሉም በሹልከታ እየወጡ በመመላለስ የንግድ ድርጅታቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን መጐብኘታቸው ሳያንስ እስር ቤት ውስጥ እያሉ ከትዳር አጋሮቻቸው ልጆች እስከመውለድ ደርሰዋል። ይህም በሙስና ምክንያት የመንግሥት ሕግ የማስከበር ብቃት መዳከም እንደጀመረ አንድ አመላካች ነው።

የፍርድ ቤቶች ሁኔታም ተመሳሳይ ነው። የሕግ የበላይነት በመጥፋቱ ፍርድ ቤቶች በደጅ ጥናት ተጨናንቀዋል። ፍትህ በገንዘብ ኃይል ይዛባል። በአንድ አገር ውስጥ እየኖርን፣ በአንድ ሕግ እየተመራን የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የበየነውን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይገለብጠዋል።

ከፍተኛው የቀየረውን ደግሞ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማጽደቅ ያጸናዋል። ሰበር ደግሞ በፋንታው ሌላ ውሳኔ ይሰጣል። በዚህ የተነሳ በአንድ ጉዳይ ላይ፣ በተመሳሳይ ማስረጃ አራትና አምስት ዓይነት ብይን ይተላለፋል። በገንዘብ መጠቃቀም፣ ጐጠኝነት፣ ለሕግ የበላይነትና ለንፁህ ሕሊና አለመታመን፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ የእውቀት ጉድለት ለዚህ የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል። የበላይ አካል በበኩሉ ይህን ለማስተካከል በነበረው ችሎታና ዕድል ሊጠቀም ባለመቻሉና ባለመፍቀዱ ፍትህ በሕግ ሳይሆን በሰዎች፣ በተለይ በጥቅም ቡደኖች መልካም ፈቃድና ምህረት ሥር ወድቋል። ተበዳይ ከሶ በዳይ የሚካሰበት ሁኔታ በመበራከቱ "መክሰስ እንጅ መክሰስ አያዋጣም" የሚል አስተሳሰብ ይፋ መመሪያ እስከመሆን ደርሷል። በዚያው ልክ ደግሞ "መበደል መበደሉን ባላባት በድሏል፣ ግን ገበሬ ይካስ" ወደሚባልበት ዘመን መመለስ ጀምረናል።

ይህ ችግር በሌሎች የሕግ አስከባሪ አካላት ዘንድም የሚታይ ነው። ፖሊስና የትራፊክ ደንብ አስከባሪዎች ቀላል በማይባል አጋጣሚ የዜጐችን መብት ይጋፋሉ:: ለበዓል የተጠራን ህዝብ፣ በተለይ ደግሞ ሕጻናትን በዱላ ከማስበርገግ ጀምሮ የአልፎ ሂያጅን መብት ሳይቀር መጋፋት ተበራክቷል። እንደደርግ ጊዜ ኢ-ሰብአዊና በሕገ-መንግሥቱ የተከለከሉ ቅጣቶች በእሥር ቤቶች ይፈጸማሉ:: የተከለከሉ የምርመራ ቴክኒኮች በሥራ ላይ ይውላሉ:: ይህ ሁሉ ተዳምሮ በተለይ በአመራር አካላት ዘንድ ሕግ የማክበርና የማስከበር አስተሳሰብና ዝንባሌ ተዳከሞ ራስን ከሕግ በላይ አድርጐ መመልከት እንደተስፋፋ ያሳያል። ችግሩ በመንግሥት ብቻ የታጠረና የሚታጠር፣ ወደዜጐችም የማይዛመት ቢሆን ኑሮ ባልከፋ ነበር። ነገር ግን መንግሥት የራሱን ሕግ በሚጥስበት አገር ሕግ ማክበር ብሎ ነገር ሊታሰብ ስለማይችል ዜጐችም በዚህ ቅኝት ይንቀሳቀሳሉ:: ተገዶና ጫና በዝቶበት ካልሆነ በስተቀር የግብር ግዴታውን ሳያማርር የሚወጣ፣ ኮንትራት የሚያከብር፣ የተበደረውን በጊዜና ከምስጋና ጋር የሚመልስ ዜጋ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እየቀነሰ እንደሆነ "ያበደርኩትን አልመለሰልኝም"፣ "በስምምነታችን መሠረት የሠራሁበትን አልከፈለኝም"፣ "ዕቃ አቅርቤለት እያለ እርሱ ግን ከፍያ ባለመፈፀም ያጉላላኛል" በማለት ከመካካድ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ የግል በደሎችንና ስሞታዎችን ማየትና መስማት እየተለመደ ሆኗል።

አሁን ባለው ሁኔታ የመልካም አስተዳደር አንድ አካል የሆነው የግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራርም ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጧል። በእርግጥ መንግሥት በየዓመቱ መጀመሪያ፣ በየሩብ ዓመቱና በማጠቃለያው ለምክር ቤቶች ስለእቅዱም ሆነ አፈጻጸሙ ሪፖርት ማቅረቡ የተለመደ ነው። አልፎ አልፎ ከጋዜጠኞችና ከምክር ቤት አባላት ለሚቀርቡ ጥያቄዎችም ማብራሪያ ይሰጣል። ይህም ሆኖ ከጊዜ ወደጊዜ ማድበስበስ የበዛባቸውና የነገሮችን ሥረ-መሠረት የማያሳዩ ሪፖርቶችና ምላሾች መስጠት ተበራክቷል። ይህን የማድበሰበስና ነገሮችን የመሸፋፈን አካሔድ

በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ከሚታየው የጊዜ መጓተትና የሀብት ብክነት ጋር በማያያዝ ማረጋገጥ ይቻላል።

አገራችንን ለፈጣን ዕድገት ያበቃውና ቀደም ሲል የነበረው የፕሮጀክቶች ቀልጣፋ አፈጻጸም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአሳፋሪ የመጓተትና ብክነት አፈጻጸም እንደተተካ፣ በዚያው ልክ ደግሞ የህዝብና የአገር ጥቅም ለኢደጋ እንደተጋለጠ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነው። ይህን ሩቅ ሳንሔድ በስኳር ፕሮጀክቶች አፈጻጸም መመልከት ይቻላል። የስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ እየተጓተተና ከፍተኛ የሀብት ብክነት እየታየበት ቢሆንም የትኛውም የሚመለከተው አካል በጉዳዩ ላይ የጠራ ግንዛቤ ይዞ ለመፍትሔው ሲረባረብ አይታይም። ለህዝቡም ተገቢ ማብራሪያ አይሰጥም። ከፍተኛ ተስፋ በተጣለበት በዚህ ፕሮጀክት ላይ የታየው ጉድለት ምንጭና ተጠያቂው ማን እንደሆነ ደፍሮ የሚናገር የለም። የስኳር ኮርፖሬሽንም ሆነ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን አፈጻጸምና የሥራ አመራር ሂደት አገርን ዋጋ የሚያስከፍል ስለመሆኑ ሥፍር ቁጥር የሌለው መረጃና ማስረጃ ማቅረብ የሚቻልና የሚታወቅም ሆኖ እያለ "ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ" እንዲሉ ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ጭምር መፍትሔ መስጠት ይቅርና ስለጉዳዩ የተሟላ ማብራሪያ ለመስጠት የሚደፍርም የሚችልም የለም።

ችግሩ በልማት ፕሮጀክቶች ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ቀውሶች ዙሪያም የሚታይ ነው። ሌላው ቀርቶ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመስፋፋት ላይ ያሉትን ግጭቶች መንስዔም ሆነ መፍትሔ በትክክል ለማብራራት ባለመቻሉ ህዝቡ የየራሱን ግምት ከመውሰድ አልፎ በግልጽነት ላይ ለተመሠረተ ችግር ፈቺ ተሳትፎ የሚበቃበት ዕድል ተዳከሚል። የበላይ አካላት ራሳቸው የተሟላ የሁኔታዎች ዕውቀት ይዘው ጉዳዩን ለማብራራት ሲቸገሩ ማየትም የተለመደ ነው። በዚህ የተነሳ በየአካባቢው የሚቀሰቀሱ ግጭቶችና ቀውሶችን የማንባር ሥጋ በሆኑ የመንግሥት ቃል አቀባዮች የተወሰነ አቅም፣ ለዚያውም የበላይ አካላት ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ ለማብራራት ይሞከራል። ከበላይ አካላት ግልጽ የሥራ መመሪያና አቅጣጫ በማይሰጣቸው፣ ግን ደግሞ ዝም ከማለት አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ማብራሪያ ለመስጠት በሚፍጨረጨሩና በዚህም ሂደት ያልጠበቁትን ስህተት በሚፈጽሙ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች የሚሰጠው ማብራሪያም ብዙ እንድትመኝ የሚያደርግ ሆኗል።

ከእነዚህ ችግሮች ሁሉ በመነሳት የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የአገራችንን ህልውናና ቀጣይ ዕድላችንን የሚወስን ጉዳይ ሆኗል። በተጨባጭ እንደሚታየው ሙስናና መሰል ችግሮች ሲሰፋፉ በህዝቡ ላይ ከሚደርሰው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳት በተጨማሪ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰትም ይባባሳል:: ብልሹ አስተዳደር ሲስፋፋ ሙሰኛው ጉልበት እየተሰማው ችግሩ እንደሰደድ እሣት እየተቀጣጣለ ይሔዳል:: የህዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይታፈናሉ። ሙሰኛው ባገኘው የገንዘብ አቅም በመተማመንና በፈጠረው የሙሰኝነት መረብ

በመታገዝ ዝርፊያውን የሚቃወሙትን ሁሉ ማጥቃትና ማሸማቀቅ ይጀምራል፡፡ በዚህ ምክንያት ሙስና በሰፋበት ቦታ ሁሉ ዴሞክራሲ ይጠባል፡፡ የሕግ የበላይነት ይሻራል፡፡ ዜጐች በሕገ-መንግሥት የተጐናጸፏቸው መብቶች ደረጃ በደረጃ ይሸረሸራሉ፡፡ ድሃው ይበልጥ ይደኸያል። ሕገ-ወጡ ደግሞ በማይገባው ደረጃ ይከብራል። ይህም ሲሆን ህዝቡ ቁጣውን ሰላምና መረጋጋትን በሚያጠፋ አመጽና ነውጥ መልክ እንዲገልጽ በር ይከፍታል። በዛሬዋ ኢትዮጵያ እየተመለከትን ያለነው አዲስ እውነታ ይህ ነው።

ለማንም ግልጽ እንደሚሆነው ከመልካም አስተዳደር ጉደለት ጋር ተያይዞና በዚሁም የተነሳ "የአይጡች" የሩጫ እሽቅድድም ሲበራከት የሚገኘው ውጤት ከዚህ የተለየ አይሆንም። "አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ" የሚል የመተሳሰብ መንፈስ ጠፍቷል። አንዱ በሌላው አናት ላይ ተረማምዶ መቅደም የወቅቱ ፈሊጥ ሆኗል። በሁሉም የሕይወት መስኮች ለተገለሉና ለተጐዱ አቅመ ደካሞች፣ ለብዙኀኑ ድሆች መቆርቆር ቀስ በቀስ መረሣት ጀምሯል። ትግሉ ሲጀመር ይዞት በተነሳው በጐ መንፈስ መንቀሳቀስ እየቀረ ራስን ማስቀደም ተለምዷል። ጉልበትና ብልጠት ያለው በአቅመ ደካማና ህጋዊ ዜጐች አናት ላይ እየተረማመደም ቢሆን ሌላውን ጥሎ ለመጠቀም ይሮጣል። እስከቅርብ ጊዜ ስናደርገው እንደነበረው አስተውለን በመራመድ፣ አደጋን በመቆጣጠርና መልካም ዕድልን በማስፋት ወዳሰብነው መድረስ እየቻልን በኪራይ ሰብሣቢነት የጋራ እብደት ውስጥ ገብተን ራሳችንና ማኅበረሰባችንን ለከፋ አደጋ ማጋለጥ ጀምረናል። በዚህ የተነሳ በመረጋገጥ የሚጐዳውና ለአካልና ለመንፈስ ጉዳት የሚዳረገው ተበራክቷል።

በአገራችን ለመልካም አስተዳደር መጥፋት ዋናው ምክንያት በድርጅትና በመንግሥት የአመራር አካላትና በሕብረተሰብ ውስጥም ካለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ መስፋፋት መጀመሩ ነው። በዋነኛነት ደግሞ መንግሥትና ድርጅት በባለሀብቱ የመማረክ አደጋ ስለገጠማቸው ነው። ራሱ አመራሩ በ2008 ዓ.ም. ክረምት ግምገማው በጥገኛ ባለሀብቱ የመማረክ አደጋ በግልጽ የሚታይና ሥርዓቱን ከመስመር ሊያስወጣ የሚችል እንደሆነ እያንገራገረም ቢሆን አረጋግጧል፡፡ ይህም የጉዳዩን አሳሳቢነት ደረጃ ያሳያል፡፡

አንድ የአገራችን ሚኒስትር "እዚህ ወንበር ላይ መቆየት ከፈለክ?" ብሎ በዛቻ መልክ ያስጠነቀቀው ባለሀብት እንዳጋጠመውና እርሱም "እስኪ እናያለን" ብሎ እንደመለሰለት አጫውቶኛል። ይህ ሚኒስትሩን ለማስጠንቀቅ የሞከረ "ባለሀብት" መንግሥት የመደበውን ሰው የማውረድ ችሎታ እንዳለው አድርጐ የሚቆጥረውም ሆነ ይህንኑ አስነዋሪ አስተሳሰብ በድፍረት የሚገልጸው ካለአግባብ መጠቀም በመልመዱና ለዚህም ደጋፊ የሚሆኑት ኃላፊዎች እንዳሉት አድርጐ በመተማመን ነው። በዚህ የተነሳ በአግባቡና በሕጋዊ መንገድ መጠየቅ የነበረበት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ይህ እርምጃ ተወሰደበት ሲባል አልሰማሁም። ሚኒስትሩ ይህን ሲነግረኝ የታወሰኝ በአንድ ወቅት ያነበብኩት የፕሬዚዳንት ፑቲን ገጠመኝ ነበር ።

ፑቲን ሥልጣን ላይ የወጡ ሰሞን እንደሚካኤል ኮዶሮክቭስኪና ቦሪስ ብሬዞቭስኪ የመሳሰሉ በየልሲን ጊዜ የናጠጡ ሌቦች ቢሯቸው ድረስ ሔደው "እኛ የምንልህን ከፈጸምክ ብቻ ነው እዚህ ወንበር ላይ መቆየት የምትችለው" ብለዋቸው ነበር። ይህን የሰሙት ፑቲን "የምትሉትን እስክትፈጽሙ ድረስ እዚሁ ሆኜ እጠብቃችኋለሁ" ብለው መለሱላቸው። ፑቲንም ብዙም ሳይቆዩ ደግሞ ሩስያን ሙልጭ አድርገው የዘረፉትን ግዙፍ ባለሀብቶች (ኦሊጋርኮች) አንድ በአንድ እየለቀሙ እስር ቤት ጨመሩዋቸው። ከሩስያ በዝርፊያ የወሰዱትን ሀብትም መልሰው ወደአገራቸው ይዞታ አዛወሩት። በእኛም አገር ሌቦችን የመቅጣት ሥራ ለዚያውም ከሩስያ በጠነከረ ሁኔታ ሊፈጸም የሚችል ነበር። ዛሬም ቢሆን የሚቻል ነው። ነገር ግን ይህ ህዝብና አገሩን የሚወድና በህዝብና በራሱ የሚተማመን ደፋር አመራር መሆንን ይጠይቃል።

"ጌታዋን ያመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች" እንዲሉ እንደዚህ ዓይነት ባለሀብቶች እንዲበራከቱ የሚፈቅድ ሁኔታ በመስፋቱ ወንጀለኞቹ ባለሀብቶች መረን በለቀቀ ሁኔታ የመንግሥት ባለሥልጣናትን እስከማስፈራራት ይደርሳሉ። በዚህና ሌሎች በርካታ የጥገኝነት ምክንያቶች የተነሳ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መካከል የየራስ ተቋምን ማዕከል በማድረግ እንጂ፣ የጋራ ዓላማን በማሳካት ቅኝት መንቀሳቀስ ተዳከሟል። ብዙ መሥሪያ ቤቶች የየራሳቸውን ሥራ በተናጠል የሚፈጽሙ ከመምሰል አልፈው፣ ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት ፍላጐት አያሳዩም። አንዱ መሥሪያ ቤት የተናገረውን ሌላው ያፈርሰዋል። የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች አንድን ነባራዊ እውነታ እንደተለያየ ነገር ያቀርቡታል። ሌላው ቀርቶ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች መካከል የጋራ አተያይ፣ ግንዛቤና ተግባር አይታይም። አንዱ የተናገረውን ሌላው ይቃረነዋል። የበላይ አካል የፈቀደውን ትከክለኛ ነገር፣ መካከለኛ ወይም የበታች አመራር ሕግን ተጻርሮ ይከለክለዋል። የበታቹ ሕግን ተክትሎ የከለከለውን የበላዩ ሕግን ጥሶ ይፈቅደዋል። ብዙ ሥራዎች ኃላፊነትን ለመሸከም በመድፈር ሳይሆን ተጠያቂነትን በማስወገድ ቅኝት ይፈጸማሉ። በአንድ ልብ ሳይሆን በብዙ ልብ፣ በብዙ አቅጣጫ ይዘመታል። ይህን ተከትሎም ውሉ እንደጠፋ ልቃቂት እርስ በእርስ መጠላለፍ ይከሰታል። በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲና የመንግሥት የአመራር አካላት በራሳቸውም ሆነ ካለአግባብ መጠቀም በለመዱ የሕብረተሰብ ክፍሎች ኪራይ ሰብሳቢ ተፅዕኖ ሥር ሲወድቁ መለስን ያሰጋው የመንግሥት መዳከምና ዋጋ ቢስነት በማይቀር ሁኔታ ፈተና ሆኖ ብቅ ማለት ጀምራለች።

ይህም ሆኖ ልማታዊው መንግሥት በእስካሁን ሥራው የፈጠረው አቅምና ተቀባይነት፣ እንዲሁም ያካበተውን መልካም ልምድ ሁሉ በመቀመር ያሉትን ተጨባጭ ችግሮች ለይቶ ለመፍታት በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ከጀመረ፣ ብዙውን ብልሽት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠራርጐ አገር ምድሩን ለማስተካከል ይችላል። ኪራይ ሰብሣቢነትንና በተለይ በዚህ ቅኝት የሚፈጸሙ

ስህተቶችን እንደማይታገስ ማሣየት ቢጀምር፣ የውስጥና የውጭ አልጠግብ ባዮች ቁጥሩ ተመናምኖ ሰልፉን በማስተካከል ወደ አዎንታዊው አዙሪት እነዲገባ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ግን በአንድ ወቅት የኮሪያው ጄኔራል ፓርክ እንዳደረገው አገሩን ወደጥፋት የሚጐትተውን ኪራይ ሰብሣቢነት በጽናት ለመታገል የሚችል ቁርጠኛ አመራር መሆንን ይጠይቃል፡፡

ትዕግስትና ቻይነት ሊታይበት የማይገባው ያለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌና ድክመት፣ ይህን በመሰለ የአመራር ጉድለት ምክንያት እየተበራከተ ከቀጠለ፣ ሕብረተሰብን የሚያስመርር ብቻ ሳይሆን ራሱን ጅምሩን ልማታዊ ጉዞ በእጅጉ የሚፈትንና እንዲያም ሲል በአጭር የሚያስቀር ይሆናል፡፡ የመልካም አስተዳደር እጦትና የዚህ መንስዔ የሆነው ያለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌም (ኪራይ ሰብሣቢነት) በማባበል፣ ወይም በመፈክርና በእርግማን ሊሞት አይችልም፡፡ ይህን አርሶ አደሩ ሳይቀር ከራሱ የሕይወት ልምድ በመነሳት ያረጋገጠው ነው።

በደርግ ጊዜ አንድ ነጭ በሬ የነበራቸው የዋግ ኽምራ አርሶ አደር ነበሩ። ነጩ በሬ ሌሊት ሌሊት የሰው ቡቃያ እየሰረቀ በመብላት ከጐረቤቶቻቸው ጋር እያጣላ ያስቸገራቸው ገበሬ ስሞታ በመጣ ቁጥር በሬያቸውን "ይንቀልህ" እያሉ ይረግማሉ። ልማደኛው የቡቃያ ሌባ ግን እንኳን በእርግማን ሊነቀል እየደለበ ሔደ። ታዲያ አንድ ቀን የወረዳው የደርግ ካድሬ የቀበሌያቸውን ህዝብ ለስብሰባ ጠርቶ ተሰብሣቢዎቹን "ኢምፔርያሊዝም ይውደም!" የሚል መፈክር በጩኸት እንዲያሰሙ ይመራቸዋል። በመካከሉ ነጩ በሬያቸውና ኢምፔርያሊዝም የተመሳሰሉባቸው አርሶ አደር ስለእርግማን ፋይዳ ቢስነት ለካድሬው ትንሽ ምክር ሊሰጡት ፈለጉ። በእርግማን የሞተ ነጭ በሬ እንደሌለው ሁሉ፣ "ኢምፔርያሊዝም ይውደም!" በሚል መፈክር የሚሞት ኢምፔርያሊዝም የለም ብለው ያመኑት ገበሬ ፈራ ተባ እያሉ ወደካድሬው ተጠግተው "ጓዱ! ነጭ በሬ መች በእርግማን ይሞታል" አሉት። በአገራችንም የፖለቲካ ኢኮኖሚው ነጭ በሬ በመፈክርና ዲስኩር፣ በእርግማንና ውግዘት ብዛት ይሞታል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ከመልካም ባሕርይና ጅምር መልካም መንገድ ያፈነገጠውን ብልሽት በመፈክር እየደቆሱ በተግባር ማስታመም ለዲሲፕሊን ግድፈት መበራከትና በዚያው ልክ በልማታዊው መንግሥት መሠረታዊ ባሕርይ ላይ እንከን እየበዛ እንዲሔድ አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ "ህዝብን ለማገልገል ቃላትን አሳክቶ ዓረፍተ ነገር የመጻፍ ችሎታ፣ ወይም የኮሌጅ ዲግሪ አያስፈልግም፣ ህዝብን ለማገልገል ትልቅ ልቦና መያዝ ብቻ ይበቃል፡፡" ይላል። በዚህ ትክክለኛ ሀሳብ በመመራት ብቻ በአገራችን ብዙ ችግሮችን ማቃለል ይቻልና ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ለህዝብ የሚያስብ ትልቅ ብቻ ሳይሆን፣ ትንሽም ልቦና እየጠፋ ሲሔድ በመቆየቱ በተደጋጋሚ ለሚታይና ለሚሰማ መሠረታዊ የህዝብ ችግር መፍትሔ የመስጠት ችሎታ ተዳክሟል። በአገራችን የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳይቀረፉ አንዱ ምክንያት ህዝባዊ ወገንተኝነትና በዚህ የተቃኘ የህዝብ አገልጋይነት ሥነ-ልቦና እየተዳከመ መሔዱ ነው፡፡

ይህ ችግር በዚህ የጥልቀት ደረጃ ግንዛቤ አግኝቶ መነጋገሪያ ካልሆነ፣ መፍትሔውም ሥር-ነቀል መሆን ካልጀመረ፣ የመልካም አስተዳደር ጉዳይ በእርግጥም አገራዊ ሕልውናን የሚፈታተን መሆኑ የጊዜ፣ ለዚያውም የጥቂት ጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው። የመልካም አስተዳደር እጦት አንድ ተጨባጭ የሥርዓት ፈተና ሆኗል የሚባለው ከዚህ ሁሉ በመነሳት ነው።

የአውራ ፓርቲና የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፈተናዎች፣

በኢትዮጵያ የፍላጐቶችና ጥቅሞች ብዙኅነት መኖሩን በመገንዘብ የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከመገንባት ውጭ የተሻለ አማራጭ እንደሌለ የታመነበት ከትጥቅ ትግሉ ዘመን ጀምሮ ነው። በእርግጥም አንድን የጥቅሞች ልዩነትና የፖለቲካ ብዙኅነት ያለው ሕብረተሰብ በአንድ ፓርቲ ብቻ መወከል አይቻልም። ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የብዙ ፓርቲዎችን ሕልውና ያረጋገጠ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሂደት እንዲኖር ሁኔታው ተመቻችቷል። ሂደቱ የተለያዩ ችግሮች የተለዩት ባይሆንም እነዚህን ደረጃ በደረጃ በመፍታት ወደፊት ለመራመድ ጥረት ተደርጓል። በዚህ ሂደት የነባር ችግሮች መፈታት ለአዳዲስ ፈተናዎች መቀስቀስ በሩን እየከፈተ እነሆ አሁን ባለንበት ወቅት ደግሞ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱን የሚፈታተኑ አዳዲስ ተግዳሮቶች ተፈጥረዋል። እነዚህን በትክክል መገንዘብና መፍታት፣ አገሪቱን ለዘላቂ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያበቃታል። በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፈተናዎች ሆነው የሚገኙ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። የመጀመሪያው ከአውራ ፓርቲ መፈጠር ጋር ተያይዞ ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ገንቢ ተቃዋሚ ፓርቲ ከማግኘት ጋር የተያያዘው ፈተና ነው።

ቀደም ካሉ ዓመታት ጀምሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁኔታ ንጽጽራዊ ትንተና ላይ በመመሥረት በአገሪቱ አውራ ፓርቲ የመፈጠር ዕድል ሊኖረው እንደሚችል ለመገመት ብዙም አስቸጋሪ አልነበረም። ኢህአዴግ ከአውራ ፓርቲ ይልቅ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ሥርዓት የተሻለው እንደሆነ የሚቀበል ድርጅት ነው። ይህን በማስመልከት መለስ ዜናዊ (2002ዓ.ም.) ለማሠልጠኛ ባዘጋጀው መጽሐፍ፡-

> "የምንገነባው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመደበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው። በመድበለ ፓርቲ ማዕቀፍ አንድ ፓርቲ አውራ ሆኖ በመውጣት ለረጅም ጊዜ ሥልጣን ላይ የሚቆይበት አጋጣሚ ቢኖርም ይህ የተለመደም ተመራጭም መፍትሔ አይደለም። የተለመደው የመደበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውጤት ፓርቲዎች እየተቀያየሩ ሥልጣን የሚይዙበት ነው። ... ምንም እንኳ የህዝቡን አመኔታ በማትረፍ አንድ ፓርቲ በተደጋጋሚ በምርጫ የማሸነፍ ዕድል

የሚኖረው ቢሆንም፣ ይህ አማራጭ መቸም ቢሆን መቶ በመቶ አስተማማኝ ሊሆን አይችልም።"[61] ይላል።

ኢህአዴግ ቢያንስ በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ ከአውራ ፓርቲ ይልቅ የተተካኪ ፓርቲዎች ሥርዓት ተመራጭ እንደሆነ ቢያምንም፣ ነባራዊው የአገራችን የፖለቲካ ሂደት ደግሞ በመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱ ውስጥ አውራ ፓርቲ ገዝፎ እንዲመጣ አድርጓል። በዚህ የተነሳ በተለይ ከ2002 ዓ.ም. ምርጫ ውጤት በኋላ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱ የተተካኪ ፓርቲዎች ሳይሆን፣ የአውራ ፓርቲ ፈለግ መያዙን አሳይቷል። እንደገናም በአምስተኛው አገራዊ ምርጫ ማግሥት ተመሳሳይ ውጤት ከተከሰተ በኋላ የአውራ ፓርቲ ሕልውና ይበልጥ የማያጠራጥር ሆኗል። በሁለቱ ምርጫዎች ኢህአዴግ ከሞላ ጐደል ሁሉንም የምክር ቤት ወንበሮች አሸንፏል። ተቃዋሚዎች ደግሞ በተኪ ፓርቲነት ሊሰለፉ ቀርቶ፣ ወደፓርላማም ለመግባት ሳይችሉ ቀርተዋል።

ይህ መቶ በመቶ በማሸነፍ ለሚረካ የደስታ ምንጭ ሊሆን ቢችልም፣ በኢትዮጵያ የጥቅምና የአስተሳሰብ ብዙኀነት ያለው ሕብረተሰብ መኖሩን ለሚገነዘብ ሁሉ ግን እንቅልፍ የሚነሳ መሆን ያለበትና የሚገባው ነው። አገሪቱ በብዙኀነት የተዋቀረችና ይህንንም በአግባቡ ማስተናገድ ያለባት በመሆኑ፣ በየደረጃው የሚገኙ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ቢያንስ ቢያንስ ብዙኀነትን በአግባቡ የሚያንጸባርቁ መሆናቸው አማራጭ የሌለው ነው። ዴሞክራሲ የብዙኀኑን ድምጽ ያገኙ የሚያስተዳድሩበት፣ የውሑዳን ድምጽ ያገኙ ፓርቲዎች ደግሞ ባያስተዳድሩም ድምጻቸው በሕጋዊ መድረኮች የሚደመጥበት በቂ ዕድል የሚያጐናጽፍ ሥርዓት ነው። የአገሪቱ ምክር ቤቶች በዚህ አሰራር ብዙኀነትን ማንጸባረቅ ያለባቸው ቢሆንም ከሁለቱ ምርጫዎች በኋላ የአገሪቱ ምክር ቤቶች ይህንኑ የሚያንጸባረቁ አለመሆናቸው በግልጽ ታይቷል። ይህ ውጤት በህዝብ ነጻ ድምፅ ለተሾመው ፓርቲ መልካም ሥራዎች በተሰጠ እውቅናና ይሁንታ ጭምር የተገኘ ስለሆነ ብቻ ችግር የሌለበት ነው ማለት አይቻልም።

በአምስተኛው አገራዊ ምርጫ፣ ህዝቡ ኢህአዴግን በማስጠንቀቂያ ጭምር የመረጠው መሆኑ ሲታወስ ደግሞ የችግሩ አሳሳቢነት ይጐላል። በዚህ ላይ አውራ ፓርቲው የህዝቡን አስተያየት ከልብ ለመቀበልና በተግባር የሚያረካ ለውጥ ለማምጣት የሚቸገር፣ ወይም ደግሞ የህዝብን አቤቱታና ምሬት ከንፈር ከመምጠጥ ባልዘለለ ግድ የለሽነት የሚያልፍ ሲሆን ችግሩ የባሰ ይሆናል። ሥልጣን የያዘው ፓርቲ ጥራቱን ለማስጠበቅ የሚሰጠው ትኩረት እያነሰ የሚሔድ ከሆነ፣ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ አውራ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን ሞኖሊቲክ ፓርቲ መገንባትም ሊከተል ይችላል። ሞኖሊቲክ የፓርቲ ሥርዓት በብዙ የምሥራቅ አውሮፓና የምሥራቅ እስያ አገሮች፣ በተለይ በሰሜን ኮሪያ እንደታየው በአንድ ግዙፍ፣ አንድ ወጥና ግትር ፓርቲ ፍፁም

ርዕዮተ ዓለማዊ የበላይነት ላይ የተመሠረተና ሕብረተሰቡን የማያፈናፍን የፖለቲካ ሥርዓት ነው፡፡ ይህም ሆኖ እንኳን ዴሞክራሲ በሰፈነበት አገር፣ ሁሉም በሮች ጥርቅም ብለው በተዘጉባት ሰሜን ኮሪያም ሞኖሊቲክ የፓርቲ ሥርዓት ከውድቀት በስተቀር ሌላ ውጤት አላስገኘም፤ አያስገኝምም፡፡ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ወደሥልጣን የመጡና በሂደት ራሳቸውን ወደአምባገንነት የቀየሩ ፓርቲዎች በታሪክ ተደጋግመው ታይተዋልና ይህ ጉዳይ መሠረታዊና በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ሆኗል፡፡ ከዚህ በመነሳት በአገራችን የወቅቱን የመድበለ ፓርቲ ግንባታ ተግዳሮት በዝርዝር መመልከት ተገቢ ይሆናል።

በፖርቲዎች መካከል ያለመተካካት ችግር በብዙ ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል፡፡ ፓርቲዎች የማይተካኩበት ሁኔታ የሚፈጠረው በተለያዩ ነባራዊና ሕሊናዊ ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት ተመጣጣኝ አቅም ያላቸው፣ አነሰም በዛም ሕብረተሰብን ወደፊት የማራመድ ግብና ተቀራራቢ የማስፈጸም ችሎታ ያዳበሩና በቀላሉ ሊተካኩ የሚችሉ ፖርቲዎች ካለመኖር ጋር የተያያዘ ነው። በተቃዋሚ ፖርቲዎች ገራ ጥቂትም ቢሆኑ ጠንካራና ወደፊት የሚመለከቱ ፖርቲዎች ሲኖሩና ገዥው ፖርቲም በተመሳሳይ የብቃት ደረጃ ላይ ሲገኝ ተመጣጣኝ ፉክክርና መተካካት ይኖራል፡፡ በሌላ በኩል አንደኛው ፖርቲ በጣም ጠንካራና ወደፊት የሚመለከት፣ ሌላው ደግሞ ደካማ፣ የተበታተነና ሕብረተሰብን ወደፊት ከማራመድ ይልቅ ወደኋላ ለመመለስ የሚጥር ሲሆን፣ በ1997 ዓ.ም. እንደታየው ፉክክሩ አስቸጋሪ፣ መተካካቱ ደግሞ ይበልጥ ከባድ ይሆናል፡፡

በአንድ አገር ገዥው ፖርቲ እንደ ኢህአዴግ ብዙ መልካም ሥራዎች ያከናወነና በዚህም ምክንያት ህዝቡ እስከተወሰነ ደረጃ ከአንድ ፖርቲ ጋር መቀጠልን የተሻለው አማራጭ አድርጎ የሚመለከትበት ሁኔታ ከተፈጠረም የአንድ ፓርቲ ረጅም የሥልጣን ቆይታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ህዝቡ በሥልጣን ላይ ያለው ፖርቲ በሁለመናው ጥሩ ነው ብሎ ባያምንም፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ያንኑ ፓርቲ ከነችግሮቹም ቢሆን ደጋግሞ ሊመርጠውና በተነጻጻሪ ለረዥም ጊዜ ሥልጣን ላይ እንዲቆይ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡ ይህም ሲሆን ፓርቲው ካልተጠነቀቀ በስተቀር ከሥልጣን ቆይታ መብዛት ጋር ለተያያዙ አደጋዎች መጋለጥ ይጀምራል፡፡ በተለይ ድርጅቱ በድሎቹ እየተኩራራ፣ ራሱን የመፈተሽ ባሕሉን ቀስ በቀስ እያዳከመና ለአድርባዮች ሰፊ ቦታ እየሰጠ መሔድ ከጀመረ ራሱን የማይነካና የማይተካ አድርጎ ወደመመልከት ያመራል፡፡ ለውጥ (Change) አስፈላጊ ሆኖ ቢመጣም፣ የነበረውን ብልሽት እንደነበረ ለመጠበቅና ለማስቀጠል ሲል ቀጣይነትን (Continuity) ብቻ ማስተናገድ ይጀምራል፡፡ ይህም ሲሆን ጅምሩ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ጉዞ በአጭር ወደመቀጨት ያመራል፡፡

እንደኢትዮጵያ ባሉ ድሃና ያልበለጸጉ አገሮች ከቀጣይነት ይልቅ ለውጥ እጅግ ተፈላጊ በመሆኑ የላቀ ከብደት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ሁሉም ነገር በየቀኑ እየተገለባበጠ

መሔድ አለበት ማለት አይቻልም። በተለይ የለውጥ መሣሪያዎች የሆኑት ልማታዊ አቅጣጫዎት፣ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ለተነጻጻሪ ረዥም ጊዜ ማገልገል ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ነባራዊው እውነታ ያለማቋረጥ መቀየር አለበት። ኢኮኖሚውና የህዝቡ አኗኗር በቀጣይነት መሻሻል አለበት። ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወትም ሆነ የሕብረተሰብ አስተሳሰብና ባሕል በማያቋርጥ ሁኔታ መቀየርና ማደግ አለበት። ትላንት በተሰጡ መፍትሔዎች ሳይዘናጉ፣ ነባርና አዳዲስ ችግሮችን በፍጥነት መፍታትና ነባራዊ ሁኔታውን ያለማቋረጥ መቀየር ያስፈልጋል። ስለሆነም ፓርቲው የነበረውን እንደነበረ አስቀጣይ (የStatus Quo ኃይል) ከመሆኑ ይልቅ የለውጥ ኃይልነቱ ማመዘን ይገባዋል። ፖርቲው ሥልጣን ላይ ደጋግሞ ስለወጣ ብቻ የሚቀየረው ነገር እያነሰ፣ እንደነበረው ሆኖ እንዲቀጥል የሚፈለገው ጉዳይ ደግሞ እየበዛ የሚሔድ ከሆነ፣ የለውጥ ኃይል ከመሆን ይልቅ ፖርቲው የነበረውን እንደነበረ አስጠባቂና እንቅፋት ኃይል ይሆናል። ለዚያውም ወደኋላ መመለስ ካልተከተለ።

ኢህአዴግ አውራ ፓርቲ ወደመሆን የደረሰበት ሂደት በማንኛውም መስፈርት ሲታይ የገላ ስሕተት አለበት ሊባል የሚችል አይደለም። በዚህ ድምዳሜ የማይስማሙ እንደሚኖሩ ባያጠያይቅም ድርጅቱ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን አሐዱ ብሎ ካሰፈነበት የሽግግር ወቅት ጀምሮ አቅሙ የፈቀደውን ያህል መሠረታዊ ነገሮችን በትክክል ለመመለስ ተንቀሳቅሷል። ገና ከጠዋቱ ዴሞክራሲን በገደብ ሳይሆን ያለገደብ አስፍኗል። ሀሳብን ከመግለጽ መብት ጀምሮ የመደራጀትና ተቃውሞን በሁሉም ሕጋዊና ሰላማዊ መንገዶች የመግለጽ መብትን አክብሯል፣ አስከብሯል። በዚህ መብት በመጠቀም የተደራጁ ሕጋዊና ሰላማዊ ፓርቲዎች ሁሉ በሂደቱ እንዲሳተፉና እንዲፎካከሩ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል። ከፓርቲዎች ጋር በተደጋጋሚ በመደራደር የመወዳደሪያ ሜዳው ለሁሉም እኩል እንዲደለደል ጥረት አድርጓል።

በዚህ ሜዳ የሚወዳደሩ ፓርቲዎች ያላቸው የጥንካሬ ደረጃ በጣም የተለያየ እንደሆነ በመገንዘብ ለተቃዋሚዎች ሕጋዊ ሥርዓቱ ከሚፈቅደውም በላይ አድቫንስ ሰጥቷል። በተቃዋሚዎችም ሳይቀር በዴሞክራሲያዊነቱ አንደኛ ተብሎ በሚታመነው ምርጫ 97 ለቃኩከር ከተመደበው ወደ አንድ ሺህ ሰዓት የሚጠጋ የሬድዮና ቴሌቪዥን የአየር ጊዜ 54 በመቶ የሚሆነውን ተቃዋሚዎች እንዲጠቀሙበት መስማማቱ ይህን ያሳያል። መራጩ ህዝብ ሁሉንም ፓርቲዎች አውቆ ድምፁን በንቃትና በነጻነት ይሰጥ ዘንድ ሁኔታውን አመቻችቷል። እንደማንኛውም ተፎካካሪ በቀረበበት በዚህ የውድድር ሂደት ህዝብን ለማሳመን ተንቀሳቅሷል። ኢህአዴግ በዚህ ሂደት የህዝብን አመኔታ አትርፎ ለአምስት ጊዜ ለመመረጥና አውራ ፓርቲ ለመሆን የቻለው፣ በተግባር የህዝብን መብትና ጥቅም አስከብሮ በመጓዝ ረገድ በልጦ በመገኘቱ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጐልቶ በመታየት ላይ ያለው የድርጅቱ ድክመት ይህን የቆየ እውነታ ሊሸፍነው አይገባም።

በተጨባጭ እንደሚታየው በኢትዮጵያ ልማትን ከዴሞክራሲ አዋህዶ ያመጣው ድርጅት ከሌሎቹ ፖርቲዎች ፈጽሞ የማይነጻጸር ብቃት የነበረው ነው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢህአዴግን በአርቆ አሳቢነት የሚስተካከለው አፍሪካዊ ፖርቲ እንኳን አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያን በልዩ የዕድገት ምሕዋር ውስጥ ያስገባው ኢህአዴግ፣ ከአገር ውስጥ ፖርቲዎች ጋር ያለው የብቃት ልዩነት ደግሞ በጥቂት ሜትሮች ሳይሆን በብርሃን ዓመታት የሚለካ ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ ሕብረተሰቡ የተሻለ መስሎ የታየውን ይህን ድርጅት ደግሞ ደጋግሞ መርጦታል፡፡ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ክብር ያለውና በሚዛናዊ አስተሳሰባቸው ለሚተማመን ሁሉ፣ ኢህአዴግ የህዝብን ይሁንታ ደጋግሞ በማግኘት እንደተመረጠ አያከራክርም፡፡ ይህ በዴሞክራሲያዊ መንገድ አሸናፊ በመሆን ሥልጣን ላይ ደጋግሞ መውጣት የቻለ ድርጅት ግን፣ የዚህን ሂደት ትርጉምና ምክንያት በውል መገንዘብ ይኖርበታል። እንዲሁም ከረዥም የሥልጣን ቆይታ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን አደጋ ተመልክቶ መፍትሔ ሊያበጅለት ይገባል። ይህን ካላደረገ በስተቀር ራሱን ብቻ ሳይሆን አገሪቱንም ወደከፋ አደጋ ሊወስድ ይችላል፡፡ ይህ በምንም ዓይነት የእስካሁን መልካምነትና የድል ከምር ሊሸፈን የማይገባው ነው፡፡

በኢትዮጵያ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱ የአውራ ፓርቲ መልክ ከመያዙ ጋር ተጓዳኝቶ፣ የሥርዓቱን ጤንነት የመጠበቅና የማስጠበቅ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚሻ እየሆነ መጥቷል። ፓርላማው የኢህአዴግ ብቸኛ መድረክ ሆኗል፡፡ ፓርቲው ፓርላማውንና አስፈጻሚውን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠር በመሆኑ በዚህ መስክ ተቀናቃኝ የለበትም። በዚህ ምክንያት በፓርቲውና በመንግሥት መካከል ያለው ልዩነት ደብዝዞ ሚዛናዊ ለሆነ ቁጥጥር የማይመች ወይም ይበልጥ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በአንድ ፓርቲ አባላት መካከል የፖሊሲ ልዩነት የሚኖር ባለመሆኑ በይፋ የፖለሲ ክርክር ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ጠፍቷል፡፡ ይህ ጉዳይ ዛሬ ችግሩ በነባራዊነት ፍንትው ብሎ ስለሚታይ የተነሳ አይደለም። በግንቦት 2002 ዓ.ም ከተካሔደው አራተኛው አገራዊ ምርጫ ጥቂት ቀደም ብሎ የነበረውን ሂደትና የነገሮችን አዝማሚያ በቅርብ በመገምገም በኢህአዴግ ምርጫ ኮሚቴ ውስጥ የተነሳ ሀሳብ ጭምር ነበር።

ከምርጫው ትንሽ ቀደም ብሎ በነበሩት ወራት በተለይ ተቃዋሚዎች በከፍተኛ ድምፅ ሊሸነፉ እንደሚችሉ ከሁኔታው በመገንዘብ "የተወሰነ ቁጥር ያላቸው አባሎቻቸው ወደፓርላማ እንዲገቡ ቦታ እንለቅላቸው" ዘንድ በምርጫ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ሀሳብ ቀርቦ ነበር። ከዚህ በተጻራሪ ደግሞ "እንዴት መራጫችን የሆነውን ህዝብ አንፈልግህም እንለዋለን" በሚል መከራከሪያ ይህን ሀሳብ በጽናት የተቃወሙ ጓዶች ነበሩ። በውይይቱ ማጠቃለያ አብዛኛው የኮሚቴ አባል የኋለኛውን ሀሳብ በመደገፉ የቀረበው ሀሳብ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።

የመጀመሪያው ሀሳብ ከመርሕ (Principle) ሳይሆን ከፖለቲካ ጠቀሜታ (Political Expediency) አኳያ ትክክል ነበር። በሌላ በኩል በአብዛኛው የተደገፈው ሀሳብ ከመርሕ

አጓጃ ተክክል ነበር። ነገር ግን ታላቁ ፈላስፋ አሪስቶተል "አዋቂ ሰው ደንብ ከማስከበር መርህ ወጣ የሚልበትን ጊዜ በውል ይገነዘባል።" (A wise person knows when to make an exception to the rule) እንዳለው፣ መርሐን ከአገራዊ ሁኔታውና የፖለቲካ ጠቀሜታው ጋር አገናዝቦ የመመንዘር ችግር ነበረበት። ሀሳቡ በአራተኛው አገራዊ ምርጫ ዋዜማ ባያሸንፍም ከምርጫው በኋላ መለስ "የምርጫ ሕጉን በማሻሻል ተቃዋሚዎች ወደምክር ቤት የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብን" በማለት ያመጣው ሀሳብ ተቀባይነት በማግኘቱ የምርጫ ሕጉን አጥንቶ የማሻሻያ ሀሳብ የሚያቀርብ ኮሚቴ ተደራጀ።

ኮሚቴው በተወሰነ ጥናት ላይ በመመሥረት የመጀመሪያ ምክረ-ሀሳቡን መለስ እያለ ያቀረበ ቢሆንም ሰነዱ ግድፈት እንደነበረው ታምኖበት ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ አቅጣጫ ተቀመጠ። የሚሻሻለው ረቂቅ የምርጫ ሕግም እንደተለመደው ከተቃዋሚዎች ጋር ድርድር ተካሂዶበት በፓርላማ እንዲጸድቅና አገራዊ ምርጫዎች የሚገዙበት መመሪያ እንዲሆን ተወሰነ። ነገር ግን የመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱ የገጠመውን ተግዳሮት ለማቃለል ከፍተኛ አስተዋጽዖ የነበረው ይህ ረቂቅ ሰነድ ከአምስተኛው አገራዊ ምርጫ በፊት ሊታይ ሲችልና ሲገባው፣ በጊዜ ሳይመከርበትና ለድርድር ሳይቀርብ በይደር ተላላፈ። "ከልብ ካዘኑ እንባ አይገድም" እንዲሉ ረቂቁ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ሌት ተቀን በመሥራት የምርጫውን ሂደትና ውጤት ለመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጠናከር ማዋል ይቻል ነበር። ጉዳዩ ከምር ተይዞ መነጋገሪያ የሆነው ከ2008 ዓ.ም. አለመረጋጋት በኋላ ብቻ ነው። ይህም በአመራሩ አባላት ዘንድ ስለድርድር ፋይዳና ጠቀሜታ ካለው ጥልቀት የጐደለው ግንዛቤ ጋር የተያያዘ ነው።

አንዳንዱ "ከተቃዋሚ ጋር መደራደር" የድክመት ምልክት መስሎ ይሰማዋል። ድርድር አንድ የፖለቲካ ሥልት እንደሆነ የማይገነዘበ፣ ቢገነዘብም ድርድር የድክመት ውጤት ብቻ የሚመስላቸውና ከድርድር በመሸሽ የኢህአዴግን ጥንካሬ የሚያሳዩ የሚመስላቸውም ጥቂት አይደሉም። ምናልባትም በድርድር ሥልጣኑን የሚያጣ የሚመስለውም አይታጣም። በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደተገለጸው ኢህአዴግ እንኳን በሕጋዊነት ተመዝግበው ከነችግራቸው በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ ከሚሞክሩ ተቃዋሚዎች ጋር ይቅርና ከኃይልና አመጽ ውጭ ሌላ ቋንቋ ከማይገባው ከደርግ ጋርም ተደራድሯል። ቀጥሎም ከአነግ፣ ከቅንጅት፣ ከኢዴፓ፣ ከመኢአድና ከሌሎች በርካታ ፓርቲዎች ጋር በመደራደር ብዙ ጠቃሚ ተግባራትን አከናውኗል። በ2002 ዓ.ም. ሦስት ጊዜ ከድርድር ገበታ አቋርጦ ከወጣው መድረክ ጋር ለመደራደር ተደጋጋሚ መከራዎችን አድርጓል። ከዓለም ገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ ጋርም ተደራድሯል። እናም ድርድር ለማንኛውም ፓርቲ፣ አብሶ ደግሞ በሥልጣን ላይ ላለና በየእለቱ ለብዙ ፈተናና መሞት ለተጋለጠ ኢህአዴግን ለመሰለ ፓርቲ ከፖለቲካ ሕይወቱ የማይነጠል የእለት ተዕለት ተግባር ነው።

ድርድሮቹ ሁሉ አንድም ኢህአዴግ በአንጻራዊ ድክመት ላይ በነበረበት (1997ዓ.ም.)፣ ወይም በአንጻራዊ ጥንካሬ ላይ በሆነበት (2002ዓ.ም.) ጊዜ የተካሔዱ ናቸው። ይህም ሆኖ መነሻቸው ጥንካሬና ድክመትን ማሳየት አልነበረም። ይልቁንም በተለዩ አጋጣሚዎች የተፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት የጋራ ሥጋቶችን መቀነስ ወይም መልካም ዕድሎችን የማስፋት ግብ ነበራቸው። በዚህም የአገራችንን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሂደት ይበልጥ የማጠናከርና የህዝቡን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ሚና ተጫውተዋል። ማኅበራዊ ሕይወት ምንጊዜም ቢሆን ከድርድር ውጭ ስላልሆነ ጥንካሬና ድክመትን ከግምት ማስገባት የሚያስፈልገው ስለመደራደር አቋም ሰጭውሰድ አይደለም። ጥንካሬና ድክመትን መመዘን የሚያስፈልገው ሰጥቶ በመቀበል መርሕ ምንና ስንት ድርጉ (Concession) ለመስጠት ወይ ለመቀበል ብቻ ነው። ተነጻጻሪ ድክመትም ሆነ ጥንካሬ ብዙ ድርጉ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት የምትችልበት ቅድመ ሁኔታ ነው። ያም ሆነ ይህ የምርጫ ሕጉ ማሻሻያ በሥራ አስፈጻሚው በጊዜ ተመክሮበትና ታምኖበት እንዳሁኑ በድርድሩ ተቀባይነት አግኝቶ በፓርላማ ቢጸድቅ ኖሮ የኢትዮጵያ መድበለ ፓርቲ ቢያንስ ከ2007 ዓ.ም. ወዲህ የተለየ ፓርላማዊ መልክ ይይዝ ነበር።

ይህ ባለመሆኑ ፓርላማው ተቃዋሚዎች የሚሳተፉበት እስኪሆን ሊያጋጥም የሚችለውን ውሱንነት ለመቀነስ በአፈጻጸም ዙሪያ የሚካሔደው ቁጥጥርና ትግል እንዲጠነክር ማድረግ ይቻላል። ይህም ሆኖ በዚህም ረገድ እርስ በእርስ ያለመጨካከን አዝማሚያ ሚዛናዊ የሆነ ቁጥጥርን የሚያሳንስ ሊሆን ይችላል። በተለይ ደግሞ የአስፈጻሚው ኃላፊዎች በተነጻጻሪ ከፓርላማ አባላት የተሻለ የመረጃ ይዞታ ወይ ድርጅታዊ ኃላፊነት ሲኖራቸው ችግሩ ቀላል አይሆንም። የአስፈጻሚው ኃላፊዎች ከሌላው የተሻለ ብቃት ሳይኖራቸው፣ ምናልባትም ከአማካዩ ሰው ላቅ ብለው መገኘት የማይሹ (Mediocres) ሆነው እያለ ከፍተኛውን የፓርቲ ወይም የመንግሥት ኃላፊነት የያዙ ከሆኑ ደግሞ ችግሩ ይበልጥ ጉልህና አሳሳቢ ይሆናል። የፓርላማ አባላት የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አካላት ሳይሆኑ፣ በአኳያው የአስፈጻሚው ኃላፊዎች የፓርቲው ከፍተኛ አመራር በሚሆኑበት ጊዜ ደፍሮ አስፈጻሚውን መቆጣጠር ዳገት ሊሆን ይችላል።

ከአውራ ፓርቲ መፈጠር ጋር ተያይዞ በገዥው ፓርቲ በኩል ሊከሰት ከሚችለው አደጋ በማይተናነስ ደረጃ ሊቀመጥ የሚገባው ሌላው ችግር፣ በኢትዮጵያ አሁንም የገንቢ ተቃዋሚ ፓርቲ አለመኖር ወይም የታማኝ ተቃዋሚ ፓርቲ ክፍተት ነው። በኢትዮጵያ የተተካኪ ፓርቲዎች ሥርዓት ሳይገነባ እንዲቆይ ካደረጉት ምክንያቶች ሌላው አገር የመምራት ብቃት ያለውና ለሕገ-መንግሥቱ ታማኝ የሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ አለመኖሩ ነው።

በተጨባጭ እንደሚታየው የአገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአብዛኛው ራሳቸውን ለጽንፈኛ ፖለቲካ ተገዥ ያደረጉ ናቸው። በዛሬና በነገ የህዝብና የአገር አጀንዳዎች ሳይሆን፣

በአምናና ካቻምና የራሳቸው አጀንዳዎች የሚወዳደሩ በመሆናቸውም የህዝብን አመኔታ አጥተዋል። አገሪቱን ቀና አቅጣጫ ያስያዘውን ሕገ-መንግሥት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ዝግጁ መሆናቸው ቀርቶ፣ ይህንኑ በኃይል ለመናድ መሻታቸው ለመብታቸው ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና ያገኙትን ህዝቦች ድምፅ እንዲያጠ አድርጓቸዋል። በዚህ ላይ የመረጠት የትግል ሥልት በአብዛኛው የግጭትና የነውጥ መሆኑም የሥላም ፍላጐቱ እጅግ ባደገው ህዝብ ልቦናና ዓይን ተቀባይነትን አላስገኘላቸውም። ይህ በተለይ ከ1997 ዓ.ም የነውጥ ሙከራቸው በኋላ በነበሩት በአራተኛውና በአምስተኛው ምርጫዎችና በእነዚህ ወቅቶች በታዩት አስቸጋሪ አጋጣሚዎች ሁሉ በግልጽ የታየ ነው። በተወሰነ ደረጃ ለዘብተኛ አቋም እየያዙ የመጡትም አንድም ጠንክረው አልወጡም፣ አሊያም የሚያገረሽባቸው ናቸው።

ከእነዚህ በተለየ ሁኔታ የዛሬና የነገ አጀንዳዎችን በትክክል ለይተው እነዚህን ለመፍታት የሚያስችል ፕሮግራም ነድፈው የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች እምብዛም የሉም። የአብዛኞቹ ፓርቲዎች ማኅበራዊ መሠረት የትላንት ሥርዓት ወኪሎች ናቸው። ፓርቲዎቹ አንድም በሕብረተሰቡ ውስጥ እየተመናመኑ በሚሔዱና ባኮረፉ ማኅበራዊ ኃይሎች ወይም ደግሞ ኃላፊነት በማይሰማቸውና በማይወስዱ የዲያስፖራ ጽንፈኞች የሚተማመኑ ናቸው። በእነዚህ አላፊና (Transient) ልማቱ መሠረተ-ሰፊ ሆኖ በሒደ ቁጥር በራሳቸው ስህተት እየተዳከመ በሚንባለሉ (Mariginalized በሚሆኑ) ጽንፈኛ ኃይሎች ላይ የተመሠረተ ሕልውና ያላቸው በመሆኑ ፓርቲዎቹም በባሕርያቸው አላፊዎች ናቸው።

በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ መድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሣቱ በማይደርስበት የምዕራቡ ዓለም ላይ ሆነው፣ "ውረድ እንውረድ" ብሎ መፎከርና ማቅራራት በሚቀናቸው ፖለቲከኞችና ከእነዚህ በሚገኝ የገንዘብ ድጐማ በሚተማመኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ የተመሠረተ ሆኖ ተሚልቶ ሊገነባ አይችልም። ስለሆነም የአገር ውስጥ ባለሀብቱን የሚወክል፣ በእርሱ የፋይናንስ አስዋፅኦ የሚደገፍ፣ ከጽንፈኝነት የተላቀቀና ሰላማዊ ፖለቲካን የሚያራምድ አዲስ አማራጭ ሊበራል ፓርቲ መፈጠር አለበት። ወይም ደግሞ ያሉት ፓርቲዎች ተሰባስበው አዲስና ለወደፊቱ የሚያልም፣ ራሱን ካለፈው ጽንፈኛ ፖለቲካ ፈጽሞ የለየ ፓርቲ ወደመሆን ማምራት ይገባቸዋል። ይህ እስኪሆን ድረስ አውራውን ፓርቲ በብቃት መፎካከር የሚችል አማራጭ ታማኝ ተቃዋሚ ፓርቲ ይኖራል ለማለት አያስደፍርም። በዚያው ልክ ደግሞ የኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለሁሉም ዓይነት ችግሮች የተጋለጠ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ህዝቦች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ባለፉባቸው ወቅቶችም ሳይቀር፣ የተቃዋሚዎችን የዐመጽ ጥሪ ተከትለው ለመሔድ እንደማይሹ አሳይተዋል። በ2003/04 የዋጋ ግሽበት ከ50 በመቶ በላይ ባሻቀበበት፣ የአረቦች ፀደይ ሰሜን አፍሪካና መካከለኛውን ምሥራቅ

ባናጋበተ፣ በመለበ ሕልፈተ አንዳንድ የሠሜካ የሠበጥ ጋይሎጥ ሊህለዴግ ለገዞፐቢታል ብለው ባመኑበት ጊዜ ሁሉ ተቃዋሚዎች የማያቋርጥ የአመጽ ጥሪ አቅርበዋል። ይህም ሆኖ ሰላምን አጥብቀው የሚሹት የአገራቱ ህዝቦች ለተቃዋሚዎች የአመጽ ጥሪ ለመሰለፍ የማይሹ ብቻ ሳይሆኑ፣ ይህን አማራጭ በጽናት የሚቃወሙት እንደሆነ በድምፃቸው አረጋግጠዋል። በዚህ ላይ ተቃዋሚዎች አንድ ዓይነት ዓላማ ይዘው እያለም ኢህአዴግን ተሰባስበው እንኳ ለመግጠም ፍላጐት የሌላቸው መሆኑም የህዝብን በጐ አመለካከት ነስቷቸዋል።

እነዚህ የኢትዮጵያ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ሁለት የማይመጣጠን አቅም ያላቸው ፓርቲዎች በሚፎካከሩበት ሂደት እንዲያልፍ ያደረጉ ምክንያቶች ነበሩ። ውጤቱም ከማንም ቁጥጥር ባሻገር የአውራ ፓርቲ ሥርዓት እንዲሆን አድርጓል። ይህ ማለት ግን የአውራ ፓርቲ ሥርዓትን ጥቅምና ጉዳቶች አንሥቶ መነጋገር፣ ወይም ደግሞ በራሱ በኢህአዴግም ሆነ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ የሚታዩ ድክመቶችን እያነሡ የሥርዓቱን ፈተናዎች መፈተሸና ተጨባጭ ሆነው ከተገኙ ማስተካከል አይገባም ማለት አይደለም። አልፎ ተርፎም የአውራ ፓርቲ ሥርዓቱ ወደሞኖሊቲክ ፓርቲ የመሸጋገር አደጋ የተጋረጠበት ከሆነ ይህንኑ አንሥቶ አደጋው ስለሚወገድበት መንገድ መምከር አይቻልም ማለትም አይደለም። ይህን መሠረታዊ እውነታ በመገንዘብ ከፍተቱን በአንድ በኩል በራሱ በገዥው ፓርቲ ውስጥ ዴሞክራሲን በማስፋትና የህዝብ ማኅበራትና ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ንቁ፣ ነጻና ሰፊ ሚና እንዲጫወቱ በማድረግ መሙላት ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ ያሉትን ሰላማዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕገ-ወጥነትንና የነውጥ አዝማሚያን በማያበረታታ መልክ ሰፊ መድረክ ከፍቶ በማስተናገድ ሕጋዊ፣ ሰላማዊና ገንቢ ሚና በሚጫወቱበት አኳኋን ማጠናከር ይገባል።

በዚህ መሠረት በአውራ ፓርቲ መሪነት የሚካሔድ የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከባድ ፈተናዎች የሞሉበት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል። ነገር ግን ፓርቲው ጤንነቱን የመጠበቅ ችሎታ እስካለው ድረስ፣ ይህን ችግር መፍታትም ሆነ ማቃለል ይሳነዋል ሊባል አይችልም። የፓርቲው ጤንነት የተጠበቀ ከሆነ፣ በልዩ ልዩ የፈጠራ ስልቶች የታገዘ ጤናማ ቁጥጥር ማድረግና ከዚህም አልፎ ችግሩን በመካከለኛ የጊዜ ከልል አሟልቶ ለመፍታት ይቻላል። በዚህ ረገድ ከባድ ችግር የሚፈጠረው ፓርቲው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየሆነ እንዳለው ራሱን በራሱ የማረም ብቃቱ እየተዳከመ፣ ጥራቱ እየቀነሰና ጤንነቱ እየተጓደለ የሚሔድ ከሆነ ብቻ ነው።

ኢህአዴግ መልካም ነገሮች በመሥራት የህዝብን ልቦና ለመማረክ በመቻሉ በምርጫዎች ደጋግሞ ሊያሸንፍ ቢችልም፣ ይህ ውጤት ግን ችግሮች የሌሉበት ስለሆነ የመጣ አይደለም። የመልካም አስተዳደር ችግር አገር ምድሩን እያስለቀሰ ነው። አሁን አሁን በከተሞች ማንኛውም ዓይነት አገልግሎት ከገንዘብ ውጭ የማይሰጥበት አሠራር እየሰፋ መጥቷል።

ኤሌክትሪክ ሲቋረጥ ለማስቀጠል ገንዘብ ይከፈላል፡፡ ገንዘብ ያልከፈለ ዜጋ ከጐረቤቶቹ ተነጥሎ በጨለማ ይከርማል፡፡ በየማዘጋጃ ቤቱ ለተሰገሰጉ ቢሮክራቶች ጠቀም ያለ ብር ያልሰጠ ዜጋ፣ መኖሪያ ቤት ለመስራትም ሆነ ተቋሙን ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን መሬት በሕጋዊ መንገድ ለማግኘት ሳይችል ይቀራል፡፡ ብድር ለማግኘት ጉቦ፣ ውሃ ለማስገባት ጉቦ፣ ፈቃድ ለማግኘት ጉቦ በፍጥነት እየሰፋ ያለው መንገድ መሆን ጀምሯል፡፡ ይህ አስከፊ እውነታ አገር ካወቀው ፀሐይ ከሞቀው ሰንብቷል፡፡ ይህ እውነታ እያለ ነው ህዝቡ ለኢህአዴግ ድምፁን የሰጠው፡፡

ኢህአዴግ በምርጫ ያሸነፈው ህዝቡ የሳንቲሙ አንድ ገጽታ የሆነውን የእስካሁኑን ስኬት በመመልከት ስለመረጠው ብቻ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ህዝቡ የድርጅቱን ድክመቶች ይገነዘባል፡፡ እንዲስተካከሉም ይፈልጋል፤ ይጠብቃልም፡፡ ከዚህም አልፎ የመፍትሔው ቁልፍ ከማንም በተሻለ ደረጃ በኢህአዴግ እጅ እንዳለ በመገንዘብና ተስፋ በማድረግ ጭምር ነው ድምፁን የሰጠው፡፡ ስለዚህም ህዝቡ ከአመራሩ በኩል ቀጣይ ለውጥና መሻሻል ይጠብቃል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ካላገኘ በስተቀር ሌላ የመፍትሔ አማራጭ ሊያማትር ይገደዳል፡፡ በቱርክ ስኬታማ ለውጥ ሲያመጣ የቆየው የፕሬዚዳንት ሬሲፕ ታይፕ ኤርዶጋን ፖርቲ በ2007 ዓ.ም. ምርጫ ከፍተኛ የድምፅ ቅናሽ ማግኘቱ ይህን ያሳያል። ህዝብ አንዴ በተገኘ ወረቤት ለዘላለሙ ረከቶ አይቀመጥም። ይልቁንም የማያቋርጥ ለውጥ ይሻል። በተለይ ደግሞ ትንሽ የለውጥ ጭላንጭል ከተመለከተና በተጨባጭም መጠቀም ከጀመረ ለውጥን እንጅ የቆየበትን ሕይወት እንዳለ ማስቀጠል አይመርጥም። ኢትዮጵያን በቅርብ የሚታዘቡ ቅን አሳቢ የውጭ ሰዎች አገሪቱ በቅርብ ርቀት ከዕድገቷ የመነጨ ችግር ሊገጥማት እንደሚችልና ይህን በማስተዋል ልትፈታው እንደሚገባ ይመክራሉ። አባሳንጆና ጓደኞቻቸው በቅርቡ (2017) ባሳተሙት መጽሐፍ፡-

> "በኢትዮጵያ ሁኔታ የመንግሥት ትልቁ ፈተና ምጸታዊ ሊባል በሚችል ሁኔታ ከስኬታማው ኢኮኖሚ ጋር የተያያዘ ሆኗል። አገሪቱ ሀብታም በሆነች ቁጥር መካከለኛው መደብ የሚያቀርበው ሰፊ ነጻነት የመገናጸፍ ጥያቄ፣ በደንብ መጠቀም ያልጀመሩ ከሚያቀርቡት የተጠቃሚነት ጥያቄ ጋር እየተዳመረ ይሐዳል። ይህን የመሰለው ሁኔታ በ1990ዎቹ በኢንዶኔዥያ እንደታየው የኢኮኖሚ ቀውስ ባለበት ወቅት ከተከሰተ ከባድና በቀላሉ ሊቆጣጠሩት የሚያስቸግር የለውጥ ግፊት ሊያስከትል ይችላል። ኢትዮጵያ ላለባት የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ተግዳሮት ታሪክ ዴሞክራሲን በቀጣይነት የማስፋት አቅጣጫ መከተልን ይመክራል።"[62] ብለዋል።

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በኬንሞ ፓርቲሦተ የራባተው ድል አበረናፕ ናቸው። "ነብር በዋሽንት ይመሰጣል" ሲባል ሰምቶ፣ ይህን አደገኛ ፍጥረት ጥዑም የዋሽንት ዜማ ያስለመደ ከብት ጠባቂ ትንፋሽ ያጠረው ጊዜ በነብር እንደሚበላው ሁሉ፣ ህዝብን መልካም ነገር ያቀመሰ ፓርቲ ትንፋሽ ያጠረው እለትም እጣ ፈንታው ተመሳሳይ ይሆናል። ተሳክቶልኛል ብሎ በመኩራራት ወይም ችግር የለም ብሎ በመዘናጋት መልካም ከመሥራት ወደኋላ ያለ እንደሆን፣ አልፎ ተርፎም ህዝብን ከማገልገል መስመር ወጥቶ የግል ምኞቱን ያስቀደመ እለት ከለውጥ ፈላጊው ማኅበረሰብ ጋር ከመላተምና ይህን ከመሰለው አደጋ ማምለጥ አይችልም።

ይህ እውነታ በሁሉም አመራር ዘንድ ምን ያህል ግንዛቤ ተይዞበታል? የሚለውን ጥያቄ ማንም በእርግጠኛነት ሊመልሰው አይችልም:: ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚታየው አዲስ ባሕል ግን ብዙ እንድንመኝ የሚያደርግ ነው:: ስኬት የሚያስቦርቀው፣ ውድቀት የማያሳፍረው፣ ድጋፍ ጮቤ የሚያስረግጠው፣ ተቃውሞ የሚያስደነብረው አመራር መመልከት ከጀመርን ሰነባብተናል። ህዝብ ምሬቱን መግለጽ ሲጀምር፣ ወጣቶች በብሶት ተነሳስተው የግጭት መንገድን መያዝ ሲቃጣቸውና በየቦታው ሁከት ሲቀጣጠል ብቻ እሣት ለማጥፋት የሚሯሯጥ አመራር ሞልቶ ተርፏል:: እንደ ቻይናዎቹ በደህናው ቀን የጎርፍ መንገድን አስቀድሞ ለመጥረግ የማይነሳሳ፣ ተቀጣጣይ ቁሳቁሶችን እሣት ከመነሳቱ በፊት ጥግ ጥጋቸውን የማያስይዝ ዝንባሌ ጐልቶ ይታያል:: ትንሽ ፋታ ሲገኝ መዝናናት፣ "አሳሳቢ ችግር የለም" ብሎ መዘናጋት ዋናው የአስተሳሰብ ዘውግ ሆኗል:: ተጠያቂነት የተዳከመበት፣ ያጠፋና ህዝብን ያስመረረ ሰው ቦታ ቀይሮ ሹመት የሚያገኝበት፣ ይህን በተመለከተም ህዝብና አባላት ደጋግመው የሚያቀርቡት ምሬትና አቤቱታ በተደፈኑ ጆሮዎች ላይ የሚያርፍበት ሂደት ተበራክቷል:: ይህም አመራሩ ለረዥም ጊዜ ሥልጣን ላይ ከመቆየት ጋር ተያይዞ በመፈጠር ላይ ያለውን አደጋ በቅን ልቦናና በፍፁም ህዝባዊነት ተመልክቶ ለመፍታት ባልተዘጋጀበት ሊከሰት የሚችለውን ችግር ሰፊና ቅርብ እንዲሆን አድርጐታል:: ህዝብ አመኔታ ከሰጠው አመራር መፍትሔዎችን ይሻል:: የአመኔታው መሠረት መልካሞቹ ሥራዎቻችን የመሆናቸውን ያህል፣ ብቸኞቹ ምክንያቶች ግን አይደሉም::

ህዝብን የሚያከብር፣ ህዝብን የሚያዳምጥና አዳምጦም ችግሩን የሚፈታለት ድርጅት አለ የሚለው ግንዛቤ ትምምኑ የተመሠረተበት መነሻ ነው:: ህዝብን በማዳመጥ ትክክለኛ ጥያቄዎችን በጊዜና በትክክል በመመለስ፣ የተሳሳቱትን ደግሞ በብቃት በማብራራትና በማሳመን መፍታት ባልተቻለበት ጊዜ ሁሉ ህዝቡ አስቀድሞ ያዳበረው አመኔታ መሸርሸር ይጀምራል:: ህዝብ አመኔታው እየተሸረሸረ እያለም፣ አንዳንድ ጊዜ "የተሻለውን ክፉ መምረጥ" /The lesser evil/ በሚለው ፈሊጥ እየተበላሸ በመሔድ ላይ ያለ ፓርቲን ሊመርጥ መቻሉ፣ ከአመክንዮ የተጣላ ክስተት /Anomaly/ እንጅ አሁን አሁን የፓርቲው አማላይነት ውጤት አይደለም:: ከምርጫው በፊት በነበሩ የህዝብ መድረኮች ላይ "ቀድሞ ችግራችንን ባትፈቱም

ቢያንስ ታዳምጡን ነበር፣ አሁን ግን መስማቱንም እየተዋችሁ ነው" የሚለው ህዝብ፣ በምርጫው ድምፁን በስፋት የሰጠው ለድርጅቱ ያለፉ መልካም ሥራዎች እውቅና በመስጠትና ከስህተቱ ተመልሶ በፍጥነት ችግሮቹን መፍታት ይጀምራል ብሎ ተስፋ በማድረግ እንጅ በሌላ ምክንያት አይደለም። ይህ በአመራሩ ልቦና ውስጥ ካልተጻፈ በስተቀር አደጋው ትንሽ አይደለም።

ከሁለት ተከታታይ የመቶ ፐርሰንት ምርጫ አሸናፊነት በኋላ የፖርቲው የመላወሻ ምሕዳር በእጅጉ ጠቧል። ግጭት ከመጣ በተቃዋሚና በህዝብ መካከል የሚሆንበት ዕድል በእጅጉ ቀንሶ፣ በህዝቡና ሥርዓቱን በሚመራው ድርጅትና መንግሥት መካከል የሚሆንበት ዕድል ሰፍቷል። ይህ ለረዥም ጊዜ ሥልጣን ላይ ከመቆየት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ወጥመዶችን /Entrapments of Power/ ለማለፍ የመቸገር ውጤት ነው። ኢህአዴግ እንደ አውራ ፓርቲ በነባራዊነት ለረዥም ጊዜ ሥልጣን ላይ መቀመጡ አይቀሬ ቢሆን፣ ይህ በራሱ ችግር ሊሆን አይችልም፤ አይገባምም ነበር። በጃፓን፣ በታይዋንና በስዊድን ለረዥም ዓመታት ሥልጣን ላይ ተቀምጠው ፈጣን ዕድገት ብቻ ሳይሆን፣ የተሻለ ፍትሃዊነት ያለው ሥርዓት የገነቡ ፓርቲዎች ታሪክ ይህን ያረጋግጣል። በሌላ በኩል ለአጭር ጊዜ ሥልጣን ላይ ወጥቶ ዘርፎና አገር አተራምሶ የሚወርድ ፓርቲም ሞልቷል። ዋናው ልዩነት የመሪ ፓርቲው ጤናማነትና ህዝባዊነት ወይም ዘራፊነትና ለህዝብ ደንታቢስነት ነው። ስለሆነም ችግሩ ከረዥም ወይም አጭር የሥልጣን ቆይታ ጋር ሳይሆን፣ መጥፎ ባሕርይን ከማረቅ ወይም ካለማረቅ ጋር ተያይዞ ብቻ የሚከሰት እንደሆነ በመገንዘብ፣ ራስን በራስና በህዝብ ትግል እያስተካከሉ በመጓዝ የድርጅቱን ህልውናና ጤንነት በታላቅ የኃላፊነት መንፈስ ማረጋገጥ ይገባል።

ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ከገዥው ፓርቲ በኩል ሊደቀን የሚችለው አደጋ ራስን ወደአዲስ ገዥ መደብነትና ሞኖሊቲክ ፓርቲነት የማሸጋገር አደጋ ነው። ስለዚህም ፓርቲው ይህን አደጋ ከልብ ተገንዝቦ ለማስተካከል መሥራት ያለበት መሆኑ አማራጭ የሌለው ሆኗል። በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከአንድ ፓርቲ በላይ የሆነ ተግባር ነው። ስለሆነም ከፓርቲው በላይ የመላውን የአገሪቱን ህዝቦች ጥቅም መነሻ በማድረግ፣ በዚህ መስክ ሊያጋጥም የሚችለውን ይህን አደጋ በውል ለመፍታት መዘጋጀት አማራጭ የሌለው ይሆናል። "ዝናብ ሳይመጣ የጐርፍ መንገድ ጥረግ" በሚለው አገርኛ ብሂል በመመራት፣ ከአውራ ፓርቲ ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችለውን ይህን አደጋ በቅን ልቦና ተመልክቶ መፍታት፣ የኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን፣ የህዝቡና ኃላፊነት የሚሰማው የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጭምር ግዴታ ሆኗል።

ፌዴራሊዊ ሥርዓትን ከጥቃት ጠብቆ የመገንባትና የማስቀጠል ፈተናዎች፣

ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አኳያ የሚታየው ሌላው ፈተና በዋነኛነት ፌዴራላዊ ሥርዓቱን ከጥገኛ አስተሳሰቦች በማላቀቅ የመገንባት ፈተና ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለዘመናት ሥር ሰዶ የኖረውን ብዙነትን በአግባቡ ያለማስተናገድ ችግር ለመቅረፍ ያስቻለ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመገንባት ላይ ነው፡፡ ሥርዓቱ የሁሉንም ብሔር፣ ብሔረሰቦች መብት ያስከበረ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ አገሪቱ ከሞላ ጎደል ለሁለት ተኩል አሥርት ዓመታት ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሕይወት እንድትመራ አድርጓታል፡፡ በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ የተገነባው ፌዴራላዊ ሥርዓት ብዙነት ባለባቸው ሌሎች ማኅበረሰቦችም እንደአብነት ሊወሰድ የሚገባው እንደሆነ በመስኩ ጥናት ባደረጉ ከፍተኛ ምሁራን ሳይቀር የታመነበት ነው፡፡

ይህም ሆኖ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለተለያዩ አደጋዎች የሚያጋልጡ ዝንባሌዎች እየተበራከቱ በመሔድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተወሰነ ደረጃ በየክልሉና በተጐራባች ክልሎች መካከል፣ በአንድ ክልል ውስጥ በሚኖሩ የተለያዩ ማኅበረሰቦች መካከል እንዲሁም በህዝብና በመንግሥት መካከል ተደጋጋሚና አውዳሚ ግጭቶች ተከስተዋል። ይህን የሚያመላክቱ ብዙ አብነቶች ማቅረብ ይቻላል፡፡ በአማራ ክልል ከቅማንት የማንነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተቀሰቀሰው ደም መፋሰስ፣ በአንዳንድ የአማራና የትግራይ ተዋሳኝ ቦታዎች የተከሰተው ውጥረትና በክልሉ በ2008 ዓ.ም. ማብቂያ የተቀሰቀሰው ግጭትና መፈናቀል፣ በ2006 ዓ.ም. አምቦ ላይ የተቀሰቀሰው ግጭት፣ በ2007 ዓ.ም. የተቀሰቀሰው ምርጫ ነክ ግጭት፣ እንደገናም በ2008 ዓ.ም ከሞላ ጐደል ሁሉንም ክልሎች የሸፈነው እጅግ አውዳሚ ግጭት፣ እንደገና በ2009 ዓ.ም. መጨረሻና በ2010 ዓ.ም. መጀመሪያ በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል የተቀሰቀሰውና በቅርበም በኦሮሚያ ክልል የተስፋፋው ግጭት ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው ናቸው። እንደገናም በደቡብ ክልል በማንነት ጥያቄ ዙሪያ የሚነሱት ውዝግቦችና በዲላ ከተማ የተቀሰቀሰው አውዳሚ ግጭት፣ በጋምቤላ የታዩት ተደጋጋሚ ግጭቶች ሁሉ የሚያመላክቱት ማኅበራዊ ቅራኔዎች ያልተፈለገና ያልተገባ አቅጣጫ ይዘው መጓዝ እንደጀመሩ ነው።

ይህም ሆኖ የዚህ ችግር መሠረቱ የህዝብ ለህዝብ ቅራኔ አይደለም። በኦሮሚያና በሶማሌ ክልል አርብቶ አደሮች መካከል መሠረታዊ የጥቅም ግጭትና ቅራኔ ለኖር አይችልም። በአማራና በትግራይ ገበሬዎች መካከል የመብትና የጥቅም ቅራኔና ግጭት ለኖር አይችልም። በሌላውም እንደዚሁ። ይህም ሆኖ በግጭት መልክ የሚገለጽ ግንኙነት እየሰፋና እየተደጋገመ በመከሰት ላይ መሆኑ አይካድም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የፌዴራላዊ ሥርዓቱ ስህተት ሳይሆን በየአካባቢው በመታየት ላይ ያለው ካለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌና የህዝብን አንገብጋቢ ጥያቄ ለመመለስ አለመቻል ነው።

ይህን እጅግ አንገብጋቢ ሆኖ የሚገኘውንና በየቦታው ለሚቀሰቀሱ ግጭቶች የቅርብ ምክንያት እየሆነ ያለውን የወጣቶችን የልማትና የተጠቃሚነት ጥያቄ በትክክለኛና ውጤታማ መንገድ ካለመመለስ ድክመት በመነሳት ማረጋገጥ ይቻላል። በእርግጥ በሕብረተሰብ ደረጃ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን መመለስና ዴሞክራሲውን የማስፋትና የማዳበር ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ለማንኛውም ችግር ቀዳሚው መፍትሔ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የወጣቶች የሥራና የገቢ ዕድል እንዲሰፋ፣ ከተስፋ መቁረጥ ወጥተው አገራቸውን በሙሉ መተማመን የሚገነቡ ዜጐች እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።

ይህ ጉዳይ ለወጣቶች ከልብ በማሰብና በመቆርቆር እንዲሁም ራስን ከአልባሌ ጥቅሞች አርቆ ችግራቸውን በሚፈታ አቅጣጫ እንጂ፣ ስሜት ብቻ በመኮርኮርና እዚህም እዚያም አልሚዎችን እያደናቀፉ ንብረት የመውረስ ጉጉታቸውን በሚቀሰቅስ የተሳሳተ መንገድ የሚመለስ አይደለም። መንግሥት በደንብ ካወቀበት ኢትዮጵያ ወጣቶቿን አዳዲስ እሴት ለመፍጠር በሚያስችል አቅጣጫ ለማሰማራትና ለማበልጸግ በሚያስችል የመሬትና ሌላም የተፈጥሮ ጸጋ የታደለች አገር ነች። አሁን ደግሞ ይህን አሟልቶ ለመደገፍ የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያላት አገር ሆናለች። ይህ በውል ታምኖበት አመራሩ ከስግብግብነት፣ ከትምክሕትና ጠባብነት እንዲሁም ወጣቶችን መጠቀሚያ ከማድረግ በጸዳ መንፈስ ከተንቀሳቀሰ ችግሩ ደረጃ በደረጃና በአስተማማኝ አኳኋን ሊፈታ ይችላል። ከዚህ ውጭ ወጣቶችን ሠርተው የሚበለጽጉበትን መንገድ ከመፍጠር ይልቅ በስሜት እያነሳሱ ንብረት የመቀራመት ዝንባሌ እንዲያድርባቸው በማድረግም ሆነ ችል በማለት የአርማጌዲዮንን አደጋ ማስወገድ ፈጽሞ አይቻልም። አሁን ባለው ሁኔታ ግን አመራሩ አንድም የዚህን ችግር አሳሳቢነት በውል ባለመረዳት፣ አለያም በሌላ አዲስና የተሳሳተ ቅኝት በመመራት ሲያወሳስበው እንጅ ሲፈታው አይታይም። በዚህ የተነሳ የወጣቶችን ጥያቄ በትክክለኛ አቅጣጫ ከመፍታት ይልቅ ወጣቶችን በየብሔሩ ያለው ጥገኛና ተስፈኛ ገዥ መደብ በአገር ደረጃ ለበላይነት በሚያደርገው ሽኩቻ ውስጥ አስገብቶ አቅጣጫ የማሳት ዝንባሌ ይታያል። ይህም በአገራችን አዲስ አይነት የኃይል አሰላለፍና ክዚህም የሚፈልቅ ቅራኔ ከመከሰቱ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው።

ዛሬ በአገራችን እየገሳ በመሔድ ላይ ያለው የብሔር ቅራኔ ሳይሆን በኢኮኖሚያዊ ወይም መደባዊ ጥቅሞች ላይ የተመሠረተው ቅራኔ ሆኗል። በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ ቀደም ሲል የነበረው የብሔር ቅራኔ ቀዳሚነት ተቀይሮ በመደባዊ ጥቅሞች ላይ የተመሠረተው ቅራኔ የበላይነት በመያዙ መሠረታዊውና አንገብጋቢው ቅራኔ የብሔር ሳይሆን የመደብ ሆኗል። ይህም በአንድ በኩል ተጠቃሚነታቸው እንዲሰፋ የሚሹ የከተማና የገጠር ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ አርሶ አደርና አርብቶ አደሮች፣ የፋብሪካና አገልግሎት ሠራተኞች፣ ሌላው የከተማ ሰፊ ህዝብና ብዙኀኑ የመንግሥት ሠራተኛ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመንግሥት ውስጥና በሕብረተሰብ ደረጃ የሚገኙ ጥገኞችና አይዞህ ባዮቻቸው ተፋጠው የተሰለፉበት ነው። በዚህ አሰላለፍ ላይ

የተመሠረተ ቀራኔ በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ዋኖሚነተን መያዝ ደሃራል። ሠላተተ ለሥራና የገቢ ዕድል መስፋት፣ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ከመሬታቸው ያለበቂ ካሣና የመቋቋም ዕድል እንዳይፈናቀሉ ዋስትና ከማግኘት ጀምሮ የምርታማነት ዕድገትና የገበያ ተጠቃሚነት መብታቸው እንዲከበር፤ የፋብሪካ ሠራተኞች ሕጋዊ የመደራጀት መብታቸውን በተግባር ከማዋል ጀምሮ ለተሻለ ከፍያና ተጠቃሚነት እንዲበቁ የማድረግ፣ የመንግሥት ሠራተኛውም ከአገሪቱ ዕድገት እኩል ተጠቃሚ ለመሆን የሚያካሂዱት ትግል የዚህ ቅራኔ አንደኛውና ዋነኛው ገጽታ ሆኗል።

የብሔር ጥያቄ በሕገ-መንግሥቱና በተግባር ከተመለሰ ሃያ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል። ምንም እንኳ በዚህ ረገድ እንደቅማንት ማኅበረሰብ ዓይነት ዘግይተው መፍትሔ ያገኙ ጥያቄዎችና ሌሎችም መለስተኛ ከብደት ያላቸው ፍትሃዊ ጥያቄዎች ሊኖሩ ቢችሉም በመሠረቱ የብሔር ጥያቄ የተሟላ ምላሽ አግኝቷል። በፌዴራል ከልሎች ውስጥና በከልሎቹ መካከል የሚከሰቱ ጊዜያዊና አላፊ ግጭቶች መበራከት ይህን አዲስ እውነታ ሊሸፍነው አይገባም። ይልቁንም ሁሉም ግጭቶች በአካባቢ መስተዳደርና በህዝብ መካከል ባለው አለመጣጣምና ግጭት መልክ መከሰት ጀምረው በሂደት አቅጣጫ የሳቱ ናቸው። የብሔር እኩልነት በተከበረባትና በተግባር ረጅም ርቀት በተጓዘባት አገራችን የወቅቱ ቅራኔ በዘራፊዎችና በህዝብ መካከል ያለው ቅራኔ ነው። በተግባር እንደሚታየው ዘራፊዎችና የመዝረፍ ፍላጐት ያላቸው አንድ ላይ የሚሰለፉበት፣ ብዙኀኑ ህዝብ ደግሞ መብትና ጥቅሙን ለማስጠበቅና ለማስፋት የሚፋለምበት ቅራኔ ነው። ይህን በተሻለ ደረጃ ለመገንዘብ የሚቻለው በአገራችን ውስጥ ባሉት ቅራኔዎች ቅደም ተከተል ላይ የመጣውን ለውጥ ዘርዘር አድርገን በመመልከት ነው።

ከተማከለ መንግሥት ምሥረታ ወዲህ ተቋማዊ በሆነ መንገድ የሚካሔድ ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ጭቆና ተንሰራፍቶባት ወደመበታተን አፋፍ ተጠግታ በነበረችው አገራችን የተለያዩ ቅራኔዎች እንደነበሩ በየወቅቱ የተካሔዱት ትግሎች ያሳያሉ። የመደብ፣ የብሔር፣ የሃይማኖት፣ የፆታ ጭቆናና በዚህ ላይ የተመሠረቱ ቅራኔዎች የሥርዓቱ መገለጫዎች የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የመደብ ቅራኔው መሠረታዊው ቅራኔ (Basic Contradiction) ነበር። የብሔርና የሃይማኖት ቅራኔዎችን የመሳሰሉት ደግሞ መሠረታዊም ባይሆኑ ቀዳሚ ቅራኔዎች (Primary Contradiction) ነበሩ። ይህም ይህም በመሆኑ እስከደርግ ውድቅት ድረስ መሠረታዊ የነበረው የመደብ ቅራኔ ለጊዜው ጐልቶ በወጣው የብሔር ቅራኔ ምክንያት ወደሁለተኛ ደረጃ ወርዶ ነበር። የብሔርና የሃይማኖት ቅራኔዎች ሳይፈቱ የመደብ ቅራኔው ቀዳሚው ወደመሆን ሊሸጋገር አይችልም ነበር። ኢህአዴግ ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ በመነሳት የብዙኀኑን መብትና ጥቅም በማስከበር ማዕቀፍ በአገራችን ቀዳሚ የሆኑትን ቅራኔዎች ለመፍታት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መታገል ነበረበት።

በዚህ ትንታኔ መሠረት ኢህአዴግ አገራችን በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሰፈነባት እንድትሆን የብሔርና የሃይማኖት ጭቆናን ማስወገድና እኩልነትን ማስፈን የመጀመሪያው ግቡ እንዲሆን አደረገ። በእኩልነት ጥያቄዎች ዙሪያ የተካረረ ቅራኔ ሞልቶ የተረፈባትን አገራችንን ከመበታተን አደጋ ለማላቀቅ የሚቻለው ጥያቄዎቹን ከማንኛውም ዓይነት ከፊልና አስመሳይ መፍትሔ ርቆ በተሟላ የእኩልነት መሠረተ-ሀሳብና ልባዊ ቁርጠኝነት በመፍታት ብቻ ነበር። ይህ ሲሆን ሁሉም የእኩልነት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ አግኝተው እንደሚረግቡ እርግጠኛ ነበር። የብሔርና የሃይማኖት እኩልነት ጥያቄዎች የተሟላና መሠረታዊ መፍትሔ ከተሰጣቸው የሕብረተሰባችን ዋነኛ የመታገያ አጀንዳዎች መሆናቸው ያቋርጣል። በአንጻሩ በዋነኛነት ጎልተው የሚወጡት የመላው አርሶ አደርና ሠራተኛ እንዲሁም የመካከለኛው መደብ የዕድገትና የፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች እንደሚሆኑ፣ ስለዚህም ደግሞ አሰላለፉ መደባዊ እንጂ ብሔራዊ መሆኑ እንደሚቀር ግንዛቤ ተያዘበት። የወጣቶች የመብትና ተጠቃሚነት ጥያቄም በዚህ ማዕቀፍ ሊታይ የሚችልና የሚገባው ነው። ወጣት አርሶ አደሮች መሬት ወይም ሌላ የሥራና የገቢ ዕድል ለማግኘትና ለተሻለ ሕይወት ለመብቃት ይታገላሉ። እነዚህ ሁሉ ማኅበረሰቦች የቋንቋ፣ የባሕል፣ የታሪክ፣ ራስን በራስ የማስተዳደርና በፌዴራል ደረጃ እኩል የመሳተፍና የመጠቀም መብታቸው በተከበረበት የብሔር አጀንዳ ፋይዳው በእጅጉ ይቀንሳል።

ከዚህ ንድፈ-ሀሳባዊና ፖለቲካዊ አቋም በመነሳት ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የእኩልነት ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የተሠራው ሥራና አገራችን የተጓዘችበት ርቀት ሲታይ ይህ የፌዴራሊዝም ሥርዓት ምን ያህል ትክክለኛ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል። በተለይ የእኩልነት ጥያቄዎች አንዱና ዋነኛ ገጽታ የነበረው የብሔር እኩልነት የተከበረበትን ደረጃና ውጤቱን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል። በዚህ ረገድ የተወሰደው የመጀመሪያው እርምጃ በአገራችን ተቋማዊ በሆነ መልክ ይፈጸም የነበረውን ብሔራዊ ጭቆና ሙሉ በሙሉ ማስወገድ በመሆኑ ብሔራዊ ጭቆናን በመፈጸምና በማስቀጠል የሚያምነው ጨቋኝ መደብ ከሥልጣን እንዲወገድ ተደርጓል። በዚያ ዘመን የበላይነት የነበረው ብዙኅነትን የማይቀበለውና ልዩነትን በኃይል አጥፍቶ ህዝቦችን በግድ አንድ ለማድረግ የተቀየሰው መንግሥታዊ ፖሊሲም ተወግዷል። ይህን ፖሊሲ የሚያራምደው የአመጽ መሣሪያ ሠራዊትና የደህንነት አውታርም እንዲፈራርስ ተደርጓል።

በዚህ ምትክ የኢትዮጵያ ብዙኅነት የማያዳግም ሕጋዊና ፖለቲካዊ እውቅና እንዲያገኝና የበላይነት ያለው አስተሳሰብ እንዲሆን ተደርጓል። ሁሉም የአገራችን ብሔር ህዝቦች ያልተገደበ ሕገ-መንግሥታዊ የእኩልነት መብት ተጐናጽፈዋል። የቋንቋ፣ የባሕል፣ የታሪክ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ እኩል የመሳተፍ መብታቸው ተከብሯል። ከዚህም ባሻገር መብቶች፣ ሳይሸራረፉ በተግባር ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

ማንኛውም ህዝብ እስከፈለገ ድረስ ከሕብረቱ ወጥቶ የራስን ነጻ መንግሥተ በአብላጫ ድምጽ እስከ ማቋቋም ድረስ የሚዘልቀው መብትም በዘመናችን በየትኛውም አገር ባልታየ ደረጃ እውቅና አግኝቷል። ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በትግላቸው በተገኙጸፉት ሕገ-መንግሥታዊ መብት የሚመሩና የሚተዳደሩ፣ ስለዚህም ደግሞ በላያቸው ላይ አንዳችም ዓይነት ብሔራዊ ጭቆና የማይፈጸምባቸው መሆናቸውን አረጋግጠዋል። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጭቆና ተወግዶ የብሔሮች እኩልነት የተከበረባት ሆናለች። በእርግጥ ከዴሞክራሲያዊ ባሕልና ልምድ እጥረት እንዲሁም ከኪራይ ሰብሣቢነት በሚመነጩ የተዛቡ አመለካከቶችና ድርጊቶች የሰፈነውን እኩልነት፣ የሚፈታተኑበት ሁኔታ መፈጠሩ ግልጽ ነው። በተለይ ደግሞ ተስፈኛ ገዢዎችና ጥገኞች፣ ያለአግባብ በመበልጸግ በአገርና በህዝብ ላይ የሚፈጽሙት በደልና ዝርፊያ አልበቃ ብሏቸው፣ በብሔራቸው ስም በመነገድና የየብሔራቸው ህዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል ህዝብ ለህዝብ እንዲጠላላና እንዲጋጭ በማድረግ የህዝቡን ፍትሃዊ ጥያቄ አቅጣጫ በማሳት ላይ ይገኛሉ።

ይህ ሁሉ የፌዴራል ስርዓቱ ያመጣው ችግር አይደለም። ይልቁንም ፌዴራላዊ ስርዓቱ ባለፉት ሩብ ምእተ አመት በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መካከል ከመቼውም ጊዜ በላይ መፈቃቀርና መከባበርን እንዳመጣ በተግባር የተረጋገጠ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የየክልሉ ህዝብ እራሱ በመረጣቸው አስተዳደሪዎቹ አማካይነት እንዲተዳደርና አካባቢውን አልምቶ እንዲጠቀም በመደረጉ በአገራችን የመጣው ለውጥ የማይካድ ነው። ይህ ለውጥ ግን ቀጣይነትና አስተማማኝ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የየክልሉም ሆነ የፌዴራል መንግሥታት ባሳዩት ድክመት የተነሳ፣ የፌዴራላዊ ስርዓቱን አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት መሆን የለበትም።

የወጣቱም ሆነ በአጠቃላይ የህዝቡ የመልካም አስተዳደር፣ የዴሞክራሲና ፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነትና ማንኛውም አይነት ጥያቄ ብሔርና ክልል ሳይገድበው በአግባቡ መነሳት ይገባዋል። ይህም ተገቢውን ምላሽ ማግኘት የሚችለው፣ የሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰብ ህዝቦች በመተባበር መንግሥትን አጥብቆ በመታገልና በመጠየቅ እንዲሁም ትግላቸውን በኪራይ ሰብሳቢነት፣ በትምክህትና ጠባብነት ላይ መሆን ይገባዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ከተመሳሳይ የጥቅም አጋሩ ጋር በመጋጨት የሰላማዊ ዜጎችን ሕይወት በማጥፋትና ንብረት በማውደም ችግሮቹን ከማባባስ በተጨማሪ ለጥቂት ለተስፈኛ ገዢዎች መሣሪያ ከመሆን አይዘልም።

ከሃይማኖት እኩልነት አኳያም ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጥሯል። ሕገ-መንግሥቱ በኢትዮጵያ የሃይማኖት ብዙኃነት እንዳለና ይህንንም መነሻ በማድረግ ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል እንደሆኑ፣ መንግሥታዊ ሃይማኖት የሚባል እንደማይኖርና መንግሥት በሃይማኖት፣ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳዮች ውስጥ እጃቸውን እንደማያስገቡ፣ ትምህርትና ሃይማኖት እንዲነጣጠሉ ተደርጓል። በአጠቃላይ ሃይማኖት የምዕመናንና የሃይማኖት ተቋማት ግላዊ ጉዳይ እንደሆነ

ዘመነ-መሳፍንት ተደጋግሞ ተግባራዊ በመደረጉ የዘላይነተኛ የዘታተገተ ተወግዷል። እዚህም ላይ ኋላቀር ልማዶችና የኪራይ ሰብዓቢነት አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲቀጥሉ የሚያበረታታቸው ቅሪት አመለካከቶች ባይታጡም በመሠረቱ ኢትዮጵያ የሃይማኖት ጭቆና ተወግዶ የሃይማኖት እኩልነት የተከበረባት አገር ሆኗለች። ስለዚህም በማንኛውም መስፈርት ሲታይ የሃይማኖት ጭቆና ደረሰብኝ ብሎ አገር ለማናወጥ የሚያበቃ ስህተት እንዲፈጸም በቂና አጥጋቢ ምክንያት የለም። በኢትዮጵያ የሃይማኖት ጭቆና ተቋማዊና መሠረተ-ሰፊ እንደሆነ አስመስሎ የሚካሔድ ማንኛውም ዘመቻ ተጨባጭ መሠረት የሌለውና ህዝብን በስሜት አነሳስቶ ወደጥፋት ለማምራት ሰበብ የተቀየሰ ኋላቀር ዘዴ ብቻ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ከእነዚህ መሠረታዊ እውነታዎች በመነሳት በብሔር ጭቆና ሥም የሚቀሰቀሱ ጥያቄዎች በአብዛኛው መነሻና መድራሻቸው ኪራይ ሰብዓቢነት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። በእርግጥ ፍትሃዊ ገጽታ ኖሯቸው የሚቀሰቀሱ አንዳንድ ጥያቄዎች የሉም ሊባል አይችልም። ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን በተግባር ከመተርጎም አኳያ የአፈጻጸም ጉድለቶች ፈጽሞ አይታዩም ማለትም አይቻልም። ቀላል የማይባሉ የአመለካከትና የአፈጻጸም ችግሮች እንዳሉ ይታወቃል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ የብሔር ጭቆናን በማስወገድና የእኩልነት መብቶችን በፅሑፍነት በማከበር ለብሔር ጥያቄ የተሟላ ምላሽ ሰጥቷል።

ዛሬ በአገራችን ብሔራዊ ጭቆና ሙሉ በሙሉ በተወገደበት በዚህ መድረክ ፈጦ የወጣው ቅራኔ በየከልሉ ህዝብና በመንግሥትና በሕብረተሰብ ውስጥ ባሉ ጥገኛ ኃይሎች መካከል ያለው ቅራኔ ሆኗል። የብሔር ቅራኔ ሲፈታ የመደብ ቅራኔው ገፅፍ ይወጣል በተባለው መሠረት በፊዴራልም ይሁን በከልል ደረጃ ዋናው አደናቃፊና የሥርዓቱ ፀር የሆነው ኃይል ኪራይ ሰብዓቢው ኃይል ነው። ይህ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን፣ የሠራተኛውንና፣ የመካከለኛ መደቡን መብትና ጥቅም የሚጻረረው ዋናው ኃይል ነው። በማንኛውም ምክንያት የአንድን ብሔር ህዝብ በሌላ ህዝብ ላይ፣ ወይም አንድን ሃይማኖት በሌሎች ላይ ለማነሳሳት የሚደረግ ሙከራ ሁሉ ይህን መሠረታዊ የመድረክ አሰላለፍ የሚያዘበራርቅና በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለጥገኛው ኃይል የበላይነት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርግ ነው።

ኪራይ ሰብዓቢው ኃይል በተጨባጭ እንደሚታየው የብሔር መልክ ሳይገድበው የተገኘውን ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ሥርዓቱን እየገጠመ እንደሆነ በብዙ ማስረጃዎች ሊረጋገጥ የሚችል ነው። ኪራይ ሰብዓቢው አልፎ አልፎ በጥቅም ክፍፍል እንደሚጋጭ የሚታይ ቢሆንም በመሠረቱ የየብሔሩ ጥገኛ ሥርዓቱን የሚፈታተነው በተግባር በተባበረ መንገድ ነው። የአንድ ብሔር ጥገኛ ብሔራዊ መልክ የተላበሰ ዝርፊያ ወይም በደል ቢፈጽም እንኳ፣ ለብሔሩ ህዝብ ጥቅም በማሰብ ሊሆን አይችልም። ይህ በየትኛውም ክልል ውስጥ ያለው ተጨባጭ እውነታ እንደሚያሳየው ጥገኛው ኃይል አብራኩ በሆነው በብሔሩ ብዙኃን ህዝብ ላይም ምሕረት የለሽ

ዝርፊያ ያካሂዳል። ይህን ለመሸፈን ሲልም የህዝቡ ያልሆኑ ስሜት ኮርኳሪ ጥያቄዎችን በማንሳትና በስሙ በመነገድ የጥገኛ ፍላጐቱን ያስጠብቃል። በብሔሩ ህዝብ ስም መነገዱና ምስኪኑን ገበሬ ጭምር ማስጠላቱ ሳያንስ የራሱ ብሔር ህዝብ በትግል እንዳይነሳበትና አቅጣጫውን ወደ እርሱ እንዳያዞር መንገድ ያስታል። ከፋፍሎ ለመግዛት ሲል ከሌላ ብሔር ህዝብ ወገኖቹ ጋር እንዲጋጭ ያደርገዋል። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በመንግሥትም ውስጥ ይህን ከመንግሥት ውጭ ያለው ጥገኛ ጥቅሙን ለይቶ ያውቃልና ሲያመቸው የብሔር ልዩነትን እያገነነ፣ ሳሳያመቸው ደግሞ እያድበሰበሰ ተባብሮ መዝረፍና ሥርዓቱን ማዳከም ዋነኛ ሥልቱ ሆኗል። ሃይማኖትን በመሣሪያነት በሚጠቀምበት ጊዜም ተመሳሳይ ቅኝትና ሥልት ይዞ ይንቀሳቀሳል። በኢትዮጵያ በመለስተኛ አርማጌድዮን መልክ የሚከሰቱትና አገራዊ ተግዳሮት መሆን የጀመሩት ግጭቶች ዋነኛ መንሥዔ ይህ ነው። ይህ ተግዳሮት በጊዜና በአስተማማኝ ደረጃ ካልተፈታ በስተቀር ጥገኛው ኃይል መንግሥትን ወደማንኛውም አፍሪካዊ ዘራፊ መንግሥትነት መቀየሩና አገሪቱን ወደጠቅላላ ቀውስ ማምራቱ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ይሆናል።

ከዚህ ጋር በማያያዝ ሕብረተሰብን ለማደራጀትና ለማንቀሳቀስ ጥቅም ላይ መዋል ስላለበት አስተሳሰብ ወይም ርዕዮት የተወሰነ ሀሳብ ማንሳትና መግባባት አስፈላጊ ይሆናል። ይህም ሕብረተሰብን ለማንቀሳቀስና ለመገንባት ጥቅም ላይ የሚውሉትን የማደራጃ መርሆዎች /Organizing Principles/ በትክክል ከመገንዘብና ከመምረጥ ይጀምራል። በለውጥ ሂደት የሚጓዙ አገሮች በሚያማልል ርዕዮትና የለውጥ መርሐ ግብር /Program/፣ ወይም ደግሞ ብሔረተኝነትና /Nationalism/ የሃይማኖት አክራሪነትን (Religious Extremism) በመሳሰሉ የማደራጃ መርሆዎች በመመራት ሕብረተሰብን ለማንቀሳቀስ ይሞክራሉ። ርዕዮት የማደራጃ መርሆ በሚሆንበት ጊዜ፣ እንደመሪ ድርጅቱ ባሕርይና ዝንባሌ እጅግ አብዛኞቹን የአገሪቱን ህዝቦች ወይም ደግሞ በወሳኝነት በጣም ጥቂት የሕብረተሰብ ልሂቃንን ብቻ የሚጠቅም አስተሳሰብ በማደራጃ መርሆነት ሊወሰድ ይችላል። ይህም ሆኖ አንዳንዴ አስተሳሰቡ ከሕብረተሰብ ውስጥ በጣም ጥቂቶችን ብቻ የሚጠቅምና ብዙኃኑን የሚጐዳ ሆኖ እያለም የበላይነት አግኝቶ በብዙኃኑም ታምኖበት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። ኒዮ-ሊበራሊዝም ለጥቂቶች ጥቅም የቆመና ብዙኃኑን የሚጐዳ አስተሳሰብ ሆኖ እያለ፣ ለጊዜው በዓለም ህዝቦች ላይ የበላይነት ያለው አስተሳሰብ ሊሆን የቻለው በዚህ የተነሳ ነው። የርዕዮቱ ባለቤት የሆኑት ኃይሎች በሚዲያ፣ በትምሕርት ቤቶችና በእምነት ተቋማት ታግዘው በርዕዮቱ ተጐጅ በሆኑ ማኅበረሰቦች ሳይቀር የሚታመንበት እንዲሆን አድርገውታል።

ከዚህ በተቃራኒ ሕብረተሰብን የማደራጃ መርሆዎች ተራማጅ አስተሳሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ዓይነቱ የማደራጃ መርሆ በተጨባጭ ሕብረተሰብን በሚጠቅምና መብቱንም በሚያሰፋ ተራማጅ የለውጥ መርሐ-ግብር መልክ ሊቀረጽ የሚችልና ተግባራዊ የሚደረግ

ነው:: ቀደም ሲል በብዙ ልማታዊ መንግሥታት፣ ዛሬ ደግሞ በአገራችን እንደታየው ተራማጅ የለውጥ መርሐ-ግብር ወይም አስተሳሰብ ሕብረተሰብን ካሉበት ችግሮች በማላቀቅ ወደፊት እንዲገሰግስ ለማድረግ ያስችላል:: በዚያው ልክ ደግሞ በብዙኀኑ ህዝቦች ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝና ሊታመንበት ይችላል:: ይህ መሠረታዊ ጥንካሬ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በብዙ አገሮች እንደታየው የተለየ ጥረት ካልተደረገ በስተቀር፣ ተራማጅ አስተሳሰብ በሂደት የመደብዘዝ ወይም የመዳከም አደጋ ሊጋረጥበት የሚችል ነው:: በተለይ የንቅናቄው መሪዎች ለፖለቲካና ስብዕና ግንባታ ሥራው የሚሰጡት ትኩረት ያነሰ ከሆነ፣ የማደራጃ መርሆው ቀስ በቀስ ፋይዳ ወይም ጉልበት /Vitality/ እያነሰው ሊሔድ ይችላል::

በአንድ ወቅት ተአምራዊ የህዝብ ንቅናቄ ለማቀጣጠል ያስቻሉ የለውጥ ፕሮግራሞችና የማደራጃ መርሆዎች ከዘመኑ ጋር እያደጉ እንዲሔዱ ለማድረግ ሳይቻል ሲቀር፣ ምንም ዓይነት የማማለል ችሎታ የሌላቸው መሆን ይጀምራሉ:: ይህ የሚሆነው የብዙኀኑን ህዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅ ተራማጅ አስተሳሰብ ለአዳዲስ መድረኮች ምላሽ የመስጠት ችሎታ ወይም ባሕርይ ስለሌለው አይደለም:: ይልቁንም የአንድ ተራማጅ አስተሳሰብ ዋነኛ ባሕርይ ዘመን ተሻጋሪ መሆኑ ነው:: የተራማጅነቱ ባሕርይም ለአንዴና ለዘላለም የረጋ ከመሆኑ ይልቅ መሠረቱን ሳይለቅ ራሱን ከአዳዲስ መድረኮች ጋር እያጣጣመ ለመጓዝ ከመቻሉ የሚመነጭ ነው:: ነገር ግን ርዕዮቱ ዘመን ተሻጋሪ ሊሆን እየቻለ፣ በየመድረኩ የአመራር ኃላፊነትን የሚወስዱ ሰዎች ርዕዮቱን ለአዲሱ መድረክ በሚስማማ ደረጃ አዳብረው ሕብረተሰብን የማደራጀና የማንቀሳቀሻ መርሆ ሊያደርጉት ሳይችሉ ሲቀሩ ተራማጁ አስተሳሰብ ፋይዳውን ሊያጣ ይችላል::

መሪዎች በዚህ አኳኋን ከዘመን ጋር አብሮ ማደግና መዳበር ያለበትን አስተሳሰብ ማዳበር ሲያቅታቸው፣ በእጃቸው የገባውን ጅምር ለውጥ ቀጣይ ማድረግ ይሳናቸዋል:: የማታ ማታ ደግሞ በተራማጅ ፕሮግራም ሊያነሳሱት ያልቻሉትን ሕብረተሰብ በብሔረተኝነት ወይም እምነት ተኮር (Religiuos) የማደራጃ መርሆዎች ወደማንቀሳቀስ ያመራሉ:: ራሱን በተራማጅ ርዕዮተ ዓለም እየመራ ሕብረተሰብን ወደዚህ ከፍታ ለማውጣት ያልተዘጋጀ አመራር፣ ሁሌም ቢሆን አፍራሽ ገጽታና መልክ ያለውን ብሔረተኝነት ወይም ሌላ አስተሳሰብ እንደማደራጃ መርሆ መውሰዱና መጠቀሙ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ነው::

ትምክሕት፣ ጠባብነት፣ ጐሰኝነት፣ አክራሪነትና አሸባሪነት እንደማደራጃ መርሆዎች ብቅ የሚሉት በዚህ ምክንያትና ወቅት ነው:: ነገር ግን ይህን የመሳሰሉ አማራጭ የማደራጃ መርሆዎች በራሳቸው በጣም መሠረታዊ ችግር ያለባቸውና ከባድ ጥፋት ሊያስከትሉ የሚችሉ እንደሆኑ በብዙ የዓለማችን አገሮች ታሪክ የታየ ነው:: በአሁኑ ጊዜ የምዕራቡን ዓለም በማጥለቅለቅ ላይ ያለው ቀኝ አክራሪ ብሔረተኝነት ለዚህ የቅርብ ማረጋገጫ ነው:: እንግሊዝ ከአውሮፓ ሕብረት የወጣችበት ብሬግዚት (Brexit)፣ ዶናልድ ትራምፕ ከአርባ ዓመታት

በኋላ የደርግን "ኢትዮጵያ ትቅደም" መፈክር ተውሰው "አሜሪካ ትቅደም" (America First) በማለት ራሷ አሜሪካ ከጀመረችውና እኛን ሁሉ አስገድዳ ካስገባችበት ግሎባላይዜሽን ማፈግፈግ መጀመራቸው፣ ትምክህት ወይም ጠባብ ብሔረተኝነት የሰውን ልጅ ለሌላ መከራ ማጨት እንደጀመሩ ያመላክታል።

ብሔረተኝነትን እንደአንድ የህዝብ ማደራጃ መርሆ ጥቅም ላይ በማዋል ሕብረተሰብን ለመለወጥ የሚደረግ ጥረት የተወሰነ ጥቅም የለውም ባይባልም፣ በየትኛውም ሕብረተሰብ እንደታየው ግን ጉዳቱ የሚያመዝን ነው። ኢህአዴግ ህዝብን በብሔረተኝነት የማደራጃ መርሆ ለማሰባሰብ ጥረት የሚያደርግ ለሚመስላቸው ሁሉ ይህ አባባል ሊያስገርማቸው ይችል ይሆናል። ስለሆነም የኢህአዴግ የማደራጃ መርሆ ቀደም ሲል እንደተገለጸው አብዮታዊ ዴሞክራሲና በሂደት ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲ በመባል የተሰየመው የአስተሳሰብ ዘውግ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ብሔረተኝነት ሕብረተሰብን የማደራጃና የማንቀሳቀሻ ዋናው መርሆ በሚሆንበት ጊዜ፣ ከሁሉ በፊት በሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን ብዙኃነት መድፈቅ ያስከትላል። የኢኮኖሚ ልዩነቶች ተሸፍነው የአገሪቱ ህዝቦች በሙሉ አንድ ዓይነት ፍላጎ ተመስለው መቅረባቸውን የግድ ይላል። በህብት ደረጃ የተለያየ ሆኖ እያለ ጀርመናዊ የሆነ ሁሉ አንድ የአርያን ዘር ነው ይባላል። በነዳጅ ህብቱ ላይ ያላቸው ባለቤትነትና ተጠቃሚነት የተለያየ ሆኖ እያለ አረብ የተባለ ሁሉ አንድ ተመስሎ ይቀርባል። በግልባጩም በየአገሩ (ብሔሩ) የሚገኙ ድሃ ህዝቦች በኢኮኖሚያዊ ደረጃቸው ዝቅተኛ፣ ከዚህ በሚለቀቁበት ልማታዊ መንገድ ተመሳሳይና አንድ ሆነው እያለ፣ በአገራቸው ወይም በብሔራቸው መለያየት ምክንያት ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው እስከመባል ይደርሳሉ። በዚህ ልዩነት ላይ ለተመሠረተ አድሎና በደልም ይዳረጋሉ።

ብሔረተኝነትን እንደዋነኛ የማደራጃ መርሆ የሚጠቀም አመራር፣ ሁሌም ቢሆን የአገሩን ህዝቦች ከሌሎች አገሮች ህዝቦች ፍፁም በተለየ መንፈስና መንገድ ለመገንባት ይሞክራል። በዓለም የሚኖሩ ህዝቦች እንዲሁም መንግሥታት በብዙ ገጽታቸው ተመሳሳይ ቢሆኑም፣ ብሔረተኝነትን የማደራጃ መርሆ ለማድረግ የሚፈልግ መንግሥት ሁሉ ልዩነትን አጉልቶ ማሳየት ይመርጣል። የአሜሪካ፣ የጀርመን፣ የጃፓን፣ የአረብ፣ የቻይና ልዩ ህዝብነት /Exceptionalism/ የሚባለው መለያ በብዙ አገሮች ተደጋግሞ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ይህም እነዚህ አገሮች ከማንም የማይጋሩት ባሕርይ እንዳላቸው የሚያስመስል አሳሳች አቀራረብ ነው። በተለያዩ ወቅቶች አሜሪካኖች ከአውሮፓውያን፣ ጃፓኖች ከጀርመኖች፣ ኮሪያዎች ደግሞ ከነጃፓን፣ ቻይናም ከነኮሪያና ጃፓን ብዙ ነገሮችን መኮረጃቸው እውነት ሆኖ እያለ፣ ራሳቸውን ከእነዚህ አገራት መሪዎችና ልሂቃን በላይ፣ "እኛ የተለየን ህዝብ ነን" ማለት የተለመደ ነው። ይህም ሁሉ ሆኖ ብሔረተኝነት፣ በተለይም ደግሞ በአንድ አገር ፍፁም የተለየ መሆን ላይ

ተመሥርቶ የሚገነባ ብሔረተኝነት፣ በታየባቸው አገሮች ሁሉ ከባድ ውድቀትን አስከትሏል። በጀርመንና ጃፓን "ፍፁም የተለየ ህዝብ ነን" በሚል ቅኝት የተገነባው ብሔረተኝነት ፋሽዝምና ወታደራዊነትን ወልዷል። የእስራኤልን ፍፁም ልዩነት ከመስበክ የማይቦዝነው ጽዮናዊነትም በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ እጅግ አደገኛ ከሆኑ የነዳጅ አምራች ሱልጣኔቶች ጋር ተባብሮ ህዝብን ለድኅነት፣ ኋላቀርነትና ሽብር ሰለባ አድርጓል። የዚህ መንትያ የሆነውና በተመሳሳይ ቅኝት የተቀሰቀሰው የአረብ ብሔረተኝነት በበኩሉ፣ ጽዮናዊነትን የመታገል የተቀደሰ ዓላማ አንግቦ የተነሳ ቢመስልም፣ በመላው መካከለኛ ምሥራቅ የተንቀለቀለውን እሣት ለማብረድ ሳይችል ቀርቷል።

ከሃይማኖት ጽንፈኝነት አኳያም ተመሳሳይ ነው። አገራዊ የመሪነት ኃላፊነትን የሚወስዱ ሰዎች ለሕብረተሰብ ታዳጊ ፍላጐት አርኪ ምላሽ መስጠት በሚያቅታቸው ጊዜ ሁሉ ሃይማኖትን እንደአንድ መሣሪያ በመጠቀም ለማስተዳደር ይሞክራሉ። ለግላሰብ አማኞች መተው ያለበትን እምነት መንግሥታዊ ይዘትና ቅርጽ አላብሰው የሕብረተሰብ መመሪያ ያደርጉታል። ከዚህም አልፎ የእምነቱን ጽንፈኛ አተረጓጐም (Religious Extremism) የሕይወት መመሪያ እስከማድረግ ይደርሳሉ። ይህ የተለያዩ እምነቶች በሚመለኩበት አገር የሃይማኖት እኩልነትን አጥፍቶ ኢድሎና መናቆር እንዲከተል ያደርጋል። በገሪቤታችን ሶማሊያ እንደታየው አንድ ሃይማኖት ብቻ በሚመለክባት አገርም ቢሆን የሃይማኖት ጽንፈኝነት ጦሱ ብዙ ነው። በሰላምና መቻቻል አቅጣጫ የሚጓዝን ሕብረተሰብ ወደምስቅልቅል ያስገባል። መንግሥታዊ ሥልጣን የያዙ ከፍሎች መንግሥትና ሃይማኖትን መነጣጠል ተስኗቸው የሃይማኖት ጽንፈኝነትን የማደራጃ መርሆ ካደረጉት ዳፋው ከአገራቸው አልፎ ጐረቤቶቻቸውን ከዚያም አልፎ ራቅ ብለው የሚገኙ አገሮችን ማተራመስ ይሆናል።

በእኛም አገር ብሔረተኛነትና የሃይማኖት ጽንፈኝነት ዋናዎቹ የማደራጃ መርሆ ከሆኑ ውጤቱ ተመሳሳይ መሆኑ አይቀርም። በእነዚህ አስተሳሰብ መሠረት እጅግ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን በሀብት ደረጃቸው ዝቅተኛ ሆነው እያለ፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ወይም የአንዱ ብሔር አባል በመሆናቸው ብቻ፣ ልክ ከሌላው የአገራቸው ወይም የብሔራቸው ሀብታም ጋር አንድና እኩል ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህ ዓይነት ብሔረተኝነት የማደራጃ መርሆ ሲሆን፣ ወሰጣዊ የገቢ ልዩነትን በማንነት ካባ መሸፈን ያስከትላል። በዚያው ልክ ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ወገኖች ሁሉ በራሳቸው የመብትና የተጠቃሚነት አጀንዳ ዙሪያ ለማታገል ያለው ዕድል እየጠበበ ይሄዳል። ብሔረተኝነት ዋናው የመንግሥት የማደራጃ መመሪያ ሲሆን፣ መንግሥት ለድሃ የወገነና የእነርሱንም መብትና ጥቅሞች የሚያስከብር መሆኑ ያቋርጣል። የሃይማኖት ጽንፈኝነት የማደራጃ መርሆ ሲሆንም ውጤቱ ተመሳሳይ ነው።

ከእነዚህ ጥቂት አብነቶች አንድን ሕብረተሰብ አደራጅቶ ለማንቀሳቀስ ስለሚያገለግሉት መርሆዎች ፋይዳ የተወሰነ ግንዛቤ ለመያዝ ይቻላል። በኢትዮጵያ ሁኔታ ኢህአዴግ የተከተለው የማደራጃ መርሆ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ በማለት የሰየመውን አስተሳሰብ ነው። ይህ በብዙ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሔ ሊሆን የሚችል የማደራጃ መርሆ ነው። መለስ እድሜ ልኩን ባደረገው ጥረት የቀመረውና ከመድረክ ወደመድረክ በተሸጋገርን ቁጥር እያዳበረው የመጣ ንድፈ-ሀሳብ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ወደፊት ለምንገባባቸው መድረኮችም ጭምር ይሆን ዘንድ ይበልጥ እየዳበረ ሊሔድ የሚችል ንድፈ-ሀሳብ ነው። የዳበረ ካፒታሊስታዊ ሕብረተሰብ ደረጃ ላይ ሲደረስ ይህ የማደራጃ መርሆ ወደ ሶሻል ዴሞክራሲ የማደግ ወይም የመቀየር ዕድል እንደሚኖረው ይገመታል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጣይ የአመራር ትውልዶች ይህንኑ የማደራጃ መርሆ እንደመነሻ ጨብጠው፣ በየራሳቸው መድረክ ለሚገጥሟቸው አዳዲስ ችግሮችና ተግዳሮቶች አዳዲስ መፍትሔ እያከሉበትና እያዳበሩት ሊሔዱ ከቻሉ፣ በእርግጥም ኢትዮጵያን እስከ ወዲያኛው ለዕድገት የሚያበቃ የአስተሳሰብ ማዕቀፍ ነው። ፈረንጆች "ወላጆችህ የቱንም ያህል ረጅም ቢሆኑ የራስህን ቁመት ማደግ አለብህ" እንደሚሉት፣ የየትውልድ ዘመኑ አመራር መሠረታዊውን አቅጣጫ ሳይለቅ፣ የየራሱን ቁመት መፈለግና መገንባት እስከቻለ ድረስ፣ ልማታዊ ዴሞክራሲ በርግጥም የኢትዮጵያን ህዳሴ እስከወዲያኛው እውን ለማድረግ የሚያስችል የማደራጃ መርሆ ነው። ይህ በመሆኑ ትከከለኛውን የማደራጃ መርሆ ይዞ ከመጀመር አኳያ ኢትዮጵያ በጣም የተሻለ መነሻ የጨበጠች አገር ነች።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሕብረተሰብ ውስጥም ሆነ በመንግሥት ደረጃ በብሔረተኝነትና በሃይማኖት ጽንፈኝነት ቅኝት መንቀሳቀስ ጐላ ብሎ የሚታይ ዝንባሌ ሆኗል። ለጊዜው በሕብረተሰብ ደረጃ የሚታየውን ችግር ወደጐን አቆይተን ከጊዜ ወደጊዜ አሳሳቢነቱ እየጐላ የመጣውን የመንግሥት ኃላፊዎች ስህተት መነሻ በማድረግ ብዙ ነገር ማንሳት ይቻላል። በፌዴራላዊ ሕብረትና በቡድን መብቶች መከበር ምክንያት በተፈጠረ እኩል ተሳትፎ እየተገነባች ባለች አገር እየኖርን፣ አሁን አሁን ጥቂት የማይባሉ ከፍተኛ አመራሮች የሁሉም ህዝቦች ወኪል መሆናቸውን ዘንግተው ራሳቸውን የአንድ ብሔር ወይም ሃይማኖት ጠበቃ አድርገው ሲቆጥሩ መመልከት የተለመደ ሆኗል። በየትኛውም ከልል በህዝብ ተመርጦ ሥልጣን ላይ የወጣ መሪ በከልሉ ውስጥ የሚኖሩ የሁሉም ኢትዮጵያውያንን ሕይወት በእኩልነት የማቃናት ኃላፊነት አለበት። ይሁንና በብሔር ወይም በሃይማኖት ጽንፈኝነት አስተሳሰብ መመራት የመረጡ አንዳንድ ኃላፊዎች ይህን ከማድረግ ይልቅ አደገኛ ስህተቶች ሲፈጽሙ ይታያሉ።

እነዚህ ግለሰቦች የጋራ አገራዊ ኃላፊነት መሸከማቸውን ዘንግተው የብሔር ወይም

የሃይማኖት ዘውግን በመከተል "የእኛ" አይደሉም በሚሉዋቸው ወገኖተ ላይ በደል ሲፈጽሙ ይታያሉ። እነርሱ በደል ካልፈጸሙም ሌሎች የሚፈጽሙትን በደል የማስቆም ኃላፊነታቸውን ሳይወጡ ይቀራሉ። በብሔር "ፍቅር" ወይ ጥላቻ ላይ የተመሠረተ የራሳቸውን የተሳሳተ ፖሊሲ ይከተላሉ። መንግሥት በሁሉም ህዝብ የተመረጠ ተቋም ሆኖ እያለ በጠባብ ጥቅሞችና እሳቤዎች ላይ የተመሠረተ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም እንዲሆን ያደርጉታል። ለመሬትም ሆነ ኮንትራት እደላ፣ ለሥራ ቅጥርም ለአገልግሎት አሰጣጥ የብሔር ዘውግን መስፈርት ያደርጋሉ። መንግሥት ከሃይማኖት ገለልተኛ ሆኖ እያለ እምነትን መስፈርት ያደረገ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ያደርጉታል። በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገውን ሁሉንም ዜጐች ያለእምነት ልዩነት እኩል የማገልገል መርሕ ጠቅጥቀው፣ አርቶዶክስ ከንቲባ ሲሆን ለተዋህዶ አብያተ ክርስቲያን፣ ሙስሊም ከንቲባ በሆነበት ለመስጊድ፣ ኢቫንጀሊስት ከንቲባ ሲሆን ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን መስፋፋት ሌላውን ያገለለና ከመሥመር የወጣ ድጋፍ ይሰጣሉ። ሁሉንም እኩል በማገልገል ሁሉንም እኩል መመልከትና መጥቀም ሲቻልና ሲገባ ህዝብን ለያይተው ይመለከታሉ።

ይህም ሆኖ የእነዚህ ግለሰቦች መነሻና መድረሻ ህዝብ ሳይሆን የራሳቸውና የቅርብ ወዳጆቻቸው ጥቅም ብቻ ነው። በዚህ ረገድ የሚታየው ስህተት እነዚህ አመራሮች "የእኛ" በሚሉት ህዝብ ፍቅር ስለነደዱ ወይም ለህዝቡ የተለየ አከብሮት ስላላቸው የሚፈጸም አይደለም። ህዝብን የሚወድ ማንኛውም ሰው ብሔር ወይም የሃይማኖት ዘውግን እያማረጠ ህዝብን ሊወድ አይችልምና። በተለይ ደግሞ ሁሉን ህዝብ በጋራና በእኩልነት አስተባብሮ የማልማትና የመጥቀም ግዴታውን ለመወጣት ሲሞከር የቆየ አመራር፣ በብሔር ወይም በሃይማኖት ዘውግ እየተመራ አድሎ መፈጸም ከጀመረ ይህ የሚሆነው ከራሱ ግላዊና ጠባብ ጥቅም በመነሳት መንቀሳቀስ ስለጀመረና የነበረውን መልካም ባሕርይ እየተወ ስለመጣ ብቻ ነው።

ሐቁ ይህ ቢሆንም ይህን በግላጭ ማራመድ የህዝብን ቁጣ የሚጋብዝ እንደሆነ ስለሚያውቁ ራስ ወዳድ መሆን የጀመሩ አመራሮች በብሔረተኝነት ወይም በእምነት ጭምብል መሸፈን ይመርጣሉ። በዚህ የተነሳ ከሁለቱ አንዱን መስፈርት በመጠቀም አንዱን ማኅበረሰብ ያቀረቡ መስለው ሌላውን ያርቃሉ። አንዱን የጠቀሙ መስለው ሌላውን ይጐዳሉ። ነገር ግን ራሳቸውን ለመጥቀም በቀየሱት በዚህ አደገኛ ስልት ሳይውሉ ሳያድሩ የ"እኛ" የሚሉትን ህዝብ ሳይቀር ጉዳት ላይ ይጥላሉ። የሁሉም ከልሎች ህዝብ በራሱ ብሔር ልጆች እየተዳደረ ባለበት በአሁኑ ወቅት በሁሉም የመልካም አስተዳደር መስፈርቶች የሚደርስበት በደል ከሌላ ሳይሆን በብሔር ወይም በሃይማኖት ሰበብ ሊያነሳሱት ከሚሞክሩት የራሱ ልጆች የፈለቀ መሆኑም ግልጽ ነው። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን በብሔርና ሃይማኖት ሰበብ በሚቀሰቀሱ ግጭቶች ሁሉ የሚደርሰው የአጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ ጉዳት የተናጠል ሳይሆን የጋራ (Colateral Damage) እየሆነ የመጣውም በዚህ የተነሳ ነው። የአገራችንን ሕብረተሰብ በብሔረተኝነት ወይም የሃይማኖት

ጽንፈኝነት አቅጣጫ ከማንቀሳቀስ ይልቅ የጋራ በሆኑ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አጀንዳዎች ወይም ፕሮግራሞች ዙሪያ የማንቀሳቀስ ጉዳይ ወቅታዊ ፈተና ሆኖ የሚገኘውም በዚህ የተነሳ ነው።

የግንባሩን ጤንነትና የመምራት ብቃት የማረጋገጥ ፈተና፣

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የልማታዊ ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዳይ በመሠረቱ በፖርቲ መሪነት የሚካሔድ የለውጥ ተግባር ነው፡፡ በጃፓንና በኮሪያ የልማታዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱ በመንግሥታዊ ቢሮክራሲ እየተመራ ለስኬት በቅቷል። ስለዚህም አገሮቹ የጀመሩትን የልማት ሂደት ዳር ለማድረስ ቁርጠኛ መንግሥታዊ አመራርና ብቁ የማስፈጸም አቅም ያለው ቢሮክራሲ ከገነቡ በቂያቸው ነበር፡፡ እንደቻይናና ታይዋን በመሰሉ አገሮች ደግሞ የልማታዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱ ከመንግሥት በተጨማሪና ምናልባትም በላይ ከጠንካራ ፖርቲ ሕልውናና አመራር ጋር የተያያዘ ስለነበር ውጤቱ በፖርቲዎቹ ጤንነትና ተልዕኮዋቸውን በብቃት ለመፈጸም በነበራቸው ችሎታ የሚወሰን ነበር። ይህም ሆኖ ልማታዊ ጉዞውን ፓርቲውም ይምራው ቢሮክራሲው፣ ንቅናቄው ከአንድ ምዕራፍ ወደሌላ በተሸጋገረ ቁጥር፣ በሂደቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችና ተግዳሮቶች እየተለዩ መፍትሔ ሊሰጣቸው በመቻሉ፣ እነዚህ አገሮች ከአምሳ ዓመታት ብዙም ባልበለጠ ጊዜ የልማት "ተዓምር" ለመሥራት በቅተዋል፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ህዝባዊ ትግልን እንመራለን ብለው የተነሱ ፓርቲዎችና ተቋማት ከትክክለኛው መሥመር ሲያፈንጣጡ፣ ከምንም ነገር በላይ ደግሞ "በአይጦች ሩጫ" መርሕ እየተመሩ በስግብግብነት እየተሸቀዳደሙ ሲጓዙ ራሳቸውንና የሚመሩትን ሕብረተሰብ ለብዙ ችግሮች ማጋለጥ ይጀምራሉ፡፡ በዓለማችን በዚህ ዓይነት ዝንባሌ ተበክለው ራሳቸውን ለውድቀት የዳረጉ ፖርቲዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ ቻይና በምሥራቅ አውሮፖና በሩሲያ የነበሩ ተራማጅ ፖርቲዎችን የውድቀት ምክንያት ካጠናች በኋላ የወሰደችው ቀዳሚ ትምሕርት ይህ ነበር፡፡ ይህን ትምሕርት በማስመልከት በአንድ ወቅት የቻይና ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ዜንግ ኪንግሆንግ፣ እ.ኤ.አ በ2004 በተካሔደው 4ኛው የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ማግስት፣ የቀድሞዋን ሶቭየት ሕብረትና የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ልምድ መነሻ በማድረግ በሥልጣን ላይ ላሉ ፓርቲዎች በጣም ጠቃሚ ምክር ለግሰው ነበር፡፡ ዜንግ አገራቱ በጀመረችው ለውጥና ተሃድሶ ከፍተኛ ድል እያስመዘገቡት ከተጓዘች ከ26 ዓመታት በኋላ በወቅቱ ብዙም ባልተለመደ ግልጽነት በፒፕልስ ዴይሊ ጋዜጣ ላይ ፡-

> "ሶቭየት ሕብረት በዓለማችን ቀዳሚዋ ሶሻሊስት አገር ነበረች፡፡ ነገር ግን የ88 ዓመታት ታላቅ ታሪክና 15 ሚሊዮን አባላት የነበረው የሶቭየት ኮምዩኒስት

ፖሊሲ ከለጋሽ ድርጅቱ ቤሊጥ ሠደዋ። ለዚህም በሃገሪንያቱ መካከል አንዱ ፓርቲው በሥልጣን ላይ በቆየባቸው ረዥም ዓመታት፣ የአገዛዝ ሥርዓቱ ግትርነት የሞላበት መሆኑ ነበር። ይህን ተከትሎ የፓርቲው የማስተዳደር ብቃት ተዳከመ። ህዝቡም በፓርቲና በመንግሥት ኃላፊዎች የሥራ አፈጻጸም ላይ የነበረው ቅሬታ ተበራከተ።" ካሉ በኋላ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ የተነሡበትን ምክንያት ሲያብራሩ "በፓርቲያችን ውስጥ ያሉ ጓዶች ሁሉ፣ በተለይ ደግሞ በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙት መሪ ካድሬዎች በጊዜ ይነቁ ዘንድ፣ የሚጠበቃቸውን አደጋ በደህናው ጊዜ ለይተው በብቃት እንዲዘጋጁ፣ ችግርን የመቋቋም ብቃታቸውና በጥሩ ሁኔታ የማስተዳደር መንፈሳቸውንና የፓርቲውን በመልካም ሁኔታ የማስተዳደር ብቃት ለማጐልበት ነው።"[63] ብለው ነበር።

ቻይና ይህን ልምድና ማስገንዘቢያ መነሻ በማድረግ የጀመረችውን ተሃድሶ ያለአንዳች መኩራራት አጠናክራ ቀጥላለች። ድሮም ለዕድልና አጋጣሚ ሳይሆን፣ ለጥረት ልዩ ትኩረት በሚሰጠው ሥነ-ልቦና አርቃ እያሰበች፣ "ተሃድሶና ግልጽነት" /Reform & Opening/ በማለት የጀመረችውን እንቅስቃሴ፣ "ለተሃድሶው ጥልቀት መስጠት" /Deepening the Reform/ በሚል ሌላ ሪፎርም በማጐልበት ከዕድገት ወደዕድገት ተረማምዳለች።

ከዚህ የምሥራቅ አውሮፓ ፓርቲዎችና የቻይና ልምድ በመነሳት ብዙ ትምሕርት ሊወሰድ ይችላል። ያስመዘገባቸውን ድሎችና ያመጣቸውን ለውጦች እያሸሞነሞነ፣ በሕብረተሰብ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በራሱ በፓርቲው ውስጥ የተደቀኑ ችግሮችን ሁሉ በቸልታ የሚያልፍ ገዥ ፓርቲ ብዙም ርቀት እንደማይጓዝ ለመገንዘብ ይቻላል። በአንጻሩ ከግትርነት ተላቆ የሥርዓት ችግሮችን በቅን ልቦናና በህዝባዊ ወገንተኝነት መንፈስ የሚመለከት ፓርቲ ደግሞ፣ የፈተናው ከብደት ምንም ይሁን ምን፣ የየመድረኩን ተግዳሮቶች እየፈታ ወደፊት መጓዝና መመንደጉ እንደማይቀር መማርም ይቻላል።

በመሪ ተቋማት መካከል ያለው የብቃትና ሌላም ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሥልጣን ላይ የሚገኙ ፓርቲዎችን በእጅጉ ከሚፈታተኗቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በሥልጣን ላይ ለረዥም ጊዜ ከመቆየት ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችል የባሕርይ ለውጥና በሥልጣን መባለግ ነው። በዚህ የተነሳ ከፍተኛ ጥንቃቄ ካላደረገ በስተቀር በሥልጣን ላይ የሚገኝ ፓርቲ ለብዙ ችግሮች ተጋላጭ የሚሆንበት ዕድል ሰፊ ነው። ሥልጣን የያዘ ፓርቲ ይህንኑ የለውጥ መሣሪያ አድርገው ሊጠቀሙበት የሚፈልጉትን ብቻ ሳይሆን፣ የግል መጠቀሚያ ለማድረግ የሚሹ የአድርባይነት አስተሳሰብ የተጠናወታቸውን ሰዎችም ያማልላል። መለስ ከመጀመሪያው ተሃድሶ ጥቂት ቀደም ብሎ ሥርዓቱ የገጠመውን ብልሽት መነሻ በማድረግ ባዘጋጀው "የቦና ፓርቲስት

"በብዙኃን እንቅስቃሴ ላይ ጉድለቶች ስለነበሩብን፣ የሕብረተሰቡን ምርጥ አካላት በተፈጥሯዊና በማያሳስት መንገድ እየመለመልንና እያበቃን አስተማማኝ ሰፊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ለመገንባት የምንችልበትን ወሳኝ ትጥቅ አጥተናል። እንዲህም ስለሆነ ምልመላችን በአብዛኛው የአጋጣሚ ባሕርይ ነበረው። በትውውቅና በመቀራረብ ልንመለምል የምንችለው ልናያቸው የቻልናቸውን ሰዎች ብቻ ነው። ይህም ዞሮ ዞሮ የዕድልና ሎተሪ ጉዳይ መሆኑ አይቀርም። በመሆኑም በዚህ አግባብ ተመልምለው ወደከፍተኛ ቦታዎች የመውጣት ዕጣ የደረሳቸው ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ ዕጣው የማይገባቸው እንደሆነ በተግባር ያረጋገጡበት ሁኔታ ተፈጠረ። ችግሩ ግን ይህ ብቻ አልነበረም። ሥልጣን የያዝን እንደመሆናችን መጠን ወደእኛ የተጠጋ ልዩ ልዩ ጥቅሞችን ማግኘቱ አይቀርም። ማር ባለበት ቦታ ላይ ቀድሞ የሚያንጣብበው ዝንብ ነው። ሥልጣን ባለበትም አስቀድሞ የሚያንጣበበው ከዚህ ሥልጣን ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈልግ ነው። ይህን[ዝንብ] ከንብ ለመለየት የሚቻልበት ነባራዊ መመዘኛ እስከሌለ ድረስ ምልመላው የአጋጣሚ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ዝንብና ንብ ተቀላቅልው ለመለየት የሚያስቸግርበትና በርካታ ዝንቦች የሚሰፍሩበት ይሆናል። ዝንቡንና ንቡን ለመለየት የሚያስችል ቀጣይና ዴሞክራሲያዊ የብዙኃን እንቅስቃሴ ስለማይኖር ደግሞ ዝንቡ በማያሳስት አኳኋን እየተወገደ፣ ንቡ ደግሞ እየፈረጠመ የሚሔድበት ዕድል ይጠባል።"[64] በማለት አመላክቶ ነበር።

ከዚህ ጥቅስ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ፓርቲው በሥልጣን ላይ በሚሆንበት ጊዜ ህዝብን ለማገልገል ወይም በህዝብ ለመገልገል የሚሹ ሰዎች ሊቀርቡት ይችላሉ። ስለሆነም በሥልጣን የመገልገል ቅኝትና አስተሳሰብ ያላቸውን ሰዎች እያስተካከለ፣ የማይስተካከሉትን ደግሞ በማያቋርጥ ሁኔታ እያጠራ መጓዝ ይጠበቅበታል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሚፈጸም ማንኛውም ዓይነት ቸልታ ፓርቲውን ቅጽበታዊ በሆነ ፍጥነት ከልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ፈለግ አውጥቶ ወደስህተት ያመራዋል። ይህ በሥልጣን ላይ ያለን አንድ ፓርቲ ሊገጥመው የሚችልና ብዙዎቹን ጥሩ ፓርቲዎች ከመስመር በማስወጣት አደገኛ ውጤት የሚያስከትልና ከባድ ዋጋ የሚያስከፍል ፈተና ነው።

ይህ ማንኛውንም ብቁ አመራር ከሌላው ሰው የሚለየው መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ከዚህ በመነሳት ዋናው የአመራር ሥራ ችግር መፍታት ከሆነ ዘንዳ፣ ችግሮችን መለየት (Problem

Identification) ደግሞ ቀዳሚው የአመራር ተልዕኮ መሆን አለበት። ያልተለየ ችግርን ለመፍታት ስለማይቻል አመራሩ አሉ የሚባሉ ችግሮችን ለመስማት ዝግጁና ዴሞክራሲያዊ መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ አመራሩ የሚለየውም ሆነ የሚፈታው ችግር አይኖርም። ስለችግር የሚያነሡ ተቆርቋሪዎችን እያገለለ የድል ብሥራት የሚያሰሙና በመለስ አገላለጽ፣ "መንጋቱን አብሳሪ አውራ ዶሮዎችን" እየመረጠ የሚሰማ ከሆነም የሚፈታው የህዝብ ችግር አይኖርም። በትግል ድርጅት ውስጥ አድርባይነት ሲገነግን የተፈጥሮ ሕግ ሆኖ የመጣውን ብርሃን ለማምጣት አንዳችም አስተዋጽኦ ያላበረከቱ ንጋት አብሳሪ አውራ ዶሮዎች፣ "ፀሐይ የወጣችው የእኛን ድምጽ ሰምታ ነው" እንደሚሉ በብዙ አገሮች ታይቷል። በሥልጣን ላይ ያለ ማንኛውም ፓርቲ በውስጡ እንዲህ ዓይነት አድርባይነት እንዲነግስ ምቹ ሁኔታ ከፈጠረ ለድክመቶቹና ለስኬቶቹ ያለው ሚዛን እየተዛባ ይሔዳል። ይህ ብዙ ጥሩ ፖርቲዎችን በእጅጉ የተፈታተነና በንድፈ-ሀሳብ ብቻ የማይወሰን ተጨባጭ አደጋ ያስከተለ በመሆኑ አፋሽ አጎንባሽነትን የማያበረታታ አመራር መሆን ይገባዋል።

ራሱን በህዝቡ ጫማ ውስጥ አስገብቶ የሚመለከት አመራር ሁሌም ቢሆን የህዝቡን ችግሮች መነሻና መድረሻ ያደርጋል። ራሱን ወደአዲስ ገዥ መደብነት የሚቀይር አመራር ደግሞ ደግ ደጉን ብቻ እያጐላ፣ እጅግ ግዙፉን ችግር ጭምር እስከመካድና መዘንጋት ይደርሳል። ይህ በብዙ የዓለማችን ክፍሎች የታዩ ህዝባዊ ንቅናቄዎችን የፈተነ ከባድ በሽታ ነው። ይህን አደገኛ የአዲስና ተስፈኛ ገዥ መደብ የአገማገም ሥልት ጥሰው መሔድ የተሳናቸው ንቅናቄዎች ሁሉ አጣ ፋንታቸው ውድቀት ሆኗል።

በኢትዮጵያ ላለፈው ሩብ ምእተ ዓመት የመንግሥት ሥልጣን አገር የመለወጫ መሣሪያ እንዲሆን ለማድረግ በተለየ ትኩረት ጥረት ተደርጓል። ኢህአዴግ ራሱን በዝርፊያ ከሚከብሩ ያልበለጸጉ አገሮች መንግሥታት ስህተት በመጠበቅ፣ የህዝብን ልማታዊ ጥረት በሚያጐለበት ቅኝትና ከሥልጣን ጋር ተያይዞ የሚመጣን ብልግና ለመከላከል በሚችልበት አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ ከባድ ትግል ተካሂዷል። በዚሁ ልክ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የመንግሥት ሥልጣን በህዝብ አገልጋይነት ቅኝት እንዲመራና በአገሪቱ ለተመዘገበው ፈጣን ለውጥ መንስዔ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፣ በጥልቅ ተሐድሶው መጀመሪያ ላይ በራሱ በአመራሩ እንደታመነበት የፖርቲ ኃላፊነት ከጊዜ ወደጊዜ የመንግሥታዊ ሥልጣንና የሀብት ምንጭ የመሆን አደጋ ተጋርጦበታል። በዚህ የተነሳ ኢህአዴግ ከራሱ ውስጥና ከውጭም በተፈጠሩ የጥቅም ቡድኖች የመማረክ ስጋት ላይ እንደወደቀ የሚያሳዩ ድርጊቶች ተበራክተው ቆይተዋል። ስለዚህም ጤናማ የትግል ድርጅት የነበረው ኢህአዴግ በእነዚህ የጥቅም ቡድኖች ተፅዕኖ ሥር መውደቅ መጀመሩ በአገራችን የፈተናዎች ሁሉ እናት መሆን ጀምሯል።

እነዚህ የጥቅም ቡድኖች የፖርቲ ሥልጣን በያዙበት ሁሉ መሬት ሲያግበሰብሱ፣ ወይም በኪራይ ሰብሣቢነት ቅኝት መሬትን ሲያድሉ ይታያሉ። የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች የሚጓተቱበት፣ በዋጋ ንረትና በጥራት መጓደል የሚሰቃዩበት፣ በአንጻሩ አንዳንድ ባለሥልጣኖችና ከእነርሱ ጋር የተሻረኩ ሰዎች አላግባብ የሚበለጽጉበት ሁኔታ የሰፋውም ለዚሁ ነው። ቀደም ሲል እንደተመላከተው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአራቱ ብሔራዊ ድርጅቶች ወይም ከአጋር ድርጅቶች የአንዱ ድርጅት የአባልነት መታወቂያ የያዘን ሰው መንካት ወይም በሕግ ተጠያቂ ማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል።

ይህን የመሰለው ሂደት ፖርቲውን ተጠልሎ ወደሥልጣን በመምጣት የመክበር ፍላጐት ያላቸውን ሰዎች ይበልጥ ወደፖርቲው እንዲያቀኑ አበረታትቷል። ኢህአዴግ የቆመለት ትክክለኛ ዓላማ ተዘንግቶ አመራርነት የሥልጣንና የሀብት ምንጭ እየሆነ በሄደ ቁጥር፣ እንደምንም ብሎ የድርጅት፣ በተለይ ደግሞ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የመሆን ዝንባሌ አይሏል። የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የመሆን ዕድል ያገኙ ሰዎች ብቃቱ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ለሚኒስትርነትና ለቢሮ ኃላፊነት እንደሚታጩ ሳይታለም የተፈታ ሆኗል። የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል መሆን የሚኒስትርነትና የቢሮ ኃላፊነት ቦታን ከመቆጣጠር አልፎም በአገራዊና ክልላዊ ጸጋዎች ላይ የማዘዝ ሥልጣን የሚያጐናጽፍ ተደርጐ ተወስዷል። ስለዚህም ለሥልጣን መሚሚት ተበራክቷል። ለምሣሌ ከ2007 ዓ.ም. ምርጫ ማግስት ገና አዲሱ መንግሥት መደራጀት ሳይጀምር አንዳንድ የድርጅት ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች የሚኒስትርንት ቦታ እንዲሰጣቸው አማላጅ በመላክ ደጅ መጥናት እንደጀመሩ በአመራር ስብሰባ ላይ ተገልጾ ነበር። እነዚህ የከፍተኛ አመራር አባላት ራሳቸውን በሚኒስትርነት ወንበር ላይ ከተቀመጡ ሌሎች "ጓዶቻቻው" ጋር በማነጻጸር "እኔስ በምን አንሳለሁ? ካላነስኩ ደግሞ ለምን ሚኒስትርነት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች እርቃለሁ?" በሚል አመክንዮ የሚመሩ መሆናቸው አያጠራጥርም። ይህ እንዲሆን የሚገፋፉ በርካታ ምክንያቶችም አሉ። ሚኒስትርነት ብትሠራበትም ባትሠራበትም ለተንጣለለ ቢሮና ቅንጡ መኪናዎች ያበቃሃል። ከቀደምቱ አቻህ የወረስከው ቢሮ ሰፊና ምቹ መስሎ ካልታየህ፣ የመንግሥትን ቢሮ እየለቀቁ በጣም ውድና ዘመናዊ የሆነ ህንፃ፣ በብዙ ሚሊዮኖች ብር ወጪ ከግለሰቦች እስከ መከራየት ድረስ በመሄድ "ከኔ በላይ ላሳር" ትላለህ። አሁን አሁን በብዙ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንደሚታየው፣ የአዋሳኝ ቢሮ ግድግዳዎችን አፈራርሰህ በመጠቅለል የተንጣለለ እንዲሆን በማድረግ ምኞትህን ትጠብቃለህ። ይህም የበታች አካላት አግባብ ያለውን የሥራ ሁኔታ እስከመጉዳት ሊደርስ ይችላል። ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ህዘባዊ አገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቤቶች በቢሮ ጥበት ምክኒያት ተጨናንቀው ህዝብን ማስተናገድ እስኪቸገሩ ድረስ እየተመለከትክም ቢሆን የራስህን ቅንጦት ታስቀድማለህ። ይህ እነደተጠበቀ ሆኖ፣ በራስህ አቅም ልትገዛቸው የማትችላቸውን መኪናዎች ታማርጣለህ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሚታየው ከሆነ ደግሞ በሚኒስትሮች፣ በክልል አስተዳዳሪዎች እንዲሁም በጄኔራሎች መካከል በሚካሄድ የምርጥ መኪና ግዥ ውድድር ከቶዮታ ቪ8 ወደኒሳን ቪ8ና ኢንፊኒቲ ትሸጋገራለህ። መኪናና ቢሮ ህዝባዊ አገልግሎት ሰጭ መሆኑ ቀርቶ የዝነጣ አገልግሎት መስጫ ሆኗል። እናም የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት፣ በዚህም አድረጉ የሚገኝ ሚኒስትርነትና የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ለመብቃት የሚሻኮቱበት ቦታ እየሆነ መጥቷል። ሲሻር እንዳይቆጨው አስቦ ሥልጣኑን እስከጥጉ የሚጠቀምበት ታላፊ እየበዛ በሄደበት በዚህ ዘመን ሹመት በሥራ ብቃት ሳይሆን በአማላጅነት የሚገኝ ታላፊነትና በሽኩቻ የሚያዝ የግል ርስት ወደመሆን ተሸጋግሯል።

በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደደቡብ አፍሪካ በሄድኩ ጊዜ የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ የከፍተኛና መካከለኛ አመራር አባላት በሥልጣን ምክንያት እስከመጋደል እንደሚደርሱ እታዘብ ነበር። በተለይ ደግሞ ምርጫ ሲቃረብ ከሥልጣንና ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጥቅሞች ምክንያት የእርስ በእርስ ሽኩቻና አልፎ አልፎም ፖለቲካዊ ግድያ እንደሚካሄድና አንዳንዶች የተፎካካሪዎቻቸውን ሕይወት እስከ ማጥፋት እንደሚደርሱ ከአገሪቱ ጋዜጦች ተመልክቻለሁ። ከዚህ በመነሳት ይህን የመሰለው አደገኛ ዝንባሌ በተለይ ወደ ኢህአዴግ እንዳይጋባ ለማድረግ ይብዛም ይነስም የተለያዩ ሙከራዎች አድርጌያለሁ። በየሥልጠና መድረኩ ከአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ አደገኛ ስህተቶች እንድንማር ደጋግሜ ለማመላከትም ሞክሬያለሁ። ሆኖም ግን እኔም ሆንኩ ሌሎች ጉዳዩ የሚያሳስባቸው የአመራር አባላት ያደረግናቸው ሙከራዎች በቂ ስላልነበሩ፣ በድርጅት ደረጃም በጉዳዩ ላይ መሠራት የነበረበት ሁሉ ባለመሠራቱና ተገቢው ጥንቃቄ በመጓደሉ ለጊዜው ወደአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ደረጃ ቢደርስም ባይደርስም በዚሁ ቅኝት የሚካሔደው እንቅስቃሴ እየተበራከተና እየሰፋ በመሔድ ላይ ነው።

አሁን አሁን ሥልጣን የብልጽግና ምንጭ ተደርጐ በመወሰዱ፣ በእጅም በአፈርም ብሎ ይህንኑ ሥልጣን ለመቆጣጠር ሲባል የማይፈጸም ስህተት የለም። ብሔራዊ ድርጅቶቹና ራሱ ኢህአዴግ ወደጥፋት እንዳያመሩ የሚያስጠነቅቁና የሚታገሉ ድምፆችን የማፈንና በአልባሌ ምክንያቶች የማስወገድ፣ በአንጻሩ ደግሞ በሥልጣን ብልግና ለመጠቀም የሚፈልጉ ሰዎችን አሰባስቦ የአመራር አካላትን የመሙላት አካሔድ በግልጽ እየታየ መጥቷል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙዎች የተነካኩበትና ቀደም ሲል በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ወስጥ ከሞላ ጐደል አልነበረም ሲባል የሚቻለው የሥልጣን ሽኩቻ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። በየክልሉም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ለመሪነት የሚያበቃ መልካም ስብዕናና ራስን በጤናማ አስተሳሰብ የመገንባት ፍላጐትና ጥረት እንደሌላቸው የሚታወቁ ሰዎች ሳይቀር፣ ስሜት እየቆሰቆሱና እያነደዱ በጤናማ መንገድ የመምራት መርሆዎችን (Principles) በማዳከም ወደላይ ለመውጣት መሻኮት ጀምረዋል። አገራችን በጀመረችው የለውጥ ሂደት ላይ እጅግ አደገኛው ጥቃት በመሠንዘር ላይ

ያለው ከሌላ ሳይሆን ከድርጅቱ ውስጥ በተለይ ከራሱ ከከፍተኛው አመራር መሆኑ በገሃድ የሚታይ ሆኗል። ይህ የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ በሽታ በአንዳች ተዓምር ከኢህአዴግ የአመራር ሠፈር እንዲወጣ ካልተደረገ በስተቀር በአገሪቱና በህዝቦቿ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማስከተሉ አይቀሬ ነው።

ፖርቲው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተመርጦ ሥልጣን የያዘና በዚህ ሥልጣን በብዙ ቢሊዮኖች በሚቆጠር ገንዘብ ላይ ማዘዝ የሚችል ሆኗል። ይህ ሥልጣን የፖርቲው ነው ቢባልም ድርጅታቸውን በመወከል በዚህ ግዙፍ አገራዊ ጸጋ ላይ የሚወስኑት ግለሰቦች ናቸው። ግለሰቦቹ በህዝባዊ ወገንተኝነት አስተሳሰብና ልማታዊ ዲሲፕሊን ቅኝት የሚመሩ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ይህ ገንዘብ ህዝብን በሚጠቅም የልማት ሥራ ላይ ውሎ ፈጣን ዕድገትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ያስከትላል። በአንጻሩ መሪዎች በራስ ወዳድነት አስተሳሰብ የሚመሩ በሆኑ ቁጥር፣ ይህ ጸጋ ተወደደም ተጠላም በሥልጣን ላይ ያሉትን የፖርቲ ወኪሎች ወደማበልጸግ ያመራል። እነዚህ ሁለት ዝንባሌዎች በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በግልጽ የሚታዩ ሆነዋል። በሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጡ የፖርቲው ወኪሎች ረዘም ላሉ ዓመታት በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ፣ ከጊዜ ወደጊዜ በትግሉ ላይ እየታየ በመጣው ቸልተኛነት የተነሳ በተሰጠው ህዝባዊ ኃላፊነት ራስን ለማበልጸግ ቅድሚያ መስጠት ጥቂት በማይባሉ ሰዎች ዋናው ዝንባሌ ሆኗል።

አንድ አብዮታዊ ቅኝት የነበረውና ሥልጣንን የራስ ሳይሆን የህዝብ መገልገያ የማድረግ መንገድ የሚከተል ፖርቲ ወደዚህ ደረጃ ከወረደ ድርጅቱ ምንም ዓይነት የኋላ ታሪክ ሊኖረው ቢችልም፣ ዞሮ ዞሮ ራሱን ወደአንድ አፍሪካዊ ዘራፊ መንግሥት ደረጃ ዝቅ ማድረግ ይጀምራል። ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የሚታዩት ስህተቶችና ከዚህም ተከትለው የሚመጡ ስጋቶችና አደጋዎች አይነተኛ መንስኤ ነው። መሪዎች በያዙት ሥልጣን ሌሎች እንዲበለጽጉ መንገድ መጥረጋቸው ቀርቶ፣ የራሳቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጡ ሲሆን፣ በአገር ላይ የሚደቀነው አደጋ ትንሽ አይሆንም። ከ2006ዓ.ም. ጀምሮ በየአካባቢው የተቀሰቀሱትና በ2008 ዓ.ም. ወደመለስተኛ አርማጌድዮን ደረጃ የተሸጋገሩት ግጭቶች በግላጭ ያሳዩት ይህንኑ ነው። በፖርቲው ውስጥ ሥልጣንን የግል ብልጽግና መሣሪያ የሚያደርጉ ሰዎች በተበራከቱ ቁጥር የህዝብን በተለይም የወጣቱን ድኅነትና ተስፋ መቁረጥ እያባባሱ ወደግጭት ያመራሉ። በድኅነት የሚማቅቅና መውጫ መንገዱን የሚያሳየው መልካም አመራር በማጣት ተስፋ የቆረጠ ህዝብ ማንኛውንም ዓይነት አርምጃ በመውሰድ ራሱንና ቤተሰቡን ለመከላከል መሞከሩ የታወቀ ነው። በኢትዮጵያ በፖርቲው ውስጥ ሥልጣንን የግል ሀብት ምንጭ የማድረግ አመለካከት ያላቸው ሰዎች እየተበራከቱ መሔዳቸው ሥርዓቱን ከገጠሙት ፈተናዎች ሁሉ ዋናው ወይም የፈተናዎች ሁሉ እናት የሆነው በዚህ የተነሳ ነው። ይህም በመሆኑ ሥርዓቱን ከተደቀነበት አደጋ የማላቀቅ ጉዳይ ድርጅቱን ወደጥንት ባሕርይው ከመመለስና የህዝብ አገልጋይነቱን ከማጠናከር

ውጭ የማይታሰብ ሆኗል።

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ የመንግሥት አደረጃጀትን በተመለከተ እንደገና ማሰብ እንደሚገባም ያሳያል። በፖርቲ ካርድ ተመርጠው ራሳቸውን ለመጥቀም ቅድሚያ የሚሰጡ "አይነኬዎች" የበዙበት ሥርዓት፣ የጥፋት ምንጭ እንደሚሆን ከተገነዘብን፣ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ለመቆየት የፖርቲ ካርድ የማያስፈልጋቸው፣ ይልቁንም በውጤት ብቻ የሚመዘኑ ሙያተኞች (Proffesionals) የሚመሩት መንግሥት ወደመመሥረት ማምራት ያስፈልጋል። በእርግጥ የፖርቲው ካድሬዎች በተለይ የብዙኃን ንቅናቄ የመደራጀትና የመምራት ብቃት ኖሯቸው በአመራር ኃላፊነት የተቀመጡ ሰዎች፣ አገሪቱን እዚህ ድረስ ማምጣታቸው በልዩ ሁኔታ አድናቆት ሊቸረው የሚገባው ነው። ህዝብን አደራጅቶ በማንቀሳቀስ ለውጡን በገጠርና በግብርና የጀመሩት ካድሬዎች፣ ከከፈሉት መስዋዕትነት ውጭ የህዝብን ጉልበት በሰፊው በማንቀሳቀስ የአገሪቱን ስኬታማ የለውጥ ሂደት መጀመር አይቻልም ነበር። በመሆኑም ግብርናና ገጠርን ለመለወጥ የተደረገው ርብርብና የተገኘው ውጤት በርግጥም ከፍተኛ ምስጋና የሚገባው ነው። አሁንም ከድኅነት መውጫ ዋነኛው መንገድ በዴሞክራሲያዊ መንገድ አስተባብሮ የህዝብን ጉልበት ለለውጥ በማነሳሳትና በማሰማራት በመሆኑ የካድሬዎች ሚና በምንም ነገር ሊተካ የማይችል እንደሆነው ሁሉ አገራችን ወደላይ በተነሳች ቁጥር የምትገባበት የተወሳሰበ የዕድገት ደረጃ ከሰፊ የሙያተኞች ድጋፍና ተሳትፎ ውጭ ሊታለፍ እንደማይችል ደግሞ ሊሰመርበት ይገባል።

በፈጣን ለውጥ "ያልታሰበ ቀጠና" ውስጥ የገባ የሽግግር ማኅበረሰብን የመምራት ፈተና፣

ብዙ ጊዜ ፈጣን ለውጥ በሚካሔድባቸው አገሮች ለውጡን ተከትሎ በጣም ብዙ መልካም ነገሮች ይፈጠራሉ። እንደኢትዮጵያ ለዘመናት በማሸቆልቆል ሂደት የኖሩ አገሮች፣ በፈጣን ለውጥ ሂደት ውስጥ ሲገቡ፣ እጅግ ብዙ ችግሮችን ለመቅረፍ ያስችላቸዋል። ስለዚህም ለውጥ በተለይ ደግሞ በጣም ፈጣን ለውጥ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሌም ቢሆን ፈጣን ለውጥን ተከትሎ ያልተጠበቁ ልዩ ልዩ ችግሮች መከሰታቸው፣ ወይም ደግሞ የነበሩ ችግሮች ለጊዜውም ቢሆን መባባሳቸው አይቀሬ ሊሆን ይችላል። ይህም ፈጣን ለውጥ ምንጊዜም ቢሆን ሰዎችን ወይም ሕብረተሰብን ከዚህ ቀደም ከኖሩበት፣ ከለመዱትና ከሚያውቁት ሁኔታ አውጥቶ ወደማያውቁትና ያልለመዱት አዲስ ቀጠና የሚያስገባቸው ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው። በብዙ መልኮች ሊከሰት የሚችለው ይህን የመሰለው እንግዳ ሁኔታና የሚገባበት አዲስ መድረክ በማኅበራዊ ሳይንስ "ያልታሠሠ ቀጠና" (Uncharted Territorry) በመባል ይታወቃል።

አገራችን አሁን ያለችበት ሁኔታና ደረጃ በዚሁ ባልታሰሰ ቀጠና መልከ ሊገለጽ የሚችል ነው። ዛሬ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት ከነበረችው ኢትዮጵያ በጣም በተለየ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን። ከብዙ በጥቂቱ ከአምሳ ሚሊዮን በእጥፍ ያደገው የህዝቧና፣ በዚያው ልክ የተበራከቱትና ፋታ የሚነሱት ወጣቶቿ ከዚህ ቀደም ከምናውቀውና ከለመድነው የተለየ አዲስ ቀጠና ውስጥ እንደሆንን ያሳያሉ። ከእያንዳንዱ ቀበሌ እስከፊዴራል ሥርዓቱ የተቀሰቀሰው የመለወጥና የመጠቀም ፍላጐት፣ ከመሐይምነት በመላቀቃቸው ዓይናቸው የተገለጠ በአሥሮች ሚለዮኖች የሚቆጠሩ ዜጐቿ የዴሞክራሲና ተጠቃሚነት ፍላጐት ማየል፣ በፊዴራል ከልሎች መካከል ያለው የመፎካከር መንፈስ፣ መጠነ ሰፊ የሆነ ገንዘብ የመፍጠርና የማንቀሳቀስ ደረጃ ላይ መድረሷ፣ አባሳንጆና ጓደኞቻቻው እንዳሉት "አገራቱ ሀብታም በሆነች ቁጥር በደንብ መጠቀም ያልጀመሩ ወገኖች ከሚያቀርቡት የተጠቃሚነት ጥያቄ ጋር ተዳምሮ መካከለኛው መደብ የሚያቀርበው ሰፊ ነጻነት የመጐናፀፍ ጥያቄ" ትላንት ያልነበሩ ዛሬ ግን በተጨባጭ የሚታዩ አዳዲስ እውነታዎች ናቸው። መሠረተ-ልማት ተስፋፍቶ ምርታማነት ከፍተኛ ጭማሪ ማምጣት መጀመሩ፣ በሁሉም የሕይወት መስኮች ማሽቆልቆል ተገትቶ ወደላይ መነሳታችን ፈጥኖ ለመለወጥና ለመጠቀም ባለው ፍላጐት ፋታ የሚነሳ ህዝብ መፈጠሩና የተለወጠ ብቻ ሳይሆን እጅግ ተነቃናቂ ሕብረተሰብ መሆናችን ሁሉ በእርግጥም ባልታሰሰ አዲስ ቀጠና ውሰጥ መግባታችንን የሚያሳዩ ናቸው።

አገራችን ያለችበት ይህ ወቅታዊ ሁኔታ ከዚህ ቀደም ያልነበሩ ብዙ መልካምና አስፈሪ ጉዳዮች ተደባልቀው የሚገኙበትና ላይ ላዩን ሲያዩት ቀላል የሚመስል ግን እጅግ ከባድና የተወሳሰበ ሁኔታ ነው። በኪራይ ሰብሣቢነት የተሳከረውን ባለሀብትና የራሱን ጥያቄዎች ይዞ መነሳት የጀመረውን መካከለኛ መደብ ቀና መንገድ ማስያዝ ከባድጥረትና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ፈተና ሆኗል። በዚህ ላይ ይህችን እያደገ የሚሔድ ገበያና ድልብ ጸጋዎች ያሉዋት አገር ተቆጣጥረው ሊያልቡ ያሰፈሰፉት የውጭ ባለሀብቶችና የድንበር የለሽ ኩባንያዎች ፍላጐት ሲታከልበት አገራዊ ፈተናው በእጅጉ የበዛ ይሆናል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ከራሱ ከኢህአዴግ ጀምሮ ከብዙዎች ግምት ባሻገር በተለወጠው አገራዊ ሁኔታ ወደአዲስና ውስብስብ መድረክ መግባታችንን የሚያረጋግጥ ነው። ከዚህ በመነሳት በቅድሚያ "ያልታሰሰ ቀጠና" ወደሚባለው መድረክ ያስገባንን ፈጣን ዕድገትና ተፅዕኖውን መመልከት አስፈላጊ ይሆናል። ፈጣኑ ዕድገት በራሱ በተወሰነ ደረጃ የመፍትሔ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ያልተገመቱ ችግሮች ምንጭ ሆኗልና።

ባለፉት ጥቂት አሥርት ዓመታት እንደቻይና የመሳሰሉ ለፈጣን ዕድገት የበቁ አገሮች በዓለማችን መነሳት ሲጀምሩ የገበያ አክራሪዎች "የዕድገቱን ፍጥነት መግታት ወይም በለወጠ

ላይ ልጓም ማስገባት እንደመፍትሔ መታየት አለበት" ሲሉ መስማት የተለመደ ነበር። ከቻይና ፈጣን ዕድገት ጋር ተያይዞ ችግር በተከሰተ ቁጥር የአገራቱ መሪዎች ፍጥነታቸውን እንዲቀንሱና ፍሬን እንዲይዙ ያልመከሩበት፣ ቻይናም ለዚህ አጓጉል ምክር ጆሮ ዳባ ልበስ ያላለችበት ጊዜ አልነበረም። በዚህ ጽሁፍም ፈጣኑ ዕድገት ያልተገመተ የፈተና ምንጭ ሆኗል ሲባል የዕድገታችንን ፍሬን መያዝ አለብን የሚል ብሽቦታ በመያዝ አይደለም። ይልቁንም በእኛም አገር እንደቻይና ፈጣኑ ዕድገት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ከድኅነት ጋር ለረዥም ጊዜ አብሮ መቆየት ወደከሰመ መንግሥት /Failed State/ የሚያሸጋግር በመሆኑ ከድኅነት ጋር በፍጥነት መፋታት አማራጭ የለውም። ስለዚህም ስለፈጣኑ ዕድገት ያልተገመተ ተዕዕኖ ሲነሳ ይህንኑ እናቀዝቅዝ ለማለት አይደለም። ችግሩ ሌላ ገጽታ ያለው በመሆኑ ይህንኑ በትክክል መገንዘብና መፍታት ይጠይቃል።

ፈጣን ዕድገትና የነበረውን እንዳልነበረ አድርጐ የሚገለባብጥ የለውጥ ጉዞ የሚያስከትለው ፈተና ምን እንደሆነ በትክክል ለመገንዘብ፣ ጆሴፍ ስቲግሊዝ በዚህ ጉዳይ ላይ የተናገረውን መነሻ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ዘመን ተሻጋሪው የካርል ፖላኒ "The Great Transformation" መጽሐፍ በድጋሚ ሲታተም ስቲግሊዝ በጻፈው መግቢያ ላይ፣ "ፈጣን ለውጥና ትራንስፎርሜሽን፣ በአንድ በኩል ነባር የችግር መፍቻ መንገዶችንና የቆዩ የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓቶችን ያፈራርሳል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ችግርን የመቋቋሚያ አዳዲስ መንገዶችና ሥልቶች ሳይቀየሱ በርካታ አዳዲስ ፍላጐቶችን ወይም ጥያቄዎችን ይቀሰቅሳል።"[65] ይላል።

በርግጥም ፈጣንና መሠረተ-ሰፊ ለውጥ በተቀሰቀሰበት ሕብረተሰብ አሮጌው የችግር መፍቻ ልማድና ተቋማዊ ሁኔታ በቅጽበት ይፈራርሳል። በአካያው ተኪውን ተቋማዊ ሥርዓት መገንባት ደግሞ የራሱን ረጅም ጊዜ ይወስዳል። በዚህ መሐል የማያቋርጥ አዳዲስ ሕብረተሰባዊ ፍላጐትና ጥያቄ ይቀሰቀሳል። የአገራችን አርሶ አደር "የፊተኛው አልቆ የኋለኛው ርቆ" እንደሚለው፣ ፈጣን ለውጥ ውስጥ የገቡ አገሮች የቆየው የችግር መፍቻ ሥልት በጠፋበትና አዲሱም ባልደረሰበት ሁኔታ በተቀሰቀሰ አዳዲስ ፍላጐቶች የተወጠሩ ይሆናሉ። ይህ ፈጣን ለውጥን ተከትሎ በማንኛውም ሕብረተሰብ ሊከሰት የሚችልና በአብዛኛው አይቀሬ የሆነ ከስተት ነው። በኢትዮጵያም ከዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም።

በኢትዮጵያ የሚካሔደው ለውጥ ፈጣን ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም ሰፊ ሽፋን ያለው ነው። ለውጡ ገጠሮችን ትቶ በከተሞች ብቻ የታጠረ አይደለም። ይልቁንም ማዕከሉ ገጠር ነው። አርሶ አደር ብቻ ሳይሆን፣ አርብቶ አደር የሚኖርባቸውና በተለምዶ ቸል የሚባሉ አካባቢዎች ጭምር በለውጡ ማዕበል ውስጥ ገብተዋል። በኢትዮጵያ የማይለወጥ ነገር የለም። የማይለወጥ የገጠር ቀበሌ፣ የማይለወጥ ከተማና ፈርሶ የማይገነባ ከፍለ ከተማ የለም።

በአንድ ጊዜ አሥርና አሥራ አምስት ዩኒቨርሲቲዎችና ሃያ ሠላሳ ሆስፒታሎች ይገነባሉ፡፡ ሁለት ሺህ ጤና ጣቢያዎች በተጀመሩ በጥቂት ዓመታት ዳር ይደርሳሉ፡፡ የባቡር መሠረተ-ልማት በተቀመጠ ማግሥት ግንባታው መጧጧፍ ይጀምራል፡፡ ከዕድገቱ ጋር የማይሔዱ መሠረተ-ልማቶች በአዳዲስና ቀጣዩን በሚሸከሙ መሠረተ-ልማቶች ይተካሉ፡፡ ጠባብ መንገዶች ፈርሰው ሰፋፊ አውራ ጐዳናዎች ይገነባሉ፡፡ በኤሪክሰን የተተከሉ ጠባብ የስልክ መሥመሮች፣ ዜድቲኢ በተከላቸው ሰፍተዋል በተባለ ማግሥት፣ ይህም እንደገና በሌላ መተካቱ አማራጭ የሌለው ይሆናል፡፡ ከ132 ኬቪ ወደ220 ኬቪ ብቻ ሳይሆን፣ ወደአራትና አምስት መቶ ኬቪ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መሥመሮች ሽግግር የሚደረግበት፣ ያለፉት መንግሥታት የገነቡዋቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ ራሱ ኢህአዴግ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የገነባቸው መሠረተ-ልማቶች ከዕድገቱ ጋር የተቀሰቀሰውን ፍላጐት የማይሸከሙ በመሆናቸው በቀጣይነት እንዲሻሻሉ ወይም እንዲሰፉ ይደረጋል፡፡ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ጨምሮ ኢትዮጵያ ከማንም ግምት ውጭ ከባድ ግንባታ ከሚካሔድባቸው የዓለም አገሮች አንዷ የሆነችባቸው አዳዲስ የሜጋ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በመሆን ላይ ናቸው፡፡ በርግጥም ነገሮች በፍጥነት ብቻ ሳይሆን፣ ለግምት በሚያስቸግር ስፋትና ፍጥነት የሚገለባበጡበት ሂደት የዕለት ተዕለት ክስተት ከሆነ ሰነባበቷል፡፡ ይህ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ እውነታ ነው፡፡

ይህን በመሰለ ፍጥነት ካልተሠራ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ አገር መሆን አይቻልም። ስለሆነም አቅም ቢገኝ ኖሮ የተጀመረው ግንባታ ከዚህም በላይ እንዲሔድ ቢደረግ ተገቢ ይሆናል። ነገር ግን መሥራት የሚቻለው ባለውና ተፈጥሮ በቆየው አቅም ብቻ ነው፡፡ ይህም ሆኖ መካሔድ ባለበት ሰፊ፣ ፈጣንና መሠረታዊ ለውጥና ይህን ለመምራት በሚያስፈልገው ብቃት ያለው የሰው ኃይል አቅርቦት መካከል ከባድ አለመመጣጠን ተከስቷል፡፡ ተቋማት እንደ እንጉዳይ በመፍላት ላይ ቢሆኑም፣ እነዚህን ብቃት ባለው የሰው ኃይል የመሙላት ጉዳይ ከባድ ዳገት መሆን ጀምሯል፡፡ አዳዲስ ከተሞች እየተፈጠሩ፣ ነባሮችም ወርድና ቁመታቸው ሲጨምር የሚቀሰቀሰውን ብቁ የሰው ኃይል ማቅረብ ፍላጐት ማሟላት ፈታኝ ሆኗል፡፡ ማዘጋጃ ቤቶችን፣ የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የቴሌ፣ የባንክ አገልግሎቶችን ደረጃውን በጠበቀ ታዳጊ አኳኋን ለማቅረብና የህዝብን እርካታ ለማረጋገጥ የሚያስችል አመራር የማሟላት ጉዳይ መንግሥትና ሕብረተሰብን የሚፈትን ሆኗል፡፡ ማስፋፋት የተቻለውን አገልግሎት ጥራቱን አሟልቶ እንኳ ባይሆን፣ ተስፋ የሚሰጥ መሻሻል መኖሩን በሚያመላክት ደረጃ መስጠት አስቸጋሪ እየሆነ የመጣውም ከዕድገቱ ጋር የሚመጥን ብቁ የሰው ኃይል አቅርቦት ባለመሟላቱ ነው፡፡ የአገሪቱ ጥራት ያለው የሰው ኃይል ፍላጐት ሰማይ ወጥቶ፣ አቅርቦቱ በዚያው ፍጥነትና መጠን አላደገም፡፡ በዚህ የተነሳ ጥራት ያለው የሰው ኃይል የሚፈልጉ ክፍት ቦታዎችን እንደነገሩ በሆነ የሰው ኃይል መሙላት ተበራክቷል፡፡

ድርጅቱና መንግሥት ይህን አሳሳቢ ውሱንነት በመገንዘብ ሰፊ ሥልጠና ከመስጠት አልቦዘኑም፡፡ ከፍተኛ ትምሕርትን ለማስፋፋት ልዩ ትኩረት ሰጥተው የተንቀሳቀሱትም ቀጣዩን ዕድገት የሚሸከም የአመራር አቅም ለመፍጠር ነበር፡፡ ይሁንና በመደበኛ ትምሕርትና በአመራር ማሠልጠኛ ተቋማት እየተመረቁ ሥራ የሚይዙ ወይም የሚመደቡ ወጣት ምሁራን ቁጥር በእጅጉ የጨመረ ቢሆንም፣ የአገልግሎት ጥራቱን ከፈጣኑ ዕድገት ጋር የተመጣጠነ እነዲሆን ለማድረግ ፈታኝ መሆኑ አልቀረም፡፡ ድርጅቱና መንግሥት በልማታዊ አስተሳሰብ የታጠቀ፣ በዲሲፕሊን የዳበረና ብቃት ያለው አመራር በመፍጠር ረገድ በነበረባቸው መሠረታዊ ውሱንነት ከአዲሱ መድረክ ጋር የሚመጣጠን የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ ሳይገነቡ ቆይተዋል። ይልቁንም በአልባሌ መስፈርት እየተመለመለ የፓርቲውን ሰልፍ የተቀላቀለ ኃይል እርስ በርስ እየተጓተተ ከዚህ ዝንባሌ ለመላቀቅ አለመቻሉ ይህን የአመራር ከፍተት የሚያባብስ ሆኗል፡፡

በዚህ የአመራር ከፍተት የተነሳ በዲሲፕሊኑ ብቻ ሳይሆን በመወሰን ችሎታው የሚታወቀው የቆየ ተቋም፣ ዲሲፕሊኑ የላላና ውሳኔ የሚሰጥ የጠፋበት ተቋም ወደመሆን ተሸጋግሯል፡፡ "አትቁም ያሉት 'ለማኝ' ከሰጡት ቁጥር ነው" በሚል ብሂል ለሚያምነው ህዝብ፤ "አይሆንም" ወይም "አይገባህም" የሚል ውሳኔ ሊሰጠው የተዘጋጀ የሰው ኃይል በቁጥሩ ተመናምኗል፡፡ ፈጣንና ትክክለኛ ውሳኔ የሚሰጥ ሰው በመጥፋቱ በየቢሮው መንከራተት የዕለት ተ'ለት ሥራ ሆኗል፡፡ በዚህ ዓይነት ባሳለፈው ውሳኔ ደፍሮ ለመጠየቅ የተዘጋጀ ኃይል ሲጠፋ ቁጥጥርና ተጠያቂነትም አብሮ ይዳከማል፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ በየመንደሩ ያሻቸውን የሚያደርጉ ሰዎች መፈጠር ይጀምራሉ፡፡ ይህም ህዝቡን በእጅጉ እንዲማረር አድርጐታል፡፡ ታዳጊውን የህዝብ ፍላጐት ማርካት አስቸጋሪ እየሆነ የመጣው ፈጣኑ ዕድገት ባስከተለው የሰው ኃይል ፍላጐትና በአቅርቦቱ መካከል ይህን የመሰለ ትልቅ ከፍተት በመፈጠሩ ጭምር ነው።

ከፈጣን ዕድገት ጋር ተያይዞ ቁጥጥርና ተጠያቂነትን ጨርሶ እያደበዘዘ ያለ ይህን መሳይ ሁኔታ በሽግግር ውስጥ የሚያልፉ ማኅበረሰቦችን ሁሉ የሚፈትን ነው፡፡ በአንድ ወቅት ቻይና በዚሁ መልክ ችግሮች አጋጥመዋት ነበር፡፡ ቻይና የለውጥና ተሃድሶ ሂደቱን በጀመረች በጥቂት ዓመታት በተለይ ለውጡ በተቀሰቀሰባቸው የአገሪቱ ምሥራቃዊ ክፍሎች ከማዕከላዊ መንግሥቱ ቁጥጥር ውጭ መሆን የጀመሩ ክፍለ አገሮች መበራከት ጀምረው ነበር፡፡ ሻንግሐይ፣ ቾንችንግና ጓንዡን የመሳሰሉ ከተሞች ከቤንጅንግ የማይተናነስ ብቻ ሳይሆን፣ የበለጠ ጡንቻ አለን በሚሉ ሰዎች ተሞልተው ነበር። በወቅቱ ቻይናን የታዘቡ ሁሉ አገሪቱ በዘመናዊ የጦር አበጋዞች መዳፍ ሥር ትወድቅ ይሆናል ብለው እስከመተንበይ ደርሰው ነበር፡፡ ነገር ግን በቻይና አገራዊና ብሔራዊ ጥቅሙን በትክክል የሚያውቅና የጠንካራ መንግሥት አንድ መለያ ልማታዊ ቁርጠኝነትና ዲሲፕሊን እንጅ መልፈስፈስ እንዳልሆነ የተገነዘበ መንግሥት ስለነበር አገሪቱ ይህን ጊዜያዊ ከስተት ፈጥና ተሻግራዋለች፡፡ በቻይና ፈጣን ዕድገት አሮጊውን ንዶ፣ አዲሱን ቅጽበታዊ

በሆነ መንገድ መትከል አስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም፤ መንግሥትና ፓርቲው የአደጋውን ግዝፈተና አሳሳቢነት ተገንዝበው በመረባረባቸው ሥጋቱን ለመቅረፍ ችለዋል።

በኢትዮጵያ ፈጣን የለውጥ ሂደትም አሮጌውን ነቅሎ በአዲስ ለመተካት ጊዜ መውሰዱ የራሱን ጣጣ ይዞ መጥቷል። እናም በአመራርና በሕብረተሰብ ደረጃ ከፈጣን ለውጥ ጋር ተያይዞ ጥራት መስዋዕት ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ ከተቻለ፣ አደጋውን ፊት ለፊት እያዩ እንጅ እንደ ሰጐን ራስን በአሸዋ ውስጥ ቀብሮ ማለፍ እንደማይቻል መግባባት ከተፈጠረና በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ከተጀመረ ይህን ችግር መቅረፍ ያዳግታል ሊባል አይችልም። ለዝቅተኛ አፈጻጸም፣ ለመናኛ ብቃትና ለኪራይ ሰብሣቢነት ዜሮ ታጋሽነት በማሳየት ከፈጣን ለውጥ ጋር ተያይዞ የሚመጣው ችግር ቀላል ባይሆንም፣ መፈታት የማይችል ግን አይደለም። በዚህ ችግር አፈታት ዙሪያ ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣትም ቁልፉ ጉዳይ አመራር ነው። በአመራር ደረጃ ነባሮችን ቀድሞና አርቆ በመመልከት እንዲሁም ያሉትን ችግሮች በመፈተሽና በመፍትሔያቸው ላይ የተሟላ መግባባት በመያዝ፣ ጅምሩን ለውጥ አጐልብቶ ዳር ለማድረስ ይቻላል። ፈጣኑ ለውጥም በራሱ ባሕርይ የተነሳ የሚፈጥራቸውን ችግሮች ለመቅረፍ አማራጭ የማይገኝለት ይሆናል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይ እንዲህ እንደእኛ አገር ከዝቅተኛ ደረጃ ወደበለጸገ ሕብረተሰብ በፍጥነት መሸጋገር በጀመሩ ማኅበረሰቦች ሊላም ተግዳሮት ያጋጥማል። ይህም ከሸማግር ማኅበረሰቦች ባህርይ ጋር የተቆራኘ ነው። የሸማግር ማኅበረሰቦች በአንድ በኩል ከትላንት የተወረሱና መቀየር ያለባቸው ብዙ ያረጁ ያፈጁ ነገሮችን ይይዛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሊፋፉ የሚችሉና የሚገባቸው የቆዩና አዳዲስ መልካም ባሕርያትና ገጽታዎችም አሉዋቸው። ሁለቱ አንድ ላይና ጐን ለጐን ይኖራሉ። በእነዚህ ማኅበረሰቦች አዲሱ ማሸነፍ ቢጀምርም ሙሉ በሙሉ የበላይነቱን አላረጋገጠም። አሮጌው ደግሞ ቢሸነፍም ሙሉ በሙሉ አልተወገደም። በመሆኑም አዲሱ መሉ በሙሉ የበላይነቱን ለመጐናጸፍ፣ አሮጌው ደግሞ ጨርሶ ላለመሞት ሰሉ በመካከላቸው ቀጣይና ከባድ ፍልሚያ ያካሂዳሉ። በመሆኑም የሸግግር ወቅት ማኅበረሰቦች የአሮጌውንና የአዲሱን ሥርዓት ባሕርያት አዳብለው የያዙ መሆናቸው ራሱን የቻለ ፈተና ይደቅንባቸዋል። ይህ በለውጥ ሂደት ውስጥ በገቡ አገሮች ሁሉ የታየ ነው።

በዚህ የተነሳ በሸግግር ማኅበረሰቦች ዘንድ ወደፊት መራመድና ወደኋላ መመለስ ይከሰታል። የለውጥ ፈላጊው ወገን የኃይል ሚዛን የላቀ ሲሆን፣ ወደፊት መራመድ የጀመረው ሂደት ተጠናክሮ ይቀጥላል። በአንጻሩ የአሮጌው ሥርዓት ወኪሎች ጡንቻ ሲጠነክር ደግሞ ወደኋላ መመለስ ይከሰታል። ወደኋላ የመመለሱ ጉዳይ ትላንት ከታለፈው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በፍፁም ተመሳሳይነት የሚከሰት ባይሆንም፣ በሕብረተሰቡ የለውጥ ጉዞ መደነቃቀፍ መልክ መከሰቱ ግን አይቀርም። በትላንትና በነገ ኃይሎች መካከል የሚካሔደው የዚህ ፍልሚያ ውጤት የሚወሰነው በመካከላቸው ባለው የኃይል ሚዛን ነው። ስለዚህም ማኅበረሰቦቹ

ከባድና የተወሳሰቡ ናቸው። ያለማቋረጥ ወደፊት ለመራመድ ደግሞ ብቃት ያለው አመራር የግድ የሚሉ ናቸው።

ብቃት ያለው አመራር ሲኖር፣ የአዲሱንና የታዳጊውን አቅም የሚገነቡ አቅጣጫዎችን ተልሞ ለውጡ ያለማቋረጥ እንዲፈጸም ያደርጋል። ትግሉ በሚያልፍባቸው መንገዶች ሁሉ የተሟላ የሁኔታዎች ትንተና በማካሄድ ብቁ ስትራቴጂና ስልቶችን እየነደፈ ለአፍታም ሳይዘናጋ ታግሎ ያታግላል። ስለዚህም የሽግግር ማኅበረሰብን የሚመራ አንድ የለውጥ ኃይል፣ ይህን ውስብስብና እጅግ በጣም በቀላሉ ለአደጋ ሊጋለጥ የሚችል ሂደት የመምራት ብቃት የተጐናጸፈ ሊሆን ይገባዋል።

ከሽግግር ማኅበረሰቦች መሠረታዊ ባሕርይ የሚመነጨው ይህ የትግል ሁኔታ፣ ለብቁ አመራር ፍላጐት አንድ መነሻ ቢሆንም ብቸኛው ግን አይደለም። የሽግግር ማኅበረሰቦች አብዛኛውን ጊዜ ከትንሽ ወደትልቅ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ የሚሸጋገሩ ናቸው። ትግሉ በተሳካ ቁጥር የሚገባበት አዳዲስ መድረክ ሌላ ሰፋፊና የተወሳሰበ ችግር ወይም ጥያቄ የማይለየው ያልታሠሠ ቀጠና ይሆናል። በመሆኑም ያለ ብቁ አመራር እየተወሳሰበ የሚሄደውን የለውጥ ጉዞ በትክክል ለመምራት አይቻልም። በዚያው ልክ ደግሞ የዕድገት መገታት መከሰቱ አይቀሬ ይሆናል። መለስ ደጋግሞ ይለው እንደነበረው "በቀላሉ የሚሸመጠጡት ፍሬዎች /The low hanging fruits/ በተለቀሙ ቁጥር ቀጣዩ ሥራ እየከበደና እየተወሳሰበ" ይሔዳል። በዚያው ልክ ደግሞ ከአመራር የሚጠበቀው ብቃትም ከፍ ይላል። ይህ በአገራችን ንድፈ-ሀሳባዊ ወይም መላምታዊ በሆነ መንገድ የሚደረስበት የነገ ችግር ሳይሆን ዛሬ ዛሬ ወጥሮ የያዘን በአመራር ብቃት መጓደልና የላቀ ብቃት በሚጠይቀው አገራዊ ሁኔታ መካከል ባለው ተቃርኖ መልክ የሚገለጽ ተጨባጭ ችግር ሆኗል።

በሽግግር ማኅበረሰቦች ዘንድ ታዳጊ ብቃት ያለው አመራር የሚጠይቀው ሌላው ሁኔታ፣ የነገውን ማኅበረሰብ ለመቅረጽ በርካታ አማራጮች ከፊት ለፊት የሚደቀኑና ከእነዚህም መካከል ትክክለኛውን በጥንቃቄ መምረጥ የሚያስፈልግ መሆኑ ነው። የሚካሔደው ትግልም በዛሬና በትላንት ኃይሎች መካከል ብቻ የተገደበ አይደለም። የነገው ማኅበረሰብ፣ "ለማን ጥቅም? በየትኛው አቅጣጫ ይገንባ?" የሚለው ጉዳይ ብዙ አማላይ አማራጮች የሚቀርቡበትና ትግልም የሚጠይቅ ነው። በተለይ ከኋላ ቀርነት ወደዕድገት፣ ከቅድመ ካፒታሊዝም ወደተሟላ የገበያ ሥርዓት በሚካሄደው ሽግግር ለውጡ ስቃይ የበዛበትና ዋጋም የሚያስከፍል በመሆኑ መድረኩ ከባድ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው በመስኩ ጥናት ባደረጉ ሶሻል ሳይንቲስቶች በውል የተረጋገጠ ነው። ይህን በማስመልከት ኤድዋርድ ፍሬድማንና ጀምስ ሲ.ስኮት ለባሪንግተን መ·ር መጽሐፍ ባበረከቱት መግቢያ ላይ፣

"ዕድገት (Progress) በማይቀርና ልዩነት በሌለው ሁኔታ በሰው ልጆች ላይ ከባድ ስቃይን ያስከትላል። ይህ ፈጽሞ የማይቀርልን በመሆኑ ከገበያ ኢኮኖሚና የፓርላማ ሥርዓቱ ምድራዊ ገነትን የሚሰብኩም ሆነ የሚጠብቁ ሰዎች ካሉ እጅግ የዋሆች ብቻ መሆን አለባቸው። ይህን በመሰለው የለውጥ ሂደት መቅረብ ያለበት ዋነኛ ጥያቄ ወደዕድገት በሚደረገው የሽግግር ጉዞ ከባዱን ሸክም የሚሸከመውና ዋጋም የሚከፍለው የትኛው የሕብረተሰብ ከፍል ነው የሚለው ጉዳይ ነው።"[66] ይላሉ።

ይህ ከሩብ ምእተ ዓመት በላይ በአገራችን ውስጥ በተካሄደውና ዛሬም በመካሄድ ላይ ባለው ለውጥ የታየ ነው። ወደገበያ ኢኮኖሚ በሚደረገው ሽግግር መሬትን ከአርሶ አደሩ እጅ ለማውጣትና በእጁ አቆይቶ እርሱን ተጠቃሚ እያደረጉ ለማሳደግ የተካሄደው ትግል የዚህ ማረጋገጫ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል። በዛሬዋ ኢትዮጵያ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመርና በኒዮ-ሊበራሊዝም መካከል የሚካሔደውም ትግል እዚያው በዚያው የአገሪቱን መጻኢ ዕድልና ለውጡ በማን ጉዳትና በማን ተጠቃሚነት ይካሄዳል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ለመወሰን የሚካሔድ ነው። በይፋም ሆነ በስውር፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቀነቀኑ ኒዮ-ሊበራል አስተሳሰቦች፣ አገሪቱ ለድንበር የለሽ ኩባንያዎች ጥቅም ተገዥ እንድትሆን ይዳርጓታል። በዚህ ውስጥ በፈረንጅ አምላኪነት ተሰልፈው ትርፍራፊ በማግኘት የሚጠቀሙ የአገር ልጆች ባይታጡም፣ ማንኛውም የኒዮ-ሊበራል ፖሊሲ ሄዶ ሄዶ የርዕዮቱን ባላባቶች ዋነኛ ተጠቃሚ ከማድረግ ውጭ ሊሆን አይችልምና። ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በፋንታው ህዝቡንና አገሪቱን ተጠቃሚ ለማድረግ አልሞ የተነሳ ነው። ስለሆነም የነገን ዕድል ለመወሰን እነዚህን በመሳሰሉ አማራጮች መካከል የሚካሔደውን ትግል በብስለት መምራት የሚችል ብቃት ያለው አመራር አማራጭ የሌለው ይሆናል። ይልቁንም እንደኢትዮጵያ በመሰሉ ጅምርና ተስፋ የፈነጠቀ ለውጥ በሚካሔድባቸው አገሮች፣ ዋናው ፈተና የትላንቱ ሳይሆን፣ የዛሬና የነገ ዕድልን ከመወሰን ጋር የተያያዘው ነው። ይህ ደግሞ ብቃት ያለውን አመራር ተፈላጊነት ከመቸውም ጊዜ በላይ ጉልህ ያደርገዋል።

በአመራር ኃላፊነት ላይ የተቀመጡ ሰዎችን አንዳንድ ጊዜ የአጭር ጊዜ ጥቅም ኖሯቸው በዘላቂነት ግን ሕብረተሰብን የሚጐዱ አስተሳሰቦች ያጋጥሟቸዋል። በአጭር ጊዜ ፋይዳቸው አማላይ የሆኑት እነዚህ ሀሳቦች በጥልቀት የማይፈተሹ ከሆነ፣ ወይም ደግሞ ዘላቂ ጥቅምና ጉዳታቸውን በብቃት ለመመዘን ካልተቻለ፣ ብዙዎችን እስከማደናገር ሊደርሱ ይችላሉ። ብቃት ያለው አመራር ለጊዜው የሚያማልሉ አስተሳሰቦች ወጥመድ እንዳይጠልፈው፣ ከምንም ነገር በፊት የእያንዳንዱን ሀሳብ ወይም የፖሊሲ አማራጭ ዘላቂ አዋጭነት በጥልቀት መፈተሽና

ማሀበራዊ ይገባዋል። "የሚያብረቀርቀው ሁሉ ወርቁ አይደለም" እንዲሉ፣ ሐሳቦቹን ከረጅም ጊዜ ህዝባዊና አገራዊ ፋይዳቸው በመነሳት መፈተሽ ይገባዋል። ይህ ሲሆን ሁሉም የአመራር ብቃት ከጅምሩ ተሟልቷል ማለት ባይቻል እንኳ፣ በሂደት የሚገነባ ብቃት እንደሚኖር መተማመን ይቻላል።

በተወሳሰበው መድረክ ውስጥ አገርና ህዝብን ይዞ በስኬት ለማለፍ የሚችል አመራር በጣም መሠረታዊ ሊባሉ የሚችሉ ብቃቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል። ከምንም ነገር በፊት የትንታኔው መነሻና መድረሻውን የኢትዮጵያና የህዝቦቿ መሠረታዊ መብቶችና ጥቅሞች ሊሆኑ ይገባል። ሁሌም ከእነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች እየተነሳ ፈጣን ተለዋዋጭነት የሚታይበትን አገራዊና ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለማዊ ሁኔታና በየጊዜው የሚከሰቱ አዳዲስ ሁኔታዎችን በጥልቀት መተንተንና መገንዘብ ይገባዋል። የነገሮችን አዝማሚያ በቅርብ እየተከታተለ እነዚህ ለአገራችንና ለህዝባችን ያላቸውን ትርጉም በመለየት መብትና ጥቅሞቻችንን ለማስፋት የሚያስችሉ ትክክለኛ ስትራቴጂና ሥልቶችን መቀየስ አለበት። በዚህ ላይ የተመሠረተ የጋራ መግባባት ፈጥሮ መላውን ሕብረተሰብ ማንቀሳቀስም የግድ ይለዋል። ይህ ከማንኛውም ዓይነት ታካችነት ወይም የሉበ ሉበ ሥራ ነጻ በሆነና በከፍተኛ የኃላፊነት መንፈስ መከናወን ያለበት ነው። ብቃት ያለው አመራር በስንፍናም ሆነ በማንኛውም ዓይነት ላይ ላዩን የመጋለብ አዝማሚያ፣ ወይም ደግሞ አጉል ተወዳጅነትን ለማትረፍ አስቦ በመንቀሳቀስና ለዚህ የሚበጁ ወቅታዊ ችግሮችን እያነሱ በፌስቡከና በትዊተር በመጋለብም ሊሟላ የሚችል አይደለም። እነዚህ መንገዶች እንኳን በእኛ በታላቋ አሜሪካንም እንዳልሠሩ የፐሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የትዊተር መልዕክቶች የሚፈጥሩትን ቀውስ በመመልከት መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አመራሩ መልካም ባህርያትን የተላበሰ ሊሆን ይገባዋል። ትሁትነት፣ ሐቀኝነትና ከራስ ወዳድነት መታቀብ ይገባዋል። ጠንካራ የመማር ሥነ-ልቦና ማዳበር፣ ስንፍናን ማስወገድና አቅም በፈቀደ ሥራን አጥርቶ መሥራት፣ ችግሮችን ፈልፍሎ ማውጣትና መፍታት፣ ብቃት ያላቸውን ሰዎች ለይቶ ማሰባሰብና ማሠራት፣ ሁሉንም እኩል መመልከትና ከአድሎና ፍርሐት የጸዳ አገልግሎት መስጠት በመጨረሻም ራስን ከአፋሽ አጎንባሾች መጠበቅና ኃላፊነትን መውሰድ የሚያስችሉ ባህርያትን ማዳበር ይገባዋል።

እነዚህ ባሕርያት ለማንም ሳይሆን፣ የተጀመረው ለውጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሲባል የግድ መሟላት ያለባቸው ናቸው። ይህም ሆኖ እነዚህ ብቃቶች ከትግልና በአግባቡ ታስቦበት ከሚካሔድ ግንባታ ውጭ የሚሟሉ አይደሉም። በእኛ ተጨባጭ ሁኔታ ትግሉን ከድል ወደድል ለማረማመድ የተቻለው፣ ለየመድረኩ የሚመጥን ብቃት ያለው አመራር ለመፍጠር በዚህ አቅጣጫ ከባድ ርብርብ ሲደረግ የቆየ በመሆኑ ነው። ስለዚህም በተነጻጻሪ እያንዳንዱ የትግል መድረክ የሚጠይቀውን ብቁ አመራር ለማረጋገጥ የሚያስችል የሰው ኃይል ለመፍጠር

ተተሎ ቆይቷል፡፡ አሁንም ይህንኑ አበዘተሠበ ደረዳ ሎግዘዞበል ፑ ፈያበቦል ሀኤል ያለ ቢሆን፣ በዚህ ረገድ ያሉ ችግሮችና ፍላጐቶች ግን ቀጣዩን የአመራር ግንባታ ጥረት ይበልጥ አሳሳቢና ትኩረት የሚሻ እንዲሆን አድርገውታል፡፡ በተለይ ከፈጣኑ ዕድገት ጋር ተያይዞ ወደ አዲስና ያልታሠሠ ቀጠና የገባ የሸግግር ማኅበረሰብ መፍጠራችን የአዲሱ ሥርዓት ፈተና ሆኗል የሚባለው በዚህ ሁሉ የተነሳ ነው። ከፖለቲካ አኳያ በዚህ መድረክ አገራችንን የገጠሟት ዋና ዋና ተግዳሮቶች የላይኞቹ ሲሆኑ ከእነዚህ የማይተናነሱ የኢኮኖሚ ፈተናዎችም ተደቅነውባታል። ከእነዚህ አንዳንዶቹ ቀደም ሲልም የተገመቱ፣ የቀሩት ደግሞ ባልታሠሠ አዲስ ቀጠና ውስጥ መግባት ስንጀምር የተከሰቱና አስቀድሞ ያልተገመቱ ፈተናዎች ናቸው። እያንዳንዳቸውን ዘርዘር አድርጐ መመልከት ይህን ያሳያል።

ምዕራፍ ዘጠኝ፣

ልማታዊ መንግሥታትን የፈተኑ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ሁሉ ኢትዮጵያንም...፣

ኢትዮጵያ በየዘመኑ ከደረሰችበት የዕድገት ደረጃ ጋር የተያያዙ በርካታ ፈተናዎችን ያስተናገደች አገር ነች፡፡ ለገናና ሥልጣኔ ስትበቃም ሆነ ስታሽቆልቁል ከገባችበት የዕድገት ምዕራፍ የሚመነጩ በርካታ ፈተናዎች ገጥመዋታል፡፡ ዛሬም ቢሆን እንደዚሁ ነው፡፡ አገሪቱ በፈጣን የዕድገት ጎዳና መራመድ የጀመረች ብትሆንም፣ በዚሁ የተነሳና ከዚህም ለሚፈልቁ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች መጋለጧ አልቀረም፡፡

የተጀመረው ፈጣን የዕድገት ጉዞ መሐንዲስ የስድሣዎቹና የሰባዎቹ ትውልድ ቅጥያ የሆነው ኢህአዴግና ልማታዊ መንግሥቱ ናቸው፡፡ ስለዚህም ደግሞ በዚህ የዕድገት ደረጃ ፖርቲውንና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥቱን የሚገጥሟቸው ፈተናዎች የሥርዓቱ ዋነኛ ተግዳሮቶች መሆናቸው አይቀርም፡፡ ይህን የመሰለው ችግር ለኢትዮጵያ አዲስ ቢሆንም፣ ከሞላ ጐደል በተመሳሳይ ፈለግ ለመራመድ የሞከሩ አገሮችና መንግሥታትን በመላው ዓለም ያጋጠመ ነበር፡፡ ስለዚህም አዲስ ግኝት ፍለጋ መኳተን ሳይጠይቅ፣ ልማታዊ መንግሥታትን ካጋጠሟቸው ፈተናዎች በመጀመር ነገርየውን መፈተሽና ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ መመልከት የተሻለ ይሆናል፡፡

የልማታዊ መንግሥታት ባሕርያት ናቸው በመባል የሚነሱ በርካታ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም፣ ብዙዎች በሦስት መሠረታዊ ባሕርያት ላይ እንደሚስማሙ መለስ በልዩ ልዩ ጽሁፎቹ[67] ላይ ያስቀመጠውን እንደ መነሻ መውሰድ ተመራጭ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ልማትን የሞት የሽረት ጉዳይ ማድረግ፣ ወይም ልማታዊ ቁርጠኝነትና ዲሲፕሊን ያለው መንግሥት መሆን ነው፡፡ ሁለተኛው መንግሥት ራሱን ከባለሀብቱና ከራሱ ውስጥ ሊፈልቁ ከሚችሉ የጥቅም ቡድኖች ነጻነቱን የማስጠበቅ ዲሲፕሊንና ብቃት ማዳበርና በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ በሕብረተሰብ ደረጃ የልማታዊ አስተሳሰብ ልእልና እንዲፈጠር የማድረግ ችሎታ ያለው መንግሥት መሆን ናቸው፡፡

እነዚህን ባሕርያት የተላበሰ መንግሥት የፈጠሩ አገሮች ሁሉ፤ አልሚዎችን የመደገፍና የመገንባት፣ ኪራይ ሰብሣቢዎችን ደግሞ የማከሰም ተልዕኮውን በብቃት በመፈጸም፣ ሕብረተሰብን ለዘላቂ ልማትና ለዴሞክራሲ ማብቃት ተችሏል፡፡ ለውጡን የሚመራው ፖርቲና መንግሥት እንደ ኢህአዴግ ከጅምሩ ዴሞክራሲያዊ ከሆኑ፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጉዳይ ከልማቱም ቀድሞ ተጀምሮ ጥሩ መሠረት የተጣለበት ሊሆን ይችላል፡፡ በኮሪያም ሆነ በታይዋን እንደታየው ዴሞክራሲ ከአርባ ዓመታት ልማታዊ ጉዞ በኋላ ሳይሆን፣ ከልማታዊ

ጉዞው ቀድሞ ወይም አቡል አንዚደሞርና ተጠነበር አንዚዋኮል ቦሃድርሃ ይታላል። በአካያው ልማታዊ መንግሥቱ ዴሞክራሲያዊ ባይሆንም፣ በእነዚህ አገሮች እንደታየው ሦስቱን መስፈርቶች የሚያሟላ የዳበረ የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በአስተማማኝ ደረጃና አኳኋን ለገነባና፣ ይህን ተከትሎ በተነጻጻሪ ረዘም ካሉ ዓመታት በኋላ ዴሞክራሲውን ሊያስከትል ይችላል። ከዚህ በተጻራሪ በተለይ በደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች እንደታየው እነዚህ ባሕርያቶች ባልተሟሉበትም ሆነ በከፊል ብቻ በተሟሉበት አገር ልማታዊ ጉዞው በውል ሳይጀመር ሊቀር፣ ወይም ደግሞ እንደምንም ቢጀመርም በውጤት ላይዘልቅ ይችላል። በእነዚህ አገሮች እንደታየው፣ ልማታዊ ጅምሩ ከታሰበው መድረሱ ቀርቶ በመሐል ቢት የከሸፈ ልማታዊ ሂደት ሊከሰት፣ መንግሥታቱም የከሸፈ ልማታዊ መንግሥታት ወደመሆን ሊቀየሩ ይችላሉ። በዓለማችን የከሸፈ መንግሥት (Failed State) እንዳለው ሁሉ፣ የከሸፈ ልማታዊ መንግሥትም በብዛት (Failed Developmental state) አለና።

ልማታዊ መንግሥት በዚህ አኳኋን ሊከሽፍ የሚችልበት ሁኔታ የሚፈጠረው መሠረታዊ መለያዎቹ የሆኑትን ጠንካራ ጉኖች አስጠብቆ ለማስቀጠል ሳይችል ሲቀር ነው። አንድን መንግሥት ልማታዊ የሚያደርጉት ሦስቱ መሠረታዊ ባሕርያት እየተሸረሸሩ ከሄዱ ልማታዊ ጅምር መጨናገፍ ይጀምራል። ይህን በምድራችን የመጀመሪያውን ልማታዊ መንግሥት ከገነባችውና በሂደት ደግሞ ይኸው መንግሥት ፈር እየሳተ ከሄደባት ኔዘርላንድስ /ደች/ በመነሳት መመልከት ይቻላል። አሚያ ኩማር ባግቺ (2004) የተባለው የልማታዊ መንግሥት ንድፈ-ሀሳብ ተንታኝ፣ በልማታዊ አቅጣጫ ጅማሪነቱና የመጀመሪያው የዓለማችን ልዕለ ኃያል በመሆን ይታወቅ ስለነበረው የደች መንግሥት ያቀረበው ትንታኔ ይህንኑ ያረጋግጣል። ባግች የልማታዊ መንግሥት ጥንካሬና ነጻነት ቁልፍ ማረጋገጫ በሆነው ግብር የማስከፈል ጉዳይ ላይ ደቾች መጀመሪያ ጥሩ ዲሲፕሊን እንደነበራቸው ሲገልጽ፡-

> "እጅግ ተግባራዊ የነበሩት ደቾች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሪዎቻቸውን መሥዋዕት ከማድረግ የማይመለሱ ብቻ ሳይሆኑ፣ መሪዎቹም ተራውን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን ገዥዎቹንም ጭምር ግብር ለማስከፈል ወደኋላ የማይሉ ነበሩ። በሚገርም ሁኔታ የደች ሪፐብሊክ ስፓኒሾች የከተማ ባለሀብቶችን ያስከፍሏቸው ከነበረው ግብር የላቀ ያስከፍል ነበር።"[68] ይላል።

ልክ እንደባግች ሁሉ በዘመናችን የዓለም አቀፍ ግንኙነት ታዋቂ ጸሐፊዎች ከሆኑት አንዱ የሆነው ሮበርት ዲ.ካፕላን (2010) የደች መንግሥትና ሕብረተሰብ ምን ያህል ለልማት የቆረጡና ጠንካራ ዲሲፕሊን እንደነበራቸው ሲገልጽ፣

"ደቾች ከኢምፔርያሊስቶች ሁሉ እጅግ በጣም በተጠቃሚነት የሚያምኑ (Utilitarian) ህዝቦች ነበሩ:: የትም ቢሔዱ የከበባቸው የውሃ ድምፅ ሁሌም የሚያስታውሳቸው ስፍር ቁጥር የሌላቸውን አደጋዎች ስለነበር፣ ሁሌም በስጋትና በጭንቀት ሊኖሩ ተገደዋል:: ይህም በመላው ኔዘርላንድ እጅግ ለተዋጣለት ቅንብርና ትብብር፣ ወይም የኢንጂነሮች ሥነ-ልቦና ለሚባለው ዘይቤ እንዲጋለጡና በእጅጉ ሥርዓት ያላቸው ህዝቦች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል:: ይህን ተከትሎም በደች ዘግይቶ መምጣት የውድቀትና የኃላፊነት መጓደል ምልክት ተደርጐ በመወሰዱ ጠንካራ የቀጠሮ አክባሪነት አስተሳሰብ ሊዳብር ችሏል:: በእነርሱ ዘንድ ሮም ላይ ይታይ እንደነበረው መዝናናትና የካቶሊክ አስረሽ ምቾው ፈጽሞ አይታይም ነበር:: ሕይወት የምትቀጥለው ጥብቅ የሆነውን ካልቪኒስቲክ የሞራል ሕግ በመከተል ብቻ ነበር፣"[69] ይላል::

ይህን ያህል በጠንካራ ዲሲፕሊን ይታወቁ የነበሩት ደቾች ግን በዚሁ እስከመጨረሻው አልዘለቁም:: ዲሲፕሊናቸው እየላላና እየተሸረሸረ፣ በዚያው ልክ ደግሞ የኢኮኖሚያቸው ተወዳዳሪነት ዘግይተው በመጡት እንግሊዞች እየተበለጠ ሔደ:: በዚህም ሂደት የመጀመሪያው የዓለም ሉዓላዊ ልዕለ ኃያልነት (Hegemonic Super Power) ደረጃቸውን ሊያጡ ተገደዱ:: በደች የዲሲፕሊን መላላትና ይህም ያስከተለውን ውድቀት በማስመልከት ባግች፡

"ድሃውን ብቻ ሳይሆን የላይኛውንና ሀብታሙን መደብ (Upper Class) ግብር በማስከፈልና ዲሲፕሊን በማድረግ ቀና አቅጣጫ ማስያዝ የማንኛውም ልማታዊ መንግሥት ባሕርይ ነው:: ይሁንና በደች ተጨባጭ ሁኔታ የላይኛው መደብ ዲሲፕሊኑን አላልቶ ምቹ ሕይወት ከመምረጡ ጋር ተያይዞ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ውድቀት መፋጠን ጀመረ::"[70] ይላል::

ጀው ስቱድዌል (2013) የተሳካላቸውን የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮችና በተነጻጻሪ እምብዛም ያልተሳካላቸውን የደቡብ ምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታት ልምድ በማነጻጸር በተነተነበት መጽሐፉ፣ በኋለኞቹ አገሮች ክፖሊሲ ልዩነት በተጨማሪ በልማታዊ መንግሥታቱ ባሕርይ ላይ የታዩ ለውጦች የተጀመረውን የለውጥ ጉዞ እንዴት እንዳደናቀፉት በዝርዝር ያወሳል:: ስቱድዌል፡-

"መንግሥታት ከላይ ከተጠቀሱት ባህርያት አፈንግጠው፣ ልማትን የትርፍ ጊዜ ሥራ እንጂ የሞት የሽረት አጀንዳ የማድረግ አተያይና ዲሲፕሊን የሚጐድላቸው ሲሆን፣ ኪራይ ሰብሣቢነትን እያመከነ ልማታዊነትን የሚያጐለብት የመንግሥት

የተመረጠ ጣልቃ ገብነትና ዲሲፕሊን ሲዳከም፣ ከባለሀብቱ ነጻ መሆን የነበረበት፣ ልማታዊ መንግሥት በባለሀብቱ ወይም ከውስጥ በሚፈጠሩ ትንንሽ ጥቅመኛ ቡድኖች ተፅዕኖ ሥር ሲወድቅ፣ ተስፋ ማሳየት ጀምሮ የነበረ ልማታዊ ጉዞ በአጭር ሊቀጭ ይችላል"[71] ይላል::

የዲሲፕሊን መላላትና የልማታዊ መንግሥት የማሽቆልቆል ጉዞ ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸው ጉዳዮች ናቸው:: ልማታዊ መንግሥቱ ጠንካራ ዲሲፕሊን ሲኖረው፣ ልማታዊ ሀሳብና እቅዶችን በጠንካራ ዲሲፕሊን የማስፈጸም ብቃት ይኖረዋል:: ስቱድዌል በኮሪያ የነበረው መንግሥት ከምንም ነገር በላይ ለኤክስፖርት ልዩ ትኩረት በመስጠት ላይ የተገነባ ስለነበር፣ "በኮሪያ ድጐማና የኤክስፖርት ዲሲፕሊን የአገሪቱን ኢንዱስትሪያላይዜሽን ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ እንዳሳደገው"[72] ይገልጻል:: ስቱድዌል ከሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች ልምድ በመነሳት የኤክስፖርት ዲሲፕሊን ምን ማለት እንደሆነ ያብራራል። በኮሪያና በታይዋን ከታየው የባለሀብቱ ዲሲፕሊን ለየት ባለሁኔታ ጊዜያቸውን ኤክስፖርት በማድረግ ሳይሆን፣ ባለሥልጣኖችን በማጭበርበር ላይ ያሳልፉ የነበሩትን የደቡብ ምሥራቅ እስያ ባለሀብቶች ከሰሜኖቹ በማነጻጸር ሰፋ ኢድርጐ የገለጸው ስቱድዌል:-

> "[በሰሜን ምሥራቆቹ] የኤክስፖርት ዲሲፕሊን ከመንግሥት ድጐማና የተከለለ የገበያ ዕድል የሚሰጣቸው የአገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ በማያቋርጥ ሁኔታ የሚለኩና የሚመዘኑበትን ፖሊሲ በጥብቅ ተግባራዊ በማድረግ፣ ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት እንዲያደርጉና ዓለም አቀፉን ፉክክር እንዲጋፈጡ ማድረግ ነው:: ከመንግሥት የሚሰጣቸውን ድጋፍ የሚያገኙበት ደረጃ የሚወሰነው ኤክስፖርት በሚያደርጉት ምርት መጠን ልክ እንዲሆን በመደረጉ የኤክስፖርት ዲሲፕሊን ኮሪያ ከእሥር ቤት የምትወጣበት የፋይናንስ ቁልፍ ነበር:: በደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች ደግሞ ባለሀብቶቹ የተራቀቁት ለአረቦች አሸዋ፣ ለኤስኪሞዎች በረዶ በመሸጥ የማጭበርበር ጥበብ ነበር:: ይህን ኢድርገውም የአገሪቱን ውድ ልማታዊ ካፒታል በአብዛኛው የኢኮኖሚ ግሽበት ወደሚያስከትለው፣ የማታ ማታ ደግሞ በምሥራቅ እስያ ለተቀሰቀሰው የፋይናንስ ቀውስ ምክንያት ወደሆነው የሕንጻ ወይም ሪል-ስቴት ግንባታ ያፈሱት ነበር::"[73] ይላል::

በደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች የታየው ይህን የመሰለ ችግር ያለምክንያት የመጣ አይደለም:: መንግሥት በባለሀብቱ ተፅዕኖ ሥር ስለወደቀ የተከሰተ ችግር ነው:: መንግሥት ከባለሀብቱ ነጻ መሆን ሲያቅተው፣ የባለሀብቱ ጉዳይ አስፈጻሚ ለመሆን ይገደዳል። በዚህም ልማታዊ ባሕርዩን ማጥፋትና መሠረታዊ አቅጣጫውን መሳት ይጀምራል። መንግሥት በዚህ

ተፅዕኖ ምክንያት ልማታዊ ዲሲፕሊን፣ የኤክስፖርት ዲሲፕሊን፣ የኢንዱስትሪ ልማትን የመምራት ዲሲፕሊን እየጐደለው ሲሔድ ጅምሩ ልማታዊ ጉዞ ለኢደጋ ይጋለጣል፡፡ ጠቅላላ ሥርዓቱም ለመክሸፍ ይበልጥ የተጋለጠ ይሆናል፡፡

በዓለማችን የከሸፉ ልማታዊ መንግሥታት መፈጠር የሚጀምሩት በባለሀብቱና በውስጥ ጥቅመኛ ቡድኖች ያልተገባ ተፅዕኖ ሥር እየወደቁ ተልዕኮዋቸውን በተመረጠና ሚዛናዊ ጣልቃ ገብነት መፈጸም ሲሳናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ የተነሳ ኢንዱስትሪያዊ ልማትን በተለይ ደግሞ ፋብሪኬሽንና ማኑፋክቸሪንግን የማስፋፋት ችሎታቸው ሲዳከም፣ የገጠር ኢንዱስትሪን ማልማት ሲያቅታቸውና ለእነዚህ ሁሉ ቁልፍ የሆነውን ልማታዊ የፋይናንስ ስምሪት ማረጋገጥ ዳገት ሲሆንባቸው ነው። ደህና ጀምረው ረጅም ርቀት መራመድ የተሳናቸውም ሆኑ የተሳካላቸው አገሮች ታሪክ ይህን ያረጋግጣል። ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ፊት የተደቀኑትን ፈተናዎች ከእነዚህ ዓለማዊ ልምዶች በመነሳት መፈተሸና በጉዳዩ ላይ መግባባት የመጀመሪያው ነጥብ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ለዚህ ሲባል በእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ዓለም አቀፍ ልምዱን በተመጋጋቢነት እያቀረቡ የወቅቱን አገራዊ የኢኮኖሚ ፈተናዎች አንድ በአንድ መመልከት ይገባል።

ከባለሀብቱ ተፅዕኖና ቁጥጥር የጸዳ ልማታዊ መንግሥት የመገንባት ፈተና...

በአገራችን ከባለሀብቱ ተፅዕኖና ቁጥጥር ነጻ የሆነ መንግሥት የመገንባት ጉዳይ መለስ ደጋግሞ የጻፈበትና የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ግንባታ ትግሉ መነሻ ነጥብ ያደረገው ነበር፡፡ መለስ ለአመራር ማሠልጠኛ ይሆን ዘንድ "የተሃድሶው መስመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው መጽሐፍ፡-

> "በነጻ ገበያ ማዕቀፍ የሚካሔድ ልማት የግል ባለሀብቱን በአንቀሳቃሽ ሞተርነት መጠቀሙ አይቀሬ ነው፡፡ ስለሆነም ባለሀብቱን በሙሉ ልብ በመደገፍ በአጋርነት መውሰዱ ተገቢ ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ መርሕ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በድህ አገሮች ካለው የኪራይ ሰብሣቢነት የፖለቲካ ኢኮኖሚ የበላይነት በመነሳት መንግሥት ከባህብቱ በፖለቲካና ኢኮኖሚ ነጻ ካልሆነ ልማታዊነቱን ጠብቆ መቀጠል አይችልም፡፡ ባለሀብቱ መንግሥትን በኪሱ ውስጥ ካስገባው፣ በእነዚህ አገሮች ሰፍኖ በቆየው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምክንያት፣ ባለሀብቱ በቅድሚያ የሚፈልገው በአቋራጭ መክበር ነውና መንግሥትን የኪራይ ሰብሣቢነቱ መጠቀሚያ ማድረጉ በፍፁም የማይቀር ይሆናል፡፡"[74] ይላል፡፡

ከዚህ የመለስ አገላለጽ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ መሠረተ-ሰፊ ልማትን በማረጋገጥ ህዝብን ወደ ብልጽግና የማሸጋገር ጉዳይ፣ ከማንኛውም ዓይነት የግል ባለሀብት ተፅዕኖ በወሳኝነት ነጻ የሆነ መንግሥት መኖሩን የግድ ይላል። በአንጻሩ መንግሥት ከራሱ ውስጥም ሆነ ከውጭ ለሚፈልቁ የጥቅም ቡድኖች ተፅዕኖ ከተጋለጠ በማያጠራጥር ሁኔታ የከሸፈና እርባና ቢስ መንግሥት ይሆናል። ባለሀብቱ ኢህአዴግን ወደሥልጣን የሚያወጣ ወይም ከሥልጣን የሚያወርድ መሆን እንደሌለበት፣ ወይም ደግሞ መንግሥት በባለሀብቱ ድጐማ የሚተዳደር እንዳይሆን ማድረግ ተሠምሮበታል። ይህ ነጻነት ልማታዊ ባለሀብቱን መደገፍ በሚያስፈልግበት ለመደገፍ፣ ሳይሠራ ለመከበር የሚፈልገውን ደግሞ ለመገሠጽና በሕግ አስገዳጅነት ወደመልካም አቅጣጫ ለመመለስ የሚያስችል መሆን አለበት። ስለዚህም የአገራችን መንግሥት ከባለሀብቱ ቁጥጥር የተላቀቀ ብቻ ሳይሆን፣ ባለሀብቱን ከኪራይ ሰብሳቢ መንገዶች እያወጣ ልማታዊ መንገድ የሚያስይዝ፣ ነጻና ጠንካራ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተወስኗል። መንግሥት በባለሀብቱ ገንዘብና መልካም ፈቃድ ላይ ተንጠልጥሎ ባለሀብቱ ሥልጣን ላይ የሚወጣ ወይም የሚወርድ እንዳይሆን ማድረግ የተፈለገበትን ምክንያት አንድ ተጨባጭ ምሣሌ በማንሳት ይህን ማሳየት የቀለለ ይሆናል።

ኢህአዴግ ከ1997 ዓ.ም. ምርጫ ተገቢውን ትምሕርት በመውሰድ አንዳችም የባለሀብቱ ድጋፍ ሳያስፈልገው በ2002 ዓ.ም. በተካሔደው አገራዊና ከልላዊ ምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍ የሚያስችለውን ፖለቲካዊ ዝግጅት ጨርሶ ነበር። በዚህ መሠረት ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ የህዝብን መሠረታዊና አጣዳፊ ችግሮች ለመፍታት ጥረት በማድረግ ህዝቡ በገጠርም በከተማም በተለይ በልማት ከመጠቀምና ከመልካም አስተዳደር ጋር አያይዞ ያነሳቸውን ችግሮች ለመፍታት ተንቀሳቅሷል። የድርጅቱ ማኅበራዊ መሠረቱ የሆኑትን ብዙኀን ለመጥቀምና የቻለውን ያህልም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ ሞክሯል። ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቱና የመሠረተ-ልማት አውታር ግንባታው ህዝብን በሚያሳትፍና በሚጠቅም አኳኋን እንዲከናወንም አድርጓል። ይህ ሁሉ የህዝቡን መብትና ጥቅም ለማስከበር ከልብ ታምኖበት እንጅ አጉል ተወዳጅነት በማትረፍ (Populism) ለመመረጥ ሲባል የተወሰደ እርምጃ አልነበረም። ይህም ሆኖ ኢህአዴግ አራተኛውን አገራዊ ምርጫ በአሸናፊነት ያጠናቅቅ ዘንድ ከተፈላጊው በላይ አስተዋጽኦ ነበረው። በዚህ ምክንያት ግንባሩ የባለሀብቱ ፖለቲካዊም ሆነ የፋይናንስ ድጋፍ ሳያስፈልገው በምርጫው ተፈላጊውን ወንበር ለማግኘት ይቸገራል የሚል ግምት አልነበረንም።

ይህም ሆኖ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ተግባራቱን በአባላቱ መዋጮና በጣም በዝቅተኛ በጀት በመተማመን ሲፈጽም የቆየው ኢህአዴግ፣ አንዳንድ ቀዳዳዎችን ለመድፈን በሚል ከባለሀብቶች የገንዘብ እርዳታ ይጠይቃል። ይህ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከሚያደርገው ሕጋዊ የገንዘብ ድጋፍ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ የተለየ አልነበረም። በዚህ መሠረት በጥገኝነት

የሚታወቁ አንዳንድ ግለሰቦች ጭምር ባደረጉት አስተዋጽዖ፣ ከባለሀብቶች አስራ ሁለት ሚሊዮን ያህል ብር ተሰባስቦ ለድርጅቱ ገቢ ተደረገ። በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ መሠረት የተከናወነው ይህ ድጋፍ የማሰባሰብ ጥረት ግን ከባለሀብቶቹ በኩል የራሱን ጣጣ ይዞ የመጣ ነበር።

ባለሀብቶቹ ገንዘቡን ባስረከቡ ማግስት፣ በተለይ በጥገኝነት ከሚጠረጠሩት አንዳንዶቹ፣ "እኛ ይህን ያህል ገንዘብ አዋጥተናል፣ ኢህአዴግ በፋንታው የሚያደርግልን የፖሊሲ ማሻሻያ አይኖርም ወይ?" የሚል ጥያቄ አቀረቡ። ይህ ከባለሀብቶች የማይጠበቅ ነገር ባይሆንም "የፈሩት ይደርሳል" እንዲሉ አስገራሚው ጉዳይ በሕገወጥ ሥራቸው የሚታወቁት ጊዜው የወለዳቸው ጥገኛ ባለሀብቶች ዋነኞቹ ጥያቄ አቅራቢዎች መሆናቸው ነበር። ይህ ግልጽ ጥገኛ ጥያቄ የቀረበለት ኢህአዴግ በበኩሉ አሉታዊ መልስ ሰጠ። ጥያቄው አገራዊ የፖሊሲ ነጻነትን ለማስከበር በቢሊዮን ዶላር ከሚያበድሩ ተቋማት ጋር ለሃያ ዓመታት ያህል ለተፋለመው ኢህአዴግ እንደስድብ የሚቆጠርም ነበር። ድርጅቱ ብድርና እርዳታ ለሰጠ ሁሉ የፖሊሲ ማሻሻያ የሚያደርግ ቢሆን ኖሮ፣ ቀደም ሲል የዓለም ባንክና የዓለም ገንዘብ ድርጅትን፣ አሁን ደግሞ የቻይና መንግሥትን ያህል ያበደረን አልነበረምና አገሪቱን ከፍተኛ ገንዘብ ለከፈለው ሁሉ አሳልፎ በሰጠ ነበር። በመሆኑም የፖሊሲ ጫና ለማሳረፍ በሚከጅሉ ለጋሽና አበዳሪ ተቋማትና አገሮች ተፅዕኖ ተገፋፍቶ የፖሊሲ ለውጥ ለማድረግ ቃል መግባት የማይሞክረው ኢህአዴግ፣ አሥራ ሁለት ሚሊዮን ብሩን ተከትሎ የመጣውን ጥያቄም ሳያስተናግድ ቀረ። በዚህም አጋጣሚ ከባለሀብቱ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ ከሚያውቀው በተጨማሪ ተጨባጭ ትምሕርትም ቀሰመ።

የትላንቱን ኢህአዴግ ለሚያውቁ ሁሉ፣ ያልተገባው ተፅዕኖ ከየትም ይምጣ ከየት ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚያጠራጥር አልነበረም። የገንዘብ ድጋፍ ከሰጡት ባለሀብቶች አንዳንዶቹ አገራቸውን የሚወዱና ለልማትም የሚተጉ ነበሩ። ሌሎቹ ደግሞ ከባለሥልጣን ወዳጆቻቸው ጋር ተሻርከው ታክስ ሲያጭበረብሩ፣ የመንግሥትን ሕግ በማን አለብኝነት ሲሸሩ በመገኘታቸው በወንጀል ተጠያቂ የሚፈለጉ ነበሩ። ከእነዚህም አንዳንዶቹ መንግሥት የተጠያቂነት ሕጉን ተፈጻሚ ከማድረጉ በፊት ከአገር ጠፍተው ዛሬ በመካከለኛው ምሥራቅ የመሸጉ ናቸው። ከዚህ አብነት ለመገንዘብ የሚቻለው፣ ባለሀብቱ እንኳን የመንግሥትን ዕድል እንዲወስን ሰፊ በር ተከፍቶለት፣ በተከፈተች ትንሽ ቀዳዳ አልፎም መንግሥትና ተቋማቱን ተላላኪው ለማድረግ የሚሻና በተግባርም ዕድሉን የሚሞክር እንደሆነ ነው። ለዚህ ነው የልማታዊ መንግሥት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕልውና በባለሀብቱ መልካም ፈቃድና ችሮታ ላይ የተመሠረተ ሊሆን አይገባም የተባለው።

በአዲሲቱ ኢትዮጵያ መንግሥት እንደኮንትራት ሰጭ፣ ለግምት የሚያስቸግር ትልቅ የገንዘብ መጠን ይዞ የቀረበ ተዋናይ መሆን ጀምሯል። ይህን ተከትሎ የመንግሥትን ኮንትራት

ማግኘት ወይም አለማግኘት በሀብት ማማ ላይ ወይም ከተራራው ግርጌ የመቀመጥ ዕድልን የሚወስን ሆኗል። ይህ በሁሉም ዜጐች፣ በተለይ ደግሞ የገንዘብን ጥቅም በተገነዘቡ ባለሀብቶች ዘንድ ግልጽ ግንዛቤ የተያዘበት ነው። ከግንዛቤም አልፎ በጨረታዎች አሸናፊ ለመሆን ያለ የሌለውን ቀዳዳ መፈተሽና ሕገ-ወጥ መንገዶችን ጨምሮ በሰፊው የመረባረብ ባሕል እንዲፈጠር አድርጓል። ጨረታ ሰጭው የመንግሥት ኃላፊ ደግሞ በእጁ የገባው የመስጠት ወይ የመከልከል ችሎታ፣ ሎተሪ የደረሳቸውን ወደሰማይ የሚያጐን እንደሆነ የተገነዘበበት ነው። ስለዚህም ደግሞ "እኔስ ምን በወጣኝ በዕድሉ ሳልጠቀም እቀራለሁ" ብሎ እንዲያስብ፣ አስቦም ወንበሩን እንዲያከራይ በር የከፈተ ነው። ይህ በኮንትራት አሰጣጥና በባለሀብቱ ያለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ ብቻ የማይታጠር፣ በአንዳንድ የመንግሥት ኃላፊዎች ዘንድ ጭምር ጉልህ አዝማሚያ እየሆነ የመጣ ነው። በመሬት ኢደላ፣ ግብር በማስከፈል፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመስጠት ተግባራት ቀላል በማይባል ደረጃ የሚንጸባረቅ ዝንባሌ ነው። ይህን ለመገንዘብ አንዱን ሴክተር በምሣሌነት አንስቶ ጉዳዩን መፈተሽ ብቻ በቂ ነው።

በኢትዮጵያ ሙስና እንደ ሰደድ እሣት እንዲቀጣጠል በር ከከፈቱት መስኮች ቀዳሚውና ዋናው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ነው። ይህን ከሌላ ሳይሆን ራሱ "የኢትዮጵያ ሥራ ተቋራጮች ማኅበር" ከፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመሆን እ.ኤ.አ. በ2012ና 13 ባካሔደው ጥናት ያረጋገጠው ነው። ማኅበሩ በአገራችን ያሉ ኮንትራክተሮች በተናጠልና በትብብር አምስት ዓይነት ስልቶችን በመጠቀም በአገር ሀብት ዝርፊያ ላይ እንደተሰማሩ አረጋግጧል። የመጀመሪያው ስልት ተመሳጥሮ በመጫረት ዋጋ ማናር ወይም በሥምምነት ተመሳጥሮና ዛሬ አንዱ፣ ሌላው ደግሞ ነገ በሚጠቀምበት መንገድ ተባብሮ በጨረታ መሳተፍ (Collusion) ነው። ሁለተኛው ከአማካሪዎች ጋር ተመሳጥሮ መሠራት የሌለበትን ሥራ እንደሠሩ በማስመሰል ከፍያ መውሰድ ነው። ሦስተኛው በልዩነት (Variation) አሳብቦ ጠቀም ያለ ገንዘብ መዝረፍ ነው። በአራተኛ ደረጃ ደግሞ አንዴ ኮንትራት ከወሰዱ በኋላ ቀጣይ ሥራዎችን በቀላሉና በጉቦ እያገኙ ማለብ ሲሆን አምስተኛው የዝርፊያ መንገድ ደግሞ በኮንትራክት አንቀፁ ውስጥ መንግሥትን ጥፋተኛ የሚያደርጉ ቀዳዳዎች እንዲበዙ በማድረግ የ"ይገባኛል" ጥያቄ (Claims) በማቅረብ መዝረፍ ይገኝበታል። እነዚህን በመሳሰሉ ሥልቶች በመታገዝ በዚህ ኢንዱስትሪ የማይፈጸም የሙስና ቅሌት ወይም ወንጀል የለም። በዘርፉ ውስጥ በንጽህና የሚሠሩ ወገኖች መኖራቸው ባይካድም፣ በዘርፉ ያለው ዋናው ዝንባሌ ከሕጋዊ ሥርዓቱ ባፈነገጠ መልኩ የጥቂቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው።

በአገሪቱ ውስጥ በብዙ ቢሊዮን ወጭ ከሚሠሩት መንገዶች መካከል አብዛኛዎቹን የሚያሸንፉት በዚህ የዝርፊያ ሥልት የተካኑ ኩባንያዎች ናቸው። ከእነዚህ ዋናዎቹ ደግሞ በጣት የሚቆጠሩ ሲሆኑ ብዙ ኮንትራት የመውሰድ ዕድል ያገኘውን አንድ ኩባንያ መነሻ በማድረግ

ፍተሻ ቢካሔድ፣ የሚገኘው እውነታ የሚያስገርም ብቻ ሳይሆን የሚያስደነግጥም ጭምር ነው፡፡ እድሜ ለመንገዶች ባለሥልጣን ይህ ኩባንያ በተሰማራበት ከልል በርካታ የመንገድ ግንባታ ዕድል አግኝቷል፡፡ ነገር ግን ኩባንያው ከትግራይ እስከአማራ፣ ከኦሮሚያ እስከደቡብ፣ ከጋምቤላ እስከሶማሌ ከልሎች ከተሰጡት ኮንትራቶች እጅግ አብዛኛውን በጥራትም ሆነ በጊዜ አልፈጸመም፡፡ ይህ በብዙ የመንግሥት ኃላፊዎች የሚታወቅ ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው፡፡ የብቸና-ሞጣን መንገድ እንዳልሆነ አድርጐ ካረሰው በኋላ በፕሮጀክቱ መጓተት የድሮው መንገዳቸው ቢናፍቃቸው የአካባቢው ኗሪዎች "የጐጃምን ገበሬ የሚያስንቅ መንገድ አራሽ" መጣ ብለው የተሳለቁበት የሥራ አፈጻጸም የነበረው ነው፡፡ የመንግሥትን ልማታዊ እቅድ አፈጻጸም በንቃት የሚከታተሉት የጐጃም ገበሬዎች የለበጣ አድናቆት እስኪሰጡት ያስገረማቸው ይህ ኮንትራከተር ግን በወደቀ ቁጥር በላይ በላዩ ኮንትራት ሲያገኝ ቆይቷል፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ሥርዓታችን ይህን እንዴት አይቶ እንዳላየ አለፈው? ይህስ የሆነው መንግሥት ስለችግሩ ስላላወቀ ነወይ? ካወቀስ ለምን በጊዜ እርምጃ አልወሰደም? ብሎ ለመጠየቅ መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላም ነገር ማንሳት ይቻላል፡፡

የልማታዊ መንግሥት ኃላፊዎች ዋነኛ ተግባር ባለሀብቶችን ጨምሮ ሁሉንም ዜጐች አላላውስ ያለ አረሞችን በመንቀል ውድድርን ማበረታታት ነው። ከተወዳዳሪዎች መካከል አንዱን መርጦ አሸናፊ ማድረግ አይደለም፡፡ ማሸነፍም ሆነ መሸነፍ መወሰን ያለበት ተፎካካሪዎች ለጨረታ ባቀረቡት ምርት ወይም አገልግሎት ጥራትና በሚሰጡት ዋጋ ብቻ መሆን አለበት። ስለሆነም ልማታዊ መንግሥታት አሸናፊን ከውድድር ውጭ አይመርጡም፡፡ ይህ መሆኑ ቀርቶ በበላይ ኃላፊዎች አሸናፊን የመምረጥ አሠራር ተግባራዊ ከሆነ መቼም ቢሆን አሸናፊው አድልዎ መፈጸሙ አይቀርም፡፡ ልማታዊ መንግሥታት አሸናፊው በውድድሩ ሂደትና ፍጻሜ በልጦ በመገኘት እንጂ፣ ከውድድሩ በፊት እንዲለይ የማድረግ አቅጣጫ አይከተሉምና፡፡ ስለዚህም መላ ትኩረታቸውን ሁሉንም ተወዳዳሪዎች ገትተው የሚይዙ አረሞችን በመንቀል ላይ ያደርጋሉ፡፡ በኢትዮጵያ የኮንስትራከሽን ኢንዱስትሪ ግን ይህ መርሕ አይታወቅም፡፡ ይህን የሚያረጋግጡ በርካታ ምሣሌዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

ለምሣሌ በአንድ ወቅት በምዕራብ ኦሮሚያ ያዩ በተባለው ቦታ ላይ የሚገነባውን "ያዩ የማዳበሪያ ፋብሪካ" ፕሮጀክት መመልከት ይቻላል። ይህ የማዳበሪያ ፋብሪካ ይገነባል ከተባለ በኋላ ፕሮጀክቱን የሚያስፈጽመው መሥሪያ ቤት ከፕሮጀክት ቦታ ላይ አፈር የማንሳት ሥራን ለማስፈጸም ያቅዳል፡፡ ሥራው መሬት መቁረጥ፣ አፈር መግፋትና ቦታ ማጽዳት በመሆኑ አንዳችም የቴክኖሎጅ ልዩነትን የሚጋብዝ አይደለም። ስለዚህም ዶዘር፣ ሎደርና ዳምትራኮች ያሉት ማንኛውም ባለሀብት ሊሠራው የሚችለው በመሆኑ በዚህ አፈር የማንሳት ሥራ ብዙ ኮንትራከተሮች ለመወዳደር ተመዘገቡ። በወቅቱ አገራዊ የገበያ ዋጋ መሠረት አንድ ሜትር

ካሬ አፈር 40 በመቶ የተርፍ ሕዳግን ጨምሮ በሰማኒያ ብር ይነባ የነበረ ፒሆ'ንም፣ ሥራው በጨረታ መከናወኑ ቀርቶ በኃላፊዎቹ የተመረጠ አንድ ኮንትራክተር ሜትር ካሬውን በሦስት መቶ ብር እንዲሠራው ተደረገ፡፡ በዚህ ሥራ ይህን ያህል የዋጋ ልዩነት መኖር ያልነበረበት ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ከተሠራም በኃበያ ዋጋ መሠራት ነበረበት፡፡ ነገር ግን በማን አለብኝነት የተመሳጠሩት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና ኮንትራክተሩ ከጨረታ ውጭ አሸናፊን በመምረጥ በሌለ ዋጋ እንዲሠሩት ተደረገ።

በዚህ መልክ አገሪቱና መንግሥት ያጡትንና ግለሰቦቹ የከበሩበትን ገንዘብ መጠን ለመረዳት ያግዝ ዘንድ ጥቂት ሂሳብ ነክ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለምሣሌ የሚጓጓዘው ወይም ወደዳር የሚገፋው አፈር መጠን ሁለት መቶ ሸ ሜትር ኩብ ቢሆን፣ በኃበያ ዋጋ በ16 ሚሊዮን ብር ሊሠራ ይገባው የነበረው ይህ ሥራ፣ በዚህ ኪራይ ሰብሳቢ መንገድ በ60 ሚሊዮን ብር ተሠራ እንደማለት ነው፡፡ የአፈሩ መጠን በጨመረ ቁጥር ኮንትራክተሩና ባለሥልጣናቱ የሚዘርፉት ገንዘብ መጠን በዚያው ልክ ይጨምራል። በዚህ ሥሌት ኩባንያው ያልሠራበትን ብዙ ብር እንዲያገኝ ያደረገው ይህ አካሔድ፣ ስንት ወንበር አልባ ትምሕርት ቤቶችን ባለወንበር፣ ስንት አልጋና አምቡላንስ አልባ ጤና ጣቢያዎችን ባለአልጋና ባለአንቡላንስ ያደርግ ነበር፡፡ ኪራይ ሰብሣቢነት ከሕጋዊና ልማታዊ አስተዋጽኦ በላይ በመጠቃቀም ላይ በተመሠረተ ግንኙነት ያልተገባ ትርፍ ማጋበስ ወይም አገርን መዝረፍ ከሆነ፣ ይህ ተራ ዝርፊያ እንጅ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

ብዙዎቹ ኮንትራክተሮች ቢፈተሹ በኢንዱስትሪው ውስጥ ይህን የመሳሰሉ በርካታ የጥገኝነት ግንኙነቶች እንደተንሰራፉ ለመመልከት አያስቸግርም፡፡ "ሌባን ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው" ነውና፣ ይህ ለጊዜው የዝርፊያ አውራ የሆነ ሴክተር በጠራራ ፀሐይ በራሱ ሠራተኞች የሚዘረፉ ኩባንያዎች የተበራከቱበት ሆኗል፡፡ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በዓለማችን እጅግ ውድ ከሆኑት መካከል አንዱ እንዲሆን ያደረገው ዋነኛው ምክንያት ይኸው ኪራይ ሰብሣቢነት ነው፡፡ መንግሥትን በምርኮኝነት የያዘው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ፣ በኢትዮጵያ ማንኛውንም ልማታዊ ግንባታ ተወዳዳሪ እንደይሆን አድርጎ ሰንጎ ይዞታል፡፡ አፈር ለማጓጓዝ በሜትር ኪውብ የ750 ብር ልዩነት በሚታይባትና በዚህ ምክንያት ደግሞ ከፋብሪካ ዋጋ የሲቪል ግንባታ ዋጋ በሚንርባት ኢትዮጵያ፣ ይህ አደገኛ አዝማሚያ መፍትሔ ካልተበጀለት በስተቀር የማኑፋክቸሪንግ ልማትና ተወዳዳሪነት የቀን ሕልም መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ የትኛውንም ቀዳዳ በርሜል በመሙላት መቼም ቢሆን የተወዳዳሪነት ብቃት ተረጋግጦ አያውቅምና፡፡

ከጥገኛው ባለሀብት ተፅዕኖ ጋር ተያይዞ የሚታየው ችግር በወሳኝነት ከፖለቲካ ኢኮኖሚው ጋር የተቆራኘና አንዱ የሥርዓቱ ቀዳሚ ችግር ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ የሚፈልቁና በተለይ እሰት አመንጭ በሆኑ ሴክተሮች ልማት ዙሪያ የሚታዩ

ትግሮት በተናጠል ተወስደው ሲዳሰሱም ጉዳዩ የሥርዓት ተግዳሮት መሆን እንደጀመረ ለመገንዘብ ይቻላል። በተለይ በኢንዱስትሪ ልማት መስክ በመታየት ላይ ያለው ሁኔታ ለየት ያለ ተግዳሮት የደቀነ ሆኗል።

ኢንዱስትሪያዊ ልማትን የማሳካት ተግዳሮቶች፣

ከብዙ ዘግይተው የለሙ አገሮች ታሪክ በመነሳት በአጠቃላይ የመልማትና ያለመልማት ጉዳይ የማታ ማታ የሚወሰነው በኢንዱስትሪ ልማት ነው። በኢንዱስትሪ ለመልማት የመቻልና ያለመቻል ጉዳይ ደግሞ የሚወሰነው በአመራር ብቃት ነው። የኢንዱስትሪ ልማት ሞካከረው ያልተሳካላቸውም ሆኑ ተሳኩቶላቸው የበለጸገ ሕብረተሰብን የተቀላቀሉ አገሮች ልምድ ቁልፉ የስኬት መሣሪያ ብቁ አመራር እንደሆነ ያረጋግጣል። ጀርመን ኢንዱስትሪያዊ ባለከባድ ሚዛን የሆነችው በቮን ኦቶ ቢዝማርክ አመራር ነበር። ጃፖንም ኢንዱስትሪያዊ አገር የሆነችው በሚጅ ሥርወ መንግሥት ጠንካራ አመራር ነው። ደቡብ ኮሪያ በጀኔራል ፖርክ፣ ታይዋን በሻንግ ካይሸክ፣ በቅርቡ ደግሞ ቻይና በዴንግ ዣዎ ፒንግ አመራር አገራቸውን ከኋላቀርነት እያላቀቁ የበለጸጉ ኢንዱስትሪያዊ አገራትን ገሥራ ተቀላቅለዋል። ብቁ አመራር ሲገኝ ወደፈጣንና ዘላቂ ኢንዱስትሪያዊ ልማት የሚወስደው አቅጣጫ በጥራት ሊነደፍ ይችላል። ይህን የሚያስፈጽም አስተማማኝ ተቋማዊ ብቃትም ይገነባል። ስለሆነም ኢንዱስትሪያዊ ልማትን ለማሳካት ከዬት ተነሥቶ ወደዬት እንደሚሔድ የተገነዘበ፣ በየትኛው የፖሊሲ ማዕቀፍና ስትራቴጂ በመመራት ለውጡን ማስፈጸም እንዳለበት የሚያውቅና ከራሱም ሆነ ከሌሎች የስኬትና የወድቀት ልምዶች እየተማረ የሚሔድ አመራር ወሳኝ የለውጥ ቅድመ ሁኔታ ነው።

ይህ የአመራር ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ በሁሉም የኢኮኖሚ መስኮች ከመረባረብ ይልቅ ቁልፍ አስተዋጽኦ ያላቸውን ዋና ዋና መስኮች ለይቶ፣ እነዚህን በልዩ ብቃት ማልማት ደግሞ ወደበለጸገ ሕብረተሰብ የሚደረገውን ጉዞ ይወስናል። ሰፊ ገጠርና ገበሬ ማሕበረሰብ በነበራቸው ዘግይተው የለሙ የምሥራቅ እስያ አገሮች እንደታየው ፈጥኖ የመልማትና ያለመልማት ዕድልን የሚወስኑት ጥቂት ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው። የመጀመሪያው ግብርናን በተለይ የአነስተኛውን አርሶ አደር ግብርና በፍጥነት ማልማት ነው። ቀጥሎና በተከታይነት ደግሞ ፋብሪካዎችን በአገር ውስጥ የመገንባት ብቃትን /Fabrication/ በመፍጠር ዘመናዊ ምርቶችን አምርተው ለውጭና ለአገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት (Industrialisation) ነው። ሦስተኛው በየደረጃው ልማትን የሚደግፍ በቂና ዘመናዊ መሠረተ-ልማት ማስፋፋት ሲሆን ከእነዚህ በማይነጠል መልኩ ደግሞ ውጤታማ የልማታዊ ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የመገንባት ጉዳይ ይገኛል። እነዚህ ተግባራት ኪራይ ሰብሳቢነትን ከመታገልና ከማዳከም ጋር በተመጋጋቢነት ከተፈጸመ፡ በእርግጥም ፈጣንና ህዝብ የሚጠቀምበት አገራዊ ኢንዱስትሪያዊ ልማትን

ለማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በአንጻሩ በእነዚህ መስኮች ልማትና አጠቃቀም ላይ ስህተት መፈጸም ኢንዱስትሪያዊ ልማት በቅርብና መካከለኛ ጊዜ ውስጥ እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያዊ ልማትና የብልጽግና ዕድልም በእነዚህ ቁልፍ መስኮች ልማት የሚወሰን ነው፡፡ ይህ ከግብርናው በመጀመር ሊረጋገጥ የሚችል ነው።

አብዛኛው ህዝባቸው አርሶ አደር፣ ዋናው የልማት ጸጋቸው ደግሞ መሬት በሆኑ አገሮች የለውጥና ዕድገት መጀመሪያ ነጥብ ገጠርና ግብርና መሆን አለበት። አብዛኛው ህዝብ በገጠር የሚኖረው በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ከፍተኛ ሀብት ለመፍጠር የሚያስችል ጉልበትና መሬት እያለ አርሶና አርብቶ አደሮችን የሚደግፍ ሥርዓት ባለመኖሩ የግብርናው ምርታማነት ዝቅተኛ መሆን ነው። ሁለተኛው ምክንያት ኢንዱስትሪና ከተሜነት ባልተስፋፋባቸው አገሮች ከገጠር ወደከተማ ሊፈልስ የሚችለው ህዝብ ለተሻለ ሕይወት የሚበቃበት ዕድል አናሳ በመሆኑ እዚያው ገጠር ላይ መቆየት የሚመርጥ መሆኑ ነው። ግብርናው ከፍተኛ የምርታማነት ደረጃ ላይ ቢደርስና ኢንዱስትሪና ከተሜነት ቢስፋፋ ኖሮ ብዙ ሰው ከገጠር እየወጣ በከተሞች መኖር ይመርጥ ነበር። በመሆኑም ባልበለጸጉ አገሮች የሚገኘው አብዛኛው ህዝብ ገጠርና ግብርና ላይ የተመሠረተ ኑሮ መምራትን የተሻለ የሕይወት ዋስትና የሚሰጥ አድርገው ይቆጥረዋል።

በዚህ የተነሳ በእነዚህ አገሮች ለዕድገትና ብልጽግና ለመብቃት ከሁሉ በፊት ግብርናና ገጠርን ማልማት የግድ ይላል። የግብርናውን ምርታማነት በመጨመር ገጠሩ በየደረጃው የሚስፋፉትን ከተሞችና ነዋሪያቸውን ለመሸከም የሚችል የምግብ አቅርቦት የሚያሟላበት ደረጃ ላይ ማድረስ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ገጠርና ግብርና ለኢንዱስትሪ ልማት መፋጠን ተፈላጊ የሆኑ ብዙ ነገሮችን እንዲያሟላ ማድረግ ያስፈልጋል። አስቀድሞ የተፈጠረና የተከማቸ ካፒታል በሌለበት አገር ግብርናው የመነሻ ካፒታል መፍጠሪያና ማከማቺያ መድረክ ሆኖ ማገልገል አለበት። ለኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ የሆነው ጥሬ ዕቃ አቅርቦትና እንደሁኔታውም የውጭ ምንዛሬ ምንጭ የሚሆነው ግብርናና ገጠሩ ነው። ቀስ በቀስ ከገጠር ወደከተማ የሚፈልሰው ህዝብ ቁጥር ሲጨምር ደግሞ ለኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ የሆነው ወጣት አምራች ኃይል የሚገኘው ከገጠሩ ነው። በመጨረሻም እነዚህን ሁሉ በመጠቀም ገቢው እየተሻሻለ የሚሔደው የገጠር ህዝብ ለኢንዱስትሪ ምርቶች ተፈላጊው የአገር ውስጥ ገበያ በመሆን ማገልገል ይገባዋል።

ይህ በንድፈ-ሀሳብ የሚታወቅ ሲሆን ስኬታማ በሆኑ ልማታዊ መንግሥታት በተመሩ አገሮች ሁሉ በተጨባጭ የታየ ነው። በእነዚህ አገሮች የዕድገቱ መሠረታዊ መነሻ በአነስተኛዋ የአርሶ አደር ማሳ ላይ የተካሔደው ፈጣን የግብርና ልማትና ይህን ተከትሎ የተፈጠረው የህዝብ ብልጽግና ሲሆን የኢንዱስትሪ ልማቱም የተወሰነው በዚሁ የገጠርና ግብርና ልማት ነው፡፡ ይህ ገጠር የሚባል ነገር በሌላቸውና የከተማ መንግሥታት በሆኑት ሆንግ ኮንግና

ቢንጋፖር በስተቀር፣ በብዙዎቹ ስኬታማ ልማታዊ መንግሥታት ሁሉ በተጨባጭ የታየ ነው፡፡ ሁለቱ የከተማ መንግሥታት ገጠርና ግብርና የሚባል ነገር ስላልነበራቸው ሲንጋፖር በንግድና ኢንዱስትሪ፣ ሆንግ ኮንግ ደግሞ በንግድና ፋይናንስ ዘርፍ ላይ የተመሠረተ ልማት ወደማስፋፋት አምርተዋል፡፡ ሰፊ አርሶ አደር የነበራቸው ሌሎቹ የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች ልማት ግን በገጠርና ግብርና ላይ የተመሠረተና በዚሁ ቅኝት የተመራ ነበር። ይህን ለኢትዮጵያም ልምድ በሚሆን መልኩ ዘርዘር አድርገ መመልከት የወቅቱን ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት ከእነመፍትሔው በትክክል ለመገንዘብ ሰፊ ዕድል ይሰጣል።

የሰሜን ምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታት ለውጡን የጀመሩት በቅድሚያ ለአርሶ አደሩ መሬት በማከፋፈል ነው፡፡ በዚህም አርሶ አደሩ ከማንኛውም ዓይነት ፊውዳላዊ የመሬት ሥሪት ነጻ እንዲወጣ አድርገዋል፡፡ መሬት የማከፋፈል እርምጃው አርሶ አደሩ ከአሽከርና ጌታ ግንኙነት ነጻ ወጥቶ በመሬት ተጠቃሚነት መብቱ ተጣምሮ ወደልማት እንዲገባ አድርጐታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የእርሻ ቤተሰቦች እኩል ጸጋ ይዘው በብቃት ለመፎካከር እንዲችሉ በር ከፍቷል። በዚህ የተነሳ በእነዚህ አገሮች ሚሊዮኖች በአምራችነትና በሻጭነት የሚወዳደሩና የሚያድጉበት፣ ስለዚህም ደግሞ መሠረተ-ሰፊ ተጠቃሚነት የሰፈነበት የገበያ ሥርዓት ሊፈጠር ችሏል፡፡ አሊስ አምስደን በኮሪያ የተካሔደውን የመሬት ክፍፍል ሩይዳ በማስመልከት፡-

> “በኮሪያ የነበሩት የአሜሪካ ዘማች ኃይሎች አርሶ አደሩ በአመጽ እየተነሳሳ ያቀረበውን ጥያቄ ለማለዘብ፣ በሰሜኑ ከፍል በነበረው የሶቭየት ሞዴል የተፈጠረውን መሰግለል ለመግታትና ወንድም ከወንድም ይተላለቅበት ለነበረው ጦርነት ተፈላጊውን ድጋፍ ለማሰባሰብ ሲሉ መሬት ወደማካፈል አመሩ፡፡ በዚህ የተነሳ ጃፓኖች በገጠር የጀመሩትን የለውጥ ሂደት /Reform/ እንደገና አንድ እርምጃ ከፍ በማድረግ ለአርሶ አደሩ መሬት አከፋፈሉ። የዚህ እርምጃ የረዥም ጊዜ ፋይዳ ከፍተኛ ሲሆን፣ ለውጡ በገጠር የተከማቸውን ሥራ የፈታ ካፒታል ከአራጣ አበዳሪነት ወደማኑፋክቸሪንግ እንዲዞር አስችሏል። ተራማጅ ያልነበረውን መደብ ደግሞ ከሥረ መሠረቱ ነቅሎታል፡፡ በተጨማሪም በምግብ አቅርቦት ረገድ የነበረውን ማነቆ በመፍታት ለዋጋ ግሽበት ምክንያት የሚሆኑ ግፊቶችን አርግቧል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር አድርጓል፡፡”[75] ትላለች፡፡

መሬት ማካፈል ይህን የመሰለ ተራማጅ ሚና የሚጫወት ከመሆኑ በተጨማሪ መሬት የተካፈሉት አርሶ አደሮች በቴክኖሎጂ የሚደግፉትው መንግሥት ሲያገኙ ደግሞ አርዎጅቧ

ከዚህም ልቆ የሚሔድ ልማታዊ ተፅዕኖ ማሳረፍ ይጀምራል፡፡ አርሶና አርብቶ አደሮቹን የሚደግፍ ዘመናዊ የኤከስቴንሽን አገልግሎት፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ፋይናንስ ከተሟላ አነስተኛዎቹ ማሳዎች ከሰፋፊ እርሻዎችም በላይ ምርታማ ይሆናሉ፡፡ ይህን ድምዳሜ በጥናት ላይ ተመሥርቶ ያረጋገጠው ጆ ስቱድዌል፡-

> "ለምሣሌ ሸንኮራ አገዳ በደንብ እንዲያድግ ከአንድ ዓመት ያላነሰ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በትራክተር አማካይነት በጥልቀት በታረሰ መሬት ላይ ሲተከል ይበልጥ ይመቸዋል፡፡ በመሆኑም በትላልቅና ሚካናይዝድ እርሻዎች ላይ የሚለማ ሸንኮራ የበለጠ አዋጭ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን በታይዋንና ቻይና አነስተኛ የአርሶ አደር ማሳዎች ላይ በሚተከል ሸንኮራ የሚገኘው የምርት መጠን፣ ከቅኝ አገዛዝ በፊትም ሆነ በኋላ በፊሊፒንስ ወይም በኢንዶኔዥያ ከነበሩ ሰፋፊ እርሻዎች በ50 በመቶ የበለጠ ነበር፡፡ ማሌዥያ፣ ኬንያና ዚምባቡዌን በመሳሰሉ የእስያና የአፍሪካ አገሮች የነበሩ የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች፣ ሰፋፊ እርሻዎችን ከጀመሩ በኋላ ከአነስተኛው አርሶ አደር እርሻ ውድድር እንዳያጋጥማቸው አርሶ አደሩን ሆን ብለው ያዳከመት ነበር፡፡ በተጨማሪም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለትልልቅ እርሻዎች ከፍተኛ ድጎማ ይሰጡ፣ በታክስ ከሚሰበሰብ ገንዘብም መሠረተ-ልማት ይገነቡላቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ሰፋፊ እርሻዎች አዋጭ ቢሆኑ ኖሮ ይህ ሁሉ ድጎማ ባላስፈለገ ነበር"[76] ይላል፡፡

ይህን ሩቅ ሳንሄድ በምዕራብ አማራ ወይም ትግራይ በሰሊጥ አምራችነት የተሰማሩ አነስተኛ ገበሬዎችን ምርታማነት ከሰፊ እርሻዎች በማነጻጸር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በእነዘህ አካባቢዎች አነስተኛ ባለሀብቶች በሔክታር ከስድስት እስከስምንት ኩንታል ሰሊጥ ሲያገኙ በትልልቅ እርሻዎች ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ግን በሔክታር ሶስት ግፋ ሲል ደግሞ አራት ኩንታል ብቻ ያመርታሉ፡፡ በቅርበ በወንጅ ስኳር ፋብሪካ የታዘብኩት ጉዳይም ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ ያደርሳል።

የወንጂ ስኳር ፋብሪካ በአንድ በኩል በራሱ ሰፋፊ ማሳዎች በዘመናዊ መንገድ በሚያመርተው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ራሱ ፋብሪካው በገነባላቸው መሠረተ-ልማት እየታገዘ በሚያመርቱ አነስተኛ አርሶ አደሮች ሸንኮራ አገዳ በመቶ ሜትር ስኳር የሚያመርት ተቋም ነው፡፡ የፋብሪካው መሪዎች ባዘጋጁልን ጉብኝት ሂደት አርሶ አደሮቹ በሔክታር ምን ያህል ኩንታል ሸንኮራ እንደሚያመርቱ ላቀረብኩት ጥያቄ ጉብኝቱን ይመራልን የነበረው ወጣት መሐንዲስ በጣም የተሻሉት ጥቂት አርሶ አደሮች እስከ ሦስት ሺህ ኩንታል ሸንኮራ ሲያመርቱ በአማካይ ደግሞ 1500 ኩንታል እንደሚያመርቱ ገለጸልን፡፡ በአንጻሩ በፋብሪካው ዘመናዊ እርሻ ደግሞ

በአማካይ የሚመረተው 1200 ኩንታል እንደሆነ ተረዳን፡፡ ወጣቱ ሙያተኛ ከጠበቅኩት በላይ የሁኔታዎች እውቀት የነበረው፣ ሥራውን በደንብ የሚያውቅና እንደአንዳንድ የመንግሥት ኃላፊዎች የራስን የሥራ ውጤት የማጉን ዝንባሌ ያልነበረው በመሆኑ ባቀረበልኝ መረጃ ብዙም አልተጠራጠርኩም፡፡ ይህም የራሳችን አገር ልምድም የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ በርግጥም ከሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች በላይ ምርታማ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡

ጆ ስቱድዌል እንደሚለው ይህ የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ የምርታማነት ብልጫ ካለምክንያት የሚመጣ አይደለም፡፡ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩት መሬት የተካፈሉ አርሶ አደሮች፣ ከሰፋፊ እርሻ ገበሬዎች ይልቅ ሰፊ የጉልበት ተጠቃሚነት ስላላቸው ነው። ገበሬዎቹ ባላቸው ጉልበት ማሳቸውን እንደጓሮ እርሻ ተንከባክበው ስለሚይዙ ከፍተኛ የምርት ጭማሪ ያመጣሉ። የአትክልተኛ የጉልበት እንክብካቤ ያልተለያቸው የአትክልትና አበባ አጸዶች ማራኪ እንደሚሆኑት ሁሉ፣ አርሶ አደሩ ብዙ ጉልበት የሚያፈስባቸው አነስተኛ ማሳዎችም ከሰፋፊ እርሻዎች የበለጠ ምርታማነት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ የአነስተኛ ማሳዎች ምርታማነት በእጅጉ ጨምሮ ለኢንዱስትሪያዊ ዕድገት መፋጠን ተፈላጊ የሆነውን ጥሬ ዕቃ ለማሟላት ያስችላሉ፡፡ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው ሰብዓዊ ኃይል፣ የኑሮ ውድነት የማይጫነው የኢንዱስትሪ የሥራ ኃይል እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ፋይዳ ያለውን የምግብ እህል በተመጣጣኝ ዋጋ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ አርሶ አደሮቹ ከምርት ሽያጭ በሚያገኙት ገንዘብ የኢንዱስትሪ ምርቶች ሸማች በመሆን ለዘርፉ ልማት የሚያስፈልገውን የአገር ውስጥ ገበያም ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

ይህ የሰሜን ምሥራቅ እስያ ነብሮች ተብለው በተሠየሙት አገሮች ሁሉ የታየ ነው፡፡ ከጃፖን እስከታይዋን፣ ከኮሪያ እስከቻይና መሬት ያላካፈለና አነስተኛውን አርሶ አደር ደግፎ ሀብት ፈጣሪ በማድረግ አገሩንና ህዝቡን ለከፍተኛ ልማት ያላበቃ አገር የለም፡፡ በአንጻሩ በደቡብ ምሥራቅ እስያዎቹ ኢንዶኔዥያ፣ ማሌዥያ፣ ታይላንድና ፊሊፒንስ የመሬት ክፍፍል አልተካሔደም፡፡ አርሶ አደሩም ከጭሰኝነትና ከፊል ጭሰኝነት ነጻ አልወጣም፡፡ የሚደግፈው የተሟላ የኤክስቴንሽን አገልግሎትም አላገኘም፡፡ በዛው ልክ በእነዚህ አገሮች የዳበረ ኢንዱስትሪያዊ ልማትና የበለጸገ ሕብረተሰብ ግንባታ ብሎ ነገር የቀን ሕልም ሆኖ ቀርቷል፡፡

ከገጠር ልማት አኳያ ኢትዮጵያ የመረጠችው መንገድ ከደቡብ ምሥራቅ ይልቅ ከሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ከደርግ ዘመን ጀምሮ ከሞላ ጐደል አርሶ አደሩን ያሳተፈ የመሬት ክፍፍል ተካሂዷል፡፡ በዚህ ላይ አሁን ባለው መንግሥት ደግሞ የገበሬውን ምርታማነት ለማሳደግ የማያቋርጥ ድጋፍ እየተደረገለት ይገኛል፡፡ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ እንዲቀርብ፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የብድር አቅርቦትም እንዲሟላ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ በመነሳት ሲታይ፣ ልክ እንደሰሜን ምሥራቅ እስያ ነብሮች በኢትዮጵያም ለዘላቂ ብልጽግና ተፈላጊ

የሆነው አንዱ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ ተሟልቷል፡፡ ከዚህም አልፎ ለውጡ ዴሞክራሲን በማስፈን ጭምር የተካሔደ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ገጠሮች ከእስያውያን በተሻለ ደረጃ ለዘላቂ ፍትሃዊ ዕድገት አስተማማኝ መሠረት የተጣለባቸው እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከልምድ ተገቢው ትምሕርት እየተወሰደ የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ልማት ይበልጥ ወደላቀ እሴት ፈጠራ እንዲሸጋገር ማድረግ ከተቻለ፣ በእርግጥም በኢትዮጵያ ለዘላቂ ልማትና የበለጸገ ሕብረተሰብ ግንባታ የሚያስፈልገው የገጠር ቅድመ ሁኔታ ተሟልቷል ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ከደቡብ ምሥራቅ ይልቅ ሰሜን ምሥራቅ እስያን እንድትመስል የሚያደርጋት የገጠር ሁኔታ እጅግ በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል ነው፡፡ አገሪቱ በኢንዱስትሪ ልማት መስክ የምትከተለው ፖሊሲና ስትራቴጂ የጠራ እስከሆነ ድረስ፣ የገጠሩ ሁኔታ በእርግጥም እጅግ በጣም ጥሩ መነሻ ተደርጉ ሊወሰድ የሚችልና የሚገባው ነው፡፡ ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ ገጠሩን ከመለወጥ አኳያ ያለባት ሥራ ተጠናቋል ማለት አለመሆኑ ሊስተዋል ይገባዋል፡፡ ይልቁንም አሁን ያለውን ዋነኛ የዕድገት ምንጭ አሟጦ ለመጠቀምና ቀጣዮቹን የግብርና ዕድገት ምንጮች ደግሞ በትክክል ለይቶ ለማልማት ከባድ ትግልና ጥረት ይጠይቃል፡፡

በኢትዮጵያ አሁን ያለው ዋነኛ የዕድገት ምንጭ የሰብል ምርት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው የዕድገት ዕድል ገና ያልተሟጠጠ ወይም ተገቢው የምርታማነት ቅልጥፍና (Efficiency) ደረጃ ላይ ያልደረሰ ነው፡፡ በአገራችን አሁን በሔክታር የሚመረተው አማካይ ምርት ሃያ አራት ኩንታል ብቻ ነው፡፡ ይህን ቢያንስ ወደ አርባና አምሳ ኩንታል ማድረስ ይገባል፣ ይቻላልም፡፡ በመሆኑም እዚህ ደረጃ ላይ እስኪደረስ ዋናው የግብርና ዕድገት ምንጭ የሰብል ምርት መሆኑ አይቀርም፡፡ በምሣሌያዊ አገላለጽ በዚህ ረገድ እስካሁን የተደረሰው በቀላሉ የሚሸመጠጠውን (Low Hanging Fruits) መሰብሰብ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቀውና ሁሉንም አርሶ አደሮች ወደምርጥ አምራቾች የማድረሱ ከባድ ሥራ ገና በቅጡ አልተከናወነም፡፡ አርሶ አደሩን ከፍተኛ ዋጋ ወደሚያስገኙ ምርቶች የማሸጋገር ሥራውም ገና በውል አልተጀመረም፡፡ ኢህአዴግ በ2002 ዓ.ም. ባካሔደው ስምንተኛ ጉባዔ የተወሰነውና ሁሉንም አርሶ አደር ምርጦቹ ወደደረሱበት ደረጃ የማድረስ ጎብ ከስምንት ዓመታት ርብርብ በኋላም ገና ያልተሳካ መሆኑ እንደገና ብዙ ማሰብና መሥራትን የሚጠይቅ ነው፡፡

ይህን እያሳኩ ቀጣዮቹን የግብርና ዕድገት ምንጮች ለይቶ እነዚህን ከወዲሁ በብቁ ዝግጅት ማልማት ደግሞ ሌላው ፈተና ነው፡፡ ከሰብል ምርት ቀጥሎ በገጠር መተማመኛ የሚሆኑት አዳዲስ የዕድገት ምንጮች በአነስተኛው አርሶ አደር የሚለሙ የአትክልት ፍራፍሬና ደን፣ እንዲሁም የእንሰሳት ሀብት ልማትና እነዚህን የሚደግፍ የመስኖ፣ የምርምር፣ የገበያ መሠረተ-ልማት ዝርጋታ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው ሁኔታ ገና ምኑም ነገር በቅጡ ያልተጀመረበት ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ መስክ ከተሠራው ይልቅ ያልተሠራው እንደሚልቅ

ላይዘነጋ፣ የግብርናና ገጠር ልማቱ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነባር ግኝ ስኬታማ የልማት ጅምር እንደሆነ ማስተዋልና ለላቀ ለውጥ መሥራት አማራጭ የለላው ይሆናል። ይህም ሆኖ ኢህአዴግ በዚህ መስክ ያለው መልካም አፈጻጸም እንደጥሩ መነሻ ሊወሰድ የሚችል ነው። ሆኖም ልማቱን በመስክ ከሚታዩ ችግሮች እያላቀቁ፣ በተጀመረው አቅጣጫ አጠናክሮ ማሳካት እንዲቻሉን ረዥም ርቀት ሊወስዳትና ለኢንዱስትሪ መስፋፋት የሚያመች መሠረት ሊጥል ይችላል።

ልክ እንደግብርናው ሁሉ ኢትዮጵያ ከኢንዱስትሪ ልማት አኳያ የምትገኝበትን ሁኔታ፣ አሁንም ከምሥራቁ የዓለማችን ክፍል ልዩ ልዩ ተሞክሮዎች በመነሳት እያነጻጸሩ መመልከት በዚህም መስክ የተሠራውንና የሚቀረውን ለመገንዘብ ያግዛል። ከኢንዱስትሪ ልማት አኳያ በምሥራቁ ዓለም አሁንም ሁለት ልምዶች አሉ። አንደኛው የሰሜን ምሥራቅ እስያ ነብሮች ስኬታማ የኢንዱስትሪ ልማት ልምድ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ኢንዱስትሪያዊ ልማትን ያዳከመውና በአጭር ያስቀረው የደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች ልምድ ነው። በሰሜን ምሥራቁ ከፍል ከስኬታማ የኢንዱስትሪ ልማት አኳያ ተጠቃሽ የሆኑት ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋንና አሁን ደግሞ ቻይና ናቸው። የቶሚላ የኢንዱስትሪያዊ ትራንስፎርሜሽን ባለማካሔድ ደረጃ ደግሞ አሁንም የደቡብ ምሥራቅ እስያዎቹ የማሌዥያ፣ የኢንዶኔዥያ፣ የታይላንድና የፊሊፒንስ ልምድ ይገኛል። ሁለቱ ጐራዎች በገጠር መሬት ከማካፈል ጀምሮ አርሶ አደሩን እስከመደገፍ ድረስ በዘለቀው መንገዳቸው የተለያዩ እንደነበሩት ሁሉ፣ ራሱን ኢንዱስትሪን በማልማት ጉዳይ ላይም መሠረታዊ ልዩነት ነበራቸው።

የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች የነደፉትን የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ያስፈጸሙት በወሳኝነት በራሳቸው ዜጐችና አገራዊ ባለሀብቶች በመተማመን ነበር። ሰሜን ምሥራቆቹ አገራዊ ኢንዱስትሪያዊ ባለሀብቶችን እንደአዲስ ከመፍጠር ጀምሮ በጥብቅ ዲሲፕሊን በመምራትና ይከመት ሲፈጽሙ ደግሞ ተጠያቂ በማድረግ ልማቱን ዳር ለማድረስ የቻሉ ናቸው። መንግሥታቱ በዚህ ቅኝት እየተመሩ ባለሀብቶቹን ከከረሙበት የኪራይ ሰብሣቢነት አረንቋ በማውጣት ወደልማት እያስገቡ ተገዘዋል። የተሳካ አገራዊ የካፒታል፣ የቴክኖሎጂ፣ የመሠረተ-ልማት፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የሰበዓዊ ኃይል አቅም ግንባታ አካሂደዋል። በዚሁ ልክ ደግሞ ከዝቅተኛ ደረጃ ተነስተው ከአምሳ ባልበለጡ ዓመታት ከፍተኛ ብልጽግና ወዳለው ሕብረተሰብ ተሸጋግረዋል። በእነዚህ አገሮች የነበሩ መንግሥታት ለውጡን ገና አለሑዱ ብለው የጀመሩት ባለሀብቶችን ጨምሮ ለመላው ህዝባቸው በልማትና በኢንዱስትሪ ልቆ የመገኘት ፍላጐት እንዳላቸው በማሳወቅ ሲሆን፣ ሁሉም ዜጐች ይህን ተገንዝበው የዚህ ታላቅ አገራዊ ራዕይ ተጋሪዎች እንዲሆኑም ጥረት አድርገዋል።

በጣም ፈጣን ልማት እውን በሆነባት ኮሪያ ልማታዊ መንግሥት ሂደቱን የጀመረው ከጥገኛ ባለሀብቶች ጋር በመጣላት ነበር። ብዙም ሳይቆይ ባለሀብቶቹ ከጥገኝነት ወጥተው

በልማት አጋርነት የሚሰለፉ ከሆነ እንደሚደግፋቸው በማሳወቅ ግልጽ የልማት ግብ ሰጥቶ እንዲሰማሩ ማድረግ ጀመረ። ይህን በማስመልከት የኮሪያ ፈጣን ልማት መሐንዲሶች ከነበሩት አንዱ የሆነው አ ዎን ቾል "The Korea Story" በሚለው መጽሐፉ፣ እ.ኤ.አ. በ1962 ከተዘጋጀው የአምስት ዓመት እቅድ ጋር በማያያዝ፡-

> "በመጀመሪያው አምስት ዓመት የኮሪያ የልማት እቅድ በጥበቅ ይታመን የነበረው የፋብሪካዎች ግንባታ የግሉ ሴክተር ዋነኛ ተግባር እንደሆነ ነው። ይህም ሆኖ በዚህ ወቅት ኮሪያ ይህን ለማሳካት ሊሰማሩ የሚችሉ ጥቂት ልማታዊ ቅኝት ያላቸው ሰዎች /Entreprenuers/ ብቻ የነበሯት አገር ነበረች። ከዚህም ብሶ ከባለሀብቶቹ መካከል ብዙዎቹ ካለአግባብ በመጠቀም ቅሌት ታስረው ንብረታቸውም ተወርሶ ነበር። አብዮታዊው መንግሥት (በኮሪያም ልማታዊ መንግሥቱ አብዮታዊ መንግሥት ይባል እንደነበር ልብ ይሏል) ባለሀብቶቹ በአምስቱ ዓመት እቅድ ከተሳተፉ ሊለቀቁ እንደሚችሉ ካሳወቀ በኋላ፣ ይህን ጥሪ ተቀብለው ወደልማቱ ገቡ። መንግሥትም ከእነርሱ ወርሶት የነበረውን በሕገ-ወጥ መንገድ የሰበሰቡትን ሀብት በአቅዱ ማጠቃለያ ዓመት በአከስዮን መልክ እንዲመለስላቸው አደረገ።"[77] በማለት ገልጾታል።

የኮሪያ ልማታዊ መንግሥት የአገሪቱ ባለሀብቶች የተቀመጠውን አቅጣጫ ተቀብለው ወደልማት ለመግባት መዘጋጀታቸውን እያረጋገጠ ተልዕኳቸውን ያሳኩ ዘንድ የፋይናንስና የመሠረተ-ልማት አገልግሎት በማቅረብ ረድቷቸዋል። ጥናትና ምርምር በማካሔድና ገበያ በማፈላለግ አግዟቸዋል። የወጭ ኩባንያዎች ቴክኖሎጂን እንዲያጋኙዋቸው አስገድዶላቸዋል። ለምሣሌ በአንድ ወቅት ሚትሱቢሺ የተባለውን የጃፓን ኩባንያ "በኮሪያ መፈጠር በጀመረው የገበያ ዕድል ለመጠቀም ከፈለገ፣ ገና በጀማሪነት ደረጃ ላይ ለነበረውና ሐንዳይ ለሚባለው ኮሪያዊ የመኪና አምራች ኩባንያ ቴክኖሎጅውን እንዲያካፍል" ማስገደዱን ስቱድዌል (2013) ይገልጻል።

ይህን የመሰለው ድጋፍ ከሞላ ጎደል በሁሉም ልማታዊ መንግሥታት ዘንድ የተፈጸመ ነው። ዘግይተው የለመኑ ቻይናዎችም ቢሆኑ፣ የአገራቸውን ሰፊ ገበያ በመሻት ወደእነርሱ የሚመጡትን የምዕራቡ ዓለም ኩባንያዎች በሚያማልል ገበያቸው ተመክተው ወይም በራሳቸው ልዩ ልዩ ስልቶች በመታገዝ ሳይወዱ በግድ ቴክኖሎጅ እንዲያጋሯቸው ሲያስገደዱ ቆይተዋል። ዛሬ ለቻይና ሸማቾች በየዓመቱ ከሚቀርቡት ከሃያ ሚሊዮን በላይ መኪኖች እጅግ አብዛኞቹ የሚመረቱት በቻይናውያን ነው። ስምንት መቶ ሚሊዮን የኢንተርኔት ተጠቃሚ እንዲኖር ያስቻሉት ኮምፒውተሮችና ሞባይል ስልኮች፣ መደበኛና እንደጥይት ሲወረወሩ

የሚታዩት ቻይና ሰራሽ ባቡሮች በዚሁ ድጋፍና አመራር እውን የሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግር ውጤቶች ናቸው፡፡ ባለሀብቱን በጠንካራ ዲሲፕሊን የመምራት፣ የመግራትና የመደገፍ አካሔድ ለፈጣን ኢንዱስትሪያዊ ልማት ብቻ ሰሳይሆን ለቴክኖሎጅ ሽግግርም አማራጭ ያልነበረው ነውና፡፡

የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች በአጭር ጊዜ ኢንዱስትሪያዊ እመርታ ለማምጣት የቻሉት፣ መንግሥት የራሱን አገር ባለሀብት ከመገንባት ጐን ለጐን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ዋነኛ ልማታዊ መሣሪያ አድርጐ ስለተንቀሳቀሰ ነው፡፡ የውጭ ካፒታል በተመረጡ መስኮች ብቻ፣ ለዚያውም በከባድ ቁጥጥር እንዲንቀሳቀስ ያደረጉት የምሥራቅ እስያ ነብሮች፣ ከምዕራብ ኩባንያዎች ጋር የጋራ ሽርክና /Joint Venture/ ያላቸው ኩባንያዎች ስለተፈጠሩ ብቻ "የቴክኖሎጅ ሽግግር" ይፈጸማል የሚል ብዥታ አልነበራቸውም፡፡ የኢንዱስትሪ ፖርኮችን በመክፈት የውጭ ባለሀብቶች በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ ልብስ ሰፍቶ የመሸጥ ዕድላቸው እንዲሰፋ በማድረግም ኢንዱስትሪያላይዜሽንን እውን እናደርጋለን ብለው ገምተው አያውቁም፡፡ ልብስ መስፋት እንደቴክኖሎጂ ዘመን ያስቆጠረና የማይደበቅ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ሮኬት ሳይንስ አይደለም፡፡ ስለዚህም "የውጭ ካፒታል ልብስ ካልሰፋ በስተቀር አይሳካልንም" የሚል ብዥታን ገና ከጠዋቱ ያስወገዱት የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች፣ ጨርቅ ሰፍቶ ለመሸጥ የአሜሪካ ወይም የእንግሊዝ ባለሀብቶችን የሚጠብቁ አልነበሩም፡፡

በዚህ ላይ የውጭ ካፒታል በዘላን ባሕርዩ ትርፉ ያሽቆለቆለ ቀን፣ ከመጣበት በላቀ ፍጥነት ጓዙን ጠቅልሎ እንደሚወጣና ለቀውስ ሊዳርጋቸው እንደሚችል ለአፍታም ተጠራጥረው አያውቁም፡፡ ስለሆነም የውጭ ካፒታል በገዛ ፈቃዱ ቴክኖሎጂውን ያጋራናል ብለው በማመን የአገራቸውን የኢንዱስትሪ መሠረት ለመገንባት መና ከሰማይ እስኪወርድ አንጋጠው አልጠበቁም፡፡ መካከለኛ ገቢ እስኪደርሱ ቴክኖሎጂን በመኮረጅ፣ ወደከፍተኛ ገቢ ለመሸጋገር ደግሞ በምርምር ላይ ተመስርተው ቴክኖሎጂን በማመንጨት መወዳደር እንዳለባቸው አምነው፣ ለዚህ ሌት ተቀን ስለሠሩ የተሳካላቸው ናቸው፡፡ ፈጽሞ ለድርድር ሊያቀርቡት ባልሞከሩት የኤከስፖርት ዲሲፕሊን አቅጣጫ በመመራት ባለሀብታቸውን ዲሲፕሊን ያደረጉ፣ ብድር በወሳኝነት ለልማታዊ ፕሮጀክቶች እንጅ ለኪራይ ሰብሳቢ ፕሮጀክቶች አለመቅረቡን ያረጋገጡ አገሮች ነበሩ፡፡ የሰሜን ምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታት፣ በተለይ ደግሞ የደቡብ ኮሪያ ልማታዊ መንግሥት፣ የውጭ ባለሀብትን ስለያዘበት ጠበቅ ያለ አቅጣጫ የሚያብራራው ሐ ጁን ቻንግ፣ ይህን በማስመልከት፡-

> "የኮሪያ መንግሥታዊ ጣልቃ ገብነት አንዱ ይዘት የፖሊሲ አውጭዎች ስለውጭ ኩባንያዎች ከነበራቸው አተያይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የኮሪያ ፖሊሲ

አመንጭዎች በአገር ውስጥ ተቋማት የሚካሔድ የዳበረ ቴክኖሎጂ ኩረጃና ማላመድን ውጤታማ ለሆነ ኢንዱስትሪያዊ ልማት ቁልፍ ቅድመ ሁኔታ አድርገው ይመለከቱት ነበር:: ለእነርሱ ይህ በውጭ ካፒታል ላይ ጥብቅ የመንግሥት ቁጥጥር ማድረግ ማለት ነበር:: በዚህ ምክንያት ከ1962-1982 በነበሩት ዓመታት ከብድር በመለስ የውጭ ቀጥተኛ መዋእለ ንዋይ፣ ከአጠቃላዩ የውጭ ካፒታል ፍሰት የነበረው ድርሻ እዚህ ግባ የማይባል 5% ብቻ ነበር:: (አምስደን፣ 1989፣ ገጽ 9 ሠንጠረዥ5) ... በኮሪያ ፖሊሲ አውጭዎች ዘንድ እንደሊበራል የሚቆጠረውና የውጭ ካፒታልን ስለመፍቀድ ዘግይቶ የወጣው ሕግም ቢሆን፣ መንግሥት እስከፈለገ ድረስ የውጭ ቀጥተኛ መዋእለ ንዋይ፤ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች፣ ከለጋ ኢንዱስትሪዎች፣ የውጭ ጥሬ ዕቃ በብዛት ከሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች፣ የፍጆታ (በተለይ ደግሞ የቅንጦት) ዕቃዎች ከሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች፣ ከበካይ ኢንዱስትሪዎችና ከእርሻና አሳ ልማት፣ በጥቅሉ ደግሞ ከሁሉም ኢንዱስትሪዎች ስምሪት ሊገደብ እንደሚገባ ያብራራል:: የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ሲፈቀድም የውጭ ባለሀብቶች ነጻ የንግድ ቀጠና በተባሉ ቦታዎች ከተሰጣቸው መለስተኛ ፈቃድ በመለስ አብላጫውን የባለቤትነት ድርሻ መያዝ እንዳይችሉ በተግባር የተከለከለ ነበር:: በንግድ ቀጠናዎች የነበሩትን ጨምሮ፣ በኮሪያ ከነበሩት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች መካከል ስድስት በመቶው ብቻ፣ ሙሉ በሙሉ የውጭ ተቀጥላ ኩባንያዎች ነበሩ:: ከባለቤትነት ይዞታም አኳያ በሜክሲኮ አምሳ በመቶ፣ በብራዚል ደግሞ ስድሣ በመቶ ከነበረው ተነጻጻሪ አኃዝ ጋር ሲተያይ፣ መንግሥት በውጭ ቀጥተኛ መዋእለ ንዋይ ላይ የነበረው ቁጥጥር ከፍተኛ ነበር:: (ኢቫንስ፣ 1987፣ ገጽ 208):: ከውጭ ቀጥተኛ መዋእለ ንዋይ ይልቅ የላቀ ትኩረት ይሰጠው የነበረው የቴክኖሎጂ ፈቃድ አሰጣጥ /Licensing/ ሳይቀር ከባድ ቁጥጥር የሚደረግበት ነበር:: ለምሣሌ የውጭ ካፒታልን ስለማስገባት በቅርቡ የተሻሻለው ሕግ ከቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ አኳያ ተስፋ የሚጣልባቸው የአገር ውስጥ ሙከራዎች ባሉበት ጊዜ ሁሉ፣ ለውጭ ቴክኖሎጂ ፈቃድ መስጠትን ይከለክላል:: ይህም እንደገና ሚዛኖውንም ኢንዱስትሪ የሚመለከት ሊሆን ይችላል።[78] (አጽንኦት የተጨመረ)" ይላል::

ከዚህ ምርጥ የሰሜን ምሥራቅ እስያ ልምድ በተለየ ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱት የደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች ደግሞ ወደኢንዱስትሪ ልማት የማያመራውን መንገድ ተከትለዋል። ከሁሉ በፊት አንዳቸውም የረባ የመሬት ስሪት ለውጥ በማካሔድ አርሶ አደሩን ነጻ ለማውጣት

አልሞከሩም። በተጨማሪ በኢንዱስትሪ መስክ ቴክኖሎጂ የመኮረጅም ሆነ የማመንጨት ሥራውን ለውጭ ባለሀብቶች መልካም ፈቃድ በመተው የጀመሩ ነበሩ። የውጭ ባለሀብቶች ደግሞ ብዙ የለፉበትንና በከባድ ምስጢርነት የሚጠብቁትን ቴክኖሎጂ ለማንም የማካፈል ፍላጐትም ሆነ ብቹታ አልነበራቸውም። እንኳን አዲሱንና የተራቀቀውን ቴክኖሎጂ፣ ዘመን ያለፈበትን ጭምር በመደበቅ የትርፍ ምንጭ ማድረግ ከቻሉ ዓይናቸውን የማያሹናቸው። መንግሥትም ይህን ተገንዝቦ አስገዳጅ ሁኔታ አላስቀመጠባቸውም ነበር። ይህን ያልተገነዘቡትና ቢገነዘቡም ደግሞ ያልተጠነቀቁት ደቡብ ምሥራቅ እስያውያን፣ አገራቸውን በረጋግደው ቢከፍቱም በቴክኖሎጂ ግን ወደፊት መራመድና የበለጸገ ሕብረተሰብን መቀላቀል ተስኗቸው ቀረ።

እነዚህ አገሮች ቴክኖሎጂ ለማግኘት ያግዙናል ብለው የተማመኑባቸው የጋራ ሽርክና ኩባንያዎች አስገዳጅ ሁኔታ በሌለበት የቴክኖሎጅ ሽግግር መሣሪያ ሆነው ሊያገለግሉዋቸው አልቻሉም። በመሆኑም መሠረታዊ ብቃት (Core Competence) በሚጠይቁት ፋብሪኬሽንና በመሳሰሉት የኢንጅነሪንግ ምርቶች ላይ ሳይሆን፣ በሪል ስቴትና ሆቴሎች ግንባታ፣ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማትና ግፋ ቢል በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ላይ የታጠረው የደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች ጉዞ ወንዝ የማያሻግር እንደሆነ ለዓመታት ዘለቀ። አልፎ ተርፎም በእሴት ፈጠራና ሌሎች ልማታዊ መስኮች ከተሰማሩት ይልቅ፣ በተለይ በሪል ስቴት ግንባታ ላይ የተሰማሩት ኩባንያዎች የብድር ቅድሚያ በማግኘታቸው ልማታዊ የሆኑ ጅምሮች ሳይቀር ተጨናገፉ። ሰሜን ምሥራቆቹ ከባድ የኤክስፖርትና የልማታዊ ፋይናንስ ዲሲፕሊን የነበራቸውን ያህል፣ በደቡብ ምሥራቆቹ ዘንድ ግን ይህ አይታወቅም ነበር።

ማሌዥያን በዚህ ወቅት የመራው የጠቅላይ ሚኒስትር ማህቲያር መንግሥት፣ በልዩ ትኩረት ያስገነባትና ፕሮቶን የተባለች መኪና ታሪክ ይህን ያሳያል። ይህች ተስፋ የተጣለባት መኪና ከማሌዥያ ገበያ ስድሣ በመቶ ድርሻ ከመያዝ በተጨማሪ በአውሮፓ ገበያ ዘልቃ መግባት ጀምራ ነበር። ይሁንና ለባለቤቶቿ ብቻ ተከልሎ የሞኖፖል ትርፍ ምንጭ ለሆነላቸው የአገር ውስጥ የገበያ ድርሻዋ ቅድሚያ የሰጠው የማህቲያር መንግሥት፣ የኤክስፖርት ዲሲፕሊንን ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቁረጡ፣ እዚያው የማሌዥያ ገበያ ላይ እንደተወሰነች ጀንበር ጠልቆባታል። በዚህ የተነሳ ተወዳዳሪ የመሆን ትልቅ ተስፋ የነበራት ፕሮቶን ማሌዥያን በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ማድረግ ሳትችል ቀረች። የኢንዶኔዥያ መንግሥት በበኩሉ የማሌዥያን አቅጣጫ በመከተል ያስገነባት አስትራ የተባለች መኪናም ብትሆን፣ ተከልሎ በተሰጣትና ከፍተኛ የትርፍ ምንጭ ሆኖ ባገለገላት የአገር ውስጥ ገበያ እንድትታጠር በመደረጉ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ተስኗታል። በአንጻሩ ከዚህ በተመሳሳይ ጊዜ ከጃፓን ኩባንያዎች የግድ እንዲተላለፍ በተደረገ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ለኤክስፖርት ገበያ ማምረት የጀመሩት የኮሪያ ኩባንያዎች

በየዓመቱ ከአምስት እስከስድስት ሚሊዮን መኪኖች ለዓለም ገበያ ያቀርባሉ፡፡ በትንሹ ከመቶ ቢሊዮን ዶላር የማያንስ የውጭ ምንዛሬም ያስገኛሉ፡፡ ይህ የኮሪያ ታሪክ የኤክስፖርት ዲሲፕሊን የውጭ ምንዛሬ ከማስገኘት ጠቀሜታውም በላይ የአንድ አገር ምርቶች ከዓለም ገበያ በሚገኝ የጥራት መረጃ ያለማቋረጥ እንዲሻሻሉና ለተወዳዳሪነት ሊበቁ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡

ከዚህ አጭር መረጃ የደቡብ ምሥራቅ እስያውያን የውጭ ካፒታል አያያዝና አመራር ከሰሜኖቹ የተለየና ደካማ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ደቡቦቹ የውጭ ካፒታል በራሱ ተነሳሽነት ቴክኖሎጂ ያካፍለናል ብለው የሚጠብቁ ነበሩ፡፡ በ20ኛው ክፍለ ዘመን እየኖሩ፣ ከመቶ አምሳ ዓመታት በፊት እንግሊዞችን አስገድደው ቴክኖሎጂ ለመካፈል ጥረት ካደረጉት ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር የማይነጻጸር አቋምና የመማር ሥነ-ልቦና ነበራቸው፡፡ ኮሪያውያን በተሳካ ደረጃ ያስገደዱትን ሚትስቡሽ ኩባንያ እንኳ አጥብቀው መያዝ የተሳናቸው ነበሩ፡፡ ደቡብ ምሥራቆቹ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን በጠንካራ የኤክስፖርት ዲሲፕሊን ከመምራት ይልቅ፣ ለአገልግሎት ዘርፉ ሰፊ ቦታ በመስጠታቸው፣ እንደታይላድ ዓይነቶቹ የቱሪዝምና የወሲብ ኢንዱስትሪው የላቀ ከብደት ያገኘባቸው አገሮች ሆነው ቀርተዋል፡፡ እነዚህ አገሮች መሬት ባለማካፈል ከፈጸሙት የመጀመሪያ ኃጢአት በተጨማሪ፣ በኢንዱስትሪ ልማትና በፋይናንስ ልማታዊ ሥምሪት ላይ ደጋግመው በፈጸሙዋቸው የፖሊሲ ስህተቶች ምክንያት የመካከለኛ ገቢ ወጥመድን ማለፍ እንደተሳናቸው ቀርተዋል፡፡

ይህን የሰሜንና የደቡብ ምሥራቅ እስያ ልምድ እንደማነጻጸሪያ በመጠቀም ኢትዮጵያ በየትኛው አቅጣጫ እንደምትጓዝ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በምርጫ ደረጃ እስከ አሁን ያለው የመንግሥት ይፋዊ አቋም፣ በአርባና አምሳ ዓመታት ኮሪያና ታይዋን የደረሱበት ደረጃ ላይ መድረስ ነው፡፡ ወደዚህ ለመድረስ አሁንም የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች ያደረጉትን ሁሉ እየፈጸምን መጓዝ እንደሚገባ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ረገድ በመለስ ጊዜ ጥርት ብለው የተቀመጡ አቅጣጫዎችና መንገድ አመልካቾች ሁሉ የእነማሌዥያን ሳይሆን፣ የእነደቡብ ኮሪያን አቅጣጫ እንደምንከተል የሚያመላክቱ ነበሩ፡፡ ይህ አቅጣጫ በጥብቅ ተይዞ ወደዚህም መሥራት ተጀምሮ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ጅምር ብቻ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ልማትን በዋነኛነት የምንያያዘው ከእንግዲህ በመሆኑ፣ ይህን መሠረታዊ ተግባር ለማሳካት ከተያዙ አቅጣጫዎች በመነሳት ሂደቱን መመርመር በየትኛው አቅጣጫ እየተጓዝን እንደሆነ ለመገንዘብ ያስችላል፡፡

ፋብሪኬሽንና ማኑፋክቸሪንግን የማስፋፋት ፈተና፣

በአጠቃላይ ስለኢንዱስትሪ ልማት ሲታሰብ ማኑፋክቸሪንግን ስለማስፋፋት መሆኑ አያከራክርም፡፡ የማኑፋክቸሪንግ መስፋፋት ደግሞ አንድም ፋብሪካዎችን ከውጭ በመግዛት አለያም በአገር ውስጥ እያመረቱ በመትከል ብቻ የሚሳካ ተግባር ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ

አንድ አገር በኢንዱስትሪ በልጽጓል የሚባለው ብዙ ፋብሪካዎች ስላሉት ሳይሆን የፋብሪኬሽን ወይም ፋብሪካዎች የመሥራት አቅም የገነባ ሲሆን ነው። ፋብሪካ የመሥራት ችሎታና አቅም የሌለው በኢንዱስትሪ የበለጸገ አገር የለም። ፋብሪካ የመሥራት አቅም ያዳበረ አገር ብዙ ትንንሽ፣ መካከለኛና ከዚህም አልፎ ትልልቅ ፋብሪካዎችን ለማምረት ይችላል። ይህን አቅም የገነባ አገር፣ ሌሎች ቢያግዙትም ባያግዙትም፣ ከሌሎች ጋር በገበያ ቢተሳሰርም ባይተሳሰርም፣ በወሳኝነት ራሱን ችሎ የኢንዱስትሪ ልማቱን ለማስፋፋት ይችላል። ከዚህ አኳያ ሲታይ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ማዕከሉ ፋብሪኬሽን ወይም ጠንካራ የኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ብቃት ነው ማለት ይቻላል።

በእርግጥ ይህን የመሰለው ፋብሪካዎችን የመገንባት አቅም በአንዴ ዘሎ የሚደረስበት አይደለም። ደረጃ በደረጃ የተከማቸ አቅም በመፍጠርና ከአንድ የብቃት ደረጃ ወደሌላው ያለማቋረጥ በመሸጋገር የሚፈጠር ነው። መጀመሪያ ግብርናን በማልማትና ተፈላጊውን የካፒታል ከምችት በመፍጠር፣ በዚህ ሂደት ፋብሪካዎችን እየገዙ ነገር ግን ደግሞ መሠረታዊ ባሕርያቸውን እያጠኑና እየኮረጁ በማስፋፋት፣ የማታ ማታ ደግሞ የራስን ቴክኖሎጂ የማመንጨት ብቃት በመገንባትና ይህንኑ ያለማቋረጥ በማዳበር የሚፈጸም ነው። መለስ ዜናዊ ደጋግሞ እንደገለጸው የመካከለኛ ገቢ ከፍተኛ ደረጃ ወይም የዜጐች የነብስ ወከፍ ገቢ አምስት ሺህ ዶላር እስኪደርስ ቴክኖሎጂን በሰፊው በመኮረጅ የሚፈጸም ነው። ከዚህ በላይ በነፍስ ወከፍ ገቢ ደረጃ ወደኢሥር ሺህ ዶላር ወይም ወደከፍተኛ ገቢ ሕብረተሰብ ለመሸጋገር ደግሞ ቴክኖሎጂን በማመንጨት መወዳደር ሲቻል ብቻ የሚገነባ ብቃት ነው። መነሻ መሠረቱ ቴክኖሎጂ መኮረጅ ቢሆንም፣ በዚህ ብቻ ወደዳበረና የበለጸገ ሕብረተሰብ ደረጃ ለመድረስ ስለማይቻል ከወዲሁ ቴክኖሎጂ የማመንጨት ዙሪያ መለስ ብቃትን ደረጃ በደረጃ በመገንባት የሚሳካ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ አስተማማኝ የብልጽግና መንገድ የለም።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በፋብሪኬሽን መስክ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የቴክኖሎጂያዊ አቅም ግንባታ ጉዳይ የሚወሰነው ምንጊዜም ቢሆን በተቀባዩ አገር ፍላጐትና ዝግጁነት መሆኑ አይቀርም። መንግሥትና መላው ሕብረተሰብ ቴክኖሎጂን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የመማር ብሔራዊ ሥነ-ልቦና ካላቸው የቴክኖሎጂ ሽግግር በተነጻጻሪ የቀለለ ይሆናል። ይህም ከመንግሥት በኩል የውጭ ባለሀብቶች መጉረፍ ስለጀመሩ ብቻ የቴክኖሎጂ ሽግግር ይፈጸማል የሚል ብዥታ እንዳይሰፍንበት ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ የሚጀመር ነው። ለልማት ከተነሱ አገሮች ልምድ እንደታየው ሌላው ቀርቶ ቴክኖሎጂ በመኮረጅ ያደጉት ልማታዊ መንግሥታትም ቢሆኑ፣ ከኋላ ለሚከተሉዋቸውና ከእነርሱ ለመኮረጅ ለሚሹ አገሮች ያላቸውን ሁሉ በነጻና በቀላሉ አያካፍሉም። ጆ ስቱድዌል በመጽሐፉ ላይ ለረጅም ጊዜ የማሌዥያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ዶከተር ማህቲያር ጃፓንና ኮሪያን በጐበኙበት በአንድ ወቅት በጀማሪ

የዕድገት ደረጃቸው ከሌሎች በመከረጅና በመማር ያደጉት ሁለቱ ልማታዊ አገሮች የቴክኖሎጅ ሚስጥራቸውን ለማሌዥያ የማካፈል ፍላጐት እንዳላሳዩ ይገልጻል። ይህም በስቱድዌል ትንተና መሠረት "የሁለቱ አገሮች መንግሥታት ዋነኛ ፍላጐት ማሌዥያን ለመሳሰሉ አገሮች የተሟላ ፋብሪካ (Turnkey)ና የግንባታ አገልግሎት መሸጥ"[79] ከመሆኑ እንደመነጨ ይገልጻል።

ይህ ማንኛውም ልማታዊ መንግሥት ቴክኖሎጂን ከሌሎች አንጋጦ መጠበቅ እንደሌለበት፣ ይልቁንም በራስ ጥረት ከሌሎች ለማግኘትና ለማስቀረት፣ በሂደት ደግሞ የራሱን ለማመንጨት እጅግ የተመቸ ሁኔታ መፍጠር እንዳለበት ያሳያል። የመንግሥት ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ የግሉ ሴክተር፣ በተለይ ደግሞ የአገሪቱ ምሁራንና የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በቅድሚያ ቴክኖሎጂን ለመከረጅና ለማስቀረት፣ በሂደት ደግሞ ለማመንጨት በሚያስችል ሥነ-ልቦና መገንባትና መንቀሳቀሳቸውን ማረጋገጥ ይገባል። ዝቅተኛ እሴት በመጨመር የሚታወቁ የውጭ ባለሀብቶች ከእጅ አይሻል ዶማ እንደሆኑ ተገንዝቦ፣ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ከፍተኛ ጭማሪ የሚያስገኙና ቴክኖሎጂያቸውን በአንድ ወይም በሌላ ምክንያትና ግፊት የሚያጋሩ ተቋማትን መምረጥና ማስገባት ይገባል። በአጭሩ ከሌሎች አገሮችና ኩባንያዎች ቴክኖሎጂን ለመካፈል አስገዳጅ ሁኔታዎች እየፈጠረ ለመጓዝ በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራ አገር መሆን የግድ ይላል። ቻይና እንዴት በቴክኖሎጂ ኩረጃ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደደረሰች የሚገልጸው ፖልሰን "Dealing with China" በሚል መጽሐፉ፣ "በቻይናዊ አካል ላይ የውጭ ቴክኖሎጂ" (Chinese Bodies, Foreign Technologies) በሚል ንውስ ርዕስ፣

> "ይህ ሥልት ከቅርብ አሥርት ዓመታት ወዲህ የታየውን የቻይና ትንሳኤ አብስሯል። ይህም በአገሪቱ የተቀሰቀሰው የለውጥና ግልጽነት ንቅናቄ ዋናው ቁም ነገር ነው። ቻይናውያን ያላቸውን እጅግ ትልቅ ሰብአዊ ኃይል በልመና፣ በብድር፣ በግዥና ስለእውነት ከተናገርን ደግሞ ከምዕራቡ ዓለም በስርቆት ካገኙት ፈጠራና ምርጥ የአሠራር እውቀት፣ ጋር አዋህደውታል። የእነዚህ ጥምረት ቻይናውያን ከልእለ ኃያላን ሁሉ በግዙፍነቱና በፈጣን ዕድገቱ ቀዳሚ የሆነ ሠራዊትና በቅርብ ርቀት ከአሜሪካ የሚልቅ ኢኮኖሚ ባለቤት እንሆናለን በማለት እንዲመኩ ዕድል ሰጥቷቸዋል።"[80] (አጽንኦት የተጨመረ) ይላል።

ከዚህ ዓይነቱ ሥነ-ልቦናና ለልማት፣ በተለይ ለቴክኖሎጂ ሽግግር በአንድ ልብ ከመዝመት ውጭ፣ ቴክኖሎጂ መከረጅና ማመንጨት እውን ሊሆን አይችልም። በተለይ ደግሞ በውጭው ባለሀብት መልካም ፈቃድ ላይ በተመሠረተ የቴክኖሎጂ ሽግግር በመተማመን ዋነኛ የዕድገት ማረጋገጫ የሆኑት ፋብሪኬሽንና የኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትም ሊሳኩ አይችሉም። ከእያንዳንዱ የውጭ ግዥ "ምን ያህል ኮሚሽን አገኛለሁ" የሚል ግዥ ክፍል፣

ሁሉን ነገር በሚወስንበትና ሞልቶ በተረፈበት አገር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እውን ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም። "አገሬ ምን ያህል ቴክኖሎጂ ተላለፈላት" ማለት ቀርቶ፣ ከግብርና ሽያጭ ምን ያህል ኮሚሽን እንደተገኘ እያሰበ፣ ኢንዱስትሪን ማልማት እንደማይቻል፣ የደቡብ ምሥራቅ እስያ የከሸፉ ልማታዊ መንግሥታት ተሞክሮዎች ዓይነተኛ ማሳያዎች ናቸው።

ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዕድገት ከገጠር ኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ በተጨማሪ ፋብሪኬሽንን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት። ፋብሪካዎችን፣ በተለይ ደግሞ የአርሶ አደር የግብርና ምርቶችን ፕሮሰስ የሚያደርጉና ሌሎች የተፈጥሮ ግብዓቶችን ተጠቅመው የግንባታ ቁሣቁሶችን (Construction Materials) ለማምረት የሚያስችሉ ፋብሪካዎችን እዚሁ በአገር ውስጥ በማምረት መጀመር፣ አገራዊ አቅምን ከመገንባት አኳያ የተለየ የመነሻ ብቃት ያጐናጽፋል። በሂደት ደግሞ የተወሳሰበውን ቴክኖሎጂ ማመንጨት ይቻላል፣ ይገባልም።

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዝግጅት ወቅት "በብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን" (ብኢኮ) እጅ የሚገኙ የፋብሪኬሽን አቅሞች ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ እንዲውሉ፣ በእነዚህም ዙሪያ ብዙ አነስተኛና ጥቃቅን አምራች ተቋማት እንዲስፋፉ መደረግ እንዳለበት ተቀምጦ ነበር። ይህ በእርግጥም በኢትዮጵያ ገጠሮች ተፈላጊ የሆኑ ኢንዱስትሪዎችን እዚሁ በማምረት፣ አገሪቱ ደረጃ በደረጃ ራሷን እንድትችል የሚያደርጋት አቅጣጫ ነው። የአትክልት መጭመቂያና ማሸጊያዎችን የሚሠሩ ትንንሽ ፋብሪካዎች መገንባት ሮኬት ሳይንስ አይደለም። የቲማቲም ድልህ፣ የዱቄት፣ የቆዳ ማለስለሻ፣ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካዎችም እንዲሁ። ሁሉም እዚሁ በአገር ቤት ሊመረቱ የሚችሉ ናቸው። ረዥም በማይባል ርቀትም ኤክስፖርት ሊደረጉና ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉም ናቸው። በየፖሊቴክኒክና መሰል ኮሌጆች የሚገኙ ወርቅ ማምረት የሚችል አእምሮና እጅ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን በዚሁ መስክ ኮትኩቶ በማሳደግ የኢንዱስትሪ እመርታዊ ለውጥ ለማምጣት ይቻላል። የብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ የተሰጠውን ይህን ተግባር በምን ደረጃ እየፈፀመው እንደሚገኝ የጠራ መረጃ የለኝም። ነገር ግን በመለዋወጫነት የሚያገለግሉ አላቂ ዕቃዎችን እየኮረጀ ከመስራት አልፎ ፋብሪካዎቹን ለመገንባት በሚያስችል ደረጃ "ገልብጦ እየሠሩ በመለማመድ" /Reverse Engineering/ የተዋጣለት እንደሆነ የሚያሳዩ ውጤቶች እምብዛም አንመለከትም። ተቋሙ በስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ መከራና ተሳትፎው ውጤታማ እንዳልሆነ እስካሁን በጊዜ ብክነትና በዋጋ ንረት የሚሰቃዩትን ፕሮጀክቶች ከንግድ ባንክ የብድርና እዳ ሰነዶች በመመልከት ሊረጋገጥ የሚችል ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ችግሩ በሌሎች መስኮችም ተስፋፍቶ ይታያል። አሁን አሁን በአንዳንድ የመንግሥት ኃላፊዎች ዘንድ ጐልቶ የሚታየው ከአገራዊ ኢንዱስትሪያዊ አቅም ግንባታ ይልቅ የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ ልማት እስከወዲያኛው በሚገድቡ ጉዳዮች ማተኮር

ሆኗል። ለምሣሌ እዚሁ ሠርተን ልናሟላቸው የምንችላቸውን ምርቶች ከውጭ ለማስገባት ከፍተኛ ፍላጐት አለ። ስንዴ ከማምረትና ያለውን ለገበያ ከማቅረብ ይልቅ ከውጭ ማስመጣትና የራሳችንን ገበሬዎች መጉዳት ተለምዷል። አገራችን ከፍተኛ የቅባት እህል ምርት ማምረት እየቻለችና ይህንኑ በፋብሪካ አዘጋጅቶ ጥራቱ የተጠበቀ የምግብ ዘይት ወደውጭ መላኩ ይቅርና ለአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ እየተቻለ፣ ዘይት ከውጭ ለማስመጣትና ኮሚሽን ለመበላት የሚሰጠው ትኩረት አሳፋሪ ደረጃ ላይ ደርሷል።

ከመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ወዲህ ባሉት ሰባት ዓመታት ከውጭ ዘይት ለማስመጣት ንግድ ባንክ በየአመቱ በአማካይ ከአራት መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጭ አድርጓል። ከዚህ ውስጥ ሲሶውን ብቻ እንኳ ዘይት ፋብሪካዎች ለማስፋፋት አውለነው ቢሆን ኖሮ አገራችን ዛሬ ጥሬ ዕቃውን ሳይሆን ያለቀለት የሰሊጥና ሌሎች የቅባት እህሎች ምርት ወደውጭ ገበያ በማቅረብ የውጪ ምንዛሬ ወጭዋን በእጅጉ ቀንሳ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ ማምጣት ትጀምር ነበር። ከውጭ የምናስመጣቸውን አልባሳት በቀላሉና በቤት ውስጥ ለማምረት የሚያስችሉ ጥቃቅን ማሽኖችን በማስመጣትና እነዚህን ገልብጦ እየሠራ በመለማመድና (Reverse Engineering) ደረጃ በደረጃ በማምረት የእግር ሹራብና ቲ-ሸርት፣ ጫማና መሰል ምርቶችን ከራሳችን አልፈን ኤክስፖርት ማድረግ እንችል ነበር።

ብኢኮ እነዚህን በኩረጃ በመለማመድና በማምረት የኢንዱስትሪ ልማቱ ማዕከል ይሆናል ቢባልም፣ ራሱ ተቋመም ሆነ የኢንዱስትሪ ዘርፍን እንዲመሩ የተመደቡ ሰዎች በተሳሳተ ቅኝት መጓዝ በመምረጣቸው ዘርፉ ተፈላጊውን ዕድገት ማስመዝገብ ተስኖታል። የኢንዱስትሪያዊ ልማት አልፋ ኦሜጋ ፋብሪኬሽን ነው። አንድ አገር በኢንዱስትሪ የበለጸገ የሚሆነው ፋብሪኬሽንና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪው ልማት ሲሳካ ብቻ ነው። በእርግጥ ከዚህ ያነሰ ብቃት የሚያጐናጽፉ ሥራዎች ሁሉ በደረጃቸው ተፈላጊ ናቸው። ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት የማዘጋጀት ተግባር በደንብ የለመ አገሮች ሁሉ ያከናወኑት የመጀመሪያ ሥራ መሆኑ አይካድም። ይህም ሆኖ የፋብሪኬሽን ብቃት በሚሞትበት አቅጣጫ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ የልማቱ አልፋ ኦሜጋ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም፣ አይገባምም። ፋብሪኬሽንን ማዕከል አድርጐ ጨርቃ ጨርቅን በደጋፊነት ሳይጠቀም የለማና የበለጸገ አገር እንደሌለ ሁሉ፣ ጨርቃ ጨርቅ ላይ ብቻ ተለጥፈው ይህንኑ በማስፋፋት እንለማለን ያሉ አገሮች ደግሞ ከባንግላዴሽ እስከ ኢንዶኔዥያ ፈቅ ማለት እንደተሳናቸው ይገኛሉ። "ለፋብሪኬሽንና ለገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ትኩረት እንስጥ፤ በአገር ውስጥ ባለሀብት ሞተርነትና በውጭው ደጋፊነት፣ የራሳችንን ወሳኝና ደጋፊ ተቋማትን ለይተን እናልማ" በሚል ግልጽነት የተቀመጠው አቅጣጫ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበትም ለዚሁ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በውጭ ካፒታል ግንባር ቀደምትነትና ሞተርነት፣ በጨርቃ ጨርቅና ሪርኮች የኢንዱስትሪ ልማት ማዕከልነት፣ ፋብሪኬሽን ከስም ያልዘለለ

ትኩረት በሚቸረው አኳኋን ወይም ይህን መጽሐፍ ወደ ህትመት ላስገባው በተቃረበኩበት ጊዜ ከአንድ የፈጠራ ወጣት የደረሰኝ የሚከተለው አጭር የስልክ ጽሁፍ መልዕክት አንደሚያሳየው እንቅፋት የሚበዛበት ከሆነ በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪን ዘላቂ ልማትና አገራዊ ትራንስፎርሜሽንን ለማምጣት አይቻልም። መልዕክቱም ቃል በቃል እንዲህ ይላል፡-

"ታሪክ ስሰማ ድሮ በለሳ እያላችሁ ምህረት ታዬ እርስዎንና አቶ አዲሱ ለገሰን አግኝቶ "መቼም ደርግ እኔን ካገኘኝ አይምረኝም ልጄን ሳልሞት ላጋባው" ብሎ ያስፈቅዳችኋል። እናንተም ለሠራዊታችሁ አባል ለሆነው ሰጠኝ ምህረት ሚስት እንዲያገባ ትፈቅዱለታላችሁ። ጀግናው ምህረት ታዬም ከኔ በላይ በምታውቁት ሁኔታ ለአገሩና ለኔ ትውልድ ነጻነት መስዋዕት ሆነ፤ በከብርም አለፈ። ከዛም እኔ ተወለድኩ። ታሪካችሁን እየሰማሁ በቁጭት አደግሁ። Mechanical Engineering ተማርኩ። አሁን አ.አ.ዩ አስተምራለሁ። ከዩኒቨርሲቲ ተማሪነቴ ጀምሮ ማሽን መፍጠር ጀመርኩ። በሰራሁት የከር ማጠንጠኛ ማሽንም በጠቅላይ ሚኒስትራችን 2 ጊዜ ተሸለምኩ። እስከመጨረሻው እንደግፍሀለን ወደሥራ ግባ ብለውም መሥሪያ ቦታና ብር 500,000 ብድር ሰጡኝ። 2006 ዓ.ም ሞዴል የከር ማጠንጠኛ ፋብሪካ አቋቁሜ 2007 ላይ ሥራ ጀመርኩ። ከር ማግኘት አስቸጋሪ ሆነ። ከወረዳ እስከሚኒስትሮች ሄድኩ በተግባር ማንም ችግሩን ሊፈታው አልቻለም። እናም 2008 ዓ.ም መስከረም ላይ ሥራ አቆምኩ። ከተሸለምኩ በኋላ ቴክኖሎጂውን ወደሥራ ለማስገባት ላለፉት 5 አምስት አመታት ብዙ ደክምኩ። ግን በዋነኛነት ሥራው ከከር ንግድ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ሆን ብለው ጊዜዬን በማባከንና እንቅፋት በመሆን ድካሜንና ራዕዬን ከጅምሩ ከጉቡ ሊያደርጉት ነው። ብሎም በደመወዝና በቼክ ዋስትና ያበደረኝ አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ብድሩን በዚህ ወር ካልከፈልክ ቼኩን በማስመታት በወንጀል እንከስሃለን ብለውኛል። ሥራ ካልሠራሁ ከየት አምጥቼ ይሄን ሁሉ ብር እከፍላለሁ። ዘመዶቻችን እንኳ ተስፋ የሚያደርጉት እኔን ነው። ስለዚህ አቶ በረከት እባኮዎትን ቀጠሮ ያዙልኝ እና ላናግርዎት። አዲስ ብድርም እንዳይከሰኝ ያድርጉልኝ።

የፈጠርኩት ማሽን የሸማኔውን ምርታማነት እስከ 300% የሚጨምር ሲሆን ከ20,000 በላይ የሥራ ዕድል ይፈጥራል። ሀሳቤም ቢያንስ 1,000 ተቀጥሮ ትመርቁልኛላችሁ፣ ጀግናውን ምህረት ታዬን እና ሌሎች

ሰማዕታትን እንዘክራለን የሚል ነበር አንድ በዚህ ሁኔታ አልዝረፃም፡፡ ለዚህም በጣም አዝናለሁ፡፡ ይቅርታ፡፡" [81]

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በኢትዮጵያ ስለኢንዱስትሪ ልማት በሚታሰብበት ጊዜ አዲስና ያልተለመደ ሥራን ብቻ ሳይሆን፣ በጣም የተወሳሰበ ሂደትን ስለመምራትና በፍጥነት ብቻ ሳይሆን በትክክለኛው አቅጣጫ የመጓዝ ጉዳይ መሆኑም ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥርት ያለና የተሟላ ግልጽነት መያዝ ካልተቻለ፣ በገጠር በመፈጠር ላይ ያለው አዲስና አስተማማኝ አገራዊ ካፒታል የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ ለመገንባት መዋለ ይቀርና የቻይናን የኢንዱስትሪ ምርቶች የሚሸምት አርሶ አደር ወደመፍጠር ሊያመራ ይችላል፡፡ በአገራዊ ባለሀብት ሞተርነት መገንባት ያለበት የኢንዱስትሪ ልማት፣ እነማሌዥያና ኢንዶኔዥያ ከሠሩት ስህተት ባለመማር የመካከለኛ ገቢ ሕበረተሰብን ወጥመድ ማለፍ ሊሳነው ይችላል፡፡ ተገቢው ግልጽነት ተይዞ በአንድ ልብ በመዝመት ርብርብ ካልተደረገ በስተቀር "ልማታዊ መንግሥት ነን" ስለተባለ ብቻ መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ይሆናል ማለት አይደለምና፡፡

የገጠር ኢንዱስትሪን የማልማት ፈተናዎች፣

ከኢንዱስትሪ ልማት አኳያ በብዙዎቹ የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች ጉልህ ሥፍራ የነበረው የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ነበር፡፡ በዓለማችን የገጠር ኢንዱስትሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በውል የታየው በአውሮፓ ሲሆን፣ ይህም የሰሜን ምሥራቅ እስያ ልማት ከመቀስቀሱ ከመቶ ዓመታት በፊት ቀድሞ የተፈጸመ ነበር፡፡ አሁን ድረስ የአውሮፓ ኢንዱስትሪ ማዕከል ሆና የዘለቀችው ጀርመን ገና ከጠዋቱ በራይን ወንዝ ዙሪያ በሚገኙ ገጠሮች በተስፋፋ የገጠር ኢንዱስትሪ የለማች ከመሆኗ በተጨማሪ ይኸው ሴክተር ዛሬም ድረስ ጉልህ ስፍራ እንደያዘ የሚገኝባት አገር ነች፡፡ በብዙ የጀርመን አካባቢዎች በአንድ የገጠር ቀበሌ ሲሆን አንድ መካከለኛ ኢንዱስትሪን ጨምሮ፣ ካልሆነም በርካታ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ማግኘት የተለመደ ነው፡፡ ለምሣሌ በዓመት የ48 ቢሊዮን ዩሮ እንቅስቃሴ ያለው ቦሽ (Bosch) የተባለው ኩባንያና የ6 ቢሊዮን ዩሮ ገቢ ያለው አከርማን (Akerman) በገጠር ውስጥ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ሰፊ የግብርና መሠረት ያላቸው አገሮች ወደ ኢንዱስትሪያዊ ልማት በሚያደርጉት ሽግግር፣ ገጠሩን እንደ አንድ የኢንዱስትሪ ልማት የመነሻ ነጥብ መውሰዳቸው የተለመደ ነው፡፡

ይህም ያለምክንያት የመጣ አይደለም፡፡ ከዙሉ በፊት ኢንዱስትሪያላይዜሽን አብዛኛውን ህዝብ በግብርና ላይ ከተመሠረተ ሕይወት ማላቀቅ ማለት በመሆኑ ነው፡፡ አብዛኛው ህዝብ በግብርና ላይ በሙተማመን በሚኖርበት አገር፣ መቼም ቢሆን የገጠርና የግብርና እንጂ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍና የከተማ ሕይወት የበላይነት ይዟል ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም

ዘሊንሱዘፐሪ የሥልጦፕ ጉዳይ ገጠር ን ወደከተሜነተ የመቀየር ጉዳይ ከመሆን አይዘልም፡፡ በዚህ ምክንያት የኢንዱስትሪ ልማት የገጠር ጂኡ-ግራፊን ወይም ሥነ-ምህዳርን ታሳቢ ከማድረግ ውጭ ሊታለም አይችልም፡፡

በገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ዙሪያ መለስ የተለያዩ ሥራዎችን ያበረከተ ሲሆን፣ ከመለስ ሕልፈት በኋላ ደግሞ በዚህ ጽንሰ ሀሳብ ላይ በመመሥረት የተወሰነ ጥናታዊ ሥራ ተከናውኗል፡፡ በበኩሌም የመለስን የገጠር ኢንዱስትሪ የልማት አቅጣጫ መሠረት በማድረግና በመስኩ የተጻፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በማጣቀስ፣ በኢትዮጵያ ለገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ትኩረት እንድንሰጥ የሚያሳስብ አንድ ሰፋ ያለ ጥናታዊ ጽሁፍ በ2006 ዓ.ም አቅርቤ፣ ከየብሔራዊ ድርጅቶቹ ሊቀ መናብርትና ምክትል ሊቀመናብርት ጋር በጥቂቱ ተወያይተንበት ነበር። በተጨማሪም በብአዴን መድረክ ከተወሰኑ ፈቃደኞች ጋር ተመሳሳይ ውይይት ተካሂዶበት በሰነዱ ጽንሰ-ሀሳቦች ላይ ይበልጥ ለመወያየት ፍላጐት ታይቶ ነበር። ነገር ግን ይህ ሁነኛ የልማት አቅጣጫ በልዩ ልዩ ሰበቦችና ውሃ የማይቋጥሩ ምክንያቶች በመደርደሪያ ተቆለፈበት። በትንሹም ቢሆን እንደገና ነገርዬውን የማንሳት ሙከራ የታየው በ2008ዓ.ም. ወጣቶች በኃይል ተነሳስተው ሰላምና መረጋጋቱን አጣብቂኝ ውስጥ ሲያስገቡት ብቻ ነበር። በዚህ የተነሳ መንግሥት ሁሌም ውጥረት ውስጥ ሲወድቅ እንደሚያደርገው በዚህ ወቅት ቃል በቃል ስመ-ጥ ከመጥራት ተቆጥቦ ይህን ሁነኛ አቅጣጫ የሁከቱ መፍትሔ አደርገዋለሁ እስከማለት ደረሰ። በ2009 ዓ.ም. የአማራ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በዚህ ያልፀደቀ ፖሊሲ ሥልጠና እንድሰጥለት ሲጠይቀኝ ደግሞ ባልፀደቀ አቅጣጫ ማሠልጠን ችግር እንዳለው ለማሳየት ያደረግኩት ሙከራ ሳይሳካ ወደሥልጠና አመራን።

ከእነዚህ ትንንሽ መልካም አጋጣሚዎች ባሻገር በሂደት ይህን ሁነኛ የልማት አቅጣጫ የሚያሳንሱ ወይም የሚያጣጥሉ አመለካከቶች መከሰት ጀመሩ። በዚህ ጽሁፍ ላይ በአደባባይ ለመወያየት ፍላጐት ባይኖርም፣ ሀሳቡን ለማብጠልጠል ሞራል ያላቸው አንዳንድ የአመራር አባላት "ኢንዱስትሪን የገጠርና የከተማ ብሎ መከፋፈል ለምን ያስፈልጋል? በጂኡግራፊ ላይ የተመሠረተ ኢንዱስትሪያዊ ልማትስ ምን ማለት ነው? ኢንዱስትሪ የከተማ እንጂ እንዴት የገጠር ሊሆን ይችላል?" በሚል ያልበሰለ አመክንዮ የልማት አቅጣጫውን ውድቅ የማድረግ ዝንባሌ አሳዩ። በመሆኑም ዛሬም የአገራችንን ዕድል ከሚወስኑ መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱ በሆነው በዚህ ሁነኛ የልማት አጀንዳ ላይ በግልጽ መነጋገር የግድ ይላል፡፡ በታሪካዊ መረጃዎችና በኢኮኖሚ ሕጐች በተደገፈ መከራከሪያ የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ፋይዳን በዝርዝር መመልከት ያስፈልጋል። በአመራር ድክመት ሳቢያ ከመልካም ዕድልነት ወጥቶ ወደፈተናነት በተቀየረው የገጠር ኢንዱስትሪያዊ ልማት ላይ አንድ የኒዮ-ሊበራሊዝም መሲሕ የሆኑ ግለሰብ ያላቸውን ትዝብት በማቅረብ ጉዳዩን መመልከት እንጀምር።

በአንድ ወቅት የጐልድማን ሣክስ ሊቀ-መንበርና እ.ኤ.አ. ከ1998-2001 የአሜሪካ ትሬዠሪ ሴክሬታሪ የነበሩትና በዓለምም ሆነ በአሜሪካ አዲሶቹ ወግ አጥባቂዎች (Neo-Cons) ከሚባሉት ሰዎች አንዱና ዋናው የሆኑት ሔነሪ ኤም. ፖልሰን ጁንየር በኒዮ-ሊበራሊዝም መሲሕነት ወደቻይና ይመላለሱ በነበሩበት ወቅት ቻይናን በኢኮኖሚ ነጻ አውጥቶ የተወዳዳሪነት አቅሟን በእጅጉ ስላሳደገው የገጠር ኢንዱስትሪ፡-

> "የአርሶ አደር ቤተሰቦች የተወሰነ ኮታ የማቅረብ ግዴታቸውን ከተወጡ በኋላ የቀረውን ደግሞ በነጻ ገበያ የመሸጥ ነጻነታቸው ተከበረ። በእነዚህ ማትጊያዎች የተነሳ ምርታማነት ከፍተኛ ጭማሪ አስመዘገበ። (እ.ኤ.አ.) ከ1978 እስከ 1984 በነበሩት ዓመታት የሰብል ምርት በ34 በመቶ አደገ። የሚነሳሳ...የተመዘገበው የምርታማነት ጭማሪ በገጠርና ግብርና ሥራ ላይ የሚፈለገውን ሠራተኛ ቁጥር አሳነሰው። ከዚህ ትርፍ ጉልበት ውስጥ እጅግ የሚበዛው በገጠር በተስፋፉት አዳዲስና ጐልብተው መውጣት በጀመሩት ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጠረ። እነዚህ የገጠር ከተሞችና የመንደር ፋብሪካዎች በአካባቢ መስተዳድር ባለቤትነት የተያዙ እንጅ በአጠቃላዩ አገራዊ የኢኮኖሚ እቅድ ውስጥ የሚካተቱ አልነበሩም። እንደግል ሴክተር ኩባንያዎች በገበያ ከፍተኛ ተፈላጊነት የነበራቸውን ምርቶች በሰፊው በማምረትም ሆነ፣ ከመንግሥት ግዙፍ ተቋማት ጋር በመወዳደር ረገድ በነጻነት የመንቀሳቀስ ችሎታ ነበራቸው።"[82] ብለዋል።

በገበያ አክራሪ አስተሳሰብ አራማጅነት የሚታወቁት ፖልሰን በእውነታው አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር በዚህ መንገድ ምስክርነት በመስጠት ሌሎች ከዚህ የሚማሩና ነጻ የሚወጡበትን መንገድ አያመላክቱም ነበር። ከጀርመን እስከጃፓን፣ ከኮሪያ እስከታይዋን፣ አሁን ደግሞ ቻይና ለፈጣንና አስተማማኝ ልማትና ብልጽግና የታደሉት በዚሁ አቅጣጫ ነው። የበለጸገ የገበያ ሥርዓት በመገንባት ረገድ የተሳካላቸውን አገሮች ሂደት በተወሰነ ደረጃ ዘርዘር አድርጐ በመመልከት ብቻ ይህ መሠረታዊ የዕድገት አቅጣጫ ምን ያህል ትክክል እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በእኛ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ የዚህን ልማታዊ አቅጣጫ ፋይዳ ሌላው ቀርቶ በአሁኑ ጊዜ በየክልሉ የከፍተኛ ትምሕርታቸውን ጨርሰው በገጠር ውስጥ ሥራ ፈትተው የተቀመጡ ወጣቶችን ሁኔታ በመመልከት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የትምሕርት መስፋፋትን ተከትሎ የገጠር ልጆች በስፋት የመማር ዕድል አግኝተዋል፡፡ ቀለል ባሉ ጥናታዊ ትዝብቶች በአንዳንድ ቀበሌዎች ወደከፍተኛ ትምሕርት የገቡና የተመረቁ ከአሥር እስከ ሃያ የሚደርሱ ወጣቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወደልማዳዊው የግብርና ሥራ ለመመለስ አይፈልጉም፡፡ በአኳያው በባለቤትነት የሚቆጣጠሩትም ሆነ በተቀጣሪነት የሚሳተፉበት ሌላ

የሥራ መስክ አልተስፋፋላቸውም። በዚህ የተነሳ በኢንዱስትሪም ሆነ በአገልግሎት ዘርፉ ውስጥ በአምራችነት ለመሰማራት ዕድል ስላላገኙ ሥራ ፈትተው ተቀምጠዋል። የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ይህን ካለአግባብ የመከነ አቅም ወደሥራ ለማስገባትም ሆነ የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አማራጭ የሌለው መፍትሔ የሚሆነው በዚህ የተነሳ ነው።

ካፒታሊዝም ወይም የገበያ ሥርዓት ለኢንዱስትሪ ልማት የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ወይም ኢንዱስትሪያዊ ተጠባባቂ ኃይል (Industrial Reserve Army) የሚያገኘው ከገጠር ነው። ይህ የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት ከተካሔደባት እንግሊዝ ጀምሮ፣ በሌሎች በኢንዱስትሪ የለሙ አገሮችም በብዛት የታየ ነው። ካፒታሊዝም የትም ይሁን መች መላ ትኩረቱ አርሶ አደሩን በውድም በግድም ከእርሻ ማሳውና ከገጠር በማፈናቀል በከፈታቸው ኢንዱስትሪዎች ተቀጥሮ እንዲሠራ ማድረግ ነው። ባለሀብቱ በዝቅተኛ ምንዳ የሚቀጥረውን ሠራተኛና በዚህ ሰብዓዊ ኃይል መካከል የሚካሔደውን ውድድር ዋናው የትርፍ ምንጭ አድርጐ ይመለከተዋል። በሠራተኛው መካከል ከፍተኛ ውድድር ሊካሔድ የሚችለው ደግሞ በኢንዱስትሪ የሥራ መስክ ተቀጣሪ ለመሆን የሚሻ ሥራ የፈታ የሰው ኃይል፣ በተለይ ደግሞ ወጣት ሥራ ፈላጊ በብዛት ሲኖር ነው። ይህም የሚገኘው በዋነኛነት በገጠር ነው።

የሥርዓቱ አንቀሳቃሽ የሆነው ባለሀብት፣ በአገሩ ውስጥ ያለውን ገጠሬ የሰው ኃይል በዚህ አኳኋን ከምላ ጐደል ሙሉ በሙሉ ከተሜ ካደረገና ከተጠቀመበት በኋላ የጉልበት ዋጋ ሲንርበት፣ ይህንኑ ሌላ ጂኦግራፊያዊ መፍትሔ /Spatial Fix/ ይፈልግለታል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሶሻል ዴሞክራሲ ለአውሮፓ ሠራተኛ መደብ ሰፊ መብት አጐናጽፎ የመደራደር ዕድሉንና ችሎታውን ባሳደገለት ጊዜ ከዚሁ ክፍለ ዓለም የተነቀሉ ፋብሪካዎች ያመሩት ኢንዱስትሪያዊ ተጠባባቂ ኃይል በብዛት ወደሚገኝባቸው ወደምሥራቅ እስያ ገጠሮች ነው። የምዕራቡ ዓለም ካፒታል ከሶሻል ዴሞክራሲና የሠራተኛ ንቅናቄው በኩል ያጋጠመውን ትርፍ የመጋራት ጥያቄ ለማለፍ በተለይ በቻይና ገጠሮች የነበረውን በብዙ መቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ኢንዱስትሪያዊ ተጠባባቂ ኃይል ወደማንቀሳቀስ አምርቷል። ይህን ተከትሎ በቻይና ባልተማከለ አቅጣጫ የገጠር ኢንዱስትሪና አምራች የገጠር ከተሞች መስፋፋት ሲጀምሩ ለዘመናት መከኖ የኖረው የገበሬ ጉልበት ከፍተኛ ምርታማነት ማሳየት ቻለ። እ.ኤ.አ በ1980ዎቹ "ባአን" በመባል ትታወቅ የነበረችው የአሳ አጥማጆች መንደርና የአሁኗ ሽንዘን ሠላሳ ሺህ የማይሞላ ህዝብ መኖሪያ ነበረች። ይህች የገጠር መንደር ግን ከሠላሳ ዓመታት በኋላ 12 ሚሊዮን ቻይናውያን የሚኖሩባት ሜትሮፖሊ ከተማ ሆናለች። ይህም በቻይና ስኬታማ በሆነ ደረጃ በተካሔደው የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት አማካይነት የተመዘገበ ውጤት ነው። ይህ ሁሉ የኢንዱስትሪ ልማትን ጨምሮ ማንኛውም ልማት አንዳች ዓይነት ጆግራፊያዊ ታሳቢ ሳይኖረው እንደማይካሔድ ያመለክታል። የገጠር ልማትን በማስመልከት አፍሪካን ኢኮኖሚክ

አውትሉክ እ.ኤ.አ በጁላይ 2015 እትሙ፡-

> "እስካሁን ድረስ ለየት ያሉ የሪጅናዊ ዕድገትና አካባቢያዊ (Spatial) ተሳትፎ ፖሊሲዎች አፍሪካ ላይ ያስገኙትን መጠነኛ ውጤት መነሻ በማድረግ ሁሉም መንግሥታት ከመካከለኛና ረጅም ጊዜ አኳያ አዳዲስ አቀራረቦችን መሞከር አለባቸው፡፡ አፍሪካ ያለባት እያደገ የሚሔድ የህዝብ ጫናና ከባቢያዊ ተግዳሮት (Spatial Challenge)፣ ህዝብና አካባቢዎች በልማት ስትራቴጂ ቀረጻ ላይ ቁልፍና ማዕከላዊ ቦታ መያዛቸውን፣ እንዲሁም የሴክተር ፖሊሲዎች ሲቀረፁ፣ እነዚህ ግምት ውስጥ መግባታቸውን ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡ በተለይ ደግሞ አፍሪካ በአግባቡ ያልተጠቀመችበት ሀብት ባለበት ሁሉ፣ እነዚህ ህዝብና አካባቢ ተኮር ስትራቴጂዎች ንዑሳን የአገር ክፍሎችን እንዲሁም ወሰን ተሻጋሪ ሁኔታዎችን በውል ማጤን ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ የአካባቢ ጸጋዎችን ለማወቅና ጥቅም ላይ ለማዋል እጅግ የቀረቡ ናቸውና፡፡ የልማት ስትራቴጂዎች ምንጊዜም ቢሆን እያንዳንዱ አገር ባለው ሰብዓዊ ኃይል፣ የኢኮኖሚና ከባቢያዊ ሁኔታ ተለያይነት ምክንያት በተለየ ሁኔታ የሚዘጋጁ፣ ብዙኅነት ያላቸው አቀራረቦችን የሚጠይቁ ናቸው፡፡"[83] ይላል፡፡ [ሠረዝ የተጨመረ]

ይኸው ሰነድ አካባቢ ተኮርና አሳታፊ ፖሊሲ የመከተል ችግር በሚኖርበት ጊዜ ከባድ ምስቅልቅል እንደሚከተል ኬንያን ዋቢ በማድረግ ሲገልጽ፡-

> "በኬንያ ከነጻነት በኋላ ባለው ጊዜ ሁሉ ለኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ባለው የተለያየ ዕድል ምክንያት በልማት አካባቢዎችን ማካተት /Spatial inclusion/ ከባድ ፈተና ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህም በ1992, 1997ና በ2007/08 ከባድ መፈናቀልና ምስቅልቅል ያስከተሉ ፖለቲካዊና የብሔር ግጭቶች እንዲቀሰቀሱ ምክንያት ሆኗል፡፡ በ2010 በፀደቀው የተሻሻለ ሕገ-መንግሥት 47 የአካባቢ አስተዳደሮችን በማቋቋም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ መዋቅሮችን በማደራጀት ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን በማረጋገጥ የነበረውን ልዩነት ለማስተካከል የተሞከረውም ለዚሁ ነው፡፡"[84] በማለት ያስረዳል፡፡

ከእነዚህ ጥቅሶች ኢንዱስትሪን በማልማት አገራዊ ትራንስፎርሜሽን የማምጣት ሂደት አንዳች ዓይነት ከባቢያዊ ወይም መልክዓ-ምድራዊ ባሕርይ ሳይኖረው እንደማይካሔድ ያመላክታል፡፡ የኢንዱስትሪ ልማት ጅግራፊያዊ ሁኔታን በተለይ ደግሞ አብዛኛው ህዝብ

የሚኖርባቸውን ገጠሮች ታሳቢ ሳያደርግ ሊሳካ እንደማይችልም ያሳያል፡፡ ከዚህ ሀቅ በመነሳት በገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን አስፈላጊነት ላይ መስማማት አስቸጋሪ መሆን አልነበረበትም፡፡ ይህም ካስቸገረ የህዝቡ ጉልበት አካባቢውን ሳይለቅ እንዲለማና እንዲያለማ ከማድረግና ከአካባቢው ርቆ እንዲሰማራ ከማድረግ የተሻለው የቱ ነው? ከሚለው ጥያቄ በመነሳት፣ በገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ፋይዳና በስትራቴጂው ላይ ጠንካራ መግባባት መፈጠር ነበረበት፡፡

ለኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ የሆነውን ጉልበት በተገቢው ቦታ/Space/ ከመጠቀም አኳያ ሁለት አማራጮች አሉ፡፡ በአንድ በኩል ገበሬዎች ከቀያቸው ርቀው በዋና ዋና ከተሞች በሚስፋፉ ኢንዱስትሪዎች እንዲሰማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ አቅጣጫ ከተመረጠ ከሞላ ጐደል ሰፊ ቁጥር ያለው የአገሪቱ ህዝብ ከየማዕዘኑ ወደጥቂት ትልልቅ ከተሞች እንዲጐርፍ ማድረግን ያስከትላል፡፡ ነገር ግን ይህ የራሱ ብዙ ጣጣ አለው፡፡ ከሁሉ በፊት አስቀድሞ የለመት ትልልቅ ከተሞች አዲሱን የሰው ኃይል በሥራ ያስተናግዱ ዘንድ ተጨማሪ ኢንዱስትሪ ሊስፋፋባቸው ይገባል፡፡ ይህም ድሮውንም የተለጠጡትን ከተሞች እንደገና እጅግ በጣም በመለጠጥ በከተሞቹ ላይ ከባድ ተፅዕኖ ያሳርፋል፡፡ በተጨማሪም ፋብሪካዎቹ ከጥሬ ዕቃ ምንጩ በራቁ ቁጥር ይህንኑ ከረጅም ቦታ አጓጉዞ ማምጣት የኢንዱስትሪዎቹን ተወዳዳሪነት በእጅጉ ይጫነዋል፡፡ ባልተማከለ የኢንዱስትሪ ልማትና አከታተም እጅግ ብዙ ሚሊዮኖችን በየመኖሪያ አቅራቢያቸው በባለቤትነትና በሥራተኝነት ማሳተፍ እየተቻለ፣ በጥቂት ከተሞች የተከማቹ የተወሰኑ ባለሀብቶች ሁሉን ነገር እንዲቆጣጠሩት በር በመክፈት ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል የሚሰፍንበትን ዕድል ያሳንሰዋል፡፡

ኢንዱስትሪ በጥቂት ከተሞችና በጣት በሚቆጠሩ ባለሀብቶች ብዙ መሠረታዊ ችግሮች ባልተለዩት አኳኋን ከለማባቸው አገሮች ይልቅ፣ የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት ባልተማከለ ቅኝት የተስፋፋባቸው አገሮች የተሻለ ፍትሃዊነትና ዘላቂነት ያለው ዕድገት አረጋግጠዋል፡፡ መጀመሪያ ታይዋን፣ በኋላ ደግሞ ቻይና እንዳደረጉት አርሶ አደሩ "የገጠር ቀዬውን ሳይለቅ፣ የእርሻ መሬቱን እየለቀቀ (Leaving the land without leaving the rural area) በባለቤትነትና በሥራተኝነት የሚሳተፍበት ኢንዱስትሪያዊ ሕብረተሰብ መገንባት ችለዋል፡፡

በእኛም አገር ይህንኑ ፈለግ መከተል ከቻለ በእርግጥም ሰፊ መሠረት ያለው፣ የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ኢንዱስትሪያዊ ሕብረተሰብ ይፈጠራል፡፡ ከተሞቹም ጥቂት፣ ትላልቅና ተፈጥሮን የሚበክሉ መሆናቸው ቀርቶ፤ ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተው የሚገነቡ፣ ለሥራና ለኑሮ የተመቹ በርካታ ትንንሽ ከተሞች እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ መለስ የኢትዮጵያ የግብርና ልማት በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ላይ የተመሠረተ እንደሆነና ይህም ለገጠር ኢንዱስትሪ ልማት መስፋፋት አስተማማኝ መሠረት እንደሚያነጥፍ በመገንዘብ የኢትዮጵያ

የኢንዱስትሪና የአከታተም ልማት አቅጣጫ የጀርመንና የሰሜን ምሥራቅ እስያ ሞዴሎችን አጣምሮ የያዘ እንዲሆን የማድረግ ጥልቅ አሳቤ ነበረው፡፡ ይህም በጥናት የተረጋገጠ አሳቤ እንደነበር ለማስተርሱ ማሟያ ባቀረበው የመመረቂያ ጽሁፍ ላይ ፡-

> "ሰፊ መልከዓ-ምድራዊ ሽፋን ያለው የግብርና ዕድገትና ይህን ተከትሎ የሚከናወን የከተሞች መስፋፋት ከፍተኛ ብዜታዊ ተፅዕኖ (Multiplier effect) አለው፡፡ የግብርና ዕድገት በተወሰነ መልከዓ-ምድር ላይ የተገደበ ከሆነ፣ ከኢንዱስትሪው ጋር የሚኖረው ተመጋጋቢነትና በአጠቃላይ ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽዖ የተገደበ ይሆናል፡፡ በአንጻሩ የግብርናው ዕድገት ሰፊ መልከዓ-ምድርን የሚሸፍንና መላውን አገሪቱን የሚያዳርስ ከሆነ ብዜታዊ ተፅዕኖው ያንኑ ያህል ትልቅ ይሆናል፡፡ ግብርናን እንዲያገለግል ታስቦ የሚስፋፋው መሠረተ-ልማትም እዚያው በዚያው ከግብርና ውጭ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ልማትን በእጅጉ የሚደግፍ ይሆናል፡፡ የግብርና ዕድገትንና ኮሜርሻላይዜሽንን ተከትሎ የሚፈጠረው ዕድገትም ከግብርና ውጭ ያሉ [ኢንዱስትሪያዊ] ኢንተርፕራይዞችን የሚያሳድግ ይሆናል፡፡ በዚህ አኳኋን የሚፈጠረው የግብርናና ከግብርና ውጭ ያሉ ሴክተሮች ልማታዊ መስተጋብር ደግሞ የኢንዱስትሪ ክምችት ዕድልን (Clustering) የሚያሰፋ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ግብርና በሌሎች ሴክተሮች ልማት ላይ የሚኖረው ብዜታዊ ተፅዕኖ በሰፊ መልከዓ-ምድር ላይ በሚካሔድ የግብርናና ያልተማከለ ተጓዳኝ የከተሞች ፈጣን ልማት አማካይነት እንጂ በአንድና ሁለት ትልልቅ ከተሞች ላይ በሚታይ የህዝብ ክምችት የሚፈጠር አይደለም፡፡"[85] ይላል፡፡

ከዚህ የመለስ አገላለጽ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ መሠረተ-ሰፊና መልከዓ ምድራዊ ሽፋኑ መላ አገሪቱን የሚያካልል የግብርና ልማት፣ መላውን አገር የሚሸፍንና ፍትሃዊ ሥርጭት ያለው የኢንዱስትሪ ፈጣን ልማትን የሚያስከትል ይሆናል፡፡ አንድና ሁለት ትልልቅ ከተሞች በመፍጠር ሳይወሰን የገጠር ከተሞች እንደእንጉዳይ እንዲፈሉ ያስችላል፡፡ ከዚህም አልፎ በገጠር ከተሞች ሳይቀር የኢንዱስትሪ መከማቸትን የሚያስከትል ይሆናል፡፡ መለስ የታይዋን የኢንዱስትሪያላይዜሽን ልማት አፈጻጸም በተጨባጭ መላውን የደሴቷን ዳር ድንበር የሚያካልል እንደነበር ሲገልጽ፡-

> "በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የኢንዱስትሪ ልማትን ጨምሮ ሁሉንም ዕድገት የሚያመጣው ዋናው ሞተር የግብርና ዕድገት ነው፡፡ ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተመለከትነው ከዚህ አኳያ በታይዋንና በኮሪያ መካከል በጣም ትርጉም

ያለው ልዩነት ነበር፡፡ በታይዋን ግብርና በከፍተኛ ፍጥነት ያድግ ስለነበር፣ በዚህ ዕድገት ሳቢያ ቀልጣፋና ኃይለኛ የተወዳዳሪነት ብቃት ያዳበሩ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በመላ ደሴቷ ሊስፋፉ በቅተዋል፡፡ በአገሪቱ የቁጠባ ምጣኔ እጅግ ከፍተኛ ነበር፡፡ በታይዋን የነበረው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካት ምዕራፍ ይህን በመሰለ የግብርና ስኬታማ ፈጣን ዕድገት ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡"[86] በማለት ገልፆታል፡፡

በተጨማሪም በዚሁ ክፍል ግብርናን መሠረት ያደረገው ዕድገት መላውን የደሴቲቱን ግዛት በሚሸፍን ደረጃ ለገጠር ኢንዱስትሪያዊ ልማት ያበረከተውን ሰፊና ጉልህ አስተዋጽዖ፡-

"በከፍተኛ ፍጥነት የተስፋፋው የገጠር መሠረተ-ልማት በገጠር አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ከማድረጉም በላይ፣ ይህንኑ በመክተል የገጠር ከተሞች ባልተማከለ አኳኋን እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ይህን የመሰለው ያልተማከለ የኢንዱስትሪያዊ ልማት ሂደቶችና የከተሞች መስፋፋት አምራቾች [Entrepreneurs] በገጠር ያላቸውን ማኅበራዊ ሀብት፣ መሬት፣ ማኅበራዊ ግንኙነትና የቤተሰብ ጉልበት በመጠቀም የምርት ተቋሞቻቸውን እንዲያስፋፉ አስችሏቸዋል፡፡ እነዚህ መልካም ዕድሎች የመነሻ ካፒታላቸውና የሥራ ማስኬጃ ወጭያቸው አነስተኛ እንዲሆን ብቻ ሳይሆን፣ ማኅበራዊና ቤተሰባዊ ትስስሮችን ለችግር መፍቻነት እንዲጠቀሙባቸው ያስቻሉ ነበሩ፡፡ ይህ ሁሉ ተዳምሮ በመላ ደሴቷ አነስተኛ የምርት ተቋማት እንደእንጉዳይ ሊፈሉ በቅተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተቋማቱ ለግብርና ዕድገት ተፈላጊ የሆነውን ግብዓት በፍጥነት በማቅረብ በግብርና በኩል ለሚቀስቀሰው ፍላጐት ቀልጣፋ ምላሽ የመስጠትና ተጨማሪ የሥራ ዕድል የመፍጠር ብቃትም ነበራቸው፡፡ ሚሊዮኖች ከግብርና በመውጣት ግብርና ነክ ወዳልሆኑ የሥራ መስኮች ከመሸጋገራቸው በተጨማሪ፣ በጣም ብዙ አርሶ አደሮች ከግብርና ውጭ ባሉ ተጨማሪ የሥራ ዕድሎች በመታገዝ ገቢያቸውን እንዲደጉሙ አስችሏቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት በ1966 አካባቢ [በገጠር] ከግብርና ውጭ ይገኝ የነበረው የአርሶ አደሮች ተጨማሪ ገቢ 34% ብቻ የነበረ ሲሆን በ1980 ግን ይህ አሐዝ ወደ 70% ከፍ ብሏል፡፡"[87] በማለት ባቀረበው በጥናት የተደገፈ ማስረጃ አመላክቷል፡፡

ከዚህ የመለስ ጥናታዊ ጽሁፍ የታይዋን ዕድገት መሠረቱ ግብርና ቢሆንም፣ የታይዋን ግብርና መሠረተ-ሰፊ የኢንዱስትሪና በዚህ ላይ የተመሠረቱ ያልተማከሉ ከተሞች ልማትን

ያዘዘተለ ዝቤታዊ ጥፀዐና አንደገዘረው ለመገንዘብ ይታላል። ከፍ ሰል በገጠር የአርሶ አደሩን የግብርና ምርታማነት ለማሳደግ ተፈላጊ የነበሩትን ግብዓቶችና አገልግለሎቶች ያቀርበ የነበሩት የገጠር ኢንዱስትሪዎች፣ ካፒታል ከግብርና ወደኢንዱስትሪ ያለማቋረጥ እንዲሸጋገር በር የከፈተ ነበሩ። በመሆኑም የገጠር ኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ እዘያው በዚያው በግብርናና ኢንዱስትሪ መካከል ያለውን የካፒታል ሽግግር ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለመፈጸም ያስቻላል። የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያዊ ልማት ቀጣይና ዘላቂ ዕጣ ፈንታ፣ የአቅጣጫውን ፋይዳ ተገንዝቦ በዚሁ ከልብ በመመራት ከብከለት የጸዱ ፋብሪካዎች በአገሪቱ ገጠሮች የሚስፋፋፉበት እንዲሆን ከማድረግ ወይም ካለማድረግ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። ኢንዱስትሪ "የገጠርና የከተማ ተብሎ ሊከፈል አይገባም" የሚለው በቅጡ ያልተጤነ አስተሳሰብ ውሃ የማይቋጥር የሚሆነውም ለዚህ ነው። ሺ ቹንግ (2006) እንደሚለው የገጠር ኢንዱስትሪ ያልተማከሉ ከተሞችን በማስፋፋት የማታ ማታ ራሱን ወደከተሜነት የሚቀይር አቅጣጫ ነውና።

የአገራችን አርሶ አደር ገንዘብ እያገኘ ነው። በዚህ ገንዘብ የራሱን የግብርና ምርቶች በፋብሪካ እሴት ሊጨምርባቸው ወደሚችልበት የገጠር ኢንዱስትሪያዊ ስምሪት ሊሸጋገር ይችላል። በዚህ ኢንዱስትሪ የአገሪቱን የውስጥ ገበያ ከመከላከል አልፎ በውጭ የሚገኙ ገበያዎችን ወደማጥቃት ሊሸጋገር ይችላል። ቻይና ለኤክስፖርት ከምታቀርባቸው ምርቶች 43 በመቶ ያህሉ በቻይና የገጠር ኢንዱስትሪ የተመረቱ ናቸው። በቻይና ገጠሮች የተመረቱ ሴራሚከስ የቤት ወለልና የግድግዳ ንጣፎች፣ በሮችና መስኮቶች፣ የአሉሚኒየም ፍሬሞች፣ ኮርኒሶች ወዘተ... የዓለምን ትልልቅ ከተሞችና ሰማይ ጠቀስ ሕንጻዎች የሚያቆሙና የሚያስውቡ ምርቶች እንደሆኑ ነቃሽ መጥራት አያሻም። የቻይና ገበሬዎች የሚያመርቷቸው ኑድልስና ሌሎች ምርቶች እዚህ አገራችን ድረስም ዘልቀው ገብተዋል። ይህም በገጠር ለጥሬ ሀብቱ በቀረበ አካባቢ፣ ለዚያውም በአርሶ አደር ባለቤትነት የሚገነቡ የግኑፋክቸሪንግ ተቋማት አማራጭ የማይገኝላቸው የኢንዱስትሪ ልማት መሠረቶች እንደሆኑ የሚያመለክት ነው። ሺ ቹንግ "የቻይና የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ፖሊሲ" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ መግቢያ ላይ፡-

> "የቻይና ኢኮኖሚ ዋነኛ ባሕርይ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ነው። ይህ በአርሶ አደሮች የተያዘ የገጠር ኢንዱስትሪ ወደ 130 ሚሊዮን ያህል የሰው ኃይል ይቀጥራል። የገጠር ኢንዱስትሪ በቻይና ኢኮኖሚ ውስጥ እጅግ ተነቃናቂውና /Dynamic/ ጠቃሚው ዘርፍ ሆኗል። የገጠር ኢንዱስትሪ ከቻይና ሪፎርሞች መካከል እጅግ ስኬታማውና ለአገሪቱ ኢኮኖሚ የላቀውን አስተዋጽኦ ያበረከተ ነው። በገጠር ኢንዱስትሪ ረገድ ስኬት ባይኖር ኖሮ በቻይና ውስጥ የኢኮኖሚ ሪፎርም ሆነ ፈጣን ዕድገት አይኖርም ነበር። የቻይና የተጋጋለ የገጠር ኢንዱስትሪ

ዕድገተ፡ ዘየአካባዚዚው ዘመኑ ሚሊዮኖተ የሚቀጠሩ አርሶ አደሮቸን ከግብርና ወደኢንዱስትሪ ለማሸጋገር፣ የመንግሥትን የኢንዱስትሪ ባለቤትነት ለማለፍና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ፍጥነት ወደኢንዱስትሪያዊነት ለመግፋት አስችሏል። ስለሆነም የገጠር ኢንዱስትሪ የቻይና ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አንቀሳቃሽ ሞተርና ተዓምር እስከመሆን ደርሷል። እናም ከዘመናዊ ቻይና ጠቃሚ የኢኮኖሚ ባሕርይ መካከል አንዱ የገጠር ኢንዱስትሪያዊ ልማት ነው።

... ቻይና ትልቅ አገር ብትሆንም ቀደም ሲል ኢኮኖሚዋ ትንሽና በዓለም ላይ ትርጉም ያለው ተፅዕኖ ያልነበረው ነው። አሁን ባለው የግሎባላይዜሽን ማዕበል ግን የቻይና ኢኮኖሚ እጅግ ፈጣን የዕድገት ምጣኔ በማረጋገጥ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓትን እየተቀላቀለ ትርጉም ያለው ተፅዕኖ በማሳረፍ ላይ ሲሆን የአገሪቱ የገጠር ኢንዱስትሪ ደግሞ እጅግ የተለየ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። እ.ኤ.አ. በ2002 ከቻይና አጠቃላይ የወጪ ንግድ 43 በመቶ ያህሉ የገጠር ኢንዱስትሪዎች አስተዋጽኦ ነበር። ቻይና በዓለም ገበያ ላይ ያላት ተፅዕኖ እውን የሆነው በዋነኛነት በገጠር ኢንዱስትሪዋ ምክንያት ነው። ዛሬ የቻይና የገጠር ኢንዱስትሪ ምርቶች የትኛውንም የዓለማችን ማዕዘን እያጥለቀለቁ ይገኛሉ። ጨርቃ ጨርቅና አልባሳትን ጨምሮ በብዙ ምርቶች ረገድ የቻይና የገጠር ኢንዱስትሪ ለዓለም ገበያ ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ያበረከታል። የማይነጥፍ የጉልበት አቅርቦትና ተመጣጣኝ ዋጋ የቻይና የገጠር ኢንዱስትሪ በዓለም ላይ ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆን ያበቁት ምክንያቶች ናቸው። ቻይና የዓለም ንግድ ድርጅትን ከተቀላቀለች በኋላ ደግሞ በቻይናና በዓለም ገበያ መካከል ያለው ትስስር ይበልጥ እየተቀራረበ የገጠር ኢንዱስትሪዋ ከባድ ተፅዕኖ አድራጊ ይሆናል። እናም በአሁኑ ወቅት እያንዳንዱ አገር በቻይና የገጠር ኢንዱስትሪ በተፈጠረለት መልካም ዕድልና በተደቀነበት ፈተና ፊት ቆሞ ይገኛል።"[88] ይላል።

ሺ ቹንግ እንዳለው ይህን የመሳሰሉ ኢንዱስትሪያዊ ተቋማት በገጠር በሚበራከቱበት ጊዜ፣ በግብርና መፈጠር የጀመረው ካፒታል በአጭር ጊዜ በከፍተኛ መጠን ይባዛል። በትንሹ መከማቸት የጀመረው ካፒታል ለሌላ ሰፊ የካፒታል ክምችት መነሻ እየሆነ፣ ከባድ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት የሚያስፈልገው የገንዘብ አቅም በአስተማማኝ ደረጃ መጠራቀም ይጀምራል። መለስ *"ሰፊ መልከዓ-ምድራዊ ሽፋን"* ያለው የግብርና ዕድገትና ይህን ተከትሎ የሚከናወን የከተሞች መስፋፋት ከፍተኛ ብዜታዊ ተፅዕኖ [Multiplier effect] አለው"

በማለት እንደገለጸው፤ በቻይና ግብርናን ማዕከል አድርጐ የተካሄደው ፈጣን የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት፣ ከተሞችን የማስፋፋትና እጅግ ተነቃናቂ ልማታዊ አገር ለመፍጠር ያስቻለ ከፍተኛ ብዜታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ ሊሆን ቻለ፡፡ በነገራችን ላይ አዳም ስሚዝም በግብርና ዙሪያ የሚካሔደው ልማት ለኢንዱስትሪ መሠረቱ እንደሆነ *"የሰው ልጅ ተቋማት የነገሮችን ተፈጥሯዊ ሂደት ባያውኩ ኖሮ፣ በየትኛውም የፖለቲካ ማኅበረሰብ ውስጥ ታዳጊ የሀብት ፈጠራና የከተሞች ልማት ከየአካባቢው የግብርና ልማት ጋር በጥብቅ የተቆራኘና የዚህም ውጤት ይሆን ነበር።"*[89] በማለት ያረጋግጣል።

ይህ አቅጣጫ በቻይና ብቻ ሳይወሰን ለኢትዮጵያም የሚሠራ ነው፡፡ መሠረቱ ግብርናና ገጠር የሆነው የኢትዮጵያ ፈጣን ልማት፣ የገጠር ኢንዱስትሪንና በዚህ ላይ የተመሠረቱ ከተሞችን ለማልማት እጅግ የተመቸ ሁኔታ የሚፈጥርና መፍጠርም የጀመረ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ለአገራዊ ምርት ዕድገት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያለው የገጠሩ ኢኮኖሚ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ ለኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል በርከት ያሉት በገጠር መፈጠር ጀምረዋል፡፡ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት ለሚጨምሩም ሆነ የግንባታ ቁሳቁሶች በማምረት ተግባር ላይ ለሚያተኩሩ ኢንዱስትሪዎች ልማት ተፈላጊ የሆነው ጥሬ ዕቃ በስፋት የሚገኘው በግብርናና ገጠር ነው። የሠራተኛ ጉልበት፣ ካፒታልና በተወሰነ ደረጃ የመሸመት አቅም ያለው ገበሬ በብዛት እየተፈጠረ ያለውም በገጠር ነው፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያ በገጠር መፍጠር የጀመረችውን ለኢንዱስትሪ ልማት መተማመኛ የሆነ አቅም በአግባቡ ልትጠቀምበት ይገባታል፡፡ አርሶ አደሩን ጨምሮ አገራዊ ባለሀብቶች ለጸጋዎቹ በቀረቡት የገጠር አካባቢዎች በሚካሔዱ የኢንዱስትሪ ልማት ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህም የሀብት ፈጠራ ሂደቱን በኢንዱስትሪ ልማት ላይ የተመሠረተ ወደማድረግ መሸጋገር ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በተጻራሪ በኢትዮጵያ ገጠሮች ኢንዱስትሪ እንደ እንጉዳይ ካልፈላ በስተቀር፣ የግብርና ምርቱን አሳድጐ ይህንኑ እየሸጠ ገንዘብ ማከማቸት የጀመረው አርሶ አደር፣ የራሱን አገር ሳይሆን የቻይናን ኢንዱስትሪያዊ ምርት ሲሸምት የሚመሸበት ይሆናል፡፡ ሺ ቼንግ ከገለጻቸው ሁለት አማራጮች መካከል በቻይና ከተፈጠረለት የገጠር ኢንዱስትሪ መልካም ዕድል ይልቅ፣ የተደቀነበትን ፈተና ለመጐንጨት ይገደዳል፡፡ በኢትዮጵያ ይህን አደጋ ተገንዝቦ ለገጠር ኢንዱስትሪ መስፋፋት ትኩረት የማይሰጥ አቅጣጫ፣ መቼም ቢሆን አገራዊ የኢንዱስትሪ ልማትን እውን ሊያደርግ አይችልም፡፡ ይህ በተዘነጋበትና በተሳሳተ የመማለል አቅጣጫ የቱንም ያህል የውጭ ካፒታል ወደኢትዮጵያ ቢፈስ፣ የኢንዱስትሪ ልማትን በሩቁ ካልሆነ በስተቀር በቅርቡ መመልከት አይቻልም፡፡ ወደባንግላዴሽ የጐረፉ የቱርከና የእንግሊዝ ባለሀብቶች ባንግላዴሽን ወደኢኮኖሚ ከፍታ እንዳላወጧት ሁሉ፣ ከባንግላዴሽ የሸሹ የውጭ ባለሀብቶች

ኢትዮጵያንም ወደልማት ማማ ሊያወጧት አይተሉምና::

ይህ ጉዳይ የዛሬና የቅርብ ርቀት አገራዊ ፈተና እንዲሆን የሚያደርገው ሌላም ብዙ ነገር ማንሳት ይቻላል:: ግብርና መሻሻል ባሳየበት በዚህ አገራዊ የትንሳኤ ዘመን፣ ከገጠር ወደከተማ የሚፈልሰውን የሰው ኃይል በየአቅራቢያው መምጠጥ የሚችል ኢንዱስትሪ ካልተስፋፋ በስተቀር፣ የዚህ የሰው ኃይል ዕጣ ፈንታ በትልልቅ ከተሞች የተከማቸ ሥራ አጥ መሆን ይጀምራል:: ስለዚህም በኢትዮጵያ ገጠሮች ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ ይህን ወደትልልቅ ከተሞች ሊጐርፍ የሚችል ኃይል በየአካባቢው ማስቀረት ይገባል:: ኢንዱስትሪ በገጠር እንዲስፋፋ የማድረግ ጉዳይ ያልተማከለ ስምሪትና ርብርብን ይጠይቃል:: ያልተማከለው የኢንዱስትሪ ልማት በየአካባቢው የህዝብ ሰፊ ተነሳሽነት እንዲኖር ያደርጋል:: በአንጻሩ የተማከለውና በትልልቅ ከተሞች ላይ የሚታጠረው የኢንዱስትሪ ልማት፣ ከባቢያዊ ተነሳሽነትን በመገደብ ዕድገቱ የሚፈለገውን ያህል እንዳይሆን ያደርጋል:: የቻይናና የቬትናምን ልምድ በንጽጽር የሚተነትነው ክሪስ ብራማል ይህን በማስመልከት:-

> "ቻይና ከ1978 በኋላ ባለው የምሥራቅ እስያ ማዕቀፍ የገጠር ኢንዱስትሪን በማስፋፋት ያስመዘገበችው ስኬት ከቬትናም ውድቀት ጋር ተነጻጽሮ ሊታይ የሚችል ነው:: እንደሚታወቀው ቻይናና ቬትናም በተመሳሳይ ቅኝት ደረጃ በደረጃ የሚካሔደውን /Gradualist/ የሽግግር ፖሊሲ የመረጡ አገሮች ነበሩ:: ይሁን እንጅ ቬትናም የተከተለችው የኢንዱስትሪ ፖሊሲ እጅግ የተማከለ ነበር:: አብዛኛው የኢንዱስትሪ ምርት በተማከለ እቅድ ከመመራቱ በተጨማሪ፣ በገጠር ከሚካሔድ የማዕድን ቁፋሮ በተጓዳኝ የሚካሔድና በከተሞች የታጠረ ነበር:: የገጠር ኢንዱስትሪም ደብዛው አልነበረም:: በዚህ ምክንያት በሽግግሩ ዋዜማ ላይ የነበረው የቬትናም የገጠር ኢንዱስትሪ መሠረት በጣም ደካማ፣ ስለሆነም ደግሞ የ1990ዎቹ የልማት ስትራቴጂዋ ተፈላጊውን ፈጣን ዕድገት መቀስቀስ የተሳነው ሊሆን ተገደደ:: ይህም በቬትናም ውስጥ እየሠሩ የመማርን ሂደት በእጅጉ በመገደብ ፈጣን የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን እውን እንዳይሆን አደረገ::"[90] ይላል::

ስለሆነም ልማታዊ መንግሥታት ኢንዱስትሪን በመገንባት ረገድ የሚኖራቸውን ስኬት ወይም ውድቀት ከሚወስኑ ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ ባልተማከለ አቅጣጫ የሚስፋፋ የገጠር ኢንዱስትሪ ነው:: ከዚህ በተለየ ሁኔታ የተማከለ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ በሚከተሉ አገሮች፣ ወደከተሞች የሚፈልሰው ማኅበራዊ ኃይል በትልልቅ ከተሞች የተከማቸ ሥራ አጥ ለመሆን ይገደዳል:: ይህ በብዙ የደቡብ አሜሪካና የደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች በግልጽ

የታየ ነው፡፡ በነታይላንድ ከእድሜ በታች የሆኑ እድግ በፊ ቁጥር ያላቸው ቤተ ልዶቱን ጨምሮ ዝሙት አዳሪነት እንዲስፋፋ፣ ከዚህም ጋር የወሲብ ንግድ አንድ ማኅበራዊ ጉድፍ ሆኖ እንዲወጣ ያደረገው ም ይኸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ የዕድገት ፈለግ በገጠርና ግብርና ኢንዱስትሪ ተመጋጋቢ ልማት ላይ እንጅ፣ የቹላሎንኮን ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ በሆኑት ዶክተር ኒቴት ቲናኩል መረጃ መሠረት "ከ2.8 ሚሊዮን በላይ የወሲብ ሠራተኞችን" (Sex Workers) ባመረተው በታይላንድና መሰሎቿ አቅጣጫ የተቃኘ እንዳይሆን ከባድ ትግል ሲካሔድ የቆየው ከዚህ ሁሉ በመነሳት ነው፡፡

በእነዚህ አገሮች የታየውን መሰል ማኅበራዊ ጉድፍና መሠረታዊ ችግር ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ፣ ገበሬዎች ከገጠር መፍለስ ሲጀምሩ አካባቢያቸውን ሳይለቁ በአቅራቢያቸው እንዲከትሙ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህም አከታተም የገጠር መሸታ ቤቶችን ሳይሆን፣ ኢንዱስትሪን መሠረት ያደረገ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ልማታዊ አከታተም የሚያበቃቸው መሠረታዊና ሳይንሳዊ አቅጣጫ ደግሞ በገጠር የኢንዱስትሪ ልማትን ማስፋፋት ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ከአሁኑ የራሳችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ሊረጋገጥ የሚችል ነው፡፡ በየከልሉ ትምሕርት ጨርሰው በገጠር ውስጥ ሥራ ፈትተው የተቀመጡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች የሚያነሡትን የልማትና የእኩል ተጠቃሚነት ጥያቄ በትክክል ለመመለስ የሚቻለው በአንድ በኩል የገጠር ኢንዱስትሪ ልማትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ላይ የሚካሔድ መጠነ ሰፊ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የደንና የእንስሳት ሀብት እንዲሁም የመስኖ ልማትን በማስፋፋት ነው፡፡ ስለሆነም የገጠር ኢንዱስትሪ ልማትን ዘንግቶ ወይም ይህንኑ በማጣጣል፣ በተለይ ደግሞ በወጭ ካፒታልና በኢንዱስትሪ ፓርኮች አምልኮ ላይ የተመሠረተ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ መከተል ተፈላጊውን ዘላቂና አስተማማኝ የአገር ልማት እንደማያመጣ በጥብቅ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

አገራዊ ባለሀብት የመገንባትና የውጭ ባለሀብትን በብቃት የመምራት ፈተናዎች፣

የተፋጠነ አገራዊ ልማት ለማምጣት ሲታሰብ ይህንኑ ከማሳካት አኳያ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ኃይሎችን በትክክል መለየትና ሚናቸውን በብቃት እንዲጫወቱ ማድረግ ያሻል፡፡ በኢትዮጵያ ከዚህ አኳያ በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል የልማት አቅሞችን የመለየት ሥራ ተከናውኗል፡፡ መንግሥት፣ ህዝብ፣ አገራዊ ባለሀብቶችና ምሁራን አስተማማኝ የለውጥ አቅሞች እንደሆኑ ተለይተዋል፡፡ እነዚህ ተወደደም ተጠላም የኢትዮጵያ ዘላቂ ልማት መተማመኛ አቅሞች ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪና በደጋፊነት ደግሞ "የተመረጠ" የውጭ ካፒታል (አሁን አሁን በቁልምጫ ስሙ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመት /FDI/ ተብሎ ይጠራል) አንድ የልማት አጋር ሆኖ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም እነዚህ አስተማማኝና ደጋፊ ኃይሎች ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ ምቹ

ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል::

እነዚህ የልማት ኃይሎች በተለይ ደግሞ የአገር ውስጥና የውጭ ካፒታል ለአገራችን ዕድገት የሚበጅ ሚና ይጫወቱ ዘንድ ግን በአጠቃላይ ስለካፒታል በተለይ ደግሞ ስለውጭ ካፒታል ምንነት የጋራ መግባባት ይዞ መጀመር ተገቢ ይሆናል። የውጭ ካፒታል በሰው ልጆች የምርት እንቅስቃሴ ሂደት የተፈጠረ አንድ አይነት ማኅበራዊ ኃይልና ግንኙነት ነው። ካፒታልን የተቆጣጠሩት የሕብረተሰብ ክፍሎች ምን ጊዜም ቢሆን መነሻ ካፒታላቸውን አስማርተው የላቀ ካፒታል ለማከማቸትና ይህም የማያቋርጥ የክምችት ሂደት እንዲሆን ይሻሉ። ካፒታልን በቀጣይነት ለማከማቸት የሚችሉት ቅኝ ግዛት በማስፋፋትና በወረራ ከሆነ፣ አዳም ስሚዝ አውሮፓውያን "በቅኝ ተገዥ ህዝቦች ላይ በፍፁም ሕሊና ቢስነት ያልፈጸሙት ዘግናኝ ግፍ አልነበረም" እንዳለው የካፒታል ክምችት ሂደቱን በዘግናኝ መንገድ ጭምር ይፈጽሙታል። የካፒታል ክምችት በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ወይም ባልተመጣጠነ ንግድ ወይም በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መልክ የሚካሄድ ከሆነም በእነዚህ መንገዶች በጣምራ ወይም በማፈራረቅ የሚፈጸም ይሆናል። ስለሆነም በዘመነ ግሎባላይዜሽን ለትርፍና ለተስፋፋ የካፒታል ክምችት እንጅ ለጽድቅ ተብሎ የሚካሄድ የካፒታል ስምሪት አይኖርም። በዚህ ላይ ሌሎችን እያደኸዩ የመበልጸግ ቅኝት ያለው ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት ተያይዞ በማደግ መርህ የሚመራበት ቅንልቦና የለውም። በመሆኑም በተለይ አገራዊ ነጻነታቸውንና የህዝባቸውን ዴሞክራሲያዊ ዕድገትና ተጠቃሚነት ለማምጣት የሚሹ የታዳጊ አገሮች መንግሥታት የውጭ ካፒታልን "ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት (FDI)" በሚል የ"ክርስትና" ስሙ እያሸሞነሞኑ ይዞት የሚመጣውን ጣጣና በዚህ ረገድ ያለውን የአገራዊ ጥቅም ልዩነትና ትግል መሸፋፈንና ማድበስበስ አይገባቸውም። እርሱ ሊጠቀምብን እንደሚመጣው ሁሉ እኛም አገራዊ ጥቅማችንን ለማስፋት፣ የህዝባችንና የአገራችንን ጥቅም ለማሰጠበቅና ለማስፋት መዘጋጀት ይገባናል። የየራሳቸው የተለያየ ጥቅም ባላቸው ኃይሎች መካከል የሚደረግ ስምምነት በቅን ልቦና ሳይሆን በትክክለኛ አዕምሮ በማሰብና በመመራት ብቻ መፈጸም እንዳለበት ከአፍሪካውያን ቅንነትና ይህ ብቻውን ከአስከፊው ቅኝ አገዛዝ ሊያላቅቃቸው ካልቻለበት የራሳችን አህጉራዊ ታሪክ በመነሳት መገንዘብ የሚጠይቅ ነው።

ከዚህ በመነሳት ከኢንዱስትሪ ልማት አኳያ ዋናው አቅም ወይም አንቀሳቃሽ ሞተር የአገር ውስጥ ባለሀብት መሆኑን በማስመር መጀመር ለማንኛውም ሥራና ትግል መሠረቱ ሊሆን ይገባዋል። ይህ በመንግሥትም ሆነ በውጭ ባለሀብት (ካፒታል) ሊተካ የማይችል ሞተር ነው:: የተመረጠ የውጭ ካፒታል በመንግሥት ልማታዊ አቅጣጫ እየተመራ በደጋፊ ኃይልነት መንቀሳቀሱ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ቢሆንም፣ የአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚመሠረትበት መተማመኛ አቅም ሊሆን አይችልም፤ አይገባውምም:: ይህ የውጪው

ባለሀብት በጭፍን ስለሚጠላ ወይም ስለሚፈራ የተደረሰበት አቋም አይደለም፡፡ ከራሱ ከውጪው ባለሀብት ደካማና ጠንካራ ጐኖች፣ እንዲሁም እነዚህ በብዙ አገሮች ላይ ካሳረፉት ተፅዕኖና ድሃና ታዳጊ አገሮች ካለባቸው ከባድ የብቁ አመራር እጥረት ጋር ተያይዞ በተሠማራበት አገር ሁሉ ከሚፈጥረው ምሥቅልቅል በመነሳት የሚደረስበት ድምዳሜ ነው፡፡

የውጪው ባለሀብት እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉ አገሮች ላይ ሲሰማራ ብዙ መልካም ነገሮችን ይዞ የመምጣቱን ያህል፣ አያሌ ደካማ ጐኖች ያሉትና ጉዳቶችም የሚያስከትል ነው፡፡ ከመልካም ጐኖቹ በመጀመር ሲታይ ቀዳሚ ጥንካሬው ካፒታል ወይም የውጭ ምንዛሪ ማምጣቱ ነው፡፡ በተጨማሪም ቴክኖሎጂና የውጭ ገበያ ትስስር ይዞ ይመጣል፡፡ በሚከፍታቸው ተቋማት ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራል። በውጭ ተቋማት ተቀጥረው የሠሩ የአገር ልጆች ለሥራ ያላቸው አመለካከት እንዲሻሻል፣ እጅና አእምሮዋቸው እንዲፋታታ በማድረግ የሥራ ዲስፕሊንም ያስተምራል፡፡ ከአገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር በሽርክና በሚሰራበት ጊዜ ደግሞ አነሰም በዛም ልምድ ያካፍላል፡፡ በተለይ ደግሞ የእኛ ሰዎችና ተቋማት ቴክኖሎጂ ለመማር ትጋቱ ካላቸው የእውቀት ሽግግር ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ በራሱ መልካም ፈቃድ የሚያሸጋገረው የተሟላ ቴክኖሎጂ ባይኖርም፣ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ሽግግሩ እንዲፈጸም ማድረግ ከተቻለ ለቴክኖሎጅ ልማት በር ሊከፍት ይችላል፡፡

ይህም ሆኖ የላይኞቹ ጠቀሜታዎች የሳንቲሙ አንድ ገጽታ እንጂ ብቸኛ ገጽታዎች አይደሉም፡፡ የውጪው ባለሀብት ይዞዋቸው የሚመጣ ብዙ ደካማ ጐኖች ወይም አደጋዎችም አሉ፡፡ ይህን እ.ኤ.አ. ከ1870 ጀምሮ የነበሩ የሠራተኛ ንቅናቄዎችን በዝርዝር ያጠናችው ቢቨርሊ ጀ. ሲልቨር፡-

> "በሠራተኛው ንቅናቄ ዘንድ ስለሚታየው መዳከም ከሚቀርቡ የተለመዱ ትንታኔዎች አንዱ፣ በሃያኛው ክፍለ-ዘመን እጅግ ፈጣን ተነቃናቂ / Hypermobile/ የሆነው ካፒታል በዓለም ደረጃ ሁሉም ላብአደሮች እንዲፎካከሩ የሚያስገድድበት አንድ ዓለማዊ የጉልበት ገበያ መፍጠሩ ነው፡፡ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች የምርት ተግባርን ከአንዱ የዓለም ግማሽ ወደሌላው በቅጽበት በማዛወር ወይም አዛውረዋለሁ ብሎ በማስፈራራት፣ እጅግ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ላብ አደሮች ጉልበታቸውን በርካሽ ሸጠው ለማደር እርስ በርስ እንዲፎካከሩ ጫና ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የሠራተኛው የመደራደር አቅም ቀንሶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሥራና ከከፍያ አኳያ ወደታች እየወረዱ መፎካከር /Race to the Bottom/ ተቀስቅሷል፡፡"[91] ትላለች፡፡ከዚህ የሲልቨር አገላለጽ በመነሳት ስለውጭው ባለሀብት ወይም ካፒታል ብዙ

ማለት ይቻላል። ስለተነቃናቂነቱ፤ የምርት ተቋማትን ትርፍ ወደሚያገኝበት ቦታ በቅጽበት የሚያዛውር ስለመሆኑ፤ ሉዓላዊ መንግሥታትን የሚያስፈራራ ስለመሆኑ፤ ሠራተኞችን በዝቅተኛ ምንዳ ለመሰዝበር ሳይተኛ የሚያድር ስለመሆኑ፤ በዘመነ ግሎባላይዜሽን የሠራተኛው ዕጣ ፈንታ ወደታች እየወረዱ መወዳደር ስለመሆኑ፤ በአጠቃላይ የውጭ ካፒታልን ድክመት ወይም እርሱን ተከትለው ስለሚመጡ አደጋዎች ብዙ ነገሮችን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል።

የውጪው ባለሀብት ዘላን ባሕርይ ያለው መሆኑ ቀዳሚ ድክመቱ ነው። በብዙ አጋጣሚዎች እንደታየው በተሰማራባቸው አገሮች ላይ ትንሽ ችግር ካጋጠመ በመጣበት ፍጥነት ይወጣል። ሲወጣም ካፒታሉን ጠራርጎ በመውጣት የአገራቱን ቀውስ ያባብሳል። ይህ ባሕርይው የውጭውን ባለሀብት አስተማማኝ የልማት አጋር እንዳይሆን ያደርገዋል። በሌላ በኩል የውጪው ባለሀብት ካፒታልና የውጭ ምንዛሪ ይዞ የሚመጣ ቢሆንም፣ አብዛኛውን ጊዜ ትንሽ ገንዘብ አስገብቶ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወደአገሩ የሚመልስበትን የስምሪት ቦታ ይመርጣል። በትንሽ ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ትርፍ የሚያጋብስበትን (Low Volume High Return Investment) እንደማዕድን ዓይነት የስምሪት መስክ መምረጡ ይህን የሚያረጋግጥ ነው። የተራቀቀ ቴክኖሎጂ አምጥቶ ከመሥራት ይልቅ በአገሩ ለዘመናት የተጠቀመባቸውን፣ ነገር ግን ደግሞ የጉልበት ዋጋ በመናሩ ተወዳዳሪ መሆን ያልቻሉ መሣሪያዎቹን አድሶና ቀለም ቀብቶ መጠቀም ይመርጣል። ይህ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ፋብሪካዎችን በመመልከት ሊረጋገጥ የሚችል ነው። የውጭ ካፒታል ቴክኖሎጂን የማጋራት ፍላጎት፣ ባሕልና ሥነ-ልቦናም እጅግ ደካማ ነው። የተራቀቀውንና በከፍተኛ ምስጢርነት የሚጠብቀውን ቴክኖሎጂ መቼም ቢሆን በቀላሉ ያካፍላል ተብሎ አይታሰብም። ሊላው ቀርቶ ዘመን የሻረውን ቴክኖሎጂ ጭምር ምስጢር በማድረግ የትርፍ ምንጭ አድርጎ ሊጠቀምበት ከቻለ ይህን ከማድረግ ዓይኑን አያሽም። በዚህ ምክንያት የውጭ ካፒታል በማዞር፣ በማስገደድ፣ ከእርሱ ፈቃድ ውጭ በመኮረጅ ወይም በፖልሰን አገላለጽ ቻይናዎች አደረጉት በሚለው የቴክኖሎጂ ስርቆት ካልሆነ በስተቀር፣ በራሱ መልካም ፈቃድ ቴክኖሎጅ ያካፍላል ተብሎ በሰፊው አይጠበቅም።

የውጭ ካፒታል አብዛኛውን ጊዜ ወደአንድ አገር ገንዘብ የሚያስገባው አንዴ ወይም ሁለቴ ብቻ ሲሆን፣ ትርፉን ግን በየዓመቱ ወደአገሩ ያሸጋግራል። ከሚያስገባው ይልቅ የሚያስወጣው የውጭ ምንዛሪ እየበዛ መሔዱ በብዙ አገሮች ታሪክ በግልጽ የታየ ነው። ይህ በዛሬዋ ኢትዮጵያም በግልጽ የሚታይ ሆኗል። የውጭ ካፒታል ይዞት ከመጣው የውጭ ምንዛሬ ከአገር የሚያስወጣው መብለጥ ጀምሯል። በዚህ ላይ እንደ ኢትዮጵያ በሥላሳ ሰባ የብድር

አቅርቦት ፖሊሲ የሚያስተናግደው "አዛኝና ሩህሩህ" መንግሥት ሲያገኝ ደግሞ የውጭው ባለሀብት ከአገሬው ሰውም በላይ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል። ባለው የገንዘብ ኃይል ምርጥ ሙያተኞችን በመቅጠር ጥራት ያለው ፕሮጄክት የማዘጋጀት ብቃት የሚኖረው እርሱ ዘንድ ነውና፣ በርግጥም ዋናው የፖሊሲ ተጠቃሚ መሆን ይችላል። በዚህ ላይ በየመሥሪያ ቤቱ ፈረንጅ አምላኪ ሰዎች ሲኖሩ፣ የአገሬው ዜጋ ይበልጥ ወደዳር መገፋት ይጀምራል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ማንኛውም የውጭ ካፒታል ወደአንድ አገር ስለመጣ ብቻ ተፈላጊው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ይገኛል ማለት አይደለም። የተሻለ ጥቅም የሚያስገኙ የውጭ ባለሀብቶች እንደሚኖሩት ሁሉ የባሰ ጉዳት የሚያስከትሉ የውጭ ባለሀብቶችም አሉ።

እነዚህ ከኢኮኖሚ አኳያ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳትና ጥቅሞች ናቸው። በፖለቲካው መስክ ተጨማሪ ጉዳቶች የሚያስከትል መሆኑ ደግሞ ችግሩን የሚያባብስ ነው። የውጭ ካፒታል የተደራጀ የሠራተኛ እንቅስቃሴ የሚጠላና የሚፈራ ስለዚህም የአገሬው ሠራተኛ ተደራጅቶ እንዳይደራደረው ባለ በሌለ አቅሙ የሚያደናቅፍ መሆኑ የመጀመሪያው ፖለቲካዊ ጉዳት ነው። በምዕራቡ ዓለም የተፈጠረው ካፒታል የራሱን አገር ለቆ ወደ እስያና ደቡብ አሜሪካ ከተሰደደባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው ለተደራጀ የሠራተኛ ኃይል ያለው ጥላቻና ፍርሀት ነው። ሠራተኛው ለመብትና ጥቅሙ የሚያካሂደው ትግል የተደራጀና ጠንካራ በሆነ ቁጥር ባለሀብቱ ትርፉን ለማጋራት መገደዱ አይቀሬ ነው። ይሁንና ከምንም ነገር በላይ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት የሚሻው ባለሀብት የትርፍ ክፍፍል የሚባል ጉዳይን በእጅጉ ይጠላዋል። ትርፉን ከሠራተኞቹ ጋር ከመካፈል ይልቅ፣ አገሩን ለቆ መሰደድን የመረጠው ከዚህ በመነሳት ነው። በመሆኑም የአገሩን የተደራጀ የሠራተኛ ንቅናቄ ፈርቶ የተሰደደ ካፒታል በደረሰበት አገር ሁሉ ሠራተኛው እንዳይደራጅ ባለ በሌለ አቅሙ ይረባረባል። ከራሱ አልፎ መንግሥት የሠራተኞችን የመደራጀትና ለመብትና ጥቅማቸው የመደራደር እንቅስቃሴ እንዳይደግፍ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርጋል። ይህ የሁሉንም ህዝብ፣ በተለይ ደግሞ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የአርሶ አደርና ሠራተኛ ማኅበረሰቦች ተጠቃሚነት ለማስፋት አልሞ ለሚሠራ ልማታዊ መንግሥት ከባድ ፈተና ነው። መንግሥት ለራሱ አገር ህዝቦች ጠንካራ ወገናዊነት ኖሮት፣ ይህንኑ በሚያወጣቸው ሕጐችና ጥብቅ አፈጻጸም ካላረጋገጠ፣ በተለይ ደግሞ ባለሥልጣናቱና ሲቪል ሰርቪሱ ከፈረንጅ አምላኪነት ፀድተው ህዝብን በማገልገል ቅኝት የሚንቀሳቀሱ ካልሆኑ በስተቀር፣ በእርግጥም ከባድ ፖለቲካዊ ፈተና መሆኑ አይቀርም።

የውጭ ካፒታል ወደአንድ አገር እንደመንጋ በሚፈስበት ጊዜ የመንግሥታት ሉዐላዊ ሥልጣን መሸርሸር የሚጀምር መሆኑም ሌላው ከባድ ፈተናና አደጋ ነው። ይህን በማስመልከት ሲልቨር በመስኩ ብዙ የጻፉ ምሁራንን ዋቢ በማድረግ "እጅግ ፈጣን ተነቃናቂ የሆነው ካፒታል የመንግሥታቱን ሉዐላዊ ሥልጣን በማያከራክር አኳኋን አዳክሞታል። መንግሥታት በተዳከሙና

የካፒታልን ፍሰት መቆጣጠር በተሳናቸው ቁጥር ደግሞ፣ የድጐማ /Welfare/ መንግሥቱን [በእኛ አገር ሁኔታ ልማታዊ መንግሥቱን] መልካም ባሕርይና እውነተኛ ዴሞክራሲ ጨምሮ የዜጐቻቸውን የኑሮ ሁኔታ የማሻሻልና የሠራተኞችን መብቶች የማስከበር ችሎታቸውን ያጣሉ::"[92]ትላለች::

ልማታዊ መንግሥታት በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ የሚከሰቱ አደጋዎችን ቀንሰው፣ የህዝባቸውን ተጠቃሚነት ለማስፋት ይችሉ ዘንድ፣ ጠንካራ መንግሥታት መሆን እንዳለባቸው አያከራከርም:: በአንጻሩ የውጭ ካፒታል የሚመራበት ርዕዮት ሊበራል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፣ በገባበት አገር ሁሉ መንግሥት ደካማና ማንንም የመቆጣጠር አቅም የሌለው እንዲሆን ይፈልጋል:: የመንግሥትን መዳከም ለማረጋገጥም ሳይተኛ ያድራል:: በተጨማሪም ትልቁ የኢኮኖሚ ግቡ፣ ገንዘብ ያለአንዳች ቁጥጥር መግባት መውጣቱን ማረጋገጥ በመሆኑ፣ የሉዓላዊ መንግሥታት ካፒታልን የመቆጣጠር አቅም እንዲዳከም ለማድረግ ከቶም ሳይቦዝን ይሠራል:: በመሆኑም በሩ ሁሉ ለውጭ ካፒታል ተበረጋግዶ ሲከፈት፣ ልማታዊ መንግሥታት የቆሙለትን ዓላማ በጥብቅ ለማስፈጸም ያላቸው አቅም በተነጻጻሪ መዳከም ይጀምራል።

ይህ እንኳን እንደኢትዮጵያ ለመሳሰሉ ገና የዜጐች የነፍስ ወከፍ ገቢ አንድ ሺህ ዶላር እንኳ ያልደረሰባቸው አገሮች ቀርቶ፣ ወደሠላሳ ሺህ ዶላር በተጠጉት በነደቡብ ኮሪያ ላይ ሳይቀር ትልቅ ቀውስ ያስከተለ ነው:: ከሪስ ብራማል(2000) በሃያኛው ከፍለ ዘመን መጨረሻ በምሥራቅ እስያ ለተከሰተው የፋይናንስ ቀውስ አንድ መሠረታዊ ምክንያት አድርጐ የገለጸው ይህንኑ ያልተገባ ሊበራላይዜሽን ነበር:: አንድ ድሃና ያልበለጸገ አገር ተስፋውን ሁሉ በውጭ ካፒታል ላይ ማንጠልጠልም ሆነ ደረጃውን ያልጠበቀ የሊበራላይዜሽን አቅጣጫ መከተል የማይኖርበት ለዚህ ነው። እንደ ኢትዮጵያ የመሰሉ አገሮች ዕጣ ፈንታ በበጐ የሚወሰነው ለራስ ዜጐችና አገር በቀል ካፒታል የበለጠ ምቹ የሥራ ሁኔታ በመፍጠርና በቅድሚያ የራስን አገራዊ አቅም በመገንባት ነው።

ስለሆነም የውጭ ካፒታል በማንም የማይተካ ነገር ግን ደግሞ አገራዊ ጥቅሞችን በሚያሰፋና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ደግሞ በሚቀንስ አኳኋን መያዝ ይኖርበታል። የውጭ ካፒታል ብሔራዊ ጥቅምን ማዕከል የሚያደርግ የተለየና ጠንካራ አያያዝ ያስፈልገዋል። ስለሆነም ይህን ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ መያዝ ያለበት ኃይል ለማስተዳደር የተገነባን ብቃት በወከባና በጥድፊያ መናድ አይገባም:: ከዚህ በመነሳት አርከበ ዑቕባይ "አምራች ካፒታል እስከሆነ ድረስ በአገር ውስጥና በውጭ ካፒታል መካከል ልዩነት ሊደረግ አይገባውም"[93] በማለት ያመጣው የተሳሳተ የፖሊሲ አቅጣጫ በጥብቅ ሊስተካከል ይገባል። የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎችን ሁለቱ የሚመሳሰሉባቸው ብቻ ሳይሆን የሚለያዩባቸው ብዙ መሠረታዊ ጉዳዮች መኖራቸውን መነሻ በማድረግ ለአገራዊ ባለሀብት በሚወግን ቅኝት የተቀረጸ ነው። ስለሆነም

የተመረጠ የውጭ ካፒታል አስፈላጊና ጠቃሚ ቢሆንም፣ በማንኛውም መስፈርት ቢለካ የአገር ውስጥ ባለሀብት ከውጭ አምራች ባለሀብት የበለጠ ብሔራዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑ ለከርከር መቅረብ የለበትም::

በውጭ ባለሀብትና በአገር ውስጥ ባለሀብት መካከል ልዩነት የለም የሚለውና አርከበ በግሉ የፖሊሲ መመሪያ ያደረገው ይህ አቋም በአገራችን ላይ ብዙ ጉዳት እያስከተለ ነው። ይህን ጥቂት አብነቶች ወስዶ በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል:: ከሁሉ በፊት ከአገር ባለሀብትና ከውጭ ባለሀብት ዋናው የኢንዱስትሪ ልማት ሞተር ማነው? የሚለው ቀደም ሲል በትክክል ተቀምጦ የነበረው አቅጣጫ በበቂው ሳይመከርበት በኮንትሮባንድ መመሪያ እንዲሆን መደረጉ የፈጠረው ትርምስ አለ። አርከበ ያራመደው ይህ አቋም በ2007 ዓ.ም. መጀመሪያ በተከታታይ በተከፈቱ ሁለት መድረኮች በተካሔደ ውይይት መሠረታዊ ስህተት እንደሆነ በስብሰባው የተካፈሉ ከፍተኛ አመራሮች በግልጽ አመላክተው ነበር። ይሁንና አርከበ በእነዚህ ስብሰባዎች ያራመደው አቋም ከብዙኃኑ ጠንካራ ተቃውሞ አጋጥሞት እያለ በቀጣዩ ሳምንት በወጣው የፎርቹን ጋዜጣ የእርሱ አቋም የበላይነት እንዳለው አስመስሎ መግለጫ ሰጠ።

ለዚህ ስህተት አንዱ መነሻ አገሪቱ የምትመራበት በጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ የለም የሚለው የተሳሳተ ድምዳሜ ነው። አርከበ እ.ኤ.አ በ2012 "Made in Africa" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በእርሱ ከተካሔደው ጥናት ውጭ የኢንዱስትሪያዊ ልማትን በጥልቀት የዳሰሰ የቆየ ሥራ እንደሌለ አድርጎ ያቀርባል። የራሱን ሥራም በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ በኢንዱስትሪ ፖሊሲ ዙሪያ ለሚካሔደው ሙግት "ለመጀመሪያ ጊዜ የተበረከተ አስተዋጽኦ" (Novel Contribution) ሲል ያሞካሸዋል። እንደገናም "መጽሐፉ ቀደም ሲል ባልተሞከረ ደረጃ የፖሊሲ አስተዋጽኦ" (the most original policy implication of this book) የሚያበረክት እንደሆነ ከገለጸ በኋላ "የመጽሐፉ ደራሲ እስከሚያውቀው ድረስ "ከዚህ ሪሰርች በፊት ቀደም ሲል የተሠራ ይህን የመሰለ ጥልቀት ያለው ትንታኔ የለም" [94]ይላል።

ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ቢያንስ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ አላት:: ፖሊሲው እንደመና ከሰማይ የወረደ ሳይሆን ኒዮ-ሊበራሎች "የኢንዱስትሪ ፖሊሲ አያስፈልጋችሁም" በማለት ከሰጡት ምክረ-ሀሳብ በማፈንገጥ የተዘጋጀ ነው:: ጥልቀት ባለው ሪሰርች ላይ የተመሠረተና በተጨባጭ ከተገኙ ልምዶች በመነሳት በየጊዜው እየተሻሻለና እየዳበረ የመጣ ፖሊሲ ነው። ይህ የፖለሲ ሰነድ የኢንዱስትሪም ሆነ የገጠር ልማታዊ አብዮት መሐንዲስ የነበረው መለስ ዜናዊ ለረዥም ዓመታት ባካሄደው ጥናት ላይ በመመሥረት ከተዘጋጀና በ1994 ዓ.ም. ለውይይት ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ ሰፋፊ ሥልጠናዎች የተሰጡበትና የተግባር መመሪያ ሆኖ የተሠራበት ነው። አርከበ በጥናቱ ዳስሻቸዋለሁ የሚላቸውን

ጨምሮ ኢትዮጵያ ከቅርብ፣ ከመካከለኛና ሩቅ ዘመን በኋላ በትኩረት ልታለማቸው የምትችልና የሚገባትን ሴክተሮችና መተማመኛ አቅሞቿን በዝርዝር፣ በሳይንሳዊና የህዝብ ወገናዊነትን ባረጋገጠ መንገድ አስቀምጧል:: መነሻና መድረሻው የውጭ ካፒታል ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ካፒታልን መፍጠር ሆኖ የተዘጋጀና በመጽሐፍ መልክ ታትሞ ለህዝብ በይፋ የተሰራጨ ሰነድ ነው::

ይህ ክተሐድሶ በኋላ በነበሩት አስራ አምስት ዓመታት ያለው እውነታ ሲሆን፣ አርከበን ጨምሮ ብዙዎቻችን ነባር ታጋዮች እንደምናውቀው ኢሕአዴግ "የነጻ አገራዊ ግንባታ ጥያቄን" በተሟላ ጽሁፍ መልክ ያዘጋጀው በ1980ዓ.ም. ነው። ይህም መለስ ገና ትጥቅ ትግሉ ሳይጠናቀቅ ያዘጋጀውና ኢሕአዴግ ሥልጣን ሲይዝ ኢኮኖሚውን የመምራት ችግር እንዳይገጥመው ታስቦበት የተዘጋጀ ሰነድ ነበር። ጥናታዊ ሥራው ብዙዎቹ የትግሉ መሪዎች ገና ስለየትኛውም ዓይነት ኢኮኖሚክስ ማሰብ ባልጀመርንበት ጊዜ፣ መለስ ምን ያህል በጥናትና ምርምር ላይ ተሰማርቶ እንደነበር፣ ምንስ ዓይነትና ብዛት ያላቸው ልማት ላይ የሚያተኩሩ ጽሁፎች ያመርት እንደነበር ያሳያል።

መለስ በዚህ መጽሐፉ የደቡብ ኮሪያን ኢኮኖሚ በጥልቀት አጥንቶ በሚገርም ብስለት ተንትኖታል:: ብዙዎቻችን ስለልማታዊ መንግሥት ከማወቃችን 15 ዓመታት በፊት የሀያኛውን ክፍለ ዘመን ዋና ዋና ልማታዊ መንግሥታት ያጠናው መለስ፣ የኮሪያና ታይዋንን ኢንዱስትሪያላይዜሽን ያኔ ከነበረው ግራ ዘመም አስተሳሰብ እየተነሳ ተንትኖታል። መለስ በዚህ ሥራው በደቡብ ኮሪያ የተሟላ ነጻነት የተከበረበት ባይሆንም ኢንዱስትሪያላይዜሽን እውን እንደሆነ በማረጋገጥ የያቀረበው ትንታኔ ሁላችንም በወቅቱ እናልመው የነበረውን ግብ ለማሳካት ያነሳሳን እንደነበር መጽሐፉን ያነበቡ ሁሉ የሚያስታውሱት ነው። ስለሆነም በወቅቱ በአመራር ኃላፊነት ላይ የነበርን ሰዎች ከአገራችን አልፈን በደቡብ ኮሪያ ስላለው የልማት ዕድገት ይህ ነው የሚባል ግንዛቤ ባልያዝንበት ጊዜ፣ መለስ መሠረታዊ በሆነው የኢንዱስትሪ ልማት ዙሪያ ረጅም ርቀት የሔደ ሪሰርች ማድረጉ የሚያከራክር አይደለም:: ስለደቡብ ኮሪያ ዕድገት በልዩ ትኩረት ጥናት የሚያካሂድ ሰው አገሪቱ በአምሣ ዓመታት ውስጥ ግሎባል የኢኮኖሚ ኃይል /Economic Power House/ ስለሆነችበት ምስጢር፣ በተለይ ደግሞ ስለኢንዱስትሪ ፖሊሲዋ ሳያጠና ይቀራል ተብሎ ሊገመት አይችልም:: ስለዚህም የአርከበ ሪሰርች በኢትዮጵያም ይሁን በአፍሪካ ቀዳሚው ተደርጎ ሊቀርብ የሚችልበት እውነታ የለም።

ይህ በዚህ ከተቋጨ የባለሀብቶችን አያያዝ በተመለከተ፣ እስካሁን ባለው ቅኝትና ተግባራዊ አካሄድ ተወደደም ተጠላም ለውጭ ባለሃብቶች ቅድሚያ የሚሰጡ የኢንዱስትሪ ፖርኮች ልማትን ማስፋፋት ተጀምሯል። ሁለቱም እኩል እናያለን እስከተባለ ድረስ ቢፈለግም ባይፈለግም፣ እጅግ የላቀ የተወዳዳሪነት ብልጫ ይዘው የሚመጡት የውጭ ባለሃብቶች

በተጨባጭ ቅድሚያውን መውሰዳቸው አይቀርምና። ደካማ ኢኮኖሚዎችን ምንም እንኳ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደረጃውን በጠበቀ አኳኋን አስፈላጊ በመሆናቸው መልማት ያለባቸው መሆኑ ባያከራክርም፣ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ብቸኛ መነሻና መድረሻ ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም፣ አይገባቸውምም። ኢንዱስትሪያዊ ፖርኮች በራሳችን አገራዊ ባለሀብቶች በየገጠሩ እንደአንጉዳይ መፍላት የነበረባቸውን የማኑፋክቸሪንግ ተቋማት በመተካት ሳይሆን በመደገፍ ቅኝት ቢገነቡም ተቃውሞ የሚነሳበት አይሆንም። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ብቃት ለመገንባት ስትራቴጂ ተሸሽ በሚሆኑ የውጭ ኩባንያዎች ተባባሪ ሚና ላይ የተመሠረቱ ቢሆንም፣ ይህ መሠረታዊ አቅጣጫ እስካልተለቀቀ ድረስ አስቸጋሪ ይሆናል ተብሎ ባልተገመተም ነበር። አሊስ አምስደን፡-

> "ደካማ ኢኮኖሚዎች ተበረጋገደው በተከፈቱ ጊዜ ሁሉ በዓለማችን ከፍተኛ የመወዳደር ብቃት የገነቡት ኢኮኖሚዎች ከደካሞቹ የሚመጣባቸውን የኢምፖርት ጥቃት መቋቋምና መበልፀግ ይችላሉ። ጠንካራ ኢኮኖሚዎች ከነጻ ገበያ ለማትረፍ ሁሉም ነገር ተሟልቶላቸዋልና። በአንጻሩ ከውጭ የሚገባ የሸቀጥ ምርት የታዳጊ አገሮችን ጀማሪ ኢንዱስትሪዎች እየደመሰሰ ቢሆንም ሊበራላይዜሽን በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ ድሃ አገሮች እንደሚጠቅማቸውና በውጭ ኢንቬስተሮች ነጻ እንደሚወጡ ተደርጎ ይቀርባል። የድሃ አገሮች ኢንዱስትሪዎች የሚገነቡትና በባለቤትነት የሚያዙት በውጭ ኢንቬስተሮች ሆኗል። ገበያው ባለቤትነትን ከግምት ባያስገባም ድሃ አገሮች አስቀድመው ሊበራላይዝ ከማድረግ የሚያገኙት እምብዛም ጥቅም የለም።" ትላለች።

በእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ እየሆነ ያለው የዚህ ቀጥተኛ ግልባጭ ነው። የውጭ ባለሀብቶች ቁጠማ ተጐዝጉዘላቸው አሪቲ ተነስንሶ እሹሩሩ በሚባሉበት አገር፣ አንዳንዶቹ በመንግሥት ትከሻ የታዘሉና የለየላቸው ኪራይ ሰብሣቢዎች እስከመሆን ደርሰዋል። የሄንንም በተመለከተ በርከት ያሉ ጉዳዮችን ማንሳት የሚቻል ቢሆንም በዚህ መጽሐፍ ጥቂቶቹን በምሳሌነት ማንሳት ያስፈልጋል። ኢትዮጵያውያን የፐላስቲክ አምራች ኩባንያዎች መሬት የሚሰጣቸው አጥተው በኪራይ ቤት ተወዳዳሪ መሆን ሲያቅታቸው፣ የሕንድ ፐላስቲክ አምራቾች መሬት በፍጥነት አግኝተው ኢትዮጵያውያን አምራቾችን ባልተገባ የዋጋ ተፅዕኖ ከጨዋታ ውጭ ያደርጋሉ። አንድ ኢትዮጵያዊ ኩባንያ ለውጭ ገበያ(Export) መቅረብ የጀመረ የመጸዳጃ ቤት ንጽህና መጠበቂያ (Anti Septic) ያመርታል። በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን የመሰለውን ምርት አንድ የቱርክ ኩባንያ ለአገር ውስጥ ገበያ ያመርታል። የእኛው ልጅ በኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ተቃኝቶ ሲያመርት፣ ቱርካዊው ግን የቱርክን ገበያ ተከላክሎ፣

እዚህ በእኛ ገበያ ላይ የማጥቃት ስትራቴጂ ይሰነዝራል። በዚህ ላይ ኢትዮጵያዊው የውጭ ምንዛሬ ሲያስገባ፣ የቱርክ· ግን በከባድ ትግል ያገኘናትን የውጭ ምንዛሬ ወደ አገሩ ያሻግራል። በሁለቱ መካከል የምርት ተመሳሳይነት ያለ ቢሆንም፣ የእኛው· አምራች ኢትዮጵያዊው· የአገር ልጅና ዘላቂ መተማመኛችን በመሆኑ ቅድሚያ ሊሰጠው· ይገባል። ልማታዊው· የወንዛችን ልጅ ከልማታዊው· የባሕር ማዶ ሰው· በሁለመናው· ለነፍሣችን የቀረበ ነው·ና። በዚህ ጉዳይ ላይ እየሆነ ያለው· ግን ከዚህ በጣም የራቀ ነው። ቱርካዊው· በቀላሉ መሬት ያገኘ ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊው· ኩባንያ ግን ለረዥም ጊዜ መሬት የሚሰጠው· አጥቶ በኪራይ ቤት ያመርታል። ሌላም ቀላልና የባሰ አታሰማን የሚያሰኝ ምሣሌ, ማቅረብ ይቻላል።

አንድ ወጣት ኢትዮጵያዊ በአገራችን ፓርኮች እየተዘዋወረ ካሉን ከ900 በላይ ብርቅዬ ወፎች ከ770 በላይ የሆኑትን በፎቶና ፊልም ይቀርጻል። ያልገባበት ፓርከና በፎቶና ፊልም ቀርፆ ያላስቀረው· ነገር ጥቂት የሆነው· ይህ ወጣት፣ ለናሽናል ጂኦ-ግራፊ ሳይቀር ፊልምና ፎቶግራፎችን እስከ መሸጥ የደረሰ ነው። ያገኛትን አዲስ የወፍ ዝርያ ጨምሮ በቅርቡ ለንደን ላይ ባቀረበው· የፎቶግራፍ ትርዒት ትልቅ ተፅዕኖ አድራጊ ሊሆንና በራሱ ስም የተሰየመች ወፍ ባለቤት እስከመሆንም ይደርሳል። ይህን ሁሉ ምርጥ ሰነድ ይዞ የኢትዮጵያን ገጽታ የሚገነቡ· ፊልሞችን ማምረት የጀመረው· ይህ ወጣት፣ ባለው· ምርጥ የፊልምና ፎቶ ሀብት በመታገዝ ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቅ ቅንብር ለማዘጋጀት ወደቱሪዝም ቢሮ ሲሔድ፣ ያገኘው· ምላሽ ከአውስትራሊያ በመጡ ሰዎች ነው የምናሠራው የሚል ነበር። እዚህ ላይ አስገራሚው· ጉዳይ የአውስትራሊያው· የፊልም ኩባንያ የዚህን ወጣት ኢትዮጵያዊ ፊልሞች እየገዛ ለራሳችን መንግሥት ማቅረቡ ነው። የራሳችንን ምርት ለአውስትራሊያ ሰዎች በርካሽ ሸጠን፣ ያንኑ እንደገና ከእነርሱ በውድ መግዛታችን ምን ያህል አሳፋሪ እንደሆነ ለመገንዘብ ጠንቋይ መቀለብ የሚያሻው አይደለም።

በአገራችን ረዥም ታሪክ ያለውና ሠላሳ ሦስት ማሽኖች ተከለ· "ኮንጐ ጫማ" ያመርት የነበረው· የተካ ኤርጋንዶ ፋብሪካ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ቻይናውያን ኮንጐ ጫማ እንዲያመርቱ ፈቃድ ካገኙ በኋላ ተዘግቷል። ኮንጐ ጫማ ለማምረት የሚያስፈልገው· አንድ ማሽን ዋጋ 25ሺህ የአሜሪካን ዶላር ወይም በቆየው· የምንዛሬ ተመን አምስት መቶ ሺህ ብር ያህል ነው። ይህን ማንኛውም መቶ ሺህ ብር ያጠራቀመ ወጣት በባንክ ብድር ታግዞ ሊተክለው· ይችላል። በኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ኮንጐ ጫማ የሚያመርቱ ቻይናውያን ሳያስፈልጉን ራሳችን ልንሠራው· እንችል ነበር። የኤርትራው· ህዝባዊ ግንባር ገና መንግሥት ሳይሆን በበረሀ እያለ ያመርት የነበረው· ኮንጐ ጫማ የቴክኖሎጂ ውስብስብነትም ሆነ ክብደት የለውም። ስለዚህም ለአገራችን ልጆች ብቻ ተከልሎ መለማመጃ መሆን የነበረበት ኢንዱስትሪ ነው። ነገር ግን አርከበ እቁባይ "ሁለቱም እኩል ይታያሉ" የሚል ፖሊሲ በኮንትሮባንድ አስገብቶ ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ በኋላ የኮንጐ ጫማ ፋብሪካ በተግባር ለቻይና የገበሬ ኢንቨስተሮች ተክልሎ የተሰጠ

ኢትዮጵያውያን የማይደርሱበት ዘርፍ ሆኗል። ቻይናውያን የቤት ሠራተኛ ሳይቀር የሚያቀርቡ ደላሎች መሆን በጀመሩበት፣ በዚህ ወቅት የኢህአዴግን መንገድ በኮንትሮባንድ እየተካ ያለው የአርከበ የተምታታ ፖሊሲ አገራችንን ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍላት ዓመታት መጠበቅ ሳያስፈልግ ዛሬውኑ ለመገንዘብ የሚያዳግት ሆኗል።

ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ እንዲሉ ኢትዮጵያውያን የተለየ ድጋፍ ባይደረግላቸው እንኳ፣ "በአምራች ካፒታል መካከል የአያያዝና የባለቤትነት ልዩነት አናደርግም" በሚለው የተሳሳተ ሀሳብ በመመራት እኩል መስተንግዶ ሊደረግላቸው በተገባ ነበር። ነገር ግን የውጭ ሰው አምላኪነት በተጠናወተን ቁጥር የራሳችንን ወገኖች መጉዳታችን አይቀሬ ሆነና አድልዎው ለባእድ በማጋደል የሚፈጸም ሆነ። ይህ በብዙ ዘርፎችና ንዑስ-ዘርፎች በመታየት ላይ ያለ አደገኛና አሳፋሪ ዝንባሌ ነው።

በቅርቡ ወደሰሜን ፓርክ በሔድኩበት ጊዜ በዚህ ትልቅ ፓርክ ውስጥ ወዳለችው ብቸኛ ሎጅ ጐራ ብዬ ነበር። ይህች ሎጅ በአንድ ኢትዮጵያዊና እንግሊዛዊ የተመሠረተች ብትሆንም፣ ፈረንጁ ኢትዮጵያዊ ባልደረባውን አስወግዶ ሎጇን በብቸኝነት ተቆጣጥሯታል። ይህ በሁለት ኢንቨስተሮች መካከል የሆነ ጉዳይ በመሆኑ እንደፍጥርጥራቸው ሊባል ይችላል። የሚገርመውና ቁናው ነገር በታላቁ የሰሜን ፓርክ ውስጥ ይህ ፈረንጅ ካልፈቀደ በስተቀር ሌላ ሰው አዲስ ሎጅም ሆነ ሆቴል ሊገነባ የማይችል መሆኑ ነው። ይህ ያህሰ ይመስል ደግሞ መንግሥት በፓርኩ ውስጥ ወደበየዳና ጀናሞራ የሚያልፍ የኤሌክትሪክ መስመር ለመዘርጋት ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ የዚህ ፈረንጅ እንቅፋት ያልተለየው መሆኑ ነው። ይህ ነው የሚባል የማገዶ ምርት ለሌላቸው የሁለቱ ወረዳዎች ህዝቦች የኤሌክትሪክ አቅርቦት እጅግ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ አጋዥነት እንዳለው ታምኖበት የኤሌክትሪክ መስመር ለመዘርጋት እንቅስቃሴ ሲጀመር፣ እንግሊዛዊው የሎጅ ኢንቬስተር መንግሥትን "የዓለም ቅርስን በማበላሸት" ወንጀል ለዩኔስኮ እስከመክሰስ ደርሷል። ይህን የመሰለው ሁኔታ አፓርታይድ ተንሰራፍቶባት በኖረችው በደቡብ አፍሪካ ባለው በትልቁ የክሩገር ፓርክ ላይ ቢሆን አያስገርምም በተባለ ነበር። በፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ድል አድራጊ በሆነችው ኢትዮጵያ ላይ ሲታይ ግን ከማስገረምም አልፎ ያስደምማል።

ጨርቃ ጨርቅ ላይ የተሰማሩ የውጭ ኩባንያዎች ከኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ይልቅ በብዙ መልኩ ቅድሚያ ያገኛሉ። ከብድር እስከመሬት አቅርቦት በቀላሉ ይሳካላቸዋል። ይህም ሆኖ እነዚሁ ኩባንያዎች በከፊል ኪራይ ሰብሳቢ ቅኝት ሲንቀሳቀሱ ማየት ደግሞ እየተለመደ በመሔድ ላይ ነው። አንዱ የቱርክ ጨርቃ ጨርቅ ኩባንያ የኤሌክትሪክ ወጭ ላለመሸፈን ሲል፣ ጉቦ ሰጥቶ ቆጣሪ የሌለበት የኤሌክትሪክ መሥመር እንዲዘረጋለት አድርጐ ሲጠቀም እጅ ከፍንጅ ተይዟል። በአሥር ሚሊዮኖች ብር የሚገመት የኤሌክትሪክ ወጭ ላለማወጣት

የነፃ ገበያ ሥርዓት የፍላጎትና አቅርቦት ሁኔታዎች በመንደል መጠየቁ ነበረበት፡፡ ይህም ቀርቶ አስፈጻሚው መሥሪያ ቤት እንዳሰበው እንደገና ሂሳቡን ከፍሎ ቆጣሪ አስገብቶ እንዲሠራ መገደድ ነበረበት፡፡ ነገር ግን በውጭ ባለሀብት ከፉኛ መተማመን የተጠናወተው ኃይል ያለ ሥራው ገብቶ "ፈጽሞ እንዳትነኩት" በማለቱ፣ ኪራይ ሰብሣቢው የቱርክ ኩባንያ ሳይጠየቅ ሊሔድ ችሏል፡፡ ነገር ግን ይህ አነስተኛው ችግር ነው፡፡ ለኤክስፖርት ገበያ ምለው ተገዝተው ወደ አገር ውስጥ የገቡ የውጭ ኩባንያዎች አብዛኛውን ምርታቸውን እዚሁ መሸጥ ጀምረዋል፡፡

የውጭ ካፒታል አያያዛችን ከልማታዊ አቅጣጫ ያፈነገጠ ሲሆን በጉዳዩ ላይ ሁለት ተመጋጋቢ ስህተቶች ይሠራሉ፡፡ የመጀመሪያው ስህተት የአገራችንን ተስፋ ዋነኛ መተማመኛችን ባለሆነ ኃይል ላይ መገንባታችን ነው። ሁለተኛው ደግሞ ዋነኛ መተማመኛችን የሆነውን የራሳችን ኃይል ፈጽሞ ችላ የማለት መሠረታዊ ስህተት ነው፡፡ "የውጭ **ባለሀብት ከአገር** ውስጥ ባለሀብት **እኩል** ነው የሚታየው" የሚለው ዝንባሌ የአገሪቱን የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ከሥረ መሠረቱ የሚንድ የሆነው ይህን የመሰለ ስህተት ላይ ስለሚጥል ነው፡፡ ነባሩ ፖሊሲ ሁለቱን በእኩልነት የማያስቀምጥ ሆኖ እያለ እኩል ይታያሉ የሚለው አስተሳሰብ የመንግሥትን ትከከለኛ የፖሊሲ አቅጣጫ መናድ አስከትሏል፡፡ መንግሥት የውጭ ካፒታልን ሆነ የአገር ውስጥ ባለሀብቱን በጭፍን ጥላቻ ወይም ፍቅር ሳይሆን በተነጻጻሪ ጠቀሜታቸው መመልከት አለብኝ ብሎ ሁለቱን በማወዳደር ላይ ፖሊሲውን የገነባው አንድና እኩል የሚታዩ ስላልሆኑ ነው፡፡ የውጭ ባለሀብት የማይገባባቸው መስኮች እንዳሉ፣ ከእነዚህም ውስጥ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች መለማመጃ ሊሆኑ የሚገባቸው መስኮች ለውጭ ባለሀብቱ ፈጽሞ ሊከፈቱ የማይገባቸው እንደሆነ ወስኗል፡፡ የሃያ አምስት ሺህ ዶላር ዋጋ ያለው ማሽነሪ አምጥቶ አርሶ አደሮች የሚጠቀሙበት ኮንጐ ጫማ ለማምረት የቻይና ባለሀብቶች እንደማያስፈልጉንና በራሳችን ልንሠራው እንደምንችል ብዙ ማረጋገጫዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

የውጭ ካፒታል ዋናው የኢንዱስትሪ ልማት ምንጭ እንዳልሆነ በተሠመረበት ዓለም፣ ፈረንጅን ማማለል **የእውቀት** መጀመሪያና መጨረሻ ተደርጐ ተወስዷል፡፡ የአገር ውስጥ ካፒታል፣ በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ከምችት መፈጠር የጀመረው የገጠር ካፒታል ችላ ተብሎ አገር ምድሩ ለውጭ ካፒታል መስገድ ጀምሯል፡፡ ጆይንት ቬንቸር ሌጣውን ለቴክኖሎጂ ሽግግር የማያበቃ ሆኖ እያለ፣ከውጭ ኩባንያ ጋር ተሻርኮ ኪራይ ሲሰበስብ የሚውል ሁሉ ቴክኖሎጂን እንደሚያሸጋግር ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ በፋብሪኬሽን ምትክ፣ በኢንዱስትሪ ፖርኮች የገቡ ዝቅተኛ እሴት አመንጭ /Low Value Addition/ ሸቀጦችን በማምረት ጥበብ የተካኑ፣ ለዛውም ዘላን ባለሀብቶች የሚከፍቷቸው የውጭ ኩባንያዎች የኢንዱስትሪ ልማት የመጨረሻ ግብ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ፋብሪኬሽን ምን ማለት እንደሆነና እንዴት እንደሚከናወን ሳይገነዘቡ ገለጻ የሚሰጡ፣ "በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽንን እያስፋፋን ነው" ማለት

የማይታክቱ፣ ግን ደግሞ "የገጠር ኢንዱስትሪን በዓይናችን አያሳየን፣ በጆራችን አያሰማን" የሚሉ በበዙበት አገር፣ ቢያንስ የኢንዱስትሪ ልማት ይመጣ ይሆን? ወይ ብሎ ግራ መጋባትና ጥያቄ ማንሳት አይቀሬ ነው። ማርክ ትዋይን የአገሩን ዜጐች ታዝቦ ታዝቦ "ብዙዎቹ የአዋቂነት ካባ የደረቡ ቢሆኑም፣ የሚያውቁት ትክክለኛውን ሳይሆን የተሳሳተውን ጉዳይ ነው" ያለው ይህን ከመሰለው ሁኔታ ተነስቶ ነው።

ይህ ለራሳችን ወገኖች መብትና ጥቅም መከበር መንግሥት ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት ለማመላከት እንጅ የውጭ ሰዎች ፈጽሞ ሊደርሱብን አይገባም በማለት የቀረበ አይደለም። በውጭ ሰዎች ላይ ጭፍን ጥላቻ (Xenophobia) የማሳደር አመለካከት ከተቻለ እንዳይታይ፣ ካልሆነ ደግሞ በአገራችን የበላይነት ያለው አስተሳሰብ እንዳይሆን ማድረግ ይገባል። ከሁሉ በፊት አንድ ሰው ዜጋ ሆነ አልሆነ በአጠቃላይ በሰው ልጆች መልካምነትና መብታቸውን በማወቅና በማክበር ማመን ይገባል። ወደአገራችን የመጡ የውጭ ኢንቬስተሮች፣ በተለይ ደግሞ አፍሪካውያን ስደተኞች ተያይዞ በማደግ ቅኝት ሠርተው የሚከብሩበትም ሆነ በሰላም የሚኖሩበት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ ኢትዮጵያዊና አፍሪካዊ ግዴታችን ነው። ስለሆነም የውጭ ካፒታል አያያዛችን ይስተካከል ሲባል በኢ-ሰብዓዊነት አስተሳሰብ የሚነሳ አይደለም። መንግሥት ዋነኛ ኃላፊነቱ የሆነውን የአገሬውን ህዝቦችና የዜጐቹን ዕድገትና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ግዴታውን ይወጣ ለማለት ነው። የውጭ ባለሀብቶች ደጋፊ የዕድገት መተማመኛ አቅሞቻችን ብቻ እንደሆኑ በመገንዘብ በአግባቡና ሚዛኑ በተጠበቀ አኳኋን አመራር ይሰጣቸው ማለት ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዘመን እንዲመጣ ከተፈለገ እነዚህ እውቀት የሚመስሉና በየጊዜው በሚደረቱ ንግግሮች የሚደጋገሙ የተለመዱ ስህተቶች መወገድ አለባቸው። በኢንዱስትሪ ልማት ዙሪያ ኢህአዴግ ይዞት የተነሳው ጥርት ብሎ የተቀረጸ ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ በዲሲፕሊን ሥራ ላይ ሊውልና ኢትዮጵያን ወደኮሪያና ታይዋን ከፍ ማድረግ ይገባል። በኮንትሮባንድ እየገቡ በነማሌዥያና ኢንዶኔዥያ ደረጃ ገድበው የማስቀረት ውጤት የሚያመጡ (ለዚያውም ከባንግላዴሽነት አልፎ እነማሌዥያ ላይ ከተደረሰ ነው) የተሳሳቱ አሳቤዎች በትግል መወገድ ይኖርባቸዋል። በተለይ በፋይናንስ ተቋማትና በኢንዱስትሪ ልማት አመራር ላይ የሚታየው ይህ አደገኛ አዝማሚያ በፍጥነት መገታት ይገባዋል። በኮንትሮባንድ የሚገቡት የተሳሳቱ ሀሳቦች በትንሹ የመንግሥትና የድርጅት ይፋ መመሪያዎች መሆን የጀመሩ እለት፣ ሁሉ ነገር አቅጣጫውን መሳት እንደሚጀምርና አገሪቱን ከባድ ምስቅልቅል ላይ እንደሚጥላት ለማረጋገጥ አያዳግትም። በብዙ አገሮች የኮንትሮባንድ ሀሳቦች ቀስ በቀስ ሾልከው ከገቡ በኋላ የመንግሥት ይፋ መመሪያ ሆነው ከፍተኛ ምስቅልቅል የሚፈጥሩበት ሁኔታ በተደጋጋሚ የታየ ብቻ ሳይሆን ከወዲሁ በተጨባጭ መታየት የጀመረ ነውና። በአንድ ወቅት በሩሲያ በጥንቆላ

ሥራ ተሠማርቶ የነበረና ንግስቲቱን በአባይ ጠንቋይ ችሎታው አሳምኖ ቤተ መንግሥቱን የተቆጣጠረው ራስፑቲን የተባለ ገበሬ ለዚህ ዓይነተኛ አብነት ነው::

ራስፑቲን ከአንድ የሩሲያ አርሶ አደር ቤተሰብ ተወልዶ አባይ ጠንቋይ የሆነ ሰው ነበር:: እ.አ.አ. በ1905 በአንድ አጋጣሚ በሽታ የመፈወስ ችሎታ አለኝ ብሎ ከተዋወቃቸው የሩስያዋ ንግሥት ጋር ተቀራርቦ ወደቤተ-መንግሥቱ ከገባ በኋላ ቀስ በቀስ የዛሪናዋ (በሩሲያውያን ዘንድ ንግስታት ዛሪና ተብለው ይጠራሉ) የልብ ወዳጅና አማካሪ እስከመሆን ደረሰ:: ይህን ዕድል ያገኘው ራስፑቲን፣ ንጉሡ እንዲፈጽሙት የሚፈልገውን ነገር በሙሉ መጀመሪያ ለንግሥቲቱ ይናገራል:: ንግሥቷም አባይ ጠንቋዩ ራስፑቲን የነገራቸውን ለንጉሱ ያቀርባሉ:: ከዚህ በኋላ ንጉሡ በሚስታቸው የቀረበውን ነገር እምቢ ማለት ተስኗቸው የራስፑቲንን ሀሳቦች ሁሉ ተግባራዊ ያደርጋሉ:: በባህላዊ ፈዋሽነቱ ወዳጅነት የጀመረው ራስፑቲን ቀስ በቀሰ በቤተ-መንግሥቱ ውስጥ አድራጊ ፈጣሪና ሿሚና ሻሪ እስከመሆን ደረሰ። የአባይ ጠንቋዩ ራስፑቲን ምጸታዊ ሕይወት ለፍጻሜ የበቃው ለአሥር ዓመታት ያህል ቤተ-መንግሥቱን፣ የብዙ ንጉሣውያን ቤተሰቦችንና የባለሥልጣናቱን ሕይወት ካመሰቃቀለ በኋላ የቅርብ አልጋወራሽ የሆኑት ልዑላን በመርዝ አዳክመው በጥይት ከገደሉት በኋላ ብቻ ነበር። አገር ከጠፋ በኋላ መሆኑ ከፋ እንጅ:: ስለሆነም በፋይናንስና በኢንዱስትሪ ዘርፎች በኮንትሮባንድ የሚገቡ ፖሊሲዎች በማመንጨት ያልተገባ ተፅዕኖ ማሳረፍ የጀመሩት የአገራችን ራስፑቲኖች ከወዲሁ መልክ እንዲይዙ መደረግ ይገባዋል። ይህ ካልሆነ በአንድ ወቅት በሩስያ የሆነው መመሰቃቀል ሁሉ በእኛም አገር ላለመደገሙ ከማንም ቀላል ዋስትና ማግኘት አይቻልም::

የውጭ ካፒታል ኢንቨስትመንት ኢትዮጵያን መዳረሻው ማድረግ እንደሚሻ መታየት ከጀመረ ወዲህ በመከሰት ላይ ያለው ተግዳሮት ትንሽ የማይባል ሆኗል:: በዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ሽፋን ልማታዊ መንግሥቱን ሲያብጠለጥል የከረመው የምዕራቡ ካፒታል ብቻ ሳይሆን፣ መዳረሻውን ኢትዮጵያና አፍሪካ ያደረገው የምሥራቁ ካፒታልም የሚደቅኗቸው እነዚህ ፈተናዎች ከወዲሁ በውል ተለይተው መፍትሔያቸውም ሊመከርበት ይገባል::

ልማታዊ የፋይናንስ ስምሪትን የማረጋገጥ ፈተና፣

በሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮችና በደቡብ ምሥራቆቹ መካከል የነበረው ሦስተኛው መሠረታዊ ልዩነት ልማታዊ የፋይናንስ ስምሪትን ከማረጋገጥ ጋር የተያያዘ ነው:: የተፋጠነ ኢንዱስትሪያዊ ልማትም ሆነ የተሟላ አገራዊ ትራንስፎርሜሽን፣ ለልማት ተፈላጊ የሆነውን ፋይናንስ በቀጣይነት ከማቅረብና ከትክክለኛ የፋይናንስ ስምሪት ውጭ ሊሳካ አይችልም:: የልማት ፋይናንስ የመፍጠርና የማከማቸት ጉዳይ (Primitive Accumulation of Capital) ለዳበረ የገበያ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ የመነሻ ነጥብ ነው:: ከዚህ በመነሳት እየሰፋ የሚሔድ

ካፒታል የመፍጠርና የማከማቸት ሂደት ሲኖር ካፒታሊዝም ይገነባል። ካፒታል መከማቸቱን (Accumulation) ወይም ተንቀሳቃሽነቱን (Mobility) ሲያቆም ሥርዓቱ ቀውስ ውስጥ ይገባል። ስለዚህም ካፒታሊዝም ከማያቋርጥ የካፒታል እንቅስቃሴና የካፒታል ከምችት ውጭ የማይታሰብ ሥርዓት ነው።

ለካፒታሊዝም ግንባታ ተፈላጊ የሆነው ይህን የመሰለው የፋይናንስ አቅርቦት በብድርና እርዳታ በዘላቂነትና በአስተማማኝ ደረጃ ሊሟላ አይችልም፡፡ ስለዚህም አንድ ድሐና ያልበለጸገች አገር ለልማት ስትነሳ፣ ከሁሉ በፊት አስተማማኝ የፋይናንስ አቅርቦት የሚኖራት መሆኑን ማረጋገጥ ይገባታል፡፡ ይህ ፋይናንስ አስቀድሞ በተካሔደ ልማታዊ ጥረት ተፈጥሮ የተከማቸ ካልሆነ፣ ወይም እንደነዳጅ አምራች አገሮች ከተፈጥሮ ሀብቶች ሽያጭ በሚገኝ ፋይናንስ በቀላሉ ሊሟላ የማይችል ከሆነ፣ ከምንም ነገር በላይ በእጅዋ የሚገኙትን ጸጋዎቿን በማልማት እንደአዲስ ሊፈጠርና ሊከማች ይገባዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ጉዳይ ከአገራችን መልካም ዕድሎች አንዱ የሆነው የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ስለሚገኝበት ደረጃ በምዕራፍ 13 ሰፋ ባለ ደረጃ የሚዳሰስ በመሆኑ፣ በዚህ ንዑስ-ምዕራፍ ትኩረት የተሰጠው የተገኘውን ፋይናንስ ልማታዊ ሂደቱን በሚያጐለብት ሁኔታ ከመጠቀም ጋር እየገጠመን ያለውን ፈተና በማመላከት ላይ ይሆናል፡፡

ለኢንቨስትመንት የሚውል ብድር በስፋትና በተነጻጻሪ አነስተኛ ወለድ በማይቀርብበት አገር የኢንዱስትሪ ልማት ሊፋጠን አይችልም፡፡ ስለዚህም ፋብሪካ ለመገንባትና ከተገነባም በኋላ ያለማቋረጥ የምርት እንቅስቃሴውን እያሻሻሉ ለማስቀጠል ሰፊ የፋይናንስ አቅርቦት ሊሟላ ይገባዋል። በተለይ ደግሞ የግሉ ሴክተር በኢንዱስትሪያዊ ስምሪት ሂደቱ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያግዝ መንቀሳቀሻ ገንዘብ በተገቢው መጠንና ቀጣይነት ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ በታሪክ ይህን የመሰለውን ልማታዊ ፋይናንስ በትክክለኛ ምንጭ ላይ ተመሥርቶ ከማሰባሰብና ከመጠቀም አኳያ ከልማታዊ መንግሥት የተሻለ ኃይል እንደሌለ ታይቷል፡፡ በኮሪያ ልማታዊ ሂደት ልማታዊ መንግሥቱና ፋይናንስ የነበራቸውን ጠንካራ ትስስር መነሻ በማድረግ የጻፈው ጁንግ ኤን ዉ፡-

> “ኮሪያውያን በ1950ዎቹ ያገኙትን ልግስና የተሞላበት የሁለትዮሽ (Bilateral) የእርዳታ ገንዘብ፣ የመንግሥት ጠንካራ ማኅበራዊ መሠረት ለመፍጠር ተጠቅመውበታል፡፡ እያደር ደግሞ ከብዙ ለጋሾች (Multilateral) የሚገኘውን ገንዘብ የተለጠጡ የልማት ፕሮጀክቶችን ለመገንባት አውለውታል፡፡ ከዚህ በመነሳት የኢንቨስትመንት ምንጮች ከባድ የፖለቲካ እንድምታ እንዳላቸው ተረጋግጧል፡፡ በኮሪያ ለልማት የዋለው ካፒታል ምንጩ ከውስጥም ይሁን

ከውጭ የመንግሥትን ሚና የማጐልበት ውጤት ነበረው፡፡ በላቲን አሜሪካ አገሮች ግን ዋናው የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ምንጭ ሁሌም ቢሆን የራሳቸውን የኢንቨስትመንትና የገበያ ግቦች ለማሳካት የሚያልሙት ድንበር የለሽ ኩባንያዎች ወይም የውጭ ካፒታል ነበሩ፡፡ በዚህ የተነሳ የውጭ ካፒታል መንግሥትን በጐን ማለፉ ሳያንስ፣ የመንግሥትን እግር ቀፍድዶ የሚይዝ ከባድ የአገር ውስጥ ተዋናይ ወደመሆን ተሸጋገረ፡፡ በአንጻሩ ኮሪያ የተከተለችው አቅጣጫ ከዚህ የተለየ ስለነበር፣ በአንድ በኩል የመንግሥትን አቅም ሲገነባ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ታይሎችን የፖሊሲ አቅጣጫ የሚያዳክም ሊሆን ቻለ፡፡ ኮሪያና ታይዋን ከጥገኝነት ሊላቀቁ የቻሉት በዚህ አቅጣጫ ነው፡፡”[95] ይላል፡፡

በታሪካዊ ንጽጽር ላይ ከተመሠረተው ከዚህ የጁንግ አገለላጽ በመነሳት፣ አንድ ለልማት ቆርጦ የተነሳ መንግሥት፣ ለግሉ ሴክተርም ሆነ ለመንግሥታዊ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከየትኛው ምንጭ የሚያሰባስብና በትክክል የሚጠቀምበት መሆኑ፣ ፈጣን ልማት የማምጣትን ሆነ አገራዊ ነጻነትን የማረጋገጥ ጉዳይን የሚወስን ነው፡፡ በሁለትዮሽ ወይም በበርካታ አገሮች መካከል ባለ የትብብር ስምምነት የተገኘውን ፋይናንስ በደጋፊነት ተመልከቶ ለአገራዊ ልማት የሚያውል መንግሥት፣ አገሩን ከጥገኝነት እያላቀቀ ለማልማትና ለመገንባት አይቸገርም፡፡ በአንጻሩ እንደላቲን አሜሪካ አገሮች የውጭ ካፒታልን ዋናው መተማመኛ ያደረገና በውጭ ካፒታል ላይ ቁጥጥር የማያደርግ መንግሥት፣ ራሱን የድንበር የለሽ ኩባንያዎች ተላላኪ ወደማድረግ ያመራል፡፡ ይህ ከልማታዊ ፋይናንስ ከምችትና ስምሪት አኳያ ሊወሰድ የሚችልና የሚገባው ቀዳሚ ትምሕርት ነው፡፡ ገንዘብ “ከየትም ይምጣ” በሚል ቅኝት፣ ይህንም ያንንም እየለመኑና እያባበሉ ከማደር ይልቅ፣ የራስን አገራዊ የፋይናንስ ምንጮች መፍጠርና ማጐልበት አማራጭ የማይኖረው በዚህ የተነሳ ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህንኑ ፋይናንስ በማኑፋክቸሪንግ ላይ በተለይ አገራዊ ኢንዱስትሪያዊ ባለሀብት ለመፍጠር መጠቀምም ዓይነተኛ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ይህን በማስመልከት ጁንግ፡-

“የኮሪያ መንግሥት ከዓለምአቀፍ የገንዘብ ተቋማት ያጋጠመውን ተቃውሞ ችላ በማለት የፋይናንስ ስምሪቱ ወደከባድ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያጋደለ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ለዘርፉ በ‘ፖሊሲ ብድር’፣ በዝቅተኛ የወለድ ምጣኔና በሌሎች መልኮች በሚሰጥ ማትጊያ አገራዊ የልማት አቅጣጫውን ተከትለው የሚሔዱ ኢንቨስትመንቶች የሚገጥሟቸውን ፈተናዎችና ኪሳራዎች ለመጋራት በሚያስችል ደረጃ ጣልቃ ገብቷል፡፡ በዚህም የመንግሥት ዋናው ትኩረት የረዥም ጊዜ ቅኝት ያለውና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትንና ኢንዱስትሪያዊ ትራንስፎርሜሽንን

ማረጋገጥ መሆኑን አሳይቷል፡፡... ረጅም የማበቢያ ጊዜ ባላቸው ትልልቅ ፕሮጀክቶች ላይ ለመሰማራት የሚደረግ ጥረት፣ በተለይ ደግሞ ወደፊት በእነዚህ ኢንዱስትሪዎች ለሚመረቱ ምርቶች የሚኖረው ገበያ አጠራጣሪ በሆነበት ጊዜ ሁሉ፣ መንግሥት ኪሳራን ለመጋራትና ድጐማ ለመስጠት የማይፈቅድ ከሆነ፣ የግሉ ሴክተር በእነዚህ መስኮች ኢንቨስት ለማድረግ መግባቱ አጠያያቂ መሆኑ አይቀርም”[96] ይላል፡፡

ከዚህ መሠረተ-ሀሳብ በመነሳት፣ ገበያው ባልለማባቸው ድሃና ኋላቀር ማኅበረሰቦች፣ አገራዊ ባለሀብቱ ከመንግሥት የቅርብ ድጋፍ ውጭ ወደኢንዱስትሪ ለመሰማራት እንደሚቸገር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህም ባለሀብቱ በዚህ የስምሪት ሂደት ከመጀመሪያው አንስቶ በሚሰጠው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ አቅሙን መገንባት ካልተቻለ በስተቀር፣ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው አገራዊ ኢንዱስትሪያዊ ካፒታል መፍጠር አይቻልም፡፡

የብድር አቅርቦት ትንሽ ብቻ ሳይሆን፣ በከፍተኛ ወለድ ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት አገር ከኢንዱስትሪ ይልቅ ሌሎች በጣም አትራፊ መስኮች ቅድሚያ ይወስዳሉ፡፡ አገልግሎት በተለይ ደግሞ የአስመጭነት ንግድና ሪል ስቴት ማስፋፋት በአንፃራዊነት በቀላሉ ብዙ ትርፍ የሚዛቅባቸው መስኮች ይሆናሉ፡፡ ባለሀብቱም በኢንዱስትሪ ከመሰማራት ይልቅ ሪል ስቴትና ንግድን ይበልጥ አዋጭ አድርጐ በመመልከት፣ እነዚህን አትራፊ መስኮች ተቆጣጥሮ ለግምት የሚያስቸግር ትርፍ እየሰበሰበ መኖርን ይመርጣል፡፡ በመሆኑም ኢንዱስትሪን በፍጥነት ማልማት ካስፈለገ ለልማቱ የሚያስፈልገው ብድር በተመጣጣኝ ወለድ ሊቀርብ ይገባዋል፡፡ የአገር ውስጥ ባለሀብቱ የሚደርስበትን ኪሳራ ለተወሰነ ጊዜ እስከመጋራት ድረስ በሚሔድ ድጋፍ ጭምር አቅሙን በዘላቂነት መገንባትና ተወዳዳሪ መሆን መቻሉን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህም በኢንዱስትሪ መስክ የተሰማራው የግል ባለሀብት ለዘላለም በመንግሥት ጀርባ ላይ የታዘለ ሽከም እንዳይሆን በሚያደርግ ቅኝት ሊፈጸም ይገባዋል፡፡

ለልማት ተነስቻለሁ የሚሉ አገሮችን ከሚያጋጥሟቸው ከባድ ፈተናዎች መካከል አንዱ ጤናማና አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጮች መፍጠርና የተስተካከለ የፋይናንስ ስምሪት መኖሩን ማረጋገጥ እንደሆነ ከዚህ ለመገንዘብ ይቻላል። እንደምንም የተሰባሰበው ገንዘብ፣ በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መስክ ላይ ሊሰማራና እንደየተሰማራበት መስክ የተለያየ ውጤት ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ፣ ፋይናንስ የሚሰባሰብና የሚሰማራባቸውን መስኮች በጥንቃቄ መለየትና መወሰን ቁልፍ ነው፡፡ በድሀና ኋላቀር አገሮች ፋይናንስ እጥረት የሚታይበት ውድ ሀብት /Scarce Resource/ ነው፡፡ ይህን ውድ ሀብት አዲስ እሴት ለመፍጠር በሚያስችልና አስተማማኝ ዕድገት በሚያመጣ የኢንዱስትሪና ግብርና ልማት መስክ ማሰማራት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል

ነጠላ ነጥቃሪ በቅጥና ጥርቅ በሚያበገን፣ ነገር ግን የኢንዱስትሪን ያህል አገራዊ ዕድገትን በማያፋጥን እንደ ሪል ስቴትና ንግድ በመሳሰሉ መስኮች ላይ ማሰማራትም ይቻላል። እንደገናም መሠረተ-ልማትን በማስፋፋት ወይም በሌላ የአገልግሎት ሴክተር ላይ ማሰማራት ይቻላል።

ከዚህ የስምሪት መስክ ልዩነት በተጨማሪ፣ ፋይናንስን ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ ደረጃ እንዲጠቀሙበት አድርጐ ማሰማራት ይቻላል። በአገራችን አሁን እየሆነ እንዳለው በዋነኛነት መንግሥት ሊጠቀምበትና ለመሠረተ-ልማትና በመንግሥት ለሚገነቡ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ሊያውለው ይችላል። ይህ የተመረጠ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በመባል የሚታወቅ ሲሆን በገበያውና በባለሀብቱ መቅረብ የማይችሉ መሠረታዊና ተፈላጊ ምርቶችና አገልግሎቶች በማስፋፋት ላይ የሚካሄድ ስምሪትን ያመለክታል። በአንጻሩ የተመረጠ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት መኖር አለበት በሚል ትክክለኛ መርህ የተጀመረው ይህ ስምሪት፣ በሂደት በሁሉም መስኮች ላይ ወደመሰማራት የተሳሳተ አቅጣጫ ሊያመራና የግሉን ዘርፍ እንቅስቃሴና ዕድገት በሚያቀጭጭ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውልም ይችላል። ከሁለትና ሦስት ዓመታት በፊት መንግሥት ነዳጅ ማደያዎች በመከፈት ላይ እሰማራለሁ በማለት የሰጠው መግለጫ የዚህን የተሳሳተ አቅጣጫ ይዘት የሚያሳይ ነው። ይህ አንድ ሚሊዮን ብር ባላቸው ዜጐች ሊሠራ በሚችለውና ከፍተኛ ውድድር በሚያስተናግደው የነዳጅ ማደያዎች ኢንቨስትመንት ውስጥ መግባት በግሉ ሴክተር አቅም ሊሠሩ በማይችሉት እንደባቡር ወይም የታላቁ ህዳሴ ግድብ ዓይነት መስኮች ከመሰማራት በጣም የተለየ ነው። የመጀመሪያው የግሉ ሴክተር ከሚችለው ስምሪት በመንግሥት ተገፍቶ እንዲወጣ ሲያደርግ፣ የኋለኛው ደግሞ በአቅመ አናሳነት ምክንያት ሊሠራው ያልቻለውን ተግባር በመንግሥት ስምሪት ለማሟላት ያስችላል። አገራዊው ፋይናንስ ከዚህ በተለየ አቅጣጫ በዋነኛነት በግል ሴክተር እጅ ተሰማርቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ይቻላል። በግሉ ሴክተር ደረጃም በአምራች ዘርፎች የሚሰማራው ልማታዊ ባለሀብት ወይም በኪራይ ሰብሣቢነት የሚሰማራው ባለሀብት በሚጠቀምበት ቅኝት ሊሰማራ ይችላል። እነዚህ ሁሉ የተለያየ ውጤት የሚያስገኙ ስምሪቶች ናቸው። ይህ የስምሪት ልዩነት በሰሜን ምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች ተጨባጭና ጉልህ የውጤት ልዩነት ያስከተለ ነበር።

በሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች የፋይናንስ ስምሪቱ በዋነኛነት መሠረተ-ሰፊ የዜጐች ልማታዊ እንቅስቃሴ እንዲጐለብት የሚያደርግ አቅጣጫ የተከተለ ነበር። እነዚህ አገሮች በልዩ ልዩ ጥረት ያከማቹትን ፋይናንስ ከምንም ነገር በላይ ኢንዱስትሪንና ግብርናን ለማልማት ተጠቅመውበታል። ይህም በመሆኑ ፈጣን፣ ዘላቂና ፍትሃዊ ልማት ሊያመጡ ችለዋል። ፋይናንስ በአምራች ሴክተሮች ላይ ተሰማርቶ በቀጣይነት እሴት ለመፍጠርና ለመጨመር በማስቻሉ ከግማሽ ምዕት ዓመት ባለበለጠ ጊዜ አገራዊ ትራንስፎርሜሽን እንዲመጣ አስችሏል።

ከዚህ በተጻራሪ የደቡብ ምሥራቅ እስያ አገሮች በዚህም በዚያም ብለው ያከሠቱተን ፋይናንስ በዋነኛነት በሪል ስቴት ግንባታና ንግድን በማስፋፋት ላይ አውለውታል። የሪል-ስቴት ዋጋ ያለማቋረጥ ወደሰማይ ማሻቀቡን ተከትሎ፣ የላቀ ትርፍ የሚገኝበት ዘርፍ መሆኑን የተገነዘቡ ሁሉ ተበድረውም ተለቅተውም የሪል-ስቴት ግንባታ ላይ ተረባረቡ። "ሰማይ የነካው ዋጋ ተመልሶ ወደመሬት አይወርድም" ብለው የተመኩት የየአገሮቹ ቱጃሮች ዋነኛ የስምሪት መዳረሻ ኢንዱስትሪ ሳይሆን፣ ሪል ስቴትና በዚህ ዙሪያ የተቀሰቀሰው ዕድገት ሆነ። በሪል ስቴትና በንግድ ላይ ያነጣጠረው የደቡብ ምሥራቅ እስያውያን የፋይናንስ ስምሪት ልማታዊውን ሳይሆን፣ ከራይ ሰብሣቢውን የሚደግፍና የአራጣ አበዳሪነት(Speculative) ባሕርይ ያለው ነበር። ይህም አገሮቹ ለችግር እንዲጋለጡና በዚያው ልክ ደግሞ አገራዊ ትራንስፎርሜሽን እንዳያመጡ አገዳቸው። በዚህ የተነሳም የመካከለኛ ገቢ ወጥመድን ማለፍ የተሳናቸው ሊሆኑ ተገደዱ።

ይህ በሪል ስቴት ዙሪያ የተፈጠረ ዕድገት እንደሳመና አረፋ መተንፈሱ እንደማይቀር በብዙ ኢኮኖሚስቶች ተተንብዮ ነበር። የማታ ማታም ትንበያው እውን ሆኖ ከልክ በላይ የተገነባው ሪል ስቴት በአርግጥም የኢኮኖሚ አረፋ (Economic Bubble) ወደመሆን ተሸጋገረ። እ.ኤ.አ በ1997 የተከሰተውና ከቻይና በስተቀር መላውን ምሥራቅ እስያ ወደከባድ ምስቅልቅል ያስገባው የፋይናንስ ቀውስ አንዱና ዋነኛው መንስዔ ይኸው የሪል ስቴት ዘርፍ ነበር። እ.ኤ.አ ከ2007 ጀምሮ የተከሰተው ግዙፍ ዓለማዊ የኢኮኖሚ ቀውስም ቢሆን መሠረቱ በተዛባ የፋይናንስ ስምሪት የተፈጠረውና ከቤት ብድር ቀውስ (Sub Prime Mortgage Crisis) ጋር የተያያዘ ነው። በኢንዱስትሪ የበለጸጉ አገሮችን ጭምር ከባድ ቀውስ ውስጥ የከተተው ይኸው ችግር፤ ካፒታል ከፍተኛ አትራፊነት ኖሯቸው፣ ነገር ግን ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን ለአደጋ ወደሚያጋልጡ ቁማር መሰል መስኮች ከመሰማራቱ የመነጨ ነበር። ከዚህ በመነሳት ጆ ስቱድዌል መንግሥት በዚህ ጉዳይ ላይ በፍፁም ጥንቃቄ መንቀሳቀስ እንዳለበት ሲያስረዳ፡-

> "ልማት በወሳኝነት ጠንካራ የፖለቲካ ተግባር ነው። መንግሥት በኢኮኖሚስቶች ዘንድ ኪራይ ተብሎ የሚታወቀውንና በመንግሥት ይዞታ ሥር ሊቀርብ የሚችለውን ጸጋ፣ ባለሀብቶች አንዳችም ልማታዊ አስተዋጽኦ በማያበረክቱበት አኳኋን እንዲጠቀመበት ከፊቀደ ፖለቲካዊ ኃላፊነቱን በእጅጉ እንደዘነጋ ይቆጠራል። የደቡብ ምሥራቅ እስያ ህዝቦች የቤተ-ዘመዳሞች ካፒታሊዝም /Crony Capitalism/ ብለው የሰየሙትና ባለሀብቶች አንዳችም ልማታዊ ግዴታ ሳይጫንባቸው ከፍተኛ ድርጎ የሚያገኙበት ሥርዓት በባለሀብቶች ዘንድ የኢንተርፕርነርሽፕ አለመኖር ሳይሆን የመንግሥት ፖለቲካዊ ውድቀት

የፈጠረው ነው።።[97] ይላል።።

ይህን የመሰለው ድክመት አንዴ መታየት ከጀመረና በጊዜ ካልታረመ በስተቀር፣ በብድር አቅርቦት ብቻ የማይወሰን ችግር ማስከተሉና በፍጥነት ወደሌሎች ሴክተሮች መዛመቱ የማይቀር ነው።። ልክ እንደብድር ሥርዓቱ ሁሉ የግብር ሥርዓቱም ብዙ ድካም በሌለው ሁኔታ ከፍተኛ ትርፍ የሚገኝባቸውን ሪል ስቴትና ንግድ ከኢንዱስትሪው የተሻለ ተጠቃሚ ማድረግ ይጀምራል።። ጭስ በሚታይበት ቦታ ሁሉ ፈልጎ ኢንዱስትሪን ማግኘትና ግብር ማስከፈል ስለማይከብድ ብቻ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከባድ ግብር ከፋይ ሊሆን ይገደዳል።። በአንድ ላፕቶፕ ኮምፒውተርና ገመድ አልባ የኢንተርኔት ግንኙነት በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ አስመጭዎች ከግብር ነጻ ይሆናሉ።። በዚህ አቅጣጫ በሚጓዙ አገሮች ሁሉ ቀስ በቀስ ደፍሮ ወደኢንዱስትሪ የሚሰማራ ዜጋ ይታጣል።። ቢኖርም ለስቃይ የጣፈው ብቻ ይሆናል።። የአገራዊ ፋይናንስ የተዛባ ስምሪት የሚያስከትለው ጦስ ይህን ያህል ከባድና የአገር ልማትን ክፉኛ እስከመጉዳት የሚደርስ ነው።። በመሆኑም ልማትን የሚሹ አገሮች የፋይናንስ ሥርዓታቸው አንድ አካል የሆነው የግብር ሥርዓትም ኢንዱስትሪንበፍፁም ወገናዊነት የሚያገለግል ሆኖ እንዲቀረጽና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይገባቸዋል።።

የአንድን አገር ልማት በከፍተኛ ደረጃ ለማፋጠን ቁልፍ ሚና የሚጫወቱት አምራች ዘርፎች ናቸው።። ከእነዚህም ዋናዎቹ ግብርናና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ናቸው።። ሁለቱም አገራዊ የካፒታል ስምሪት መናኸሪያ በሆኑ ቁጥር እሴት ፈጣሪነት እየጨመረ ይሔዳል።። ከዚሁ ጋር በእነዚሁ ልማታዊ መስኮች ተሠማርቶ የሚሠራው የሰው ኃይል በማያቋርጥ ደረጃ እየተበራከተና ለከፍተኛ የክፍያ መሻሻል እየበቃ፣ በዚያው ልክ ደግሞ የሕብረተሰብ የኑሮ ደረጃ እየተሻሻለ ይሔዳል።። በአንጻሩ ካፒታል ከእነዚህ ከፍተኛ እሴት አመንጪ ዘርፎች እየራቀ፣ በቀዳሚነት ዝቅተኛ እሴት ፈጣሪ በሆኑ የሪል ስቴትና፣ የአስመጭና ጥሬ ዕቃ ላኪነት የመሳሰሉ የንግድ ዘርፎች ሲሰማራ ውሎ አድሮ ቀውስ ይከሰታል። ይህ ዓይነቱ ስምሪት ለባለሀብቶቹ ከፍተኛ የትርፍ ምንጭ ሊሆን ቢችልም፣ አገራዊ ሀብትን በመፍጠርና በማበራከት ደረጃ የሚጫወተው ሚና ዝቅተኛና በማይቀር ሁኔታ ደግሞ ልማታዊ ትራንስፎርሜሽንን የሚገድብ ይሆናል።።

ከዚህ በተጨማሪ አነስተኛ እሴት ፈጠራ ባላቸው ዘርፎች የሚከፈተው የሥራ ዕድል በአብዛኛው የሰውን ልማታዊ አቅም መገንባት የማይጠይቅና በቀላሉ ሊተካካ የሚችል ያልሠለጠነ ጉልበት /Unskilled Labour/ የሚሰማራበት ብቻ ነው።። በዚህ ባሕርይው በሥራው መስክ ለሚቀጠሩት ለአብዛኞቹ ሠራተኞች የሚያስገኘው ክፍያ ዝቅተኛ ይሆናል።። ስለሆነም ዕድገቱ የህዝብን ገቢና የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የጐላ አስተዋጽዖ የማያደርግና የአገርን ተወዳዳሪነት የማረጋገጥ ችሎታ የሌለው ይሆናል።። በመሆኑም ካሉት የፋይናንስ ስምሪት አማራጮች መካከል፣

አገራዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ፋይዳተው ከፍተና የሆኑ ዘመናዊ ግብርናን ማስፋፋት የላቀ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህ ከመደበኛ ባንኮች በሚገኘው ብድርም ሆነ በባንኮች በኩል ሳያልፍ ወደስምሪት የሚገባ ካፒታልን የሚመለከት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ለዚህም ሲባል መንግሥት ትከከለኛውን የማበረታቻ ሥርዓት ሊቀርጽና በተጨባጭም አንዱስትሪና ዘመናዊ ግብርና ተወዳዳሪ የካፒታል ስምሪት መስኮች ብቻ ሳይሆን፣ ቀዳሚዎቹና ዋነኞቹ የልማታዊ ፋይናንስ መሰማሪያ መስኮች መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

በኢትዮጵያ በፖሊሲ ደረጃ እነዚህ ጉዳዮች በአብዛኛው ተስተካከለዋል፡፡ መንግሥት በጠንካራ የፋይናንስ ዲሲፕሊን እየተመራ ከሁለት አሥርት ዓመታት ለማያንስ ጊዜ አገሪቱ ከልዩ ልዩ ምንጮች ያገኘችው ገንዘብ በዋነኝነት ከፍተኛ ልማታዊና ህዝባዊ ፋይዳ ባላቸው መስኮች ላይ እንዲሰማራ አድርጓል፡፡ በዚህም ፈጣን ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ ፍትሃዊነት ያለው ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ መንግሥት ለመሠረተ-ልማት መስፋፋት የሰጠው ትኩረት፣ በተለይ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በሚያጎለብቱ ትምሕርትና ጤናን በመሳሰሉ ድሃ ተኮር ማኅበራዊ መስኮች ላይ ያፈሰሰው ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ የአገሪቱ የፋይናንስ ስምሪት ትከከለኛ ሆኖ እንደቆየ ያመላከታል፡፡ ስቲግሊዝ እንደገለጸው መንግሥት ከተለያዩ ምንጮች ያገኘውን የፋይናንስ ሀብት ከእነ አይኤምኤፍና የዓለም ባንክ ጋር እየታገለ፣ ልማታዊና ፍትሃዊ ፋይዳቸው በላቀ መስኮች ላይ ሲያውለው ቆይቷል፡፡ በግብርም ሆነ በቱጠባ፣ በብድርም ሆነ በእርዳታ ያሰባሰበውን ገንዘብ፣ በእነዚህ መስኮች ላይ በከፍተኛ ዲሲፕሊን ሲያውል መቆየቱም በኢትዮጵያ ልማታዊ የሚባል የፋይናንስ ስምሪት ተስፋፍቶ መቆየቱንና ከዚህ አኳያ በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል መነሻ እንዳለ የሚያመላክት ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገሪቱ ውስጥ መፈጠር የጀመረውና ከመንግሥት ይዞታ ውጭ የሚንቀሳቀሰው ካፒታል፣ ከጊዜ ወደጊዜ ከልማታዊ ይልቅ የአራጣ አበዳሪነት ባህርይ ወዳለው ስምሪት ሲያመራ መመልከት የተለመደ ሆኗል፡፡ ብዙዎቹ የአገራችን ባለሀብቶች በዋነኛነት የሚሰማሩት በሪል ስቴት ግንባታ ላይ ሆኗል፡፡ በእርግጥ ሪል ስቴት ግንባታው ተጀምሮ እስኪያልቅ ሰፊ የኮንስትራክሽን ሠራተኛ ይቀጥራል፡፡ በዚሁ ልከ ለኢኮኖሚው የራሱን አስተዋጽኦ ያበረከታል፡፡ በተጨማሪም የቢዝነስ እንቅስቃሴን ለማካሔድ የመሠረተ-ልማት አቅርቦትን ያሟላል። ለዜጐች የቤት ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ሆኖም ያገለግላል፡፡ ከዚህ ውጪ የፋብሪካን ያክል አዲስ ሀብት የመፍጠር ችሎታ የለውም፡፡ ፋብሪካ የጥሬ ዕቃና የጉልበት አቅርቦት እስካልተቋረጠ ጊዜ ድረስ ቀን ከሌት ሊንቀሳቀስና ሰፊ አዲስ ሀብት ሊፈጥር ይችላል፡ ፡ ሪል ስቴት ግን አንዴ ከተገነባ በኋላ ሀብትን ከሸማች ወደሻጭ፣ ከተከራይ ወደአከራይ በማሸጋገር አስቀድሞ የተፈጠረን ገንዘብ ከአንድ ኪስ ወደ ሌላ ያዛውራል። ይህም በመሆኑ ሪል ስቴት የሚገነቡ ሰዎች ከፍተኛ ትርፍ የማግበስበስ ዕድል ተጐናጸፈዋል፡፡ የአገሪቱን ካፒታል

በመምጠጥ ላይ የሚገኘው ይህ ሴክተር፣ ሀብት ከፍተኛ ልማታዊ ፋይዳ ካላቸው መስኮች ይልቅ፣ ዝቅተኛ ልማታዊ ፋይዳና የጋራ ተጠቃሚነት በሚያስገኙ መስኮች ላይ እየተሰማራ እንደሆነና በዚያው ልክ ደግሞ አገራዊው ትራንፎርሜሽን ለአደጋ እየተጋለጠ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል::

መንግሥት በኢንዱስትሪ ለሚሰማሩ ሁሉ የተሻለ የትርፍ ሕዳግ ለማስገኘት የሚሰጠው ማትጊያ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ፣ ኢንዱስትሪ ከመገንባት ይልቅ ትልልቅ ፎቅ መገተር ዋናው የስምሪት መስክ ሆኗል:: መንግሥት ኢንዱስትሪ ከንግድና ሪል ስቴት የሚመጣጠን ትርፍ የሚያስገኝ እንዲሆን ባለማድረጉ፣ ይህን ያልተመጣጠነ የትርፍ ህዳግ ማስተካከል ሳይቻል ቆይቷል:: ከኢንዱስትሪ ይልቅ ሪል ስቴትና አስመጭነት የተሻለ ትርፍ የሚዘቅበት የሆነውም በዚህ ምክንያት ነው:: በዚህ የተነሳ ማኑፋክቸሪንግ የዕድገት ቀዳሚነቱን ሊወስድ አልቻለም። በዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ ሪል ስቴት ግንባታ ከልክ በላይ እየተለጠጠ ሔዷል። ይህ ከመንግሥት ጀምሮ የሚታይ የተዛባ የፋይናንስ ስምሪት ሳይውል ሳያድር የሀብት ብክነት የሚታይበት እንደሚሆን ለመገንዘብ የአቅርቦትና ፍላጐት (Demand & Supply) ኢኮኖሚያዊ ሕግን ማወቅ ብቻ በቂ ነው። ከወዲሁ ተከራይ ያጡ ሕንጻዎች በትንሹም ቢሆን መታየት መጀመራቸው ይህን ያመላክታል።

በዚህ ምክንያት ኢንዱስትሪ መልማት አለበት ስለተባሉና በራሳቸውም ኢንዱስትሪያሊስት መሆን ፈልገው ሥራውን የጀመሩ ሁሉ በተገቢው ደረጃ አልተደገፉም:: የብድር ሥርዓቱ በጣም ግትርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚሰማሩትን ሁሉ የሚፈትን ነው:: በኢንዱስትሪ መስክ ለሚሰማሩ ብድር የሚያቀርበው ልማት ባንክ የቀረቡለትን ሁሉ የማስተናገድ አቅም የለውም:: ንግድ ባንክም ለኢንዱስትሪ የሚሰጠው ብድር ከሞላ ጐደል እዚህ ግባ የሚባል አይደለም::

ይህ ነባራዊ ተግዳሮት ያነሰ ይመስል ብሔራዊ ባንክ በሚያዝያ 2009 ዓ.ም. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1987 ዓ.ም. ያወጣውን አዋጅ በቀላጤ ሽሮ ንግድ ባንክ ከረዥም ጊዜ ብድር እንዲወጣ መመሪያ ማስተላላፉ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ስምሪትን ከመሠረታዊው ልማታዊ አቅጣጫ እንዲወጣ አድርጐታል:: ፋይናንስን ለልማት፣ በተለይ ለኢንዱስትሪ ልማት በሚበጅ አቅጣጫ መምራት የልማታዊ መንግሥት መለያ ባሕርይ ነው:: ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ፈጽሞ ለድርድር ሊቀርብ የማይገባው ሲሆን አስፈጻሚዎቹ ደግሞ መንግሥትና በመንግሥት እጅ ያሉ ባንኮች ናቸው:: መንግሥት ባንኮቹን የልማታዊ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ አድርጐ በመጠቀም፣ ባንኮቹ ደግሞ በዚህ አቅጣጫ ፖሊሲውን ተከትለው በአጠቃላይ እሴት ፈጣሪ ዘርፎችን፣ በተለይ ደግሞ ኢንዱስትሪን በሚያስፋፉ አቅጣጫ ሲሰማሩ አገራዊ ትራንስፎርሜሽን በአስተማማኝ ደረጃ ይካሔዳል::

ከዚህ በመነሳት በአገራችን በትልቅነቱ ተወዳዳሪ የሌለውን፣ በተለይ ደግሞ ከቅርብ

ዓመታት ወዲህ ቁጠባን በማሰባሰብ እጅግ የላቀውን ሚና እየተጫወተ ያለውን ንግድ ባንክ በልማታዊ አቅጣጫ ለመምራት እጅግ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር። ይህም ባንኩ ለረጅም ጊዜ በተለመደው የንግድ ባንክነት ቅኝት ሲንቀሳቀስ ከነበረበት ማዕቀፍ በማውጣት ልማታዊ አቅጣጫ እንዲይዝ በማድረግ የተጀመረ ነበር። ይህን ተከትሎ ባንኩ ቁጠባ በሰፊው እያሰባሰበ በዋነኛነት መንግሥት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ፕሮጀክቶችና በተወሰነ ደረጃ ደግሞ በኤክስፖርትና ማኑፋክቸሪንግ ለተሰማራው የግል ዘርፍ እያበደረ ቆይቷል። ይሁንና የባንኩ አመራር ቀደም ሲል ለኢንዱስትሪ በቂ መጠን ያለው ገንዘብ እንዳላበደረ በመገንዘብ በ2009 ዓ.ም. ኢጋማሽ በዋነኛነት አገራዊ የግል ሴክተር በማኑፋክቸሪንግ እንዲሰማራ ለማገዝ የሚሰጠውን ብድር በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ እንዳለበት ተገነዘበ። ባንኩ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ወደኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለሚደረገው ሽግግር አጋዥ ሚና መጫወት እንዳለበት በማመን ለኢንዱስትሪ የሚያበድርበትን የወለድ ምጣኔ 6.5 ከመቶ ለማድረግ ወሰነ። የሥራ አመራሩ በራሱ ተነሳሽነት ያመጣው ይህ ሀሳብ ወጣቶቹ የንግድ ባንክ አመራሮች ባንኩ ባሰባሰበው ቁጠባ አገራዊ ልማቱን ለማገዝ የወሰዱትን ኃላፊነት የተሞላበት እርምጃ ያሳያል። በመጨረሻም ረቂቅ ሀሳቡ ለቦርዱ ቀርቦ ፀደቀ። ጉዳትና ጥቅሙ ተመዛዝኖ ምክረ-ሀሳቡ ተቀባይነት አግኝቶ ፀደቀ። አቋምም ተወሰደበት። ይህ ውሳኔ ከባንኩ ትርፍ ላይ ወደአንድ ቢሊዮን የሚጠጋ ብር ቅናሽ የሚያስከትል ቢሆንም፣ ይህ ገንዘብ ማኑፋክቸሪንግን የሚደጉም በመሆኑ እንደትርፍ እንጂ ኪሳራ ሊቆጠር እንደማይገባውም ስምምነት ተያዘ።

ንግድ ባንክ ይህን አቋም በወሰደ ማግስት ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የንግድ ባንክ መመሥረቻ አዋጅን ብቻ ሳይሆን የመንግሥትን ልማታዊ አቅጣጫ የሚሸር አንድ ቀላጤ አስተላለፈ። ይህም "ንግድ ባንክ ለአጭር ጊዜ ስምሪቶች ካልሆነ በስተቀር ለኢንዱስትሪ ማበደር የለበትም" የሚል ይዘት ያለው ነው። ውሳኔው በአንድ በኩል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1987 ዓ.ም. ያወጣውን አዋጅ በቀላጤ የሚሸር በመሆኑ ሕገ-ወጥና የብሔራዊ ባንኩን ገዥ ተጠያቂ ማድረግ የነበረበት ነው።

ከፍ ሲል ከተገለጸው የፋይናንስ ስምሪት አቅጣጫ መሳት በተጨማሪ የመሬትና የመሠረተ-ልማት አቅርቦት በተፈላጊው ደረጃ ለመሟላት ባለመቻሉ፣ ሲቀርብም እደላው በልማታዊ ፋይዳው ሳይሆን ለመሬት አዳዮች ጉቦ በመሥጠት ብቃት የሚወሰን በመሆኑ፣ ወደትግበራና ምርት መሸጋገር ያቃታቸው፣ በአቅርቦት እጥረትና በሥራ አመራር ድክመት ሲባባስ በቆየው የኤሌክትሪክ አቅርቦት መቆራረጥ ምክንያት በሙሉ አቅማቸው መሥራት የተሳናቸው፣ ይህን ሁሉ ተቋቁመው ትንሽ ሲያመርቱ በግብር ጫናና አልፎ አልፎ ደግሞ በአራጣ አበዳሪዎች ተፅዕኖ ሥር የሚወድቁ ፕሮጀክቶች ብዙ ናቸው። በኢትዮጵያ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ውስጥ በጥራቱ የታወቀ ፋብሪካ የነካባው ማሜ ስቲል የተባለ ኩባንያ በዓይናችን ሥር በአራጣ አበዳሪዎች መዳፍ ሊወድቅ መገደዱና እነዚሁ ወገኖች የአገሪቱ ተስፋ የሆነውን ይህን ኢንዱስትሪ

ለመቀራመት ሲረባረቡ መመልከታትን ለዚህ እንደአብነተ ሊጠቀስ የሚተል ነው፡፡ በተግባር እንደታየው ኢንዱስትሪው በአራጣ አበዳሪዎች ተከሶ ንብረቱ ለሐራጅ እንዲቀርብ በተደረገበትና የአገሪቱ ፍርድ ቤቶች ኢንዱስትሪን ሳይሆን አራጣ አበዳሪነትን ደግፈው በሚበይኑበት አገር፣ ፖሊሲው ምንም ያህል ትክክል ይሁን ኢንዱስትሪ በአሸናፊነት ሊለማ፣ የፋይናንስ ስምሪቱም ልማታዊ ሊሆን ይችላል ተብሎ አይታመንም፡፡

ምዕራፍ አሥር፣

ዓለም አቀፍ ሁኔታውና ተፅዕኖዎቹ፣

ኢትዮጵያ በእጅዋ ውስጥ ያስገባችውን እጅግ በጣም የተመቸ ዕድል በአግባቡ ለመጠቀም የምትችለው ከፍ ሲል የተገለጹትንና ያለማቋረጥ እየፈተኗት የሚገኙትን ውስጣዊ ችግሮች ለይቶ በመታገልና በመፍታት ነው፡፡ ይህ በተፈጠረው መልካም ዕድል ሁሉ በብቃት ለመጠቀም አማራጭ የማይገኝለት ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በብዙ ምክንያቶች ቀላል የማይባል ተፅዕኖ የሚያሳርፍባት ውጫዊ ዓለም ደግሞ አለ፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ተዋናዮች በኢትዮጵያ መጻዒ ዕድል ላይ ተፅዕኗቸውን ለማሳረፍ መፈለጋቸውና መሞከራቸው አይቀርም፡፡ ካሰቡበት መድረስ የሚቻለው ይህን የመሰለው ተፅዕኖ ከየትም ይምጣ ከየት እየለዩና እየፈቱ በመጓዝ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ሳይታጠቁ መያዝና በዘመነ ግሎባላይዜሽን ራስን ለከባድ አደጋ ማጋለጥ የማይቀር ይሆናል፡፡

ከዚህ መሠረታዊ እሳቤ በመነሳት ከዓለም አቀፍ ሁኔታው ከሚመነጩና በኢትዮጵያ ላይ ከባድ ተፅዕኖ ከሚያሳርፉ በርካታ ጉዳዮች መካከል ሦስቱን ለይቶ በመውሰድ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ከባድ ተፅዕኖ ምንጭ በዓለማችን በመታየት ላይ ያለው የልእለ ኃያላን ሽኩቻ ነው፡፡ ሁለተኛው ከዓለም አቀፉ የገበያ አከራሪነት ኃይል በኩል የሚመጣው ከባድ ተፅዕኖ ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ከባድ ተፅዕኖ የማሳረፍ አቅም ሊኖረው የሚችለው በአካባቢያችን በመስፋፋት ላይ ያለው ጽንፈኛና የጭፍን ጥላቻ ኃይል ነው፡፡ እነዚህ ሦስት የተፅዕኖ ምንጮች በኢትዮጵያና እርሷን በመሳሰሉ አገሮች ላይ በቅርብ ርቀት ከባድ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ መሆናቸው ሊገመት የሚችል ነው፡፡

የልእለ ኃያላን ሽኩቻና የቀይ ባሕር ወደ ወታደራዊ ቀጠናነት መመለስ፤

ዓለማችን በጠንካራ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር በምትገኝበት በዚህ መድረክ በአንደኛው የዓለም ጫፍ የሆነው ሁሉ በሌላኛው የዓለም ጫፍ ያሉ አገሮችንና ህዝቦችን በእጅጉ ተፅዕኖ ያሳርፍባቸዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ2007 መጀመሪያ ላይ የተቀሰቀሰው የቤት ቀውስ፣ ሳይውል ሳያድር ወደፋይናንስ ቀውስ ተሸጋግሮ ነበር፡፡ በፋይናንስ ሴክተሩ ውስጥ የተቀሰቀሰው ይህ ቀውስ ሳይውል ሳያድር ወደተሟላ የመንግሥታት ቀውስ ተሸጋግሯል፡፡ አሜሪካ በቀውስ ተመትታ የቻይናን ምርቶች መግዛት ስታቆም፣ በአንድ ጊዜ ሃያ ሚሊየን ቻይናውያን ለሥራ አጥነት የተዳረጉበት፣ አይስላንድ የተባለች ትንሽ ደሴት ባንኮች ሲቃወሱ፣ መላውን አውሮፓ

ይዛ ወደታች የወረደችበት ሁኔታ ታይቷል። በዚህም ፈረንጆቹ የኦሪጊ ሠለፕ /Domino Effect/ የሚሉት ተያይዞ የመነሳት ወይም የመውደቅ ዕድል የዘመነ ግሎባላይዜሽን ዓይነተኛ መለያ ባሕርይ እንደሆነ ተረጋግጧል። የስደተኞች ጉርፍ፣ የአሸባሪነትና ጽንፈኝነት እንደሰደድ እሳት መዛመትና መላውን ዓለም ሥጋት ላይ መጣል፣ በዓለም ዙሪያ እየተስፋፋ የመጣው የሳይበር ወንጀልና የመሳሰሉት ሁሉ በዚህ ማዕቀፍ የሚታዩ ናቸው። በሰሜን ኮሪያና በአሜሪካ መካከል የተከሰተው ከባድ ውጥረትና የኑክሌር ግጭት ሥጋትም በዘመነ ግሎባላይዜሽን ትስስሩና አንዱ አገር በሌላው ላይ የሚያሳርፈው ተፅዕኖ ለግምት በሚያስቸግር ደረጃ የተጠናከረና ሥር የሰደደ እንደሆነ ያሳያል።

ይህን የመሰለ ከባድ ትስስርና መስተጋብራዊ ውጤት በሚታይባት ዓለማችን፣ በበጐም ይሁን በከፉ መላውን ዓለም እንደሚጫን የሚነገርለት አንዱ ጉዳይ በልእለ ኃያላን መካካል ያለው ግንኙነት፣ በተለይ ደግሞ በአሜሪካና በቻይና መካከል አዲስ መልክ ይዞ የተቀሰቀሰው ሽኩቻ ሆኗል። ይህ ሽኩቻ በብዙ መልኮች ይገለጻል። በሁለቱ ግዙፍ ኢኮኖሚዎች መካከል ዓለማዊ የመሪነት በትረ ሙሴውን ለመጨበጥ የሚካሔደው ፉክክር የሽኩቻው አንዱና ዋናው መገለጫ ነው። አሪጊና ሲልቨር ይህ ሽኩቻ ከተራ መቀናቀን ይልቅ ለዓለማዊ የበላይነት በሚደረግ "የልእለ ኃያላን የመሪነት ቦታ ሽግሽግ"[98] (Hegemonic Transition) መልክ ይገልጹታል። ይህም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በልእለ ኃያላኑ መካከል ያለውን ግንኙነትና ሽኩቻ እንዲሁም ይህ ከስተት ለኢትዮጵያ የሚኖረውን ትርጉም አጠር አድርጐ መመልከት ጠቃሚ ይሆናል።

በብዙ የዓለማዊ ሁኔታ ተንታኞች ዘንድ እንደሚታመንበት፣ የበርሊን ግንብ ተንዶ የምሥራቁ ካምፕ በተንኮታኮተ ማግስት ዓለማችን ተፎካካሪ የሌለው አንድ ልእለ ኃያል የበላይነቱን ያረጋገጠባት ወደመሆን ተሸጋግራ ነበር። በሶቭየት ሕብረት ይመራ ከነበረው የምሥራቁ ካምፕ ገጥሞት የነበረውን ከባድ ፉክክር እ.ኤ.አ. በ1989 በድል አድራጊነት የተወጣው የምዕራቡ ዓለም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አሜሪካ ብቸኛ አለቃ ወይም ልዕል ኃይል (Hegemonic Power) መሆኗን አበሰረ። ላይ ላዩን ሲታይ አሜሪካ ቢያንስ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በቅርብ የሚፎካከራት ሌላ ልእለ ኃያል የሌለባት የዓለማችን ዋነኛ የኃይል ልዑል ሆና ነበር። ምንም እንኳ ይህ ሂደት በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ሩብ ብቻ ያልተፈጠረ፣ ይልቁንም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ጀምሮ የተገነባ ቢሆንም፣ የምሥራቁ ጐራ ከፈረሰበት ከ1989(እ.ኤ.አ) ጀምሮ ግን ፀሐይ የሞቀው እውነታ ሆኗል። ይህን ተከትሎ እንደፍራንሲስ ፉኩያማ የመሳሰሉ የፖለቲካ ተንታኞች "የምዕራቡ ዓለም አስተሳሰብ አሸናፊነት የተረጋገጠበት የመጀመሪያው መንገድ እርሱን ሊተኩ የሚችሉ አማራጮች በሙሉ የተዳከሙና ያለቀላቸው መሆኑ በመረጋገጡ ነው። እየተመለከትን ያለነው ነገር የቀዝቃዛውን ጦርነት መጠናቀቅ ብቻ ሳይሆን፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ያለውን አንድ የታሪክ ምዕራፍ መጠናቀቅ ብቻ

ሳይሆን የታሪክ መጨረሻ መሆኑንም ጭምር ነው።" (ፉኩያማ 1992)እስከማለት ደፍረው ነበር። ታሪክ መጨረሻ ያለውና ኒዮ-ሊበራሊዝምም የመጨረሻው የሰው ልጆች መዳረሻ ይመስል። ነገር ግን እንኳን ወደፊት ዛሬም ቢሆን ከኒዮ-ሊበራሊዝም የተሻሉ የተለያዩ አማራጮች በምድራችን መታየታቸው አልቀረም። በሰሜን አውሮፓ የኖርዲክ አገሮች የሚታዩ የበጎ አድራጐት መንግሥታትና የሰሜን ምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታት በዚህ ማዕቀፍ የሚታዩ የተለዩ አማራጮች ናቸው።

ይህ የነፉኩያማ አስተሳሰብ በምዕራቡ ዓለም መሪዎች ዘንድ በጥብቅ የታመነበት ከመሆኑም በላይ፣ ከበርሊን ግንብ መፍረስ በኋላ አሜሪካኖች በውጭ ግንኙነት ልሂቃኖቻቸው እየተመሩ በቅርብ ርቀት ሌላ ተቀናቃኝ እንዳይነሳባቸው ለማድረግ ልዩ ስትራቴጂ ነድፈው መንቀሳቀስ ጀምረው ነበር። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ ለአጭር ጊዜ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩትና በሂሮሺማና ናጋሳኪ ላይ አቶሚክ ቦንብ እንዲተኮስ ትዕዛዝ ያስተላፉት ሐሪ ትሩማን በጦርነቱ "ጀርመን የምታሸንፍ ከመሰለን ሩስያን መርዳት አለብን። ሩስያ የምታሸንፍ ከሆነም ጀርመንን መርዳት አለብን። በዚህ አኳኋን የቻሉትን ያህል እንዲጨራረሱ መፍቀድ አለብን"[99] እንዳሉት፣ በሃያኛው ከፍለ ዘመን መጨረሻም እርስ በእርስ የማናቆር አቅጣጫ በከፊልም ቢሆን ተግባራዊ አድርገውታል። ከአሜሪካ ታላላቅ የዲፕሎማሲ ጠበብቶች አንዱ የነበሩት ብሬዥንስኪ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ አውሮፓውያን እርስ በእርሳቸው፣ አውሮፓውያንና እስያውያን እንዲሁም እስያውያን እርስ በእርሳቸው ተባብረው የአሜሪካንን ልዕልነት የሚፈታተን ጐራ እንዳይፈጥሩና አገራቸው አሜሪካ በምንም ዓይነት ሁኔታ አዳዲስ ተቀናቃኞች እንዳይነሱባት ማድረግ እንዳለባቸው፣

> "አጣዳፊው ጉዳይ ከአውሮፓና ከእስያ (Euro Asia) አገሮች መካከል አንድ ወይም የተባበሩ ተቀናቃኞች ተነስተው አሜሪካንን ከኢሮኤዥያ እንዳያስወጧት፣ አነሰ ሲባል ደግሞ በአለቃነት የምትጫወተውን የዳኝነት ሚና እንዳይቀንሱባት ማድረግ ነው።"[100] በማለት አበክሮ አስገንዝበዋል።

ያለፉትን ሃያ አምስት ዓመታት የዓለም አቀፍ ግንኙነት ዋነኛ ገጽታዎች በመመርመር አሜሪካኖች ይህን አቅጣጫ ተከትለው ሲንቀሳቀሱ እንደቆዩ ለማረጋገጥ ይቻላል። ጀርመን ከፈረንሳይ፣ ሩስያ ከጀርመን፣ ወይም ፈረንሳይ ከሩስያ በመተባበር እንዳይፎካከሩዋቸው ጥረት አድርገዋል። ሩስያና ቻይና ወይም ቻይናና ሕንድ አንድ ላይ ገጥመው እንዳይገዳደሩዋቸው ለማድረግ ሞክረዋል። ሌላው ቀርቶ አሁን በቅርቡ እንኳ ከሩስያ መናቆር በሚመርጡት የአገሪቱ ገዥ ተቋማት ያልተወደደላቸውና ከባድ ወቀሳ ያስከተለባቸውም ቢሆን ዶናልድ ትራምፕ ሩሲያን ከጐናቸው ለማሰለፍና ከቻይና ለመነጠል የሚያካሂዱት ጥረት ይህንኑ ይመሰከራል። በመሆኑም

ከበርሊን ግንብ መፍረስ በኋላ በነበሩት ዓመታት አሜሪካኖች በየትኛውም የዓለም ጫፍ አንዳች ዓይነት ተቀናቃኝ የአገሮች ሕብረት እንዳይፈጠር በማድረግ ላይ ያነጣጠረ ጥረት በማድረግ የታሪክን ጉዞ ለማቆም ሞክረዋል። ነገር ግን ታሪክ ወደፊት መገስገሱን ሊያቆም አይችልምና አሜሪካኖቹ የተመኙትና ያሰቡት መሆኑ ቀርቶ አዲስ እውነታ ተፈጥሯል።

ይህን እውነታ አሁን አሁን ብዙዎች "የአሜሪካን ማሽቆልቆልና የቻይና መነሳት" በሚለው ማዕቀፍ እየገለጹት ይገኛሉ። በዚህ ምክንያት አሁን ያለውን የዓለማችን ፖለቲካ ከሚወስኑት ጉዳዮች አንዱና አቢይ የተባለው ይሸው በልእለ ኃያላን፣ በተለይ ደግሞ በአሜሪካና በቻይና መካከል ያለው አዲስ የፉክክር ግንኙነትና አይቀሬ መተካካት ሆኗል። የአንዱ ልእለ ኃያል የበላይነት ዘመን የማብቃት፣ የሌላው ደግሞ የመነሳት ምልክቶች የመበራከታቸውን አዲስ እውነታ ተከትሎ ከባድ ፉክክርና ሽኩቻ ተቀስቅሷል። ይህን ሽኩቻ በትክክል ለመገንዘብ የዓለማዊ ሥርዓቶች ተንታኞች የሆኑት ጆቫኒ አሪጊና ቢቨርሊ ጀ. ሲልቨር በተለያዩ ዘመን ተሻጋሪ ጥናታዊ ሥራዎቻቸው ካቀረቧቸው መላምቶች መነሳት ተገቢ ይሆናል። አሪጊና ሲልቨር ባለፉት አምስት መቶ ዓመታት በዓለማችን ላይ የበላይነቱን ያረጋገጠውን ካፒታሊስታዊ የገበያ ሥርዓት መነሻ በማድረግ ሦስት የልእለ ኃያልነት ዘመኖች እንደታዩና በእነዚህም መካከል መተካካት እንደተፈጸመ አረጋግጠዋል። በዚህ ጥናት መሠረት ደች ከ1650-1790፣ እንግሊዝ ከ1800-1920፣ አሜሪካን ደግሞ ከ1945 እስካሁን የዓለም አለቃ ሆነዋል። በእነ ሲልቨር ጥናት መሠረት በልእለ ኃያላን መካከል የሚካሔደው መተካካት ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ የሚፈጸም ነው። ይህን በማስመልከት፡-

> "ከልእልና [መተካካት]ጋር ተያይዞ የሚከሰተው ቀውስ በሦስት የተሳሰሩ፣ ነገር ግን ራሳቸውን ችለው በሚታዩ ሂደቶች መልክ የሚገለጽ ነው። የመጀመሪያው በመንግሥታትና መንግሥታት፣ እንዲሁም በኩባንያዎቻቸው መካከል ሽኩቻ መጧጧፉ ሲሆን፣ ሁለተኛው መገለጫ ደግሞ የማኅበራዊ ግጭቶችና ምስቅልቅል መባባስ ነው። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ አዲስ የኃይል ድልድል የሚጠይቁ አዳዲስ ተፎካካሪዎች በአንዱ የዓለማችን ጫፍ ብቅ ማለታቸው ነው። እነዚህ ሂደቶች እርስ በእርስ ያላቸው መስተጋብርም ሆነ የሚገለፁበት መልክ በጊዜና በቦታ የተለያየ ሊሆን መቻሉ እንደተጠበቀ በደች፣ ብሪትሽና አሜሪካ የልእልና መተካካት ጉዞዎች ላይ የተከሰቱ ነበሩ። በተጨማሪም ሶስቱ የመተካካት ቅድመ ሁኔታዎች በገበያ ሥርዓት ውስጥ ከልእልና የሚወርደው ልእለ ኃያል አገርና አጠቃላዩ የገበያ ኢኮኖሚ በፋይናንስ መስክ ታይቶ ወደማይታወቅ የመስፋፋት ደረጃ በሚሸጋገርበት ልዩ ማዕቀፍ ውስጥ የተከናወኑ

ነበሩ።።"[101] ይላሉ።።

እንደነጆቫኒ አሪጊ አገላለጽ አንድ ልዑላዊ ልእለ ኃያል አገር /Hegemonic Super Power/ በሌላ ከመተካቱ በፊት የሚታዩት እነዚህ ምልክቶች በዓለማችን የመጀመሪያው ልእለ ኃያል የነበረው የደች መንግሥት በእንግሊዝ ሲተካ፣ ቀጥሎም የእንግሊዝ አለቃነት በአሜሪካ ሲተካ ታይተዋል።፣ ዛሬ ደግሞ የወቅቱ የዓለማችን አለቃ አሜሪካ በቻይና መሪነት በሚንቀሳቀሰው የምሥራቁ ዓለም ሊተካ ተቃርቧል በሚባልበት ወቅት እየተከሰቱ ናቸው ይላሉ።

ከሦስቱ ምልክቶች አንዱ የሆነው በአንዱ የዓለማችን ጫፍ አዲስ የሥራ ክፍፍልና የኃይል ድልድል የሚጠይቅ የአዳዲስ ተፎካካሪዎች ብቅ የማለት ጉዳይን በመመልከት መጀመር የዚህን መላምት ትክክለኛነት ያሳያል። የመጀመሪያው የዓለም አለቃ ሆኖ ብቅ ያለው የደች (ኔዘርላንድስ) መንግሥት ነበር። የተባበሩት ሰባት ግዛቶች ኔዘርላንድስን ከፈጠሩ በኋላ ደቾች በአውሮፓ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ልእልናቸውን ማረጋገጥ ጀመሩ። ደቾች በባሕርና በየብስ የበላይ የሆኑበት ይህ ዘመን ከማብቃቱ ጥቂት አሥርት ዓመታት ቀደም ብሎ እንግሊዝ ቀስ በቀስ በኢንዱስትሪ አብዮት ተጠናክራ መውጣት ጀመረች። ከነባሩ ሉዓላዊ ልእለ ኃያል ጐን ብቅ ያለችው እንግሊዝ አቅሟ በጠነከረ ቁጥር በነባሩ የሥራ ክፍፍል አለመርካቷን በማሳየት አዲስ የሥራ ክፍፍልና የኃይል ድልድል እንዲቀረጽ መጠየቅ ጀመረች። አሜሪካኖች በእንግሊዝ የበላይነት ማብቂያ ወቅት ብቅ ብለው ነባሩን ሉዓላዊ ልእለ ኃያል እንግሊዝ ሲገዳደሩም ተመሳሳይ የሚና መሸጋሸግ ይፈጠር ዘንድ ባለ በሌለ አቅማቸው ተረባርበዋል።። ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች በኋላ ብዙም ጉዳት ያልደረሰባት አሜሪካ፣ ደረጃ በደረጃ የዓለም ፖሊስነት ሚናን በእጇ ወደማስገባት ያመራችው ከምዕራብ አትላንቲክ በኩል አዲስ ተቀናቃኝና ወቅታዊ የሚና ሽግሽግ የምትጠይቅ አገር ሆና በመነሳት ነው።።

ሁለተኛው አመልካች ከነባሩ ልዑላዊ ልእለ ኃያል ጐን አዲስ ተቀናቃኝ ልእለ ኃያል ብቅ ሲል፣ በነባሩ ልእለ ኃያልና በአዲሱ ተፎካካሪ መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ በሁለቱ አገሮች ኩባንያዎች መካከል ከባድ ፉክክር የሚቀሰቀስ መሆኑ ነው።። የልእለ ኃያላን መተካካት ታሪክ እንደሚያሳየው ኔዘርላንድስና እንግሊዝ ለበላይነት ሲፋለሙ ሽኩቻው ከመንግሥታት አልፎ በሁለቱ አገሮች ድንበር ዘለል ኩባንያዎች መካከል ጭምር የተካሔደ ነበር።። በዚህ ምክንያት ዓለምን በቀዳሚነት ይቆጣጠሩ ከነበሩት እንደ ደች ኢስት ኢንዲስ ኩባንያ ዓይነቶች ጐን ለጐን የብሪቲሽ ኢስት ኢንዲስ ኩባንያና መሰሎቹ ብቅ ብለው ቀስ በቀስ ቦታ እየተረከቡ መሔድ ጀምረዋል።። አሜሪካ የእንግሊዝን ልዑልነት በሻረችበት በሁለተኛው መተካካት ወቅትም የአሜሪካን ድንበር ዘለል ኩባንያዎች የእንግሊዝን ድንበር ዘለል ኩባንያዎች እየተገዳደሩና እየተኩ ሄደዋል።። ዛሬ ዛሬ ደግሞ በቻይናና አሜሪካ መንግሥታት መካከል ከሚካሔደው ጠንካራ ፉክክር

ጐን ለጐን የቻይና ድንበር ዘለል ኩባንያዎች የአሜሪካንን ኩባንያዎች መገዳደር መጀመራቸው፣ በነባርና አዲስ ልእለ መንግሥታትና ኩባንያዎች መካከል የሚታየው ይህ ፉክክርና ቦታ መነጣጠቅ በእርግጥም የመተካካቱ አይቀሬነት ሌላው አመልካች ተደርጐ ይወሰዳል::ይህን እውነታ በዓለማችን ካሉት 500 ግዙፍ ኩባንያዎች ውስጥ በአሜሪካ፣ ቻይናና ጃፓን ትልልቅ ኩባንያዎች መካከል ከ2007-2013 ድረስ በነበሩት ሰባት ዓመታት ብቻ የተካሄደው የቦታ ሽግሽግ ለቻይና እያጋደለ መምጣቱን ከሚከተለው ሠንጠረዥ በመመልከት መገንዘብ ይቻላል።

በዓለም 500 ትልልቅ ደረጃ የተመዘገቡ የየአገራቱ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር 2007.201.[102]

ሠንጠረዥ 5

ተ/ቁ	አገር/ ሪጅን	2013	2012	2011	2010	2009	2008	2007
1	የተባበረው አሜሪካ	132	132	133	140	140	155	162
2	ቻይና (ታይዋንና ሆንግኮንግን ጨምሮ)	95	79	69	54	43	35	30
3	ዋናዋ ቻይና (MainLand)	85	69	57	42	34	25	22
4	ጃፓን	62	68	68	71	68	64	67

ከዚህ ሠንጠረዥ በሰባት ዓመታት ውስጥ አሜሪካ ከ500 የዓለም ታላላቅ ኩባንያዎች ውስጥ ከነበሯት 162 ያህል ግዙፍ ተቋማት 30 ያህሉ ደረጃቸውን ተነጥቀዋል። ጃፓንም አምስት ያህል ኩባንያዎቿ ከረድፉ ወጥተዋል። በአኳያው ቻይና ደግሞ ታይዋንና ሆንግ ኮንግን ሳይጨምር ከነበሯት 22 ኩባንያዎች ላይ 63 አዳዲስ ግዙፍ ኩባንያዎች በመጨመር በድምሩ 85 ኢንተርፕራይዞችን ከዓለም ታላላቅ ኩባንያዎች ተርታ አስገብታለች። በኩባንያዎች መካከል የተካሄደው ይህ ሽግሽግ በርግጥም መተካካቱ በአይናችን ሥር ለዚያውም በከፍተኛ ፍጥነት እየተፈጸመ እንደሆነ ያረጋግጣል።

በመጨረሻ ደግሞ መተካካት አይቀሬ ለመሆኑ እንደሦስተኛ ማረጋገጫ ምልክት ሆኖ የቀረበው በልእለ ኃያላን መካከል ከባድ ፉከክር በሚቀሰቀስበትና መተካካት አይቀሬ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ማኅበራዊ ቀውስ የሚበራከት መሆኑ ነው:: ለለምሣሌ በደቾች የልእልና ዘመን መጨረሻና እንግሊዝ መሪነቱን ልትረከብ በተቃረበችበት ወቅት በአውሮፓ የእርስ በርስ ጦርነቶች በእጅጉ ተበራክተው ነበር:: ከ1618-1648 የተካሔደው የ30 ዓመታቱ ጦርነት፣ በእንግሊዝና በደች መንግሥት መካከል ከ1652-1674 በነበሩ ሃያ ሁለት ዓመታት ውስጥ

የተካሔዱት ተደጋጋሚ ጦርነቶች፣ በስፔንና በፈረንሳይ መካከል የተካሔዱት ትልልቅ ጦርነቶች፣ በመጨረሻም አውሮፓን በደም የነከሩት ናፖሊዮናዊ ጦርነቶች ሁሉ በርግጥም ከመጀመሪያው የልእል ኃያልነት መተካካት ጋር ተያይዞ በአውሮፓ ከባድ ማኅበራዊ ምስቅልቅል ተከስቶ እንደነበር የሚያረጋግጡ ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ የእንግሊዝ ልእልና ከማከተሙ በፊት አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች መከሰታቸው በዓለም ደረጃ የሚከሰት የማኅበራዊ ምስቅልቅል መበራከት የመተካካቱ ሦስተኛ ቅድመ ሁኔታ እንደተፈጠረ የሚያመላክት ነበር።

ነባሩ ልዑላዊ ልእለ ኃያል አገር አሜሪካ መንበሩን ሳይለቅ፣ እነሆ ቻይና አዲሱ ተፎካካሪ አገር በመሆን ከጐን ብቅ ብሏል። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓመታዊ ጉባዔዎች፣ ከቡድን-7 እስከ ቡድን-20 ባሉት የመሪዎች ስብሰባዎች፣ በዳቮስና ዶሃ መድረኮች፣ በዓለም የኢኮኖሚ ፎረሞች የሚሰሙ የመንግሥታት ዲስኩሮች ሁሉ በአንድ ወይ በሌላ መንገድ በሁለቱ ተቀናቃኝ ኃይሎች መካከል የተጧጧፈውን የመተካካት ፉክክር ያመላክታሉ። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩት ባራክ አባማ በቅርቡ ምሥራቅ አፍሪካን በጐበኙበት ጊዜ በአፍሪካ አዳራሽ ባሰሙት ንግግር ላይ ቻይና በአንዳች ቀጭን ገመድ ተጐትታ እንደገባች ሲታይ፣ አሁን ደግሞ ዶናልድ ትራምፕ ቻይናን አንድ ጊዜ "የሥራ ዕድል ነጣቂ"፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ "የምንዛሬ ተመን አምታች"(Currency Manipulator) እያሉ ማጥላላታቸው በእርግጥም በነባሩ ልዑላዊ ኃይል አሜሪካና በተተኪነት ባለተስፋ በሆነው ቻይና መካከል በቃላት ጦርነት ጭምር የተደገፈ ከባድ ሽኩቻ እየተካሔደ እንደሆነ ያሳያል። ዶናልድ ትራምፕ "አሜሪካ ትቅደም" በሚል መፈክር እየተመሩ በሜክሲኮ ድንበር አሠራዋለሁ ባሉት አጥር ከግሎባላይዜሽን የማፈግፈግ አዝማሚያ ማሳየታቸውን ተከትሎ የቻይናው መሪ ሺ ጂን ፒንግ በ2016 የዳቮስ መድረክ ላይ "ቻይና የመሪነት ክፍተቱን እንድትሞላ ብትጠየቅ ደስታውን አንችለውም" ብለው ነበር። በዚያው ወቅት የመሪነት ሚናውን ከዴቪድ ካሜሮን የተረከቡት አዲሷ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ቴሬዛ ሜይ ደግሞ ወደአሜሪካ አቅንተው በፊላደልፊያ ከተማ ለተሰበሰቡ የአሜሪካ ሕግ አውጭዎች "ምዕራባውያን የተለመደውን የመሪነት ሚና ለማንም አሳልፈው ሊሰጡ አይገባም" ብለው ዲስኩር አሰምተዋል። ከእነዚህ ፍላጐቶች ባሻገር ደግሞ ለባለይነት የሚደረገው ሽኩቻ በተግባር ረጅም ርቀት ተጉዟል። አሜሪካውያን "የእስያ ሽብልቅ" (Pivot to Asia)፣ ቻይናውያን ደግሞ "የሉል ሰንሰለቶች" (String of Pearls) በሚል ስያሜ ቀርፀው ይከተሉዋቸዋል የሚባሉት ስትራቴጂዎች የዚህን ሽኩቻ ጥልቀት ያመላክታሉ።

አሜሪካኖቹ "የእስያ ሽብልቅ" በሚል ማዕቀፍ በቀረፁት ስትራቴጂ ዙሪያ፣ በእስያ የሚገኙ ደጋፊዎቻቸውን ከቻይና ጋር ለማፋለም መነሳታቸው በብዙ የዓለም አቀፍ ተንታኞች ዘንድ አነጋጋሪ ከሆነ ከርሟል። የሕንድን መነሳት ተከትሎ ከፓስፊክ ይልቅ የሕንድ ውቅያኖስ ዋናው የፍልሚያ ቀጠና ይሆናል ብሎ የሚገምተው ሮበርት ዲ. ካፕላን ይህንኑ ሽኩቻ

በማስመልከት፡-

> "የአሜሪካ መንግሥት እ.ኤ.አ በ2007 ሮድ አይላንድ፣ ኒውፖርት ላይ የባሕር ኃይሉን የማሪታይም ስትራቴጅ ይፋ ሲያደርግ፣ በዋነኛነት በምዕራብ ፓስፊክና በሕንድ ውቅያኖስ ላይ ዘላቂና ወደፊት የሚወነጨፍ ህልውና ለማረጋገጥ እንደተዘጋጀ አሳውቋል፡፡ ...አሜሪካ በፓስፊክ ውቅያኖስ ላይ ገንብታው ከቆየችው የበላይነት ጋር በደቡብ እስያ ላይም ተፎካካሪ የማይገኝላት ኃይል መሆን ትሻለች፡፡ ይህም ትኩረቷን ከአትላንቲክና ከአውሮፓ ወደእስያ የማዞር ታሪካዊ እርምጃ መውሰዷን ያመላክታል፡፡"[103] ይላል።

ዌን ሊዩ የተባለች የፖለቲካ ተንታኝ በበኩሏ በተለይ የአሜሪካኖችን የፒቮት ስትራቴጂ መነሻ በማድረግ ፉክክሩ ምን ያህል እየደራ እንደሔደ፡-

> "ቻይናውያን እንደሚሉት አንድ ቃል በሺ የወርቅ ቁርጥራጮች የሚለካ ትርጉም የሚኖረው ከሆነ፣ ቻይና ላይ ያነጣጠረውና 'ፒቮት' የሚል ስያሜ የተሰጠው የአሜሪካ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ፋይዳና ክብደት የትየለሌ ነው፡፡ ፖሊሲው ከባድ ወታደራዊ ይዘት አለው፡፡ አሜሪካ በ2010 ከደቡብ ኮሪያ ጋር በመሆን የቻይና አዋሳኝ በሆነው በየሎ ሲ /Yellow Sea/፣ በ2011 ደግሞ ከቬትናም ጋር በመሆን የባሕር ኃይል የጋራ ልምምዶችን አድርጋለች፡፡ ፊሊፒንስ ላይ ያላትን ወታደራዊ ኃይልም አሳድጋለች፡፡ በዚሁ ዓመት ጃፓን ከቻይና ጋር ባላት ግንኙነት ወደቀውስ ካመራች በኋላ፣ ጃፓንን ለመከላከል የሚያስችል የአሥራ ሁለት ቀናት ወታደራዊ ልምምድ አድርጋለች፡፡ ፕሬዚዳንት አባማ በ2011 መጨረሻ አገራቸው አሜሪካ አውስትራሊያ ላይ ተጨማሪ የባሕር ኃይል እንደምታሰፍር ካሳወቁ በኋላ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩ ሊዮን ፓኔታ በአትላንቲክና በፓስፊክ ውቅያኖስ ላይ የነበረውን የባህር ኃይል አቅም ተመጣጣኝነት በመቀየር ፓስፊክ ላይ ያለውን የባሕር ኃይል ወደ60% እንደሚያሳድጉት ገልጸዋል፡፡"[104] ትላለች።

ቻይና በበኩሏ የሉል ሰንሰለቶች /String of Pearls/ በሚል ስትራቴጂ በሕንድና ፓሲፊክ ውቅያኖሶች ላይ የተፅዕኖ ክልሏን ማስፋቷና በእነዚህ ሁሉ መፋጠጣቸው ይህን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ክርስቶፎር ጀ. ፐርሰን ይህን በማስመልከት፡-

> "የሉል ሰንሰለቶቹ ከቻይና የባሕር በር በመነሳት በደቡብ ቻይና ባሕረ ሰላጤና በማላካ የመተላለፊያ በር አልፈው በሕንድ ውቅያኖስ በማቋረጥ

ወደአረብ ባሕርና የፋርስ ባሕረ ሰላጤ ድረስ የሚዘልቁ ናቸው፡፡ ቻይና በእነዚህ አካባቢዎች ስትራቴጂያዊ ግንኙነቷን እያጠናከረች ከመሆኑም በላይ ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋር በባሕር ላይ የሚያገናኛትን መስመሯን በመገንባት ላይ ነች፡፡"[105] ይላል፡፡

የፖሲፊክ ውቅያኖስ ሰላማዊነቱ ቀርቶ የአሜሪካና የቻይና ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ የፉክክር ቀጠና ሆኗል፡፡ በምሥራቁ ካምፕ መፍረስ ምክንያት ለዓመታት ረገብ ብሎ የነበረው ቅራኔና ሽኩቻ፣ ዛሬ ዛሬ በዩክሬን ቀውስ ሳቢያ ማገርሸቱን ተከትሎ የአትላንቲክ ውቅያኖስም በሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን አገሮችና በሩሲያ መካከል በተቀሰቀሰው የተፋፋመ ቀዝቃዛ ጦርነት መናጥ ጀምሯል፡፡ በቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ወደአፎታቸው ተመልሰው የነበሩ ጦር መሣሪያዎች እንደገና ብቅ ብቅ እያሉ፣ የኑክሌር እሽቅድድምን ገትተው የቆዩ ስምምነቶች እየተሻሩ አዳዲስ የኒውክሌር ጦር መሣሪያዎች ማምረትና መሞከር ተጀምሯል፡፡ የፕሮፖጋንዳ ጦርነቱ ከመቸውም ጊዜ በላይ ተጧጡፏል፡፡ ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ሕንድ፣ ቻይናና ደቡብ አፍሪካ የተሰባሰቡበትና በምኅጻረ ቃል BRICS ተብሎ የሚታወቀውን ስብስብ የመሰረቱ አዳዲስ ዓለም አቀፍ ሕብረቶች ተፈጥረዋል፡፡ ለሩብ ምእተ ዓመት ያህል ጂኦ ስትራቴጂያዊ ፉይዳው ቀንሶ የነበረው ቀይ ባሕር እንኳ እንደገና የወታደራዊ ፉክክር ቀጠና ሆኗል። ከጅቡቲ ጋር በቆየ ስምምነት እዚያው የኖረችውን ፈረንሳይና በባሕረ ሰላጤው ጦርነት ማግስት ገብታ እዚያው ለምዳ የቀረችውን አሜሪካንን ጨምሮ ቻይና፣ ጃፓን፣ ኢራን፣ ሳዑዲ አረቢያና እስራኤል ቀጠናውን ወታደራዊነት አላብሰውታል። የቀይ ባሕርን ወታደራዊነት ባስከተለው በዚህ እሽቅድድም ትንሿ ኳታርም አልቀረችም። እነዚህ ሁሉ በዓለማችን ሌላ ከባድ ጂኦስትራቴጂያዊ ፉክክር እንደተቀሰቀሰ የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ በአገራቱ መካከል የሚካሔደውን ይህን ፉክክር ተከትሎ የቻይናና የአሜሪካ ኩባንያዎች በከባድ ፉክክር ተጠምደዋል፡፡ በኤሌክትሮኒክስ አምራችና ቴሌኮም ኩባንያዎች መካከል በነዳጅ አቅራቢ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች፣ በሚዲያ ተቋማት መካከል በመንግሥታቱ መካከል ካለው የማይተናነስ ሽኩቻ ይካሔዳል። ይህም በልዑላዊ ልእለ-ኃያልነት ከመተካካት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ምልከት ሌላው ገጽታ መሟላቱንና የመተካካት ወቅት መቃረቡን ያሳያል፡፡

በዓለማችን ታይቶ የማይታወቅ ግጭትና ማኅበራዊ ቀውስ መበራከቱም በዘመናችን የልዑላዊ ልእለ ኃያልነት መተካካቱን አይቀሬነት ያመላክታል፡፡ ሁለቱ የፋርስ ባሕረ ሰላጤ ጦርነቶች፣ ሁለቱ የአፍጋኒስታን ጦርነቶች፣ የማይበርደው የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭት፣ በመስከረም አንዱ የአይሮፕላን ጥቃት ተጀምሮ ተሸከርካሪዎችን እንደሽብር መሣሪያ እስከመጠቀም የዘለቀው አሸባሪነት፣ እንደ አይሲስና ቦኮ ሐራም የመሳሰሉ የሃይማኖት ጽንፈኝነት

መገለጫ ነቀናቄሥተና በዓለም ዙሪያ የተበራከቱት ማኅበራዊ ቀውሶች፣ የመንግሥታት መከሰም፣ ስደትና ሁሉም ዓይነት ማኅበራዊ ምስቅልቅሎች፣ ታላቁ ልዑላዊ አለቃ አሜሪካ የዓለምን ሰላም ማረጋገጥ እንደተሳነው አመላካች ተደርገው ይወሰዳሉ:: በእነዚህ ተንታኞች አስተያየት ምድራችን እንደገና በሌላ ማኅበራዊ ምስቅልቅል መሞላቷ ሌላው የመተካካት ቅድመ ምልከት ተደርጐ ይወሰዳል::

የዓለማዊ ሥርዓቶች ተንታኝ የሆኑት እነጆቫኒ አሪጊ፣ በዓለማዊ የልዑልነት ወንበር ላይ የሚኖር የታላላቆቹ መተካካት፣ ከላይኞቹ ሦስት ምልከቶች በተጨማሪ ቀደምቱ ልእለ-ኃያል አገር መንበሩን ከማስረከቡ በፊት ራሱን ወደአራጣ አበዳሪነት በሚቀይርበት ማዕቀፍ እንደሚፈጸም ያረጋግጣሉ:: በዚህ የተነሳ ነባሩ ልዑላዊ ልእለ ኃያል አገር የዓለምን ገንዘብ በሙሉ የሚሰብሰብና ይህንም መልሶ በከፍተኛ ወለድ የሚያበድር መሆን ይጀምራል:: እነ ጆቫኒ አሪጊ ይህን ወቅት "የከፍተኛ ፋይናንስ ዘመን " (High Finance) በማለት ይገልፁታል:: ቀደም ሲል በነበሩ መተካካቶች ደች ለእንግሊዝ፣ እንግሊዝ በፋንታዋ ደግሞ በትረ ሙሴውን ለአሜሪካ ከማስረከባቸው በፊት ከዚያ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የዓለምን ገንዘብ የሚሰቡ ማግኔቶች የመሆን ተመሳሳይ ዝንባሌ አሳይተው ነበር:: ከዚህ በመነሳት ጆቫኒ አሪጊና ቢቨርሊ ሲልቨር "ጀንበር የጠለቀችበት ልዑላዊ አገር ራሱን ወደ አራጣ አበዳሪነት ሲቀይር ወይም የዓለም ፋይናንስ ማግኔት መሆን ሲጀምር ለመተካካቱ መቃረብ አጠቃላዩ ማዕቀፍ ተፈጥሯል"[106] ይላሉ:: እነዚህ ምልከቶች በሁሉም የልእለ ኃያላን መተካካት ወቅት የተከሰቱ በመሆናቸው በአሁኑ ጊዜ ሊካሔድ ይችላል ተብሎ በሚገመተው ወይም በሚነገርለት መተካካት ዋዜማም የሚታዩ ከስተቶች ሆነዋል::

አሜሪካኖች በዚህ ፉከከር መካከል የዓለም የፋይናንስ ማዕከል ሆነው ወጥተዋል። የቻይና፣ የሩቅና የመካከለኛው ምሥራቅ ካፒታል ሁሉ መዳረሻው አሜሪካ ሆኗል:: አሜሪካ ከሚያመርተው በላይ ተበድሮ የሚበላ አገር መሆኑ በተረጋገጠበት በዚህ ዘመን፣ አሜሪካንን ሳይሳለም የሚያድር የዓለም ፋይናንስ አለ ማለት አይቻልም:: ኢንቨስትመንቱም ሆነ ሌሎች የቆጠቡት የውጭ ምንዛሬ መዳረሻ አሜሪካ ነው:: ይህ ሁሉ ተዳምሮ በእርግጥም የቅድመ መተካካት ምልከቱ ገዝፎ መምጣቱን ያሳያል:: :

አሜሪካኖች በቀዝቃዛው ጦርነት ማሸነፋቸው ባይካድም፣ ከቬትናም ጦርነት ሽንፈታቸው ጀምሮ እነዚህ ምልከቶች በገሃላ ደረጃ ሲታዩ ቆይተዋል:: በአሜሪካኖች ሽንፈት የተደመደመው የቬትናም ጦርነት አሜሪካኖች ዓለምን በበላይነት ሰላማዊ አድርገው ማስተዳደር እንዳቃታቸው ያመላከተው የመጀመሪያ አጋጣሚ ነበር:: በዚህ ጦርነት ትልቁ የዓለም ፖሊስ በአንድ ትንሽ አገር መሸነፉ በየትኛውም ዓለም ሰላም ለማስከበር የነበረውን ብቃት ጥያቄ ምልከት ውስጥ አስገብቶታል:: አሪጊ የቬትናምን ጦርነት የአሜሪካኖች የልዑላዊ ልእለ ኃያልነት ዘመን

ማክተም "የመጀመሪያው የቀውስ ምልክት /Signal Crisis/ ነበር" ይለዋል። ይህ ቀላል የቀውስ ምልክት መከሰት በጀመረበት በ1960ዎቹ ጃፖን ከባድ ተፎካካሪ ሆና ብቅ ብላ ነበር። ቻይና ደግሞ ተስፈንጥራ ለመውጣት የመጨረሻውን ዝግጅት ታደርግ ነበር። ነገር ግን በሂደት የጃፖን መነሳትና አሜሪካንን የመተካት ዕድል ወደእውነትነት መቀየር ሳይችል ቀረ። ቻይና ግን ግዙፉን የህዝብ ብዛቷን ይዛ በጣም ፈጣን ታዳጊ ኢኮኖሚ በመገንባት መጀመሪያ ጃፓንን በከፍተኛ ርቀት ቀደመች። ይህም ሳያንስ በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ከአሜሪካ የሚተልቅ ኢኮኖሚ እንደሚኖራት የማያጠራጥር ሆነ። የቻይና መነሳት በቀደምት የልእለ ኃያላን መተካካቶች ወቅት የተከሰቱት ምልክቶች ሁሉ በዘመናችንም ተሟልተው መታየት ጀመሩ። እናም ቀደምት ምልክቶችን ተከትሎ መተካካቱ በተግባር እንደተፈጸመው ሁሉ አሁንም መተካካቱ አይቀሬ ነው ቢባል ከመስመር የወጣ አይሆንም። መተካካቱ አይቀሬ በሆነበት በዚህ ዘመን ዋናው ጥያቄ ይህ መተካካት ሰላማዊ ወይስ የግጭት ይሆናል የሚለው ብቻ ነው።

በልእለ ኃያላን መካከል ከሁሉም የላቀ ልእለ ኃያል ለመሆን የሚካሔደው ሽኩቻ በጠነከረበት በዚህ ዘመን መተካካቱ ሰላማዊ ወይም በግጭት መልክ ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑ ብዙዎች የሚያነሱት ጥያቄ ሆኗል። ይህ ከሞላ ጐደል ጀንበሩ ያዘቀዘቀችው ልእለ ኃያል በሰላም ቦታውን ለማስረከብ የሚሻ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ሳይሆን፣ ፀሐይ ወጣችለት የሚባለውም በሰላም ለመረከብ ዝግጁ ሆኖ ሲገኝ ሊመጣ የሚችል ነው። ልእለ ኃያላኑ ከማንም በላይ ጉልበት ያላቸውና ለከብራቸውም የሚሟሟቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ በልዑልነት መንበሩ ላይ ከመቀመጥ ጋር ተያይዘው ለሚመጡ ጥቅሞች የሚታደሉ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ መተካካቱ የግጭት ሊሆን የሚችልበት ዕድል ትንሽ አይደለም። በዓለማችን ከዚህ ቀደም በሰላም የተቋጨ የልእለ ኃያላን መተካካት አልነበረም። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጦርነቶች ያልታጀበ የልእለ ኃያልነት መተካካት ተካሒዶ አያውቅም። አሁንም በእጅ አዙር የመቀጣቀጥ ሁኔታ እየሰፋ በመሔድ ላይ ነው። ይህም ሆኖ ግልጽ የልእለ ኃያላን ግጭት ከተቀሰቀሰ ሁሉም ኒውክሌራዊ መሣሪያዎችን የታጠቁ በመሆናቸው አሸናፊም ተሸናፊም ሊኖር አይችልም። ስለዚህም ይህን እውነታ እንደሚገነዘቡ የሚገመቱት ልእለ ኃያላን ለመተካካት በሚያደርጉት ሽኩቻ ከተፋፋመና የእጅ አዙር መቀጣቀጥ ከበዛበት ቀዝቃዛ ጦርነት በላይ ይሔዳሉ ተብሎ አይገመትም።

በዓለም ልእለ ኃያላን አገሮች መካከል የተቀጣጠለው ይህ ሁሉ ሽኩቻ እንደገና ዓለምን ጐራ የለየ ቀዝቃዛ ጦርነት የሚካሔድባት መድረክ አድርጓታል። ሁሉም ልእለ ኃያላን ኒውክሌር የታጠቁ በመሆናቸው ዓለም አቀፋዊ ጦርነት ከመቀስቀስ እስካሁን ድረስ የተቆጠቡ ቢሆኑም፣ በተለይ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን አገሮች ድርጅት (NATO) ከዚህ በመለስ የሚታዩ ግጭቶችን በቀላሉ እንዲበርዱ የማድረግ ፍላጐት ያለው አይመስልም። ይህ አዲስ የዓለማችን እውነታ ቀስ በቀስ ደጋፊዎችን ወደማሰባሰብ በማምራት የየራስ ጐራ

መገንባት ማስከተሉ አይቀሬ በመሆኑ እኛን ለመሳሰሉ ታዳጊና ያልበለጸጉ አገሮች ከባድ ፈተና መሆን ጀምሯል፡፡ "ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ከጠላቴ ጋር ነው" ብለው የሚፈርጁ አለቆች ባሉበት ዓለም፣ በእያንዳንዷ ከስተት የታዳጊ አገሮችን ድጋፍ በውድም በግድም ማግኘት እንደ ግብ ተይዞ መንቀሳቀስ ከተጀመረ ከርሟል፡፡ በመጋቢት 2017 የቻይናው ጠቅላይ ሚኒስትር ሊ ኬኪያንግ አውስትራሊያን በጎበኙበት ወቅት ለጠቅላይ ሚኒስትር ማልኮም ተርንቡል በፓስፊክ ቀጠና ውስጥ እየኖሩ በተፋላሚ ልእለ ኃያላን መካከል ማማረጥ እንደማይችሉ በግልጽ ቻይንኛ "በበኩላችን በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት እንደነበረው ወገን የለየ አሰላለፍ እንዲኖራችሁ አንፈልግም" በማለት አስጠንቅቀዋል። ከቻይና ጋር ባላት ዓመታዊ የ150 ቢሊዮን ንግድ ለሃያ አምስት ዓመታት ከኢኮኖሚ ቀውስ የተጠበቀችው አውስትራሊያ በበኩሏ ለዚህ ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር "ጎራ የለየ አሰላለፍ ምን ሲባልስ ይሞከራል" ብላ ለመመለስ ተገዳለች፡፡

ይህን በመሰለ ሁኔታ ከራስ አገር ብሔራዊ ጥቅምና መብት በመነሳት አቋም መውሰድ ምንጊዜም ቢሆን ሉዐላዊ መንግሥታትን የሚፈታተን ይሆናል፡፡ በተለይ ደግሞ በልእለ ኃያላኑ መካከል ለኖር ይችላል ተብሎ የሚገመተው መተካካት ሰላማዊ መልከ ኖሮት የማይፈጸም ከሆነ ፈተናው ከባድ መሆኑ አይቀርም፡፡ በተለይ እንደኢትዮጵያ ላለና ብዙ ህዝብ ይዞ በመነሳት ላይ የሚገኝ ተፅዕኖ ፈጣሪ አገር ፈተናው ከባድ መሆኑ አይቀርም። ስለዚህም ይህን የመሰለውን ችግር ከወዲሁ ለመቋቋም በሚያስችል ደረጃ ራስን ማዘጋጀት አማራጭ የሌለው ይሆናል፡፡ ይህ ዝግጅት አገራዊ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲያችንን ይህን አዲስ እውነታ መነሻ በማድረግ እንደገና በማዳበር ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል። ምንም እንኳ ከውስጥ ወደውጭ የሚያነጣጥረው ፖሊሲያችን በጥራት የተቀረጸ ቢሆንም፣ ይህንኑ ባለፉት አሥራ አምስት ዓመታት የተመዘገቡትን አገራዊ፣ ከባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ለውጦች ታሳቢ ባደረገ አኳኋን ማዳበር ወቅታዊ ሆኖ ይገኛል። ከሩብ ምእተ ዓመት የለውጥ ጉዞ፣ በተለይ ደግሞ ከአስራ አምስት ዓመታት ፈጣን ዕድገት በኋላ፣ ተመሳሳይ ነገር እየሠሩ የተለየ ውጤት መጠበቅ አይቻልምና ጥልቀት ባለው ግምገማ ላይ በመመሥረት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችንን ማዳበር አጣዳፊ ይሆናል። ይህ ተግባር በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም በኩል "ኤርትራን የሚመለከት አዲስ ፖሊሲ አዘጋጅተናል" በተባለ ማግሥት ፖሊሲውን ፈልጎ ማግኘት እንዳስቸገረው፣ ምንም ነገር ሳይያዝ መግለጫ በመስጠት የሚፈጸም እንዳልሆነም በወ·ል ሊሰመርበት ይገባል።

ፈጣን ዕድገት ውስጥ የገባችው ኢትዮጵያና የኒዮ - ሊበራሊዝም ተፅዕኖ፣

ኢትዮጵያን በቅርብ ርቀት ከባድ ፈተና ከሚደቅኑባት ጉዳዮች ሌላው በኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮት በመመራት የሚንቀሳቀሱ የገበያ አከራሪ ኃይሎች የሚሰነዝሩት የተለመደው ጥቃት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ኒዮ-ሊበራሊዝም ሌሎችን በማራቆት መከበርን

ብቸኛ አማራጭ አድርገው በሚያምኑ የምዕራቡ ዓለም ልሂቃን ዘንድ ዘጠኙ ዐሥታሥ ዝርዮ እንደማንኛውም ርዕዮት ደግሞ የእነርሱ ጥቅም ማስጠበቂያ መሣሪያ ነው። በዚህ ርዕዮት የሚመሩ አገሮች እጃቸው ሊያርፍበት የቻለውን የተፈጥሮ ሀብት ሁሉ በቁጥጥራቸው ሥር ለማስገባት ርዕዮቱን እንደመሣሪያ ከመጠቀም ወደኋላ የማይሉ ናቸው።

ሁኔታው በንግድ ልውውጥ አማካይነት የሌሎችን ሀብት ወደ እነርሱ ለማምጣት ዕድል የሚከፍትላቸው ከሆነ፣ ያልተመጣጠነ የንግድ ሥርዓት ገንብተው አገሮችን ይዘርፋሉ። በአንድ በኩል እነርሱ ለሚያቀርቡት ምርትና አገልግሎት ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈሉ፣ ከሌሎች ለሚያገኙት ጥሬ ዕቃ ደግሞ ዝቅተኛ ዋጋ እየከፈሉ መመዝበራቸው የነበረና ዛሬም ያለ ቀዳሚ ስልታቸው ነው። ለዚህ ሲሉ የሌሎች አገሮችን በር በርግደው ለማስከፈት ይሰራሉ። በአንድ ወቅት የራሳቸውን ገበያ በከባድ የመንግሥት ጥበቃ እንዳልተከላከሉ፣ ዛሬ የአገር ውስጥ ገበያቸውን የሚከላከሉ አገሮችን ሁሉ ፀረ-ነጻ ገበያ በሚል ክስ እያጠራቀቁ መተንፈሻ ያሳጣሉ። የአገር ውስጥ ገበያቸውን ለመከላከል በቆራጥነት የሚቆሙ ሉዓላዊ መንግሥታትንም በቀለም አብዮትና በቀጥተኛ ወረራ እስከማፍረስ ይደርሳሉ። ኒዮ-ሊበራሎቹ በሁለተኛው የባሕረ ሰላጤ ጦርነት የሳዳም ሁሴንን መንግሥት ውሃ በማይቋጥር መሠረተ-ቢስ ምክንያት ያፈረሱት በኢራቅ የነዳጅ ሀብት ላይ እጃቸውን ለማሳረፍ ነበር። በሩሲያ የተፈጥሮ ሀብት ላይ እጃቸውን ለማሳረፍ ያደረጉት ጥረትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። በቅርቡ የፕሬዚደንት ፑቲን መንግሥት የሩሲያን ክብርና የተፈጥሮ ሀብት ለማስመለስ በጽናት መፋለም መጀመሩን ተከትሎ ሩሲያን ለማፍረስ የሚካሔደው የፕሮፖጋንዳ ዘመቻና ዓይን ያወጣ ትንኮሳ፣ ይህንኑ ርዕዮተ ዓለማዊ ጥቃት በግልጽ የሚያሳይ የእለት በ'ለት ከስተት ሆኗል።

ይህ ጥቃት በማንኛውም መንግሥት ላይ የሚሰነዘር እንደሆነ ሊበራል ኢኮኖሚ የገነባቸውን ግሪክ በማየት ብቻ ሊረጋገጥ የሚችል ነው። አንዳንድ ጊዜ አገሮች ለወራራም ሆነ ለጥቃት የሚጋለጡት ወራሪውም ሳይቀር በቂ ምክንያት ሳይኖረው በሚያስተላልፈው ውሳኔ ነው። ናኦሚ ክሌን (2007) አሜሪካኖች በሁለተኛው የባሕረ ሰላጤ ጦርነት የትኛውን እስላማዊ አገር መውረር እንዳለባቸው ሲወስኑ ከነበረው ሁኔታ ጋር በማያያዝ ያቀረበችው ይህን በግልጽ ያሳያል። ናኦሚ ይህን በማስመልከት፡-

> "ከመስከረም አንድ በኋላ አንድን የአረብ አገር በመውረር ወደሞዴል መንግሥትነት የመቀየር ውጥን ሀሳብ ተቀባይነት እያገኘ መሔድ ሲጀምር በርካታ የአረብ አገሮች ስም መነሳት ጀምሮ ነበር። የማይከል ሌደን ምርጫ የሆነችውን ኢራን ጨምሮ፣ ኢራቅ፣ ሶርያ፣ ግብጽ እየተነሱ ለወረራው በአማራጭነት ተይዘው ነበር። ነገር ግን ኢራቅ በብዙ ምክንያቶች የላቀ ዒላማ ሆና ተመረጠች።

በሰፊው ከሚገኘው የነዳጅ ሀብቷ በተጨማሪ ሳኡዲ አረቢያ [በአከራሪነት መስፋፋት የተነሳ] አስተማማኝ እየሆነች አለመሔዷን ተከትሎ ማዕከላዊ ወታደራዊ ሠፈር ልትሆን መቻሏ የተሻለ ተመራጭነት አጐናጸፋት። በዚህ ላይ ሳዳም ሁሴን በራሱ ህዝቦች ላይ ኬሚካል የጦር መሣሪያ መጠቀሙ ባስከተለበት ጥላቻ የተነሳ በቀላሉ ሊነጥሉት የሚቻል ነበር። የመጀመሪያው ጦርነት ኢራቅን የተለመደች ዒላማ ማድረጉም ዘመቻውን የሚያቀለው ነበር።"[107] ትላለች።

ከዚህ በመነሳት አንድ የዓለም አለቃ ጉልበቱን ለመፈተሽም ሆነ በሌላ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምክንያት አገሮችን መውረር ከፈለገ አንዳች ዓይነት ሰበብ መፍጠሩ የማይቀር ብቻ ሳይሆን ከፈለገ በማንኛውም አገር ላይ ሊያደርገው እንደሚችልም ለመገንዘብ ይቻላል። ከኢራቅ የተሻለ ሌላ ኢላማ ቢገኝ ኖሮ ሁለተኛው የባሕረ ሰላጤ ጦርነት ከኢራቅ ጋር ባልሆነ ነበር። ስለዚህም በዚህ ዘመን ታዳጊ አገሮች የልእለ ኃያላንን ቁጣ ይቀሰቅሱ ዘንድ ተራ ምክንያቶች ከበቂ በላይ ናቸው። ከወንዙ አናት ሆኖ በወንዙ የታችኛው ጫፍ ላይ ሆና የምትጠጣውን የፍየል ግልገል "የምጠጣውን ውሃ አደፈረስሽብኝ" ብሎ ለመብላት እንደተነሳው ነብር ውሃ በማይቋጥር ምክንያት አገሮችን መቅጣት ያልተለመደ አይደለም። በእኛዋ አቅም እንኳ እንደታየው ጉልበት ሲሰማህ "ነፋስ ከአንተ በኩል ወደእኔ አገር መጥቷል" በሚል ሰበብ የመዋጋት ሀሳብ ሊራመድና በተግባርም ሊሞከር ይችላል። የመንደር ጐረምሳ እንዲህ ማሰብ ከቻለ የዓለም አለቃ ከዚህ ባነሱ ምክንያቶች አገሮችን ለመውረር ሲል አንዳች "ሰበብ" ለመፍጠር ሊከብደው አይችልም።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደሚታየው ከሆነ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች በገበያ ሥርዓት ማዕቀፍ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያሰፉ ልማታዊ መንግሥታትን ማዳከም ዋነኛው ዒላማቸው አድርገዋል። ከሶሻሊዝም መከሰር በኋላ፣ በዓለማችን ለሰው ልጆች የተሻለ ሆኖ የተገኘው ልማታዊ ሥርዓት ቢሆንም፣ ይህ ብዙኀንን ከድኅነት በማላቀቅ የሚታወቅ ሥርዓት በከባድ ጥላቻ የሚታይ ሆኗል። የኒዮ-ሊበራል ርዕዮት የማዕዘን ድንጋይ በሆነው ሌሎችን እያራቆቱ የመበልጸግ ፍልስፍና ላይ የተዋቀረው ይህ ጥላቻ የገበያ አክራሪዎች በልማታዊ መንግሥታት ላይ ለሚሰነዝሩት ጥቃት ዋነኛው መሠረት ነው። የቻይና የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦችን ከድኅነት ለማላቀቅ ስላበረከተው አስተዋጽኦ የጻፈው ከሪስ ብራማል፣ ኒዮ-ሊበራሊዝም ልማታዊ መንግሥታትን ለማዳከም ከልቡ እንደሚሠራ፡-

"የበላይ የሆነው ርዕዮት [ኒዮ-ሊበራሊዝም] የምሥራቅ እስያ የዕድገት ሞዴል ስኬታማ እንደነበረ የሚከድ ከመሆኑም በላይ፣ የምሥራቅ እስያ ኢኮኖሚዎችን የሚያመሰቃቅሉ ፖሊሲዎችን ይከተላል።...ከዚህ በመነሳት የኒዮ-ሊበራል ርዕዮት አራማጆች በ1997-98 ቀውስ በግልጽ እንደታየው የምሥራቅ እስያን

ኢኮኖሚ ለማመሰቃቀል በአጭር ታጥቀው ሠርተዋል፡፡ በእርግጥ ይህን ጣልቃ ገብነት ለቀውሱ እንደ-ብቸኛ ምክንያት መውሰድ ስህተት ነው፡፡ አገሮቹ ኢኮኖሚውን በቅጡ የመምራት ድክመት የነበረባቸው መሆኑም የራሱ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋሽንግተን ላይ የመሸጉት ተቋማት የምሥራቅ እስያውን ቀውስ በመፍጠርና በማባባስ ረገድ ትልቅ ሚና መጫወታቸው አይካድም፡፡ መጀመሪያ የምሥራቅ እስያ አገሮች የወጪ ንግዳቸውንና የውጭ ምንዛሪ ተመናቸውን ሊበራላይዝ እንዲያደርጉ አስገደዷቸው፡፡ ቀጥሎም ለዓለም አቀፍ አራጣ አበዳሪዎች ያልተገባ ጥቃት እንዲጋለጡ አደረጓቸው። በመጨረሻ ደግሞ ጃፓን የደቡብ ኮሪያን ኢኮኖሚ ከቀውስ እንዳትታደግ ከለከሉ፡፡ በምትኩ አገራቱ የአይ ኤም ኤፍን ገበያ ተኮር የኢኮኖሚ ማሻሻያ በግድ እንዲውጡ የሚያስገድድ ብድር እንዲቀርብ አደረጉ፡፡ ይህ በቅድመ ሁኔታ የተተበተበ ብድር የደቡብ ኮሪያን ኢንዱስትሪያዊ አቅም በከፊል እስከማውደም ደረሰ፡፡ በዚህ የተነሳ አልፎ አልፎ ማጋጠሙ የማይቀረውን መለስተኛ ቀውስ ወደተሟላ ቀውስ አሸጋገሩት"[108] በማለት ይገልጻል፡፡

ከዚህ የብራማል ገለጻ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች በልማታዊ መንግሥታት ላይ የሚሰነዝሩት ጥቃት ጥልቅ መሠረት ባለው የኢኮኖሚ ጥቅምና ርዕዮተ-ዓለማዊ እምነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም ተራና ቀላል ጥቃት አይደለም፡፡ አገሮች በቀውስ በሚመቱበት ጊዜ ለዝርፊያ ይመቸናል ብለው የሚያስቡት ምዕራባውያን አገሮች፣ በልማታዊ ቅኝት ተመርተው ለህዝብ መሠረተ-ሰፊ ጥቅሞችን በማጋራት መርሕ ሀብት መፍጠር የጀመሩ አገሮችን አይተው እንዳላዩ ማለፍ አይመርጡም፡፡ እ.ኤ.አ በ1997 በተከሰተው የምሥራቅ እስያ ቀውስ ላይ ኮርያዊያን ላባቸውን አንጠፍጥፈው የገነቡዋቸውንና አንጡራ ሀብታቸው የሆኑትን እንደ ሳምሰንግና ዴው የመሳሰሉ ኩባንያዎችን ለምዕራባውያን እንዲሸጡ ያስገደዱት በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ይህም ጥርሳቸውን ነቅለው ካደጉበት ሌሎቹን በማደህየት የመከበር ፍልስፍናቸው ጋር ፈጽሞ የማይነጠል መርሆዋቸው ነው፡፡ የአሜሪካንን የፊዴራል ሪዘርቭ ለበርካታ ዓመታት የመሩትን አለን ግሪንስፓንን ጨምሮ ታላላቅ የምዕራቡ ዓለም የገንዘብ ተቋማት መሪዎች አጋጣሚው ለኒዮ-ሊበራሊዝም ያተመቸ እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩ እንደነበር ናኦሚ ከሌን በመጽሐፏ ታረጋግጣለች፡፡ ናኦሚ ከሌን(2007) የግዙፉ አሜሪካዊ ድንበር ዘለል የፋይናንስ ድርጅት ሞርጋን ስታንሊ ዋና ስትራቴጂስት የሆነው ጄይ ፔሎስኪ "በበኩሌ ኩባንያዎች ሲዘጉና ንብረት በሽያጭ ሲዘዋወር ማየት እፈልጋለሁ፡፡ በተለይ ባለንብረቶቹ እንዲሸጡ ካልተገደዱ በስተቀር የንብረት ዝውውር ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ኮርፖሬሽኖች ላይ ግፊቱን ለማጠናከርና ንብረታቸውን አሳልፈው እንዲሸጡልን

ሲባል ቀውሱ እንዲባባስ መደረግ አለበት" እንዳለ ታወሳለተ። የአሜሪካ ፌዴራል ሪዘርቭ ባንክ ሊቀ-መንበር በመሆን ለ19 ዓመታት ያገለገሉት አለን ግሪንስፓንም የምሥራቅ እስያውን ቀውስ በማስመልከት "ቀውሱ በብዙ የእስያ አገሮች በመንግሥት ልማታዊ አቅጣጫ ይንቀሳቀስ የነበረውን ኢንቨስትመንት በማስወገድ እኛ አሜሪካውያን ካለን የገበያ ሥርዓት ጋር ወደሚመሳሰል ለውጥ የሚያመራ መልካም አጋጣሚ ነው።"[109] እንዳሉ ናአሚ ታረጋግጣለች።

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ ምዕራባውያኑ ለእነርሱ ልእልና የሚያመቸው ሁሌም በበታችነት የሚመጻውቱት ድሃ ህዝብና አገር ሲኖር እንደሆነ በማመን፣ ከቻሉ ልማታዊ መንግሥታት የጀመሯቸውን ውጥኖች ለመቆጣጠር፣ ይህን ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ ሥርዓቱን በመናድ ለመጠቀም ይንቀሳቀሳሉ። ለዚህም ሲሉ ከቻሉ አምስተኛ ረድፈኞችን በማዘጋጀት ቀስ በቀስ ልማታዊ መንግሥታትን ፈር እያሳቱ ለመቆጣጠር ይሞክራሉ። ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ልማታዊ መንግሥታትን በቀጥታ እስከማፍረስ የሚዘልቅ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። ይህ ትላንት የነበረ፣ ዛሬም ያለና እነዚህ ኃይሎች እስካሉ ድረስ ነገም የሚቀጥል ጉዳይ ነው።

በኢትዮጵያ በመሠረተ-ሀሳብ ደረጃ ከዓለም አቀፉ ኒዮ-ሊበራል ኃይል በተለየ የፖሊሲ አቅጣጫ የተጀመረው የለውጥ ሂደት፣ ደረጃ በደረጃ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫውን ትከከለኛነት እያረጋገጠ ሲሔድ ቆይቷል። በኒዮ-ሊበራል ምከረ-ሀሳብ ተመርተው ከተመሰቃቀሉት በርካታ ያልበለጸጉ አገሮች በተለየ ሁኔታ፣ ፈጣንና ህዝብ የሚጠቀምበት ዕድገት እንዲረጋገጥ በማስቻሉ የኢትዮጵያ የዕድገት አቅጣጫ በአፍሪካዊያን ዘንድ እንደአንድ ትከከለኛ ሞዴል መታየት ጀምሯል። በዚህ የተነሳ ዓለም አቀፉ ኒዮ-ሊበራል ኃይል እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በዚህ አፍሪካዊ ሞዴል ላይ ከባድ የማጥላላት ዘመቻ ሲያካሂድ ቆይቷል። ናአሚ ከሌን "ከእኛ የሚለዩትን ሁሉ የተሳሳቱ ብቻ ሳይሆኑ አምባገነኖች፣ ፋሽስቶች፣ ወይም ነፍሰ ገዳዮች ብሎ መፈረጅ ቀላል መስሎ ቢታየንም ይህ በከፍተኛ ጥንቃቄ መታየት የነበረበት ጉዳይ ነው" በማለት ይህን የመሰለውን ዘመቻ ትቃወማለች። ትከከለኛው መንገድ ይህ ቢሆንም ኒዮ-ሊበራሎች የራሳቸው አጀንዳ ስላላቸው ጥንቃቄውን ወደጐን ብለውና በማያገባቸው ገብተው "ሥርዓቱ አምባገነናዊ ነው" በሚል መልዕክት ሲዘምቱ ቆይተዋል። "ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" እንዲሉ በሌሎች አገሮች በተደጋጋሚ የሞከሩትን የቀለም አብዮት የዛሬ አሥር ዓመት ገደማ በኢትዮጵያም ላይ በማካሔድ ሥርዓቱን ለማንበርከክ ጥረት አድርገው ነበር። ያ ማዕበል እንደምንም ከታለፈ በኋላ ደግሞ መጀመሪያ በለሆሳስ አሁን አሁን ደግሞ በተባባሪነት ሥርዓቱን አቅጣጫ በማሳት በእቅፉ ውስጥ ሊያስገቡት ቆርጠው ተነስተዋል።

ይህ በግልጽ የሚታይ ፈተና ነው። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ ሰፊ ገበያ መሆን ከመጀመሯና በመንግሥትና በህዝብ ጥረት የሚገነቡ ግዙፍ የመሠረተ-ልማትና የምርት ተቋማት እየተስፋፉ ከመሔዳቸው ጋር ተያይዞ፣ አገሪቱ በርግጥም በቸልታ የማትታይ አገር መሆን

ጀምራለች፡፡ በአማካይ በየዓመቱ ከአሥር በመቶ በማያንስ ምጣኔ እያደገች ያለችው አገር፣ በዚሁ ከቀጠለች በጥቂት ዓመታት የአፍሪካ ግዙፍ ኢኮኖሚ መሆን ትጀምራለች፡፡ ግዙፍ ብቻ ሳትሆን በልማታዊ ፖሊሲው ምክንያት በሚሰፍነው ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የገቢ ደረጃው በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድግ በመቶ ሚሊዮን መቆጠር የጀመረ ህዝብና የሚያማልል የውስጥ ገበያ ያላት አገር ትሆናለች። በዚህ ላይ የተጀመሩ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ሲታከሉበት ኢትዮጵያ አፍን በውሃ የሚሞላ ጉጉት የምትቀሰቅስ አገር እንደምትሆን አያጠራጥርም፡፡ አገሪቱ እጅግ በአብዛኛው ከውሃ፣ በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ከነፋስና ሌሎች ታዳሽ ምንጮች በምታመርተውና ከራሷ አልፋ ምሥራቅና ሰሜን አፍሪካን በብርሃን ወደማላበስ ብቃት የምትሸጋገርበት የኢነርጅ ልማት፣ ይህን ወደግል ከማዞር ውጭ ሌላ ሕልም በሌላቸው መንግሥታትና ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ኮምፓስ ውስጥ እንድትገባ ያደርጓታል፡፡ በመዘርጋት ላይ ያለችው ባቡር፣ በዚህ ባቡር ለጓጓዝ የሚችለው እጅግ ከፍተኛ ምርት በዝርፊያና ህዝብን በማደኸየት መከበር ለሚፈልጉ ኃይሎች ጉጉት የሚቀሰቅስ ነው፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ በለማች ቁጥር በኒዮ-ሊበራል ጥቃት ሥር መውደቋ አይቀርም፡፡

ይህ ጥቃት በቀለም አብዮት መልክ ሊመጣ ይችላል፡፡ አገራቸውንና ህዝባቸውን ለመሸጥ በተዘጋጁ የውስጥ አርበኞች አማካይነትም ሊመጣ ይችላል፡፡ የውስጥ አርበኞች በሁሉም አገሮች ለሌላ አገር የሚሠሩ አሻንጉሊቶች ናቸው፡፡ ማንኛውም አገር ራሳቸውን ለአልባሌ ጥቅም የሚሸጡ የዚህ ዓይነት ሰዎች የለኝም ብሎ ሊያስብ እንደማይችለው ሁሉ፣ ኢትዮጵያም የራሷ ፈረንጅ አምላኪዎች አይኖሯትም ብሎ ማሰብም፣ መከራከርም ተጨባጭ መሠረት የለውም፡፡ ይህን የመሰለውን ሥጋት ታሳቢ በማድረግ፣ ሂደቱ በዓለማችን የበላይነት ይዞ የቆየውን ኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብና የርዕዮቱ ባለቤት የሆኑትን የምዕራባውያንን ሆነ በእነርሱ እግር ተተክቶ የበላይ የሚሆነውን አገር ከማስደሰት ቅኝት ነጻ ሆኖ፣ መላ የአገራችንን ህዝቦች መብትና ጥቅም ማዕከል በማድረግ በተቀየሰለት ትክክለኛ አቅጣጫ መጓዙን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

አክራሪነትና የመካከለኛው ምሥራቅ ግጭቶች ተፋሳሽ (Spillover) ተፅዕኖዎች፣

ኢትዮጵያን በቅርብ ርቀት ከሚፈታተኑ ችግሮች ሌላው አክራሪነትና በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚታዩ ቀውሶች ጋር ተያይዞ የሚመጣው አደጋ ነው፡፡ ይህ በአፍሪካና በአካባቢያችን የሚገኙ ብዙ አገሮችን ከጊዜ ወደጊዜ እየባሰ በሚሔድ ደረጃ በመፈታተን ላይ ያለ ችግር ሲሆን፣ በዋነኛነት ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የተቀሰቀሰና ለግምት የሚያስቸግር ጥፋት እያስከተለ የሚገኝ እጅግ ኋላቀርና አደገኛ የፖለቲካ ንቅናቄ ነው፡፡ ቀደም ሲል በተለያዩ ስሞች ብቅ ብለው ለግምት የሚያስቸግር ጥፋት ያደረሱትን አክራሪ ንቅናቄዎች ሳይጨምር፣ በዚህ ወቅት የሚገኙት እንደ ዳሚሽና (አይ ኤስ) ቦኮ ሐራም የመሳሰሉ አክራሪና ጽንፈኛ ንቅናቄዎች በማድረስ ላይ

የሚገኙት ጥፋት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ በሁሉም የሚታወቅ ነው::

ከሶሪያ እስከ ኢራቅ፣ ከሊቢያ እስከ ናይጀሪያ፣ ከፈረንሳይ እስከ እንግሊዝና አሜሪካ በዘለቁ የጥፋት እርምጃዎች የሚታወቁት እነዚህ አክራሪና ጽንፈኛ ንቅናቄዎች፣ ሰዎችን "በሃይማኖት ሽፋን በመቅረብ ማማለልና ለምትፈልገው ዓላማ ማስፈጸሚያ ማድረግ ይቻላል" ብለው ያምናሉ። ለዚህ ሲሉም ሃይማኖትን በሽፋንነት ይጠቀማሉ:: እነዚህ ኃይሎች የሚያራምዱት አክራሪነትና ጽንፈኝነት ከትክክለኛው ሃይማኖታዊ አምልኮ ያፈነገጡ ቢሆኑም፣ እንደአመቸነቱ ራሳቸውን በክርስትና ወይም በእስልምና እምነት ለመሸፈን ይሞክራሉ:: ክርስትና ባለበትና በእርሱም መሸፈን አዋጭ ይሆናል ብለው ሲገምቱ በክርስትና እምነት ስም ተሸፋፍነው እየቀረቡ ዜጐችን በማሳሳት ተክታዮች ለማድረግና ዓላማቸውን ለማስፈጸም ይጣጣራሉ:: በእስልምና ስም መንቀሳቀስ የሚያዋጣ ነው ብለው የሚያምኑትም እስልምናን በሽፋንነት በመጠቀም የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማራመድ ጥረት ያደርጋሉ:: ክርስትና ወይም እስልምና አናሳና ተጨቋኝ እምነት በሆኑበት አካባቢም ሆነ በአኩልነት በሚታዩበት አገር በሃይማኖት በማስታከክ ህዝብን የጥፋት ዓላማ ማስፈጸሚያ ለማድረግ ይሠራሉ:: ይህ ቦታና ጊዜ ሳይለይ በሁሉም ሃይማኖቶች ሽፋን ሲራመድ የሚታይ ዝንባሌ ነው:: ይህም ሆኖ ንቅናቄዎቹ በሃይማኖት ካባ ቢሸፈኑም አንዳችም ሃይማኖታዊ ይዘት የላቸውም:: አክራሪነትም ሆነ ጽንፈኝነት የሃይማኖት ይዘት የሌላቸው፣ ነገር ግን ሃይማኖትን መጠጊያ ለማድረግና ፖለቲካዊ ይዘት የሌላቸውን እምነቶች ለፖለቲካ ዓላማ ተገዥና መሣሪያ ለማድረግ የሚሞክሩ ኢደገኛ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ናቸው::

ይህን መሰሉ አስተሳሰብ አብዛኛውን ጊዜ ከተለያዩ ፍላጐቶች ይነሳል:: በዓለማችን "ለተገፉ ህዝቦች መብት እንታገላለን" የሚሉ አንዳንድ ኃይሎችም ሆኑ፣ የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘም የሚሹ ገዥ መደቦች እንደአመቸነቱ አክራሪነትን መቀስቀስና የዓላማቸው ማስፈጸሚያ ማድረጋቸው የተለመደ ነው:: በተጨባጭ እንደሚታየው አንዳንድ ጨቋኝ መንግሥታት፣ የህዝቦችን ትግል ፈር በማሳት የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘም ሲሉ አክራሪነትን ስፖንሰር በማድረግ ለማስፋፋት ጥረት ያደርጋሉ:: በአፍጋኒስታን ሙጃሂዲኖችና ታሊባኖች፣ አሁን ደግሞ አይሲስ የተፈጠረና የተደገፈበት ሂደት ይህን የመሰለ ነው:: እዚህ በቅርባችን መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚገኙ በርከት ያሉ በነዳጅ ሀብት የታደሉ መንግሥታት፣ ከዚህ ሽያጭ በሚያገኙት ሀብት ማንንም በገንዘብ ለማማለል እንደሚችሉ በመተማመን አክራሪነትን ስፖንሰር ያደረጋሉ:: በክርስትና ስም ተሸፍነው በገንዘብ ኃይል ተክታዮች ለማፍራት የሚዘምቱ አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም አገሮችና ተቋማትም በዚሁ ተመሳሳይ ቅኝት ይጓዛሉ:: ይህ በዓለማችን አገሮችን በማተራመስ ላይ የሚገኘውን አደገኛና ወቅታዊ ፈተና ዋነኛ መነሻ መሠረት ያሳያል::

ከዚህ በተወሰነ ደረጃ ለየት የሚል መልክና አነሳስ ኖሮት ነገር ግን ከየአካባቢው

ኋላቀር አገዛዞች ጋር እጅና ጓንት ሆኖ የሚራመድና የህዝቦችን ፍትሃዊ ጥያቄ ተጠልሎ የሚስፋፋ አክራሪነትም አለ። እነዚህ "ከጭቆና ነጻ ለማውጣት በመሻት የምንፋለም ነን" ማለት የሚቀናቸው ኃይሎች ቢሆኑም፣ የሕብረተሰብን ችግሮች በትክክል ለመተንተን፣ ለመገንዘብና ትክክለኛ መፍትሔ መስጠት ሲያቅታቸው አክራሪነትን እንደ አማራጭ መፍትሔ የሚያራምዱ ናቸው። በዚህ መልክ የሚቀነቀነው አክራሪነት አብዛኛውን ጊዜ የሚነሳው ሕብረተሰብን የሚያስጨንቁ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ችግሮች ሲበራከቱና በትክክል ሳይፈቱ ሲቀሩ ነው።

የኢኮኖሚ ልማት ዕድል ጠፍቶ አገሮች በድኅነትና በኋላቀርነት የሚሰቃዩ ሲሆኑ፣ ወይም ደግሞ ዕድገትም ኖሮ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ባለመስፈኑ፣ ህዝቦች ምድራዊ ሲዖል ውስጥ ሲኖሩ፣ ወይም ደግሞ አንድ የሕብረተረሰብ ክፍል በሌላው ላይ ክፍተኛ በደል የሚያደርስበት ሁኔታ ሲበራከት የሚፈጠረው ተስፋ መቁረጥ ለአክራሪነት እጅግ የተመቸ ሁኔታ ይፈጥራል። በቅኝ ገዥዎች ዘግናኝ አመራር የሚሰቃዩ ህዝቦችም ይህን ለማስወገድ የሚያስችል ትክክለኛ አቅጣጫ ሳያገኙ ሲቀሩ ለአክራሪነት የተመቸ ፖለቲካዊ ሁኔታ ይፈጠራል። አንድ ብሔር በሌሎች ላይ የበላይ ሲሆን፣ ወደትክክለኛ ጐዳና የሚመራቸው ብቁ ድርጅት ያላገኙ ዜጐች፣ ከዚህ ዓይነቱ ግፍ ለመላቀቅ በመሻት የብሔረተኝነትን ጽንፍ ይይዛሉ። በአንድ ሃይማኖት የበላይነት ምክንያት የሃይማኖት አድሎ ሲበራከትም ሃይማኖታዊ ጽንፈኝነት አማራጭ ሆኖ ብቅ ይላል። በተለይ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ንቃታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ማኅበረሰቦች ሌሎች ወንድምና እህቶቻቸውን፣ ከዚያም አልፎ በአጠቃላይ የሰውን ልጅ የችግራቸው ሁሉ ምንጭ አድርገው በመመልከት የቅሬታና ጥላቻ ዝንባሌ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ሰዎች የሚሰማቸውን ቁጣ አንዱ በሌላው ላይ እጁን በመሰንዘር ማብረድ በሚሹበት ይህን በመሰለ ወቅት ሐሳዊ መሲሕች ዓላማቸውን ለማሳካት እጅግ የተመቸ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። በሕብረተሰብ ውስጥ የተንሰራፉ ችግሮችን መሠረታዊ ጠንቆች ከማስወገድ ይልቅ ሰዎችን በሃይማኖታቸው፣ በብሔራቸው ወይም በዘራቸው ከፋፍሎ በማናቆር፣ የአክራሪነትና ጽንፈኝነትን ግቦች ማሳካትን የትግል ስልት ያደርጋሉ። ይህ አክራሪነት በተንሰራፋባቸው አገሮች ሁሉ የታየ ክስተት ነው።

አክራሪነት ይህን የመሰለ አደገኛ ዝንባሌ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍጥነትና በሚያስደነግጥ ስፋት የሚከሰትና የሚያድገው ደግሞ ከሞላ ጐደል የከሸፈ መንግሥት ባለባቸው፣ ወይም ሕብረተሰብ በተስፋ መቁረጥና ጨለምተኝነት በተሞላባቸው አገሮች ነው። ፍልስጥኤም፣ ሶማሊያ፣ አፍጋኒስታን፣ ፖኪስታን አሁን ደግሞ ሊቢያና ኢራቅ እንዲሁም ሶሪያና የመንን የመሳሰሉ አገሮች ሁሉ በዚህ ማዕቀፍ የሚታዩ ናቸው። በእነዚህ አገሮች በአንዳንዶቹ መንግሥታት ከስመዋል። በአንዳንዶቹ ደግሞ ቢኖሩም ሕልውናቸው ከመክሰም ብዙ ያልራቀ ነው። በመሆኑም በክሽፉትም ሆነ ለዚህ በጣም በቀረቡት አገሮች አክራሪነት ሥር ሲሰድ

ይታያል፡፡ ሶማሊያ፣ ኤርትራ አሁን ደግሞ ደቡብ ሱዳን በአካባቢያችን በርከት ያሉ የከሸፉና በመከሸፍ ላይ ያሉ መንግሥታት እንደሚገኙ ይጠቁማሉ፡፡ በነዳጅ ሀብት የበለጸገው ነገር ግን ደግሞ ለፍትሃዊ የሀብት ከፍፍል ያልታደለው መካከለኛው ምሥራቅ እዚሁ ከደጃፋችን ላይ መሆኑም ከአከራሪነት ጋር የተያያዘው ሌላ የሥጋት ምንጭ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ዙሪያ ትንሽ የማይባሉ የከሸፉ ወይም በዚህ ሂደት ውስጥ የገቡ መንግሥታት ባሉበት በዚህ ዘመን፣ ይህ ለአገሪቱ ትንሽ የማይባል የሥጋት ምንጭ ነው፡፡

የምዕራቡም ዓለም የራሱን አከራሪነት በከርስትና እምነት ሽፋን ለማስፋፋት የሚጣጣርና የህዝቦችን ትግል የሚያዳክም መሆኑ በብዙ አገሮች የታየ ነው፡፡ በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ አንዳንድ ተቋማትና የሕብረተሰብ ከፍሎች፣ ትንሽ በማይባል አጋጣሚ ከመካከለኛው ምሥራቅ ስለተፈጠሩ ወይም የእስልምና እምነትን ስለተከተሉ ብቻ የዚህ አካባቢ ሰዎችን ሁሉ እንደአሸባሪ በመመልከት ሁሌም ተጠርጣሪ ሲያደርጉ ማየት የተለመደ ነው። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በቅርቡ ሙስሊም የሚበዛባቸውን አገሮች ነጥለው የጉዞ ማዕቀብ የጣሉባቸው መሆኑ ይህን ያሳያል። ከዚህም አልፎ ምዕራባውያን አንዳንድ የእምነት ተቋሞቻቸውን የኒዮ-ሊበራል እምነት መሲሆች በማድረግ ያሰማሩዋቸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የእነርሱን የበላይነት የሚያረጋግጥ እስከሆነ ድረስ አከራሪና ጽንፈኛ እንቅስቃሴዎችን ከሥልጠና እስከትጥቅ፣ ከገንዘብ እስከጦር መሣሪያና ምከር በሚደርስ ድጋፍ ያንቀሳቅሰሳሉ፡፡ የኔቶ ቃል ኪዳን አገሮችና ራሱ ወታደራዊ ተቋሙ የመካከለኛ ምሥራቅ አሸባሪዎችን በተጨባጭ ሲደግፉ መኖራቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። ከሶቭዬት ሕብረት ጋር የነበራቸውን ፉክክር መነሻ በማድረግ ለሙጃሂዲን፣ ታሊባንና፣ ለቸችኒያ አማጽያን መጠነ ሰፊ ድጋፍ ሰጥተዋል። አሁን ደግሞ ለአይሲስ መነሳትና መፈርጠም ያበረከቱት ጉልህ አስተዋጽዖ ይህን የሚመስከር ነው፡፡ ዛሬ አከራሪነትና አሸባሪነት በተናጠል አገሮች ሳይወሰን፣ ድንበር ተሻግሮ ዓለምን ሲያተራምስ የምንመለከተው የእነዚህ መንስዔዎች ድምር ውጤት ነው፡፡

በአንድ በኩል በውስጣዊ ተጋላጭነት፣ በሌላ በኩል በውጭ ኃይሎች ገፋፊነት የሚዛመት ይህን የመሰለው አከራሪነትና ጽንፈኝነት ለኢትዮጵያ ከፍተኛ የሥጋት ምንጭ የሚሆንበት ሌላም ምክንያት አለ፡፡ ይህም አንድንድ የመካከለኛው ምሥራቅም ሆኑ የምዕራቡ ዓለም አገሮች ኢትዮጵያን ከሃይማኖት አኳያ የሚመለከቱበት ከእኛ በመሠረቱ የተለየ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው። እነዚህ አገሮችና ተቋማት ኢትዮጵያ ቢያንስ ከሳውዲ አረቢያ እኩል እስልምናን የተቀበለችና ከእርሷም የሚበዛ ሙስሊም ማኅበረሰብ ያላት መሆኑን ሽፍነው “የከርስቲያን ደሴት” አስመስለው ይመለከቷታል፡፡ በተጨማሪም ሁለቱም “ኢትዮጵያ እስልምና ወደደቡባዊ አፍሪካ እንዳይስፋፋ ገትታ የያዘች አገር ነች፡፡” ብለው ያምናሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ምዕራባውያኑ ኢትዮጵያ በፀረ-እስልምና አቅጣጫ እንድትጠናከር፣ የመካከለኛው ምሥራቆቹ ደግሞ እስልምና

ወደ ደቡባዊ አፍሪካ አቅጣጫ እንዲስፋፋ ሲባል እንድትዳከም ይፈልጋሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ሁለቱም የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያን የሃይማኖታዊ ፍልሚያ አውድማ ማድረግ ይሻሉ ማለት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያውያን የጀመርነውን የሃይማኖት እኩልነትና መቻቻል በሕገ-መንግሥታችን መሠረት አጠናክረን፣ አንድነታችንና ሰላማችንን ዘላቂ ካላደረግን በስተቀር፣ አገራችን በዚህ መልክ ከውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ጋር ተያይዞ ለሚቀሰቀስ አስከፊ የእክራሪነት ተፅዕኖና አደጋ አትጋለጥም ብሎ መዝናናት አይቻልም፡፡

ኢትዮጵያ ይህን የመሰለው ድንበር ተሻጋሪ አደጋ ከምንም ነገር በፊት በራሷ ውስጣዊ ተጋላጭነት ላይ እንደሚመሠረት ተገንዝባ ይህንኑ ለመቅረፍ ስትታገል ቆይታለች፡፡ በሃይማኖት ሰበብም ይሁን በሌላ በማንኛውም ሽፋን የሚቀሰቀስ አክራሪነት፣ በኢትዮጵያ ላይ ጐጅ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችለው ድኅነትና ኋላቀርነት ሲንሰራፋ ነው፡፡ ይህን መሠረታዊ ሐቅ በመገንዘብ ከምንም ነገር በላይ ልማትና ዴሞክራሲን ለማስፈንና ይህን ለማዳበር ጥረት አድርጋለች፡፡ ልማቱ በዜጐች ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት በማመን ልማታዊ ሥርዓት ስትገነባ ቆይታለች፡፡ በተጨባጭ ደግሞ ከፍተኛ ተስፋ የቀሰቀሰ ለውጥና ዕድገት መመዝገብ ጀምሯል፡፡ ይህም በመሆኑ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሽንቁሩ ጫፍ አሻግረው ደማቅ ብርሃን መመልከት የጀመሩ ባለተስፋ ህዝብ ሆነዋል፡፡ ሰርቶ መለወጥ እንደሚችልና እንደሚገባው የሚያምን ትጉህ ሕብረተሰብ መገንባት ጀምሯል፡፡ ይህ ሁኔታ ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ አክራሪነትን የማይሸከም ሕብረተሰብ የተፈጠረባት አገር እንድትሆን ኤድርጓታል፡፡ በአምስተኛው አገራዊ ምርጫ ሕብረተሰቡ በሃይማኖት መልክ የሚገለጽን አክራሪነት ቀርቶ ሕጋዊነትን ተላብሶ የሚራመድን የፖለቲካ ጽንፈኝነት እንኳ ለመሸከም ትዕግሥቱ እንደሌለው በድምፁ ማረጋገጡ ለዚህ ዓይነተኛ ማስረጃ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ አሁንም ከአክራሪነት አደጋዎች ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆነችበት ደረጃ ላይ ደርሳለች ማለት አይቻልም፡፡ በአንድ በኩል ዛሬም በአጠቃላይ ሕብረተሰቡን በተለይ ደግሞ ወጣቱን የሚያስመርሩ ቀላል የማይባሉ ውስጣዊ ችግሮች አሉባት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከባድ ተስፋ መቁረጥ በሰፈነበት የአፍሪካ ቀንድ ውስጥ የምትገኝ አገር ነች፡፡ የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ ተጐራባች አገር መሆኗም ሆነ ምዕራባውያንም በራሳቸው አጀንዳ የሚፈጥሩት ችግር አደጋው የሩቅ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭና የቅርብ ወቅታዊ አደጋ እንዲሆንባት ያደርጋል፡፡ ይህን አደጋ በቅጡ ተገንዝቦ መፍታት ካልተቻለ፣ አገሪቱ በዚህ ምክንያት ልትከፍለው የምትችለው ዋጋ ትንሽ ይሆናል ተብሎ አይገመትም፡፡

ይህን የመሰለውን አደጋ በብቃት ለመመከት ህዝባዊና ሕገ-መንግሥታዊ አቅጣጫዎች ማጠናከር ይገባል፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የሃይማኖትና የብሔር እኩልነትን ለማጠናከር የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲጐለብቱ፣ በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት መስክ የተጀመረው ፍትሃዊና

የአሳታፊ ተጠቃሚነት መርሕ ይበልጥ እንዲጠናከር ማድረግና ዜጐች ሁሉ ለማንኛውንም ዓይነት ችግራቸው በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ አስተማማኝ መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የመልካም አስተዳደርና ተዛማጅ ችግሮች፣ ጅምሩን የልማትና መልካም አስተዳደር ሂደት ከማኮላሸት አኳያ የሚጫወቱትን እጅግ አደገኛ ሚና በመገንዘብ፣ ይህን ድክመት ለመቅረፍ በጥብቅ መሥራት ይጠይቃል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በብሔርና በሃይማኖት በመሸፈን ሕብረተሰብን መቆጣጠር የሚሻውን ኪራይ ሰብሳቢነት መታገልና ማዳከም የግድ ይላል፡፡ የልማታዊ መንግሥቱ ከሃይማኖት ገለልተኛ የመሆኑን (Secular) ባሕርይ፣ ከማንኛውም ውስጣዊና ውጫዊ የተሳሳቱ ተፅዕኖዎች ጠብቆ ማዳበርና የተጀመረውን ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ጉዞ አጠናክሮ መቀጠል የግድ ይላል፡፡ ውስጣዊ ተጋላጭነትን የሚቀንሱ መፍትሔዎች በተሳካ አኳኋን ከተፈጸሙና አገሪቱ ፍትሃዊ የልማት ሂደትን ለማጠናከር ከቻለች፣ ማንኛውንም አክራሪነት በተባበረ የህዝቦቿ ጥረት ለመመከት የማትቸገር ትሆናለች፡፡ ከውጭ በኩል የተደቀኑትን አደጋዎችም በብቃት ለመመከትም ትችላለች። ይህ አገራችን እስካሁን ከተጓዘችበት ስኬታማ የለውጥ ሂደት በመነሳት ሊወሰድ የሚችልና የሚገባው መሠረታዊ ድምዳሜ ነው፡፡

ከአፍሪካ ቀንድ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅና ከሰሜን አፍሪካ በኩል የሚያንጥብበውን የአክራሪነት አደጋ በብቃት ለመመከት በወሳኝነት በራሳችን ውስጣዊ ሁኔታ ላይ ከማትኮር በተጨማሪ ለሪጅኑ ዘላቂ ሰላም አበክሮና ተባብሮ መሥራት ይገባል፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት አይሲስ በኢትዮጵያዊያን ወገኖች ላይ ያካሔደው የሚዘገንን ጥቃት፣ በጣም ብዙ ዜጐቿ በእነዚህ አገሮች ለሚገኙባት ኢትዮጵያ ከአክራሪነት ጋር የተያያዘ አደጋ ተቃሎ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ በመነሳት የሚዘመተው አክራሪነት በከባድ የገንዘብ ድጋፍ የተሸኘ ነው፡፡ በሌላ በኩል "ከመካከለኛው ምሥራቅ የሚስፋፋው አክራሪነት ያሳስበናል" በሚል ሽፋን ክበለጸገው ዓለም የሚመጣው ተመሳሳይ ዘመቻም እንደዚሁ፡፡ ስለዚህም ፍላጐታቸውን በኢትዮጵያ ላይ ለመጫንና አገሪቱ በራሳቸው የሃይማኖት ጦርነት አጀንዳ ውስጥ እንድትሸከረከር ከሚፈልጉ ኃይሎች አገራችንን መጠበቅ ይገባል፡፡

በኪራይ ሰብሳቢነት ምክንያት ሊፈጸም የሚችልን አድሎ ተከትሎ አክራሪነት በኢትዮጵያ ከባድ ምስቅልቅል ሊፈጥር የሚችልና በትንሽ በትንሹም መፍጠር የጀመረ አደጋ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን አደጋ በትኩረት አይቶ መታገልና ማስተካከል ለነገ የማይባል ጉዳይ ይሆናል፡፡ ጽንፈኝነት በማንኛውም መለኪያ ተያይዞ ከመጥፋት ውጭ ሌላ ውጤት እንደሌለው በመገንዘብ፣ ይህን ከሁሉም አቅጣጫ የሚመጣ ተጨባጭና ወቅታዊ አደጋ በጽናትና በሕብረት መፋለም ይገባል፡፡ ይህም በመሆኑ ዜጐችን በገንዘብ በማባበል እንዲስፋፉ የሚፈለጉ አስተሳሰብና ዝንባሌዎችን መለየትና እነዚህን በብቃት ታግሎ መመከት ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ አሥራ አንድ፣

ኢትዮጵያና በእጇ የገቡ መልካም ዕድሎች፣

"የኢህአዴግ ታሪክ በጅምር ላይ ያለ ግንባታ ነው ማለት ይቻላል። አጀማመሩ እጅግ ያማረ ሕንጻ ነው። መሐል ላይ ግንባታው ተሰናክሎ የተበላሻሸበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም፣ የተበላሸው ተቃንቶ ውብ ይዘቱን ጠብቄ በመገንባት ላይ ያለ ነው። እንደ አጀማመሩ ከዘለቀ የዓለም ድንቅ ቅርሶች እየተባሉ እንደሚወሰዱ ሕንጻዎች ሁሉ ድንቅ ሥራ ሆኖ በታሪክ ይኖራል። መሐል ላይ ከተሰናከለ ከፍተኛ ብርሃን ፈንጥቀው፣ ተሰፋ ጭረው ብልጭ ድርግም እንዳሉ አጅግ ብዙ የታሪክ ከስተቶች ሁሉ አንድ ተጨማሪ ትራጀዲ ሆኖ ያልፋል። ለዚህ ነው የኢህአዴግ ታሪክ ገና እየተጻፈ ነው የምንለው። ቀጣይ የኢህአዴግ ትውልዶች ከድርጅታቸው ልምድ በመማር ግንባታውን ያጠናቅቃሉ ተብሎ ይታመናል። ኢህአዴግ ድርግም ብሎ ለመጥፋት የታጨ ድርጅት እንዳልሆነ የእስካሁኑ ታሪክ ያመላክታልና የመጨረሻው ድንቅ ታሪኩ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንደሚጻፍ ብናምን ከንቱ እምነትና ተሰፋ አይሆንብንም።"[110]

መለስ ዜናዊ

ከፍ ሲል የተመላከቱት ፈተናዎች፣ አዲሲቱ ኢትዮጵያ የያዘችውን የመካከለኛ ገቢ፣ ከዚያም አልፎ የከፍተኛ ገቢ ሕብረተሰብ የመገንባት ራዕይ በማሳካት ሂደት ውስጥ ከፊቷ የተደቀኑ ፈተናዎች ናቸው:: የፈተናዎቹ ብዛትና ውስብስብነት በጥሬው ሲታይ መውጫ የሌለው ይመስላል:: ነገር ግን አገሪቱ ማንኛውንም ችግር ተጋፍጦ የመፍታት ባሕል በነበረው አመራር በየመድረኩ ያጋጠሟትን ችግሮች ስትፈታ ቆይታለች:: በተጨማሪም ችግሮቹ ኢትዮጵያ በጣም የተሻለ መሠረት ባነጠፈችበት፣ ራሳቸው ችግሮቹም ቢሆኑ ብቁና ጽናት ያለው አመራር እስካለ ድረስ ሊፈቱ የሚገኙባት አገር ነች:: ኢህአዴግና መንግሥት እስካሁን ባስመዘገቧቸውም ሆነ በየመድረኩ በሚገኙ ድሎች ሳይኩራሩ፣ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ሁሉ አሳንሰው በመመልከት ሳያጣጥሉ፣ በትክክለኛው መፍትሔ ዙሪያ መላውን ህዝብ በማሳተፍ ለማታገል ከቻሉ በእርግጥም እነዚህ የማይታለፉ ችግሮች አይደሉም:: መሪዎቹ ዕድገትን ከሚገታ ከማንኛውም ዓይነት ግብዝ አስተሳሰብ ርቀው፣ ይህችን ታላቅ አገርና ይህን ታላቅ ህዝብ ለመምራት የሚያስፈልገውን ብቃት በትሁትነትና በትጋት መገንባት ከቻሉ የሚታለፉ ችግሮች ናቸው። የኢህአዴግ መለያ የነበረውን ጠንካራ ዲስፒሊንና ህዝባዊ ወገናዊነት ከማንኛውም

ዓይነት ጉድፍ ጠብቀው ሊያዳብሩት ከቻሉ፣ እነዚህን ፈተናዎች መሻገር በእርግጥም የጊዜ ጉዳይ ብቻ ይሆናል:: መሠረታዊው ጉዳይ ራስን እንደሰጐን አሸዋ ውስጥ ሳይቀብሩ መራሩን እውነትና የአገራችን ዕድል በተጀመረው መልካም አቅጣጫ እንዳይጓዝ ሊያደርጉ የሚችሉትን እነዚህን ፈተናዎች፣ በድፍረት ተመልክቶ በጽናት መፍታትና መልካም ዕድሎችን ደግሞ በብስለት መጠቀም ነው:: በተለይ ደግሞ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መልካም ዕድሎች በትክክል ጥቅም ላይ ማዋል የተጀመረው ለውጥ መሠረት በማድረግ፣ ወደታለመው ደረጃ እንዲደርስ ለማድረግ ያስችላል::

የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን በማሳካት የተፈጠረው መልካም ዕድል፣

በብዙዎቹ የአውሮፓ አገሮች ከገበያ ሥርዓት መስፋፋት ጋር ተያይዞ መሠረተ-ሰፊ የኢንዱስትሪ ልማት መካሔዱ በታሪክ የተመዘገበ እውነታ ነው:: አሁን አሁን ደግሞ ምዕራባውያኑ ከኢንዱስትሪም አልፈው ድኅረ-ኢንዱስትሪያዊ (Post Industrial) ማኅበረሰብ ወደሚሉት ደረጃ በመሸጋገር ላይ እንደሆኑ እየገለፁ ይገኛሉ:: በበለጸገው ዓለም የኢንዱስትሪ ልማት የተስፋፋበትና ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ይህ እውነታ ግን ሂደት እንጂ በአንዴ ተገጣጥሞ ያለቀ ውጤት አልነበረም:: ይህ ሂደት በአውሮፓ ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊትና በኋላ ከሞላ ጐደል ከሦስት ምእተ ዓመታት ያላነሰ ጊዜ ፈጅቶ የተሳካ ነበር:: ኢንዱስትሪያዊ ልማትን ዘግይተው ለማሳካት በቻሉ የምሥራቅ እስያ አገሮች ደግሞ ከአምሳ እስከ ስድሣ ዓመታት ወስዶ የተጠናቀቀ ነበር:: ስለዚህም በኢንዱስትሪ የበለጸገ ደረጃ ላይ መድረስ በእርግጥም ሂደት እንጂ አንድ ተናጠል ፍጻሜ አልነበረም፣ ዛሬም አይደለም:: በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ መውደቅና መነሳት የሚያጋጥም ከመሆኑ በተጨማሪ በብዙ አገሮች እንደታየው የመከሸፍ ዕድልም ሰፊ ነው::

አንድን በግብርና ላይ የተመሠረተ አገር በኢንዱስትሪ ወደበለጸገ አገር ለማሸጋገር በቂ የሆነ መነሻ ካፒታል መያዝ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው። ይህም በፖለቲካ ኢኮኖሚ ጽንሰ-ሀሳብ መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት (Primitive capital Accumulation) የሚባለውን ሂደት በተሳካ ሁኔታ በመፈጸም የሚሟላ ነው። በመሆኑም የአንድ አገር ዘላቂና ከፍተኛ ልማት መጀመሩም ሆነ ቀጣይነቱ ከሚወሰንባቸው ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ስኬታማ አፈጻጸም ነው:: ለኢንዱስትሪ ልማት የሚፈለገው ካፒታል ከአንድ ወይም በርከት ያሉ ምንጮች ፈልቆ በሂደት እየተበራከተ እንዲሔድ ማድረግ ካልተቻለና ሰፊ የካፒታል ይዞታ ካልተፈጠረ በስተቀር የኢንዱስትሪ ልማት እውን ይሆናል ተብሎ አይታሰብም:: ይህም ሆኖ ካፒታሉ ስለተያዘ ወይም ለግምት የሚያስቸግር የገንዘብ አቅም ስለተያዘ ብቻ ደግሞ በኢንዱስትሪ መልማት ይቻላል ማለት አይደለም:: በኢንዱስትሪ

የመበልጸግ ጉዳይ የቴክኖሎጅያዊ አቅም ግንባታ፣ የሰብዓዊ ኃይልና የመሠረተ-ልማት አቅም ግንባታ መኖሩንም የግድ ይላል:: ነዳጅ ሸጠው፣ ብዙ ዶላር ሰብስበው በኢንዱስትሪ ወደኋላ የቀሩት የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ካፒታል ስለተያዘ ብቻ በልማት ዳብሮ ለበለጸገ ሕብረተሰብ መብቃት እንደማይቻል የሚያረጋግጡ ናቸው:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በኢንዱስትሪ ለመልማት በአንድ ወይ በሌላ መንገድ ካፒታል ማከማቸት ቁልፍና የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ግን ሊሰመርበት ይገባል::

በኢንዱስትሪ ልማት የበለጸገ አገር ለመሆን ከሁሉ በፊት የማኑፋክቸሪንግ ተቋማት በአገር ምድሩ እንደእንጉዳይ እንዲፈሉ ማድረግን ይጠይቃል:: በቁጥር ጥቂትና እዚህም እዚያም የተንጠባጠቡ ፋብሪካዎች ስላሉ ብቻ አንድ አገር የተሳካ የኢንዱስትሪ ልማት አካሂዳለች ሊባል አይችልም:: ወይም ደግሞ አንዲት አገር በርካታ ቀላል ኢንዱስትሪዎችን እየገዛች ስለተከለችና የፍጆታ ዕቃዎችን ስላመረተች በኢንዱስትሪ ልማት ተሳክቶላታል ልትባል አትችልም:: በኢንዱስትሪ የበለጸገ አገር ለመሆን መሠረተ-ሰፊ የኢንዱስትሪ ልማት መኖሩ የግድ ነው:: የፋብሪካ ምርቶችን ከሞላ ጐደል ለራስ አገር በሚያስፈልገው ደረጃና ከተቻለም ለሌሎች አገሮች ከማቅረብ ጀምሮ፣ ራሱን ከባዱን ኢንዱስትሪ ደረጃ በደረጃ ወደማምረት እስከመሸጋገር በሚደርስ ብቃት ማምረት ይጠይቃል:: አነስተኛና ጥቃቅን፣ ቀላልና መካከለኛ እንዲሁም ከባድ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፋትን የግድ ይላል:: በፍጆታ ዕቃዎች ብቻ ሳይወሰኑ ከጥቃቅን ጀምሮ ግዙፍ የማምረቻ መሣሪያዎችን ማምረትም የዚሁ ኢንዱስትሪያዊ ልማት የማይነጠል ገጽታ ነው::

ምንም እንኳ በከባድ ሁኔታ በተሳሰረው ዓለም አንዲት አገር የሚያስፈልጋትን ነገር በሙሉ ካላመረተች የበለጸገ ሕብረተሰብ አልገነባችም ባይባልም፣ በወሳኝነት የሚያስፈልጓትን ነገሮች ሁሉ የማምረት ብቃት ካልገነባች ደግሞ በኢንዱስትሪ የለማች አገር ልትባል አትችልም:: ብቃቱን ገንብታ በአዋጭነት መርሕና በልዩ ልዩ ሚዛናዊ የኢኮኖሚ እሳቤዎች /Rationals/ በመገፋፋት አንዳንድ አስፈላጊ ምርቶችን ከሌሎች አገሮች ልትገዛ ትችላለች:: ይህም ሆኖ ከሌላ ስለገዛች በኢንዱስትሪ አልለማችም እንደማትባለው ሁሉ፣ ራሷን ችላ ሁሉን ነገር ማምረት ስለምትችል ደግሞ ከሌላ መግዛት አያስፈልጋትም ሊባል አይችልም::

ከዚህ በመነሳት በኢንዱስትሪ የበለጸገ አገር ከሁሉ በፊት መሠረተ-ሰፊ የማኑፋክቸሪንግ አቅም የገነባ ማለት በመሆኑ ላይ መግባባት ያሻል:: የማኑፋክቸሪንግ ተቋማትን የማስፋፋት ጉዳይ አንድም ፋብሪካዎችን ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ማምረት ወይም ደግሞ በከፊል ማምረትና በከፊል መግዛት የሚጠይቅ ሥራ ነው:: በመሆኑም ፋብሪካዎችን በአገር ውስጥ በማምረትም ሆነ በከፊል ከውጭ በመግዛት ኢንዱስትሪያላይዜሽንን እውን ማድረግ ሰፊ የገንዘብ አቅም ይጠይቃል:: ፋብሪካን በራስ አገር ለማምረት በአንድ በኩል የቴክኖሎጂ

አቅም ግንባታና ለዚህም የሚበጅ ተሞክሮ፣ ሥርዓተ ሥልጠና ማዘጋጀት ይጠይቃል። በሌላ በኩል ደግሞ ለግብዓትና የማምረቻ መሣሪያዎች መግዣ የሚሆን መጠነ-ሰፊ ካፒታል ማሟላትን የግድ ይላል። በከፊል ፋብሪካዎቹን ከውጭ ገዝቶ ማቅረብም ቢሆን ብዙ ገንዘብ በተለይ ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ይፈልጋል። በአጭሩ በአንድ አገር ውስጥ ሰፋ ባለ መጠን ተከማችቶ የሚገኝና በየጊዜውም መጠኑ እየጨመረ የሚሔድ ካፒታል ካልተያዘ በስተቀር በኢንዱስትሪ የበለጸገ አገር ለመገንባት አይቻልም። ከፍ ያለ የካፒታል ክምችት በሌለበት የኢንዱስትሪ ልማት በወጉ አይስፋፋምና።

አውሮፖውያን ወደ ኢንዱስትሪ ልማት ለማምራት የቻሉት ከሁሉ በፊት የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም በመቻላቸው ነው። ካርል ማርክስ "የመጀመሪያ ካፒታል ከምችት የካፒታሊሥታዊ የአመራረት ሥልት ውጤት ሳይሆን የመነሻ ነጥብ ነው።"[111] እንደሚለው በእርግጥም ሥርዓቱ አሐዱ ብሎ መገንባት የሚጀምረው ካፒታል በልዩ ልዩ መልኮችና መንገዶች እየተፈጠረና እየተሰባሰበ የኢንዱስትሪ ልማት መሣሪያ ሆኖ ሲያገለግል ነው። አንዳንድ ተንታኞች የሚያቀርቡትን የባሕር ላይ ወንብድና ጨምሮ፣ የቅኝ ግዛቶችን አንጡራ ሀብት መዝረፍ፣ እንዲሁም ያልተመጣጠነ ንግድ ለአውሮፓውያኑ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋቸዋል። ለምሣሌ እንግሊዞች ለኢንዱስትሪያዊ ልማት መነሻ ሆኖ ያገለገላቸውን የኢንቨስትመንት ካፒታል ያከማቹት በቅኝ ከያዟቸው ስፓኒሽ አሜሪካዎች የብር ማዕድናት እስከሩቅ ምሥራቅ የአጥየምና የሻይ ንግዶች ባካሔዱት ዝርፊያ (Plunder) ነው። በአገሮች ውስጥና በልዩ ልዩ አገሮች መካከል የተዘረጋው የብሔራዊ እዳና የብድር ሥርዓትም (National debt and the Credit System) የካፒታል ክምችት የተካሔደባቸው መንገዶች ነበሩ። ከጃፓን እስከቻይና ድረስ ዘግይተው በለሙ አገሮች ደግሞ በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳና ጉልበት የተፈጠረው አዲስ ሀብት የካፒታል ክምችትና የካፒታሊዝም መነሻ ነጥብ ሆኖ አገልግሏል። የሩቁን ትተን የቻይናን የካፒታል ክምችት ሂደት በማየት ብቻ ይህን ማረጋገጥ ይቻላል።

ቻይና ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ባካሔደችው ሪፎርም ከምንም ነገር በፊት ያደረገችው ሕይወቱ በአነስተኛ ማሳ ላይ የተመሠረተውን የአርሶ አደሯን ጉልበት በሰፊው ማንቀሳቀስ ነበር። ቻይና በወቅቱ ወደአንድ ቢሊዮን ይጠጋ ከነበረው የአገሪቱ ህዝብ 80 በመቶ ያህል የነበረውን የገጠር ህዝቧን በማንቀሳቀስ፣ አፍሪካ በብድርና ምጽዋት ያላገኘችውን በትሪሊየኖች የሚቆጠር ፋይናንስ ለማከማቸት በቅታለች። ይህን በቀላል ስሌት ለመመልከት በወቅቱ ስምንት መቶ ሚሊዮን ያህል ከሚሆነው ህዝቧ ሁለት ሦስተኛ ያህሉ የገጠር ነዋሪ በነበረችው ቻይና ገበሬው በየቀኑ አንድ አንድ የቻይና ብር/ዩዋን/ የሚያስገኝ ልማት ቢያካሂድ፣ በየቀኑ ግማሽ ቢሊዮን ተጨማሪ ካፒታል ወይም በዓመት ለስምሪት ዝግጁ የሆነ ወደሁለት መቶ

ቢሊዮን የቻይና ዩዋን (ካፒታል) ይፈጥራል። ይህም ቻይና በወቅቱ በነበራት የምንዛሬ ተመን ሲሠላ በዓመት ከሠላሳ ቢሊዮን ዶላር በላይ መሆኑ ነው። በቀን የሁለት ብር የምርታማነት ጭማሪ ቢያመጣ ደግሞ አጠቃላይ ውጤቱ በእጥፍ ያድጋል። በቻይና በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ብቻ የግብርና ምርታማነት በሦስት እጥፍ አድጓ ነበር። ይህ በራሱ ቻይና ጉልበትን በማንቀሳቀስ ብቻ ከገንዘብም አልፎ እጅግ ከፍተኛ ልማታዊ አቅም እንደገነባች የሚያሳይ ነው። ቻይና በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ፣ ከሌሎች ያልበለጸጉ አገሮች ተለይታ ወደፊት እንድትራመድ ያደረጋት መነሻም ይኸው በገጠር የተፈጠረ ካፒታል ነበር። /አሪጊ 2000/

ይህን የመሰለው የካፒታል ክምችት በቻይና ብቻ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል በጃፓን በኋላም በኮሪያና በታይዋን የተፈጸመ ነበር። ነገር ግን እነዚህ አገሮች ይህን ለማድረግ የቻሉት በቅድሚያ በሥር-ነቀል የመሬት ክፍፍል የአርሶ አደሩን ነጻነት ለማረጋገጥ በመቻላቸው ነበር። በአንጻሩ ሥር-ነቀል የመሬት ክፍፍል ባለማካሔዳቸው የአገራቸውን አርሶ አደር ከከፊል ጭሰኝነት ማላቀቅ የተሳናቸው እንደማሌዥያ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ፊሊፕንስ፣ ታይላንድና ሕንድ የመሳሰሉ አገሮች ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትን በተሟላ ደረጃ ለመፈጸም ባለመቻላቸው ልማታቸውን ትንሽ ከማን቏ቀቅ አልፈው የበለጸገ ኢንዱስትሪያዊ ሕበረተሰብ ለመገንባት ሳይችሉ ቀርተዋል። በመሆኑም በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት አንድ ገጽታ የሆነውን እጅግ ግዙፍ ፋይናንሳዊ አቅም መገንባት የኢንዱስትሪ ልማትን ለመጀመር የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ ነው።

በገጠር በአነስተኛ ማሳ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ በተነጻጻሪ ሰፋ ያለና በማያቋርጥ ሁኔታ ምርታማነቱን እየጨመረ የሚሔድ ህዝብ በሚኖርበት አገር ቀስ በቀስ ለኢንዱስትሪ ልማት የሚያስፈልገው ካፒታል ወይም መጠነ ሰፊ ፋይናንስ እየተፈጠረ ይሔዳል። በእርግጥ አርሶ አደሩ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት የሚሆን ትርፍ ፋይናንስ ከማመንጨቱ በፊት የራሱን ፍጆታ ማሟላት መጀመሩ አይቀርም። ይህ የፍጆታ ጥያቄ ተሟልቶ መመለስ ከጀመረ በኋላ የሚገኘው ተጨማሪ ምርት ግን ዞሮ ዞሮ ወደካፒታል ክምችት መሸጋገር ይጀምራል። ለምሣሌ አንድ አርሶ አደር በዓመት በሔክታር አሥር ኩንታል የሚያመርት ቢሆንና አምስት አባላት ያሉት ቤተሰብ ቢኖረው ለእያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል በየቀኑ 550 ግራም ምግብ ለማቅረብ ይችላል። ይህ ከሞላ ጐደል በአስቸኳይ የምግብ እርዳታ መልክ ከሚሰጠው ምግብ ጋር ተመጣጣኝ ነው። መጠኑ ዝቅተኛና ከግል ቀለብ የማያልፍ በመሆኑ ይህን በመሰለ ዝቅተኛ ምርታማነት ላይ የሚገኝ አርሶ አደር የሚያስገኘው ሊቆጠብና ወደ ኢንቨስትመንት ሊሸጋገር የሚችል ትርፍ ገንዘብ አይኖርም። ይሁንና ገበሬው ምርታማነቱን በእጥፍ ቢያሳድግ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ቢያንስ በቀን አንድ ኪሎ ምግብ የማቅረብ ብቃት ይፈጠራል። ይህ ሲሆን የቤተሰቡ አባል ሁሉ በየቀኑ ከሚበላው በላይ የተወሰነ ማትረፍ ይጀምራል። ይህ ትርፍ ተሸጦ ገንዘቡ

በቁጠባ በተቀመጠ ቁጥር ወደሌላ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት የሚሸጋገር ካፒታል ይፈጠራል። የአርሶ አደሩ ምርታማነት በሔክታር ከ20 ኩንታል ተነስቶ ወደ 40 ቢደርስ ደግሞ፣ የተገኘው የምርት ጭማሪ በቀለብ ሊያልቅ የማይችል በመሆኑ ተጨማሪው ምርት ተሸጦ ተለውጦ በገንዘብ መልክ የመከማቸት ዕድሉ የሰፋ ይሆናል።

ይህን የኢትዮጵያ ገበሬዎች በአሁኑ ጊዜ ከደረሱበት በሔክታር የ23 ኩንታል አማካይ ምርት በመነሳት መመልከትም ይቻላል። በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ሁሉንም ገበሬዎች በጣም ትጉህ ገበሬዎች ወደደረሱበት በሔክታር አማካይ የ50 ኩንታል የማምረት ደረጃ ለማድረስ በቤተሰብ ደረጃ በየዓመቱ የሦስት ኩንታል ጭማሪ ማምጣት ይጠይቃል፡ ፡ እስካሁን በተደረገው ጥረት አልፎ አልፎ ከሁለት ኩንታል በላይ አማካይ ዓመታዊ የምርት ጭማሪ ማምጣት የተቻለ በመሆኑ ይህን ወደሦስት ኩንታል ማድረስ የማይቻል አይደለም፡ ፡ በመሆኑም ይህን ማሳካት ከተቻለ 15 ሚሊዮን ያህል ኢትዮጵያውያን የገበሬ ቤተሰቦች በየዓመቱ በድምሩ 45 ሚሊዮን ኩንታል እሕል ለገበያ ሊያቀርቡ ይችላሉ። እያንዳንዱ ኩንታል በአማካይ አንድ ሺህ ብር ቢያወጣ ከመነሻው ዓመት ጀምሮ እያደገ የሚሔድ ሰፊ የኢንቨስትመንት ካፒታል ይፈጠራል። በመጀመሪያው ዓመት ብቻ 45 ቢሊዮን፣ በሚቀጥለው ዓመት ዘጠና ቢሊዮን፣ በሶስተኛው ዓመት ደግሞ 135 ቢሊዮን ብር ያህል የካፒታል ከምችት ይካሔዳል ማለት ነው። ይህ ዕድገት የግብርና ምርት ዋጋ መውደቅ እስኪጀምርና የሰብል ምርት ዕደገት የምርታማነት ዳርቻው (Production Frotier) ላይ እስኪደረስ ሊቀጥል ይችላል። በዚያው ልክ ደግሞ ግብርናው ለኢንዱስትሪ ልማት የሚሆነውን ካፒታል በሚፈለገው ደረጃ ሊያመነጭ ይችላል።

ይህ ባለፉት አሥር ዓመታት ኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪ ልማት በብድር ከሰጠችው ካፒታል በብዙ እጅ የበለጠ ከመሆኑም በላይ በመጀመሪያው ዓመት ብቻ እያንዳንዳቸው በአማካይ እስከ 100ሚሊዮን ብር በሚደርስ ወጭ ሊገነቡ የሚችሉ 500 አዳዲስ ቀላል ፋብሪካዎችን ለመገንባት የሚያስችል አቅም ነው። በቁጥር ደረጃ ኢትዮጵያ ዘመናዊ ፋብሪካዎች መገንባት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ እስከደርግ ውድቀት ድረስ የተገነቡትን ፋብሪካዎች ግፋ ቢል በሁለት ዓመት የመገንባት ችሎታን መገንዘብ ማለት ነው። ወይም ደግሞ በየዓመቱ ሁለት ሦስት የሀዳሴ ግድቦችን ፋይናንስ የማድረግ አቅም መገንባት ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት ሲታይ በገጠር በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ የተሳካ ልማት ላይ የተመሠረተ ካፒታል የመፍጠር ሂደት ለኢንዱስትሪና ለመሠረተ-ልማት መስፋፋት አማራጭ የሌለው ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ ነው። በዚህ ላይ በአገሪቱ የሚገነባው ኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፉ የላቀ እሴት ፈጣሪ በመሆን ለካፒታል ከምችት የሚያበረከተው አስተዋጽዖ ሲታከልበት፣ ትከከለኛ አቅጣጫ ይዞ በሚጓዝ አገር የካፒታል ከምችት ከባድ ችግር ሊሆን አይችልም የሚል

ድምዳሜ ላይ ያደርሳል።

በኢንዱስትሪ የለማ አገር ለመሆን መሟላት ያለበት ሁለተኛው ቅድመ ሁኔታ ሰፊ የማኑፋክቸሪንግ የሥራ ኃይል መፍጠር ነው። ይህም በዋነኛነት በገጠር ከሚገኘው ህዝብ ሰፊ ቁጥር ያለው በእርሻ ወይም በከብት እርባታ ከመተዳደር ወጥቶ የኢንዱስትሪ የሥራ ኃይል ወይም ላብ አደር ወደመሆን ሲሸጋገር እውን የሚሆን ነው። በኢንዱስትሪ ልማት የመበልጸግ ራዕይ እንዲሳካ ከህዝቡ ከፊሉ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሠማርቶ በማሽነሪ የታገዘ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስገኝ ምርት ወደማምረት መሸጋገር ይኖርበታል። ተፈላጊው ብዛት ያለውና ከግብርና በተለየ የሥራ ዲሲፕሊንና ከህሎት የታነጸ የሠራተኛ ጉልበት (Skilled Labour) ባልተፈጠረበት የኢንዱስትሪ ልማት ተሳክቷል ሊባል አይችልም። በመሆኑም አብዛኛው ህዝብ ሕይወቱን በግብርና ላይ በሚያስቀጥልበት አገር የኢንዱስትሪ ልማት ሊፋጠን አይችልምና የገጠሩ ህዝብ ደረጃ በደረጃ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሰማርቶ ወደሚያመርት ማኅበረሰብ መሸጋገር ይገባዋል። ይህም ማኑፋክቸሪንግ እንደእንጉዳይ እንዲፈላ ከማድረግ ሂደት ጐን ለጐንና በተመሳሳይ ወቅት መካሔድ ያለበት ሌላ ሂደት ነው።

በእርግጥ የገጠሩ ህዝብ በአንዴ ነቅሎ ከተማ እንደማይሆነው ሁሉ፣ በዛ ያለው የአርሶ አደሩ ከፍልም በአንድ ጀምበር ምሽት ወደፋብሪካ ሠራተኛነት አይሸጋገርም። ይህ ለውጥ እንዲመጣ አስቀድመው መሟላት ያለባቸው በርካታ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ በሠለጠነ የሰው ኃይል ላይ የተመሠረተ ኢንዱስትሪያላይዜሽን አይፈጠርም። በብዙ የላቲን አሜሪካ አገሮችና እንደታይላንድና ፊሊፒንስን በመሳሰሉ አገሮች እንደታየው ቅድመ ሁኔታዎቹ በከፊል ብቻ ተሟልተው ሲገኙ ኢንዱስትሪ አልባ ከተሜነት መሥፋፋት ይጀምራል። በአንጻሩ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ከምችት መፍጠሪያ ሂደቱ በትክክል ከተከናወነ፣ በተለይ ደግሞ ይህ ሂደት ከአገራዊ የቴከኖሎጅ አቅም ግንባታ ጋር ተጐራረሶ እንዲሔድ ከተደረገ ለኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ የሆነውን ሰፊ የሠለጠነ ሠራተኛ ለማቅረብ ያስችላል። ይህ ትክክለኛ ሂደት በጣም አስተማማኝ በሆነ ደረጃ የተከናወነው በሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮች ከተካሔደው የገጠር ልማት ጋር ተያይዞ ነበር።

በሰሜን ምሥራቅ እስያ ልማታዊ አገሮች ለኢንዱስትሪ ተፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል በተገቢው መጠን የማቅረብ ችሎታ የተፈጠረው በቅድሚያ አርሶ አደሩ ከመሬቱ ሳይፈናቀል ምርታማነቱን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሳድግ በማድረግ ነበር። እንደሚታወቀው በገጠር የአርሶ አደሩ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ካልጨመረ ለከተሞች የሚቀርበውን ምግብ ይቅርና የራሱን የአርሶ አደሩን ቀለብ ማሟላት እንኳ አይቻልም። በዚህ የተነሳ የእሕል አቅርቦት እጅግ አስተማማኝ ባልሆነባቸው አገሮች ሰዎች ከከተማ ይልቅ በገጠር መኖር ይመርጣሉ። በተለይ የራሳቸው ትንሽ መሬት የሚኖራቸው ከሆነ ደግሞ፣ በከተማ አንዳችም

የገቢ ምንጭ ሳይኖራቸው በረሀብ ከሚገረፉ በገጠር ባለቻቸው መሬት እንደምንም ቀለባቸውን እያሟሉ መኖር ይመርጣሉ፡፡ ስለዚህም ዝቅተኛ ምርታማነት ባለባቸው ሕብረተሰቦች ሁሉ፣ ቢሳካም ባይሳካም፣ የበሬ ግንባር የምታህል መሬት ይዞ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መሞከር ተመራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ የሚኖር ፍልሰት ለዘመናት እንደተገደበ ሊቆይ ይችላል፡፡ በዚህ ላይ በገጠር እርሻ ሥራ ላይ የተሰማራው ሰው ምርታማነት ዝቅተኛ መሆኑ ታክሎበት ለኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ገጠርን ላይለቅ ይችላል፡፡ በተሻለ የግብርና የምርታማነት ብቃት /Efficiency/ በአንድ ሰው ሊመረት የሚችለውን ምርት፣ በዝቅተኛ የምርታማነት ብቃት ምክንያት አምስት የቤተሰብ አባላት ካልተረባረቡበት በስተቀር የማይመረት ከሆነ ሌላው ቀርቶ ቤተሰብም ልጆቹ ወደከተሞች እንዳይፈልሱ መከልከሉ አይቀሬ ነው፡፡

በገጠር ምርታማነት እየጨመረ ሲሔድ ግን እነዚህ ሁለት ችግሮች መቃለል ይጀምራሉ፡፡ ከሁሉ በፊት የአርሶ አደሩ የማምረት አቅም በተሻሻለ ቁጥር፣ ብዙ ሰዎች ያከናውኑት የነበረው ሥራ በጥቂት ሰዎች መከናወን ይጀምራል፡፡ ስለዚህም በገጠር ትርፍና አላስፈላጊ ጉልበት ይፈጠራል፡፡ ይህን ጉልበት በገጠር ማቆየት ሥራ እንዲፈታ ከማድረግና ከማባከን ውጪ ሌላ ጥቅም የማይገኝበት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ይህ ትርፍ ጉልበት ተወደደም ተጠላ ገጠርንና ግብርናን ለቆ ወደኢንዱስትሪ፣ አገልግሎትና ከተሞች መሔድ ይፈልጋል፡፡ ከመፈለግም አልፎ መንቀሳቀስ ይጀምራል፡፡ በከተሞች ይህን የሰው ኃይል ለመሸከም የሚችል ኢንዱስትሪያዊ መስክ ተስፋፍቶ ከቆየ፣ ይህን ሰብዓዊ አቅም በአጭር ጊዜ ተቀብሎ ወደ ልማት ሥራ እንዲገባ ያደርገዋል፡፡ ወይም ደግሞ ሰፊ ጉልበት መገኘቱን የተመለከተ ኢንተርፕረነር ሁሉ ማኑፋክቸሪንግን በማስፋፋት ያለብዙ ችግር ከሞላ ጐደል ሙሉ በሙሉ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

በገጠር ምርታማነት ከመጨመሩ ጋር ተያይዞ ሰፊ የሰው ኃይል ወደ ከተሞች በሚፈልስበት ጊዜ የኑሮ ውድነት ከባድ ፈተና ሊሆን ቢችልም፣ በምርታማነት ጭማሪ ምክንያት ከሚፈጠረው የእሕል አቅርቦት ጋር ተያይዞ በትንሽ ወጪ ለመኖር የሚቻልበት ዕድል እየሰፋ መሔዱ ግን አይቀርም፡፡ በተሳካው የገጠር ልማት የተነሳ በገጠር ብቻ ሳይሆን፣ በከተሞችም የምግብ አቅርቦት በዓይነትና በመጠን ከፍተኛ መሻሻል ይታይበታል፡፡ ይህ ሲሆን ከተሞች የሚያስፈሩ መሆናቸው ቀርቶ የገጠር ሰዎችን የሚያማልሉ መሆን ይጀምራሉ፡፡ በገጠር ትርፍ የመሆን ዕድላቸው እየጨመረ የሚሔዱት መሬት አልባ ወጣቶች፣ ገጠሩን እየለቀቁ በገፍ ወደከተሞች ያመራሉ፡፡ ባለሀብቱ እነዚህን ወጣቶች በተነጻጻሪ የተሻለ ከፍያ ለማሠራት በሚችልበት የምግብ እሕል አቅርቦት በመታገዝ ፋብሪካዎችን ለማስፋፋት ይችላል፡፡

ከዚህ በመነሳት ሲታይ በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ የተሳካ የምርታማነት ጭማሪ ማምጣት ከተቻለ፣ በአጠቃላይ ለተፋጠነ ኢንዱስትሪ በተለይ ለገጠር ኢንዱስትሪ ልማት እውን

መሆን ሁለቱ ወሳኝ ቀድመ ሁኔታዎች ይሟላሉ፡፡ ለማኑፋክቸሪንግ መስፋፋት ተፈላጊውና መነሻ ሊሆን የሚችለው የፋይናንስ አቅም ይፈጠራል፡፡ ከዚህ ጐን ለጐን በፋብሪካዎች ተቀጥሮ መሥራት የሚችል መጠነ-ሰፊ የሰው ኃይል ወደ ከተሞች ይጐርፋል፡፡ በዚህም የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ከምችት ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ይሟላሉ፡፡ ለኢንዱስትሪ ልማት ቁልፍ ተፈላጊነት ያላቸው ካፒታልና ብዛት ያለው ሠራተኛ የሰው ኃይል በብዛት መቅረብ ይጀምራል፡ ፡ በእነዚህ በመጠቀም የቴከኖሎጂ አቅም ግንባታ ተግባሩን በሥኬት ለመፈጸም የቆረጠ መንግሥት ሲኖር፣ ደግሞ ኢንዱስትሪያላይዜሽን ራዕይ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ የሚዳሰስ እውነታ ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያ ከድኅነት ወደ ብልጽግና በምታልመው ሽግግር፣ ከመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ከምችት ውጭ ሌላ አቋራጭ መንገድም ሆነ ዕድል አልነበራትም፡፡ ዛሬም የላትም፡ ፡ ይህም ለኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ የሆነውን የኢንቨስትመንት ካፒታልና የሰለጠነ የሰው ኃይል በሥፋት በማቅረብ ብቻ ሊሳካ የሚችል ነው፡፡ ሁለቱም ደግሞ የአነስተኛውን አርሶ አደር ማሳ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ብቻ የሚሟሉ ናቸው፡፡ አገራችን ለኢንዱስትሪ ልማት የሚያስፈልጋትን ካፒታል በብድርና በእርዳታ ልታሰባስበው አትችልም ነበር፡፡ እንደእንግሊዞች ቅኝ ግዛቶችን በመያዝና በመመዝበር ወይም ባልተመጣጠነ የውጭ ንግድ ልታሟላውም ትችላለች ተብሎም አይታሰብም። የነበራትና ያላት አንድና ብቸኛ መንገድ የአነስተኛውን አርሶ አደር ማሳ ማልማት ነበር፡፡ መለስ የኢትዮጵያን ዕድገት ለማስጀመርና በአስተማማኝ ደረጃ ለማስቀጠል በአነስተኛው አርሶ አደር ልማታዊ አቅም የሚተማመን ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን እንድንከተል ያመላከተው ከዚህ በመነሳት ነበር፡ ፡ ይህን በመገንዘብ ከሽግግሩ ወቅት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጀምሮ፣ በአንደኛውና በሁለተኛው የልማት መርሐ ግብሮች የአነስተኛውን አርሶ አደር ማሳ ለማልማት ተሞክሯል፡፡ ባለፉት አሥራ አምስት ዓመታት ደግሞ አዲሱን የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ለተፋጠነ የኢንዱስትሪ ልማት ተፈላጊ የሆነውን የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ከምችት ለማሳካት ጥረት ተደርጓል፡፡ ኢትዮጵያ ደረጃ በደረጃ በዚህ አኳኋን እየተጓዘች አሁን ኢንዱስትሪያላይዜሽንን እውን ማድረግ እንድትጀምር በሚያስችላት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የኢንዱስትሪ ልማትን እንደ ነገሩ ለማስፋፋት ያደረገችው ሙከራ ሁሉ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ከምችት የመፍጠር ብቃትን ባላረጋገጠችበት ወቅት የተካሔደ ጥረት ነው፡፡ በመሆኑም እዚህም እዚያም የተንጠባጠቡ ፋብሪካዎች ከመትከል አልፎ፣ አገሪቱን ኢንዱስትሪ በኢንዱስትሪ የማድረግ ችሎታ አልተፈጠረም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ከመጀመሪያ ደረጃ ካፒታል ከምችት አንጻር ፋብሪካዎችን በከፍተኛ መጠን ለማስፋፋት የምትችልበት የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ ጀምራለች፡፡

የሰብል እሕልን ብቻ መነሻ በማድረግ ይህን ማረጋገጥ ይቻላል። ኢትዮጵያ በ2006 ዓ.ም ሁለት መቶ ሠባ ሚሊዮን ኩንታል አምርታለች። ይህ በመሥኖና በርከት ባሉ የአገሪቱ ደቡባዊ ከፍሎች የሚመረተውን የሥራ-ሥር ምግብ ሳይጨምር ነው። ሁለቱንም በመደመር በአገሪቱ የተገኘው ምርት ከዚህም በጣም ልቆ የሚሔድ እንደሚሆን ቢታወቅም በመኸር ወቅት የሚመረተውን የእሕል ምርት ብቻ መነሻ አድርጐ ይህ ለካፒታል ከምችት ያለውን አስተዋጽኦ መለካት ይቻላል። ምርቱና የህዝቡ ብዛት ተገናዝቦ ሲታይ አገሪቱ ያመረተችው ይህ የእሕል መጠን፣ በአሁኑ ጊዜ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዓመት በነብስ ወከፍ ሦስት ኩንታል እንዲደርሰው ሊያደርግ ይችላል። ይህም በቀን 820 ግራም መሆኑ ነው። ይህ መጠን ቻይና ወደ ኢንዱስትሪ ልማት ከመሸጋገሯ በፊት እ.ኤ.አ በ1978 ሪፎርምና ግልጽነት በማወጅ ወደ መጠነ ሰፊ ኢንዱስትሪ ልማት ሥታመራ የተነሳችበት መጠን ነበር። ቻይና በዚህ ጊዜ ለእያንዳንዱ ቻይናዊ በዓመት 297 ኪሎ እህል የምታቀርብበት ደረጃ ላይ ደርሳ ነበር። የቻይና የኢንዱስትሪ ልማት እንደሮኬት የተወነጨፈው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚህ አኳያ ሲታይ ኢትዮጵያ ለእያንዳንዱ ዜጋ በዓመት ቢያንስ 300 ኪሎ ምግብ ለማቅረብ የምትችልበት ደረጃ ላይ መድረሷ፣ ልከ እንደ ቻይና ሁሉ እጅግ በጣም የተመቸ የመነሻ ነጥብ መቆናጠጧን የሚያሳይ ነው።

ቻይና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግብርናዋ በየዓመቱ የ4 በመቶ ዕድገት እያሳየ ለአገሪቱ የካፒታል ክምችት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በየዓመቱ በአማካይ 7 በመቶ በማደግ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ግብርና ከቻይናም በተሻለ ደረጃ ለካፒታል ክምችት ጥሩና እያደገ የሚሔድ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል። ቻይና የግብርናዋ ምርታማነት በጨመረ ቁጥር ከገጠር ወደከተማ እየፈለሰ ወደኢንዱስትሪ የሚሸጋገር የሰው ኃይሏ በእጅጉ ጨምሯል። በኢትዮጵያም ገበሬው በተለይ የተማረውና መሬት አልባው የገጠር ወጣት፣ ወደከተሞች ለመፍለስ የሚችልበት ሁኔታና ግፊት መፈጠር ጀምሯል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ሥኬታማ በሆነ መንገድ በመልማት ላይ ያለውን የአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ትሩፋት ለማፈስ የሚቻልበት ወይም ወደተጨባጭ ኢንዱስትሪያዊ አቅም ለመቀየር የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

ይህን በኢትዮጵያ በግብርና ቁጠባ መልክ በመሰባሰብ ላይ ያለውን መጠነ ሰፊ ካፒታል በተመለከተ ጥቂት አኃዞችን በማቅረብ ብቻ ለማረጋገጥ ይቻላል። ብሔራዊ ቁጠባችን የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከጀመረበት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ከነበረበት 88 ቢሊዮን ብር በመነሳት በአማካይ በ2008 ዓ.ም. መጨረሻ ወደ337.7 ቢሊዮን ብር አድጓል። ዛሬ የኦሮሚያ ወይም የአማራ ክልል ዓመታዊ ድጐማ ብቻ ፌዴራል መንግሥት በ1986 የነበረውን አጠቃላይ አገራዊ በጀት የሚያክል መሆኑ ኢትዮጵያ ለልማት የሚሆን

ካፒታል ከመፍጠር አኳያ የተራመደችውን ረዥም ርቀት ያሳያል። ይህም መለስ "ትክክለኛውን አቅጣጫ እስከተከተልን ድረስ አገርን ለማልማት በሚደረገው ጥረት ገንዘብ ትንሹ ፈተና ነው" በማለት ይገልጸው የነበረው አስተሳሰብ ትክክል እንደነበረ ያረጋግጣል። በማምረት አቅም ግንባታ ላይ የተመሠረተ ልማት ለሚያካሂዱ አገሮች በርግጥም ገንዘብ የመጨረሻው ትንሽ ፈተና ነው።

ኢትዮጵያ ጠብታ ነዳጅ ሳይኖራት እንዴት በፍጥነት መልማት እንደጀመረች የሚገርማቸው የውጭ ሰዎች ብዙ ናቸው። ነገር ግን በገጠር አርሶ አደሩ በማምጣት ላይ ያለውን ለውጥ በቅርብ የሚከታተሉ ሁሉ ገጠሩ በርግጥም አዲስ የሀብት ፈጠራ አውድማ እንደሆነ ለመገንዘብ አይቸገርም። በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያም እንደቻይና ከራስ መሬትና ጉልበት የሚፈልቅ የካፒታል ክምችት እውን መሆን ጀምሯል። የኢትዮጵያ ትልቁ ፈተና፣ ገንዘብ ማግኘት መሆኑ ቀርቶ ያገኘሽውን ገንዘብ የት ቦታ ላይና ለምን ዓላማ ማዋል እንዳለብህ ማወቅና ይህንም በጥብቅ ዲሲፕሊን መፈጸም ሆኗል። ንግድ ባንክ "ከአንዱስትሪ ፋይናንስ መውጣት" አለበት የሚለው የብሔራዊ ባንክ ገዥ ቀላጤ ገንዘብ መፍጠር በጀመረ አገር ውስጥ በእርግጥም መንግሥት የፈጠረውን ገንዘብ የት ላይ እንደሚያውል ግራ መጋባት እንደጀመረ የሚያመላክት ነው።

አገራችን የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ውስጥ መግባቷ የህዳሴ ጉዞ ያስገኘው ተጨባጭ ውጤት ነው። ከዚህ ውጤት ላይ በመነሳትና በእርሱም በመታገዝ ቀጣዩን ምዕራፍ በትክክል መያያዝና መፈጸም ከተቻለ፣ እንደቀደምት ሥኬቶች ሁሉ በመጪው ጊዜም ለሌላ አዲስ ታሪክ ይፈጥራል። በአንጻሩ ይህን ዕድል በአንድ ወይም በሌላ ግብዝ ምክንያት ማበላሸት ደግሞ እንደሕንድ "ያልተረጋገጠ ባለዝና" መሆንን ሊያስከትል ይችላል። አማርትያ ሴንና ጄን ድረዜ "ሕንድ በፍጥነት እየተነሳች ነው" እየተባለ የጐረፈላት ውዳሴ ከተጨባጩ የሕንድ ጉዞ አልጣጣም ሲላቸው ምሬታቸውን "An Uncertain Glory; India and Its Contradiction" በማለት እንደገለፁት ኢትዮጵያም "ባልተረጋገጠ ውጤት" ላይ ለተመሠረተ ዝና ልትጋለጥ ትችላለች። እናም ከረዥም ዓመታት ትግልና ጥረት በኋላ አገሪቱ መፍጠር የጀመረችውን ውድ ካፒታል፣ ወደኢንዱስትሪ በተለይ ወደገጠር አንዱስትሪ ልማት ለማሰማራት እንዲቻል በከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ መራመድ ይገባል። ይህ ውድ ሀብት ከቅርብ አመታት ወዲህ እየሆነ እንዳለው፣ በተለያዩ ምክኒያቶችና ወሳኝ ባልሆኑ መስኮች ላይ በማፍሰስ ፈጽሞ መባከን የሌለበት መልካም ዕድል ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያ በከባድ ትግል የተቆናጠጠችውንና ሥኬታማ በሆነ መንገድ የፈጠረችውን የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችትና የሰው ኃይል ከየትኛውም ዓይነት ብክነትና አደጋ ጠብቃ ኢንዱስትሪን በተለይ ደግሞ የገጠር አንዱስትሪን በከፍተኛ ፍጥነት ለማልማት መረባረብ ይገባታል። ይህን ተገንዝቦ

በዕድሉ ለመጠቀም ከተቻለ፣ ኢትዮጵያ በእርግጥም ከምሥራቅ እስያ ነብሮች በማይለይ አኳኋን አፍሪካዊት አንበሳ ትሆናለች።

ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ የመሥመር ትጥቅ እንደልዩ መልካም ዕድል

አንድ አገር መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት ከፍተኛ የብልጽግናና የዴሞክራሲ ደረጃ ትደርስ ዘንድ ቀዳሚ መተማመኛ የሚሆናት መሠረታዊው የለውጥ አቅጣጫ በጥራት መነደፉ ነው። ይህ ከሁሉ በፊት ያለህበትን ሁኔታ በትክክል ከመተንተንና የሥርዓቱን ችግሮች መለየት የግድ ይላል። በተጨማሪም ችግሮቹን በመፍታት ሊደረስባቸው የሚገባ የትግሉን የረጅም፣ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ግቦችና ወደእነዚህ የሚያመሩ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ታክቲኮች መንደፍን ይጠይቃል። በዚህ ላይ የተመሠረቱ የአጫጭር ጊዜ እቅዶችን እያዘጋጁ መላውን ድርጅታዊ፣ መንግሥታዊና ህዝባዊ አቅም በማሳተፍ ወደውጤታማ አፈጻጸም ማስገባትም ያሰፈልጋል። የትግል መስመር እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ መሠረታዊና ትክክለኛ አስተሳሰቦች ድምር ሲሆን፣ ይህም በዘፈቀደ የማይገኝ አቅም ወይም ጸጋ ነው። ይልቁንም ምርጥ የሚባለውን የለውጥ ንድፈ-ሀሳብ በመታጠቅና በዚሁ መሣሪያ እየታገዙ የዓለምና የአገርህን ሁኔታ በጥልቀት በመተንተን አገራዊ ባሕርይ አስይዞ የሚነደፍ የለውጥ መሣሪያ ነው። በዚህ አኳኋን ጥራት ያለው የትግል መስመር ከተያዘና ይህንንም በዲሲፕሊን ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ አገር ምድሩን መገለባበጥ ይቻላል።

ከዚህ አኳያ ሲታይ ኢትዮጵያ ግልጽ የአገራዊ ለውጥ አቅጣጫ ወይም መሥመር አላት። ይህ መስመር ባለፉት በርካታ ዓመታት በተግባር ላይ ውሎ ለውጥ ማምጣት የጀመረ በመሆኑ ከንድፈ-ሀሳብነት አልፎ በተግባር ፍቱንነቱ የተረጋገጠ ነው። በዚህ የለውጥ አስተሳሰብ በመመራት በተካሔደ ትንተና አገራችን በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ ትገኛለች። አገራችን ለዘመናት በኖረችበት ቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓት የፖለቲካ ኢኮኖሚው ለኪራይ ሰብሣቢነት በጣም የተመቸ ስለነበር ለዕድገትና ፍትሃዊ ተቃዋሚነት ለመብቃት አለመቻሉና ድኅነትና ኋላቀርነት የሕብረተሰቡ ጣምራ ጠላቶች እንደሆኑ ታውቋል። ድኅነት የቁሳዊ ሀብት እጥረትና በዚህ መሰክ የሕብረተሰቡን መሠረታዊ የምግብ፣ የልብስና የመጠለያ ፍላጐት እንዳይሟላ ያገደው ዋናው ኢኮኖሚያዊ ችግር ነው። ኋላቀርነት ደግሞ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እጦት የወለደው የአስተሳሰብና የባሕል እንዲሁም የዘመናዊ አስተዳደር ሥርዓት አለመኖር ነው። በመሆኑም የለውጡ ዓላማ ድኅነትና ኋላቀርነትን በማስወገድ በህዝባዊ ብልጽግናና መሠረተ ሰፊ ዴሞክራሲ መተካት ነው። ይህ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫው መሠረታዊና ዋነኛ መነሻ ነው።

ከመጀመሪያው ተሃድሶ ሚኒስቴር ጀምሮ በተከታታይ በመማር እየዳበሩ በመጡት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች አገሪቱ ትከከለኛውን የለውጥ አቅጣጫ ስትከተል ቆይታለች። በኢኮኖሚው መስክ ፈጣን ዕድገት ማምጣትና በየደረጃው የብዙኃኑን ህዝብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ተግባራዊ እንቅስቃሴ አካሂዳለች። የአገራችንን የድኅነትና ተያያዥ ችግሮች ለመቅረፍ ዕድገቱ ፈጣንና ከፍተኛ የዕድገት ምጣኔ የተረጋገጠበት እንዲሆን ለማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥታለች። በዚህ መሠረት ረዘም ላሉ ዓመታት ባለሁለት አኃዝ ተከታታይ ዕድገት ማምጣትን መሠረታዊ ግብ አድርጋ ለዚሁ ተግባራዊነት ተንቀሳቅሳለች፡፡ ዕድገቱ ጥቂቶች ብቻ የሚጠቀሙበትና ብዙኃኑ የበይ ተመልካች የሚሆንበት እንዳይሆን ለማድረግ አሳታፊና መሠረተ-ሰፊ እንዲሆን ማድረግን መርጣለች፡፡ ፈጣን ዕድገት በማምጣት ሂደት፣ በቅድሚያ በአሥር ዓመት ከዝቅተኛ ገቢ ወደመካከለኛ ገቢ ሕብረተሰብ የመጀመሪያ ደረጃ (1,500 ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ) ለመሸጋገር፣ በመቀጠል ደግሞ በአሥራ አምስት ዓመት ውስጥ ወደመካከለኛ ገቢ ከፍተኛ ደረጃ (5,000 ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ) ለመሸጋገር፣ በመጨረሻ ደግሞ ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ዓመት ስሚፈጅ ጊዜ በድምሩ ከአርባ እስከ አምሳ ዓመታት በሚፈጅ ጊዜ ወደ ከፍተኛ ገቢ ሕብረተሰብ (10,000 ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ) ለመሸጋገር ታልማለች፡፡

ይህ በጊዜ ተወስኖ የተያዘ ግብ ብቻ አይደለም። ግቦቹን ለማሳካት የሚከናወኑ ትከከለኛ ተግባራት ተቆጥረውና እነዚህን እንዳናሳካ የሚያደናቅፉ ችግሮች ተለይተው የተቀመጡበት፣ ስለዚህም ደግሞ ምን? ለምንና እንዴት? መሥራት እንዳለብን ትከከለኛ አቅጣጫ የተያዘበት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በቅድሚያ ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል እንዳለብን ታምኖበታል፡፡ ግብርናችን በተለይ የአነስተኛው አርሶ አደር ይዞታ ዋናው መተማመኛችን መሆኑ ተሰምሮበት ይህንኑ ማልማት የሞት የሽረት ጉዳይ ተደርጐ ተወስዷል፡፡ ግብርናችን ለምቶ ለተፋጠነ የኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ እንዲያሟላ ማድረግና በሂደት ደግሞ መሪነቱን ለኢንዱስትሪ ማስረከብ እንዳለበት በጠራ መንገድ ተቀምጧል፡፡ ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እስከከባድ ኢንዱስትሪ ልማት ድረስ የተቀመጡት አቅጣጫዎች በንድፈ-ሀሳብም ሆነ በተግባር ትከከለኛና ከድኅነትና ኋላቀርነት መላቀቂያ መንገዶቻችን ናቸው። ከዚህ ጋር ኢንዱስትሪው የመሪነት ሚና መጫወት ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በኋላ የኤከስፖርት ዘርፉ ሴከተሩን መምራት እንዳለበት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ "አከራካሪው" የገጠር ኢንዱስትሪ ልማትም ግባችንን ለማሳካት አማራጭ የሌለው አንድ ትከከለኛና መሠረታዊ አቅጣጫ ነው።

እነዚህን መስኮች ከማልማት አኳያ ህዝቡ በተለይ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ፣ ሠራተኛውና ልማታዊው አገራዊ ባለሀብት እንዲሁም ምሁሩ መተማመኛ አቅሞቻችን እንደሆኑ በስትራቴጂው ላይ በግልጽ ተመላክቷል፡፡ በዚህ ሂደት መንግሥት ለልማት እንቅፋት

የሆኑ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል የተመረጠ ጣልቃ ገብነትና አጠቃላይ የመሪነት ሚና መጫወት እንዳለበት ተሰምሮበታል፡፡ በተለይ ደግሞ የመሠረተ-ልማት ማነቆዎችን የመፍታት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥኬትን የማረጋገጥ፣ መሠረታዊ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች የሞኖፖል አደጋ እንዳይጋረጥባቸው የማድረግ ወዘተ... ሚና መጫወት እንዳለበት በግልጽ ተመላክቷል፡፡ እነዚህ መሠረታዊ የዕድገት ግቦችና አቅጣጫዎች በአዋጅ የተነገሩ፣ መንግሥት ሌት ተቀን የሚለፍፋቸው ከዚህም አልፎ መላው ህዝብ የመንግሥትን ጥረትና ውጤት ከእነዚህ ግቦች እየተነሳ እንዲመዝን ለማድረግ በቁርጠኝነት የተንቀሳቀሰባቸው የለውጥ አቅጣጫዎችና ግቦች ነበሩ፡፡

ኢትዮጵያ በማኅበራዊ ልማት መስክ የምትመራባቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎችም በጥራት ተነድፈዋል፡፡ አገሪቱ የተያያዘችውን መልካም የልማትና የዴሞክራሲ አቅጣጫ ከማስፈጸም አኳያ ዋናው ውሱንነት ከአቅም ግንባታ ጋር የተያያዘ እንደሆነ በመገንዘብ ለትምሕርት መስፋፋት የሚበጅ ትክክለኛ አቅጣጫ ተይዟል፡፡ ትምሕርት በመጠን ብቻ ሳይሆን በጥራት ጭምር እንዲስፋፋ ለማድረግ የመንግሥትና የሕብረተሰብ ሚና በግልጽ ተለይቶ እያንዳንዳቸው ይህንኑ ሚናቸውን የሚጫወቱበት አቅጣጫ ተቀይሷል፡፡ የዜጐች መብትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል ቅኝት የመሠረተ-ሰፊ የጤና ልማት ፖሊሲና አቅጣጫ ተተልሟል፡፡ ኢትዮጵያ በማኅበራዊ ልማት መስክ የሚሌንየሙን የልማት ግቦች ካሳኩ ጥቂት አገሮች አንዷ ልትሆን የበቃችው በዚሁ የተስተካከለ ፖሊሲና ስትራቴጂ በመመራት ነው፡፡

የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ-ልማትን የማስፋፋት አቅጣጫውም ሆነ ተግባራዊ እንቅስቃሴው በእጃችን ያለው የለውጥ መሥመር ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆነ ያሳያል። ከገጠር መንገዶች እስከ አገር አቋራጭ የባቡር መሠረተ-ልማት፣ ከጫራ ጫራ እስከታላቁ የህዳሴ ግድብ የኃይል ማመንጫ ግንባታ ሥራዎች የተመሩበት ትክክለኛ አቅጣጫ አለን። አገራዊ ጥቅምን ማዕከል በማድረግ የተቀረጸውና ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለዘመናዊነት በሚያበቃ ደረጃ እየተስፋፋ ያለው የቴሌኮም አገልግሎት ልማትም ሌላው የለውጥ አቅማችን ነው። የኢንዱስትሪና የመስኖ ፍላጐትን ጨምሮ ከገጠር እስከከተማ ለሰውና እንሰሳት የንጹህ ውሃ አቅርቦትን ለማሟላት የተያዘውና የትምሕርትና ጤና መሠረተ-ልማቶች አቅጣጫዎቻችን ሁሉ ለፈጣን ዕድገት የሚያበቁ እንደሆኑ ከንድፈ-ሀሳብ አልፎ በተግባርም ተረጋግጧል። ይህ ትልቅ አገራዊ አቅም በኢትዮጵያ እጅ ያለ መልካም ዕድል ነው።

ከዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር አኳያም ብዙኃኑ ህዝብ ከአገራዊና ከባቢያዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ርቆ ጥቂቶች እሱን ተክተው የሚወስኑበት ሁኔታ እንዳይፈጠር፣ ይልቁንም ህዝቡ ከጐጥ እስከ ፌዴራል መንግሥት ድረስ ባሉ መድረኮች በንቃት የሚሳተፍበትና የሚወስንበት ዴሞክራሲ የማስፈን አቅጣጫ ተቀይሶ በተግባር ሲተረጐም ቆይቷል። ይህን

የመሰለው ዴሞክራሲ መንግሥት ለህዝብ ራሱን የሚያስገዛበት ቅድመ ሁኔታ ነው። በማንኛውም ከባቢያዊና አገራዊ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግና ሚናውን የሚጫወት ህዝብ ለዴሞክራሲ አስተማማኝ ዋስትና እንደሆነ ታምኖበት የአገራችን ዴሞክራሲ በህዝብ ንቁ ሚናና ተሳትፎ ላይ እንዲመሠረት ተደርጓል። ይኸው ዴሞክራሲ ከተደራጀ የህዝብ ተሳትፎ ውጪ እውን ሊሆን እንደማይችል ታምኖበት የተግባር መመሪያ እንዲሆን ተደርጓል። መልካም አስተዳደር የሕልውና ጉዳይ እንደሆነ ታምኖበት ዋና ዋናዎቹ የትኩረት መስኮች ተለይተው በመመሪያነት ጸድቀዋል። የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥና ማስፋት፣ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ ፍትህን ማስፈን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ሕብረተሰብ መገንባት፣ እንዲሁም ውጤታማና ቀልጣፋ አስተዳደር መኖሩን ማረጋገጥ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ሆነው ተቀምጠዋል። ለብዙኃነት እውቅናና ክብር በመስጠት ላይ የተመሠረተ ያልተማከለ ፌዴራላዊ ሥርዓት ግንባታ፣ የእምነት ነጻነትና እኩልነት እንዲሁም የሴቶች እኩልነት አቅጣጫዎች ሁሉ በዴሞራሲያዊና ፍትሃዊ መርሕ በመገዛት የተነደፉ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ናቸው። ሁሉም በአገራችን ኢትዮጵያ እጅ የሚገኙ የለውጥ ሀሳቦች ናቸው። በእነዚህ መልካም ዕድሎች በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ በርግጥም ፈተናዎቹን ሁሉ ለማለፍ የሚያስችሉ እንደሚሆኑ በሙሉ ልብ መናገር ይቻላል።

እነዚህ ሁሉ ታሳቢ ሲደረጉ በእርግጥም ኢትዮጵያ የገጠሙዋትንና ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን ችግሮች በመፍታት የጀመረችውን የለውጥ ጉዞ ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ እጅግ የተሻለ ዕድል አላት። ፈተናዎቹ ብዙ ቢሆኑም አስተማማኝ መፍትሔ የሆነውን የጠራ የትግል መሥመር የያዘች አገር ነች። ይህ የትግል መሥመር ከኒዮ-ሊበራሊዝም፣ ከአክራሪነት፣ ከጠባብነትና ትምክሕት እንዲሁም የእነዚህ መሠረት ከሆነው ኪራይ ሰብሣቢነት የሚሰነዘሩበትን ጥቃቶች በብቃት እየመከቱ ጥራቱ እንደተጠበቀ እንዲቀጥል ማድረግ ከተቻለ በእርግጥም የኢትዮጵያን ትንሳኤ በተሟላ ደረጃ እውን ማድረግ ይቻላል።

ኢትዮጵያ ጥራት ባለው የትግል መስመር መሥፈርት ከሌሎች መሰል አገሮች ጋር በንጽጽር ስትመዘን ጉልህና መሠረታዊ ብልጫ አላት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን የሚታየው ወደሀሳብ ድኅነት የማምራት ዝንባሌና ተጨባጭ አደጋ ተቃልሎ መታየት የሌለበት ቢሆንም፣ በርግጥም ብዙ መሰል አገሮች አሁንም ከሀሳብ ድኅነት አልወጡም። ዛሬም የሚገኙበትን ነባራዊና ሕለናዊ ሁኔታ በትክክል ተንትኖ የጋራ የትግል መነሻ የሚያደርግ አመራር ያላገኙ አገሮች እጅግ ብዙ ናቸው። የለውጥ ግባቸውንና ወደዚህ የሚያደርሱ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ታክቲኮችን በትክክል መንደፍ ተስኖዋቸው፣ ከአንድ ውድቀት ወደሌላ ውድቀት የሚሸጋገሩ አገሮችም ጥቂት አይደሉም።

በአካባቢያቸን ያሉ አገሮች ሁሉ በህዝብ ብዛት ከእኛ እኩል ባይሆኑም የየራሳቸው የተፈጥሮ ጸጋ አላቸው። ይህም ሆኖ እነዚህ አገሮች ወደፊት መራመድ ተስኖዋቸው ባለህበት

እርገጥ ሲሉ የምናየው ከሌሎች ምክንያቶች በተጨማሪ የጠራ የለውጥ መሥመር በማጣታቸው የተነሳ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ግን ለውጡን በትክክለኛ አቅጣጫ ለመምራት የሚያስችል የአስተሳሰብ ግልጽነት የተያዘባት አገር ነች፡፡ ይህ በምትመራበት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡ በቅርቡ ወደኢትዮጵያ በመምጣት አገሪቱን ተዘዋውሮ የጐበኘው ጆ ስቱድዌል ከአመራር አባላት ጋር ባካሔደው ውይይት፣ የኢትዮጵያ የለውጥ ጉዞ ከተሳካላቸውም ሆነ ካልተሳካላቸው የምሥራቅ እስያ አገሮች በተለየ ሁኔታ በተተነተነ ንድፈ-ሀሳብ የሚመራ መሆኑ እንዳስገረመው ገልጾልን ነበር፡፡ በርግጥም ኢትዮጵያ ለውጥን ለመቀስቀስና ውጤታማ ኢድርጉ ለማስቀጠል የሚያስችል የሀሳብ ድኅነት የሚያሰቃያት አገር አልነበረችም፡፡ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ የሀሳብ ድኅነት የተቃለለባት አገር ሆናለች ማለት፣ ሁሉም የፓርቲና የመንግሥት ኃላፊ፣ እንዲሁም ዜጋ ከሀሳብ ድኅነት ተላቋል ማለት ባይሆንም፣ አገሪቱ በእውቀት መመራት ለሚሻ ሁሉ የሥራ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል የጠራ የለውጥ አቅጣጫ እንዳላት በግልጽ ሊቀመጥ የሚችል ነው፡፡ ይህን የአስተሳሰብ ሀብት ከማንኛውም ዓይነት ጥቃት ተከላክሎ፣ በተለይ ደግሞ ከኒዮ-ሊበራልና ኪራይ ሰብሳቢ የአስተሳሰብ ጉድፎች ጠብቆ ማዳበርና ከአዳዲስ የዕድገት ደረጃዎች ጋር አጣጥሞ ማበልጸግ ከተቻለ፣ በእርግጥም ኢትዮጵያ ከፍተኛ የለውጥ አቅም ሆኖ የሚያገለግላት ተራማጅ አስተሳሰብ የተጐናጸፈች አገር ነች ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ለአገራችን እጅግ መልካም ሊባል የሚችል ዕድል ነው።

ለውጥ የማቀድ፣ የማደራጀትና የመፈጸም የተከማቸ ልምድ መኖር እንደ መልካም ዕድል፣

ኢትዮጵያ የተደቀኑባትን ፈተናዎች ሁሉ በብቃት እንድትቋቋም ለማድረግ ከፍተኛ አቅም የሚሆናት ወይም በእጇ ውስጥ ያለ መልካም ዕድል ተደርጐ የሚወሰደው ሌላው ጉዳይ ለውጥ የማቀድ፣ በብቃት መርቶ የማስፈጸምና የማሳካት የትግል ታሪክ ያለው ድርጅት ባለቤት መሆኗ ነው፡፡ አሁን አሁን የራሱን ችግሮች እንኳ በጊዜና በአስተማማኝ ሁኔታ መፍታት ተስኖት እንደቆየ በግልጽ የሚታይ ቢሆንም ኢህአዴግ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የዘለቀውን ለውጥ የመራ ድርጅት ነው። ኢህአዴግ በ1960ዎቹ መጨረሻና በሰባዎቹ መጀመሪያ በደርግ መንግሥት ጭፍጨፋ የተዳከመውን ህዝባዊ ትግል፣ በተራዘመ የትጥቅ ትግል ሥልት እንደገና ነፍስ የዘራበትና ለውጤት ያበቃ ድርጅት ነው፡፡ በሰብ-ሰሐራ አፍሪካ እጅግ ግዙፍ የነበረውን ወታደራዊ ኃይል በብቁ ስትራቴጂና ታክቲኮች እየተመራ በማሸነፍ አሮጌውን ሥርዓት ያስወገደ ድርጅትም ነው፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላ ደግሞ ከእዝ ወደገበያ ኢኮኖሚ የተደረገውን ሽግግር መርቶ ያሳካ፣ በህዝብና በፖለቲካ ኃይሎች ሰፊና ቀጥተኛ ተሳትፎ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት እንዲቀረጽና እንዲጸድቅ ያደረገ የትግል ድርጅት ነው፡፡

ድርጅቱ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በነበረው ሂደት ለዚህ ሕገ-መንግሥት ታማኝ ሆኖ አገር በመምራት የዜጐችና የቡድን መብቶችን አስከብሯል፡፡ የሃይማኖትና ብሔር እኩልነት ጥያቄዎችን በትክክል መልሷል፡፡ ፌዴራላዊና ያልተማከለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደትን መርቶ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ያመጡ ተግባሮችን በስኬት አስፈጽሟል። በተለይ ባለፉት አሥራ አምስት ዓመታት ከነውሱንነቱም ቢሆን በአነስተኛው አርሶ አደር ማሳ ላይ ከተመሠረተው ልማት እስከ ማኑፋክቸሪንግ፣ ከትምሕርት እስከጤና ልማት በተዘረጉ መርሐ ግብሮች እጅግ መጠነ-ሰፊና የብዙኀኑን ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ለውጥ መርቷል፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ አዲስ ሥምና ዝና እንድታገኝ፣ ለበርካታ ዓመታት የቆየው የድርቅና ረሀብ ተምሳሌት መሆኗ መሰረዝ እንዲጀምር አድርጓል፡፡ በአፍሪካ ተጨባጭ ሁኔታ ኢህአዴግ ያመጣውን ያህል ለውጥ በአጭር ጊዜ ያስመዘገበ ድርጅት አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይህ ትልቅ ጸጋና መልካም ዕድል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች ለምርጫ ወ·ድድር በቀረበበት ሁሉ ኢህአዴግን ሲመርጡ የቆዩት ድርጅቱ ያለፈበት የለውጥ ሂደት በስኬት የተሞላ እንደሆነ በመገንዘባቸው· ነው፡፡ መነሻቸው ድርጅቱ በእስካሁን ጉዞው በተሳካ አኳኋን ያስፈጸማቸው የለውጥ ሂደቶች ናቸው·፡፡ እንደገና በአምስተኛው አገራዊ ምርጫ ድምጻቸውን የሰጡትም ድርጅቱ ከራሱ ድከመቶች ተላቆ የጀመረውን መልካም የለውጥ ሂደት ዳር ያደርሳል ብለው ተስፋ ስላደረጉ ብቻ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በድርጅቱ በኩል እየተበራከቱ የመጡት ድከመቶች እጅግ እያሳሰቧቸው እያለም ድምጻቸውን ለኢህአዴግ የሰጡት ድርጅቱን እንደመልካም ዕድል በመቁጠራቸው ብቻ ነው። ህዝቡ በምርጫ ሂደትና ከዚያም በኋላ በየአጋጣሚው በዚህ መልካም ዕድል ዙሪያ ያነሳቸውን ድክመቶች ከልብ ተገንዝቦ፣ ራሱን ለቀጣዩ ትግል ብቁ ማድረግ እስከቻለ ድረስ በርግጥም ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ አንድ መልካም ዕድል ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህም ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጐልቶ ሲታይ እንደከረመው ድርጅቱ ባመጣው ለውጥ የተነሳ በጐረፈለት ዝና በመሳከር ራሱን ለስህተት ከመዳረግ እየጠበቀ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የሩስያው ፕሬዝዳንት ፑቲን በአንድ ወቅት "ዝናዎችህን ማሰብ ስትጀምር ከእጅህ እያፈተለኩ መውጣት ይጀምራሉ" እንዳሉት፣ ፓርቲው ዝነኛ ያደረጉትን ስኬቶች መቁጠር ካበዛ ድሎቹ ከእጁ ማፈትለካቸው አይቀርም፡፡ ስለዚህም ግዙፉ ፓርቲ ኢህአዴግ፣ በዝና የመኮፈስ አባዜ ከተጠናወተው ከመልካም ዕድልነት ይልቅ ራሱን የቻለ ተግዳሮት መሆኑ አይቀሬ እንደሚሆንና ድርጅቱ ይህን አደጋና አስከፊ ውጤቱን ከወዲሁና ከማዶ ተገንዝቦ በከፍተኛ ጥንቃቄ እስከተጓዘ ድረስ በዚህ መድበለ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ ጠንካራ ተቃዋሚ የመፍጠር አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ወደሌላ ደረጃ ለማድረስ በመሪነትም ሆነ በተቃዋሚነት ሊሰለፍ የሚችል መልካም

ከፍ ሲል የተገለፁት ድክመቶች አኩሪ የትግል ታሪክ ባለው ድርጅት ላይ የተከሰቱ ጊዜያዊ ጉድፎች ናቸው፡፡ ኢህአዴግ ከእነዚህ ውሱንነቶች የሚልቁ መሠረታዊ ጥንካሬዎች ያሉት ድርጅት ነው፡፡ ልማታዊ መንግሥቱም እንደዚሁ፡፡ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ለውጡን የመራው ይህ ድርጅትና በእርሱም የሚመራው መንግሥት ለኢትዮጵያ መልካም ዕድሎች የሚሆኑት በዚሁ የተነሳ ነው፡፡ ድርጅቱ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተጠናወተውን በሽታ በፍጥነት አክሞ ራሱን ለአዲሰ ትግል ካዘጋጀ የማይለወጥ ነገር የለም። በተለይ ደግሞ አመራሩ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት ከነበረችው ብቻ ሳይሆን ከአሥራ አምስት ዓመታት በፊት ከነበረችውም ያደገች፣ የተወሳሰበችና በጣም በቀላሉ ለአደጋ ሊጋለጥ በሚችል የታሪኳ ምዕራፍ ላይ የምትገኝ መሆኗን ተገንዝቦ እንቅፋትነቱን ካስወገደ አገሪቱ ከመስቀለኛ መንገድ ወጥታ ወደ አዲስ የዕድገት ምኩራብ ልትሸጋገር ትችላለች።

አመራሩ ወንበሩንና ጥቅሙን ብቻ እያሰላ መልካም አሳቢዎችን ሁሉ በማስወገድ አገርና ህዝብን ወደአደገኛ አቅጣጫ ከማምራት ተቆጥቦ፣ በውስጡም ሆነ ከራሱ ውጭ ያሉ ምሁራንና መላውን ህዝብ በሰፊው በማሳተፍ ከታገዘ መስቀለኛ መንገድ ላይ የወደቀው የኢትዮጵያ ህዳሴ ከአደጋ ወጥቶ በአጭር ጊዜ የመካከለኛ ገቢ ሕብረተሰብን ለመቆናጠጥ ይቻላል። በረጅም ጊዜ ማዕቀፍ ደግሞ ከዚያም ርቆ ለመሔድ ይችላል።

ከእነዚህ ጐን ለጐንና ምናልባትም በማይተናነስ ደረጃ በፖለቲካ ኢኮኖሚው መስክ የመጡት ለውጦችም በርካታ መልካም ዕድሎች ይዘው መጥተዋል፡፡ እነዚህን ዘርዘር አድርጐ መመልከት በጉዳዩ ላይ ለበለጠ ግልጽነት የሚያግዝ በመሆኑ በይደር በቆየው የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ከምችት ዙሪያ የተፈጠረውን መልካም ዕድል ዘርዘር አድርጐ መመልከት ያስፈልጋል።

የመሠረተ - ልማት መስፋፋት እንደመልካም ዕድል፣

ኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪያላይዜሽን እጅግ አመቺ ሁኔታ ከፈጠረችባቸው መስኮች ሌላው መሠረተ-ልማት ነው፡፡ ከገበያ ጉድለት ንድፈ-ሀሳብ በመነሳትና ይህን በተመረጠ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ለመፍታት በተካሔደው አገራዊ ትግል፣ የመሠረተ-ልማት ግንባታ ከነውሱንነቱም ሆኖ ከአንድ ምዕራፍ ወደ ሌላ እየተሸጋገረ ቀጥሏል፡፡ ግንባታው ዘርፈ ብዙና ከትንሽ እስከሜጋ ፕሮጀክቶች የደረሰ ነው፡፡ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በእጅጉ ተስፋፍቷል፡፡ የኤሌትሪክ ኃይል የማመንጨትና የማከፋፈል ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የመንገድ ሥራ ከሁለንተናዊ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ጀምሮ የባቡር መንገድ ወደ መገንባት ተሸጋግሯል፡፡ የውሃ ግድቦችና የመስኖ አውታሮች ግንባታ በመጠንና በዓይነት

ጨምሯል። የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተስፋፍቷል። የጥራትና የማኔጅመንት ችግር የልማቱ የማይነጠል አካል ሆኖ መቆየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቶቹ ከመስፋፋት የተገቱበት ሁኔታ አልነበረም። የጥራትና የማኔጅመንት ችግሩ እየተቃለለ እንዲሔድ ማድረግ የሚገባ መሆኑ ሳይሳት፣ ኢትዮጵያ በአርግጥም በአፍሪካ ከብዙ መሰል አገሮች እጅግ በላቀ የመሠረተ-ልማት ግንባታ ላይ ተጠምዳለች። ግንባታው በተግባራዊ ጠቀሜታው ብቻ ሳይሆን፣ ርዕዮተ ዓለማዊ በሚባል ቁርጠኝነት ላይ ተመሥርቶ እየቀጠለ ነው። ስለኢትዮጵያ የመሠረተ-ልማት ማስፋፋት ዘመቻ ብዙ ሊጻፍለት የሚችልና የሚገባው ቢሆንም፣ በዚህ ክፍል ለኢንዱስትሪያላይዜሽን ባለው ትርጉም በመወሰን በመስኩ የተፈጠረውን የተከማቸ አቅም (Critical Mass) ፋይዳ መመልከት ተመራጭ ይሆናል።

መሠረተ-ልማት ተሟልቶ መገኘት አለመገኘቱ በሠለጠኑና ባልሠለጠኑ አገሮች መካከል የሚታየው ልዩነት አንድ መሠረታዊ መገለጫ ነው። ይህም በአጠቃላይ በሥልጣኔ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በኢንዱስትሪ በመልማት መስክ ያለውን ልዩነት ያስከተለ ነው። በእኛና በበለጸጉት አገሮች መካከል ያለው አንድ መሠረታዊ ልዩነት ይህ ከሆነ ዘንዳ፣ ኢትዮጵያ ይህን ችግር መቅረፍ መጀመሯ ለኢንዱስትሪ ልማት እጅግ የተመቸ ሁኔታ ላይ እንድትገኝ የሚያደርጋት ነው። የኤሌትሪክ ኃይል በተመጣጣኝ ዋጋና በሰፊው ለማቅረብ የሚቻልበት ዕድል መስፋቱ ማኑፋክቸሪንግ እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። የተመረተው ኤሌክትሪክ ሳይቆራረጥ ወደተጠቃሚው እንዲደርስ ማድረግ አዳዲስ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ቀደም ብሎ የተስፋፋውም ያለማቋረጥና በተሻለ ኤፊሸንሲ እንዲያመርት ያስችላል። የኤሌትክሪክ አገልግሎት በገጠር ኤሌክትሪክፊኬሽን አማካይነት ወደ ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ሲዳረስ፣ በኢንዱስትሪ ልማት ላይ የተመሠረቱ ትንንሽ የገጠር ከተሞች በብዛት እየተፈጠሩና እየተበራከቱ ይሔዳሉ። ስለሆነም ህዝቡን ያስመረረውን የመቆራረጥ ችግር ቀርፎ የተጀማመሩ ፕሮጀክቶችን ዳር ማድረስ ብቻ በኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪ ልማት እጅግ የተመቸ ሁኔታ ይፈጥራል። ከገበያ አከራሪዎች ምክር በማፈንገጥ በራሱ ልማታዊ ቅኝት እየተመራ የኢነርጂ ልማት ያስፋፋው መንግሥት፣ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር የሚያስችለውን ይህን ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። አገሪቱ በሚቀጥሉት ሁለትና ሦስት ዓመታት አሥር ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት ብቃት ላይ ከደረሰች፣ በርግጥም በመስኩ ትርጉም ያለው የተከማቸ አቅም ይኖራታል። በዚህ ዕድል በአግባቡ የሚጠቀምበት ሕብረተሰብ ከተገኘ በእርግጥም የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ዘመን ሩቅ ሊሆን አይችልም።

ለኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው የመንገድ መሠረተ-ልማትም በተከማቸ ደረጃ መገኘት ጀምሯል። ከገጠር ጀምሮ በመስፋፋት ላይ ያለው መንገድ በኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የሆነ ኢንዱስትሪያዊ ምርት ለማምረት በጣም አመቺ ቅድመ ሁኔታ ነው። ቀበሌን ከቀበሌና

በወረዳ ማዕከላተ በኩል ከአውራ ጐዳናዎት ጋር የሚያገናኙት መንገዶት ከሁሉ በፊት ለአርሶ አደሩ የምርት ግብዓቶችን በፍጥነትና በተመጣጣኝ የትራንስፖርት ዋጋ ለማቅረብ ዕድል የሚሰጡ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም አርሶ አደሩ ያስገኘውን የምርት ጭማሪ ወደ ኢንዱስትሪና ሌሎች ገበያዎች በፍጥነትና አሁንም በተነጻጻሪ ዝቅተኛ የትራንስፖርት ወጪ ለማጓጓዝ ይችላል፡፡ የአገሪቱ ኢንዱስትሪ በዚህ በመታገዝ የሚያመርታቸውን ምርቶች እንደገና ወደ አገር ውስጥና የውጭ ገበያዎች ለማጓጓዝ ከፍተኛ አጋዥነት ያላቸው አውራ ጐዳናዎች መገንባታቸው፣ ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ሁሉ ትራንስፖርት ማነቆ እንዳይሆን ማድረግ እንደጀመረች ያሳያል፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ሰፊ መጠን የሚኖረውን የማኑፋክቸሪንግ፣ የማዕድንና የግብርና ምርት በባቡር ለማጓጓዝ የሚያስችል አቅም መገንባት መጀመሯ በእርግጥም የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት ዘመን መበሰሩን የሚያሳይ የመሠረተ-ልማት መስፋፋት ነው፡፡

ከቴክኖሎጂ ሽግግር አኳያ ቁልፍ ሚና የሚጫወተው የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ-ልማት መስፋፋትም በአገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማት በሰፊው እንዲጀመር ቅድመ ሁኔታው እየተሟላ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ልክ እንደ ኤሌክትሪክ ሁሉ፣ በዚህም ረገድ የሚታየውን መቆራረጥ በማስወገድና አገልግሎቱን ይበልጥ በማስፋት፣ ቴሌኮም ለሁሉም ዘርፎች በተለይ ደግሞ ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት መፋጠን ልዩ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ይቻላል፡፡ በአገሪቱ የተዘረጋውን የፋይበር ኦፕቲክስ አውታር በመጠቀም በዓለም ዙሪያ ያሉ በሚስጥርነት የማይጠበቁ ቴክኖሎጂዎችን ሁሉ መቅሰም የቀለለ ሥራ ሆኗል፡፡ በኢንተርኔት ውስጥ የሚገኙ እውቀቶችን፣ መልካም የአሰራር ልምዶችንና ላቅ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በቀላሉ በማግኘትና በመኮረጅ በተለይ ወደመካከለኛ ገቢ ሕብረተሰብ ለመሸጋገር እጅግ የተሻለ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ትምሕርትንና የጤና አገልግሎትን ብቻ ሳይሆን መልካም አስተዳደርን በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ አውታሮች ታግዞ በማስፋፋት በሁሉም መስክ ወደ ፊት ለመገስገስ የሚችል ሕብረተሰብ በቀላሉ መፍጠር የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ በዚህ ላይ አገሪቱ በሰባ ሠላሳ የትምሕርት ፖሊሲዋ በመታገዝ ማምረት የጀመረቻቸውን ቴክኖሎጂስቶች፣ ኢንጂነሮችና ሳይንቲስቶች፣ በአጠቃላይም ፕሮፌሽናሎቿን በአግባቡ መያዝና መጠቀም ከቻለች፣ በእርግጥም ኢትዮጵያ ከእንግዲህ የምትገባበትን የኢንዱስትሪ ልማት ዘመን በአስተማማኝ መነሻ ልትጀምረው የምትችልበት ሁኔታ በእጇ ገብቷል፡፡

የተማረና ጤንነቱ የተጠበቀ ሕብረተሰብ ሌላው የተከማቸ አቅም፣

ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የፈጠረችው አቅም ጐልቶ የሚታይበት ሌላው መስክ የተማረና ጤንነቱ የተጠበቀ ሕብረተሰብ መፍጠር ከመጀመሯ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት ከእንግዲህ የምትገባበትን የለውጥ መድረክ አስተማማኝ ለማድረግ

ከፍተኛ አቅም ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ የአንደና ደረጃ ተሃህሐርጥን አሰዘዘ ሀሃ ፖፕኒ ዘኮፍለ ለማዳረስ መቻሏና በዚህም በየዓመቱ ከአንድ ሚሊዮን የሚበልጡ ተማሪዎች ትምሕርታቸውን ጨርሰው መውጣታቸው በቀላሉ የሚሠለጥንና የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማቅረብ እንድትችል ያደርጋታል፡፡ ይህን የመሰለው በመሠረታዊ ትምሕርት የታጠቀ ዜጋ በብዛት ሲፈጠር፣ የኢንዱስትሪ ልማትን በአስተማማኝ የሰው ኃይል ለማስቀጠል የተሻለ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ከዚህ አልፎ የሁለተኛ ደረጃና የመለስተኛ ኮሌጆች ትምሕርታቸውን የሚያጠናቅቁ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ወደሥራ ገበታ በሚቀላቀሉ ጊዜ ለውጡን ይበልጥ አስተማማኝ ያደርጉታል፡፡ መንግሥት ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት የጀመራቸው የቴክኒክ ሙያና የፖሊ-ቴክኒክ ሥልጠና ፕሮግራሞች፣ ጥራታቸው ተጠብቆ ሊጠናከሩ ከቻሉ፣ የኢንዱስትሪ ልማትን በቀላሉ ወደአዲስ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚያስችል የሰው ኃይል ለማቅረብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ በመስፋፋት ላይ ባሉት ዩኒቨርሲቲዎች እየተመረቁ የሚወጡት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ምሑራን ሲታከሉበት፣ በእርግጥም ኢትዮጵያ የተማረ ኃይል በተከማቸ ደረጃ የሚገኝባትና በአጭር ጊዜ ውስጥ የላቀ ፍትሃዊ ልማት የሚረጋገጥባት አገር እንድትሆን ያስችላል፡፡

በትምሕርትና ሥልጠና መስክ እየተፈጠረ ያለው የተከማቸ አቅም በአንድ በኩል ጥራትን በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በማድረግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለፕሮፌሽናሊዝም መዳበርና ይህንኑ በጥቅም ላይ ለማዋል አመቺ ሁኔታ በመፍጠር እንዲጠናከር ማድረግ ከተቻለ፣ አገሪቱ በትምሕርትና ሥልጠና ላይ ያካሔደችው ኢንቨስትመንት በቅርብ ርቀት ዋጋውን መመለስ ይጀምራል፡፡ ይህ እንዲሆን ግን የትምሕርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡ የትምሕርት ተቋማት ብቃት ባላቸው አመራሮች እንዲተዳደሩ መደረግ አለበት፡፡ በብዙ የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት የሚታየው የአመራር ድክመት ሊቀረፍና የምደባ ሥርዓቱ ፖለቲካዊ መሆኑ ቀርቶ በፕሮፌሽናሊዝም ላይ የተመሠረተ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ የፖለቲካዊ ምደባው በአድርባይነትና የጥቅም ትሥሥር ላይ የተመሠረተ በሆነበት ከሁለቱም ሳይሆን መቅረት የማያጠያይቅ ነው፡፡ ፕሮፌሽናሊዝምን መሠረት ያደረገ ምደባ ግን ቢያንስ የትምሕርት ተቋማቱ ተፈላጊውን ፕሮፌሽናል ለማምረት የተሻለ ዕድል እንዲኖራቸው ማድረጉ አይቀርም፡፡ ስለሆነም እስካሁን የተፈጠረውን የተከማቸ አቅም በአግባቡ ለመጠቀምና ወደፊት የሚፈጠረውን አቅም ደግሞ በላቀ ውጤታማነት ለማንቀሳቀስ ለትምሕርትና ሥልጠና ጥራትና ለፕሮፌሽናሊዝም የላቀ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡

በመከላከል ፖሊሲው አማካይነት የሕብረተሰቡ ጤንነት ከመቸውም ጊዜ የተሻለ እየሆነ መሔዱ በራሱ ከፍተኛ ሰብዓዊ ጥቅም መሆኑ እንደተጠበቀ እዚያው ሳለም ለልማት በጣም የተመቸ ዕድል ነው፡፡ በተላላፊና ሌሎች በሽታዎች ምክንያት የአልጋ ቁራኛ የሚሆኑ

ዜጐቶ በሚበዙበት አገር የሚኖረው የጉልበት ብክነት ብዙ መልካም ዕድል እንዲያመልጥ ከማድረጉ በተጨማሪ፣ ሰዎችን ለመፈወስ በሚወጣው ወጭ ብዛት አገር መራቆቱ አይቀርም። በአንጻሩ የዜጐች ጤንነት የተጠበቀ ሲሆን በበሽታ በመማቀቅ የሚባክን የልማት ጊዜ አይኖርም። ዜጐችን ለመፈወስ የሚወጣው ወጭም በእጅጉ ቀንሶ ለልማትና የህዝብ ተጠቃሚነት ይውላል። በዚህም በድኅነት፣ በተለይ ደግሞ በበሽታና ድንቁርና መንሰራፋት ምክንያት የሚከፈለው ውድ ዋጋ ተወግዶ ወደብልጽግና ለመረማመድ ከፍተኛ ብዜታዊ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ አዎንታዊ የተከማቸ አቅም ይፈጠራል። በኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በጤናና ትምሕርት መስኮች የተፈጠረው የተከማቸ አቅም ይህን ያህል ግዙፍ ብዜታዊ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ነው። በመሆኑም በማኅበራዊ ልማት መስክ የተፈጠረውን ይህን የተከማቸ አቅም፣ በሌሎች መስኮች ከተፈጠረው አቅም ጋር በማዋሐድ ለላቀ ትራንስፎርሜሽንና ለውጥ መጠቀም ተገቢ ይሆናል። በዚህም ላይ የተከማቸውን አቅም የሚያመክኑ ዝንባሌዎችን ያለማቋረጥ እየመከቱ መጓዝ በመልካም ዕድሉ አሟልቶ ለመጠቀም አማራጭ የሌለው ይሆናል።

ንቁና ሞጋች መሆን የጀመረ ህዝብ እንደወሳኙ መልካም ዕድል፣

ልክ በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንዲሁም በመሠረተ-ልማት መስኮች የተከማቸ አቅም መፍጠር ለተደማሪ ለውጥ ቁልፍ ተፈላጊነት እንዳለው ሁሉ፣ አንድ አገር በፖለቲካዊ መስክም ወደፊት ለመራመድ የምትበቃው ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ የሚሆን የተከማቸ አቅም ስትፈጥር ነው። መላውን ሕብረተሰብ በአንድ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ቦይ ውስጥ እንዲፈስ የማድረግ ብቃት ያለው የጋራ አስተሳሰብ ካልተፈጠረ በስተቀር፣ ሕብረተሰብ በየራሱ አቅጣጫ ተበታትኖ መኳተኑ አይቀርም። በዚያው ልክ ደግሞ ውጤቱም ዝቅተኛ ይሆናል። ስለሆነም ሕብረተሰብ ወደላቀ የዕድገት ደረጃ ይሸጋገር ዘንድ በመሠረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው። ብሔራዊ መግባባቱ የሚፈጠርባቸው ጉዳዮች እንደ ወቅቱና እንደ መድረኩ ሁኔታ ሊለያዩ ይችላሉ። ይህም ሆኖ ሕብረተሰብ በመሠረታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባባት እየፈጠረ መጓዙ ቀጣይነት ላለው ለውጥ ቅድመ ሁኔታ ነው። ብሔራዊ መግባበቱ ከሁሉ በፊት በሥርዓቱ ችግሮች ዙሪያ በግልጽ በመወያየት የሚጀምርና ለእነዚህ በሚበጀው ትክክለኛ መፍትሔ ላይ መግባባትን ጭምር የሚያጠቃልል መሆን አለበት። በተጨማሪም በየደረጃው በተለዩት ወቅታዊ ችግሮች ላይ በጋራ በመንቀሳቀስ ለውጥ በመጣ ጊዜ ሁሉ አዲሱ መድረክ በሚወልዳቸው አዳዲስ ችግሮችና በመፍትሔያቸው ላይ ጭምር መግባባት ይገባል። ያለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የኢትዮጵያ ጉዞ ይህን በግልጽ የሚያመላክት ነበር።

መጀመሪያ የሁሉም ችግሮች ምንጭ የነበረውን አምባገነናዊ ሥርዓት ለማስወገድ በመላው ሕብረተሰብ ደረጃ መግባባት አስፈላጊ ነበር። በእርግጥ ይህን የመሰለው ብሔራዊ መግባባት አንድም ሰው ሳይቀር ሁሉንም ዜጐች በአንድ የአስተሳሰብ ቦይ ውስጥ ማስገባት ማለት አልነበረም። አምባገነናዊው ሥርዓት መወገድ እንዳለበት የሚያምን የተከማቸ አቅም /Critical mass/ መገንባት፣ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር በቂ መነሻ ነበር። ኢህአዴግ በሕብረተሰብ ደረጃ ይህን መግባባት ከፈጠረ በኋላ ስትራቴጂያዊ ማጥቃት በሰነዘረ በአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ የደርግ ግብዓተ መሬት ተፈጸመ። ይህን ተከትሎም ለዘመናት የተንከባለሉት ችግሮች ሁሉ ደረጃ በደረጃ የሚቀረፉበት ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ። ለተከማመሩት አገራዊ የፖለቲካ ችግሮች ዋናው መፍትሔ በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት በመመራት አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት ስለነበር፣ በዚህ ዙሪያ በተፈጠረ ብሔራዊ መግባባት ላይ ተመሥርቶ የአዲሱ ሥርዓት ግንባታ መሠረት ተጣለ። ግንባታው በቀጠለ ቁጥር ብሔራዊ መግባባቱ ይበልጥ እየገሰበተ፣ አገሪቱ ከጫፍ እስከጫፍ በለውጥ ምህዋር ውስጥ የምትሽከረከር ልትሆን ቻለች።

አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት ከጀመረ በኋላ፣ የሥርዓቱ ፈተና ሆኖ የተለየው ካለአግባብ የመከበር ወይም የኪራይ ሰብሣቢነት ዝንባሌ ነው። ይህ አገራዊ ችግር መሆኑ ከተለየ በኋላ አደጋውን በሁሉም መሣሪያዎች ታግዞ በመፋለም ደረጃ በደረጃ ማዳከምና መርታት አስፈላጊ እንደሆነ ታመነበት። በዚህ ጉዳይ ላይ የጋራ መግባባትና ተፈላጊውን የተከማቸ የአስተሳሰብ አቅም ለመፍጠር ጥረት ማድረግም ተጀመረ። ላለፉት አሥራ ሦስት ዓመታት በዚህ ረገድ በተካሔደው ትግል፣ ከነውሱንነቱም ቢሆን ለመነሻ የሚሆን ፀረ-ኪራይ ሰብሣቢነት አመለካካት መፍጠር ተጀምሯል። በእርግጥ ከዚሁ ጐን ለጐን በኪራይ ሰብሣቢነት ዝንባሌ የመበከል አዝማሚያ እየሰፋ ቢሆንም፣ በዝንባሌው ተጐጅ በሆኑት ማኅበረሰቦች ዘንድ በዚህ አደገኛ ዝንባሌ ላይ ያለው ምሬትና ጥላቻ እየጨመረ ሔዷል።

በኢትዮጵያ በመገንባት ላይ ያለው ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከምንም ነገር በላይ በህዝብ ንቁ ተሳትፎና ወሳኝነት መተማመን የሚችል መሆን እንዳለበት የተሰመረው ገና በጠዋቱ ነበር። ሕብረተሰቡ ሁሉንም ነገር ከሰማይ እንደሚወርድ መና አንጋጦ የሚጠብቅ ከሆነ በራሱ መብትና ጥቅሞች ላይ ሉዓላዊ የመሆን ብቃት አይገኖጸፍም። እናም የራሱን ዕድል በመወሰን ንቁ ተሳታፊ ከመሆን አልፎ፣ በማያቋርጥ ሁኔታ ለመብቱና ጥቅሙ የሚታገል ህዝብ እንዲሆን ንቁ የፖለቲካ ሕይወት ሊኖረው ይገባል። የዳር ተመልካች በመሆን ያልተወሰነ፣ በሁሉም መሠረታዊ ጥያቄዎች "ያገባኛል" የሚልና የሚሳተፍ መሆን አለበት። ይህ እንዲሆን ህዝቡ ንቁ የዜግነት ሚና የሚጫወትና ይህም በቀላሉ የማይዳከም ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግን ይሻል። ህዝቡ በሁሉም መሠረታዊ አጀንዳዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆን ዘንድ ደግሞ፣ በቀጣይነት የተስተካከለ መረጃ ሊቀርብለት ይገባል። በመረጃ ያልበለጸገ ሕብረተሰብ፣ በአገር ውስጥ

መሠረታዊ ጉዳዮችም ሆነ በሌሎች ተዛማጅ ነገሮች ላይ በተገቢውና በቀጣይነት የመሳተፍ ዕድሉ ዝቅተኛ መሆኑ አይቀርም።

ከዚህ በመነሳት በኢትዮጵያ ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት፣ ህዝቡ በሁሉም መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ የመረጃ ሀብት እንዲኖረው ሲደረግ ቆይቷል። እድሜ ለአገሪቱ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲ ከህዝብ የተደበቀ የመንግሥት ውሳኔ የለም። የተደበቀ ነገር እንዳይኖር ብቻ ሳይሆን መንግሥት ሆን ብሎ በተከተለው የግልጽነት ፖሊሲ ምክንያት ለሕብረተሰቡ የማይደርስ መረጃ የለም። በዚህ ምክንያት ህዝቡ በመረጃ እጦት የሚሰቃይና አስተያየት አልቦ ህዝብ አይደለም። መረጃ ለዚያውም ሰፊ መረጃ ያለውና በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የግልና የቡድን አስተያየት ያዳበረ፣ እንዲሁም በርካታ የጠሩ አቋሞች ያሉት ሕብረተሰብ ሆኖ ተገንብቷል። ይህን ጥቂት አብነቶች በማቅረብ መመልከት ይቻላል። መንግሥት ከልማት አኳያ የነደፋቸውና በተለይ ደግሞ ሁሉንም አካባቢዎች ተጠቃሚ ለማድረግ የተቀየሱ ፕሮጀክቶች ሁሉ በህዝብ ተወካዮች ተመክሮባቸው ከጸደቁ በኋላ ለህዝብ ይፋ ይደረጋሉ። የተመደበላቸው በጀት፣ የሚጀመሩበትና የሚያልቁበት ጊዜ ሁሉ ይታወቃል። አልፎ አልፎ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወይም በበጀት መጓደል ፕሮጀክቶች ሲታጠፉ ወይም ሲጓተቱ ህዝቡ መንግሥትን አስጨንቆ ይይዛል። ፕሮጀክቶች በኮንትራክተሮች ወይም በኮንትራት አስፈጻሚዎች ኪራይ ሰብሳቢ አዝማሚያ ዳር መድረስ ሲያቅታቸውም ያውቃል። የተቃውሞ ድምፁንም ጮላ አድርጉ ያሰማል። እንዳንዴ የመሠረታዊ ዕቃዎች አቅርቦት የተሟላ በማይሆንበት ጊዜም ተመሳሳይ ትግል ያካሂዳል። "መንግሥት ያውቃል" ብለው፣ ሁሉንም ነገር ለመንግሥትና ለፈጣሪያቸው ትተው ከሚኖሩ የበለጸገው ዓለም ህዝቦች በተለየና እጅግ ተስፋ በሚሰጥ ደረጃ አስተያየትና አቋም ያለው ህዝብ በአገሪቱ መፈጠር ጀምሯል።

ይህ በኢትዮጵያ ማንኛውንም መልካም ሥራ ለማጠናከር ብቻ ሳይሆን መንግሥትን ጨምሮ በማንም ዘንድ የሚታዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል የተፈጠረ ቁልፍ አቅም ነው። ይህ አቅም እንዳልተፈጠረ ወይም እንደሌለ አድርጉ በመቁጠር ለጊዜው በድብቅ የሚፈጸሙ ስህተቶች፣ ወሎ አድሮ በጥልቅ የተያዙ አስተያየቶች ካሉት ከዚህ ሕብረተሰብ ጋር በግላጭ መጋጨትን ማስከተላቸው አይቀርም። ኢህአዴግ ገና ከጠዋቱ የተጀመረውን ላውጥ በአስተማማኝ ደረጃ የሚያስቀጥለው፣ በፖርቲውና በመንግሥት ምሕረት ሥር ያልወደቀ ሕብረተሰብ ብቻ እንደሆነ በማመን፣ ንቁና ሞጋች ሕብረተሰብ ለመፍጠር የተረባረበው ከዚህ በመነሳት ነው።

የዘሩት መብቀሉ አይቀርምና በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የዳበረ አስተያየትና አቋም ያለው ህዝብ በሚያስመካ ደረጃ ተፈጥሯል። በከተማም በገጠርም የአገሩን ሂደት በባለቤትነት የሚከታተል፣ የሚሳተፍና በሂደቶች ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ሕብረተሰብ ተፈጥሯል። አርሶ አደሩ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ደረጃ በሁሉም የሕይወት መስኮች ንቁ ተሳታፊና ሞጋች ሆኗል። በከተሞች የሠራተኛው መደብ ቁጥሩ እየሰፋና እየተበራከተ ተፅዕኖ አድራጊነቱም እየጠነከረ የሚሔድበት ሁኔታ ጨምሯል። ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና በልዩ ልዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በባለቤትነት ስሜት መሳተፍ የጀመሩት ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ሲቪል ሰርቫንቶች፣ ዝቅተኛ ነጋዴዎች፣ የአነስተኛና ጥቃቅን ተዋናዮች ሁሉ ዓይናቸውን ከፍተው መብትና ጥቅማቸውን የሚያሰፋ ሂደት መኖሩን ለማረጋገጥ በትኩረት ይንቀሳቀሳሉ። በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ አልፎ አልፎ ከሚያጋጥመው የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ጋር በተያያዘ፣ ችግሩ ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሔ ያገኝ ዘንድ ከፍተኛ ጉጉት ያሳያሉ። አገራዊው ባለሀብትም በራሱ አጀንዳዎች ዙሪያ ሂደቱን በቅርብ ይከታተላል። ይህ ከማንም መሰወር የሌለበት ጉዳይ ነው። በተለይ ደግሞ በሥልጣን የመባለግ አዝማሚያ ለሚጠናወታቸው ሁሉ ለመብቱና ለጥቅሙ የሚፋለም ንቁ ህብረተሰብ እንደተፈጠረ በግልጽ ሊታያቸው የሚገባ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ አዲስ እውነታ ነው።

ከመጀመሪያው የተሃድሶ እንቅስቃሴ በኋላ በተገባበት መድረክ መንግሥትና ኢህአዴግ ልማት የቀመሰ ህዝብ መፍጠርን እንደስትራቴጂያዊ አቅጣጫ ነድፈው በመንቀሳቀሳቸው በልማት አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን ልማቱ መሠረተ-ሰፊ ሆኖ መካሔድ እንዳለበት በጥብቅ የሚያምን ሕብረተሰብ በመፈጠር ላይ ነው። መልማት መብት ነው። መብት ብቻ ሳይሆን በትግል እውን የሚሆንና ተከብሮ የሚቀጥል መብት ነው። ልማት የመሪዎችና የመንግሥት ቅን ልቦና እስካለ ድረስ የሚቀጥል፣ መንግሥትና መሪዎች ልቦናቸው የተዘናበለ ቀን የሚዘጋ ፕሮጀክት መሆኑ ቀርቶ፣ በማያቋርጥ ሁኔታ ሊቀጥል የሚችለው ሞጋች /Demanding/ ሕብረተሰብ የተፈጠረ እንደሆነ ብቻ ነው። ፈረንሳዊው የፖለቲካና የታሪክ ምሁር አሌክስ ዱ ቶክቪል ይህን ሁኔታ በማስመልከት በአንድ ወቅት የገለጸው ነገር ብዙ ትምሕርት የሚገኝበት ነው። ቶክቪል በመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮት ወቅት የታየውን የህዝብ መነሳሳትና ከዚያ በፊት የተመዘገበውን ዕድገት በማዛመድ ሊታላቁ የፈረንሳይ አብዮት መቀስቀስ ዋናው ምክንያት የህዝብ ዓይን መገለጥ እንደሆነ፡-

> "የ1789 አብዮት ከመቀስቀሱ በፊት የነበሩት ሃያ ዓመታት ፈረንሳይ ታይቶ የማይታወቅ ብልጽግና ያመጣችባቸው ዓመታት ነበሩ። ይሁንና ፈረንሳዊያኑ ሕይወታቸው በተሻሻለ ቁጥር የኑሮ ሁኔታቸውን ፈጽሞ ለመሸከም የማይችሉ

ሀገሡ ተገ ኑ፡፡ ...ለኅ ሃ" ህዝ ሀተ ን ለአመጽ የሚገፋ ተው ተጨ ባጭ ስቃይ ሳይሆን መልካም ነገሮች መቅመሳቸው ነው፡፡"[112] በማለት ያብራራል።

ይህ የቶክቪል አባባል አንድ አገር ለማያቋርጥ ለውጥና መሻሻል መብቃቷ ለበለጠ ጥያቄዎችና የህዝብ መነሳሳት እንደሚያጋልጣት ያሳያል፡፡ የኢህአዴግ የተሃድሶ መሥመርም ቢሆን በዚህ ቅኝት "አርሶ አደሩና የከተማው ህዝብ በመልካም አቅጣጫ ከመተዳደር በስተቀር ለማንም የማይገዙ ይሆኑ ዘንድ፣ በተቻለው ፍጥነት ሁሉንም መልካም ነገሮች እንዲቀምሱ ማድረግ አለብን" በሚል መርሕ ላይ የተዋቀረ ነው፡፡ በዚህ ጥልቅ እሳቤ ላይ የተገነባው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ ከተሃድሶው በኋላ ልማት የቀመሰና ለቀጣይ ልማት የሚነሳሳ ማኅበረሰብ መፍጠርን ዋነኛ ዒላማው አድርጐ ተንቀሳቅሷል፡፡ ህዝቡ በልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን ሲጀምር መንግሥት ሲፈልግ አገር የሚያለማ፣ ሳይፈልግ የሚተወው መሆኑ ይቀራል፡፡ የመንግሥት ልማታዊ ተነሳሽነት ችሮታ ሳይሆን፣ የህዝብ መብትና ልማታዊ ግፊት ውጤት ይሆናል፡፡ መንግሥት ስለፈለገ የሚከፍተው፣ ሳይፈልግ ደግሞ የሚዘጋው የልማት ቧንቧ መኖሩ ይቀራል፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ተፈጥሮ የምንመለከተው ይህንኑ ሞጋች ሕብረተሰብ ነው፡፡ ሞጋችነቱ ገና ይበልጥ መጠናከር ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለመነሻ ያህል ግን ለመብቱና ጥቅሙ የሚሞግት ሕብረተሰብ መፈጠሩ፣ በኢትዮጵያ ለውጡን ወደሌላ ከፍታ ለማውጣት የሚያስችል የተከማቸ አቅምና አገራዊ መልካም ዕድል ነው፡፡

ኪራይ ሰብሣቢነት የሥርዓት አደጋ መሆኑን የተገነዘበ ህዝብ መፈጠሩም ሌላው በተከማቸ ደረጃ የሚገኝ የለውጥ አቅም ነው፡፡ ኪራይ ሰብሣቢነት የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ የተዋወቀውና ጥቅም ላይ የዋለው ከተሃድሶ ንቅናቄው በኋላ ጥቂት ቆይቶ ነበር፡፡ መጀመሪያ ጥገኛ ዝቅጠት በመባል የተመላከተው ይህ ሀሳብ፣ በሂደት ካለአግባብ የመጠቀም ዝንባሌ በሚል፣ በመጨረሻ ደግሞ በፖለቲካ ኢኮኖሚ ተንታኞች በተሰጠው ኪራይ ሰብሣቢነት በሚል ስያሜ ወደመገለጽ ተሸጋግሯል፡፡ ካለአግባብ ተጠቃሚነት ከሚለው ራሱን በራሱ ከሚያብራራ ሀሳብ በመለስ፣ ጥገኛ ዝቅጠት ሆነ ኪራይ ሰብሣቢነት የሚለው አገላለጽ የተሟላ ግንዛቤ ይያዝባቸው ዘንድ ብዙ ልፋት ጠይቀዋል፡፡ በመጨረሻ ግን እነዚህ በምንገኝበት መድረክ የፈተናዎች ሁሉ ምንጭ የሆኑ ጽንሰ-ሀሳቦች ከሞላ ጐደል ሉበዙ ሰው ስሜት በሚሰጥ ደረጃ ግንዛቤ የተያዘባቸው ሆነዋል፡፡

ባለፉት የተሃድሶ ዓመታት የተፈጠረው የተከማቸ አቅም ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በገጠር ደረጃ በደረጃ ለገበያ ብሎ የሚያመርት ሕብረተሰብ መፈጠር ጀምሯል፡፡ ተሃድሶው በተጀመረ ሰሞን ለቦናፖርቲስታዊ ዝቅጠት መሠረት ይሆናል ተብሎ የተሠጋው አርሶ አደር በገበያ የተሳሰረና ለጥቅሙ የሚሞግት መሆን ጀምሯል። አርሶ አደሩን ከልቡ የሚወደውና

የሚያከብረው ኢህአዴግ፣ "ገበሬው በዚህ ሁኔታ ላይ መገኘቱ ሥርዓቱን ለአደጋ ያጋልጠዋል" ብሎ በማመን፣ እርካታ የማይሰማውና ሁሌም ለለውጥ የሚባትል ሕብረተሰብ ለመፍጠር ባደረገው እንቅስቃሴ፣ የአገራችን አርሶ አደሮች ሰፊ ለውጥ አምጥተዋል። ምርታማነትን ከገበያ ጋር አስተሳስሮ ለማሳደግ በተካሔደው ጥረት፣ ከራሳቸውና ከቤተሰባቸው ፍጆታ ባሻገር ገበያን እያሰቡ የሚያመርቱ አርሶ አደሮች መፈጠር ጀምረዋል። ድሮ ለምርታቸው የሚያገኙት ዋጋ ምንም ይሁን ምን፣ ገበያ የሰጣቸውን ተቀብለው ይሔዱ የነበሩት የአገሪቱ ገበሬዎች፣ አሁን ለዋጋ ግብረ-መልስ የሚሰጡ መሆን ጀምረዋል። የጤፍ ዋጋ ወደቀ፣ የበቆሎ ዋጋ አሽቆለቆለ፣ የማዳበሪያና ምርጥ ዘር ዋጋ አሻቀበ ብለው የሚሞግቱ ገበሬዎች ተፈጥረዋል። መንግሥት የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር ስንዴ ከውጭ መግዛቱን የሚቃወሙ ገበሬዎች ሆነዋል።

በ2008 ዓ.ም. በምሥራቅ ጐጃም ዞን አዋበል ወረዳ የተንጣለለ የስንዴ ምርት ጉብኝት ስናደርግ ድንገት ያገኘሁዋቸውን አርሶ አደሮች "ምን ችግር አለ?" በማለት ጠይቄያቸው ነበር። ላቀረብኩት ድንገተኛ ጥያቄ ከአርሶ አደሮቹ መካከል አንዱ ቆጣ ባለ ድምጽ "ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ከካናዳ ስንዴ መግዛትህን አቁም ብለህ ንገርልን፣ የገበያና የዋጋ መውደቅ ሥጋት እንጅ ሌላ ችግር የለንም" የሚል ምላሽ ሰጠኝ። ድሮ ያለ የሌላቸውን ምርት፣ በገና ሰሞን ለገበያ ዘርግፈው ባገኙት ዋጋ ይሸጡ የነበሩ ገበሬዎች፣ አሁን አሁን ምርታቸውን ከሚያገኙት ዋጋ ጋር አያይዘው በተመጠነ ደረጃ ለገበያ እያቀረቡ፣ ዋጋን ብቻ ሳይሆን ገበያንም የሚቆጣጠሩ መሆን ጀምረዋል: : ከዚህም አልፎ ባላቸው አቅም የከተማውን ህዝብ በሸማችነት ተመልከተው አቅርቦትን በመቆጣጠር ፍላጐትን ተገዥዎቸው ለማድረግ ይሠራሉ። በዚህ የተነሳ በተሃድሶ እንቅስቃሴው መጀመሪያ ላይ የሥጋት ምንጭ ተደርጐ ይታይ የነበረው የተበተነ አርሶ አደር፣ አሁን አሁን በከፊልም ቢሆን የተደራጀ፣ በገበያ መመራት የጀመረና አስተማማኝ የለውጥ ግፊት አመንጭ ወደ መሆን ተሸጋግሯል። ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ ደረጃ በደረጃ መከማቸት የጀመረ የለውጥ አቅምና ከምንም ነገር በላይ ጐልቶ ሊታይ የሚገባው መልካም ዕድል ነው።

እነዚህ አቅሞችና መልካም ዕድሎች መፈጠር በመጀመራቸው ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በተለየና በተሻለ ደረጃ ለለውጥ የምትመች አገር ሆናለች። የተሃድሶ እንቅስቃሴው ልማትን ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊነትን በማዳበር መርሕ በመመራት አገሪቱ ያለማቋረጥ ወደፊት እንድትራመድ አድርጓል። ይህም ሆኖ በእስካሁኑ ጉዞ ለለውጥ ተፈላጊው መነሻ መሠረት ስለተጣለ ብቻ ቀጣዩ ጉዞ የሰመረ ይሆናል ማለት አለመሆኑ ሊስተዋል ይገባዋል። "እያንዳንዱ ድርጊት የራሱን ተጻራሪ ድርጊት ማስከተሉ አይቀርም" በሚለው የፊዚክስ ሕግ በመታገዝ ሕብረተሰብን ለመተንተን መሞከር የራሱ አስቸጋሪነት እንደሚኖረው ባያጠያይቅም፣ በትግሉ ከተፈጠሩት አዎንታዊ የተከማቹ አቅሞች በማይተናነስ ሁኔታ በዚህ ጉዞ የተፈጠሩ አሉታዊ የተከማቹ አቅሞች እንደሚኖሩ ሊሰት አይገባውም።

በእኔ አስተያየት አገራችን ባልታሠሠ ቀጠና ውስጥ እንድትገባ ካደረጓት ልዩ ልዩ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከፍ ሲል የተዘረዘሩት የሥጋትና የመልካም ዕድል ሁኔታዎች ናቸው። ዛሬ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት ከነበረችው የተለየች አገር ውስጥ እንገኛለን። ያኔ ዋናው ጉዳይ በሁሉም የሕይወት መስኮች ይታይ የነበረውን ማሽቆልቆል የማስቆምና ወደላይ የመነሳት ሙከራ ማድረግ ነበር። ሥራው ቀላል ያልነበረ ቢሆንም ብዙም የተወሳሰበና የተለየ የአስተሳሰብ ምጥቀት የሚጠይቅ አልነበረም። በሁሉም መስክ የተደረጉት ሙከራዎች መሳካት ከጀመሩና በተለይ ደግሞ ለሃያ አምስት ዓመታት ያህል በዕድገት ጐዳና ከተረማመድን በኋላ የገባንበት መድረክ ግን በጣም የተወሳሰበና ከመቸውም ጊዜ የተሻለ ብቃት የሚጠይቅ ሆኗል። በአንድ በኩል ከባድ ፈተናዎችና ከመስመር ሊያስወጡ የሚችሉ ችግሮች፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወደፊት ለመመንደግ የሚያስችሉ መልካም ዕድሎች በተከማቸ አኳኋን በእጃችን የገቡበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ስለሆነም የምንገኝበት መድረክ በተመዘገቡ መለስተኛ ውጤቶች በመኩራራት አቅጣጫ መሳትም ሆነ ወደኋላ መመለስ እንዳይኖር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተገነባው ላይ የላቀ ውጤት ማስገኘት የሚችል ተጨማሪና ውጤታማ ሥራ መሥራት የግድ የሆነበት መድረክ ሆኗል። በዚህ የተነሳ አዲሱ የኢትዮጵያ እውነታ ይህን ሂደት በመምራት ላይ ያለነው ወገኖችን ጨምሮ ከተወሰኑ ጉዳዮች በመለስ ብዙም የማናወቀው ነገር የሞላበት አዲስ ቀጠና ሆኗል። ለሩብ ምእተ ዓመት ወደላይ የተነሳቸው አገር በዚሁ የዕድገት አቅጣጫ ትቀጥል ዘንድ ይህን እውነታ የተገነዘበና ሲታቱን እየቀረፈ መልካም ዕድሎቹን ደግሞ እየተጠቀመና እያሰፋ የሚሔድ አመራር ያሻታል። ምንም እንኳ በፍጥነት ለመማር ዝግጁነቱና አሳታፊነቱ እስካለ ድረስ ይህን ማሟላት የሚቻል ቢሆንም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለውን ሁኔታ በትኩረት ለሚመለከት ሁሉ ይህን የተወሳሰበ መድረክ በብቃት ከመምራት አኳያ መቸገር እንደጀመርን ለመገንዘብ አያስቸግርም።

ቀጣዩ የለውጥ ሂደት በተከማቹት አዎንታዊና አሉታዊ አቅሞች መካከል በሚካሔደው ትግልና በሚፈጠረው የኃይል ሚዛን ልዩነት የሚወሰን መሆኑ አይቀርም። ይህን በትክክል መገንዘብ ሲቻል ብቻ በቀጣይ ትግል የለውጥ ኃይሎችን አቅም በማያቋርጥ ሁኔታና በትክክለኛ አቅጣጫ እየገነቡ ተፈላጊውን ለውጥ አሟልቶ ማምጣት ይቻላል። ዋናው ነገር በመንታ መንገድ ላይ መሆናችንን በትክክል መገንዘብና ከዚህ ለመውጣት በኃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስ ነው።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት፣

ጥቂት ሃሳቦች ከመንታ መንገድ በፍጥነት ለመውጣት፣

ኢህአዴግም ሆነ መላው ሕብረተሰብ በበቂ ደረጃ ባልተዘጋጁበት ሁኔታ የገባንበት አዲሱና ምናልባትም በአገራችን ታሪክ ውስጥ እጅግ የተወሳሰበው ይህ መድረክ የስኬት ውጤት ነው፡፡ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት የተረከብነውን እንደነበረው ወይም በጥቂቱ ብቻ አሻሽለን ብንቀጥል ኑሮ ይህ የተወሳሰበ ሁኔታ አይፈጠርም ነበር፡፡ ያሸለበችውን አገር ቀስቅሰን ዓለምን ባስደነቀ ፍጥነት ወደላይ ከፍ ስላደረግናት ግን ማናችንም በዚህ ደረጃ ባልገመትነው ያደገና የተወሳሰበ ሁኔታ ላይ ራሳችንን አግኝተነዋል፡፡ ይህን መድረክ በልዩ ጥንቃቄና የኃላፊነት መንፈስ በመምራትና መልክ በማስያዝ እስከተራመድን ድረስ ኢትዮጵያችን እንደገና ወደሌላ ከፍታ መውጣቷ፣ ህዝቦቿም እንደገና ለተሻለ ሕይወት መብቃታቸው አያጠራጥርም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አገርና ሕብረተሰብ መንታም ወይም መስቀለኛ መንገዶች ደረጃ ላይ ከደረሰ ከያዙት ትክክለኛ ጐዳና የመውጣት አደጋ በአያሌው ተደቅኖባቸዋል ማለት ነው። ስለዚህ መንታም ይሁን መስቀለኛ መንገድ ተፈልጐ የሚገባበት አማራጭ አይደለም፡፡ በእኛ ሁኔታ ከዕድገቱ ጋር የመጣ፣ ሳይወዱ የሚገፉበት የቀውስ ጊዜ ነባራዊ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን የቀውስ ሁኔታ ትርጉምና አደገኛ ውጤት በትክክል በመገንዘብ ለመፍታት ጥረት ማድረግ ይገባዋል። መልካም አመራር ያለው አገርና ንቅናቄ ራሱን በመንታ መንገድ ወይም የቀውስ ሁኔታ ላይ ሲያገኝ ይህን በሕብረተሰብ የዕድገት ሂደት ውስጥ ሊያጋጥም እንደሚችል አንድ ክስተት ተቀብሎ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ላለመቆየት መጠንቀቅ አለበት። ችግሩን ለመገንዘብም ሆነ ለመፍታት በቅን ልቦናና አሳታፊ መንገድና በጊዜ የለንም መንፈስ መረባረብ ይገባዋል።

ቀውሶች በግልም ሆነ በሕብረተሰብ ሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩ ያልታሰቡና እቅድ ያልተያዙ ድንገተኛ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ በዚህ ባህርያቸውም በጥንቃቄና በብስለት ካልተያዙ በስተቀር ግለሰቦችንም ሆነ ሕብረተሰብን ለከፋ ምስቅልቅልና ጉዳት ሊያጋልጡ የሚችሉ ናቸው፡፡ በግለሰቦች ላይ የሚደርሰውን ከፉ ነገር ወደጐን ብሎ በቀውስ የተመታ ሕብረተሰብ ለብዙ ዓይነት ጉዳቶች እንደሚጋለጥ በታሪክ ተደጋግሞ ታይቷል። ከብዙ የበለጸጉ አገሮች ታሪክ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በቀውስ ወቅት የመጀመሪያውና ትልቁ ጉዳት በሕብረተሰብ የሀብት ይዞታ ላይ ድሃውን የሚጐዳ ሽግሽግ የሚከተል መሆኑ ነው፡፡ በሁሉም የበለጸጉ አገሮች ውስጥ የተከሰቱት ቀውሶች መነሻና መድረሻ ይኸው የሕብረተሰብ የሀብት ይዞታ ሽግሽግ ነበር።

ከአሥር ዓመታት በፊት ያጋጠመው ዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ ቀውስ ለዚህ እንደአንድ ማረጋገጫ ሊቀርብ ይችላል። በዚህ ቀውስ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የመካከለኛ ገቢ መደብ አባላት እድሜ ልካቸውን ያጠራቀሙትን ቁጠባ አጥተዋል። በሞርጌጅ ከገዟቸውና ከፊል ዋጋቸውን ከከፈሉላቸው ቤቶቻቸው ተፈናቅለዋል። የጡረታ ዋስትናቸውን በጠራራ ፀሐይ ተዘርፈዋል።

በመንታም ሆነ በመስቀለኛ መንገድ መዳረሻነት የተፈጠሩና የሚፈጠሩ ቀውሶችም በዚህ ዓይነት የሚሊዮኖችን የድካም ውጤት ለጥቂቶች አሳልፎ መስጠትን ሊያስከተሉ የሚችሉ የኢኮኖሚ ሀብት ሽግሽግ መሣሪያዎች ይሆናሉ። ካልተጠነቀቅን በስተቀር በኢትዮጵያም አንድም አገራችን የፈጠረችውን ኃብት በቀላሉ ለባእድ ኃይሎች አሳልፈን የምንሰጥበት፣ አሊያም በራሳችን ጥቂት ስግብግቦች በጠራራ ፀሐይ የምንዘረፍበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። እናም መንታም ይሁን መስቀለኛ መንገድ ብዙም ልንቆይበት የማይገባ፣ ከዚያም አልፎ ይህን በመሰለው ሁኔታ የሚፈጠር ቀውስ ቢኖር የሀብት ሽግሽግ ድሃውንና መካከለኛውን መደብ በሚጐዳና የውጭና የውስጥ አልጠግብ ባዮችን ይበልጥ በሚያደልብ መንገድ የሚፈጸም እንዳይሆን አበክሮ መሥራት ይጠይቃል። በመንታ መንገድም ሆነ ባልታሰሰ ቀጠና ውስጥ ለገባችው አገራችን ይህን ጊዜያዊ ቀውስ መልካም ዕድሎቻችንን በማስፋትና ህዝብን በሚጠቅም አቅጣጫ እናልፍ ዘንድ ለሚከተሉት ጥቂት ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ይገባል። እነዚህንና ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያቀርቧቸውን ገንቢ የመፍትሔ ሀሳቦች በማካተት ይህን ጊዜያዊ ችግር ማለፍ ከተቻለ ጅምሩ የለውጥ ሂደት ወደታሰበለት ግብ መድረሱ የማይቀር ይሆናል።

ከሁሉ በፊት ከመንታ መንገድ ወጥቶ በትክክለኛው አቅጣጫ መጓዝና አገራችንና ህዝባችንን ለሌላ አዳዲስ ድሎች ማብቃት እንደሚቻል መግባባት የመፍትሔው መነሻ ሊሆን ይገባዋል። ይህን በመሰለው ሁኔታ ላይ የሚገኝ ሕብረተሰብ በግራ መጋባት ውስጥ ላለመግባት ተጠንቅቆ ሁኔታው ሊያጋጥም የሚችልና የሚታለፍም ጭምር እንደሆነ በማስተዋልና በመግባባት መራመድ ይገባዋል። በመሪዎችና በሕብረተሰብ ደረጃ መያዝ ካለበት ከዚህ አዎንታዊ አስተሳሰብ በተጨማሪ ቀጣዩ ጉዳይ በኢትዮጵያና በህዝቦቿ ላይ በደል ለማድረስ የሚራወጡና የአገራችንን ተስፋና መልካም ዕድል ሊነጥቁ የተሰለፉ የጥፋት ኃይሎችን ማስቆም ሊሆን ይገባዋል። እነዚህ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ በሕገ-ወጥ መንገድና በዝርፍያ መክበር የጀመሩ ኃይሎች ናቸው። የመንግሥትና የአገርን ጸጋ በሕገ-ወጥ መንገድ ለማግበስበስ የተሰለፉትን እነዚህን ኃይሎች ከማስቆምና እንዲሸማቀቁ ከማድረግ ውጭ ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ተስፋቸውን ሊጠብቁና ሊያለመልሙ አይችሉም። ስለዚህ በየክልሉ የሚገኙ የዝርፊያ ኃይሎችን ማስቆም፣ ሕጋዊ ወደሆነው አቅጣጫ ገብተው ደረጃውን በጠበቀ ጥረትና ሂደት ሠርተው ብቻ ወደሚከብሩበት አቅጣጫ መመለስ ያስፈልጋል። ይህን የብሔር ወይም የሃይማኖት ዘውግ በለየ ፍቅርና ጥላቻ በመመልከት ሳይሆን፣ በየትኛውም ክልል የሚገኝ አልጠግብ ባይ ህዝብና

አገርን የሚጐዳ ኃይል እንደሆነ ተወስዶ በሚመከተበተ አኳኋን መፈጸም ያስፈልጋል። ከዚህ ውጭ አንድም በብሔር አለያም በሃይማኖት ሽፋን በሚካሔዱ መጠቃቃቶች የጋራ ጥፋትን ማስቀረት አይቻልም። ብሔርና ሃይማኖትን ሳይለዩ ህዝብና አገርን የሚጐዱ ዘራፊዎችን በጋራ በማጥቃትና በመከላከል የአገርና የህዝብን ጥቅም ማስፋት ያስፈልጋል።

በዚህ ሂደት የውጭ ኃይሎች ከኢትዮጵያ ላይ እጃቸውን እንዲያነሱ ማድረግ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ኢትዮጵያ የህዝቦቿ ብቻ ነች። የውጭ ኃይሎች አይደለችም። ለዘመናት በተከፈለው መስዋዕትነት የራሷ ህዝቦች ሆና እንደኖረችው ዛሬም የህዝቦቿ ሉዓላዊ ይዞታና ጉዳይ ሆና ብቻ መቀጠል አለባት። ይህም ሆኖ የምንገኘው ከድኅነት በፍጥነት መላቀቅ የጀመረች፣ ሰፊ ገበያ በመሆን ላይ ያለችና ይህችን አገር ተቆጣጥሮ እንደጥገት ሊያልባት ለሚፈልግ የውጭ ኃይል ሁሉ ከፍተኛ ጉጉት መቀስቀስ በጀመረችበት ወቅት ነው። ይህ ብቻ ቀላል ለማይባል የውጭ ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት እንደሚያጋልጠን በመገንዘብ አገራችን የህዝቦቿ ብቻ ሆና መቀጠሏን ማረጋገጥ ይገባናል። መምጫው በማይታወቀው ሶሻል ሚዲያ ዘመን ላይ የመገኘታችንን እውነታ መነሻ በማድረግ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አገራችንን ከባዕድ ኃይሎች መጫወቻነት እንደሚታደግ መገንዘብ ያሻል። በዚያው ልክ ደግሞ በተለመደው የአርበኝነት መንፈስ ከየትም ይምጣ ከየት የህዝባችንን ሉዓላዊነት የሚገፍ ነገር እንዳይጫነን ማድረግ ይገባናል።

ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ከምንም ነገር በላይ ዴሞክራሲያችን ሲሰፋ ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የራሱ ባሕርይ ይዞ የተጀመረና እዚህ ድረስም ያመጣን ፍቱን የለውጥ መሣሪያ ነው። ይህም ሆኖ ከገባንበት ያልታሠሠ ቀጠና ጋር ተያይዞ በእጃችን ያለው ዴሞክራሲ በቂ እንዳልሆነ ተረጋግጧል። ስለዚህም ዴሞክራሲያችን ይበልጥ መስፋትና መዳበር ይገባዋል። አገራችን ይበልጥ ነጻና ሰፊ ዴሞክራሲ ጥቅም ላይ የሚውልባት አገር ልትሆን ይገባታል። ይህም በሕገ-መንግሥቱ የተደነገጉና ዋስትና የተሰጣቸውን ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመጠበቅና በስፋት በመጠቀም ሊገለጽ ይገባዋል። በተጨማሪም ከገባንበት አዲስ መድረክ የሚፈልቁ አዳዲስ ዴሞክራሲያዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም ሂደቱን ማስፋትና ማጐልበት ይገባል። ህዝብና ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በአገራቸው ጉዳይ ላይ በባለቤትነት የሚሳተፉበትን ዕድል የሚያጠቡ ዝንባሌዎችና ሕጐችን፣ አሠራሮችና ባሕሎችን በፍጥነት ማስተካከል ይገባል። የመቻቻል ባሕልን የሚያዳብሩ፣ በልዩነቶች ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል እያካሔዱ፣ በሚያስማሙ ነጥቦች ደግሞ የጋራ አገር ግንባታን በማጠናከር ኢትዮጵያን ወደሚይቀረው ዴሞክራሲያዊ የዳበረ የገበያ ሥርዓት ማሸጋገር አማራጭ የሌለው ይሆናል።

ዴሞክራሲን የማስፋት ጉዳይ ሲታሰብ ከምንም ነገር በላይ ለህዝቡ ሰፊ ምሕዳር መፍጠር ማለት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሁሉም ሕጋዊና ሰላማዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች

ተመሳሳይ ሰፊ ምህዳር ማረጋገጥን የግድ ይላል። የመድብለ ፓርቲ ሥርዓታችን በዚህ ረገድ ያለበትን ውሱንነት መነሻ በማድረግ ይህን ችግር በአጭር ጊዜ ለመቅረፍ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። በዚህም ላይ ልበ-ሰፊና አስተዋይ፣ በመቻቻልና ድርድር ልዩነትና አንድነትን እያስመሩ፣ የህዝብ ብይንን ተቀብሎ በመራመድ ማዕቀፍ የሚያስብና የሚሠራ ሕብረተሰብ ሆነን መገኘት ይኖርብናል። አሁን ያሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች አንጻራዊ ጥንካሬና ድክመት ምንም ይሁን ምን በመቻቻልና በተሳትፎ የጋራ አገር እየገነቡ ወደ ተተኪ ፓርቲ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ሽግግር የምናደርግበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል። ይህ መፍትሔ የራሱን ጊዜ የሚጠይቅ እንደሆነ በማስተዋል ከማንኛውም ያልተገባ ጥድፊያና አጉል ተፅዕኖ በራቀ ሁኔታ ዴሞክራሲያችንን የማስፋትና በፓርቲዎች መካከል የጋራ ጥንካሬን የሚፈጥር ሂደት እንዲጐለብት ማድረግ ያሻል። ከዚሁ በማይነጠል መልኩ ፕሬስ በአገር ጉዳይ ላይ ሰፊ የህሳብ ልውውጥ የሚካሔድበት ነጻና ዴሞክራሲያዊ መድረክ ሆኖ እንዲያብብ ጥረት መደረግ አለበት። እዚህም ላይ መቻቻል፣ ከጭፍን ፍቅርና ጥላቻ የራቀ አቀራረብ መዳበር ይገባዋል። በመንግሥት እጅ ያለው ሚዲያ ከፍርሀት፣ አድልዎና የባለሥልጣናት ያልተገባ ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆኖ የተለያዩ ሀሳቦች በነጻነት የሚንሸራሸሩበት መድረክ ሆኖ ማገልገል አለበት። የግሉ ፕሬስም በኃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

የአገራችንን ዴሞክራሲያዊ ምሕዳር የማስፋት ጉዳይ ሲታሰብ በሲቪል ሰርቪሱና ከዚያም ውጭ ያሉትን ምሁራን ቀጥተኛና ሰፊ ተሳትፎ ማጐልበት የሂደቱ የማይነጠል አካል መሆን ይገባዋል። አገራችን ባልታሠሠ ቀጠና ውስጥ ባለችበት በዚህ ወቅት ምሁራን ልዩ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም። እስካሁን የተጓዝንበትና የደረስንበት ሂደት ከምሁራን ተሳትፎና የትግል አስተዋጽኦ ውጭ እንዳልሆነው፣ አሁን ያለው የመንታ መንገድም ሆነ ከዚህ ወጥተን የምንገባበት አዳዲስ የለውጥ መድረክ ከምሁራን ተሳትፎና ገንቢ አስተዋጽኦ ውጭ ይሠምራል ተብሎ አይታሰብም። በመሆኑም ከመቼውም ጊዜ የላቀ የምሁራን ተሳትፎ ለአገራችን እጅግ አንገብጋቢ የሆነበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል። ፕሮፌሽናሊዝም እንደ አንድ ወቅታዊና አማራጭ የሌለው መፍትሔ ተግባር ላይ እንዲውል መደረግ አለበት። ይህም ምሁራን ከማንኛውም ዓይነት ራስ ወዳድነት ርቀው አገርንና ህዝብን ማዕከል ባደረገ አኳኋን የመንቀሳቀስ ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ሳይዘነጋ መሆን አለበት። ራስን ማዕከል በማድረግና የአጭር ጊዜ ጥቅሞችን በማስላት ላይ የተመሠረተ ጉዞ ከመንታ መንገድ እንደማያወጣና በተሳሳተው አቅጣጫ እንድንጓዝ የሚያደርግ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ምሁራን አገራዊ ሚናቸውን እንዲጫወቱ መድረኩን ማስፋትና አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል።

በእርግጥ ዛሬም ሆነ ነገ በፕሮፌሽናሎች ብቻ የማይሠሩ፣ ብቃት ያላቸውን የድርጅት ካድሬዎች የግድ የሚሉ ዘርፈ ብዙ የፖለቲካ ተግባራትም ይኖራሉ። ለሥልጣን የሚወዳደሩ

ፓርቲዎች ገና ከፋካከር ወቅት ጀምሮ ህዝብን በማስተማርና ደጋፊያቸውን በማብዛት ሥራ ላይ መጠመዳቸው አይቀርም። ሥልጣን ከያዙ በኋላም ህዝቡን በገቡት ቃል መሠረት አስተባብረው ወደ ለውጥ መምራት ይገባቸዋል። ይህም ከፕሮፌሽናሎች ባሻገር በካድሬዎች የሚከናወን ራሱን የቻለ የለውጥ ተግባር እንደሚኖር ያሳያል። ስለሆነም ልክ እንደፕሮፌሽናሎች ሁሉ ህዝብን በቅንነት እያገለገሉ፣ እያነሳሱና እያደራጁ ለለውጥ የሚያረባርቡ ካድሬዎች ማስፈለጋቸው አያጠራጥርም:: ስለሆነም ፖርቲው የፕሮፌሽናሎች መንግሥት አቋቁሞ ይህን በጥቂት ምርጥ ካድሬዎች አቅም እያንቀሳቀሰ፣ በዋነኛነት በፖለቲካዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ተግባራት ላይና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በብዙኃን አደረጃጀት አማካይነት ዓላማውን ዳር ለማድረስ ትኩረት ሊሰጥ ይገባዋል:: ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራው ላይ በማተኮር፣ ሥልጣን የፓርቲ አባላት የግል ብልጽግና መሣሪያ ሳይሆን፣ አገር የመለወጫና የህዝብ ችግር መፍቻ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል:: በየደረጃው ይህን ለመምራትና ለመፈጸም የሚችሉ ካድሬዎችን መገንባት፣ ተሳትፏቸውን ማጐልበትና ለዚህ የሚያበቃ ውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ እንድያብብ ማድረግ ያስፈልጋል።

የአገራችን ወጣት ወንዶችና ሴቶች የነገው ዘመን ተረካቢዎች በመሆናቸው ከእነርሱ ተሳትፎ፣ መብትና ጥቅሞች መረጋገጥ ውጭ ስለነገዋ ኢትዮጵያ ፈጽሞ ማሰብ አይቻልም። በመሆኑም አገራዊ ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ እንዲሰፋ በማድረግ ከመንታ መንገድ የመውጣት ጉዳይ ወጣት ወንዶችና ሴቶች በዚህ ዕድል በሰፊው እንዲጠቀሙ ማድረግን የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባዋል:: ወጣቶች ሰፊ ፍላጐት አላቸው:: ይህም ሁሌም እያደገና እየዳበረ የሚሔድ ነው:: ይህ ፍላጐት የሚያስከትላቸው ጥያቄዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ ካልተስተናገዱ በስተቀር በኃይልና ግጭት መንገድ መገለጻቸውና ይህም ሕብረተሰብን የሚጐዳ እንደሆነ በራሳችን የቅርብና ሕያው ልምድ የተረጋገጠ ነው:: ስለሆነም የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ ከማስፋት ጋር ለወጣቶቻችን ትርጉም ያለው ተሳትፎና ተፅዕኖ ኢድራጊነት ሰፊ ዕድል የማጐናጸፍ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ይሻል:: ዛሬን ለማቃናትና ነገን መልካም ለማድረግ የሚቻለው በወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ብቻ ነውና::

ዴሞክራሲያችን ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያንን ጭምር የሚያቅፍና የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባዋል:: የሌላ አገር ዜግነት የወሰዱትም ሆኑ ያልወሰዱት ሁሉ በአገራቸው ጉዳይ ያገባቸዋልና:: ምንም እንኳ አገራችን ድርብ ዜግነት እንደማትፈቅድ በሕገ-መንግሥቷ የደነገገች ብትሆንም የትውልደ ኢትዮጵያውያንን ፍላጐትና መብት መነሻ በማድረግ ተሳትፏቸውን ለማረጋገጥ የተወሰኑ እንቅስቃሴዎችን ስታደርግ ቆይታለች:: ይህ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። ከአሁን በኋላ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል:: እናም ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያንን ለማሳተፍና ለማስተናገድ የሚያስችል ዴሞክራሲ መኖሩን

ማረጋገጥ ወቅታዊ ይሆናል። ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁና በዚህም ማዕቀፍ መንቀሳቀስ ግዴታ መሆኑን በሚያረጋግጥ አኳኋን ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን በአገር ግንባታ ተገቢ ሚናቸውን እንዲጫወቱ ማድረግ ለአገራችን ልዩ ተፈላጊነት ይኖረዋል። ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያንም ራሳቸውን ከሻዕብያና ግብፅ ተላላኪዎች ተፅዕኖ አላቅቀው በቀና መንፈስና ሰላማዊ የትግል ስልት ከነልዩነታቸው አገራቸውን ለመገንባት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ሩቅ በማይባል ጊዜ በአንዳች ምክንያት ያኮረፉና አገራቸውን ለማየት ዕድል ያላገኙ ሁሉ በነጻነት መንፈስ የሚመላለሱበት ሁኔታ መፍጠር ይገባል።

የፖለቲካ ፈተናዎችን ለመቋቋምም ሆነ በመልካም ዕድላችን ለመጠቀም የዴሞክራሲ ተቋሞችን ማጠናከር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ስለሆነም መንግሥታዊ የዴሞክራሲ ተቋማት ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ማድረግ ይገባል። ሕገ-መንግሥቱ መሠረተ-ሰፊ ዴሞክራሲን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል ቅኝት የተዋቀረ በመሆኑ ሁሉም መንግሥታዊ ተቋማት ዴሞክራሲያዊ አሠራርና ባሕላቸውን ማስፋት ይገባቸዋል። የህዝብ ምክር ቤቶች፣ የሰብዓዊ መብትና እንባ ጠባቂ ተቋማት፣ ፍርድ ቤቶችና የሕግ አስከባሪ ተቋማት ሁሉ ሕገ-መንግሥታዊ አቅጣጫውን ተከትለው መጠናከር ይገባቸዋል። በመንግሥትም ሆነ በግል ዘርፍ ሥራ ላይ ሆነው የአገራችን ህዝቦች የተጐናጸፏቸውን መብቶች የሚጥሱ ኃይሎችን በሕግ ተጠያቂ የማድረግ ብቃት ሊኖራቸው ይገባል። በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ህዝቦች የማያቋርጥ የተደራጀ ተሳትፎ እንዲኖሯቸው አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ይገባቸዋል። ከዚህ በማይተናነስ ምናልባትም በሚበልጥ ደረጃ የዜጐችና የማኅበረሰብ አደረጃጀቶች የሆኑ ልዩ ልዩ ተቋማት (ሲቪል ማኅበረሰብ) እንዲስፋፉና ሚናቸውን በተጠናከረ አኳኋን እንዲጫወቱ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። የህዝብ ማኅበራት፣ የሙያ አደረጃጀቶች፣ በአጠቃላይ መንግሥታዊ ያልሆኑ አገር በቀል አደረጃጀቶች ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል።

አገራችን ከመንታ መንገድ ወጥታ በትክክለኛው አቅጣጫ ትራመድ ዘንድ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ በተቀየሰለት አቅጣጫ መጓዝ ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ያለን ምርጫ የጨበጥነውን የእኩልነት ሥርዓት ማስቀጠል ብቻ ነው። የትላንት ጭቆናና ሆነ የዛሬ አዲስ ዓይነት የበላይነት አስተሳሰብ በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ቦታ የለውም። የቡሔርም ሆነ የሃይማኖት እኩልነት ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና ባገኘበት ሁኔታ ይህን በአንድ ወይም ሌላ መልክ ለመቀልበስ የሚደረግ ሙከራ ከየትኛውም ክልል ሆነ እምነት ይምጣ ሊመከት ይገባዋል። እነዚህ የፖለቲካ አቅጣጫዎች በጋራ ታምኖባቸው ተግባራዊ ከተደረጉ ኢትዮጵያ ከመንታ መንገድ ወጥታ ወደ ትክክለኛው የዕድገትና የለውጥ መንገድ ትገባለች። ከዚህም አልፋ የአስካሁን ድሎችን ጠብቃ ኦዲፒስ የዴሞክራሲ ድሎችን ትጐናጸፋለች።

በኢኮኖሚ መስክም እንደዚሁ ነው። ፈጣኑ ዕድገት የነብር ጭራ አስይዞናል። ስለዚህም የያዝነውን አቅጣጫና በእጃችን የገባውን መልካም ዕድል ፈጽሞ ልንለቀው አይገባንም። አሁንም ፈጣን ዕድገት የመጀመሪያው መፍትሔያችን ሆኖ መቀጠል አለበት። በገጠር የአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ማሳና ጉልበት ቀዳሚው የአገራዊ ሀብት መፍጠሪያ አቅማችን ነው። በከተሞች በአነስተኛና ጥቃቅን ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ዜጐች ዋናዎቹ መተማመኛ አቅሞች ናቸው። አገራዊ ባለሀብቱም እንደዚሁ። የውጭ ባለሀብቱ ደግሞ በደጋፊነት ሊሰለፍ የሚችልና የሚገባው ነው። ስለሆነም ለእነዚህ ልማታዊ አቅሞች ያለማቋረጥ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ (Enabling Condition) መፍጠር ይገባናል። አዳዲስ እሴትና አገራዊ ሀብት መፍጠር እንጂ አስቀድማ የተፈጠረችን ጥቂት ሀብት መቀራመት የጋራ ብልጽግናን በዘላቂነት ማረጋገጥ አይችልም። ስለሆነም አገራዊ የሀብት ፈጠራ ሂደቱ በልዩ ትኩረት መጠናከር አለበት።

አገራዊ ሀብት መፍጠር ቀዳሚ ሥራችን ከመሆኑ በማይተናነስ ደረጃ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልም ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ምልዓተ-ህዝቡ በተለይ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ከኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ገበታው ተቋዳሽ መሆን ይገባቸዋል። እነዚህን ያገለለ ልማት ከቀውስ በስተቀር ሌላ ውጤት እንደማይኖረው የቅርብ ዓመታት ግጭቶች ሁሉ ያረጋገጡት በመሆኑ ለፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ትኩረት መስጠት ይገባል። እንደእኛ በመሳሰሉ ታዳጊ አገሮች ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ ሁለት መንገዶች አሉ። አንደኛው ደርግ እንዳደረገው ጥቂት ሀብት ያፈሩ ሰዎችን ወርሶ ለሌላቸው በማከፋፈል ሥም የሚፈጸመው ነው። ሌላው ንብረት ከመውረስ በመለስ ቀደም ሲል የተዘነጉት ዜጐችና ብዙኀኑ ህዝብ በሀብት ፈጠራ እየተሳተፉ እንዲበለጽጉና የገቢ ልዩነት እየጠበበ እንዲሔድ ማድረግ ነው። የኋለኛው ባለፉት ሁለት ተኩል አሥርት ዓመታት በተግባር ተሞክሮ የተሻለ ውጤትአስገኝቷል። ስለሆነም ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን የማረጋገጥ ጉዳይ ሀብትን እየፈጠሩ መካፈልን እንጂ ሀብትን ሳይፈጥሩ ያለችውን በመቀራመት የሚፈጸም መሆን የለበትም። የደርግ ንብረት የመውረስ እርምጃ ድኅነትን በማካፈል ላይ ለተመሠረተ "ሶሻሊዝም" እንደዳረገን ልብ ይሏልና።

እነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ አገራዊ ፖሊሲዎቻችንን ፈትሾ ትከከለኛዎቹን ማጽናት፣ የተጣመሙትን ማቃናት፣ በኮንትሮባንድ የገቡ ፖሊሲዎችን ነቃቅሎ በትክክለኛ ፖሊሲዎች መተካት ያሻል። ከሁሉ በላይ ደግሞ አገራዊ የፋይናንስ ስምሪትን እየተጫጫነው ከመጣው ግብታዊ አቅጣጫ ነጻ ማውጣትና ሚዛኑ በትክክል በተጠበቀ አቅጣጫ እንዲሰማራ ማድረግ ይገባል። መንግሥት ከልክ በላይ ከሚሰማራባቸው ቦታዎች መውጣት መጀመር አለበት። የግሉ ሴክተር በልኩ እንዲሰማራ ባልተደረገባቸው መስኮች በሰፊው እንዲሰማራ ማድረግ ያሻል። መንግሥት በተመረጠ ጣልቃ ገብነት ጠቃሚና አስፈላጊ የኢኮኖሚ ሚና መጫወት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር

ኢንዱስትሪያዊ ስምሪትን በዋነኛነት ለአገራዊ ባለሀብት መተው ይገባዋል፡፡ በተጨባጭ እንደሚታየው መንግሥት ግዙፍ የኢንዱስትሪ ተቋማትን የማስተዳደርና በውጤታማነት የመምራት አቅሙ ከፍተኛ ውሰንነት አለበት፡፡ ስለዚህም የብድር ገንዘብ ማዘዝ ስለሚቻል ብቻ ልቅ በሆነ ስምሪት ውስጥ የሚገባበት ሂደት መቋረጥ ይገባዋል፡፡ የተመረጠ ጣልቃ ገብነት መርሕ ቃሉ ብቻ ሳይሆን ተግባሩም መጐልበት አለበት፡፡ በመሠረተ-ልማት መስክ የሚያደርገው ስምሪትም ከኢንዱስትሪ ልማት ጋር በተጣጣመ ቅኝት የሚፈጸም መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በተወሰነ ደረጃ ረዘም ያለ ርቀት የሚያስጉዘን የመሠረተ-ልማት ኢንቨስትመንት ያካሒድን መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ለኢንዱስትሪ፣ በተለይ ለገጠር ቀላል ኢንዱስትሪ መስፋፋት ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ከመንታ መንገድ ለመውጣት የቀረቡት እነዚህ ጥቂት ሀሳቦች አገራችን ላለፉት ጥቂት አሥርት ዓመታት የተመራችባቸውንና ዛሬም ተግባራዊ እያደረገቻቸው የምትገኘውን ውጤታማ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች መነሻ በማድረግ ለውይይት መነሻ ሆነው እንዲያገለግሉ በማሰብ የቀረቡ ናቸው። ከመንታ መንገድ በፍጥነት ለመውጣት እንችል ዘንድ እያንዳንዳችን ያለንን እውቀትና እውነት በማበርከት፣ በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ሁሉ መልካሙን ለመሥራት፣ በተለይ ደግሞ ለአገራችንና ለህዝባችን ሕይወት መቃናት ልንጠቀምበት ይገባናል።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት፣

ማጠቃለያና መሰናበቻ ወግ፣

በእኔ አመለካከት ኢትዮጵያ ከደርግ ውድቀት በኋላ የተጓዘችበት የሀያ ስድስት ዓመታት ወይም የቅርብ ዓመታቱ የዘመናዊ ታሪክ ሂደት (Contemporary History) ከሞላ ጐደል ከፍ ሲል የተገለጸውን ይመስላል። ይህን የታሪክ ሂደት በትክክል ለመተርጐም ኢህአዴግ ገና ከጠዋቱ አሳካዋለሁ ብሎ አልሞ የተነሳውን ግብ ታሳቢ ማድረግ የሚገባ ቢሆንም፣ የሃያኛው ከፍለ ዘመን የቀኝ ከንፍ ታዋቂ ዲፕሎማት የሆኑት ሔንሪ ኪሲንጀር በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፍ ማጠቃለያ ላይ እንደገለጹት የታሪክ አተረጓጐም መቼም ቢሆን ከመ·ግት የፀዳ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም:: እንደስድሳዎቹና ሰባዎቹ ትውልድ በተለይ ደግሞ እንደኢህአዴግ አይነት አርቆ ተመልካች ድርጅት ሂደቱን ካልመራው በስተቀር አብዛኛውን ጊዜም "የታሪክ ትርጉምም ተፈልጐ ሊገኝ እንጂ ሊታወጅ"[113] አይችልም። ኢህአዴግን የመሰለ የነበረውን እንደነበረ ለማቆየት ሳይሆን አገር የመለወጥ ራዕይ አንግቦ በመንቀሳቀስ፣ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ትውልድ የሚሠራውን እያወጀ፣ ያወጀውን ደግሞ እየፈጸመ፣ እንደገናም ከፈጸመው በመነሳት ሌላ ግብ እያወጀና ያንንም እየፈጸመ የተጓዘ ነውና የታሪክን ትርጉም አስቀድሞ ተገንዝቦ በከፈተው አዲስ ቦይ ማስጓዝ ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ የአገሮች ሂደት አስቀድሞ የተተለመለት የጉዞ መስመር ላይ ጥገኛ (Path Dependent) ነውና።

ይህን ድምዳሜ በአገራችን ስለፈው·ዳሊዝም መገርሰስ፣ ስለመሬት ከፍፍል አስፈላጊነት፣ ስለብሔርና የሃይማኖት እኩልነት፣ ስለሴቶች መብት፣ በኋላ ደግሞ ስለደርግ አምባገነንነትና ውደቀት ቀዳሚ ትንታኔ እያቀረበ ታግሎ ያታገለውን ትውልድ ገድሎች በመዘርዘር ማረጋገጥ ቢቻልም፣ የዚሁ ንቅናቄ አካል የሆነውንና በኢህአዴግ የተመራውን የአርባ ዓመታት የለውጥና የሃያ አምስት ዓመታት የአገር ግንባታ ጉዞ ዋና ዋና መገለጫዎች በጥቂቱ በማስታወስ ብቻ ማረጋገጥ ይቻላል::

ኢህአዴግ መጀመሪያ ደርግን "በተራዘመ የገጠር ትግል አሸንፋለሁ" አለ:: እንዳለውም አደረገው:: ቀጥሎም "የሽግግር መንግሥት እመሰርታለሁ" አለ:: ይህም ተፈጸመ:: "በህዝብ ተሳትፎ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት ተዘጋጅቶ በህዝብ ወሳኝነት ይፀድቃል" እንዳለው ይህንም አደረገው:: "የዕዝ ኢኮኖሚን በገበያ ኢኮኖሚ እተካለሁ" ብሎ የገባው ቃል ኪዳንም በተሳካ ሁኔታ ተከናወነ:: ምርጫዎች ማካሔድና የህዝብን ሉዓላዊነት ማከበር፣ ፌዴራላዊ ሥርዓት ማደራጀት፣ በማኅበራዊና ኢኩኖሚያዊ መስክ ፈጣን ዕድገት ማምጣትና የህዝብን

ተጠቃሚነት ደረጃ በደረጃ ማሳደግ ሁሉ በተግባር የተተረጐመ፡ የኢህአዴግ ቃል ኪዳኖች ነበሩ፡፡ አሁን ደግሞ "አባይን እንገድባለን" አለ፡፡ መላ ኢትዮጵያውያንን ይዞም አደረገው፡ ፡ ኢትዮጵያንም እንደገና ወደታላቅነት ምኩራቧ መመለስ ጀምረናል። እናም ይህ ትውልድ በተጨባጭ የማሽቆልቆልን ታሪካዊ ጉዞ ገትቶ፣ ወደላይ በሚደረግ የዕድገት ጉዞ የተካ ነውና፣ በቃሉ የኖረና ያሰበውን የፈጸመ፣ በታሪክ ሂደትና ጉዞ ላይ ንቁ ተፅዕኖ ያሳረፈ ነው፡፡ ይህስ ታሪክን ባሰብክውና በከፈትክለት ቦይ፣ በወሰንከለት አቅጣጫና ፍጥነት ማስጓዝ አይደለምን? ከዚህ በመነሳት ነው የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር የተፋለመው የለውጥ ትውልድ፣ በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ ላለፉት አርባ ዓመታት የተጓዙችበትን አቅጣጫ በመሐንዲስነት የቀየሰው የስድሣዎቹና የሰባዎቹ ታጋይ ትውልድ፣ ህዝብን ይዞ ታሪክ የቀየረ ትውልድ ነው ሊባል የሚገባው፡፡

በእርግጥ ታሪክ ሠሪው ሰፊ ህዝብ በብቃት የሚመራው ሲያገኝ፣ በታቀደ አካኋን የሚሠራ አዲስ ታሪክ መኖሩ፣ ይህንም ታሪክ ገና ከጠዋቱ በአዋጅ አስነግሮ መጀመርና ዳር ማድረሱ አያስቸግርም፡፡ ባለፉት አርባ የትግል ዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የራሱን ሚና በመጫወት ሂደቱን ከቀረፀው የአመራር ቡድን በአንዱ የቀረበው አተያይና ትርጉም ከፍ ሲል የተዘረዘረውን ይመስላል፡፡ ኪሲንጀር እንዳሉት ሌሎችና ቀጣይ ትውልዶች ደግሞ የራሳቸው አተያይና ትርጉም ይኖራቸው ይሆናል፡፡ ያም ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ በተቻለ መጠን እውነታው ሳይዛነፍ እንዲቀርብ የቻልኩትን ያህል ጥረት አድርጌያለሁ ብዬ አስባለሁ። ሂደቱን በመተንተን፣ አዝማሚያና እንድምታዎችን በማመላከት ጉዳይ ላይ ደግሞ በነጻነት መቅረብን መርጫለሁ። ይህም የ"ሁለት ምርጫዎች ወግ" በሚለው የመጀመሪያ መጽሐፌ ላይ እንደገለጽኩት የታሪክ ጸሐፊያን በአንድ በኩል እውነታውን እንዳለ የማቅረብ ግዴታ ስላለባቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሂደቱን በገባቸው መልክ የመተርጐም ነጻነት ስላላቸው ነው፡፡ ስለዚህም በጥሬ ሐቆች ላይ ተስማምቶ በአተረጓጐምና አተያይ ጉዳዮች ላይ ግን መለያየትና ጤናማ ሙግት መቀስቀስ ይገባል፡፡ ይህ መጽሐፍ ለዚህ አስተዋጽኦ ካበረከተ ግቡን አሳከቷል ብዬ አምናለሁ፡፡

መሰናበቻ ወግ፣

ይህ መጽሐፍ በሚያዝያ ወር 2007 ዓ.ም ተጀመረ፡፡ የመጀመሪያው ረቂቅ ያዘ ለቀቅ ከበዛበት አምስት ወራት በኋላ በነሐሴ መጀመሪያ ላይ ተጠናቀቀ፡፡ መጀመሪያ ላይ ከኢህአዴግ ጉባዔ በፊት ታትሞ ለንባብ እንዲበቃ የማድረግ ፍላጐት ነበረኝ፡፡ ነገር ግን በረባ ባልረባው ምክንያት እስከ ጉባዔው ማጠናቀቂያ ድረስ ሳይቋጭ ቆየ፡፡ እየቆየ ደግሞ በራሳችን የአመራር ድክመት በተፈጠረው ምስቅልቅልና ይህን ለማስተካከል በሚካሄዱ የጋራ ሥራዎች በመጠመድ እያነሳሁ እየጣልኩ አቆየሁት። እስካሁን ወደህትመት ባለመግባቱ የኋለኞቹን

ዓመታት ትዝብቴን ለመጨመር እድል ቢሰጠኝም ያለቀ መጽሐፍ በእጄ ይዤ ለሁለት ዓመታት ተቀመጥኩ። መጽሐፉ በተጀመረበትና በተጠናቀቀበት ጊዜ መካከል ግን ላለፉት አርባ ሁለት ዓመታት ከኖርኩበት ድርጅት አመራር ጋር ለጊዜውም ቢሆን በሀሳብና በተግባር መሠረታዊ ልዩነት ፈጠርኩ።

ከአመራሩ ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ጠንከር ያለና በመርህ ደረጃ የሚፈረጅ የሀሳብ ልዩነት ላይ የደረሰኩት በረጅም ጊዜ ሂደት ነው። ቀደም ባሉት ጥቂት ዓመታት በሁኔታችን ባለመደሰትና የተቻለውን ያህል በተደረገው ጥረት ችግሮችን ሥር-ነቀል በሆነ መንገድ መፍታትና በትግሉ ለውጥ ማምጣት እያቃተን ሲሄድ አልፎ አልፎ ከአመራር መድረኮች ራሴን ያገለልኩባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች ነበሩ። በተለይ ደግሞ በ2004 መጀመሪያ ላይ ራሴን ከኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አግልዬ፣ ከድርጅቱ አመራር ሙሉ በሙሉ የመገለል ሃሳቤን በ10ኛው የብአዴን ጉባዔ ላይ አስፈፅመዋለሁ የሚል ቁርጥ ያለ ሃሳብ ላይ ደርሼ ነበር። በመሀል ቤት ግን የታጋይ መለስ ህልፈት አጋጠመ።

መለስ በድንገት ሲያልፍ ዋናው ጉዳይ "የትግል ኃይላችንን አለማመናመን ነው" ብዬ በማመን እንደገና ለመመለስ ወሰንኩ። "ለመገለል ያበቁኝ ምክንያቶች ምንም ይሁኑ ምን፣ በዚህ ወቅት ከድርጅቱ ኃላፊነት መልቀቅ ነውር ነው" ብዬ በማሰብም ወደድርጅቱ አመራር ኃላፊነት በሕጋዊ መንገድ ተመለስኩ። ከመለስ በኋላ ያለው ሽግግር የተቻለውን ያህል ሰላማዊና ምስቅልቅል የሌለበት እንዲሆን አቅሜ የፈቀደልኝን ያህል ለማበርከት ሞከርኩ። አስተዋፅዖው አረረም መረረ ሽግግሩና መተካካቱ በሰላም ተፈፀመ። ነገር ግን ከባድ ዋጋ የተከፈለበት ነበር። አንዳንዴ እንደገና ለመመለስ የወሰንኩበትን ቀን እስክረግም ድረስ የሚያስመርር ነበር። ይህም ሆኖ ከዛሬ ነገ ይሻላል በሚል ተስፋ የማይታለፍ ነገር ስላልነበር ትልቁን ስዕል እያየሁ በትንንሾቹ ከፋቶች ላለመንበርከክ እየተፍጨረጨርኩ ቀጠልኩበት።


ካርል ማርክስ "በሕይወታችን ለሰው ልጆች መልካሙን ነገር ለመሥራት ቆርጠን እስከተነሳን ድረስ ምንም ዓይነት ሸክም አይሰብረንም" ይላል። እኛም ህዝብን የማገልገል ከባድ ሸክም ሳይሰብረን ይሽው እስካሁን ተፋለምን። የኒዮ-ሊበራዝምና የኪራይ ሰብሣቢነት ጥቃቶች ሳያንበረክኩን አሁን ድረስ ዘለቅን። ዴሞክራሲን በድርጅት ውስጥና በሕብረተሰብ ደረጃ እያሰፈንን፣ ህዝብን የዳር ተመልካች ሳይሆን ዋናው የለውጥ ኃይል አድርገን ታገልን። ኢትዮጵያ ለበርካታ ምእተ ዓመታት የተጓዘችበትን የማሽቆልቆል ጉዞ የገታውን መሠረታዊ የትግል አቅጣጫ የተለምነው እኛ የስድሣዎቹና የሰባዎቹ የትግል ትውልዶች ነን። ለአርባ ምናምን ዓመታት በተካሔደ እልህ አስጨራሽ ትግል ህዝብን ይዞ በመፋለም ኃላቀርነትና ድኅነትን ድል መንሳት እንደሚቻል ያሳየነው ስኬታማ ትውልዶች።

ራሳችንን ሁሌም የትጥቅ ትግሉን በተቀላቀልንበት የወጣትነት ዕድሜ እያስቀመጥን የተጓዝንባቸው እነዚህ አርባ የትግል ዓመታት እንደቀልድ ሳይታወቀን ያለፉ ቢሆኑም፣ እንደዋዛ የማይነገር ውጣ ውረድ የበዛባቸው ዓመታት ነበሩ። አርባዎቹ የትግል ዓመታት፤ አርባ ከረምትና በጋ፣ አርባ ፀደይና መፀው፣ አርባ ዓቢይ ጾምና ረመዳን፣ አርባ ገናና መውሊድ፣ አርባ ሠርግና ተዝካር የተፈራረቁባቸው ዓመታት ብቻ አልነበሩም። ጦርነትና ሰላም፣ ማጥቃትና ማፈግፈግ፣ መቁሰልና መድማት፣ መሞትና መግደል የእለት ተዕለት መራር የሕይወት ገጠመኞቻችን የነበሩባቸውን ዓመታት ጭምር የያዙ ነበሩ። ድርቅና ረሐብን፣ ድካምና ሕመምን፣ ስቃይና እንግልትን ከህዝባችን ጋር በገፍ የተጐነጨንባቸው፣ እንባችንን ዋጥ አድርገን ውዶቻችንን በየሸለቆው የቀበርንባቸው ውድ የተጋድሎ ዓመታት ነበሩ። "የትግሉ ነው ሕይወቴ"ን እየዘመርን የተፋለምንባቸው አራት መቶ ሰማኒያ የመሥዋዕት አዋርሕ ነበሩ። "ያልተንበረከከነውንና ዘይንድይቦ ጐቦን"[114] እያዜምን መራሩን የትግል ሕይወት የተጋፈጥንባቸው ሁለት ሺህ ሰማኒያ የጽናት ሰሞናት ነበሩ። አዲስ አበባ ገብተንም ከግዙፎቹ ዓለም አቀፍ ተቋማትና መንግሥታት የሚመጡ ተፅዕኖዎችን በአስተሳሰባችን እንደፀናን የተፋለምንባቸው፣ ተፋልመንም ድል የነሳንባቸው፣ ነገር ግን ደግሞ ብርታታችን በእጅጉ የተፈተነባቸው ውድ ዓመታት ነበሩ። በጨለማነት በሚታወቀው ከፍለ ዓለማችን፣ ኢትዮጵያ የምትባል ብርሃን ደምቃ እንድትበራ ማድረግ የጀመርንባቸው፣ በእርግጥም አርባ ህዝብን ይዞ ታሪክ የመሥራት፣ አርባ የመሥዋዕትነትና የድል ዓመታት ነበሩ። የተመሰከረለት የመሥዋዕትና የድል ትውልድ ነበርንና።

በእነዚህ አርባ ዓመታት ስንቱን ሸፍጥና ከህደት ተመለከትን? "ራሳችንን ሳናበለጽግ ሌሎች ዜጐች እንዲበለጽጉ በር እንከፈት" እንዳልተባባልን፣ ይህን መሠረታዊ ቃል ኪዳን ያፈረሰውን ስንቱን ራስ ወዳድ አየነው? ሰማዕታቱን በቀበረ ማግስት ለብርቅርቅ የከተማ ሕይወት እጁን የሰጠ፣ አደራውን የበላ፣ ስንቱን ባስቀመጡበት ያልተገኘ ታዘብነው? ስንቱን ሕሊና ቢስ ሸፍጠኛስ አየነው? ኧረ ስንቱን?! ከእነዚህ ሸፍጠኞች ጐን ደግሞ ስንቱን ጀግንነትና ጽናት፣ ስንቱን ድፍረትና አይበገሬነት፣ ስንቱን ላመነበት ሟች ታጋይ ተመለከትን። ስንቷን የትግል አውራ፣ ስንቷን የሕዝብ ቤዛ፣ ስንቷን የጽናት ተምሣሌትስ ተመለከትን? ሥንቶችስ ነገን ከዛሬ የተሻለ ለማድረግ እሣት ከሚተፋ የጦር መሣሪያ ጋር እየተናነቁ በየተራራው ጥግ ወደቁ? ስንት ያልተዘመረላቸው የህዝብ ልጆችስ ቀድመውን አለፉ? ዛሬስ? ዛሬም እንደትላንቱ ከገጠር እስከከተማ ለህዝብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብትና ጥቅም ሲሟገቱ ውለው የሚያድሩ፣ አስቸጋሪውን የገጠር ሕይወት ተቋቁመው ክእያንዳንዷ የገበሬ ማሣ ከፍተኛ ምርት ለማፈስ የሚባትሉ፣ የተፈጥሮ ሀብታችንን በመጠበቅና በማልማት አገራችንን አረንጓዴ ለማልበስ ከድኅነትና ኋላ ቀርነት ጋር ግብግብ የገጠሙ ስንት ምርጥ ታጋዮችን ተመለከትን? እነዚህን ምርጥ የህዝብ ልጆች ይዘን ምን ሊሰነን ይችላል? ምንም!

የለርነ ገሥጋዥ የነገሬል ቦሮ ሁነሃ ፖሊ ዘሰቱ የነገሳዘኑ የጥፈራረዛነጥ ሽዚ፡፡ ዘዚህ ሁሉ መካከል ግን እምነትና ህዝብ ነበሩ፡፡ ዛሬም አሉ፡፡ ከልጅነት እስከአውቀት ያነገብነውና ማርከስ እንዳለው "ዓለምን ለማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ለመለወጥ" የተጠቀምንበት ጽኑ እምነት፡ ፡ ኢትዮጵያን ለማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ከማሽቆልቆል አውጥተን ሽቅብ ወደላይ መምጠቅ እንድትጀምር ያደረግንበት ታላቅ እምነት፡፡ ከዚህ እምነት ፊት ደግሞ ታጋይ ህዝብ አለ፡፡ ያውም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ፡፡ ብዙኅነትን ጸጋው አድርጐ፣ ከፉና ደጉን እየተሸከመና ለመብትና ጥቅሙ እየታገለ የኖረና ዛሬም እየታገለ የሚገኝ ታላቅ ህዝብ። ይህን ኃያል ህዝብ ይዘንስ ምን የሚሳነን ነገር ሊኖር ይችላል? ያለፈው ሩብ ምዕተ ዓመት የለውጥ ሂደት ምስክርነቱን እንደሰጠው ከሆነ ምንም ነገር ሊሳነን አይችልም። ይህን ባለገድል ህዝብ በዓላማና እምነት እንደጸኑ፣ በቅንነትና በታማኝነት ከማገልገል በላይ ዛሬም ሆነ ነገ ምንስ የእርካታ ምንጭ ይኖራል? ምንም!

ዘልዓለማዊ ክብር ለትግሉ ሰማዕታት!!



ማጣቀሳና ዋቢ መጽሐፍተ (*Endnotes*)

1. ፊልድ ማርሻል ዝኮብ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ ጀርመንን ወታደራዊ ኃይል ያንኮታኮተው የሶቭዬት ሕብረት ቀይ ሠራዊትመሪ ነበር። እጅግ የተዋጣለት ወታደራዊ ስትራተጂና ታክቲክ ነዳፊና የነደፈውንም በተግባር ላይ የማዋል ከፍተኛ ብቃት የነበረውየጦር መሪ ነበር።
2. ባሴ ሀብቴ፣ ጭጋግና ጠል እና ሌሎች፣ ገጽ 83-84
3. አሊስ አምስደን፣ ESCAPE FROM EMPIRE; The Developing World's Journey through Heaven and Hell. The MIT Press, Cambridge, Massachusettes, London, England, 2007. ገጽ 1-2
4. ዝኒ ከማሁ ገጽ 3
5. ዶናልድ ሌቪን፣ Greater Ethiopia; The Evolution of a Multiethenic Society. The University of Chicago Press, 1974 ገጽ 29
6. ጆቫኒ አሪገ. Adam Smith in Beijing, Lineages of the Twenty-First Century, Verso, London-New York, 1994፣ ገጽ 224.
7. ባሪንግተን ሙር "The Social Orign of Democracy and Dictatorship: Lord and Peasant in the making of the Modern World, Boston, Beacon Press 1966 ገጽ 20
8. ሃ ጁን ቻንግ፣ Kicking away the ladder, Development Startegy in Historical perspective, Anthem Press,London 2002 ገጽ 53-54
9. አዳም ስሚዝ፣ An Inquiry into the Nature and Causes of the Wealth of Nations London, Methucn, 1961 ቅጽ.II ገጽ141
10. ጆን ሜይራንድ ኪይንስ Essays in Persuasion,New York, Classic House Books, 2009 ገጽ199
11. ካኦሩ ሰጊሃራ፣ The East Asian Path of Economic Development: a Long term Perspective, Routledge, London and NewYork, 2003, ገጽ 78
12. አዳም ስሚዝ An Inquiry into the Nature and Causes of the Wealth of Nations ቅጽ.II ገጽ 202
13 ጆቫኒ አሪጊ The Long Twentieth Century: Money, Power and The Origins of our Times, Verso 1994 Verso, London-New York ገጽ 224.
14. ኪም ኞንግ ዩም From Despair to Hope: Economic Policymaking in Korea 1945-1979, A memoir by Korean Development Institute (KDI) ገጽ 40
15. መለስ ዜናዊ፣ የተሃድሶው መስመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ፣ 2003ዓ.ም.ገጽ 10-11,
16. ከርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር ጋዜጣ ኤፕሪል 03/2010 (እ.ኤ.አ)
17. ጆሴፍ ስቲግሊዝ፣ ዘ ጋርዲያን ጋዜጣ ጁላይ 25/2015
18. ጆናታን ዲ. አስትሪ፣ ፕራካሽ ሉነጋኒ እና ዬቪድ ፉርቸሪ Finance & Development, June 2016, Vol. 53, No. 2
19. ዳንኤል የርጊንና ጆሴፍ ስታኒስላቭ The The Commanding Heights; The Battle for the World Economy, Free Press, New york, London, Toronto, Sydney 2008 ገጽ 237
20. ናኦሚ ከሌን፣ The Shock Doctrine: The Risc Of Disaster Capitalism; Penguin Books Ltd., (2007) ገጽ 223
21. መለስ ዜናዊ፣ የተሃድሶው መሥመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ፣ 2003 ዓ.ም.ገጽ 10-11,
22. ጆሴፍ ስቲግሊዝ፣ Globalization and Its Discontents፣ Norton, ገጽ 26-27
23 ዝኒ ከማሁ ገጽ 30
24 ዝኒ ከማሁ ገጽ 30
25 ኬኒቺ አኖ፣ Learning to industrialize: From Given Growth to Policy-aided value creation, Routledge, London & New York, 2013, ገጽ 268
26 አርተር ሉዊሥ፣ Politics in West Africa, Allen and Unwin, London, 1965 52

27 ሞሃሙድ ሙሬዲኒ፣ The fate of Africa, From the Hopes of Freedom to the ... history of Fifty years of Independence, Public Affairs, New York 2005 ገጽ 53
28 መለስ ዜናዊ፣ Dead Ends; The Neo liberal paradigm and the African Renaissance ገጽ 195 / ያልታተመ ሥራ/
29 ዳንኤል ዬርጊንና ጆሴፍ ስታኒስላው The COMMANDING HEIGHTS; THE BATTLE FOR THE WORLD ECONOMY, FREE PRESS,NEW YORK LONODON TORONTO SYDNEY
30. ሕይወት ተፈራ Tower in the Sky, ADDIS ABEBA UNIVERSITY PRESS, 2012 ገጽ 167
31. ቢቨርሊ ጀ. ሲልቨርና ጆን ማርኮፍ "Forces of Labor: Workers' Movements & Globalization Since 1870, CAMBRIDGE UNIVERSITY PRESS,(2003) ገጽ 4
32. የኢህአዴግ የልማት፣ የሰላምና ዴሞክራሲ መርሐ ግብር፣ 1987 ዓ.ም. ገጽ 9
33. ዴቪድ ሃርቬይ፣ A Brief History of NEO LIBERALISM, Oxford University Press, (2005) ገጽ 23
34. ከሪስቲያ ፍሪላንድ፣ Sale of the Century: Russia's Wild Ride From Communism to Capitalism, Crown Business, NewYork (2000) ገጽ 169
35. ዴቪድ ሓርቬይ Seventeen Contradictions and the End of Capitalism OXFORD UNIVERSITY PRESS 2014 ገጽ 29
36. መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለዘጠነኛው የኢሠፓ ጉባኤ የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ያቀረቡት ሪፖርት 1977 ዓ.ም.
37. ጆ ስቱድዌል How Asia Works, Success and Failure In the World's most Dynamic Region. Grove Press, New York (2013) ገጽ 13-14
38. ጀን ድረዚ እና ኣማርቲያ ሲን፣ An uncertain Glory: India & Its Contradictions Press. Prinston. Edu. (2013) ገጽ፡ 112
39. ተፈራ ደገፈ፣ Minutes of An Ethiopian Century, Shama Books, 2006, ገጽ 28
40. የውጭ ፖሊሲ ምንነትና የጥናቱ ይዘት፣ (1976) ገጽ 59
41. ዝኒ ከማሁ ገጽ 64
42. መለስ ዜናዊ፣ ትግላችን ከየት ወደየት፣ የአብዮታችን የወደፊቱ አጠቃላይ አቅጣጫ በ1982 ዓ.ም.ለኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚና ለአባላት የቀረበ የውይይት ሰነድ ገጽ 113፣
43. ኔት ሲልቨር፣ The Signal and The Noise; Why so many predictions fail and some don't, The PENGUIN PRESS NEW YORK 2012 በሚል መጽሐፉ ላይ ካቀረበው የስኪፐ ጌትስ ጥቅስ የተወሰደ፣ ገጽ 417
44 መለስ ዜናዊ የቦና፣ፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋ ፣ 1993 (ያልታተመ ሥራ)ገጽ 21
45 ምንጭ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ግብርና ሚኒስቴር
46 ምንጭ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት የግብርና ሚኒስቴር
47 ምንጭ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት የግብርና ሚኒስቴር
48 አፍሮባሮሜትር ከሰላሳ በላይ የአፍሪካ አገሮች፣ በዴሞክራሲ፣ በአስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችላይ የህዝብን አስተያየትለማጥናት የሚንቀሳቀስ አንድ ገለልተኛ ፓን አፍሪካዊ የሪሰርች ተቋም ነው። አፍሮባሮሜትር መላሾች በሚጠቀሙበት ቋንቋና የቡሐር ውክልናን ከግምት ውሰጥ ባስገባ አካኋን የፊት ለፊት ቃለ ምልልሶችን ያካሂዳል። በኢትዮጵያ የሚገኘውና በኤቢሲአን የግል ኩባንያና አማካሪ ተቋም የሚመራው የአፍሮባሮሜትር የጥናት ቡድን ከ2,400 ጎልማሳ ኢትዮጵያውያን ጋር ቃለ-ምልልስ አድርጓል። ይህን የመሰለው አገር አቀፍ ከ+2 እስከ -2% በማደርስ የስህተት ሕዳግ 95% እመኣታ የሚጣልበት ውጤት ያስገኘ ጥናት ነው።
49. ሮበርት ማቲስና ሙሉ ተካ፣ Ethiopians' views of democratic government: Fear, ignorance, or unique understanding of democracy? Working Paper No.164 ገጽ 5
50. ዝኒ ከማሁ ገጽ I
51. The African Economy, October-December 2015, ገጽ 13
52. ዣራርድ ፕሩንዬና ኤሎይ ፊኬ [አርታዕያን]፣ Understanding Contemporary Ethiopia, Monarchy,

Revolution and the legacy of Meles Zenawi. HURST&COMPANY, LONDON 2015, ገጽ 357
53. ቻርሎት አሸተን ቢ.ቢ.ሲ. ሬድዩ (እ.ኤ.አ) ኖቬምበር 15 ቀን 2011
54. ዴቨ.ድ ስሚዝ፣ ዘ-ጋርዲያን ጋዜጣ የዴሴምበር 4 ቀን 2013 (እ.ኤ.አ) አትም
55. ኦውዮርክ ታይምስ የማርች 3 ቀን 2015 (እ.ኤ.አ) አትም
56. ባርባራ ቱችማን The March of folly; From Troy to Vietnam, An Abacus Book London, 1985, ገጽ 2
57. በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች 1994 ዓ.ም. ገጽ 12
58. ፍራንዝ ፋነን የተወለደው እ.ኤ.አ በ1925 የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት በሆነችውና በምሥራቅ ካሪቢያን በምትገኘው ማርቲኒክ በተባለች ደሴት ሲሆን በስነ -ልቦናና (psychiatry) በፍልስፍና ትምሕርት ተመርቆ ወደትግል ዓለም የተሰማራ በተለይ ለፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግሉ ከፍተኛ ንድፈ-ሀሳባዊ አስተዋጽኦ ያበረከተ ሰው ነው። The Wretched of The Earth (የምድራችን ነስቋሎች)፣ Black Skin White Masks (ጥቁር ቆዳ በነጭ ጭንብል) በሚሉና ሌሎች ሥራዎቹ በተለይ በአገራችን የስድሣዎቹ የትግል ትውልድ ላይ ከፍተኛ የአስተሳሰብ ተፅዕኖ ለማሳረፍ የበቃ ታጋይ ነው።
59 ማርቲን ሜሪድዝ፣ The fate of Africa; A history of Fifty years of Independence Public Affairs, New York 2005 ገጽ173
60 መለስ ዜናዊ Dead Ends and New Beginnings: The Neo Liberal paradigm and African Renaisance (ያልታተመ ሥራ) ገጽ 203
61 መለስ ዜናዊ የተሃድሶው መሥመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ፣ ሚጋ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ 2002 ዓ.ም. ገጽ 110
62 ግሬግ ሚልስ፣ ኦሉሲጉን አባላንጆ፣ ጀፍሪ ሄርስት እና ዲኪ ዳቪስ Making Africa Work; A Handbook for Economic Success CTP Printers,Capetown,South Africa 2017 ገጽ 241
63 Kjeld Erik Brodsgaard and Zheng Yongnian, The Chinese Communist Party in Reform, Routledge, London and NewYork, 2006 ገጽ 2
64. መለስ ዜናዊ የቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት አደጋ..... 1992ዓ.ም. ገጽ 36 (ያልታተመ ሥራ)
65. ጆሴፍ ስቲግሊዝ፣ በካርል ፖላኒ "The Great Transformation; The Political and Economic Origins of Our Time. BEACON PRESS, BOSTON ገጽ XI
66. ባሪንግተን መር "The Social Origin of Democracy and Dictatorship: Lord and Peasant in the making of the Modern World, Boston, Beacon Press 1966 ገጽ XII
67. መለስ ዜናዊ፣ የህዳሴው መሥመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ 2003 ዓ.ም. ገጽ 39-57፣
68. አሚያ ኩማር ባግቺ፣ The Developmental State in History & in the Twentieth Century; Regency Publications, New Delhi-2004 ገጽ 12
69. ሮበርት ዲ.ካፕላን፣ MONSOON; The Indian ocean and the future of American power, Random House 2010, ገጽ 265፣
70. አሚያ ኩማር ባግቺ፣ The Developmental State in History & in the Twentieth Century; Regency Publications, New Delhi-2004 ገጽ 18
71. ጆ ስቱድዌል፣ How Asia Works; Success and Failure In the World's Most Dynamic Region, Grove Press, New York ገጽ 131
72. ገዛኒ ከማሁ ገጽ... 201
73. ዝኒ ከማሁ ገጽ 182 እና ገጽ 76
74. መለስ ዜናዊ ፣ "የተሃድሶው መሥመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ" 2003ዓ.ም. አዲስ አበባ ገጽ 43፣
75. አለ.ስ አምስደን፣ Asia's Next Giant: South Korea and Late Industrialization, Oxford University Press, New York 1989 ገጽ 37
76. ጆ ስቱድዌል "How Asia Works: Success and Failure in the World's Most Dynamic Region.

Profile Books 2013 ገጽ 4
77. ኦ ዎን ቾል፣ The Korea story, Wisdom Tree (2009) ገጽ 73
78. ሃ ጁን ቻንግ፣ The Political Economy of Industrial Policy (1994) ገጽ 112-113
79. ስቱያዊል "How Asia Works: Success and Failure in the World's Most Dynamic Region.Profile Books (2013) ገጽ 131.
80. ሄንሪ ኤም ፖልሰን ጁንዩር፣ Dealing with China: An insider unmasks the new economic Superpower, Headline PublishingGroup, London (2015) ገጽ 18
81. ዝኒ ከማሁ ገጽ 20
82. አቶ ቻላቸው ሰጠኝ በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ያቀረበልኝን የድጋፍ ጥያቄ ፈቃደኝነቱን በመጠየቅ የቀረበ
83. www.africaneconomicoutlook.org/.../regional-development-and-spatial-inclusion/28 Jul 2015
84. ዝኒ ከማሁ·
85. መለስ ዜናዊ DEAD ENDS: The Neo Liberal paradigm and African Renaissance ገጽ 58 (ያልታተመ ሥራ)
86. ዝኒ ከማሁ· ገጽ 125
87. ዝኒ ከማሁ· ገጽ 116
88. ዊ ቾንግ፣China's Rural Industrialiazation Policy; Growing under orders since 1949 ገጽ 2
89. አዳም ስሚዝ፣ Wealth of Nations: PROMETHEUS BOOKS, NewYork, 1991, ገጽ 321
90. ከሪስ ብራማል፣ The Industrialization of Rural China, Oxford University Press, 2007 ገጽ 141
91. ቢቨርለ. ጄ. ሲልቨርስ፣ Forces of Labor: Workers' movements and Globalization since 1870; Cambridge University Press, 2003 ገጽ 3-4
92. ቢቨርለ. ጄ. ሲልቨርስ፣ Forces of Labor: Workers' movements and Globalization since 1870; Cambridge University Press, 2003 ገጽ4
93. አርከበ ዐቕባይ በፎርቹን ጋዜጣ የOctober 26/2015 ዕትም ያደረገው· ቃለ ምልልስ
94. አርከበ ዐቕባይ Made in Africa, ገጽ 79
95. ጁንግ ኤን ዉ፣ Race to the Swift; State and Finance in the Korean Industrialization, Columbia University, New York,1991 ገጽ 8
96. ጁንግ ኤን ዉ፣ Race to the Swift; State and Finance in the Korean Industrialization, Columbia University, New York,1991 ገጽ 10-1
97. ጆ ስቱድዊል "How Asia Works: Success and Failure in the World's Most Dynamic Region. ገጽ...Profile Books 2013 ገጽ 108
98. ጆቫኒ አሪገና ቢቨርለ. ጄ. ሲልቨር፣ Chaos and Governance in the Modern world System, University of Minnesota Press Minneapolis, London 1999 ገጽ 21
99. ፔሪ አንደርሰን NEW LEFT REVIEW September-October 2013 ገጽ 24
100. ዚ·ብግኒው ·ብሬዝዞንስክ. The Grand ChessBoard; American Primacy And It's Geostrategic Imperatives, Basic Books,1997 ገጽ 198
101. ጆቫኒ አሪገና ቢቨርለ. ጄ. ሲልቨር፣ Chaos and Governance in the Modern World System, University of Minnesota Press Minneapolis, London 1999 ገጽ.30
102. SERVING THE PEOPLE: The Governance Philosophy of the CPC, Party Building Books Publishing House, FOREIGN LANGUAGES PRESS, 2015 ገጽ 160-61
103. ሮበርት ዲ.ካፕላን Monsoon; The Indian Ocean & The Future of Amcriacan Power. Random House ገጽ 9፣

104. ቄን ሺሊፉ From Pivot to Rebalance: The Weight of Words in U.S.-Asia Policy Communication Context China.com ገጽ1
105. Christopher J. Pehrson, String of Pearls: Meeting the Challenge of China's Rising Power Across the Asian Littoral, p July 2006
106. Giovanni Arrighi & Beverly j.Silver, Chaos & Governance in the Modern World system 1999 ገጽ.30,
107. ናኦሚ ክለን The Shock Doctrine: The Rise of Disaster Capitalism, Penguin Books, London 2007 ገጽ 329
108. ከሪስ ብራማል፣ Sources of Chinese Economic Growth 1978-96, Oxford University Press, 2000 ገጽ 4
109. ናኦሚ ክሌን The Shock Doctrine: The Rise of Disaster Capitalism, Penguin Books, London 2007- ገጽ 268
110. መለስ ዜናዊ፣ ኢህአዴግ ከምሥረታ እስከ 2002፣ ገጽ 133፣ ታህሳስ 2003 ዓ.ም።
111. ካርል ማርክስ፣ ካፒታል ቅጽ 3 Moscow, Foreign languages Publishing House 1959 ገጽ 450-51
112. ኤሪክ ሆፈር፣ The True Believer Thoughts on the Nature of Mass Movements, HARPERPERENNAl, MODERNCLASSICS 2010 ገጽ 29
113. ሄንሪ ኪሲንጀር "World Order: Reflections on The Character of Nations and the Course of History ገጽ 374
114. የትግሉ ነው ሕይወቴ የኢህአፓ፣ ያልተንበረከከነውና ዘይንድይበ ጐቦ የበአዴንና ሕወሓት መገመሮች ናቸው።።



በአገራችን በመገንባት ላይ ያለው ሥርዓት በዚህ ረገድ ያጋጠመውን ፈተና ለመገንዘብ የራስ ወዳድነት ዓይነተኛ ምሣሌ ከሆነው "የአይጦች የሩጫ እሽቅድድም" (Rat Race) መነሳት ጥሩ ይሆናል። የአይጦች የሩጫ እሽቅድድም የሚባለው ተምሣሌታዊ አገላለጽ አንድ ነገር ለማግኘት ወይም ከአንድ አደጋ ለመሸሽ ከሚሸቀዳደም የአይጥ መንጋ ባሕርይ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ዓይነቱ እሽቅድድም ውስጥ የገቡ አይጦች በድንገት በመረጡት አንድ አቅጣጫ ግር ብለው ይጓዛሉ። "አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ" የሚል መተሳሰብ በሌለበት፣ አንዱ በሌላው አናት ላይ ተረማምዶ ለመቅደም ይሞክራል። ለአቅመ ደካማ፣ ለትንንሾቹ አይጦችም ሆነ ለነፍሰ ጡሮች ማሰብ ብሎ ነገር የለም። ጉልበት ወይ ብልጠት ያለው በውድ ጓደኛው ወይ የአገሩ ልጅ አይጥ አናት ላይ እየተረማመደም ቢሆን ሌላውን ጥሎ ይሮጣል። በዚህ ዓይነቱ የጋራ እብደት (Collective Madness) ውስጥ ሲገቡም ራሳቸውንና ማኅበረ-አይጣቸውን ለከፋ አደጋ ያጋልጣሉ። በመረጋገጥ ብዛት የሚሞተውና ለአካልና የመንፈስ ጉዳት የሚዳረገው ይበዛል። የማታ ማታ ደግሞ ወደተዘጋጀላቸው ወጥመድ ሰተት ብለው መግባታቸው የማይቀር ይሆናል። ይህን በመሰለው የአይጦች የሩጫ እሽቅድድም መርሕ የሚመራ ማንኛውም ፍጥረት ከዚህ ክፉ ዕድል (Predicament) ሊያመልጥ አይችልም። ቤተሰብም ሆነ ማኅበረሰብ፣ ካፒታሊዝም ይሁን ሶሻሊዝም፣ መንግሥትም ይሁን ፓርቲ በዚህ ራስን የማስቀደም መርሕ እስከተመራ ድረስ የስኬትን ሳይሆን የውድቀትን አዝመራ ማጨዱ አይቀሬ ይሆናል። በአገራችንም ከዚህ የተለየ አይሆንም። ይህ ቋሚ የተፈጥሮና የሕብረተሰብ ሕግ ነውና።

ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ስኬታማ ፓርቲዎች የራሳቸው ድል እስረኞች ናቸው። "ነብር በዋሽንት ይመሰጣል" ሲባል ሰምቶ፣ ይህን አደገኛ ፍጥረት ጥዑም የዋሽንት ዜማ ያስለመደ ከብት ጠባቂ ትንፋሽ ያጠረው ጊዜ በነብር እንደሚበላው ሁሉ፣ ህዝብን መልካም ነገር ያቀመሰ ፓርቲ ትንፋሽ ያጠረው እለትም እጣ ፈንታው ተመሳሳይ ይሆናል። ተሳክቶልኛል ብሎ በመኩራራት ወይም ችግር የለም ብሎ በመዘናጋት መልካም ከመሥራት ወደኋላ ያለ እንደሆን፣ አልፎ ተርፎም ህዝብን ከማገልገል መስመር ወጥቶ የግል ምቾቱን ያስቀደመ እለት ከለውጥ ፈላጊው ማኅበረሰብ ጋር ከመላተምና ይህን ከመሰለው አደጋ ማምለጥ አይችልም።

ከመጽሐፉ የተቀነጨበ

ISBN 978-99944-72-42-0

ETB 300.00
USD 30.00
EUR 25.00
GBP 22.00

9 789994 472420 >

www.tinssaezeethiopia.com